# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 13

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸው ውሣኔዎች በቀጣይ የፍርድ ቤቶች ሥራዎች ወሣኝ እንደመሆናቸው ቶሎ መሠራጨት እንዳለባቸው እሙን ነው፡፡ የሰበር ውሣኔዎችን ኮፒ ውሣኔ እንደተሠጠ ባለጉዳዮች ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ውሣኔዎችን በአንድ ላይ ለማሣተም ግን ቀደም ሲል ይፈጅ የነበረውን ጊዜ ያህል ባይሆንም የተወሰነ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም፡፡ ይህን የአሁኑ ዕትም ከቀደሙት 12 ቅጾች በተሻለ አጭር ጊዜ ማሣተም ተችሏል፡፡

ውሣኔዎቹን በቶሎ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ያለውን ችግር ለመቅረፍ እየተከተልናቸው ያሉ አሠራሮች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የሕትመት ሥራውን ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው እና ምናልባትም ውሣኔዎቹን በተለይም ለፍርድ ቤቶች ጊዜ ሣይጠፋ እንዲደርሱ ከማድረግ አንፃር እንደ ጥሩ አማራጭ ያየነው ውሣኔዎቹ እንደተሰጡ በፍርድ ቤቱ ድረ ገጽ ማለትም www.fsc.gov.et እንዲቀመጡ ማድረግና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ አሰራር በአሁኑ ወቅት የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ወረዳ ድረስ የተዘረጋ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በቶሎ የሰበር ውሣኔዎችን የሚያገኙ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የተሻለ ሥራ ሰርተን ለህብረሰባችን ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ለምናደርገው ጥረት የባለሙያዎችን አስተያየትና ድጋፍ እንፈልጋለን፡፡ የጠበቅነውን ያህል ባይሆንም ለተሠጡን ጥቂት ገንቢ አስተያየቶች እያመሰገንን ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

## በ2004 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች

## ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት | | | | |
| 1 | በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ የተሰጠ ውሣኔ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቀርቦ በተወሰነ መልኩ ተሻሽሎ መወሰኑ በጉዳዩ ቅር የተሰኘ ወገን ውሣኔውን አስመልክቶ ለሰበር ችሎት የሚያቀርበው አቤቱታ የመጨረሻ ፍርድ ያልተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የትግራይ ብ/ክ/መ/ አዋጅ ቁ.93/97 አንቀፅ 30(2)(ሀ),<br>አዋጅ ቁ.49/94 አንቀፅ 16(ለ) እና 17 | 61480 | አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደ<br>እና<br>ወ/ት ሁላማዊት ወ/ገብርኤል | ጥቅምት 22/2004 | 2 |
| 2 | • የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በሰበር ችሎት የተሻረ ሲሆን በውሣኔው መብቱ የተነካ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ 358 መሰረት ለሰበር ችሎት መቃወሚያ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• መብታቸው የተነካ ወገኖች ሊስተናገዱ ስለሚችሉበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ. 358<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10 | 31264 | ወ/ሮ እመቤት መኰንን<br>እና<br>ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት<br>ተቃዋሚ አቶ አይናዲስ ገዳሙ | ህዳር 06/2004 | 5 |
| 3 | በተከሳሽ ወይም ከሳሽ ሞት ምክንያት በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ የነበረ ክርክር በተቋረጠ ጊዜ ክርክሩ በወራሾች አማካኝነት ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታና በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣ | 62452 | እነ የሟች ወንድሙ ደምሴ ሚስትና ወራሾች (ሶስት | ጥር 03/2004 | 7 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49(1), 55(2) | | ሰዎች)<br>እና<br>አቶ በርሄ ንስራን | | |
| 4 | በንብረት ላይ በፍ/ቤት የተሰጠን የእግድ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 መሠረት መልሶ ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 | 71316 | የኢት/ያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>ለገሠ ጌታሁን | ግንቦት 9/2004 | 13 |
| 5 | •በአንድ ጉዳይ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተካሄደ ክርክር የተሰጠ ፍርድ ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ወይም እርሱ ባልተካፈለበት ሁኔታ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር መብቱ/ጥቅሙ የሚጐዳበት ሰው በክርክሩ በመግባት መብቱን በህግ አግባብ ሊያስከብር ስለሚችልበት ሁኔታ፣<br>• ከላይ በተመለከተውና ባልተካፈልኩበት ክርክር የተሰጠ ፍርድ ሥርዓትን ባለመከተል የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ፍርዱ ዋጋ እንዲያጣ ወይም አንዴ የተሰጠ ፍርድን ወደ ጐን በመተው በሌላ ጊዜ በሚሰጥ አዲስ ፍርድ እንዲቀየር ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህቁ. 41, 358, 212 | 67127 | አቶ አበራ ሁንዴ<br>እና<br>ፍንፍኔ የደን ደርጅት | ሰኔ 08/2004 | 16 |
| 6 | በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዝ አንድን በነጥብ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ጉዳይ አይቶ እልባት እንዲሰጥበት የተላለፈለት ፍ/ቤት የተመለሰውን ጉዳይ የበላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ መሠረት በማድረግ በአግባቡ ውሣኔ ለመስጠት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍብ/ሥም/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) | 72189 | አቶ ካሳዬ ያደቴ<br>እና<br>ሲኞር ፍራንችስኮ ቬንሲያ | ሰኔ 18/2004 | 20 |
| 7 | •በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ውስጥ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች የሚታዩበት አግባብ በፍ/ብ/ህጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች ስለመሆኑ፣<br>• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ ይነሳልኝ በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በህጉ የተመለከተው የአንድ ወር ግዜ ገደብ በፍታብሔር ህጉ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌት መሠረት ሊሰላ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1848, 1856(2)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78, 195 | 76601 | አቶ ሽመልሽ አማረ<br>እና<br>አቶ አማረ መኮንን | ሰኔ 18/2004 | 23 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ግዜው ያለፈበት የይግባኝ አቤቱታን ማስፈቀጃ በመቀበል ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በበላይ ፍ/ቤት በተካሄደ ክርክር የማስፈቀጃ አቤቱታው ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ወሣኔ የተሰጠ እንደሆነ የስር ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 325,326,349 | 74785 | አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሐምሌ 03/2004 | 27 |
| 9 | • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ በግልጽ ያልሸፈናቸውና ለፍ/ቤት የቀረቡ ጉዳዮችን አካሄድ (አሰራር) በተመለከተ ህጉ ከመውጣቱ በፊት ተጽፈው በሥራ ላይ የነበሩ አግባብነት ያላቸው ህጐች እንደ አግባብነቱ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br>• ክስ አቅርቦ ለከሳሽ የሚላከውን መጥሪያ ከፍ/ቤት ወጪ አድርጐ ነገር ግን ለተከሣሽ መጥሪያውን ከማድረሱ በፊት ክሱ እንዲቋርጥ ያደረገ ከሣሽ ለዳኝነቱ የከፈለው ገንዘብ በመሉ እንዲመለስለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• በፍ/ቤት ክስ የመሰረተ (ያቀረበ) ወገን የክስ መሰማቱ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ክሱን በማንሣት መዝገቡ እንዲዘጋ ያደረገ ከሆነ ለዳኝነት ከከፈለው ገንዘብ ለፍ/ቤቱ በኪሣራ ስም የሚቀነሰው ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሊመለስለት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 232(1) (ለ) ,245(4),3,278(1)<br>የህግ ክፍል ማስታወቂያ 177/74 አንቀጽ 11 | 76786 | አቶ አልዩ ተክሉ እና አቶ መስፍን ስለሺ | ሐምሌ 03/2004 | 31 |
| 10 | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 የተመለከተው የጣልቃ ገብነት ሥርዓት አፈፃፀም | 77322 | የደብረ ዘይት መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያ እና እነ እሌኒ ዓለማየሁ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 17/2004 | 34 |
| 11 | በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ በህግ ስልጣን ባላቸው የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ክርክር ተካሂዶ በፍርድ ያለቀን ጉዳይ በተመለከተ እንደ አዲስ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.188/92 አንቀፅ 4(2), 5(4)<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 78(5), 34(5) | 58119 | ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል እና አቶ ዓሊ በከር | ጥቅምት 21/2004 | 37 |
| 12 | በህጉ አግባብ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር ባልተሟላበት ሁኔታ የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ | 73696 | ወ/ሪት ሃና አበባው | ሚያዝያ | 39 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንደተሰጠ የማይቆጠርና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73,337 | | እና<br>አቶ አብዱ ይመር | 9/2004 | |
| **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | | **43** |
| 13 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሠራተኛን ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የቅጥር ሁኔታ ለመወሰን የተቋሙን ድርጅታዊ አቋም ብቻ መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10 | 67533 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒሽን ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ በረከት በለጠ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 08/2004 | 44 |
| 14 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ አስቀድሞ በሥራ ላይ የነበረን የድርጅት መዋቅርን መሰረት በማድረግ ሆኖ ጉዳዩ ለአፈፃፀም በቀረበ ጊዜ የድርጅቱ መዋቅር የተለወጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ሊፈፀም የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.392(1),(2) | 69471 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን<br>እና<br>አቶ ጥበቡ ተሰማ | ጥቅምት 20/2004 | 46 |
| 15 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ለሠራተኛ የሚከፈል የሥራ ስንብትና ካሣ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ሊቀነስ የሚገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 13, 10(2), 2(10)<br>ደንብ ቁ.78/94 | 61549 | የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ ብርቄሣ አብራሂም | ህዳር 06/2004 | 48 |
| 16 | አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከአሰሪው ፈርሞ የተረከበው ንብረት በጠፋ ጊዜ ተጠያቂ የሚሆነው ንብረቱ በእጁ እያለ እንዳይጠፋ ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም ለንብረቱ መጥፋት የሠራተኛው ቸልተኛነት መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.515/99 አንቀፅ 65 | 69179 | የኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ታሪኩ ጫኔ | ህዳር 04/2004 | 50 |
| 17 | በህግ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በግልጽ በተላለፈ መመሪያ መሰረት የሠራተኛን የሥራ | 69125 | ወ/ሪት ሠላም | ታህሣሥ | 53 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ውል ያቋረጠ አሠሪ የሥንብትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 28, 12(1)(ሀ) | | ተስፋዬ<br>እና<br>አልካን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | 02/2004 | |
| 18 | ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪና የሥራ መሪ የሆነ ሰው መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ለመፍታት ተፈፃሚነት ያለው ደንብ (መመሪያ) በስምምነት የተዘጋጀ እንደሆነ ይሄው ደንብ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ | 60489 | አቶ አምባዬ ወ/ማሪያም እና የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት | ጥር 14/2004 | 55 |
| 19 | •ከአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሰራተኛው ከሥራ ሲሰናበት ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት አላስረከበም በሚል ሰራተኛው ሊከፈለው ከሚገባው ክፍያ ቀንሶ ለማስቀረት የሚቻለው በሰራተኛው በኩል ዕዳ ስለመኖሩ መተማመን ላይ ሲደረስ ስለመሆኑ<br>•ሰራተኛው ከተረከበው ንብረት አለመመለስ ጋር በተገናኘ ዕዳ ስለመኖሩ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር (አለመግባባት) ያለ እንደሆነ አሰሪው ጉዳዩን በፍ/ቤት አቅርቦ መብቱን ማስከበር ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 36-38, 59(1), 53(2)(1) | 67382 | እነ አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አርጋው አበበ | ጥር 04/2004 | 58 |
| 20 | •ከአምስት አመት በላይ ያገለገለ ሰራተኛ የጡረታ መዋጮው ተመላሽ የተደረገለት መሆኑ የጡረታ አበል ተጠቃሚ እንደሆነ ተቆጥሮ የስራ ስንብት የሚያስከለክለው ስላለመሆኑ<br>•በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የጡረታ "አበል" በሚል የተመለከተው ሀረግ የጡረታ መዋጮ ተመላሽንም የሚጨመር ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀፅ 2(13),(14)<br>አዋጅ ቁ.494/98 አንቀፅ 2(1)(ሸ) | 73258 | እነ ወ/ሮ አበራሽ ፈይሳ (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>ጂ. ሰቨን ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር | ጥር 16/2004 | 61 |
| 21 | •ሠራተኛ በሥራ ቦታና በሥራ ወቅት ሆን ብሎ በራሱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሰሪው ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ<br>•የአደጋ መከላከያ ደንቦችን በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በአደንዛዥ ዕፅ አስክሮ በሥራ ላይ በመገኘቱ በሠራተኛ ላይ የደረሰ ጉዳት ሆን ተብሎ እንዳደረሰ የሚቆጠርና አሠሪው ጉዳቱን ለመካስ የማይገደድ ስለመሆኑ | 67201 | አቶ ምትኩ ኃይሉ<br>እና<br>አቶ መስፍን ጥላሁን | የካቲት 26/2004 | 64 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 96(ሀ)(ለ), 96(1) | | | | |
| 22 | ከስራ ክርክር ጋር በተገናኘ በዲሲፕሊን ተከስሶ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ሠራተኛው በፈፀመው የማታለል ድርጊት ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን መነሻ በማድረግ የተሰናበተ ሰራተኛ የዲስፕሊን ኮሚቴው አባላት በሥራ ክርክር ሰሚው አካል ፊት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ስላልሰጡ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) እና (መ) | 73881 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን<br>እና<br>አቶ ተፈራ ሹና | የካቲት 27/2004 | 67 |
| 23 | የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰና ጥፋተኛ ተብሎ በጽኑ እስራት ቅጣት በተቀጣ ጊዜ የጡረታ መብቱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 95/1967 አንቀጽ 34<br>አዋጅ ቁ. 345/1995 አንቀጽ 52(2) እና (3)<br>አዋጅ ቁጥር 209/1955 | 50590 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ በርገኔ ኢንኮ | መጋቢት 28/2004 | 70 |
| 24 | ከሚሠራበት ድርጅት ብድር ወስዶ ከፍሎ ያላጠናቀቀ ሠራተኛ በገዛ ፈቃዱ ሥራ ሲለቅ ተከፍሎ ያላለቀው ብድር ከሚያገኘው ፕሮቪደንት ፈንድ ሊቀንስ የሚችለው ሠራተኛው ዕዳ እንዳለበት ያመነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1) | 71507 | ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ሰይፉ ተፈሪ | መጋቢት 10/2004 | 73 |
| 25 | አንድ ሠራተኛ በአሠሪው በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ የሚባለው ንብረቱ የአሰሪውን ወይም ከአሠሪው ድርጅት ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(ሸ) | 74400 | ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሺያል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ናርዬ | ግንቦት 07/2004 | 76 |
| 26 | ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች (መያዶች) በስራቸው የሚቀጥሯቸውን ሠራተኞች በተመለከተ አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች የሚዳኙ መሆኑን በመግለጽ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ያደረጉ እንደሆነ በድርጅቶቹ እና በሰራተኞቻቸው መካከል የሚነሱ | 67996 | ሳሳካዋ ግሎባል 2000 ፕሮጀክት<br>እና | ሰኔ 19/2004 | 79 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለመግባባቶች በስምምነቱ መሠረት እልባት ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(3) | | አቶሸዋድንበር ደቻሳ | | |
| 27 | በሥራ ላይ በደረሰ ጉዳት በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሠራተኛው የጉዳት ካሣ በመድን ፖሊሲ ተሸፍኖ ሲገኝ የካሣ ክፊያውን ሊጠይቁ ስለሚችሉ ወገኖች፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 110(1)(2),134(2),128,129,133<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 842, 1732, 1735, 1736, 1734 | 72645 | የኢትዩጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ አቶ ክፍለዩሐንስ ተሰማ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 03/2004 | 82 |
| 28 | አሰሪ ሲሰራው የነበረው ሥራ በመቀነሱ ወይም በመቀዝቀዙ ምክንያት ካሉት ሠራተኞች መካከል ከአሥር ፐርሰንት በታች የሆኑትን የሥራ ውል ሚቋረጡ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥና ሥራ የሚቀጥሉትን ሠራተኞች ለመለየት ሊከተለው ስለሚገባ አካሄድ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28(8), 29(3) | 74230 | አቶ አስቻለው ጌታሁን (አስር ሰዎች)<br>እና<br>አልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ | ሐምሌ 17/2004 | 90 |
| 29 | •የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራ ቦታው አምቧጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆን..." በሚል የተመለከተው ሀረግ ሊተረጐምና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ፣<br>• "የሥራ ቦታ" የሚለው ሀረግ አሰሪው (ተቋሙ) ለሥራና ለመኖሪያ በሚል ለሰራተኞች የሚሰጠውን ቦታ እንዲሁም ተፈፀመ የተባለውን የአምባጓሮ ድርጊት ከሥራ ሰዓት ሙጪ መሆኑንም ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ረ),97,4 | 79105 | ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ<br>እና<br>አቶ መዘምር መክብብ | ሐምሌ 03/2004 | 94 |
| 30 | አሰሪ ደንብን ባልጠበቀ መንገድ ሠራተኛው ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሰራ ተመድቦ ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ሠራተኛውን ማሰናበቱ ተገቢ ስላለመሆኑ | 77113 | አኪኮ ቦዲዋይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ገረመው አበበ | ሐምሌ 27/2004 | 97 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 31 | በሥራ ላይ ንብረትንም ሆነ ህይወትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት መፈፀም ህገ ወጥ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ቀ) 14(2)(ሀ) | 79096 | ሪመምበር ዘ ፐረሰት ኮሚዩኒቲ<br>እና<br>ዘውድነሽ ማሞ | ሐምሌ 20/2004 | 100 |
| 32 | በሥራ ላይ ከሚደረስ አደጋ ጋር በተያያዘ አደጋው የደረሰው ከሥራ ሰዓትና ከሥራ ቦታ ውጪ ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌለው አጋጣሚ እና ከአሰሪው ትዕዛዝ ሳይኖር እንደሆነ አሰሪው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95, 96, 97 | 68138 | ወ/ሮ ጥሩሰው ጥላሁን (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>ሲቪል ወርክስ አማካሪ መሃንዲሶች ኃ/የተ/የግል ማህበር | ጥር 17/2004 | 103 |
| 33 | በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት አንድን ጉዳት  በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ (ሁኔታ) እና በጉዳቱ ሞት በተከሰተ ጊዜ የጉዳት ካሣ ለሚች ቤተሰብ የሚሰጥበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ)<br>አዋጅ ቁ. 262/94 አንቀጽ 46(2)(5)(ለ) | 61717 | ወ/ሮ አበበች አዱኛ በራሳቸውና በህጻን ረቂቅ ተክሉ ስም<br>እና<br>በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት | ጥር 15/2004 | 111 |
| 34 | የሠራተኞች ስንብት ተከትሎ አሰሪ የሆነ አካል የከራካሪ የሆኑ ክፍያዎችን በተመለከተ ሊያዘገይ እንደሚችልና ክፍያ በማዘግየት በሚል ሊቀጣ የሚችለው ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ሳይኖር ወይም የሚያከራክር ክፍያ ሳይኖር ያለአግባብ ያዘገየ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 37, 38, 36 | 74636 | ኢትዮ ቴሌኮም<br>እና<br>ትዕግስት ሙሉዓለም (15 ሰዎች) | ሰኔ 21/ 2004 | 116 |

| | **ቤተሰብ** | | | | 120 |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | በፍርድ ቤት የተቋቋመ የውርስ አጣሪ አበል መጠን ሊወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 959, 946-1125 | 69153 | ብርሃኑ ከፍያለው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሮማን<br>ይርጋ (11 ሰዎች) | ጥቅምት<br>06/2004 | 121 |
| 36 | የጋብቻ ፍቺን በተመለከተ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ከሌለ በስተቀር የባልና ሚስት የጋራ ንብረትን አስመልክቶ የፍቺ ውጤት የሆነውን የክፍፍል ጥያቄ በፍ/ቤት ማቅረብ አይቻልም ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 76 | 61357 | አቶ ፍቅሬስላሴ<br>እሸቴ<br>እና<br>ወ/ሮ ዋጋዬ ጋይም | ህዳር 22/2004 | 124 |
| 37 | በባል ወይም በሚስት ለጋራ መተዳደሪያቸው በሚል ከሚካሄድ የንግድ ሥራ ማስኬጃ ጋር በተያያዘ የተገባ ዕዳ የተጋቢዎች የጋራ እዳ እንደሆነ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ.19<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92, አንቀፅ 70 | 68190 | የኢትዮጵያ ልማት<br>ባንክ<br>እና<br>ወ/ሮ እመቤት<br>ቱርፋ | ታህሣሥ<br>05/2004 | 127 |
| 38 | ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ጋር በተገናኘ በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት ከባንክ ወጪ ተደርጐ ለ3ኛ ወገን የተላለፈ (የተሰጠ) ገንዘብ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመትበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 85-93 | 70442 | አቶ በቀለ ቱፋ<br>እና<br>ወ/ሮ ባዩሽ እሸቴ | ታህሳስ<br>30/2004 | 130 |
| 39 | የወራሾች የጋራ ሀብት የሆነን ንብረት ለመሸጥና ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1262, 1060(1) | 64371 | ፍቅረዲን ሰይፈዲን<br>እና<br>እነ አበራ ለማ<br>(አምስት ሰዎች) | ጥር 02/2004 | 134 |
| 40 | ከባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ በአንደኛው ተጋቢ በውርስ የተገኙ ንብረቶች (ሀብቶች) ለልማት በሚል በመፍረሳቸው የተገኘ የካሳ ክፍያ በግብይት እንደተገኘ ተቆጥሮ የግል ስለመሆኑ በፍ/ቤት አልተረጋገጠም በሚል እንደ የጋራ ሀብት ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ | 65708 | አቶ አራጋው አበበ<br>እና<br>ወ/ሮ ራሔል | ጥር 02/2004 | 137 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 58, 57 | | ውብሸት | | |
| 41 | •የጋብቻ ፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሣኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነትን ሲያገኝ ብቻ ስለመሆኑ<br>•ፍቺን እና የፍቺን ውጤት በተመለከተ ውሣኔ የመስጠትና የማፅደቅ ስልጣን የፍ/ቤት ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 83(3), 117<br>የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.69/95 እና አዋጅ ቁ.83/96 አንቀፅ 110(5) | 69657 | ወ/ሮ ሐምዚያ ሼክ ኢብራሁም<br>እና<br>አቶ አብዲ ኡስማኤል | የካቲት 28/2004 | 141 |
| 42 | በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ ሰዎች ግንኙነታቸው እስካልተቋረጠ ድረስ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው በመኖራቸው ብቻ በመካከላቸው ያለው የትዳር ግንኙነት ፈርሷል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ | 67924 | ወ/ሮ ምንያ ገ/ሥላሴ<br>እና<br>ወ/ሪት መሠረት ዓለማሁ | መጋቢት 26/2004 | 144 |
| 43 | ከባልና ሚስት ጋብቻና ፍቺ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የቀረበን ጉዳይ ስልጣን ያለውና ተከራካሪዎቹ ለመዳኘት ፈቃዳቸውን የገለፁለት የሸሪአ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ መዝገቡን የዘጋው እንደሆነ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. አንቀጽ 37(1), 34(5), 78(5), | 72420 | ወ/ሮ ኬሪያት ያህያ<br>እና<br>ሐጂ ጅሀድ ኡመር | ሚያዝያ 22/2004 | 148 |
| 44 | የውርስ ሀብት ማጣራት ጋር በተገናኘ የንብረት አጣሪው የሟች ያለኑዛዜ ወራሾች በሚል የተጠቀሱ ወራሾች በአካባቢው በሚገኘው የመረዳጃ እድር ሰፍሯል በማለት የውርስ ድርሻ አላቸው በሚል የሚያቀርበው የውሣኔ ሀሳብ ህጋዊ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 842, 856, 962, 944(ሀ),1097,1113 | 71895 | አቶ ሞላ ንጉሴ<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ገለታ | ግንቦት 10/2004 | 151 |
| 45 | የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድን የጋራ ንብረት በዓይነት ለመካፈል ተጋቢዎቹ ከስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነና ሁለቱም የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ያቀረቡ እንደሆነ ንብረቱ ለጨረታ ቀርቦ እንዲሸጥ በማድረግ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀጽ 103(1) | 71126 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ሰብስቤ<br>እና<br>እነ ሻለቃ ባሻ እንደሻው (ሁለት | ሰኔ 05/2004 | 154 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሰዎች) | | |
| 46 | ሚች አድርጐት የነበረ ኑዛዜ በተመሣሣይ ንብረት ላይ በኂላ በተደረገና ከሞተ በኂላ ተፈፃሚነት ባለው ስጦታ የተተካ እንደሆነ ኑዛዜው በስጦታው እንደተሻረ የሚያስቀጥረው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2428, 2443, 881, 826(2), 856, 898 | 72286 | አቶ ኃ/ስላሴ ወርቂ<br>እና<br>ወ/ሮ ምስራቅ ወርቂ | ሰኔ 19/2004 | 157 |
| 47 | በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ስም የተመዘገበና በጋብቻ ወቅት ዕጣው የወጣ የኮንዶሚንየም ቤት ላይ ያለ መብት የቤቱ ውል ከጋብቻ መፍረስ በኂላ የተፈፀመና ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ (የንብረት ክፍፍል እስካልተፈፀመ ድረስ) ንብረቱን የግል የሚያስብል ስላለመሆኑ | 75562 | ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ<br>እና<br>አቶ መሐመድ ይመር | ሰኔ 18/2004 | 160 |
| 48 | ፍቺን በስምምነት ለመፈፀም ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡ ባል እና ሚስት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ያደረጉትን ስምምነት ፍ/ቤት ለህግና ለሞራል የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ያፀደቀው እንደሆነ ስምምነቱ ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80,83(3)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277(2) | 74376 | አቶ ብዙአየሁ ታደሰ<br>እና<br>ወ/ሮ ሰሎሜ ሻወል | የካቲት 27/2004 | 163 |
| 49 | አንድ ወንድ ሁለት ሚስቶች ጋር ተጋብቶ በሚገኝ ጊዜ የንብረት ክፍፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የፌዴራል የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 102(1),86(1),62(1),63(1)<br>የአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 113(1),97(1),73(1),74(1) | 45548 | ወ/ሮ አሚናት አሊ<br>እና<br>ወ/ሮ ፋጡማ ውበት | መስከረም 24/2003 | 167 |
| 50 | ውል አዋዋይ ወይም ዳኛ ፊት የተደረገ ኑዛዜ በህጉ የተመለከተውን የኑዛዜው መነበብ ሥርዓትን ያላሟላ ከሆነ ህጋዊ ፎርማሊቲን የሚያሟላ እንደሆነ ለመቁጠር የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 881(2), 882, 857 | 70057 | እነ ወ/ሮ አበበች ቡልቻ (ሶስት ሰዎች)<br>ተጠሪ፡- የለም | ህዳር 06/2004 | 171 |
| **ውል** | | | | | **174** |
| 51 | የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(ረ) ድንጋጌ ከስልክ አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(ረ), 2023, 2022 | 61331 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ጥቅምት 10/2004 | 175 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እና<br>ሚ/ር ጀርመን<br>ግናሆ | | |
| 52 | ከማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ሻጭ የሆነ ወገን የሸጠውን ነገር ባለሃብትነት ለገዢው የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2875, 2281,1808(2) | 61913 | ወ/ሮ እታለማሁ መስፍን<br>እና<br>አጋ አንጼ | ጥቅምት 20/2004 | 179 |
| 53 | ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት ውል ምንም እንኳን የተፈፀመ ቢሆንም ውሉ የ3ኛ ወገኖችን መብትና ጥቅም የሚነካ ከሆነ ይህንኑ በመግለፅ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ይወሰን ዘንድ ለፍ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1806 | 61808 | ወ/ሮ ፀሐይ ፍቃዱ<br>እና<br>እነ አቶ ብቻዬ ተስፋዬ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 07/2004 | 181 |
| 54 | አንድ ማህበር ለሰጠው ብድር የሚያገኘውን የወለድ መጠን ከመደበኛው የባንክ ማበደሪያ ወለድ መጠን ከፍ አድርጐ ለማበደር ስለመቻሉና ይኸውም ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.147/91 አንቀፅ 34(2)<br>አዋጅ ቁ.402/96 አንቀፅ 5<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731,1678<br>የትግራይ ብ/ክ/መንግስት አዋጅ ቁ. 145/2000 | 62162 | መትከል ልምዓት ሁለገብ መ/ህ/ስ ማህበር<br>እና<br>ቄስ ካላዩ ኪሮስ | ህዳር 21/2004 | 186 |
| 55 | ከውል መፈፀም ጋር በተገናኘ ተዋዋይ ወገኖች ውልን በተናጠል ለመሰረዝ (unilateral cancellation of contract) ስለሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1771, 1774, 1757, 1787, 1785, 1786, 1789, 1788 | 57280 | እነ ሴንትራል ቬኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (አራት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 03/2004 | 189 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 56 | የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 ከብድር ውጪ በሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 | 64397 | አቶ አንዳርጌ እምሩ<br>እና<br>ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ | ጥር 01/2004 | 200 |
| 57 | ውሎች በቃል፣ በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ሊደረጉ ስለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1681(1) | 71375 | ዳሽን የህትመትና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ፍስሐ ይሁን | ጥር 16/2004 | 203 |
| 58 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የጠፋበት ሰው የሽያጭ ውሉ የጠፋ ስለመሆኑ ለማስረዳት በሚል የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለውና የሚቀርቡት ማስረጃዎች በተገቢው ሁኔታ ተመርምረው አሳማኝ መሆናቸው ከታወቀ (ሲረጋገጥም) ተከራካሪው የሽያጭ ውሉን በምስክሮች ለማስረዳት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የማገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ህ/ብ/ህ/ቁ 2003,2002 | 69208 | ወ/ሮ ንፁህ በላይ<br>እና<br>ወ/ሮ ምንትዋብ አዳነ | መጋቢት 10/2004 | 206 |
| 59 | በወለድ አገድ ውል መሰረት የማይንቀሣቀስ ንብረቱን ያስያዘ ተዋዋይ ወገን በውል የተገለፀው ጊዜ ካለፈ በኂላም በማናቸውም ጊዜ ዕዳውን ከፍሎ ንብረቱን ለማስለቀቅ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 3128/2/ 3117-3130 | 72463 | እነ አቶ ንጉሴ ሀይሌ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ሁሬሣ ደበል (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 26/2004 | 209 |
| 60 | እንደ ውል አልተፈፀመልኝም በሚል የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች የጥያቄ አቅራቢውን ተነፃፃሪ የውል ግዴታ ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዳት ኪሣራ ሊወስኑ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1771, 1802 | 69915 | ሻምበል ይኩኖ ለገሠ እና<br>አቶ መሐመድ በሽርና ቤተሰቦቹ ጨው አምራች ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 25/2004 | 211 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 61 | በሰነድ ላይ የተመለከተ ፊርማ በተካደ ጊዜ ሰነዱ ሲፈረም የነበሩ የምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ /Authenticate ለማድረግ/ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472(1) እና (3) | 71927 | ቄስ አብርሃ በርሄ<br>እና<br>ወ/ሮ ብርነሽ ሕሉፍ | ሚያዝያ 10/2004 | 215 |
| 62 | የፀና የውል ግዴታ የገባ ሰው ውሉ በፍርድ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችለው ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ግዴታውን በአግባቡ ያልፈፀመ (ያልተወጣ) እንደሆነ ወይም የፈፀመው ፍፁም ባልሆነ አኳኋን ከሆነ ስለመሆኑ<br>በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1784 1785(2),(1) | 66935 | አቶ ሽመልስ አበራ<br>እና<br>አቶ ጌታቸው አያልቄ | ሰኔ 05/2004 | 218 |
| 63 | አንድ ቀድሞ በመያዣ የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ካርታ ቁጥሩና የቤት ቁጥሩ ተለውጦ እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ቤት ተሠርቶና አዲስ ካርታና የቤት ቁጥር ተሰጥቶ በተገኘ ጊዜ አዲሱን ቤት በመያዣ የያዘ አበዳሪ ቀድሞ የነበረውን ቤት በመያዣ ከያዘው አበዳሪ የቅድሚያ መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3066 | 75902 | የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሰኔ 22/2004 | 224 |
| 64 | • ከስጦታ አድራጊው ሞት በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን የስጦታ ውልን በተመለከተ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>•የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ስጦታ በህጉ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ አስራርን በተከተለ መልኩ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.881, 2428, 2443, 2436 | 61421 | አቶ ጌታቸው በየነ<br>እና<br>እነ የሕፃን ታቦት በቀለ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 17/2004 | 227 |
| 65 | በአሰሪው በኩል የተመቻቸን የውጪ የትምህርት እድል ተጠቃሚ በመሆን በምትኩ ለተወሰነ ጊዜ ለማገልገል ከተደረገ ውል ጋር በተገናኘ ሠራተኛው በውሉ ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ከሚጠበቅበት ጊዜ በፊት ከአሰሪው ፈቃድና እውቅና ውጪ ለሌላ ትምህርት ወደ ሌላ አገር በመዛወር የመጀመሪያው ውል ውጤት እንዳይኖረው ያደረገ እንደሆነ ሠራተኛው በውሉ የተመለከተውን ግዴታ ለመፈፀም እንዳልቻለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ | 70963 | ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ<br>እና<br>እነ አቶ ተመስገን ማጉሌ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 30/2004 | 231 |
| 66 | • የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውል መኖሩን በማመን ነገር ግን ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሠረት የተከናወነ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 36887 | ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ<br>እና<br>እነ አቶ ገብሩ እሸቱ | ህዳር 18/2001 | 233 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723(1) መሠረት የሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ምዝገባ ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል መኖሩን ለማስረዳት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723(1),2878 | | (ሁለት ሰዎች) | | |
| 67 | ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2782,2800,2802,2472 | 64887 | አቶ አደም የሱፍ<br>እና<br>አቶ አብዱሠላሣ ሙሐመድ | ሐምሌ 29/2003 | 236 |
| | **ወንጀል** | | | | **239** |
| 68 | በአንድ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ወይም ድጋሚ ቅጣት (principle of double jeopardy) ክልክል ስለመሆኑ የተደነገገው መርህ ሊተረጐም ስለሚችልበት አግባብ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 23<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.42(1)(ሀ) | 60217 | እነ ም/ኢ/ር ኃይላይ አስገለ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የቤ/ጉ/ፍ/ት/ሕ ቢሮ | ጥቅምት 15/2004 | 240 |
| 69 | • ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የዋስትና ጥያቄን ላለመቀበል ሥልጣን (discretion) ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>• ዋስትናን ለመከልከል ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ምክንያት በቂና ህጋዊ ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ፣<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.67 | 67874 | እነ አቶ ፅጌብርሃን ተሰራ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን | ጥቅምት 23/2004 | 243 |
| 70 | ማዕድናትና የከበሩ ድንጋዮችን ከማዘዋወርና ለሽያጭ ከማቅረብ ጋር በተገናኘ ስለሚኖር የወንጀል ኃላፊነት፣<br>የወ/ህ/ቁ 346፣347፣378<br>አዋጅ ቁ. 52/85 አንቀጽ 53(1), (5), 26(4)<br>ደንብ ቁ. 182/80/ አንቀጽ 30(1)(ሀ), 3(ለ) እና 4(ሐ), 38-40 | 60345 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና .<br>ገዳ ፎጫ በሲ- | ሕዳር 07/2004 | 247 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) | | ግለሰቦቹ (ሶስት ሰዎች) | | |
| 71 | በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ከአንድ አይነት የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ በሁለት የተለያዩ የወንጀል ክሶች የተከሰሰ ተጠርጣሪ በአንዱ የወንጀል ክስ የተመለከቱ ፍሬ ነገሮች መከሰት ጋር በተገናኘ ጥፋተኛ ለማለት ያልተቻለ እንደሆነ በሌላኛው ክስ ጥፋተኛ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የወ/ህ/ቁ 407(ሐ), 670, 677<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141, 142, 149(1) | 65325 | ሣጅን ታዬ ተክለጊይማኖት እና የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ | ህዳር 22/2004 | 256 |
| 72 | • በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር ክርክሩ አግባብነትና ብቃት የሚኖረው በወንጀል ክሱ ተከሳሹ በወንጀል ፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነ ከሆነና ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች በፍ/ብሔሩ ጉዳይም ቀርበው የተሰሙ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>• በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ማስረጃ ለፍትሐብሔር ጉዳይ አግባብነትና ብቃት የሚኖረው በሁለቱም ጉዳዩች የተሰሙት ማስረጃዎች አንድ አይነት ሲሆኑ ስለመሆኑ፣<br>• በወንጀልና በፍ/ብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍ/ብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁልጊዜ በፍ/ብሔር ክስ ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2149<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 702(2) | 46386 | አቶ ሃይሉ ተስፋሁ እና አቶ ብርሃነ መብራቱ | ታህሣሥ 06/2004 | 259 |
| 73 | ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ በመገኘት ወንጀል አንድ ሰው ተጠያቂ የሚሆነው የምዝገባ ሥርዓት የተዘረጋ እንደሆነ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ<br>የወ/ህ/ቁ.419 | 67411 | እነ አቶ ታረቀኝ ተክሉ ገመዳ (ሶስት ሰዎች) እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን | ታህሣሥ 30/2004 | 262 |
| 74 | በወንጀል ህግ ቁጥር 448 ስር አንድ ሰው ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሆኗል በሚል ወዲያውኑ ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት ለመቅጣት ስለሚቻልበት አግባብ | 67777 | እነ ተወልደ ብስራት (ሶስት | ታህሣሥ 04/2004 | 266 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወ/ህ/ቁ 448(1), (3), 23(2), 58 | | ሰዎች)<br>ተጠሪ የለም | | |
| 75 | በኤግዚቢትነት በፖሊስ ከተያዙ ንብረቶች ጋር በተገናኘ የንብረቶቹ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ንብረቱ ይመለስለት ዘንድ በፖሊስ ጽ/ቤቱ ላይ የሚያቀርበው ክስ በተገቢው ማስረጃ ተጣርቶ እልባት ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ | 62504 | አቶ ታደሰ ናማጋ ሀያቱ እና የፌዴራል ፖሊስ ወ/ምርመራ መምሪያ ዋና ሣጅን ደምሴ ሰጠኝ | ታህሣሥ 06/2004 | 271 |
| 76 | አንድ ሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 407 መሰረት በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ተደርጐ ቅጣት ሊጣልበት የሚችልበት አግባብ፣<br>የመ/ህ/ቁ 407(1)(ሀ) | 60518 | አቶ ፈለቀ ሊቤ<br>እና<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ጥር 15/2004 | 273 |
| 77 | አንድ ሰው በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር ልኳል በሚል ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ<br>የወ/ህ/ቁ 598(2) | 71753 | አቶ ወርቅነህ ዳቲ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ጥር 03/2004 | 277 |
| 78 | •የግንባታና የኮንስትራክሽን ማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር በተያያዘ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና ፈቃድ ሣይኖር ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የመግዛትና የመሸጥ ውል መፈፀም በወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለመቻሉ<br>•ህገ ወጥ ወይም ወንጀል ስለመሆኑ የተደነገገ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተደረጉ ውለታዎችን (ውሎችን) በህግ ኃይል እንዲፈፀሙ በሚል ለፍ/ቤት ጥያቄውን በቀረበ ጊዜ ዳኞች ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1718, 1716<br>የወ/ህ/ቁ.353(1)(ለ)<br>አዋጅ ቁ.52/85 አንቀፅ 53(5) | 69822 | ዲ - ኤም - ሲ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ኢብራሂም ኢቲሶ | ጥር 15/2004 | 280 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ደንብ ቁ.182/86 አንቀፅ 39 | | | | |
| 79 | •የሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አዋጅ ቁ.632/2002 በመተላለፍ ሊኖር ስለሚችለው የወንጀል ተጠያቂነት<br>•ከቀረበ የወንጀል ክስ ጋር በተያያዘ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው ቀርቦ ካልመሰከረ በስተቀር ክሱን ለማስረዳት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማለት ብቁ አይደሉም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.632/2002 አንቀፅ 16(1)(መ), 18(1)(ሀ), 20(2), 40(3) | 71184 | ዓሕመድልሃዲ ካህሳይ<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ህግ | ጥር 18/2004 | 286 |
| 80 | የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ ነገር ግን ከመንግስት ሰራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስ በሙስና ወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.434/97 አንቀፅ 7<br>የወ/ህ/ቁ.407(1)(ሀ),33 | 60542 | አቶ ተክለድንግል ገ/ሚካኤል<br>እና<br>የፌ/ሥ/ም/ፀ/ሙስና ኮሚሽን | የካቲት 27/2004 | 289 |
| 81 | •ከመንግስት ሰራተኞች ውጪ በሆኑ ሰዎች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን በተመለከተ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ ሊያቀርብ ስለመቻሉ<br>•ኮሚሽኑ የወንጀል ክስ ለመመስረት ስልጣን ከተሰጠው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ወይም ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ከሙስና ወንጀሉ ጋር አንድ ላይ መከሰስ ያለበትን የወንጀል ድርጊት አንድ ላይ (አጣምሮ) ሊያቀርብ ስለመቻሉ<br>የወ/ህ/ቁ 379(2), 375, 404(4)(3)<br>አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀፅ 58<br>አዋጅ ቁ.236/93 አንቀፅ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.110 | 64612 | እነ ሐሰን አማን መሐመድ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የፌ/ሥ/ፀረ-ሙስና ኮሚሽን- | የካቲት 27/2004 | 292 |
| 82 | አንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር ሙከራ ደረጃ ላይ ደርሷል (Attempt) ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወ/ህ/አ 32(1)(ሀ),27(1),671(1) | 66856 | ውድማ አበጀ<br>እና<br>የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል | መጋቢት 26/2004 | 296 |
| 83 | የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጋር በተያያዘ የክስ ቻርጅን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን በወ/ህ/አ.438 | 73953 | ከፋለ ሰፈነ | መጋቢት | 299 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በየመንግስት ሥራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ ወንጀል ሊያስጠይቅ ስለመቻሉ፣<br>የወ/ህ/አ.348 | | እና<br>የአማራ ክልል<br>ዓ/ህግ | 13/2004 | |
| 84 | በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ለማቅረብ በህጉ ተለይቶ ስለተመለከተ የጊዜ ገደብ፣<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 187(2) | 73264 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልስልጣን እና እነ አቶ አልፈድል አሻፊ (ሶስት ሰዎች) | ሚያዝያ 9/2004 | 302 |
| 85 | •በወንጀል ፍርድ ሂደት አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ወይም በክርክሩ ሂደት ተሳታፊ ሳይደረግ (ሳይሆን)(default procedure) ነው የታየው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• የቅጣት አስተያየት በሚሰጥበት ጊዜ ያለመቅረብ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ ነው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.161, 164, 197, 202, 149 (4) (1)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(4)) | 76909 | ወ/ሮ ፈትያ አወል<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቢ ህግ | ግንቦት 10/2004 | 205 |
| 86 | •ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግና ሥርዓት መሠረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም (Principle of Double Jeopardy) በሚል የሚታወቀው የወንጀል ህግ መርህ ሊተረጉምና ሥራ ላይ ሊውል የሚችልበት አግባብ፣<br>• አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቴ ተጥሷል በሚል ክርክር ለማቅረብ ሊሟሉ ስለሚገቡ ህጋዊ መስፈርቶች፣<br>• ዐቃቤ ህግ በአንድ ተከሳሽ ላይ የወንጀል ክስ ከማቀርቡ በፊት ተከሳሹ አንድ ወንጀል በመፈፀም ሀሣብ የሠራው አንድ የወንጀል ድርጊት ያስከተላቸውን ወይም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች ሁለተናዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመለየትና በመጥቀስ የወንጀል ክሱን በጥንቃቄ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ 2(5), 24(1) | 72304 | የትግራይ ክልል አጽቢ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ<br>እና<br>ተማሪ ሐጎስ ወልደሚካኤል | ሰኔ 18/2004 | 308 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130,131, 41, 111, 112<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህግ መንግስት አንቀጽ 23,13(2) | | | | |
| 87 | • አንድ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችል የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>• የሙስና ክስ ከሚመራበት ሥርዓት ጋር በተገናኘ ተከሳሽ የሆነ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ለማቅረብ ስለሚችልባቸው ህጋዊ ጉዳዮች፣<br>• ለሰበር ችሎት የሚቀርቡ ማናቸውም ጉዳዮች የይግባኝ አቅራረብ ሥርዓትን ያጠናቀቁና የመጨረሻ ፍርድ የተሠጠባቸው መሆን የሚገባቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 22<br>አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36(2) 40, 55<br>አዋጅ ቁ. 236/93 | 74041 | እነ አንተነህ መኮንን (አራት ሰዎች)<br>እና<br>የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ | ሰኔ 04/2004 | 313 |
| 88 | አንድ ሰው በወ/ህ/አ. 675(1) የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል ሊከሰስና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የወ/ህ/አ.675(1),23 | 74530 | ጀማል መሐመድ<br>እና<br>የፌዴራል ዐ/ህግ | ሰኔ 22/2004 | 316 |
| 89 | አንድ ሰው በወ/ህ/አ. 429 ጉቦ ማቀባበል የወንጀል ድርጊት ክስ ሊቀርብበትና ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የወ/ህ/አ. 429,23(4,(1),58) | 78793 | አቶ ብስራት ወልደመስቀል<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ሰኔ 21/2004 | 320 |
| 90 | በፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሣኔ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት ለመንግስት እንዲወረስ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አ 98(1)(2), | 66943 | እነ ታምራት ገለታ (አራት ሰዎች)<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ሐምሌ 18/2004 | 324 |
| 91 | በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ለማስረዳት መቅረብ የሚገባው | 75922 | እነ አፈወርቅ ሌሊሳ | ሐምሌ | 329 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማስረጃ አይነት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት የሚችልና ድርጊቱ ሲፈፀም አይቻለሁ ወይም/እና ሰምቻለሁ የሚል ቀጥተኛ ማስረጃ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 137, 141, 149 | | (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የደቡብብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት | 04/2004 | |
| 92 | አንድ የወንጀል ድርጊትን ማስረዳት ጋር በተያያዘ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ (circumstantial evidence) በይዘቱ አንድ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት፣ ክስተቱ ሲፈጠር ወይም ድርጊቱ ሲፈፀምና ክስተቱ ከተፈጠረ ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ፣ ያሉትን አካባቢያዊ ሁኔታዎች የሚያሣይና የሚገልጽ በመሆኑ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 137(1) | 75980 | ስማቸው ልንገርህ ዓለሙ<br>እና<br>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የደቡብ ክልል ቅርንጫፍ | ሐምሌ 02/2004 | 322 |
| 93 | የባንክ ሥራ ጋር በተገናኘ የሥራ አመራር ላይ ጉድለት በመፈፀም ስለሚደረግ ወንጀል፣<br>የወ/ህ/አ. 703 | 77989 | እነ አቶ ለይኩን ብርሃኑ (አምስት ሠዎች)<br>እና<br>የፌዴራል ዐ/ህግ | ሐምሌ 04/2004 | 337 |
| 94 | የወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1)ን በመተላለፍ አንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት ሁኔታ፣<br>የወ/ህ/አ. 692,32(1)(ለ) | 77592 | ተካልኝ ጌታቸው<br>እና<br>የፌ/ዐ/ሕግ | ሐምሌ 27/2004 | 347 |
| 95 | አንድ ወኪል ከወካዩ በውክልና ስልጣኑ የወሰደውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 676(2) ድንጋጌ መሰረት ሊያስጠይቀው ስለመቻሉ<br>የወ/ህ/ቁ 676(2) | 67408 | አቶ ፋሲል በላይነህ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | ጥር 01/2004 | 350 |
| 96 | በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብቱ በፍ/ቤት ከተከበረለት በኋላ ህጋዊ ምክንያቶችን በማቅረብ የዋስትና መብቱን በመተው ያስያዘው ገንዘብ ተመልሶለት ጉዳዩን ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል የሚያቀርበውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ | 73569 | አቶ ደረጀ ጎሳዬ<br>እና<br>የኢትዮጵያ | ጥር 17/2004 | 353 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቤ ሕግ | | |
| 97 | በወንጀል የተከሰሱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ፣<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20(5)<br>አዋጅ ቁ.27/88 አንቀፅ 35<br>አዋጅ ቁ.123/90<br>አዋጅ ቁ.27/885 | 65566 | የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐ/ህግ | ታህሣሥ 04/2004 | 357 |
| 98 | የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን የሌለው ቢሆንም በሥር ፍ/ቤቶች ወይም የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት መሰረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ስርዓትን ሳይከተሉ፣ መመስረት የሚገባቸውን ጭብጥ ሳይመሰርቱና ጭብጡን የማስረዳት ግዴታ (Buden of proof) ያለበት ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና መጣራት ያለበትን (የሚገባውን) ፍሬ ጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡትን ውሣኔ በሰበር አይቶ ለማረም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>በወ/ህ/አ. 419 | 63014 | እነ አቶ ወርቅነህ ከንባቶ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የደቡብ ክልል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | ሚያዝያ 09/2004 | 359 |
| | **የንግድ ህግ** | | | | 366 |
| 99 | •በባህር ላይ እቃ አመላላሽ በእቃዎች ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>•በባህር ላይ እቃን ለማመላለስ የውል ግዴታ የገባ ወገን ከእቃዎቹ መጉዳት ጋር በተያያዘ ስላለበት የኃላፊነት አድማስና ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የባህር ህግ ቁ.196,138,205,197,180(3) | 54117 | ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አ.ማ | ጥቅምት 13/2004 | 367 |
| 100 | እቃን ከማጓጓዝ ጋር በተገናኘ ከእቃው አደገኛ (ጉዳት አድራሽ) ባህሪ የተነሣ ዕቃውን በሚያጓጉዘው ተሸከርካሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት የእቃው ባለቤት (ባለንብረት) የዕቃውን በአግባቡና በጥንቃቄ አለመታሸግ | 60385 | ጎልደን ሮዝ አግሮ ፋርምስ ኃ/የተ/የግ | ጥቅምት 24/2004 | 371 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (አለመያዝ) ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁ.578(2) | | ማህበር<br>እና አቶ ሐሊፎም ተስፋ ማሪያም | | |
| 101 | ከንግድ ስም አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የንግድ ሚኒስቴር በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ በይግባኝ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.686/2002 አንቀፅ 6, 7, 30, 2(9), 16, 61 | 69603 | አቶ ሀብተወልድ ዘርጋው የጄትሮ የስራ አመራር የማማከር አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>እነ አቶ ሳሙኤል አሰፋ የጄትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 08/2004 | 374 |
| 102 | ከንግድ ስም ወይም ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ጋር በተገናኘ በሚመለከተው ተቋም በተሠጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማሳረም ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 501/98/ አንቀጽ 6,17,36,49 | 63454 | ዳት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/ባለቤት ዶ/ር ጤና አብተው<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 26/2004 | 378 |
| 103 | •ለገንዘብ እዳ የሚሰጥ ዋስትና አንድ የመድን ተቋም ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ ስለመሆኑ፣<br>•በመድን ሰጪ ድርጅቶች ተዘጋጅቶ የሚሰጥ የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial | 36935 | አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>እና | የካቲት 27/2004 | 383 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | Guarantee Bond) ስለሚኖረው ውጤት<br>•የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ ሊያሟላቸው የሚገቡ ፎርማሊቲዎች እና አቤቱታ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ስለሚኖረው የይርጋ ደንብ<br>አዋጅ ቁ.86/86 አንቀፅ 2<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1845, 1922(2)(3), 1725(ሀ), 1727, 1926, 1929, 1930, 1931<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀፅ 1(1), 2(1) መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀፅ 1(3), 2(1), 3<br>የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ)<br>አዋጅ ቁ.110/90 አንቀፅ 2(2)<br>አዋጅ ቁ.57/89 አንቀፅ 2(18) | | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | | |
| 104 | •ስለ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantee Bond)<br>• የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ውል በባህሪው ከመድን ውል የሚለይና በፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1921, 1719, 1720, 1727, 1719(2), 1920, 1845, 1924(1), 1922(3), 1926<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ23/2002 አንቀጽ 1(1),<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ 24/2002 አንቀጽ 1(3)<br>የንግድ ህግ ቁ. 654(1), 657(1), 712<br>አዋጅ ቁ. 57/1989<br>አዋጅ ቁ 648/2001 አንቀጽ 2/20 አንቀጸ 2(18)<br>አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2) | 47004 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ባሌ ገጠር ልማት ድርጅት | መጋቢት 11/2004 | 392 |
| 105 | •አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንዲፈርስ ለመጠየቅ በቂና ህጋዊ መስፈርቶች መሟላታቸው መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• የማህበር ሥራው በአግባቡ አልተመራም ከሚል ጥያቄ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው አካል የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች መሠረት በማድረግ እንዲስተካከል ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁጥር 217, 218, 511, 543 | 71134 | አቶ ያሬድ ሲሳይ<br>እና<br>አልግሪን አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሰኔ 04/2004 | 399 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 106 | • ስለ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarangee Bond) እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ የተከለከሉ ስለመሆኑ<br>• የአክሲዮን ማህበራት ፕሬዚዳንት ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ ስላለው ስልጣን እና በህግ አግባብ ስልጣኑ ተገድቧል ለማለት ስለሚቻልበት ሁኔታ<br>• የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንደ የኢንሹራንስ ፖሊሲ የማይቆጠር ስለመሆኑና በፍ/ብሔር ህጉ ስለ ዋስትና ግዴታ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣<br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ፡<br>ቁ. 24/2004 አንቀጽ 3,1(3)<br>ቁ. 23/2004 አንቀጽ 1(1)<br>አዋጅ ቁ. 86/86 አንቀጽ 2(4) ,6,4 32-34<br>አዋጅ ቁ. 87/89 አንቀጽ 2(18)<br>አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1725(ሀ),1727,1922(2),(3)<br>አዋጅ ቁ. 648/2001 አንቀጽ 2(20)<br>የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ), 348(3), 313(1)-(7), 313(10-12), 34(1),1 09(ረ), 323(2-3), 35(1), 26, 120 | 40186 | አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>እና<br>ዳሽን ባንክ (አ.ማ) | የካቲት 27/2004 | 402 |
| 107 | የአክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ያለአግባብ ከስልጣኔ (ከስራ አስኪያጅነቱ) ተሸሬያለሁ በሚል በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤት ግለሰቡን ወደ ስራ አስኪያጅነቱ እንዲመለስ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁ. 525-537 | 63200 | እነ ጣና ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር(አራት ሰዎች)<br>እና<br>ሚስተር አልቸዲ ዴልጋውዲዮ | ታህሳስ 30/2004 | 417 |

| | ንብረት | | | | 422 |
|---|---|---|---|---|---|
| 108 | • የመሬት ይዞታና በመሬት የመጠቀም መብት ያለው ወገን በውል ለ3ኛ ወገን ሊያስተላልፍ ስለሚችለው የመብት አድማስ<br>• በመሬት የመጠቀም መብት የተላለፈለት ሰው በመሬቱ ላይ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ያፈራ እንደሆነ ንብረቱን አፍርሶ (ነቅሎ) የመውሰድ መብትን ብቻ ሊያገኝ የሚችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3), (4)<br>አዋጅ ቁ.456/97<br>የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.130/99 አንቀፅ 6 | 69291 | አቶ ጀማል አማን<br>እና<br>ወ/ሮ ተዋበች ፈረዶ | ህዳር 08/2004 | 423 |
| 109 | •የመሬት ባለ ይዞታ የሆነና በመሬቱ የመጠቀም መብት ያለው ሰው ለሁለት ዓመት ያህል መሬቱን በመተው ከአካባቢው ከጠፋ የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬቱ የመጠቀም መብቱ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ<br>•በገጠር የእርሻ መሬት ላይ አርሶአደሮች ያላቸውን የይዞታና የመጠቀም መብት መደፈር ጋር በተያያዘ የሚነሣ ጥያቄ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.456/97<br>የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.130/99<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(4)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677(1)(3), 1845 | 69302 | አቶ ሽለማ ነገሰ<br>እና<br>አቶ ፋይሣ መንግስቱ | ታህሣሥ 20/2004 | 426 |
| 110 | የገጠር መሬት ባለይዞታነትን በማረጋገጥ የተሰጠ የምስክር ወረቀት የመጨረሻና የማይስተባበል ማስረጃ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.133/99 አንቀፅ 24(4)<br>ደንብ ቁ.51/99 አንቀፅ 20(4) | 69821 | አቶ ጥላሁን ጎበዜ<br>እና<br>እነ አቶ መኩተ ኃይሉ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣሥ 17/2004 | 430 |
| 111 | • በአንድ ንብረት ላይ የጋራ መብት ካላቸው ሰዎች ጋር በተገናኘ የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ፣<br>• የጋራ ባለሃብቶች ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ ካለበት ያልተከፈለ ዕዳ የተነሣ ንብረቱ የሚሸጥ ቢሆን ሌሎቹ የጋራ ባለሃብቶች ሊሸጥ ያለውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው | 59504 | እነ አቶ እንዳለ ወርቅነህ (ስድስት ሰዎች) | የካቲት 27/2004 | 433 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1289(1)(2), 1290, 1261, 1388, 1406, 1281 | | እና<br>አቶ ተሸለ ቱቾ | | |
| 112 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ከሚሰጥ የምስክር ወረቀት (ካርታ ወይም ደብተር) ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል የተሰጠን የምስክር ወረቀት መሰረት በማድረግ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በሌላ ጊዜ ሰነዱ በአስተዳደር አካሉ መምከን የተሰጠውን ፍርድ በአንድ ጊዜና ሙሉ ለሙሉ ዋጋ የሚያሳጣ ሳይሆን ካርታው በመምከኑ የተጐዳው ወገን የአስተዳደሩን አካል እርምጃ (ውሳኔ) ክርክር ሊያቀርብበት የሚችልና ፍ/ቤቶችም የእርምጃውን አግባብነትና ህጋዊነት ሊያጣሩት የሚችሉት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195, 1196, 1206<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(1)(2) | 64014 | ዶ/ር ገነት ሥዩም<br>እና<br>እነ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 አስተዳደር ፅ/ቤት (ሶስት ሰዎች) | የካቲት 28/2004 | 437 |
| 113 | በከሳሽነት የተሰየመ ወገን አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጄ ገብቷል በይዞታዬ ላይ እያለ ሁከት ተፈጠረብኝ በሚል የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ በእርግጥም ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚል ጭብጥ በመያዝ ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ ክርክር የተነሣበት ንብረት በከሳሹ እጅ እንዴት እንደገባ ወይም ወደ ከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 | 70801 | ዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ወ/ሮ ፎዚያ ቃዲ | የካቲት 30/2004 | 441 |
| 114 | • የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ጋር በተያያዘ የሚመለከተው የአስተዳዳር አካል አንዴ የሰጠውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ደብተር (የምስክር ወረቀት) በሌላ ጊዜ የሰረዘው እንደሆነ ይኼው ተግባር በፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት የማይችል ወይም የማይስተናገድ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>•የአስተዳደር አካል ህጋዊ ምክንያት ሣይኖረው በአንድ ወቅት የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር ከሰረዘ ይኸው አካሄድ ህጋዊ አይደለም የሚለው ወገን በፍ/ቤት መብቱን ለማስከበር ክስ ሊያቀርብና ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195,1196 | 57186 | ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ ከፈሉ ታረቀኝ | መጋቢት 10/2004 | 443 |
| 115 | የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የደረሰው ሰው እዳውን ከፍሎ ያጠናቀቀ ቢሆን እንኳን እጣው ከደረሰው ቀን አንስቶ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ | 65140 | ወ/ሮ በላይነሽ ቢያድግልኝ | መጋቢት 10/2004 | 447 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማይችል ስለመሆኑና ከዚህ ጊዜ በፊት ቤቱን አስመልክቶ የሚደረግ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 370/95 አንቀጽ 14(2)<br>የአ.አ አስተዳዳር አዋጅ ቁ 19/97 አንቀጽ 21<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1678,1808(2) | | እና<br>ወ/ሮ አስቴር ገበሬ | | |
| 116 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት እና ደንብ በመከተል የተሰጠ መሆን ያለበት ስለመሆኑና በተመሳሳይም በአንድ ወቅት የተሰጠን የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመሰረዝ አግባብነት ያላቸውን ስርዓቶች በመከተል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195-1198 | 67011 | እነ የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ጥሩነሽ ኃየሌ (ሶስት ሰዎች) | መጋቢት 11/2004 | 450 |
| 117 | ከአዋጅ ውጪ የተወሰደ ንብረት ነው በሚል ንብረትን ከመንግስት አካል ያስመለሰ ወገን የንብረቱ አመላለስ አግባብነት የሌለው ሆኖ በመገኘቱ ንብረቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ ሲወሰን ንብረቱን ያለአግባብ በእጁ ያቆየው ወገን ንብረቱ ያስገኝ የነበረውን ገቢ ወይም የታጣ ገቢ ጭምር የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ 572/2000 አንቀጽ 6 | 67631 | የአቶ አሰፋ አባዲዮ ባለቤትና ወራሾች እነ ወ/ሮ ፅጌ ሽኔ (ሰባት ሰዎች)<br>እና<br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ሚያዝያ 24/2004 | 453 |
| 118 | አንድ ጉዳይ ለመፈፀም (ለማስፈፀም) በሚል ምክንያት መነሻነት የሰጠሁትን ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለተሰጠበት ዓላማ አላዋለም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የአደራ ህግ ጽንስ ሀሳብን መሠረት በማድረግ ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና ጉዳዩን ለማስረዳት የሰው ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣ | 69160 | አቶ ሶሬሳ ጋሪ<br>እና<br>አቶ አብርሃም ፍቃዱ | ሚያዝያ 24/2004 | 457 |
| 119 | አከራይ የሆነ ወገን ተከራይ ለሆነው ወገን ቤት እንዲለቀቅ በሚል የሚፅፈው ማስጠንቀቂያ ከአከራይና ተከራይ ውልና ግንኙነት አንፃር የሚታይ እንጂ እንደ ሁከት ተግባር የማይቆጠር ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(1), 2966(1) | 67691 | የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር<br>እና | ታህሣሥ 16/2004 | 460 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወ/ሮ አለምፀሐይ ወልዴ | | |
| **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | | 463 |
| 120 | በፎርክሎዠር ህግ መሰረት የሚከናወን ሐራጅ በፍ/ቤት የሚሰረዝበት አግባብ ስላለመኖሩና ሐራጁ በህግ አግባብ ያለመከናወኑ በባንኩ ላይ የጉዳት ካሣ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.97/90 አንቀፅ 7, አዋጅ ቁ.216/92<br>የፍ/ብ/ሥ/ሣ/ህ/ቁ 447(1), 423(2)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(1), 2027, 2028, 2035 | 68708 | እነ የአቶ ናስር አባጃቢር አባጅፋር ሚስትና ወራሾች(ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ታህሣሥ 05/2004 | 464 |
| 121 | ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ንብረቶች አሻሻጥ ቅደም ተከተል ጋር በተገናኘ አቤቱታ ሊቀርብበትና ፍ/ቤቶችም ውሣኔ ሊሰጡበት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ97/90 አንቀፅ 7, 6<br>አዋጅ ቁ.216/92 | 70824 | ወጋገን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>እነ አቶ ብሩክ ጫካ (ሠባት ሠዎች) | የካቲት 27/2004 | 467 |
| 122 | • የደረሰን ጉዳት ከመካስ ጋር በተገናኘ በንግድ ህጉ እውቅና ስለተሰጣቸው የመድን ሽፋን (የኢንሹራንስ ውል) አይነቶችና ባህሪያት<br>• ለንብረት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን አደጋው በደረሰበት ጊዜ ንብረቱ የነበረውን ዋጋ ለመካስ የሚያስችል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁ. 654(2)(3),657, 674, 675, 688, 665, 678, 681, 680 | 69966 | አቶ በላቸው እሸቴ<br>እና<br>የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሚያዝያ 10/2004 | 472 |
| 123 | •የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ በህጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የባለዕዳው ንብረት እዳውን ለመሸፈን ባለመቻሉ በከፊል ተፈጽሞ ከቆየ በኋላ የፍርድ ባለመብት የባለዕዳውን ንብረት አፈላልጐ በማግኘት አፈፃፀሙን ለመቀጠል ሲፈልግ ይርጋ ሊቆጠር ስለሚችልበት አግባብ፣<br>•አበዳሪ የሆነ ባንክ ከዕዳው አከፋፈል ጋር በተያያዘ በባለዕዳው ላይ የአፈፃፀም ክስ መስርቶ እንደ | 74898 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ ፍቃዱ | ሚያዝያ 25/2004 | 475 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፍርዱ ለመፈፀም የማይችል መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ በሌላ ጊዜ በባለዕዳው ንብረት ላይ በፍርድ ባለመብቱ የሚቀርበው የአፈፃፀም አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384, 329(2)<br>አዋጅ ቁ. 97/90 | | ተስፋዬ (ሶስት ሰዎች) | | |
| | **ከውል ውጪ ኃላፊነት** | | | | **478** |
| 124 | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ ለተጐጂው የሚከፈል የጉዳት ካሣ አከፋፈል በአንድ ጊዜ እንዲከፈል ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2154, 2095(2) | 67225 | አቶ ኤርሚያስ ሓይሉ የሆነስት የረር ማኔጂንግ ዳይሬክተር<br>እና<br>አቶ ብርሃኑ ዳምጠው | የካቲት 26/2004 | 479 |
| 125 | በኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ከደረሰ የቃጠሎ አደጋ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የጉዳት ኃላፊነትንና ካሣን ለመወሰን፣ ጉዳቱ በምን ምክንያትና ሁኔታ እንደደረሰ፣ መብራት ሀይል ጥፋት ሳይኖር ኃላፊ ሊያደርጉ የሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎችን ስለመፍጠሩ ወይም በሥራው ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ አለማድረጉ ወዘተ ተገቢነት ባላቸው ማስረጃዎች ማንጠር ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2028,2066,2069,2027<br>በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.246,247,259 | 63231 | የኢትዩጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ ወልደ ሚካኤል ሻንቆ | ግንቦት 06/2004 | 483 |
| 126 | ለጉዳት ከሚከፈል የሞራል ካሣ ጋር በተያያዘ ልጃቸውን በሞት ያጡ ወላጆች ሁለት በመሆናቸው ለእያንዳንዳቸው 1000 ብር ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2116(3) | 69428 | አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>እነ መሐመድ አባ አሊ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 26/2004 | 486 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 127 | ብዙ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ለደረሰ ጉዳት ካሣን እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ እያንዳንዳቸው ለደረሰው አጠቃላይ ጉዳት ኃላፊ የሚሆኑ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2155(1) | 68613 | ሐጂ መሐመድ አመዴ<br>እና<br>አቶ መኮንን መስፍን | ሰኔ 18/2004 | 488 |
| 128 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ማንኛውንም ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍና የማከፋፈል ብሎም የመሸጥ ስራዎች በሚያከናውንበት ወቅት ሁሉ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የወጡ ህግጋትን በማክበር መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.86/89 አንቀፅ 13(1)<br>ደንብ ቁ.49/91 አንቀፅ 23(2), 35 | 65395 | አቶ ትዕዛዝ ኮሬ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን | የካቲት 26/2004 | 490 |
| 129 | ከአሰሪና ሠራተኛ አገናኝ አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሰዎችን ወደ ውጪ አገር የላከ ሰው በተላኩት ሰዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ካሣ የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 632/2001 | 74111 | የማህደር ኤጀንሲ ባለቤት ወ/ሮ አለምነሽ ኤርሞ<br>እና<br>ወ/ሪት አለም መስፍን ተወካይ ገበየ ደጉ | ሐምሌ 04/2004 | 495 |
| | **ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር** | | | | **498** |
| 130 | በኃላፊነት ይዞት በሚገኝ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን በመተላለፍ ዕቃን ሲያጓጉዝ የተያዘ ሰው ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብና ተፈፃሚ ስለሚሆነው የህግ ድንጋጌ<br>አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ<br>አዋጅ ቁ.368/95 አንቀፅ 79,80(1), 81,64(4)74<br>ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.113(2) | 54889 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን<br>እና<br>አቶ ንጉሴ ገብረፃዲቅ | መስከረም 26/2004 | 499 |
| 131 | በጉምሩክ ወንጀል የተከሰሰ ሰው በነፃ የተለቀቀ ቢሆንም ወንጀሉ የተፈፀመበት እቃ ወይም ማጓጓዣ | 64115 | እነ አቶ አህመድ | ጥቅምት | 502 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚወረሰው የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት ስለመፈፀሙ ፍርድ ቤቱን የሚያጠግብ ማስረጃ ሲቀርብ ስለመሆኑና ማስረጃው አጥጋቢ ካልሆነ ብቻ ፍ/ቤት እቃውን (ማጓጓዣውን) እንዳይወረስ በማድረግ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ሊያዝ የሚገባው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 104(3)(ሀ), 104(3)(ለ) | | ሁሴን (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | 08/2004 | |
| 132 | የበጐ አድራጐት ሥራን የሚሰሩ ድርጅቶች ከቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር ነፃ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.80/68 አንቀፅ 14(ለ)<br>የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ.36/68 አንቀጽ 8 | 66474 | የኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የአቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ት/ቤት<br>እና<br>የአቃቂ ቃልቲ ክፍል ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት | ጥቅምት 17/2004 | 506 |
| 133 | • ህንፃን (ቤትን) በኪራይ ይዞ የሚገለገል ወገን ለአከራዩ ከሚከፍለው የኪራይ ዋጋ ላይ በህግ የተመለከተውንና ለመንግስት ገቢ ሊሆን የሚገባውን ግብር ተቀናሽ ለማድረግ ስለመቻሉና ይህንን ለማድረግም የግዴታ የፍ/ቤት ውሣኔ የማያስፈልገው ስለመሆኑ<br>• በፍርድ የኪራይ ዋጋን ለአከራይ እንዲከፍል የተወሰነበት ተከራይ ለመንግስት የሚከፈልና ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ እንዲያስቀር የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት በመሆኑ ሙሉውን የኪራይ ዋጋ ለአከራዩ እንዲያስረክብ በአፈፃፀም ሊገደድ ስላለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 91, 101, 53(1)<br>ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 24, 2(ሽ) | 69677 | ዳሽን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ ኑረዲን መሐመድ | ታህሣሥ 20/2004 | 511 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 134 | የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ መወጣት ጋር በተያያዘ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን የመጠቀም ግዴታ የሚኖርባቸው የንግድ ፈቃድ የሥራ ዘርፍ በግልፅ ተለይቶ በተመለከተባቸው ሽያጮች ጋር በተገናኘ ብቻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.285/94 አንቀፅ 55<br>አዋጅ ቁ.609/201 አንቀፅ 50(መ)(2)<br>ደንብ ቁ.139/99 አንቀፅ 5(1)(ለ)<br>የወ/ህ/ቁ.23(2) | 74753 | እነ ሐበሻ የባህል ማዕከልና የስእል ጋለሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓቃቤ ህግ | ታህሣሥ 17/2004 | 514 |
| 135 | ከታክስ/ግብር አከፋፈል ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ያለውን ቅሬታ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱን ተግባራዊ ስለማድረግ<br>አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 107(2), 108 | 66350 | አቶ ቴዎድሮስ ደበላ<br>እና<br>የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስሥልጣን የልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | ጥር 02/2004 | 518 |
| 136 | ግብር ከፋይ የሆነ ወገን ምንም አይነት የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደ ሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሣብ መዝገቡንና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ሊከፈል የሚገባው የግብር መጠን በግምት ሊወሰን ስለመቻሉ<br>አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 69(1), 71 | 69921 | አቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር<br>እና<br>አራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ | ጥር 02/2004 | 521 |
| 137 | •ከጉምሩክ ባለስልጣን ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ወቅት የእቃ መያዣ ላይ የተደረገን ማሸጊያ መፍታት በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ | 65041 | አቶ አንዳርጌ እሸቱ<br>እና | የካቲት 30/2004 | 524 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | •በጉምሩክ ወደብ በምርመራ ላይ ካሉ ዕቃዎች ለሳምፕልነት በሚል ወስዶ አለመመለስ በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 100, 95(ሀ) | | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ | | |
| 138 | የተጨማሪ እሴት ታክስን ተግባራዊ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 49 መሰረት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ላይ ቅጣት ሊጣል ስለሚችልበት ሁኔታ፣<br>አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 49,47,50(2)<br>የወ/ህ/አ 2(2) | 68422 | እነ ጀሪኮ ሰርቪስ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | መጋቢት 14/2004 | 527 |
| 139 | ተከራይ የሆነ ወገን ለአከራይ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ለመንግስት የሚከፈለውን ግብር ሳይቀንስ ለአከራዩ እንዲከፈል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716, 1718, 1711<br>አዋጅ 286/94 አንቀጽ 56, 91, 83 | 65361 | ዘመነ ዮሐንስ ጀኔራል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ ዳውድ ኢብራሂም | ሚያዝያ 09/2004 | 532 |
| 140 | •የግብር ከፋይ የሆነ ሰው ገቢውን በህጉ አግባብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ከማሣወቅ ውጪ ደረጃውን በራሱ ሊወስን /ሊለውጥ/ የማይችል ወይም የማይገባ ስለመሆኑ፣<br>•የግብር አከፋፈል ስርዓት ለግብር ከፋዩ ግልጽ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 38<br>ደንብ ቁ. 78/94 አንቀጽ 18,22<br>አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀጽ 10(2)(ሐ)<br>አዋጅ ቁ. 587/2001 | 72824 | የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሚሊዮን አሰፋ | ሐምሌ 18/2004 | 534 |
| 141 | • ለግል አገልግሎት ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባን መኪና ለብድር መያዣነት መስጠት በወንጀል ኃላፊነትን (ተጠያቂነትን) የሚያስከትል ስለመሆኑ | 69602 | እነ አቶ አካሉ አለሙ (ሁለት | የካቲት 06/2004 | 539 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • በወንጀል ጉዳይ በቀጣት መልክ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍ/ብሔር ጉዳይ ከሚኖረው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የተለየ ስለመሆኑና ቅጣቱ በእያንዳንዱ አጥፊ ላይ ለየብቻ ሊጣል የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 73(1)<br>አዋጅ ቁ. 60/89<br>አዋጅ ቁ.280/94<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ), 41 | | ሰዎች)<br>እና<br>የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ | | |
| | **ውክልና** | | | | 543 |
| 142 | • የውክልና ውሎች በጠባቡ ሊተረጐሙ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• "በስማችን ውል እንዲዋዋል" በሚል በደፈናው የተሰጠ ውክልና ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2181(3), 2205, 2204 | 50985 | እነ አቶ ስሻህ ክፍሌ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አፀደ ዱቤ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 05/2004 | 544 |
| 143 | •ልዩ የውክልና ስልጣን ለመስጠት በተዘጋጀ ሰነድ ላይ ልዩ ውክልና ስለመስጠት በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ያለመጠቀስ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዳልተሰጠ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ<br>•የአስተዳደር አካል የሆነ ተቋም በአንድ ወቅት የሰጠውን የፅሁፍ ማስረጃ በሌላ ጊዜ ማስተካከሉ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያዩ ሰነድ ቀርቧል በሚል እንደማስረጃ ሰነድ ዋጋ የሚያጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>•በውክልና ሰነድ ላይ ለተወካይ የተሰጠው ስልጣን በይዘቱ ልዩ ውክልና የሚያመለክት ሆኖ ሰነዱ ስለ ልዩ ውልክና አስፈላጊነት የተቀመጠውን የፍ/ብ/ህ/ቁ 2208 ያለመጥቀሱ ብቻ ለተወካዩ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዳልተሰጠ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣<br>•ከሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት ጋር በተያያዘ የሚነሣ ጥያቄ የህግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 2205, 2005(1), 2179, 2199, 2203, 2204 | 72337 | ወ/ሮ ንግስቲ እምነት<br>እና<br>ቴዎድሮስ ተክሌ | የካቲት 26/2004 | 549 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 144 | አንድን ተቋም ወክሎ ውል ለመዋዋል በህግ ስልጣን የተሰጠው ሥራ አስኪያጅ ስልጣኑን ለሌላ ሰው በህግ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ አስተላልፎ ውል የተደረገ እንደሆነ ተቋሙ በሥራ አስኪያጁ በራሱ በመፈረም ውል አላደረገም በሚል ምክንያት ብቻ በውሉ አንገደድም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 2274 2214(1 2215(3),2180) | 68498 | አቶ ገብረ ክርስቶስ ገብረ እግዛብሔር<br>እና<br>ሳባ እምነበረድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ሰኔ 07/2004 | 553 |
| 145 | የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር የተደረገ ውል ከጅምሩ ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2232(2),2015(ሀ),2005(2),1204 | 73291 | እነ አቶ አፅብሃ ወልዳይ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ዙሪያሽ አሰግድ የክልሉ ፍትህ ቢሮ | ሐምሌ 04/2004 | 559 |
| 146 | •የውክልና ውል ሳይኖር ወኪል ነኝ በሚል የሚደረግ ውል ህጋዊ ውጤት አግኝቶ የሚፀናበት አግባብ ስላለመኖሩ፣<br>• የውክልና ሥልጣኑ ከመሰጠቱ በፊት የተደረገ ውል ውክልና ከተሰጠ በኋላ ሊፀና ይችላል ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑና ወካይ የሆነ ሰው የወካዩን ድርጊት እንደተቀበለ ሊቆጠር የሚችለው በህግ የሚፀና የውክልና ውል ኖሮ ነገር ግን ወኪሉ ከተሰጠው ስልጣን በላይ ሰርቶ የተገኘ እንደሆነ ወይም የውክልና ስልጣኑ ካበቃ (ከተቋረጠ) በኋላ ወካዩን በመወከል የሰራቸውን ሥራዎች በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2190, 1678 (ሐ),1719(2),1723 | 74538 | ወ/ሪት አሊያት ይማም ሙዘይን<br>እና<br>አቶ እምነቴ እንደሻው | ሐምሌ 20/2004 | 563 |
| 147 | ወካይ የሆነ ወገን በተወካይ አማካኝነት የተደረገን ህገ ወጥ ውል እንዲፈርስ በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)(2),2198,1810,1808(1),1845 | 67376 | እነ ወ/ሮ ንግስት ኪዳኔ (ሁለትሰዎች)<br>እና እነ አቶ በለጠ ወልደሰማያት(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2004 | 567 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **አፅምሯዊ ንብረት** | | | | 572 |
| 148 | ከቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጋር በተያያዘ የፊልም ባለቤት ለመሆን በማሰብ በባለሃብትና ፊልሙን ለመስራት በሚል በተደረገ ስምምነት መነሻነት ፊልሙን ለህዝብ ከማቅረብ ጋር ተያይዞ ጉዳዩ በፍ/ብሔር ክርክር ተደርጐበት በተሰጠ ውሣኔ መሰረት ፊልሙን በእጅ አድርጐ መገኘት በወንጀል ተጠያቂነት የማያስከትል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 7(1)(ሀ), 36(1)<br>የወ/ህ/ቁ.23(2), 57-59 | 70500 | ኢንጅነር አድማሱ ገብሬ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ታህሣሥ 17/2004 | 573 |
| 149 | •ከቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጋር በተያያዘ የመብቱ ተጠቃሚዎችና የመብቱ አድማስ<br>•የቅጅ መብት እንዲከበር ለመጠየቅ መሟላት ስለሚገባቸው ነገሮችና መብቱ እንደተጣሰ የሚቆጠርበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7, 9-19, 2(6) | 68369 | እነ ሳሙኤል ሃይሉ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ስምረት አያሌው /ዘጠኝ ሰዎች/ | ጥር 04/2004 | 576 |
| | **አፈፃፀም** | | | | 582 |
| 150 | ፍርድን ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በተጀመረ የአፈፃፀም መዝገብ የተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ቀርቦበት በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዙ ከተለወጠ የአፈፃፀም ሂደቱ መቀጠል ያለበት አፈፃፀሙን በጀመረው የበታች ፍ/ቤት ደረጃ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 371-385 | 64129 | ኢስላሚክ ሪሊፍ ኢትዮጵያ<br>እና<br>አቶ መሐመድ ሠይድ | ህዳር 21/2004 | 583 |
| 151 | •ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የሚንቀሳቀስ ንብረት የሀራጅ ሽያጭን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያላቸው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች<br>•የሚንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተካሄደ ጨረታ ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.432-438, 445 | 70378 | እነ አቶ ልኡልሰገድ አጥላባቸው (አራት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ፍሎራ ኢኮ ፓወር ኃ/የተ/የግል | ጥር 04/2004 | 585 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ድርጅት (ሁለት ሰዎች) | | |
| 152 | ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠን ትዕዛዝ አለማክበር ስለሚያስከትለው ውጤት፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 156, 409(1)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.400 | 65814 | ሚ/ር ቺዛኖ ቤነኛ<br>እና<br>አቶ ዘውዱ ወልደሥላሤ | የካቲት 29/2004 | 588 |
| 153 | ለባልና ሚስት በብድር ገንዘብ የሰጠ ባንክ የባልና ሚስቱ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ተወስኖ ንብረት ለመከፋፈል በአፈፃፀም ደረጃ ለሚገኝ ፍ/ቤት መብቱን ለማስከበር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 418 የሚያቀርበው የተቃውሞ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፡<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.418, 419<br>አዋጅ ቁ. 97/90<br>አዋጅ ቁ.97/90<br>የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 89 | 69385 | ዳሽን ባንክ (አ/ማ)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 28/2004 | 593 |
| 154 | አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በሚል ፍርድ ከተሰጠ በኂላ ክፍፍሉን በተመለከተ ጥያቄ የቀረበለት የአፈፃፀም ችሎት ንብረቱ ሰነድ አልባ ነው የሚል ምክንያትን ብቻ በመያዝ ለአፈፃፀም የቀረበውን መዝገብ በመዝጋት የሚሠጠው ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 225(2),423,392(1),371(1) | 73041 | ወ/ሮ ሰይዳ ደበሌ<br>እና<br>አቶ ሸሪፍ ሽኩር | ሰኔ 22/2004 | 596 |
| **የዳኝነት ስልጣን** | | | | | **598** |
| 155 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳዳር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸው የሊዝ ውሎችን መሠረት አድርጐ የሚነሱ የውል አፈፃፀምና ተያያዥ ጉዳዮችን አይቶ ለመወሰን የከተማው ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸው (የተሰጣቸው) ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ሀ) እና (መ) | 77175 | አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኢትዮጵያ<br>እና<br>እነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር (ሶስት ሰዎች) | ሐምሌ 19/2004 | 599 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 156 | ሃይማኖታዊ ከሆኑ አለመግባባቶች ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የአምልኮት ሥርዓትን ሆነ ሃይማኖታዊ ህገ-ደንቦችን በመተርጐም ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 11(1)(3), 37(1) | 66957 | የኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን<br>እና<br>በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትቤተክርስቲያን የሐዋሳ ቁጥር 2 ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት፡- | የካቲት 26/2004 | 603 |
| 157 | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የከተማው አስተዳዳር የሚያስተዳድራቸውን የንግድ ቤቶች ባለቤትነትን በተመለከተ በግለሰቦች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ)<br>አዋጅ ቁ. 408/96 አንቀጽ | 69064 | ወ/ሮ አክሊለ ገብሬ<br>እና<br>አቶ መለኮት ክንፈሚካኤል | ጥር 18/2004 | 607 |
| | **ልዩ ልዩ** | | | | **610** |
| 158 | የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ከብር 5000 በታች የሆኑ ማናቸውም የፍትሐብሔር ክርክር ለመመልከት ስልጣን አላቸው ተብሎ በአዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 50(1) የተመለከተው ድንጋጌ ተግባራዊ መሆን ያለበት የቀረበው ጉዳይ ልዩ ባህሪ እየታየ በጉዳዩ ላይ የሚነሣው የህግ ጥያቄ ውስብስብነት በመመዘኛነት (በመለኪያነት) ተይዞ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 50(1)<br>አዋጅ ቁ.25/88 አንቀፅ 5(1), 6<br>አዋጅ ቁ.416/96 አንቀፅ 41 | 54990 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን<br>እና<br>አቶ ማርቆስ አበበ | ህዳር 18/2004 | 611 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 159 | • የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች ላይ የሰጡትንና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ ለማረም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• የሰበር ስርዓት በባህሪው ከይግባኝ ሥርዓት የተለየ ስለመሆኑና በሰበር ደረጃ ተጨማሪ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን አስቀርቦ መስማትና የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ተቀብሎ ማስተናገድ አግባብነት የሌለውና ህገ-ወጥ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገመንግስት አንቀፅ 80(3)ለ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.343(1) | 55273 | አቶ ዘውዱ ግዛው እና ወ/ሮ አየለች ደስታ | ህዳር 18/2004 | 615 |
| 160 | የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለው የውክልና ስልጣኑ በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የለወጠው ከሆነ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከመቅረቡ በፊት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ), (2)(4)<br>አዋጅ ቁ.322/95<br>አዋጅ ቁ.25/88 አንቀፅ 9(2), 5(2) | 64845 | አቶ ሀብቱ ሀጋዚ እና እነ የኮምቦልቻ ግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 26/2004 | 618 |
| 161 | የፌዴራል መንግስት ተቋማት በአጠቃላይና የከፍተኛ ት/ት ተቋማት በተለይ የራሳቸው የሆነ የእድገት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አፈታትና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከናወንበት አግባብ ያለ በመሆኑ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ቀርቦ ውሣኔ የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 515/99 | 73549 | የዲላ ዩንቨርስቲ እና እነ አቶ የትናየት ጣፋ (ሶስት ሰዎች) | ሰኔ 22/2004 | 620 |
| 162 | የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ወቅት የሰጠውን የህግ ትርጉም በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ የተለየ የህግ ትርጉምና የተለየ አቋም መያዙ በቀደመው የህግ ትርጉም መሠረት ዳኝነት የተሰጠበት ጉዳይን እንደገና እንደ አዲስ እንዲስተናገድ ለማድረግ የማያስችል ስለመሆኑ፣ | 68573 | እነ አቶ ጌታቸው ዳየስ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ሩስያ ከድር | መጋቢት 12/2004 | 623 |

# ፍትሐብሔር

# ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 61480

ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደው - ጠበቃ አንተነህ ተካልኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ት ሠላማዊት ወ/ገብርኤል - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመቀሌ ቀዳማዊ ወያኔ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ መሰረትም ሟች እናታቸው ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ከአመልካች ጋር በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በጋራ ያፈሯቸው የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ጠቅላላ ድምሩ ብር 426,900.00 (አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) ከሆነው የእናታቸውን ድርሻ ግማሽ ብር 213,450.00 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር) እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ጉዳዩ በፍርድ ቀድሞ ማለቁንና በድጋሚ ዳኝነት የማይጠይቅበት መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተው ከመከራከራቸው በተጨማሪ የዋና ጉዳይ ክርክርም አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተጠሪ በክሱ የጠየቁትን ግማሽ ገንዘብ ከአራት ወንድሞቻቸው ጋር እንዲወስዱ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለመቐሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት የገንዘቡን መጠን ብቻ ወደ ብር 123,450.00 (አንድ መቶ ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር) ዝቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ ሁለቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሠጡበት በመሆኑ በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከሚቀርብ በስተቀር ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት አይደለም

በማለት መዝገቡ የመዘጋቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በጽሑፍ እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትእዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ክርክሩ የነበረው በሁለት በተመሳሳይ ክልል ኗሪ በሆኑ ግለሰቦች ሲሆን ክርክሩም የንብረት ግምት ክርክር መሆኑን፣ ክርክሩ የተጀመረው በወረዳ ፍርድ ቤት ሁኖ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን ግምት እንዲከፍሉ ወስኖ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ይኸው ፍርድ ቤትም አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑን እንዳለ በመቀበል የኃላፊነት መጠኑን ብቻ በማሻሻል መወሰኑን ነው፡፡ እንግዲህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ሲቀርብለት የመጨረሻ ፍርድ አልተሰጠበትም በማለት መዝገቡን የዘጋው በሁለቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የተለያየ ነው በማለት ነው፡፡ እኛም የዚህኑ ትዕዛዝ ተገቢነት ተሻሽሎ ከወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀፅ 16(ለ) ድንጋጌ አኳያ ተመልክተነዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለባቸው የክልል ጉዳዮች የሰበር ስልጣን የሚኖረው በወረዳ ፍርድ ቤት ተወስነው በይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለቁ ጉዳዮች መሆናቸው ሲረጋገጥ መሆኑን ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ሁለት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ ከሰጡ ውሳኔው የመጨረሻ እንደሚሆንና በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን በአዋጁ አንቀጽ 17 መሰረት አዘጋጅቶ እንደሚያቀርብ ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 93/1997 አንቀፅ 30(2(ሀ)) ስር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሁኖ የበታች ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ውሳኔ የሠጡበት ጉዳይ በድጋሚ ይግባኝ የሌለውና ሊቀርብ የሚችለው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ለመቅረብ ብቁ አይደለም በማለት መዝገቡን የዘጋው የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ሰጥተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካችን ኃላፊነትን በተመለከተ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ የወሰኑ ከመሆናቸውም በላይ ይግባኝ አቅራቢም የአሁኑ አመልካች የነበሩ በመሆኑና የይግባኝ መብት የተፈቀደው ከአንድ ጊዜ በላይ ስለመሆኑ የሚያመላክት የክልሉ የሕግ ማዕቀፍ በሌለበት ሁኔታ (ከይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አንፃር) በጉዳዩ ላይ የተለያየ ውሳኔ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበትና ሊታይ የሚችለውም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሁኖ እያለ መዝገቡ መዘጋቱ ከተሻሻለው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀጽ 16(ለ) እና 17 ድንጋጌዎች እና ከይግባኝ መብት አንፃር መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 34685 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በጉዳዩ ላይ ሁለት የበታች ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ውሳኔ የሰጡበት በመሆኑና የመጨረሻ ውሳኔ ያረፈበት በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን ለማቅረብ የሚችሉት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ነው በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ትእዛዝ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 31264

ህዳር 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ወ/ሮ እመቤት መኰንን- ጠበቃ ነቃጥበብ በየነ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት - አልተጠራም

ተቃዋሚ፡- አቶ ዓይናዲስ ገዳሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

መዝገቡ በውሳኔ ከተዘጋ በኋላ እንደገና የተንቀሳቀሰው ተቃዋሚ ሁነው የቀረቡት አቶ ዓይናዲስ ገዳሙ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደገው ክርክር መሠረት የተሰጠው ውሳኔ የእኔን መብት የሚነካ በመሆኑ ሊለወጥ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ በዚህ መሠረትም የሰበር አመልካች በቀረበው የመቃወሚያ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሁፍ ተከራክረዋል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች እና ተጠሪ በመሃከላቸው የነበረው የሆቴል ንግድ ድርጅት ቤት የኪራይ ውል ሊቋረጥ ይገባል፣ አይገባም ላይ ሲከራከሩ ቆይተዋል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልች፣ተከሳሽ ደግሞ ተጠሪ የሆነው የቀበሌ አስተዳደር፣የአሁኑ የፍርድ ተቃውሞ አቅራቢና አቶ አንተሁነኝ ገዳሙ ናቸው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪና የአሁኑ ተቃውሞ አቅራቢ ለአመልካች የንግድ ድርጅቱን እንዲያስረክቡ፣ የንግድ ድርጅቱን አከራይተው አመልካች ሊያገኙ ይችሉ የነበሩትን ገቢም እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ የሠጠ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደሩ እና የአሁኑ የፍርድ ተቃውሞ አቅራቢ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተጠሪ የሚያስተዳድረውን ቤቱን ከፈለገው ሰው ጋር የኪራይ ውል ሊያደርግ ይችላል እንጂ ከአመልካች ጋር ኪራዩን ሊቀጥል አይገባም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው አመልካችና ቀበሌ አስተዳደሩ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመጽናቱ የአመልካች የድርጅት ቤት ተከራይነት መብት ከመረጋገጡም በተጨማሪ ድርጅቱን ቢያከራዩ

ሊያገኙ ይችሉ የነበረው ገቢ ሁሉ ታስቦ እንዲከፈላቸው የገንዘቡ መጠን ተለይቶ ተወስኖላቸዋል፡፡ እንግዲህ የአመልካች የድርጅት ተከራይነት መብት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ የአሁኑ ተቃዋሚ የእኔን መብት ይነካል የሚሉትም ይህንን ውሳኔ ነው፡፡ የአሁኑ የፍርድ መቃወሚያ አቅራቢ አቤቱታውን ሊያቀርቡ የቻሉት ለአመልካች ይሰጥ የተባለው የንግድ ድርጅት ቤት በይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለተቃዋሚ እንዲሆን ተወስኖላቸው አመልካች ተቃዋሚን በሚመለከት ከአሁኑ ተጠሪ ነጥለው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሶስቱ ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ የሰ/መ/ቁጥር 31038 በሆነው ተዘግቷል በማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የተቃዋሚ አቤቱታ ወይም ክርክር በሰበር ሰሚ ችሎት ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እርሳቸውን የሚመለከት የአመልካች የሠበር አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶ እያለ አምስቱ ዳኞች የተሰየሙበት የሠበር ችሎት ደግሞ ተቃዋሚ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መብታቸውን የሚነካ ውሳኔ ሰጥቷል በሚል ነው፡፡ ይህም ተጣርቶ እንዲወሰንላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የፍርድ ተቃውሞ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ስር በተመለከተው ሥርዓት ሲሆን አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ የሚወሰነው ይሆናል፡፡ የሰበር ችሎቱ ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ የማጣራትም ሆነ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን የለውም፡፡ በእግርጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ የሚስተናገደው ለመቃወሚያው መነሻ የሆነውን ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ ይሁንና አቤቱታው የሚጣራው ወይም የሚስተናገደው ማንኛውም ክስ በሚስተናገድበት ሥርዓት በመሆኑ እና ይህም ማስረጃ መስማትንና ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ መስጠትን የሚጠይቅ በመሆኑ በሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመውን ስህተት የማረም ስልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ለተሰጠው በዚህ የሰበር ችሎት የሚታይ አይሆንም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ክርክሩ የተጀመረውና የሰበር ችሎቱም ያፀናው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሆኑ መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ለዚሁ ፍ/ቤት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ፍርድ ቤት የፍርድ ተቃውሞ አቅራቢ የክርክሩ ተካፋይ ሁነው ተረቺ የነበሩ ሲሆን በአገሪቱ የፍርድ ሰጪ አካላት የመጨረሻ አካል በሆነው ሰበር ሰሚ ችሎትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ውጤቱ ከመጽናቱም በተጨማሪ አፈጻጸሙም እንዲቀጥል በሠበር መዝገብ ቁጥር 68827 የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ምናልባት ተቃዋሚ አለኝ የሚሉትን መብት ለማስከበር ይችሉ ዘንድ መብቴን ተጋፍቶአል በሚሉት ሰው ላይ በስሙ ክስ መመስረት የሚችሉ ከሚሆን በስተቀር ቀድሞ በዚህ መዝገብ የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ለማስተናገድ የሚቻልበትን ሥርዓት ስላላገኘን ተቃዋሚ ያቀረቡትን አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ የሚስተናገድ አይደለም ብለናል፡፡ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ. 62452

ጥር 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- የሟች ወንድሙ ደምሴ ሚስትና ወራሾች

1. ወ/ሮ ዘውድነሽ እሸቱ
2. አቶ ደረጀ ወንድሙ
3. ወ/ሮ ብርሃኔ ወንድሙ

} ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ በርሄ ንስራን - ጠበቃ ከበደ ጊሹ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 49 ድንጋጌ መሰረት ክርክሩ እንዲቀጥል አቤቱታው የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች አውራሽ አቶ ወንድሙ ደምሴ ሲሆኑ ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የክሱ ይዘትም ነሀሴ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. የተጻፈና በአጭር ስርዓት እንዲታይ የቀረበ ሆኖ ዝርዝሩ፡- ተጠሪ ለሟች አቶ ወንድሙ ደምሴ ብር 440,000.00 (አራት መቶ አርባ ሺህ ብር) የያዘና በሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. የሚከፈል ቼክ ሰጥተዋቸው አቶ ወንድሙ በሕይወት እያሉ ግንቦት 02 ቀን 1997 ዓ.ም. ቼኩን ለባንክ ሲያቀርቡ በተጠሪ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ ቼኩ የተመለሰላቸው መሆኑን ገልፀው ተጠሪ የቼኩን ዋጋ ከሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድና ብር 1480 (አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ) ኮሚሽን ጋር እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ክሱ ከተመሰረተ በኂላ መስከረም 03 ቀን 1998 ዓ.ም. አቶ ወንድሙ ደምሴ ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን አመልካቾች መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ.ም. ፍርድ ቤት ቀርበው ሟች መሞታቸውን በመግለፃቸው ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ወደ ክርክሩ ለመግባት እንዲችሉ ረዘም ያለ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው በጠበቃቸው አማካኝነት ለፍርድ ቤቱ አመልክተው ፍርድ ቤቱ የከሳሽ ወራሾች የወራሽነት ማረጋገጫ ባገኙ ጊዜ መዝገቡን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትለው የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቆ ለጊዜው ተዘግቷል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካቾች ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ክርክሩ እንዲቀጥል አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ክስም በስማቸው አሻሽለው አቅርበዋል፡፡ አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ተጠሪ መከላከያ መልስ ካላቸው እንዲያቀርቡ ማስፈቀጃ እንዲያቀርቡ ተደረጎ ተጠሪ ቀርበው የመከላከያ ማስፈቀጃ አቅርበዋል፡፡ በዚህም ዋናው የቼኩ ተቀባይ ከነበሩት ከሳሾች አውራሽ ጋር የነበራቸውን የግል ግንኙነት መሰረት በማድረግ ገንዘቡ በጊዜው የተከፈለ መሆኑን ለማስረዳት እና በቼኩ ላይ

የይርጋ ክርክር ለማቅረብ ክሱን ልከላከል ብለዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ መከላከያ እንዲያቀርቡ የፈቀደላቸው ሲሆን ተጠሪ ክሱ በይርጋ እንደሚታገድና ገንዘቡም ስለመከፈሉ በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም መዝገቡ በወራሾች የተከፈተው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን ጊዜ ባለመጠበቅ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በን/ህ/ቁጥር 881(3) መሰረት የተነሳውን ይርጋ በተመለከተ ክሱ በአመልካቾች ወራሾች መቅረቡን፣ በአመልካቾች ክሱ የተሻሻለውም ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ስለቀረቡ የአውራሻቸውን ስም በራሳቸው እንዲተኩ እንጂ አዲስ ክስ በማቅረብ ያለመሆኑን ገልጾ የይርጋ ተቃውሞውን ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ተቃውሞም ከሳሾች (የአሁኑ አመልካቾች) ቀደም ብሎ አውራሻቸው የነበሩት አቶ ወንድሙ ደምሴ ክስ በተጠሪ ላይ ከአቀረቡ በኋላ መሞታቸውን እና መዝገቡም የእነርሱን ወራሽነት እስከሚረጋገጥ ድረስ ተዘግቶ ቆይቶ ከሳሾች ወራሽነታቸውን እንዳረጋገጡ መዝገቡን ማንቀሳቀሳቸውን ገልጸው ክሱን መቀጠላቸውንና ይህም በፍርድ ቤቱ ፈቃድ የተከናወነ መሆኑን ገልጾና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁጥር 49(1) እና 55(3) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ አለኝ ያሉትን መከላከያ ማስረጃ እንዲያሰሙ ቀጠሮ ተይዞላቸው የሚያሰሙት ምስክር የሌላቸውና ይህንኑ መብታቸውን የተው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማረጋገጣቸው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 440,000.00 (አራት መቶ አርባ ሺህ ብር) ቼኩ ለባንክ ቀርቦ ከተመለሰበት ከግንቦት 02 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ ከ9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድና ብር 1466.00 (አንድ ሺህ አራት መቶ ስድሳ ስድስት ብር) ኮሚሽን በመጨመር ለአመልካቾች እንዲከፍሉ፣ የክሱን ወጪ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸውን በመጠበቅ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች በወራሽነታቸው ክሱን የቀጠሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1) እና 55(3) ድንጋጌዎች ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው ተብሎ ብይን የመስጠቱን አግባብነት በጭብትነት በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ በወራሽነት ክርክር ለመቀጠል ጥያቄው በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ከአንድ አመት ከስድስት ወር የማይበልጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1)፣55(2) እና 33(3) ድንጋጌዎች ጥምር ንባብ እንደሚያስረዳ በመዘርዘር ይኸው የጊዜ ገደብ ከአለፈ በኋላ አመልካቾች ክሱን ማቅረባቸውን ማረጋገጡን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች በአውራሻቸው የቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ በሰጣቸው ፈቃድ መሰረት ለጊዜው አዘግተው ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ ክሱን የቀጠሉና የወራሽነት ማስረጃ በሕጉ አግባብ የተሰጠው ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ቢሆንም መብት አለኝ በሚል ወገን ተቃውሞ በመቅረቡ ምክንያት በፍርድ ቤት ታግዶ ቆይቶ የተቃውሞ ክርክር ውድቅ ከሆነ በኋላ መጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. የወራሽነት ማስረጃው ለአመልካቾች ሲሰጥ መዝገቡን ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ማንቀሳቀሳቸው ተረጋግጦ እያለ ቀድሞ ባለቀ ጉዳይ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመስርቶ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49/(1)፣55(2) እና 55(3) ድንጋጌዎች መሰረት በአንድ አመት ከስድስት ወር ይርጋ የታገደ ነው በማለት መወሰኑ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃ

ባገኙ ጊዜ መዝገቡን እንዲያንቀሳቅሱ በፍርድ ቤት ፈቃድ መዝገቡ ተዘግቶ ከቆየ በኋላ የወራሽነት ማስረጃው በተገኘ ጊዜ ተሻሽሎ ለቀረበው ክስ ሟች የሞቱበት ጊዜ መሰረት ተደርጎ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1)፣ 55(2) እና 55(3) መሰረት በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1) ድንጋጌ መሰረት ክሱን ለመቀጠል መብት አለኝ የሚሉ ወገኖች ዋናው ከሳሽ ወይንም ከሳሾች በሞቱ በአንድ አመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድላቸው ሳያመለክቱ የቀሩ እንደሆነ የተጀመረው ክርክር ውድቅ እንደሚሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(2) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ ክሱን ለመቀጠል መብት አለኝ የሚል ወገን ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድለት ማመልከቻውን የሚያቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ሲሆን ከሳሽ ወይም ከሳሾች በሞቱ በአንድ አመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል ሳያመለክቱ መቅረታቸው ከተረጋገጠ የተጀመረው ክርክር ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚደነገግ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላም ጥያቄው ሲቀርብ ተቀባይነት የሚገኝበት አግባብ መኖሩን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 55(2) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት ከሳሹ ራሱ ወይም ከሳሽ የነበረው የሟቹ ንብረት አስተዳዳሪ ነኝ የሚል ባለአደራ ወይም የከሰረው ከሳሽ ንብረት አስተዳዳሪ የሆነ ሰው ወይም የዋናው ከሳሽ መብት ተላልፎልኛል የሚል ሰው ክሱ ቀሪ በሆነ ወይም በተሰረዘ በስድስት ወር ውስጥ የቀረበው ክስ እንዲቀጥል ወይም መሰረዙን እንዲነሳለት ለማመልከት የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክሱ ቀሪ የሆነው ወይም የተሰረዘው በከሳሹ ጉድለት ያለመሆኑን የተረዳው እንደሆነ ይህ ምክንያት ስላደረሰው ኪሳራ ተገቢ መስሎ የታየውን ወስኖ የቀረው ወይም የተሰረዘው ክስ እንዲቀጥል ለማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 55(3) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ይህ ድንጋጌ አቤቱታው ክሱ ቀሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ በሚቆጠር ስድስት ወራት ውስጥ መቅረብ እንዳለበትና በበቂ ምክንያት መደገፍ እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን በቂ ምክንያት የሚለውን ሐረግ ግን መመዘኛው ምን እንደሆነ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ ይሁን እንጂ በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሚለው ጥያቄ አመልካቹ በተገቢው ጊዜ አስፈላጊውን ስርዓት ያልፈፀመበት ምክንያት ተገቢ የሆነ ምክንያት ስለነበረው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን በመመልከት በፍርድ ቤቱ አዎንታዊ ምላሽ ከአገኘ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ለመደምደም የሚችልበትን አግባብ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49 እና 55(2) እንዲሁም 55(3) ድንጋጌዎች ሲታዩ ክርክሩን ለመቀጠል የአንድ አመት ጊዜ ከአለፈ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑንና ይህ የጊዜ ገደብ በማለፍ መዝገቡ ከተዘጋ ወይም ክሱ ቀሪ ከሆነ በኋላ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ክርክሩ እንዲቀጥል ወይም ቀሪ የሆነ ክስ እንዲንቀሳቀስ በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን አቤቱታ አቅራቢው ከገለፀ እና ፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅራቢው አስፈላጊውን ስርዓት ያልፈፀመበት ምክንያት ተገቢ በሆነ ምክንያት መሆኑን ከተረዳው ክርክሩ እንዲቀጥል ማድረግ የግድ የሚል መሆኑን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ከሳሽ በመሞቱ ምክንያት የተዘጋ መዝገብን ለማንቀሳቀስ ፍጹም የሆነ ይርጋ የአንድ አመት ስድስት ወራት ጊዜ ነው ቢባል እንኳ ፍርድ ቤት መዝገቡ ተዘግቶ የቆየበትን ጊዜ በማስላት ብቻ ጊዜውን መቁጠር ያለበት ሳይሆን

በጊዜ ገደቡ ውስጥ ጥያቄውን ያቀረበው አቤቱታ አቅራቢ የቆየበትን ሁኔታ ሁሉ አግባብነት ካላቸው ሌሎች የመሰረታዊ ህግ ድንጋጌዎችና አንድ ሰው ከሳሽ ለመሆን መሟላት ያለባቸውን የስነ ሥርዓት ሕግ መስፈርቶች ማየትን የግድ የሚል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ሟች ክስ መስርተው ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ መዝገቡን እንዲዘጋላቸው የጠየቁት የወራሽነት ማስረጃ ይዘው እስከሚቀርቡ ለጊዜው መሆኑን፣ ፍርድ ቤቱም አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃ ይዘው እንዲቀርቡና በስነ ስርአት ሕጉ መሰረት አቤቱታቸውን እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው መዝገቡ ተዘግቶ የቆየ ሲሆን አመልካቾች የሟች አቶ ወንድሙ ደምሴ ወራሽነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በፍርድ ቤት እንዲሰጣቸው ጥቅምት 17 ቀን 1998 ዓ.ም. አቤቱታ አቅርበው ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ውሳኔ የተሰጣቸው ሚያዝያ 29 ቀን 1998 ዓ.ም. መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ይኸው የወራሽነት ማስረጃ በሌላ ወራሽ ተቃውሞ ቀርቦበት ወዲያውኑ እንዳይሰጣቸው ታግዶ ቆይቶ ማስረጃው መጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. ከተሰጣቸው በኋላ ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም. በፍርድ ቤቱ ፈቃድ የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው ጥያቄ ማቅረባቸው በፍሬ ነገር የተረጋገጡት ነጥቦች ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ አቤቱታውን ማቅረብ የሚችሉት የወራሽነት ማስረጃ ከተሰጣቸው በኋላ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ድንጋጌ መንፈስ የሚያሳየን ነጥብ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ መሆን የሚችለው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ለመሆን የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነውና፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49 እና 55(3) ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች እንደመሆናቸው መጠንም የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው መቼ ነው? ከሚለው ጥያቄ አንጻር ጉዳዩ መታየት ያለበት ነው፡፡ ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 48 ድንጋጌዎችን ይዘት መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 ድንጋጌ መሰረት የይርጋ ጊዜ መነሻው በመብት መስራት የሚቻልበት ጊዜ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 48 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ ክርክሩ እንዲቀጥል የሚያስችለው መብት የማይቋርጥ ከሆነ የከሳሽ ወይም የተከሳሽ መሞት ክርክሩን እንዲቆም አያደርገውም በሚል ተቀምጧል፡፡ ከዚህ የስነ ስርዓት ድንጋጌ ውስጥ "ክርክሩ እንዲቀጥል የሚያስችለው መብት የማይቋረጥ ከሆነ" የሚለው ሐረግ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826(2) እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1986 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ የሚታይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ መብት አንድ ሰው ሊሰራ ይችላል ተብሎ የሚታሰበው ተገቢውን የወራሽነት ማስረጃ ከያዘ በኋላ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን የያዙበት ጊዜ መጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. በመብታቸው መስራት የሚችሉበት ጊዜ ነው ተብሎ መያዝ የሚገባው ሲሆን ከዚህ ጊዜ በፊት ያለፈው ጊዜ ፍርድ ቤቱ ፈቅዶና በተቃውሞ የተነሳ በወራሽነት ማስረጃ ላይ ክርክር ሲደረግ ያለፈ በመሆኑ በአመልካቾች ጉድለት እንደአለፈ ጊዜ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ ይኸው ጊዜ ሟች ከሞቱበት ከመስከረም 4 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ካለው ጊዜ ጋር ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49፣ 55(2)፣55(3) ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ አልፏል ብሎ መደምደም ምክንያታዊነት ያለውና በሕግ የሚደገፍ ነው ብሎ ለማሰብ የሚቻል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የይርጋ ጊዜ ማለፍ አይነተኛ አላማም ዳተኛውን ተከራካሪ ወገን መቅጣት ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን ለማግኘት ያለፈባቸው ጊዜ በዳተኝነታቸው ያለፈ ጊዜ ነው ሊባል አይችልምና፡፡ በመሆኑም ከመጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲታይ አመልካቾች አቤቱታቸውን ያቀረቡት ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም. መሆኑ በመረጋገጡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49፣55(2) እና 55(3) ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ አልፏል ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም

መሰረት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ቀጥሎ የተመለከትነው ኃላፊነትን የሚመለከተውን ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የቼክ ጉዳይ ሲሆን ክሱ የቀረበው በአጭር ሥነ-ሥርዓት ሆኖ ተጠሪ በተከሳሽነታቸው የመከላከያ ማስረጃ ካላቸው ማስፈቀጃ እንዲያቀርቡ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንዳላቸው ለስር ፍርድ ቤት ገልጸው ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው የነበረ ሲሆን ተጠሪ ግን ማስረጃ የማሰማት መብታቸውን የተውት መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማረጋገጣቸው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ከክሱ ነፃ ያደረጉት በዚህ ችሎት ተገቢነት የለውም የተባለውን የስነ ስርዓት ይርጋ መሰረት በማድረግ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረጉ ተጠሪ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት ከአረጋገጡት ነጥብ እና ከፍትሃ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አይነተኛ አላማ አንጻር ሲታይ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቼክ ሆኖ የመከላከያ ማስረጃ ያልቀረበበት እንደመሆኑ መጠን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከደረሰበት መደምደሚያ ውጪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚመለከተው የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጥያቄ የሌለ በመሆኑ በዚህ ችሎት ውሳኔ የመጨረሻ እልባት መስጠቱ የሥ-ሥስርዓት ሕጉን የጠበቀ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሰረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና እንደቀረበም የሚከፈል ገንዘብን ተክቶ የሚሰራ ሰነድ ስለመሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 827/ሀ/እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ቼክ መብቱ ከሰነዱ ተነጥሎ የማይሰራበት፣ የቼኩ አውጪውም ቼኩ ላይ ለተፃፈው ገንዘብ አከፋፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑንም ከእነዚህ ድንጋጌዎችና ከን/ሕ/ቁጥር 840፣ 868(ሐ) እና 872 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም ቼክ ባልተከፈለ ጊዜ አውጪውም ሆነ ፈራሚዎቹ ለቼኩ አከፋፈል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡ ቼክ በባሕሪው ገንዘብን ተክቶ የሚሰራና በቀላሉ ወደ ተለያዩ ሰዎች ሊተላለፍ የሚችል በመሆኑም ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ ሕጉ ለይቶ በአስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ በማንኛውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ አይችልም፡፡ በዚህም መሰረት በን/ሕ/ቁጥር 717 እና 850 ስር የተመለከቱት መቃወሚያዎች ባጋጠሙ ጊዜ አውጪው ወይም ፈራሚዎች ቼክ ሊከፈል የማይገባበትን መቃወሚያ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በቼክ አከፋፈል ላይ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው እዳ ከፋዩ ሰነዱን በያዘው ሰው በሁለቱ የግል ግንኙነት ላይ በተመሰረቱት በሰነዱ አፃፃፍ ፎርምና እንዲሁም በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች ላይ፣ ፊርማን በማስመሰል የተሰራ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሥልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የተነሱት መቃወሚያዎችን፣ አምጪው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ እዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው ከሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በድንጋጌው ተዘርዝረው በተገለፁ ሁኔታዎች በቼክ የተከሰሰ ሰው አንዳንድ መቃወሚያዎችን በማቅረብ ከእዳው ራሱን ነፃ ማድረግ እንደሚችል ሕጉ ሥርዓቱን ዘርግቷል፡፡ በቼኩ የተከሰሰ ሰው የግል ግንኙነትን መሰረት ያደረገ መቃወሚያ ሊያነሳ የሚችለው ከአምጪው ጋር ያለውን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ለቼኩ ኃላፊ ተብለው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠው ቼኩን አውጪ መሆናቸውና ቼኩ ባንክ ሲቀርብም በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ በመመለሱና ተጠሪ በን/ሕ/ቁጥር 717 መሰረት አለኝ ያሉትን መቃወሚያ ሊያስረዳ

የሚችል ማስረጃ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው ከላይ የተጠቀሱት የንግድ ሕግ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49፣55(2) እና 55(2) ድንጋጌዎችን በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጋር ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ግን ሕጉን የተከተለ ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77636 ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 52763 መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57668 ጥር 08 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰጠው ብይንና በ6/6/2001 ዓ.ም. የተሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ. 71316

ግንቦት 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገፈ ፈጅ ዮሴፍ ቀውዬ

ተጠሪ፡- ለገሠ ጌታሁን ጠበቃ አቶ ለገሠ ማሞ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ፍ/ቤት በንብረት ላይ የሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 እንደተደነገገው መልሶ ለማስነሳት የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

በከሣሽ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በተከሣሽ አቶ ኃይሉ ሃብቴ መካከል በነበረው የብድር ገንዘብ ክርክር ከሣሽ ለፍርድ አፈፃፀም ዋስትናው ይሆነው ዘንድ በተከሣሽ እና በባለቤቱ ስም ተመዝግቦ በሚገኘው ት/ቤት ላይ ክሱ በቀረበበት ፍ/ቤት አማካኝነት ታግዶ እንዲቆይ የሚያስችል ትዕዛዝ ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡

የአሁን ተጠሪ በበኩል ህዳር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ይህ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ንብረት ከተከሣሽ እና ከባለቤቱ ጋር በተደረገ የሽያጭ ስምምነት በግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 80,000.00 ገዝቻለሁ፡፡ ይህንንም የሽያጭ ውል ያደረግነው በሲዳማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ነው፡፡ እንደውሉ ሻጭ ሊፈጽሙ ስላልቻሉ ለሽቢዳኖ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤ ስመ-ሀብትነቱን ወደ ስሜ ለማዞር ስሞክር መታገዱን ተረድቻለሁ፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በህግ አግባብ በገዛሁት ቤት ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሣልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካችም የዕግድ ትዕዛዙን የማይነሳበትን ምክንያት በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በቀድሚያ የተመለከተው የሲዳማ ዞን ከፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ለማንሳት የሚያበቃ ክርክርና ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የዕግዱ ትዕዛዝ አይነሣም የሚል ዳኝነት ሲሰጥ፤ ይግባኝ ሰሚው የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ የሽያጩ ተግባር የተፈፀመው የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለሆነ የሽያጭ ውሉም በሚመለከተው አካል በመመዝገቡና በህግ የሚጠየቀውም መስፈርት ውሉ በመዝገብ መፃፍን እንጂ የስመ ሃብትነት ዝውውር በግልጽ

በሕግ እንደ ማሚያ ስላልተመለከተ ቀደም ሲል የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ሊነሣ ይገባል በማለት ሽሮታል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የተለየ ዳኝነት ጉድለት የለበትም በማለት የአሁን ተጠሪን ሳይጠራ አመልካችን በማሰናበቱ ይህ የሰበር ክርክር ሊቅርብ ችሏል፡፡

በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሑፍ ያቀረቡ ሲሆን በይዘቱ ከዚህ በፊት ካቀረቡት የተለየ አይደለም፡፡ የተለየው ነጥብ ቢኖር ቀደም ሲል በሻጭ ላይ ባቀረቡኩት ክስ መሠረት አስወስኜ የፍርድ ባለመብት መሆኔም ይታወቅልኝ የሚለው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአሁን ተጠሪ በፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ሊነሣልኝ ይገባል ሲል ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ፤ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሣ ይገባል ለሚለው ዳኝነቱ መሠረት ሆኖ የተያዘው የአሁን ተጠሪ የት/ቤቱን የሽያጭ ውል በሲዳማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤቱ አድርጓል፤ አስመዝግቧል የሚለውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ፊት ውል የማድረግ ተግባር አስፈላጊነቱ ከውል አመሠራረት ጋር የተያያዘ፤ ውሉ ተደርጓል፣ አልተደረገም? የሚለውንና በውሉ ስለተካተቱት ዝርዝር ጉዳዮች (As to any terms of the contract) ወደ ፊት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ክርክር እንዳይፈጠርና እንዳይነሣ ለማድረግ ሲባል የውል አደራረግን ሂደት የማረጋገጥ (authentication) መሆኑንና ውጤቱም በተዋዋይ ወገኖች መካከል ለሚነሳ ክርክር እልባት በመስጠት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

አንድን ንብረት በሽያጭ ውል ገዝቻለሁ፤ ስለሆነም በዚህ ንብረት ላይ ያለ እኔ ሌላ ሶስተኛ ወገን መብት የለውም በማለት ማናቸውንም ሶስተኛ ወገን ለመመለስ ግን ት/ቤቱ በሚገኝበት ሥፍራ በሚገኘው ንብረትን መዝግቦ ለመያዝ ስልጣን በተሰጠው ማዘጋጃ ቤት የምዝገባ ሥርዓቱ ሊከናወን እንደሚገባ በንብረት ህጉ እና በውል ህጉ ከተመለከቱት አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር በእነዚህ በውል አደራረግ ሥርዓት ማሚያነት በቀረበው ውልን የማረጋገጥ ተግባር እና ሶስተኛ ወገንን ለመጠበቅም ሆነ ለመመለስ እንዲያስችል የተቀመጠውን የምዝገባ ሥርዓት (registration) ምንነትና ተግባር በውል ካለማጤን በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት የተሰጠበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እንዲሁም የአሁን ተጠሪ በንብረቱ ላይ አስወሰኜ በፍርድ ባለመብትነት ደረጃ ላይ እገኛለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር እንደ አግባብነቱ ይኸው ንብረት ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል ለማድረግ በተከበረ ጊዜ የቀደምትነትን መብት ለማስረዳት የሚያግዘው ካልሆነ በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 የተሰጠን የእግድ ትእዛዝ ለማስነሣት የሚያስችል አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የዕግድ ትእዛዙ ሊነሳ ይገባል በማለት የሰጡት ትርጉም የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 67656 ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፤ እንዲሁም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 51779 መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሸሯል፡፡
2. በአንፃሩ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19703 ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ የዕግድ ትዕዛዝ ይነሣልኝ ሲል ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የህግ መሠረት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 67127
ሰኔ 08 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አበራ ሁንዴ ከጠበቃ አቶ ደረጀ ኢተቻ ጋር ቀረቡ
ተጠሪ፡- የፊንፍኔ የደን ደርጅት ነገረ ፈጅ አቶ ዳንኤል ኢፎ - ቀረቡ
መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት የተገኘን መብት መቃወም የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በሱሉልታ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት በአሁን አመልካች በአቶ አበራ ሁንዴ እና በሥር 1ኛ ተከሣሽ በነበረው የኦሮሚያ ኢንቪስትመንት ኮሚሽን መካከል ከከሣሽ ዕውቅና ውጭ በከሣሽ ይዞታ ላይ ያደረጉት ውል/ስምምነት ይፍረስልኝ በማለት የአሁን ተጠሪ የፊንፍኔ የደን ድርጅት መጠየቁን የሚያስረዳ ነው፡፡

ተከሣሽም ቀርቦ ያነሳውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ፍ/ቤቱ ውድቅ ካደረገ በኋላ ከሣሽ የፊንፍኔ የደን ድርጅት  በእኔ ይዞታ ላይ ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ይፍረስልኝ በሚል ክስ ያቅርብ እንጂ ይዞታው የእራሱ ለመሆኑ በቀጥታ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በኢንቨስትመንት ቢሮ አማካኝነት ለ2ኛ ተከሣሽ ለአሁን አመልካች የተሰጠው የመሬት ይዞታ የከሣሽ የፊንፍኔ ደን ድርጅት ይዞታ ለመሆኑ የሚያሳይ ካርታ የለም በሌላ በኩል የፊንፍኔ የደን ድርጅት ከክሱ ጋር አያይዞ ካቀረበው የማስረጃ ዝርዝር ውስጥ 2ኛ ተከሣሽ አበራ ሁንዴ ይህንን ክርክር የተነሳበትን የመሬት ይዞታ አስመልክቶ በሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ካስወሰነ በኋላ ከኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ካርታ እንዲሰጣቸው ተብሎ የተወሰነ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳቀረበ ተረድቻለሁ ስለሆነም 1ኛ የመሬት ይዞታው ባለመብት ለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡና 2ኛ ክርክር ያስነሳውን የመሬት ይዞታ አበራ ሁንዴ በውሣኔ ያገኘው መሆኑን ስለተረጋገጠ በዚህ የመሬት ይዞታ ላይ ከሣሽ የፊንፍኔ የደን ድርጅት ክስ የማቅረብ መብት ያለው ሆኖ አልተገኘም በማለት ወስኗል፡፡

በአሁን ተጠሪ በፊንፍኔ የደን ድርጅት  የይግባኝ ቅሬታ አቅራቢነት መነሻ ጉዳዩን  በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ  ሰሜን ሸዋ  ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ፤ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የሁከት ይወገድልኝ ጉዳይ  እንደሆነ ገልፆ ተከሣሽ አበራ ሁንዴ በፊንፍኔ ደን ድርጅት የመሬት ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥሯል ወይስ አልፈጠረም? የሚለውን ጭብጥ ለመለየት እራሱ ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ማስረጃ ተመልክቻለሁ፡፡ እንደተመለከትኩትም በጉዳዩ ላይ የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በቁጥር ከአይኦ/ፋይ/127/2001 በ08/03/2001 ዓ.ም የተፃፈው ደብዳቤ የሚያስረዳው አበራ ሁንዴ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መስርቶ

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይዞታው የአበራ ሁንዴ መሆኑን አረጋግጦ ውል እንዲፈርምና የተዘጋጀለት የይዞታ ካርታ እንዲሰጠው በወሰነው ውሣኔ መሠረት በዚህ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ታዞ ፈቃድና የመሬት ይዞታውን ማረጋገጫ ካርታ እንደሰጠ የሚያረጋግጥ ነው የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ፈቃድና የመሬት ይዞታ ካርታ ለአበራ ሁንዴ የሰጠው ኮሚሽኑ እራሱ ሳይሆን በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ስለመሆኑ ከላይ እንደተገለፀው የእራሱ የከሣሹ ማስረጃ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በዚህ ውሣኔ ላይ ተቃውሞ ቀርቦ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ ማንኛውም አካል በፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ አበራ ሁንዴም መሬቱን ያገኘው በፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ስለሆነ በፊንፍኔ ደን ድርጅት ላይ ሁከት ፈጥሯል ለማለት አይቻልም፡፡

ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ የእራሴ የመሬቱ ይዞታ ከህግ ውጭ ተሰጥቶብኛል የሚል ከሆነ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ ማስረዝና የውሣኔውን ህገ-ወጥነት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን አላደረገም ስለሆነም መልስ ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት የሥር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁን ተጠሪ ከዚህ በላይ የተገለፀው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ላቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 103065 የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት በፊንፍኔ ደን ድርጅት ወሰንና ቁጥጥር ስር ያለ ስለመሆኑ ተከሣሽ ክዶ ያቀረበው ክርክር ስለሌለ እንዳመነ ይቆጠራል ከዚህም በቀር የይዞታ መሬቱ የፊንፍኔ ደን ድርጅት ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃ ቀርቧል፡፡ የኢንቨስትመንት ቢሮም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ተገዶ በዚሁ መሬት ላይ ፈቃድና ካርታ ለአበራ ሁንዴ መስጠቱን እንጂ በኢንቨስትመንት ቦርድ ታይቶ የተሰጠ አለመሆኑን በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ከአበራ ሁንዴ ጋር ተከራክሮ የተሰጠ ውሣኔ ካለ ሁለቱ ወገኖች በፈለጉት ሁኔታ ተከራክረው በተሰጠ ውሣኔ የመሬቱን ባለይዞታ ያስገድዳል የሚለው በጥርጣሬ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው የሚለውን ሁሉ መሠረት አድርጎ የኢንቨስትመንት ቢሮ እና አበራ ሁንዴ ያደረጉት ህገወጥ ውል እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁን አመልካች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ከተለያዩ የመከራከሪያ ነጥቦች አንፃር ቅሬታውን ዘርዝሮ ለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ተጠሪ የፊንፍኔ ደን ድርጅት ቀርቦ የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡

እኛም ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር እና በሥር በየደረጃው ከተሰጡት ውሣኔዎች አንፃር ጉዳዩን እንደተመለከትነው ግራ ቀኙን ያለያያቸው ነጥቦች ከአንድ በላይ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህ ጭብጦች መካከል ለጉዳዩ አወሳሰን ለአንዱ ቀድሞ ዕልባት መስጠት ብቻ ሌላውንም ክርክር ሊያስቀር እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/3/ እንደተደነገገው የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሳውን መሬት በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት በይዘታው ሥር የገባ መሆኑ ከተረጋገጠ የመሬቱ ባለይዞታ ነኝ የሚለው የአሁን

ተጠሪ ይህንኑ ይዞታ በዳኝነት ሊያስመልስ የሚችልበት ሥርዓት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በቅድሚያ ምላሽ የሚያሻው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአሁን አመልካች በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12536 በሆነው በቀረበው ክስ መነሻ ይህንኑ ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን የመሬት ይዞታ በሚመለከት የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ጽ/ቤት ከአመልካች ጋር ውል እንዲፈፅም፣ ፈቃድ እና ካርታም እንዲሰጥ የተወሰነበት ለመሆኑና በዚህም ውሣኔ መሠረት ውሉን እንዲደረግ ፈቃድና ካርታም እንደሰጠ በየደረጃው በሶስት እርከን በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ውሣኔ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳቀረበው የሚያነሳው ክርክር እኔ በማላውቀው ውሣኔ ልገደድበት አይገባም የሚል ነው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰጠው ትንታኔ የተመረኮዘው ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በፈለጉት አኳኋን በሌላ ሰው የይዞታ መብት ላይ ተከራክረው ውሣኔ ቢያስወስኑ ይህ ውሣኔ የንብረቱን ባለይዞታ ሊያስገድደው አይችልም ህግና ደንብን ተከትሎ ባልተሰጠ ውሣኔ መሠረት ኢንቨስትመንት ቢሮ ተገዶ የፈፀመው ውል  እና የሰጠው ፈቃድ እና ካርታ ህገ ወጥ ነው፡፡ ይህ ህገ ወጥ ውል ደግሞ ሊሰረዝ ይገባል በሚለው ምክንያት ላይ ነው፡፡

እኛም ይህንኑ የተጠሪን ክርክር እና የሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ፍርድ መነሻ ያደረገውን ትንታኔ ያለውን ህጋዊ መሠረት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በአንድ ጉዳይ በከሣሽነትና በተከሣሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል ብቻ ክርክር ቢጀመር እነዚህ ወገኖች በሚከራከሩበት ጉዳይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ካለ ክርክር መጀመሩን እንዳተረዳ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ በመግባት መብቱን የማስከበር መብት ያለው ስለመሆኑ የጉዳይ አመራር ፍትሃዊ እንዲሆንና በሥርዓት እንዲከናወን ለማስቻል ሲባል በተደነገገው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ሥርዓቱ ተዘርግቷል፡፡

ክርክሩ መጀመሩን ሳይረዳ እና ሳያውቅ ጉዳዩ በከሣሽነትና በተከሣሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል የተደረገው ክርክር ተጠናቆ መወሰኑ እንኳ ቢታወቅ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በውሣኔው መብቴ ተነክቷል የሚለው የክርክር ተካፋይ ያልነበረው ሰው ይህንኑ ውሣኔ ለመንቀፍ፣ ለመቃወም የሚችልበትም ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 እና ተከታይ ድንጋጌ ተበጅቷል፡፡

በዚህ ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት መብቱን ከማስከበር ጀምሮ ከታች ወደ ላይ በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች አማካኝነት ይህ መሰል ተከራካሪ ወገን እርሱ የክርክር ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠው ውሣኔ ያስከተለበትን የፍትህ መጓደል ለማረም በሚያስችል  ሁኔታ የተሟላ የማስተካከያ  ሥርዓት በሀገራችን የህግ ሥርዓት  ተቀምጧል፡፡

አንዱ በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በጎኒዮስ ክርክር ከጀመረበት ጊዜ  ጀምሮ በውሣኔ እስኪቋጭ  ድረስ ባለው የክርክር ደረጃ የተፈፀሙት የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶች በእራሱ በፍ/ቤቱ የሚታረሙበትን አግባብ እና ሥርዓት ካስቀመጠ እንዲሁም በውሣኔ ከተቋጨም በኋላ እንኳ ውሣኔው በእራሱ ውሣኔውን በሰጠው ፍ/ቤት እንደገና የሚታይበትን  አማራጭ፣ ከዚህም በቀር እንደሁኔታው ከታች ወደ ላይ በይግባኝ አማካኝነት የተፈፀሙ የክርክር ግድፈቶች የሚታረሙበትን ሥርዓት በበቂ ሁኔታ ከዘረጋ በኋላ በዚህ በተዘረጋው ሥርዓት አለመፈፀም

ወይም በዚሁ የማስተካከያ ሥርዓት አለመመራት ምን ውጤት እንደሚያስከትል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

በአንድ ጉዳይ የክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች እነማን ናቸው? በክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባው ሲታለፍ በምን አኳኋን መታረም እንደሚገባው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሠረት አንዱ በሥነ-ሥርዓት ህጉ ሽፋን የተሰጠው ጉዳይ ሆኖ ልዩ ልዩ አማራጮች ተደንግገዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ጉዳዩ ሊመራ ያልቻለ መሆኑን የተገነዘበ ወገን ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ ጣልቃ በመግባት፤ ከተወሰነም በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት አማካኝነት ውሣኔው ተነስቶ እንደገና በሚታይበት ሥርዓት መጠቀም እንደሚችል በህጉ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በቀር ሥርዓት ሳይከተሉ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ የሥነ-ሥርዓት ጉድለት አለበት በማለት ብቻ ውሣኔው ዋጋ አልባ ሊሆን እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 ተደንግጓል፡፡

ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ክርክሮችን በዘፈቀደ ሳይሆን በሥርዓት በመምራት በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ወጭ እንዲቋጭ ለማስቻልና የሀገሪቱ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ተገማች እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው የህግ ትርጉም ላይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ከሣሽና ተከሣሽ በፈለጉት አኳኋን ተከራክረው የሚሰጠው ውሣኔ በክርክሩ ተሳታፊ ያልነበረን ወገን ከቶውንም ቢሆን ሊያስገድደው አይችልም በማለት የተከተለው አተረጓጐም ሥርዓት ያልተከተለ፤ ማናቸውም ክርክር በሥርዓት ሳይሆን በዘፈቀደ እንዲከራከር በር የሚከፍት ለህግ የበላይነት ተፃራሪ የሆነ አተረጓጐም በመሆኑ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሳውን የመሬት ይዞታ በእጁ ያደረገው በፍ/ቤት ውሣኔ መሆኑ ስለተረጋገጠ የአሁን ተጠሪ ይህ ውሣኔ መብቴን ነክቷል የሚል ከሆነ ሥርዓቱን ጠብቆ ማስለወጥ ከሚችል በቀር በዚያው ጉዳይ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሥርዓት በሌለበትና ይህንን ለማድረግም ተጠሪ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ያለ ሥርዓት የቀረበውን ክስ መነሻ አድርጎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓታዊ ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 103065 በ07/6/2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪ በዚህ የፍርድ ሐተታ እንደተገለፀው ቀደም ሲል በመ/ቁ 12536 የተሰጠው ውሣኔ የይዞታ መብቴን ያስቀረ፤ መብቴን የነካ ነው በማለት ለመንቀፍ በሥነ - ሥርዓት ህጉ መሠረት መጠየቅና ማሳረም የሚችል ከሆነ በዚሁ ሥርዓት መሠረት ከመፈፀም በቀር በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ ሌላ አዲስ ክስ በሌላ ፍ/ቤት በማቅረብ ለማስለወጥ የሚያስችል መብት የለውም ብለናል፡፡
3. የዚህ ሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 72189

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ካሳዬ ያደቴ ከጠበቃ ኮ/ል መላኩ ካሣዬ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሲኞር ፍራንችስኮ ቬንሲያን የቀረበ የለም

መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች ከፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በአደራ የተረከባቸውን የተጠሪ ንብረቶች አልመለሰም በሚል ተጠሪ የንብረቶቹን ዝርዝር እና ግምት በመጥቀስ ባቀረበው ክስ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረ ሁኖ አሁን የሚያከራክረው መቆፈሪያ ማሽን በተመለከተ ሲሆን ይሄው ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማሽኑ ተገምቶ ፍርድ እንዲሰጥበት በመለሰው መሠረት አመልካች ማሽኑ ያለበትን ቦታ ማሳየት ባለመቻሉ ከዚህ ቀደም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አሁንም በርትዕ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በመወሰኑ እና ይሄው ውሣኔ በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመጽናቱ የተፈጸመው መሠረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች በማንሳት ያቀረቡ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፡- በዚህ ጉዳይ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማሽኑ ተገምቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት ወደ ታች ፍርድ ቤት መልሶ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይሄንን ሳያከብሩ አሁንም በድጋሚ በርትዕ ውሣኔ መስጠታቸው ተቀባይነት ያለው አካሄድ ባለመሆኑ አመልካች በበታች ፍርድ ቤትም ሆነ በተለያዩ አካላት ባቀረበው አቤቱታ ሌሎች እቃዎችን እንጅ የመቆፈሪያ ማሽን ያልተረከበ ስለመሆኑ ተከራክሮ እያለ እና ሌሎቹን የተረከባቸውን ደግሞ በብር 8,000 /ስምንት ሺህ ብር/ መሸጣቸውን የተከራከሩ በመሆኑ፣ በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረብናቸውም ሰዎች ብረታ ብረት መግዛታቸውን እና መቆፈሪያ ማሽን ያልገዙ ስለመሆኑ እና ይሄንንም የገዙትን እቃ ብር 400 /አራት መቶ ብር/ በማትረፍ የሸጡ ስለመሆኑ የገለጹ በመሆኑ ተጠሪ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ክሱ ወድቅ መሆን ሲገባው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲታረምላቸው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ በእርግጥ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሌሎቹ እቃዎች ላይ በበታች ፍርድ ቤት

የተላለፈው ፍርድ በአግባቡ ስለመሆኑ በማመላከት ያጸናው ሁኖ የዚህ አከራካሪ ማሽን ግን አይነቱ ሊታወቅ እና በባለሙያ ሊገመት እየተቻለ ይሄ ሳይደረግ መታለፋ እና በርትዕ መወሰኑ አግባብነት የሌለው ነው ተብሎ ወደ ታች መመለሱ ግልጽ ቢሆንም አመልካች ማሽኑን የገዛውን ሰው ማቅረብም ሆነ ማሽኑ ያለበትን ቦታ ማሳየት ባለመፈለጋቸው፣ ያቀረቡትም ሰው ስለማሽኑ ሲጠየቁ ማሽን ያለመግዛታቸውን ሁኖም ግን ብረታ ብረት ስለመግዛታቸው ብቻ በመግለጻቸው ታልፎ የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ እና ንብረቶቹን ስለመረከቡ ደግሞ ፈርሞ የተረከበበት ሰነድ ስላለ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን የመቆፈሪያ ማሽን ግምት በተመለከተ ወደ ድምዳሜ የደረሱት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በመጀመሪያ ደረጃ የመቆፈሪያ ማሽኖቹን በተመለከተ አመልካች አልተረከብኩም የሚል ክርክር በዚህ ደረጃ እያነሳ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ ሁኖም ግን ኃላፊነትን በተመለከተ ከዚህ በፊት እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገ ክርክር እልባት ያገኘ እና የፌ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ .ቁ 50776 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ወደ ፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲመልስ አሁን የሚያከራክረውን ማሽን ግምት በርትዕ ለመወሰን በባለሙያ በማስገመት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚቻል በመሆኑ ይሄው ስርዓት ሊፈጸም ይገባል በሚል ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የመቆፈሪያ ማሽኑን አልተረከብኩም በማለት ያነሳው ክርክር ቀደም ሲል በውሣኔ በተቋጨ ጉዳይ ላይ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 5/1/ መሠረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁኖም ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤት አከራካሪውን ማሽን ለማስገመት ተገቢውን ትጋት አድርጓል ወይ ? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ጉዳዩ ወደ ታች ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ ፍርድ ቤቱ ማሽኑ ያለበትን ቦታ ወይም የገዛውን ሰው እንዲያቀርብ የተጠየቀ ሲሆን አመልካችም ማሽኑን እንደቀድሞ ሁሉ እንዳልተረከበ የተከራከረ ሲሆን የገዛውንም ሰው እንዲያቀርብ ታዞ አመልካች ያቀረበው ሰው ማሽን እንዳልገዛ እና ብረታ ብረት እንደገዛ የገዛውንም ብረታ ብረት ብር 400 /አራት መቶ ብር/ በማትረፍ እንደሸጠ ገልጧል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ምክንያት በማድረግ ቀድሞ በርትዕ ብር 200,000/ ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ተብሎ የተወሰነውን ውሣኔ በድጋሚ በመቀበል ወስኗል፡፡

ሁኖም ግን አንድ ጉዳይ በበላይ ፍርድ ቤት በነጥብ ሲመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በመጣራት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተገቢውን ትጋት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 343/1/ ድንጋጌ ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሄ አከራካሪው የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ያገለገለ ስለመሆኑ እስከታወቀ ድረስ ፍርድ ቤቱ ዓይነቱን በተመለከተ ከግራ ቀኙ ወይም በመዝገቡ ውስጥ ካሉት ሰነዶች በመመልከት እና በመግለጽ አግባብነት ባለው ባለሙያ እንዲገመት በማድረግ ቢያንስ በርትዕ ለሚሰጠውም ውሣኔ መነሻ ነገር ማስቀረብ እየተቻለ እንደዚህ ዓይነት እና ተመሳሳይ ጥረት ሳይደረግ በደፈናው በርትዕ ቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ

በድጋሚ በመቀበል  ውሣኔ መስጠቱ ከፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት የተሰጠውን ጉዳዩ የሚጣራበትን አግባብ ያልተከተለ በመሆኑ አግባብነት የሌለው የክርክር አመራር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ቀደም ሲል  ከዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን መመሪያ ሳይከተሉ እና ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ የደረሱበት ድምዳሜ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው   ሳ   ኔ</u>**

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 67129 ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 65277 በቀን 24/5/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ያገለገለ ስለመሆኑ እና ሌሎች ስለማሽኑ ከመዝገቡ እና ከክርክሩ የተገኙትን ነጥቦች ለሚመለከተው ባለሙያ በመግለጽ በወቅቱ የነበረው ዋጋ ሙያዊ ግምት እንዲቀርብ በማድረግ እና በማስገመት ቀደም ሲል በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን  ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 76601

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-አቶ ሽመልሽ አማረ - ጠበቃ ታምሩ ወልደማርያም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አማረ መኮነን - ከጠበቃ ወልደስላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ውሳኔ የተሰጠበት ወገን በሌለበት ታይቶ የተሠጠው ውሳኔ እንዲነሳለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78(1) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚያቀርበው ጥያቄ የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ቀን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡የስር ከሳሽ በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱ ለአሁኑ ተጠሪ በሥርዓቱ መሰረት መጥሪያ እንዲደርሳቸው ትዕዛዝ ሰጥቶ የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽን ሊያገኙ እንዳልቻሉ ገልጸው ምትክ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲደረግ አመልከተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል አመልካችን በጋዜጣ እንዲጠሩ አድርጎ በጥሪው መሰረት አመልካች ስላልቀረቡ ጉዳዩን አመልካች በሌሉበት በማየት ዋናውን ጉዳይ ለተጠሪ ወስኗል፡፡ ከዚኅም በኋላ የአሁኑ አመልካች የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት ውሳኔው ተነስቶ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ በሕጉ የተመለከተውን የአንድ ወር ጊዜውን ጠብቆ ያልቀረበ መሆኑን ጠቅሰው አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ውሳኔው መሰጠቱን የተረዱት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አቤቱታ ያቀረቡት የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በመሆኑና ይህም የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በሁዋላ በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከዚኅም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ውስጥ የተመለከቱት የይርጋ ጊዜዎች አቆጣጠር መታየት ያለበት በራሱ በፍትሕብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ መሰረት እንጂ በፍትህ ብሔር ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ያለመሆኑን፣ ከዚህ አንፃር ጉዳዩ ሲታይም አመልካች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን ከተረዱበት ከጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር ያለበት መሆኑን፣ ይህም ጊዜ እስከ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም. ድረስ መሆኑን ገልፆ አመልካች የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ያቀረቡት አቤቱታ በሕጉ የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በሚሉ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠርን በተመለከተ ሕጉ የማይገልጽ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያላቸው በፍትሓብሔር ሕጉ ከቁጥር 1948 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች ናቸው፣ ከዚህ አንፃር ጉዳዩ ሲታይም አመልካች በጉዳዩ ላይ በሌሉበት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን የተረዱት ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም. ከሆነ የይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ይህንኑ ቀን መነሻ ሊያደርግ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪ ቀርበው በጽሑፍ በሠጡት መልስ በፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ውስጥ ያሉት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጣር በራሱ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርኣት ሕጉ መሰረት እንጂ በፍትሀብሄር ሕጉ ሊሆን አይችልም ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረመው የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስር የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠር መታየት ያለበት በራሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት ነው? ወይንስ በፍ/ብ/ህጉ በቁጥር 1848 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስና በሁለተኛ ደረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ ስለመወሰኑ የተረዱት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. መሆኑንና ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይላቸው አቤቱታቸውን ያቀረቡት የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. መሆኑን ነው፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉት ደግሞ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78(1) ስር የተመለከተው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ የሚያበቃው የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም. ስለሆነ እና አመልካችም ከዚህ ቀን በኂላ አቤቱታቸውን ማቅረባቸው ተቀባይነት የለውም በማለት መወሰናቸውን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ በፍትሓብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ ስር የተለያዩ የይርጋ ድንጋጌዎች ያሉ ሲሆን አቆጣጠራቸውን በተመለከተ ግን ግልጽ ድንጋጌዎች የሉም፡፡ በሌላ በኩል በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስር ስላሉት የይርጋ ድንጋጌዎች የአቆጣጠር ሁኔታ ሕጉ በቁጥር 1848 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ግልፅ ስሌት አስቀምጧል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጎች ዋነኛ ዓላማ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሰ ወጪ፣ በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ህጎች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም ባንድ ጉዳይ ካሉት ተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ተከራካሪዎች ጥቅም ፣ በፍርድ ቤት መኖር ያለበትን የሙግት አመራርና አጠቃላይ የሀብትና የጊዜ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ የሰፈሩ ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ይርጋን አስመልክቶ በፍትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1856/2/ ከሰፈረው የይርጋ ጉዳይ በተከራካሪዎች ካልተነሣ ፍርድ ቤት አይነሳም ከሚለው ሕግ የተለየ ነው፡፡በፍትሐብሔር ሕግ የሰፈረው የይርጋ ሕግ ዋነኛ ዓላማ የተዋዋዮችን ጥቅም መጠበቅ ነው፡፡ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆነ ተከሣሽ ይርጋውን ካላነሣም የሚጎዳው ራሱ

ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገን የተወውን መብት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት እንዲያነሣው አይፈቀድም፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች መከበር አለመከበራቸውን ግን ፍርድ ቤቱ የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡ በተከራካሪ ወገን ባይነሣ እንኳን በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 195 እንደተደነገገው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከናወነው ነገር ሁሉ እንዳልተፈፀመ ሆኖ ስለሚቆጠር የሥነሥርዓት የጊዜ ገደቦች ተሟጋቾችን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱንም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ሕጉ በግልጽ የሰፈረው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሚቀርብን ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ እንዲሚችል ይህ ችሎት ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ ምክንያቶችን በማንሳት በመ/ቁጥር 17362 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህን ጉዳይ በዚህ መዝገብ ማንሳት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በስነ ስርዓት ሕጐች ያሉት የጊዜ ገደቦች በመሰረታዊ ሕጎች ካሉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ ናቸው በማለት የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሥነ-ሥርዓት ሕጎች የተካተቱትን የይርጋ ገደቦችን አቆጣጠር በተመለከተ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስር ከተቀመጡት የጊዜ ገደብ አቆጣጠር አንጻር ማየትም አይቻልም የሚል ክርክር ማስነሳቱ የማይቀር በመሆኑ ይህንኑ እልባት ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰው የአስገዳጅ የሕግ ትርጉም ምክንያቶች የሚያጠነጥኑት በስነ ስርዓት ሕጎች ያሉትን የጊዜ ገደቦች ሊነያሳ የሚችለው ፍርድ ቤት ነው? ወይስ ተከራካሪ ወገን ብቻ? በሚለው ጥያቄ በመሆኑ በሥነ-ሥርዓት ሕጉች ያሉትን የጊዜ ገደቦችንና በመሰረታዊው ሕግ ውስጥ የተካተቱትን የይርጋ ገደቦችን ባሕርይ መለየቱን የሚያሳይ ከሚሆን በስተቀር በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይም ሁለቱም ህጎች መሰረታዊ ልዩነት አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም ሕጉቹ እርስ በእርሳቸው ያላቸው ትስስርና አላማቸው ሲታይ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በግልጽ ምላሽ ያላገኙትን ጉዳዮች በዋናው ሕግ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች ምላሽ በመስጠት ሕጉቹ ውጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲወሉ የሚያስችል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንጻር ሲታይ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ስለይርጋ አቆጣጠር ግልፅ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ይህንኑ የሕጉን ክፍተት መሙላት የሚቻለው ስለጊዜ አቆጣጠር በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመመልከት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ አይነቱ አተረጓጎምም ሕጉቹ ውጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል በመሆኑ በጠቅላላ የሕግ አተረጓጎም ደንቦችም ተቀባይነት ያለው አካሄድ ነው፡፡

አንድ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ የተሰጠበት ወገን ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ መሰጠቱን ወይም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78(1) ድንጋጌ የሚያሳይ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጅም "Any defendant against whom a decree is passed or order made ex-parte or in default of pleading; may, within one month of the day when he became <u>aware of</u> such decree or order, apply, to the court by which the decree was passed or order made for an order to set it aside." በሚል የተቀመጠ ሲሆን የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አቤቱታ አቅራቢው ስለሁኔታው ከተረዳበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በግልጽ አያሳይም፡፡ በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስር ባሉት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች ግን የመጀመሪያው ቀን ለይርጋው ጊዜ መቆጠር መነሻ ሊሆን እንደማይገባ በግልጽ በቁጥር 1848 ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ መሰረት ሲደረግም አመልካች ጉዳዩን ተረዳሁ የሚሉበት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ/ም ጊዜ ለአንድ ወሩ የጊዜ አቆጣጠር መነሻ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍትሃ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ያሉት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር በፍትሐ

ብሔር ሕጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌቶች ሊመሩ የሚችሉ አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ሕጉቹ ያላቸውን ትስስርና የትርጉሜው ውጤት በመሰረታዊ ሕጉ ጥበቃ ባገኙት መብቶች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ እንድምታ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

በፍተሐብሄር ስነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠር መገዛት ያለበት በፍተሐብሔር ሕጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች አንፃር ነው ወደሚለው ድምዳሜ ከደረሰን የአመልካች አቤቱታ የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ያለፈበት መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ መሰጠቱን የተረዱት በ30/05/2003 ሲሆን ውሳኔው ተነስቶ ባሉበት ጉዳዩ እንዲታይላቸው አቤቱታ ያቀረቡት በ30/06/2003 ዓ.ም. ነው፡፡ ከላይ በተሰጠው ትርጉም መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1848 መነሻ ሲሆን የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከየካቲት አንድ ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አንድ ወር ሲቆጠር ደግሞ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የሚታገደው ከመጋቢት 01 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት ጊዜያት ከቀረበ ነው፡፡ አመልካች ጥያቄአቸውን ያቀረቡት ግን የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ከይርጋ በመለስ ያሉት ሌሎች ሕጋዊ መመዘኛዎች በስር ፍርድ ቤት ታይተው ሊስተናገድ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 164816 ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1111116 ጥር 09 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስር የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠር መታየት ያለበት በራሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት ሳይሆን በፍ/ብ/ህጉ በቁጥር 1848 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ነው ብለናል፡፡
3. የጊዜ አቆጣጠሩ ከዚህ አንፃር ሲታይም የአመልካች ጥያቄ የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ያላለፈበት በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ከይርጋ በመለስ ባሉት ሌሎች ክርክሮች ጉዳዩ ታይቶ አመልካች በሌሉበት ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ ሊነሳ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ጭብጥ እና በሕጉ አግባብ ተከታዩ ሂደት ታይቶ ጉዳዩ እንዲወሰን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 74785
ሐምሌ 03 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ-ነ/ፈጅ ብርሃኑ ታደሠ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አብዱልከሪም ዳውድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የማቅረቢያው ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ይከፈት ዘንድ እንዲፈቀድ የቀረበውን ጥያቄ አንድ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በበላይ ፍርድ ቤት ክርክር ሲደረግ በቆየበት ጊዜ የበታች ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሚመራው ክርክር ሳይታገድ ቆይቶ የበላይ ፍርድ ቤቱ የይግባኝ ማስፈቀጃው ተቀባይነት ያገኘው ያላግባብ ነው በማለት በስነ ስርዓቱ ላይ ውሳኔ ቀድሞ ከሰጠ እና የበታች ፍርድ ቤቱ ይህንኑ የበላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ማስፈቀጃው ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሳይመለከት በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ቢሰጥ ይኸው የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈፃሚነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡የማስፈቀጃ ጥያቄው የቀረበው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲሆን፣ ጥያቄ አቅራቢው የአሁኑ ተጠሪ ነበር፡፡ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ሊያልፍበት የቻለው ወይም ይግባኙን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሊያቀርብ ያልቻለው ጉዳዩን ይዞ ሲከታተል በነበረው ነገረ ፈጁ ስህተት /ጥፋት/ እንደሆነም በማመልከቻው ላይ ገልጾአል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን መነሻ በማድረግ የአሁን አመልካችን በመልስ ሰጪነን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ጊዜው ያለፈው በነገረ ፈጁ ጥፋት ነው፡፡ ነገረ ፈጁም በዚህ ምክንያት የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዶበታል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት የተጠሪን ጥያቄ ተቀብሎአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይህ ችሎት ጊዜ ካለፈ በኋላ ይግባኝ እንዲከፈት ጥያቄ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 325 በተደነገገው መሠረት ሁኖ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ የሚመረመረው /የሚመዘነው/ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326 መሠረት መሆኑን፣ ጥያቄው ተቀባይነት አለው ወይንስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሊወሰን የሚገባው እንደየአግባቡ በንኡስ ቁ/1/ ወይም /2/ መሠረት እንደሆነም ግልፅ ስለመሆኑ፣ በንዑስ ቁጥር 1 እንደተመለከተው አመልካቹ ወይም የፈቃድ ጥያቄ አቅራቢው ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑ ፍ/ቤቱን ማሣመን ከቻለ ይግባኙን በአሥር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ እንደሚፈቅድለት፣ በዚህ ረገድ ምክንያቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ፍሬ ነገር በፍ/ቤቱ የሚመዘን ከመሆን አልፎ በሕጉ የተቀመጠ የታወቀ /የተለየ/ መስፈርት እንደሌለው፣በንዑስ ቁ./2/ የተቀመጠው ድንጋጌ ግን አመልካቹ ያቀረበው ምክንያት በንኡስ ቁ./1/ አባባል ሊስተናገድ የማይገባ ወይም ተቀባይነት የሌለው ነው የሚባልበትን አግባብ የሚያመለክት

ድንንጋጌ መቀመጡን፣ይኸውም በፈቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ማቅረብ ያልቻለው በአመልካቹ ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጁ ወይም በወኪሉ ያለመቅረብ እና በእነዚሁ ጉድለቶች መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ ምክንያቱ በንኡስ ቁ./1/ እንደተነገረው በቂ ነው ሊባል እንደማይገባ በግልጽ መደንገጉን፣ በዚህ ምክንያትም የይግባኝ ይከፈትልኝ ጥያቄው ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በማለት ግልጽ ድንጋጌ ሕጉ ማስፈሩን በምክንያትነት ይዞ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን መፍቀዱ ግልፁን ሕግ በሚጻረር አኳኋን ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሻረው መሆኑን የሰ/መ/ቁጥር 57360 ያሳያል፡፡

ከዚህ በሁዋላም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ዋናውን ጉዳይ ሲያከራክር ቆይቶ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም፣በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው የገንዘብ ዋስትና ቦንድ ሕጋዊ ውጤት አለው በማለት በፍሬ ነገር ደረጃ የቀረበውን ክርክር አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመለሰ ሲሆን ይኸው ውሳኔ የተሰጠው ከሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ውጪ ነው በሚል የአሁኑ አመልካች ውሳኔው እንዲታረም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2004 ዓ/ም አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይኸው ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ የሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ መኖሩን እንዲያውቅ ያለመደረጉንና ክርክሩም እንዳይካሄድ ያለመታገዱን በምክንያትነት ይዞ የራሱን ውሳኔ መልሶ የሚሽርበት አግባብ ያለመኖሩን ጠቅሶ የአመልካችን አቤቱታ ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ የሠጠው ውሳኔ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔን ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው በማለት በጊዜውም የሰበር ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚው ችሎት እንዲደረሰው ለማድረግ ተገቢውን ሁሉ በሚመለከተው አካል በኩል አቅርቦ የይግባኝ ሰሚው ችሎት በክረምት ጊዜ በነበረው ስራ ዋናውን መዝገብ መርምሮ ውሳኔ በመስጠቱ ችግሩ መከሰቱን ገልፆ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ያለመቅረቡንና በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለውም በአመልካች ነገረ ፈጅ ችግር ስለመሆኑ ዘርዝሮ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማናገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመ/ቁጥር 60886 በሆነው የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው በተጠሪ በኩል የቀረበውን የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታውን በመመርመር ተቀባይነት አለው ወደሚለው ድምዳሜ ከደረሰ በኋላ መሆኑን፣የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ፈቃጅ ውሳኔ ግን በፌዴራሉ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሻረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ መስጠቱን፣ይህ ውሳኔ የተሰጠውም ይግባኙ የማቅረቢያ ጊዜውን ጠብቆ ያልቀረበ፣ጊዜው አልፎም ይግባኙን ለማቅረብ በቂና ሕጋዊ ምክንያት የለም ተብሎ በሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነው፡፡የሰበር ሰሚው ችሎት ስለማስፈቀጃው በሰጠው ውሳኔ ላይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 325 እና 326 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ የተረጎመ ሲሆን በዚህ ችሎት ሕግ በመተርጎም የሚሰጠው ውሳኔም በየትኛውም እርከን በሚገኝ ፍርድ ቤት አስገዳጅ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

የተጠሪ ነገረ ፈጅ የአመልካች ነገረ ፈጅ የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ያልቀረበ ነው በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች ነገረ ፈጅ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60886 ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. የሠጠው ውሳኔ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57360 ከሰጠው ውሳኔ አንፃር ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ያለመሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በዋናው ጉዳይ ላይ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. ውሳኔ ከተሰጠና ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ቅሬታ ካለው አመልካች የሰበር አቤቱታውን ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ ዘጠና ቀናት ውስጥ ለሰበር ሰሚው ችሎት ማቅረብ የሚችል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች የሚያሳዩት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ህዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በመሆኑና በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ የተሰጠው ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. እንደመሆኑ መጠን በሕጉ የተመለከተው የዘጠና ቀናት የሰበር አቤቱታ ማቅራቢ ጊዜ ሳያልፍ አቤቱታውን ያቀረበ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ በአንድ ፍርድ ቤት የተሠጠ ውሳኔ ስህተት አለበት የሚል ወገን በሕጉ አግባብ ቅሬታውን ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ወገኖች ከተራከሩ በኋላ በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት ከተሻረ በተሻረው ውሳኔ መሰረት የሚፈጸም ነገር ሊኖር አይችልም፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስም ይህንኑ ድምዳሜ የሚያጠናክር ነው፡፡ በበታች ፍርድ ቤት የሚደረገውን ክርክር ሳያሳግድ በበላይ ፍርድ ቤት ክርክር አድርጎ የበላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚታወቅ ድረስ መቆየትና የበላይ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተከራካሪ ወገን ከአወቀው በኋላ ለበታች ፍርድ ቤት የበላይ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሳያስታውቅ በመቆየቱ ወይም በመቅረቱ ብቻ የበላዩን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚቃረን የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት እንዲኖር የሚደረግበት የስነ ሥርዓት ሕግ አግባብም የለም፡፡በመሆኑም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 ድንጋጌ መንፈስም ሆነ ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ አንፃር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60886 ጥቅምት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት የሌለው በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 60886 ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 60886 ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ይግባኙ እንዳይቀርብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 57360 ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ/ም ውሳኔ ከሠጠ በሁዋላ የተሰጠ በመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 76786

ሐምሌ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ አልዩ ተክሉ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ መስፍን ስለሺ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ክስ ያቀረበ ወገን ክሱን ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችል ዘንድ መጥሪያውን ለተከሳሽ ለማድረስ በፊት ክሱ እንዲዘጋለት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ክሱ በተዘጋ ጊዜ ሙሉ የዳኝነት አገልግሎት አገኛለሁ በሚል በሰበር ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ተገቢው ተቀንሶ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

ከላይ የተመለከተውን ጉዳይ አስመልክቶ በቅድሚያ ጉዳዩን የተመለከተውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ክሱን በተከሳሽ አድራሻ ማቅረቡ ለአፈፃፀም የተሻለ ሆኖ ስላገኙት ወጭ አድርገው የወሰዱትን መጥሪያ እና የእግድ ትዕዛዙን በመመለስ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው እና የከፈሉትም የዳኝነት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ጠይቀዋል፡፡ በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278/1/ መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ይሁን እንጂ ከሳሽ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ተገቢው ተቀንሶ የሚመለስበትን አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 232 እና 245 ከመደንገጉ በቀር ከሳሽ በእራሱ አነሳሽነት መዝገብ እንዲዘጋ ባደረገ ጊዜ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ሊመለስ የሚችልበትን ሁኔታ የደነገገ ሕግ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

ይህንኑ ትዕዛዝ በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የከሳሹን ክስ ሕጋዊ ብቃት መርምሯል፡፡ የእግድ ትዕዛዝም ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽም ስለጉዳዩ መከላከል እንዲፈቀደለት የሚጠይቅ ከሆነ ፈቃድ እንዲጠይቅ መጥሪያ እና የክስ ማመልከቻ ግልባጭ ተልኮለታል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የፍ/ቤቱን የፅሕፈት መሣሪያ ከሳሽ የተጠቀመ ከመሆኑም በላይ ተገቢውን የዳኝነት አገልግሎት አግኝቷል፡፡ ይህን አገልግሎት ማግኘቱ ከተረጋገጠ የፍ/ቤት ዳኝነት አገልግሎት ተሰጥቷል ማለት የሚቻለው ክሱ ከተሰማ በኋላ እንጂ ክሱ ከመሰማቱ በፊት ነው የሚለው ክርክር ከግንዛቤ እጥረት የመነጨ ነው የሚለውን ለጉዳዩ

ምክንያት በመስጠት እና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/45 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ሁሉ ጠቅሶ ውሣኔውን አፅንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ዳኝነት ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፤ ተጠሪ በጥሪው መሠረት ቀርቦ ለመከራከር ካለመፈቀዱም በላይ በጉዳዩ ላይ ሊከራከር የሚችልበት ምክንያት ላይኖርም የሚችል መሆኑ ተጠቅሶ ክርክሩ ከአመልካች የሰበር አቤቱታ ጋር ተገናዝቦ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ እኛም አመልካች ያቀረቡትን የሰበር መከራከሪያ ነጥብ ከላይ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሥር ፍ/ቤቶች ዳኝነት ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ እንደገለፀው ከሳሹ ክሴን ትቼዋለሁ በማለት ተከሳሹ ቀርቦ መልስ ከመስጠቱ በፊት ወይም የጉዳዩ መሰማት ከመጀመሩ በፊት በማመልከቱ የተነሣ መዝገብ በተዘጋ ጊዜ ፍ/ቤቱ ለሚሰጠው የዳኝነት አገልግሎት ሲባል ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ውስጥ የሚቀንሰው ተቀንሶ ቀሪው የሚመለስለት ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በ1958 ዓ.ም በወጣው የፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አልተደነገገም፡፡ በዚህ ሕግ ይህ ነጥብ በዝምታ ታልፏል፡፡ የሕግ ሽፋን አላገኘም፡፡

ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ክፍል በሆነው በአንቀጽ 3 ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ በግልፅ ለሸፈናቸው ጉዳዮች ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ተፅፈው ሥራ ላይ የነበሩ ሕጐችና ደንቦች የተሻሩ መሆኑን ከመግለፅ በቀር ሕጉ ሳይሸፍናቸው ለታለፉ ጉዳዮች የፍ/ብሔር ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ተፅፈው በሥራ ላይ የነበሩ አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደ አግባብነቱ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በዚህም መሠረት በ1945 ዓ.ም በወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177 አንቀጽ 11 ላይ ከሳሹ ክሱን ካቀረበ በኋላ በእራሱ ጠያቂነት ክሱን የተወው እንደሆነ አስቀድሞ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ምን ያህል ተቀንሶ ምን ያህል እንደሚመለስለት በዝርዝር የተደነገገ በመሆኑ ከላይ በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህም እንኳ ቢታለፍ ይህ በሕግ ሽፋን ሳይሰጠው በዝምታ የታለፈውን ጉዳይ ከጉዳዩ ጋር ተመሣሣይ ይዘት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማመሳሰል ተገቢውን ትርጉም መከተል እንደሚቻልም ቋሚ ከሆኑት የሕግ አተረጓጐም ዘዴዎች አግባብነት ያለው የሕግ ትርጉም ዘይቤ አመልካች ነው፡፡

ከዚህም አንፃር ሲታይ ተከሳሽ ከመጠራቱ በፊት ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሕ/ቁ 232/1/ሀ/ እና /ለ/ መዝገብ በተዘጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232/1/ለ/ እንደተመለከተው ከሳሹ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ውስጥ ተገቢው ተቀንሶ ቀሪው እንዲመለስለት ሕጉ ከፈቀደ ተከሳሹ በመጠራቱ ምክንያት ተከሳሹ ሥልጣንን አስመልክቶ ባነሳው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተነሣ መዝገብ በተዘጋ ጊዜ እንደ አግባብነቱ ከተከፈለው የዳኝነት ገንዘብ የሚቀነሰው ተቀንሶ ተራፊው እንዲመለስለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 245/4/ መደንገጉ ከታወቀ መጥሪያው ወጭ መሆኑ ቢታወቅም፣ የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ከሳሹ ለተከሳሹ መጥሪያውን ከማድረሱ በፊት በእራሱ ጠያቂነት ክሱን መተውን ገልፆ መዝገቡን ፍ/ቤቱ በዘጋው ጊዜ ክርክሩ ከደረሰበት የክርክር ደረጃ እና ሙሉ የዳኝነት ገንዘብ የተከፈለበት ምክንያት የተሟላ ክርክር ተደርጎ ፍ/ቤቱ የተሟላ የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጥ ተከራካሪውም ይህንኑ የተሟላ የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት ያለውን መብት መነሻ በማድረግ የሚከፈል ለመሆኑ ከላይ የተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232 እና 245/4/ በግልፅ የሚያመለክቱ

በመሆኑ በዚህ ጉዳይም የከሳሹ የዳኝነት ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ በይዘቱም ሆነ ከሕግ ግብ አንፃር ሕጉ በግልፅ ከሸፈናቸው ጉዳዮች ተመሣሣይ እንጂ የተለየ ሆኖ አይገኝም፡፡

ከዚህም አንፃር ምንም እንኳ ከሳሽ የከፈልኩት የዳኝነት ገንዘብ በሙሉ ይከፈለኝ በማለት የከፈሉትን የዳኝነት ክፍያ የማግኘት መብት ያላቸው ባይሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232/1/ለ/ እና 245/4/ በተነገረው መሠረት ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ የሚቀነሰው ተቀንሶ ተራፊውን መልሶ የማግኘት መብት እያለው የከሳሽ ጥያቄ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 185730 በ30/9/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 111729 በ4/5/2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡

2. አመልካች አስቀድሞ ከከፈለው የዳኘነት ገንዘብ ውስጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232 በተመለከተው መሠረት ተገቢው የዳኝነት ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ይመለስልለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 77322

ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የደብረ ዘይት መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያ - ጠበቃ አቶ ዓለሙ ደገፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. እሌኒ ዓለማየሁ - ጠበቃ አቶ ጣባ ጨፋ ቀረቡ

2. የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ አቶ መስፍን ኮርሜሶ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 የተመለከተውን የጣልቃ ገብነት ሥርዓት አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ ውል ከአቶ ገረመው ጥላሁን እና ከወ/ሮ ልባዊት ዓለሙ ቁጥሩ 154 የሆነውንና በ800 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ገዝቻለሁ ሆኖም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በውል ላገኘሁት ቤት ካርታና ፕላን በስሜ ሰርቶ ሊሰጠኝ ሲጠየቅ እምቢተኛ ስለሆነ ካርታና ፕላን በስሜ ሰርቶ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርባለች፡፡

2ኛ ተጠሪም በቃል ክርክር ወቅት ቀርቦ ይህ ካርታና ፕላን ይሠራለት የተባለው ንብረት በቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን አካባቢ ስለሚገኝ እና ህዝብና መንግስት እንዳይጋጭ ብለን ሌላ ተለዋጭ ቦታ ለመስጠት እየተዘጋጀን በመሆናችን እንጂ እምቢተኛ ሆነን አይደለንም የሚለውን አስመዝግቦ ጉዳዩ በክርክር ላይ እንዳሉ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሰረት ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር ይፈቀድልኝ፣ በማለት ጣልቃ ሊገባ የሚችልበትን አቤቱታ ከእነማስረጃው አቅርቧል፡፡ በማስረጃነትም ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የይገባኛል መብት ያለው መሆኑን የሚያመለክት የከተማ ቦታ ባለቤትነት ማስረጃ ወረቀት አያይዞ እንደቀረበ የስር የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካች ጣልቃ ልገባ ይገባል በማለት ላቀረበው አቤቱታ በማስረጃነት ይህንኑ ሰነድ ያቀረበ ለመሆኑ በትዕዛዙ መግቢያ ላይ ፍ/ቤቱ መግለፁ እየታወቀ እንደገና ወረድ ብሎ ጣልቃ ልግባ ባዩ ጣልቃ እገባለሁ በማለት ለቤተክርስቲያን ህጋዊ ሰውነት ሰጭ የሆነውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ 398 እና ለአስተዳደሩ የተሰጠውን ሥልጣን ከመጥቀሱ በቀር ያቀረበው ክርክርና

ማስረጃ የለም የሚለውን ምክንያት በመያዝ፤ እንዲሁም ከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆነችው በውል ምክንያት ባገኘችው ካርታና ፕላን ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል መብትም የለውም የሚለውን በመጥቀስና ጣልቃ ገብ ራሱን የቻለ ካርታና ፕላን አለው በአሁን 1ኛ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ከሳሽ በነበሩትና በአሁን 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ በነበሩት መካከል የተነሳው ክርክር በጣልቃ ገብ ካርታና ፕላን ላይ አይደለም። ከድሮ ጀምሮ ለሌላ አካል በተሰጠ ካርታና ፕላን ላይ መብት ያለው አይደለም፤ ከፈለገም በሌላ በኩል መብቱን ያስከብር እንጂ የሚለውን በማከል ጣልቃ ሊገባ አይገባም በሚል አሰናብቶታል።

የአሁን አመልካች ደረጃውን ጠብቆ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ጣልቃ ሊገባ እንደሚገባ በመግለፅ ይኸው ትዕዛዝ በይግባኝና በሰበር ሥርዓት እንዲታረምለት ዳኝነት ቢጠይቅም የወረዳው ፍ/ቤት ከሰጠው ዳኝነት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ምክንያት ጥያቄው ተቀባይነትን አላገኘም። በዚህም የተነሳ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል።

1ኛ ተጠሪም የጣልቃ ልግባ ባዩን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ዳኝነት መስጠታቸውን እንጂ የህግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን አያመለክትም የሚልበትን ምክንያት በመጥቀስ ሲከራከር፤ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በአንድ በኩል ክርክር ያስነሳውን ንብረት ከአሁን አመልካች በፊት 1ኛ ተጠሪ በግዥ ያገኙት ነው የሚል፤ በሌላ በኩል የዚህ ንብረት ህጋዊ ባለይዞታ አመልካች ናት የሚል እንድመታ ያለው እርስ በእርሱ የተምታታ ሐሳብ ከሰጠ በኋላ በሁለት ግለሰቦች መካከል ባለ ክርክር 2ኛ ተጠሪ በሰበር ደረጃ ተጣርቶ ለመከራከር የሚያስችለው የህግ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለፅ መልስ ሰጥቷል።

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል። እንደመረመርነውም ዳኝነት ሰጭ የሆነ አካል በሥራው የሚሰጠው ማናቸውም ዳኝነት በተከራካሪ ወገኖች በማስረጃ ተረጋግጦ የቀረበ ጉዳይ ከህግ ጋር በማገናዘብ ክርክርን፤ ማስረጃንና አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል። ከዚህ አንፃር የአሁን አመልካች በሥር የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ጣልቃ ገብቼ ለመከራከር ያስችለኛል የሚለውን ምክንያት ለዚሁ ምክንያቱ ደጋፊ የሆነ የከተማ ቦታ ባለቤትነት ማስረጃ ማቅረቡ እየተገለፀ፤ የወረዳው ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ ህጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ህግና በአስተዳደሩ የተሰጠውን ሥልጣን ከመጥቀሱ በቀር ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም በሚል የተሰጠው ትንታኔ/ዳኝነት ከላይ ከዳኝነት ሰጭ አካል የሚጠበቀውን መሰረታዊ የስራ ግዴታ ምርኩዝ ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም። በሌላ በኩል በሥር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ ላቀረቡት የክስ አቤቱታ በማስረጃነት ያቀረቡት ቤቱን በግዥ አግኝቻለሁ ያሉበትን ውል በማያያዝ መሆኑ ቢታወቅም ይህ ውል በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ሆኖ ተገኝቷል ከተባለ የዚህ ውል የአስገዳጅነት ባህሪይ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተወሰነ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 የተመለከተ በመሆኑ የውለታው ጉዳይ በሆነው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉትን ሌሎች ሦስተኛ ወገኖችን በንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ሲሉ ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክርክር ከጅምሩ ሊገደብ የሚችል አይደለም ይልቁንም ተዋዋዩ ወገን ሆነ ከነዚህ ሦስተኛ ወገኖች በየፊናቸው በሚያቀርቧቸው ክርክር እና ማስረጃ እየታየ የህግ መሰረት ያለው መሆኑንና አለመሆኑ እየተለየ ሊወሰን ከሚችል በቀር ከዚህም በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 የተዘረጋው ሥርዓት በከሳሽና በተከሳሽ ተሰይመው በሚከራከሩበት ጉዳይ የመጨረሻ ውጤት የተነሣ በማጣት ሆነ በማግኘት ረገድ ጥቅሙ/መብቱ የሚነካበት፤ ማናቸውም ወገን ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልገው በጉዳዩ ገብቶ የክርክር ተካፋይ እንዲሆን በማድረግ ከአንድ ጉዳይ ሊመነጭ

የሚችልን ክርክር በአንድ ፍ/ቤት በአንድ መዝገብ አጣምሮ በአጭር ጊዜ እና በአንስተኛ ወጭ እንዲቋጭ ለማድረግ እንዲረዳ ታስቦ የተደነገገ መሆኑ እየታወቀ የአሁን አመልካች ከፈለገ በሌላ መንገድ መብቱን ያስከብር እንጂ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ሊገባ አይገባም በሚል የተሰጠው ትርጉም የህጉን ይዘት ግብና ዓላማ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከዚህም በቀር የአሁን አመልካች ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያስችለው አመልካች የሆነ ክርክርና ማስረጃ ማቅረቡ አስከተረጋገጠ ድረስ የክርክር ተካፋይ በማድረግ ጉዳዩን መምራት ሲቻል የአሁን አመልካች የክርክር ተካፋይ ሆኖ በዋናው ክርክርና ሙግት ጊዜ ክርክሩን ለማስረዳት ማቅረብ በሚገባው የክርክር ጥንካሬ እና የማስረጃ ሚዛን ዓይን በመለካት የተሟላ የክርክር አመራር ሥርዓት ሳይጠበቅ ለፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 በተሰጠው የተዛባ ትርጉም የተነሣ የአሁን አመልካች በጣልቃ ገብነት የክርክር ተካፋይ ሊሆን አይገባም በሚል ከታች ወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የተሰጠው ትርጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25636 በ01/11/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ በማስከተልም በ22/11/2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ፤ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25740 በ09/3/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 117229 በ05/6/2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ሁሉ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆኖ ክርክር በጀመሩበት በመ/ቁ 25636 በ22/11/2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ በዚሁ መዝገብ ላይ የአሁን አመልካችን በጣልቃ ገብነት በመሰየም ክርክሩን እንደ አዲስ ከጅምሩ በመምራት በጉዳዩ ላይ ተገቢው ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ጉዳዩን ለአደአ ወረዳ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. የዚህ ሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ሁሉም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 58119

ጥቅምት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች**፡ - ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- አቶ ዓሊ በከር - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር ተያያዥነት ያለው ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን በማመልከት በጋራ ያፈራናቸዉን ንብረት ተጠሪ ታካፍለኝ በማለት ተንቀሳቃሽ ንብረቶቹን ከተራ ቁጥር 1-13 ከነ ግምታቸው የዘረዘሩ ሲሆን ስፋቱ 400 ካ.ሜ የሆነ ቦታና ቤት ታካፍለኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽን በተመለከተ መልስ እንዲሰጡበት ተጠርተው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎአል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል በተሰጠው ውሳኔ በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል የሚገኘው ቤት እንዲሁም አንድ ቴሌቪዥን ባለ 14 ኢንች እና አንድ ቴፕ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ናቸው በማለት ከተቻለ በዓይነት እኩል ይካፈሉ፣ካልተቻለ በስምምነት ተገምቶ አንዱ ለሌላው ግምቱን ከፍሎ ያስቀር፣በዚህ ካልተስማሙ በራሣቸው ወይም በጨረታ ተሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝዋን ለፌ/የከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች አጥብቃ የምትከራከረው ከዚህ በፊት በሸሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔም ሆነ የንብረት ክፍፍል ጉዳይ የተቋጨ ሆኖ እያለ ሌላ ክስ መቅረቡ ያለአግባብ ነው፣ በሸሪዓ ፍ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ የቤት ቁሣቁስ በተመለከተ በሠፈር ሽማግሌ ይካፈሉ ሌላ ንብረት ካለ ደግሞ በመደበኛ ፍ/ቤት ይጠያየቁ በማለት የድሬዳዋ የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪአ ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ይሄንን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ከአንድ ሻንጣ ልብስ በስተቀር ሌላ ንብረት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ ውሣኔ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪም የተስማማበት ስለመሆኑ በሽማግሌዎች ፊት የፈረመ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበው

ክርክር አመልካች በቀረበባት ክስ መጥሪያ ደርሷት ቀርባ ያልተከራከረች በመሆኑ፣የጋራ ንብረት ደግሞ ለመካፈል ህጉ መብት የሚሰጠኝ በመሆኑ እና የሽሪዓ ፍ/ቤት ደግሞ በመደበኛ ፍ/ቤት የመጠየቅ መብት የሰጠኝ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

በዚህ የክርክር ሂደት በእርግጥም ተጠሪ እንደሚከራከረው የሽሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በአካባቢ ሽማግሌዎች እንዲከፋፈሉ እና ሌሎች ንብረቶችን በመደበኛ ፍ/ቤት የመክሰስ መብቱ እንደጠበቀ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ አመልካች የምትከራከረው በሽሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ይግባኝ በመውሰድ በከፍተኛው የሽሪዓ ፍ/ቤት ተሽሯል፡፡ በዚሁ በከፍተኛ ሽሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረት ተጠሪ ከአንድ ሻንጣ ልብስ በስተቀር የሚደርሰው ንብረት የሌለ መሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶበታል በሚል ነው፡፡ ይሄንን አመልካች በግልፅ ያነሣቸውን የክርክር ነጥብ ተጠሪ ያላስተባበለና የመጀመሪያ ደረጃ ሽሪዓ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ብቻ በመንጠልጠል መልስ የሰጠ በመሆኑ በግልፅ እና በዝርዝር ያልተስተባበለ ነጥብ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 234/መ/ እና 235 መሰረት እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑ ቀድሞ በሽሪዓ ፍ/ቤት ፍርድ ያረፈበትን የንብረት ክፍፍል ጉዳይ በተመለከተ እንደ አዲስ ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አግባብነት አለው? ወይስ የለውም የሚለውን መመልከት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሽሪዓ ፍ/ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78/5/ እና 188/92 መሰረት በማድረግ የተቋቋሙና እውቅና የተሰጣቸው መሆኑን ስለሚያመለክት፣በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34/5/ መሰረት በተከራካሪዎች ፍቃድ መሰረት የግል ወይም የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በሃይማኖት ህጎች የመዳኘት መብት የተጠበቀ በመሆኑና በዚሁ ሂደትም የተሰጡት ፍርዶች ተቀባይነት ያላቸው ስለመሆኑ ከነዚህ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት ድንጋጌዎች ይዘት፣ዓላማና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት በህግ ስልጣን በተሰጠው የሽሪዓ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ተከራክረውበት በፍርድ ያለቀን ጉዳይ ተጠሪ በውሣኔው ቅሬታ እንኳ ቢኖረው በዚያው በሽሪዓ ፍ/ቤት መዋቅር መሰረት ቅሬታውን ለሚመለከተው የይግባኝ ወይም የቅሬታ ሰሚ ክፍል ማቅረብ ሲገባው እንደ አዲስ ጉዳይ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5/1/ መሰረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክስ በሌለበት የተሰማ ቢሆንም በሂደት ግን ጉዳዩ ቀድሞ በውሣኔ ያለቀ መሆኑን እንደተረዱ የቀረበውን ክስ ወድቅ ማድረግ ሲገባቸው በቀረበው ክስ መሰረት ውሣኔ መስጠታቸው አግባብነት የሌውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 05327 ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 27905 በቀን 26-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በፍርድ የተቋጨን ጉዳይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማንኛውም ዓይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ አይቻልም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

የሰ/መ/ቁ 73696

ሚያዝያ 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሃና አበባው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱ ይመር በሌለበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለብድር የተሰጠው ገንዘብ ከብር አምስት መቶ በላይ ሲሆን ለማስረዳት የሚያቀርበውን የማስረጃ አይነት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም ለአመልካች ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ አበድረው አመልካች በብድር ውሉ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ገንዘቡን ያልመለሱላቸው መሆኑን ገልፀው የብድር ገንዘቡን ሊመለስ ይገባ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ለማስረጃነትም የብድር ውሉ በወቅቱ የጠፋ በመሆኑ ለፖሊስ ያመለከቱ መሆኑን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ የወሰዱት የብድር ገንዘብ የሌለ መሆኑን፣ ከብር 500.00 በላይ ለሆነ የብድር ስምምነት ማስረጃነትም የሰው ምስክር ሊቀርብ የማይችል መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም ተጠሪ የብድር ሰነዱ የጠፋባቸው ስለመሆኑ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚችሉ ገልፆ ተጠሪ ምስክሮችን አቅርበው ምስክሮቹ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የካቲት 07 ቀን 2002 ዓ/ም የብድር ውል ስምምነት መኖሩን፣ ሰነዱ የጠፋበት መሆኑን እንደሚያውቁ ያረጋገጡላቸው መሆኑን እንዲሁም በአመልካች በኩል የተሰሙት ምስክሮች ግን የብድር ውሉ ስለመኖሩ አናውቅም ከማለት ውጪ የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል የሚችል የምስክርነት ቃል ያልሰጡ መሆኑን ገልፆ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ውል ስምምነት መኖሩ ተረጋግጧል ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ለተጠሪ ብር 10,000.00 ከእነ ሕጋዊ ወለዱ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ባሉበት የሚጣራ የሕግ ነጥብ አለ በማለት ነጥቡን ለይቶ ለተጠሪ ጥሪ አድርጎላቸው የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት ለመስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ ይዞ ተጠሪ ሲቀርቡ አመልካች አልቀረቡም፣ የቀረቡት ተጠሪም

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ክደው ተከራክረዋል በማለት የጉዳዩ ክርክር ሊሰማ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ አመልካች ስላልቀረቡና ተጠሪም ክደው ስለተከራከሩ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባው ነው በማለትና በዋቢነትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን በመስማት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን መዝገብ የዘጋው አመልካች ቀርበው እያለና ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔም ስለብድር ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ስር የተደነገገውን ደንጋጌ ይዘት ያላገናዘበና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2003 ድንጋጌን ያለቦታው በመጠቀም የተሰጠ መሆኑን ገልፀው ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው ነጥብ በመኖር ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው በስርዓቱ መሠረት ጥሪ ተደረጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትዕዛዝና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቀረበበትን መዝገብ የዘጋበት ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡

አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው የሕግ ነጥብ መኖሩ ታምኖበት የአሁኑ ተጠሪ በተጠሪነት የተመዘገቡበት በመሆኑ ክርክሩን ተጠሪ ባሉበት ለመስማት ተብሎ ቀነ ቀጠሮ ተይዞ መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ተጠሪ ሲቀርቡ አመልካች ያለመቅረባቸው ስለመረጋገጡና ተጠሪም ክደው መከራከራቸውን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ከመዝገቡ ከአሰፈረው መረዳት የሚቻል ሲሆን ይህንኑ ምክንያት በማድረግም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ አመልካች ስላልቀረቡና ተጠሪም ጉዳዩን ክደው ስለተከራከሩ መዝገቡን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን በመጥቀስ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ዘግቶታል፡፡ ከዚህ በቀላሉ መረዳት የሚቻለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለመስማት በያዘው ቀነ ቀጠሮ ተጠሪ ቀርበው አመልካች ያለመቅረባቸውን ፣ ችሎቱ ላይ የተሰየሙት ዳኞች ቁጥር ሶስት ከመሆናቸውም በተጨማሪ መዘገቡን ሲዘጋውም በሶስት ዳኞች ብቻ መሆኑና መዝገቡ ሲዘጋ የተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌም መልስ ሰጪን ሳይጠራ ይግባኙን ለመሰረዝ ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግገው ቁጥር 337 መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም የፍርድ ቤት ክርክር በሕጉ አግባብ በተደነገገው የሥነ ሥርአት ሕግ መሠረት መመራት አለበት፡፡ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ችሎትም በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠለት ሥርዓት እስከሌለ ድረስ ተፈፃሚነት ባለው የስነ ስርዓት ሕግ መሠረት ከተዘረጋው ሥርዓት አንፃር ጉዳዮችን መምራት አለበት፡፡ ጉዳዮች በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት የሚመሩትም አይነተኛ አላማም ክርክሮችን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ እንዲቋጩ ማድረግ ስለመሆኑም ይታመናል፡፡ ይህንኑ የሥነ ሥርዓት ሕጉን አላማ ለማሳካት ደግሞ በሕጉ የተመለከቱትን የስነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን እንደየአግባብነታቸው መከተልን የግድ ይላል፡፡ በስነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎችን እንደየአግባብነታቸው ያለመከተል በተከራካሪ ወገኖች መሰረታዊ መብት ላይ አሉታዊ ውጤት ማስከተሉ አይቀሬ ነው፡፡ ስለሆነም በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት

ሊኖራቸው የሚገባው ለጉዳዩ  አግባብነት ሲኖራቸው እንጂ በዘፈቀደ ሊሆን አይገባም። ድንጋጌዎቹ አግባብነት ያላቸው ስለመሆኑ ከመለየቱ በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ ተገቢነት አለው የሚለውን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ የሚሰጠው ችሎትም በሕጉ አግባብ የተመለከተው የዳኞች ቁጥር የተሟላ ሊሆን ይገባል። በሕጉ አግባብ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ የሚሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ደግሞ  እንደተሰጠ የማይቆጠርና ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባ አይደለም።

ወደተያዘው ጉዳዩ ስንመለስ በክልሉ የሰበር ችሎት በክልሉ አዋጅ ቁጥር 153/2000 እና ይህንኑ አዋጅ በአሻሻለው አዋጅ ቁጥር 169/2002 ተደራጅቷል። በእነዚህ አዋጆች መሠረት  የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ብለው ሶስት ዳኞች ተሰይመውበት አምስት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ሊታይ ይገባል ተብሎ ትእዛዝ ተሰጥቶበት አመልካችንና ተጠሪን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ መያዙ ተረጋግጦ እያለ ጉዳዩ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት አይደለም። ጉዳዩ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲቀርብ ከተደረገ በሁዋላ የቃል ክርክርን ለመስማት ሶስቱ ዳኞች በእለቱ ተሰይመው ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ቢሆንም መዝገቡን ለመዝጋት ግን በዚህ የዳኞች ቁጥር የሚቻል ስለመሆኑ የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ያደራጀው የክልሉ ሕግም ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች አያሳዩም። ስለሆነም የአመልካች የሰበር አቤቱታ የተዘጋው በሕጉ አግባብ የተመለከተውን የዳኞችን ቁጥር ባሟላ ችሎት በአለመሆኑ ትዕዛዙ እንደተሰጠ የማይቆጠርና ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባው አይደለም።

ሌላው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሲዘጋ መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን ነው። እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅራቢን ክርክር ለመስማት ቀጠሮ ይዞ እንደነበርና የመስማቱ ዓላማም የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል አልተፈፀመበትም የሚለውን ለይቶ በተሟላ ችሎት የሚታይ መሆኑንና አለመሆን ለማዘዝ ስለመሆኑን  ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ክርክሩን የሚመራበት የእራሱ የሆነ የጉዳይ አካሄድ ሥርዓት የለውም። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመራው መደበኛ ችሎቶች በሚመሩበት በ1958 ዓ.ም በወጣው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት ነው።

ይህንን መነሻ አድርገን ጉዳዩን ስናየው መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚለውን የፅሑፍ ቅሬታ በማብራራት ረገድ የሰበር አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ እንዲያሰማ ችሎቱ ቀጠሮ ከያዘ ይህን ሥርዓት ለመፈፀም የሚያዘው ቀጠሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ለመፈፀም የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የግድ እንዲቀርብ የሚጠበቅበት አይደለም። አመልካቹ ጉዳዩን የበለጠ ለማብራራት የሚጠቀምበት መብት ቀሪ ከሚሆንበት በስተቀር ችሎቱ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ወይም አያስቀርም የሚል ትዕዛዝ ከመስጠት የማያግደው ሲሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 73 ድንጋጌም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው  የክርክር ደረጃ አይሆንም። ጉዳዩ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ ወደ አምስቱ የሰበር ችሎት ከቀረበ እና ክርክሩን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ከተያዘ ደግሞ  የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖርበት ሥርዓት የለም። በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ እንዲያሰሙ በችሎቱ ቀጠሮ ከተያዘ በኂላ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን በመጥቀስ መዝገቡን መዝጋቱም ሕጋዊ አካሄዱን የተከተለ አይደለም። በአጠቃላይ  አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ

እንዲያሰሙ ችሎቱ ቀጠሮ ከያዘ ይህን ሥርዓት ለመፈፀም የሚያዘው ቀጠሮ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር አምስት ሁኖ እያለ መዝገቡን በሶስት ዳኞች መዝጋቱና መዝገቡን ለመዝጋት የተጠቀሰው የስነ ስርአት ሕጉ ድንጋጌም አምስት ዳኞች በተሰየሙት ችሎት ባለው የክርክር ደረጃ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01515 መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም በመዝገብ መዝጋት ረገድ የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቀድሞ ያስቀርባል በተባለው መሠረት ተጠሪ ባሉበት ግራ ቀኙ በተሟላ ችሎት እንዲሰሙ እንዲደረግና ተገቢ ስርዓት መሠረት ተደርጎም ክርክሩ ተካሂዶ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አምስቱ ዳኞች ወደሚሰየሙበት ችሎት መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

# አሠራና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ 67533

ጥቅምት 8 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒሽን ኮ/ን

**ተጠሪዎች፡-** 1. በረከት በለጠ

2. ታሪኩ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሠራተኞች መካከል የተነሣውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በአዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የሥራ ውላችንን ከሕግ ውጪ አቋርጦብናል በማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ወደ ሥራቸው እንዲመልሳቸው፤ ይህ ካልተቻለ ደግሞ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ይከፈላቸው ዘንድ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት ነው፡፡ የተሰናበቱትም በውሉ መሠረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኂላ፣ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በውሉ እና በሕጉ መሠረት ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በዚህ መሠረትም በሕጉ መሠረት መከፈል አለበት ያለውን ክፍያ ብቻ ተከፍሎአቸው ይሰናበቱ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ውሣኔውን በመቃወም ለአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የተጠሪዎችን ክርክር በመቀበል ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ ተጠሪዎች ወደ ሥራቸው ይመለሱ በማለትም ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ የሰበር ችሎቱ አቤቱታ በቀረበበት ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተደርጎ የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው የመባሉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪዎች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገው ክርክር እና የተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት እንዳየነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሥራ ውል በሚሰራው ሥራ ዓይነት እና በጊዜ የተወሰነ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሳይሰበሰብ የቆየውን የስልክ አገልግሎት ክፍያ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ በፍ/ቤት እየቀረቡ ለመከራከር ወይም የነገረ ፈጅነት አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ ውሉ ይህ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ አለማከራከሩ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡአቸው ውሣኔዎች ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ አመልካች ውሉን ለአንድ ጊዜ አራዝሞት እንደነበር በክርክሩ ተገልጾአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ ያደረገው /ውሉ በሕጉ አግባብ ነው የተቋረጠው ያለው/ የውሉን ይዘት እና የሥራው ማለቅ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይግባኙን የሰማው ፍ/ቤትም ቢሆን በውሉ ይዘት ላይ የተለየ ግንዛቤ እንዳለው አልገለጸም፡፡ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ አላለቀም እሚል መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው ለማለት የበቃው አመልካችን እንደተቋም በመውሰድ ብቻ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት መለስተኛ የሕግ ባለሙያ የሚል ነው፡፡ ይህ የሥራ መደብ ደግሞ ተቋሙ እስካለ ድረስ ያለ ነው የሚል ምክንያት ነው የሰጠው፡፡

በእርግጥ አመልካች እንደተቋም አሁንም አለ፣ መኖሩም ይቀጥላል፡፡ ለክርክሩ አወሳሰን መያዝ ያለበት ጭብጥ ተጠሪዎች የተቀጠሩት በአሰሪና በሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሠረት ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ጭብጥ መፈታት ያለበትም የአመልካችን ድርጅታዊ አቋም መሠረት በማድረግ ሳይሆን፣ በሥራው አይነትም የተወሰነ ነው፡፡ በውሉ መሠረት ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ የሚያልቅ አይደለም ወይም አላለቀም አልተባለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪዎችን በሠራተኛነት ይዞ የሚቀጥልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ውሉ ለተወሰነ ሥራ የተደረገ በመሆኑ አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበተው በአንቀጽ 10/1 እና 24/1/ መሠረት ነው፡፡ ይግባኙን የሰማው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ.ቁ. 09768 መጋቢት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 52288 ሚያዝያ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተደርጎ የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 69471
ጥቅምት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች:- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮፕሬሽን ደቡብ ሪጅን - ነገረ ፈጅ አየነው ዲለሌቻ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አቶ ጥበቡ ተሰማ - ጠበቃ ወርቀአገኘሁ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፍርድ ባለመብትነት ባቀረበው የአፈፃፀም አቤቱታ በማቅረቡ በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረ ነው። ቀረቦ የነበረው የአፈፃፀም አቤቱታ በተመደብኩበት የሥራ መድብና ደሞዝ ቀድሞ በተሰጠው ፍርድ መሠረት እንዲፈፀምልኝ የሚል ነው። አመልካች ለቀረበው የአፈፃፀም አቤቱታ መልስ ሲሰጥ ቀድሞ የነበረው መዋቅር በመንግሥት መመሪያ የተሰረዘ በመሆኑ እንደውሣኔው መፈፀም ያልቻለ መሆኑና አዲስ በወጣው መዋቅር መሠረት ደግሞ የሚመደብበትን ቦታ እንዲጠባበቅ በማለት ተከራክሯል።

የአፈፃፀም መዝገቡን የያዘው ፍርድ ቤት በአፈፃፀሙ ዙሪያ በዚሁ መልኩ ካከራከረ በኋላ የፍርድ ባለመብት (የአሁኑ ተጠሪ) ፍርድ ያገኘው የቀድሞ መዋቅር ሥራ ላይ በነበረበት ወቅትና አዲሱ መዋቅር ባልነበረበት ወቅት በመሆኑ በፍርዱ መሠረት ሊፈፀም ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ የቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 337 መሠረት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል።

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምተናል። ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከታያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመረው ለአሁኑ ተጠሪ ተሰጥቶት የነበረው ፍርድ ሊፈፅም የሚችል ፍርድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ይሄ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁ መሠረት አመልካች አጥብቆ እየተከራከረ ያለው ለተጠሪ በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ መኖሩን ሳይክድ ቀድሞ የነበረው የድርጅት መዋቅር አደረጃጀቱን ለማሻሻል በተወሰዱ እርምጃ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 197/2003 መሠረት የፈረሰ በመሆኑ እንደፍርዱ ለመፈፀም ያልተቻለ መሆኑን ነው። በሌላ በኩል የተጠሪ

ክርክር ቀድሞ የነበረው የድርጅቱ መዋቅር የፈረሰ ስለመሆኑ ሳያስተባብል ውሣኔውን ከመፈፀም የሚከለክል ባለመሆኑ እንደፍርዱ ሊፈፀምልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የክርክር ሂደት አመልካች ድርጅትን በተመለከተ መንግሥት ባወጣው ደንብ መሠረት ቀድሞ የነበረው መዋቅር የፈረሰ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በተጨማሪም የመዋቅር ለውጡ ከመምጣቱ በፊት ተጠሪ በፍርድ ቤት ውሣኔ የፍርድ ባለመብት ስለመሆኑ እና ይሄው የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሣኔ ሣይፈፀም የድርጅቱ አደረጃጀት በመንግስት መለወጡ በተመሳሳይ መልኩ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ የቀድሞውን የድርጅቱን አደረጃጀት መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ከመፈፀሙ በፊት መንግሥት በሚያወጣው ደንብ መሠረት አደረጃጀቱ ቢለውጥ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በክርክሩ ሂደት የታወቁትን ፍሬ ነገሮች ይዘን ወደ ህጉ ስንመለስ ቀድሞ በሥራ ላይ የነበረው የአመልካች ድርጅት አደረጃጀትና በፍርድ ቤት ለተሰጠው ፍርድና ተጠሪን የፍርድ ባለመብት ያደረገው ውሣኔ መሠረት ያደረገው መዋቅር በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በሥራ ላይ በሌለ መዋቅር መሠረት የተሰጠው ፍርድ ለተጠሪ ይፈፀም ማለት ደግሞ የማይቻል ነው፡፡ በመሠረቱ በመርህ ደረጃ የተሰጡት የፍርድ ቤት ውሣኔዎች ተፈፃሚነት የሚያገኙ ሲሆን አልፎ አልፎ ሊፈፀም የማይቻል ፍርድ ሊኖር እንደሚቻል ከፍታሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 392(1) መሠረት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ሊፈፀም የሚቻል ውሣኔ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ማረጋገጥ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ የማይፈፀምበት አግባብ ካለ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 392(2) መሠረት ይሄንኑ በማመልከት ሊፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል ያመለክታል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይም በሌለ አደረጃጀት ላይ ውሣኔ ማስፈፀም የማይቻል መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች በፍርድ መሠረት ይፈፀም በማለት ትዕዛዝ መስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 53298 በቀን 26-9-2003 ዓ.ም እና የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 10229 በቀን 22-9-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በህግ አግባብ ቀሪ በሆነ አደረጃጀትን መሠረት በማድረግ ፍርድ እንዲፈፀም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ 61549

ህዳር 6 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኦሮሚያ መንገዶች በለሥልጣን - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብርቄሣ አብራሂም - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካች የገቢ ግብር ሣይቀንስ ለተጠሪ የሥራ ስንብትና ሌሎች ክፍያዎችን እንድንከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተትና ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር በነበራት የሥራ ክርክር እንዲከፈላት የተወሰነላት የስራ ስንብት የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ግብር ተቀናሽ ሣያደረግ በደመወዟ በጥቅሉ አስቦ እንዲከፍል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን የአገልግሎት ካሣና ግብር ሣይቀንስ በሙሉ ደመወዝ (gross income) ታስቦ ይከፈላት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያና የአገልግሎት ካሣ ክፍያ ግብር ሣይቀነስ በሙሉ ደመወዟ አስበን እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 286/94 እና ደንብ ቁጥር 78/1994 የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ክርክር የህግ መሠረት የለውም የሚል መስከረም 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ የገቢ ግብር ሣይቀናነስ በሙሉ ደመወዙ በማስላት የስራ ስንብት ክፍያና የአገልግሎት ካሣ ክፍያ እንዲከፈል የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ውሣኔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 10 ገቢ ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፍዩ

የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ሁሉ ጥቅም ይጨምራል በማለት ሰፊ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

ከላይ በተገለፀው አዋጅ አንቀጽ 10 ማናቸውም ሰው በመቀጠር ከሚያገኘው ገቢ ግብር የመክፈል ሃላፊነት እንዳለበት ማናቸውም ቀጣሪ በሚከፍለው እያንዳንዱ ክፍያ ግብሩን የመቀነስና ለመንግስት ገቢ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት የተደነገገውን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 ከግብር ነፃ የሚሆኑ ክፍያዎች የተዘረዘሩ ሲሆን በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 3 ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች በዝርዝር ተደንግገዋል ስለሆነም የስራ ስንብት ክፍያንና ካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 ግብር የማይከፈልባቸው ስለመሆኑ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ስለሆነም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በተጣለበት ሃላፊነት መሠረት ለተጠሪ ከሚከፈለው ክፍያ የገቢ ግብር በመቀነስ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ በሙሉ ደመወዝ አስልቶ የሥራ ስንበት የካሣ ክፍያ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የገቢ ግብር በመቀነሰ ለተጠሪ በፍርድ የተወሰነለትን የሥራ ስንብት ክፍያና የካሣ ክፍያ ይክፈላት በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 69179

ሕዳር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ጨረር መካላከያ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ኃይሉ ታደሠ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ታሪኩ ጫኔ - ጠበቃ ካሣኝ ይበልጣል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስራ ምክንያት የወጣ ንብረት ባለመመለሱ የተነሳ የንብረቱ ጉድለት በገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ተጠሪ ለስራ የተረከቡትን ግምቱ ብር 23,423.39 (ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) የሆነ የጨረር መጠን መለኪያ(Universal survey meter- model RDS-200) እና ግምቱ ብር 53,443.85 (ሃምሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ አርባ ሶስት ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም) የሆነ የራጅ ጥራት መለኪያ (Digital quality control sit- 1 set) መጠበቅ ሲገባቸው በቸልተኝነትና በጥንቃቂ ጉድለት ምክንያት ለተገዛበት ጉዳይ ሳይውል ያጠፉ መሆኑን ገልፆ የመሳሪያዎቹን ጠቅላላ ድምር ብር 76,867.34 (ሰባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከሰላሳ አራት ሳንቲም) እንዲከፍሉ፣ የንብረቶቹ ዋጋ ከገበያ ውስጥ ከጨመረ ይኸው ታክሎበት ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም በአመልካች መስሪያ ቤት ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ ንብረቶቹን ለስራ መረከባቸውን ሳይክዱ ንብረቶቹን ለስራ ይዘው ከሄዱበት ቦታ ላይ በመኪና ውስጥ በጥንቃቄ አስቀምጠው እያለ በስራ ቦታ ላይ በሥርቆት ምክንያት የጠፉባቸው መሆኑን ገልፀው ከአቅም በላይ ለተከሰተው የንብረት መጥፋት በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 65 እና አግባብነት ባለው የመንግስት ንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት ሃላፊነት የለብኝም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በሁዋላ ለክርክሩ መሰረት የሆኑት ንብረቶች ተጠሪ በስራ ላይ እያሉ በጥንቃቄ ካስቀመጡበት ቦታ በስርቆት የጠፉ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝና የአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 65 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ለስራ የተረከቡትን ንብረት ያላስረከቡ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ለንብረቱ መጥፋት ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለደረሰ የንብረት መጥፋት ኃላፊ አይሆኑም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ምላሽ የሚያስፈልገው የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪ ከአመልካች የተረከቧቸውን እቃዎች  የዋጋ ግምታቸውን ለመክፈል ይገደዳሉ? ወይስ ይገደዱም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን እቃዎች ከአመልካች ላይ የተረከቡ መሆኑን ሳይክዱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩት ለመስሪያ ቤቱ ስራ በሄዱበት ቦታ በስራው ቦታ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሁኖ ፣ በመስሪያ ቤቱ መኪና ውስጥ አስቀምጠው እና መኪናውን በመቆለፍ የአበል ክፍያ ለመቀበል ወደ መ/ቤቱ ሂሳብ ክፍል በሄዱበት ጊዜ እቃዎቹ ሊሰረቁ ወይም ሊጠፉ ችለዋል በማለት ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የቻለው የተረከቧቸው እቃዎች በስርቆት ምክንያት የጠፉ መሆኑ ተረጋግጧል ፣ ይህም ከተጠሪ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ንብረቶቹ የጠፉ መሆኑን ስለሚያሳይና በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት የነበረ መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ፍሬ ነገርን አጣርቶና የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መዝኖ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀፅ 65 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት ያልነበረ፣ እቃዎቹ በስርቆት ምክንያት የጠፉ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ ተጠሪ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ነው፡፡ ይሁንና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈጠረው የሥራ ውል መነሻነት ለክሱ መነሻ የሆኑትን እቃዎችን ስለመረከቡ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በተጠሪም ያልተካደም ቢሆንም ተጠሪ እነዚህን ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን እቃዎች ከአመልካች ከተረከቡ በኋላ በአሰሪው መስሪያ ቤት ወደ ታዘዙበት የስራ ቦታ ይዘው ሄደው በተገቢው ቦታና ጥንቃቄ መሰረት አስቀምጠው በነበሩበት ሁኔታ ንብረቶቹ መሰረቃቸው ወይም መጥፋታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህንኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሱበትን ድምዳሜ ይህ ችሎት እንዳለ ከመቀበል ውጪ የማስረጃ ምዘናን መሰረት በማድረግ ሊመረምረው የማይገባው መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ይህ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ማረም ነው፡፡ በመሆኑም ንብረቶቹ የጠፉት በስርቆት መሆኑና ስርቆቱ ደግሞ የተፈፀመው ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው በነበሩበት ጊዜ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር

መረጋገጡን ይዘን በሕጉ አተረጓጎም ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን እንመለከታለን፡፡ ተጠሪ አከራካሪ እቃዎቹን ለአመልካች መስሪያ ቤት እስከሚያስረክቡ ጊዜ ድረስ  በንብረቶቹ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ፣ ብልሽት ወይንም መጥፋት በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህ ችግር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው መስሪያ ቤት ለስራ እቃዎቹን ሲረከብ የሚፈርመበት ዋናው ምክንያትም ይህንኑ ግዴታውን ካልተወጣ ኃላፊነት ሊከተልበት ስለሚገባው እንደሆነ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪ ፈርሞ የተከረባቸውን እነዚህን እቃዎች እንዳይጠፉ፣ እንዳይሰረቁም ሆነ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅበት በሥራ ሰዓት ሲሆን ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት ከራሱ ጥንቃቄ ጉድለት ውጪ በሆነ ምክንያት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭና በራሱ እጅ ባልነበሩበት ጊዜ የጠፉ ስለመሆኑ የማስረዳቱ ሸክም  አለባቸው፡፡ ይህንኑ ግዴታውን የተወጡ ስለመሆኑ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን መዝነው አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተጠሪ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ያለመስተባበሉም በበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ሸክማቸውን ከተወጡ ወይም እቃዎቹ በስራ ላይ ቆይተው በጥንቃቄ ከተቀመጡበት ቦታ በስርቆት መጥፋታቸውን በማስረጃ ከአረጋገጡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2027 ድንጋጌ መሠረት  በቸልተኝነት ጥፋት  መፈጸማቸውን የማያረጋግጥ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ባለው በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 65 ስር ደግሞ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ፈርሞ ላወጣው ንብረት መጥፋት በእዳ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው  ፈርሞ ላወጣው ንብረት መጥፋት የሰራተኛው ቸልተኝነት የታየ ወይም በሰራተኛው በኩል ሆነ ተብሎ የተፈፀመ ድርጊት ያለ እንደሆነ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 28865  በኪራይ ቤቶች ኤጀንሲና በአቶ ካሳ ግዛው መካከል በነበረው ክርክር ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ለዚህ ጉዳይም አግባብነት ያለው መሆኑን ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን ይህ ችሎት ይህንኑ መዝገብ ሲመለከተው በመዝገቡ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ አሁን ከታያዘው መዝገብ ጉዳይ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው ለማለት የማይቻል ሁኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ንብረቶቹ  በሥራ ሰዓት በጥንቃቄ አስቀምጠው ባለበት ሁኔታ በስርቆት የጠፉ ስለመሆኑ በማረጋገጥና የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከላይ ከተጠቀሰው አዋጅ ጋር በማዛመድ ተመልክቶ ተጠሪ ጥፋት መፈጸማቸውን አመልካች አላረጋገጠም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ መቀበሉ  በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት  ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 79143 ታህሳስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103031 ሚያዚያ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚኅ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 69125
ታህሣሥ 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሠላም ተስፋዬ ጠበቃ ዳንኤል ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አልካን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሙሉጌታ ሀመነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የሥራ ውል ከህግ ውጭ ያቋረጠ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ አመልካች የተቀጠሩት በዲፕሎማ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር ነበር፡፡ በዲፕሎማ ኮርስ እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳይሰጥ ከመንግሥት ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ ከሥራ የተሰናበቱ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በአዋጁ መሠረት የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያለውን የሥራ ውል ያቋረጠው በህግ በተደነገገው መሠረት ነው በማለት ከወሰነ በኂላ ተጠሪ ለአመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪ ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተው በህጉ በተደነገገው መሠረት ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች በመንግስት ትዕዛዝ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለዲፕሎማ ተማሪዎች እንዳይሰጥ መከልከሉና በዚህ ምክንያት ተጠሪ የሥራ ውሉን ማቋረጡ ተጠሪን የማስጠንቀቂያ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ የሥራ መደቡን አልሠረዝኩም፡፡ የሥራ መደቡ ለዲፕሎማ ትምህርት እንደማያስፈልግ ትዕዛዝ የተሰጠው በመንግስት ነው፡፡ ስለዚህ በመንግስት ትዕዛዝ የሥራ መደቡ አላስፈላጊ የሆነ በመሆኑ የማስጠንቀቂያና የሥራ ስንብት ክፍያ የምከፍልበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት የተቀጠሩት ድርጅቱ በዲኘሎማ ትምህርት ለሚያስተምራቸው ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር እንደነበር በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ እያስተማሩ በነበሩበት ጊዜ መንግስት በዲኘሎማ ደረጃ ለሚሰጥ ትምህርት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መሰጠት የሌለበት መሆኑን የሚገልፅ መመሪያ ማውጣቱ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አመልካች የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርት ለሚሰጡ ተቋማት እንደማያስፈልግና አመልካች ያስተምሩት የነበረው ትምህርት ሊሰጥ እንደማይችል መንግስት መመሪያ ያወጣበት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው ከዚህ በኂላ በተቋሙ የሚሠሩት ሥራ የለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው በራሱ አነሳሽነት አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው በህግ ሥልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በተላለፈው መመሪያ መሠረት አመልካች የሚያስተምሩት የእንግሊዝኛ ቋንቋ በዲኘሎማ ደረጃ መሰጠት የሌለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ አስገዳጅ ትዕዛዝ ስለደረሰው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከአቅሙ በላይ በሆነ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት በመሆኑ በጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ መሠረት ለአመልካች ተሠጥቷት የነበረው ሥራ ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል ባወጣው መመሪያ መሠረት አመልካች እየሠራች ለመቀጠል የማትችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሚሰጠው ሥራ በሌለበት ሁኔታ የሥራ ውሉ እንዲቀጥል የማድረግ ህጋዊ ግዴታ የለበትም፡፡ የሥራ ውሉ በመንግስት በወጣ መመሪያ ተፈፃሚነት ምክንያት የተቋረጠ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያም ሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 60489

ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ አምባዬ ወ/ማሪያም- የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪዎች፡-** የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት - ነገረፈጅ በየነ ቢቂላ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አመልካች የስራ መሪ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ከተጠሪ ድርጅት ጋር ባለው የስራ ውልን መሰረት ያደረገ ክርክር ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአማራ ብሔ/ክል/መንግስት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ አመልካችን ከስራ ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት በህገ-ወጥ መንገድ በመሆኑ የስራ ውሉ ተቋርጦ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ያልተከፈለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው ይመለስ በማለት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን በማመልከት ክፍያን በተመለከተ ግን ተፈጻሚነት ያለው የፍታሐብሔር ህጉ መሆኑን በመግለጽ የሶስት ወራት ደመወዝ በካሳ መልክ እና የሁለት ወራት ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብቻ ተፈጽሞለት እንዲሰናበት በማለት በመወሰኑ እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ውሳኔ በማጽናቱ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች ያነሱ ሲሆን ነሐሴ 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በሶስት ገጽ በተጻፈ የቀረበ የቅሬታ ፍሬ-ሃሳብ፡- የአመልካች የስራ ውል በተጠሪ አነሳሽነት በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠ ስለመሆኑ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ያለውን የድርጅቱን የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ በግልጽ በሚቃረን መልኩ ውሳኔ የሰጡ በመሆኑ የተሰጡት ፍርዶች ተሽረው የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቶልኝ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 59(2) መሰረት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመለስ እንዲወሰንልኝ፣ ይህ አይቻልም የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት ቢኖር ግን በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃነት ተያይዞ በቀረበውና በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በስራ ላይ ባለው የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 54(1)(ሀ)፣ 53(3)(ሀ)ና(ለ)፣ እንዲሁም 60(2) መሰረት የስልሳ ቀን ደመወዝ በካሳ መልክ፣ የ12 ወራት ደመወዝ የስራ ስንብት ክፍያ እና የአንድ ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ

የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዞ ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ በተጻፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- አመልካች ክስ ሲያቀርቡ የሶስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ስራዬ ልመለስ የሚል እንጂ የስራ ስንብት ክፍያ አላቀረቡም፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሱትን ክርክር በማንሳት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈጸሙለት ሊጠይቅ አይገባውም፣ በተጠሪ እና አመልካች መካከል ያለው ክርክር መታየት ያለበት በፍታሐብሔር ህግ እንጂ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መሆን የለበትም፣ የበላይ እና ገዥ የሆነው ህግ የፍታሐብሔር ህጉ የስራ መሪ ከስራ ሲሰናበት የሚከፈለው ክፍያ የሶስት ወራት ደመወዝ ብቻ ስለመሆኑ እየደነገገ እና ከዚህ በፊት የሰበር ሰሚው ችሎትም የሶስት ወራት ደመወዝ ብቻ የሚገባው ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የመተዳደሪያ ደንቡ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም የሚል ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯቸዋል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተወሰደው የስራ ስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ውጤቱን በተመለከተ ግን ተፈጻሚነት የሚኖረው የፍታሐብሔር ህጉ ነው በማለት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተፈጻሚ ያለመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ የተያዘው ጉዳይ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በሚሰሩት የስራ መሪዎች ላይ ተፈጻሚነት ያለው መተዳደሪያ ደንብ ስለመኖሩ እና አመልካችም የስራ መሪ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ስራ ላይ ያለው ልዩ ህግ እስካለ ድረስ እና ያለው ደንብ ደግሞ ለሞራል እና ለህግ ተቃራኒ ነው ወይም ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይገባበትን ህጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ ተፈጻሚነት የሚኖረው ይሄው ልዩ ህግ በመሆኑ ወደ አጠቃላይ የፍታሐብሔር ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፍ ፍለጋ የሚኬድበት አግባብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በግራ ቀኙ መካከል ስራ ላይ ያለው መተዳደሪያ ደንብ ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይገባ ስለመሆኑ ያቀረበው ህጋዊ ምክንያት በሌለበት፣ ወደ ፍታብሔር ህግ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚኬደው ለዚህ ጉዳይ የተለየ ህግ በሌለበት ሁኔታ በመሆኑ፣ ከዚህ በፊት ይሄ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል በማለት የተነሳውም ቢሆን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ባለመሆኑ እና ለደንቡ ተፈጻሚ አለመሆን የቀረበ ህጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ በተጠሪ በኩል በደንቡ ተፈጻሚነት ዙሪያ የተነሳው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው ብለናል፡፡

አመልካች ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 59(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበተው የስራ መሪ ወደ ስራ ለመመለስ መብት እንዳለው በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ፍርድ ቤቶች በስራው መልካም አካሄድ ላይ የስራ መሪው ወደ ስራው መመለስ ችግር ያስከትላል በማለት ሲያምንበት ለዚሁ ለህገ-ወጥ ስንብት ተገቢነት ያላቸው ክፍያዎች ተፈጽመውለት እንዲሰናበት መወሰንን የሚከለክል አይደለም፡፡ በዚሁ መሰረት የአመልካች ወደ ምድብ ስራው የመመለስ ጥያቄን በተመለከተ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውድቅ አድርገው ማለፋቸውን በውጤት ደረጃ ይሄም ችሎት ተቀብሎታል፡፡ በመቀጠል የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪ እንደሚከራከረው ክስ ሲያቀርብ የሶስት ወራት ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ እንጂ የስራ ስንብት ክፍያ አልጠየቀም በሚል ነው፡፡

አመልካች ክስ ሲያቀርብ ከስራ ተሰናብቶ በሶስተኛ ወሩ መሆኑ የተቋረጠው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የአመልካች ወደ ስራው መመለስ ለስራው መልካም አካሄድ ችግር ሊኖረው ይችላል ብሎ ሲያምን ከዚሁ ከህገ-ወጥ ስንብት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች ተፈጽመውለት እንዲሰናበት መወሰንን የሚከለክልና ህጉም የመጀመሪያው አማራጭ (ወደ ስራ የመመለስ የዳኝነት ጥያቄ) ተቀባይነት ካጣ ወደ ሁለተኛውና ተያያዥ ክፍያዎች መፈጸም በሚቻል መልኩ የተደነገገ በመሆኑ ተያያዥ ክፍያዎች እንዲፈጸምለት ውሳኔ መስጠት ያልተጠየቀ ዳኝነት ነው የሚባልበት አግባብ የለም፡፡

ተያያዥ ክፍያዎችን በተመለከተ በደርጅቱ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 54(1)(ሀ)፣ 53(3)(ሀ)(ለ)፣ እና 60(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበተ የስራ መሪ የካሳ፣ የስራ ስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ክፍያዎች ለአመልካች ሊፈጸሙለት ይገባል ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረት የክፍያ መጠኑን ስንመለከት አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራ የነበረ ስለመሆኑ እና የደመወዝ መጠኑ ደግሞ ብር 1,200 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ) ስለመሆኑ ያከራከረ ነጥብ ባለመሆኑ በዚሁ መሰረት ስሌቱን ሰርተናል፡፡ ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ክፍያውን ስናሰላ በደንቡ አንቀጽ 54(1)(ሀ) መሰረት የሁለት(2) ወራት ደመወዝ በካሳ መልክ 1200 x 2= 2,400 ብር (ሁለት ሺህ አራት መቶ ብር)፣ በደንቡ አንቀጽ 53(3)(ሀ)(ለ) መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ የ26 ዓመት አገልግሎት መሰረት በማድረግ ስናሰላ 1,200 + 1/3 X 1,200(26-1)= 11,200 ብር (አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እና በደንቡ አንቀጽ 60(2) መሰረት ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የአንድ ወር ደመወዝ ብር 1,200 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ባጠቃላይ ተጠሪ ለአመልካች ብር 14,800 ( አስራ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ሊከፍለው ይገባል ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የበታች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ተፈጻሚነት ያለው ህግ በተመለከተ በድርጅቱ ውስጥ በስራ ላይ ያለው የስራ መሪዎች ደንብ ሆኖ እያለ ያለ በቂ ህጋዊ ምክንያት ማለፉ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት የውሳኔ ክፍል በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 51756 ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 14504 ጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት መታየት ያለበት በተጠሪ ድርጅት በስራ ላይ ባለው የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በህገ-ወጥ መንገድ አመልካችን ከስራ ያሰናበተው በመሆኑ የካሳ፣ የስራ ስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ባጠቃላይ 14,800 ብር (አስራ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለአመልካች እንዲከፍል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 67382

ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1.አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር ነ/ፈጅ ሰላማዊት ጌታቸው ቀረቡ

2. ባዜን የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪዎች ፡- አቶ አርጋው አበበ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የግል የስራ ክርክር ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን ክርክር በመመልከት ተጠሪ በራሱ ፍቃድ ስራ መልቀቁን ተከትሎ የሚፈጸሙት የስራ ስንብት፣የአመት እረፍት እና ሌሎች ጥቅሞች ወርሃዊ ደመወዝን መሰረት በማድረግ ስለሚከፈሉ እና እንደ ደመወዝ የሚታዩ በመሆናቸው ከተጠሪ ላይ የሚፈለጉ የተለያዩ ዕዳዎች አሉ በማለት ለዕዳው ተብሎ ከስራ ሲሰናበት ሊቀነስበት አይገባም በማለት ውሳኔ በመስጠቱ እና ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337 መሰረት በማጽናቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ ነው፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች በማመልከት ያቀረቡ ሲሆን በቀን 27-7-2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ የተጻፈ የቅሬታቸው ፍሬ-ሃሳብ፡- በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 59(1) በግልጽ እንደሚደነግገው በዕዳ ሊያዝ የማይችለው ደመወዝ ብቻ ነው እንዲባልልን፤ አመልካቾች የተጠሪን ዕዳ የቀነሱት እንደፕሮቪደንት ፈንድ፣ የአገልግሎት ክፍያ እና ከመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች ላይ በመሆኑ ከተጠሪ ላይ ዕዳው መቀነሱ ተገቢ ነው ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በአንድ ገጽ በተጻፈ የጽሁፍ መልስ የሰጡ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- ያልተወራረደ ሂሳብ አለበት የሚለው አመልካች በመሆኑ፣ በዚህ ድርጅት ውስጥ ከአስር አመት በላይ ስሰራ ምንም ዓይነት ዕዳ የሌለብኝ እና በየወሩ ሙሉ ደመወዜ የሚከፈለኝ በመሆኑ፣ አሁን ስራ በመልቀቄ ምክንያት የአገልግሎት ክፍያ ላለመፈጸም ሒሳቡን እንዳሻቸው ሰርተው ያቀረቡት በመሆኑ፣ዕዳው በትክክል ያለብኝ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥብኝ አመልካች እንደፈለገው ቀንሶ እንዲሰጥ መደረግ ስለሌለበት በበታች

ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ እና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ ተጠሪ አላወራረደም የተባለውን ሒሳብ አመልካቾች ለተጠሪ ከሚከፍሉት ክፍያዎች ላይ መቀነስ አይችሉም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ ጉዳዩ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምር የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ተጠሪ ስራውን በገዛ ፍቃዱ ሲለቅ ከሚከፈልለት ክፍያ ላይ ዕዳዎች አሉበት በማለት ሊቀንስበት አይገባውም ወደ ሚለው መደምደሚያ የደረሰው ከስራ በመሰናበቱ ምክንያት ለተጠሪ የሚፈጸሙለት ክፍያዎች ከደመወዝ ጋር የተያያዙ ናቸው በማለት እና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1) ን በመጥቀስ ስለመሆኑ ከውሳኔው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ደመወዝ ማለት ምን እንደሆነ እና የትኞቹ ክፍያዎች እንደ ደመወዝ የሚቆጠሩ ስለመሆኑ በዚሁ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 53(1) ስር ደመወዝ ማለት አንድ ሰራተኛ በስራ ውሉ መሰረት ለሚያከናውነው ስራ የሚከፈለው መደበኛ ክፍያ ማለት ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የትርፍ ሰአት ክፍያ፣አበል፣ከአሰሪ የሚከፈል ጉርሻ(ቦነስ)፣ኮሚሽን፣ሌሎች የማትጊያ ክፍያዎች እና ከደንበኞች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያዎች እንደ ደመወዝ የማይታዩ ስለመሆናቸው በዚሁ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 53(2) ስር ተደንግጓል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ አጠቃላይ ንባብ መገንዘብ የሚቻለው ደመወዝ የሚባለው በግራ ቀኙ መካከል ባለው የስራ ውል መሰረት ለተከናወነ ስራ የሚከፈል መደበኛ ክፍያ እንጂ ከዚህ ውጪ ያለውን በተለይም አሁን እያከራከረ ያለውን በስራ ስንብት ምክንያት የሚፈጸሙትን ክፍያዎች የማያጠቃልሉ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪ በስራ መሰናበቱ ምክንያት የሚፈጸሙለት ክፍያዎች እንደ ደመወዝ ይታያሉ በማለት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1)ን በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ምዕራፍ ሶስት ዘርፍ ሁለት ከአንቀጽ 36 እስከ 38 ድረስ ያለውና የስራ ውል ሲቋረጥ ደመወዝ እና ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች የሚፈጸምበትን አግባብ የሚደነግገው ክፍል ነው፡፡ አንድ የስራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ደመወዝ እና ተያያዥ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት ቀናት ውስጥ መከፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፣ሆኖም የክፍያው ጊዜ ሊራዘም የሚችለው ከአሰሪዉ የተረከበዉን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸዉንም ሂሳብ በማወራረድ በራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየዉ ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 36(1) ስር ተደንግጓል፡፡

በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 37 ስር በክፍያ መጠኑ ላይ አለመግባባት ሲኖር አከራካሪ ያልሆነዉ ክፍያ ሊፈጸም የሚገባ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ግራቀኙ በተጠሪ ላይ አመልካቾች ያልተወራረደ ሒሳብ አለ በማለት በሚከራከሩበት እና ተጠሪ በበኩሉ ምንም ዓይነት ዕዳ የሌለበት እና ራሳቸዉ የፈጠሩት ነዉ በማለት በሚከራከርበት ወቅት የእነዚህ ሁለቱ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የሚያስገነዝቡት አመልካቾች የተጠሪን ክፍያ ገንዘቡ በእጃቸዉ ስላለ ብቻ ቆርጠዉ ማስቀረት ሳይሆን በፍርድ ቤት አለ የሚሉትን ዕዳ በትክክል ያለበት ስለመሆኑ ማስወሰን የሚገባቸዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡ አመልካቾች ይሄንን ባልፈጸሙበት ሁኔታ እና ግራቀኙ

ያልተማመኑበትን ዕዳ ለተጠሪ ሊፈጸምለት ከሚገባዉ ክፍያ ላይ ቀንሶ ማስቀረቱ ከላይ የተመለከቱትን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና ተቀባይነት ያለዉ አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ ከስራ በመሰናበቱ ምክንያት ከሚከፈሉት ክፍያዎች ላይ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሆነዉን ሒሳብ መሰረት በማድረግ ቀንሶ ክፍያ መፈጸም አግባብነት የሌለዉ ነዉ ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም በሰጡት ዉሳኔ በስንብት ወቅት የሚፈጸሙት ክፍያዎች እንደደመወዝ ይቆጠራሉ በማለት የሰጡት ምክንያት ተቀባይነት ባይኖረዉም የደረሱበት መደምደሚያ ተቀባይነት ያለዉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 342 መሰረት ከዉጤት አኳያ ተቀብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.103360መጋቢት 26 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 70595 በቀን 17-6-2003ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በተጠሪ እና አመልካቾች መካከል አከራካሪ የሆነን ዕዳ በትክክል ዕዳዉ ስለመኖሩ በፍርድ ቤት ሳይወሰንበት በስንብት ወቅት ከስንብቱ ጋር በተያያዘ ለተጠሪ ከሚፈጸሙለት ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ የሚከፈልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 13-8-2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 73258

ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አበራሽ ፈይሳ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ነገት አብዲ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ እለፏ አበራ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጂ ሰቨን ንግድና ኢንዲስትሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ብርሃኔ አባይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-በተጠሪ ድርጅት መጋቢት 05 ቀን 1983 ዓ.ም በተለያዩ የስራ መደቦች ላይ ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው በየካቲት ወር 2003 ዓ.ም ስራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ ቢሆንም ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ ሊከፍላቸው ፈቃዳኛ ሊሆን ያለመቻሉን በመግለጽ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው፣ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ደግሞ ተገቢውን ክፍያ እንዲፈጽም እንዲሁም ለ3ኛ ተጠሪ ያላግባብ የቆረጠባቸውን የስድስት አመት ከስድስት ወር እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በድርጅቱ ከ20 ዓመታት በላይ ማገልገላቸውን፣3ኛ አመልካችም ከ10 ዓመት በላይ ማገልገላቸውን ገልዖ አመልካቾች በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2 ንዑስ ቁጥር 13 እና 14 ድንጋጌዎች መሰረት የጡረታ አበል ተመላሽ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፣የታመኑ ክፍያዎች ለአመልካቾች ተሰጥተዋል፣3ኛ አመልካችም የተቆረጠባቸው የአመት እረፍት ፈቃድ የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ከማህበራዊ ዋስትና አመልካቾች የጡረታ ተሸፋኝ ለመሆን የሚያበቃ የአገልግሎት ጊዜ እና የእድሜ ጣሪያ ያሚሉ መሆን ያለመሆኑን በሚመለከት ተጣርቶ እንዲቀረብለት ትእዛዝ ሰጥቶ ይኸው አካል አመልካቾች የጡረታ ተሸፋኝ ያለመሆናቸውን ከአረጋገጠለት በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ለአመልካቾች የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል ይገባል፣ሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎች ግን ተቀባይነት የላቸውም በማለት ወስኗል፡ተጠሪ የስራ ስንብት ለአመልካቾች ሊከፍል ይገባል ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የጡረታ ተመላሽ ተጠቃሚ ናቸው በሚል

ምክንያት የስራ ስንብት አገልግሎት ክፍያ አይገባቸውም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች የተመለሰላቸው ራሳቸው ያዋጡት የጡረታ ገንዘብ ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ከፍተኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ የጡረታ መብት ተጠቃሚ እንደሆኑ በመቁጠር የአገልግሎት ክፍያ አይገባቸውም በማለት መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 2(13)(14) እና አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና ይህንኑ ድንጋጌ ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀፅ 2(ሽ) ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች የጡረታ መዋጮአቸው ተመላሽ የተደረገላቸው በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ አመልካቾች የጡረታ ተመላሽ የሆነውን ገንዘብ ከወሰዱ የስራ ስንብት ክፍያ ሊያገኙ የሚችሉበት ሕጋዊ መሰረት የለም በማለት በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋለው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከአምስት አመታት በላይ ያገለገሉና ስራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን፣አመልካቾች ለጡረታ መብት የሚያበቃ እድሜና ያገልግሎት ዘመን ላይ ያልደረሱ መሆኑን የሚመለከተው አካል ማረጋገጡንና አመልካቾች ራሳቸው ለጡረታ ያዋጡት 4% መዋጮ ብቻ ተመላሽ የሆነላቸው መሆኑን ነው፡፡

ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያውን መክፈል የለበኝም የሚለው የጡረታ መዋጮ የተመለሰላቸው በመሆኑ በጡረታው ሕግ መሰረት የጡረታ አበል ተጠቃሚነታቸው ተረጋግጧል የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ወይም የጡረታ መብት ያለውና በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ የተገለለ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንደሌለው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሰ፣ሽ) ተመልክቶአል፡፡ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥበት የስራ ስንበት ክፍያ የሚፈጸምለት ለአሰሪው አገልግሎት ስለሰጠና ሊቋቋመው የማይችል ድንገተኛ የገንዘብ ችግር እንዳይገጥመው በሚል እሳቤ መሆኑ ይታመናል፡፡ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው አስተሳስብ ወይም ምክንያት ሲሆን በሕጉ እንደተመለከተው ሰራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት ካለው ግን የስራ ውሉ ቢቋረጥም፤ ገንዘብ ማግኘቱን ስለሚቀጥል (ስለቀጠለ) የስራ ስንብት ክፍያው አይከፈለውም፡፡የጡረታ አበል ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚነት ካለ የስራ ስንብት የማይከፈለው ከአንድ ምንጭ(አሰሪ) ሁለት ጊዜ ገንዘብ እንዳይከፈል ለመከልከል ታስቦ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የስራ ውሉን ያቋረጡት በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከአምስት አመታት በላይ ካገለገሉ በኋላ ነው ቢባልም፤በጡረታ ሕጉ መሰረት የጡረታ እድሜና አገልግሎት ዘመን ላይ ስለመድረሳቸውና የጡረታ አበል የሚያገኙ ለመሆኑ ተጠሪ አላስረዳም፡፡ አመልካቾች የስራ ውሉን እንዳቋረጠ የጡረታ አበል ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ የሚል ክርክርም

ሆነ ማስረጃ ከሌለ ደግሞ ለስራ ስንብት መከፈል መሰረት የሆነውን በሕጉ በስተጀርባ ያለውን ምክንያት መሰረት በማድረግ የስራ ስንብቱን ክፍያ ማስከፈል የግድ ይሆናል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ካልተተረጐመም ሰራተኛውን ለድንገተኛ የገንዘብ ችግር ማጋለጥ ይሆናል፡፡ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 13 እና 14 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ የሚከራከረው አመልካቾች ለጡረታ ያዋጡትን የራሳቸውን 4% ገንዘብ ወስደዋል በማለት ሲሆን አመልካቾችም ይህንኑ አይክዱም፡፡ ስለሆነም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ መሆን በሕጉ አነጋገር የጡረታ መብት ተጠቃሚነትን ያሳያል ወይ? የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ነው፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾች ክሱን ሲመሰርቱ በስራ ላይ በነበረው በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2(13) ስር አበል የሚለው ቃል የጡረታ መዋጮ ተመላሽንም የሚጨመር መሆኑን፣በአዋጁ አንቀፅ 21 ደግሞ ተመላሽ መዋጮ የሚሰጠው ከአስር አመት ያላነሰ፣ሃያ አመት ያልሞላ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ስራውን ከለቀቀ ወይም ከሃያ አመት ያነሰ አገልገሎት ፈጽሞ በአዋጁ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት ከስራ ከተሰናበተ ሰራተኛው የከፈለው አራት በመቶ 4% የጡረታ መዋጮ የሚመለስ መሆኑና በአዋጁ አንቀጽ 2(14) ደግሞ ባለመብት ማለት በአዋጁ መሰረት አበል የሚቀበል ወይም አበል ለመቀበል የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሰራተኛ ወይም ተተኪ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ይህ ድንጋጌ መታየት ያለበት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀፅ 2(1(ሸ)) ይዘት፣መንፈስ እና ዓላማ ጋር ተጣጥሞ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2(13 እና 14) እና 21 ድንጋጌዎች የተቀመጠውን ድንጋጌ አንድ ላይ ስንመለከተው የጡረታ መዋጮ የሚመለሰው የሰራተኛው ድርሻ ብቻ ነው፡፡የአሰሪው መዋጮ የማይከፈል መሆኑን ድንጋጌዎቹ በግልፅ ያሳያሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለት ጊዜ ከአሰሪው ኪስ ገንዘብ ወጥቷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ እንዲሁም ሰራተኛው ለአሰሪው ባበረከተው አስተዋጽኦ ምክንያትና የስራ ስንብት የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን (Social Security Scheme) ተብሎ ከሚታሰብበት አግባብ አንፃር ሲታይ አመልካቾች ከተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ የማያገኙበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጡረታ አበል ተጠቃሚነት የሚለውን ሐረግ ብቻ ይዞ የአዋጁን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ዓላማ ጋር ባግባቡ ሳይመረምር አመልካቾች የስራ ስንብት ክፍያ አይገባቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11287 መስከረም 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአሰሪ ዘንድ ከአምስት አመታት በላይ አገልግሎ በራሱ ፈቃድ ስራውን የለቀቀ ሰራተኛ እድሜውና የአገልገሎት ዘመኑ የጡረታ መብት ተጠቃሚ የማያደርገው እስከሆነ ድረስ ራሱ ያዋጣውን መዋጮ ተመላሽ ሁኖለታል በሚል ምክንያት የስራ ስንብት አይከፈልም ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64257 ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር በግራ ቀኙ የወጣውን ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 67201

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- አቶ ምትኩ ኃይሉ ጠበቃ ለገሰ ማሞ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ መስፍን ጥላሁን የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው እና በስራ ላይ የደረሰን ጉዳት ካሳ መሰረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ በእንጨት መሰንጠቂያ ማሽኒስትነት በወር ብር 750 /ሰባት መቶ ሀምሳ ብር/ እየተከፈለኝ በማገልገል ላይ እያለሁ በጥር 08 ቀን 2002 ዓ.ም የማሽኑ መጋዝን በግራ እጅ ላይ ባደረሰው የመቆረጥ አደጋ ሶስት ጣቶቼ ተቆርጠው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ በዚህ የተነሳ ከዚህ በኂላ ስራ ላይ ተሰማርቼ ስራ መስራት እንዳልችል አድርጎኛል፡፡ በመሆኑም በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109/1/ መሰረት ለደረሰብኝ ጉዳት ካሳ እና የህክምና ወጪ እንዲከፈለኝ በማለት ባጠቃላይ ብር 45,000 /አርባ አምስተ ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ በማለት ነው፡፡ የቀረበው ክስ ለተከሳሽ ደርሶት መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ባቀረበው መልስ አመልካች በድርጅቱ ውስጥ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ሠ/መሰረት የስራ መብዛት በሚኖርበት ጊዜ ስራው እስኪያልቅ ድረስ ብቻ ለመስራት የተዋዋለ በመሆኑ፣አመልካች ከተጠሪ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌላ ስራ ተቋራጭ ጋርም የሚሰራ በመሆኑ፣የጉዳት መጠኑንም የሚያሳይ ነገር ያላቀረበ በመሆኑ፣አመልካች ጉዳት የደረሰበት አዕምሮውን በሚገባ መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ሰክሮ በስራ ላይ በመገኘት በመሆኑ በራሱ ላይ ሆነ ብሎ እንዳደረሰ ስለሚቆጠር፣በወቅቱ ከሳሽ ወደ ድርጅቱ ሲመጣ ሰክሮ ስለነበር ወደ ስራ እንዳይገባ በአሰሪው ጭምር ትዕዛዝ ቢሰጠውም እምቢተኛ በመሆን በመስራት ላይ እንዳለ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ፣ኃላፊነት የሌለብኝ ቢሆንም እንኳ በሰብአዊነት የህክምና ወጪውን የሸፈንኩ በመሆኑ፣ከዚያም በመዳን ወደ ስራው ተመልሶ ስራውን ሲሰራ ቆይቶ የማሽን ካፖስተሮችን በመለወጡ በፈጸመው ጥፋት ምክንያት ከስራ የተሰናበተ በመሆኑ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት እና ማስረጃ በመቀበል ከሳሽ በስራ ገበታው ላይ የተገኘው በስካር መንፈስ ስለመሆኑ እና በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መስራት እንደሌለበት የተላለፈለትን የስራ ኃላፊውን ትዕዛዝ

በመተላለፍ በመስራት ላይ እንዳለ የደረሰበት ጉዳት በመሆኑ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ተብሎ የማይወሰድ በመሆኑ የቀረበው የካሳ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሰረት አጽንቶታል፡፡ ሆኖም የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ቅሬታ በመቀበል የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በግራ ቀኙ መካከል የስራ ውል ስለመኖሩ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ያረጋገጠው ነጥብ ባለመኖሩ፣ስራው ደግሞ የአደገኝነት ጠባይ ያለው በመሆኑ እና በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2088/1/ መሰረት የኃላፊነት ደንቦችን በመጥቀስ አመልካች ከኃላፊነት ሊድን ስለማይችል የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት በማለት የካሳ መጠኑን በርትህ 20,000 ብር/ሀያ ሺህ ብር/ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ቀደም ሲል ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ በዚህ ጉዳይ አመልካች ኃላፊ ነው የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96/ሀ/እና/ለ/ አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ተመልክቶ እልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በመጀመሪያ ደረጃ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ያነሳውን ነጥብ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ ራሱ ክሱን ሲያቀርብ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ እና በወር የሚያገኘውን የደመወዝ መጠን በማመልከት በመሆኑ ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ እና ተጠሪም ራሱ ክሱን ሲያቀርብ አመላክቶ ያቀረበውን ነጥብ ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሳቱ እና ሰራተኛ ስለመሆኑ አመልካች አላረጋገጠም ወደ የሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ሰራተኛ መሆን አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት በራሱ በማንሳት ሰራተኛ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ መድረሱ ተቀባይነት ያለው ድምዳሜ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ስንመለከት ተጠሪ በስራ ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት በደረሰበት ዕለት ጠዋት ወደ ስራ ከገባ በኂላ፣የስራ ኃላፊው ለሌላ ስራ ሲወጣ ተከትሎ እንደወጣ እና የስራ ኃላፊው ተመልሶ ሲመጣ ተጠሪም ተከትሎት እንደመጣ፣በዚህን ወቅት ተጠሪ በስካር ውስጥ እንደነበር ወይም ይንገዳገድ እና የመጠጥ ጠረንም እንደነበረዉ፣ከዚህ የተነሳ አመልካች እንዳትሰራ በማለት አስጠንቅቆት እንደነበር፣ሆኖም አመልካች ለስራ ሲወጣ አስፈቅዳለሁ በማለት ለመደወል በሚል የሞባይል ስልክ በመያዝ እንደወጣ፣ተመልሶም አሰሪው ፈቅዶልኛል በማለት እምቢተኛ በመሆኑ መስራት እንደጀመረ፣ስራውን መስራት ከጀመረ ብዙም ሳይቆይ አደጋው እንደተከሰተ፣ከአደጋውም በኂላ አመልካች ወደ ተለያዩ የህክምና ቦታዎች የወሰደው እና በመዳንም ስራ የጀመረ ስለመሆኑ፣ ሆኖም ስራውን ከጀመረ በኂላ እንዲቀይር የተሰጠውን የማሽን ካፖስተሮችን በማጥፋቱ በፈጸመው ጥፋት ከስራ የተሰናበተ ስለመሆኑ ነው፡፡

ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት በእርግጥ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96/1/ን ስንመለከት አንድ አሰሪ በስራ ላይ በሰራተኛው ለሚደርስ ጉዳት ለመካስ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ሆነ ብሎ በራሱ ላይ ባደረሰው ማንኛውም ጉዳት አሰሪው ኃላፊነት እንደሌለበት፣በተለይም አሰሪው አስቀድሞ በግል የሰጡትን የደኅንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አዕምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በስራ ላይ በመገኘቱ የደረሰ ጉዳት በሰራተኛው ሆን ተብሎ የደረሰ ተደርጎ ስለሚወሰድ አሰሪው ለመካስ ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96/ሀ//ለ/ ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ ጉዳት በደረሰበት ቀን ሰክሮ በስራው ላይ የተገኘ ስለመሆኑ፣እንዳይሰራ ተብሎ በስራ ኃላፊውም የተሰጠውን መመሪያ በመጣስ በእምቢተኝነት ወደ ስራ በመግባት ስራ የጀመረ ስለመሆኑ እና በወቅቱም ይንገዳገድ የነበረ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ እንደደረሰ ተቆጥሮ ለደረሰው ጉዳት አሰሪው/አመልካች/ ኃላፊነት የለበትም በማለት በክልሉ የመጀ/ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ አያሳይም፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም ግራቀኙ ያልተካካዱበትን እና ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ ተጠሪ ራሱ ባልካደበት ሁኔታ ሰራተኛ መሆኑ አልተረጋገጠም በሚል፣በግራቀኙ መካከል ተፈጻሚነት ያለው የህግ የአሰሪና ሰራተኛ ስለመሆኑም በላከራከረበት ሁኔታ የፍተሐብሔር ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ እና የአመልካች ድርጅት ስራ የአደገኝነት ባሕርይ ያለው ነው በማለት አመልካች ኃላፊነት አለበት ወደ ሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባጠቃላይ በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመሆኑ ከተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች ሰጥተውት የነበረውን ውሳኔ በመሻር አመልካች ኃላፊነት አለበት በማለት መወሰኑ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ/ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.51342 በቀን 22-7-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.08825 በቀን 25-1-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 00347 በቀን 15-11-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. በአሁን ተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመሆኑ አመልካች የደረሰውን ጉዳት ለመካስ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኝ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 73881

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን ሥርከብርሃን ተክሌ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- አቶ ተፈራ ሹና የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በይርጋ አለም ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ያኔ ከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ስላቋረጠብኝ ውዝፍ ደመወዜን በመክፈል ወደስራዬ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ነጥብ ተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ በማለት ያቀረቡት ክስ በሶስት ወር ይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ተጠሪ ተመድበው በሚሰሩበት በይርጋዓለም ዲስትሪክት በለኩ ቅርንጫፍ ጣቢያ በተለያዩ ጊዜያት በእዳ ምክንያት ተቆርጦ ከተመለሰ ቆጣሪ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ወደ ድርጅቱ መግባት የሚያስፈልገውን ክፍያ ለእራሱ አውሎ ከሕጉ ውጪ በሆነ መንገድ ከአስራ ሶስት በላይ የሆነ ቆጣሪ ለመግጠም በዲስፐሊን ጉድለት በሪጅኑ የዲስፐሊን ኮሚቴ አጣርቶ በሕብረት ስምምነትና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ))እና((መ)) ነው በማለት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ለስራ የታገዱት በስራ ላይ ባጠፉት ጥፋት ነው ፣ ይህ ጥፋትም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ))((መ)) መሰረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ነው በማለት የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሰረት ነው ሲል ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በይርጋዓለም ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የአስር ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ስራው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በስራ ላይ እያሉ የአመልካችን ድርጅት ጥቅም ለግል ጥቅማቸው ማውላቸውና ማጭበርበራቸው በዲስፐሊን ኮሚቴ ተረጋግጦ እያለ ይኸው ማስረጃ በቂ አይደለም ተብሎ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ

ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የዲሲፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ በቂ አይደለም ተብሎ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት የፅሑፍ መልስ የዲስፕሊን ኮሜቴ የዳኝነት ሥልጣን የሌለው አካል በመሆኑ ውሳኔው ውድቅ መደረጉ ባግባቡ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ከአላቸው ውሳኔዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱት ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ከሕግ ውጪ ተቋርጧል በሚል ሲሆን አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በስራ ላይ በፈፀሙት የማጭበርበርና የእምነት ማጉደል ድርጊት ምክንያት መሆኑን ገልፆ መከራከሩንና ግራ ቀኙ ወገኖች ክርክራቸውን ይደግፉልናል የሚሏቸውን ማስረጃዎችን ማቅረባቸውን ፣ የተጠሪ ምስክሮች ቃል የስራ ውሉ ከሕጉ ውጪ መቋረጡን ለማስረዳት የማይችል መሆኑ በሁለቱም ፍርድ ቤቶች ስምምነት ያገኘ ነጥብ መሆኑን ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያዩበት ነጥብ የአመልካች መስሪያ ቤት የሪጅን ዲስፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ በማስረጃነት ስላላው ተቀባይት ላይ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በዲሲፕሊን ኮሜቴው የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በስራ ላይ የማጭበርበርና የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈፃማቸውን እንደሚያስረዳ ገልፆ ይኸው የዲስፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ የአመልካችን ክርክር የሚደግፍ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዲሲፕሊን ኮሜቴው ውሳኔ የተጠሪን የማጭበርበር ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ውድቅ ያደረገው የኮሚቴው ውሳኔ በገልለተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ አይደለም ፣ በኮሜቴው ፊት የተሰሙት ምስክሮችም በፍርድ ቤት ያልተሰሙ በመሆኑ የኮሜቴው ውሳኔ ተጠሪ የአመልካችን ጥቅም ለራሳቸው ጥቅም ማዋላቸውን ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀማቸውን አያሳይም በሚል ምክንያት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የኮሚቴው ውሳኔ በቂ አይደለም ተብሎ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በማለት ውሳኔ የመሰጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ተጠሪን ከስራ እንዲሰናበት ያደረገው ተመድበው በሚሰሩበት የይርጋዓለም ዲስትሪክት ለኩ ንዑስ ጣቢያ በተለያዩ ወቅቶች በእዳ ምክንያት ተቆርጠው ተመላሽ የተደረጉትን የኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪዎችን ለአመልካች መግባት የነበረበት ክፍያ ለግል ጥቅሙ በማዋሉ በሕገ ወጥ መንገድ ከአስራ ሶስት የፍጆታ ቆጣሪዎች በላይ በመግጠም በአመልካች ድርጅት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት ሲሆን ይህ የተጠሪ አድራጎት ስለመኖሩ የዲሲፕሊን ኮሜቴው ጉዳዩን አጣርቶ በፍሬ ነገር ረገድ አረጋግጧል፡፡ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ይህን መሰረት በማድረግ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ተመስርቶ የነበረውን የስራ ውል ስለሚቋረጥባቸው ሕጋዊያን ምክንያቶች በሚመለከት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 27 ሲሆን፣ ይህም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል

የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር አስቀምጦአል፡፡ ተጠሪ በአሰሪው (በአመልካች) ጥቅም ላይ በማጭበርበር ድርጊት ጉዳት ማድረሱ የዲሲፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ በሰነድ ማስረጃነት ቀርቦ ተረጋግጧል፡፡ በዲሲፕሊን ኮሜቴ የተሰጠ ውሳኔ በስራ ክርክር ችሎት ለሚቀርብ ክርክር በዲስፕሊን ኮሚቴ ፊት ቀርበው የመሰከሩት ምስክሮች የስራ ክርክር በሚሰማው አካል ወይም ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው ካልተሰሙ የእነዚህን ምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ የተሰጠ የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ በስራ ክርክር ጉዳይ የሰራተኛውን ጥፋት ለማስረዳት ለማስረጃነት ሊቀርብ አይገባም የሚባልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ለማስረጃነት ሊቀርብ የሚገባ ሲሆን ይኸው የሰነድ ማስረጃ በተጠሪ ማስረጃ ያልተስተባበለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የኮሚቴው ውሳኔ ተጠሪ በስራ ላይ የማጭበርበርና በአመልካች ላይ ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን የሚያረጋግጥ በመሆኑና እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ከሚያቋርጡ ምክንያቶች መካከል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) እና((መ)) ስር ተመልክተዋል፡፡ እንግዲህ ሕጉ ይህን ያሕል ግልጽ ከሆነ ከዚህ በተቃራኒ መወሰን የሚቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሲጠቃለል የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተቃራኒው መወሰኑ ውሳኔው በማስረጃ አቀባበል ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23119 ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(1(ሐ)እና((መ)) በመሆኑ በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡ ስለዚህም የይርጋዓለም መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው በማለት በመ/ቁ. 00612 ሰኔ 09 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የውሳኔ ክፍል በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 50590

መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ በርገኔ ኢንኮ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የተወሰደ የጡረታ አበል /ገንዘብ/ ይመለስልኝ በማለት አመልካች በመሠረተው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን የከሰሰው በጡረታ መለያ ቁጥር ወ/407216 ተመዝግቦ ከጥቅምት 1 ቀን 83 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ የጡረታ አበል ሲቀበል የቆየ ሲሆን፣ በተከሰሰበት ወንጀል በመጋቢት 23 ቀን 1995 ዓ.ም የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበታል፡፡ ስለዚህ የጽኑ እስራት ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ከሕጉ ውጪ የወሰደው ገንዘብ /ብር 7,892.27/ ከነወለዱ ይመለስ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ የጡረታ አበሉን በኃይል አልተቀበልኩም፡፡ በወንጀል ከተፈረደብኝ በኋላ ገንዘቡን የወሰድኩት ከፋዮቹ እኔ ጋ እየመጡ ስለሰጡኝ በመሆኑ የምመልስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር የመረመረ ሲሆን፣ በመቀጠልም ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት በኋላ በሥራ ላይ ያለው የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.345/95 ተጠሪ የወሰደውን ገንዘብ ለማስመለስም ሆነ ለወደፊቱ እንዳይከፈለው ለማድረግ የሚያስችል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ኅዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 52/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ስለመሆን አለመሆኑ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ በተከሰበበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው እና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በመጋቢት 23 ቀን 1995 ዓ.ም ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ቅጣቱም የእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ አመልካች ክስ የመሰረተው ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ፅኑ የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት ተጧሪ የጡረታ መብቱን ያጣ ዘንድ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁ.5/1967 አንቀጽ 34 ተደንግጓል የሚል መነሻ ምክንያት በመያዝ ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ቅጣቱ በተወሰነበት ጊዜ ሥራ ላይ የነበረው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.345/1995 ሥራ ላይ ያለ አይደለም፡፡ ተፈፃሚነት የሌለው እና ተከሣሽ የተቀበለውን ገንዘብ ለማስመለስም ሆነ ለወደፊቱም እንዳይከፈለው ለማገድ የሚችልም አዋጅ አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በበኩላችን እንዳየነው ለክርክሩ አወሳሰን በቅደም ተከተል ሊታዩ የሚገባቸው አዋጆች አዋጅ ቁ.5/1967 እና አዋጅ ቁ.345/1995 ናቸው፡፡ የመጀመሪያው "የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁ.5/1967 ዓ.ም" በሚል የወጣው ሲሆን፣ ተጧሪ የነበረ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መብቱ የሚያጣበትን ሁኔታ በአንቀጽ 34 ደንግጎአል፡፡ ይህ አንቀጽ "የወንጀል ቅጣት" የሚል ርእስ ያለው ሁኖ ይዘቱም፡- "አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ሲረጋገጥና ቢያንስ የሦስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ሲወሰንበት የጡረታ መብቱን ያጣል፡፡ ወይም በመከፈል ላይ ያለውን የጡረታ አበል ይቀርበታል፡፡" የሚል ነው፡፡ ይህ አዋጅ የወጣው ቀደም ሲል የወጣውን አዋጅ ቁ.209/55 `ን' ለማሻሻል ሲሆን በዚህ መልክ የተሻሻለው አዋጅ /ቁ.ቁ.209/55/ ደግሞ ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ በዋለው "የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.345/1995" ተሽሮአል /ተተክቶአል/፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ምክንያት ሲታይም የቀድሞውን አዋጅ በሻረው አዲሱ አዋጅ ተጧሪ የነበረ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ በሚመለከት በግልጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም የሚል መነሻ እንዳለው መገመቱ አያስቸግርም፡፡

እንደሚታየው የቀድሞዎቹ አዋጆች ማለትም ቁ.5/67ም ሆነ ቁ.209/55 በአዋጅ ቁ.345/95 ሙሉ በሙሉ እስከተተኩ ድረስ ለተያዘው ክርክር አወሳሰን በዋቢነት ሊጠቀሱ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል ግን እነሱን የተካው አዲሱ አዋጅ ለክርክሩ አወሳሰን ስላለው አግባብነት በሚመለከት ሊፈተሹ የሚገባቸው ድንጋጌዎችን ስለመያዝ አለመያዙ መመልከት ተገቢ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በብዙ አዋጆች እንደሚታየው አዋጅ ቁ.345/95 'ም' የመሸጋገሪያ ድንጋጌ አለው፡፡ ይህም በአንቀጽ 52 የተቀመጠውን ሲሆን፣ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ሕጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በንዑስ አንቀጽ/1/ ባስቀመጠው ድንጋጌ አመልክቷል፡፡ ቀጥለው ያሉት ንኡስ አንቀጽ /2/ እና /3/ም በተመሣሣይ ሁኔታ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ አሰራሮች እንደሚቀጥሉ ያመለክታሉ፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በአዋጅ ቁ.5/1967 አንቀጽ 34 የተቀመጠው የጡረታ መብት የሚታጣበት አግባብ በአዋጅ ቁ.345/95 በግልጽ አልተሻረም፡፡ ይልቁንም በአዋጁ የተፈጠሩ ሕጋዊ ሁኔታዎችም ሆኑ ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች በነበሩበት ሁኔታ ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ነው የኋለኛው አዋጅ /ቁ.345/95/ በግልጽ ያመለከተው፡፡ በወንጀል ተከሶ ሦስት ዓመት ጽኑ የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት ተጧሪ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ እየተደረገ እንደቆየ ግልጽ ነው፡፡ የአዋጁ አስፈፃሚ የሆነው የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ /አመልካች/ ሥራውን ሲሠራ የቆየው የአፈፃፀም መመሪያ እያወጣ እንደሆነም ማሰቡ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ

በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው እና በእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የተወሰነበት አዋጅ ቁ.345/95 ሥራ ላይ ባለበት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የቻሉት ሥራ ላይ የነበረው አዋጅ ቁ.345/95 በአንቀጽ 52 ያስቀመጠውን ድንጋጌ ባለመመርመራቸው እና በአግባቡ ባለመተርጎማቸው ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታው የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የወላይታ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 11964 ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 30909 መስከረም 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ የጡረታ መብቱን ካጣ በኋላ የወሰደው ገንዘብ ብር 7,892.27 /ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ ለአመልካች ይመልስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 71507

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

**አመልካች፡-** ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ወርቆ ምራጭ ቀረቡ

**ተጠሪዎች ፡-** አቶ ሰይፉ ተፈሪ - በሌለበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በሚገዛው ግንኙነት ውስጥ ሰራተኛው ስራውን ከመልቀቁ በፊት የወሰደውን ብድር ሳይመልስ ስራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ አሰሪው ለሰራተኛው ሊከፍለው ከሚገባው የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ ቀንሶ ለማስቀረት የሚችልበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩ ከቆዩ በሁዋላ በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን መልቀቃቸውን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ከዘረዘራቸው የክፍያ ዓይነቶች አንዱ የፕሮቪደንት ፈንድ ሲሆን አመልካች ለዚሁ ለተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በሰጠው መከላከያ መልስ ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆኑን ሳይክድ ለተጠሪ ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ/ መስጠቱን፣ ቀሪውን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪ ብድር አበድሮት እንደነበረና ብድሩን ሙሉ በሙሉ ባለመክፈሉ በመካከላቸው ባለው ስምምነት መሰረት ያስቀረው መሆኑን ጠቅሶ ልከፍለው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ ብር 9,000 መውሰዳቸውንና ከአመልካች በብድር የወሰዱት ገንዘብ መኖሩን ያለመካዳቸው ተረጋግጧል በማለት አመልካች ከተጠሪ ለእዳ መክፈያነት ያስቀረውን የፕሮቪደንት ፈንድ ቀሪ ለመክፈል ሊገደድ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፕሮቪደንት ፈንድ ከደመወዝ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ካላቸው ክፍያዎች አንዱ መሆኑን ገልጾና ያለተጠሪ ስምምነት ደግሞ አሰሪ የሆነው አመልካች ለእዳ መክፈያነት የፕሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ ለማስቀረት የማይችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59/1/ ስር የተመለከተ መሆኑን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ቀሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 11,000.00 /አስራ አንድ ሺህ ብር/ ለተጠሪ

ይክፈላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በድርጅቱ ሕብረት ስምምነትና በብድር ፖሊሲ መሰረት የወሰዱትን ብድር ሳይከፍሉ ስራውን በገዛ ፍቃዳቸው ከመልቀቃቸውም በላይ ብድሩ መኖሩንና ስምምነት መኖሩንም ሳይክዱ አመልካች ከፕሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ እዳውን ማስቀረት አይችልም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59 ድንጋጌን ይዘት፣ የግራ ቀኙን ክርክርና የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በድርጅቱ የብድር ፖሊሲ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅእኖ በአግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከስራ ስንብቱ በፊት የነበረበትን እዳ ከፕሮቪደንት ፈንድ ላይ ሊቆረጥ/ሊቀነስ/ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ ከተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የስራ ውል ግንኙነት ያቋረጡት በገዛ ፈቃዳቸው መሆኑን፣ የስራ ውሉ ከመቋረጡ በፊት ደግሞ በሰራተኝነታቸው ከአሰሪው በተሰጣቸው መብት መሰረት ብድር ወስደው ብድሩን እንደተጠቀሙና እዳውን ሙሉ በሙሉ ሳይከፍሉ የስራ ስንብት ጥያቄን ያቀረቡ መሆኑን፣ ብድሩ ያለባቸው መሆኑንም ደግሞ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ያመኑ መሆኑ መረጋገጡን እንዲሁም የብድሩ መሰረትም በአሰሪው ድርጅት ውስጥ ያለው የሕብረት ስምምነት እና የብድር ፖሊሲ መሆኑ አከራካሪ ያለመሆኑን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአሁኑ ተጠሪ ዕዳ የለብኝም በሚል ያቀረበው ክርክር የለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የታለፈ ስለሆነ አመልካች እዳው የተጠሪ መሆን ያለመሆኑን ሌላ ክስ እንዲመሰረት የሚጠበቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 59/1/ በሕብረት ስምምነት በተወሰነው መሠረት ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ መቀነስ እንደሚቻል የሚያስረዳ ሲሆን የፕሮቪደንት ፈንድ ከደመወዝ ጋር ጥብቅ ቁርኝነት ያለው የክፍያ ዓይነት ነው ቢባል እንኳ ተጠሪ እዳ ያለባቸው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት ባልካዱት ሁኔታ ሌላ ግልጽ ስምምነት የሚያስፈልግበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ሳይመልሱ በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን በለቀቁበትና እዳው መኖሩንም በስራ ክርክር ችሎት ባመኑበት ሁኔታ እዳውን ከፕሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ ለማስቀረት ሌላ ግልጽ የሆነ ስምምነት ያስፈልግ ነበር ተብሎ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ከድንጋጌው መንፈስ እና ይዘት ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሳይመልሱ ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው በለቀቁበትና እዳውም የሚመለከታቸው መሆኑን በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በአመኑት ሁኔታ ከፕሮቪደንት ፈንድ እዳውን ቀንሶ ለማስቀረት ግልጽ ስምምነት የለም ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59/1/ ስር የተመለከተውን የድንጋጌውን መንፈስ ከአመልካች ድርጅት

የሕብረት ስምምነት እና የብድር ፖሊሲ ጋር ባለገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 107857 በ06/11/200 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 57350 በ19/08/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪው ፕሮቪደንት ፈንድ በዕዳው ምክንያት ቀንሶ የወሰደውን ገንዘብ ሊመልስ አይገባም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ለተካሄደው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን በየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ.ቁ.74400

ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሺያል ኃ/የተ/የግል ማህበር-ነ/ፈጅ ያሬድ ወርቅዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ናርዬ ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ኪዳኔ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚስተናገደውን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ግንኙነት ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት ስለመኖሩ ሳይክድ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ሲያሽከረክሩ በነበሩት በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ በግጭት ጉዳት ያደረሱ በመሆኑ ነው በማለት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ ጉዳት አድርሷል በማለት አመልካች የሚከራከረው የአመልካች ድርጅት እህት ኩባንያ የሆነው የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረት በሆነው ተሽከርካሪ ላይ መሆኑ መረጋገጡን፣ ተጠሪ የስራ ቅጥር ውል የፈፀሙት ከአመልካች ጋር እስከሆነ ድረስ የአመልካች ድርጅትና የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር ባለቤት አንድ መሆን ድርጅቶቹ የራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው እስከሆነ ድረስ በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ ተጠሪ ጉዳት አድርሰዋል ለማለት የማያስችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካች እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት ደምድሞ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከእህት ኩባንያው ለስራ ተከራይቶ ሲጠቀም በነበረው ተሽከርካሪ ተጠሪ ጉዳት ያደረሱ ሁኖ እያለ ኩባንያዎቹ የተለያየ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው በማለት ስንብቱን ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪን የቀጠረውና ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ የአመልካች ድርጅት ሆኖ እያለ በአመልካች ድርጅት የደረሰ ጉዳት የለም ተብሎ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የተለያዩ

ክፍያዎች ለተጠሪ ይፈጸሙ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት የተጠሪ ቀጣሪ ፣ ተጠሪ ጉዳት አደረሰ የተባለበት ተሽከርካሪ ደግሞ የአመልካች ድርጅት ባለቤት የሆኑት ግለሰብ ባለቤት የሆኑበት ሁኖ ጉዳቱ ደረሰ በተባለበት ጊዜ አመልካች ድርጅት ተሽከርካሪውን ለራሱ ጥቅም በመገልገል ላይ በነበረበት ሁኔታ ተጠሪ ግጭት ያደረሱ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የህግ ሰውነት ያለው ሲሆን በዚህ ሕጋዊ ችሎታ የመከሰስም ሆነ የመክሰስ ችሎታ ይኖረዋል፡፡ አንድ የተፈጥሮ ሰው ከአንድ በላይ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበሮች ባለቤት ሁኖ መገኘት በአንዱ ድርጅት ውስጥ ያለ ሰራተኛ በሌላኛው እህት ድርጅቱ ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉደት በሌላኛው ድርጅት ውስጥ በሕጉ አግባብ የተቀጠረውን ሰራተኛ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰሃል በማለት የስራ ውሉን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚስችለው ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ አሰሪው ሊያቋርጥ የሚችለው ሰራተኛው በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከያዛቸው ቁም ነገሮች ውስጥ “የአሰሪው ንብረት” እና “ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት” የሚሉት ሐረጎች ይገኙበታል፡፡ ስለዚህ ጉዳት ደርሷል ለማለት መሟላት ካለባቸው ነገሮች አንዱ ንብረቱ የአሰሪው መሆኑና በቀጥታ ከድርጅቱ ስራ ጋር የሚገናኝ መሆኑ ነው፡፡ አሰሪ ማለት ደግሞ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ስለመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀፅ 2/1/ ስር ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ተፈጥሯል ሊባል የሚችለው የስራ ወሉ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት ሲመሰረት መሆኑንና በዚህ አግባብ የስራ ውሉ መመስረቱ ከተረጋገጠ የስራ ውል ግንኙነት በሕጉ አግባብ የሚገዛው ይህንኑ ውል በመሰረቱት ሰዎች መካከል ብቻ ይሆናል፡፡ የስራ ውል ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት መመስረቱ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ተጠሪን ማሰናበቱን ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከረው የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሆነ መኪና ላይ በግጭት ምክንያት ጉዳት አድርሰዋል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ከዚህ የተሽከርካሪው ባለቤት ከሆነው ድርጅት ጋር የፈፀሙት የቅጥር ውል የሌለ ሲሆን ተሽከርካሪውን አመልካች ለስራ ምክንያት ተከናትሮ ሲጠቀምበት የነበረ ወይም ንብረቱ ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የነበረው ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጅት ተጠሪ በሌላ ድርጅት ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተመሰረተውን የስራ ግንኙነት ውል

ለማቋረጥ የሚስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የስራ ውሉን ከአመልካች ጋር መመስረታቸውንና ጉዳት ደርሶበታል የተባለው ተሸከርካሪም የአመልካች ድርጅት ባለቤት የሆኑት ግለሰብ የሆኑበት ግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር መሆኑን በማረጋገጥ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2/1/ ፣ 4 እና 27/1/ሸ/ እና በንግድ ሕጉ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማህበራት ስላላቸው ሕጋዊ ችሎታን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55719 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107754 ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕገወጥ ነው ተብሎ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 05 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 67996

ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሳሳካዋ ግሎባል 2000 ፕሮጀክት ነ/ፈጅ ባልቻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሽዋድንበር ደቻሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ተከሳሽ ከህግ ውጪ የስራ ውሌን ስላቋረጠብኝ የተለያዩ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 93,288.338 እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በበኩሉ ባቀረበው የመ/ደ/መቃወሚያ ተከሳሽ ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 3(2) (መ) መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል ብሏል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 (2) መሰረት የተከሳሽ ተቃውሞ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ በመልስ ሰጪና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል የተፈጸመው ውል አንቀጽ 3(5) እንደሚገልጸው ድርጅቱ ለትርፍ ያልተቋቋመ ቢሆንም ባለሙያዎችን ሲያሰራ የቅጥር ውል የሚፈጽመው በኢትዮጵያ ህግ መሰረት እንደሆነ በውሉ በግልጽ ተጠቅሷል እንደመልስ ሰጪ ያሉ ድርጅቶች የሚመሩበትን ደንብ የሚንስትሮች ም/ቤት እስካላወጣ ድረስ ደግሞ ሰራተኞቹ የሚተዳደሩት በአዋጁ መሰረት ይሆናል፡፡ በመልስ ሰጪውና ይግባኝ ባይ መካከል በተመሰረተው የቅጥር ውል መነሻ ይግባኝ ባይ ደመወዝ እየከፈለ ሲያሰራ መቆየቱ የታመነ ሲሆን በዚሁ የቅጥር ውል መሰረት ለይግባኝ ባይ መፈጸም የሚገባውን ግዴታ አለመፈጸሙ ተገቢነት የለውም በሚል የወረዳውን ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመሻር በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343 (1) መሰረት የመለሰው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለውም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁኑ አመልካችም በከፍተኛውና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ሲጠቃለል አመልካች ድርጅት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር እ.ኤ.አ ዲሴንበር 2008 በተፈረመ ስምምነት የተቋቋመ ሲሆን በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 2 (3)

መሰረት ለትርፍ ያልተቋቋመ ፕሮጀክት በመሆኑ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 3(2) (መ) መሰረት በዚህ አዋጅ ሊከሰስ አይገባም በሚል ያቀረብነውን መቃወሚያ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ባለመቀበል ከተከራከርንበት ጭብጥ በመውጣት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሰረት መርምሮ ያቀረብነውን የመ/ደ/መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ማጽናቱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች በአዋጁ ልዳኝ አይገባም ይበል እንጂ ክልከላው በሚንስትሮች ም/ቤት በሚወጣው ደንብ ሽፋን ስለማግኘቱ ያስረዳው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከሰስ የማይችልበት ምክንያት ስለሌለው አቤቱታው የህግ መሰረት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአመልካች ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የሚሸፈን አይደለም በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ ከፍተኛው ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪው ከአመልካች ድርጅት ጋር በተደረገው የቅጥር ስራ ውል መነሻ በአመልካች ድርጅት እየሰራ መቆየቱን ገልጾ የሚከራከር ሲሆን አመልካች ድርጅትም በመካከላቸው የቅጥር ስራ ውል የለም ሲል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ሆኖም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ድርጅቱ ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በሚል ነው፡፡ ለዚሁ ክርክር በማስረጃነት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የጽሁፍ ሰነድም በአመልካችና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል በ2000 ዓ/ም የተፈረመውን የተሻሻለውን የመግባቢያ ሰነድ( Memorandum of Understanding) ነው፡፡ በዚሁ በተሻሻለው የመግባቢያ ሰነድ አንቀጽ 3 (5) ደግሞ ድርጅቱ የአገር ውስጥ ሳይንቲስቶችን፣የሰብል ምርት ልዩ ባለሙያዎችን፣ ቴክኒሽያኖችን፣የፅህፈት እና አስተዳደራዊ እንዲሁም የኦፕሬሽን ድጋፍ ሰጪ ፐርሶኔሎችን በኢትዮጵያ መንግስት አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የምደባና የቅጥር ሁኔታዎችን እና ገደቦችን እንደሚያስቀምጥ ተመልክቷል፡፡ የመግባቢያው ሰነድ በዚሁ መልክ ከተቀመጠና በአመልካችና በተጠሪው መካከል የስራ ቅጥር ውል መደረጉ በአመልካች እስከታመነ ድረስ ለትርፍ ያልተቋቋመ የውጪ ድርጅት ቢሆንም ለጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ አዋጁ ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይችለው በአዋጁ አንቀጽ 3(3) የተደነገገው ልዩ ሁኔታ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይሄውም እንደአመልካች ያሉ ድርጅቶችን በተመለከተ አዋጁ ተፈጻሚነት አይኖረውም በሚል የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ያወጣ ከሆነ ወይም ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የተወሰነ ከሆነ ነው፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ እንደአመልካች ያሉ ድርጅቶችን በሚመለከት የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ካለመኖሩም ሌላ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም እንደ አመልካች ያሉ ድርጆቶች በሀገር ውስጥ የሚቀጥሩአቸውን ሰራተኞች በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት የለውም በሚል በግልጽ የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ እንዲያውም በዚህ በሚያከራክረው ጉዳይ የስራ ቅጥር በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ይደረጋል በሚል በስር ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው የመግባቢያው ሰነድ ላይ መስፈሩ አዋጁ ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ የሚረጋግጥ ነው፡፡

በመሆም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ህጋዊ ምክንያቶች የተነሳ የስር ከፍተኛ እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ድርጅት የተቋቋመው ለትርፍ ባለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት የለውም ሲል ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክርክር እንዲደረግ ክርክሩን ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት መመለሳቸው ተቀባይነት ያለው ስለሆነ በውሳኔያቸው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26939 በቀን 27/07/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/129113 በቀን 11/08/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348 (1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ለተያዘው ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብነት አለው ተብሎ ጉዳዩ በዚሁ አዋጅ መሰረት እንዲታይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነው ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 72645

ሐምሌ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ማህሌት ዓለሙ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1.አቶ ክፍለዮሐንስ ተሰማ

2.አቶ ታምራት ተሰማ } ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ጉዳት ካሳ በመድን ፖሊሲ ተሸፍኖ ሲገኝ ካሳውን ሊጠይቁ የሚችሉትን ወገኖችን ማንነት አተረጓጐም የሚመለከት ነው፡፡የተጠሪዎች ወንድም አቶ ተገኜ ተሰማ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ተቀጥረው በስራ ላይ እያሉ ሕይወታቸው በማለፉ አሰሪው የሆነው የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ብር 20,286.60 (ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም)፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ በስራ ላይ ለሚደረስ የሰራተኛ ጉዳት ካሳ በመድን ፖሊሲው በገባው ግዴታ መሰረት ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ለመክፍል የመድን ፖሊሲ ሽፋን መስጠቱን ገልጸው ይኸው ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡በአሰሪነቱ የተከሰሰው የወንጂ ስኳር ፋብሪካም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 107 መሰረት ካሳውን ለማግኘት የማይችሉ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት የጠየቀ ሲሆን በአማራጭም የአሁኑ አመልካች ለሰራተኞች የጉዳት ካሳ የመድን ፖሊሲ ሽፋን የሰጠ መሆኑን ገልፆ ወደ ክርክሩ እንዲገባለት ጠይቋል፡፡ በዚህም መሰረት የአሁኑ አመልካች ወደ ክርክር እንዲገባ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስ ወደክርክሩ ሊገባ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ተጠሪዎች ካሳውን ለመጠየቅ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአሁኑን አመልካችና የስር ተከሳሽ የሆነውን የወንጂ ስኳር ፋብሪካን ለክሱ ሃላፊ አድርጎ አመልካች ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺኅ)፣አሰሪ የሆነው ፋብሪካው ደግሞ ብር 20,286.60 (ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካችና የወንጂ ስኳር ፋብሪካው ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስኳር ፋብሪካውን ካሳውን ከመክፈል ነፃ

ሲያደርገው የአሁኑን አመልካች ግን ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት የሰበር አቤቱታውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገበት አግባብ ስነ ስርዓቱን የተከተለ ያለመሆኑንና ተጠሪዎች የጉዳት ካሳውን ሊከፈላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔም በአመልካችና በወንጂ ስኳር ፋብሪካ መካከል የተደረገውን የሰራተኞች የጉዳት ካሳ የመድን ፖሊሲውን ይዘትና መንፈስ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 107፣110 እና 134(2) ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ መሆኑን የሚገልፅ ሁኖ አመልካች ለተጠሪዎች የጉዳት ካሳውን ሊከፍል አይገባም ተብሎ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ካሳው ለሟች ሕጋዊ ወራሾች እንደሚከፈል የሕብረት ስምምነቱም በግልፅ የሚሳይ መሆኑን ጠቅሰው በመድን ፖሊሲው ብር 150,000.00 ለሰራተኛ መሞት እንደሚከፈል በተገለጸው መሰረት ተጠሪዎች የሟች ህጋዊ ወራሾች መሆናቸው ስለተረጋገጠ የማይከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካች የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው አመልካች ለወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የጉዳት ካሳ ለመክፈል በመድን ፖሊሲው መሰረት ግዴታ መግባቱ በድርጅቱ ወንጂ ስኳር ፋብሪካና ሰራተኞች መካከል የተደረገውን የህብረት ስምምነት መሰረት በማድረግ የሚመጣውን የሰራተኞች የጉዳት ካሳ ኃላፊነት ጭምር ያጠቃልላል? ወይስ አያጠቃልልም? የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት ተብሎ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በክርክሩ ሂደት የተጠሪዎች ወንድም የሆኑት አቶ ተገኜ ተሰማ በስራ ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው ማለፉም ሆነ የአሁኑ አመልካች በስራ ላይ ለሚደርስ የሞት ጉዳት እስከ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ድረስ የመድን ሽፋን መስጠቱ ያላከራከሩ ነጥቦች መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በሥራ ላይ በሞት የተለዩ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሞት ጉዳት ካሣ ለጥገኞች ስለሚከፍልበት ሁኔታ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 110 ስር በዝርዝር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 110/1/ የተመለከተው ሊከፈል የሚገባው የክፍያ ዓይነት ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንዱ ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ ነው፡፡ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ መጠን እና ጥገኞች የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ድንጋጌው በቀጣይ ንኡስ አንቀጾች በዝርዝር አስፍሯል፡፡ የሟች ጥገኞች ብሎ ሕጉ የዘረዘራቸው የሟች ልጆች ሆነው 18 ዓመት በታች የሆኑ፣የሟች ሕጋዊ ባል ወይም ሚስት እና በሟች ሰራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሟች ወላጆች መሆናቸውን አንቀጽ 110/2/ በመዘርዘር ከዚኅ ውጪ ያሉት ወገኖች የሟች ጥገኞች ያለመሆናቸውን በሚያስገነዝብ መልኩ ሕጉ መቀረፁን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ለሚቀርበው የሞት ጉዳት ካሳ ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉ ወገኖችን ማንነት ሕጉ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን አሁን ለክርክሩ መሰረት የሆነው የሞት ጉዳት ካሳ ጥያቄ መሰረት አድርጓል በማለት ተጠሪዎች የሚከራከሩትም ይኸው ድንጋጌ በዚህ

መልክ የተቀረፀ መሆኑን መከራከሪያ ሳያቀርቡ ለጥያቄው ሕጋዊ መሰረት ነው በማለት የሚጠቅሱት የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 134(2) ድንጋጌን ነው፡፡ይኸውም የሕብረት ስምምነቱ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የተሻለ መብት የሚሰጥ ከሆነ በዚሁ መሰረት የሰራተኛው መብት ሊጠበቅለት ይገባል፣ሟች ተቀጥረው ይሰሩበት የነበረው ድርጅት ህብረት ስምምነት ሰራተኛው በስራ ላይ እያለ ከሞተ የጉዳት ካሳው ለሕጋዊ ወራሾች ይተላለፋል በማለት አስቀምጧል የሚሉትን ምክንያቶችን በማንሳት ነው፡፡

በእርግጥ የህብረት ስምምነት ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሕግ የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ ይኸው ስምምነት ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 134(2) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ የህብረት ስምምነት ማናቸውም የስራ ግንኙነቶችና የስራ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲሁም አሰሪዎችና ማህበሮቻቸው ከሰራተኞች ማህበራት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ሊሸፈን እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 128 ስር በግልፅ የሰፈረ ሲሆን ይህ ባአጠቃላይ እንደተጠበቀ ሁኖ የህብረት ስምምነት ይዘት በዚሁ አዋጁ ወይም በሌሎች ሕጎች ለሕብረት ስምምነት የተተዉ ጉዳዮች ስለሚወሰኑበት፣የሰራተኛ የሙያ ድህንነትና ጤንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታዎች፣ እንዲሁም የማህበራዊ አገልግሎቶች ስለሚስፋፉበት፣ስለሰራተኞች ተሳትፎ፣በተለይም በእድገት፣በደመወዝ፣በዝውውር፣በቅነሳ እና በዲሲፒሊን አፈጻጸም ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፣ስለ ስራ ሁኔታ፣ ስለስራ ደንብና ስለቅሬታ አቀራረብ ስነ ሥርዓት፣ስለስራ ሰዓት ድልደላና በስራ መካከል ስለሚሰጥ እረፍት እና የሕብረት ስምምነት ስለሚሸፍናቸው ወገኖች ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ መያዝ እንደሚችል በአንቀፅ 129 ተዘርዝሯል፡፡ከዚኅም በተጨማሪ የህብረት ስምምነት ልዩ ሁኔታዎች ሊባሉ በሚችሉትና በአዋጁ አንቀጽ 133 ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች እንዴት መፈፀም እንደአለበት ተጠቃሹ ሕግ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የተባለው የህብረት ስምምነት ስለተፈፃሚነት ወሰኑ በአንቀፅ 2 ስር የደነገገ ሲሆን ህብረት ስምምነቱ በድርጅቱ የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ከታቀፉት የስራ መሪዎች በስተቀር በቋሚ፣ ቁርጥና በወርሃዊ/ሲዝናል ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚነት እንደሚሆን በተጠቃሹ ድንጋጌ ቁጥር አንድ ስር የተቀመጠ ሲሆን የህብረት ስምምነቱ ስለህብረት ስምምነቱ አተረጓጎምና ያልተጠቀሱ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚገዛ ድንጋጌም በአንቀፅ 4 ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ በዚህም መሰረት የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ በህብረት ስምምነቱ ውስጥ ባሉት ድንጋጌዎች የአተረጓጎም ወይም ግልጽ ያልሆኑ/ያልተጠበቁ ጉዳዮች ላይ ድርጅቱና የሰራተኛው ማህበር በውይይት መፍትሔ እንደሚፈልጉ፣ጉዳዩ በውይይት የማይፈታ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ቀደም ሲል በተሻሻሉትና ወደፊትም በሚወጡት ማሻሻያ አዋጆች መሰረት እንደሚፈፀም ያስቀምጣል፡፡እንግዲህ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው እና ትርጉም የሚያስፈልገው ሁኖ የተገኘው ነጥብ በህብረት ስምምነቱ በአንቀጽ 40(1) ስር ስለጉዳት ካሳ ተጠቃሚዎች በሚመለከት የተቀመጠው ድንጋጌ በስራ አደጋ ለሚመጣ ኢንሹራንሽ/የመድን ዋስትና የአካል ጉድለትና ጉዳት ካሳ ተጠቃሚ የሚሆኑት የሰራተኛው ሕጋዊ ወራሾች ስለመሆናቸው ተገልፆ ከተቀመጠው ድንጋጌ ውስጥ ሕጋዊ ወራሾች የሚለው ሐረግ የትርጉም አድማሱ በውርስ ሕግ የሚታወቁትን በሕጋዊ ወራሽነት የሚታወቁትን ነው ወይስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110 ስር የተዘረዘሩትን ብቻ ነው የሚመለከተው ለሚለው ጥያቄ የሕብረት ስምምነቱ ግልጽ የሆነ ምላሽ አይሰጥም፡፡ይሁን እንጂ በህብረት ስምምነቱ ትርጉም ሲያስፈልግ በምን አግባብ ሊተረጎም እንደሚችል በአንቀፅ 4(1) የተመለከተ ሲሆን ትርጉሙ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ቀደም ሲል በተሻሻሉትና ወደፊትም በሚወጡት ማሻሻያ አዋጆች መሰረት እንደሚፈፀም የተመለከተ

በመሆኑ በህብረት ስምምነቱ ሕጋዊ ወራሾች የሚለው ሐረግ የሚያመላክተው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110 ስር የተመለከቱትን የተጎጂ ሰራተኛ ጥገኞችን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ሕጉ መዘርዝሩን ከላይ ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110 ስር ከተዘረዘሩት ውጪ ያሉትና በውርስ ሕጉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ሕጋዊ ወራሾች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በስራ አደጋ ለሚመጣ ኢንሹራንስ/የመድን ዋስትና የአካል ጉድለትና ጉዳት ካሳ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ አይኖርም፡፡

አመልካችና ተጠሪ በአደረጉት የመድን ዋስትና ፖሊሲ ስር በስራ ላይ ለሚደርሱ የሞት፣ለአካል ጉዳት፣በስራ ላይ ለሚከሰት በሽታ ጉዳቶች በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የጉዳት ካሳ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በፖሊሲው"……if at any time the period of insurance any worker in the insured's immediate service engaged in a category of work described in the Schedule shall sustain death or bodily injury by accident or occupational disease occurring at the place assigned to him for work or arising from his work and during the time of his work by the insured in the Business and if the insured shall be liable to pay compensation for such death, bodily injury, or occupational disease under Ethiopian law,……" በሚል ከተቀመጠው አረፍተ ነገርም መገንዘብ የሚቻለው መድን ሽፋኑ በስራ ላይ ለሚደርሱ የሞት፣ለአካል ጉዳት፣በስራ ላይ ለሚከሰት በሽታ ጉዳቶች በሚገዛው የኢትዮጵያ አሰሪና ሰራተኛ ሕግ መሰረት የሚታይ መሆኑን ግራ ቀኙ ስምምነት የደረሱ መሆኑን ነው፡፡ ይህ አተረጓጎም ተዋዋይ ወገኖች በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ጉዳዩ ይታያል ብለው ሲስማሙ ሐሳባቸው ምን ነበር? የሚለውን የውል አተረጓጎም ደንብን በመከተልም የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732፣1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሰረት መተርጐም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ሕ/ቁጥር 1734፣1735 እና 1736 ሲሆኑ የተዋዋዮች፡ ሐሳብ፣ በውሉ ላይ የኢትዮጵያ ሕግ በሚለው የተቀመጠው ጠቅላላ አነጋገር በመድን ፖሊሲው ስር የተዘረዘሩት የጉዳት አይነቶችን እርስ በርሳቸው በማስተሳሰር በመድን ፖሊሲው የኢትዮጵያ ሕግ የሚለውን ሐረግ ለማስቀመጥ የፈለጉትበት ሁኔታ ሐሣባቸውን ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብነት ያለውን ትርጉም በመስጠት አዎንታዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም አንፃር የተያዘው ጉዳይ ሲታይ በመድን ፖሊሲው ስር የጉዳቶቹ አይነቶች መዘርዘራቸውና በኢትዮጵያ ሕግ አግባብ ተብሎ መቀመጡ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የሚገዛ መሆኑን በመፈለግ ውሉን ያደረጉ መሆኑን የሚያስገነዝበን ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 377/1996 ስለመሆኑ የግራ ቀኙ ፍላጎት ነበር ከተባለ ደግሞ ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ 110(2) ድንጋጌ አገላለፅ መሰረት የወንድማቸው የሞት ጉዳት ካሳ በውርስ ህጉ ሕጋዊ ወራሽ ነን፣የሕብረት ስምምነቱም የተሻለ ተጠቃሚነትን የሚሰጥ ነው በሚል የሞት ጉዳት ካሳውን የሚጠይቁበትና የሚያገኙበት ሕጋዊ መሰረት የለም፡፡ለአንድ ሰው የመብት ጥያቄ መሰረቱ ውል ወይም ሕግ ሲሆን ተጠሪዎች የሞት ጉዳት ካሳውን ለመጠየቅ ከሕጉም ሆነ ከውል የመነጨ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች ክስ መመስረታቸውም ሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሞት ጉዳት ካሳ ለተጠሪዎች ይገባል በማለት

መወሰናቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ስር የተመለከተውን መመዘኛ እና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110፣128፣129፣134 እና በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 2 እና 4 እንዲሁም 40(1) ስር ያሉን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከውል ሕግ አተረጓጎም ደንቦችና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ አንፃር ያላገናዘቡ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 49598 ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ለተጠሪዎች የሞት ጉዳት ካሳ ሊከፈል ይገባል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል፣ይህንኑ ውሳኔ ክፍል በማፅናት በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11906 ነሐሴ 13 ቀን 2003 ዓ.ም፣በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 132326 በ30/12/2003 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ  በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሟች ወንድማቸው አቶ ተገኔ ተሰማ በስራ ላይ ለደረሰባቸው የሞት አደጋ የሚቱ አሰሪ በገባው መድን ውል መሰረት የጉዳት ካሳ የሚገባቸው ሰዎች አይደሉም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው ትርጉምና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

1. የመጀመሪያው የልዩነቴ ምክንያት አብላጫው ድምፅ በንግድ ህጉ ስለ ኢንሹራንስ በተደነገገው ክፍል ግልፅ የሆነ መልስ የተሰጣቸውን ነጥቦች የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች ሣያገናዝብ፣ የህብረት ስምምነቱን፣ አመልካች የሰጠውን የኢንሹራንስ ፖሊሲና አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 101 ድንጋጌዎች ብቻ በመመርመር ትርጉም መስጠቱና መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚል ሀሳብ ስላለኝ ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ መዝገብ የሚከራከሩበትን ጉዳይ ለመወሰን ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶችና አዋጅ ቁጥር 377/96 መመርመር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ አከራካሪውን ጭብጥ ለመወሰን በአገራችን የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ በህግ የተፈቀደበትን መሰረታዊ ዓላማ፣ አመልካች እንዲሰጥ ስለተፈቀደለት የኢንሹራንስ ሽፋን አይነትና ባህሪ እንደዚሁም አመልካች በሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በህግ ተጠቃሚ የመሆን መብት ስላላቸው ሰዎች የሚደነግጉ የህግ ማዕቀፎችን መመርመር ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘረውን መስፈርት በማሟላት የተቋቋመ የኢንሹራንስ ኩባንያ ነው፡፡ አመልካች የሚሰጣቸው የኢንሹራንስ ሽፋኖች አንደኛው የረዥም ጊዜ የመድን ሥራ ነው፡፡ የረዥም ጊዜ የመድን ሥራ የሚባሉት፣ የሕይወት መድን ሥራ፣ በየጊዜው ገንዘብ የመክፈል ግዴታ፣ የጡረታ መድን፣ ቋሚ የጤና መድን ሥራ፣ እንዲሁም ከመድን ሰጭው በተዛመደ ሁኔታ በሰው አካል ላይ የሚደርስ አደጋ መድንና የህመም መድን የሚያካትት ስለመሆኑ በአዋጅ

ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 16 የተደነገገ ሲሆን የሕይወት መድን በንግድ ህጉ አንቀጽ 691 የተሰጠው ትርጉም የሚኖረው መሆኑን በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 ይደነግጋል፡፡

አመልካች ለተጠሪዎች ወንድም አቶ ተገኔ ተሰማ የሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በሥራ ላይ ለሚደርስ ህመም፣ ዘላቂ የአካል ጉዳትና ለህይወት ኢንሹራንስ መሆኑን ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም አመልካች የሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በንግድ ህጉ አንቀጽ 654 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የኢንሹራንስ አይነትና የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የተጠሪዎች ወንድም አሰሪ የሆነው ወንጂ ስኳር ፋብሪካ የተጠሪዎች ወንድም አቶ ተገኔ ተሰማ በስራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት ህመም ካጋጠመው ወይም ቋሚ የአካል ጉዳት ከደረሰበት፣ የወንጂ ስኳር ሰራተኛ የሆነው የተጠሪዎች ወንድም እንዲጠቀምበት፣ ሰራተኛው በሥራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የኢንሹራንስ ፖሊሲው ተጠቃሚ ለሚሆኑ ሰዎች የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ እንደሚከፈል ታሳቢ በማድረግ ከአመልካች ጋር የተዋዋለ መሆኑን የኢንሹራንስ ፖሊሲውና የህብረት ስምምነቱ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ወንጂ ስኳር ፋብሪካ በህብረት ስምምነት ከገባው ግዴታ፣ (ከውል የመነጨ) በመነሳት የተጠሪዎች ወንድም አሰሪ፣ የተጠሪዎች ወንድም በስራ ላይ ለሚደርስበት ህመምና የአካል ጉዳት ወይም በስራ ላይ ለሚያጋጥመው የሞት አደጋ አመልካች ለተጠቃሚው ወይም ለተጠቃሚዎቹ የኢንሹራንስ ገንዘብ እንደሚከፍል በማሰብ በንግድ ህግ ቁጥር 661 በገባው ውል መሰረት ለአመልካች ፕሪሚየም ሲከፍልና የበኩሉን ግዴታ ሲወጣ ቆይቷል፡፡

የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከአመልካች ጋር ያደረገው የህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎች የሠራተኛው ወራሾች እንደሆኑ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ ሲሆን የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከአመልካች ጋር የኢንሹራንስ ውል የተዋዋለው ይህንን በህብረት ስምምነቱ የገባውን የውል ግዴታ ለመወጣት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ይህ ከሆነ የተጠሪዎች ወንድም በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሲሞት አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን ለማን መክፈል ይገባዋል የሚለውን ጥያቄ ለመወሰን፣ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመልከት የሚጠይቅ ነው፡፡ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ እና በአመልካች መካከል የተደረገው የህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ በንግድ ህጉ አንቀጽ 702 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 705 የተደነገገ ሲሆን በተለይ የኢንሹራንስ ፖሊሲው በንግድ ህግ ቁጥር 695 የተደነገጉትን ዝርዝር ጉዳዮች ባልያዘ ጊዜና ክርክር የሚያነሱ የሟች ባል ወይም ሚስት ወይም ልጆች የሌሉት በሆነ ጊዜ፣ የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚሆኑት የሟች ወራሾች መሆናቸው የንግድ ህግ ቁጥር 705 "ተጠቃሚው ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ፣ ወይም ተሸሮ እንደሆነ ወይም በህይወት የሌለ በመሆኑ ውድቅ የሆነ እንደሆነ ስለሞት የተደረገው ኢንሹራንስ ዋናው ገንዘብ የሚከፈለው ኢንሹራንሱን ለተዋዋለው ሰው ውርስ ነው " በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ወንጂ ስኳር ፋብሪካ የተጠሪዎች ወንድም በሥራ ላይ በሞት ሲለይ የኢንሹራንሱ ተጠቃሚዎች የሟች ወራሾች እንደሚሆኑ የተገለፀው ሀሳብ በንግድ ህጉ አንቀጽ 701 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የሟች ባል ወይም ሚስት፣ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 827 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በንግድ ህግ ቁጥር 705 መሰረት የሟችን ልጆች ወይም ሌሎች ወራሾች ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚያደርግና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 110 አደጋው በደረሰ ጊዜ በህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ሰዎች በሟች ጥገኞች ላይ የተወሰነ እንዳይሆን የሚያደርግ ነው፡፡

የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠው የመድን ድርጅት በአገሪቱ ህግ የህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ መሆናቸው የተረጋገጠላቸውን የሟች ወራሾች (ወንድሞች) ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ለሰራተኛው በገባው የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያቀርቡት ክርክር የኢንሹራንስ ስራ የንግድ ሥራ ብቻ ሣይሆን በአንድ አደጋ የሚደርስ ጉዳትን የመጋራትና ማህበራዊ ግልጋሎት የመስጠት ሥራ መሆኑን ያላገናዘበ ክርክር ነው፡፡ አመልካች ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጋር የመድን ውል ሲዋዋል፣ ውሉ ስለ ህይወት በሚደረግ የኢንሹራንስ ውል በኢትዮጵያ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች የሚያመጣበትን ኃላፊነት እያወቀ ነው፡፡ አመልካች በአገሪቱ ውስጥ የመድን ንግድ ስራ የሚሰራበት ልዩ ፈቃድ የተሰጠውም አሰሪው የመድን ውል የገባበት የሞት አደጋ የሚያደርስ ጉዳት በሰራተኛው ላይ በደረሰ ጊዜ፣ በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 እና በንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ለህይወት ኢንሹራንስ የሚከፈለውን ክፍያ ለኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚዎች በመክፈል ግዴታውንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣል በሚል ዕምነት ነው፡፡ አመልካች በህግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለማስቀረት ወይም በቻለው አጋጣሚ ሁሉ ኃላፊነቱ እንዲጠብቅለት የሚያቀርበው ክርክርም አመልካች ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጋር ለተጠሪዎች ወንድም ጥቅም ከገባው የረዥም ጊዜ የመድን ሽፋን ውል ልዩ ባህሪና ውጤት ጋር የማይሄድና አስገዳጅ የሆኑትን የንግድ ህግ አንቀጽ 701 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና አንቀጽ 705 ድንጋጌዎች ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም አብላጫው ድምጽ ከላይ የተጠቀስኳቸውን አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች ሳያገናዝብ የመድን ፖሊሲውንና የህብረት ስምምነቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 ከአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች ጋር ብቻ በማጣመር በሰጠው ትርጉምና ውሳኔ የማልስማማ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

2.ሁለተኛው የልዩነቴ ምክንያት አብላጫው ድምጽ በመድን ፖሊሲውና በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የሟች ወራሾች (legal heirs) የሚለውን ሀሳብ የሟች ጥገኞች (Dependent) ማለት ነው በማለት የሰጠው ትርጉም የህግ አተረጓጎም መርሆዎችን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሟች ወራሾች (legal heirs) "የሚለው" መሰረተ ሀሳብ በፍ/ብ/ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎችና ስለ ህይወት ኢንሹራንስ በሚደነግገው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ወጥ የሆነ ሀሳብ እንዲያራምዱ ተደርጎ በህግ አውጭው ተገልፀዋል፡፡ አመልካች የመንገድ ንግድ ሥራ የሚሰራ የኢንሹራንስ ኩባንያ በመሆኑ የኢንሹራንስ ውል (ፖሊሲ) አዘጋጅቶ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጋር የመድን ውል ከመዋዋሉ በፊት የወንጂ ስኳር ፋብሪካ የህብረት ስምምነት ውስጥ የተገለጹትን ሀሳቦች ሥራ ላይ ባሉት የኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፎች የተሰጣቸውን ትርጉም መሰረት በማድረግ የኢንሹራንስ ፖሊሲውን ያዘጋጃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የመድን ፖሊሲው (ውሉ) በአመልካች በኩል ተዘጋጅቶ የሚቀርብ (Adhesive contract) በመሆኑ በፖሊሲው በተገለፀው ሃሳብ ላይ አከራካሪ ነገር ቢነሳ ውሉን ያዘጋጀው አመልካችን በሚጠቅም መንገድ ሳይሆን ለውል ተቀባዩ በሚጠቅም መንገድ መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1738 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጎ እያለ የአመልካች ወራሾች (legal heirs) ብሎ ያዘጋጀው የመድን ፖሊሲ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 የተገለፀው ጥገኞች (Dependent) ተብሎ ውሉን ላዘጋጀው ለአመልካች በሚጠቅም መንገድ መተርጎሙ ይህንን የውል አተረጓጎም መርህ የሚጥስ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ህጋዊ ወራሽ (legal heir) የሚለው ፅንስ ሀሳብና ጥገኞች (Dependent) የሚለው ፅንስ ሀሳብ የተለያየ ትርጓሜ ያላቸው መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ ከሟች ወራሾች መካከል የሟች ጥገኛ ተብለው ካሳ የሚያገኙት የሟች ልጆች ሆነው 18 ዓመት በታች የሆኑ፣ የሟች

ህጋዊ ባል ወይም ሚስትና በሟች ሰራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ ወላጆችን ብቻ እንደሆኑ በአንቀጽ 110 ንዑስ አንቀጽ 2 ተዘርዝሯል፡፡ ስለሆነም እጅግ ሰፊ የሆነ የህግ ትርጉምና ዕውቅና የተሰጠውን የሟች ወራሾች (legal heirs) የሚለውን ቃል ከመጠን በላይ በማጥበብ Dependent ጥገኞች የሚለውን ቃል ያሣያል ተብሎ መተርጎሙ የውሉን ፅንሰ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ የመለወጥና የመተካት ሥራ እንጅ የህግ ትርጉም ስራ ነው ብዬ የማላምን በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አብላጫው ድምጽ አግባብነት ያላቸው "የኢትዮጵያ ህጎች" የሚለውን ሀረግ ለመተርጎም መሞከሩ ተገቢነት አለው ብዬ አላምንም፡፡ አሰሪው ለሰራተኛው የገባው የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ አግባብነት ያለው ህግ አዋጅ ቁጥር 377/96 ብቻ አይደለም፡፡ ከላይ በዝርዝር የተገለፁት ስለ ኢንሹራንስ ሥራ ፈቃድ የወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 ስለህይወት ኢንሹራንስ ውል የሚደነግገው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎችና ለህይወት የተደረገ ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎች በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 827 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፎች መሆናቸው ግልፅ ሆኖ እያለ ይህንን አባባል በጠበበ ሁኔታ በመተርጎም በተሰጠው ውሳኔ አልተስማማሁበትም፡፡

3.ሶስተኛው የልዩነት ምክንያቴ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 ሰራተኛው በስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት ካሣ ሊጠይቁ የሚችሉ ሰዎች የሟች ጥገኞች ብቻ እንደሆኑ ህግ አውጭው የኃላፊነት መጠኑን ያጠበበው አንድ ሰራተኛ በሥራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት (አደጋ) ህይወት ሲያልፍ ጉዳት የሚደርስባቸው የሟች ጥገኞች ብቻ ናቸው በሚል ሀሳብ አይደለም፡፤ ነገር ግን ከጥገኞች ባለፈ በአደጋው ምክንያት ሰራተኛው በመሞቱ የተጎዱ ሌሎች የሟች ዘመዶችን ወራሾች ሁሉ አሰሪው ካሣ ይክፈል ቢባል በአሰሪው ላይ የሚያስከትለውን ጫና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

አሰሪው ሰራተኛው በሥራ ላይ በሚደርስበት አደጋ የሚከፈል የኢንሹራንስ ውል ሲዋዋል፣ የውሉ ተጠቃሚ የሚሆኑት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 የተዘረዘሩት ጥገኞች ብቻ ሣይሆኑ ሟች በመሞቱ የጉዳቱ ሰለባ የሆኑ የሟች ወራሾች ጭምር ናቸው፡፡ ስለዚህ አሰሪው የኢንሹራንስ ውል ሲገባ በህብረት ስምምነቱ የተጠቀሱት የሟች ወራሾችን ጭምር የኢንሹራንስ ፖሊሲው ተጠቃሚ ለማድረግ አስቦ የተዋዋሉ በመሆኑ ይህም የኢንሹራንስ ውል አሰሪው (ወንጂ ስኳር ፋብሪካ) የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለተጠሪዎች ወንድም ባይገባ ካሣ ከሚያገኙት ሰዎች የተሻለ መብት የሚያጎናጽፉ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134(2)ን በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 74230

ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ አስቻለው ጌታሁን
2. አቶ ሽመልስ ከበደ
3. አቶ ኤርሚያስ ኢያሶ
4. አቶ መላኩ ካሣ
5. አቶ ሰለሞን አባተ
6. አቶ ንጉሴ ወ/አገኘሁ
7. አቶ ዋጋሁን ተከሰተ
8. አቶ እሽቱ አሰን
9. አቶ ገረመው ገብሬ
10. ወ/ሮ ሂሩት ደምሴ

ጠበቆች አቶ አዲስ ወልዴና አቶ አለማየሁ ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካቾችን ያሰናበተው በአግባቡ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች በከሳሽነት ቀርበው የተቀጠርንበት የሥራ ግዜ ሳይጠናቀቅ፣ የተመደብንበት የሥራ ባህሪ ቀጣይነት ያለው ሆኖ እያለ ተከሳሽ /አመልካች/ የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር በ2003 ዓ.ም የርቀት ትምህርት ተማሪዎችን እንዳይቀበሉ መመሪያ አውጥቷል በሚል ምክንያት የሠራተኞች አቀናነስ ሥርዓትን በተመለከተ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተደነገገውን ሳይከተል በሕገወጥ

መንገድ የሥራ ውል ያቋረጠ በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ትምህርት ሚኒስትር ባወጣው መመሪያ አዲስ ተማሪዎች እንዳንቀበል በመመሪያ የከለከለን በመሆኑ በድርጅቱ መዋቅርና የሥራ እንቅስቃሴ በከፊል፣ በቀጥታና በዘለቄታው እንዲቀንስና እንዲቀዘቅዝ አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት አሁን ያሉንን ተማሪዎች ለማስጨረስ የሚያስችሉ መምህራኖችን ብቻ በማስቀረት ከሳሾችን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት አሰናብተናቸዋል፡፡ ስንብቱ ሕጋዊ በመሆኑ ከሳሾች የጠየቁትን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ያሰናበተው ስለሠራተኛ ቅነሳ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ሳይከተል በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ /አመልካች/ ለከሳሾች /አመልካቾች/ የስድስት ወር ደመወዛቸውን ይክፈላቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ አስራ ዘጠኝ ሠራተኞችን ከሥራ በማሰናበት የወሰደው እርምጃ ካሉት ሠራተኞች ከአስር ፐርሰንት በታች በሚሆኑት ላይ የተደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29 መሠረት የሠራተኛ ቅነሳ አለመኖሩን ያሣያል፡፡ ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ጥቅምት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስትር በ2002 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ በጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የተባረረ ሠራተኛ ወደ ሥራው እንዲመለስና የስድስት ወር ክፍያ እንዲከፈለው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ወስኗል፡፡ ተጠሪ የሠራተኛ ቅነሳ አድርጌአለሁ ቢልም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አላደረገም፡፡ ሠራተኛ ለመቀነስ የሚያስገድድ ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡ ተጠሪ ሠራተኛ ለመቀነስ ይገደዳል ቢባል እንኳን ቅነሳው የተሻለ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ያለንን ከሥራ በማሰናበት፣ ከእኛ በታች የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያላቸውን እንዲቀጥሉ በማድረግ በዘፈቀደ እንዲወስን የሚፈቅድለት የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይህም የተጠሪ የሠራተኛ አቀናነስ በዘፈቀደ የተከናወነና በግለሰብ ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያሳያል፡፡ ተጠሪ የሥራ መደባችንን በመመሪያው የማይነካ ሠራተኞችን ያካተተ ነው፡፡ ስለዚህ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 19 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በመንግስት መመሪያ መሠረት የተጠሪ ሥራ ቀንሷል፡፡ ካሉን ሠራተኞች 3-8 ፐርሰንት የሚሆኑ መምህራንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን በሕግ አግባብ ተጠሪ ቀንሷል፡፡ የተማሪዎች ቁጥር አለመቀነሱ ከስንብቱ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ተጠሪ ሠራተኛ ቀንሷል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ አመልካቾች በሚሰሩበት የሥራ ክፍሎች እንደገና እንዲከፈቱ አልተፈቀደም፡፡ ተጠሪ አመልካቾችን ሲያሰናብት በሕጉ መሠረት ማስጠንቀቂያ የሰጠና መክፈል የሚገባውን ክፍያ የከፈለ በመሆኑ፣ አመልካቾች ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በሕግ መሠረት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ

ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ከሥራ ያሰናበታቸው ሠራተኞች በአጠቃላይ ካሉት ሠራተኞች ቁጥር 3-8 ፐርሰንት ብቻ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 373/96 ቁጥር 29 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የሠራተኞች ቅነሣ መሠረት እንዳልሆነ የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔያቸው ገልፀውታል፡፡

ተጠሪ ከትምህርት ሚኒስትር በተላለፈው መመሪያ መሠረት አዳዲስ ተማሪዎችን የማይቀበል በመሆኑ የሥራ እንቅስቃሴው የቀነሰና በዚህ ምክንያት በፊት የነበሩትን መምህራንና ሠራተኞች ይዞ ለመቀጠል ባለመቻሉ የአመልካቾችን የሥራ ውል ማስጠንቀቂያ በመስጠት በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሠረት እንዳቋረጠ በማንሣት የተከራከረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህንን የተጠሪን ክርክር በመቀበል የሥራ ስንብቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 ቁጥር 28 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሠረት የተከናወነና ሕጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ የተጠሪ የሥራ መጠን የቀነሰና የተቀዛቀዘ ቢሆንም አመልካቾች የሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና ይሰሩበት የነበረው የሥራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ያልተዘጋና ያልተሰረዘ መሆኑንና ተጠሪ ቀደም ብሎ የተቀበላቸውን ተማሪዎች የጀመሩትን ትምህርት ለማስጨረስ የሚችሉ መምህራንና ሠራተኞች በማስቀረት አመልካቾችን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የሥራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን ተጠሪ በሥርም ሆነ በሰበር በግልፅ ክርክር ያቀረበበት መከራከሪያ መሆኑን ተረድተናል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች የሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና የሥራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ባልተዘጋበትና ባልተሰረዘበት ሁኔታ ተጠሪ የሥራ መጠኑን መቀነሱንና ሥራው መቀዝቀዙን መነሻ በማድረግ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ለማስቀረትና ሥራ የማይኖራቸውን ሠራተኞች ለማሰናበት ውሣኔ ሲሰጥ የተጠቀመባቸው መስፈርቶች ምንድን ናቸው፡፡ ተጠሪ ሊጠቀምባቸው የሚገቡ መስፈርቶችስ ምንድን ናቸው? የሚሉት ነጥቦች ናቸው፡፡

አመልካቾች ተጠሪ እነሱን ከሥራ ለማሰናበት ሲወስን ምንም አይነት ተጨባጭነት ያለው መስፈርት ያልተጠቀመ መሆኑንና ተጠሪ በትምህርት ደረጃ በሥራ ልምድና የሥራ አፈፃፀማቸው ከአመልካቾች የሚያንሱ መምህራንና ሠራተኞችን በማስቀረት እነሱን በዘፈቀደ ከሥራ ያሰናበታቸው መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት፣ በይግባኝና በሰበር ደረጃ የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ለማሰናበትና ሌሎችን ለማስቀጠል የተጠቀመባቸው ተጨባጭ መመዘኛዎች ያሉ ለመሆኑ አልተጣራም፤ አሰሪው ሲሰራው የነበረው ሥራ በመቀነሱ ወይም በመቀዝቀዙ ምክንያት ካሉት ሠራተኞች ከአስር ፐርሰንት በታች የሆኑትን የሥራ ውል ማቋረጡ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ካሉት ሠራተኞች የተወሰኑትን የሥራ ውል በዘፈቀደ እንዲያቋርጥና የተወሰኑትን የሥራ ውላቸው እንዲቀጥል ለማድረግ የማይፈቀድለት መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 28 ንዑስ አንቀጽ 8 እና የአዋጅ ቁጥር 29 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ሠራተኞች የሚሰሩበት የሥራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ባልተሰረዘበት ወይም ባልተዘጋበት ሁኔታ የአሰሪው ሥራ በመቀዝቀዙ ምክንያት ከነበሩት ሰራተኞች የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን ሠራተኞች የሥራ ውል ማቋረጥ የግድ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አሰሪው የሚሰናበቱትንና የሚቀጥሉትን ሠራተኞች ለመለየት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገጉትን መመዘኛዎች በመጠቀም በትምህርት ክፍሉና በሥራ ክፍሉ ያሉትን ሠራተኞች አወዳድሮ ከሥራ የሚሰናበቱትንና በሥራ ላይ የሚቆዩትን ሠራተኞች በመለየት በሥራ ለማይቀጥሉ ሠራተኞች ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የሥራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት ከዚህ አንፃር ሲታይ፡-

1. ተጠሪ አመልካቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና በሚሰሩበት የሥራ ክፍል የሚገኙትን ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 በተቀመጡት መመዘኛዎች መሠረት በማወዳደር የአመልካቾችን የሥራ ውል አቋርጧል ወይስ አላቋረጠም?

2. ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ማስጠንቀቂያ በመስጠት ያቋረጠው አመልካቾች በትምህርት ደረጃቸው በሥራ ልምዳቸውና በሥራ አፈፃፀማቸው አመልካቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና የሥራ ክፍል የሥራ ውላቸው እንዲቀጥል ከተደረጉ ሠራተኞችና መምህራን አንሰው በመገኘታቸው ነው ወይስ አይደለም?

3. ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው አመልካቾችና በሥራ እንዲቀጥሉ የተደረጉ ሠራተኞች ተመሣሣይ የትምህርት ደረጃ ፣ የሥራ ልምድና የሥራ አፈፃፀም ውጤት ኖሯቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 ከ/ሀ/ እስከ /ረ/ የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል በመጠቀም ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች በሥር ፍርድ ቤት ያልተረጋገጡና ያልተጣሩ ነጥቦች ናቸው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ ነው ወይስ ከህግ ውጭ ነው ብሎ ለመወሰን ከላይ የገለፅናቸው ነጥቦች መጣራትና በማስረጃ መረጋገጥ ያለባቸው ሆኖ እያለ እነዚህን ጭብጦች በመያዝ ሣያጣሩና በማስረጃ ሳያረጋግጡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 3 የተያዙት ጭብጦች ለማስረዳት በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችንና ክርክሮችን በመመርመርና አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145/1/ መሠረት በማስቀረብ ተጠሪ አመልካቾችን ያሰናበተው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 79105
ሐምሌ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ - ጠበቃ ሜላት ወርቅ ኃይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መዘምር መክብብ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት ሲታይም ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ያለጥፋት የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በድርጅቱ ግቢ ውስጥ ድብደባ ፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የጠብ አጫሪነት ተግባር በመፈፀማቸው ስለመሆኑ ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በአመልካች ኤዲፒ ካምፕ እና ለሰራተኞች መኖሪያነት በተሰራው ግቢ ውስጥ /በስራ ቦታ/ የድርጅቱን ሰራተኛ በመደብደብና የዛቻ ተግባር መፈፀማቸው መረጋገጡንና ለዚህም ተጠያቂ መሆናቸውን ገልፆ የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ወሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ የድብደባ ተግባሩን የፈፀሙት ከስራ ሰዓት ውጪ በመሆኑ ድርጊቱ በስራ ቦታ ላይ እንደደረሰ የሚቆጠር አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካች ለተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤተታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ለስራ ስንብቱ ምክንያት የሆነውን የድብደባ ተግባር ስለመፈፀማቸው ከመረጋገጡም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው በስራ ቦታ ላይ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ድርጊቱ ከስራ ሰዓት ውጪ የተፈፀመ ተግባር ነው በሚል ጠባብ ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ

የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና አግባብነት ያለውን ሕግ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው ተጠሪ አምባጓሮ ፈጥሮ የስራ ባልደረባውን መደብደቡን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀብሎ ድብደባው የተፈፀመው ተጠሪና የግል ተበዳይ አመልካች ባዘጋጀላቸው የስራና የመኖሪያ ግቢ ካምፕ ቢሆንም ድብደባው የተከናወነው ከስራ ሰዓት ውጪና በመፀዳጃ ቤት አካባቢ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ረ)) ስር የተደነገገውን አያሟላም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውድቅ ማድረጉና ወደ ስራው ይመልሰው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት በሚል ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪው የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ላይ የስራ ቦታ በሆነው የአመልካች ካምፕ እና በስራ ጉዞ ላይ የድብደባ ፣ የዛቻ ተግባር መፈጸማቸውን ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑንና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቢሆን የድብደባውና የዛቻው ተግባር በተጠሪ በመፈፀሙ ረገድ ከስር ፍርድ ቤት የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክርም ተጠሪ የድብደባውን ተግባር ስለመፈፀማቸው ግልፅ የሆነ የክህደት ክርክር የሌላቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የተጠሪ ድርጊት የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ የተደነገገውን ጥፋት አያሟላም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የአመልካች ሰራተኛ የተደበደበችው ማታ ከመሆኑም በላይ የድብደባው ተግባር የተፈጸመው አመልካች ለሰራተኞቹ በመኖሪያነት ባዘጋጀው ቦታ መጸዳጃው አከባቢ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በሕጉ አነጋገር የስራ ቦታ እና ሰአት የሚለውን መለኪያ የሚሸፈን አይደለም በሚል ነው፡፡ አመልካች ሰዓቱም ሆነ ቦታው የስራ ቦታ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜን ተገቢነት ለመመርመር የተጠቃሹን ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ በዝርዝር መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ረ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ፡- “ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ተጠያቂ መሆን ” ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ከሚያስችሉ ምክንያቶች አንዱ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሐረግ "....በስራው ቦታ...." የሚለው ሲሆን ይኸው ሐረግ ሰራተኛው ስራውን በስራ ሰዓት የሚያከናውንበትን ቦታ ወይም የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ ሊያውል የተገኘበትን ቦታ ሁሉ የሚያጠቃልል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 97 እና 4 ድንጋጌዎችን ይዘት በማገናዘብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አሰሪው ስራው በሚሰራበት ካምፕ ውስጥ ለሰራተኛው በመኖሪያነት የመደበውን ቦታ እና በዚህ ቦታ ሠራተኛው ያለበትን ሠዓት ጭምር ሁሉ ሊጠቃልል እንደሚችል ከሕጉ መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ሰራተኛው በስራ ሰዓት ስራውን በሚያከናውንበት ቦታ ወይም የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ ሊያውል በተገኘበት ቦታ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠበት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ድርጊት ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ አላማም በሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ምርትና

ምርታማነትን ለማሳደግ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ሊተረጎም የሚገባውም ይህንኑ የድንጋጌውን ዓላማ መሰረት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባም እሙን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ሰራተኛ መደብደቡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠና በተጠሪም የታመነ ፍሬ ነገር መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ይህ የተጠሪው ድርጊት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ የጠብ አጫሪነት ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ፍ/ቤት ተጠሪው የድብደባውን ድርጊት መፈፀማቸውን ተቀብሎ ድርጊቱ የተፈጸመው ከስራ ሰዓት ወጪ ነው በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠውና ከሕጉ መንፈስና አላማ ውጪ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የአሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው ትእዛዝ በማክበር ካምፑ በሚገኝበት ቦታ መኖሪያ ተሰጥቶት በመኖር ላይ ባለበት ሁኔታ በዚሁ አካባቢ በድርጅቱ ሰራተኛ ድብደባ ከተፈፀመበት የድብደባውን ተግባር የፈፀመው ሰራተኛ ተግባሩን የፈፀመው በስራ ጊዜና ቦታ አይደለም ተብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ሕጉ ሊያሳካ ያሰበውን ፤ በስራ አካባቢ ሰላምን በማስፈን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የሚለውን አላማ ያላገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የድብደባውን ተግባር የፈፀሙ ስለመሆኑና ድብደባውን የፈፀሙትም ለስራ ጉዳይ ከተጠሪ ጋር እንዲሄዱ በአመልካች የታዘዙትን ሴት ሰራተኛ ቀኑን ሙሉ ሲያስቸግሯቸው ውለው አሰሪው በስራው ቦታ ውስጥ ባዘጋጀው የሠራተኞች መኖሪያ ቤት መፀዳጃ ቤት ሰራተኛዋ ቆይተው ሲወጡ ማታ ላይ መሆኑ የተጠሪን ድርጊት ጥፋት ከባድነት አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪው ድርጊት የአዋጁን አንቀጽ 27/1/ረ የተመለከተውን ጥፋት አያሟላም ሲል የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጉ ያስቀመጠውን የሰራተኛውን ግዴታ የሚመለከተውን ድንጋጌ እና የጥፋቱን አደገኛነት ከተጠቃሹ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ አንፃር በአግባቡ ሳያገናዝብ መሆኑን ስለተረዳን ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116083 ሚያዚያ 08 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 74140 ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 77113

ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አኪኮ ቦዲዋይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ ጌታቸው ወንድሙ ቀርበዋል

**ተጠሪ**፡- አቶ ገረመው አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ህግ በደነገገው መሰረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክርና በማስረጃ ከተረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ ጋር በማገናዘብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ሥራዬን በአግባቡ እየተወጣሁ እያለ አሠሪው ወደ ሌላ የሥራ መደብ ተዛውረሃል በአዲሱ የስራ መደብ ሄደህ ሥራ በማለት በቃል ሲገልጽልኝ፤ በተዛወርኩበት ቦታ ሥራዬን በኃላፊነት በአግባቡ እንድወጣ የዝውውር ደብዳቤ ይድረሰኝ በማለት በመጠየቁ በጥበቃ ኃላፊው ተገድጄ እንድወጣ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተነሣ የሥራ ውሉ የተቋረጠ ስለሆነ ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ የሚገባኝ ልዩ ልዩ ክፍያ እንደ ህጉ ይፈፀምልኝ በማለት ዳኝነት ስጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ከአሰሪነቱ በመነጨ ሥልጣን ሠራተኛው በሌላ የሥራ መደብ ተዛውሮ እንዲሰራ፤ የዝውውር ደብዳቤ በቀጣይነት እንደሚደርሰው በሥራ ኃላፊው ግልፅ ትዕዛዝ ቢደርሰውም ሥራ አልጀመረም፡፡ በዚህም የተነሳ በቀድሞው የሥራ ቦታ ሊያቆያቸው የሚችል ምክንያት የሌለ መሆኑ ተገልፆ ወደ መደብ የሥራ ቦታቸው እንዲሄዱ ሲነገራቸው ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው ሄደዋል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙ የሥራ ውል የተቋረጠው በሠራተኛው ፈቃደኝነት ወይስ በአሰሪው አነሳሽነት? የሚለውን በአከራካሪ ነጥብነት ይዞ በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በተሰማው ማስረጃ መሰረትም አሠሪው ሠራተኛውን የድርጅቱ የሥራ ቦታ በሆነ በሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሰራ በቃል መገለፁንና ሠራተኛውም ዝውውር በፅሁፍ ይድረሰኝ በማለት ሲጠይቅ እንደነበር አሰሪውም በድርጅቱ የጥበቃ ኃላፊ አማካኝነት ሠራተኛው ተገዶ እንዲወጣ ያደረገ መሆኑንና ሠራተኛውም ልብ አድርጉ እያለ ተገዶ ወጥቶ መሄዱን ከዚያም ወደ ሥራ ቦታ ሊመለስ ያልቻለ መሆኑን በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ እንደሆነ ከውሳኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም

አመልካች ሠራተኛው ወደ ተዛወረበት ቦታ አልሄድም በሚል ምክንያት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቋል የሚለው ክርክሩ በማስረጃው የተረጋገጠውን ጉዳይ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ለግራ ቀኙ ክርክር መነሻ የሆነው የዝውውር ጉዳይ እንደሆነ በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ ሁለቱንም ወገኖች ያለያያቸው ነጥብ አይደለም፡፡ የተለያዩበት ነጥብ አመልካች እንደ አሰሪነቱ የዝውውር እርምጃውን በቃል ትዕዛዝ አስተላልፌያለሁ፣ በቀጣይም የዝውውር ደብዳቤ እንደሚደርሰው እየተገለፀለት ወደ ምድብ ሥራው መሄድና ሥራ መጀመር ሲገባው ይህንን አላደረገም የሚለውን በማስቀደም በሠራተኛው በኩል ጥፋት እንዳለ ለማሳየት ሲል ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ይሁን እንጂ ሠራተኛው የተዛወረበት ክፍል ከቦታም ሆነ ከሥራ መደብ አንፃር ሲታይ ቀድሞ ተመድቦ ይሰራበት ከነበረው የሥራ አድራሻም ሆነ የሥራ መደብ የተለየ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፣ አመልካች ለዚህ ያቀረበው ማስተባበያ ክርክር የለም፡፡ ይህም ከሆነ አሰሪው የዝውውሩን እርምጃ በቃል በማስተላለፍና የሚያስገድድ አጣዳፊ ሁኔታ መኖሩን ካላስረዳ በቀር የዝውውር እርምጃውን በቃል አስተላልፌያለሁ፣ በቀጣይም በደብዳቤ እገልፃለሁ ማለቱ የአስተዳዳሪነት ሥልጣኑን በዘፈቀደ ለማከናወን ከመሻት የመነጨ ምክንያት ነው ከሚባል በቀር የእርምጃውን ህጋዊነት አያሳይም፡፡ ተጠሪም ይህ የዝውውር ውሳኔ በቃል መሆኑ ቀርቶ በፅሁፍ ይደረግልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተዛውሮ እንዲሄድ ከተገለፀለት የሥራ አድራሻ እና የሥራ መደብ አንፃር የአንድ መ/ቤትን አግባብ የሆነ የዝውውር አፈፃፀም ተከትሎ ያቀረበው የመብት ጥያቄ ነው የሚያሰኝ እንጂ የአሰሪውን ትዕዛዝ ላለመፈፀም ያደረገው ተግባር ሆኖ አይገኝም፡፡ በመሆኑም ለግራ ቀኙ ውዝግብ የሆነው ምክንያት አሰሪው በእራሱ በፈፀመው ያልተገባ ተግባር እንደሆነ መረዳት ችለናል፡፡

አሰሪው የወሰድኩት እርምጃ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው በሚል ያመነበት ቢሆን እንኳ ተጠሪ ወደ አዲሱ የስራ ቦታ ሄዶ ሥራ ባለመጀመሩ ምክንያት የሥራ ደንቡ እና ህጉ በሚፈቅደው ቅደም ተከተሉ የጠበቀ አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰድ ከሚችል በቀር ሠራተኛውን የጥበቃ ኃላፊ በሆነው አማካኝነት ከስራ ቦታ አስገድዶ እንዲወጣ በማድረጉ በእራሱ እጅ የመዳኘት ተግባሩ ሌላው ህጋዊ መሰረት የሌለው እርምጃ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በሠራተኛው ፈቃድ ሳይሆን ሠራተኛው/የአሁን ተጠሪ/ ደንቡን ባልጠበቀ ዝውውር ምክንያት ለመሄድ እቸገራለሁ በማለት ተገቢው እንዲፈፀም በመጠየቁ ምክንያት አሠሪው ከሥራ ቦታው በድርጅቱ ጥበቃ ሰራተኛ አማካኝነት አስገድዶ በማስወጣቱ ህገ-ወጥ ድርጊት ሆኖ ስለተገኘ የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ህጉ ከደነገገው ውጭ የተፈፀመ ነው በሚል የሰጡት ዳኝነት በማስረጃ የተረጋገጠውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በስንብቱ አግባብነት ዙሪያ ክርክር ከማቅረቡ በፊት በክፍያው ጉዳይ ላይ ያነሳው ክርክርም የለውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በወሰደው ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሳቢያ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ተገንዝበው የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 115625 በ29/3/2004 ዓ.ም የሰጠውና የመጨረሻ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ከዚህ በፊት በዚህ የሰበር መዝገብ ሚያዝያ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የተነሳ የደረሰውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 79096

ሐምሌ 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሪመምበር ዘ ፑረስት ኮሚዩኒቲ - ጠበቃ ለሜሳ ያደታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዘውድነሽ ማሞ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸውና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የተጠሪ የስራ ድርሻ ሕጻናትን መንከባከብ ሲሆን ከምትንከባከባቸው ሕጻናት ውስጥ ፍፁም ወርቁ የሚባለውን ደብድባ ሰውነቱ እስኪላጥ ድረስ ጉዳት ማድረሷ በመረጋገጡ የተፈጸመ ስንብት በመሆኑ ሕጋዊ ስለሆነ የሚከፈላት ክፍያ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ ህፃኑ መደብደቡ ቢረጋገጥም ድብደባውን የፈፀሙት ተጠሪ ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ብሎ አመልካች ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት የክፍያዎችን አይነትና መጠን ለይቶ ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩና ተደበደበ የተባለው ሕፃን ቀርቦ ከተሰማ በኋላ ተጠሪ ድርጊቱን መፈጸማቸው ተረጋግጧል ተብሎ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(2)፣14(2)(ሀ)) እና 27(1(ረ)) መሰረት ሕጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ ከዚህ በኂላም ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በሚንከባከቡት ሕፃን ላይ በድብደባ ተግባር ጉዳት ያደረሱ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረው ያላአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ

ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍል መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገነዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል የህጻናት እንክብካቤ የሚገኝበት መሆኑንና የተጠሪ ስራም ሕጻናትን መንከባከብ መሆኑን፣ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ሊቋረጥ ችሏል በማለት አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ፍጹም ወርቁ የተባለ ሕፃን ላይ በድብደባ ተግባር ጉዳት አድርሰዋል በሚል መሆኑንና ይህንኑ ክርክሩን ለማስረዳትም የሰነድ ማስረጃዎችን ማቅረቡን፣ የወረዳው ፍርድ ቤትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ለድርጊቱ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሰው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ለማለት የቻሉት ድርጊቱን ተጠሪ ስለመፈጸማቸው አመልካች አምነዋል በማለት ያቀረበው ሰነድ ቢኖርም ተጠሪ በፍርድ ቤት ሲቀርቡ ሰነዱን ክደው የተከራከሩ በመሆኑና የህክምና ማስረጃውም ጉዳቱ በተጠሪ ስለመድረሱ ያረጋግጣል ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን፣የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ድብደባው ተፈፅሞበታል የተባለውን ሕጻን አስቀርቦ ጉዳቱ በተጠሪ የደረሰበት ስለመሆኑ በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረው መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ ከተገለፀው የፍርድ ቤቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው በሕፃኑ ላይ አካሉ ላይ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በሁሉም ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሁኖ ጉዳቱ በምን ምክንያት ነው የደረሰው? በሚለው ጥያቄ ላይ ግን  የተለያየ ድምዳሜ ፍርድ ቤቶቹ የያዙ መሆኑን ነው፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን በሕፃኑ ላይ ጉዳቱ እንዴት ደረሰ? ለሚለው ጥያቄ ሕፃኑን በችሎት በማስቀረብ ሰምቶ ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ ተጠሪ ጉዳቱን ስለማድረሳቸው አረጋግጧል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግን በወረዳው ፍርድ ቤት የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ተጠሪ ጉዳቱን አድርሰዋል ለማለት የሚቻል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠውን የሕፃኑን ቃል በመተው ነው፡፡ይህ ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ለ)) እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64(2(ሐ) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀፅ 31  የተሠጠውን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ባግባቡ ያላገናዘበ ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ከተጠቃሽ ሕጎች ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላልና፡፡በመሆኑም ድብደባውን ማን አደረሰው የሚለው ጥያቄ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ እያለ ይኸው ፍሬ ነገር በክልሉ ሰበር ሰሚ ሳይታይ መታለፉ በህጋዊ ምክንያት ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕፃኑን በራሱ ተነሳሽነት አስቅረቦ መስማቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345(1) መሰረት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲል ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ እንደሚችል በሕጉ የተሠጠውን ስልጣን መጠቀሙን ያሳያል ከሚባል በስተቀር በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት የሚቻልበት ምክንያት የለም፡፡የዞኑ ከፍተኛ

ፍርድ ቤት ህጻኑ የተደበደበውና ጉዳቱ የደረሰበት በተጠሪ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የተከተለው መንገድ ሕጋዊ ነው፣ጉዳቱም በተጠሪ በተፈፀመው የድብደባ ተግባር የደረሰ ነው ከተባለ ይህ ጥፋት አንድን ሰራተኛ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ምክንያት መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ማናቸውም ሰራተኛ ሕይወትና ንብረትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት መፈፀም ሕገ ወጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 14(2(ሀ))ስር የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 27(1(ቀ)) ስር ደግሞ በአንቀጽ 14(2) ስር የተመለከቱትን ሕገ ወጥ ድርጊቶችን መፈፀም የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም ተጠሪ በሚንከባከቡት ሕፃን ላይ የድብደባ ተግባሩን መፈፀማቸው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደረገው የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና የተረጋገጠ ሁኖ በሕፃኑ ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳትም ሲታይም ሕይወቱን ለአደጋ ሊያጋልጥ የማይችል ነው ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በአዋጁ አንቀፅ 27(1(ቀ)) ድንጋጌ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡በዚህም ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ ለሰበር ችሎቱ በሕጉ ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345 መሰረት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ስልጣን ያላገናዘበና በውጤቱም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ቀ)) ድንጋጌን የጣሰ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 135103 መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12443 ሕዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡አመልካች ከተጠሪ ደመወዝ ብቻ በመቁረጥ ሲያጠራቅም የነበረ የፕሮቪደንት ፈንድ ካለ ይህንኑ ተጠሪ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 68138

ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- ወ/ሮ ጥሩሰው ጥላሁን የቀረበ የለም

2- ወ/ሮ ቦጋለች አስፋው ቀረቡ

3- እነ ወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ / ወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ እና

እማኂይ ድንቁ ቢሆነኝ / ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሲቪል ወርክስ አማካሪ መሃንዲሶች ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ ዜና ደባስ ቀረቡ

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 68139 ፣ 68140 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሞት ጉዳት ካሣ የሚጠይቅበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ ተከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ነበር፡፡ ከሣሾች ክሳቸውን ያቀረቡት በተለያዩ መዛግብት ሲሆን በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሱት አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ባለቤታቸውና የተፀነሰው ልጅ አባት የሆኑት ኢንጂነር ዳዊት ኃ/ማርያም በተጠሪ ድርጅት በኮንስትራክሽን መሐንዲስትነት የስራ መደብ በወር ብር 12,675 ደመወዝና በመስክ ስራ ሲመደቡ ደግሞ በቀን 200 ብር አበል እየተከፈላቸው ለመስራት ተቀጥረው ስራውን በመስራት ላይ እንዳሉ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሚቆጣጠረው በቀይ አፈር ቱርሚ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት አብሯቸው እንዲሰሩ ከተመደቡት ከኢንጂነር ሉሊት ታምራት ጋር የካቲት 23 ቀን 2002 ዓ/ም በመስክ መኪና በሾፌር ወደ ኘሮጀክቱ ቦታ ሄደው የተጠሪን ስራ እየሰሩ ሳለ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ/ም የተጠሪ ሹፌር በሚያሽከረክረው መኪና የሄዱበትን የመቆጣጠር ስራ ለማከናወን ኦሞራቴ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለውን ድልድይ ተመልክተው ሲመለሱ ደሞኮ ከተማ ሊደርሱ ሁለት ኪሎ ሚትር ሲቀር መኪናው ተንሸራቶ አሸዋ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ለመውጣት ሲሞክር ደራሽ የጎርፍ ውሃ ደርሶ ተሽከርካሪውን ከእነ ተሳፋሪዎች ይዞ በመሄዱ የተነሳ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ ገልጸው በሚስትነታቸውና ከሟች የጸነሱት ልጅ በአዋጁ መሠረት የሚገባቸው ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሱት አመልካች ባቀረቡት ክስ ልጃቸው የሆነችው ሟች ኢንጂነር ሉሊት ታምራት በተጠሪ ድርጅት ውስጥ

ተቀጥራ ደመወዝ 4055.50 /አራት ሺህ ሃምሳ አምስት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ እና አበል በቀን አንድ መቶ ብር እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ/ም በስራቸው ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ የሞቱ መሆኑን በመግለፅ የጉዳት ካሣ እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በተራ ቁጥር ሶስት የተጠቀሱት አመልካቾች ደግሞ የወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ ባለቤት የህፃን ናሆም ወላጅ አባት፣ የእማኀይ ድንቁ ቢሆነኝ ልጅ የሆኑት ሟች ኢንጅነር ደምስ ወርቁ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በወር ብር 11,135.00 የመስክ አበል ብር 270.00 እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ በየካቲት 28 ቀን 2002 ዓ/ም ከእነ ኢንጂነር ዳዊት ኃ/ማርያም ጋር በደረሰባቸው አደጋ የሞቱ መሆኑን ገልጸው በሕጉ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም በውሃ አደጋ ሕይወታቸው ያለፈው መሃንዲሶች ሰራተኞቹ መሆኑን ሳይክድ አደጋው የደረሰው ከተመደቡበት የስራ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በራሳቸው ፍላጎት ስራ በሌለበት እሁድ ቀን በመሄድ ሲመለሱ የደረሰ አደጋ በመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ ሊቆጠር አይችልም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮችን ከሰማ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ሟቾች ሕይወታቸው በአደጋ ምክንያት ባለፈበት ጊዜ ከተጠሪ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን ተጠሪ ያለመካዱንና በማስረጃም መረጋገጡን ከገለጸ በሁዋላ አደጋው የደረሰው ግን ሟቾች በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ሳይሆን ከስራ ቀንና ቦታ ውጪ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል ፣ አመልካቾች ሟቶች የሞቱት በስራ ላይ ሆነው ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም በማለት ደምድሞ ክሱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተናጠል አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባለመስማማት ሲሆን አመልካቾች አቤቱታቸውን በተለያዩ መዛግብት ያቀረቡ ቢሆንም የሁሉም አመልካቾቹ የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ግን ሟቾች በተጠሪ መኪና እና ሹፌር ኦሞራቴ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለውን ድልድይ ተመልክተው ሲመለሱ ጉዳቱ የደረሰባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 95 እና 97 ስር ላይ በስራ ላይ ስለሚደርስ አደጋ የተቀመጠውን የሕጉን መንፈስ ባግባቡ ሳይመለከቱ አደጋው የደረሰው በስራ ላይ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸውን ከሕግ ውጪ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ በሟቾች ሞት ምክንያት ለአመልካቾች ካሣ የመክፍል ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም በሁሉም መዛግብት በሰጠው የጽሑፍ መልስ ሟቾች ሰራተኞቹ መሆናቸውን ሳይክድ አደጋው በደረሰበት እለት ግን የስራ ቀን ካለመሆኑም በላይ ሟቾች ሊመለከቱት የሄዱበት ድልድይ ሟቾች እንዲሰሩ ከተመደቡበት ሳይት ውጪ በሌላ አቅጣጫ ያለና በእለቱም ሟቾቹ እንዲመለከቱት ከአሰሪው ተገቢው ትዕዛዝ ባልተሰጠበት ሁኔታ ሟቾቹ በራሳቸው ፍላጎት ሄደው ድልድዩን ተመልክተው ሲመለሱ አደጋው የደረሰ በመሆኑ አደጋው በስራ ላይ የደረሰ ነው ሊባል እንደማይችልና ኃላፊነት የለበትም ተብሎ መወሰኑ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዎቹ መነሻ ከሆኑት ውሣኔዎች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሪናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ሟቾች አደጋው በደረሰበት እለት በመስክ ስራ ላይ የነበሩ መሆኑን ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረው አደጋው የደረሰው ሟቾቹ ከተጠሪ ፈቃድና እውቅና ውጪ በሆነ ሁኔታ ተጠሪ በአማካሪነት በተቆጣጣሪ መሃንዲስነት ከሚሰራበት ቦታ ውጪ ወደአለው በኦሞራቴ ወንዝ ላይ የሚሰራውን ድልድይ ለመመልከት ሄደው ሲመለሱ አደጋው የደረሰ በመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ አይቆጠርም በማለት መሆኑን አመልካቾች ደግሞ ሟቾች በተጠሪ ትዕዛዝ ወደ ቀይ አፈር ቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ለመስክ ስራ መሄዳቸው የተረጋገጠና ወደ ኦሞራቴ ወንዝ ድልድይ ጉብኝት የሄዱትም በተጠሪ ሹፌርና መኪና እንዲሁም በወቅቱ የመስኩ ስራ ኃላፊ ከነበሩት ሰው ጋር ጭምር በመሆኑ አደጋው በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋጧቸው ነጥቦች ደግሞ ሟቾች በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆናቸውን አደጋው ደረሰ የተባለበት እለት እሁድ ሁኖ የእረፍት ቀን መሆኑን ፣ በዚህ እለት ሟቾች በተጠሪ ድርጅት መኪና አሞራቴ ወንዝ ላይ በሌላ ድርጅት የሚሰራውን ድልድይ ለመመልከት ሄደው ሲመለሱና ደመኮ ከተማ ለመድረስ ሁለት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው የተሳፈሩበት መኪና አዋሽ ወንዝ ውስጥ ገብቶ የጎርፍ ደራሽ ውሃ የወሰዳቸውና ለህልፈት የዳረጋቸው መሆኑን ሟቾች ከተመደበቡት የመስክ ስራ ቦታ ውጪ ወደ ሚገኘው ወደ ኦሞራቴ ወንዝ ድልድይ ግንባታ ጉብኝት የሄዱት ከተጠሪ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ኖሮ ሳይሆን በራሳቸው ፍላጎት ስለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸውን ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ በመቀበል የሚኖረው ሚና በሕጉ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ ስህተት ካለ ማረም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሕጉ ረገድ ያለውን ጉዳይ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ /occupational injury/ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ /occupational disease/ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95/2/ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 97 ደግሞ በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ወጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ማለት ደግሞ ሰራተኛው የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ እና በስራ ሰዓት ሲፈጽም የደረሰበት ጉዳት ፣ ሰራተኛው ከስራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ስራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በስራው ቦታ ወይም በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የደረሰበት ጉዳት ፣ ሰራተኛው ወደ ስራ ቦታ ወይም ከስራ ቦታው ድርጅቱ ለሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው መጓጓዣ በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀፅ 97 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአሰሪው ሓላፊነት በስራ ምክንያት ለሚመጡ ጉዳቶች የተወሰነ ስለመሆኑ ድንጋጌዎቹ ያስረዳሉ፡፡ በዚህም

መሠረት በአዋጁ የጉዳት ካሣ ለመጠየቅ የሚቻለው ጉዳቱ በስራ ምክንያት የመጣ ሁኖ በስራ ሰዓት ፣ በስራ ቦታና ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው አጋጣሚ የተከሰተ መሆኑ በሚገባ ሊረጋገጥ ይገባል ። በመሆኑም የአዋጁ አንቀፅ 96 እና 97 ድንጋጌዎች ጠቅላላ ይዘት ሲታይ ደግሞ አሰሪው በስራ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ የመከላከል እርምጃ የመውሰድ ፣ አደጋው በሕጉ በተቀመጠው ትርጉም መሠረት በስራ ላይ ከደረሰ ደግሞ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 95 ድንጋጌ መሠረት የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ጉዳቱ የደረሰው በአንቀፅ 97 በተመለከተው አኳኋን በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት መሆኑንና እንደዚሁም በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖሩን /proximate cause and effect relationship/ ማስረዳት እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል የአሰሪው አላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ /strict/ ስለሆነ ካሣ ጠያቂው ወገን በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማሳየት ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የጉዳት አድራሹን ወይንም የአሰሪውን የአእምሮ ሁኔታ /state of Mind/ ማስረዳት እንደማይጠበቅበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ሟቾች በተጠሪ መስሪያ ቤት ተቀጣሪ ሰራተኞች መሆናቸውና በመስክ ላይ እያሉ በደረሰባቸው አደጋ ሕይወታቸው ማለፍ እና ይኸው አደጋ የደረሰው ደግሞ በተጠሪ ተመድበው በሚሰሩበት የሥራ ቦታና ሰዐት ሳይሆን ከዚህ ውጪ በራሳቸው ፍላጎት በአካባቢው በሌላ ድርጅት የሚሰራውን የድልድይ ግንባታ ለመመልከት ሄደው ድልድዩን ተመልክተው ሲመለሱ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ አደጋው የደረሰው ከስራ ሰዓትና ከስራ ቦታ ውጪ ከስራው ጋር ግንኙነት በሌለው አጋጣሚ እና ከአሠሪው ትዕዛዝ ሳይኖር መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ በአሰሪነቱ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆንበት ምክንያት የሌለ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 95፣ 96 እና 97 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች የሞቱት በስራ ላይ በደረሰ አደጋ አይደለም በማለት የካሣ ክፍያ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 68011 ሕዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም በመ/ቁጥር 68045 ሕዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም ፣ በመ/ቁጥር 68012 ሕዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 98936 የካቲት 26 ቀን 2003 ዓ.ም. በመ/ቁጥር 99000 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም. ፣ በመ/ቁጥር 98933 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ጸንቷል፡፡
2. ሟቾች ሕይወታቸው ያለፈው በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ባለመሆኑ ለአመልካቾች የሚከፈል የካሣ ክፍያ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ግልባጩ ከሰ/መ/ቁጥር 68139 እና 68140 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሀሣብ ልዩነት

እኛ ስማችን በሶስተኛ ተራ ቁጥር እና በአራተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምነው ዳኞች አብላጫው ድምፅ ሟችዎች ህይወታቸው ያለፈው በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ባለመሆኑ ለአመልካቾች የሚከፈል የካሣ ክፍያ የለም በማለት በሰጠው ውሣኔ የማንስማማ በመሆኑ በሀሣብ ተለይተናል፡፡

ከአብላጫው ድምፅ የምንለይባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጀመሪያው ልዩነታችን የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች የተጠሪን ሠራተኞችና የተጠሪ የሥራ መሪ የሆነውን ሰው አደጋው በሥራ ላይ እያሉ የደረሰ መሆኑን ያለባቸውን የማስረዳት ግዴታና ተጠሪ ሠራተኞቹ በሥራ ላይ አደጋ ያልደረሰባቸው መሆኑን ያለበትን የማስረዳት ግዴታ የተረጎመበትና የተረዱበት አግባብ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር ባደረገው የሥራ ውል  ከቀይ አፈር አስከቱርሚ ያለውን መንገድ ለመገንባት የሥራ ተቋራጭነት ውል የተዋዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በውል የተረከበውን የመንገድ ሥራ ለማከናወን የቀጠራቸውን ሠራተኞችና የግንባታ መሣሪያዎች እንዲያስተዳድርለትና የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱን በበላይነት እንዲመራለት ሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁን የቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አድርጎ መድቦት የነበረ መሆኑ ግራ ቀኙ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር በተደረገው ክርክር ያልተካደና የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱ በመደባት የመለያ ቁጥር 3-43639 መኪና የትራንስፖርት አገልግሎት እያገኙ እያሉ "ወራባ" ከተባለው ወንዝ በደራሽ ጎርፍ ውሀ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ተወስደው ህይወታቸው ካለፈው አራት ሰዎች ውስጥ አንደኛው ማለትም ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የነበረ ነው ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ በአዋጅ ቁጥር  377/96 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ እንደተሻሻለ በተደነገገው መሠረት የድርጅቱ /የተጠሪ/ ሥራ መሪ ናቸው፡፡

ሌሎቹ በአደጋው ህይወታቸው ያለፈው ሰዎች ማለትም ኢንጅነር ዳዊት ሀይለማርያም ኢንጅነር ሉሊት ታምራትና የተጠሪ ሠራተኞች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በእኛ እምነት ሟች ኢንጅነር ዳዊት እና ኢንጅነር ሉሊት የሞት አደጋ የደረሰባቸው ሥራ በመሥራት ላይ እያሉ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት ወደ "አምራቴ" ወንዝ የመስክ ሥራ ጉብኝት ለማድረግ የሄዱት በአሰሪው /በተጠሪው/ ትዕዛዝ በተሰጣቸው የሥራ ስምሪትና ትዕዛዝ መሠረት ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነጥብ መመለስ አለበት፡፡ የቀይ አፈር ቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ ተጠሪ በተቋራጭነት የሚሠራውን የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት  ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት አስፈላጊ ነው የሚለውን ሥራ እንዲሰሩና ከሙያቸው ጋር ተያያዥነት ያለውን

የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ በሥሩ የሚገኙትን ሰራተኞች የማሰማራት ሥልጣን እንዳለው ይገመታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ካሉት ሠራተኞች የተወሰኑትን ብቻ ለይቶ ከመደበኛ የሥራ ቀናት ፣ ከመደበኛ የሥራ ሠዓትና ከመደበኛው የሥራ ቦታ ውጭ ለሥራ ሊያሠማራና የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሚኖረው የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ልዩ የሥራ ባህሪና በግንባታው ሥራ መስክ የዳበሩ የአሠራር ልምዶችን በተለይም ስለግንባታ አካሄድ የወጣውን የሥራ መመሪያ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ የኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ለነበረው ለኢንጅነር ደምሴ ወርቂ የሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ሠራተኞችን ለሥራ የማሰማራትና ለሥራው አፈፃፀም ጠቀሜታ ያለው የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደረጉ ለማድረግ የሚያስችለው እንደነበር የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ከመደበኛው የሥራ ቀናት ከመደበኛ የሥራ ሠዓትና ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ የድርጅቱን ሠራተኞች ለሥራ የማሰማራትና የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያልነበረው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም እንጅ ማስረጃ ቢያቀርብ እንኳን በሥራ አስኪያጅ ሥልጣን ላይ ተጠሪ የጣለውን ገደብ የኘሮጀክቱ ሠራተኞች በጠቅላላውና ሟችዎች ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት በግልፅ እንዲያውቁት ያደረገ መሆኑንና ሟችዎች ሥራ አስኪያጅ ከሥራ ከመደበኛ ሥራ ቀናቶች ከመደበኛ የሥራ ሠዓታቸውና ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጭ እንዲሰማሩና የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ የማዘዝ ሥልጣን እንደሌለው የሚያውቁ መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ከቀረበው ክርክርና በሰበር ከቀረበው ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ በነበረው የኢንጅነር ደምሴ ወርቂ ሠራተኞችን ከመደበኛ የሥራ ቀናቶች ውጭ ለሥራ የማሰማራት ሥልጣንና ኃላፊነቱ የተገደበ መሆኑን አላስረዳም፡፡ አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉና በሥራ ደንቡ መሠረት በአሰሪው የሚሰጠውን የሥራ ስምሪትና ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት የካቲት 23 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ውጭ "በአሞራቴ" ወንዝ ላይ በመሠራት ላይ የነበረውን ድልድይ ከቦታው ድረስ በመሄድ የሙያ የመስክ የሥራ ጉብኝት ያደረጉ መሆኑን አመልካቾች ያልካዱትና የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት ከመደበኛ የሥራ ቀናት ውጭ በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጭ የሚገኘው በአሞራቴ ወንዝ ላይ እየተሠራ የነበረውን ድልድይ ለማየት የሄዱት ተጠሪን በመወከል የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱን በኃላፊነት ሲመራ የነበረው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የድርጅቱን መኪና እና ሹፌር በማንቀሣቀሥና ሥራ አስኪያጅም አብሮ በመጓጓዝ እንደሆነ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ሟችዎች በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ የመሥክ የሥራ ጉብኝት ማድረጋቸው ተጠሪ በተቋራጭነት የያዘውን የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት ጠቃሜታ እንዳለው አምኖበትና አውቆት እንደዚሁም የድርጅቱ ሥራ መሪ የመስክ የሥራ ጉብኝቱ ተካፋይ ሆኖበት የተከናወነ ነው፡፡

ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ሟች ኢንጅነር ሉሊት በደራሽ ጎርፍ ውሀ የተወሰዱት ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ከቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ክልል ውጭ ሣይሆን በመደበኛ የሥራ ቦታቸው በተለይም ከመኖሪያ ሠፈራቸው በሁለት ኪሎ ሜትር ዕርቀት በሚገኘው "ወራባ" በተባለው ወንዝ መሆኑ

በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ሟችዎች በእረፍት ቀን ከመኖሪያ ሠፈራቸው ወጥተው በአሞራቴ ወንዝ ላይ እየተሠራ የነበረውን ድልድይ ለመጎበኘት የተጓዙትና ከዚያም በኂላ ከሄዱበት የመስክ የሥራ ጉብኝት ተመልሰው በቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ክልል ውስጥ በደራሽ ጎርፍ የተወሰዱት የተጠሪ የሥራ መሪና የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ በነበረው ኢንጅነር ደምሴ ወርቄ ተግባራዊ እንዲሆን ባደረገው የመስክ የሥራ ጉብኝትና በሰጠው የሥራ ስምሪት ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡ ሟችዎች በእረፍት ቀናቸው የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ የሰጠው የሥራ ስምሪት በአሰሪው ማለትም በተጠሪ እንደተሰጠ የሥራ ሥምሪት ትዕዛዝና የመስክ የሥራ ጉብኝት የሚቆጠር መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ ድንጋጌዎች ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2188 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብና ህጋዊ ውጤት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ሟች ኢንጅነር ሉሊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት ከአሠሪያቸው /ከተጠሪ/ በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጭ እንዲያከናውኑ የተሰጣቸውን የመስክ ሥራ ጉብኝት ትዕዛዝ አከናውነው ሲመለሱ በቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ክልል አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 ፣ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2188 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የማስረዳት ግዴታቸውን ተወጥው እያለ የሥር ፍርድ ቤት ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ሟች ኢንጅነር ሉሊት በሥራ ላይ እያሉ አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን አመልካቾች አላስረዱም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ከላይ የዘረዘርናቸውን ሁኔታዎችና የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሀሣብ አለን፡፡

ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ሟች ኢንጅነር ሉሊት አሠሪያቸው /ተጠሪ/ ኘሮጀክቱን በበላይ ኃላፊነት ይመራ በነበረው ሥራ አስኪያጅ የተሰጣቸውን የመስክ ሥራ ስምሪትና የመስክ ሥራ ጉብኝት በማክበር በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጭ የሚገኘውን "የአሞራቴ" ወንዝ ላይ የሚሰራውን ድልድይ ጎብኝተው ከተመለሱ በኂላ በቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ክልል ውስጥ በደራሽ ጎርፍ ተወሰደው የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል ፡፡ አንድ ሠራተኛ ከሥራ ቦታው ወይም ከመደበኛ ሥራ ሠዓት ውጭም ቢሆን የአሠሪውን ትዕዛዝ ሥራ ላይ ሲያውል በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሟችዎች የመስክ የሥራ ጉብኝት በማድረግ በእረፍት ቀናቸው አይተውት የተመለሱት በአማራቴ ወንዝ ላይ እየተሠራ ያለው ድልድይ ከሟችዎች የመደበኛ የሥራ ቦታ ክልል ውጭ የሚገኝ መሆኑን በመመልከት ብቻ የበታች ፍርድ ቤቶች አደጋው በሥራ ላይ የደረሰ አይደለም በማለት የሰጡት ትርጉምና የደረሱበት መደምደሚያ ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ሟች ኢንጅነር ሉሊት በኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ የተሰጣቸውን የሥራ ስምሪትና ትዕዛዝ በመፈፀም ላይ እያሉ አደጋው የደረሰ መሆኑን ያላገናዘበና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በመሆኑም አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካቾች ሟች ኢንጅነር ዳዊትና ሟች ኢንጅነር ሉሊት በእረፍት ቀናቸው እንዲያከናውኑ በአሠሪያቸው/ በተጠሪ/ የተዘጋጀውን የመስክ ሥራ ጉብኝት በማከናወን ላይ እያሉ "ወራባ " ተብሎ በሚጠራው ወንዝ በገጠማቸው በደረሰ የጎርፍ ውሀ ተወሰደው የሞት አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታቸውን የተወጡ በመሆኑ አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካቾች በሟችዎች መሞት ለደረሰባቸው ጉዳት ከአሠሪና

ሠራተኛ ጉዳይ  አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 መሠረት ተጠሪ ካሣ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ ፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2188 ንዑስ አንቀፅ 1 ፣ የአዋጅ ቁጥር 37796 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ መሠረት ያደረገ ህጋዊ ጥያቄ ነው በማለት በሀሣብ ተለይተናል፡፡

2. የተጠሪ የሥራ መሪ የነበረውና የቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የነበረው ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ በእረፍት ቀኑ ከሌሎቹ ባለሙያዎች ጋር የመስክ የሥራ ጉብኝት አድርጎ ሲመለስ በደረሰበት አደጋ ህይወቱ ያለፈ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ሟች ኢንጅነር ደምሴ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅና የሥራ መሪ ቢሆንም ከአሠሪው ጋር ያለው ግንኙነትና ሌሎች መብቶችን በተመለከተ የሥራ ውሉንና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው  መሆኑን በተጠሪና በሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ መካከል ከተደረገው የሥራ ውል ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የመንገድ ሥራ ግንባታን በኃላፊነት የሚመራ ሥራ አስኪያጅ በሌላ የሥራ ተቋራጭ በመሠራት ላይ የሚገኝ ድልድይ በአካል  ተገኝቶ መጎብኘት ሙያዊ ልምድ መቅሰሙና ሌሎች ባለሙያዎችም የሙያ ልምድ የሚያገኙበትን የመስክ የሥራ ጉብኝት ማመቻቸቱ በግንባታ ኘሮጀክት የሥራ አመራር ሂደት ያልተለመደና የአመራር ጉድለትና ጥፋት መሆኑን ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ እንደሌለ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የተጠሪ የሥራ መሪ ሆኖ የመንገድ ኘሮጀክት ሥራ በሀላፊነት ሲመራ በእረፍት ቀኑ ጭምር ሥራውን በትጋት በመፈፀም ላይ እያለ የሞት አደጋ የደረሰበት መሆኑን ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸው ዝርዝር ጉዳዮች ያሣያሉ፡፡ ስለሆነም ሶስተኛ ተጠሪዎች ሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የተጠሪን የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ በትጋት ሲመራና በእረፍት ቀኑ ሲሰራ የሞት አደጋ የደረሰበት በመሆኑ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 መሠረት ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሥራ ውሉን መሠረት ያደረገና ህጋዊ ጥያቄ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ሊሻርና ተጠሪ ለአመልካቾች ካሣ እንዲከፍል ሊወሰንበት ይገባል በሚል ዕምነት በሀሣብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 61717

ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አበበች አዱኛ በራሳቸውና በህጻን ረቂቅ

ተክሉ ስም - ከጠበቃ ሓጎስ አብርሃ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተንዳሆ ቤቶች ልማት

ፕሮጀክት ጽ/ቤት- የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ በስራ ላይ በደረሰ የሞት አደጋ ምክንያት ለጥገኞች የሚከፈል ክፍያ ጋር በተያያዘ የተነሳ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነዉ፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ባለቤታቸውና የህጻን ረቂቅ ተክሉ አባት የነበሩት አቶ ተክሉ አያኖ በተከሳሽ ዘንድ በጊዜያዊ ሰራተኝነት ተቀጥረው ከመጋቢት 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምረው ብር 6,710 የወር ደመወዝ እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበረ፣ መስከረም 07 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ስራ ቦታቸው በተከሳሽ መኪና በመጓዝ ላይ እያሉ በደረሰ አደጋ መሞታቸውን፣ ተከሳሽ በህጉ መሰረት ተገቢውን ክፍያ ለመፈጸም ፍቃደኛ መሆኑን በ26-6-2000 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ገልጾ የነበረ ቢሆንም ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም በባንክ በኩል ለከሳሽ የከፈለው ግን ብር 27,051 ብቻ መሆኑን፣ ተከሳሽ በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 94(2) እና አዋጅ ቁ.262/94 አንቀጽ 46 መሰረት ለሟች ተተኪዎች የሟቹን የዓመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን፣ በዚህ መሰረት ከከፈለው ሌላ የሚቀርበትን ብር 375,549 እንዲከፍል ተጠይቆ በ22-9-2000 ዓ.ም በጻፈው መልስ ፈቃደኛ ያለመሆኑን ማሳወቁን ገልጸው ተከሳሽ ይሄንን ቀሪ የካሳ ክፍያ ከየካቲት 30 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድና ከክሱ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንበት የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ የፍርድ ቤቱ ስልጣን ተነስቶ ውድቅ ተደርጎ የታለፈ ስለመሆኑ ተመልክቶ በፍሬ-ጉዳዩ ላይ የተሰጠው የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- በእርግጥ ሟችን በጊዜያዊ ሰራተኝነት ቀጥሯቸው በኤርታሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የኮንስትራክሽን እና ኦፊስ ኢንጅነሪንግ መምሪያ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ እንደነበረ በመግለጽ ሟች የሞቱት ያልተፈቀደላቸውን የሠ.ቁ.3-27289 የሆነ ፎርድ ፒክአፕ መኪና እያሽከረከሩ ከአዲስ አበባ ወደ ዱብቲ ሲጓዙ በደረሰባቸው የመገልበጥ አደጋ መሆኑን፣ ሟች የተቀጠሩት ባላቸው የምህንድስና ሙያ እንጂ በሹፌርነት

ያለመሆኑን፣ ሟች ይዘውት የነበሩውን መኪና የተረከቡት አቶ ሞገስ ጀንበሩ የተባሉ ሹፌር ቢሆኑም ሟች መኪናውን ከሹፌሩ ነጥቀው አዲስ አበባ ውስጥ ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኂላ በራሳቸዉ አሽከርካሪነት 4 የፕሮጀክቱን ሰራተኞች ጭነው ወደ ዱብቲ ሲጓዙ መኪናዋ አቅጣጫ ስታ ከመንገድ ወጥታ መገልበጧን፣ ሟች በራሳቸው ስህተት በፈጠሩት አደጋ ተከሳሽ ተጠያቂ ስለማይሆን፣ በአገራችን ባለው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት በሚወስኑት ህጎች እንዲሁም በአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(ሐ) በተቀመጠው ትርጉም መሰረት በሟች ላይ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ሊባል የማይችል በመሆኑ በህጉ ላይ ለተተኪዎች ይከፈላል ተብሎ የተወሰነውን ካሳ ከሳሾች የመጠየቅ መብት የሌላቸው በመሆኑ፣ ጉዳቱ በስራ ላይ የደረሰ ባይሆንም ሟች ከዚህ በፊት በቋሚነት በተለያየ ቦታ ያገለገለ መሆኑን ከግምት በማስገባት ከብር 100,000 በላይ ሰራተኞችን አስተባብሮ ለከሳሽ የከፈለ መሆኑን ገልጾ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ እና የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ሟች የሞቱት በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን በመመርመር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በዚሁ የበታች ፍርድ ቤት የተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች አደጋው በደረሰ ጊዜ ሟች ያሽከረክሩት የነበረው መኪና በእርግጥ ከፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ለበዓል ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ይዘውት ያልመጡ እና ሌላ ተሽከርካሪ በመያዝ የመጡ ስለመሆኑ፣ አዲስ አበባ የሚሊንየም በዓሉን አሳልፈው ወደ ስራ ቦታ ሊመለሱ ሲዘጋጁ የስራ አስኪያጁ መኪና በመበላሸቱ ሟች ይዘውት የመጡት መኪና ለስራ አስኪያጁ ተሰጥቶ አደጋው የተከሰተበት መኪና በዚህ ሂደት ሊይዝ እንደቻለ፣ ቀድሞ ሟች ይዘውት የመጡት መኪና በኃላፊነታቸው የተሰጣቸው እና አሁን አደጋው የተከሰተበት መኪና ደግሞ ከኃላፊው ጋር በመቀያየር ሂደት ሟች እጅ የገባ ስለመሆኑ፣ ሟችም ወደ ስራ ቦታቸው ዱብቲ ሲሄዱ 4 የፕሮጀክቱን ሰራተኞች ይዘው በመጓዝ ላይ እያሉ በአደጋው ምክንያት ህይወታቸው ሊያልፍ ስለመቻሉ ናቸው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ የተመለከቱትን ፍሬ-ነገሮች ካጣራ በኂላ ጉዳቱ የደረሰው በስራ ላይ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) አኳያ መርምሮታል፡፡ የተሰጠውም ውሳኔ የዚህ ድንጋጌ ይዘት "…….መስሪያ ቤቱ ለሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የማጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት……" ከሆነ ብቻ በመሆኑ፣ አደጋዉ የደረሰበት ሰራተኛ ይጓዝ የነበረው መስሪያ ቤቱ "…for the common use…." እየተጠቀመ ባለበት ወቅት እንጂ በዚህ ጉዳይ ሟች ለግሉ መጠቀሚያ በቀጥታ ተሰጥቶት ወይም ከሌላ ባለስልጣን ጋር ተቀያይሮ ሲያሽከረክር የደረሰን አደጋ አይመለከትም፣ አደጋውን ያደረሰው መኪና ተጠሪ ለሰራተኞች መጓጓዣ እንዲያገለግል በመደበው የጋራ መጓጓዣ ሳይሆን በስራ ኃላፊነታቸው የተነሳ እንዲጠቀሙበት በግል የተሰጣቸውን መኪና ሲያሽከረክሩ የደረሰ አደጋ በመሆኑ በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ሊባል ስለማይችል ከሳሾች በጠቀሱት ህግ ላይ ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ ጊዜያዊ ሰራተኛ ሲሞት ለተተኪዎች የሚከፈለውን ካሳ ተጠሪ እንዲከፍል አመልካች ለመጠየቅ መብት የላቸውም የሚል ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ግራ ቀኙ ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የፌ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ በተጻፈ አቤቱታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን

ነጥቦች ያነሱ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- ሟች አደጋው የደረሰባቸው መስሪያ ቤቱ በመደበላቸው መኪና እየተጓዙ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ በጋራ ለሰራተኞች አገልግሎት የተመደበ ካልሆነ በኃላፊነታቸው ለሟች የተመደበን መኪና ለሰራተኞች በጋራ የተመደበ ባለመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ አይቆጠርም ወደሚለው መደምደምያ መደረሱ የድንጋጌውን ይዘት ያላገናዘቡ ከመሆኑም በላይ በወቅቱ ሟች 4 የፕሮጀክቱ ሰራተኞችን በመያዝ ወደ ስራ ቦታቸው በመጓዝ ላይ እያለ የደረሰ አደጋ በመሆኑ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት ታርሞ በክሳችን የተመለከተው ክፍያ እንዲፈጸምልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በቀን 17-5-2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ በተጻፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- ድርጅታችን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚተዳደር ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ይሄ የፌ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.38250 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ የፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ፣ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በተመለከተ ደግሞ ሟች የስራ መሪ በመሆኑ ይሄንንም መሰረት በማድረግ ክስ ሊያቀርብ የማይችል በመሆኑ፣ ሟች አዲስ አበባ ካለው መኖሪያ ቤታቸው ድርጅቱ ወደ አዘጋጀላቸው ዱብቲ ወደ ሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በመጓዝ ላይ እያሉ የደረሰ አደጋ በመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ የማይወሰድ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆኑ በዚሁ መልሳቸው 2ኛ ገጽ ላይ መስቀለኛ ይግባኝ በማለት የተጻፈ ሲሆን ተገቢውን ስነስርዓት በመጠበቅ የቀረበ ባለመሆኑ ታልፎአል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን በዚህም ላይ በሟች እና ተጠሪ መስሪያ ቤት መካከል የቅጥር ውል ሲደረግ በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ለሚከፈለው ክፍያ ተፈጻሚነት ያለው ህግ አዋጅ ቁ.262/94 በአዋጅ ቁ.515/99 እንደተሻሻለው ስምምነት ያለ በመሆኑ በዚሁ ስምምነት መሰረት ክፍያ እንዲፈጸምልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ የአመልካች ባለቤት(ሟች) የሞቱት በስራ ላይ በደረሰ ጉዳት አይደለም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በግራ ቀኙ መካከል ባለው ክርክር አግባብነት ያለው የህግ ማዕቀፍ እና ጉዳዩን ለመመልከት ስልጣን ያለውን አካል በተመለከተ በበታች ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እና የፌዴራል መንግስት ሰራተኞቸ አዋጅ በመጥቀስ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመሆኑን ከመከራከር ውጪ አዋጆቹ በግራ ቀኙ ባለው ክርክር ላይ ተፈጻሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ ያነሳው ነጥብ ስለመኖሩ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ደግሞ በአንድ በኩል የተጠሪ ጽ/ቤት ውስጥ የሚነሳው ተመሳሳይ አለመግባባት የሚታየው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ይሄ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመጥቀስ በፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ሊታይ እንደማይገባ ሲከራከር በሌላ በኩል ደግሞ ሟች የስራ መሪ መሆኑን በመጥቀስ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በዚህ ክርክር ላይ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በተጨማሪም አመልካች ቀደም ሲል ጉዳዩን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩን የመመልከት ስልጣን የሌለው መሆኑን በማመልከት ክሱን የዘጋ ስለመሆኑ ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ክሳቸውን ሲያቀርቡ በግራ ቀኙ መካከል ባለው የስራ ውል መሰረት

ተገቢው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መልኩ ሟች የተቀጠረው በኮንስትራክሽንና ኦፊስ ኢንጂነር መምሪያ ኃላፊ ሆኖ በጊዜያዊነት መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ የስራ መሪ ሊባል የሚችል የስራ መደብ ላይ የተቀጠረ በመሆኑ በሟች እና ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የስራ ውል ደግሞ ለህግ እና ሞራል ተቃራኒ ነው የሚል ክርክር ያልተነሳ በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ስምምነት ደግሞ በተስማሙት አካላት መካከል ህግ ሆኖ የሚያገለግል ስለመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁ.1731 የሚያስገነዝበን በመሆኑ ከዚሁ በሟች እና በተጠሪ ጽ/ቤት መካከል ተደርጎ በነበረው ስምምነት መሰረት የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ተመሳሳይ አለመግባባቶች ሲከሰቱ ማለትም በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመሆን አለመሆኑ ለመወሰንም ሆነ የካሳ አከፋፈልን በተመለከተ ሊፈቱ የሚገባቸው በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት መሆን እንዳለበት በግራ ቀኙ በተደረገው የስራ ውል አንቀጽ 5 ስር በግልጽ በማመልከት የስምምነታቸው አካል አድርገውታል፡፡ በዚሁ መሰረት የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት የበታች ፍርድ ቤቶች በሟች ላይ የደረሰው አደጋ በስራ ላይ የደረሰ አይደለም ወደሚለው መደሚደሚያ የደረሱት አደጋውን ያስከተለው መኪና ሟች ይዞት የመጣው ተሸከርካሪ የስራ አስኪያጁ መኪና በመበላሸቱ ለስራ አስኪያጁ እንዲሰጥ ተደርጎ በዚህ መቀያየር ሂደት በእጁ የገባ ስለመሆኑ እና ሟች ለሚሊኒየም በዓል የተሰጠውን እረፍት ጨርሶ ወደ ስራ ቦታው እየተመለሰ ባለበት ወቅት የተከሰተ አደጋ መሆኑን በፍሬ-ነገር ተቀብለው እያለ መኪናው በጋራ ለሰራተኞች የተመደበ ባለመሆኑ በሚል ነው፡፡ የፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) ስንመለከት መስሪያ ቤቱ ለሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት በማለት ከሚደነግግ ውጪ አንድ ሰራተኛ ባለው ኃላፊነት በግሉ ተሽከርካሪ ተሰጥቶት እየተገለገለበት ባለበት ሁኔታ የተከሰተን አደጋ አይጨምርም ማለት ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በህጉ በግልጽ ከተመለከተው የድንጋጌው ይዘት ውጪ የደረሱበት መደምደሚያ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች ሟች ህይወቱ ሊያልፍ የቻለው በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ ሁነው እያለ በስራ ላይ የደረሰ አደጋ አይደለም መባሉ ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ በሟች ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ብለናል፡፡

የካሳውን መጠን በተመለከተ ሟች የተቀጠረው በጊዜያዊነት በመሆኑ እና በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ የተቀመጠውና ለጊዜያዊ ሰራተኛ ተፈጻሚነት ያለው የካሳ ክፍያ በግራ ቀኙ የስራ ውል መሰረት በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው እና በዚህ የካሳ ክፍያ መጠን ላይ የተነሳ ክርክር የሌለ በመሆኑ እና ለዚህም አግባብነት ያለው ድንጋጌ የአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 94(2) እና አዋጅ ቁ.262/94 አንቀጽ 46(2)(5(ለ)) በመሆኑ ከዚሁ አኳያ ተሰልቶ ለአመልካች የጉዳት ካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት የቅጥር ውል መሰረት የውላቸው አካል ባደረጉት እና በዚህ መልኩ አለመግባባት ሲፈጠር ተፈጻሚነት እንደሚኖረው በተስማሙት ድንጋጌ መሰረት የካሳውን መጠን ማስላት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በስራ ላይ በደረሰ ጉዳት የሞተው ሰራተኛ ጊዜያዊ ተቀጣሪ ከሆነ የአንድ ዓመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ ለተተኪዎች በጉዳት ካሳ መልክ እንደሚከፈል ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል የሟች የወር ደመወዝ 6,710 (ስድስት ሺህ ሰባት መቶ አስር ብር) ስለመሆኑ ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ በመሆኑም (6,710 x 12)5 = 402,600 ብር (አራት መቶ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ብር) ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ የካሳ ክፍያ መጠን ውስጥ ቀደም ሲል አመልካች 27,051 ብር (ሃያ ሰባት ሺህ

ኃምሳ አንድ ብር) በተጠሪ መስሪያ ቤት የተከፈላቸው ስለመሆኑ ያመኑ በመሆኑ ይሄው ገንዘብ ሲቀነስ ቀሪ ክፍያ 402,600 — 27,051 = 375,549 ብር (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር) ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የተጠሪ ድርጅት ለአመልካች 375,549 ብር (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍል ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በሟች ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በስራ ላይ የደረሰ አደጋ አይደለም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. በቀን 10-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.122319 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሸሯል፡፡

2. በሟች አቶ ተክሉ አያኖ ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ድርጅት ለሟች ተተኪዎች (ለአመልካች) ብር 375,549 (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍላቸው ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 74636

ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም

ተጠሪዎች፡-1.ትዕግስት ሙሉዓለም

2. መስፍን ምስጌ

3. እቴነሽ ወጋዬሁ

4. ከተማ ዋና

5. ዲላወርቅ ግርማ

6. ጽጌረዳ አዲሱ

7. ሰናይት ማዘንጊያ

8. ትዝታነሽ በሬዩ

9. ጌትነት መሀሪ

10. አንተነህ አጋር

11. መስፍን ምትኩ

12. ሂሩት ሚዴቅሳ

13. ብርቱካን በረሳ

14. መንበረ ወንድማገኝ

15 .ተስፋዬ ማሞ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ለሰበር መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት በሐዋሳ ከተማ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ተከሳሽ የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ የመዋቅር ለውጥ አድርጌአለሁ በሚል የስራ ውላችንን ሲያቋርጥ የስንብት ክፍያ ብቻ በመክፈል ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር የ15 ቀናት ደመወዝ ሳይከፍል ያዘገየ በመሆኑ ያልከፈለውን ደመወዝና በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ እንዲከፍልና የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠን ይወሰንል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ ተከሳሽ በመዋቅር ለውጥ ምክንያት ሰራተኞችን ስመድብ ከሳሾች በምደባው ባለመካተታቸው ክፍያ በጠየቁት ወቅት በስራ ላይ አልተገኙም፣ የ15 ቀናት ደመወዝ አልተከፈለንም ለሚሉትም ስራ የሰሩ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፣ ለከሳሾች በተሰጣቸው የስንብት ደብዳቤ ከእዳ ነጻ ለመሆናቸው ክሊራንስ በማቅረብ ክፍያ እንዲቀበሉ ከመገለጹም በላይ በማስታወቂያና በግል ስልካቸው ጭምር የተዘጋጀላቸውን ክፍያ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ የታመነውን ክፍያ በመክፈል የሚፈለግብኝን ግዴታ የተወጣሁ ስለሆነ  ስራ ስለመስራታቸው ባልተረጋገጠበት የ15 ቀናት ደመወዝና ለዚሁ አከራካሪ ለሆነ ክፍያ  ክፍያ ዘግይቷል በሚል የ3ወር ደመወዝ ሊከፈላቸው ስለማይገባ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ጉዳዩን የመረመረው የመ/ደ/ፍርድ ቤትም በሰጠው ፍርድ የስራ ውሉ በተቋረጠበት ወቅት ለ15 ቀናት ከሳሾች ስራ ላይ ስለመሆናቸው መዝገቡ የሚያስረዳ ሲሆን ተከሳሽ ድርጅትም በእነዚህ ቀናት ከሳሾች ስራ ያልሰሩ ስለመሆናቸው የሚያስረዳ ማስረጃ ባለማቅረቡ እስከ ሐምሌ 06 ቀን 2003 ዓ.ም. ድረስ ሥራ ላይ የቆዩበትን የ15 ቀናት ደመወዝ ሊከፍል ይገባል በሚል የወሰነ ሲሆን፣ ለዚሁ አከራካሪ ለሆነው ክፍያ የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ ለዘገየበት በቅጣት መልክ እንዲከፍል የጠየቁት ግን ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

በስር ከሳሾች ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን የመረመረው የከተማው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ በሰጠው ፍርድ የሐምሌ ወር የ15 ቀናት ደመወዝ በሐምሌ ወር መክፈል ሲገባው ሳይከፍል በማዘግየት በነሐሴ ወር  የከፈለ ስለመሆኑ የሰነድ ማስረጃዎች ስለሚያሳዩና መልስ ሰጪው ክፍያውን ለማዘግየቱ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስለመኖሩ ስላላስረዳና ሰራተኞቹ በስራ ላይ በተባለው ጊዜ ያልነበሩ መሆን አለመሆናቸውን በበቂ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም የመልስ ሰጪው ሆኖ እያለ ይህንኑ ስላላረጋገጠ ክፍያው ለዘገየበት የ2ወር ደመወዝ ለእያንዳንዳቸው ሊከፍል ይገባል በሚል የስር የመ/ደ/ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የይግባኝ ባዩን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን በማሰናበቱ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

ሰበር አቤቱታም አመልካች በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብ፡- በሰራተኛ ምደባና ቅነሳ መሀል ባሉት ጊዜያት ሰራተኛው በሥራ ገበታ ላይ ለመገኘቱ ጊዜ ተወስዶ ከተረጋገጠ በኋላ ለተሰናበቱት ሰራተኞች የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ በአንድ ጊዜ ከተፈጸመላቸው በኋላ የ15 ቀናት ክፍያ አጠራጣሪና አከራካሪ በመሆኑ ምክንያት ክፍያው የቆየ ሆኖ ሳለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ክፍያው  ዘግይቷል በሚል ለተጠሪዎች የ2 ወር ደመወዝ

እንዲከፈላቸው የወሰነውም ሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ያጸናው የቅጣት ክፍያን ዓላማ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር በክሱ በተጠቀሱት ቀናት ተጠሪዎች ስራ አልሰሩም ከማለቱ በስተቀር በማስረጃ ማረጋገጥ ባለመቻሉ ምክንያት ክፍያ ላዘገየበት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል የስር ከፍተኛና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወሰኑት በአግባቡ ስለሆነ ይጽናልን ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች የ15 ቀናት ደመወዝ በጊዜ ባለመክፈሉ የተነሳ ክፍያ ለዘገየበት ለተጠሪዎች የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸው የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወሰኑት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ድርጅት ባደረገው የአሰራር ለውጥ ምክንያት ሰራተኞቹን ሲቀንስ ተጠሪዎችም ከስራ የተቀነሱ ስለመሆናቸው መዝገቡ የሚያመለክት ሲሆን በቅነሳው ምክንያት ከስራ ውጪ ለተደረጉ ሰራተኞችም የተለያዩ ክፍያዎችን ከፍሎ እንዳሰናበታቸው ገልጾ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪዎችም ቢሆኑ በህጉ መሰረት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን የከፈላቸው ስለመሆኑ የሚያምኑት ጉዳይ ነው፡፡ ዋናው የሚያከራክራቸው ጉዳይ ግን የስራ ውሉ ሲቋረጥ የ15 ቀናት ደመወዝ አመልካች በህጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መክፍል ሲገባው ክፍያውን አለመፈጸሙ ነው፡፡ አመልካች ለክፍያው አለመፈጸም በስር ፍርድ ቤት እንደምክንያት የጠቀሰው ተጠሪዎቹ በእነዚህ ጊዜያት ስራ አልሰሩም የሚል ሲሆን ስራ ስለመስራታቸው የተረጋገጠ መሆኑን ደግሞ የከተማው የመ/ደ/ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልጿል፡፡ የመ/ደ/ፍርድ ቤትም ክፍያው የዘገየ መሆኑ ቢረጋግጥም ክፍያው አከራካሪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የቅጣቱን ገንዘብ ሳይቀበል ያለፈ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግን ተጠሪዎች ስራ ያልሰሩ ስለመሆናቸው የማስረዳት ሸክም የአመልካች ነው በሚል ክፍያውን አመልካች ማዘግየቱ ስለተረጋገጠ የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፍል ሲል ወስኖበታል፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠው ፍሬ ነገር መሰረት ደግሞ አመልካች ሌሎች ክፍያዎችን ከፍሎ የ15 ቀናት ደመወዝ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 መሰረት በ7 የስራ ቀናት ውስጥ አለመክፈሉ ግልጽ ነው፡፡ አመልካች የ15 ቀናት ደመወዝ ያልከፈለው ደግሞ ክፍያው አከራካሪ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 37 ስር እንደተመለከተው አሰሪው ያመነውን ክፍያ በመፈጸም አከራካሪ የሆነ ክፍያን እስከሚጣራ ድረስ ማዘግየት የሚችል ስለመሆኑ ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 38 መሰረትም አሰሪው በቅጣት እስከ 3 ወር ድረስ የሚደርስ የሰራተኛውን ደመወዝ ያህል ቅጣት ሊከፍል የሚገደደው ከቁጥጥር ወጪ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ወይም በአንቀጽ 37 በተደነገገው መሰረት የሚያከራክር ክፍያ በሌለበት ከቅን ልቦና ወጪ ሰራተኛውን ለመጉዳት ተነሳስቶ ክፍያውን ማዘግየቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች የስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎችን ሳያዘገይ ለተጠሪዎች መክፈሉን መዝገቡ የሚያመለክት ሲሆን ዘግይቷል የተባለውም 15 ቀናት ደመወዝ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለ15 ቀናት ተጠሪዎች ስራ ባለመስራታቸው የተነሳ በህጉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ አከራካሪው ክፍያ ሳይከፈል ቀርቷል ሲል እየገለጸ ባለበት የክፍያ ጊዜ በመዘግየቱ ብቻ እንደበቂ ምክንያት በመውሰድና አመልካች ሌሎች ክፍያዎችን ሁሉ ስለመፈጸሙ ግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገየበት ለእያንዳንዳቸው የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የወሰኑት በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 37 ስለአከራካሪ ክፍያ የተደነገገውን

መሰረት ያደረገ ካለመሆኑም ሌላ በአዋጁ አንቀጽ 38 የተቀመጠውን የገንዘብ ቅጣት ዓላማ ባላገናዘበ መልኩ ስለሆነ ክፍያ ለዘገየበት ለተጠሪዎች የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የሰጡት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የሐዋሳ ከተማ የከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/11103 በቀን13/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 55825 በቀን 21/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1)መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. አመልክች ለተጠሪዎች የ15 ቀናት የደመወዝ ክፍያ ላዘገየበት ለእንዳንዳቸው የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸው የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348 (1) መሰረት ሽረናል፡፡ ስለሆነም ክፍያ ላዘገየበት ለተጠሪዎች የሚከፍላቸው ክፍያ የለም ብለናል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች አመልካች የ15 ቀን ደመወዝ እንዲከፍላቸውና የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ሲሉ የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡ መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ 69153

ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ብርሃኑ ከፍያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ሮማን ይርጋ/ 11 ሰዎች/

1. ጠበቃ ናኦድ አየናቸው/ ስለፋሲል ይርጋና ፍሬ ህይወት
2. ጠበቃ ዘውዱ ዓሊ/ ስለ 10ኛ ና 11ኛ ተጠሪዎች ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተቋቋመ የውርስ አጣሪ አበል መጠን ሊወሰን የሚችልበትን ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ወ/ሮ ሮማን ይርጋ ፣ ወ/ሮ ቅድስት ይርጋ እና ወ/ሮ ቆንጂት ይርጋ አመልካች ፣ አቶ መስፍን ይርጋ ደግሞ ተጠሪ ፣ እነ አቶ ተፈሪ ይርጋ ስድስት ሰዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ ሁነው በተካሄደው የሟች አቶ ይርጋ እንደታ የውርስ ንብረት ማጣራት ክርክር ሲሆን የውርስ ይጣልራልኝ ጥያቄ ያቀረቡት የስር አመልካቾች እነ ወ/ሮ ሮማን ይርጋ ሶስት ሰዎች ናቸው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የአሁኑን አመልካች የውርስ ሃብቱን ለማጣራትና ለማስተዳደር የሾሚቸው ሲሆን አመልካች የውርስ ሃብቱን አጣርተው የውርስ ሃብት ሪፖርቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ ሪፖርቱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በተጣራው የውርስ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ በውርስ ሪፖርቱ ከተካዱት ጉዳዮች አንዱ የውርስ አጣሪው የስራ ዋጋ መጠንን የሚመለከት ሲሆን ውርስ አጣሪው ላጣሩት የውርስ ስራ ከጠቅላላው ንብረት 5% ይገባኛል በማለት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበው የውርስ አጣሪ ስራ ዋጋ መጠን ከተጣራው የውርስ ንብረት መጠን አንፃር ሲታይ የተጋነነ ነው፣ ከወራሽነትም የሚተናነስ አይደለም፣ ወራሾች እያንዳንዳቸው ተጠይቀውም እያንዳንዳቸው ብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ ለመክፈል ፈቃደኞች መሆናቸው ተረጋግጧል የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ለአመልካች እያንዳንዳቸው ብር ሶስት ሺህ ፣ በጠቅላላው ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሺህ ብር/ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ የውርስ ማጣራቱና የውርስ ንብረት ማስተዳደሩን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገውን የሥራ ዋጋ አስመልክቶ ከተጠሪዎች መካከል ስምንቱ አስቀድመው በስምምት መጠንኑ የቆረጡ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ፍርድ ቤቱ

መጠኑ የተጋነነ ነው በማለት መቀነሱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ፣1711 ፣ 959 ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ ያልታየ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ሊጣራ የሚገባው የሕግ ነጥብ መኖሩ ታምኖበት ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ተጠሪዎች ቀርበው የተወሰኑት ከአመልካች ጋር የ5% ስምምነት ማድረጋቸውን በማመን መልስ ሲሰጡ የተወሰኑት ደግሞ ከአመልካች ጋር ያደረጉት ስምምነት የሌለ መሆኑን በመግለፅ በእየራሳቸው በኩል ተገቢው እንዲወሰን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የስር ፍርድ ቤት የአጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ መጠን በመቀነስ የሠጠው የውሣኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም ?የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በመሰረቱ የውርስ አጣሪ መሆን የሚችለው፡- ያለኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው፣ ይህም ልጅ፣ ልጅ ከሌለ ወላጅ ፣ ወንድም እህት፣ በኑዛዜ ጠቅላላውን የሟች ንብረት እንዲወርስ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው፣ አካለመጠን ያልደረሱ ወይም በህግ የተከለከሉ ህጋዊ ወራሾች ሞግዚት፣ በወራሾች ስምምነት የሚመረጥ ሰው፣ ወራሾች ካልተስማሙ በፍ/ቤት የሚመረጥ ውርስ አጣሪ፣ ወይም (…) በኑዛዜ የሚመረጥ የውርስ አጣሪ ነው፡፡ የውርስ አጣሪው ዋና ዋና ስራዎች ደግሞ፣ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግ ወራሾቹ እነማን እንደሆኑ መለየት ፣ የውርስ ሀብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ ሀብቶች መቀበል ፣ እዳዎችን መክፈል ፣ ሟች በኑዛዜው ያደረጋቸውን ስጦታዎች ኑዛዜው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ መክፈልና የሟች ኑዛዜ እንዲፈፀም አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ፣ ሟች ኑዛዜ ያልተወ ከሆነ የሟች ያለኑዛዜ ወራሾችን በመለየት የኑዛዜውን ድልድል እንዴት እንደሆነ ለወራሾች ማሣወቅ ፣ እና በአጠቃላይ ሌሎች ስራዎችን ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 946-1125 ድረስ ያሉትን እንደ አግባብነታቸው መስራት ነው፡፡ በዚህ መልኩ በሕጉ የተሰጡትን ስራዎች የሚያከናውን የውርስ አጣሪ የስራውን አገልግሎት ዋጋ የሚያገኝበት አግባብም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 959 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አጣሪው በሟቹ በተወሰኑት ሁኔታዎች /ውለታዎች/ መሠረት ወይም በወራሾቹ ወይም በዳኞቹ መካከል በተደረገ ስምምነት <u>***የሚሰራው ሥራ የሚያረጋግጥለት ከሆነ***</u> አንድ የአገልግሎት ዋጋ ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋ ሊወሰን የሚችለው አጣሪው ከሟች፣ ወይም ከዳኞች መካከል በሚደርገው ስምምነት ሁኖ የሚሰራው ስራ አረጋጋጭ ሁኖ ሲገኝ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የሥምምነቱ መኖር ብቻውን አሳሪ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ሲሆን የማጣራቱ ስራ ክብደቱ ፣ ውስብስብነቱ ከወሰደው ጊዜና ድካም አንፃር እየታየ የአገልግሎት መጠኑ የሚወሰን መሆኑንና ይህም ለፍርድ ቤቱ በሕጉ የተሰጠ ስልጣን መሆኑን የድንጋጌው መንፈስና ይዘት ከውርስ ማጣራት ስራ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ለክርክራቸው መሰረት ያደረጉት ስምምነቱን መኖሩንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌን ሲሆን በእርግጥ በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ሁሉ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሕግን ያህል አስገዳኝነት ኃይል ያላቸው መሆኑን ተጠቃሹ ድንጋጌ የሚያሳየን ጉዳይ ሁኖ

ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711 እና 959 ድንጋጌዎች ጋር ተጣምሮ ሲታይ የስምምነቱ መኖር ብቻውን ስምምነቱ ሕጋዊ ጥበቃ እንዲደረግለት የሚያደርግ ሲሆን ስምምነቱ የውርስ ማጣራቱ ስራው ክብደቱና ውስብስብነቱ እየታየ የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋ መጠን በፍርድ ቤት የሚወሰንበት ሕጋዊ አግባብ ያለ ከመሆኑ ጭምር ሲታይ የአመልካች ክርክር ሕጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስምምነቱ መኖር ያለመኖር በራሱ ክርክር ያስነሳ ከመሆኑም በተጨማሪ ከወራሾች መካከል ሁለቱ ስምምነቱ ላይ ፈቃዳቸውን ያልገለፁ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበው ክርክርም ስምምነቱ መኖሩን ያመኑት የተወሰኑት ተጠሪዎች ብቻ መሆናቸው፣ የውርስ ንብረቱ ክፍፍሉ እስከሚፈፀም ድረስ እንደ አንድ የተለየ ንብረት የሚቆጠርና ሳይነጣጠል የሚቆይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060/1/ ድንጋጌ ከተቀመጠው መርህ እና የውርስ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ ለመቀነስ ፍርድ ቤት በሕጉ ስልጣን የተሰጠው ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ከወራሾች መካከል የተወሰኑት ስምምነት ማድረጋቸው የውርስ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ መጠኑን በግል ለያይቶ መወሰን የግድ አስፈላጊ ነው ብሎ ለመደምደም የማያስችል ነው፡፡ አመልካች ከውርስ ንብረቱ ተገኘ ከተባለው ብር 5,498,400.00 ውስጥ 5% ይገባኛል ያሉት የተጋነነ እና ከወራሽነት የማይተናነስ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ግምት የወሰደበት ሲሆን አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የስራውን አድካሚነት እና በራሳቸው ጥረት የተነሳ ከውርስ ንብረቱ ይፈለጋል ተብሎ በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ተጥሎ የነበረውን የግብር መጠን ማስቀረታቸውን ፣ በንብረት ጥበቃ ወቅትም የፈፀሙትን ተግባር ሁሉ በመዘርዘርና በምክንያትነት በመጥቀስ ክፍያው የተጋነነ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊጣራና ሊመዘን የሚችል ካለመሆኑም በላይ በፍ/ብሕ/ቁጥር 959 ድንጋጌ መሠረት ለስር ፍርድ ቤት ከተሰጠው ፈቃድ ስልጣን አንጻር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋን በተመለከተ በተወሰኑት ወራሾችና በአጣሪው መካከል ስምምነት ቢኖርም በክርክሩ የተረጋገጡትን የተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶችን በመያዝ ፍርድ ቤት የአገልግሎት ዋጋ መጠኑን ለመቀነስ የሚችል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 959 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳይ በመሆኑና በተያዘው ጉዳይም በዚህ አግባባም የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋ መጠን የተወሰነ በመሆኑ በውሣኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06321 ሐምሌ 23 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99123 መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በፍርድ ቤት የተሾመ የውርስ አጣሪ የአገልግሎት ዋጋን በተመለከተ አጣሪው የሚሰራው ስራ የሚያረጋግጥለት መሆኑን በመመርመር ፍርድ ቤት የመቀነስ ስልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 61357

ሕዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፍቅሬስላሴ እሸቴ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዋጋዬ ጋይም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሚያዚያ 17 ቀን 2002 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ከአመልካች ጋር ከ22/05/1968 ዓ/ም ጀምሮ ተጋብተው ሲኖሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 504 የሆነውን ቤት በጋራ እንዳፈሩ እንዲሁም ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ተለያይተው በመኖራቸው የተነሳ ጋብቻቸው በራሱ ጊዜ እንደፈረሰ ገልጸው በጋብቻ ወቅት በጋራ አፈራነው ያሉትን ቤት በተመለከተ የክፍፍል ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መስርተው የቆዩ መሆኑ የማይካድ መሆኑን፣ቤቱን ግን በጋብቻ ወቅት በጋራ ስለመፈራቱ ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ቀደም ብሎ ፍርድ ቤት ቀርቦ በነበረው ጉዳይም በፍቺ ጥያቄው ላይ የተሰጠ ውሳኔ የሌለ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ ሳይራራቁ እየተጠያየቁ እንደሚኖሩ እንዲሁም ግራ ቀኙ ተነጋግረው በግል መፍትሄ ለጉዳዩ ለመስጠት እንደሚችሉ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮና ቤቱን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ማጣሪያ ማስረጃ እንዲቀርብ ከአደረገ በሁዋላ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ የመሰረቱት ጥር 22 ቀን 1968 ዓ.ም. መሆኑን፣አከራካሪው ቤት የተሰራው ደግሞ በ1974 ዓ/ም መሆኑን መረጋገጡን፣አመልካች ቤቱን ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ተለያይተው መኖር ከጀመሩ በሁዋላ ያፈሩት ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑ መረጋገጡን በመዘርዘር ቤቱ የጋራ ነው በማለት እኩል እንዲካፈሉ ሲል በሕጉ የተመለከተውን የአከፋፈል ሥርዓት በመግልጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካችና ተጠሪ ለረዥም አመታት ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ የፍቺ ውሳኔ አይሰጥም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ የፍቺ

ውጤት የሆነው ንብረት ላይ ግን ክፍፍሉ ይቀጥላል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በመ/ቁጥር 117245 ላይ ጋብቻ የለም ተብሎ ተወስኖ እያለ በዚሁ ጉዳይ የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክፍፍል በተጠሪ በኩል በመቅረቡ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የቤት ቁጥር 504 የሆነ የጋራ ሃብት ነው በማለት እኩል እንዲካፈሉ ሲል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ከዚኅም በኂላ ተጠሪ በክርክር ላይ እንዳሉ ከዚህ አለም በሞት መለየታቸው በመገለፁ ለወራሾቻቸው በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው ቢሆንም አልቀረቡም፡፡እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 139762 ቀርቦ የግራ ቀኙ ክርክር እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በ22/05/1968 ዓ.ም. ጋብቻ ፈፅመው አከራካሪው ቤት በ1974 ዓ.ም. የተሰራ መሆኑን፣አከራካሪውን ቤት አመልካች ከጋብቻ በፊት የሰሩት ወይም ከተጠሪ ጋራ በስምምነት ተለያይተው መኖር ከጀመሩ በሁዋላ ያፈሩት ንብረት ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 በሆነው የፍቺ ጥያቄ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ ሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ ተለያይው መኖር ከጀመሩ ረዥም ጊዜ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ ጋብቻው በራሱ ጊዜ የፈረሰ በመሆኑ የፍቺ ጥያቄ የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም በማለት ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መወሰኑን፣ከዚህም በሁዋላ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ያሉትን አከራከሪውን ቤት ለመካፈል ይወሰንላቸው ዘንድ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በሌላ መዝገብ (በመ/ቁጥር 13972) በሆነው ለስር ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካች እንዲቀርቡ ተደርጎ ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት የመከላከያ መልስ የፍቺ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ የንብረት ክፍፍል የሚቀርብበት አግባብ የለም በማለት መከራከራቸውን ነው፡፡በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የፍቺ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ በሕጉ ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 ላይ ጋብቻው በራሱ ስለፈረሰ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ የለም በማለት መወሰኑ የጋብቻውን ውጤት ከመጠየቅ የማይከለክል ነው፣ይርጋውን በተመለከተ ደግሞ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሱት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲደርሱ ሊያነሱ የሚችሉበት ሥርዓት የለም በማለት በጽሁፍ ክርክር ወቅት ተከራክረዋል፡፡እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በመመልከትና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ጉዳዩን መርምረነዋል፡፡

በመሰረቱ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በተግባር ተጋቢዎች ተለያይተው በየፊናቸው የራሳቸውን ህይወት መኖር ከቀጠሉ ሊፈርስ እንደሚችል ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 76 ድንጋጌና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ከሰጠበት የመ/ቁጥር 20398 ውሳኔ መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ጋብቻ ከላይ በተመለከተው የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌ ወይም የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከፈረሰ የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረት በፍርድ

ቤት ውሳኔ መፍትሔ የማያገኝበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በራሱ ጊዜ የፈረሰ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 ውሳኔ ማግኘቱ የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ውሳኔ ግን የጋብቻ ውጤትን በተመለከተ በፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ ከማቅረብ የሚከለክልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የጋራ ንብረት ጥያቄ የግድ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ መቅረብ ያለበት ጉዳይ ስለመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አያሳይም፡፡ስለሆነም ፍቺው ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጪ በሆነ መንገድ በተግባር የተከናወነ (Defacto divorce)መሆኑ የጋብቻውን ውጤትን በተመለከተ በፍርድ ቤት ዳኝነት ከመጠየቅ የማይከለክል ሲሆን ዋናውና መታለፍ የሌለበት ነገር የክፍፍሉ ጥያቄ በሕጉ በተዘረጋው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረቡ መረጋገጡ ላይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በተግባር ፍቺ ያከናወኑ ተጋቢዎች የጋብቻውን ውጤት በተመለከተ ለፍርድ ቤት ክፍፍሉን ማቅረብ ያለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ስር በተመለከተው የአስር አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊሆን ይገባል፡፡የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ከጋብቻ መፍረስ በሁዋላ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ቀሪ መሆን ያለበት መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17937 በቀረበው ጉዳይ ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታልና፡፡ ይርጋውን ተመለከተ ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው የሚለው ወገን በስርዓቱ መሰረት በግልፅ አንስቶ መከራከር የሚጠበቅበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 234(1(ሐ)) እና 244(2(ሠ)) ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ይርጋን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የማይችለው ጉዳይ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1856(2) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ሥርአቱን ጠብቀው የይርጋን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አላቀረቡም፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት አንስተው የተከራከሩት መሰረታዊው ነጥብ የፍቺ ውሣኔ ሊሰጥ አይገባም ተብሎ በፍርድ ቤት ከተወሰነ በሁዋላ የጋብቻ ውጤት ላይ ክስ መመስረት ሕጋዊ አግባብነት የለውም የሚል ብቻ ነው፡፡ይህ ደግሞ ይርጋውን አንስተው መከራከራቸውን የሚያሳይ አይደለም፡፡ስለሆነም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሥርአቱን ጠብቀው ያላነሱትን የይርጋ ክርክር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያነሱበት አግባብ የሌለ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

- በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 139762 ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94407 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
- ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአምስት የማይነበብ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 68190

ታህሳስ 5 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ትእግስት አሰፋ ቀረበች

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እመቤት ቱርፌ - ወኪል አደፍርሰው ዘውዴ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በብድር የተወሰደን ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፣ ክሱ የተመሠረተው ባልና ሚስት በሆኑት አቶ አደፍርሰው ዘውዴ እና በአሁኑዋ ተጠሪ ላይ ነው፡፡ ተከሣሾች ገንዘቡን የወሰዱት ለእህል ንግድ ሥራ እንደሆነ እና በወቅቱ አጠናቀው ባለመክፈላቸው በቀሪ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ከእነ ወለዱ እንዲከፍሉት ይወሰንለት ዘንድ አመልካች ጠይቆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የተከሣሾችን የመከላከያ ክርክር ከሰማ በኂላ፣ የአሁንዋን ተጠሪ /ሚስት/ በብድር ውሉ ላይ ስለመፈረምዋ አልተረጋገጠም በማለት ከእዳው ነፃ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም የተባለው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ፣ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ የተከሰሰችው ከባለቤትዋ ጋር በመሆን እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ባለቤትዋ የሆነው አቶ አደፍርሰው ዘውዴ ዕዳው ይመለከተዋል ተብሎ በፍ/ቤት ተወስኖበታል፡፡ ተጠሪ ስትከራከር የቆየችው ባለቤቴ ገንዘቡን አልተበደረም በማለት ሳይሆን፣ በብድር ውሉ ላይ አልፈረምኩም በማለት ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም በፊርማው ላይ ብቻ በመመሥረት እና ይህንኑ በላብራቶሪ አስመርምሮ የመጣለትን ውጤት እንደብቸኛ እና ፍጹማዊ የሆነ ማስረጃ በመቁጠር ተጠሪን ከእዳው ነፃ አድርጎአል፡፡ አመልካች ከፊርማው በተጨማሪ ውሉ ሲፈረም የነበሩ እማኞች በምስክርነት እንዲሰሙለት ስለመጠየቁም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ክሱን የሰማው ፊርማውን በተመለከተ የመጣለትን የላብራቶሪ ውጤት እንደብቸኛ ማስረጃ በመቁጠሩ ምስክሮቹን አልሰማም፡፡ በሌላም በኩል ብድሩ የተወሰደው ለንግድ ሥራ ነው፡፡ የተጠሪ ባለቤት ነጋዴ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በንግድ ሕግ ቁጥር 19 ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ይታይልኝ በማለት ከአመልካች ለቀረበው ክርክርም ዋጋ አልሰጠም፡፡ አመልካች የሰበር

አቤቱታውን ያቀረበው በማስረጃው አቀባበል እና በንግድ ሕጉ የተመለከተውን ድንጋጌ አተረጓጎም በሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪም ሁለቱን ነጥቦች መሠረት በማድረግ ክርክርዋን /መልስዋን/ አቅርባለች፡፡

እንደምናየው አቶ አደፍርሰው ዘውዴ እና ተጠሪ ባልና ሚስት ስለመሆናቸው አላከራከረም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ በብድር የተወሰደው ለእህል ንግድ ሥራ እንደሆነ እና አቶ አደፍርሰው ዘውዴም ነጋዴ ስለመሆኑም እንደዚሁ ክርክር የተነሳበት አይደለም፡፡ ተጠሪ እዳው አይመለከተኝም የምትለው ባለቤቴ /አቶ አደፍርሰው ዘውዴ/ ከአመልካች የተበደረው ገንዘብ የለም፣ ወይም የተበደረው ለንግድ ሥራ ማስኬጃ አይደለም፤ ወይም ደግሞ ነጋዴ አይደለም በማለት ሳይሆን፣ የኔ ስምምነት እስከሌለ ድረስ ከብር 500/ አምስት መቶ ብር/ በላይ ለሆነው ብድር ተጠያቂ አይደለሁም፣ በብድር ውሉ ላይ አልፈረምኩም፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 19 የተቀመጠው ድንጋጌ በተሻሻለው የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ተሽሮአል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

አመልካች ከሥር ጀምሮ እየተከራከረ ያለው ተጠሪም ከባለቤትዋ ጋር በመሆን በብድር ውሉ ላይ ፈርማለች፡፡ ፊርማውን በሚመለከት ከባለሙያ የተሰጠው አስተያየት ብቻውን በብድር ውሉ ላለመስማማቷ /ላለመፈረሟ/ ብቸኛ እና የተሟላ ማስረጃ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ በብድር ውሉ ላይ አልፈረመችም የሚባል እንኳን ቢሆን በንግድ ህጉ በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ዕዳው እስዋንም ይመለከታል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን ከእዳው ነፃ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ውሣኔው ሕግን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪን ከእዳው ነፃ ያደረጉአት በብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የእሷ ስለመሆኑ በባለሙያ ሊረጋገጥ አልቻለም በማለት እና ይህ ከባለሙያ የመጣውን አስተያየት እንደብቸኛ ማስረጃ በመውሰድ ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ ሌሎቹን የአመልካች ማስረጃዎች አልሰሙም ወይም የባለሙያው አስተያየት ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ አልመዘኑም፡፡ የተካደን ፊርማ ለማጣራት የባለሙያ አስተያየት መጠየቁ አግባብ አይደለም የሚባል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአንድ ሰው ፊርማ በተለያዩ ምክንያቶች ሊለዋወጥ የሚችልበት ሁኔታም ስለሚኖር ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ሳይሰሙ እንደበቂና ብቸኛ ማስረጃ ተደርጎ መወሰዱ አግባብ አይሆንም፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም እነዚህን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በሰበር መ/ቁ 14981 በሰጠው ውሣኔ ፊርማን በሚመለከት የሚቀርበው የባለሙያ አስተያየት እንደመጨረሻ ማስረጃ /conclusive evidence/ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ፊርማውን በሚመለከት ከባለሙያ የቀረበላቸውን አስተያየት ብቻ መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ይህ እንግዲህ በዚህ አግባብ የሚታይ ሲሆን ፣ ቀጥሎ መታየት ያለበት ተጠሪ በብድር ውሉ ተዋዋይ አልነበረችም ቢባልስ ከእዳው ከነጭራሹ ነፃ ነች ወይም እዳው እሷን አይመለከትም ወደሚለው ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት ሊመረመር የሚገባው የሕግ ነጥብ የለም ወይ? የሚለው ነው፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለጸው ብድሩ የተወሰደው ለንግድ ሥራ ማስኬጃ ነው፡፡ የሚነግደው ባል ወይም ሚስት የተዋዋለው እዳ እንደባልና ሚስት ዕዳ እንደሚቆጠር በንግድ ሕግ ቁጥር 19 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ የንግድ ሕግ ድንጋጌ የባልና ሚስት ዕዳን በተመለከተ የተደነገገው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 ተጠቅሶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በፍትሐብሔር ሕጉ መጽሐፍ ተካቶ የነበረው የቤተሰብ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 213/92 በመሻሻሉ ወይም እራሱን የቻለ የተሻሻለ

የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ በመውጣቱ በአሁኑ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 የተቀመጠው ድንጋጌ ስለባልና ሚስት የጋራ ዕዳን በሚመለከት ለሚቀርበው ክርክር አወሳሰን በዋቢነት ሊጠቀስ አይችልም፡፡ በንግድ ሕጉ የተቀመጠው ድንጋጌ ቁጥር 19 ግን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ተሽሮአል፡፡ የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም ቢሆን በአንቀጽ 70 ስለባልና ሚስት ዕዳ በሚመለከት የተደነገገ በመሆኑ ሊባል የሚችለው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 የተቀመጠው ድንጋጌ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70 ተተክቶአል ነው፡፡ ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሃብት ፣ የግል ሃብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሃብታቸው እንደሚከፈል በተጠቀሰው አንቀጽ 70/1/ የተመለከተ ሲሆን ፣ ዕዳው የመጣው ለባልና ሚስቱ ትዳር ጥቅም ከሆነ ደግሞ ከጋራ ሃብታቸው ፣ የጋራ ሃብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሃብት እንደሚከፈል በንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጎአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ዕዳ በብድር የተወሰደው ባልናሚስቱ ለሚተዳደሩበት የንግድ ሥራ ማካሄጃ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው የተጠሪ ክርክር ዕዳውን ያመጣው ባለቤቴ ነው ከማለት ባለፈ የንግድ ሥራው የጋራ መተዳደሪያችን አይደለም የሚል አይደለም፡፡ በበኩላችን እንደምንገነዘበው ከአመልካች ባንክ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ የባልናሚስቱ የጋራ መተዳደሪያ ለሆነው የንግድ ሥራ እንዲውል የተወሰደ በመሆኑ የባልና ሚስቱ የጋራ ዕዳ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን ከወዲሁ ከዕዳው ነፃ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን የመክሰስ መብት የለውም በማለት በመ.ቁ 62817 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 102296 የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ክስ የቀረበበት ገንዘብ ብር 348,024.54 /ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሃያ አራት ብር ከሃምሣ አራት ሣንቲም/ የባልና ሚስቱ /የአቶ አደፍርሰው ዘውዴ እና የተጠሪ/ የጋራ ዕዳ በመሆኑ ተጠሪ ከዕዳው ነፃ የምትሆንበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ገንዘቡን ከነወለዱ ተጠሪ ከባለቤትዋ አቶ አደፍርሰው ዘውዴ ጋር በመሆን እንድትከፍል ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ ውሣኔው ዛሬ ታሕሣሥ 18 ቀን 2004 ዓ.ም በችሎት ተነገረ ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 70442

ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ በቀለ ቱፋ - ከጠበቃ ደጀኔ ታደሰ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ባዩሽ እሸቴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት የክስ ማመልከቻ መነሻ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው በባንክ ውስጥ ከገባው ገንዘብ ውስጥ በትዳር ጊዜ ወጥቶ ለአመልካች አባት ገንዘባቸው በአመልካች የተሰጠ ሆኖ እያለ እና በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ማዞሪያ አካባቢ የሚገኙ ሁለት የመኖሪያ ቤቶች የሶስተኛ ወገን ንብረቶች መሆናቸው ተገልፆ እያለ የጋብቻ ውጤቶች ናቸው ተብለው የጋራ ንብረቶች ናቸው በማለት አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ በሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ሲሉ አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ የጋራ ናቸው የሚሏቸውን ንብረቶች አይነታቸውንና ብዛቸውን በመለየት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያከራክሩት ንብረቶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መገናኛ ቅርንጫፍ በአመልካች ስም በነበረው የሂሳብ ቁጥር ውስጥ የነበረ ብር 455,485.00 (አራት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) እና በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ማዞሪያ አካባቢ የሚገኙት ሁለት መኖሪያ ቤቶች ሲሆኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በእነዚህ ንብረቶች ላይ የሰጡት መከላከያ መልስ ከጥሬ ገንዘቡ ውስጥ ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ከባንኩ በጋብቻ ጊዜ ወጥቶ የአመልካች አባት ንብረት በመሆኑ በአመልካች መሰጠቱንና በአጠቃላይ ገንዘቡ በትዳር ጊዜ የወጣ በመሆኑ አመልካች እንደማይጠየቁበት የሚገልጽ ሲሆን አሁን የሚያከራክሩትን ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ የአመልካች አባት ለልጅ ልጆቻቸው እንዲሆኑ የገዟቸው እንጂ የአመልካችና የተጠሪ የጋብቻ ውጤት ያለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ደግሞ ጥሬ ገንዘቡን አመልካች ያላግባብ መውሰዳቸውን በመግለጽ ለትዳር ጥቅም ያለመዋሉን ጠቅሰው እንዲሁም ቤቶቹ የጋራ ናቸው በማለት ተከራክረዋል፡፡ እነዚህን አከራካሪ ንብረቶችን በተመለከተ ክርክሩ በዚሁ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎ ንብረቶቹ የጋራ ስለሆኑ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም

ጥሬ ገንዘቡ የአመልካች አባት በመሆኑ ከባንክ በትዳር ጊዜ ወጥቶ በአመልካች የተወሰደ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ግማሹን ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተብሎ መወሰኑም ሆነ ቤቶቹን በተመለከተ የሶስተኛ ወገኖች ንብረቶች መሆናቸው ተገልጾ እያለ አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ መወሰኑ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎችን ከቤተሰብ ሕጉ ጋር ባላገናዘበ ሁኔታ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ ከባንክ ወጪ የተደረገን ብር እና በሶስተኛ ወገን ስም ያለ ንብረት ይካፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በአከራካሪ ንብረቶች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃውንና ሕጉን መሰረት ያደረገ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ የፈረሰው ጥቅምት 02 ቀን 2002 ዓ.ም. እንደሆነና እንደዚሁም ለዚህ ሰበር ችሎት ለቀረበው ክርክር ምክንያት የሆነው ጥሬ ገንዘብ ከባንኩ የወጣው መጋቢት 10፣14፣16 ቀን 2001 ዓ.ም. መሆኑን ነው፡፡ ከገንዘቡ ውስጥ አመልካች ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ከባንኩ በትዳር ጊዜ ያወጡት መሆኑን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ገንዘቡ የአመልካች አባት በመሆኑ ከባንክ አውጥተው ለአባታቸው የሰጡ በመሆኑና በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ/ም ስምምነት ሲደረግም ገንዘቡ ከባንክ ስለመኖሩ ሳይጠቀስ መታለፉ ገንዘቡ የጋራ ንብረት ያለመሆኑን ያሳያል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አለ የሚሉት የሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ/ም ስምምነት በግራ ቀኙ የንብረት ክርክር ላይ በታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው የማስረጃው ክብደት ተመዝኖ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ስለሚገልጽ ይህንን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የሚቀርበው የአሁኑ ክርክር የሚሆነው የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ከሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት በዚህ ችሎት የሚታይ ጉዳይ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ጉዳይ አይደለምና ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ሚያዚያ 23 ቀን 2000 ተደረገ የተባለውን ስምምነት መሰረት አድርገው ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ስምምነት ተቀባይነት ያጣበት ምክንያት በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል አይደለም ከተባለ በጋብቻ ውጤቱ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ብዛቱ ብር 455,485.00 (አራት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) የጋራ ስለመሆኑ ሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገው ስምምነት አልተገለጸም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ስምምነቱ በበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃነቱ ተመዝኖ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡ ሌላው አመልካች ጥሬ ገንዘቡን ከባንክ ማውጣታቸውን ሳይክዱ ለተጠሪ ላካፍል አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ገንዘቡ የሌላ ሰው በመሆኑ ከባንክ አውጥቼ ሰጥቼአለሁ የሚል

ነው፡፡ ነገር ግን ገንዘቡ ትዳሩ ጸንቶ ባለበት ጊዜ በአመልካች ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር የነበረና አመልካች ከባንኩ አውጥተው ለአባታቸው የሰጡት መሆኑ ያልተካደ ከመሆኑም በላይ ለትዳር ጥቅም ውሏል የሚል ክርክር አመልካች ያላቀረቡ በመሆኑ በትዳር ጊዜ የነበረ ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ ስለሆነ የአመልካች ክርክር ሕጋዊ መሰረት የለውም፡፡ አመልካች ገንዘቡን ለሌላ ሰው አሳልፈው መስጠታቸው እስካልተካደ ድረስ ገንዘቡ በትዳር ጊዜ ከባንክ በመውጣቱ ብቻ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ ግምት የሚወስድበትን አግባብ አመልካች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በትዳር ጊዜ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከወጣ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ ግምት የሚወስደው የጋራ ንብረትን ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠቱ የተረጋገጠበትን ሁኔታ ሁሉ ስላለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85-93 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነውና፡፡ በመሆኑም ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) አመልካች ከባንክ አውጥተው ለአባታቸው መስጠታቸውን ካለመካዳቸውም በላይ አመልካች የዚሁ ገንዘብ ባለቤት ናቸው የሚሏቸው አባታቸውም የገንዘቡ ባለቤት የሆኑበት አግባብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ግማሹን የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው ብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) የሚመለከት ሲሆን ይህ ገንዘብም ትዳሩ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከባንክ መውጣቱ ያልተካደ ሲሆን አመልካች ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለሌላ ሰው መስጠታቸውን አልገለፁም፡፡ በጋብቻ የተፈራ ገንዘብ ትዳሩ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ወጪ መሆኑ ከተረጋገጠ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 85-93 ካሉት ድንጋጌዎች አንጻር የሕግ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ በዚህ የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሆነ ወገንም ንብረቱ በጋብቻ ጊዜ የተሸጠ ወይም ጥሬ ገንዘብ ከሆነ በትዳር ጊዜ የወጣ መሆኑን ካስረዳ በቂ ሲሆን ሌላው ወገን ደግሞ ጋብቻው በፍቺ በፈረሰ ጊዜ ከንብረቱ የሽያጭ ገንዘብ ወይም የጋራ የሆነ ሌላ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል የሚገኝ መሆኑን ወይም ያላግባብ አንደኛው ተጋቢ ያባከነው መሆኑን በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካስረዳ የሽያጩ ገንዘብ ወይም ሌላ የጋራ የሆነ ጥሬ ገንዘብ በጋብቻ ጊዜ ለጋራ ጥቅም ውሏል የሚለውን የሕግ ግምት እንዳፈረሰ ይቆጠራል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ ምክንያት ከሆነው ጥሬ ገንዘብ ውስጥ ብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) በጋብቻ ጊዜ ከባንክ የወጣ መሆኑን በማስረዳት የሽያጩ ገንዘብ ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ ለወሰደው ግምት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪ ጋብቻው በፈረሰ ጊዜ ይኸው ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል በአመልካች እጅ እንደሚገኝ ወይም አመልካች ያላግባብ የወሰዱት ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ የሕግ ግምቱን ማፍረስ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች የብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) ግማሽ ለተጠሪ እንዲመልሱ የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከሩበት ነጥብ በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ዙሪያ አካባቢ ይገኛሉ የተባሉትን ሁለት መኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ነው፡፡ አመልካች እነዚህ ቤቶችን ለተጠሪ ላካፍል አይገባም የሚሉት ቤቶቹ የሌላ ሶስተኛ ወገን ንብረቶች ናቸው በሚል ነው፡፡ እነዚህ ሶስተኛ ወገኖች የሚባሉት ደግሞ ከአመልካችና ከተጠሪ አብራክ የተወለዱ ልጆች

ሲሆን ቤቶቹን ለእነዚህ ሕጻናት ገዙ የሚባሉት የአመልካች አባት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ቤቶቹ የጋብቻ ውጤት ያለመሆናቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ያላቀረቡ መሆኑን አረጋግጧል፣ በአመልካች ምስክሮችም ጭምር ያለመመስከሩንም ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ እንደዚሁም አመልካች የቤቶቹ ባለቤቶች የሚሏቸው ወገኖች ወይም በእነርሱ በሕጉ አግባብ የተወከሉ ሰዎች በሕጉ አግባብ ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡ በመሆኑም ቤቶቹ የሌላ ሶስተኛ ወገን ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ አመልካች ቤቶቹ የጋራ አይደሉም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በትዳር ጊዜ በጋራ የተገኘ እና የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ማናቸውም ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ መሆኑን ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 63(1) ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተሻሽሎ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71624 ሕዳር 15 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 103845 በ27/07/2003 በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ግማሽ ገንዘብና በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ዙሪያ አካባቢ የሚገኙትን ሁለት መኖሪያ ቤቶችን ለተጠሪ እንዲያካፍሉ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) አመልካች ለተጠሪ ሊያካፍሉ አይገባም ብለናል፡፡
4. በሌሎች ንብረቶች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 64371

ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ፍቅረ ዲን ሰይፈዲን - ጠበቃ ቴዎፍሎስ ክፍለ ወንጌል ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** 1- አበራ ለማ

2- ወ/ሮ ጋዲሴ ለማ ቀረበች

3- ወ/ሮ ጠጅቱ ለማ

4- ፍቃዱ ለማ

5- ወ/ሮ ገላዬ ለማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸምን መነሻ ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው አመልካች ሲሆን ፣ ክሱን የመሠረተው በ6-8-2001 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭ ውል በብር 30,000 ቤት ሸጠውልኛል ባላቸው ገላዩ ለማ እና በቀሉ ለማ በተባሉት ሰዎች ላይ ነው፡፡ በወቅቱ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ በውሉ መሠረት ይፈጸም በማለት ውሣኔ ሰጥቶ እንደነበር እና በኋላ ደግሞ የአሁኖቹ ተጠሪዎች መቃወሚያ በማቅረባቸው መዝገቡ እንደገና ተንቀሳቀሶ ክርክር መስማቱን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ያቀረቡት የሽያጭ ውል የተደረገበት ቤት የእኛም የውርስ ድርሻ ያለበት በመሆኑ ከእኛ ስምምነት ውጪ የተደረገው ውል ይፍረስልን በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ፣ የቀድሞውን ውሣኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን ፣ በመቀጠልም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም በወረዳው ፍ/ቤት ተቃዋሚ የነበሩት እነ አበራ ለማ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን ፣ ችሎቱም የሽያጭ ውሉን በማፍረስ ግራ ቀኝ ወገኖች ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን በማስቀረብ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ  በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር  አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካች ከእሱ ጋር የቤት ሽያጭ ውል አድርገዋል የሚላቸውን ሰዎች  የከሰሰው በሟች ወንድማቸው /አውራሻቸው/ ስም የሚገኘውን ቤት ስመሃብት እንዲያዛውሩለት ፤ ቤቱንም እንዲያስረክቡት እንዲወሰንለት ስለመሆኑ ለዚህ ሰበር ችሎት ከአቀረበው የአቤቱታ ማመልከቻ ጭምር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ያቀረቡት ሰዎችም የሟች ወንድምና እህቶች  እንደሆኑም  አላከራከረም፡፡ ተቃዋሚዎቹ መቃወሚያ ያቀረቡት ውሉ የተደረገበትን  ቤት ስመሃብት በአመልካች እንዲዛወር በማለት በተሰጠው ውሣኔ ላይ ቢሆንም፤ የጠየቁት ዳኝነት ግን ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤትም ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይፈርስም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ እንዳከራከረ እና በመጨረሻም ውሉ አይፈርስም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ የቀድሞውን ውሣኔ እንዳፀና ከሰጠው ውሣኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያሉት መቃወሚያ አቅራቢዎች ብቻ ናቸው፡፡ አመልካች የውሉ መፍረስ ወይም አለመፍረስን በሚመለከት ክርክር የሚደረግበት አግባብ ወይም ሥርዓት የለም በማለት የበኩሉን ይግባኝ አላቀረበም፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይፈርስም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ክርክሩን የሰማው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተፈጸመ የክርክር አመራር ስህተት  የለም፡፡ ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት የሚመረምረው ከዚህ አንፃር  እንጂ አመልካች መጀመሪያ አቅርቦት ከነበረው የውል ይፈጸምልኝ ወይም የስም ይዛወርልኝ ክስ አንፃር አይደለም፡፡

አመልካች የሽያጭ ውል አድርጌበታለሁ የሚለው ቤት ተመዝግቦ የሚገኘው በሻጮቹ ስም እንዳልሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ አመልካቹ ውሉን አደረግሁ የሚለው ሻጮች ሆነው የቀረቡት ሰዎች የቤቱ ባለሃብት /ሟች/ ብቸኛ ወራሾች እኛ ነን ብለውኛል፡፡ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትም አሳይተውኛል በማለት ስለመሆኑ ከሰበር አቤቱታ  ማመልከቻው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ እንደምንመለከተው ሻጭ የተባሉት  ሰዎች የሟች ወንድም እና እህት ከመሆናቸው ባለፈ በውርስ ሃብቱ ላይ ክፍፍል ስለመደረጉም ሆነ ቤቱ የውርስ ሃብት መሆኑ ቀርቶ ወደ ሻጮቹ ስለመዛወሩ አመልካች አላረጋገጠም፡፡ ውሉን ያደረገው  በዚህ መልክ ጥርት ያለ እና ግልጽ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ መሠረት በማድረግ /በመያዝ/ አይደለም፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ፈራሽ ነው ለማለት የቻለውም ቤቱ የወራሾች የጋራ ሃብት ነው በማለት ነው፡፡ በበኩላችንም እንደምናየው የሰበር ችሎቱ ከዚህ የተለየ መደምደሚያ ላይ መድረስ ነበረበት የምንልበት ምክንያት የለም፡፡

ውርሱ ወይም የውርሱ ሃብት የውርሱ አከፋፈል እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1060/1/ ተደንግጎአል፡፡ የጋራ ወራሾች የሆኑ ሰዎች ባልተከፋፈሉት የውርስ  ንብረቶች ላይ ያላቸው መብትም በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 8 ስለጋራ ባለሃብትነት፣ በአላባ ስለመጠቀም እና ስለሌሎች ግዙፍ መብቶች በማመላከት በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሚወሰን በዚሁ ቁጥር 1060/2/ ተመልክቶአል፡፡ በዚህ አግባብ የወራሾቹ ሁሉ የጋራ ሃብት የሆነውን ንብረት  ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፤ ወይም

በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1262 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን የተፈራረመው የጋራ ባለሃብት የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ስምምነት ሳያገኝ ነው፡፡ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረቡት ስምምነታቸውን ያልሰጡት ሌሎች የጋራ ባለሃብቶች በመሆናቸው ውሉ እንዲፈርስ በመወሰኑ ሕጉ በአግባቡ ተተርጉሞአል ነው ማለት የሚቻለው ፡፡ በመሆኑም አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የምንልበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 91762 ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 65708

ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አራጋው አበበ - ጠበቃ ደጉ መኮንን ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ራሔል ውብሸት - ጠበቃ ስንታየሁ በቀለ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት ግራቀኙ የጋራ እና የግል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በመስማት ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ፣ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በቃሊቲ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ ገላን ሳይት ላይ የሕንጻ ቁ.133 ሆኖ የቤት ቁ.GA-B/33/01/11 የሆነውን ኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ ብቻ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ሲያዝ በሌሎቹ ሀብቶች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት በመወሰኑ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች ያቀረቡ ሲሆን በቀን 14-6-2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ የተጻፈ የቅሬታ ፍሬ-ሃሳብ፡- በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 ድንጋጌ መሰረት ከጋብቻ በኂላ ያለግብይት በውርስ የተገኙ ንብረቶች በፍርድ ቤት እስካልተገለሉ ድረስ የጋራ ንብረቶች ናቸው በማለት ውሳኔ መሰጠቱ፣በስር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳባቸው የባልና የሚስት ንብረቶች የትኞቹ የግል የትኞቹ የጋራ እንደሆኑ ያስረዱልኛል ያልኳቸውን የሰው ምስክሮች እና በውርስ ንብረት ግምት የተገኘ ገንዘብ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት በትዕዛዝ ይቅረብልኝ ያልኩት የጽሑፍ ማስረጃ አስቀርቦ ሳይመለከት ከፊል ውሳኔ በማለት መወሰኑ፣በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.182(2) መሰረት ዳኝነት ሳይጠየቅ የንግድ ቤት ትርፍ አመልካች ከቤት ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ልታካፍላት ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ታዞ መልስ የሰጡ ሲሆን ሚያዚያ 3 ቀን 2003 ዓ.ም በሶስት ገጽ የሰጡት የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- አመልካች በውርስ ያገኘው ንብረት የጋራ እንደተባለ በማስመሰል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት ግን በውርስ ተገኘ የተባለውን ንብረት የጋራ ሀብት ነው በማለት ሳይሆን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ በውርስ ያገኘሁት ንብረት ለልማት ተብሎ ሲፈርስ መንግስት የሰጠኝ የካሳ ገንዘብ ነው ያለውን ሆኖ ነገር ግን ማስረጃ ያላቀረበበትን ገንዘብ የሚመለከት በመሆኑ፣ይህም ፍርድ ያረፈው በውርስ የተገኘን ንብረት

በሚመለከት ሳይሆን በውርስ ሀብት ምትክ ካሳ ሆኖ ተከፈለ በተባለው ጥሬ ገንዘብ ላይ በመሆኑ፣የውርስ ሃብት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ተገኘ የተባለውን ጥሬ ገንዘብ የግል ሀብቴ ነው በማለት ክርክር ማቅረብ የሚችለው ደግሞ በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58 መሰረት ንብረቱ የግል ይባልልኝ በማለት በፍርድ ቤት በማስገለል ብቻ በመሆኑ፣በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ያለው ገንዘብ ቀደም ሲል በተጠሪ ስም ከተከፈተ በኋላ በአመልካች ጉትጉታ በሁለታችን ስም የተደረገና በሁለታችን ጣምራ ፊርማ ብቻ የሚንቀሳቀስ የጋራ ሀብታችን በመሆኑ፣ በሌላ በኩል የሠሌዳ ቁ. 2-95871 የሆነን መኪና በውርስ ሀብት ግምት በተገኘ ገንዘብ የተገዛ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኪና በውርስ ነው ያገኘሁት የሚል ክርክር ያላቀረቡ በመሆኑ፣መኪናውም ጋብቻችን ጸንቶ በነበረበት ወቅት በግብይት የተገኘ በመሆኑ እና የግል ስለመሆኑም በፍርድ ቤት የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 58 በሚያዘው መሰረት ያላስወሰነ በመሆኑ እየቀረበ ያለው ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ፣የንግድ ቤትን ትርፍ በተመለከተም ባቀረብኩት የጋራ ሀብት ዝርዝር ውስጥ የጋራ ሀብታችን ነው በማለት ካቀረብኳቸዉ መካከል አንዱ እና ዋነኛዉ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከታያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች በውርስ ያገኘሁት ንብረት በልማት ምክንያት ፈርሶ ካሳ የተከፈለኝ ነው ያለውን ገንዘብ የጋራ ሀብት ነው የመባሉን አግባብነት እና ሌሎችንም ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች ለመመርመር በሚል በመሆኑ የተያዘው ጉዳይ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በግራቀኙ መካከል አከራካሪ የነበሩ እና ውሳኔ ያገኙ እንደዚሁም በበታች ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ በርካታ የፍቺ ውጤትን የሚመለከቱ የሀብት ክርክር ያለ ሲሆን በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት እያከራከረ ያለው እና የዚህን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሚያሻው አመልካች የውርስ ሀብትን መሰረት ባደረገ የካሳ ክፍያ አገኘሁት የሚሉት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የሚገኝ ብር 276,320 (ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ብር)፣ አመልካች ከዚሁ የውርስ ሃብት ከተገኘ ካሳ ገንዘብ ላይ ቀንሼ የገዛሁት ተሽከርካሪ ነው የሚሉት የሠሌዳ ቁ.2-95871 አ.አ. የሆነው እና ከንግድ ቤት የሚገኝን ገቢ በተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የንግድ ቤት ትርፍ በተመለከተ ተጠሪ በግልጽ ዳኝነት ባልጠየቁበት ሁኔታ መወሰኑ አግባብነት የለውም በማለት በአመልካች የቀረበውን ክርክር ስንመለከት ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በግልጽ ዳኝነት የጠየቁበት ስለመሆኑ ከመከራከራቸውም በላይ በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት ከንግድ ድርጅቱ የሚገኘውን ገቢ ከቤት ከወጣሁበት ቀን ጀምሮ ልካፈል ይገባል በማለት ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ዳኝነት ሳይጠየቅበት የተወሰነ ነው በማለት ከፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.182(2) አኳያ የተነሳው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ያነሱት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ሌላው የውርስ ሀብት መሰረት ባደረገ የካሳ ክፍያ የገዛሁት ተሽከርካሪ ነው በማለት አመልካች የሚያነሱትን ክርክር በተመለከተ ተሽከርካሪው ግራቀኙ በጋብቻ ተሳስረው ባሉበት ወቅት የተገዛ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ መኪናው በጋብቻ ወቅት የተገዛ ከሆነ ደግሞ በቤተሰብ ህጉ በግብይት ስለተገኙ ሀብቶች በሚመለከት ድንጋጌ የሚገዛ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.

የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58 መሰረት ባልና ሚስት ከተጋቡ በኂላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘዉ ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል በማለት በንኡስ አንቀጽ አንድ ስር ሲደነግግ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ስር ደግሞ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤት ሲያጸድቀው ብቻ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተሽከርካሪው የግሉ እንዲባልለት ለፍርድ ቤት በማቅረብ ያጸደቀ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች በህጉ በተቀመጠው መሰረት በፍርድ ቤት በጋብቻ ወቅት የተገዛው ተሽከርካሪ የግላቸው እንዲባልላቸዉ አቅርበው ያስወሰኑት ነገር በሌለበት ሁኔታ በዚህ የፍቺ ውጤት ክርክር ላይ የግል ሀብት ነው በማለት ያነሱት ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ብለናል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ወቅት የተገዛውን የሠሌዳ ቁ.2-95871 አ.አ. የሆነው ተሽከርካሪ የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ አለ የተባለውን ገንዘብ በተመለከተ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ አመልካች ከበታች ፍርድ ቤቶች ጀምሮ እየተከራከረ ያለው ገንዘቡ የተገኘው በውርስ የተላለፈልኝ ንብረት በልማት ምክንያት በመፍረሱ የተነሳ የተከፈለኝ ካሳ ነው በማለት ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ገንዘቡ የጋራችን ነው፣ቀደም ሲል በራሳቸው ስም የተከፈተ እና በኂላ ግን በአመልካች ጉትጎታ በሁላታችን ፊርማ ብቻ እንዲንቀሳቀስ ያደረግነው የጋራ ሀብታችን ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ አመልካች በበታች ፍርድ ቤት ይሄንን ያስረዱልኛል የሚሉትን ማስረጃዎች እንደቆጠሩና ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል በፍርድ ቤት ውሳኔ ያላስገለልክ በመሆኑ የሚያመጣው ለወጥ የለም በማለት ያለፏቸው ስለመሆኑ በቅሬታቸው አመላክተዋል፡፡ ችሎቱም በዚህ ነጥብ ላይ የተነሳውን ክርክር እንደመረመረው አመልካች በተጠቀሰዉ ንግድ ባንክ አለ የሚሉት በቀጥታ ከውርስ ሀብቱ የካሳ ክፍያ የተገኘ ነው በማለት በመሆኑ በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58 መሰረት በጋብቻ ወቅት በግብይት እንደተገኘ ንብረት በመቁጠር ቀደም ሲል የግልህ ስለመሆኑ ያላስገለልክ በመሆኑ በማስረጃ እንዲጣራ የሚፈቀድበት አግባብ የለም መባሉ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አመልካች እየተከራከሩ ያሉት በግብይት ስለተገኘው ሀብት ሳይሆን በቀጥታ ከውርስ ሀብቶች ለልማት ተብሎ በመፍረሱ ምክንያት ከተከፈለኝ ካሳ የተገኘ ነው በማለት በመሆኑ በግብይት ስለተገኙ ንብረቶች በሚመለከት በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 58 ስር የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡ የአመልካች ክርክር የሚሸፈነው ከጋብቻ በኂላ በዉርስ በግሉ ያገኘው ወገን የግል ንብረቱ ሆኖ ይቀጥላል የሚለውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ በመጥቀስ አከራካሪ የሆነው ገንዘብ የውርስ ሀብት ስለመሆን ወይም አለመሆን አመልካች የማስረዳት መብት እንደሌለው በመቁጠር መታለፉ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ አመልካች በዚህ ነጥብ ላይ ለማስረዳት ማስረጃ የቆጠረ ስለመሆኑ በቅሬታውም ያመላከተ ከመሆኑም በላይ በበታች ፍርድ ቤቶችም የተጠየቀ እና ፍርድ ቤቶቹ ቀድሞ በፍርድ ቤት የግሉ ስለመሆኑ ባላስወሰነበት ሁኔታ የማስረጃዎቹ መሰማት የሚያመጣው ለውጥ የለም በማለት የታለፈ ስለመሆኑ ከውሳኔው መረዳት ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ አለ የተባለው ጥሬ ገንዘብ የግል ሀብት ወይም የጋራቸዉ ሀብት

ስለመሆን ወይም አለመሆን ግራቀኙ ባላቸው ማስረጃ ሊያጣራ ሲገባ ሳያጣራ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡ አመልካች ገንዘቡ የግል ስለመሆኑ ለማስረዳት የቆጠራቸውን ምስክሮች እና እንዲቀርቡለት የጠየቃቸውን የጽሑፍ ሰነዶች በመስማት እና በማስመጣት እንደዚሁም የተጠሪን የማስተባበያ ማስረጃ በመስማት እና ፍርድ ቤቱም ለፍትሕ አሰጣጥ ተገቢ ነው የሚለውን ማስረጃ በመስማት ውሳኔ መስጠት ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የቤተሰብ ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ማለፉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የተፈጸመውን ስህተት ሳያርም ማለፉ ትክክለኛ አካሄድ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠቀሰው የንግድ ባንክ ያለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ ተገቢዉን ማጣራት ሳያደርጉ የደረሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌደ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 103132 በቀን 7-6-2003ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 78970 በቀን 7-4-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት አከራካሪ በሆኑት የሠሌዳ ቁጥሩ 2-95871 አ.አ. የሆነ እና የንግድ ድርጅት ገቢን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.103132 በቀን 7-6-2003ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 78970 በቀን 7-4-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. በጋብቻ ወቅት በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ካልተወሰነ በስተቀር የጋራ ሀብት ነው ተብሎ መወሰኑ እና ከጋራ የንግድ ድርጅት የተገኘ ገቢ የጋራ ነዉ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት እና ለፍትሕ አሰጣጡ አስፈላጊ ነው የሚለውን ማስረጃ በመስማት ገንዘቡ የጋራ ወይም የግል ስለመሆኑ በተመለከተ ተገቢዉን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ በዚህ ችሎት ውሳኔ ካገኙት ዉጪ ያሉትን በተመለከተ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አልተነካም፡፡
5. በዚህ ችሎት በቀን 25-6-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ የሠሌዳ ቁ. 2-95871 አ.አ. የሆነውን ተሽከርካሪ እና የንግድ ቤቱን ገቢ በተመለከተ ጉዳዩ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተነስቷል፡፡
6. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 69657

የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐምዚያ ሼክ ኢብራህም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ ኡስማኤል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክስ የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ የአመልካች ባለቤት በነበረው በአቶ ዳውድ ዩሱፍ ላይ ያስፈረደውን ገንዘብ ለማስፈጸም ሲንቀሳቀስ በአወዳይ ከተማ የሚገኘውንና አመልካች የግሌ ነው በምትለው መኖሪያ ቤት ላይ እንዲፈጸም በመታዘዙ፣አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ለተመለከተው በኦሮሚያ ብሔ/ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ሆና በመከራከር በዚህ ንብረት ላይ ሊፈጸም የማይገባ ስለመሆኑ ትዕዛዝ ያሰጠች ሲሆን፣ተጠሪ በበኩሉ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረብ እና ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የአመልካች ግማሽ ድርሻ ሳይነካባት በፍርድ ባለዕዳው ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲፈጸም ያዘዘ በመሆኑ እና የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም ይሄንኑ ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት በማመልከቷ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በቀን 06-10-2003 ዓ.ም በሶስት ገጽ በተጻፈ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች በማንሳት ያቀረበች ሲሆን ፍሬ-ሀሳቡ፡-አመልካች እና የፍርድ ባለዕዳ እ.ኤ.አ. በ1993 ወይም በ1985 ዓ.ም የነበረንን ጋብቻ በሀሮማያ ወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.815 ከፈረሰ በኋላ እ.ኤ.አ. በ24-5-94 ወይም በ1986ዓ.ም 4 የሀገር ሽማግሌዎች መርጠን በተፈራረምነው የንብረት ክፍፍል ውል የአሁን አመልካች የአቶ ዳውድ ዩሱፍ ድርሻ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሰጥቼ አሁን አፈጻጸም የቀረበበት ቤት ድርሻዬ ሁኖ ከ1986ዓ.ም. ጀምሮ የግሌ ሆኖ ስጠቀምበት የቆየሁ ስለመሆኑ በተረጋገጠበት፣የፍርድ ባለዕዳ እና የፍርድ ባለመብት የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ውል የተፈራረሙት ጋብቻችን ከፈረሰ እና ንብረት በሽማግሌዎች ከተከፋፈልን ከበርካታ ዓመታት በኋላ በ1993 ዓ.ም ስለመሆኑ ግልጽ ሁኖ እያለ፣በፍርድ ባዕዳው እና በፍርድ ባለመብት መካከል በተፈራረሙት የመኪና ግዥ እና ሽያጭ ውል ላይ ሳልፈርም እና ንብረታችንን ቀደም ሲል ተከፋፍለን የተለያየን ስለመሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ በንብረቴ ላይ አፈጻጸም እንዲቀጥል መባሉ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ ለዕዳው መክፈያ እንዲውል የታዘዘው ቤት አሁንም በፍርድ ባለዕዳ ስም ያለ

በመሆኑ፣የአመልካች የግል ንብረት ስለመሆኑ ያቀረባቸው አንድም ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ፣በፌዴራል የቤተሰብ ህጉም የንብረት ክፍፍልን የማጽደቅ ስልጣን ያለው ሽማግሌዎች ሳይሆኑ ፍርድ ቤት ብቻ ስለመሆኑ ስለሚደነግግ፣ይፈጸም የተባለውም በራሷ ድርሻ ሳይሆን በፍርድ ባለዕዳው ድርሻ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ የአመልካች ትዳር በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ባለቤታቸው በገቡት ዕዳ መነሻ ቀደም ሲል በክፍፍል ለአመልካች በደረሰ መኖሪያ ቤት ላይ ሊቀጥል ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች እና በፍርድ ባለዕዳው አቶ ዳውድ ዩሱፍ ጋር ያላቸው የጋብቻ ግንኙነት በፍቺ የፈረሰበትን ጊዜ በተመለከተ አመልካች በዚህ የሰበር አቤቱታቸው ላይ እ.ኤ.አ. በ1993 ነው በማለት ያቀረቡ ሲሆን በበታች ፍርድ ቤቶች ግን አመልካችም ራሳቸው ሲከራከሩ የነበሩት በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰው በቀን 16-8-1993ዓ.ም በመዝ.ቁ.815 በኦሮሚያ ወረዳ ሸሪአ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ እና የበታች ፍርድ ቤቶችም በፍሬ-ነገር ያረጋገጡት ነጥብ ይሄው በመሆኑ በዚህ የሰበር ሰሚ ደረጃ አመልካች ያነሱትን ክርክር ችሎቱ የሚቀበለው ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡

በዚሁ የክርክር ሂደትም በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች አመልካች እና የፍርድ ባለዕዳ አቶ ዳውድ ዩሱፍ በጋብቻ ተሳስረው የኖሩ ስለመሆኑ፣በግራቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻም በቀን 16-8-1993 ዓ.ም በወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍቺ የፈረሰ ስለመሆኑ፣የጋብቻ ፍቺ ውጤትን በተመለከተ ግራቀኙ ስምምነት ያደረጉ ሆኖ በፍርድ ቤት ግን ቀርቦ ያልጸደቀ ስለመሆኑ፣ እስከ አሁን ድረስም አከራካሪው ቤት በፍርድ ባለዕዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና በስሙም ግብር የሚከፈልበት ስለመሆኑ የተመለከቱት ነጥቦች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የፍርድ ባለዕዳ አቶ ዳውድ ዩሱፍ ለአሁኑ ዕዳ ምክንያት የሆነውን እና በባንክ ዕዳ ተይዞ እያለ ለአሁን ተጠሪ ሸጦታል የተባለውን ተሽከርካሪ የሸጠው በቀን 26-4-1993ዓ.ም ስለመሆኑ፣ለአሁን አፈጻጸም ምክንያት የሆነውን ዕዳ ተጠሪ በፍርድ ባለዕዳው ላይ ያስፈረደው ደግሞ በቀን 18-7-1995ዓ.ም ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በፍሬ-ነገር የተረጋገጡትን ነጥቦች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት ለአሁን ዕዳ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ የተገዛው በአመልካች እና በፍርድ ባለዕዳ መካከል የነበረው ጋብቻ ከመፍረሱ ከአራት ወራት በፊት በመሆኑ፣ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለዕዳው አቶ ዳውድ ዩሱፍን በዚሁ የተሽከርካሪ ግዢ ምክንያት በመክሰስ ያስወሰነበት በአመልካች እና በአቶ ዳውድ ዩሱፍ መካከል የነበረው ጋብቻ በፈረሰ በ2ኛ ዓመቱ በቀን 18-7-1995ዓ.ም. ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን የፍቺ ውጤትን በተመለከተ በህግ ተቀባይነት ያለው ህጋዊ ክፍፍል ስለመፈጸም ወይም አለመፈጸም በተመለከተ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ክርክር ነጥብ ላይ አመልካች አጥብቃ የምትከራከረው በሸሪአ ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሽማግሌዎች ዕርቅ በማድረግ የፍርድ ባለዕዳውን የአቶ ዳውድ ዩሱፍ ድርሻ በተመለከተ 200000 ብር /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በመክፈል አከራካሪውን

ቤት የግሌ አድርጌዋለሁ በሚል ነው፡፡ ሆኖም የተደረገው የፍቺ ውጤት ስምምነት ምን ያህል የህግ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.69/1995 እና 83/1996 አንቀጽ 110/5/ እንደዚሁም የፌ/የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ213/92 አንቀጽ 83/3/፣117 ስር በግልጽ እንደተደነገገው የፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሙያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሳኔው ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ፣ፍቺን እና የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት እና የማጽደቅ ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ስለመሆኑ እና ሌላ ማንኛውም አካል በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠትም ሆነ የማጽደቅ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ አስገዳጅ በሆነ ቃል ተቀምጧል፡፡ በዚህም ጉዳይ አመልካች በስምምነት የንብረት ክፍፍል ያደረጉ ስለመሆናቸው ክርክር ያቀርቡ እንጂ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የጸደቀ ወይም የተወሰነ ስለመሆኑ ያነሱት የክርክር ነጥብ የሌለ ከመሆኑም በላይ በዚህ ነጥብ ላይ የተሰጠ ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤት በፍሬ-ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ አንድ የፍቺ ውጤት ደግሞ በህጉ አግባብ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እስካልጸደቀ ድረስ በሽማግሌዎች ፊት የተደረገ የንብረት ክፍፍል ስምምነት መኖሩን በማመላከት መከራከሪያ ማድረግ የማይቻል እና ህጉም ለእንደዚህ ዓይነት ስምምነት ጥበቃ የማያደርግ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከቱት የድንጋጌዎቹ ዓላማ፣ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የአፈጻጸም ሂደት የአመልካች ግማሽ ድርሻ ሳይነካ በፍርድ ባላዕዳው ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀጥል መባሉ የሚነቀፍበት አግባብ የለም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ሂደት የአመልካችን ግማሽ ድርሻ ሳይነካ በፍርድ ባለዕዳው በአቶ ዳውድ ዩሱፍ ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀጥል በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.125214 በቀን 23-9-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.93945 በቀን 26-5-2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው አፈጻጸም የአመልካችን ግማሽ ድርሻ ሳይነካ በፍርድ ባለእዳዉ ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀጥል መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ሰኔ 06 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 67924

መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ምንያ ገ/ሥላሴ - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች** ፡- ወ/ሪት መሠረት ዓለማሁ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ ተጋቢዎች ለረዥም ጊዜ ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ይህ የትዳር ግንኙነት ተቋርጧል የሚባለው እንዴት ነው? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ አስመልክቶ የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ የሰጠውን ዳኝነት ከዚህ ቀደም በዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ የህግ ጥያቄ አስመልክቶ ከሰጠው ትርጉም ጋር በማገናዘብ አግባብነቱን ለመመልከት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚስትነታቸውን የሚያረጋግጥ ውሳኔ ካገኙ በኋላ የአሁን ተጠሪ የሟች ልጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ይኸው ውሳኔ መብታቸውን እንደሚነካ በማስረዳት የክርክር ተካፋይ ከሆኑ በኋላ አመልካችና ሟች አባቴ በህግ በታወቀ የጋብቻ ሥርዓት ግንኙነት አልመሰረቱም፤ ጋብቻ አለ እንኳ ቢባል አመልካች ከአስር ዓመታት በላይ ኑሯቸውን ውጭ አገር አድርገው ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ ጋብቻው ፈራሽ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን እንደገና አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በአመልካችና በሟች መካከል የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በሁኔታ ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳ አመልካችና ሟች ጋብቻቸው ባለበት ጊዜ በተለያየ ሀገር ተለያይተው መኖራቸው ቢታወቅም ጋብቻቸውን ቀሪ አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ አንቀጽ 55 እንደተመለከተው ተጋቢዎች በስምምነት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው መኖር እንደሚችሉና መብታቸው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የሟች ሚስት ናቸው በማለት የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሳኔ ሊሰረዝ የሚችል አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የአ/አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአሁን አመልካችና ሟች የጋብቻ ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ተቀብሎ፤ ነገር ግን ሁለቱም ለ18 ዓመታት ያህል ተለያይተው

በመኖራቸው ምክንያት የቀጠለ የትዳር ግንኙነት እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 31891 ለረዥም ጊዜ ተለያይተው ከኖሩ፣ በዚህም ጊዜ ውስጥ የባልና ሚስት ዓይነት ግንኙነት ያልነበራቸው ሰዎች ሚስትነት ወይም ባልነት ተረጋግጦ ማስረጃ ሊሰጣቸው እንደማይችል ያመለከተ ሲሆን በሌሎች የሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቦችም ተመሳሳይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ሟችና የአሁን አመልካች ለ18 ዓመት ተለያይተው የኖሩና በዚህም ጊዜ ውስጥ የትዳር ግንኙነታቸው ባቋረጡበት ሁኔታ የአሁን አመልካች ሚስት ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ሆኖ አልተገኘም በሚለው ትችቱ መነሻ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የአ/አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይኸው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም በማለት የአሁን ተጠሪን አስቀርቦ ሳያከራክር መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ይህንኑ ሲመስል ግራ ቀኙ ከዚህ ቀደም በስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር በሰበር ደረጃ የፅሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል እንደመረመርነውም የአሁን አመልካችና የተጠሪ አባት ሟች የጋብቻ ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጡት ዳኝነቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው ይህ የጋብቻ ግንኙነትታቸው ሁለቱም ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ተቋርጧል ወይስ አልተቋረጠም በሚለው ጭብጥ ስር የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው እና የሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔዎች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አከራካሪ ነጥብ ስር በሌሎች ወገኖች ክርክር መነሻ የሰጠውን ትርጉም መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

የአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ምንም እንኳ የአሁን አመልካችና ሟች በተለያየ ሀገር በመኖራቸው በኑሮ የተለያዩ ቢሆኑም የጋብቻ ግንኙነታቸው ግን ሳይቋረጥ የዘለቀ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ውሳኔ የሰጠው በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡትን የሰው እና የተለያዩ የሰነድና ገላጭ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በአኳያው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነት መቋረጡን አረጋግጫለሁ ያለው በአመልካች በኩል በቀረበው የሰነድ እና ገላጭ ማስረጃ ሆኖ የቀረበውን በቪዲዮ የተቀረፀውን ምስል ብቻ ምርኩዝ አድርጐ የማስረዳት ብቃቱን በመመዘን እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ አስረጂ ነው፡፡ ይኸውም የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦ ከተመለከተውና ለውሳኔው መነሻ አድርጎ ከያዘው ማስረጃ መካከል፣ በአመልካች አማካኝነት የቀረቡት የደብዳቤ ልውውጦችና ፍቶግራፎች ተጠሪዋ የአሁኑ አመልካች በውጭ ሀገር በነበረችበት ጊዜ ከሟች ጋር የነበራት ግንኙነት አለመቋረጡን ያመለክታል፣ የወረዳ 19 መረዳጃ እድር የቀረበው መግለጫ ሟች እና የአሁን አመልካች በባልና ሚስት መመዝገባቸውን አረጋግጦ በመላኩ፣ የቀረበውም የቪዲዮ ፊልም የአሁን አመልካች ከውጭ ሀገር ለሟች በምትልከው ገንዘብ ሟች ቤቱን እየሰሩ መሆኑን በማረጋገጥ የደረሰበትን ውጤት ለባለቤታቸው ለአሁን አመልካች ለመግለፅ መልዕክቱን ለመላክ የተቀረፀ ሲሆን ከዚሁ ምስል ሟች ከአሁን አመልካች ጋር የትዳር ግንኙነታቸው ያልተቋረጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል በሚል የማስረጃውን አግባብነትና ሚዛን የመረመረበትን ክፍል ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት ከዕድር የመጣው ማስረጃ የዕድሩ ማህተምም ሆነ ቁጥር የሌለው በመሆኑ ተአማኒነት ያለው ነው ብሎ ለመቀበል የሚቻል አይደለም፣ የግል ደብዳቤዎችና ፍ/ቤቱ የተመለከተው የቪዲዮ ማስረጃ የትዳር ግንኙነቱ ስለመቀጠሉ የሚያመለክት ነገር የሌላቸውና

እምነት የሚጣልባቸው ማስረጃዎች አይደሉም፡፡ ለሚች 40 ቀን መታሰቢያ የታተመው የጥሪ ወረቀትም በማንኛውም ጊዜ ሊታተም የሚችል በመሆኑ ታማኝነት ያለው አይደለም የሚለውን ትችት በመስጠት ከጋብቻ የመነጨው ግንኙነት ስለመቀጠሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

በእርግጥ ይህ በፍሬ ነገርና ፍሬ ነገርን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃ ታማኝነት የመመርመርና የማስረዳት አቅሙን የመመዘን ሥልጣኑ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንጂ ለዚሁ የሰበር ሰሚ ችሎት በህግ የተሰጠው ሥልጣን ባለመሆኑ በዚህ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማስረጃ አመዛዘን ረገድ የሰጠውን ዳኝነት እንደገና ለመመርመርና፤ አግባብነቱን ለማየት የሚቻል አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ በአሁን አመልካችና በሚች መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነት በመኖሪያ ቦታ መለያየት የተነሳ ሳይቋረጥ ግንኙነቱ እንዳለ፤ እንደቀጠለ ነበር በማለት የአሁን አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ እና የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ለሰጠው ውሳኔ ምርኩዝ አድርጎ የያዘው ማስረጃ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ ትችት ባሳረፈበት የሰነድ እና ገላጭ ማስረጃዎች ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ የሚች እህት የሆኑትን እና የሚች ጐረቤትን የምስክርነት ቃል ሁሉ የያዘ ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የምስክርነት ቃል ውስጥ ሁለቱም በአካባቢው በእድር፣ እና በቤት ስራ ማህበር በባልና ሚስትነት እንደሚታወቁ፤ ሚች ሥራ ስላልነበራቸው ተጠሪዋ የቤተሰባቸውን ኑሮ ለመለወጥ ከባለቤታቸው ጋር ባደረጉት ስምምነት ወደ ውጭ አገር ሄደው ሥራ በመስራት በሚልኩት ገንዘብ ቤት መስራታቸውን ሚችም ሲታመም ገንዘብ በመላክ ታስታምመው እንደነበር እስከ ሚች ዕለተ-ሞት በትዳር ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ በመግለጽ ያረጋገጡበት ይገኝበታል፡፡

ስለዚህ የሰው ማስረጃ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያለው የለም፡፡ ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ከማስረጃው አግባብነት ተቀባይነት እና የማሳመን ብቃት አንጻር በማየት የማይቀበለው ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሳይመለከተው የቀረ ካልሆነ በቀር ክርክርን በማስረዳት የቀረበን የተከራካሪ ወገን ማስረጃ በዘፈቀደ ውድቅ ማድረግ እንደማይችል ስለማስረጃ አቀባበል በተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 257፣ 258 እና 259 ተመልክቷል፡፡ ይህም የተከራካሪ ወገንን የመደመጥ መብት ለማስከበር ሲባል የተዘረጋ ሥርዓት ነው፡፡ እንዲሁም የበታች ፍ/ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤ የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መስጠት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 በተመለከተው የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት ተደንግጓል፡፡ የበላይ ፍ/ቤትም ይህ ዳኝነት የፍርድ አፃፃፍ ስህተት የማስረጃ አቀባበል ሥርዓት ጉድለት መፈፀሙን የሥር ፍ/ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ የሚያስረዳና ሳይመረመርና ሳይታይ የታለፈው የማስረጃ ይዘት በመዝገቡ ላይ ሰፍሮ ከተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 242 መሰረት በዚሁ የመዝገብ ግልባጭ ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊውን ዳኝነት መስጠት እንደሚቻልም ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካችና የሚች የጋብቻ ግንኙነት ሳይቋረጥ እስከ ሚች ዕለተ ሞት ድረስ ግንኙነት የቀጠለ ስለመሆኑ የሥር የአ/አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰው ማስረጃ ያረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ይህም ከሆነ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎምና አፈጻጸም ማስፈን ይቻል ዘንድ እንደ አንድ ስልት ተቀጥሮ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 454/97 ድንጋጌ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው የሰጡት የህግ ትርጉም በበታች ፍ/ቤቶች የአስገዳጅነት ኃይል ወይም ባህርይ

የሚኖረው ትርጉም በተሰጠበት እና ዳኝነት እንዲሰጥበት በቀረበው ጉዳዮች መካከል የተነሳው የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የተመሳሰለ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት የተጠቀሰውንና አስቀድሞ ትርጉም የተሰጠበትን በሰበር መ/ቁ 31891 የተሰጠውን ውሳኔ ማየት እንደሚቻለው ሁለቱም ለ12 ዓመታት ተለያይተው እንደኖሩ ተጠሪም በውጭ ሀገር በመኖር ላይ እንዳለች ሌላ ባል አግብታ ትኖር እንደነበር በክርክር ደረጃ የቀረበው ሳይጣራ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ለሰጠው ዳኝነት እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በደፈናው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም በሰጠባቸው "ሌሎች መዝገቦች" የሚለው አገላለጽ በሰበር መ/ቁ 14290፤ 20938 የተሰጠውን ለመጥቀስ ተፈልጐ ከሆነም ተለያይተው የኖሩ ተጋቢዎች በየፊናቸው የየራሳቸውን ህይወት ስለመጀመራቸው ሚች ሌላ ሚስት አግብተው ስለመኖራቸው ተረጋግጦ መሆኑ ሁሉ ታይቶ ትርጉም የተሰጠበት ስለሆነ በፍሬ ነገር ረገድ በአሁን አመልካች በምንያ ገ/ስላሴ እና ተጠሪ ወ/ሪት መሰረት ዓለማየሁ መካከል ከተነሳው ክርክር ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ የሚመሳሰል ባለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሰረት ታይቶ ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃ አቀባበል ሥርዓትና ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አፈጻጸም ረገድ አንጻር ሲታይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውንም ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ 14194 በ26/2/2003 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ፤ በአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14801 በ20/7/03 ዓ.ም. በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1706/00 በቀን 6/11/2002 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
   ይህ የሰበር ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 72420

ሚያዝያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኬሪያት ያህያ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** ሐጂ ጅሀድ ኡመር በሌለበት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ አመልካች ባቀረበችው ክስ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ በጅማ ዞን የሸሪአ ፍርድ ቤት የፈረሰ መሆኑን፣ ከፍቺ በኋላ የጋብቻ ውጤትን በተመለከተ ግን በመደበኛ ፍርድ ቤት የመጠየቅ መብት ተጠብቆልኝ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ ድርሻዬን እንዲሰጠኝ በሚል ነው፡፡ ተጠሪም መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ለዚሁ የወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ውሳኔ መስጠት ያለበት የፍቺ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ራሱ ስለመሆኑ በማመልከት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ድጋሚ ሊታይ አይገባውም በሚል የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የክልሉ የወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ቀደም ሲል የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ክስ ቀርቦ ማየት ያለበት የፍቺ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ነው በማለት ይሄው ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ሊቀርብ አይገባም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.5 እና 245/2/ መሰረት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይሄው ውሳኔ በክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበችው አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች ያነሳች ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- በመካከላችን የነበረው ጋብቻ በጅማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከፈረሰ በኋላ የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድርሻዬን እንዲሰጠኝ ክስ አቅርቤ ውሳኔ የሰጠበት ሁኖ ተጠሪ ውሳኔው ላይ ይግባኝ በመጠየቁ የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ለመመልከት ስልጣን የለውም በሚል ውሳኔውን በመሻር ክሱን ግን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የማቅረብ መብቴን ጠብቆልኛል፡፡ በዚሁ

መሰረት ለጅማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቤ ስከራከር ከቆየሁ በኋላ ጉዳዩን ለማየት አልችልም በማለት ውሳኔ በመስጠቱ ምክንያት ለከተማው የወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ክስ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ ከዚህ በፊት የተመለከትኩት ነው በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የቀረበውን የፍቺ ዉጤት ክርክር ውድቅ ማድረጉ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ ፍትሕ የማግኘት መብቴን ያጣበበ ነው በማለት እንዲታረምላት ጠይቃለች፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ያቀረበችው የፍቺ ውጤት ክስ የሸሪዓም ሆነ የመደበኛ ፍርድ ቤት በመመልከት ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው መታለፉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት ፍትሕ ከማግኘት መብት አኳያ ለመመርመር በሚል ያስቀርባል በመባሉ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ ጉዳዩ ለውሳኔ አድሮአል፡፡

ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተቋጨ ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የፍቺ ውሳኔ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ አሁን እያከራከረ ያለውን የፍቺ ውጤት መመልከት ያለበት የትኛው ፍርድ ቤት ነው የሚለው ነጥብ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ በእርግጥ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 78/5/ መሰረት ለሚቋቋሙት የሐይማኖት ፍርድ ቤቶች እውቅና እንደተሰጠ እና እንደሚደራጁ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አግባብ በተቋቋሙት የሐይማኖት ፍርድ ቤቶች የተከራካሪ ወገኖችን ፈቃደኝነት መሰረት በማድረግ ሊዳኙ እንደሚችሉ በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34/5/ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኙ ጉዳያቸውን ለሸሪዓ ፍርድ ቤት በማቅረብ የፍቺ ውሳኔ ያገኙ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ግን አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት በመደበኛ ፍርድ ቤት መጠየቅ እንድችል መብቴን ጠብቆልኝ አሰናብቶኛል በሚል ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበች ስለመሆኑ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ የፍቺ ውጤትን ተመልክቶ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ የሰጠው ነው በማለት ያልተቀበሉት መሆኑን፣ ጉዳዩን ለተመለከተው የሸሪዓ ፍርድ ቤት የፍቺ ውጤቱን በተመለከተ ክስ ያቀረበች ስለመሆኑ፣ ሁኖም ግን የፍቺ ውሳኔ የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልካች በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀድሞ ክስ ማቅረባቸው በዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ያመላክታል በማለት አናስተናግድም በሚል መዝገቡን የዘጉት ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው ቀድሞ የፍቺ ውሳኔ የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል ያለውን የፍቺ ውጤት በተመለከተ ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት ያልፈለገ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት መዝገቡን ስለመዝጋቱ መመልከት ይቻላል፡፡ የፍቺውን ውሳኔ የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት የንብረት ክፍፍሉንም በተመለከተ እልባት ይሰጣል ተብሎ ቢገመትም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ይሄንን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ለመደበኛ ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ መብት በመጠበቅ መዝገብ ሲዘጉ ወይንም አናስተናግድም በማለት ተከራካሪዎችን ሲያሰናብቱ ዜጎች መብታቸውን ለማስከበር ያላቸው መፍትሔ ምን እንደሆነ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት ከላይ እንደተመለከተው በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር ይዳኛል ተብሎ የተቋቋመው አካል እና ግራ ቀኙ ፈቃደኝነታቸውን የገለጹለት አካል በተለያየ ምክንያት ጉዳዩን ለመመልከት ያልፈለገ እንደሆነ ዜጎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 37/1/ መሰረት ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ እና ፍትሕ የማግኘት መብት ሊጠበቅላቸው የሚገባ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

መደበኛ ፍርድ ቤቶችም እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ዜጎች ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትሕ የማግኘት መብታቸው ሊረጋገጥ ስለሚገባ፣ ጉዳዩን እንዲያይ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አልመለከትም በማለት በብይን ተከራካሪዎችን ያሰናበተ ስለመሆኑ እየታወቀ እና ይሄ ሲሆን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማያስተናግዱ ከሆነ ደግሞ ዜጎች ያላቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚያጣብብ በመሆኑ አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ባጠቃላይ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አላስተናግድም በማለት የዘጋውን ጉዳይ ስልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት አላስተናግድም በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.128962 በቀን 21-10-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.18872 በቀን 02-6-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 21069 በቀን 15-4-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. መደበኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችውን የፍቺ ውጤት ጥያቄ ማስተናገድ አልችልም በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው ነው ብለናል፡፡
3. የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችውን የፍቺ ውጤት ክስ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት እና በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.341/1/መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት በአመልካች ላይ የደረሰውን ወጪና ኪሳራ የራሷን ትቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 71895

ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ሞላ ንጉሴ - ጠበቃ ሙሉጌታ ዘመነ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ንጉሴ ገለታ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የአመልካች እህት ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይና የአሁኑ ተጠሪ በጋብቻ አብረው ሲኖሩ በጋራ ያፈሩት ንብረት መኖሩን፣ ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት ጋብቻው በሞት መፍረሱን ገልጸው ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብላቸው አመልካች ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ ተጠሪ ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር ከአቀረቡ በኋላ ፍ/ቤቱ የውርስ ንብረቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ የውርስ አጣሪዎችን ሹሞ የውርስ አጣሪዎች ሀብቱን አጣርተው ለፍ/ቤቱ ሪፖርቱን ሲያቀርቡ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ዙር የውርስ አጣሪዎች የውርስ ንብረቱን አጣርተው ሲያቀርቡ ሊጣሩ የሚገባቸው ነጥቦች መኖራቸውን ገልፆ እንደገና እንዲያጣሩት አድርጎ ጉዳዩ በድጋሚ ተጣርቶ ቀርቦለት ጉዳዩን መርምሮ ለወ/ሪት ሸዋዬ ንጉሴ እንዲከፈል ተብሎ በሪፖርቱ በአንድ የውርስ አጣሪ የተካተተውን የብር 21,600.00 (ሃያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ክፍያን ያለመቀበሉንና የሟች ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ወራሾች የአሁኑን አመልካች ጨምሮ አምስት መሆናቸውን ዘርዝሮ በሌሎች ነጥቦች ላይ ተጣርቶ በ05/03/2002 ዓ.ም. እና በ06/07/2002 ዓ.ም. ተጣርቶ የቀረበውን ሪፖርት ፍ/ቤቱ ተቀብሎ አፅድቆታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ተሻሽሎ የሟችን ድርሻ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የሟች ወራሾች በተገቢው መንገድ ተጣርተው ባልቀረቡበት ሁኔታ ተጠሪ የሟች ወራሾች አሉ ስላሉና ከእድገት ፋና መረዳጃ እድር ውስጥ የተዘረዘሩ ሰዎች የሟች ወራሾች ናቸው ተብሎ የሟች ድርሻ ንብረት ለአምስት እንዲከፋፈል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ወራሽ ስለመሆናቸው በሕግ አግባብ ያልተረጋገጠና በውርስ አጣሪውም ጥሪ ላልቀረቡ ሰዎች የውርሱ ተካፋዮች ናቸው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሁፍ በሰጡት መልስ የሟች ወራሾች

አመልካች ብቻ ሳይሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች ስማቸው የተጠቀሱት ሰዎች ሆነው በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን ወልዲያ አካባቢ በየጁ ቀበሌ ማህበር አካባቢ በሕይወት ያሉ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የውርስ አጣሪው ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት የሟች ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ወራሾች እንዲቀርቡ ጥሪ ተደርጎላቸው ከአመልካች ውጪ ያሉት ያልቀረቡ መሆኑን፣ ሟች ከአመልካች ውጪ ሌላ ወራሾች አሏቸው ተብሎ የሟችን ድርሻ ከአመልካች ጋር እኩል እንዲካፈሉ የተወሰነው ከእድገት ፋና መረዳጃ እድር ውስጥ በሟች ወራሽነት ስማቸው ተዘርዝሮ ተገኝቷል በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 እንደተደነገገው የአጣሪው ሥራ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻም ውርሱ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የውርሱን ሃብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ እዳዎች መክፈል እና ሟቹ በኑዛዜ ያደረጋቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለመፈጸም ማንኛቸውም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ነው፡፡

የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ ለመለየት የሟችን የኑዛዜና ያለኑዛዜ ወራሾችን ማጣራት የውርስ አጣሪው አቢይ ስራ ሲሆን ያለኑዛዜ ወራሾችን የመለየት ስራውን ለመተግበር ደግሞ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 842 እስከ 856 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት ሟች ልጅ ወይም ተወላጆች ያሉት መሆኑን ወይም የሟችን ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን እንደ የደረጃቸው መኖራቸውን መለየትን የግድ የሚል ነው፡፡ የውርስ አጣሪው ይህንኑ ስራ ሲያከናውን ሊከተላቸው ከሚገባቸው መንገዶች አንዱ የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ ካለ በተገቢው መንገድ ጥሪ ማድረግ ነው፡፡ የሟች ወራሾችን ለመለየት ውርስ አጣሪው በመጀመሪያ ደረጃ ማድረግ ያለበት የሟች ኑዛዜን ማፈላለግ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 962(1) ስር የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ ግዴታውን ለመወጣትም የሟች የተለያዩ ፅሁፎችን በመፈተሽ ኑዛዜ የተወ መሆን ያለመሆኑን ጥረት ማድረግን፣ ሟች በኖረበት ቦታ በሚገኙት በሕግ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጣቸው ክፍሎች ወይም ፍ/ቤት መዝገብ ቤቶች ውስጥ ሟች በሕይወት ዘመኑ ያስቀመጠው ኑዛዜ መኖሩን ማረጋገጥን ሁሉ እንደሚያስፈልግ የፍ/ሕ/ቁጥር 891 እና 962/2/ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሟች ጽሑፎችን ውርስ አጣሪው ይመረምራል፣ በሕግ ለማዋዋል ስልጣን ከተሰጣቸው ዘንድና በፍርድ ቤት መዝገብ ቤቶች ተገቢ የሆኑ ፍለጋዎችን እንደሚያደርግ ኃይለ ቃል ባለው አገላለፅ ሲያስቀምጡ የሚያስገነዝቡት ቁም ነገር በየትኛውም ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ማስረጃ ቀርቦ የሟች ኑዛዜ ነው ተብሎ ዋጋ የማይሰጠው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ በተመለከቱት ቦታዎች ዘንድ የሚገኙት ሰነዶች በጥንቃቄ መፈለግ አለባቸው እንጂ ከየትኛውም ቦታ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ሁሉ ዋጋ የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ በዚህም መሰረት በመረዳጃ እድር መዝገብ ይገኛል የተባለው ሰነድ የሟችን ወራሾችን ለጊዜው ለመወሰን ብቃት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ከፍ/ብ/ቁጥር 962/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሟች ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ያለኑዛዜ ወራሾች ካሉ እንዲቀርቡ በተገቢው መንገድ ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን

ከአመልካች ውጪ ሌሎች ሰዎች ያለኑዛዜ ወራሾች አሉ ወደሚለው ድምዳሜ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱት ከእድገት ፋና መረዳጃ እድር መዝገብ ውስጥ ስማቸው ተዘርዝሮ ተገኝቷል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመረዳጃ እድር መዝገብ ውስጥ ስም ተጠቅሶ መገኘት ያለኑዛዜ ወራሽነትን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ውጪ ያሉ ሌሎች የሟች ወራሾች አሉ በማለት ይኖሩበታል የሚሉትን አድራሻ ሁሉ እየጠቀሱ እየተከራከሩ እነዚህ ሰዎች ቀርበው እስካሁን ድረስ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ያለማድረጋቸውም ተገቢነት ያለውና የክርክራቸውን እውነተኝነት የሚያሳይ አይደለም፡፡ የሟች ሌሎች ወራሾች ካሉም በሕጉ አግባብ አመልካችን ከሚጠይቁ በስተቀር ከወዲሁ ተጠሪ ከሟች ድርሻ ለመውሰድ ያልቀረቡትን ሰዎች በመወከል ንብረቱን እንዲይዙ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ ሟች ከአመልካች ውጪ ሌሎች ወራሾች መኖራቸውን እየገለፁ ከመከራከራቸው በተጨማሪ ለአመልካች የሟች ሁሉም ድርሻ አይገባቸውም የሚሉበት ሌላው ምክንያት ያለኑዛዜ ወራሽ የተባሉት ነገር በጥሪው መሰረት ያልቀረቡትን ሰዎች ድርሻ ሊወስድ የሚገባው መንግስት ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 852 ስር እንደተመለከተው የሟች ውርስ ለመንግስት ሊተላለፍ የሚችለው በሕጉ አግባብ የተመለከቱት የሟች ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉ ዘመዶች ከሌሉ ብቻ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም ወራሽ ስለመሆናቸው በሕግ አግባብ ያልተረጋገጠና በውርስ አጣሪውም ጥሪ ስላልቀረቡ ሰዎች የውርስ ተካፋዮች እንዲሆኑ ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944/ሀ/፣ 962፣ ከቁጥር 842 እስከ 856 እንዲሁም 962 እና ከቁጥር 1097 እስከ 1113 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33/2/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15035 ሚያዝያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94752 ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የሟች አረጋሽ ሲሳይ ድርሻ ንብረት አመልካች ለብቻቸው እንዲወስዱት ከሚደረግ በስተቀር ከሌሎች አራት ሰዎች ጋር እኩል ድርሻቸውን እንዲወስዱ የሚደረግበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. የሟች አረጋሽ ሲሳይ ወራሽ የሚሆን ሰው ካለ በሕግ አግባብ ድርሻውን ከአመልካች ከመጠየቅ ይህ ውሣኔ አያግድም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 71126
ሰኔ 5 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ወርቅነሽ ሰብስቤ - ወኪል ፍቅርተ እንደሻው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሻለቃ ባሻ እንደሻው - ቀረበ

2. አቶ እሸቱ እንዳሌ - ቀረበ

መዝገቡ ያደረው ለውሳኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሆኖ የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ሂደት በተሸጠው የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ አመልካች የቀደምትነት መብት ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክል/መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው ይሄው የክልሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 28-10-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ባልና ሚስት በሚሸጠው የጋራ ቤት ሽያጭ ሂደት ላይ ተጫራች ሆነው እንዲሳተፉ የፈቀደላቸው ስለመሆኑ፣ በጨረታው ሂደት ግን የአሁን 2ኛ ተጠሪ ያሸነፈ ስለመሆኑ፣ ቀደም ሲልም አመልካች ያመለከቱት የቅድሚያ መብት ጥያቄ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግን በጨረታው ሂደት ተጫራች ሆነው እንዲሳተፉ መብት የሰጠ እንጅ የቀደምትነት መብት ባለመሆኑ፣ በዚሁ ቀን ጠዋት የተሰጠው ትዕዛዝ ይሄንን ሳያገናዝብ በስህተት ስለመሆኑ በማመላከት የቀረበውን የቀደምትነት መብት ጥያቄን ውድቅ በማድረግ በጨረታው ሂደት ተሳትፎ አሸናፊ የነበረው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛ ስለመሆኑ የቀረበውን ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራቀኙን ክርክር በመስማት ይሄንኑ የክልሉ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን ቅሬታ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች በማንሳት የተከራከረች ሲሆን ፍሬ ሃሳቡ፡- ቀደም ሲል የክልሉ የወረዳ ፍ/ቤት ቤቱን ቅድሚያ እንድወስድ የሰጠውን አስገዳጅ ትዕዛዝ በመለወጥ ሌላ ትዕዛዝ መስጠቱ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ባለመሆኑ፣ ስለጋራ ባለሀብትነት ከሚመለከቱት የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች አኳያ በቀደምትነት በግዥ ስለማስቀረት መብት ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች አንጻር በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ በየራሳቸው ጥቅምት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ባልና ሚስት በሚሸጠው ቤት ጨረታ ላይ እንዲሳተፉ የተደረገ እና በሂደቱ እንደማንኛውም ተሳታፊ ተሳትፈው የተሸነፉ

ስለመሆኑ፣ 2ኛ ተጠሪ በሂደቱ አሸናፊ በመሆን ቤቱን የገዛ በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪም ሆነ ለአመልካች የተሰጠው ዕድል በጨረታው ላይ የመሳተፍ እንጂ የተለየ ነገር በሌለበት ሁኔታ አመልካች የምታነሳው ቅሬታ አግባብነት የሌለው ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ቅሬታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥታለች፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ያነሳችው የቀደምትነት መብት ውድቅ መደረግ ስለጋራ ባለሀብት ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በፍቺ ውጤት አፈጻጸም ወቅት በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሆነው ቤት በጨረታ እንዲሸጥ ስለመታዘዙ፣ በዚህን ሂደት ውስጥ ሁለቱም ወገኖች የቀደምትነት መብት መጠየቃቸው፣ ሁኖም ግን ፍርድ ቤቱ በጨረታው ሂደት እንዲሳተፉ እድል በመስጠት እና ለሁለቱም ወገኖች የተለየ መብት ሳይሰጥ የጨረታው ሂደት የተከናወነ ስለመሆኑ፣ በዚህም ሂደት ባልና ሚስት ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ማንኛቸውም ያላሸነፉ እና በጨረታው ተሳታፊ የነበረው 2ኛ ተጠሪ ያሸነፈ ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካችም ብትሆን ቀደም ሲል ጨረታው ከተከናወነ በኋላ በቅድሚያ እንድወስድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ፍርድ ቤቱ በስህተት ነው በሚል ማስተካከያ መስጠቱ አግባብነት የለውም ከሚል በስተቀር ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በተመለከተ የምታነሳው ክርክር የሌለ ከመሆኑም በላይ ከጨረታው መከናወን በፊት የቀደምትነት መብት ከ1ኛ ተጠሪ በተለየ መልኩ ተሰጥቶኛል የሚል ክርክር የላትም፡፡

በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በመያዝ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት ክርክሩ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በቀጥታ ተፈጻሚነት ያለው ህግ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/1996 መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 103/1/ መሠረት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ በዓይነት ለመከፋፈል አዳጋች የሆነን እና ከተጋቢዎቹ እንደኛው ወገን ለሌላኛው ለመተው መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ የሚደረግ ስለመሆኑ እና በዚሁ ድንጋጌ ስር በአሻሻጡ ሂደት ግራ ቀኙ ያልተስማሙ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ ደግሞ ሁለቱም ባልና ሚስት ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ለሁለቱም የፈቀደው እንደማንኛውም ተጫራች በጨረታው እንዲሳተፉ የሚል እስከሆነ ድረስ እና ተሳትፈውም አሸናፊው 2ኛ ተጠሪ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች በተለየ ሁኔታ የቀደምነት መብት ይገባኛል በማለት የምታቀርበው ክርክር አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም በጨረታው ሂደት ያሸነፈውን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ይረከብ በማለት ውሣኔ መስጠታቸው በአግባቡ እና በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 439 እና ተከታዮቹ ስር መሠረታዊ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ መርህን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት ነገር አላገኘንም፡፡

ባጠቃለይ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበችውን የቀደምትነት ግዥ መብት በተመለከተ ውድቅ በማድረግ በጨረታው መሠረት አሸናፊው ወገን /2ኛ ተጠሪ/ ቤቱን እንዲረከብ በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡና የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ ብሔ/ክል/ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ. 54623 በቀን 11/11/2003 ዓ.ም. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 10567 በቀን 08/11/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝ .ቁ.21347 በቀን 28/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የቀደምትነት ግዥ መብት ወድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 72286

ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ኃ/ስላሴ ወርቄ - ከጠበቃ ያሲን እድሪስ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ምስራቅ ወርቄ - ከጠበቃ ነሲቡ አልዩ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ኑዛዜን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም የአሁኑ አመልካች እናት ወ/ሮ የሺ ይልማ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ በፍርድ ቤት ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. መጽደቁን ገልፀው ኑዛዜውን ሟች በእርጅና ምክንያት ጃጅተው እያለ ያደረጉት በመሆኑ፣ በኑዛዜው ሰነድ ላይ የተቀመጠው ፊርማም የሟች ባለመሆኑ፣ ኑዛዜው በሐሰት ውንጀላ አመልካችን የነቀለ በመሆኑ፣ የኑዛዜ ቃሉ በስጦታ ውሉ መተካቱም የኑዛዜ ተጠቃሚነትን ቀሪ የሚያደርግ ነው፣ የህጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ስላልሆነ የተጠሪ የኑዛዜ ተጠቃሚነት ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለአመልካች መቃወሚያ አቤቱታ በሰጡት መልስ ሟች በሙሉ ጤንነታቸው የሚሰሩትን ተግባር በማወቅና በመገንዘብ ያደረጉት ኑዛዜ መሆኑን፣ አመልካችን ከውርሱ የነቀሉትም ይሰድባቸው፣ ያንገላታቸው፣ ያዋርዳቸው፣ ለመደብደብ ሙከራ ያደርግባቸው ስለነበር መሆኑና ይህም በኑዛዜ ሰነዱ ተጠቅሶ ከተገኘ እንደ እውነት የሚወሰድና ከውርስ ለመንቀል በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት መሆኑን፣ የኑዛዜው ሰነድ በ24/01/2001 ዓ.ም. ስጦታ ውሉ መተካቱም እርስ በእርሱ የሚጣጣምና አመልካች ከውርስ እስከተነቀሉ ድረስ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት መቃወሚያ ሊያነሱ እንደማይችሉ በህጉ ክልከላ የተደረገ መሆኑን ገልጸው የአመልካች የመቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ሊሆንልኝ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙ ምስክሮችን በመስማትና ፊርማው በፎረንሲክ ፖሊስ እንዲመረመር አድርጎ ጉዳዩን መርምሮ የሮረንሲክ ምርመራ ውጤቱን በተመለከተ ፊርማውን መለየት አልተቻለም፣ ፊርማውን ማጣራት አልተቻለም የሚሉ ሐረጎች በአንድ ላይ የያዘ በመሆኑ ውጤቱ ፊርማው የሟች አይደለም ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ማለፉን ገልፆ የፊርማውን ክርክር በዚሁ ያለፈው ሲሆን ዋናውን ክርክር በተመለከተ የኑዛዜ ሰነዱ በስጦታ ውሉ መተካቱን፣ ይህ ሆኖ እያለ ተጠሪ የኑዛዜ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው አግባብ እንዳልነበር፣ የአመልካች ከውርስ መነቀል ያለመነቀል በኑዛዜ ሰነዱ በፀደቀበት ሳይሆን ከስጦታ ውሉ ጋር ተያይዞ በሚነሳው ክርክር ሊታይ የሚገባው መሆኑን በምክንያትነት ይዞ

ለተጠሪ የተሰጠውን የኑዛዜ ወራሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360(2) መሰረት ሰርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ሟች የውርስ ንብረታቸውን ለአሁኗ ተጠሪ በኑዛዜ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ/ም ከሰጡ በኋላ መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገ የስጦታ ውል ደግሞ ለተጠሪ መልሰው ማፅደቃቸው ንብረቱ የተላለፈለት ሰው አንድ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 900(1) መሰረት ተገቢ መሆኑን ገልጾ የኑዛዜ ሰነዱ በስጦታ አልተሻረም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 900(1) ሳይሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 898(2) መሆኑን ገልጾ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በስጦታ ውሉ በከፊል ተሽሯል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ከአሻሻለ በኋላ የስር ፍ/ቤት ያልተሻረውን የኑዛዜ ክፍል በሚመለከት በኑዛዜው ላይ የቀረበውን ክርክር ተመልክቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የከተማው ሰበር ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት አድርገውት የነበረው ኑዛዜ በ24/07/2001 ዓ.ም. በተደረገ የስጦታ ውል በከፊል ተሽሯል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሟች እናታቸውን ንብረት ለመውረስ ሲፈልጉ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ባልተደረገ የኑዛዜ ሰነድና የስጦታ ውል መሰረት የውርስ ንብረቱን ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው ክስ ሊመሰርቱ የቻሉ መሆኑና የስር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ያደረገው ደግሞ የኑዛዜ ሰነዱ በስጦታ ውሉ ተተክቷል፣ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦችን ደግሞ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ሲቀርብ የሚታዩ ናቸው በማለት የኑዛዜ ወራሽነትን ብቻ ሰርዞ ሲወስን የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የኑዛዜ ሰነዱ ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት መወሰኑን ነው፡፡ ተጠሪ ስጦታ በሟች የሺ ይልማ ተደርጎልኛል የሚሉት መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ/ም ሲሆን ሟች ከዚህ አለም በሞት የተለዩት ህዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. መሆኑን እንዲሁም መስከረም 21 ቀን 1999 ዓ.ም. ሟች ኑዛዜ ማድረጋቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባሉት የስጦታ ውል ከሟቹ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስጦታ ውል ላይ ስለኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ድንጋጌ በሐይለ ቃል ያስቀምጣል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2443 ስር ደግሞ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ስጦታ በግልፅ በሚደረግ ኑዛዜ አሰራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ አሰራር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ስር ተመልክቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ የሟች ሕጋዊ እና የኑዛዜ ወራሾች የስጦታው አሰራር በሕጉ የተቀመጠውን አሰራር የተከተለ መሆን ያለመሆኑን መሰረት አድርገው ስጦታው ኑዛዜውን ተክቷል የሚል ክርክር ቢያቀርቡ የሚከለከሉበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826(2)፣ 842 እስከ 856 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ ከሁሉም በላይ ሟች ሲሞት ተፈፃሚነት ያለው ስጦታ ከሆነ ስጦታው መሻር ያለመሻሩን

ሊረጋገጥ የሚችለው በውርስ ሕጉ ስለኑዛዜ መሻር በሚደነግጉት ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 898 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ለዚህ አይነት ስጦታም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ በግልጽ አኳኋን በተናዛዡ ሊሻር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የኑዛዜ አንዱ አይነተኛ ባህሪይ ተናዛዡ በፈለገው ጊዜ የሚሽረው አይነት መሆኑ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ የመሻሩ ተግባር እስከተከናወነ ድረስ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ኑዛዜ ተናዛዡ በፈለገው ጊዜ የሚሽረው ስለመሆኑ ሕጉ የሚያስገነዝበን ከሆነ በዚህ ረገድ የሚሰጠው ትርጉምም የተናዛዡ ኑዛዜውን የመሻር ስልጣን በሚያጣብብ መልኩ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 898 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ ጉዳዩን በማየት ሚች መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም. አደረጉ በተባሉት ኑዛዜ ስር የተዘረዘሩትን ንብረቶችን አይነት ብዛት ሚች መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. አደረጉ በተባለው የስጦታ ሰነድ ስር ከተጠቀሱት ንብረቶች አይነት እና ብዛት እንዲሁም ከሰነዶች ፎርማሊቲ አንፃር ተመልክቶ የኑዛዜ ሰነዱ በከፊል የተሻረ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 15894 ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የስጦታው አይነት ስጦታ ሰጪው ከሞቱ በኋላ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ ስጦታው ኑዛዜውን የተካ ነው በማለትና የሥጦታ ውሉ በሕጉ የተቀመጠውን ስርዓት ያሟላ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት አግኝቶ የ23/01/1999 ዓ.ም. የኑዛዜ ሰነድ በ24/07/2001 ዓ.ም. የስጦታ ውል በከፊል ተሽሯል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 75562

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ መሐመድ ይመር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ በተጠሪ ስም እጣ የደረሰው ቢሆንም ቅድመ ክፍያ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስ በኋላ የተከፈለበት የኮንዶሚኒየም ቤት የጋራ ነው ተብሎ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. በጻፉት የሰበር ማመልከቻ አከራካሪው የኮንደሚኒየም ቤት በጋብቻ ጊዜ በስማቸው የደረሰ ቢሆንም እጣው ሊደርስ የቻለው መንግስት ለሴቶች የተለየ የእጣ እድል ስርዓት በመዘርጋቱ በመሆኑ እና እጣው ከደረሰ በኋላም ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈርሶ ለቤቱ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚሉትን የቅሬታ ነጥቦችን ጠቅሰዋል፡፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ የጋራ ንብረቶች ናቸው የሚሏቸውን አይነታቸውንና ብዛታቸውን በመግለፅ ዳኝነት መጠየቃቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩበት በሰሚት ሳይት የሚገኝ ሕንፃ ቁጥር 148/11 ባለ ሁለት መኝታ በተጠሪ ስም የተመዘገበ ኮንዶሚኒየም ቤት እጣው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ የወጣ በመሆኑ በትዳር ጊዜ የተፈራ የጋራ ንብረት ስለሆነ ልንካፈል ይገባል የሚል የዳኝነት ጥያቄ ይገኝበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11 ውስጥ በ350 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሰፈረና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት፣ የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መኖራቸውን ገልፀው ክፍፍሉ እንዲደረግ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በሰጡት መልስም በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11 ውስጥ በ350 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሰፈረና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት፣ የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መኖራቸውን ሳይክዱ ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ

የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ግን የጋራ ስላልሆነ ተጠሪ ሊጠይቁ አይችሉም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የንብረት ክርክሩ በዚሁ መልኩ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በሁዋላ የኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ መሆኑ ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለቅድመ ክፍያ ከፈልኩ የሚሉትን የብር 32,048.40 (ሰላሳ ሁለት ሺህ አርባ ስምንት ብር ከአርባ ሳንቲም) ግማሽ ብር 16,024.20(አስራ ስድስት ሺኅ ሃያ አራት ብር ከሃያ ሳንቲም) ተጠሪ እንዲተኩላቸው ቤቱ ከእነ ቀሪ እዳው ግን የጋራ ነው ፣ በማለትና የታመኑትን ንብረቶች በሕጉ አግባብ ሊከፋፈሉ የሚችሉበትን መንገድ በመዘርዘር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ኮንዶሚኒም ቤቱን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሁኖ በመገኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ሚያዚያ ወር 2002 ላይ አከራካሪው የኮንዶሚኒየም ቤት በተጠሪ ስም የደረሳቸው መሆኑን ፣ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. ደግሞ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረሱን፣ ከዚህም በኋላ የጋብቻ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር ባልተካሄደበት ሁኔታ ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም. አመልካች ለኮንዲሚኒየም ቤቱ ቅድመ ክፍያ የከፈሉ መሆኑንና ጳጉሜ 04 ቀን 2002 ዓ.ም. ላይ ከሚመለከተው አስተዳደር አካል ጋር የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ውል የተዋዋሉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ አመልካች አሁን በዚህ ሰበር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት ቤቱ ሴት በመሆናቸው ባገኙት ልዩ ድጋፍ የደረሳቸውና ቅድመ ክፍያውንም ከጋብቻ መፍረስ በኋላ የከፈሉት በመሆኑ የጋራ ሊሆን አይችልም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ለእጣው እንዲመዘገቡ የተደረገው ተጠሪ ካላቸው የስራ ባህርይ አንፃር አመልካች በቋሚነት አዲስ አበባ ስለሚኖሩ ጉዳዩን ለመከታተል እንዲቻል ስለመሆኑና እጣውም ሴት በመሆናቸው በተለየ መንገድ ያላገኙት መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የቤተሰብ ሕጉን ያገናዘበ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በበላይ ፍርድ ቤት ሊነሳ እንደማይችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚመራው በ1958ቱ የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጋችን በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ችሎትም ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች ያልተነሳ የፍሬ ነገር ክርክር በሰበር ችሎት የሚነሳበት አግባብ የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ በጋብቻ ውስጥ የደረሳቸው መሆኑን ሳይክዱ እጣው በሴትነታቸው የደረሳቸው መሆኑን ጠቅሰው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት

የላቸውም በማለት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የቤቱ ዕጣ በጋብቻ ውስጥ ግራ ቀኙ እያሉ የደረሰ መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ አመልካች እጣውን በሴትነት ያገኘሁት ነው በማለት እዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክር ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች እጣው የደረሰው በጋብቻ ውስጥ መሆኑን ሳይክዱ ለቤቱ ቅድመ ክፍያ ከጋብቻ መፍረስ በኂላ በስማቸው ወይም ከግል ገንዘባቸው መክፈላቸውና ውሉንም ከአስተዳደሩ ጋር ማድረጋቸው በጋብቻ ጊዜ የደረሰውን እጣ ውጤቱን የሚቀየርው ሊሆን የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ የኮንዶሚኒየም ቤት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበትን አግባብ የሚገዙ ሕጎችም ከምዝገባ ጀምሮ የተለያዩ ሂደቶች ያሉ ስለመሆኑ የሚሳዩ ሲሆን በትዳር ውስጥ በሚገኙ ባልና ሚስት ለእጣው ሲመዘገቡ ሁለቱም ሊመዘገቡ እንደማይችሉ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም አንዱ ተጋቢ በጋብቻ ጊዜ ስሙ ከተመዘገበና እጣው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ከደረሰ በቤቱ ላይ የሚገኘው መብትና ግዴታ የተጋቢዎች የጋራ ነው ከሚባል በስተቀር የቅድሚያ ክፍያ ጋብቻው ከፈረሰ በሁዋላ በአጭር ጊዜ ወይም ወዲያውኑ በመከፈሉና ውሉም ጋብቻው ፍርሶ የንብረት ክፍፍል ባልተደረገበት ሁኔታ ከሚመለከተው አካል ጋር እጣው በስሙ የወጣለት ተጋቢ በመፈራረሙ ብቻ ንብረቱ የዚሁ ቅድመ ክፍያውን የከፈለውና ውሉን የተዋዋለው ተጋቢ የግል ንብረት ነው የሚባልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤቱ የግሌ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበና ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሁኖ ስለአገኘነው በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ በመ/ቁ. 24526 ሐምሌ 19 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 115416 በ12/03/2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የኮንዶሚኒየም ቤቱ እጣ የደረሰው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ስለሆነና አመልካች ለቤቱ ቅድመ ክፍያ በመክፈል ውሉን ከአስተዳደር አካሉ አደረግሁ የሚሉት ጊዜ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ከፈረሰ በአጭር ጊዜ ውስጥና የንብረት ክፍፍሉ ባልተደረገበት ሁኔታ በመሆኑ ቤቱን የአመልካች የግል ንብረት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 74376

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ብዙአየሁ ታደሰ - ጠበቃ ምህረትአብ ልዑልና ወ/ሮ አበባ መንግስቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሰሎሜ ሻወል - ጠበቃ አቶ ኃይሉ ንጋቱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ አመልካችና ተጠሪ የፍች ውጤትን በተመለከተ ያደረጉት ስምምነት ተፈፃሚነትን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ (ከሳሻ) አመልካች (ተከሳሽ) በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች እንዲፈርስና የፍች ውጤት በሆነው የጋራ ንብረት ክፍፍልና የልጆች አስተዳደግ ጉዳይ ከአመልካች ጋር በመስማማት ስምምነቱን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. ያስፀደቁ መሆኑን ገልፀው በስምምነቱ መሠረት አብዛኛው ሁኔታዎች የተፈፀሙ ቢሆንም በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/05 የሚገኘውና የካርታ ቁጥሩ 33799 ቁጥሩ 2310 የሆነ በተከሳሽ (አመልካች) ስም ያለና በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 20 የካርታ ቁጥሩ 33822 የሆነና ቁጥሩ 4057 የሆነ ፎቅ ቤት በስምመነታችን መሰረት ከዕዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ለከሳሽ (ተጠሪ) አላዛወሩም፡፡ ተከሳሽ በስምምነቱ መሰረት እንዲፈፀም ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም በስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመ በመሆኑ ንብረቱን ከዕዳና እገዳ ነፃ አድርገው እንዲያዛውሩ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ ይህ የማይቻል ከሆነ ግምታቸውን እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው በስምምነቱ መሰረት የቤቶቹን ስመ ንብረት ለከሳሽ (ተጠሪ) ለማዛወር አስፈላጊውን እንዳሟላ ከሳሽ ደግሞ የዴንቨሩን ጋብቻ ሰርተፊኬት አቅርበው የዴንቨሩን ጋብቻ እንድናፈርስ ስምምነት ተደርጓል፡፡ ጉዳዩ በሽማግሌ ታይቷል፡፡ ከሳሽ የዴንቨሩ ጋብቻ ሳይፈርስ ስም እንዲዛወር መጠየቋ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የስር ፍ/ቤት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለ ፍችና የፍች ውጤት አቅርበው ባፀደቁት ስምምነት ውስጥ፣ ተከሳሽ (አመልካች) ለከሳሽ (ተጠሪ) የቤቶቹን ስመሀብት የሚያዛውረው በኮሎራዶ ዴንቨር ያለው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ነው የሚል ይዘት የለውም፡፡ ተከሳሽ በሁለት ዓመት ተኩል ጊዜው ውስጥ ቤቶቹን ከዕዳና እገዳ ነፃ አድርገው ለከሳሽ ለማዛወር የተስማሙ በመሆኑ አሁን ጊዜ ሲሰላ ሶስት ዓመት የሆነው በመሆኑ በስምምነቱ መሰረት ቤቶቹን ነፃ

አድርገው ስመሀብቱን ለከሳሽ ያዛውሩ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ህዳር 11 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ በሁለት አገር የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ስምምነቱን ሲፈፅሙ የአመልካችና ተጠሪ ፍላጎት ምን እንደነበር ስለ ውሎች አተረጓጎም የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ስምምነቱን መተርጐም ሲገባው ይህንን ሳያደርግ ተጠሪ የኮሎራዶ ዴንቨር ያለውን ጋብቻ ሳታፈርስ የቤቱ ስመ ሀብት እንዲዛወር መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች በስምምነቱ መሰረት እንዲፈጽም ትዕዛዝ ሊሰጥ አይገባም፡፡ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ዓለም አቀፍ የግለሰብ የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካችና ተጠሪ የነበራቸው ጋብቻ በፍች እንዲፈርስና ጋብቻው በፍች ከፈረሰ በኂላ ስለሚኖረው የጋራ ንብረት ክፍፍልና የልጆች አስተዳደግ ሥምምነት ፈፅመው ስምምነቱ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ፀድቋል፡፡ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የተጠሪ ድርሻ ስለመሆናቸው በስምምነቱ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ የጋራ ንብረት ለመካፈል ባደረገው ስምምነት መሰረት አመልካች እንድፈጽም ያቀረብኩትን ክስ ተቀብሎ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ በሰበር የማጣሪያ ችሎት የተያዘው ጭብጥም እኔና አመልካች ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ካስመዘገብነው የፍችና የፍች ውጤት ከሚዘረዝረው ስምምነት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች የኮሎራዶ ዴንቨር ያለው ጋብቻ ሣይፈርስ ስምምነቱን አልፈፅምም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ ጉዳዩ የዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በታች ፍ/ቤቶች አመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን ጋብቻ ለማፍረስ ከፍች በኂላ የጋራ ንብረት ክፍያንና የልጆች አስተዳደግን በተመለከተ ባደረጉት ስምምነቶች ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት አቅርበው ባፀደቁት መሰረት አመልካች ክስ የቀረበባቸውን ሁለት ቤቶች ለተጠሪ ባለሀብትነቱን እንዲያስተላለፍ የሰጡት ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉትና የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ያፀደቀው ስምምነት የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የፍች የጋራ ሀብት ክፍፍልና የልጆች አስተዳደግ ስምምነት በማድረግ መጋቢት 21 ቀን 1985 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ግዛት ክልል በአዲስ አበባ የፈፀሙትን ብሔራዊ ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ፣ ጋብቻው በፍች ሲፈርስ ያሏቸውን የጋራ ሀብቶች የሚከፋፈሉበት ሁኔታና የልጆች አስተዳደግ እንዴት እንደሆነ በዝርዝር ፅፈው፣ ፍችውና የፍች ውጤቱን በተመለከተ ያደረጉት ሥምምነት የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲያጸድቅላቸው በጋራ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ፍችንና የፍች ውጤትን በተመለከተ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት የአመልካችና የተጠሪ ፈቃዳቸውን የገለጹበት፣ ለልጆች አስተዳደግና ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን በማረጋገጥ

ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀደቀው መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔና ግራ ቀኙ በሰበር ካቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ተረድተናል፡፡

የፍች ስምምነት እንዲያፀድቅ በባልና በሚስቱ ስምምነት ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት የፍች ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የፍች ስምምነቱ የባልና የሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑን ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን እንደዚሁም ስምምነቱ ለህግና ለሞራል የማይቃረን መሆኑን፣ ባልና ሚስቱ ስለፍች ውጤት ያደረጉት ስምምነት የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ የሚያስጠብቅ መሆኑና ስምምነቱ የሁለቱንም ተጋቢዎች ጥቅም ሚያስጠብቅ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለበት በተሸሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80 ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም የፍችው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ጊዜ ስምምነቱ ተፈፃሚነት የሚኖረው ፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ እንደሆነ የተሸሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል፡፡ የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. ተፈራርመው በጋራ ማመልከቻ ፍ/ቤቱ እንዲያጸድቅላቸው የጠየቁትን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት ከማጽደቁ በፊት አስገዳጅነት ባለው በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 80 ሊጣሩና ሊረጋገጡ የሚገባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች በማረጋገጥ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በህግ ስልጣን የተሰጠው ፍ/ቤት የስምምነቱን ይዘት፣ ስምምነቱ በልጆች አስተዳደግ ላይ የሚኖረውን ውጤት፣ የሁለቱንም ተጋቢዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብር መሆኑን በማረጋገጥ ካፀደቀው ስምምነቱ ህጋዊ ውጤት ያለውና በባልና ሚስቱ ላይ አስገዳጅነት ያለው ሰነድ እንደሚሆን፣ ከቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀጥ 3 ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን የጋራ ሀብታቸውን ለመከፋፈል ባደረጉት ስምምነት መሰረት አመልካች እንዲፈፅም ያቀረበችው ክስ የቤተሰብ ህጉን አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት ተጠሪ ክስ ያቀረበችባቸው ሁለት ቤቶች የተጠሪ ድርሻ መሆናቸው በግልፅ እንደተቀመጠ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው በስር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጋራ ንብረት ለመካፈል አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት የተጠሪ ድርሻ መሆናቸው የተገለጹትና ክስ የቀረበባቸውን ሁለት ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ለማስረከብ የሁለት ዓመት የስድስት ወር የጊዜ ገደብ የተሰጠው ከመሆኑ ውጭ ሌላ ቅድመ ሁኔታ ያልተቀመጠ መሆኑንና አመልካች ቤቶቹን የማስረክበው በአሜሪካን አገር የኮሎራዶ ዴንቨር ግዛት የተፈፀመው ጋብቻ መፍረስ ይገባዋል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ግልፅ የሆነውና ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ያፀደቀውን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት የሚጥስ ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ስምምነቱን የአመልካችና የተጠሪን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ትርጉም መስጠት ነበረባቸው በማለት በሰበር ያቀረቡት ክርክርም በመጀመሪያ ደረጃ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት ከማጽደቁ በፊት የአመልካችና የተጠሪ ፍላጎት በኢትዮጵያ ውስጥ መጋቢት 21 ቀን 1985 ዓ/ም ያደረጉት ጋብቻ በፍች ማፍረስ፣ እንደዚሁም የልጆቻቸውን አስተዳደግና የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል መሆኑን በማረጋገጥ ያፀደቀው በመሆኑ፣ እንደዚሁም ውሎች ግልፅ በሆኑ ጊዜ ግልፅ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጎም እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1733 በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ይህንን መሰረታዊ የውል

አተረጓጎም መርህ በሚቃረን ሁኔታ ግልጽ የሆነውን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት ፍ/ቤቶች ሊተረጉሙት ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ጉዳዩ የዓለም አቀፍ ግለሰብ ህግ ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑን በአሜሪካን አገር የሚኖር የህግ ባለሙያ የሰጣቸውን አስተያየት በሰበር አቤቱታቸው ውስጥ በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት መጋቢት 21 ቀን 1985 ዓ.ም. የፈፀሙትን ጋብቻ በፍች ለማፍረስ ያደረጉትን ስምምነትና የፍችውን ውጤት በስምምነት ለመጨረስ ተስማምተው የቀረቡትን የልጆች አስተዳደግና የጋራ ንብረት ክፍያ ውል የተሸሻለውን የቤተሰብ ህግ መሰረት በማድረግ መርምሮ ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ/ም የስር ፍ/ቤት ቀደም ብሎ በማጽደቅ የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈፀም የቀረበ ክርክር ነው፡፡ የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. ባፀደቀው ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትንና የተጠሪ ድርሻ የሆኑ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክብ ትዕዛዝ መስጠት የዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ጋብቻቸው በፍች እንዲፈርስና የፍች ውጤትን በተመለከተ ተስማምተው የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በተሸሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80 እና አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት መርምሮ ባፀደቀው መሰረት ክስ የቀረበባቸውና የተጠሪ ድርሻ የሆኑት ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ስመ ሀብቱን እንዲያስተላለፍ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ህዳር 13 ቀን 2004 እና ታህሳስ 05 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ 45548
መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አሚናት አሊ ጠ/ሙሉጌታ ዘመነ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋጡማ ውበት ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ ባቀረበችው ክስ ነው፡፡ የጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ከአቶ መሀመድ ሁሴን (የሥር ተከሳሽ) ጋር በ1987 ዓ.ም. በሰርግ ተጋብተው ሲኖሩ ቆይተው በኑሮ ስላልተሰማው ጋብቻው እንዲፈርስና ንብረት እንዲካፈሉ እንዲወሰን ሲሆን ተከሳሽ ቀርበው ጋብቻ የለንም አለ ከተባለም ሊፈርስ አይገባም የሚልና የሚፈርስ ከሆነም ከሥር ጣ/ገብ (የአሁን አመልካች) ጋር ሁለተኛ ጋብቻ ስላለ ንብረቱ ለሦስቱ ሊካፈል ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የአሁን አመልካች ሥር ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ ሆና ባቀረበችው አቤቱታ የተከሳሽ ሚስት እሷ ብቻ ስለመሆኗ እና የንብረት ክርክሩ የጋራ ንብረት መብቷን የሚጐዳ ነው በሚል ወደ ክርክሩ እንድትገባ እንዲፈቀድላት አመልክታ ወደ ክርክሩ ገብታ መከራከሪያ አቅርባለች፡፡ የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሁለቱም የአቶ መሀመድ ሁሴን ሚስቶች ስለመሆናቸው በበቂ ሁኔታ አስረድተዋል ካለ በኋላ ወ/ሮ ፋጡማ ውበት /ተጠሪ/ ጋብቻ የፈፀመችው በ1987 ዓ.ም መሆኑን በአንፃሩ ወ/ሮ አሚናት አሊ (አመልካች) ጋብቻ የፈፀመችው በ1990 ዓ.ም ስለሆነ የኋለኛው ጋብቻ በጋብቻ ላይ የተፈፀመ ነው በሚል እንዲፈርስ ወስኖ የንብረት ክርክደሩ በተጠሪ እና በተከሳሽ አቶ መሀመድ ሁሴን መካከል እንዲቀጥል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ሁለቱም ጋብቻ ያላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የፊተኛው ጋብቻ በተጠሪ ጥያቄ እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ የኋለኛውም ጋብቻ ተጠሪ ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ ሁለቱም በአንዴ እንዲፈርስ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡ በዚሁም መሠረትም የአመልካች ጋብቻ እንዲፀና ሊቀጥል ይገባል ብሏናል፡፡

የንብረት ክርክርን አስመልክቶ የሁለቱንም ጋብቻ ውጤት ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በቅድሚያ ሦስቱም ወገኖች የግል ሀብት የሚሉትን እንዲለዩ ከተደረገ በኋላ ሁለተኛው ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት የተፈራ ንብረት ለመጀመሪያ ተጋቢዎች እንዲሆን ተደርጐ የጋራ ሀብቱ ለሦስት እንዲካፈል ሲል በዚሁ አግባብ የንብረት ማጣራት ሂደት እንዲቀጥል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩላቸው በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለቱም ጋብቻ መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ሕጉ በጋብቻ ላይ ጋብቻን የማያበረታታ ነው ሲል ለቀደመው ጋብቻ ጥበቃ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ በንብረት ላይ ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚገባ አመልካች ከሁለተኛው ጋብቻ በኋላ የተፈራው ንብረት ለሦስት ይካፈሉ ሲል ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የመጀመሪያዋን ተጋቢ ጥቅም የሚጐዳ ነው በማለት በተጠሪ ተዘርዝረው ከቀረቡት ንብረቶች የግል የተባለ ከተለየ በኋላ የተቀረውን ተጠሪና አቶ መሀመድ ሁሴን እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

ንብረት የማጣራቱ ሂደትም በዚሁ አግባብ እንዲቀጥል ትእዛዝ ሰጥቷል አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበች ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ የክርክሩን አመጣጥ በሰፊው በማተት የአመልካች ጋብቻ ፀንቶ ያለ ስለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ካረጋገጡ በኋላ በንብረት ረገድ ግን አመልካች መብት የላትም መባሉ የክልሉን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74 እና 101 ድንጋጌ የሚጥስ ውሳኔ ነው በማለት እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ከሥር ተከሳሽ ጋር ከጥር ወር 1990 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ እንደነበራት ተረጋግጦ ሳለ በተጠሪ እና በአመልካች ባለቤት መካከል የነበረው ትዳር በፍቺ ሲፈርስ አመልካች በንብረት ክፍፍሉ ምንም ድርሻ የላትም መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች ጋብቻ አላት ሊባል እንደማይገባ በንብረት ረገድም ሁለተኛው ጋብቻ ህጋዊ ባልሆነበት ሁኔታ ንብረት ለመካፈል የሚያስችል አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ ከአቶ መሀመድ ሁሴን ጋር ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ መሥርተው ይኖሩ እንደ ነበር አመልካችም ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ከእኝሁ ሰው ጋር ጋብቻ መሥርተው ይኖሩ እንደነበር በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በውሳኔያቸው እንዳሰፈሩት የተጠሪ ጋብቻ ከአመልካች የቀደመ ሲሆን የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ የነበረው አመልካች በጋብቻ ላይ ጋብቻ የፈፀመች ስለሆነ ይፍረስ የሚል ሳይሆን ተጠሪና ባለቤቷ በኑሮ ባለመስማማታቸው ጋብቻው እንዲፈርስ እንዲወሰን ነበር፡፡ በዚህ አግባብ የተጠሪ ጋብቻ የፈረሰ እና የአመልካች ጋብቻ ፀንቶ እንዲቀጥል ከተደረገ በዚህ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ የተፈራ ንብረት ክፍፍል መርህ ምን ሊሆን ይገባል የሚል ጥያቄ ምላሽ የሚያሻው ነው፡፡

ይህ ጥያቄ አወዛጋቢ ሆኖ ሊቀርብ የቻለው የአማራ ብ/ክልል መንግስት የቤተሰብ ሕግም ሆነ የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ በጋብቻ ላይ ጋብቻ የማይፈቅድ በመሆኑ በሁለት ተጋቢዎች መካከል የሚፈጥር የንብረት ክፍፍል ጥያቄን አስመልክቶ ሕጉ ግልጽ ምላሽ ስለማይሰጥ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርብ አጠቃላይ የሕጉን መንፈስና ማህበራዊ ሁኔታዎነችን በማገናዘብ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

ለተያዘው ክርክር መፍትሔ ለመስጠት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ምክንያት ጋብቻው ሕጋዊ አይደለም ተብሎ ቢፈርስ እንኳን ጋብቻው ፀንቶ በቀረበት ጊዜ የተፈፀሙ ድርጊቶች ውጤት የሚያጡ አይደሉም በሚል ምክንያት ተጋቢዎቹ ያፈሩትን ንብረት እንዲካፈሉ ሲወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ለመለወጥ የሰጠው ምክንያት ይህ ዓይነት አተረጓጐም ሕጉ ጥበቃ ያደረገለትን የመጀመሪያ ጋብቻ ጥቅም የሚጐዳ ነው የሚል ነው፡፡

በእኛ በኩል እንደተገነዘብነው ሕጉ ጋብቻ ላይ ጋብቻ ባለመፍቀዱ ተፈጽሞ ሲገኝ ሕገወጥ ነው ይፍረስ በማለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት ወገኖች የቀደመ ጋብቻ ያለው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕግ ስለመሆኑ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 18(ሐ) እና የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 29/ሐ/ በተመሳሳይ ሁኔታ ደንግገው እናገኛለን፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪም ሆነች አመልካች ከአቶ መሀመድ ሁሴን ጋር ከአሥር ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ጋብቻ መሥርተው ሲኖሩ የቀረበ መቃወሚያ ስለመኖሩ በዚህ ክርክር አልተጠቀሰም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የቀደመ ጋብቻ የነበራት መሆኑ ቢረጋገጥም የአመልካች ጋብቻ እንዲፈርስ ያቀረበችው መቃወሚያ ሳይኖር ዛሬ በንብረት ክርክር ላይ ወደ ኀላ ተመልሶ ውጤት እንዳይኖር ማድረግ ፍትሀዊ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ከዚህም ሌላ የቤተሰብ ሕጉ አጠቃላይ መንፈስ ሲታይ አንደኛዋ ተጋቢ በሌላኛዋ ተጋቢ ጥረት በተፈራ ንብረት ላይ ያለአግባብ እንድትበለጽግ ወይም ሌላኛዋ ተጋቢ ያለአግባብ መብቷንና የጥረቷን ውጤት እንድታጣ ለማድረግ ያሰበ አለመሆኑን መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ለዚህ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ጋብቻ እንኳን ሳይኖር ከጋብቻ ወጪ እንደባልና ሚስት ከሦስት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ አብረው የኖሩ ሰዎች በዚህ ጊዜ ውስጥ ያፈሩት ንብረት የጋራ ሀብታቸው ስለመሆኑ በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 102(1) እና በአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 113(1) ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም በተሻለ ምክንያታዊ ሁኔታ (for a stronger reason) በጋብቻ ውስጥ በተጋቢዎች መካከል የተፈራ ሀብትን በሚመለከት በግራ ቀኙ ማስረጃ የሚጣራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወዲሁ ግን ሁለተኛዋ ተጋቢ በንብረት ረገድ መብት የላትም የሚለው የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ድምዳሜ ተገቢነት የለውም፡፡

ስለሆነም የተጠሪም ሆነ የአመልካች የንብረት ድርሻ ክፍፍል መርህ መሆን የሚገባው በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው አስቀድሞ ሦስቱም የግል ንብረት የሚሉትን በማስረዳት የየግላቸውን መውሰድ ይገባቸዋል፡፡ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97(1) እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 86(1) ይህንኑ ያመለክታል፡፡

ከዚህ ውጪ የሆነው ሀብት እና በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስቱ ወይም የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ሆኖ የሚገመት ስለመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የጋራ ሀብት የሚሰኘው በተጋቢዎች የጋራ ጥረት ወይም በአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረትም የተፈራ ሊሆን እንደሚችልና በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ ቢሆን እንኳ በጋብቻ ውስጥ

የተፈራ መሆኑ ከተረጋገጠ እና በተለያ ሁኔታ ሕጉ ባስቀመጠው አግባብ አንደኛው ተጋቢ የግል መሆኑን ካላስረደ ጭምር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62(1) ና 63(1) እንዲሁም የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 73(1) እና 74(1) ይህንኑ ያስረዳሉ፡፡

ከተያዘው ጉዳይ ጋር ስናያይዝ ሁለቱ ሚስቶች ናቸው እስከ ተባለ ድረስ በሕጉ መንፈስና ሃይል (by operation of the law) ከባለቤታቸው ጋር ያፈሩትን ንብረት ከባለቤታቸው ጋር እኩል የመካፈል መብት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንደኛዋ ተጋቢ ከሌላኛዋ ተጋቢ በተለየ ሁኔታ ንብረት ለማፍራት በቀጥታ አስተዋጽኦ ያደረገች መሆኑን ማስረዳት ከቻለች ከሌላኛዋ ተጋቢ የተሻለ መብት ሊኖራት እንደሚገባ መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአቶ መሐመድ ሁሴን ጋብቻ ከፈፀመችበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በራሷ ጥረት ከባለቤቷ ጋር በባህር ዳር ከተማ ስትኖር ያፈራችው ሀብት ላይ ከባለቤቷ ጋር እኩሌታ የመካፈል መብት እንዳላት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች በባህር ዳር ከተማ በባለቤቷ ስም የተፈራ ንብረት ላይ ሊኖራት የሚችለው መብት በሕጉ አግባብ መሠረት ከባለቤቷ ድርሻ ላይ ብቻ የእኩሌታ መብት እንዳላት በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከአቶ መሐመድ ሁሴን ጋር ጋብቻ መሥርታ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ አ.አ ከተማ እየኖረች ያለች ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በተረጋገጠው ፍሬ ነገር መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ በአመልካች ጥረት ከባለቤቷ ጋር በጋራ የተፈራ ንብረት አለ ከተባለ በዚህ ንብረት ላይ ግማሽ ድርሻ የአመልካች ይሆናል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ በጋብቻ ውስጥ የተፈራውን ንብረት የማጣራት እና የማከፋፈል መርህን አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ምንም መብት ሊኖራት አይገባም ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ የሕጉን መንፈስ ያላገናዘበ እና ፍትሀዊም ሆኖ ስላልተገኘ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም የአመራ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በንብረት ክፍፍል ረገድ ምንም መብት አይኖራትም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17623 በ20/4/ 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 010126 በ01/08/2001 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/መ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪና በአቶ መሐመድ ሁሴን ስም በጋራ በባህርዳር ከተማ ከተፈራው ንብረት ተጠሪ እኩሌታ (50%) ድርሻ ያላት ሲሆን አመልካች ደግሞ ለባለቤቷ ከሚደርሰው ድርሻ ብቻ እኩሌታ ድርሻ ይኖራታል ብለናል፡፡
3. በአመልካችና በአቶ መሐመድ ሁሴን ስም በጋራ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈራ ንብረት ካለ አመልካች እኩሌታ (50%) ድርሻ ያላት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ በባለቤቷ ድርሻ ላይ ብቻ የእኩሌታ ድርሻ ይኖራታል ብለናል፡፡
4. በዚሁ መሠረት የንብረት ማጣራትና ክፍፍል እንዲፈጸም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ግንቦት 5 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 70057
ሕዳር 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ አበበች ቡልቻ
ተጠሪ፡- የለም፡፡
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡ የአሁኑ አመልካች ሟች አቶ በቀለ በዳኔ ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ/ም የተውት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለፍርድ ቤቱ አመልክተው ሚስትነታቸውና የህጻን ግርማ በቀለና አይናለም በቀለ የሟቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የኑዛዜውን ሰነድ በተመለከተ ግን በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ያልተነበበ ነው በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2)"ን" በመጥቀስ ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ሟች ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ሁኖ እያለ ኑዛዜው ስለመነበቡ አይገልጽም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው፣ ፎርማሊቲውን ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሳት አይችልም ነበር በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን በጉዳዩ ላይ ተጠሪም የሌለበት በመሆኑ የአመልካቾችን የቅሬታ ነጥብ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካቾች የሚከራከሩት ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ሁኖ እያለ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት አልተነበበም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ስለሆነም ሟች አቶ በቀለ በዳኔ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል? ወይስ አያሟላም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባቸው ስርዓቶች ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 እስከ 883 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና በተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በውል አዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት የሚደረግ ከሆነ የምስክሮች ብዛት ሁለት በቂ

መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 883 ስር የተመለከቱት የምስክሮችን ችሎታ የሚመለከቱ ሕጋዊያን ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ፣ ሶስት ምስክሮች የፈረሙበት፣ ውል የማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ የፈረመበት፣ ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ በሰነዱ ላይ ስለመገለፁ የማያሳይ እና ተናዛዡ የፈረሙት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881(2) ሥር ከተመለከቱት ስርዓቶች ውስጥ ኑዛዜው በተናዛዡና በምስክሮች ፊት የመነበቡን ሥርዓት ያላሟላ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያሉትም ኑዛዜው ስለመነበቡ አይገልጽም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ኑዛዜው በተናዛዡና በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚያመላክት ነገር የለውም፡፡ አመልካች የሚከራከሩት ደግሞ ኑዛዜው የተደረገው ሶስቱ ምስክሮች ባሉበት ጊዜና ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ ውል የማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት፣ ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ስለሆነ በኑዛዜው ላይ ስለመነበቡ ያለመገለፁ ኑዛዜውን ፈራሽ አያደርገውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ ሲታይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ተከታይ ሁኖ ከኑዛዜ አይነቶች አንዱ ስለሆነው የግልፅ ኑዛዜን ፎርማሊቲነት የሚያወሳ ድንጋጌ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ርዕስ፣ ይዘትና ቅርፅ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ስር ከተመለከቱት የኑዛዜ ፎርማሊቲዎች መካከል ለይቶ ያወጣው የምስክሮችን ቁጥር ብቻ ሁኖ ሁለት ምስክሮች በቂ የሚሆኑበትን አግባብ የሚያሳይ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2) ስር ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ የሚለው ስርዓት ስለመፈጸሙ በኑዛዜው ላይ ያለመገለፅ ውል አዋዋይ ወይም ዳኛ ፊት ለሚደረግ ግልጽ ኑዛዜ በፎርማሊቲ የማይፈለግ መሆኑን የሚገልፅ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ውል አዋዋዩ ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም የምስክሩን ቁጥር በተመለከተ ኑዛዜው በሕጉ የተመለከተውን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው ሊባል ከሚችል በስተቀር በሕጉ የሚፈለገውን የኑዛዜውን መነበብ ሥርዓት ግን ይኸው ይተካል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ውል አዋዋይ ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም የተናዛዡን መሆኑን አይተውና አረጋግጠው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፣ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜው ቃልም የእርሱ መሆኑን ማረጋገጥ ነው የሚለው ምክንያት ሲታይም በሕጉ በግልጽ የተመለከተውን ፎርማሊቲ ወይም የኑዛዜው መነበብ ስርዓት ያለመፈፀምን አስፈላጊ አይደለም ለማለት የሚያስችል አይሆንም፡፡

በመሆኑም ኑዛዜው ለተናዛዡና ለምስክሮች ስለመነበቡ በሰነዱ ላይ ያለመገለፁ ብቻ የኑዛዜ ሰነዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2) እና 882 ስር የተመለከተውን ፎርማሊቲ አያሟላም ተብሎ ፈራሽ እንዲሆን የግድ የሚል ነው፡፡ በአጠቃላይ ከውል አዋዋይ በተጨማሪ ሌሎች ሶስት ምስክሮች በኑዛዜ ሰነዱ ላይ ያሉ ከመሆኑም በላይ በውል አዋዋይ ፊት ቃለ መሐላ የተፈጸመበትና የሰነዱ ይዘት የተረጋገጠ ስለመሆኑ ሰነዱ የሚገልጽ ቢሆንም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ተከታይ በመሆኑና ስለኑዛዜው መነበብ ስርዓት መፈፀም በኑዛዜ ሰነዱ ላይ መገለጽ የግድ የሚል ሕጋዊ ፎርማሊቲ ሁኖ ስለአገኘነው ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ ነው፡፡ የኑዛዜ ፎርማሊቲ ጥያቄ ደግሞ ሰነዱ ለማስረጃነት እስከተጠየቀ ድረስና ከጉዳዩ የክርክር አመራር ሥርዓት አንፃር ሲታይ ፍርድ ቤቱ በራሱ ለማንሳት የሚችለው እንጂ የግድ ከተከራካሪ ወገን ሊነሳ የሚገባው ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካቾች ያነሱት ክርክርም ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሟች አቶ በቀለ

በዳኔ ሕዳር 28 ቀን 2003 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2)፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 857 እና 882 ድንጋጌዎችን ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3412/03 ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16084 ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 16126 ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ሟች አቶ በቀለ በዳኔ ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2) እና 882 መሰረት ፎርማሊቲውን ያሳሟላ በመሆኑ ፈራሽ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

# ውል

የሰ/መ/ቁ. 61331

ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌ-ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን-ነገረ ፈጅ በፍቃዱ መኰንን ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ሚ/ር ጀርመን ግናሆ - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ ጋር ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፈረመ የጽሑፍ ውል ስምምነት ስልክ ቁጥር 200778 አመልካች አስገብቶላቸው ተጠሪ ሲገለገሉበት ከቆዩ በኋላ ያልከፈሉትን ገንዘብ ብር 5,873.20 እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክስ መርምሮ የአመልካች ጥያቄ የአገልግሎት ሂሳብ በየወሩ የሚመጣ እዳን የሚመለከት ነው፣ እንደዚህ አይነት ጥያቄ እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት አመት ሳይከፈል ከቀረ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚል ምክንያት ይዞ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኖታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 10 ቀን 2003 በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ግንኙነቱ ውልን መሰረት ያደረገ ሁኖ እያለ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌ መጠቀሱ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር እና አመልካች የስልክ አገልግሎት ሂሳቡን እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ዋናውና የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ለስልክ አገልግሎት ሂሳብ (ገንዘብ) አግባብነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎቸ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት (not freely rebuttable or rebuttable but in a limited way) የሕግ የህሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ 2024 በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆኑ ክፍያውን (እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌው የስልክ አግልግሎት ሂሳብን ለይቶ አላስቀመጠም፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ ተብሎ በተጠሪ የሚጠቀሰውን በስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው በፍ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌ በፊደል (ረ) ስር የተመለከተው የክፍያ ግምት ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠ ነው፡፡

<u>ቁ. 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው ፡-

(ረ)በብድር ለተሰጠ፤ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ወሰን ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡-

<u>Art. 2024 presumption of payment after two Years</u>

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚወሰንባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል (ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሠጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ

እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው በብድር ለተሠጠ ገንዘብ ወለድ ላይ ሲሆን ዋናውን የብድር ገንዘብ የማይጨምር መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና አቀራረፅ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የብድር ገንዘብንና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይፅፈውም ነበር፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 29181 እና የሠ/መ/ቁጥር 35758 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ አግባብነት የሚኖረው ለብድር ገንዘብ ወለድ እንጂ በዋናው የብድር ገንዘብ አይደለም፣ የስልክ ፍጆታ ሂሳብም ብድር ባለመሆኑ ከመነሻውም ድንጋጌው አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡

ሌላው ስለክፍያ ግምት የሚያወሳው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ጊዜ ማለፍ ክፍያው እንደተፈፀመ ያስቆጥራል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ማለፍ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥርባቸው ሁኔታዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የወርሃዊ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 ድንጋጌ ሲታይም የተከፈለው እዳ ወለዶችን ወይም በተወሰነው ጊዜ የሚከፈሉትን ሌሎች የክፍያ ድርሻዎችን የሚመለከት እንደሆነ የተከፋዩን አይነት ለይቶ ሳይገልጽ ለአንዱ የክፍያ ደረሰኝ የሰጠ ባለገንዘብ ያለፈውንም ድርሻ እንደተቀበለ ይቆጠራል በማለት በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ያስቀመጠ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም ሊታይ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ከመሰረቱ ብድር አይደለም፤ የብድር ባህርይም የለውም፡፡ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ አመልካች ለህብረተሰቡ በሚያቀርበው አገልግሎት መሰረት የሚከፈል ሲሆን መሰረቱም ውል ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው ተጠሪ በውሉ መሰረት ለተጠቀመበት ጊዜ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ እንዲከፈለው ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው መልስ ስለመስጠታቸው የስር ብይን አያሳይም፡፡ በመሆኑም የስልክ አገልግሎቱ ተጠሪ በውል አግባብ ስለመጠቀሙ አመልካች ጠቅሶ የተከራከረ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከውሉና በውሉ መሰረት ደግሞ ተጠቃሹ የስልክ ቁጥር ሂሳብ መጠን በአመልካች ክስ የተጠቀሰውን መጠን ያህል የቆጠረ መሆን ያለመሆኑን በአመልካች የሚቀርበውን ክርክርና ማስረጃ አግባብነት እና ጥንካሬ በመመርመር ተገቢውን መወሰን ሲገባ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ ለብይኑ መሰረት ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለስልክ አገልግሎት ሂሳብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) እና ድንጋጌን መሰረት ማድረጋቸው ያላግባብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 163107 ሚያዚያ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 95515 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ይከፈለኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 መሰረት የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበበት ከሆነ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕሊና ግምት የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ብር 5,873.20 (አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሃያ ሳንቲም) ለአመልካች የሚከፍሉ መሆን ያለመሆኑን፣ የሂሳቡን መጠን የአመልካችን ክርክርና ለጉዳዩ የቀረቡትን ማስረጃዎችን አግባብነትና ጥንካሬ የስር ፍርድ ቤት መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 61913

ጥቅምት 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ እታለማሁ መስፍን - አልቀረበችም

**ተጠሪ** ፡- አጋ አንጼ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል አፈፃፀምን መሠረት በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው በውል የሸጠችልኝን ቤት ስም በስሜ ለማዛወር እንድችል በውሉ መሠረት እንድትፈፅምልኝ ብጠይቃት ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡ፍርድ ቤት ያስገድድልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩልዋ ለክሱ በሰጠችው መልስ በአንድ በኩል ውል አልተደረገም የሚል ክርክር ስታቀርብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ 1723 የተመለከተውን መስፈርት ስለማያሟላ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክራለች፡፡ ክሱ የቀረበለት የሃላባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሁለቱ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የቤቱን ሰነድ እና ማናቸውም ማስረጃ ሁሉ ለተጠሪ ትሰጥ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ይግባኝ በማቅረብዋ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሉ የሕጉን ፎርም አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ ችሎቱም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻር የሃላባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበችበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የአመልካች ክርክር ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ስለመደረጉ እና በዚህ ውል መሠረትም ተጠሪ ቤቱን ተረክቦ በይዞታው ሥር አድርጎት እንደሚገኝ ክሱን በሰማው ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ አመልካችም ብትሆን በአንድ በኩል የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም፤ ቢኖርም የሕጉን ፎርም አያሟላም በማለት ስትከራከር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ ተጠሪ ተረክቦት በይዞታው ሥር መገኘቱን አልካደችም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ቤቱን ሊይዝ የቻለው በኪራይ ነው የሚል መከራከሪያ ወደ መጨረሻው አካባቢ አቅርባ እንደነበር፣ ነገር ግን በዚህ መሠረትም ማስረጃ ማቅረብ እንዳልቻለች በፍ/ቤቱ ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ እንደውሉ እንድትፈፅም የወሰነውም እነዚህን በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

እንደምናየው አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገችው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የበኩልዋን ክስ ወይም የተከሣሽ ከሳሽነት ክስ አላቀረበችም /የፍ/ብ/ሕግ. 1808/2/፡፡ ውሉን መሠረት በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዳስረከበችም ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ተረጋግጦአል፡፡ ተጠሪ ክስ ሊመሰርት የቻለው ለውሉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች እንዲሟሉለት ነው፡፡ እነዚህም ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶች ሲሆኑ፣ በፍ/ቤቶቹ የተወሰነውም አመልካች እነዚህን ሰነዶች እንድትሰጠው ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ የአንድ ነገርን ባለሃብትነት ማስተላለፍን ስለሚመለከቱ ውሎች በተደነገገው አንቀጽ 15 /የፍትሐብሔር ሕጉ/ በተመለከተው ደንብ መሠረት እንደሚመራ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2875 ተመልክቶአል፡፡ በአንቀጽ 15 ሥር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ ለያዝነው ጉዳይ ተገቢነት ካላቸው አንዱ በቁ. 2281 የተመለከተው ሲሆን፣ ይህም ሻጩ የሸጠውን ነገር ባለሃብትነት ለገዢው የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሻጩ የሸጠውን ነገር የማያስነካ መብት ለገዢው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባሮች ለመፈጸም እንዳለበትም ደንጉአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተወሰነበት በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ እንዲፈጽም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሃላባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02925 የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ. 39512 ነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁጥር 61808

ህዳር 7 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፀሐይ ፍቃዱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- አቶ ብቻዬ ተስፋዬ - አልቀረቡም

2- አቶ መሰሉ አዳነ ወኪል ታደሰ አዳነ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሃብትን አንደኛው ተጋቢ ለሌላ ሶስተኛ ወገን የፈፀመውን የሽያጭ ውል የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ ጋብቻቸው ሀምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የፈረሰ መሆኑን ገልፀው በጋብቻ ወቅት ያፈራነውን በኦሮሚያ ክልል በባቱ ከተማ ያፈራነውን ቤት አንደኛ ተከሣሽ /አንደኛ ተጠሪ/ ለሁለተኛ ተከሣሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ያለእኔ ፈቃድና ስምምነት ሸጧል፡፡ ቤቱ መሸጡን ያወቅሁት ነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ያለፈቃድና ስምምነቴ አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ ያደረገው ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ቤቱን 1994 ዓ.ም ለአቶ መስፍን ዝንቱ አስተላልፌዋለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁት በከሣሽ ፈቃድና ስምምነት ነው፡፡ ቤቱን እኔ ለሁለተኛው ተከሣሽ /ለሁለተኛው ተጠሪ/ አልሸጥኩም ቤቱ በሁለተኛ ተከሣሽ ስም ስለተዛወረ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛው ተከሣሽ ቤቱን መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል በመሸጡ የቤቱ ስመሀብት ወደ ሁለተኛው ተከሣሽ የተዛወረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አንደኛ

ተከሣሽ ቤቱን ለሁለተኛ ተከሣሽ አልሸጥኩም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ቤቱ በገኘው በሁለተኛው ተከሣሽ ስም የተዛወረ በመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1806 ውሉ ቀሪ ስለሆነ ከሣሽ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችንና የአንደኛ ተጠሪን ክርክር ከሰማ በኂላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች ቤቱን ያለ እኔ ፈቃድና ስምምነት አንደኛው ተጠሪ ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠ በመሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ንብረቱ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህንን ካጣሩና ካረጋገጡ በኂላ ውሉ ተፈፅሞ የቤቱ ስመሀብት በሁለተኛ ተጠሪ ስም የተዛወረ በመሆኑ ውሉ ቀሪ ስለሆነ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም በማለት የሰጡት የህግ ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የተሸጠው 1994 ዓ.ም ለአቶ መስፍን ዝንቱ ነው፡፡ ከእጃችን ከወጣ ስምንት ዓመት ሆኖታል፡፡ ስለዚህ የአመልካች መቃወሚያ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካች ገንዘብ ይገባኛል በማለት አላቀረበችም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ሀምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን መጥሪያ በአግባቡ አላደረሰችልንም፡፡ ቤቱን አንደኛ ተጠሪ 1994 ዓ.ም ለአቶ መስፍን ዝንቱ በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ ከዚያ በኂላ ለአቶ መስፍን ዝንቱ ባልቻ አንደኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ውክልና መስከረም 9 ቀን 2000 ዓ.ም. ከአንደኛ ተጠሪ ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በኂላ እኔ ከአቶ ዝንቱ ባልቻ ቤቱን የገዛሁት በመሆኑ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር ክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ወቅት የተፈራው የጋራ ንብረት አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተዋዋለው ውል ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ቤቱ በሁለተኛው ተጠሪ ስም ተመዝግቦ ቀሪ ስለሆነ ውል ይፍረስልኝ ብሎ ለመጠየቅ አይችልም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን መሠረታዊ ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ሁለተኛ ተጠሪ በሰበር ችሎት ያቀረባቸውን ክርክሮች ተገቢነት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ጉዳዩ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሌለሁበት የታየው አመልካች በአግባቡ መጥሪያ ስላላደረሰችኝ ነው በማለት የሰበር መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሌለሁበት የታየው አላግባብ ነው የሚል ከሆነ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለሚመለከታቸው ፍርድ ቤቶች ከሚያቀርቡ በስተቀር ይህንን ነጥብ የሰበር መከራከሪያ አድርገው ማቅረባቸው ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ክርክር ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንደኛው ተጠሪ ቤቱ የተሸጠው 1994 ዓ.ም አመልካች አውቃና ፈቅዳ ነው፡፡ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ የሸጥኩት እኔ ሳልሆን አቶ ዝንቱ ባልቻ ነው በማለት ያቀረበው የፍሬ ጉዳይ ክርክር ዕውነትነት የሌለው መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ በወኪሉ አቶ ዝንቱ ባልቻ በኩል ለሁለተኛው ተጠሪ ቤቱን መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሸጠ መሆኑን ከባቱ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተላከለትን ማረጋገጫና በሌሎች ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን በመግለፅ ቤቱን ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠለት አንደኛ ተጠሪ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልተከራከረበትንና ሁለተኛው ተጠሪ በሌለበት ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የደረሰበትን መደምደሚያ ትክክል እንዳልሆነ በመዘርዘር ለሰበር ችሎት የሰጠው መልስ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ የሚጥስና ለዚህ ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ ሀምሌ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ በመጀመሪያው ገፅ ሁለተኛው ፖራግራፍ ቤቱን የገዛው አንደኛ ተጠሪ ቁጥሩ 4039/1/2000 በሆነና መስከረም 9 ቀን 2000 ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ልዩ የውክልና ሥልጣን ከሰጠው ከአቶ ዝንቱ ባልቻ መሆኑን ግልፅ አድርጎታል፡፡ አንድ ተወካይ ከወኪልነቱ ሥልጣን ወሰን ሣያልፍ በሌላ ሰው ስም የመዋዋል ተግባሮች የፈፀመ እንደሆነ በእሱ የተፈፀሙት ተግባሮች በቀጥታ በሿሚው እንደተፈፀመ እንደሚቆጠሩ በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2189 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑ አቶ ዝንቱ ባልቻ ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በአንደኛው ተጠሪ እንደተፈፀመ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ወቅት የተፈራውን የጋራ ንብረት ያለአመልካች ፈቃድ ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠው አንደኛው ተጠሪ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት የሌለውና ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካችና አንደኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ ያፈሩትንና በኦሮሚያ ክልል በባቱ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን ቤት አንደኛ ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የውል ሰነድ ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ የሸጠው በወኪሉ አቶ ዝንቱ ባልቻ በኩል በመሆኑና አመልካች አቶ ዝንቱ ባልቻ የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት እንዲሸጥ እንዲለወጥ ውክልና ያልሰጡ በመሆኑና ቤቱ ሲሸጥ ፈቀዳቸውን ያልሰጡ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው የቤቱ ስመሀብት በሁለተኛው ተጠሪ ስም የተዛወረ መሆኑን የባቱ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ የአንድ ውል መፈፀም ውሉን ቀሪ የሚያደርገው በመሆኑ አመልካች ውሉ በሙሉ በመፈፀሙ ምክንያት ቀሪ የሆነ ውል ፈራሽ እንዲባል ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለትና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡት ግዴታ ቀሪ የሚሆንበትን መሠረታዊ ምክንያት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በህግ አግባብ ያቋቋሙት ውል በመካከላቸው ሕግ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731/1/ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች አንዳቸው ለሌላው በዉል የገቡት ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከፈፀሙ ውሉ

እንደ ህግ ሆኖ ተዋዋዮቹን ማስገደዱ ቀሪ የሚሆን መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው ተዋዋዮች በውሉ የገቡት ግዴታ ቀሪ የሚሆንበትን /Extinction of contract " ምክንያት ከሚሆኑት ነገሮች አንደኛውን የሚደነግግ ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ተዋዋይ ወገኖች የተዋዋሉትና ሙሉ በሙሉ ግዴታቸውን የፈፀሙበት ውል የእኔን መብትና ጥቅም የሚነካና ህጋዊ ዉጤት ሊሰጠው የሚገባ ውል አይደለም፡፡ ስለዚህ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ይወሰንልኝ የሚል ጥያቄ የሚያቀርቡ ሶስተኛ ወገኖች የውሉን ህጋዊነት በመቃወም ውሉ እንዲፈርስ ከመጠየቅ የሚገድብ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች አንደኛው ተጠሪ የጋራ ሀብቴ የሆነውን ቤት ያለእኔ ስምምነት ለሁለተኛው ተጠሪ ሸጧል፡፡ ስለዚህ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ቤቱ በገዥው በሁለተኛው ተጠሪ ስም መመዝገቡ የማያግዳት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ህጉ ስለውሉ ታውቆ መቅረት ለተደነገገው ክፍልና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1806 የተዛባ ትርጉም በመስጠት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. አንደኛ ተጠሪ ቤቱ የተሸጠው በአመልካች ስምምነት ነው፡፡ ቤቱ በ1994 ዓ.ም ከአቶ መስፍን ዝንቱ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ዕውነትነት የሌለው መሆኑንና ቤቱ አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የውል ሰነድ የተሸጠ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ የፈረሰው ሀምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠ የፍች ውሣኔ መሆኑንና የቤቱን መሸጥ ያወቀችው ነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበችው የክስ ማመልከቻ ገልፃለች፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገውን ቤቱ በአመልካች ስምምነት 1994 ዓ.ም ተሸጧል የሚለውን መከራከሪያ ከማቅረቡ ውጭ አመልካች አንደኛ ተጠሪ በወኪሉ ዝንቱ ባልቻ በኩል ለሁለተኛው ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የውል ሰነድ የሸጠ መሆኑን እንደምታውቅ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የሌለ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል በፍርድ ፈራሽ እንዲሆን ክስ ያቀረበችው ታህሣሥ 4 ቀን 2001 ዓ.ም. በመሆኑ ይኸም አመልካች ውሉ መፈፀሙን ካወቀችበት ከነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከአራት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ያሣያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉ ከተፈፀመበት መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ዐመት ከሶስት ወራት ውሉ እንዲፈርስ ክስ ያቀረበች መሆኑን ያሣያል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አንደኛ ተጠሪ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ያቀረበችው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር የተሻሻለውን የቤተሠብ ህግ አንቀፅ 69 ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን በባቱ ከተማ 01 ቀበሌ በአንደኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረው ቤት አመልካችና አንደኛ ተጠሪ በጋብቻ ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ይህንን የጋራ ሃብት ያለአመልካች ስምምነት ለሁለተኛው ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ውል የሸጠው የተሻሻለው የቤተሠብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 69 ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ የጋራ የሆነውን የንብረት ያለአመልካች ፈቃድ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመሸጥ የፈፀመው ውል ፈራሽና አመልካች ላይ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለው ነው ብለው መወሰን ሲገባቸው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ድንጋጌ በመጥቀስ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አንደኛ ተጠሪ የአመልካች የጋራ ሃብት የሆነውን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ባቱ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ለሁለተኛው ተጠሪ ለመሸጥ አመልካች ሣታወቅና ሳትስማማ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም በወኪሉ አማካኝነት የተዋዋለው ውል ፈራሽ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ በመሆኑ አመልካች በቤቱ ላይ ያላትን የጋራ ባለሀብትነት መብትና ድርሻ የመጠየቅ መብት አላት በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 62162
ሕዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ መትከል ልምዓት ሁለገብ መ/ህ/ስ ማህበር

ተጠሪዎች፣ ቄስ ካላዩ ኪሮስ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በብድር የተሰጠን ገንዘብ ይመለስ በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የስሃርቲሳምሬ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን የከሰሰው ታህሳስ 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የውሃ ሞተር ዋጋው 4900.00(አራት ሺኅ ዘጠኝ መቶ ብር) በ9% ወለድ ስሌት ለአራት አመት ጊዜ ከፍለው እንዲጨርሱ ፣ጊዜው ካለፈ ግን በ18% ወለድ ስሌት እንዲከፍል በአይነት በብድር ውል የሰጣቸው መሆኑን፣ተጠሪ በጊዜው ሊከፍለው ያለመቻሉን ገልጾ ተጠሪ ዋናውን ገንዘብ ብር 4900.00 በ9% ብር 1764.00፣ጊዜው በማለፉ ደግሞ በ18% ወለድ ብር 1499 በጠቅላላው ብር 8163.00(ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ብር) እንዲከፍለው ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ውሉ ስለመኖሩና የመክፍያ ጊዜው ስለማለፉ አምነው ወለዱን በተመለከተ ግን አስተያየት እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤትም ተጠሪን ለገንዘቡ ያለመመለስ ኃላፊ አድርጎ የኃላፊነታቸውን መጠን ግን ዋናው ገንዘብ በ9% ወለድ ታስቦ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የወለድ መጠኑ 18% መሆን ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች 9% ብቻ በማለት የወሰኑት የፌዴራሉን አዋጅ ቁጥር 147/1991፣402/1996 እና በክልሉን አዋጅ ቁጥር 145/2000 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ዋናውን የብድር ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር ብቻ እንዲከፍሉ በበታች ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀፅ 34(2) እና አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 5 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ከአመልካች በውል የተበደሩት ገንዘቡ በአራት አመታት ውስጥ የሚመለስ ሁኖ በዚህ ጊዜ የሚታሰብ የወለድ መጠን 9%፣ጊዜው ካለፈ ደግሞ ወለዱ 18% እንደሚሆን መስማማታቸውን የብድር ውሉ የሚያረጋግጠው ጉዳይ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ ስምምነት የሚክዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የወለድ መጠኑ 9% እንዲሆን የወሰኑት አመልካች አግባብነት ያላቸውን የማህበራት ሕጎችን መሰረት አድርጎ ክርክሩን አቅርቦ እያለ በማለፍ ነው፡፡

በመሰረቱ በሕግ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሕግን ያህል አስገዳጅነት ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡አንድ ውል ሕጋዊ ነው ለማለት ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678 ስር የተመለከቱትን የውል አቋሞችን ማሟላት ይገባዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚፀና ውል ነው ለማለት የሚቻለው ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፣በቂ የሆነ እግጠኛነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ እና በሕጉ የሚፈለገው የውሉ አፃጻፍ ፎርም መሟላት አለባቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ የወለድ መጠኑ 18% ሊሆን ይገባል ተብሎ በአመልካች የተጠየቀው ዳኝነት ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡አመልካች ይህንኑ የዳኝነት ጥያቄ ሕጋዊ ነው በማለት በዋቢነት የሚጠቀሰው የማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) እና አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 5 እንዲሁም የክልሉን የማህበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000ን ነው፡፡

በበኩላችን እንደአየነው በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) ስር አንድ ማህበር ላበደረው ገንዘብ የሚያገኘው ወለድ ከባንክ የማበደሪያ ወለድ ሊበልጥ አይችልም በሚል በሃይለ ቃል የተቀመጠ የነበረ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 402/1996 ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) ስር ተቀምጦ የነበረው ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ መሻሩን በአንቀጽ 5 ስር አስፍሯል፡፡ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 147/1991ን ለማስፀፈም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 106/1996 በአንቀጽ 11 እና 14 ድንጋጌዎች ስር ከአስቀመጣቸው ሁኔታዎች የብድር አሰጣጥ ስርኣት በማህበሩ መተዳደሪደያ ደንብ ሊወሰን እንደሚችል መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ የማህበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000ም ተመሳሳይ ይዘት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሕጉ ረገድ ያለው ማዕቀፍ ይህን የሚመስል ከሆነ አመልካች ከተጠሪ የ18% ወልድ ጥያቄ ያቀረበው በሕጉ አግባብ የተመሰረተው መተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድ መሆኑንና ይህንኑም ተጠሪ አውቀው ግዴታ የገቡ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ከተጠሪ 18% ወለድ የማይጠይቅበት እና ተጠሪም በገቡት ግዴታ መሰረት የማይወጡበት ወይም 18% ወለድ የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በዋናው ገንዘብ 9% ወለድ ብቻ ነው ሊከፍሉ የሚገባው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሰሃርቲሳምሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 004448 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡባዊ ምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02682 ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. እንዲሁም በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 40515 መስከረም 21 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. ከአመልካች ጋር በተደረገው የብድር ውል ተጠሪ የብድር ጊዜው ካለፈ በሁዋላ የሚታሰበው ወለድ 18% ነው ብለናል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ በጠቅላላው ለአመልካች ብር 8163.00(ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ብር) ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 57280

ጥር 3 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡-1. ሴንትራል ቬኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር } ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ላሉት

2. ወ/ሮ ሸዋወንድም ተስፋዬ } አመልካቾች ጠበቃ አቶ ዘላለም

3. አቶ ዳዊት ከበደ } ክፍሌ ቀረቡ

4. የወ/ሪት ነጠረች ከበደ ወራሽ ወ/ሮ አስገደች አበበ ጠበቃ ቸርነት ወርዶፋ ቀረቡ

**ተጠሪዎች** ፡-1. አቶ ሰለሞን ከተማ } ጠበቃ አቶ ጥላሁን

2. አል-ሳልቫቶር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር } ደስታ ቀረቡ

ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና የአራተኛ አመልካች ወራሽ ወ/ሮ አስገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነትና በዕርቅ ስምምነቱ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27497 መጋቢት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልካቾች በጋራ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሆቴል ንግድ ድርጅትና የሕንፃ ሽያጭ ውልን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ አመልካቾች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የሴንትራል ቬንዩ ሆቴልን ከነመገልገያ ዕቃዎቹና ህንፃው ልንሸጥላቸው በፅሑፍ ውል ተዋውለናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ቀብድ ከከፈለ በኋላ ቀሪውን ግዴታውን እንዲወጣ በሰጠነው ማስጠንቀቂያ መሠረት ግዴታውን ባለመወጣቱ ውሉን ሰርዘነዋል፡፡ ስለዚህ ሆቴሉን ከነመገልገያ ዕቃዎቹ እንዲያስረክበን፣ በውሉ መሠረት ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ መቀጫ እንዲከፍለን፣ የሆቴሉን ስም በመቀየር ላደረሰው ጉዳት ክስ የማቅረብ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ በክርክሩ አራተኛ አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች ሆነው ገብተዋል፡፡ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ እና ሁለተኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ አለመፈፀም በኃላፊነት የሚጠየቁት ከሳሾች ናቸው፡፡ እኛ በውሉ በገባነው ግዴታ መሠረት ብር 6,450,000 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ

ሀምሣ ሺህ ብር/ ዕዳ ከፍለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ወስኖ ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪዎችና የአመልካቾችን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 32299 ከሰማ በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27497 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣

1. የሥር ከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ሽዋወንድም ተስፋዬ /ሁለተኛ አመልካች/ እና አቶ ዳዊት ከበደ /ሶስተኛው አመልካች/ ውሉን በተናጠል ሰርዘነዋል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?

2. የውሉ መሠረዝ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

3. የሥር ጣልቃ ገብ የነበረችው ወ/ሮ ነጠረች ከበደ /አራተኛ አመልካች/ ውሉ እንዲፈረስ ለመጠየቅ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? መብት አላቸው ከተባሉ መብታቸው በምን ሁኔታ መከበር አለበት የሚሉትንና ሌሎች ከውል መሠረዝ ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተጨማሪ ነጥቦች በመመልከት ውሣኔ ይሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሶታል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 32299 ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ በመሠረታቸው ጭብጦችና ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቾች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችሉበት ሁኔታ የለም በማለት ወስኗል፡፡ በሁለተኛው ጭብጥ አመልካቾች ውሉን በፍርድ ቤት ውሣኔ ለማሰረዝ የሚያስችል ምክንያት ያለ ስለመሆኑ በፍሬ ጉዳዩ ደረጃ አላስረዱም ውሉ ያልተፈፀመው በአመልካቾች ቀሪ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ባለመሆኑ ሻጮች /አመልካቾች/ ውሉን በፍርድ ለማስረከብ የሚያስችል የሕግም ሆነ የፍሬ ጉዳይ መሠረት የላቸውም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አራተኛ አመልካች የሟች ወራሽ መሆናቸው የተረጋገጠው ንብረቱ በውል ከተላለፈ በኋላ በመሆኑ ድርሻዋን ከሻጮች ከምትጠይቅ በቀር ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ አትችልም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት አላት ቢባል እንኳን ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት መመለስ አይቻልም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43165 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡

አመልካቾች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንደኛው ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታውን እንዲወጣና ቀሪውን ክፍያ እንዲከፍሉ መስከረም 27 ቀን 1998 ማስጠንቀቂያ የሰጡት ቢሆንም ተጠሪ ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ውሉን በተናጠል ሰርዘውታል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚያስችላቸው ሁኔታ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሆቴል ድርጅቱን ህንፃውን በሆቴሉ ላይ ካለው ዕዳና

የሠራተኛ ዕዳ ጭምር ገዝቷል፡፡ ገዥ ለሻጮች ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ለመክፈል ከተስማማ በኋላ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ቀብድ ከፍሎ ቀሪውን ሰማኒያ ፐርሰንት ክፍያ ያልፈፀመና ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑና በእኛ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሉን በፍርድ ቤት ውሣኔ ለመሰረዝ የሚያበቃ ሁኔታ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1983/1/ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና በሰበር ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

አራተኛ አመልካችን በተመለከተ አከራካሪው ንብረት ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ባለበት ሁኔታ ያለ አራተኛ አመልካች ፈቃድና ስምምነት ንብረቱን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ እንደማይችል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1060 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1266 ተደንግጎ እያለና፣ አራተኛ አመልካች የሟች ወራሽ ናቸው ተብለው የሚያዙት ሟች ህይወት ካለፈበት ቀን ጀምሮ መሆን ሲገባው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አትችልም ተብሎ መወሰኑ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሉን አፍርሶ ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት ለመመለስ አይቻልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ምክንያት ስህተት ያለበት ነው፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ኅዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችሉ ስለመሆኑ በሽያጭ ውሉ በግልፅ አልተመለከተም፡፡ ገዥ ቀሪውን ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ ለመክፈል የውል ግዴታ የገባው የንብረቱ ስመ ሀብት ወደ ገዥ ሲዛወር መሆኑ በውሉ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በጠየቅነው ጊዜ ቀሪውን ዋጋ ስላልከፈለን ውሉን ሰርዘናል በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካቾች ኅዳር 23 ቀን 1998 ዓ.ም ለሰጡት ማስጠንቀቂያ ተጠሪዎች ኅዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም በፅሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም ይባልልን፡፡ የሆቴል ድርጅቱ ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት አመልካቾች የሚከራከሩት ተጠሪዎች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ፈፅመዋል በማለት ነው፡፡ አመልካቾች ገዥ የሽያጩን ሰማኒያ ፐርሰንት ዋጋ አልከፈለም በማለት የሚከራከሩት ገዥ በሁለት ባንኮች ይፈለግ የነበረውን ስምንት ሚሊዮን ብር /ብር 8,000,000/ ዕዳ የከፈለ መሆኑንና ሌሎች የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክና የመሳሰሉት ውዝፍ ዕዳዎች በመክፈል በውሉ የገባውን ኃላፊነት የተወጣ መሆኑን ወደ ጎን በመተው ነው፡፡ ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን ከዘጠና ፐርሰንት በላይ የተወጡ ሲሆን አመልካቾች የሰጡትን ውክልና በመሻር የንብረቱ ስመ-ሀብት ወደ ገዥ እንዳይዘወር እንቅፋት በመፍጠር ኃላፊዎች ናቸው፡፡

ሟች አቶ ከበደ ጠቅላላ ንብረታቸውን ለሁለተኛ አመልካችና ለሶስተኛ አመልካች በኑዛዜ ሰጥተው የሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛው አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሾች መሆናቸው በመዝገብ ቁጥር 1262/90 ኅዳር 2 ቀን 1999 ዓ.ም በፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ አራተኛ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ የሁለተኛና የሶስተኛ አመልካቾች የኑዛዜ ወራሽነት አላሰረዙም፡፡ ተጠሪዎች የግዥ ውል የፈፀሙት ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች የሟች ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ በፍርድ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አራተኛ አመልካች የሟች ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው ያቀረቡት ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ ከስምንት ዓመት በኋላ ሲሆን በክርክሩ ሂደት ንብረቱ ላይ የሰጡት የእግድ ትእዛዝ የለም፡፡ ስለዚህ አራተኛ አመልካች ቀደም ብሎ በፍርድ ቤት በተሰጣቸው ማስረጃ መሠረት ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች የፈፀሙትን የሽያጭ ውል እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሥር

ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማፅናት እንዲያሰናብተን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው፡-

1. ተጠሪዎች ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል መሠረት ግዴታቸውን እንዲፈፅሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸው ግዴታቸውን ያልፈፀሙ በመሆኑ ውሉን በተናጠል ሰርዘነዋል በማለት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የመጀመሪያው ጭብጥ የሚታላለፍ ቢሆን፣

2. ተጠሪዎች መሠረታዊ የውል መጣስ ተግባር የፈፀሙ በመሆኑ ውሉ በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

3. አራተኛ አመልካች ሟች ወ/ሪት ነጠረች ከበደን በመተካት በሰበር ተከራካሪ የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት ተመዝግቦ ሕጋዊ ውጤት ሊሰጠው ይገባል ወይስ አይገባም?

4. አራተኛ አመልካች የነበሩት ወ/ሪት አበራች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የእኔ የጋራ ሀብት የሆነውን የንግድ ድርጅትና ህንፃውን ለአንደኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተዋዋሉት ውል እኔ ያልተስማማሁበት በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት ያቀረበችውን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሳይቀበለው መቅረቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ጭብጦች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ካረጋገጣቸው ፍሬ ጉዳዮችና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በመመርመር ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የመጀመሪያው ጭብጥ ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 32299 ሲመልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አጣርቶ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ከመሠረታቸው ጭብጦች አንደኛውና የመጀመሪያው ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ አመልካቾች ተጠሪዎች ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው የንግድ ድርጅትና የሕንፃ ሽያጭ ውል በገቡት ግዴታ መሠረት ቀሪውን ክፍያ ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ በአእምሮ ግምት በቂ ነው ባልነው በአስር ቀን ውስጥ እንዲፈፅሙ መስከረም 27 ቀን 1998 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸዋል፡፡ ተጠሪዎች በውሉ መሠረት ክፍያ ያልፈፀሙ በመሆኑ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ውሉን በተናጠል የሰረዝነው መሆኑንና ይህንም በፍታብሔር ህግ የተደነገገ መሆኑን በማንሣት ያቀረበውን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው አላግባብ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች በውል በገቡት ግዴታ መሠረት የሸጡትን የንግድ ድርጅትና ህንፃ ስመ ሃብት ወደ ገዥዎች እንዲዛወር ተገቢውን ተግባር አልፈፀሙም፡፡ ለውሉ አለመፈፀም በኃላፊነት የሚጠየቁት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሰስተኛ አመልካቾች በመሆናቸው ውሉን በተናጠል የመሠረዝ መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመርህ ደረጃ በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሚቻቸው ሰዎች ላይ ሕግ በመሆናቸው ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡትን ግዴታ የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በሕግ አግባብ ያቋቋሚቻቸው ውሎች ተገዥ የመሆንና ግዴታቸውን በታማኝነት የመፈፀም ኃላፊነት

ያለባቸው በመሆኑ ህጉ ተዋዋይ ወገኖች በህግ መሠረት ያደረጉትን ውል አንደኛው ወገን በፈለገው ጊዜ የፈለገውን ምክንያት እየሰጠ ውለታውን እንዲሰረዝ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ በህግ አግባብነት የተቋቋመን ውል አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችለው በሕግ በግልፅ ከተመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ አንድ ውልን ለመሰረዝ የሚያስችል ልዩ ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በህግ የተደነገገው ውልን ለመሰረዝ በሚያስችል ልዩ ምክንያት ውሉን የሰረዘ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ውሉን በተናጠል ሰርዠዋለሁ የሚለው ተዋዋይ ወገን ነው፡፡

በአገራችን አንደኛው ተዋዋይ ወገን ውሉን በተናጠል ሊሰርዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍታብሔር ሕግ ውልን ስላለመፈፀም በሚደነግገው ክፍል ተዘርዝረዋል፡፡ ስለሆነም በአገራችን አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ውል ሊሰርዝ የሚችለው ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንደኛው ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተከታታይነትና ተያያዥነት ያላቸውና አንደኛው ተዋዋይ በተናጠል ውልን ሊሰርዝ ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች የሚደነግጉ መሆኑን የድንጋጌዎቹን አቀራረፅና ህግ አውጭው ለድንጋጌዎቹ የሰጠውን ተከታታይነት ያላቸው ተራ ቁጥሮች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ "በአንድ ወገን ብቻ የሚደረግ የውል ማፍረስ" የሚል ጠቅላላ ርዕስ የተሰጠው

- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786 ተራ ቁጥር 1 "የውል ማፍረሻ የሆኑ ቃሎች" በሚል

  ርእስ ሥር አንደኛውን የውል ማፍረሻ (መሠረዥያ) ምክንያትን የሚደነግግ ሲሆን

- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 በተራ ቁጥር 2 "ቁርጠኛ የሆነ የውል መፈፀሚያ"

- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1788 በተራ ቁጥር 3 "መፈፀም አለመቻል"
- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 በተራ ቁጥር 4 "መፈፀምን እንቢ ስለማለት"

በሚል ርዕስ አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ውል ሊሰርዝ የሚችልባቸውን ልዩ ሁኔታዎች ደንግገዋል፡፡ አመልካቾች ውሉን በተናጠል ሠርዘነዋል ብለው የሚከራከሩት ተጠሪዎች በውል የገቡትን ግዴታ በአስር ቀናት ውስጥ እንዲፈፀሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸው፣ በተሰጣቸው አስር ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን ያልፈፀሙ በመሆኑ ውሉን ሠርዘነዋል በማለት ነው፡፡ ይህ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሚያነሱት ክርክር አግባብነት ያለው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ በመሆኑ ሌሎቹን ማለትም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1788 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ድንጋጌዎችን ዝርዝር ይዘትና ትርጉም መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም፡፡

"ቁርጠኛ የሆነ የውል መፈፀሚያ ጊዜ" የሚል ርዕስ ያለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1787 ዝርዝር ይዘት ስንመለከተው "በውሉ ላይ አንድ ግዴታ መፈፀሚያ ሆኖ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ፤ ወይም ማስጠንቀቂያ በተሰጠበት ጊዜ በአእምሮ ግምት ይበቃል ተብሎ በተሰጠው ቀን ወይም በዳኛ በተሰጠው የችሮታ ጊዜ ውስጥ ከተዋዋይ አንደኛው ወገን የገባው ግዴታ ሳይፈፀም የቀረ እንደሆነ ውሉ ይፍረስልኝ የሚለው ወገን ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው የማፍረስ መብት አለው" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ "A party may cancel the contract where the other party has failed to perform his obligation with in the

period of time fixed in accordance with art 1770, 1774 or 1775 (b) " በሚል መንገድ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅጅ ለመረዳት እንደሚቻለው አንደኛው ተዋዋይ ወገን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ውልን በተናጠል ለመሠረዝ የሚቻለው ከሚከተሉት ሶስት ሁኔታዎች አንደኛው የተሟላ መሆኑን ለማስረዳት ሲችል ነው፡፡

የመጀመሪያ ባለዕዳው በውሉ ላይ በተመለከተው መሠረት የውሉን ግዴታ የሚፈፀምበት ቁርጠኛ ጊዜ በውሉ ላይ በግልፅ ተመልክቶ እንደሆነና በውሉ ላይ የተገለፀው ቁርጥ የሆነ የውል መፈፀሚያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ውሉን ለመሰረዝ የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1775(ለ) ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ባለዕዳው ውሉን ያልፈፀመበትን ምክንያትና ሌሎች የአካባቢ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ዳኞች ባለዕዳው ውሉን የሚፈፅምበት የችሮታ ጊዜ ከሰጡት በኋላ ባለእዳው በዳኛ ወሣኔ በተሰጠው የችሮታ ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ሣይፈጽም የቀረ እንደሆነ መሆኑን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1770 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሶስተኛውና አመልካቾች መከራከሪያ ያደረጉት ባለገንዘቡ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774 በተደነገገው መሠረት ሌላኛው ተዋዋይ (ባለዕዳው) በውል የገባውን ግዴታ የሚፈፅምበትን ጊዜ በመግለፅ ማስጠንቀቂያ የሰጠ ሲሆንና በማስጠንቀቂያው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይፈፅም ሲቀር መሆኑን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አንደኛው ተዋዋይ ሌላው ወገን በውል የገባውን ግዴታ እንዲፈፅም በአእምሮ ግምት በቂ ነው የሚለውን የውል መፈፀሚያ ጊዜ ግልፅ ማስጠንቀቂያ ለመስጠትና በማስጠንቀቂያው የተገለፀው የውል መፈፀሚያ ሲያልፍ ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችለው እሱ በበኩሉ ምን ምን ተግባራትን ፈፅሞ ነው? የሚለው ነው፡፡

አንደኛው ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ መሠረት እንዲፈፅም ለመጠየቅና ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የሚችለው በመጀመሪያ እሱ የበኩሉን ግዴታ የፈፀመ ወይም ለመፈፀም የተዘጋጀ ሲሆን እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1857 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማና ግብ እንደዚሁም የድንጋጌው የተፈፃሚነት ወሰን ለመረዳት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1757 ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው አንደኛው ተዋዋይ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 ሌላኛው ተዋዋይ ውሉን እንዲፈፅምለት ለመጠየቅ፤ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774 ድንጋጌዎች መሠረት የውል መፈፀሚያ ጊዜ ግልፅ ማስጠንቀቂያ በመስጠትና በፍታብሔር ቁጥር 1787፣ በተደነገገው መሠረት ውሉን በተናጠል ለመሠረዝ በመጀመሪያ በእሱ በኩል በውል የተጣለበትን ግዴታ የፈፀመ ወይም ለመፈፀም ዝግጁ መሆኑ በማስረጃ ለማረጋገጥ የቻለ መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1757 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌዎችን ይዘትና መሠረታዊ ግብ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሕግ አውጭው በውል ለገባው ግዴታ ተገዥ በመሆን በእሱ በኩል ያለውን ግዴታ ያልፈፀመ ወይም ለመፈፀም ዝግጁ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ ያልቻለ አንድ ተዋዋይ ወገን ሌላኛውን ተዋዋይ ወገን ቀድሞ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን በተናጠል እንዲሰርዝ በማሰብ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌን አውጇል ተብሎ አይገመትም፡፡ አንድ ተዋዋይ የውሉን መፈፀሚያ የጊዜ ገደብ በመግለጽ

ለሌላኛው ወገን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውል በተናጠል ለመሰረዝ የሚችለው በመጀመሪያ እሱ በውሉ የገባውን ግዴታ የፈፀመ ወይም ለመፈፀም ዝግጁ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከተጠሪዎች ጋር ባደረጉት የንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል መሠረት የበኩላቸውን ግዴታ አሟልተው ያልፈፀሙ መሆኑንና በተቃራኒው ውሉ እንዳይፈፀም የተለያየ ችግሮችን የፈጠሩ መሆኑን ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማረጋገጥ በውሣኔው አስፍሯል፡፡

በመሆኑም አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች በውሉ የገቡትን ግዴታ አሟልተው ያልፈፀሙና ውሉ በአግባቡ እንዳይፈፀም የተለያዩ ችግሮችን የፈጠሩ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ፣ ተጠሪዎች በአስር ቀን ውስጥ በውሉ መሠረት ግዴታቸውን እንዲፈፀሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ግዴታቸውን ያልተወጡ በመሆኑ ውሉን በተናጠል ሠርዘነዋል በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1757 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያልተከተለና የህግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ውሉን በተናጠል የሚሠርዙበት የሕግና የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ሁለተኛው ጭብጥ አንደኛ፤ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ተጠሪዎች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ስለፈፀሙ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሉ እንዲሰረዝ ውሣኔ አለመስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡትን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በአንደኛ ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ዳኞች በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል እንዲሰረዝ ውሣኔ የሚሰጠባቸው ሁኔታዎች በፍታብሔር ህጉ ተደንግገዋል፡፡ ይኸውም ውልን በፍርድ ስለማሰረዝ የሚል ርዕስ ያለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 አንደኛው ተዋዋይ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግዴታዎቹን ያልፈፀመ እንደሆነና ወይም የፈፀማቸው ሙሉ ወይም ፍፁም ባልሆነ አኳኋን እንደሆነ ዳኞች በአንደኛው ወገን ጠያቂነት ውሉን ሊያስቀሩት እንደሚችሉ ለዳኞች የሕሊና ሚዛን ፈቃድ ሥልጣን በሚሰጥ አኳኋን የሚደነግግ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 በይዘቱ ፈቃጅ የሆነ የህግ ድንጋጌ በመሆኑ ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ ሣይወስኑ ሊያልፉ የሚችሉ መሆኑንም የሚያመለክት ድንጋጌ ነው፡፡

በአንፃሩ ዳኞች በአንደኛው ወገን ጠያቂነት ውል እንዲሰረዝ ውሣኔ ከመስጠታቸው በፊት የተዋዋዩቹን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሠረት ማድረግ እንደሚገባቸው በውሉ ላይ አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልተደረገ በስተቀር ዳኞች ውሉ እንዲሰረዝ ውሣኔ መስጠት እንደሌለባቸው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ይደነግጋሉ፡፡ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካች ውሉ በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት የሚከራከሩት ተጠሪዎች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ፈፅመዋል በማለት ምክንያት በመሆኑ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በተዋዋሉት ውል የተጠሪዎች ግዴታና ኃላፊነት ምንድን ነው? ተጠሪዎች በውሉ የገቡት ግዴታ ምን ያህል ፐርሰንቱን ፈፅመው ምን ያህል ፐርሰንት ይቀራቸዋል? ተጠሪዎች ቀሪውን ግዴታቸውን ያልፈፀሙበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉት ነጥቦች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከደረሰበት መደምደሚያና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበናል፡፡

በመርህ ደረጃ ተዋዋዮች ውል የመዋዋል ነፃነት አላቸው፡፡ ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው በማለት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተዋዋዮች ለሚዋዋሉት ሰው በአንድ ነገር ላይ ያላቸውን መብት ለመስጠት ወይም አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ሊዋዋሉ እንደሚችሉና ውሎች አስገዳጅነታቸው በውሉ በተነገረው ጉዳይ ብቻ ሣይሆን ልማድ፤ ፍትሕ፣ ቅን ልቦና የውለታው ዓይነት የሚያስከትሏቸውን ነገሮች ጭምር እንደሆነ ከፍታብሔር ቁጥር 1712 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1713 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾችና ተጠሪዎች ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም.በተደረገው ውል ያለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ከላይ የተጠቀሱን የህግ ድንጌጋዎች መሠረት በማድረግ መመርመር ተገቢ ነው፡፡

በውሉ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሆቴል ንግድ ድርጅት ህንፃውንና በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን የመገልገያ እቃዎች ላይ የነበራቸው የባለሀብትነት መብት ለአንደኛ ተጠሪ ለማስተላለፍ የተስማሙ መሆኑና አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ በንግድ ድርጅቱና በህንፃው ላይ ያለውን ዕዳ ለባለመብቶች ለመክፈልና ለሻጮች ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ለመክፈል የተስማማ መሆኑን ግራ ቀኙ ያልተካካዱበትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔው ያረጋገጠው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪዎች በውሉ ሁለት መሠረታዊ ግዴታዎች ተጥሎባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው በንግድ ድርጅቱና በህንፃው ላይ ያለ የባንክ ዕዳ እና ሌሎች ያልተከፈሉ ውዝፍ ዕዳዎችን መክፈል ሲሆን ሁለተኛው ለሻጮች ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ መክፈል ነው፡፡ ተጠሪዎች ለሁለተኛና ሶስተኛ አመልካች ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የከፈሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪዎች የዕዳው መጠን በውሉ ላይ ያልተገለፀ ቢሆንም ከብር 6,450,000 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ በላይ የንግድ ድርጅቱንና የህንፃውን የባንክ ዕዳ፣ ሌሎች የውሃ፣ የመብራት የስልክና ሌሎች ውዝፍ ዕዳዎች የከፈሉ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ አረጋግጦ በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡

ይህም ተጠሪዎች በውል ከገቡት ግዴታ ከሰማኒያ አምስት ፐርሰንት በላይ የፈፀሙ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በውሉ ከተጣለባቸው ግዴታቸው አብዛኛውን ክፍል የፈፀሙ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚው ችሎት አረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች አይነተኛ የሆነ የውል ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለው ነጥብ የሚመዘነው ተጠሪዎች በውል መሠረት ለመፈፀም ከተስማሙባቸው ሁለት መሠረታዊ ግዴታዎች ምን ያህሉን ፈፅመው ምን ያህል ይቀራቸው የሚለውን በመመዘን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በማውጣት በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት የገዙት የንግድ ድርጅት ከነበረበት ዕዳ የከፈሉት ተጠሪዎች ለእኛ ሊከፍሉ ከተስማሙት ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ውስጥ የከፈሉት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ብቻ በመሆኑ መሠረታዊ የውል መጣስ ተግባር ፈፅመዋል በማለት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያላደረገና ከቅን ልቦና ውጭ የቀረበ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች በሽያጭ ውሉ የገቡትን አይነተኛ ግዴታቸውን የተወጡና ቀሪውን ግዴታቸውን እንዳይወጡ ችግር የፈጠሩት አንደኛ፣ ሁለተኛ ሶስተኛ አመልካቾች መሆናቸውን በማስረጃ በማረጋገጥ ውሉ በፍርድ ቤት ውሣኔ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት የሰጠው

ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ድንጋጌዎች ላይ የጠቀስናቸውን ሌሎች የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

3. የሟች ወ/ሮ ነጠረች ከበደ ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው በክርክሩ አራተኛ አመልካች ወ/ሮ ነጠረች ከበደን በመተካት ተካፋይ የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች አበበ ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር የዕርቅ ስምምነት ፈፅመውና ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር በጋራ ማመልከቻ ጽፈውና ፈርመው ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት እንዲመዘገብላቸው ሰኔ 15 ቀን, ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም.፣ እና ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ለችሎቱ በአካል ቀርበው አመልክተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች አስተያየት እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሶስተኛ አመልካች ዳዊት ከበደ እኔም የሟች ነጠረች ከበደ ወራሽ ስለሆንኩ የዕርቅ ስምምነቱ የእኔን መብት ይነካል በማለት ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም የፅሑፍ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ዕርቁን ትቸዋለሁ ፍርድ ቤቱ ክርክሩ እንዲቀጥል ያድርግልኝ በማለት ሀምሌ 19 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ አስተያየት ያቀረቡ ሲሆን ይህንኑ ታህሣሥ 20 ቀን 2004 ዓ.ም በአካል ለችሎቱ ቀርበው አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪዎች ዕርቁ የማይመዘገብበት ምክንያት የለም፡፡ ለህግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም የፅሑፍ አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ዕርቁ እንዲመዘገብላቸው ከጠየቁ በኋላ ዕርቁን ትቸዋለሁ ማለት አይችሉም፡፡ የዕርቅ ውሉ ተመዝግቦ ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው ይገባል በማለት የተጠሪዎች ጠበቃ ታህሣሥ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ለችሎቱ በቃል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

እኛም ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገውን የዕርቅ ስምምነት ይዘት መርምረናል፡፡ በዕርቅ ስምምነቱ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከወ/ሪት ነጠረች ከበደ በውርስ የሚተላለፍላቸውን መብት ወይም በራሳቸው የሚደርሳቸውን መብትና ጥቅም ለተጠሪዎች ለማስተላለፍና ተጠሪዎችም ለወ/ሮ አሰገደች አበበ ብር 550,000 /አምስት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ለመክፈል ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት የሟች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ወራሽነትን አረጋግጠው የሚመጡ ሌሎች መብት የማይመለከትና ወ/ሮ አሰገደች አበበ የሟች ነጠረች ከበደ ወራሽ መሆናቸው በራሳቸው ያላቸውን መብትና ጥቅም ለተጠሪዎች ለማስተላለፍ የተደረገ በመሆኑ ሶስተኛ አመልካች የዕርቅ ስምምነቱ የእኔን ጥቅም ይነካል በማለት ያቀረበውን ተቃውሞ አልተቀበልነውም፡፡ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት እንዲመዘግብላቸው ለችሎቱ ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም፣ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም እና ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም በአካል እየቀረቡ ካመለከቱ በኋላ የዕርቅ ስምምነቱን ትቸዋለሁ በማለት በፅሑፍና በቃል ያቀረቡት አስተያየት የዕርቅ ስምምነቱን ውድቅ ለማድረግ በቂ ምክንያት ባለመሆኑና የዕርቅ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ ስላላገኘነው የአራተኛ አመልካች ወራሽ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277/፩/ መሠረት በመመዝገብ የዕርቅ ስምምነቱ በወ/ሮ አሰገደች አበበና በተጠሪዎች መካከል አስገዳጅና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

4. አራተኛው ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የነበረችው አራተኛ አመልካች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡትን ጥያቄ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ነጥብ ለመወሰን ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሟች አቶ ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት

ያገኘችው የንግድ ድርጅቱና የህንፃ ሽያጭ ውሉ ከመደረጉ በፊት ነው ወይስ በኋላ የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡

ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሟች አቶ ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ የወራሽነት የምስክርነት ወረቀት ከማግኘቷ በፊት በፍታብሐር ሕግ ቁጥር 996 መሠረት የሟች አቶ ከበደ ዘለቀ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት ውሣኔ ያረጋገጡት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የንግድ ድርጅቱን እና ህንፃውን ለአንደኛ ተጠሪ የሰጡ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማረጋገጥ በውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ይህም የሚያሣየው የፀና የወራሽነት ማስረጃ ያላቸው ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች የሟች ከበደ ዘለቀ የውርስ ንብረት ክፍል የሆነውን የንግድ ድርጅትና ህንፃ ለአንደኛ ተጠሪ ከሸጡት በኋላ ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሟች ከበደ ዘለቀ ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ያገኙት መሆኑን ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያረጋገጡትን ይህንን ፍሬ ጉዳይ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997 ድንጋጌዎች አንፃር የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ተመልክተናል፡፡ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 996 ጋር ተያያዥነት ያለውና የዚሁ ድንጋጌ ተከታይ የሆነው የፍታበሔር ሕግ ቁጥር 997 "ውጤቶች" በሚል ርዕስ የወራሽነት ሰርተፊኬት መያዝ የሚያስከትላቸውን ህጋዊ ውጤቶች ይደነግጋል፡፡ የወራሽነት ወረቀቱ እስካልተሰረዘ ድረስ ወራሽ በተባለው የምስክር ወረቀት እንደተገለፀው ወራሽ እንደሆነ የሚገመት መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካች የሟች ከበደ ዘለቀ የኑዛዜ ወራሽ ናቸው የሚለውን የፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ እስከያዙና ይኸው የወራሽነት ማስረጃቸው እስካልተሰረዘ ድረስ የሟች ከበደ ዘለቀ ወራሾች ናቸው ብሎ ህጉ ግምት የሚወስድበት መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ " በወራሽነት ስም በወራሹ የተፈፀሙ ተግባሮች ያሉ እንደሆነ ተግባሮቹ በተፈፀሙበት ጊዜ የተባለው ወራሽ የወራሽነት መብት እንዳልነበረው በግልፅ ማወቁ ካልተረጋገጠ በቀር እነዚህን ተግባሮች ለመቃወም የማይቻል" መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅነት ባለው መንገድ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ሟች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሟች ከበደ ዘለቀ ወራሽ ስለመሆናቸው የፀና የወራሽነት የምስክር ወረቀት አግኝተዋል፡፡ ይህንን የፀና የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ የንግድ ድርጅቱንና ህንፃውን አንደኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተዋዋሉትን ውል እንዲፈርስ ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ለመጠየቅ የምትችለው ተጠሪዎች ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሟች አቶ ከበደ ዘለቀ ወራሾች አለመሆናቸውን እያወቁ ውል የተዋዋሉ መሆኑን በማስረጃ በማስረዳት ብቻ እንደሆነ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 997 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ይዘት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ወ/ሪት ነጠረች ከበደ እኔ የሟች ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ ነኝ የሚል ክርክር ከሚያቀርቡ በስተቀር ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሟች ከበደ ዘለቀ የኑዛዜ ወራሾች አይደሉም፡፡ አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሟች ከበደ ዘለቀ ወራሽ አለመሆናቸውን እያወቀ የንግድና የህንፃ ሽያጭ ውል ተዋውሏል የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ ይህንንም የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረቡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ይህም በመሆኑ ሟች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሟች ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ መሆኑ በፍርድ ቤት ከመረጋገጡ በፊት የፀና የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የላትም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አራተኛ አመልካች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የላትም በማለት የሰጠው

ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 996 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997ን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም አራተኛ አመልካች የነበረችው ወ/ሪት ነጠረች ከበደ በዚህ መዝገብ በክርክር በተያዘው ጉዳይ ያላት መብት የሟች ከበደ ዘለቀ የውርስ ንብረት ክፍል የሆነውን የንግድ ድርጅትና ህንፃ የሸጡት ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች ንብረቱን ሸጠው ካገኙትና ወደ ፊትም በውሉ መሠረት ከሚያገኙት የንብረቱ ዋጋ ከሆነው ገንዘብ ውስጥ በድርሻ መጠን እንዲያካፍሏት መጠየቅ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የሆቴል ንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል የሚሰርዝበትም ሆነ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27497 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የአራተኛ አመልካች ወራሽ የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች አበበና ተጠሪዎች ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ባለመሆኑ ፀድቋል፡፡
3. ተጠሪዎች ለወ/ሮ አሰገደች አበበ በዕርቅ ውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት ብር 550,000 /አምስት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ይክፈሉ፡፡
4. የአራተኛ አመልካች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ወራሽ የሆኑት የወ/ሮ አሰገደች አበበ በዚህ መዝገብና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ያላቸው መብትና ጥቅም በዕርቅ ውሉ መሠረት ወደ ተጠሪዎች ተላልፏል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 64397

ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አንዳርጌ እምሩ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ - የቀረበ የለም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቴሌቭዥን ከነሲዲው ተጠሪ እገዛልሃለሁ በማለት ተቀብላኝ ዕቃውም ተገዝቶ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡም አልተከፈለኝም በሚል የቀረበ ክስ ሲሆን የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሳሽ መስከረም 17 ቀን 2001 ዓ.ም. በከሳሽ ቤት መጥተው አንድ ባለ 21 ኢንች ሶኒ ቴሌቪዥን ከነሲዲው ቀረጡን ጨምሮ በብር 4750(አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ገዝቼ አመጣልሃለሁ ብለውኝ በምስክሮች ፊት ገንዘቡን ቆጥሬ ሰጥቼያቸው ቴሌቪዥኑን ያላስረከቡኝ ሲሆን ገንዘቡም እንዲሰጠኝ ብጠይቃቸው ወይም ዕቃውን እንዲያስረክቡኝ ብጠይቃቸው ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ዕቃውን እንዲያስረክቡኝ ወይም ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ እንደዚሁም በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዙት መሰረት መጥሪያ ተልኮላቸው ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን ከሳሽ በቃለ መሓላ ማረጋገጣቸውን በማመልከቱ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ ተሰጥቶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የሰጠውም የፍርድ ይዘት ተከሳሽ በቀረበው ክስ ላይ ቀርበው መልስ ያለመስጠታቸው የቀረበውን ክስ እንዳመኑ ስለሚቆጠር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉ በማለት በአሁኑ ተጠሪ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በቀጥታ ይግባኛቸውን ለከተማው አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበውን ቅሬታ ከመረመረ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 337 መሰረት አጽንቷል፡፡ በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍትሐ ብሔር ህግ ቁ. 2472(1)(2) መሰረት ከብር 500 (ብር አምስት መቶ) በላይ የሆነ ብድር በጽሑፍ፣ በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም ቃለ-መሓላ ካልሆነ በስተቀር በሰው ምስክር ማስረዳት እንደማይቻል፤ በተመሳሳይም ከብር 500 በላይ ከፍያለሁ በማለት የሚቀርበው ክርክር ይሄው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን በማመላከት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ከቀረበባቸው ክስ በነጻ በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩም ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ቴሌቪዥን እና ሲዲ ገዝተው እንዲያመጡላቸው ለተጠሪ የሰጡትን ብር 4750 (አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) በሰነድ እንጂ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ አይቻልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል የነበረ በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ አኳያ ተመርምሮ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምር የአሁን ተጠሪ በክሱ እንደተመለከተው ገንዘቡን የተቀበሉት ቴሌቪዢን እና ሲዲ ገዝቼ አመጣልሃለሁ በማለት እንጂ በብድር ምክንያት ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይም ተፈጻሚነት ያለው ከዚሁ ብድር ጋር በተያያዘ መልሼ ከፍያለው የሚል ተከራካሪን የሚመለከት እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ በግራ ቀኙ መካከል ብድርን መሰረት ያደረገ ክርክር በሌለበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ህግ ቁ.2472 ን በመጥቀስ ከብር 500 በላይ የሆነን የገንዘብ መጠን በሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም ወደ ሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አነስተኛ ድምጽ አስቀምጦት የነበረው ሃሳብ አግባብነት የነበረው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆናቸው ተገልጾ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ በመስጠቱ የቀረበውን ክስ ከሳሽ በቆጠረው ምስክር ተከሳሽ ባይቀርቡም በመስማት እና ጉዳዩን በማጣራት ውሳኔ መስጠት ሲገባው የተጠሪ ያለመቅረብ ጉዳዩን እንዳመኑ የሚያስቆጥር ባለመሆኑ ክሱን እንዳመኑት ይቆጠራል በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ቴሌቪዢን እና ሲዲ ለመግዛት ተጠሪ 500 ብር የተቀበሉ መሆኑን እንጂ የብድር ገንዘብ ስለመሆኑ ባልተነሳበት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለውን የብድር ውል እና ክፍያ የተመለከተን ድንጋጌ በመጥቀስ ከብር 500 (ብር አምስት መቶ) በላይ በሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የደረሰበት መደምደሚያ እንደዚሁም ጉዳዩን በመጀመሪያ ተመልክተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀርበው መልስ ያለመስጠታቸው ወይም ጉዳዩ በሌሉበት በመታየት ክሱን እንደማመን ይቆጠራል በማለት የሰጠውም ውሳኔ በተመሳሳይ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.14696 በቀን 07-04-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ በፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.04417 ህዳር 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.016/03 መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የተከሳሽ በአንድ ክስ ላይ ቀርቦ ያለመከራከር ወይም የጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት መታየት የቀረበው ክስ ክሱን ሊያስረዱልኝ ይችላሉ በማለት ከሳሽ በክሳቸው በመዘርዘር ያቀረቡትን

ምስክሮች ብቻ በመስማት እና ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ ከሚሰጥ ውጪ የተከሳሽ ያለመቅረብ ጉዳዩን እንዳመኑት ይቆጠራል በማለት በክሱ መሰረት ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በክሱ ላይ የቆጠራቸው ምስክሮች ተሰምተው እና ለፍትህ አሰጣጡ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ያመነባቸውን ማስረጃዎች በመቀበል ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 71375

ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ዳሽን የህትመትና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነ/ፈጅ አቶ ትዕዛዙ

ዓለማሁ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ፍስሐ ይሁን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ የሰበር አመልካች በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ከተከሳሽ ጋር ባደረግነው ውል ከሳሽ ለተከሳሽ ፍስሐና ስራው የሚል መፅሐፍ 300 ቅጂ ለማዘጋጀትና ተከሳሽም ለከሳሽ ብር 50,000 (ሀምሳ ሺህ ብር) ለመክፈል የተስማማን ሲሆን በስምምነታችን መሰረት ተከሳሽ ቅድመ ክፍያ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ከፍሎ መጽሐፎቹን ከሳሽ አዘጋጅቼ ባጠናቅቅም ቀሪውን ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ሳይከፍለኝ ከአንድ ዓመት በላይ ስለቆየ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ሞቷል በመባሉ ወራሾች ካሉ ቀርበው ለክሱ መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ በተከሳሽ ቤት ተለጥፎ ወራሾች ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ቀጥሎ የመ/ደ/ፍ/ቤቱ መዝገቡን በመመርመር በሰጠው ፍርድ ከሳሽ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ሁሉም በከሳሽ የተጻፉ ናቸው፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ እንደ ማስረጃ ሆነው የሚቀርቡት በራሱ በከሳሽ እንጂ በተከሳሽ ላይ አይደለም፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ግዴታ ስለመኖሩ በማንኛውም ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ በመካከላቸው አስገዳጅ ውል መኖሩን ባላስረዳበት እንደውሉ እንዲፈጸምለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ የይግባኝ ባይን የይግባኝ መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በመ/ደ/ፍ/ቤት ፍርድም ሆነ በከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው

ቅሬታ የህትመት ስራ ውል በቃል ጭምር ማድረግ የሚቻል ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሊያስገድዳቸው የሚችል የጽሁፍ ውል የለም ሲሉ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

በሰበር ደረጃም የተጠሪው ወራሾች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የፍ/ቤቱ መጥሪያ የደረሳቸው ቢሆንም ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካች ያቀረበው ክርክርና በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ፍርድ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በስር ተከሳሽ መካከል አስገዳጅ ውል ስለመኖሩ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም ሲሉ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ለስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሉ ስለመኖሩ በማስረጃነት ያቀረባቸው የጽሁፍ ሰነዶች ቅድመ ክፍያና ተጨማሪ ክፍያ ከተከሳሽ የተቀበላቸውን ደረሰኞችና አመልካች ለተከሳሽ የጻፈውን የዋጋ ማቅረቢያ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰነዶች በስተቀር ውሉ በጽሁፍ የተደረገ ስለመሆኑ ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ የለም፡፡ በፅሁፍ የተደረገውን ውል አለማቅረብ ደግሞ በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል ውል የለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ህ/ቁ/1681(1) እንደተደነገገው ውል በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታ መግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ጭምር መግባት ስለሚቻል ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉም የውል ዓይነቶች በቃል ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ይደረጋሉ ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም የ/ፍ/ህ/ቁ/1725ን መመልከት ተገቢነት አለው፡፡ በዚህ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት ለብዙ ጊዜ የሚቆዩ ውሎች፤ እንዲሁም የዋስትና ውሎች፤ የኢንሹራንስ ውሎች እና ህጉ በግልጽ በጽሁፍ እንዲደረጉ የሚያስገድዳቸው የውል ዓይነቶች ሁሉ በጽሁፍ መደረግ አለባቸው፡፡

ይህንኑ የህግ አነጋገር ይዘን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር ገብተናል በሚለው የህትመት ስራ ውል ውሉ በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር ገብተናል የሚለው ውልም በገቡት ውል መሰረት 300 ቅጂ መጽሀፎችን አባዝቶ ከመስጠት ያለፈና ለረጅም ጊዜ ይቆያል ተብሎ የማይገመት በመሆኑ የውሉ በጽሁፍ መሆን የግድ የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረባቸውን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመመርመር እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/264(2) እንደተደነገገው ውሉ ከዚህ በላይ በተጠቀሱ መንገዶች የተደረገ መሆን ስላለመሆኑ፣ በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል አለ ስለተባለው የውል ግንኙነት አመልካች ባቆይቆጠራቸውም እንኳን ምስክሮችን መስማት ጠቃሚ መስሎ ከታየ አስቀርቦ መስማት በጉዳዩ ላይ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮችን በአግባቡ አጣርተው ተገቢውን ፍርድ መስጠት ሲገባቸው ይሄንኑ በማለፍ አመልካች አስገዳጅ ውል መኖሩን አላስረዳም በሚል ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ባለመሆኑ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 69348 በቀን 26/08/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 110517 በቀን 23/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር አድርገናል በሚለው የህትመት ውል መሰረት ፍስሐና ስራው የሚል 300 ቅጂ መጽሐፎችን ማዘጋጀቱንና አለማዘጋጀቱን የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 272 መሰረት ምትክ ዳኛ እስከ ቦታው ድረስ በመላክ ምትክ ዳኛው ተገቢውን ምርመራ አድርገው በሚያቀርቡት የምርመራ ውጤት መሰረት የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥ ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/343 (1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ 69208

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንፁህ በላይ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ምንትዋብ አዳነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውል የጠፋ መሆኑን በምስክር ለማስረዳት የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በደብረማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ ፣ በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነው አቶ እንዳወቀ አያሌው ተከሣሽ አመልካች ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አቶ እንዳወቀ በማላውቀው ሁኔታ እቤቴ ውስጥ ገብቶ እየኖረ ስለሆነ ቤቱን እንዲለቅና የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ አቶ እንዳወቀ ቤቱን ያከራዩት አመልካች መሆኑን ገልፆ በክርክሩ ጣልቃ እንድትገባ ጠይቋል፡፡ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብታ ቤቱን አሁን በህይወት ከሌለው ባለቤቷ አቶ አየነው ድርሻ በ2000 ዓ.ም ከተጠሪ ገዝተው ፣ ለሥር ተከሣሽ በውል ያከራዩት መሆኑን በመግለፅ የተከራከረች ሲሆን የሽያጭ ውሉ የጠፋ ቢሆንም ፣ ለቤቱ መብራትና ውሀ አስገብቻለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ መሠረት የሽያጭ ውል አላቀረቡም በማለት አመልካች ለተጠሪ ቤቱን ለቅቀው እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የተጠሪን ቃለመሃላ ከሰማ በኋላ እንደዚሁም የሰነድ ማስረጃው ይገኝባቸዋል ከተባሉ መስሪያ ቤቶች የተሰጠውን ምላሽ በማገናዘብ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ክስ ያቀረበችበትን ቤት በሟች ባለቤቴ አየነው ድረስ ስም ብር 38,000 /ሰላሣ ስምንት ሺህ ብር/ ተጠሪ ሸጣልን ፣ ገንዘቡን ከፍለን ቤቱን ተረክበን ኖረናል፡፡ ቤቱን ከተረከብን በኋላ በብር 30,000 ወጭ በማድረግ አድሰናል፡፡ መብራትና ውሀ በሟች ባለቤቴ አቶ አየነው ድረስ ስም አስገብተናል፡፡ የሽያጭ ውሉ ባለቤቴ አቶ አየነው ድረስ በመሞቱ ምክንያት የጠፋ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 እንዳስረዳ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉና የቤት ኪራይ ብር 2850 /ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሣ ብር/ እንዲከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

ተጠሪ ነሐሴ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱን ለአመልካችም ሆነ ለሟች ባለቤቷ የቤቱ ባለሃብት የሆንኩት ተጠሪ አልሸጥኩላቸውም፡፡ አመልካች ቤቱ የተሸጠላቸው መሆኑን ያቀረቡት የፅሁፍ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ቤት አድሻለሁ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተጠሪን የማይመለከትና በማስረጃ ያልተደገፈ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች መስከረም 15 ቀን 2004 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም አመልካች ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የተዋዋለችበት ሰነድ የጠፋ መሆኑን በምስክር ለማስረዳት ያቀረበችው ጥያቄ መታለፉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ሣይሆን ቤቱን ከእሷ ተከራይቶ ይዞት ለነበረው አቶ እንዳወቅ አያሌው መድን በመሆን ጣልቃ ገብተው በክርክሩ የተሣተፉ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀረበችበትን ቤት በ2000 ዓ.ም ሟች ባለቤቷ አየነው ድረስ በውል የገዛ መሆኑና የሽያጭ ውሉ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የጠፋ መሆኑን በመጥቀስ ሰነዱ የጠፋ መሆኑንና ቤቱን በውል የገዛች መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበችውን ጥያቄ የወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አልተቀበሉትም፡፡ ውል መኖሩን በማንሣት የሚከራከር ሰው የውል ግዴታው መኖሩን የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2001 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑ ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ቤቱን ከተጠሪ በውል የገዛችው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለባት በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው፡፡ የቤት ሽያጭ ውል በፅሑፍ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመርህ ደረጃ በፅሑፍ መደረግ ያለባቸውን ውሎች ለማስረዳት የሚቻለው በፅሑፍ የተደረገውን ውል በማቅረብ መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2008 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ እንዳለ ሆኖ በልዩ ሁኔታ በፅሁፍ የተደረገን ውል በምስክሮች ወይም በህሊና ግምት ለማስረዳት የሚችልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን "ውሉ በፅሑፍ እንዲሆን ሕግ ባዘዘ ጊዜ ይህ ፅሑፍ የተቀደደ ፣ የተሰረቀ ፣ የጠፋ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ውሉን በምስክሮች ወይም በህሊና ግምት ለማስረዳት አይችልም " በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት አንድ ሰው በመጀመሪያ በፅሑፍ የተደረገው ውል የተቀደደበት የተሰረቀበት ወይም የጠፋበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ ውሉ የተሠረቀ፣ የጠፋ ወይም የተቀደደ መሆኑን በበቂ ሁኔታ

ለፍርድ ቤቱ ካስረዳ በፅሑፍ የተደረገውን ውል በምስክሮች ቃል ወይም በህሊና ግምት እንዲያስረዳ የሚፈቀድለት መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ሚች ባለቤቷ አየነው ድረስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ፣ ሚች ባለቤቷ አየነው ድረስ ከተጠሪ ቤቱን ለመግዛት ተዋውሎት የነበረው የቤት ሽያጭ ውል የጠፋበት ስለመሆኑ በምስክሮች ለማስረዳት ያቀረበችው ጥያቄ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 ድንጋጌን መሠረት ያደረገና የህግ መሠረት ያለው ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት በመጀመሪያ አመልካች ሚች ባለቤቷ አከራካሪውን ቤት ከተጠሪ ለመግዛት የተዋዋለው የፅሑፍ ውል የጠፋበት ስለመሆኑ የምታቀርባቸውን ምስክሮች በመስማት የፅሑፍ ውሉ የጠፋ መሆኑን አስረድታለች ወይስ አላስረዳችም? የሚለውን ጭብጥ መወሰንና ውሉ የጠፋ መሆኑን አመልካች በበቂ ሁኔታ አስረድታለች የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ አመልካች በሚች ባለቤቷ አየነው ድረስና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል በምስክሮች ቃልና በህሊና ግምት እንድታስረዳ በመፍቀድ ማስረጃውን በመሰማትና በመመርመርና በመመዘን መወሰን ሲገባው ፣ አመልካች የሽያጭ ውል አላቀረበችም በማለት ቤቱን ለተጠሪ እንድታስረክብ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የዞኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረበችውን ጥያቄ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 መሠረት በማድረግ መመርመርና መወሰን ሲገባው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2002 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የተጠሪን ቃለመሃላ ሰምቶ ውሣኔ መስጠቱ የአመልካችን መብት ያጣበበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከላይ የዘረዘርናቸው የህግ ስህተቶች ሣያርም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 ድንጋጌ አመልካች ያላትን መብት የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤትና ፣ የምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት ፣ በመጀመሪያ አመልካች ሚች ባለቤቷ አቶ አየነው ድረስና ተጠሪ በፅሑፍ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የጠፋባት መሆኑን ለማስረዳት የምታቀርባቸውን ማስረጃዎች በመስማት፣ በመመርመርና በመመዘን አመልካች ውሉ የጠፋ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አስረድታለች ብሎ ካመነ አመልካች የሽያጭ ውሉን በምስክሮች ቃልና በህሊና ግምት እንድታስረዳ በማድረግና የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 72463

መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. አቶ ንጉሴ ሀይሌ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ማሚቱ ለታ

መልስ ሰጭዎች፡- 1. አቶ ሁሬሣ ደበል
2. ወ/ሮ ሌሊሴ ራያ } ጠበቃ አቶ ታዬ ባንጃው ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፊንፊኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሣሽ ተጠሪዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል ጉዳዩ ወለድ አገድ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ከተጠሪዎች ጋር መስከረም 28 ቀን 03 ዓ.ም ያደረጉት የወለድ አገድ ስምምነት ቁጥሩ 777 የሆነውን ቤትና ሌሎች ሁለት ክፍል ቤቶች ተጠሪዎች በወለድ አገድ በመያዝ እንዲጠቀሙበት አስረክበው ለአንድ አመት የሚቆይ 2500 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ መበደራቸውን ገልፀው፣ ተጠሪዎች ገንዘቡን ወስደው ቤቱን እንዲለቁ ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ገንዘቡን ወስደው ቤቱን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ አይታገድም ተከሣሾች /ተጠሪዎች/ ገንዘቡን ወስደው ቤቱን ለከሣሾች /አመልካቾች/ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ብድሩን ለመመለስ የተስማሙት መስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም በመሆኑ ውሉ በይርጋ ይታገዳል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የውሉን ልዩ ባህሪ ያላገናዘበና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካቾች በአንድ ዓመት ውስጥ ለመመለስ የገቡትን የብድር ውል ሣይፈጽሙ ከአስራ ስድስት ዓመት በኃላ በመጠየቃቸው ክሱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ "ወለድ አገድ" ማለት አንድ ባለእዳ ግዴታውን ለመፈፀም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂው የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማስረከብ የሚገደድበት ውል መሆኑ በፍታብሔር ህገ ቁጥር 3117 ተደንግጓል፡፡ የወለድ አገድ፣ ውል የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3124 የተደነገገ ሲሆን ማንም ሰው በወለድ አገድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ካስያዘ ወለድ አገድ የተቋቋመበትን ግዴታ በመፈፀም በማናቸውም ጊዜ ወለድ አገድ እንዲቀር ማድረግ እንደሚችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 "እንዲሁም ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር የተባለው ወለድ አገድ የተቋቋመበትን ግዴታ በመፈፀም ባለእዳው በማናቸውም ጊዜ ወለድ አገዱ እንዲቀር ለማድረግ ይችላል" በሚል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ "ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር" የሚለውን ሀረግ ሲተረጉም የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የድንጋጌውን መንፈስ አላማና ይዘት መሠረት ባደረገ ሁኔታ መተርጎም ሲገባው ይህንን አላደረገም፡፡ በዚህ ድንጋጌ "ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር" የሚለው አመልካቾች እስከ መስከረም 28 ቀን 1984 ቤቱ ተጠሪዎች በወለድ አገድ እንዲያዝ የተስማሙ ስለሆነ ከመስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም በፊት ገንዘቡን በመክፈል ተጠሪዎች በወለድ አገድ የያዙትን ቤት ለማስለቀቅ የማይችሉ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በወለድ አገድ ውሉ የተገለፀው ጊዜ ካለፈ በኃላ አመልካቾች በማናቸውም ጊዜ እዳቸውን በመክፈል ቤታቸውን ማስመለስ የሚችሉ ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት መጠየቅ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በወለድ አገድ የያዙት ቤት ባለሀብት ሆነው የሚቀሩበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በቤቱ እየተጠቀሙና አላባ እየሰበሰቡ መኖር ካልተስማማቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 አንቀጽ 1 የወለድ አገድ መብቱን ለመተው የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ ተደንግጓል፡፡

በአጠቃላይ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3117 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 1130 የወለድ አገድ የውል መሠረታዊ ባህሪ፣ ውጤትና የወለድ አገድ ውል እንዲቋረጥ ለመጠየቅ ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ስለጠቅላላ ውል ህግ የተደነገገው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ስለሆነም የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾች ክስ በአስር ዓመት ይርጋ ይቋረጣል በማለት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወስነናል፡፡
3. የውልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካቾች ብር 2500 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ለተጠሪዎች በመክፈል በወለድ አገድ ያስያዙትን ቤት የመረከብ መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/

የሰ/መ/ቁ. 69915

ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች:- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች:- ሻምበል ይኩኖ ለገሠ ቀረቡ

ተጠሪ:- አቶ መሐመድ በሽርና ቤተሰቦቹ ጨው አምራች ኃ/የተ/የግል ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ እንደ ውሉ ያልተፈፀመለት ወገን በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ በመጠየቅ ረገድ የሚኖረው መብትና ተነፃፃሪ ግዴታን የሚመለከት ነው፡፡ ግራ ቀኙ ግንቦት 02 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ የፅሑፍ ውል የአሁን ተጠሪዎች በውል ሰጪነት/፤ አመልካች ደግሞ በውል ተቀባይነት ተሰይመው የውል ሰጭዎች የጨው ማምረቻ ቦታ ውል ተቀባይ ተረክቦ ለመጀመሪያ ሰባት አመታት በራሱ ወጪ እና ማቴሪያል ለሚያመርተው ምርት 70% ለእራሱ አስቀርቶ 30% ለውል ሰጭዎች ለማካፈል በቀሪው ሶስት አመታት ግን በግራ ቀኙ ውጭ ለሚመረተው ምርት እኩል በእኩል ለመካፈል ተስማምተዋል፡፡ እንደ ውሉ ያልፈፀመ ወገንም ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ውል ላልተፈፀመለት ወገን ከፍሎ ቀጣዩ በውሉ መሠረት እንዲፈጽም እንደሚደረግም አክለው ተስማምተዋል፡፡

ይህ ውል ከተደረገ ከአምስት ዓመት በኃላ የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በተዋዋይነው ጨው የማምረት ሥራ መሠረት ውል ተቀባይነት ሥራውን መሠረት ባለመቻሉ፣ እንደውል ባለመፈፀሙ የቀረብን የ30% ጥቅም ብር 3,548,666.00 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ስምነት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር) እና የገደብ መቀጮ ሊከፍለን ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች በተከሣሽነት እንደውሉ ያልተፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት እና ምክንያቱን በመጥቀስ የተቋረጠ ጥቅም ሊጠየቅ እንደማይገባ እንደውል አልተፈፀመም ከተባለም በውሉ መሠረት ሊጠይቁ የሚችሉት የ5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ የገደብ መቀጮ እና እንደውሉ በቀጣይ እንዲፈፀም ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ በግራ ቀኙ ከተነሣው ክርክር አንፃር የአሁን አመልካች እንደውሉ ሊፈጽም ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም፣ እንደውሉ ለመፈፀም አልቻለም፡፡ ስለሆነም ውሉ ፈርሶ ሁለቱም ወገኖች ወደ ነበሩበት ቦታ ይመለሱ፤ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ከሣሽ ይከፈለኝ የሚሉትን ገንዘብ በሌላ ክስ ይጠይቁ በማለት የአፋር ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲወስን፤ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የአሁን አመልካች

እንደውሉ ያልፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ባለመሆኑ ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ ነው፡፡ ውሉ ባለመፈፀሙ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ከሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ውሣኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ በዓመት በውል በተሰጠው መሬት ምን ያህል የጨው ምርት ማምረት እንደሚቻል የክልሉ ማእድንና ኢነርጂ ቢሮ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ እንደተመነና በተጠቀሰው ምርትም የጨው ዋጋ በስንት ሲሸጥ እንደነበር ለግብይት ማህበሩ በማጣራት አስተሳስቦ የደረሰባቸው ኪሣራ ይከፈል፤ እንዲሁም እንደውሉ ሊቀጥሉ የሚችሉ ወገኖች ባለመሆናቸው በውሉ መሠረት ገደቡን ብር 5,000 ይክፈል በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭር የተጠቀሰው ሲሆን፤ የአመልካች የሰበር ቅሬታ ነጥብ ከሥር ፍ/ቤቶች ጀምሮ ባቀረበችው የመከራከሪያ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ሲሆን ከተጠሪዎች የተሠጠ የተለየ ክርክር አልቀረበም፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተው ተመልክተናል፡፡ የአሁን አመልካች እንደውሉ ሊፈፀም ያልቻለው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስላጋጠመው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበውን ምክንያት በማስረጃ አጣርተው እና ማስረጃውን መዝነው የአሁን አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አላጋጠመም የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሱ በመሆኑ ጉዳዩ የህግ ትርጉምን የሚጋብዝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች አጠንክሮ የተከራከረበት ሌላው ነጥብ እንደ ውሉ አልተፈፀመም እንኳ ቢባል እደውሉ ሳይፈፀም በቀረ ጊዜ ምን ውጤት እንደሚከተል አስቀድመን በውላችን እንዲገዛ አድርገናል፡፡ በውሉም እንደተገለፀው ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪዎች ከፍሎ እንደ ውሉ እንድፈጽም ነው ግዴታዬ የሚለው ነው፡፡

በእርግጥ የውሉ ይዘት አመልካቹ እንደሚለው መሆኑን በፍርዱ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ቃል በቃል ሠፍሮ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ውሉ ያልተፈፀመ ከሆነ እንደ ውሉ ያልፈፀመው ወገን ብር 5,000.00 ለሌላው ወገን ከፍሎ ቀጣይ የውል ግዴታውን ይወጣል የሚለውን የውሉ አገላለጽ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተዋዋይ ወገኖች ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ተጠቅመው ለአምስት ዓመት ያህል እንደውሉ ሥራ ቢጀምሩም ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ከፍሎ ቀጣይ ሥራውን ይጀምራል የሚለውንም ሁሉ ለማጠቃለል በማሰብ ያስገቡት የውል ቃል ነው ብሎ ለመተርጎም የሚቻል አይደለም፡፡ ይልቁንም የውሉ አገላለጽ መለስተኛ የጊዜ ብክነትን ለመቆጣጠር ታስቦ የተደረገ ለመሆኑ የገንዘቡ መጠን እና ያጋጠመው መስተጓጉል የግራ ቀኙን የውል መሠረታዊ ግንኙነት የሚያውከው መሆኑን በመገንዘብ ቀጣይ ሥራውን ያከናውናል የሚለው ውጤት አስረጂ ናቸው፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ለአምስት ዓመታት ያህል እንደውሉ አለማከናወኑ ቢታወቅም ብር 5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) ከፍዬ ውሉን መቀጠል ብቻ ነው ግዴታዬ የሚለው ስለ ውል አተረጓጐም የተቀመጡትን ደንቦች መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪዎች ውሉ ከተደረገበት ከግንቦት 1996 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ዓመታት እንደ ውሉ አለመፈፀሙን እያወቁ ከውል የመነጨውን መብት ለማስጠበቅ ክስ ያቀረበችው በሰኔ 2001 ዓ.ም እንደሆነ ውሣኔው ያስረዳል፡፡

እንደውሉ ያልተፈፀመለት ወገን እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት በጥቅም መቋረጥ ስሌትም ሆነ በሌላ ኪሣራ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1771 የተደነገገ ቢሆንም፤ ከውል አለመፈፀም የተነሣ ሊደርስ የሚችለውን የጉዳት መጠንን በመቀነስ ረገድ በእርሱም ላይ በተነፃፃሪ ግዴታ የተጣለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1802 ተደንግጓል፡፡

ከዚህም አንፃር ተጠሪዎች ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ዘግይተው በአምስተኛ ዓመቱ መገባደጃ ላይ የብር 3,548,666 /የሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ስላሳ ስድስት ብር/ ኪሣራ ዓመታትን መነሻ በማድረግ አስልተው ከማቅረብ ይልቅ እንደ ውሉ ያለመፈፀሙን፤ እንደውሉ ሊፈጽም የሚችልበትን ሁኔታ በመረዳት ሊደረስ የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ ቀደም ብለው ክስ የማቅረብ ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

ስለሆነም ይህ በኪሣራ ጠያቂው በኩል በህግ የተጣለው ተነፃፃሪ ግዴታ የኪሣራ መጠንን ለማስላት ግምት ውስጥ ሊገባ የማይገባ ሌላው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል የተቋረጠ የሚባለውን ጥቅም ለማስላት ፍ/ቤቶች የባለሙያን ድጋፍ የሚጠይቁ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሚቀርበውን ሙያዊው አስተየያት በማስረጃነቱ በመያዝ ስለኪሣራው መጠን እራሳቸው የሚወስኑትና የፍ/ቤቱን ዳኝነት የሚጠይቅ ተግባር ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደገለፀው የክልሉ ማእድንና ኢነርጂ መሬት በየዓመቱ ምን ያህል የጨው ምርት እንደሚያገኝ ዋጋውም ስንት እንደሆነ ከግብይት ማህበራት በኩል ተጣርቶ ድርሻቸውን ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት አማካኝነት ፍትህ የማግኘት መብታቸውን ያስከበረ ተግባር አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔ አግባብ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሊከፈል የሚገባውን የኪሣራ መጠን በመወሰን ረገድ የተጠሪዎች ተነፃፃሪ ግዴታ ሳይያዝ፣ ይህ በተቻለ መጠን የጉዳት ኪሣራን በመቀነስ በኩል በተጠሪዎች በኩል መፈፀም የሚገባውን ግዴታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደውሉ ያልፈፀመው ወገን ሊከፍል የሚገባውን የጉዳት ኪሣራ ልክ ባባከነው ጊዜ አንፃር መሬቱ በሚያስገኘው የምርት መጠን እና በየጊዜው በነበረው የዋጋ ተመን መሠረት ይሆናል የሚለው ከተያዘ በዚህ መሠረት አስልቶ ለመወሰን የባለሙያ እገዛን ፍ/ቤቱ ከሚጠይቅ በቀር የኪሣራ አወሳሰኑን ዳኝነት ሰጭ አካል ላልሆነ አሳልፎ በመስጠት የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በዝርዝር ህጉን ባካተተው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ይህንኑ ስህተት በማረም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 2108 መጋቢት 17 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት በማሻሻል፣ የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሣራ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የሚለው የውሣኔው ክፍል እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ግንቦት /1996/ ጀምሮ ተጠሪዎች ክስ እስካቀረቡበት ሰኔ 2001 ዓ.ም. ድረስ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1802 እንደተደነገገው ኪሣራ በመቀነስ ረገድ ተጠሪዎችም

የሚጠበቅባቸውን ተነፃፃሪ ግዴታ አለመወጣታቸው የኪሳራውን መጠን በማናር አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባውን ጉዳይ መሆኑን መነሻ በማድረግ ለኪሣራው ስሌት መሠረት ሆኖ የሚያዘውን የጊዜ ርዝመት ፍ/ቤቱ ባለው የማመዛዘን ሥልጣን ተጠቅሞ እንዲቆረጥና የጊዜው ርዝመት ምን ያህል እንደሆነ ከተቆረጠ በኃላ በዚህ ጊዜ ውስጥ መሬቱ ምን ያህል የጨው ምርት ማስገኘት ይችል የነበረ መሆኑና በትይዩ ጊዜውም የጨው ዋጋ ስንት እንደነበር ፍ/ቤቱ በጠቀሳቸው አካላት ተተምኖ እና ተጣርቶ እንዲቀርብ ካደረገ በኃላ ይህንኑ ውጤት በማስረጃነት ይዞ የጉዳት ኪሣራውን ልክ መወሰን ይችል ዘንድ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት እንዲመለስ ወስነናል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 71927

ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ቄስ አብርሃ በርሄ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብርነሽ ሕሉፍ - አልቀረቡም፡፡

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በመቀሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በቀዳማዊ ወያኔ ምድብ ችሎት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የብድር ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 7 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ተጠሪ ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ እስከ የካቲት 1994 ዓ.ም ልትመልስ፣ በዚህ ጊዜ ባትከፍል መቀጫ 8,000 /ስምስት ሺህ ብር/ በድምሩ 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ለመክፈል ተስማምታ በብድር ወስዳለች፡፡ ገንዘቡን ያልከፈለችኝ በመሆኑ በውሉ መሠረት ብር 20,000 ከነወለዱ እንድትከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በከሳሽነት ቀርበው ገንዘብ በብድር አልወሰድኩም ፊርማውም የእኔ አይደለም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ ነው የተባለው ፊርማ እንዲመረመር ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ በምርመራው ፊርማው የማን እንደሆነ መለየት እንዳልተቻለ ተገልጿል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኖ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሉ ላይ የነበሩት ምስክሮች ሰምተህ ወስን በማለት በይግባኝ ሽሮ መልሶታል፡፡ በዚህ መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል ከሰማ በኋላ ምስክሮች ተጠሪ ስትበድር አይተናል፣ በውሉ ላይ ፈርመናል ብለው መመስከራቸውን በመጥቀስ ተጠሪ በብድር የወሰደችውን ብር 12,000 እና መቀጫ ብር 8,000 በድምሩ 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ የባንክ ወለድ ታስቦ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ በባንክ ወለድ እንድትከፍል የሰጠውን ውሣኔ ብቻ በማሻሻል ሌላውን የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት

የሰው ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ድንጋጌን የሚጥስ ነው በማለት የወረዳውንና የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች ነሐሴ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በብድር ገንዘብ የወሰደች መሆኑን ለማስረዳት ያቀረብኩት የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪ በሰነድ ላይ ያለውን ፊርማ ስለካዱና ፊርማውን በቴክኒክ ምርመራ ለማረጋገጥ ስላልተቻለ ውሉ ሲፈረም የነበሩ ምስክሮች ተጠሪ በሰነዱ ላይ የፈረሙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሰጡትን ምስክርነት መሠረት በማድረግ የተሰጠውን ውሣኔ አላግባብ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ ግንቦት 7 ቀን 1993 ዓ.ም ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ ተበድራ የወሰደች መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ማለትም ግንቦት 7 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈና በተዋዋይ ወገኖች የተፈረመ የብድር ውል መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ይህም አመልካች የብድር ውሉን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟላና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆኑን ያሣያል፡፡

ተጠሪ በብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የእኔ ፊርማ አይደለም በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2008 መሠረት ክዳ ተከራክራለች፡፡ በውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆኑን ለማረጋገጥ የቴክኒክ ምርመራ የተደረገ ቢሆንም ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ እንዳተልቻለ፣ የፖሊስ ፎረንሲክ ላብራቶሪ በመግለፁ፣ ፊርማው የተጠሪ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ /Authenticate/ ለማድረግ በውሉ ላይ ስማቸው የተገለፁት ሰዎች ተጠሪ በውሉ ላይ ስትፈርም ያዩ መሆኑን እንዲያረጋግጡ ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ ተበዳሪው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የብድር ውሉን ለማስረዳት በቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ ያለው ፊርማ ተበዳሪው የእኔ አይደለም በማለት የካደ በሆነ ጊዜ ፊርማው የተበዳሪው መሆኑን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት አለው የሚለው በሰነድ ላይ ያሉ ፊርማዎችን ለማረጋገጥ /Authenticate/ ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎች መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

በሰነድ ላይ ያለ ፊርማ በተካደ ጊዜ ፊርማውን የማረጋገጫው የመጀመሪያው መንገድ የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ፊርማውን በቴክኒክ ምርመራ የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ፊርማው ሲፈረም የነበሩ ምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ /Authenticate/ ለማድረግ የሚቻል መሆኑ ከማስረጃ ሕግ ጠቅላላ መርሆች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአገራችን ፊርማ በምስክሮች ቃልና በሌላ ማስረጃ እንዳይረጋገጥ /Authenticate/ እንዳይደረግ የሚከለክል ግልፅ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ በአንፃሩ ፊርማ በተካደ ጊዜና ፊርማውን በፎረንሲክ ምርመራ ለመለየት የማይቻል በሆነ ጊዜ

በምስክሮች ቃልና በሌሎች ማስረጃዎች ማረጋገጥ እንደሚቻል በፍርድ ቤቶች ለረዥም ጊዜ የዳበረው የአሰራር ልምድ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የብድር ውልን በሰነድ ማስረዳት በአስገዳጅነት የሚደነግገውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በማስረጃነት በቀረበ ሰነድ ላይ ያለ ፊርማ ሲካድ ፊርማው ከሚረጋገጥበት ሁኔታ /Authentication/ ጋር ያላቸውን ልዩነት ሳያገናዝቡ አመልካች በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ ከማረጋገጥ /Authentication/ ጋር አንድና ተመሣሣይ አድርጎ በመውሰድ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1ን ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል በብድር ውል ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ ፊርማ መሆኑን በማስረጃ ያረጋገጡት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በብድር የወሰደችው ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ በተጨማሪ 8,000 /ስምስት ሺህ ብር/ ጨምራ እንድትከፍል የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚቃረንና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ እንደዚሁም የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የቀዳማዊ ወያኔ ወረዳ ፍርድ ቤትና የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
3. ተጠሪ ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ በዚህ ጉዳይ ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ታስቦ ለአመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለባት በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 66935
ሰኔ 5 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ሽመልስ አበራ - ጠበቃ አቶ ማሩ ባዘዘው ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ጌታቸው አያልቂ - ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54218 በኅዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63616 በመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የፊልም ሥራ ውል አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ከተከሳሽ ጋር ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ ታሪክ ወደ ፊልም ለመቀየር ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም ውል ተዋውለናል፡፡ በውሉ ከሳሽ ለፊልም ሥራ ወጭ መሸፈን ግዴታ ያለብኝ ሲሆን ተከሳሽ ፊልሙን ለመሥራት የወጣው ወጭ ከተሸፈነ በኋላ ትርፍ እኩል ለመካፈል ተስማምተናል፡፡ ከሳሽ በውሉ መሰረት ፊልሙ ተጠናቆ ለእይታ እስከበቃ ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ አውጥቻለሁ፡፡ ተከሳሽ ፊልሙ ለእይታ ከበቃ በኋላ በውሉ መሰረት በፊልሙ የተገኘውን ገቢ አላሳወቀኝም፣ ለፊልሙ ሥራ ያወጣሁትን ወጭ አልከፈለኝም፡፡ ከስፖንሰር የተገኘውን ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ አልከፈለኝም፡፡ ከሣሽ ለፊልሙ ሥራ ከእንግሊዝ አገር ስመላለስ ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ አውጥቻለሁ፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ከእንግሊዝ አገር ስመላለስ ያወጣሁትን ወጭ ተከሳሹ እንዲሸፍን፣ ፊልሙ ለእይታ እንዳይቀርብና የፊልሙ ማስተር እንዲቃጠልና ለገበያ የተሰራጨው እንዲሰበሰብ፣ በፊልሙ የተገኘው ገቢ ታስቦ ድርሻዬን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስና ከሳሽ በአማራጭ ሂሳቡ ተጣርቶ ለፊልም ሥራው ያወጣሁት ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ ተከሳሽ እንዲከፍል፣ ፊልም የሚያስተዳድር ባለሙያ ተሹሞ ፊልሙን ተረክቦ በማሳየትና በማስተዳደር ገቢውን እንዲያካፍለን፣ ከስፖንሰር ከተገኘው ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ ድርሻዬን ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ተከሳሽ እንዲከፍልና ተከሳሽ የፊልሙን ፕሮዲውሰር ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስያሜ ከከሳሽ ስምምነት ውጭ ያሳተመ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት የኢኮኖሚና ሞራል ጉዳት ካሳ ከውሉ መቀጫ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሽ በውሉ መሰረት ያወጡት ወጭ ብር 232,000 /ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር/ ብቻ ነው፡፡ ከከሳሽ ጋር ውል የፈጸመው ወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ስያሜው ሪሽ የማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም በሕጋዊ መንገድ የተቀየረ በመሆኑ ክሱ የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ሪሽ የማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት ለፊልሙ ሥራ የከሳሽ ወኪል እያጸደቀው ብር 307,338.73 /ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሣንቲም/ ያወጣ በመሆኑ ከሳሽ ይህንን ገንዘብ ሊተካ ወይም ሊያቻቻል ይገባል፡፡ ከሳሽ ለፊልም ሥራ የሚሆነውን የድርሰት ሥራ በማቅረባቸው ብቻ የተከሳሽን የፕሮዲውሰርነት መብት ለመጋፋት አይችልም፡፡ ከስፖንሰር የተገኘው ገንዘብ ፊልሙን ለማስመረቅ ለወጣው ወጭ የዋለ ስለሆነ ከሳሽ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ ፊልሙን የማስተዳደር መብት ያለው ተከሣሽ በመሆኑ ክሱ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኂላ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ሊፈረስ ይገባል ወይስ አይገባም? ከሳሽ ለፊልሙ ማሰሪያ ያወጣውና ለተከሳሽ የሚከፍለው ተጨማሪ ገንዘብ አለ ወይም የለም? ተከሳሽ ለከሳሽ ካሳ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች ከመሰረተ በኂላ ውሉ በተከሳሽ ጥፋት ሊፈረስ ይገባዋል ተከሳሽ ለፊልሙ ማሰሪያ አውጥቻለሁ በማለት ያቀረበው የተጨማሪ ገንዘብ ጥያቄ ሚዛን በሚደፋ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሳሽ ፊልሙን በካሳ ክፍያነት ይረከቡት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኂላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም መጋቢት 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪ ውል የተዋዋለው በመጀመሪያ ወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ከሚባለውና በኂላ ስያሜው ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም በሕጋዊ መንገድ ከተቀየረው ድርጅት ጋር ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ አመልካችን በስሙ መክሰሱ የሕግ መሰረት የለውም፡፡ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የውል ግዴታውን በመተላለፍ የተጠሪን የስራ አመንጭነትና የኢኮኖሚ መብት አሳጥቷል በማለት ውሉ እንዲፈርስ የሰጡት ውሣኔ አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 30፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ/ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የሚተላለፍና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሰረት የሌለው ሲሆን አመልካች የተጠሪ ወኪል በመሆን ያጸደቀው ወጭ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ከሃያ አመት በፊት የደረስኩትና ተወዳጅ የሆነው የድርሰት ሥራዬን ወደ ፊልም ለመቀየር ከአመልካች ጋር ውል በመዋዋል በውሉ መሰረት ግዴታዬን ተወጥቻለሁ፡፡ አመልካች ውሉ ሲደረግ የነበረውን ድርጅት ስያሜ በመቀየር ከኃላፊነት ለማምለጥ የሞከሩ በመሆኑ ክሱ በስሙ መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ ለአዶቪዥዋል ሥራው ሙሉ ግብአት የሆነው የእኔ ድርሰት በመሆኑና ለፊልም ስራው የወጣውን ወጭ ተጠሪ የሸፈንኩ በመሆኑ የፊልሙ ፕሮዲውሰር ተደርጌ መወሰድ ያለብኝ እኔ እንጂ አመልካች አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ውሉን ያላከበረ መሆኑን በማረጋገጥ ፊልሙን እኔ እንድረከብ የሰጡት

ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከር ክርክር አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካችና ተጠሪ ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ ታሪክ ወደ ፊልም ለመቀየር ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም ያደረጉት ውል እንዲፈርስና ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከብ የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካችና ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል ስላለባቸው ግዴታና ኃላፊነትና በውል የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በሚፈጽሙበት ጊዜ ስለአከናወኗቸው ተግባራትና ሳይፈጸሙ ስለቀሩት ተግባራት፣ ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የደረሱባቸው መደምደሚያዎችን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች የወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በመቅረብ ከተጠሪ ጋር ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም ውል ተዋውለዋል፡፡

በውሉ ተጠሪ ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥ የሚያስፈልገውን ወጭ ለመሸፈን፣ አመልካች ደግሞ የፊልም ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ተግባራት ሁሉ በመፈጸም የፊልም ሥራውን በማጠናቀቅ ለዕይታ ለማብቃት ግዴታ የገቡ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥ የወጣውን ወጭ ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ በውሉ መሰረት ሸፍኛለሁ በማለት የተከራከረ ሲሆን አመልካች ተጠሪ በውሉ መሰረት ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥ ከወጣው ወጭ ብር 539,338 /አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር/ ውስጥ ብር 232,000 ብቻ የከፈለ በመሆኑ በውል የገባውን መሰረታዊ ግዴታ አልተወጣም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ለፊልሙ ሥራ የወጣው ወጭና ተጠሪ ለአመልካች የከፈለው የገንዘብ መጠን ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት መሰረታዊ ጭብጥ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ነጥብ በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃ የሰማውና የመረመረው የፊልሙን ሥራ ለማጠናቀቅ የወጣው ወጭ ብር 539,338 /አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር/ ነው በማለት አመልካች ተጠሪ ብር 307,338.73 /ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሳንቲም/ ያወጣ በመሆኑ ለአመልካች ሊተካ ወይም ሊቻቻል ይገባል በማለት ታዓሚነት ባለውና ሚዛን በሚደፋ ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህንን የሥር ፍርድ ቤት መደምደሚያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀብሎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ለፊልሙ ሥራ ማጠናቀቂያ ያወጣው አመልካች እንደሚለው ብር 232,000 /ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ/ ብር ሣይሆን ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ በውሉ መሰረት የፊልሙን ሥራ ለማጠናቀቅ የወጣውን ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ በመሸፈን በውሉ የገባውን ግዴታ ሙሉ በሙሉ የተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት

ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ የፊልም ሥራው የተጠናቀቀና ፊልሙ ለዕይታ ከበቃ በኂላ በዚህ ክርክር ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ፊልሙ ለዕይታ ከበቃ በኂላ በውሉ መሰረት ገቢውን ለተጠሪ አለማሳወቁ፣ ተጠሪ ያወጣው ወጭ በመጀመሪያ አለመተካቱና፣ ከተጠሪ ጋር በመጀመሪያ ውል የተዋዋለውን ወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ የሚባለውን ድርጅት ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም እንዲመዘገብ በማድረግ የውል ግዴታውን በመፈጸም በኩል ጉድለት ያሳየ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

2. ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው መወሰን መብት ያላቸው መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ተደንግጓል፡፡ የቅጅ መብት ባለቤቱ ኢኮኖሚያዊ መብቱን በሙሉ ወይም በከፊል በስምምነት ለማስተላለፍ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 23 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከአመልካች ጋር በውል ከተስማማ በኂላ የድርሰቱ ባለቤት እኔ ስለሆንኩ የኢኮኖሚ መብት ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክርና አመልካች የፊልሙ ፕሮዲውሰር በመሆኔ መብቱ የእኔ ብቻ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 23 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና የሕግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው ውል መሰረታዊ ይዘት የተጠሪ ድርሰት ሥራ የሆነውን ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ ወጭው ከተተካ በኂላ የሚገኘውን ገቢ በመካፈል የፊልሙ የጋራ የሞራልና ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚ መሆን ነው፡፡ ተጠሪ በውሉ መሰረት የፊልሙን ሥራ ለማጠናቀቅ የወጣውን ወጭ ሙሉ በሙሉ በመሸፈን በውሉ የገባውን ግዴታ ሙሉ በሙሉ የተወጣ መሆኑን ፍሬ-ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ የፊልም ሥራው የተጠናቀቀና ፊልሙ የተመረቀና ለዕይታ የበቃ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቀው አመልካች ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥና የፊልም ስራውን ለማጠናቀቅ የገባውን መሠረታዊ ግዴታ አልተወጣም በሚል ምክንያት አይደለም፡፡ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቀው ፊልሙ ከተመረቀና ለዕይታ ከበቃ በኂላ አመልካች ፊልሙን በውሉ መሰረት በማስተዳደር የተገኘውን ገቢ የማሳወቅና የተጠሪን የጋራ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ግዴታውን በአግባቡና በውሉ መሰረት አልተወጣም በማለት ነው፡፡

አንድ የጸና የውል ግዴታ የገባ ሰው ውሉ በፍርድ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችለው ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግዴታዎቹን ያልፈጸመ እንደሆነ ወይም የፈጸማቸው ሙሉ ወይም ፍጹም ባልሆነ አኳኋን እንደሆነ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 ተደግንጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውሉ አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልተደረገ በስተቀር ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ እንደማይወስኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን ዳኞች ውሣኔ ለመስጠት የተዋዋዮቹን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሰረት ማድረግ እንዳለባቸው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካችና

ተጠሪ የተጠሪ ድርሰት ሥራ የሆነውን ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ ወጭው ከተተካ በኋላ የሚገኘውን ገቢ በመካፈል የፊልሙ የጋራ የሞራልና ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ያደረጉትን አይነተኛ የውል ግዴታ ፈጽመው አሁን ሚከራከሩት በፊልም አስተዳደር ሥራ አመራርና ገቢ ክፍፍል በተለይም ተጠሪ ለፊልም ሥራው ያወጣውን ወጭ ፊልሙ ለዕይታ ከቀረበ በኋላ በቀዳሚነት ሊሸፈን ይገባው ነበር፤ ይህንን ባለመፈጸሙ አመልካች የውል ግዴታውን ጥሷል በማለት ነው፡፡

ውሉን ማፍረስ አመልካችና ተጠሪ፣ የተጠሪ ድርሰት ሥራ የሆነውን ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ የሚገኘውን ገቢ በመካፈል የፊልሙ የጋራ የሞራልና ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚ መሆን ለማረጋገጥ የሚያስችል አይደለም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከበቃ በኋላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳውን አለመግባባት መነሻ በማድረግ ውሉ እንዲፈርስ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በውሉ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልተደረገ በስተቀር ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ እንደማይወስኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ ከወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ከሚባለው አመልካች ሥራ አስኪያጅ ከሆነበት ድርጅት ጋር ውል ከተዋዋለ በኋላ የድርጅቱ ስያሜ ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም በሕጋዊ መንገድ መቀየሩ ተጠሪ በፊልሙ ላይ ያለውን የሞራልና የኢኮኖሚ የጋራ ባለመብትነት የሚጋፋ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውንና ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ዳኞች ውሣኔ ለመስጠት የተዋዋዮቹን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሰረት በማድረግ እንዳለበትና የውሉ መሰረታዊ ነገሮች ባልተካከበት ሁኔታ ውሉ እንዲፈርስና ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከብ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከበቃ በኋላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፊልሙ ከተጠናቀቀ በኋላ አመልካች ቀጣይነት ያለውን ፊልሙን በውሉ መሰረት የማስተዳደር፣ ገቢውንና ወጭውን ለተጠሪ የማሳወቅና የማካፈል ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በማለት የደረሱበት የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣናቸውን በመጠቀም የደረሱበት በመሆኑ በአግባቡ ነው፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ እንዲረከቡ የሰጡት ውሣኔ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 4 በመጥቀስ ካቀረቡት የጉዳት ካሳ ጥያቄ የወጣና ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ግልጽ የዳኝነት ጥያቄ ያላቀረቡበትና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከቡ የሰጡት ውሣኔ ተጠሪ በአማራጭ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ፊልሙ ገለልተኛ በሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲተዳደር ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም መነሻ ፊልሙ ከተመረቀና

ለእይታ ከበቃ በኂላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን መነሻ በማድረግ ውሉ እንዲፈርስ ከመወሰን ይልቅ ተጠሪ በአማራጭ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ፊልሙ ገለልተኛ በሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲተዳደር በማድረግ ተጠሪ ለፊልሙ ሥራ ያወጣው ወጭ ከተተካ በኂላ አመልካች ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅትና ተጠሪ ትርፉን እኩል እንዲካፈሉ ማድረግ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚያሳካ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በጠቀስናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ እንዲፈርስና ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54218 በኀዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63616 በመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል መሰረት አይነተኛ ግዴታቸውን ተወጥተው የፊልም ሥራው ተጠናቆ የተመረቀና ለዕይታ የበቃ በመሆኑ ውሉ አይፈርስም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለፊልም ሥራው ያወጣሁት ተጨማሪ ወጭ አለ በማለት የጠየቀውን ብር 307,338.73 /ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሳንቲም/ የመቻቻል ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው በማለት አጽንተነዋል፡፡
4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለፊልም ሥራው የወጣውን ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ ሙሉ በሙሉ የሸፈነው ተጠሪ ነው በማለት የሰጡት የውሣኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከበቃ በኂላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን አልተወጣም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
6. ተጠሪ በአማራጭ ባቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ፊልሙ ገለልተኛ በሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲተዳደር እንዲታይ በማድረግና ከዚህ በፊት ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከቀረበ በኂላ ፊልሙን በማሳየት የተገኘው ገቢ ፊልሙን ለማሳየት የወጣው ወጭ ሂሳብ ተሰርቶ በመጀመሪያ ተጠሪ ለፊልም ሥራው ያወጣውን ወጪ ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ እንዲተካ ከተደረገ በኂላ ትርፉን አመልካችና ተጠሪ በውሉ መሠረት እኩል እንዲካፈሉ በማድረግ በፊልሙ ላይ ያላቸው የጋራ የሞራልና የኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚነት መብት ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ በዚሁ መንገድ የውሉ ተግባራዊነት ሊቀጥል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
7. በዚህ ችሎት ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
8. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ 75902
ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ ነጋ አበበ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ደበበ ተሊሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአፈፃፀም ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአፈፃፀም ተከሳሾች ደግሞ እነ ስንዱ ሹሜ /ሶስት ሰዎች/ ነበሩ፡፡ ተጠሪው በአፈፃፀም ተከሳሾች ላይ ክስ የመሰረተው ብር 148,985.05 /አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም/ በፍርድ የተወሰነለት መሆኑን በመግለጽ ከወጪና ኪሣራ ጋር በድምሩ ብር 153,293.05 /አንድ መቶ ሃምሳ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም/ በአንድነት እንዲከፍሉ፣ ይህንን ባይፈፅሙ የካርታ ቁጥሩ MR.497052 የሆነ ቤትና ለብድሩ 2ኛ የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ሹሜ ሮቢ በመያዣ ቁጥሩ 355 የሆነ በሁሩታ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቤት ያስያዙ መሆኑን ገልፆ አፈፃፀሙ በዚህ አግባብ እንዲመራለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በዚህ መሰረት ባለእዳዎች የተባለውን ገንዘብ መክፈል ባለመቻላቸው ተጠሪ የጠቀሰው ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ ትእዛዝ ሊሰጥ ንብረቱ ተገምቶ እንዲቀርብ የሚመለከተው አካል ሲታዘዝ ቁጥሩ 355 የሆነ ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ሆቴል ቤት የተሰራ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ የገለጸ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም ይህንኑ የሆቴል ንብረት በብር 536,822.00 /አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ብር/ ብድር በካርታ ቁጥር 8205/ሹ/71/88 ይዞ ለስር 2ኛ እና 3ኛ የአፈፃፀም ተከሳሾች ብድር ያበደረ መሆኑን ጠቅሶ በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት ያለው መሆኑን ዘርዝሮ ሐራጁ በንብረቱ ላይ ሊቀጥል አይገባም ሲል ተቃውሞውን አቅርቦ የአሁኑ ተጠሪም ቤቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ራሱ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኂላ፣ አመልካች ንብረቱን የያዘው ከተጠሪ በተለየ ካርታና የቤት ቁጥር ስለመሆኑ መረጋገጡን ገልፆ የተጠሪ አፈፃፀም በሆቴል ቤቱ ሊቀጥል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቦታው ላይ የነበረውን ቤት ቀድሞ በመያዣነት የያዘው የአሁኑ ተጠሪ መሆኑን፣ አመልካች ያዝኩ

የሚለው የሆቴል ቤት በቦታው ላይ እንደ አዲስ የተሰራ እንጂ የተለያየ ቤት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ያሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በመያዣነት የያዘው ንብረት በካርታ ቁጥሩም ሆነ በንብረቱ አይነት ተጠሪ በመያዣነት ያዝኩ ከሚለው ንብረት የካርታ ቁጥርና የንብረት አይነት የተለየ ሁኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመያዣ ቀዳሚ መብት ያለው ተጠሪ ነው በማለት መወሰናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3066 ድንጋጌንና ሌሎች የመያዣ ሕግ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባግባቡ ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን ጉዳዩ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ መታየት ያለበት መሆኑ ታምኖ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርበው በፅሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች ያዝኩ የሚለው የሆቴል ድርጅት ተጠሪ ቀድሞ በመያዣነት የያዘው ንብረት በነበረበት ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ ይኸው ንብረት ተጠሪ ቀድሞ የያዘው ንብረት አካል ተደርጎ ከሚቆጠር በስተቀር የተጠሪን የመያዣ መብቱን ሊያሳጣ የሚችል አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ በመያዣ ይዞት የነበረው ንብረት መኖሪያ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ የሆቴል ድርጅቱን መሆኑን፣ የሁለቱም ቤቶች ካርታ ቁጥር የተለያዩ መሆናቸው የሚታወቅ ከሆነ አመልካች በሌላ አዲስ ካርታ ቁጥር በመያዣ የያዘው የሆቴል ድርጅት ተጠሪ ቀደም ብሎ በመያዣነት ይዞት በነበረው መኖሪያ ቤት የፈረሰበት ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ ብቻ ተጠሪ በመያዣ በተያዘው የሆቴል ድርጅት ላይ የቅድሚያ መብት አለው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዘበን መርምረናል፡፡

በመሰረቱ አከራካሪው ነጥብ የሚወሰነው ስለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች መያዣ እና አፈፃፀሙን በሚመለከት በፍትሐብሔር ሕጉ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው ተጠሪ በመያዣ ይዞት የነበረው ንብረት መኖሪያ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ የሆቴል ድርጅቱን መሆኑን፣ የሁለቱም ቤቶች ካርታ ቁጥር የተለያዩ መሆናቸውን፣ አመልካች በሌላ አዲስ ካርታ ቁጥር በመያዣ የያዘው የሆቴል ድርጅት ተጠሪ ቀደም ብሎ በመያዣነት ይዞት በነበረው መኖሪያ ቤት የፈረሰበት ቦታ ላይ የተሰራ መሆኑን፣ አመልካች ብድሩን የሰጠው ጥቅምት 18 ቀን 1989 ዓ/ም እና መስከረም 20 ቀን 1990 ዓ/ም በተፈረመ የብድር ውል ሁኖ የገንዘቡ መጠንም ብር 536,822.00 /አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ብር/ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ብድሩን የሰጠው ሰኔ 05 ቀን 1985 ዓ/ም ሁኖ የገንዘቡ መጠንም ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ነው፡፡ ይህም ማለት አመልካች ብድሩን ከተጠሪ በኋላ የሰጠ ሁኖ ለብድሩ በመያዣነት የተያዙት ንብረቶች የሚታወቁበት ካርታ ቁጥር፣ የንብረቶቹ አይነት የተለያየ ሁኖ አንድ የሚያድርጋቸው ቦታው ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በመሰረቱ የማይንቀሳቀው ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ አዲስ ሥራ ቢሰራ ወይም ማሻሻል ቢደረግ የመያዣ ውሉን አፈፃፀም በተመለከተ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? ለሚለው

ጥያቄ የፍ/ብ/ሕግ ቁ.3066 ግልጽ የሆነ መልስ ሰጥቶአል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መብት የመያዣው መብት በሚመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረትና በዚሁ ንብረት ላይ የሚሰሩትን አዳዲስ ሥራዎች እንደሚያጠቃልል ያመለክታል፡፡ ይህን ድንጋጌ ከያዝነው ክርክር ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ተጠሪ ቤቱን በመያዣነት ከተበዳሪዎች ከያዘ በኋላ ተሰራ የሚባለው አዲስ ሆቴል ድርጅት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ንብረቱ የሚታወቅበት የካርታ ቁጥርና የንብረቱ መለያ ቁጥር ተጠሪ ከያዘው ንብረት በአይነትም ሆነ በመለያ ቁጥሩ ፈፅሞ የማይገናኝ ከሆነ ስራው አዲስ ቢሆንም ቀድሞ ከነበረው ንብረት ስር የሚጠቃለል ነው ሊባል የሚችል አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በተለይ የዚህን ድንጋጌ መንፈስ እና አላማ ስንመለከት መያዣ ሰጪው ንብረቱ በመያዣ የተሰጠ መሆኑን እያወቀ በንብረቱ ላይ አዳዲስ ስራዎችን ቢሰራ መያዣ ያገኙ አዳዲስ ስራዎችን ሁሉ በመያዣ እንደያዘ የሚያስቆጥረው እና መያዣ ሰጪው እያወቀ ለሰራቸው ሥራዎች መያዣ ያገኙን ለመጠበቅ ተብሎ የተቀረፀ ድንጋጌ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ይህንን ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የንብረቱ መለያ የሆነው ካርታ ቁጥር ተለያይቶና ንብረቱ ሙሉ በሙሉ በአይነቱ ተለይቶ መሰራቱ ግንዛቤ ካልተወሰደና ይህንኑ መሰረት በማድረግ በንብረቱ ላይ እግድና እዳ የሌለ መሆኑን በመገንዘብ መያዣ የሚወስዱ ቅን ልቦና መያዣ ሰጪዎችን መብት ስንመለከት በሕግ ጥበቃ የማያገኙበት ምክንያት የለም፡፡ የፍ/ብ/ቁጥር 3052/1/ የአስተዳደር ክፍሉ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት መሆኑን አውቆለት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋራ የተደረገ የንብረት መያዣ ውል የሚፀና ነው በሚል የተቀመጠው ድንጋጌ በሕግ አግባብ የተሰጠውን ካርታ ይዞ የሚያበድረው አበዳሪ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በመያዣነት የያዘው ንብረት ካርታ ቁጥሩም ሆነ አይነቱ ከተጠሪ የተለየ ሁኖ እያለ ቦታው አንድ በመሆኑ ብቻ አመልካች የያዘው ንብረት ተጠሪ በያዘው ንብረት ስር የሚጠቃለል ነው ተብሎ ሊወሰን የማይገባውና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3066፣ 3052 እና ሌሎች ድንጋጌዎችን ዓላማና መንፈስ የሚጥስ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 106039 ጥር 21 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 66122 ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አንድ ቀድሞ በመያዣ የተሰጠ ንብረት ካርታ ቁጥሩና የቤት ቁጥሩ ተለውጦ እንዲሁም ንብረቱ ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ንብረት ተሰርቶና አዲስ ካርታና የቤት ቁጥር ተሰጥቶ በተገኘ ጊዜ ይህንኑ አዲሱን ንብረት በመያዣ የያዘ አበዳሪ ቀድሞ የነበረውን ንብረት ከያዘው አበዳሪ የቅድሚያ መብት አለው ብለናል፡፡
3. በካርታ ቁጥር 8205/ሹ/71/88 በሚታወቀው የሆቴል ቤት የቀዳሚነት መብት ያለው አመልካች ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 61421
ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ጌታቸው በየነ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. የሕፃን ታቦት በቀለ
2. የሕጻን ሒሩት በቀለ
} ሞግዚት ሙሉቀን መንግስቱ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤትና የቦታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ሞግዚት ባሁኑ አመልካች ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪዎች ክስ ይዘትም ከሴት አያታቸው ከወ/ሮ ጌጤ ለገሰ አባታቸውን አቶ በቀለ በየነን በመተካት የሚወርሱትን በባህርዳር ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ ኤ-49 በሚል የሚታወቀውን መኖሪያ ቤት የአሁኑ አመልካች ያላግባብ ይዘው እንደሚገኙና ሊለቁላቸውም ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልጸው ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡አመልካች ተጠሪዎች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ቤቱና ቦታው የሚች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ ስለመሆኑ ሳይክዱ ቤቱና ቦታውን ሚች ለአመልካች በስጦታ ያስተላለፉላቸው መሆኑን፣ስጦታው ሊደረግላቸው የቻለውም ሚችን ሲጦራቸው ስለነበርና ለሚች በ1988 ዓ.ም ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) አበድረው እስከ 1993 ዓ/ም ድረስ ሊከፍል ይችል የነበረው የጥሬ ገንዘብ ብድር ባለመመለሱ ምክንያት ቤቱን ሚች ብድሩን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው የሰጧቸውና በስጦታ ውሉ መሰረትም ስመ ሀብቱ ለአመልካች እንዲዞር ሚች ወደ ሚመለከተው አካል ቀርበው በማመልከቻ ጠይቀው ጉዳዩ በሂደት ላይ እንዳለ የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን፣ቤቱን ይዘው ግብር እየገበሩበት እንደሚኖሩና በ1997 ዓ/ም በደረሰው የጎርፍ አዳጋ ምክንያትም ቤቱ በመፍረሱ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ወስደው ብር 56,347.00 ወጪ አድርገው ቤቱን የሰሩት መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክርክሮች ሕጋዊ ያለመሆናቸውን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችንና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን፣አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችን ሁሉ በዋቢነት ከጠቀሰ በኋላ አመልካች ለተጠሪዎች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚሁ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ከዚህም በኋላ

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436 እና 1723 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላግባብ መተርጎማቸውንና በፍሬ ነገር ደረጃ ተዛማጅነት የሌላቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችን በመጥቀስ ውሳኔ መስጠታቸውን በመግለጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቹ በስጦታ ውሉ ሳይፈርም መቅረቱ ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል የመባሉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436 ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተድርጎላቸውም ሞግዚታቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ ባቀረቡት ክርክር በይዘቱ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎቸ በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ሴት አያታቸውን ሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰን የእኚሁ ሴት ልጅ የሆነውንና ሴትዩዋን ቀድሞ የሞተውን አቶ በቀለ በየነን በመተካት በውርስ የሚያገኙትን ቤት የአሁኑ አመልካች ያላግባብ ይዞ ይገኛል በሚል ምክንያት መሆኑን፣አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ በስጦታ ውሉ ላይ ስጦታ ተቀባይ የሆኑት አመልካች ባይፈርሙም ሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ በ24/03/1996 ዓ/ም ስጦታ አድርገውላቸው የቤቱ ስመ ሀብት እንዲዞር ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ አስገብተው ጉዳዩ በመጣራት ላይ እንዳለ ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ ከዚህ አለም በሞት የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ/ም የተለዩ መሆናቸውን ገልፀው ስጦታውን በተግባር የተቀበሉ መሆኑን ያሳያል በሚል መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ስጦታ በሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ ተደረጎልኛል የሚሉት ሕዳር 24 ቀን 1996 ዓ/ም ሲሆን ሟች ከዚኅ አለም በሞት የተለዩት የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ/ም መሆኑንና እስከዚህ ጊዜ ድረስ የስመ ሀብት ዝውውር ማመልከቻ ቀርቦ ነበር ከማለት ውጪ አመልካች ቤቱን በይዞታቸው ስለማድረጋቸው ያለመረጋገጡንም ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባሉት የስጦታ ውል ከሟቹ ህልፈተ ሕይወት በኂላ ተፈፃሚ የሚሆነው ነው፡፡ በእንደዚህ አይነት የስጦታ ውል ስለኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ድንጋጌ በኃይለ ቃል ያስቀምጣል፡፡በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2443 ስር ደግሞ በማይንቀሳቀስ ንብረት የሚደረግ ሥጦታ በግልፅ በሚደረግ ኑዛዜ አሰራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ አሰራር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ስር ተመልክቷል፡፡እንዲህ ከሆነ የሟች ሕጋዊ እና የኑዛዜ ወራሾች የስጦታው አሰራር በሕጉ የተቀመጠውን አሰራር የተከተለ መሆን ያለመሆኑን መሰረት አድርገው ክርክር ሲያቀርቡ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን በመመልከት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስጦታ ውሉ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን በግራ ቀኙ ክርክር የቀረበበት ሲሆን የተጠሪዎች ሞግዚት አጥብቀው የሚከራከሩት የስጦታ ሰነዱ በሕጉ አግባብ ያልፀደቀና አመልካችም ያልፈረሙበት ነው በሚል ነው፡፡የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(1) ድንጋጌ ሲታይም የስጦታ ውል ፍጹም የሚሆነው ስጦታ ተቀባዩ ለእርሱ የተደረገውን ልግስና እቀበላለሁ ብሎ አሳቡን

የገለጸ እንደሆነ ስለመሆኑ ያስቀመጠ ሲሆን በተጠቃሹ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ ሰጪው ከሞተ ወይም ችሎታ ከአጣ በኋላ ስጦታውን እቀበላለሁ የማለት ቃል ዋጋ የለውም የሚል ሃይለ ቃል በያዘ መንገድ ተቀምጧል፡፡ሁለቱ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩም የመቀበሉ አሳብ በፅሑፍ ይሁን በድርጊት ለይተው ያስቀመጡት ነገር የሌለ ሲሆን ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ በዚህ ረገድ መገንዘብ የሚቻለው የስጦታው መቀበሉ ሀሳብ በፅሑፍ(ፊርማ) ወይም በድርጊት መቀበል የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ስለሆነም ስጦታ ተቀባዩ ስጦታውን ስለመቀበሉ የሚያስረዳ የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ስለመቀበሉ ጠቋሚ የሆነ ድርጊት ስለመኖሩ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ስጦታ ውሉ ላይ ያልፈረሙ ስለመሆኑ የሚክዱት ፍሬ ነገር ሳይሆን ስጦታውን መቀበላቸውን ያሳያል በማለት የሚከራከሩት በቤቱ ላይ ግብር መገበራቸውን፣ቤቱ ላይ እድሳት ማድረጋቸውንና ሟች በወቅቱ የስጦታ ውሉን ይዘው ወደሚመለከተው አካል ቀርበው ስመ ሃብቱ ለአመልካች እንዲዞር አቤቱታ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑ መረጋገጡን ነው፡፡ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው የስጦታ መቀበል ተግባር መኖር ያለመኖሩ በጽሑፍ ማስረጃ ወይም በድርጊት ወይም በሌላ አግባብነት ባላቸው መንገዶች የሚረጋገጥ ሁኖ እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖር ያለመኖራቸውን ፍሬ ነገሩን ለማረጋገጥ እና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የሚያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን በዚህ አግባብም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የስጦታ ተቀባዩ እቀባለለሁ ስለማለቱ ሊያሳዩ የሚችሉ አይደሉም፣ሊታመኑም የሚችሉ አይደሉም በማለት ደምድሞ ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡

በመሆኑም አመልካች ስጦታውን አልተቀበሉም ተብሎ ድምዳሜ የተደረሰው ፍሬ ነገሩ ተጣርቶና ማስረጃው ተመዝኖ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አንቀጽ 25/1988 አንቀጽ 10 ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር አመልካች ስጦታውን ስለመቀበላቸው ያሳያሉ በማለት የሚጠቅሷቸው ማስረጃዎች ታዓማኒነት እና ክብደት በዚህ የክርክር ደረጃ የሚታዩ ሁኖ አላገኘንም፡፡ አመልካች ሟች ከመሞታቸው በፊት ስጦታውን መቀበላቸው አልተረጋገጠም ከተባለ ደግሞ ከስጦታ ሰጪው መሞት በኋላ የስጦታ ውሉን እቀበላለሁ ቢሉ በሕጉ ዋጋ የሚሠጠው ተግባር ያለመሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(2) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(2) ድንጋጌን በመተርጎም ረገድ የፈጸሙት ስህተት የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የስጦታ ውሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 ድንጋጌን ያላሟላ ነው በማለት የያዘው ምክንያት ሲታይ ግን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 ለስጦታ ውል ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 39803 ሐምሌ 02 ቀን 2001 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ምክንያቱ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የብድር ጉዳዩን በተመለከተ ለውሳኔው አሰጣጥ በምክንያትነት መያዙም ሆነ ብድሩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት መደምደሙ ለክርክሩ አግባብነት የሌለው ሲሆን የክፍያ ግምት በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም በፍርድ ቤት ሊነሳ ይችላል ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 15493 ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 47988 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የተለወጠ ስለመሆኑ ያላገናዘበ በመሆኑ ምክንያቱ ተቀባይነት የሌለው

ነው፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 እና ስለብድሩ የቀረበውን ክርክር በተጨማሪ ምክንያትነት በመያዝ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱበት አግባብ ተገቢ ባይሆንም የስጦታ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(2) መሰረት ዋጋ የለውም በሚል የያዙት አብይ ምክንያትና ቤቱን አመልካች ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ሲሉ የሰጡት የውሳኔ ክፍል ግን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምእራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 27822 መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 289942 ሚያዚያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 09032 ሐምሌ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የሥጦታ ውሉን ስጦታ አድራጊዋ ከመሞታቸው በፊት የተቀበሉ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ተብሎ በ24/03/1996 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የስጦታ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436 መሰረት ዋጋ የለውም፣ቤቱን ለተጠሪ ሕፃናት እንዲያስረክቡ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በቤቱ ላይ ያወጡትን ወጪ በሕጉ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት በ25/02/2003 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 70963
የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቶች፡ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ - ነ/ፈጅ እንግዳወርቅ ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ- አቶ ተመስገን ማጉሌ
2ኛ- ዶ/ር ብዙአየሁ ተስፋዬ
} አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ከዋስትና ውል የመነጨ ግዴታ የሚጠየቅበትን አግባብ በሚመለከት በክልሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የህግ ትርጉም ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ካደረጉት ክርክር ጋር በማገናዘብ ተገቢውን የህግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ 1ኛ ተጠሪ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ለመማርና ተምሮ ሲጨርስ አገልግሎት ለመስጠት አመልካችም የሚጠበቅበትን ተነፃፃሪ የገንዘብ ክፍያ ለመፈፀም ጥቅምት 03 ቀን 2001 ዓ.ም ውል አድርገው በውሉም መሠረት 2ኛ ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ 23 ወራት ያህል ከተማረ በኋላ ከስምምነቱ ውጭ ወደ ሌላ / ጣሊያን / ሀገር ስለሄደ ግዴታውን ጥሷል፡፡ ስለሆነም እንደውሉ ባለመፈፀሙ በጠቅላላው ብር 195,796 ብር ሊከፍል ይገባል 2ኛ ተጠሪም ከዋናው ባለዕዳ ጋር ከዋስትና ግዴታ የመነጨ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ስላለባቸው ይክፈሉ ሲል የአሁን አመልካች በሥር በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ያቀረበው ክስ ሲሆን ተጠሪዎችም በየግላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ዋናው ባለዕዳ የተባለው 1ኛ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የውል መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት እንደግዴታው እንዲፈፅሙ ሊጠየቁ እንደማይገባ ገልፀው ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ የጠየቁ ሲሆን፤ 2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው የ1ኛ ተከሣሽ እምቢተኛ መሆኑ ሳይረጋገጥ መከሰሴ አግባብ አይደለም የግዴታውም ዓይነት ተራ ዋስትና በመሆኑ ከሣሽ ለግዴታው አፈፃፀም የዋናውን ባለዕዳ ንብረት ከመከተል ያለፈ ኃላፊነት ስለማይጥል የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤትም ይህንኑ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ሚያዚያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክሱ የቀረበው የግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ስለሆነ የግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ከደረሰ በኋላ ከሚጠይቅ በቀር በዚህ ደረጃ ላይ ተከሣሾችን ለመክሰስ አይችልም በማለት ዳኝነት የሰጠ ሲሆን ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይሄው የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ለይግባኝ ሙሉ ክርክር የሚያበቃ ሆኖ አልተገኘም በማለት የውሣኔውን አግባብነት ተቀብሎታል ፡፡

በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡትም ክርክር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ከቀረቡት የተለየ ሆኖ ባለመገኘቱ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ግራ ቀኙ በፍሬ ነገር ክርክር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር አንፃር ሁለቱንም ወገኖች ያለያያቸውን ነጥብ ለይቶ በዚሁ ላይ ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ዳኝነት በመስጠት ረገድ በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው 1ኛ ተጠሪ የውሉ ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱም በፊት ቢሆን በእራሱ ተግባር የተነሣ እንደ ውሉ ግዴታውን ለመፈፀም በማይችልበት ደረጃ ተገኝቷል ወይስ አልተገኘም? የሚለው እንጂ የግዴታ መፈፀሚያው ጊዜ ደርሷል ወይስ አልደረሰም የሚለው ጭብጥ አልነበረም፡፡

በዚህም ረገድ አመልካች እንደሚለው ተዋዋዩ ሃያ ሶስት ወራት በውሉ በተጠቀሰው አገር ከተማረ በኋላ ከተዋዋዩ ፈቃድ ውጪ በእራሱ አነሳሽነት  ወደ ሌላ አገር መዛወሩ ከተረጋገጠ የተዛወረበት ምክንያትም በዋናው ውል ከተጠቀሰው ተግባር ጋር የተያያዘም አይደለም ከተባለ እና ይህ በማስረጃ የሚረጋገጥ ከሆነ 1ኛው ተከሣሽ እንደውሉ የመፈፀሚያው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ውሉ ውጤት እንዳይኖረው በማድረግ እንደውሉ ግዴታውን ለመፈፀም የተሣነው በመሆኑ የውሉ መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱም በፊት መረጋገጡን ስለሚያሳይ ከሣሹ የግድ የውሉ መፈፀሚያ ከደረሰ በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት ከውል የመነጨ መብትህን ማረጋገጥ አትችልም ሊባል አይገባም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን ጭብጥ በመለየት ጉዳዩን ከመምራት አንፃር የተከተለው የጉዳይ አመራር ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተከሣሽ እንደ 1ኛ ተከሣሽ ሆኖ ለመፈፀም የገባው የዋስትና ዓይነት ተራ ዋስትና ነው ወይስ የአንድነትና የነጠላ? 1ኛው ተከሣሽ ግዴታውን ለመፈፀም እንዳልቻለ ተረጋግጧል ቢባል ሊከፈል የሚገባው ገንዘብ ምን ያህል ነው? የሚለውን አስመልክቶ ግራ ቀኙ በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ ሰበር ደረጃ አንስተው የተከራከሩበት ቢሆንም በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያላሳረፈበት በመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመለከተው አይደለም፡፡ ከዚህ በላይ በፍርዱ በተመለከተው ሐተታ ምክንያት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በፍ/ብ/ መ/ቁ 09829 ሚያዚያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ፤ የሰጠው ውሣኔ ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በቁጥር 53210 በ16/9/2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፍርዱ ሐተታ በተመለከተው ጭብጥ መሠረትም ሆነ በክርክር ምክንያት  ከባከነው ጊዜ አንፃር በመካከሉ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ሁሉ አገናዝቦ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
3. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ማናቸውም ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 36887

ሕዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ ገብሩ እሸቱ ገብሬ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ወርቂት እሸቱ ሁሴን ቀርበዋል

ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ የአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኝ ባይ እንዲሁም የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የስር ከሳሽ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ ተከሳሾች በኩታበር ከተማ፣ቀበሌ 01 የሚገኘውን በ500 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈውን ሁለት ክፍል የቆርቆሮ ቤት በመስከረም 13 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ሸጠውልኝ ገንዘቡንም ሙሉ በሙሉ ተቀብለው እያለ ቤቱን እንዲያስረክቡና ስመ ንብረትነቱም ስላላዞሩልኝ ተገደው እንዲያስረክቡኝና ስመ ንብረቱም በስሜ እንዲያዞሩልኝ ውሳኔ ይስጠኝ የሚል ነው፤ውሉ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮም የቤቱን ኪራይ በወር ብር 60 (ስድሳ ብር) ሂሳብ የ26 ወራት ይክፈሉኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሾችም በሰጡት መልስ ስልጣኑ የወረዳ ፍ/ቤት በመሆኑ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ የማከራከር ስልጣን እንደሌለው እንደተቃወሙና ውሉን ፈጽመን ገንዘቡን ከተቀበልን በኋላ ውሉ እንዳፈረስንና ገንዘቡን እንዲወስዱ ለከሳሹ ቢያሳውቋቸውም ገንዘባቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም፤ በመሆኑም የውሉ ይፈፀምልኝ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ብለዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን እንደሚያይና በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ ውል መኖሩ የታመነ በመሆኑና እንደውሉ ላለመፈፀም ያቀረቡት ምክንያት ተቀባይነት ስለሌለው ተከሳሾች ውሉን ተገደው እንዲፈጽሙ፣ስመ ንብረቱንም በከሳሽ ስም እንዲያዞሩ እንዲሁም የቤቱን ኪራይ ብር 1500 ለከሳሽ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ቅሬታ በማሳደር የስር ተከሳሾቹ ወደ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታቸውን አቅርበው ከተከራከሩ በኂላ ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ.1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በግራ ቀኙ ወገኖች ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ወደ ደቡብ ወሎ አስ/ፍ/መምሪያ የውልና ማስረጃ አካል ቀርቦ በመጣራት ላይ እያለ የቆመ በመሆኑና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት ያልተፈፀመ በመሆኑ በመካከላቸው የሚጸና ውል እንደሌለና ተዋዋዮቹ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ይመለሱ፣ ስለሆነም ይ/ባዮች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ለመልስ ሰጪ የነበሩት የአሁኗ አመልካች እንዲመልሱ ወስኗል፡፡

ይህ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ውሉ በጽሁፍና በምስክሮች ፊት የተፈፀመና ለምዝገባም ወደሚመለከተው አካል ቀርቦ እያለና ተጠሪዎች ውሉን ማድረጋቸውና ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ወስደው እንደነበር አምነው እያለ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723/1/ን መሰረት በማድረግ ውሉ በአዋዋይ ፊት አልተመዘገበም በሚል አተረጓጐም ውል የለም ማለቱ ተገቢ አይደለም፣ በመካከላቻው ውል መኖሩን አምነው ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም ብለው ለመከራከር ለሚቃጡ ተከራካሪዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ አያገለግልም የሚል ሆኖ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም ውሉ በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበና በእንጥልጥል የቀረ በመሆኑ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ እንዲጸድቅላቸው ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በአጭሩ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ የሰበር ችሎትም፣በመካከላቸው ውል አድርገው እንደነበር እያመኑ የቤት ሽያጩ በውልና ማስረጃ ባለመመዝገቡ ብቻ ምክንያት በማድረግ ውላቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ን መሰረት በማድረግ ተቀባይነት የለውም ሊሉ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በማስቀመጥ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል እንዳካሄዱና ተጠሪዎች የሽያጩ ጠቅላላ ገንዘብ ብር ለተጠሪዎቹ እንደሰጡ ሲገለጽ በስር ተከሳሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎችም ውል አድርገው የነበረ ቢሆንም በውልና ማስረጃ የተመዘገበ ባለመሆኑ የሰጧቸው ገንዘብ ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) እንዲወስዱ ቢጠይቋቸውም ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንደሚያስረክባቸው ገልጸዋል፤ በዚህም የተጠሪዎች መልስ ከአመልካች ጋር የቤቱን ሽያጭ ውል አድርገው እንደነበር እንጅ ውሉ በመካከላቸው እንዳልነበረ ፈጽሞ የሚክዱ አይደለም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል እንደነበር አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለ መመዝገቡ ብቻ ውል የለም፤ ብለው የሚቃወሙ ተከራካሪዎችን የሚያጠቃልል አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት የሚከናወነው የምዝገባ ዋና አላማ በተዋዋይ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል ለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል ሆኖ ውል ማድረጉና

ገንዘብም ተቀብሎ እንደነበር አምኖ ውሉ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት ብቻ መቃወሙ ከላይ ከተቀመጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ዓላማ ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፤ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በሕግ የሚጸና የቤት ሽያጭ ውል አለ ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 013132 ሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፤የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የስር ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች በስር ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል መፈጸም ጉዳይ በሚመለከት ተጠሪዎቹ የውሉ መኖርን አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው በውልና ማስረጃ ያልተመዘገበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት መቃወም አይችሉም፣የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ሁኔታ የሰጠው አተረጓጉም ተገቢነት የለውም፤ስለሆነም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች ያስረክቡ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 64887

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ አደም የሱፍ ቀረበ

**ተጠሪ** ፡- አቶ አብዱሰላም መሐመድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤተታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርቦ ያደራ መቻሬ መንገድ በንብረቴ ላይ በመውጣቱ ምክንያት መስከረም 9 ቀን 2001 ዓ.ም. ብር 86,440 /ሰማንያ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ብር/ ካሣ ተሰጥቶኝ ተከሣሽ /አመልካች/ የባለቤቴ ዘመድ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ገጠር ይዘህ አትሂድ ይገድሉሀል ገንዘቡን እኔ በአደራ ላስቀምጥልህ ብሎኝ መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰው ማስረጃ ባለበት ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ እንደታሰረ ሰጥቸዋለሁ፡፡ ተከሣሽ በአደራ የሰጠሁትን ገንዘብ እንዲሰጠኝ ብጠይቀው ሊሰጠኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቤን እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከከሣሽ በአደራ የተቀበልኩት ገንዘብ የለም፡፡ ከብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በላይ ብድር ወይም የአደራ ገንዘብ በሰው ማስረጃ ለማስረዳት አይቻልም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተከሣሽ /አመልካች/ ከከሳሽ /ተጠሪ/ በአደራ ገንዘብ የተቀበለ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ሊመልስ ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ የነበረ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ምንም አይነት የሰነድ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ብር 70,000 እንዲከፍል በህግ ተቀባይነት የሌለውን የሰው ምስክር

በመስማት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እንደ እኔ ካሣ ተቀብለው ገንዘቡን ገጠር የወሰዱ አርሶ አደሮች በመዘረፋቸው ገንዘቡን ይዤው ገጠር ብሄድ የዘረፋ ወንጀል ሊፈፀምብኝ ይችላል በሚል ፍርሃት የሰው ምስክሮች ባሉበት የሰጡት አደራ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመተርጎም የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል አመልካች መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በፍሬ ጉዳይ ደረጃ የደረሱበትን መደምደሚያ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ በመንገድ ሥራ ምክንያት በንብረቱ ላይ ለደረሰበት ጉዳት ከመንግስት ከተከፈለው የካሣ ገንዘብ ውስጥ ወደምኖርበት የገጠር ቀበሌ ይዤው ብሔድ ሰዎች ሊገድሉኝና ሊዘርፉኝ ይችላሉ በሚል ምክንያት ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ እንደታሰረ ለተጠሪ በአደራ የሰጠ መሆኑን የግራ ቀኙን ምስክሮች በመስማት አረጋግጠዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 በአደራ ስለሚቀመጥ አላቂ ዕቃ ከሚደነግገው በተለየ ሁኔታ ተጠሪ ለአመልካች ገንዘቡን በአደራ መስጠቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ሰው የራሱ ንብረት በሆኑት ዕቃዎች ላይ የማይታገድ እርግጠኛ አደጋ የሚደርስባቸው በሆነ ጊዜ እነዚህን ዕቃዎች ከቀረበው አደጋ ለማሸሽ ሲል ሌላ ሰው በአደራ ተቀብሎ እንዲያስቀምጥለት የሰጠ እንደሆነ ይህ አድርጎት አስፈላጊ አደራ የማስቀመጥ ድርጊት የሚል ልዩ የህግ ዕውቅናና ጥበቃ እንደሚሰጠው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2800 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አስፈላጊ የአደራ ማስቀመጥ ጉዳይ በማናቸውም የአሠራር ሥርዓት ነፃ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚደነግግ ሲሆን አንድ ሰው አስፈላጊ አደራ ለሌላ ሰው የሰጠ መሆኑን በማናቸውም አይነት መንገድ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚችል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡

ከላይ ይዞታቸው ከተገለፀው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠውን የፍሬ ጉዳይ ስናገናዝበው ተጠሪ በካሣ መልክ የተቀበለውን ገንዘብ ወደሚኖርበት ገጠራማ ቦታ ቢወስደው ደህንነቱን ጠብቆ ለማቆየትና ገንዘቡን ለማስቀመጥ የማይችል በአንፃሩ ገንዘቡን ለመዝረፍ ሲሉ ሰዎች ሊገድሉት የሚችሉ መሆኑን በግልፅ ለአሁን አመልካች በማስረዳት ብር 70,000 እንዲያስቀምጥለት የፈፀመው ተግባር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 የተገለፀው አላቂ ዕቃ በአደራ የመስጠት ተግባር ሣይሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2800 ልዩ ትርጉም ህጋዊ ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠው አስፈላጊ የሆነ አደራ የመስጠት ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ የፈፀመው አስፈላጊ የሆነ አደራ የመስጠት ተግባር ማናቸውንም አይነት ማስረጃ በማቅረብ ለማስረዳት እንደሚችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ብር 70,000 አስፈላጊ የሆነ አደራ ሲሰጥ ያዩትን ምስክሮች ቃል በመስማትና በመመዘን የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2472 ድንጋጌዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የህግ ግንኙነት ለመወሰን ተፈፃሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ድንጋጌዎቹ ስለሚያልቅ ነገር አደራ አቀማመጥና የሚያልቅ ነገር በአደራ የተሰጠ ስለመሆኑ ማስረዳት ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግጉ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ሲሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 በልዩ ሁኔታ ስለአስፈላጊ አደራ አቀማመጥና አስፈላጊ አደራን ስለማስረዳት የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰው ምስክር በመስማት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2472 ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካች ተጠሪ በአስፈላጊ አደራ ብር 70,000 የሰጠኝ መሆኑን ባቀረበው ማስረጃ አላስረዳም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ብር 70,000 እንደታሰረ በአስፈላጊ አደራ እንዲቀመጥለት የሰጠው መሆኑን ባቀረባቸው ምስክሮች ከአመልካች በተሻለና ሚዛን በሚደፋ ሁኔታ እንዳስረዳ በውሣኔቸው በግልፅ አስፍረዋል፡፡ አመልካች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ በመካድ በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2800 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አመልካች ከተጠሪ የተቀበለውን የአስፈላጊ አደራ ብር 70,000 እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 2 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ. 60217

ጥቅምት 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** 1. ም/ኢ/ር ኃይላይ አስገለ } ጠበቃ ም/ኮ ደጀኔ ወንድምነህ ቀረቡ

2. ም/ኮማንደር ይልማ ጥላሁን

**ተጠሪ፡-** የቤ/ጉ/ፍትሕ ቢሮ ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ ዐ/ሕግ አመልካቾች በ1949 ዓ/ም በወጣው የወ/መ/ሕግ ቁጥር 36(1)(ለ) ፣ 27(1) እና 523 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች በአሶሳ ከተማ ክልል ውስጥ ልዩ ስፍራው ግሪን ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቦታ ሐምሌ 09 ቀን 1993 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 2፡15 በሚሆንበት ጊዜ በወንጀሉ ስራና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋዮች ሁነው ባልታወቀ ምክንያት ተነሳስተው የግል ተበዳይ አብዱል መሀሙድ ኢብራሂም የተባለውን ለመግደል አስበው፤ 1ኛ አመልካች ይዞት በነበረው ሽጉጥ ሁለት ጥይት ተኩሶ የግል ተበዳይን ቀኝ እጅ በመምታት እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከወንጀሉ ድርጊት በፊትና በሂደቱ ወሬ በማቀበል፣ ዘዴ በመፍጠርና አንድ ጥይት በመተኮስ ሰውን የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ በማቅረቡ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአቃቤ ሕጉን ክስ ለአመልካቾች በግልጽ ችሎት አንብቦላቸው እንዲረዱ ከአደረገ በሁዋላ በክሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በመጠየቅ ሁለተኛው አመልካች ክሱን እቃወማለሁ በማለት ምክንያታቸውን ገልፀው ተቃውሞ ያስመዘገቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎ ስለድርጊቱ አፈጻጸም አመልካቾችን የእምነት ክህደት ቃል ጠይቆ የድርጊቱን አፈፃፀም በመካዳቸው ምክንያት አቃቤ ሕጉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው መከላከያ ምስክሮቻቸውን ከአሰሙ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾችን መከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕጉን ማስረጃ ለማስተባበል ብቃት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ውድቅ ከአደረገ በሁዋላ አመልካቾችን በአቃቤ ሕጉ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸውን በ 5 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወሰነ፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይኸው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማፅናት ቅጣቱን

በተመለከተ ግን 1ኛ አመልካችን በአራት ዓመት ፅኑ እስራት፣ 2ኛ አመልካችን ደግሞ በሶስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ሰበር ችሎቱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አቃቤ ሕግ ከሰባት አመት በፊት ጉዳዩ አያስከስስም በማለት መዝገቡን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 42(1(ሀ)) ከዘጋው በሁዋላ እንደገና ክስ መመስረቱ ሕጋዊ ያለመሆኑንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችም የአመልካቾችን የወንጀል ተሳትፎ በበቂ ሁኔታ ባላስረዱበት እንዲሁም የአመልካቾች የመከላከል መብት ባግባቡ ባልተጠበቀበት አመልካቾች ለወንጀሉ ተጠያቂ መደረጋቸው ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በ1993 ዓ/ም በተፈጸመ ድርጊት ሆኖ ዐቃቤ ሕግ በ1994 ዓ/ም አያስከስስም በማለት ክሱን ከዘጋው ከሰባት አመት በሁዋላ በዚያው ድርጊት ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪን ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምሮታል፡፡

አመልካቾች በጉዳዩ ላይ ድጋሚ ክስ ቀርቧል የሚሉበት ምክንያት የስር የዞኑ አቃቤ ሕግ በመጀመሪያ በጉዳዩ ላይ የተከናወነውን ምርመራ ተመልክቶ የተሰበሰበው ማስረጃ ክስ ለማቅረብ የማያስችል ነው በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 42(1(ሀ)) ዘግቶት ከቆየ በሁዋላ ከሰባት አመታት በሁዋላ ክሱን ማቅረቡ ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡ ከዚህ የአመልካቾች ክርክር መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች በአንድ ጉዳይ ሁለት ጊዜ ልንከሰስ አይገባም በማለት በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የሚከለክለውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 23 ድንጋጌንና በዚህ ረገድ ተቀባይነት ያለውን የወንጀል ሕግ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ችሎቱም የዚህን የወንጀል ሕግ ጽንሰ ሀሳብ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና የማይከሰስ ወይም የማይቀጣ መሆኑን ጽንሰ ሃሳቡ እንደሚያስገነዝብና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ይህንኑ በግልፅ የሚያስቀምጥ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑንም በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የተከለከለው የመጨረሻ ውሳኔ በሆነ ጥፋተኝነቱ በተረጋጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል ሲሆን ነው፡፡ በዚህም መሰረት በወንጀል ሥነ ሥርዓቱ ለአቃቤ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ጉዳዩ ክስ ለመመስረት የሚያስችል አይደለም በማለት ተጠርጣሪውን በነፃ የመልቀቅ የውሳኔ ሃሳብ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከልን ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከሉ ጥያቄ በፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ተገቢ ነው የተባለ ውሳኔ መሰጠቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በዚህ ረገድ ያነሱት የሕግ ክርክር ስለድጋሚ ቅጣት ክልከላ መርህ (principle of double jeopardy) የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የሕግ ማስረጃዎች ክብደት እንዲሁም በክርክሩ አመራር የስር ፍርድ ቤት የተከተለውን ሥነ ሥርዓት የሕግ ግድፈት ያለበት መሆኑን አጥብቀው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ

የአመልካቾችን የክርክር ነጥብ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጉዳዩን ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለድርጊቱ ኃላፊ ያደረጋቸው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመስማትና ቃላቸው ለጉዳዩ አግባብነት፣ ክብደት ያለው መሆኑን በማመን አመልካቾች በመካላከያ ማስረጃዎቻቸው እንዲያስተባብሉ የመከላከል መብታቸውን በመጠበቅ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃዎችን ከሰማ በሁዋላ የመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል የማይችሉ መሆኑን ዘርዝሮ ቃላቸውን ውድቅ በማድረግ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አቀራረብ የስር ፍርድ ቤት ተገቢውን ሥነ ሥርዓት አልተከተለም ይበሉ እንጂ የአመልካቾች የመካላከል መብት ተጠብቆ ውሳኔ መሰጠቱን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተነሳው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ክብደትን በተመለከተ ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከተውም ጉዳዩ የማስረጃ ምዝና ጉዳይ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ችሎት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ስር የማይወድቅ ወይም የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ በመሆኑ የምንቀበለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2717 ሚያዚያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02276 ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ/ም ተሻሽሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02429 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ውሳኔው የጸና መሆኑን እንዲያውቀው ለማረ/ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 67874

ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- 1. አቶ ፅጌብርሃን ተሰራ
2. አቶ መስፍን አበበ } ጠበቃ መሠረት ተፈራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉምሩክ ወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል በሚል የቀረበውን ክስ ተከትሎ የተነሳውን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በጉዳዩ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ የሆነው የተጠሪው ባለስልጣን አቃቤ ሕግ በአመልካቾችና በሌሎች በርካታ ሰዎች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ አንድ ሁኖ አመልካቾች የጉምሩክ ባለስልጣንን ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/1989 በአዋጅ ቁጥር 368/1995 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 67 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ 1ኛ አመልካች በስር ፍርድ ቤት 5ኛ ተከሳሽ የሆነውንና በጉምሩክ አስተላላፊነት ስራ ላይ የተሰማራ ዩኒቨርሳል ሎጂስቲክ ሰርቪስ ኃ.የተ.የግል ማህበር የተባለውን ድርጅት በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድሩ ፣ 2ኛ አመልካች ደግሞ የዚሁ ድርጅት በሰነድ ምርመራ (ኦፊሰር) ሰራተኛነት የስራ ኃላፊነት ሲያከናውኑ በመላው ሃሳባቸውና አድራጎታቸው ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት በመቀበል ለመንግስት በጠቅላላ ሊከፍል የሚገባ ብር 21,602,608.64(ሃያ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስምንት ብር ከስልሳ አራት ሳንቲም) ሳይከፈል ወደ ሀገር ውስጥ የገባው ሲሚንቶ በሕገ ወጥ ጥቅም ላይ እንዲውል አድርገዋል በሚል አንድ ክስ መመስረቱን የአቃቤ ክስ ይገለፃል፡፡ አመልካቾች የዋስትና ጥያቄ ያቀረቡት በክሱ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የዋስትና መብት የሚያስነፍግ አይደለም በማለት ሲሆን አቃቤ ሕግ ደግሞ ይህንኑ የአመልካቾችን ጥያቄ የተቃወመው በአመልካቾች ላይ የተመሰረተው ክስ ከበድ ያለ ቅጣት የሚያስከትል በመሆኑ ምስክሮችን በማባበል ማስረጃ ሊያጠፉ ስለሚችሉና ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ የሚሉ ምክንያቶችን በማንሳት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ)፣(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ የስር ፍርድ ቤት ከሁለቱም ወገኖች የቀረበውን ክርክር መርምሮ እና በዚህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 59304 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በማድረግ በዚህ ውሳኔ መሰረት የስር ፍርድ ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 መሰረት ብይን ሲሰጥ በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ወስዶ የሚያስተናግዳቸው ስለመሆኑ መተርጎሙን ግንዛቤ ወስዶ አመልካቾች

የተከሰሱት የወንጀል ክስ እስከ ሃያ አምስት አመት በሚደርስ እስራትና ከሃያ አንድ ሚሊዮን ብር በላይ መቀጮ ሊያስቀጣ የሚችል ነው ፣ የኢኮኖሚ አቅማቸውም ቀላል አይደለም ፣ ምስክሮችንም አያባብሉም ፣ የዋስትና ግዴታቸውንም አክብረው ችሎት ይቀርባሉ ብሎ ፍርድ ቤቱ ሊገምት አይችልም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካቾችን የዋስትና መብት በመንፈግ ማረሚያ ቤት ሁነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም የአመልካቾች ጠበቃ ሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ጽፈው ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን በፁሑፍ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአመልካቾች አኮኖሚያዊ አቅም ቀላል የሚባል አይደለም ፣ በዋስ ቢለቀቁ ምስክሮችን አያባብሉም ፣ የዋስትና ግዴታቸውን አክብረው ችሎት ይቀርባሉ ተብሎ ፍርድ ቤቱ አይገምትም የሚሉ ምክንያቶች ተይዘውና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ) እና (ሐ)) ድንጋጌዎች ተጠቅሰው የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በሚል ውድቅ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካቾች ጠበቃ እና አቃቤ ሕግ ያቀረቡትን የጹሑፍ ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ በራሱ ዋስትና የሚከለክል አለመሆኑን የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶቹ ለዋስትናው መንፈግ መሰረት ያደረጉት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ፍርድ ቤት ተግባራዊ ሲያደርግ ግምትን መነሻ ለማድረግ የሚችለው ሕጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑንና የድንጋጌው አጠቃላይ ትርጉምም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት አስገዳጅነት ባለው የሰበር መ/ቁጥር 59304 ላይ መሰጠቱን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በመሰረቱ የዋስትና መብት በሕገ መንግስት ጥበቃ ከተደረጉት የተያዙ ሰዎች መሰረታዊ መብቶች አንዱ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 19(6) ስር የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በህገ መንግስቱ የተከበረው መብት ሊነፈግ ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ሊደረግ የሚችለውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሰረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ይኸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መሰረታዊ የሆነ ሕገ መንግስታዊ መብት ቢሆንም ፍፁም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊነፈግ ወይም ሊገደብ የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የዋስትናው ጥያቄ ተቀባይነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ልዩ ሕግ መሰረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ) እና((ሐ)) መሰረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻ ለመቀበል የማይቻልባቸው ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ)) ድንጋጌ ሲታይ በዋስትናው ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካቹ የሚፈጽም **የማይመስል የሆነ እንደሆነ** ፍርድ ቤቱ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን መቀበል እንደማይችል ሲደነግግ

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67(ሐ)) ስር የተመለከተውና የዋስትና ወረቀቱን ላለመቀበል ምክንያት የሚሆነው ነገር ደግሞ አመልካቹ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጂ የሚሆኑበትን **ያጠፋ ይሆናል ተብሎ የሚገመትበት** ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ይዘታቸው ሲታይ ፍርድ ቤቱ ግምት ለመውሰድ በሕጉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ድንጋጌዎቹን በዚህ መንገድ መገንዘቡን በውሳኔው ላይ ጠቅሷል፡፡ በእርግጥም ድንጋጌዎቹ በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካቾች የሚፈፅሙ **የማይመስሉ እንደሆነና** ማስረጃዎችን የመግዛት(የማባበል) ወይም አስረጂ የሚሆኑበትን **ያጠፉ ይሆናል ተብሎ የሚገመትባቸው** ሁኔታዎች መኖራቸው ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ እንደሚቻል ያሳያሉ፡፡ እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ዋናው ጉዳይ ግን ድንጋጌውን በመተግበር ረገድ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ/ግምት/ ውስጥ ሊያስገባው የሚገባው ምክንያት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በተጠቀሰው ድንጋጌ በግልፅ አልተመለከቱም፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈፅም የማይመስል ነው ፣ ማስረጃም ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ግምት የሚወስደው በቂና እና ሕጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይገባል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ምክንያቶች በቂና ሕጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባቢያዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር እየታየ በፍርድ ቤቱ ግንዛቤ ሊወሰድባቸው የሚችላቸው ነጥቦች ናቸው ተብሎ የሚታሰብ እንጂ ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች አሉ ለማለት የማይቻልበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67 በጠቅላላው ሲታይ ፍርድ ቤት የዋስትና መብትን የሚነፍግባቸውን ሁኔታዎች የሚያሳይ ሲሆን ምክንያቶችን ፍርድ ቤቱ ከተለያዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዝናቸው የሚገባቸው ሲሆን የድንጋጌው ቅርጽ ፣ ይዘትና መንፈስ ሲታይ በሁኔታዎቹ ግምት የመወሰድ ያለመውሰድ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን(Discretion) መሆኑን ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በዋስትና ቢወጡ የዋስትናውን ግዴታ አክብረው ይገኛሉ ለማለት የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ግምት መሰረቱ በአመልካቾች ላይ የተመሰረተባቸው ክስ ሊያስክትል ከሚችለው የእስራት ቅጣትና የገንዘብ መቀጮ የከበደ መሆኑ ፣ ምስክሮችን የማባበልና የማጥፋት እድልም አመልካቾች ሊሰሩ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች መኖራቸውን መገመቱንም ፍርድ ቤቱ በትዕዛዙ ላይ ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ዋስትናውን ነፍጎአል፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዲያደርግ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በሕጉ የተከለከለ ካለመሆኑም በላይ ግምት የመወሰድ ጉዳይ በሕጉ ለፍርድ ቤቱ የተሰጠው ስልጣን ነው፡፡ ግምቱ በቂ ነው ወይም አይደለም የሚለው ክርክር ደግሞ የጠቅላላ ሁኔታዎች ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ የማስረጃና የሌሎች ከባቢያዊ ነገሮችን ምዘና ጉዳይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ማረም አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 19(6) እና የወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67(ሀ)(ሐ) መሰረት የሠጡት ውሳኔ ሕጉ የሠጣቸውን ሥልጣን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

- በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102532 የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 65829 መጋቢት 08 ቀን 2003 ዓ/ም በውሳኔ የጸናው ትእዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 60345

ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ- ገ/እግዚአብሔር ሙናቸው ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ገዳ ፎጫ } ግለሰቦቹ አልቀረቡም

2. ነቢ ሲምሮ ኤጎ

3. ወሌና ወርቅና ታንታለም ማዕድናት አምራች እና ግብይት ኃ/የተ/የግል ማህበር } ጠበቃ ወ/ሮ ህትመት አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሠረተው የወንጀል ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት እንደቅደም ተከተላቸው ዋና እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ሲሆኑ፣ አራት ክሶች ቀርበውባቸዋል፡፡

<u>**የመጀመሪያው ክ**</u>ስ፡- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)፣ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 53(1)፣(5) እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 26(4) በተመለከተው መሰረት ለስራ ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ማካሄድ ሲገባቸው በተጠቃሹ የማዕድን አዋጅ አንቀጽ 29(2) የተመለከተውን መረጃ የማኖር ወይም የመያዝ ግዴታን በመተላለፍ እንዲሁም በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 አንቀፅ 30(1ሀ(3))፣((ለ)) እና((4(ሐ)) ስር እንደተመለከተው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የተመረቱትን፣የተከማቹትን፣የተዘጋጁትን ወይም ለሽያጭ የቀረቡትን ማእድናትን አስመልክቶ መረጃ መያዝ እንዳለበት የተቀመጠውን ግዴታ በመጣስ እንዲሁም በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጡ ጥፋት ነው ተብሎ የተደነገገውን በመተላለፍ ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም መጠኑ 15863.18 ግራም ፣ዋጋው ብር 5,065,005.12(አምስት ሚሊዮን ስልሳ አምስት ሺህ አምስት ብር ከአስራ ሁለት ሳንቲም) የሆነውን የሐገር ውስጥ ጥፍጥፍ ወርቅ ትክክለኛና ሕጋዊ መረጃ ሳይኖራቸው ወይም ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚገልፅ ሰነድ ሳይዙ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-39968 አ.አ በሆነ ቪታራ መኪና በሮቹን በመፍታት መደበቂያ አዘጋጅተው ምንም አይነት ፈቃድ ሳይዙ በህገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋዉሩ የተያዙ በመሆኑ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

__*ሁለተኛው ክስ*__ ደግሞ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም የወ/ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ መጠኑ በ1ኛው ክስ የተገለጸውን ወርቅ ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሕጋዊ ወደአልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ነው፡፡

__*ሶስተኛው ክስም*__ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) እንዲሁም በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ ተጠቅመዋል የሚል ነው፡፡

__*የመጨረሻው ክስ*__ በ3ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም፡- በወርቅና ታንታለም ማእድናት ማምረት የግብይት ስራ መስክ የሕግ ሰውነት ተሰጥቶት ሲንቀሳቀስ የወርቅ ምርትን ከማጓጓዝና ለግብይት ከማቅረብ ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ሕጋዊ ሰነድ መያዝ እና ማህበሩ ስላለው፣ ስላመረተው፣ ስላጓጓዘው እና ለግብይትም ስላቀረበው ወርቅ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ማቅረብ እንዳለበት የማእድን ሃብትን ለማስፋፋት በወጣው አዋጅ ቁጥር 52/85 እና በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በመጣስ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣የማእድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቨይ በወርቅ ግዥና አቀራረብ ሂደት ስለሚከተሉት የጋራ አሰራር የወጣውን መመሪያ ቁጥር 01/2000 በመተላለፍ ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ መጠኑ 15863.18 ግራም የሆነ ወርቅ ሕጋዊ ላልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲንቀሳቀስ ተይዟል ተብሎ በ1997 ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንደሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል በሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአቃቤ ሕግ ክስ ለተጠሪዎች እንዲደርስ አድርጎና በግልፅ ችሎትም ተነቦላቸው እንዲረዱት ካደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠይቅ ተጠሪዎች በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው፣ የድርጊቱን አፈጻጸም ግን ክደው ተከራክረዋል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰነድና የሠው ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ህግን ማስረጃዎች ሰምቶ ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ መረጋገጡን በማመን የተጠሪዎችን የመከላከያ ማስረጃዎችን የማሰማት መብት ጠብቆላቸው መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ሰምቷል፡፡ ቀጥሎም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃዎች ይዘት በአቃቤ ማስረጃዎች ይዘት ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ የፈጠረ ሆኖ ተገኝቷል የሚል ምክንያት በመስጠትና ተጠሪዎች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎች ማስተባበላቸውን በመግለጽ ተጠሪዎችን ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡በስር 3ኛ ተከሳሽ የሆነውን ግለሰብ ግን በወ/መ/ሕ/ቁጥር 375(1(ሀ))እና ((መ)) ስር ሐሰተኛ ሰነድ የመስጠት ወንጀል መፈፀማቸው ተረጋግጧል በማለት ጥፋተኛ አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት አስተላልፎበታል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችን ከክሱ ነፃ ከማድረግ በተጨማሪም በኤግዚቢትነት የተያዘው የሀገር ውስጥ ወርቅም በጊዜው ባለው የወርቅ ተመን መሠረት የወርቁን ዋጋ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች

የተከሰሱት ሕጋዊ ፈቃድ የላቸውም በሚል ሳይሆን የወርቅ ግብይቱን ለሚመለከተው አካል ሳያቀርቡ በሕገ ወጥ መንገድ ለሌላ አካል ለመሸጥ ሲሉ ሲንቀሳቀሱ ተይዘዋል፣1ኛ ተጠሪም ማስረጃው በጥቅም አሰርቶ ያመጣው ከመሆኑም በላይ ለራሱና ለ2ኛ ተጠሪ ጥቅም ላይ ሊያውል ሲል መያዙ ተረጋግጧል የሚል ሆኖ እያለ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸው ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አረጋግጠዋል በማለት በነጻ የተሰናበቱት ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት እንዲጣል እና ኢግዚቢትነት የተያዘው ወርቅ ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች ከክሱ በነጻ የተነሰናበቱት ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የተጠሪዎች ጠበቃ ባቀረቡት የፅሑፍ መልስ ተጠሪዎች በነፃ የተሰናበቱት ባግባቡ ተከላክለው በመገኘታቸው በመሆኑና አድራጎታቸውም የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትል መሆኑ በመረጋገጡ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ተጠሪዎች ከክሱ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እንዲሁም የተጠሪዎች መካላከያ ማስረጃዎች ያስረዱትን ፍሬ ነገር ይዘት ባጭሩ በሚከተለው መልኩ አይተነዋል፡፡

በአቃቤ ሕግ በኩል በ1ኛ ምስክርነት የተጠቀሱት ግለሰብ እውነት ለመመስከር ምለው በሰጡት የምስክርነት ቃል፡-ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም ከጥዋቱ 2፡30 አከባቢ 1ኛ ተጠሪ ደውለውላቸው ወርቅ አምጣልኝ፣ከአዋሳ 2ኛ ተጠሪ ይጠብቅሃል ሲሏቸው ወደ 2ኛ ተጠሪ ደውለው 1ኛ ተጠሪ አዝዞኛል ሲሏቸው 2ኛ ተጠሪ "ና!" ብሏቸው ከቀኑ 11፡30 አከባቢ አዋሳ ገብርኤል አካባቢ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተገናኝተው በጥቁር ሻንጣ ወርቁን እንዳመጣላቸው፣ከመንገድ ወጣ ብለው በመኪናው ሻግ ውስጥ በማድረግ ስድስቱን እሽግ ወርቅ በመደበቅ በእለቱ አዲስ አበባ መንቀሳቀስ እንደጀመሩ፣ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ሳሉም ከምሽቱ 4፡00 አከባቢ ወደ አቃቂ ቃሊቲ የጉምሩክ ፍተሻ አከባቢ ሲደርሱ በጉምሩክ ኦፊሰሮችና በጸጥታ ኃይሎች መያዛቸውንና ወዲያውኑ ወደ ጉምሩክ ጣቢያ እንዲገቡ መደረጋቸውን፣በጉዞ ወቅት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አፍሪካ ወርቅ ድርጅት ከተባለው ጋር በስልክ ይነጋገሩ እንደነበር፣በበነጋው ወርቁን የት እንዳስቀመጡት ሲጠየቁም ሻጉን ከፍተው እንደሳዩ፣ወርቁን በተመለከተ ቀኑ 30/08/2001 ዓ/ም የሚል ተሰርቶ ማስረጃ እየመጣላቸው መሆኑን 2ኛ ተጠሪ ሲነግራቸው እንደነበር፣በወቅቱም ምስክር አትሁን ሲሏቸው እንደነበር፣ከዚያ በፊትም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ወርቅ ሲያመጡ እንደነበር፣በሻግ ውስጥ የሚያስቀምጡትም የይለፍ ወረቀት ስለማይዙና በወቅቱም ያለመያዛቸውን፣ወርቁ ወደ ጅቡቱ እንደሚወጣም በስልክ 2ኛ ተጠሪ ሲናገር መስማታቸውን ዘርዝረው መስክረዋል፡፡

ሁለተኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ደግሞ የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር የሆኑት ግለሰብ በእለቱ ከምሽቱ 5፡00 አካበቢ ሲሆን ጉምሩክ ታስሬአለሁ ጠዋት "ና!" እንደአሏቸውና ጥዋት 1፡00 አከባቢ ጉምሩክ ሲደርሱም የታሰሩበት ምክንያት ወርቅ ጭነው እንደሆነ የተነገራቸው መሆኑን፣2ኛ

ተጠሪ አብሮት እንደነበር፣ይኸው ተጠሪ ወዲያውኑ ለ1ኛ ተጠሪ ደውልለት ብሏቸው ለምስክሩ ሲነግሩትም ምስክሩ ለ1ኛ ተጠሪ ደውለውለት 2ኛ ተጠሪና ወርቁ መያዙን የነገሩት መሆኑን፣ከዚያም ቀን ላይ 1ኛ ተጠሪ መልሶ ደውለውለት እመጣለሁ ጠብቀኝ እንዳሉት፣ከቀኑ 8:00 አከባቢም 1ኛ ተጠሪ ወረቀትም አስርቼ እያመጣሁ ነው ብለው ሲሏቸው ከኢትዮጵያ ሆቴል አከባቢ ሲገናኙ 1ኛ ተጠሪ ወርቁን ለማስለቀቅ ቀኑ በ30/08/2001 ዓ/ም ተብሎ ወደኂላ ተደርጎ የተጻፈ ወረቀት መያዛቸውን ለምስክሩ ገልፀው ወረቀቱን ለ2ኛ ተጠሪ ምስክሩ እንዲሰጥላቸው ነግሯቸው ምስክሩ "እኔ አልሰጥም፣ራስህ ስጥ ሲሉት" 1ኛ ተጠሪ ወረቀቱን ለመስጠት በሄዱበት መያዛቸውን እንደሚያውቁ መስክረዋል፡፡

3ኛ እና 5ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በበኩላቸው 2ኛ ተከሳሽን በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ሰዓት ወርቅ ጭነው ሲመጡ በደረሳቸው መረጃ መሰረት ሃና ማሪያም ቀለበት መንገድ አከባቢ መያዛቸውን፣ወርቁም በመኪናዋ በሮች መደበቂያ ተሰርቶለት በአንድ በኩል ሶስት፣በሌላ በኩል ሶስት እሽግ ሆኖ ሲጓዝ እንደነበርና በወቅቱም ማስረጃ ተጠይቀው የለንም በማለት መልስ የሰጧቸው መሆናቸውን መስክረዋል፡፡ 4ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ወርቅ ከደቡብ ጭነው ሲመጡ ከሃና ማሪያም አከባቢ የያዟቸው መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 04 ቀን 2001 ዓ/ም ከቀኑ 4:00 አከባቢ የይለፍ ወረቀት አጣጥፎ ለ2ኛ ተጠሪ በአጥር ሲያቀብሉ እንደያዙት መስክረዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ አቃቤ ሕግ 3ኛ ተጠሪ የወርቅና የታንታለም ማእድናት አምራችና ግብይት ኃ.የተ.የግል ማህበር ስለመሆኑ ከክልሉ የማዕድን ቢሮ ፈቃድ አግኝቶ ማዕድን በማምረት ስራ ላይ የተሰማራ መሆኑን፣1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የዚሁ ማህበር አመራሮች መሆናቸውን፣በአዶ ሻኪሶ የሚገኘው የገቢዎች ጽ/ቤትም 3ኛ ተጠሪ የመረጃ አያያዙ ችግር ያለበት መሆኑን የገለፀበት መግለጫ፣2ኛ ተጠሪ ከአፍሪካ ወርቅ ቤት ጋር በስልክ ሲገናኙ የነበሩ መሆኑን የሚያሳዩ ከቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የተገኘና ሌሎች የወርቁን ዋጋና 2ኛ ተጠሪ ወርቁ ከተደበቀበት የመኪና ክፍል መርተው ሲያስወጡ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ በሠነድ ማስረጃነት ማቅረቡን የሥር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ያሳያል፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረቡ ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎቻቸው ይዘትም ከአንድ አመት በፊት ማዕድን ለማምረት ተደራጅተው ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የማእድንና ኢነርጂ ልማት ጽ/ቤት ፈቃድ ማግኘታቸውን፣ፈቃዱም የታደሰ መሆኑን፣ከብሔራዊ ባንክ ጋር ወርቅ የማቅረብ ግንኙነት እንዳላቸው፣ሮያሊቲ ታክስም እንደሚከፍሉ ከተደራጁበት ጊዜ ጀምሮ የከፈሉትን የሮያሊቲ መጠን፣ለብሔራዊ ባንክ ከአስራ ሁለት ጊዜ በላይ ወርቅ አቅርበው የሸጡ መሆኑን የሚያሳዩ መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

እንግዲህ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ከላይ የተገለጹት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን ከክሱ ነፃ ያደረጋቸው ተጠሪዎች ሕጋዊ የወርቅ ማምረት ፍቃድ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፣በአዋጅ ቁጥር 52/865 አንቀጽ 2 መሰረት ማምረት ማለት መሸጥን እንደሚጨምር መደንገጉን፣ማዕድኑ ሲሸጥ ለማን እንደሚሸጥ ይህ ድንጋጌ በግልጽ ያላመለከተ መሆኑና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 182/86 ደግሞ ማእድንን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ማህበር ያመረተውን ማእድን በተመለከተ ያመረተውን፣ያጓጓዘውን፣ያከማቸውን እንዲሁም የሸጠውን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት፣ሲጠይቅም ማሳየት እንዳለበት ከሚደነግግ ውጪ ማዕድኑን ለዚህ አካል መሸጥ ወይም ማስረከብ አለበት ብሎ የደነገገው ድንጋጌ ያለመኖሩን፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ማዕድን ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ስርቬይ በጋራ ባወጡት መመሪያ ላይም ማንኛውም ሕጋዊ ወርቅ አምራች ያመረተውን ወርቅ ለባንኩ ማቅረብ ይችላል ከሚል በስተቀር የማቅረብ ግዴታ እንዳለበትና ከባንኩ ውጪ ለሌላ ሲያቀርብ

ቢገኝ በዚህ ሕግ መሰረት ይቀጣል ተብሎ ያለመደንገጉን፣በደንብ ቁጥር 182/86 አንቀጽ 38 እና 39 ስር ጥፋት ተብለው የተቀመጡት ድርጊቶች ሪኮርድ ያለመያዝ፣ስለአመረቱት ፣ስለአጓጓዙት፣ስለአከማቹት እና ስለሚሸጡት ማእድን ተገቢውንና ወቅታዊውን መረጃ ባለመያዛቸው የሚወሰድባቸው ቅጣት አስተዳደራዊ እንጂ የወንጀል ቅጣት ያለመሆኑን የደንቡ አንቀጽ 40 ድንጋጌ የሚያሳይ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ ነው፡፡ተጠሪዎች እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩትም ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው መሆኑና በተለያዩ ጊዜያት ለብሔራዊ ባንክ ወርቁን በማቅረብ ሲሸጡ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ሲሆን አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ ተጠሪዎች ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ሳይክድ የወርቅ ሽያጩን በሕገ ወጥ መንገድ ለመፈፀም ሲሯሯጡ ተይዘዋል፣ተገቢውን መረጃም በወቅቱ አልያዙም በማለት ነው፡፡እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ተመልክተነዋል፡፡

በመሰረቱ የወርቅ ማዕድን ዝውውርን ለመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው ብሔራዊ ባንክ መሆኑን ብሔራዊ ባንክን ከአቋቋሙት ሕጎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 591/2000 ሲሆን ይህ አዋጅ በአንቀፅ 27(2) እና በአንቀጽ 5 ድንጋጌዎች ስር ብሔራዊ ባንክ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካትና አዋጁን በሚገባ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት የሚያስችል ስልጣን ሠጥቶታል፡፡ይኸው አዋጅ በአንቀጽ 28 ስር ደግሞ አዋጁን የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ደንብ ወይም መመሪያ በአዋጁ ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ይገልፃል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ይዘት መገንዘብ የሚቻለውም አዋጁን የማይቃረን ሕግ፣ደንብ እና መመሪያ በአዋጁ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ነው፡፡በአዋጁ አንቀጽ 27/2/ እና አንቀፅ 5(9) ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ ሲታዩም ስለወርቅና ስለውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ባንኩ መመሪያ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ድንጋጌ እና ከአዋጁ አጠቃላይ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የገንዘብ እና የወርቅ ሥራ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት በመመልከት በተለየ ሁኔታ ሥርዓት እንዲበጅለት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረጉ የሕግ አውጪው ፍላጎት መሆኑን ነው፡፡ይህንንም በእውን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ደግሞ በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባንኩ በዝርዝር መመሪያ መሰረት ጉዳዮችን ለማስተዳደር እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን አዋጁ ያስረዳል፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች የተከሰሱበት ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው መመሪያው ቁጥር ወን/001/1997 በአንቀጽ 1 እና 2 ስለወርቅ ንግድና ዝውውር፣መያዝ ወይም ማኖር የባንኩን ፈቃድ አስፈላጊነትና የመጠኑም ገደብ አስመልክቶ ድንጋጌ ይዟል፡፡ይህ መመሪያ ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 27(2) እና 5(9) እንዲሁም አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሲሆን አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ አዋጁን ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ሰው የሚቀጣበትን አግባብ አስቀምጧል፡፡ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው በአዋጁ መሠረት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በአዋጅ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የሚወጣ መመሪያ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 43781 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በመሆኑም ባንኩ በግልጽ በአዋጁ ስለወርቅ መመሪያ ማውጣት ስልጣን አለው ተብሎ ስልጣን በሕግ አግባብ ከተሰጠው መመሪያው ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል፡፡ከዚህ አንፃር በመመሪያው የተመለከተውን ገደብ በመተላለፍ ለተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት በአዋጁ

እና በወንጀል ሕጉ በተመለከተው አግባብ የሚፈፀም በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይም መመሪያው ተፈጻሚነት አለው ብለናል፡፡መመሪያ ቁጥር ወን/001/1997 ከግንቦት 10 ቀን 1997 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ ያለ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረት የወርቅ አሻሻጥ ስርዓትን በብቸነት የመቆጣጥር ስልጣን ያለው አካል ብሔራዊ ባንኩ ነው፡፡በዚህ መመሪያ መሰረት ወርቅ የሚሸጥ ግለሰብ ወይም ሰው በቅድሚያ መሸጥ ያለበት ለባንኩ በማቅረብ ነው፡፡መመሪያው ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው ግለሰቦች ከባንክ ብቻ በሕጋዊ መንገድ ጥፍጥፍ ወርቅ መግዛት እንደሚችሉም ይደነግጋል፡፡የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት ሲታይም የወርቅ ግዥና ሽያጭ የሚከናወነው በብሔራዊ ባንክ ብቻ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡በመመሪያው መሰረት ጥፍጥፍ ወርቅ የማምረት ፍቃድ ካላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በቀጥታ የመግዛት ስልጣን ያለው ብቸኛ አካል ብሔራዊ ባንኩ ነዉ፡፡ባንኩ ጥፍጥፍ ወርቁን ለመግዛት የሚችለው ደግሞ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ወርቁን ለባንኩ በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ገቢ ሲያድርጉ ነው፡፡በዚህ በመመሪያው መሰረት በተዘረጋው የወርቅ ግብይት ስርዓት መሰረት የማይከናወን ማንኛውም የወርቅ ግብይት ሕገ ወጥ ድርጊት ነው ተብሎ የሚፈረጅ መሆኑን የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 346 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ያስረዳል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪዎች የወርቅ ማምረት ፍቃድ አለን በማለት ያቀረቡትን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች እንዳለ ሲቀበሉ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠውንና ሕገ ወጥ ነው የተባለውን ድርጊት ሳይለዩ አልፈዋል፡፡ይኸውም አቃቤ ሕግ ለክሱ መሰረት ያደረገው የተጠሪዎችን ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ሳይሆን የወርቅ ግብይቱን በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ለመሸጥ ሲንቀሳቀሱ ተይዘዋል በሚል ነው፡፡ለጉዳዩ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ደግሞ ወርቁ ለብሔራዊ ባንክ ሳይሆን ለአፍሪካ ወርቅ ቤት ቀርቦ ወደ ጅቡቲ በመላክ ለመሸጥ በማሰብ ወርቁ ሲጓጓዝ የነበረ፣በወቅቱም መያዝ የሚገባቸው መረጃዎች ሁሉ በተገቢው ሁኔታ ያልተያዙ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ለጉዳዩ ቀጥተኛ ምስክር የነበረው የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክርና ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ይህንኑ የሚያስረዱ መሆናቸውን የሥር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደሕጉ ስንመጣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በአቃቤ ሕግ የተጠቀሰው 1ኛው ክስ በዋናነት መሰረት ያደረገው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)፣ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 53(1)፣(5)፣26(4) ፣29 እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደዚሁም በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 አንቀፅ 30(1ሀ(3))፣((ለ)) እና((4(ሐ)) ስር እንደተመለከተው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የተመረቱትን፣የተከማቹትን፣የተዘጋጁትን ወይም ለሽያጭ የቀረቡትን ማእድናትን አስመልክቶ መረጃ መያዝ እንዳለበት የተቀመጠውን ግዴታ በመጣስ እንዲሁም በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ያለማቅረባቸው የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል በማለት ነው፡፡ይህ ችሎትም ጉዳዩን በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች አንፃር ሲመለከት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 ስር የወንጀል ተጠያቂነት ሊከተል የሚችለው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 346 በተመለከተው አኳኋን ማንም ሰው ሕገወጥ በሆነ መንገድ የከበሩ ማእድናት እንደወርቅ፣ፕላቲኒም፣ዩራኒየም እና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉ ማእድናት እንዲሁም የከበሩ ድንጋዮችን ለመጠበቅ ወይም ሕገ ወጥ ዝውውሩን ለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ በመጣስ ወንጀል የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ቅጣቱም ወንጀሉን የፈፀመበት

ሀብት የመውረስ ደንብ የሚጸናበት መሆኑ ሳይቀር ከአስር አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና ከሀምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ሕጉ ያሳያል፡፡በደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ያለማቅረባቸው የአስተዳደራዊ ጥፋቶች ሊባሉ እንደሚችሉ በደንቡ የተመለከተ ሲሆን የጥፋቱን ደረጃና ተደጋጋሚነት መሰረት በማድረግም የሚመለከተው አካል አስተዳደራዊ ቅጣት ሊጥል የሚችልበት አግባብ የደንቡ አንቀፅ 39 እና 40 ድንጋጌዎች በግልፅ ያሳያሉ፡፡ደንቡ የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትሉ የሚገለፀው ከደንቡ አንቀጽ 38 እና 39 ውጪ ያሉትን ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈፀመውን ተግባር ስለመሆኑ በአንቀጽ 40(5) ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡በመሆኑም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በአቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰባቸው የደንብ ቁጥር 38 እና 39 ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 347 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትሉ የማይችሉ መሆኑን ከደንቡ አንቀፅ 40(5) ስለተገነዘብን 1ኛ ክስን በተመለከተ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ኃላፊ የሚሆኑበትን አግባብ ስላላገኘን በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

ሌላው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተጠቀሰባቸው የወ/ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ መጠኑ በ1ኛው ክስ የተገለጸውን ወርቅ ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሕጋዊ ወደአልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ነው፡፡ከላይ በፍሬ ነገር ደረጃ እንደተገለጸው 1ኛ ተጠሪ የአቃቤ ሕጉን 1ኛ ምስክር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተገናኝቶ ወርቁን ወደአዲስ አበባ እንዲያጓጉዝ ማድረጉ፣2ኛ ተጠሪ ወርቁን ሲያጓጉዙ ወደ ብሔራዊ ባንክ ሳይሆን አፍሪካ ወርቅ ቤት ለተባለው የንግድ ድርጅት በማቅረብ ወደ ጅቡቲ በመላክ ለመሸጥ በማቀድ ወርቁ ሲጓጓዝ በጉምሩክ አፊሰሮችና በጸጥታ ኃይሎች አማካኝነት በመንገድ ላይ የተያዘ መሆኑ በሚገባ በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም ወርቁ በሕጉ አግባብ ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ ለገበያ ሊቀርብ ሲል የተያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ይህም ተጠሪዎች ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለማዘዋወር በማሰብ ወንጀሉን በማድረግ፣የወንጀሉን ድርጊት እስከ መጨረሻው ያልተከታተሉት ወይም ለመከታተል ያልቻሉት ወይም የወንጀሉን ድርጊት እንዲፈፀም እስከ መጨረሻው ተከታትለው አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላገኙ ቢሆንም ተጠሪዎች ወንጀሉን ለመፈፀም ከማይመለሱበት ደረጃ /Point of no return/ ደርሰው የነበረ መሆኑ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ወርቅን በሕገ ወጥ መንገድ መሸጥ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1)፣32(1(ሀ))((ለ)) እና 346 መሰረት ወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ድርጊት መፈፀማቸውን የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ተጠሪዎች ያቀረቡት የመከላከያ ሰነድም ተጠሪዎች ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ለክሱ መሰረት የሆነው ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ ወርቁን ለብሔራዊ ባንክ ሊያቀርቡ የነበረ መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ ክብደት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡በመሆኑም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ2ኛው ክስ ነፃ ሊባሉ የሚችሉበት ማንኛውም አግባብ ስለሌለና ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው ደግሞ በአቃቤ ሕግ ክስ በተመለከተው መልኩ ሳይሆን ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለመሸጥ በመሞከር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1)፣32(1(ሀ))((ለ)) እና 346 ስር በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ሆኖ አግኝተናል፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአቃቤ ሕግ ክስ ይዘትን ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ጋር በማዛመድ ጉዳዩን መመልከት ሲገባቸው ለክሱ መሰረት ያልሆነውን የተጠሪዎች ሕጋዊ ነጋዴ የመሆን ጉዳይ በምክንያትነት በመያዝ 1ኛ እና 2ኛ

ተጠሪን ከ2ኛው ክስ ሙሉ በሙሉ ነፃ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን የነፃ መልቀቅ ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2((ሀ)) መሰረት በመሻር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወ/ህግ አንቀጽ 27(1)፣32(1(ሀ))(ለ)) እና 346 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ብለናል፡፡

ሌላው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የተከሰሱበት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) እንዲሁም በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ ተጠቅመዋል የሚል ነው፡፡ተጠሪዎች ማስረጃውን በጥቅም ላይ አውለው የተገኙ መሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ሐሰተኛ ማስረጃውን ያዘጋጀው የስር 3ኛ ተከሳሽም በበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ ተገቢው ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችም ሕጋዊ የወርቅ አምራችና አቅራቢ ድርጅት የስራ ኃላፊ ከመሆናቸው ውጪ ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም ሲያንጉዙትና በሕገ ወጥ መንገድ ሊሸጡት ለነበረው ወርቅ ቀድመው ትክክለኛውን ማስረጃ የያዙ መሆኑን ሊያረጋግጥላቸው የሚችል የመከላከያ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ይልቁንም ተገቢውን ማስረጃ የያዙ ለማስመሰል ቀኑ ወደኋላ ሆኖ የተጻፈ ሐሰተኛ ሰነድ ለተገቢው አካል አቅርበው ጥቅም ላይ ለማዋል ሲሉ ተይዘዋል፡፡በመሆኑም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ3ኛ ክስም ነፃ የሚወጡበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2((ሀ)) መሰረት በመሻር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና (ለ))) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ተብለው ሊቀጡ የሚገባ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በመጨረሻም 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ይህ ተጠሪ ሕጋዊ ሰውነት የተሠጠው አካል ሲሆን የተከሰሰውም በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል በሚል ነው፡፡ከላይ እንደተለገፀው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት የስራ ኃላፊዎች ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቁን ለመሸጥ ሲሞክሩ በመገኘታቸው ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባ ሆነው ተገኝተዋል፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወ/ሕ/አንቀጽ 34 እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 3ኛ ተጠሪ ነጻ የተባለበትን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ሀ))መሰረት በመሻር በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)፣353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ሊባል የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎችን ሙሉ በሙሉ ነጻ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ሕጋዊ ባለመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ2ኛው ክስ የወ/ሕግ አንቀጽ 27(1)፣32(1)(ሀ)(ለ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቅ ለመሸጥ ሲሞክሩ የተገኙ ጥፋተኞች ናቸው፣እንደሁም ሁለቱም ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች

በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ የተጠቀሙ ጥፋተኞች ናቸው፣ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ መጠኑ 15863.18 ግራም የሆነ ወርቅ ሕጋዊ ላልሆነ ገበያ ለማቅረብ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አማካኝነት ሲንቀሳቀስ የተገኘ በመሆኑ በ1997 ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34፣27(1)፣353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 65325

ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሣጅን ታዬ ተክለኂይማኖት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሣሽ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ በተከሣሽ ላይ ቀርቦ የነበረው ክስ ሶስት ሲሆን ይዘቱ 1ኛው ክስ ተከሣሽ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 670 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ በሀዋሳ ከተማ ልዩ ስሙ ጨርቃ ጨርቅ አካባቢ በስራው አካባቢ በእጁ በሚገኙት የሀዋሳ ከተማ የፖሊስ ተሸከርካሪ የሆኑትን 1ኛ ከላይ ክፈት ላንድ ኪሩዘር የሰሌዳ ቁጥር ፖሊስ ደ.ህ 0007 2ኛ ሽፍን ሎንግ ቤዝ መኪና የሰሌዳ ቁጥሩ 4-11529 በማሽከርከር ዘወትር ማክሰኞና አርብ ከንግድ ስራቸው የሚመለሱትን የተለያዩ ስምንት ሰዎችን በተለያዩ ጊዜያት ያስጫናችሁት ዕቃ ይወረሳል ካልሆነ ገንዘብ አምጡ በማለት በማስፈራራት 10,700 ብር የተቀበለ በመሆኑ በፈጸመው የውንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፤ ሁለተኛ ክስ ደግሞ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 407/ሐ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከላይ በክስ አንድ ስር በተገለጹት ቀናት ወር ዓመተ ምህረት እና ቦታ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ድረስ ስማቸው በተገለጹት የግል ተበዳዮች የፖሊስ አባል መሆኑንና የፖሊስ መኪና ማሽከርከሩን መከታ በማድረግ ይህ የያዛችሁት የንግድ ዕቃ "ቡና" ይወረሳል አልያም ገንዘብ አምጡ እያለ ገንዘቡን እየተቀበለ እንዲያልፉ በማድረግ በስልጣን አለ አግባብ መገልገል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው 3ኛው ክስ ደግሞ በክስ አንድ ስር የተጠቀሱትን የመንግስት ተሽከርካሪዎች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 677/1ሀ/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ያለአግባብ በመገልገል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከሣሹን የእምነት ክህደት ቃል በመቀበል የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የውሣኔው ይዘት ተከሣሽ በአንደኛው ክስ ስር የውንብድና ወንጀል ሰርቷል በተባለበት ወቅት በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ ከዐቃቤ ህግ ምስክር በተሻለ ያስመሰከረ በመሆኑ ከክሱ በነጻ ሊሰናበት ይገባል 3ኛ ክስ በተመለከተም በተመሳሳይ ተከሣሽ በእረፍት የነበረ ስለመሆኑ እና በወቅቱም የተጠቀሱትን ተሽከርካሪዎች ለሌላ ተረኛ ሹፌር ያስረከበ እና በእጁ የሌለ ስለመሆኑ ከመስሪያ ቤቱ የቀረቡት

የተሽከርካሪ መረካከቢያ ቅጾች የሚያስገነዝቡ በመሆኑ የወንጀል ኂላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሁለተኛ ክስ ስር ግን ፍ/ቤቱ በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 407/ሐ/ ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በአምስት /5/ ዓመት ጽኑ እስራትና በ2000 ብር /ሁለት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመቀጠል ደግሞ ለክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን የቀረበላቸውን ቅሬታ ባለመቀበል አያስቀርብም በማለት ቅሬታውን ሰርዘውለታል፡፡
አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሁፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በሁለተኛ ክስ ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ በአግባቡ ስለመሆኑ ተመርምሮ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ሁለተኛውን የዐቃቤ ህግ ክስ እና አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበትን ድርጊት ስንመለከት ራሱን ችሎ የቆመ ሳይሆን በአንደኛው ክስ ውስጥ በተጠቀሰው ሰዓት ቀን ወር ዓመተ ምህረት ቦታ እና የግል ተበዳዮች ላይ ስለመሆኑ ከክሱ ይዞታ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ በአንደኛ ክስ ላይ በተመለከተው የውንብድና ወንጀል ክስ ስር ተከሣሽ በወቅቱ በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በማለት ከቀረበበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ይሄ ከሆነ በተመሣሣይ ጊዜ ቦታ እና የግል ተበዳዮች ላይ ተፈጸመ ለተባለው የስልጣን አለአግባብ የመገልገል ወንጀል ጥፋተኛ የሚባልበት አግባብ አይኖርም፡፡ በተመሣሣይ ሁለተኛውን ወንጀል ሲፈጽም የፖሊስ መምሪያ መኪና ተጠቅሟል ተብሎ በክሱ የተመለከተ ቢሆንም በአመልካች ላይ የቀረበው የመንግስትን ንብረት ያለአግባብ የመገልገል ወንጀል በተመሣሣይ ጊዜ ቦታ እና የግል ተበዳዮች ላይ ተፈጸመ ተብሎ በሶስተኛ ክስ ከቀረበበት ክስ በነጻ የተሰናበተ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ያለመፈጸሙን እና ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ ወንጀሉንም ሲፈጽም የፖሊስ መምሪያውን ተሽከርካሪ ተጠቅሟል የተባለውም በወቅቱ የተባሉት ተሽከርካሪዎች በእጁ ያልነበሩና ለሌላ ተረኛ ሹፌር ያስረከበ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ በአንደኛውና በሶስተኛው ክስ ላይ መደምደሚያ ላይ ደርሶ እያለ በሁለተኛው ክስ ስር በተመሣሣይ ጊዜና ቦታ እንደዚሁም የግል ተበዳዮች ላይ ተፈጸመ ለተባለው ወንጀል ጥፋተኛ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ አንድ ተከሣሽ ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ወንጀሉን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራት ስለመፈጸማቸው በፍሬ ነገር ረገድ ለማጣራት ስልጣኑ ባላቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በይግባኝ ያየው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የወ/መቀጫ ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 141,142 እና 149/1/ ዓላማ ፣ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ እና ቦታ የሌለ መሆኑን ወይም በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ እና ወንጀሉን ለመፈጸም ተጠቀመበት በማለት የተጠቀሱትንም ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ያልያዘና ለሌላ ሰው አሳልፎ አስረክቦ በነበረበት ወቅት በመሆኑ አልተረጋገጠም ወደሚለው የፍሬ-ነገር መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በመሆኑም ባልተረጋገጠ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ መልሶ በሁለተኛ ክስ ስር ጥፋተኛ ነው

በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለውና ውሣኔውም እርስ በራሱ የሚጋጭ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከቱትን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 51055 በቀን 12-4-2003 ዓ.ም ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 50973 በቀን 23-3-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመዝ.ቁ. 08979 በቀን 16-3-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 195/2/ /ለ/ /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተሰርዞ በነጻ እንዲሰናበት ብለናል፡፡ የወንጀል ኀላፊነቱን ሊያቋቁሙ የሚችሉት ተግባራት በበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በሌላ ወንጀል የሚፈለግ ካልሆነ ከማረሚያ ቤት እንዲለቀቅ መፍቻ ለሚመለከተው ይጻፍ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁጥር 46386

ታህሣሥ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ሃይሉ ተስፋሁ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ ብርሃነ መብራቱ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ገንዘብን ለማስመለስ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪና በወ/ሪት መብርሂት ቅዱስ ላይ በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁኑ ተጠሪ ዘበኛ፣ ወ/ሪት መብርሂት ቅዱስ ደግሞ የሽያጭና መዛኝ ሰራተኛ ሁነው በአመልካች የወፍጮ ድርጅት ውስጥ ሲሰሩ በወፍጮ ድርጅቱ ውስጥ ባለው መጋዝን ካዝና አመልካች ያስቀመጡትን ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺህ) መጋዝኑ ተከፍቶ ካዝናው ተሰብሮ ስለተሰረቀባቸው የተሰረቀው ይኸው ገንዘብ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የድርጅቱ ሰራተኛ መሆናቸውን ሳይክዱ ድርጅቱ ተሰረቀ በተባለበት ጊዜ በፈቃድ ለጠበል ሂደው ሌላ ቦታ ያደሩ መሆናቸውን ገልጸው ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ከክሱ ነጻ፣ ተጠሪን ደግሞ ኃላፊ በማድረግ ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺህ) ለዳኝነት የተከፈለበት ብር 662.00 ኪሳራና ሌላ ወጪ እንዲሁም የድካም ዋጋ በቁርጥ ብር 300.00 ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የደርጅቱ ዘበኛ ሁነው ተቀጥረው እየሰሩ ቢኖሩም ካዝናው ተሰብሮ ገንዘቡ በጠፋበት በ30/05/2000 ዓ/ም በአመልካች ፍቃድ ወደ ጠበል ሂደው ስለነበር አልነበሩም፣ አመልካች ራሱ የፍርድ ቤት መጥሪያ ለተጠሪ በሚሰጡበት ጊዜ ገንዘቡ አልጠፋም ከእህቴ ጋር አግኝቼዋለሁ ብለው ሲናገሩ ሰምተናል ብለው ስለመሰከሩ እንዲሁም ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺህ) ያክል በመጋዘን ውስጥ በካዝና ያስቀምጣል ተብሎ አይገመትም የሚሉትን ምክንቶችን በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ለገንዘቡ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀረቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በወንጀሉ ጉዳይ

ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው እያለ ለፍትሐብሔር ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው እያለ ለፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር፣ የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ ተጠሪ ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ተጠሪን በድርጅታቸው በጥበቃ ስራ ቀጥረው በማስራት እያሉ በድርጅቱ መጋዝን ውስጥ በሚገኘው ካዝና የተውት ገንዘብ ካዝናው ተሰብሮ እንዲሰረቅባቸው አድርገዋል በማለት ገንዘቡን እንዲተኩላቸው ሲሆን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ የበታች ፍርድ ቤቶቹ ተገቢ ነው ያሉትን ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቀው የሚከራከሩትና በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው ተብሎ የተያዘውም ተጠሪ በወንጀል ተከስሰው ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው እያለ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ከቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች መካከል ተጠሪ በጉዳዩ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉበትና የተቀጡበትን የፍ/ቤት ውሣኔ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ወይም ብቁነት ሳይገልጽ ስለማለፉ የውሣኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የተቆጠረው ወይም የቀረበው ማስረጃ ለክርክሩ መነሻ ከሆኑት ፍሬ ነገሮች ጋር ግንኙነት እያለው እና ፍሬ ነገሮችን ለማረጋገጥ በሕጉ ክልከላ ያልተደረገበት የማስረጃ ዓይነት እስከሆነ ድረስ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ሁሉም ማስረጃዎች መመዘን አለባቸው፡፡ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉን ማስረጃዎች በአንድነት ሳይመዘኑ የተወሰኑትን ብቻ ነጥሎ በመወሰድ የሚሰራ ምዘናም ሆነ ውጤት ሕጋዊነት አይኖረውም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ በወንጀል ተከሰው ፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑንና በበላይ ፍ/ቤትም አለመለወጡ ተረጋግጦ እያለ ይህ የአመልካች ማስረጃ በሰበር ፍ/ቤት በዝምታ ታልፏል፡፡ ይህም የማስረጃ አቀባበል ሥርዓትን ያልተከተለ ነው፡፡ የዚህን ማስረጃ አግባብነት እና ብቁነት ስንመለከተውም ለጉዳዩ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2149 ተቃራኒው ንባብ ያስገነዝባልና፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔሩ የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም የሚል ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎችም በፍትሐብሔሩ ጉዳይም የቀረቡና የተሰሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በወንጀሉና በፍትሐብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍትሐብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁል ጊዜ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አላማ ያስገነዝበናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የፍትሐብሔር ጉዳይ የተመለከተው የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ክብደት በመመዘን ነው፡፤ በወንጀሉ ጉዳይ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት በሰራተኝነት የጥበቃ ስራ ግዴታቸውን አልተወጡም በሚል ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ የፍትሐብሔር ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ካዝና ላይ የተቀመጠው ጥሬ ገንዘብ ስለተሰረቀብኝ ተጠሪ ይመልሱልኝ በሚል ነው፡፡ ይህም በግልጽ የሚያሳየው አመልካች ተጠሪ ሰርቀው የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን እንጂ በንዝህላልነት የተሰጠውን የስራ አመራር ግዴታ ያለመወጣትንና በወንጀል ሕጉ 702(2) ስር የሚያስጠይቀውን የወንጀል ድርጊት ፈጸመው ገንዘቡ ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን የሚያሳይ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ተጠሪ በወንጀል ተከስሰው ጥፋተኛ ከተባሉት የወንጀል ድርጊት ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 መሰረት ኃላፊ የሚሆኑበት አግባብ የለም በማለት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27225 መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 30033 ሚያዚያ 13 ቀን 2001 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 67411

ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አደነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** .1. አቶ ታረቀኝ ተክሉ ገመዳ

2. ወ/ሮ እማዋይሽ ገብረመስቀል

3. አቶ አብይ ታመነ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባር እና

የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ባለቤት ሆኖ የመገኘት የወንጀል ተግባርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ/ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የመሰረተው ክስ ይዘት በ1997 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ))፣33 እና 419(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች በግብረአብርነትና በልዩ ተካፋይነት ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ወይም ገንዘብ ለማፍራት የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ዝርዝር ይዘቱም፡-1ኛ አመልካች ከሰኔ 01 ቀን 1986 እስከ መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ በሀዋሳ ዙሪያ እና በወንዶገነት ወረዳዎች ታክስ አስተዳደር ጽ/ቤት በእለት ገቢ ሰብሳቢነት ሲሰሩ መነሻ ደመወዛቸው ብር 182.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሁሉት ብር) ሁኖ በየጊዜው በተደረገላቸው የእርከን ጭማሪ እና የደረጃ እድገት ስራቸውን እስከለቀቁበት መጋቢት 2000 ዓ/ም ድረስ ደመወዙ ብር 928.00(ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንት ብር) የደረሰ መሆኑንና የደመወዙ ከፍተኛ መጠን ሲሰላም ጠቅላላ ገቢያቸው ከብር 70,000.00(ሠባ ሺጎ ብር) እንደማይበልጥ፣2ኛ አመልካች ደግሞ የ1ኛ አመልካች ባለቤት ሁነው ከባለቤታቸው ደመወዝ ውጪ በግላቸው የሚያገኙት ሕጋዊ የሆነ የገቢ ምንጭ የሌላቸው የቤት እመቤት ሁነው እያለ በስማቸው የከተማ ቦታና እና የይስሙላ ንግድ ፈቃድ(የማይሰራበት ንግድ ፈቃድ) በመውሰድ በዚሁ ባልታደሰ ንግድ ፈቃድ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ በመውሰድ በሕገ ወጥ ንብረትና እና ገንዘብ ከ1ኛ አመልካች ጋር ግብረ አበር ወይም ልዩ ተካፋይ በመሆን ንብረቱን እንዳፈሩ፣3ኛ አመልካችም የ2ኛ አመልካች ወንድም ሁነው በስማቸው ቋሚ እና ሕጋዊ የገቢ ምንጭ የሌላቸው ተማሪ ሁነው እያለ ከ1ኛ እና ከ2ኛ አመልካቾች ጋር ያለውን ዝምድና ምክንያት በማድረግ 1ኛ አመልካች በስማቸው የሊዝ ቦታ ጠይቀው ከሊዝ ደንብና መመሪያ ውጪ G+1(Ground Plus

One) የመኖሪያ ቤት ሰርተው ከ2ኛ አመልካች ጋር የሚኖሩበትን ቤት ለ3ኛ አመልካች በሕግ የተረጋገጠ ወይም የተፈጸመ ወራሽነት ሳይኖረው ከወላጅ አባቱ ከውርስ ባገኘው ገንዘብ ቤቱን እንደሰራ በማስመሰል በስሙ ባወጣው የሐሰት ባለቤትነት ማረጋገጫ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ሕገ ወጥ ንብረት እንዲያፈሩ በማድረግ በግብረአብረት ወይም በልዩ ተካፋይነት ወንጀል መፈጸማቸውን የሚጠቅስና በጠቅላላው አመልካቾች ክስ እስከ ቀረበባቸው ድረስ ብር 3,602,000.84(ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሁለት ሺኅ ከሰማኒያ አራት ሳንቲም) የሚሆን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ማፍራታቸውንና ይህም ንብረት ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ የማፍራት የሙስና ወንጀል ነው በማለት አመልካቾች እንዲጠየቁ ክስ ማቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ክሱን ለማስረዳትም የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ዘርዝሯል፡፡አመልካቾች ክሱን ክደው በመከራከራቸውም ተጠሪ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ከዚህም በሁዋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ማስተባበላቸውን በመግለጽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በተከሰሱት የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው 1ኛ አመልካች በሌላ ጉዳይ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተቀጡ መሆናቸው በመረጋገጡ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በአንድ አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ የተወሰነ ሲሆን በሕገ ወጥ መገንድ መገኘቱ የተረጋገጠውን ንብረት ደግሞ አይነቱና መጠኑን ይኸው ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤት ከለየው በሁዋላ ለመንግሰት እንዲወረስ በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሚያዚያ 04 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካቾች በወንጀል ድርጊት እንዲጠየቁ የተደረገው የሀብት ምዝገባና ማሳወቂያ ሥርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታና የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈማቸው በተገቢው መንገድ ከሳሽ ሳያስረዳ መሆኑንና የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች ቃልም ውድቅ የተደረገው ያላግባብ መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የምዝገባ ስርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታ አመልካቾች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አፍርተዋል ተብሎ የመቀጣታቸውንና ንብረታቸውም እንዲወረስ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ተጠሪ ቀርቦ መልሱን በጽሑፍ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የሀብት ምዝገባና ማሳወቂያ ስርኣት ያለመዘርጋት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 419 ስር በተመለከተው ድንጋጌ ከመጠየቅ የማይከለክል መሆኑን፣አመልካቾች ለሰበር ችሎቱ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት ተፈጽሟል ብለው የገለጿቸው ምክንያቶች ስለማስረጃ ምዘና የሚመለከቱ እንጅ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያስረዱ አለመሆኑን፣የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲህ አይነት የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በሕጉ የማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የወንጀል ድርጊቱን መፈፃማቸው ተነግሮባቸው በመከላከያ ማስረጃዎቻቸውም የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ባለማስተባበላቸው ምክንያት መሆኑን

ዘርዝሮ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡የአመልካቾች ጠበቃም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የምዝገባ ሥርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታ አመልካቾች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አፍርተዋል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመቀጣታቸውንና ንብረታቸውም እንዲወረስ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ይሁን እንጂ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 መሰረት ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ የመገኘት የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት ለማስከተል የሚችለው የምዝገባ ሥርዓት ሲዘረጋ ስለመሆኑ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ በአመልካቾች ጠበቃ በኩል የቀረበው ክርክርም ሆነ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ተቀባይነት የሚያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ሌላው አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419(1) ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ ተገኝቷል ተብለው በወንጀል የተከሰሱባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ይግባኙን በተመለከተው የክልሉ ጠቅለይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የሰጠው የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ሲታይም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ምክንያቱም ይኸው ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ለጉዳዩ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ሲሆን የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነውና፡፡ይህ ችሎት ሊመለከተው የሚችለው የሕግ ጥያቄን ብቻ ሲሆን ከዚህ አንፃር በስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹ ተመዝነው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተይዞ በሕግ ረገድ ያለው ነጥብ ሲታይ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበትን የወንጀል ድርጊት ያቋቁማል? ወይስ አያቋቁምም? የሚለውን ጉዳይ ስንመለከተው የአሁኑ 1ኛ አመልካች በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነው ከብር 182.00 የወር ደመወዝ ተነስተው በጭማሪና በዕድገት ብር 928.00 የወር ደመወዝ ላይ ደርሰው በዚህ መጠነኛ ደመወዝ ራሣቸውን ሲያስተዳድሩ እንደቆዩና ባለቤታቸውም ሌላ ህጋዊ ገቢ እንዳልነበራቸው፣3ኛ አመልካችም ሕጋዊ ገቢ ያልነበራቸው ሁኖ ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካች ጋር በመመሳጠር ሕጋዊ ያልሆነ ንብረት 1ኛ እና 2ኛ አመልካች እንዲይዙና በሕጋዊ መንገድ የተገኘ ለማስመስል በመፈለግ በወንጀል ተግባሩ መካፈላቸው ተረጋግጦ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ምንጩ ያልታወቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ መገኘቱና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ባለቤት ሆነው መገኘታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ለ))፣33 እና 419(1) የወንጀል ተጠየቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም አመልካቾች ጥፋተኛ መባላቸውም ሆነ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ተጠይቆ ስለቅጣት በወንጀል ሕጉ የተመለከቱት የቅጣት አጣጣል መርሆች መሰረት ተደርገው እያንዳንዳቸው ላይ ተገቢ የእስራት ቅጣቱ መጣሉ  እንዲሁም ንብረቱ እንዲወረስ መወሰኑ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ

ምክንያት አላገኘንም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 33970 ተሰጥቶ በክልሉ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 50929 ጥር 17 ቀን 2003 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195 ((2(ለ-2)) መሠረት ፀንቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/.ቁ 67777

ታህሳስ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1. ተወልደ ብስራት

2. ሃይላይ ገ/መድህን

3. ገላን ሰቦቃ

ከጠበቃ ገብረ እግዚብሔር ተስፋዬ ጋር ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የለም፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 448(1 እና 3) መሰረት አንድን ሰው ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሁኖአል በማለት ወዲያውኑ ለመቅጣት መሟላት ስላለባቸው ሕጋዊ መስፈርቶችን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ በከሳሽ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግና በተከሳሾች እነ ተካበ ገ/ስላሴ ስድስት ሰዎች መካከል በነበረው የወንጀል ክስ ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ክሱ በዐቃቤ ሕግ በኩል በተከሳሾች ላይ ከተመሰረተና በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከቀረበ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲሄዱ ትዕዛዝ ሰጥቶ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ምርመራ ክፍል ኃላፊዎች ተከሳሾችን ወደ ማረሚያ ቤት ሳይወስዱ ወይም ሳይልኩ በራሳቸው ማረፊያ ቤት ለረዥም ጊዜና ወራት አቆይተዋቸዋል፣ የፍርድ ቤቱንም ትእዛዝ ሳያከብሩ ቀርተዋል በማለት የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1) እና (3) መሰረት ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸውን በሁለት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩ ከተመረመረ በሁዋላ ይግባኙ ሰሚው ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1 እና 3) ስር ጥፋተኛ መባላቸውና ቅጣት መተላለፉን አግባብነት ተቀብሎ የቅጣቱን አፈጻጸም ብቻ በገደብ እንዲሆን በማድረግ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለጉዳዩ አመልካቾች ተጠያቂ መደረጋቸው የድንጋጌውን ይዘት እና በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ባላገናዘበ መልኩ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካቾችን ቅሬታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው አመልካቾች የፍርድ ቤቱ ዋራንት በአግባቡ እንደደረሳቸው ሳይረጋገጥ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 448(1(ሀ)) እና (3) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ መባላቸው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሊባሉ የቻሉት የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን በአቶ ተካበ ገ/ስላሴ ላይ በመሰረተው የኮንትሮባንድ የወንጀል ክስ በመ/ቁጥር 162887 ፋይል ተከፍቶላቸው ፍርድ ቤት ቀርበው ፍርድ ቤቱም ጥር 03 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተከሳሹን የዋስትና መብት ጠብቆላቸው ተከሳሹ የተፈቀደላቸውን የዋስትና መብት ካላሟሉ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ ሲል የእስር ዋራንት እንዲፃፍ በማለት ትዕዛዝ የሠጠ ቢሆንም ተከሳሹ ወዲያውኑ ማረሚያ ቤት ሳይገቡ በባለስልጣን መስሪያ ቤት ደረቅ ፖሊስ ጣቢያ ከአስር ወራት በላይ ታስረው የተገኙ መሆኑን፣ ይኸው ግለሰብ በአጠቃላይ ከአንድ አመት ሁለት ወራት በላይ የታሰሩ መሆኑን፣ መስፍን ካሳሁን የተባሉት ተከሳሽም በተከሰሱበት ወንጀል በወንጀል መዝገብ ቁጥር 169690 ፋይል ተከፍቶባቸው በፍርድ ቤቱ ቀርበው ፍርድ ቤቱ ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተመሳሳይ መልኩ በመዝገቡ ላይ የዋስትና መብታቸውን ጠብቆላቸው ሲያበቃ የተፈቀደላቸው የዋስትና ግዴታ ተከሳሹ መፈፀም ካልቻሉ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ ሲል ትእዛዝ ሰጥቶ ተከሳሹ ወዲያውኑ ማረሚያ ቤት ሳይላኩ የእስር ዋራንቱ በመዝገቡ ላይ ከተሰጠ በሁዋላ በባለስልጣኑ ፖሊስ ጣቢያ ከስድስት ወራት በላይ መታሰራቸውን፣ ሃይሉ ወርቁ እና ሊዊዛ ፋርቤታ የተባሉት ሁለት ግለሰቦች ደግሞ በተከሰሱበት የጉምሩክ ማጭበርበር የወንጀል ድርጊት በመ/ቁጥር 167550 በሆነው ፋይል ተከፍቶላቸው ፍርድ ቤት ቀርበው በዋስትና መብት ላይ ትዕዛዝ ከተሰጠ በሁዋላ የዋስትና ግዴታቸውን በትዕዛዙ አግባብ መፈፀም ካልቻሉ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ ሲል ፍርድ ቤቱ የእስር ዋራንት እንዲፃፍ ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቶ በትእዛዙ መሰረት ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ሳይላኩ እያንዳንዳቸው እጃቸው በፖሊስ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ፍርድ ቤት እስከቀረቡበት ጊዜ ያለውን ሳይጨምር በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከስምንት ወራት በላይ ታስረው መቆየታቸው መረጋገጡን፣ መንግስቱ አብርሃምና አህመድ መሐመድ በተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል ደግሞ በመ/ቁጥር 172759 እና ባምላክ ይስማው የተባሉት ተከሳሽ ደግሞ በመ/ቁጥር 170203 ፋይል ተከፍቶላቸው ፍርድ ቤት ቀርበው በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ የእስር ዋራንት እንዲጻፍ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ወደ ማረሚያ ቤት ሳይላኩ እያንዳንዳቸው ቢያንስ ሶስት ወራትን ያህል በፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸውን የስር ፍርድ ቤት መገንዘቡን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከተቸዋል ያላቸውን የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት የወንጀል ምርመራ ቡድን አስተባባሪ ኃላፊዎችን ችሎት ቀርበው እንዲያስረዱና ሕጋዊ መግለጫ እንዲሰጡበት በማለት በሶስት የወንጀል መዛግብት ላይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን የአሁኑ አመልካቾችም ወደ ፍርድ ቤቱ ቀርበው አለኝ ያሉትን ምክንያት ያቀረቡ ሲሆን የአሁኑ ሁለተኛው አመልካች የባለስልጣኑ መሰሪያ ቤት ፖሊስ ጣቢያ የእስረኞች ሰነዶች ክትትል ኃላፊ መሆናቸውን ገልፀው የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሳይከበር የቀረው ከፍርድ ቤቱ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት የተላኩት የእስር ዋራንቶች የስም ስህተት ስለተከሰተባቸውና ማረሚያ ቤቱም አልቀበልም ስለአለ ነው፣ የሥም ስህተቱ በዋራንቱ እንዲስተካከልም በተደጋጋሚ ጊዜያት ወደ ፍርድ ቤቱ በመምጣት አቤት ብያለሁ፣ ከፍርድ ቤቱ ግን የተሰጠኝ አፋጣኝ ምላሽ የለም፣ ከዚህ ሌላም ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊዎች ጋር ደጋግሜ ተነጋግሬበታለሁ፣ ግን መፍትሔ ሊገኝ

ባለመቻሉ ተከሳሾች ለበርካታ ወራት ሊታሰሩ ችለዋል በማለት የዘረዘሩ ሲሆን የአሁኑ 1ኛ አመልካችም ከቦታው ላይ በኃላፊነት ከመመደባቸው ከመጋቢት 2002 በፊት ተከሳሾች በፖሊስ ጣቢያው ታስረው ነው ያገኟቸው መሆኑን፣ በፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት መታሰራቸው ኃላፊነትን እንደሚያስከትል በመገንዘብም ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ የበኩላቸውን ጥረት እንደአደረጉ፣ በመዝገብ ላይ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከሆነም ተገልብጦ እንዲመጣላቸው ዐቃቤ ሕጎችን ሳይቀር በተደጋጋሚ ጊዜያት መላካቸውን፣ ሆኖም ግን ከመስሪያ ቤቱ አቃቤ ሕጎች አንዱ የሆኑት አቶ ወንድወሰን ደሳለኝ ተከሳሾች ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ የተሠጠ ትዕዛዝ የለም ብለው ሊገልፁላቸው የቻሉ መሆኑንና ከዚያም ተከሳሾች ወደ ማረሚያ ቤት ሳይገቡ በእድገት ምክንያት ከወንጀል ምርመራ ቡድን አስተባባሪነታቸው መነሳታቸውን በምክንያትነት ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ የአሁኑ ሶስተኛ አመልካች ደግሞ የወንጀል ምርመራ ቡድን አስተባባሪ ኃላፊ መሆናቸውን ጠቅሰው የወንጀል ምርምራ አጣርተው ከጨረሱ በኂላ ምርመራውን ያጣሩበትን ተከሳሽ በዋስ ሊወጣ/ሊለቀቅ የቻለ መሆኑን፣ ከዚያ በሁዋላ በተጠረጠረበት ወንጀል የወንጀል ክስ ተመስርቶበት ፍርድ ቤት ከቀረበ በኂላ ስለሆነው ነገር እንደማያውቁ፣ ተከሳሽ መስፍን ካሳሁን ወይም ሌሎች ተከሳሾች በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት መታሰራቸውን ያወቁት ቀርበህ አስረዳ ተብሎ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲደርሳቸው መሆኑን፣ የወንጀል ምርመራውን ያጣሩት እርሳቸው ስለሆኑ ጉዳዩን እስከመጨረሻው የመከታተል ኃላፊነት እንደነበረባቸውና ሌሎች ኃላፊዎችም ተከሳሾች ለበርካታ ወራት መታሰራቸውን እንደሚያውቁ ዘርዝረው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከተው አመልካቾች እያንዳንዳቸው ያቀረቡት ምክንያት ሲሆን የሁሉም አመልካቾች የጋራ ምክንያታቸው በጥቅሉ ሲታይ ግን ተከሳሾች በፍርድ ቤቱ የእስር ዋራንት ትእዛዝ መሰረት በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው መቆየት ሲገባቸው በፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት መታሰራቸው ስህተትም ጥፋትም መሆኑን አምነው ጥፋቱ ግን የእነርሱ ያለመሆኑን፣ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ያልተከበረው በራሳቸው ምክንያት ያለመሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን ነው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት ለአመልካቾች ለወንጀሉ ተጠያቂነት ምክንያት የሆነው በጉምሩክ ወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት የቀረቡት ተከሳሾች ማረሚያ ቤት እንዲታሰሩ የፍርድ ቤት ማሰሪያ ዋራንት ተሰጥቶ እያለ በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት እንዲታሰሩ መደረጉ ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ መሆንን ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች መደምደሚያ ላይ መደረሱን ነው፡፡ ይህ ችሎትም ከላይ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውን ድንጋጌ ይዘት መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 448(1) ስር አንድ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል በያዘው ጉዳይ ላይ በተከሳሽነት፣ በምስክርነት ወይም በልዩ አዋቂ ምስክርነት ወይም በአስተርጓሚነት፣ በነባሪነት ወይም በተቺነት እንዲረዳ በሕግ መሰረት የተጠራ ወይም ተከሳሽን ወይም ማስረጃን እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ የታዘዘ ማንም ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው ሳይቀርብ የቀረ ወይም ለመቅረብ እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ፣ ተከሳሽን ወይም ማስረጃን ያላቀረበ ወይም ያልላከ እንደሆነ፣ ወይም ቀርቦ ሕግን በሚቃረን አኳኋን ለተጠየቀው መልስ ለመስጠት ወይም እንደታዘዘው ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ሲሆን ይህ አድራጎት ወንጀል ሁኖ ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ሳይሰጥ ወዲያውኑ ቅጣት የሚወሰን ስለመሆኑም የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከድንጋጌው መንፈስ የምንገነዘበው አንድን ሰው ለፍትሕ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሆኖአል በማለት በወንጀል ጥፋተኛ አድርጎ ለመቅጣት

በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ስልጣን ባለው አካል በተከሳሽነት፣ በምስክርነት፣ በልዩ አዋቂ ምስክርነት፣ በአስተርጓሚነት፣ በነባሪነት በተቺነት የተጠራ ወይም ተከሳሽን ወይም ማስረጃን እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ የታዘዘ መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባ የወንጀሉ መሰረታዊ የማቋቋሚያ ባህሪ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና 58 ጋር ተዳምሮ ሲነበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ስለመሆኑ ነው፡፡ ያለመቅረቡና የታዘዘውን ነገር ያለመፈፀሙን ምክንያት ማስረዳት ጉዳይ ደግሞ ከላይ የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ተሟልተው መገኘት ከተረጋገጠ በሁዋላ የሚፈፀም ተከታይ ተግባር መሆኑን የተጠቃሹ አንቀፅ አቀራረፅና ይዘት እንዲሁም ዓላማው የሚያስገነዝበን ነጥብ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ባለማክበር በወንጀል የተከሰሱትን ሰዎች ማረሚያ ቤት መውስድ ሲገባቸው በባለስልጣኑ ፖሊስ ጣቢያ በማሰር ለበርካታ ወራት አቆይተዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ተከሳሾች ለበርካታ ወራት በፖሊስ ጣቢያ ያላግባብ መታሰራቸውን አናውቅም በማለት ሳይሆን በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት ለማረሚያ ቤቱ ለማስረከብ ሲሞከር በስም ስህተት የተነሳ ማረሚያ ቤቱ ሊረከብ ያለመቻሉንና ፍርድ ቤቱም በማሰሪያ ዋራንቱ ላይ የተከሰተውን የስም ስህተት እንዲያስተካክል በተደጋጋሚ ጥያቄ ቀርቦለት ሊያስተካክል ያለመቻሉን፣ እንዲሁም በፍርድ ቤቱ የተሰጠ ማሰሪያ ዋራትን የሌለ መሆኑን የሚመለከታቸው የአቃቤ ሕግ ባለሙያዎች ሲገልፁላቸው የነበረ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋጋጠው ደግሞ ተከሳሾቹ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲታሰሩ በመዝገብ ላይ የማሰሪያ ዋራንት እንዲፃፍ ትእዛዝ መሰጠቱ እንጂ በትክክል የተፃፈ የማሰሪያ ዋራንቱ ለአመልካቾች ደርሷቸው አመልካቾች ይህንኑ እያወቁ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ባለማክበር ተከሳሾቹን ያሰሩ ስለመሆኑ ካለመሆኑም በላይ የስም ስህተት ተከስቷል፣ ይህም ይስተካከልልን በማለት በባለስልጣኑ መሰሪያ ቤት በኩል የቀረበው ጥያቄ በፍርድ ቤቱ በተገቢው ጊዜ ምላሽ የተሰጠበት ስለመሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሲታይ አመልካቾች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ባለማክበር ለፍትሕ እርዳታ መስጠትን እንቢ ማለት ወንጀል ፈፅመዋል ብሎ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ አመልካቾች ከላይ በምክንያትነት የገለጿቸው ፍሬ ነገሮች እውነት መሆን ያለመሆናቸው በተገቢው ማስረጃ ሊጣራ የሚገባው እንጂ ወንጀሉ የተፈጸመው በፍርድ ቤት ነው፣ ተከሳሾቹ ለበርካታ ወራት ተገቢ ባልሆነ ቦታ ታስረዋል በሚል ምክንያት ቀጠሮ ሳይደረግ ወዲያውኑ ቅጣት ለማስተላለፍ የሚያስችል አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ፈጸሙ የተባለውን አድራጎት በተመለከተ በማስረጃ ሳያጣራና ድርጊቱም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1(ሀ)) ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ በተገቢው ሁኔታ ሳያረጋግጥ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ወዲያውኑ ጥፋተኛ በማድረግ መቅጣቱም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቀበል የቅጣቱን አፈፃጸም በገደብ እንዲሆን መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 162887 ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በዚሁ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው መዝገብ ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሠጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102668 ጥር 18 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካቾች የፍርድ ቤቱ ማሰሪያ ዋራንት በትክክል የደረሳቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1(ሀ))እና (3) መሰረት ሊቀጡ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 62504

ታህሣስ 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ናማጋ ሀያቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ፖሊስ ወ/ምርመራ መምሪያ ዋና ሣጅን ደምሴ ሰጠኝ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ሰበር አመልካች በስር የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም እነዳዊት ጸጋዬ የተባሉት 23 ተከሣሾች ህዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም ከከሣሽ ብር 250,000 ዘርፈው ከተሰወሩ በኋላ በፖሊስ ታድነው በክፊል ተይዘው ክስ የቀረበባቸው ሲሆን በጊዜው ከከሣሽ ዘርፈው ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ብር 94,000 በኢግዚቢትነት ተከሣሽ ሲይዝ በተረፈው ገንዘብ እነዚህ በወንጀል የተከሰሱ ግለሰቦች ዓይነታቸውን ባላውቅም የተለያዩ የገዙአቸውንም ቁሳቁሶች ጭምር ተከሣሽ በኢግዚቢትነት ይዟል፡፡ ሆኖም በኢግዚቢትነት የተያዙትን ቁሳቁሶች እና ገንዘብ ተከሣሽ እንዲያስረክበኝ ብጠይቅም ለማስረከብ ፍቃደኛ ስላልሆነ ተገዶ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም በሰጠው መልስ በጊዜው የውንብድና ወንጀል በፈጸሙ 23 ተከሣሾች ላይ 14 ክሶች የቀረቡባቸው ሲሆን በ2ኛ ክስ ከከሣሽ ብር 250,000 ስለመዝረፋቸው በክሱ ተጠቅሷል፡፡ ሆኖም በክሱ ኢግዚቢቶቹ ከ1-8 ተራ ቁጥር ከመዘርዘራቸው በቀር የከሣሽ በኢግዚቢትነት የተያዘው ገንዘብም ሆነ ንብረት ተለይቶ አልተቀመጠም፡፡ በሌላ በኩል በኢግዚቢትነት የተያዙ ንብረቶችን ፖሊስ የመጠበቅ እንጂ የመመለስ ስልጣን የፖሊስ ሳይሆን የፍ/ቤት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡

የስር የመ/ደ/ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ ገንዘቡም ሆነ ሌሎች ቁሳቁሶች የከሣሽ ስለመሆናቸው ከሣሽ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ሌሎች ንብረትና ገንዘብ የተወሰደባቸው ሰዎችም ስላሉ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ወገኖች በማከራከር በሰጠው ፍርድ የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

አመልካችም በስር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብም፡-

ተጠሪው በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ቀርቦ ከአመልካች ወንበዴዎች የወሰዱትን ብር 94,000 እና በገንዘቡ የተገዙትን ቁሳቁሶች በኢግዚቢትነት መያዙን አምኖ መልስ ሰጥቶ እያለ በማስረጃ አመልካች አላስረዳም መባሉና ክሱ ውድቅ መደረጉ ያለ አግባብ ነው የሚል ነው፡፡
ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ መልሱን ያቀረበ ሲሆን በመልሱ ግን በስር ፍ/ቤት ከሰጠው መልስ የተለየ ነገር አላቀረበም፡፡

የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የስር ፍ/ቤቶች በኢግዚቢትነት የተያዘ ገንዘብና ንብረቶች የብዙ የግል ተበዳዮች ስለመሆኑና ከሣሽ የራሱ ገንዘብና ንብረት ነው የሚለውን ለይቶ በማስረጃ ስላላስረዳ ክሱ ውድቅ ነው ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ዐ/ሕግ በ12-7-1993 ዓ.ም በተጻፈ ክስ 14 የወንጀል ክሶችን የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል በተባሉ ተጠሪዎች ላይ አቅርቦ የነበረ ሲሆን የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል ከተባሉት የግል ተበዳዮችም አንዱ በ2ኛ ክስ ስሙ የተጠቀሰው ያሁኑ አመልካች ነው፡፡ በክሱም ወንበዴዎቹ ከአሁኑ አመልካች ብር 250,000 ዘርፈው መውሰዳቸው ተገጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከክሱ ጋር በተያያዘው የኢግዚቢት ዝርዝር በተራ ቁጥር 3 በወንጀል ክሱ ሶስተኛ ተከሣሽ በ2ኛ እና በ5ኛ ክስ በፈጸመው ዘረፋና የማታለል ወንጀል የገዛው ጃኬት ጫማ ሸሚዝ እና ደብቆ የተገኘው ገንዘብ ብር 48,740 እንዲሁም ስድስተኛ ተከሣሽ በ2ኛ እና በ5ኛ ክስ ላይ በፈጸመው የማታለል እና የዘረፋ ወንጀል ካገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 40,610 እና ከዘረፋው ባገኘው ገንዘብ የተገዛ ሙሉ ሶፋ ፣ ፍሪጅ ፣ ፔርሙስ የመሳሰሉት ንብረት መያዛቸውን ተጠሪው ገልጿል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንና ንብረቶች የተያዙት በ2ኛ ክስ በግል ተበዳይነት ከተጠቀሰው ከአሁኑ አመልካች እና በ5ኛ ክስ ከተጠቀሰው የግል ተበዳይ አቶ ገብረማርያም አሰፋ ከተባለ ግለሰብ ነው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ በኢግዚቢት በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተጠቀሰው ገንዘብና ንብረቶች ከሁለቱ የግል ተበዳዮች መካከል በሚደርሳቸውን የገንዘብ መጠንና የንብረት ዓይነት በማጣራት ከመወሰን በቀር በክሱ ውስጥ ያሉ የግል ተበዳዮች ሁሉ ንብረት እና ገንዘብ ነው በማለትና አመልካች ክሱን በማስረጃ አላስረዳም በሚል ውድቅ ማድረግ ስለማይገባ የስር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡
በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 75346 በቀን 06-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 92547 በቀን 26-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት በ5ኛ ክስ የግል ተበዳይ የሆነውን አቶ ገብረማርያም አሰፋ የተባለውን ግለሰብ ወደ ክሱ እንዲገባ በማድረግ እንዲሁም በጊዜው በወንበዴዎቹ ላይ የተጣራውን የፖሊስ ምርመራ መዝገብ አስቀርቦ በመመልከት ማስረጃዎችን በመመዘን የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት እንደገና መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ.60518

ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፈለቀ ሊቤ- ቀረበ

ተጠሪ፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የስነ- ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ- አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት በቀረበው ክስ የአሁኑ አመልካች 3ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን ከቀረቡባቸው ሁለት ክሶች ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው በ3ኛው ክስ የተላለፈበት የጥፋተኛነት የቅጣት ውሳኔ ነው፡፡ የአሁኑን አመልካች ጨምሮ በስር 2ኛ፣9ኛና 14ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበባቸው 3ኛ ክስ ፍሬ ቃሉ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)፣33 እና 407(1) እና (2) የተደነገገውን በመተላለፍ 2ኛ ተከሳሽ የጠምባሮ ወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ፣ 3ኛ ተከሳሽ የወረዳው ውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሀላፊ፣9ኛ ተከሳሽ የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ዋና ሀላፊ፣14ኛ ተከሳሽ የግል ኮንትራክተር ሆነው በሚሰሩበት ወቅት 2ኛ ተከሳሽ በቁጥር 1727/ፈ-126/99 በቀን 28/3/99 ዓ/ም እና በቁጥር 2030/ፈ-126/99 በቀን 23/3/99 ዓ/ም በተጻፉ ደብዳቤዎች ተሰርቶ ላልተጠናቀቀ ለባዳ ምንጭ ግንባታ ከተያዘው በጀት ብር 90,699.94 ላይ ብር 60,466.83 ያለ አግባብ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ህገ ወጥ ትዕዛዝ በመስጠቱ፤ 9ኛው ተከሳሽ በቁጥር 81/ፈ-126/99 በቀን 14/05/99 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ቀደም ሲል በ2ኛ ተከሳሽ ህገ ወጥ ድርጊት ሲከፈል የቀረውን ብር 30,000 ላልተሰራ ስራ እንዲከፈል ለወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ህገ ወጥ ክፍያ እንዲፈጽም ትዕዛዝ በመስጠቱ፤14ኛ ተከሳሽም ከ2ኛ፣ከ3ኛ እና ከ9ኛ ተከሳሾች ጋር በመመሳጠር በማመሳከሪያ ሰነዶች በሶስት የተለያዩ ቀናት በድምሩ ብር 90,466.83 ላልተሰራ ወይም ላላተጠናቀቀ ስራ ያለ አግባብ የመንግስትና የህዝብ ገንዘብ በመወሰዱ፣3ኛ ተከሳሽም የአሰሪው መ/ቤት ሀላፊ ሲሆን ከማንም እና ከምንም በላይ ከፍተኛ ሀላፊነት እያለው ላልተሰራ ስራ ወይም ላላተጠናቀቀ ስራ ክፍያ እንዲፈጸም በማመቻቸቱ ሁሉም ተከሳሾች ወንጀል ለመስራት በማቀድ እና በማሰብ ለራሳቸው ወይም ሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በዋና ወንጀል አደራጊነት እና በልዩ ተካፋይነት በፈጸሙት በስልጣን ያለ አግባብ የመገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተካሳሹም የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የሥር የከምባታና ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሳሽን ምስክሮች በመስማትና

ተከሳሽ ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር በሰጠው ውሳኔ ተካሳሹ በመከላከያ ማስረጃነት አንዱ ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ በቁ/ጠወ/አስም/ 372/99 በቀን 3/04/99 የወረዳው ውኃ ጽ/ቤት ሀላፊ ሆኖ በውክልና እንዲሰራ የተጻፈለትን ደብዳቤ ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆነው የባዳ ምንጭ ግንባታ ውል ደግሞ የተደረገው በ27/3/99 በመሆኑ ውሉ ሲደረግ ተከሳሽ ሀላፊነት ላይ አልነበረም፡፡

በውሉ መሰረት 1/3ኛ ክፍያ ተከሳሹ የጽ/ቤቱ ሀላፊ ሆኖ እንዲሰራ ከመወከሉ በፊት የተፈጸመ ቢሆንም ቀሪ ክፍያ ግን መፈጸም ያለበት ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ መሆን ሲገባው ተከሳሹ ከተወከለ በኋላ ላልተሰራ ስራ ከውሉ ስምምነት ውጪ በ25/4/99 ብር 30,233.30 እና በ26/4/99 ብር 30,000 በድምሩ 60,233.30 ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ስለሆነም የውክልና ማስረጃው አግባብነት የለውም፤ እንዲሁም ተከሳሽ ያቀረባቸው ሌሎች ድብዳቤዎች ማለትም በቁ/ጠወ/ውሃ/26/99 በቀን 17/12/99 እና በቁ/307/ጠጠ-35 በቀን 27/2/2000 የተጻፉት የኦዲት ውጤት ከታወቀ በኋላ ከሀላፊነት ለመሸሽ ሲል የጻፋቸው ስለሆኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የላቸውም በማለት በወ/ህ/ 32(1)ሀ፣33 እና 407(1)(ሀ)ስር ጥፋተኛ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የቅጣት ሪከርድ አልቀረበም በሚል በሁለት አመት ጽኑ እስራት እና በብር 500 መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተከሳሽ ያቀረበውን ይግባኝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/195 (1) መሰረት የሰረዘ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔም ሆነ በጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረጉ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብም፡- ላልተሰራ ስራ ወይም ላልተጠናቀቀ ስራ ክፍያው እንዲፈጸም ያዘዘው የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ ሲሆን ክፍያውን የፈጸመው ደግሞ የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ነው፡፡ ነገር ግን የወረዳው ውኃ ሀብት ጽ/ቤት ፈጸመ ተብሎ አንድም የተጠቀሰ ድርጊት በሌለበት አመልካች ሁኔታዎችን አመቻችቷል በሚል ብቻ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈብኝ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣23(2) እና 32 (1) ሀ-ሐ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ አመልካች ላቀረበው ቅሬታ በሰጠው መልስ ያልተሰራውን ወይም ያልተጠናቀቀውን የባዳ ምንጭ ውኃ ፕሮጀክት በሀላፊነት የሚያስገነባውና የሚቆጣጠረው አመልካች በሀላፊነት የሚመራው የውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሲሆን አመልካች ስራው ያለበትን ደረጃ የማወቅ ዕድል እንደነበረው ባቀረብናቸው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች አስረድተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ላልተሰራ ወይም ላልተጠናቀቀ ስራ ክፍያ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ያመቻቸ በመሆኑ የተላለፈበት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም ላልተሰራ ወይም ላልተጠናቀቀ ስራ ክፍያ እንዲፈጸም አመልካች ሁኔታዎችን አመቻችቷል በሚል 32(1)ሀ፣33 እና 407(1)ሀ ስር ጥፋተኛ ነው ተብሎ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርበው ከተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች አመሰካከር የተጣራው ፍሬ ነገር ስራው አልተሰራም ወይም አልተጠናቀቀም በሚል ለክሱ ምክንያት በሆነው የባዳ ምንጭ ግንባታ ለኮንትራክተሩ ያለ አግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣ ክፍያው እንዲፈጸም ደግሞ ትዕዛዝ የሰጠው የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ መሆኑንና ክፍያውን የፈጸመው ደግሞ የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከኮንትራክተሩም ጋር ስለ ስራው ውል የገባው የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት መሆኑ በስር ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚሁ ውል መሰረት ለኮንትራክተሩ ከጠቅላላው የውል ገንዘብ ውስጥ 1/3ኛው ውሉ በተገባበት ጊዜ ሲከፍል አመልካች በወረዳው ውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሀላፊ እንዳልነበረም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች የውኃ ጽ/ቤት ሀላፊ ሆኖ በሰራባቸው ጊዜያትም ለምንጩ ግንባታ ቀሪ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ለፋይናንስ ትዕዛዝ ስለመስጠቱ  የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ ሆኖም ተጠሪው አመልካች ለተፈጸመው ህገ ወጥ ክፍያ ሁኔታዎች አመቻችቷል የሚለው የስራው ባለቤት የአመልካች መ/ቤት በመሆኑ የስራውን መጠናቀቅና አለመጠናቀቅ ሁኔታን የመከታተልና የማወቅ ሀላፊነት አለበት በሚል ነው፡፡ ይህንኑ የተጠሪ ክርክር ደግሞ አመልካች ጥፋተኛ ነው ከተባለበት የወንጀል አንቀጽ 32 (1)(ሀ)፣33 እና 407 (1)(ሀ) አንጻር መመርመር ተገቢነት አለው፡፡

በዚሁ በተጠቀሰው ወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የተሰጠውን ሹመት ወይም ስልጣን በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት  ያለ አግባብ የተገለገለበት እንደሆነ በሥልጣን ያለ አግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሚቀጣ ሲሆን እነዚህ በአንቀጹ የተገለጹ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ደግሞ  በፍሬ ነገር ደረጃ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

ተጠሪው ምንም እንኳን ገንዘቡ በህገ ወጥ መንገድ እንዲከፈል አመልካች ሁኔታዎችን አመቻችቷል ቢልም አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለመስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማደረስ የተሰጠውን ሹመት ያለ አግባብ ስለመገልገሉ  በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ አንድም  ነገር  የለም፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ አመልካች የውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሀላፊ በመሆኑ ብቻ  በስልጣን ያለ አግባብ ስለመገልገሉ የሚያረጋግጡ ፍሬ ነገሮች በሌለበት  ደግሞ ጥፋተኛ ነው ብሎ የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ ከወንጀል ህጉ ዓላማና ግብ ውጪ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች በ3ኛ ክስ አመልካች ጥፋተኛ ነው ሲሉ የሰጡት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል ፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03201 በቀን 15/03/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በ3ኛ ክስ በአመልካች ላይ ያስተላለፈበት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ክፍል እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35038 በቀን 25/6/2002 በዋለው ችሎት የሰጠውን የትዕዛዝ ክፍል እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38944 በቀን 24/10/2002 በዋለው ችሎት የሰጠውን የትዕዛዝ ክፍል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195 (2) (ለ)(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች ከቀረበበት 3ኛ ክስ በነጻ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡ የመቀጮ ገንዘብም ከፍሎ እንደሆነ ሊመለስለት ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤት ቀርቦበት ከነበረው 2ኛ ክስም በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 141 መሰረት መከላከል ሳያስፈልግ በብይን መሰናበቱን መዝገቡ ስለሚያመለክት በሌላ ወንጀል የማይፈለግ ከሆነ ከሚገኝበት የማረሚያ ቤት ተቋም እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይጻፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 71753

ጥር 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ወርቅነህ ዳቲ ጉዳይ ተከታታይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተስፋዬ አባቡ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘቱም፡- አመልካች በ1996 ዓ/ም የወጣውን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ወንጀል አንቀፅ 32/1/ሀ/ እና 598/2/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል ምንም አይነት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከአቶ ሙሉጌታ ገ/ማርያም ጋር ግብረ አብር በመሆን የግል ተበዳይ ነፃነት መንግስቴ የተባለችውን ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 12፡30 ሠዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል በኢትዮጵያ አየር መንገድ አማካይነት ወደ ቤሩት በመላክ ሟች በአሰሪዎቿ ከባድ ድብደባ እየደረሰባት መሆኑን ለቤተሰቦቿ ውጪ አገር ባለችው ዘመዷ አማካይነት ስትናገር ይህ ጉዳይ እየደረሰባት መሆኑን በተመለከተ ለአመልካችና ለግብረ አብሩ ተገልፆ ሟች አገሯ እንድትመለስ እንዲያደርጉ ሲነገራቸው ተከሣሾች መምጣት አትችልም ፣ የሁለት አመት ከአርባ አምስት ቀናት የስራ ኮንትራት አላት በማለት መልስ ከመስጠታቸው ውጪ ወጪ በመክፈል ወደ አገር እንድትመለስ ሁኔታዎችን ጨርሳ ሟች በኢትዮጵያ አየር መንገድ መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡10 ሲሆን ስትደርስ እግሯ በጣም ያበጠና መቆም የማትችል ፣ በአውሮኘላን ሰራተኛ ድጋፍ ወርዳ ወደ ቤቷ ሄዳ መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተወስዳ ምንም እርዳታ ሳይደረግላት በደረሰባት ጉዳት ከቀኑ 5፡00 ሠዓት ሲሆን ሕይወቷ ሊያልፍ መቻሉን ዘርዝሮ ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊን ወደ ውጪ አገር መላክ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች የአቃቤ ክስ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ አሉኝ ያላቸውን የክስ ተቃውሞ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ስለድርጊቱ አፈፃፀም የአመልካችን የእምነት ክህደት ቃል በመጠየቅ አመልካች ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካች በዐቃቤ ህግ ማስረጃ ወንጀሉን መፈፀሙ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልፆ አመልካች እንዲከላከል መብቱን ጠብቆት አመልካችም አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማስቀረብ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ማስረጃዎች የአቃቤ ህግን ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ የሚችሉ አይደሉም በማለት ቃላቸውን

ውድቅ አድርጎ አመልካችን በተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር በማገናዘብ በእያንዳንዱ ክስ ተገቢ ነው ያለውን የእስራት እና የገንዘብ መቀጮ ከአስቀመጠ በሁዋላ በድምሩ ደግሞ 9/ዘጠኝ አመት /ፅኑ እስራት እና በብር 3000.00/ሶስት ሺህ / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ተሰርዟል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለግል ተበዳይ መሞት ምክንያት አመልካች ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ አመልካች ለድርጊቱ ተጠያቂ መደረጉ ያለአግባብ መሆኑን ፣ ሟችን አመልካች ወደ ውጪ በመላክ ሂደት የተሳተፈ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይረጋገጥና የመከላከያ ምስክሮች ቃልም ውድቅ የተደረገው ያለአግባብ መሆኑን ዘርዝሮ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የግል ተበዳይ የሞተችው በበረታ የሳምባ ምች በተሰራጨ የቲቢ በሽታ ታማ ሊሆን እንደሚችል የሕክምና ማስረጃ ቀርቦ እያለ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/2/ ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም በሰጠው መልስ ሟች ወደ ውጪ አገር አመልካችና ግብረ አበሩ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ልከዋት በውጪ አገር እያለች እግሯ አብጦ መምጣቷና ወደ አገሯ እንደተመለሰች ህክምና ሳታገኝ ሕይወቷ ማለፉ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የሳንባ ምች የሚባለው በሽታም ከድብደባ ጋር ተያይዞ ሊከሰት እንደሚችል ሳይንሱ የሚያረጋግጠው ሐቅ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ተጠቅሶበት ሁኖ ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ አመልካች ምንም ሕጋዊ የሆነ ፈቃድ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ነፃነት መንግስቴን ወደ ውጪ በመላክ የግል ተበዳይ ከተላከችበት አገር ድብደባ ደርሷባት እግሯ አብጦ ወደ አገሯ ከተመለሰች በሁዋላ በበነጋታው ሕይወቷ አልፏል የሚል ነው፡፡ አመልካች ክሱን የካደ ሲሆን አቃቤ ሕግ አሉኝ ባላቸው የሰውና የሠነድ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳቱን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጠብቆ የሚከራከረውና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በጭብጥነት የተያዘው ዋናው ነጥብ የግል ነፃነት መንግስቴ የሞተችው በአመልካች ድርጊት ምክንያት መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የተጠቀሰበት ድንጋጌ ይዘትም ሆነ የክሱ ዝርዝር ይዘት አመልካች ለግል ተበዳይ ሞት ምክንያት የሆነ ድርጊት ራሱ በቀጥታ ፈፅሟል የሚል ሳይሆን ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ኢትዮጵያዊ ዜጋን ወደ ውጪ በመላክ የግል ተበዳይ ድብደባ የደረሰባት መሆኑንና ይህ ጉዳትም ከዉጪ አገር ስትመለስ የነበረ ስለመሆኑና ከውጪ አገር ከተመለሰች በሁዋላ በሁለተኛው ቀን ሕይወቷ አገሯ ውስጥ አልፏል በሚል ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ድንጋጌ ስር አንድ ሰው ሊቀጣ

የሚችለው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ የላከ እንደሆነ እና በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት መሆኑ ከተረጋገጠ ሲሆን ቅጣቱም ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ሕጉ ያሳያል፡፡ ይኸው ድንጋጌ በተጠቃሹ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ቀጣይ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱ ሲታይ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያቶች መቀመጣቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ አገር በመላኩ ድርጊት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብት ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረሰ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት ፡፡ ድንጋጌው በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የተላከች ኢትዮጵዊት ላይ በሰብአዊ መብቷ፣ በሕይወቷ ወይም በአኳሏ ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጡን እንጂ በሕገ ወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ በሚፈፀመው ድርጊት ወይም በሌላ ጣልቃ ገብ በሆነ ምክንያት ጉዳቱ መድረሱ መረጋገጡን በወንጀሉ ማቋቋሚነት አያስቀምጥም፡፡ በሌላ አገላለፅ በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጪ አገር የተላከች ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረሰና ይህም ጉዳት ውጭ አገር የደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕገወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ ጉዳዩን ባያደርሰውም በሕገወጥ መንገድ በመላኩና ጉዳቱ በውጪ አገር በመድረሱ ምክንያት ብቻ የወንጀሉ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ሚችን ወደ ውጪ አገር በመላክ የግል ተበዳይዋ ውጭ አገር እያለች ድብደባ ደርሶባት እግሯ አብጦ ወደ አገሯ ከተመለሰች በሁዋላ ሕይወቷ ማለፉና በአካሏ ላይ ጉዳት መድረሱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አመልካች ለድርጊቱ ተጠያቂ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም ሆነ የተያዘው ጭብጥ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው የቅጣት መጠን ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ሲሆን ቅጣቱ የተጣለው በግራ ቀኙ የቀረቡት የቅጣት አስተያየቶች ተመዛዝነው በወንጀል ሕጉ የተመለከቱትን የቅጣት አጣጣል መርሆችን እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሠረት ተደርጎ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአመልካች ላይ የተጣለው የዘጠኝ አመት ጽኑ እስራትና የብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘውም፡፡ ሲጠቃለልም ጉዳዩ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከተዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94074 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ጥፋተኝነት ውሣኔ እና በ26/05/2003 ዓ/ም የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 65555 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሠረት ጸንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 69822

ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ዲ - ኤም - ሲ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረበም

**ተጠሪ**፡- አቶ ኢብራሂም ኢቲሶ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመደበኛ ጉዳይ ችሎትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውል አፈፃጸምና የጉዳት ካሳ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በቱላ ክ/ከተማ ቶሎ ቀበሌ ክልል ባለኝ የይዞታ ቦታዬ ላይ የነበረኝን የድንጋይ ማውጫ ካባ ተከሳሽ ለአንድ ዓመት በኮንትራት ይዞ ለመጠቀም ተስማምቷል፡፡ ተከሳሽ ለካባው ዋጋ ብር 60,000 (ስድሳ ሺህ ብር) በመጀመሪያ የከፈለ ሲሆን ቀሪውን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለመክፈል ከተስማማ በኋላ ቀሪውን ክፍያ ያልከፈለኝ ስለሆነ በውሉ መሠረት ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሽ ድንጋይ ሲያወጣ በአቅራቢያው የነበረውን የእርሻ መሬት ከጥቅም ውጭ በማድረግ ጉዳት አድርሶብኛል፡፡ በይዞታዬ በነበረው የእርሻ መሬት ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ለመክፈል የዕርቅ ስምምነት ውል የተዋዋለ በመሆኑ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ በውሉ መሰረት የካባ ድንጋዩን እንድጠቀም ያላደረገና የውል ግዴታውን ያልፈፀመ በመሆኑ ቀሪውን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ የለብኝም፡፡ የእርሻ መሬቱ ከሳሽ ድንጋይ እንዲወጣበት የፈቀደና የውል ግዴታ የገባበት ነው፡፡ ለደረሰበት ጉዳትም ብር 9000 (ዘጠኝ ሺህ ብር) ለሰጠሁት ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የሚጠይቅበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ ጉዳዩን የያዘው ችሎትም አመልካችና ተጠሪ ከሚከራከሩበት መሬት ድረስ በመሄድ የእርሻ መሬቱ ላይ የደረሰውን ጉዳት ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእርሻ መሬቱ ላይ በነበረው ንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት እንዲገመት በማድረግ ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) ግምት ያለው ንብረት የወደመ መሆኑን በግብርና ባለሞያ ግምት ተሰርቶ ቀርቦለታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ በውሉ መሰረት የካባ ድንጋዩን በማውጣት የተጠቀመ ስለሆነ ብር 40,000

(አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ እንደዚሁም ተከሳሽ የከሳሽን የእርሻ መሬት ከጥቅም ውጭ ያደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተከሳሽ በእርሻ መሬቱ ላይ ላደረሰው ጉዳት ለከሳሽ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) በካሳ መልክ ለመክፈል የተስማማ መሆኑን የሚያረጋግጥ የፅሁፍና የሰው ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑና የተከሳሽ ማስረጃ የከሳሽን ማስረጃ ለማስተባበል የማይችል በመሆኑ ተከሳሽ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስድሳ ሺህ ብር) ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የታጠረ የእርሻ መሬቱ ጉዳት የደረሰበት የድንጋይ ካባውን ለአመልካች ከማከራየቱ በፊት ሆኖ እያለ አመልካች ጉዳት አድርሷል መባሉ ተገቢነት የለውም፡፡ በእርሻ መሬቱ ላይ አመልካች ጉዳት አላደረሰም እንጅ ጉዳት አድርሷል የሚባል ቢሆን የጉዳቱ መጠን ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) አመልካች ለተጠሪ እንድከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የካባ ድንጋይ አመልካች እያወጣ እንዲጠቀም ያደረገው ውል የህገመንግስቱ አንቀፅ 43(3)ን የሚጥስ በመሆኑ ውሉ ይፈፀምልኝ በማለት ሊጠይቅ አይችልም፡፡ ተጠሪ ብር 8000 (ስምንት ሺህ ብር) መቀበሉን ባልካደበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ገንዘቡን አልተቀበለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ሀምሌ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በእርሻ መሬቱ ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በሰበር ጉዳት አላደረስኩም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) በመሬቱ ላይ የነበሩ ዛፎችና ሌሎች ንብረቶች ግምት ነው፡፡ በጉዳቱ የደረሰብኝን ኪሣራ የሚያጠቃልል አይደለም፡፡ አመልካች ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ለጉዳቱ ካሳ ለመክፈል የተስማማ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርቤያለሁ፡፡ አመልካች ብር 8000 (ስምንት ሺህ ብር) ለተጠሪ አልከፈለም፡፡ የካባው ድንጋይ ጉዳይ የተጠሪና አመልካች መከራከሪያ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪ የድንጋይ ካባ ለማከራየት አይችልም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለተጠሪ የከፈለው በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም ተገድዶ በመሆኑ የሰበር መከራከሪያ አይደለም በማለት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በተጠሪ ይዞታ መሬት ላይ የነበረውን የካባ ድንጋይ አውጥቶ ለመጠቀምና ለዚህም በበኩሉ ለመክፈል ከተስማሙበት ገንዘብ ውስጥ ቀሪውን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?አመልካች በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ ያደረሰው ጉዳት ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሣ ይክፈል በማለት የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የሚገኘውን የካባ ድንጋይ እያወጣ ለአንድ ዓመት ሲጠቀምና ለዚህም ዋጋ ይሆን ዘንድ ለተጠሪ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል ከተጠሪ ጋር ያደረገው ስምምነት ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው ውል ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንደሆነና በገፀምድርም ሆነ በከርሰ ምድር የሚገኝ ሀብት የመንግስትና የህዝብ ንብረት መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የሆነች አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ የካባ ድንጋይ ያለበት መሬት ህጋዊ ባለይዞታ መሆኑና በይዞታው የመጠቀም መብት ያለው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ ተጠሪ በህጋዊ የእርሻ መሬቱ ላይ ያለውን የካባ ድንጋይ የመጠቀም መብት ድንጋዩን እያወጣ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት በውል እስከመሸጥ የሚደርስ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ የተጠሪና የአመልካች ውል መሠረታዊ ጉዳይ የሆነው ለግንባታ ስራ የሚያገለግል የካባ ድንጋይ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ውል የተዋዋሉበት ድንጋይ "የኮንስትራክሽን ማዕድን" እንደሆነ የኮንስትራክሽን ማዕድን ማለት፣ እብነበረድ ግራናይት፣ ባዛልት፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ የሸክላ አፈር የመሣሰሉትና ሌሎች ሚኒስትሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸው ብረት ነክ ያልሆኑ መዕድናትን የሚያጠቃልል ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 ከተሰጠው ትርጓሜ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ በህጋዊ የይዞታ መሬቱ ላይ ያለውን የኮንስትራክሽን ማዕድን በማምረትና ከሌላው ዋጋ እየተቀበለ ለመሸጥ በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት ከክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ወይም ከቢሮው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የፀና ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡

ተጠሪ በህጋዊ መንገድ በያዘው መሬት ላይ የሚገኘውን ለግንባታ ሥራ የሚያገለግል ድንጋይ የመጠቀም መብት ድንጋዩን ለሌላ ሰው በውል ገንዘብ ተቀብሎ ለመሸጥ የሚያስችለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ በህጋዊ ይዞታው ላይ የሚገኘውን የኮንስትራክሽን ማዕድን የሆነውን ድንጋይ የመጠቀም መብት በህግ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠው እስከምን ድረስ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 1 "ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው ሥፍራው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 6 መሠረት የተያዘ ወይም የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር የኮንስትራክሽን ማዕድናት በይዞታው ሥር ከሚገኝ ሥፍራ ያለ ክፍያና ፈቃድ ሣያስፈልገው ለንግድ ሳልሆነ ዓላማ አምርቶ ለመጠቀም ይችላል፡፡ ሆኖም የአዋሳኝ ባለይዞታዎች መሬት ወይም ንብረት አጠቃቀም ማወክ ወይም በእነዚሁ ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም" በማለት በግልፅ ደንግጎታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ተጠሪ በይዞታው የሚገኘውን ድንጋይ ቤት ለመሥራት፣ አጥር ለመገንባትና ለሌሎች ግላዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ያለማንኛውም አካል ፈቃድ አምርቶ ለመጠቀም የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ተጠሪ ከሚመለከተው አካል ሣይፈቀድለት በይዞታው ሥር ያለውን የግንባታ ድንጋይ በውል ሌላ ሰው አውጥቶ እንዲጠቀምበት አሳልፎ መስጠትና የመሸጥ መብት የሌለው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ የፌዴራል መንግስት ባወጣውና የክልል ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን የግንባታ ድንጋይ የማምረትና የመሸጥ ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ ቀሪውን ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) አመልካች የከፈለኝ በመሆኑ እኔና አመልካች ድንጋዩን በተመለከተ ያደረግነው ውል በሰበር የቀረበው ክርክር አካል አይደለም በማለት ሀምሌ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፎ

ባቀረበው መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አግባብነት ባለው የክልሉ የህግ መዕቀፍ መሠረት ሥልጣን ካለው አካል በይዞታ መሬቱ ላይ ያለውን ድንጋይ ለንግድ ተግባር ለማዋል የተፈቀደለት መሆኑን በመግለፅ ያልተከራከረ በመሆኑ የፀና ፈቃድ ሣይኖረው በይዞታ መሬቱ ላይ ይገኝ የነበረውን ድንጋይ አመልካች እያወጣ እንዲጠቀም በውል የሸጠ መሆኑን እንዳመነ የሚያስቆጥረው እንደሆነ ከፍትሐብሄር ሥነሥርአት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ተጠሪ የፀና ፈቃድ ሣይኖረው በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀፅ 36 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) በመተላለፍ በይዞታው ሥር የነበረውን የኮንስትራክሽን መዕድን አመልካች ለአንድ አመት እያወጣ እንዲጠቀምበት የሸጠ መሆኑንና አመልካችም የፀና ፈቃድ ከሌለው ከተጠሪ ጋር የኮንስትራክሽን ማዕድኑን እያወጣ ለመጠቀም ውል በመዋዋል ድንጋዩን በመውሰድ የተጠቀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪና አመልካች የውሉ መሰረታዊ ነገር በማድረግ የተዋዋሉበት የግንባታ ማዕድን የፀና ፈቃድ ሣይኖር የመሸጥና የመግዛት ውለታ በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 53 ንዑስ አንቀፅ 5፣ በደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀፅ 39 እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 353(1)(ለ) በወንጀልነት የሚያስጠይቅ ህገወጥ ተግባር እንደሆነ የድንጋጌዎቹን ይዘት በማገናዘብ ለመለየት ይቻላል፡፡ የአንዲት አገር ህግ ህገወጥ ተግባር በተለይም ወንጀል መሆኑን በግልፅ በመደንገግ ማንኛውም ሰው ድርጊቱን እንዳይፈፅም የከለከለውን ተግባር ለመፈፀም ውል የተዋዋሉ የተስማሙ ሰዎች ውሉ በመሰረታዊ ባህሪውና ሞራላዊ ይዘቱ ህገወጥ የሆነውን ውላቸውን በፍርድ ቤት ውሣኔ በማስገደድ ለማስፈፀም አይችሉም፡፡ ዳኞችም በመሰረታዊ ይዘቱ ሞራላዊ ባህሪው ህገወጥ የሆነ ውል እንዲያስፈፅሙ ያቀረበላቸውን ጥያቄ አንቀበልም ማለት እንደሚችሉ ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1718 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በህገወጥ መንገድ በይዞታው ላይ ያለውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ለመሸጥ ከአመልካች ጋር ያደረገው ውልና አመልካችም የፀና ፈቃድ ከሌለው ተጠሪ በመግዛት የኮንስትራክሽን ማዕድን ለመጠቀም የተዋዋለው ውል በመሰረታዊ ይዘቱ ሞራላዊ ባህሪው ህገወጥ ውል ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ አመልካች በውሉ መሠረት ያልከፈለኝ ገንዘብ በማለት የሚያቀርበውን ጥያቄም ሆነ አመልካች ህገወጥ በሆነው ውል መሠረት ክፍያ ፈፅሜ ተጠሪ የውል ግዴታውን አልፈፀመም በሚል ወይም በሌላ ምክንያት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በህገወጥ ውል የከፈልኩት ክፍያ ይመለስልኝ በማለት የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች በመቀበል የሚመለከቱበትና ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉበት የህግ መሠረት የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1716 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1718 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የፀና ፈቃድ ሣይኖረው የኮንስትራክሽን ማዕድን ለአመልካች ለመሸጥ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገውን ህገወጥ ውል በህግ ፊት ምንም አይነት ውጤትና ተፈፃሚነት የሌለው ሆኖ እያለ እንደ ህጋዊ ውል በመቁጠር አመልካች ለተጠሪ ቀሪውን የማዕድን ዋጋ ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠቱና ውሳኔውንም አመልካችን በማስገደድ ማስፈፀሙ ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን የህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የሀዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው ህገወጥ ውል እንዲፈፀምለት ያቀረበውን ጥያቄ በማስተናገድና በዳኝነት በማየት የሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማረምና ማስተካከል ሲገባው የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

2. ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የኮንስትራክሽን ማዕድን በሚያወጣበት ጊዜ የተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ በነበሩ ንብረቶች ማለትም የሙዝ ተክል፣ የእንሰትና የቡና ተክልና ዋንዛ

ዛፍ፣ የበቆሎ ሰብል ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው የሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በእርሻ መሬቱ ላይ ባሉ ዛፎችና ተክሎች ላይ ብቻ ሣይሆን የእርሻ መሬቱ ላይ ለእርሻ ሥራ አገልግሎት ለመስጠት በማይችል ሁኔታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ጥፋት በሆነ አድራጎት በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ ጉዳት በማድረስ በተጠሪ ላይ ላደረሰው ኪሣራ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ ጉዳት አላደረስኩም በማለት ያቀረበው ክርክር የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በህግ በተሠጠው ሥልጣንና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 272 መሠረት ከቦታው ድረስ በመሄድ ያረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ሰበር ችሎቱ እንዲለውጥ የቀረበና የሰበር ችሎት የህገመንግስቱን አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10ን ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

የካሳውን መጠን በተመለከተ አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) ሆኖ እያለ ከደረሰበት ጉዳት በላይ ካሣ እንድከፍል ተወስኖብኛል በማለት ያቀረበውን ክርክር አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በመርህ ደረጃ ለተጎጂው የሚከፈለው የካሣ መጠን ከደረሰበት ኪሳራ ጋር የተመጣጠነ መሆን እንዳለበት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2992 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይችላል፡፡ አመልካች በፈፀመው ጥፋት የሆነ ድርጊት ተጠሪ ላይ ያደረሰበት የጉዳት መጠን ምን ያህል ነው? የሚለውን ነጥብ ስንመለከተው የግብርና ባለሙያ ተጠሪ በእርሻ መሬቱ ላይ የተከላቸው የሙዝ፣ የቡና፣ የእንሰትና የዋንዛ ዘፍ እንደዚሁም የበቆሎ ሰብል በአመልካች አድራጎት የወደሙ መሆኑን ግምታቸውም ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) እንደሆነ በማረጋገጥ እንዳቀረበ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልፆታል፡፡

ሆኖም አመልካች በተጠሪ ላይ ያደረሰው ጉዳት በመሬቱ ላይ የነበረውን ሀብት ግምት ብቻ አይደለም፡፡ የተጠሪ መሬት የእርሻ ተግባር ለመቀጠል በማያስችል ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ አርሶ አደር ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው የእርሻ ሥራውን በይዞታው ላይ ለመሥራት በማይችልበት ሁኔታ በመሬቱ ላይ ባለው የንብረቱ ግምት ብቻ ሣይሆን የመፈናቀያ ካሣ ሊከፈለው የሚገባ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀፅ 8 እና አንቀፅ 9 ድንጋጌዎች በማመሳሰል ትርጉም በመስጠት ለማገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች ተጠሪ በመሬቱ ላይ የነበረውን አትክልትና ሰብል ግምት ብቻ ሊከፈለው ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በተጠሪ መሬት፣ ሰብልና አትክልት ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሣ ለመክፈል ከተጠሪ ጋር የግልግል ውል የተዋዋለ መሆኑን ውሉን የሚያረጋግጥ የጽሁፍና የሰው ማስረጃ እንደቀረበ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ረገድ የሥር ፍርድቤት ያረጋገጠውን ይህንን ፍሬ ጉዳይ በመያዝ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር ስናገናዝበው አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው የግልግል ውል መሠረት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3312 መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ አመልካች ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በተጠሪ መሬት ላይ ለደረሰው ጉዳት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሳ ይክፈል በማለት የሰጡትን የቅጣት ውሳኔ አፅንተናል፡፡ በሌላ በኩል በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገውን ህገወጥ ውል ምክንያት በማድረግ ተጠሪ አመልካች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍለው ያቀረበውን ክስ ተቀብለው ማየታቸውና መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1.የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሸሽሏል፡፡

2.ተጠሪና አመልካች የኮንስትራክሽን ማዕድን ለመሸጥና ለመግዛት ፈቃድ ሣይኖራቸው ያደረጉት ውል ህገወጥ ውል ነው በማለት ወስነናል፡፡

3.በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው ውል ህገወጥ ውል በመሆኑ ተጠሪም ሆነ አመልካች የውሉን አፈፃፀም ሆነ ከውሉ ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ በፍ/ቤት ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

4.የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ህገወጥ ውል ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ ተቀብለው አመልካች ለተጠሪ ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍል የሰጡት የውሳኔ ክፍል ተሻሽሏል፡፡

5.የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ የነበረውን ንብረትና በእርሻ መሬቱ ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሳ እንዲከፍል የሰጡት የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

6.በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ. 71184

ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ዓሕመድልሃዲ ካህሳይ - ከጠበቃ ወ/ጊዮርጊስ ማሩ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል ዓቃቤ ህግ - በሌሉበት፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁ. 632/2002 በአንቀጽ 16(1) (መ)፣ 18(1) (ሀ)፣ 20(2) እና 40(3) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ተጠሪ በመሰረተው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የክሱም ዝርዝር ተከሳሽ (አመልካች) ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ አውጥቶ ገልፍ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚል ከፍቶ በሚሰራበት ጊዜ የግል ተበዳይ ወ/ሪት ፋኢዛ ይመር ዘገየን በኤጀንሲው ፀሐፊ አማካኝነት ማሟላት የሚገባትን ቅድመ ሁኔታዎች እንድታሟላ ከተደረገች በኂላ በኤጀንሲው በኩል የአየር ቲኬት እና ቪዛ በኢሜል ተልኮላት በአዋጁ መሰረት ውሉን በሚመለከት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ሳያዋውል ሚያዝያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ ባህሬን አገር የላካት በመሆኑ ከተላከችም በኂላ መብቷንና ደህንነቷን መጠበቅ ሲገባው ባለመጠበቁ ተበዳይዋ ለብዙ ስቃይ እንድትጋለጥ በማድረጉ እንዲሁም ተበዳይዋን የስራ ዘመንዋ ሲያልቅ ወይም ሲቋረጥ ወደአገሯ መመለስ ሲገባው ባለመመለሱ ወይም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፈጸመው የህግ መጣስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በክሱ የተጠቀሰውን ድርጊት አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቅድሚያ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ከሰማ በኂላ፣ አመልካች ሊከላከል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም አመልካች እንደክሱ አቀራረብ የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በማስረጃ ተረጋግጧል የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህም አመልካች በብር 8,000 (ስምንት ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የቀረበው የግል ተበዳይ በአመልካች ኤጀንሲ በኩል መሄድዋ ሳይረጋገጥ እንዲሁም በአካል ቀርባ እንግልት እንደደረሰባት ባላስረዳችበት አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ሊመረመር ይገባል ተብሎ ነው፡፡ በመሆኑም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር ከተሰጠው ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው ክስ በዝርዝር እና በግልጽ ፍሬ ነገሮችን ያመለከተ ከመሆኑም በላይ፤ በአመልካች ድርጊት ተጣሱ የተባሉትን የአዋጁ ድንጋጌዎችም እንደዚሁ በዝርዝር ተጠቅሰዋል፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም እንደክሱ ያስረዳሉ ተብለው በዓቃቤ ሕግ የተቆጠሩትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡ በሰማው ማስረጃ ተበዳይ ወደባህሬን የተላከችው በዓቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር በተገለጸው ሁኔታ አመልካች ባመቻቸው መንገድ መሆኑን፣ የግል ተበዳይ ወደ ባህሬን ከሄደች በኋላ ችግር እንዳጋጠማት ሲነገረው እና ወደሀገርዋ እንዲያስመጣት ሲጠየቅ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን፣በመጨረሻም የግል ተበዳይ በራሷ ወጪ ተሳፍራ ወደ ሀገሯ ብትመጣም፤ ጤንነቷ ግን ደህና እንዳልሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ በዝርዝር እና በግልጽ ማመልከቱን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የግል ተበዳይ ወደውጪ ሀገር የተላከችው ከእሱ እውቀት (እውቅና) ውጪ በኤጀንሲው ፀሐፊ በኩል መሆኑን እንደሚያስረዳ በመግለፅ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት የመከላከያ ማስረጃ ማሰማቱን እና ፍ/ቤቱ ግን የተሰማው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻለም ለማለት ክብደት እንዳልሰጠው ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው አመልካች በዓቃቤ ሕግ በዝርዝር የተመለከተውን ፍሬ ነገር ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመመስረት ማስረጃዎን ሰምቷል፡፡ በዚህ ሂደት የሰማችውን ማስረጃዎችም መዝኖ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች ግን አሁንም የግል ተበዳይን ወደ ውጭ ሀገር ስለመላኩ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም በማለት ነው እየተከራከረ ያለው፡፡ ጭብጥ ለማስያዝ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመርለት የጠየቀውም ይህን የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ የግል ተበዳይ ቀርባ እስካልመሰከረችብኝ ድረስ እንግልት ደርሶባታል ተብሎ ጥፋተኛ መባል የለብኝም የሚል ክርክርም አንስቷል፡፡ እንደሚታወቀው ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራትም/የማንጠርም/ ሆነ ማስረጃውን በመመዘን ድምዳሜ ላይ የመድረስ ሥልጣን በሕጉ አልተሰጠውም፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(30(ሀ) እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው ለሰበር ችሎቱ የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን የክርክር ሥርዓቱን ጨርሶ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የተፈጸመውን መሠረታዊ የህግ ስህተት በማረም የተወሰነ ነው፡፡ በመሆኑም ድርጊቱን ለመፈጸሜ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ነው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈብኝ የሚለውን መነሻ በማድረግ አመልካች ያስያዘውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የምንመረምርበት አግባብ የለም፡፡ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው እስካልመሰከረ በሌሎች ማስረጃዎች የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ማረጋገጥ አይቻልም የሚል የህግ ፍልስፍናም ሆነ ሕግ ስለሌለም የግል ተበዳይ ቀርባ ስለደረሰባት እንግልት ሳታስረዳ ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም የሚለው የአመልካች መከራከሪያም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው የምንልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.95035 ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 59774 ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ/ሥ-ሥ-ሕ-ቁ. 195(2)(ለ) (2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ. 60542

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ተክለድንግል ገ/ሚካኤል

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ም/ፀ/ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌሎች ስምንት ሰዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች የተከሰሱት በአንድ መዝገብ በተከፈተ ክስ ሲሆን የክሱ ይዘትም አመልካቹ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1ሀ)፣33 እና 407(1(ሀ)(ሐ))፣(2) እና (3) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘትና በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በስር ፍርድ ቤት ቀደም ሲል አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተመድቦ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በስራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን የአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን ከስራ ሲታገድ በሲዲ በመገልበጥና በኮምፒዩተር በመታገዝ በከተማው ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎችን በመለየትና ቀደም ሲል በነበረው ስርዓት ለማኅበራት ይፈቀድ የነበረውን የቤቶች ፕላን ቶፖሎጂ በወቅቱ በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሚሰራባቸውን የቤቶች አይነት በፕላን በማዘጋጀት ሕጋዊ ያልሆኑ ማህበራትን ከሕግ ውጪ በማደራጀትና ቦታን በመስጠት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በአንደኛ ተራ ቁጥር ተከሳሽ ከነበረው ከአቶ በሃይሉ ለማ ድንቁ ጋር በጥቅም በመመሳጠር በሐሰትና በተቀነባበረ ዘዴ "ሻላ" የሚባል ሃሰተኛ የመኖሪያ ቤት የሕብረት ስራ ማህበር እንዲቋቋም አድርጎ በሀሰተኛ መንገድ የተዘጋጀው የማህበሩን ፋይል ከስር ሁለተኛ ተከሳሽ(ወ/ሮ ደሃብ ገ/ሕይወት) ጋር የጥቅም ግንኙነት በመፍጠር በ1998 ዓ/ም የካ ክፍለ ከተማ ማህበር ማደራጃ ፅ/ቤት ውስጥ እንዲገባ በማስደረግና የማህበሩ አባላትም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ማህበሩን ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብና በሁለተኛ ተከሳሽ በኩል ሃሰተኛውን ማህበር ሕጋዊ አስመስሎ እንዲነገር አድርጎ 248 የማህበሩ አባላት በሕገ ወጥ መንገድ መሬት እንዲያገኙ በማድረግና ቦጋለ የተባለውን ሐሰተኛ እና ሕገ ወጥ ማህበር ፋይልም ከ1ኛ ተከሳሽ በመቀበል ለሁለተኛ ተከሳሽ ሰጥቶ ወደ ክፍለ ከተማው ማህበራት ማደረጃ ፅ/ቤት እንዲገባ አድርጎ በሁለቱም ሐሰተኛ ማህበራት ሕገ ወጥ ጥቅም በማግኘት፣በማስገኘትና በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት በማድረስ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡ጉዳዩ አግባብነት ባለው ስነ ስነ ሥርአት ተመርቶ አመልካች ክሱን በመካድ በመከራከራቸውም አቃቤ

ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተመርምረውም አመልካች "ሻላ" የሚባል የመኖሪያ ቤት ሕብረት ማህበር ሊቀመንበር ለመሆናቸው አቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ማስረዳቱ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልፆ ይህንኑ እንዲከላከሉ ተደርጎ አመልካች በበኩላቸው አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎችን ለመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ህግን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ ያልቻሉ መሆኑን በመግለፅ በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) መሰረት ዝቅ አድርጎ አመልካችን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ))፣33 እና 407(1(ሀ)) ስር ጥፋተኛ አድርጎአል፡፡ከዚኅም በኂላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በሁዋላ አመልካችን በአምስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 5,000.00(አምስት ሺኅ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 18 ቀን 2003 ዓ/ም በጻፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ በሙስና መከሰሳቸው ያላግባብ መሆኑን፣በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ነጻ በተባሉበት ጉዳይም ተመልሶ ጥፋተኛ መባላቸው ስነ ሥርኣቱን ያልጠበቀ መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እንዲቀርብና ፊርማው እንዲመረመር የተጠየቀውን የሰነድ ማስረጃ በፎረንሲክ ሳያስመረምር አልፎ ውሳኔ መስጠቱም የማስረጃ አቀራረቡና አመዛዘኑ ሥርዓት ሕጉን ያልጠበቀ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ዘርዝርው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የቤት ስራ ማህበር ሊቀመንበር ናቸው ተብሎ ጥፋተኛ መደረጋቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩላቸው መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ ከጠቀሷቸው የቅሬታ ነጥቦች መካከል አንዱ ተጠሪ ክሱን በማስረጃ አለማስደገፉንና አመልካች እንዲመረመርላቸው የጠየቁት ሰነድ በፎረንሲክ ሳይመረመር እንዲሁም ለተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች ቃል ክብደት ሳይሰጥ መታለፉን የሚመለከት ነው፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ በሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት ያልተያዘ ከመሆኑም በላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃ በማጣራትና በመመዘን የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎችን የአቃቤን ህግን ማስረጃዎችን የማስተባበል ብቃት የላቸውም በሚል ያለፉት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ ይህ ችሎት የሚመረምረው ሁኖ ስላላገኘው አልፈነዋል፡፡

ሌላው አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ በሙስና ወንጀል መከሰሳቸው አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7 ድንጋጌን በግልፅ የሚጻረር ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 33 ድንጋጌን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የተከሰሱት የመንግስት ሰራተኞቾ ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ከመሆኑም በላይ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 33 መሰረት አንድ ሰው የመንግስት ሰራተኛ ባይሆንም በሙሉ ፈቃዱና እውቀቱ የሙስና ወንጀል ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ከተረጋገጠ በሙስና የሚከሰስበት አግባብ መኖሩ የተደነገገ ነውና፡፡

በዚህ ችሎት እንዲታይ የተያዘውና አመልካች በመከራከሪያነት ያቀረቡት ሌላው ነጥብ አመልካች የቤት ማህበሩ ሊቀመንበር ናቸው በማለት ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የተከሰሱት ሕጋዊ ያልሆኑ ማህበራትን የሊቀመንበርነት ስልጣን አለኝ በማለት አደራጅተው ለማህበሩ አባለት ያላግባብ ቦታ እንዲሰጥ አድርገዋል፣በዚህም በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ሲሆን የማህበራቱ ሕጋዊ አለመሆንና ማህበራቱ ሲደራጁ እንዲሁም ቦታውን ሲወስዱ አመልካች የነበራቸው ሚና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡በመሆኑም የቤቱ ማህበራት ሕጋዊ ያለመሆናቸውና የተደራጁትም አመልካች በሊቀመንበርነት በነበራቸው ሚና ጭምር መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች በወንጀል የማይጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ሌላው አመልካች በዚህ ድርጊታቸው ነጻ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 የተሰጠ ብይን የሌለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን የተመለከትን በመሆኑ በዚህ ረገድ የተነሳው ቅሬታም እውነትነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡በአጠቃላይ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 60587 ሚያዚያ 04 እና 14 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 56628 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195((2(ለ-2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ ያስፈፅም ዘንድ ውሳኔው መፅናቱ ለማ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት የዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 64612

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1ኛ/ ሐሰን አማን መሐመድ } ጠበቃ ሚሊዮን አበራ

2ኛ/ ብርሃን መኰንን ደሣለኝ

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ፀረ-ሙስና ኮሚሽን- ዐቃቤ ሕግ- ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በተጠሪ መስሪያ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቁና ክስ ሊመሰረትባቸው የሚገባቸውን የወንጀል ድርጊቶችን እንዲሁም በተጠሪ መስሪያ ቤት ስልጣን ስር የማይወድቅ ጉዳይ በኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ ክስ ሊመሰረት የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ የመሰረተው ክስ በሁለት ምድብ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክስ፡- የወ/ሕግ አንቀጽ 32/ሀ/ እና 379/1ሀ/ን ጠቅሶ አመልካቾች በሌሎች ሀሰተኛ ሰው ስም የተዘጋጀ የጅምላ ንግድ ፈቃድ አስመስለው አዘጋጅተው ለጨረታ አቀርበው ተወዳድረዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ክስ ደግሞ የወ/ሕግ አንቀጽ 32/1ሀ/እና 696/ሐ/ የተመለከተውን ተላልፈው በ1ኛው ክስ ላይ የተጠቀሰውን ሰነድ ሐሰተኛነቱን ደብቀው ለጨረታ በማቅረብ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽኑን አታለው በመንግሥት ላይ የብር 707,805.00 ጉዳት በማድረሣቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአቃቤ ሕጉን ክሶች ለአመልካቾች አንብቦላቸው እንዲረዱት ከአደረገ በሁዋላ አመልካቾች በክሱ ላይ ተቃውሞ በማቅረባቸው ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሾች ሁሉም በግል የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው የመንግሥት ሠራተኛ ተጣምሮ ባልተከሰሰበት ሁኔታ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ ክስ ለመመስረት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 404/3/ አንፃር ስልጣን የለውም በማለት መዝገቡን በአብላጫ ድምጽ ዘግቶ ተከሣሾች ከእስር እንዲለቀቁ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ማቅረቡ ሕጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ከመንግሥት ሠራተኞች ጋር

ሣያጣምር በግለሰቦች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችልበት የሕግ አግባብ ሳይኖር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ብይን መሻሩ ያላግባብ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ የመንግስት ሰራተኞች ባይሆኑም የተጠሪ መስሪያ ቤት የማስተናገድ ስልጣን አለው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ በሰጠው መልስ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ ያቀረበው ክሱን ለማቅረብ በተሰጠን ስልጣን ነው፣በተለይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 የሙስና ወንጀል መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 404/4/ ላይ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ይህም ድንጋጌ የመንግሥት ሠራተኛን ብቻ የሚመለከት አይደለም፣አንቀጽ 379 መሠረት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 375 እስከ 378 የተደነገገውን በአንቀጽ 375 ደግሞ "ማንም ሰው…." ብሎ ነው የሚጀምረው፣ ስለሆነም አንቀጽ 379 ጠቅሰን ክስ ለማቅረብ ሥልጣን ያለን ሲሆን አንቀጽ 696/ሐ/ አጣምረን የከሰስነው ድርጊቱ በ1ኛ ክስ ከጠቀስነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 ጋር ተያይዞ የተፈፀመ በመሆኑ በማስረጃም ሆነ በውሣኔ አሰጣጥ የሚረዳ በመሆኑ እንጂ 696/ሐ/ በአመልካቾች ላይ የጠቀስነው ስልጣን አለን በሚል አይደለም፣ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ የወ/ሕግ አንቀጽ 379 በመጥቀስ በአመልካቾች ላይ ክስ መመሥረት ይችላል በማለት መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የስር ፍ/ቤት አመልካቾችን የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ከአቀረበባቸው ክስ መዝገቡን ዘግቶ ያሰናበታቸው በወ/ሕግ አንቀጽ 404/3/ መሠረት ከመንግሥት ሠራተኛ ውጭ የሆነ ሰው ከመንግሥት ሠራተኛ ጋር ተጣምሮ ካልተከሰሰ ወይም ለመንግሥት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ከሰጠ ወይም ለመስጠት ከተስማማ ብቻ በመሆኑ እና ተከሣሾች የመንግሥት ሠራተኞች ስላልሆኑ ወይም ከመንግሥት ሠራተኛ ጋር ተጣምረው ባልተከሰሱበት ሁኔታ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ክስ ሊያቀርብባቸው አይችልም በሚል መሆኑንና ይህንን የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያልተቀበለው ደግሞ በመንግስት ሰራተኛ ባልሆነ ሰውም የኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ የሙስና ክስ ለማቅረብ ሥልጣን አለው፣የሙስና ድርጊት ያልሆነውን የወንጀል ድርጊትም ከሙስና ወንጀል ጋር አጣምሮ ክስ ለማቅረብ የሚችልበት የሕግ አግባብ አለ በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 404/4/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው መንግሥታዊ ወይም ወታደራዊ ሠነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት እንደሙስና ወንጀል እንደሚቆጠር መደንገጉን ነው፡፡ይህን እንደሙስና ወንጀል የተደነገገውን ድርጊት ሊፈጽመው የሚችለው ማን እንደሆነ ለማወቅ ደግሞ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል በአንቀጽ 375 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ማየትን የግድ ይላል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ በሕዝብ ጥቅሞችና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚገዛው አራተኛ መፅሐፍ፣በሕዝብ አመኔታ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ርዕሥ ስር፣ሐሰተኛ ሰነዶችን መፍጠር፣ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ማጥፋትን በሚመለከት ምዕራፍ ስር የተቀመጡ ሆነው የአንቀጽ 375 ድንጋጌ በግዙፍ የሚፈጸም ሐሰት በሚል ርዕስ የተቀረጸ ሁኖ

የመጀመሪያው ፓራግራፍ ማንም ሰው በሚል ሐረግ የሚጀመር ሁኖ በንዑስ ድንጋጌዎቹ ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች መኖራቸው ሲረጋገጥ የወንጀል ተጠያቂነት መኖሩን በግልጽ ያሳያል፡፡ በአንቀጽ 379 ድንጋጌ በንዑስ አንቀፅ አንድ ሥር ከተመለከተው ይዘትም የመንግሥት ሠራተኛ የሆነውን እና ያልሆነውን ማንኛውንም ሰው የሚመለከት መሆኑና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር ያሰፈረው ደግሞ የመንግሥት ሠራተኛን ብቻ የሚመለከት ስለመሆኑ መረዳት የሚቻለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በአንቀጽ 379(2) ስር የሠፈረው ከመንግሥት ሠነዶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሠነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደ ሐሰት መለወጥን ተግባር ያከናወነውን የመንግሥት ሠራተኛ በግልጽ መለየቱ በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከተው ደግሞ ሰነዱ የመንግሥት ሆኖ አስመስሎ ያዘጋጀው ወይም የለወጠው ማንኛውም ሰው ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ አመልካቾች አስመስለው አዘጋጁት የተባለው የንግድ ፈቃድ ማረጋገጫ መንግሥታዊ ሰነድን እንደመሆኑ ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩበት ወንጀልም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 "ን" የሚመለከት ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 "ን" የሚሸፍን ድርጊት ደግሞ የሙስና ወንጀል ነው ተብሎ በሕግ ተደንግጓል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በተሻሻለው የፌዴራል የስነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 መሰረት የሙስና ወንጀሎችን የመመርመና የመክሰስ ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራሉ ሥነ ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የቀረበውን 1ኛ የወንጀል ክስ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ የመክሰስ ስልጣን አለው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን መሻሩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

2ኛውን ክስ በተመለከተ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ክስ የመሠረተው ስልጣን አለኝ ብሎ ሣይሆን ከ1ኛው ክስ ጋር ግንኙነት ያለውና ማስረጃውም የሁለቱ አንድ ነው በሚል እንደሆነ በስር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከተካሄደው ክርክር ተረድተናል፡፡ ኮሚሽኑ በዚህ መልኩ የሱ ስልጣን ያልሆኑ ነገር ግን ከመሠረተው የሙስና ወንጀሎች ጋር አጣምሮ ክስ ማቅረቡ ደግሞ ከወንጀል ሥነ ስርዓት ሕግ ዓላማጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነሥርአት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ክስ የሚመራበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ይሁን እንጂ አዋጁ የኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ በእራሱ ስልጣን ስር የማይወድቅ ነገር ግን የሙስና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ከዚሁ ጋር አንድ ላይ መክሰስ ያለበትን የወንጀል ድርጊት አንድ ላይ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ በግልፅ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ ሆኖም ተጠቃሹ አዋጅ በአንቀጽ 55 ስር የወንጀል ሥነሥርአት ህግ፣ የፍትሀ ብሄር ሥነሥርአት ህግ፣ የወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በሚል ደንግጎ በአዋጁ አንቀፅ 58 ስር **የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎችን ለይቶ ሲያስቀምጥ** የጸረሙስና የልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 236/1993 እንደተሻሻለ መሻሩን፣ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ለማቅረብ ስልጣን ያለው አካል በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን ጋር አንድ ላይ የሚታይና ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ስልጣኑ ከሆነው ጉዳይ ጋር ስልጣኑ ያልሆነውን ጉዳይ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ የሚደነግጉ የወንጀል ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት ከሙስና ወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ የቀረበውንም የወንጀል ክስ የማየት ስልጣን እስካለው

ድረስ ሁሉንም ክሶች አጣምሮ ቢያይ የፍ/ቤትን፣ የከሣሽን እና የምስክሮችንም ጊዜና ጉልበት የሚቆጥብ በመሆኑ የሚደገፍ ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 110 ድንጋጌ ሁለተኛው ፓራግራፍ ይዘትና መንፈስ ጋር አጣምረን ስናነበው የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ዋናውና ቁልፍ ነገር የጉዳዩ መታየት በትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጡ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አሉታዊ ውጤት የሌለ መሆኑ መረጋገጡ ላይ ነው፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተዘረዘረጉት ሕጋዊ ምክንያቶች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማቅረብ ሥልጣን አለው  በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን በመሻር የተዘጋው መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ እንዲቀጥል ሲል የሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60134 ታህሳስ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2ሀ/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡን ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 66856

የመጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ውድማ አበጀ - አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ዐ/ሕግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር በሙከራ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው መቼ፤ እንዴት ነው? የሚለውን ነጥብ በዚህ የወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች ጋር በማናገዘብ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ በክልሉ የጉራጌ ዞን ዐ/ሕግ በአሁኑ አመልካችና በግብረ-አበሮቹ ላይ ሦስቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1/ /ሀ/፣ 27/1/ እና 671/1/ለ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በጅማ ወለኔ ቀበሌ የሚመላለሱትን ተሽከርካሪዎች ለመዝረፍ የጦር መሣሪያ፣ ጭንብል፣ የእጅ ባትሪ፣ ጩቤ በመያዝ ከመጋቢት 07 ቀን እስከ መጋቢት 08 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ተንቀሳቅሰው ጠብቀው ተሽከርካሪ በማጣታቸው ሲመለሱ በተደረገው ጥቆማ መነሻ በፀጥታ ኃይሎች ስለተያዙ በፈፀሙት ከባድ የውንብድና ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበው ክስ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በተከሳሽነቱ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡

በማስረጃነትም የሰው ማስረጃና ተከሳሾች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 27 እና 35 መሠረት በምርመራ ጊዜ ለመርማሪ ፖሊስ እና በፍ/ቤት የሰጡት ቃል ቀርቧል፡፡ በሰው ማስረጃው የተረጋገጠው መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከአንድ የመኪና አሽከርካሪ ሽፍቶች ለመዝረፍ ተሰማርተዋል የሚል ጥቆማ አግኝቼ ወዲያውኑ ስከታተል ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ተሽከርካሪ በማስቆም በተደረገው ጥብቅ ክትትል እነዚህ ሦስት ሰዎች መታወቂያ ሲጠየቁ የላቸውም፡፡ በግንባታ ሥራ ተሰማርተን የግንባታ ቁሳቁስ እጥረት ስለአጋጠመ ወደ መኖሪያችን እየሄድን ነው አሉ፡፡ ዕቃቸው ሲፈተሽ ግን አንድ የጦር መሣሪያ፣ ጩቤ፣ ጭንብል ተገኝቶባቸዋል የሚል ነው፡፡ እንዲሁም በምርመራ ጊዜ በሰጡት የእምነት ቃልም ለዘረፋ ተስማምተው አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አድርገው ያመቸናል ብለው ወደ አሰቡበት ቦታ በመሄድ ጫካ ውስጥ ከአደሩ በኋላ ባገኙት

መኪና ተሳፍረው ሲመለሱ ከያዙት የዘረፋ ቁሳቁስ ጋር በፖሊስ ቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የዐ/ሕግ ማስረጃ እና ተከሳሾች እንከላከላለን ሲሉ ያቀረቡትን ማስረጃ በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ እንደ ክሱ አቀራረብ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ ከሦስተኛው ተከሳሽ በስተቀር በአሁን አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ በነበረው ሌላ ግብረአበር ላይ የቀረበውን የወንጀል ጥፋተኝነት እና ቅጣት ሪከርድ መነሻ በማድረግ በአሁን አመልካች ላይ የ22 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ጥሏል፡፡

ከዚህም ቀደም ብለው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተባለበት ፅኑ እስራት የ10 ዓመቱን በእስር ሊጨርስ በሚል በአመክሮ መለቀቁን መነሻ በማድረግ የተጣለ ቅጣት እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ በደረጃው ላሉ የበላይ ፍ/ቤቶች እንዲታረም ቅሬታ ቢያቀርብም ቅሬታው ውድቅ በመደረጉ ለመጨረሻ ጊዜ ጉዳዩን በዚህ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ክርክር ያደረጉበት ነጥብ ይህ አመልካች እና ሌሎች ግብረ-አበሮች የፈፀሙት ተግባር በሙከራ ወንጀል ሥር ሊወድቅ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ነው፡፡ እኛም በዚሁ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ቅሬታ ከሥር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በ1997 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እንደተደነገገው ማንም ሰው አስቦ ወንጀሉን ማድረግ ጀምሮ የወንጀሉን ድርጊት እስከመጨረሻው ባይከታተልም ወይም ለመከታተል ባይቻልም የወንጀል ድርጊቱ እንዲፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላስገኘ ቢሆንም የሙከራ ወንጀሉን እንደፈፀመ እንደሚያስቆጥረው ተመልክቷል፡፡

በዚህም ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ከድርጊቱ በፊት ተከሳሾች ሁልጊዜ የዘረፋ ወንጀል በሚፈፀምበት ጫካ መግባታቸው፤ ይህን በተመለከተ በሰው ጥቆማ አማካኝነት በፀጥታ ኃይሎች በተደረገው ክትትል ተሳፍረውበት ከነበረው መኪና ከጦር መሣሪያ፣ ጩቤና ጭንብል ጋር መያዛቸው፤ እንዲሁም በእራሳቸው የእምነት ቃል እንደተረጋገጠው ለዘረፋ ወንጀል አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አጠናቀው ከዚሁ ጫካ ውስጥ ሲጠባበቁ አድረው በማግስቱ በመኪና ተሳፍረው ሲሄዱ ለዘረፋ ተግባር ሲሉ ከያዙት ቁሳቁስ ጋር መያዛቸው ሁሉ ሲታይ አመልካችና ግብረ-አበሮቹ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትለው ነገር ግን የሚዘረፍ ነገር ባለማግኘታቸው ውጤቱን ያላገኙ መሆኑን አስረጂ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በአመልካችና በግብረ-አበሮቹ በኩል የተፈፀመው ተግባር በእራሱ የዘረፋ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደ ኋላ ከማይመለሱበት ደረጃ ደርሰው የነበረ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቱ ይህንን ሁሉ በማገናዘብ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ አመልካች ተላልፎታል ተብሎ በተጠቀሰው ሕግ አነጋገር መሠረት ሆኖ የተገኘ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 33619 በቀን 12/06/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡ አመልካች ይህንኑ እንዲያውቀዉ ውጤቱ ባለበት ማ/ቤት ይገለፅለት፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 73953

መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካቾች፡- ከፋለ ሰፈነ - ጉዳይ ተከታታይ አስቀናው ከፋለ ቀረበ

ተጠሪ፡- የአማራ ክልል ዓ/ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ደምቢያ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ በአመልካች ላይ የተመሰረተው ክስ ነው፡፡ አመልካች የተከሰሱት በ1996 ዓ/ም በወጣው የወ/መ/ሕግ አንቀጽ 438 ስር የተመለከተውን በመተለለፍ ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕግ በተፈቀደው ውጭ አስቦ መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ/ም ደምቢያ ወረዳ ጫሂት ከተማ ላይ ምክትል ሳጅን ሙሉጉጃም ሙለአለም የተባለችው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ሆና በመስራት ላይ እንዳለች አመልካች የታርጋ ቁጥር ኮድ 3-28371 አ.አ የሆነች አይሱዚ የጭነት መኪና እያሽከረከረ ወደ ጎንደር አቅጣጫ ሲመጣ በተደረገ ቁጥጥር መንጃ ፈቃድ ሳይዝ በማሽከርከር በሕግ አግባብ ክስ አዘጋጅታ ስትሰጠው የክስ ቻርጅ አልቀበልም በማለት እምቢተኛ በመሆን በድጋሚ ሚያዚያ 11 ቀን 2003 ዓ/ም ደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ 01 ቀበሌ በተደረገው የትራፊክ ደንብ መተላለፍ የክስ ቻርጅ የያዘ እንዲወስድ ቢጠየቅም እምቢተኛ በመሆኑ የመንግስት ስራን የማሰናከልና የመተባበር ግዴታ መጣስ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በሚል ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካች እንዲከላከል ተደርጎ የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ምስክሮችን ከአሰማ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች መከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕጉን ማስረጃ ለማስተባበል ብቃቱ የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ውድቅ አድርጐ አመልካችን በአቃቤ ሕጉ ተጠቅሶ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ አመት ከስድስት ወር እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሲጽና የቅጣት ውሣኔው ግን ተሻሽሎ አመልካች በአንድ አመት እስራት እንዲቀጣ ተደርጓል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ሳይረጋገጥና ተረጋግጧል ቢባል እንኳ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 438 ስር የማይሸፈን ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጡት ያላግባብ ነው በማለት ውሣኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 438 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት

ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው የትራፊክ ተቀጣጣሪ ፖሊስ ሆኖ በመስራት ላይ የነበረችው የትራፊክ ፖሊስ ጽ/ቤት ባልደረባ አመልካች የታርጋ ቁጥር ኮድ 3-28371 አ.አ የሆነች አይሱዚ የጭነት መኪና እያሽከረከረ ወደ ጎንደር አቅጣጫ ሲመጣ በተደረገ ቁጥጥር መንጃ ፈቃድ ሳይዝ በማሽከረከር በሕግ አግባብ ክስ አዘጋጅታ ስትሰጠው የክስ ቻርጅ አልቀበልም በማለት በተለያዩ ሁለት ቀናት እምቢተኛ በመሆን የመንግስት ስራን የማሰናከልና የመተባበር ግዴታ መጣስ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በሚል ሲሆን አመልካች ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ምስክሮች ቀርበው በመሰማታቸውና አመልካችም የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት የመከላከያ ማስረጃዎችን ያሰማ ቢሆን የአቃቤ ህግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያለመቻሉ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መገለጾን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሥር ፍ/ቤት አመልካቾችን ለድርጊቱ ኃላፊነት ያደረጉት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በመሰማትና ቃላቸው ለጉዳዩ አግባብነት፤ ክብደት ያለው መሆኑን በማመን አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎች እንዲያስተባብል የመከላከል መብቱን በመጠበቅ የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎችን ከሰማ በሁዋላ የመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል የማይችሉ መሆኑን ዘርዝሮ ቃላቸውን ውድቅ በማድረግ መሆኑን ከውሣኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም አመልካች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ክብደትን በተመለከተ ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ለዚህ ችሎት በአንቀጽ 80 (3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰርት ለዚህ ሰበር ችሎት ከተሰጠው መሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ስር የማይወድቅ ወይም የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ በመሆኑ የምንቀበለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች የትራፊክ ፖሊስ ባልደረባ የትራፊክ ደንብ መተላለፋቸውን በመግለጽ የሰጠችውን ክስ አልቀበልም በማለት እምቢተኛ መሆኑ መረጋገጡን ይዘን ይህ አድራጐት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 438 ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው የተጠቃሹ ድንጋጌ አርእስት "የመንግስት ስራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ" በሚል የተቀመጠ ሁኖ ድንጌው ለሌሎች ሰዎች በመንግስት ስራ ላይ የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች በሚል "ምዕራፍ ሶስት" ስር የሚገኝ ሲሆን ይህ ምዕራፍ የሚያሳየውን ሌሎች ሰዎች ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች በሚደነግገው ክፍል ሁለት ስር ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ የድንጋጌው ይዘት ሲታይ ማንም ሰው ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕግ በተፈቀደው ወይም በፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዘዝ መሰረት በመንግስት ሰራተኛ ሲጠየቅ ቀርቦ ለማስረዳት፤ ተገቢውን መልስ ለመስጠት፤ ሰነዶችን ለማቅርብ ወይም ለማስመርመር ወይም ልዩ ልዩ ቤቶች፣ ቦታዎችን ወይም ነገሮችን ለማስፈተሽ እምቢተኛ ከሆነ በጠቅላላው ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የመንግስት ስራ ያደናቀፈ እንደሆነ ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡ ከድንጋጌው ውስጥ "…… በሕግ በተፈቀደው….." እና "…… በማናቸውም ሌላ መንገድ……." የሚሉት ሐረጎች ሲታዩ የአመልካች አድራጐትም በዚሁ ድንጋጌ የሚሸፈን መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የትራፊክ ፖሊስ የትራፊክ ደንብን የመቆጣጠርና የማስፈፀም ስልጣን በህግ ተለይቶ የተሰጠው ሲሆን ከዚሁ ስራ ጋር በተያያዘ ኃላፊነቱንና

ተግባሩን በመወጣት ሂደት ማንም ሰው ሊያስናክለው የማይገባ፣ ይልቁንም የመተባበር ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ነውና፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(-2)) መሰርት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. ውሣኔው የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት የመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 73264

ሚያዝያ 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልስልጣን-አቃቤ ሕግ ትዝታ ዘውዴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ አልፈድል አሻፊ
2. አቶ ሰከርያ የሱፍ
3. አቶ ኢስማኤል ሐሰን

} ጠበቃ መሐመድ ከድር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ለማቅረብ በሕጉ ተለይቶ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ የተመለከተ ነው፡፡ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1ሀ) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ሳይፈጸም አስራ አምስት የቀንድ ከብቶችን ወደ ሱዳን ለማስወጣት ሲሉ ሰባት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው መያዛቸውን ገልፆ አንደኛ ተጠሪ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ በግብረ አበርነት የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ የመሰረተባቸው ሲሆን ተጠሪዎች ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉን ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ከአሰማ በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ አላስረዳም በማለት ተጠሪዎችን ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 መሰረት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኙን ለቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት አቅርቦ ጉዳዩ ተጠሪዎችን በመልስ ሰጪነት ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ አቀራረቡ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 187(2) ስር የተመለከተውን የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ጠብቆ ያልቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ጊዜውን ለመቁጠር መነሻ ያደረገበት ጊዜ ትክክለኛ ያለመሆኑንና ይግባኙን ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ.ም ግልባጩን በመቀበል ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበ ሆኖ እያለ የይግባኝ ግልባጩ ለአመልካች የደረሰው ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ አልፏል ተብሎ የይግባኝ መዝገቡ መዘጋቱ ሥነ

ሥርዓቱን ያልተከተለ መሆኑን እንዲሁም በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ያለመሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው ሊለወጥ ይገባል ሲል መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካች የይግባኝ አቤቱታው በወቅቱ ያልቀረበ ነው ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯናል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ በጭብጥነት የተያዘው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የይግባኝ ጊዜ ማቅረቢያ ሳይጠብቅ ይግባኙን አቅርቧል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቶ አመልካች የይግባኝ መዝገቡ ተገልብጦ እንዲሰጠው ውሳኔ ከተሰጠ በ2ኛው ቀን ማለትም ግንቦት 11 ቀን 2003 ዓ/ም መጠየቁን፣ ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም ደግሞ የይግባኝ መዝገቡን ግልባጩን መቀበሉንና በዚህ ቀን ሸኚ የተሰጠው መሆኑና አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም ይግባኝ ማቅረቡ መረጋገጡን መርምሮ እነዚህ ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ስር የተመለከተው የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ሲሰላ አመልካች ይግባኙን ያቀረበው የሰባት ቀናት ጊዜ ከአለፈ በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡ አመልካች ይህንኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድምዳሜ የተሳሳተ ነው በማለት በዚህ የሰበር ችሎት የሚከራከረው ይግባኙ ተገልብጦ የተሰጠው ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም ሳይሆን ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ/ም ስለመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነበረው የቃል ክርክር ጊዜ ተረጋግጧል፣ ማስረጃም ቀርቧል በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ ይህ የአመልካች ክርክር እውነትነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍሬ ነገር የፈፀመው ስህተት የለም በማለት ለዚህ ችሎት በጽሁፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ድንጋጌ የውሳኔው ግልባጭ የተሰጠው ሰው ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኙን ማቅረብ ያለበት ግልባጩ በተሰጠው በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ስለመሆኑ አከራካሪ የሆነ የሕግ ጥያቄ አይደለም፡፡ አከራካሪውና በሰበር ችሎቱ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ በአመልካች ጥብቅ ክርክር እየቀረበ ያለው የይግባኝ መዝገቡ ግልባጭ ለአመልካች የደረሰው ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ/ም እንጂ ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የይግባኝ መዝገብ ግልባጩ የደረሰው ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም ሆኖ በዚሁ ቀን በተጻፈለት ሸኚ ደብዳቤ መሰረት ይግባኙ ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ/ም መድረሱን አረጋገጠ እንጂ አመልካች እንደሚለው በቃል ክርክር ወቅት ለአመልካች ይግባኙ የተሰጠው ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ/ም ስለመሆኑና ማስረጃም በስር ፍ/ቤት መዝገብ መቅረቡ አለመረጋገጡን በውሳኔው ላይ ገልፆ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ደምድሟል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን

መመዘን ሳይሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች በሕጉ አግባብ የደረሱበትን ድምዳሜ እንደ እውነት በመቀበል በሕጉ አተረጓጐም ወይም አተገባበር ረገድ መሰረታዊ የሆነ ስህተት ተፈፅሞ ከሆነ ይህንኑ ማረም ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ለጉዳዩ ቀጥተኛ የሆነ ተፈጻሚነት ያለውን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ድንጋጌን በመተርጐም ወይም በመተግበር ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፈፀመው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለ ሲሆን በአመልካች በኩል በቅሬታነት የቀረበው ነጥብም የፍሬ ነገር እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ ባለመሆኑ ልንቀበለው የምንችለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም የአመልካች የይግባኝ ጊዜ አልፏል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በቤኒሻንጉል ጉምዝ ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 03080 መስከረም 10 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች ይግባኝ የቀረበው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ድንጋጌ ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከአለፈ በኋላ ነው ተብሎ የይግባኝ መዝገቡ መዘጋቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

**<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>**

በዚህ ችሎት መስከረም 23 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 76909

ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፈትያ አወል - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቢ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ አመልካች እኔ ባልተገኘሁበትና የቅጣት አስተያየት ባልሰጠሁበት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሰረዝ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ ተደርጎብኛል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ አመልካች አዋጅ ቁጥር 104/90 አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 18(2) በመተላለፍ የግል ተበዳይን ወደ ኩዌት እልክሻለሁ በማለት ብር 7800 በመቀበል ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ዱባይ የላከቻት በመሆኑ በክሱ የተጠቀሰውን አዋጅና የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈፅማለች በማለት ክስ አቅርቦ አመልካች ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክራለች፡፡

ዐቃቤ ህግ ክሱን የሚያስረዱለትን ምስክሮች አመልካች ባለችበት አሰምቶ አመልካች የሰውና የፅሁፍ የመከላከያ ማስረጃዎችን አሰምታለች፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በነበረው ቀነ ቀጠሮ አመልካች ባለመቅረቧ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በሌለችበት ጉዳዩን የሚቀጥል ስለመሆኑ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሀምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ወንጀል የፈፀመች ጥፋተኛ ናት በማለት በአስር ወር እስራት እንድትቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ፍርድ ይነሳልኝ (ይሰረዝልኝ) በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርባ የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካች ጥያቄ የህግ መሰረት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርባ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በነበረው ቀጠሮና የሥር ፍርድ ቤት ፍርድ በሰጠበት ጊዜ ያልቀረበችው ውጭ አገር ሄዳ ልጇ በመታመሙ ምክንያት ወደኢትዮጵያ የምታደርገው ጉዞ የዘገየ መሆኑን ገልፃ የሥር ፍ/ቤት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀፅ 4 በሚደነግገው መሰረት ጠበቃዬ እንዳይገኝ በማድረግ የቅጣት አስተያየት ሣይሰጥ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ በመሆኑ ሊሰረዝልኝ ሲገባ ጥያቄዬ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ ክርክር የተካሄደውና ማስረጃ የተሰማው አመልካች ባለችበት ነው፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ፍርድ በሰጠበት ጊዜ አመልካች አለመገኘቷ ጉዳዩ በሌለችበት ታይቷል የሚያስብል አይደለም፡፡ ፍርዱ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ያቀረበችውን የፍርድ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የወንጀል ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ወንጀሉን ያልፈፀመች መሆኑን በመግለጽ የተከራከረች መሆኑ፣ አመልካች ባለችበት ተጠሪ ማስረጃዎቹን ያሰማ መሆኑንና አመልካችም የመከላከያ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎቿን ያቀረበች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የተጠሪን ምስክሮች ቃል የመመርመርና የመጠየቅ መብቷ እና የእሷን የመከላከያ ማስረጃ አቅርባ የማሰማት መብቷ ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታ የአመልካችና የተጠሪ ክርክርና ማስረጃ የተሰማ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 በሚደነግገው መሰረት የከሳሽን ማስረጃ የመመርመርና የመጠየቅ መብቷ የተረጋገጠላትና የእሷንም የሰውና የፅሁፍ የመከላከያ ማስረጃ ያቀረበችው አመልካች የከሳሽንና የተከሳሽን ማስረጃ መርምሮ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ለመስጠት ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሣትገኝ መቅረቷ ጉዳዩ በህገመንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው መሰረታዊ መብቷ ባልተሟላበት ሁኔታ ታይቷል ከሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዐቃቤ ህግን ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና የመከላከያ ምስክሮችንና ማስረጃ ካሰማ በኋላ ቀጠሮውን አክብሮ ፍርድ ቤት ባይቀርብ ዳኞች የከሳሽንና የተከሳሽን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ፍርድ ከመስጠት የሚገድባቸው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች ቀጠሮውን አክብራ ባልቀረበችበት ሁኔታ የቅጣት አስተያየት የመስጠት መብቴ ታልፏል በማለት ያቀረበችው ክርክር የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የወንጀልኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ጉዳዩን የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ በሌለበት በሚታይበት ሥርዓት (default procedure) እንዳየው በመቁጠር ያቀረበችው አቤቱታ መጀመሪያውኑ አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት በ(default procedure) ታየ የሚባለው መቼ ነው? ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስ ስለሚታይበት ሁኔታ የሚደነግጉት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 161 እስከ 164 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት ትርጉምና ተፈፃሚነትና ውጤት እንደዚሁም ተከሳሽ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝለት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 197 እስከ 202 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘት ትርጉም ተፈፃሚነትና ውጤት ያላገናዘበና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የተጠሪን ማስረጃ የመመርመርና የመጠየቅ

መብቷ በተረጋገጠበትና የሰውና የሰነድ የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብቷን ሙሉ በሙሉ ከተጠቀመች በኋላ ፍ/ቤቱ ፍርድ በሰጠበት ቀን እኔ ስላልተገኘሁ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረበችው አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ይህ የአመልካች ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 72304
ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የትግራይ ክልል አጽቢ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ

**ተጠሪ፡-** ተማሪ ሐጎስ ወልደሚካኤል በሌለበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42048 በግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአጽቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ በአንድ የወንጀል ድርጊት ሁለት ጊዜ የመከሰስና የመቀጣት ሕጋዊነትን አስመልክቶ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአጽቢ ወረዳ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 8.00 ሰዓት በማለት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት የገደለ በመሆኑ ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ በወንጀል ክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሟችን ድንጋይ ወርውሬ መትቻለሁ፡፡ ነገር ግን ሟች ድኖ ሌላ ጊዜ የሞተ በመሆኑ ለሟች መሞት በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰው ምስክርና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ሟች በድንጋይ ከተመታ በኋላ ሕክምና ተደርጐለት ድኖ የመስኖ እርሻ ሥራ ሲሰራ የነበረ መሆኑን ያውቁልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት የገደለ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው በማለት ተጠሪ በአሥር ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውቅሮ ምድብ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ከመረመረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ

ጉዳይ ነጥብ የለም በማለት የተጠሪን ይግባኝ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ተጠሪ አመልካች ከዚህ በፊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 8.00 ሰዓት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ በመምታት በግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርቦብኝ ጥፋተኛ ተብዬ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ተቀጥቻለሁ፡፡ አመልካች ተጠሪ በተቀጣሁበት ድርጊት በማንሣት በድጋሚ በወንጀል መከሰሱና የበታች ፍርድ ቤቶችም እኔን ጥፋተኛ ብለው ቅጣት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን ነጥብ መጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አድርጐ ያላቀረበ ስለሆነ የሰበር መከራከሪያ ሊያደርገው አይገባም፡፡ ተጠሪ ከዚህ በፊት የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ነው አሁን የተከሰሰው በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል ተብሎ ስለሆነ የቀረበው ክስ በፊት ከተከሰሰበት ጋር በአንድ ጉዳይ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23ና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 በመተርጐም የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ በመሆኑ በድጋሚ በዚያው ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔን በመሻር ተጠሪን አሰናብቷታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ለዚህ የሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትና በድርድር ጥፋተኝነቱን አምኖ ጥፋተኛ ተብሎ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጣው የተሳሳተ ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አቶ ግደይ ገብረየሱስ የካቲት 21 ቀን 2002 በተጠሪ ድንጋይ ተመትተው መጋቢት 30 ቀን 2002 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ የሟች አቶ ግደይ ገብረየሱስ ህይወት ለሕልፈት የበቃው ተጠሪ በድንጋይ ጭንቅላታቸው ላይ ባደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት መሆኑ በሚኒሊክ ሆስፒታል ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ትክክለኛውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል በማለት ያቀረብነውን ክስ ተቀብለው የወረዳው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 የሚጥስ ነው በማለት በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በአድራሻው ተፈልጎ ያልተገኘ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው የሰበር ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ በወንጀል አንቀጽ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች አቶ ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል በማለት በድጋሚ መከሰሱንና ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤትና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንኡስ  አንቀጽ 5 የሚጥስ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ ስምንት ሰዓት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ የግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስን የመታቸው መሆኑን ያልካደ ሲሆን ይህ ፍሬ ጉዳይ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ይህንን ድርጊት በፈጸመ በሁለተኛው ቀን ማለትም የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ በግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበት ተጠሪ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጣ መሆኑን አመልካች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በግልጽ በማመን አቅርቦታል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በይዘቱ መጀመሪያ ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ወንጀል ክስ፣ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ የሞት አደጋ ማድረሱ ከመታወቁ በፊት ነው፡፡ አሁን ግን የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ሞት አደጋ ማድረሱ በመታወቁ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ተጠሪን በድጋሚ መክሰሳችን ሕጋዊና ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት መሠረታዊ የወንጀል ሕግ መርህ አድርጎ ከደነገጋቸው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች አንደኛው አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የለበትም የሚለው ነው፡፡ ይህ የወንጀል ሕግ መርህ በሕገ መንግስቱ ብቻ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 ተደንግጓል፡፡ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 23 "ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነሥርዓት መሰረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" በማለት ደንግጓል፡፡

የወንጀል ህግ መርሁ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ሲሆን አገራችን ባጸደቀችው በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7  " No one shall be liable to be tried or punished again for an offence for which he has already been finally convicted or acquitted in accordance with the law and penal procedure of the country " በሚል መንገድ ደንግጎል፡፡

ሆኖም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት አተረጓጐም በዕለት ከዕለት የወንጀል ክስ አቀራረብ በሚታዩ ስህተቶች የሚፈጠሩ ችግሮችን ዓቃቤ ሕግ በድጋሚ የወንጀል ክስ በማቅረብ ለማረም በሚፈቅድ ሁኔታ የተቀረጸ ነው ወይስ አይደለም፤ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ድንጋጌ እንዴት መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነጥብ አከራካሪ መሆኑን አመልካች ተጠሪ የግል ተበዳይን በድንጋይ ወርውሮ የመታው በግል ተበዳይ ላይ ቀላል የአካል

ማጉደል ለማድረስ አስቦ በድርጊቱ ቀላል የአካል ማጉደል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦ ተጠሪ በአመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ተከራክሮ ከተቀጣ በኋላ፣ አመልካች ከዚህ በፊት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ሳቀርብ የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ያስከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማገናዘብም ሆነ አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመምረጥና በመጥቀስ የተሳሳትኩ ስለሆነ ተጠሪን ሆነ ብሎ ተራ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት በድጋሚ ክስ እንዳላቀርብ የሚከለክለኝ ሕግ የለም በማለት በዚህ መዝገብ ያቀረበውን ክርክር በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቴን የሚጥስ ነው ብሎ ለመከራከርና የህገ መንግስቱም ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ለመጠየቅ ሁለት መሠረታዊ መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ተከሣሹ በተመሣሣይ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት የተከሰሰ የነበረ መሆኑ ማረጋገጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተከሣሹ ከዚህ በፊት በተከሰሰበት ወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በአንድ ተከሣሽ ላይ የወንጀል ክስ ለማቅረብ ወይም ላለመቅረብ የሚሰጠው ውሣኔና የወንጀል ክስ ለማቅረብ ከወሰነ በኋላ ተከሣሹ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበትን የወንጀል ድርጊትና የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በወንጀል የፍትህ ሥርዓቱና በወንጀል የፍርድ ሂደት ውስጥ እጅግ ወሣኝና የመጀመሪያውና መሠረታዊ ውሣኔና ክንውን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ በአንድ ተከሣሽ ላይ የወንጀል ክስ ከማቅረቡ በፊት ተከሣሹ አንድ ወንጀል በመፈጸም ሃሣብ የሰራው አንድ የወንጀል ድርጊት ያስከተላቸውን ወይም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብና አግባብነት ያላቸውን ህግ ድንጋጌዎች በመለየትና በመጠቀስ የወንጀል ክሱን በጥንቃቄ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት፣ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ከወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 41፣ አንቀጽ 111 እና አንቀጽ 112 ና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህም ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ በህግ የተጣለበትን ግዴታ ሣይወጣ ተከሣሹን በቀላል ወንጀል ኃላፊና ተጠያቂ የሚደርግ የወንጀል ድንጋጌ ጠቅሶ ክስ አቅርቦ ተከሣሹም፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የእምነት ክህደት ቃልን ከሰጠና ተከራክሮ በቀረበበት የወንጀል ክስ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀጣ ወይም በነፃ ከተለቀቀ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ከዚህ በፊት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ሳቀርብ የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ያስከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማገናዘብም ሆነ አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመምረጥና በመጥቀስ ተሳሳቻለሁ በሚል በተከሣሹ ላይ በድጋሚ የወንጀል ክስ ቢያቀርብ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 በምን መንገድ መተርጎምና ተፈጻሚ መሆን አለባቸው የሚለውን ነጥብ እንድንመረምር ያስገድደናል፡፡

በዚህ መዝገብ አመልካች ያቀረበው የዚህ አይነት ክርክር ሲያጋጥም ከሁሉም በፊት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌው ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብና ዓላማ መሠረት በማድረግ ክርክሩን በመመርመር መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 23 ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን አስመልክቶ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነቶች በተለይም ከዓለም ዓቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7 ይዘት፣ ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን ጋር ማገናዘብና መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የዚህ

ዓለም ዓቀፍ የወንጀል ህግ መርህ መሠረታዊ ዓላማ የአንዲት አገር መንግስት ህግ አስከባሪ አንድ ጊዜ የወንጀል ክስ አቅርቦበትና ተከራክሮ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት በሌላ ጊዜ ተከሳሹን በድጋሚ ለመክሰስና ለማስቀጣት የማይችል መሆኑን በመደንገግ ሰዎችን በአንድ ወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ በሚቀርብ የወንጀል ክስ ስጋት ውስጥ እንዳይወድቁ በመከልከል ለሰዎች የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ ዋስትና እና ጥበቃ መስጠት ነው፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 በአቀራረጹና በይዘቱ በአንድ በኩል ዓቃቤ ህግ ለአንድ የወንጀል ድርጊት በተለያየ ጊዜ የተለያየ የወንጀል ርዕስና የህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ተከሳሽ ተከስሶ በፍ/ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ነፃ ከወጣ ወይም ከተቀጣ በኋላ በድጋሚ በወንጀል እንዳይከሰስና እንዳይጠየቅ የሚከለክል በሌላ አነጋገር የመንግስት የወንጀል ክስ የማቅረብ ሥልጣንን የሚገድብ መሰረታዊ ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድንጋጌው አንድ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል ተብሎ ከወንጀል ክሱ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት ጉዳይ ሌላ የወንጀል ክስና ተጠያቂነት ይመጣብኛል ከሚል ጭንቀት ሥጋት እንዳይሸማቀቅ ህገ መንግስታዊ ዋስትናና ጥበቃ በመስጠት ተከሳሹ በወንጀል ተከስሶ በመጨረሻ ፍርድ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት የወንጀል ድርጊት በድጋሚ የማይከሰስና የማይፈረድበት ስለመሆኑ ህገ መንግስታዊ ዋስትና ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖር የማድረግ ዓላማና ግብ ያለው ነው፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ህግና በወንጀል ስነ ስርዓት ተከስሶ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ተቀጥቷል ወይም በነፃ ተለቋል የሚለው መከራከሪያ በመጀመሪያ የወንጀል ክስ የክስ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 የተደነገገ ሲሆን ፍ/ቤቱ ያቀረበው የክስ መቃወሚያና ማስረጃ በመመርመር ውሳኔ መስጠት ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 131 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም አንድ ተከሳሽ በወንጀል ተከስሶ በመጨረሻ ፍርድ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት የወንጀል ድርጊት በድጋሚ ያለመከሰስ ያለመጠየቅ መብት መሰረታዊና ህገ መንግስታዊ መብት በመሆኑ ክርክሩ በሚካሄድበት በማናቸውም ደረጃ ሊነሳ የሚችልና በማስረጃ ተረጋግጦ በተገኘ ጊዜ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ብይን የሚሰጡበት የመከራከሪያ ነጥብ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ይህን ነጥብ በወረዳው ፍ/ቤት ሣይነሳ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን ክርክር ተቀብሎ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ አመልካች ያቀረበውን ሁለተኛ ክስ በመቀበልና በማከራከር የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሻሩ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረታዊ ይዘት፣ ዓላማና የተፈፃሚነት ወሰን ያገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42048 በግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 74041

ሰኔ 4 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡-1. አንተነህ መኮንን
2. መንግስቱ ሞላ
3. ንግስት ከበደ
4. ታከለ መንገሻ

ጠበቃ ቀፀላ ሙላት ቀረበ

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ህግ - ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

ጉዳዩ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች እና በሌሎች ሃያ ሰዎች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ አመልካቾችና የስር ሌሎች ሃያ ተከሳሾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)፣ (ለ)) እና በተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 214/1974 አንቀጽ 23(1(ሀ)(ለ)) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በስልጣን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል ተብሎ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአቃቤ ህግ ማስረጃዎቹን ከሰማ በኋላ የአሁኑን አመልካቾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 መሰረት በነጻ አሰናብቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካቾች ድርጊቱን መፈጸማቸውን አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ አስረድቶ እያለ ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ተብሎ ብይን መሰጠቱ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ብይን ሽሮ አመልካቾች ሊከላከሉ ይገባል በማለት ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ አስረድቷል በሚል ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአሁኑ አመልካቾች ከ15% በላይ የዋጋ መረጋጋት ለማድረግ ኤሪክሰን የተባለውን ኩባንያ እንዲያልፍ ጥረት አድርገው ሳይሳካ ቢቀርም የእነሱ ሕገ ወጥ ተግባር በውጭ ግዥ ኮሚቴ ግቡን እንዲመታ ተደርጓል በሚል ጥፋተኛ ናቸው የመባላቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመረምር አስቀድሞ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው አቢይ ነጥብ ሆኖ ያገኘው ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት ለመታየት ብቁ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የአሁኑ አመልካቾች በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከመሰረተባቸው የሙስና ወንጀል ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ ተሰናብተው የነበሩ ሲሆን ይኸው የስር ፍ/ቤት የአመልካቾች በነፃ መለቀቅ ብይን ግን ይግባኙን በተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሽሮ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት የመከላከያ ማስረጃ እንዲያሰሙ የተወሰነ ሲሆን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይኸው የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐቡሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ባገኙ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ይህንኑ ስህተት ማረም ነው፡፡ የአቤቱታው አቀራረብ ሥርዓትም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩ ለሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ ጉዳዩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት በማመልከቻው ላይ ዘርዝሮና ጽፎ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፣ ከማመልከቻው በተጨማሪ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ቅጅዎችን በማያያዝ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በዘጠና ቀናት ውስጥ ማቅረብ እንደአለበት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22 በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰማው አስቀድሞ በሶስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት ውሳኔው ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለው ብሎ ሲወሰን ነው፡፡ በድንጋጌው "የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው ሀረግ የሚያስገነዝበው ለሰበር ችሎቱ የሚቀርቡት ማናቸውም ጉዳዮች የይግባኝ አቀራረብ ስርዓቱን ያጠናቀቁና የመጨረሻ ፍርድ የተሰጣቸው መሆን ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የመጨረሻ ፍርድ ያላገኘ ጉዳይ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የሚችለበት አግባብ የለም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የተከሰሱት በሙስና ወንጀል ሆኖ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነሥርዓት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ክስ የሚመራበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ አዋጁ ከደነገጋቸው ጉዳዮች አንዱ የይግባኝ መብት ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 40 የትዕዛዝ ይግባኝን የሚደነግግ ሲሆን ይግባኝ ሊባል የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 36(2) መሰረት በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚቻል የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 36(2) መሰረት የሚሰጡ ውሳኔዎች ደግሞ በቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት ፍ/ቤቱ የማስረጃ ተቀባይነትን በተመለከተ በሚነሳ ጥያቄ፣ መደበኛው የክስ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ውሳኔ ሊያገኝ በሚገባው በማናቸውም የሕግ ጥያቄ ላይ ስለመሆኑ ድንጋጌው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ አዋጁ አንድ ሰው በሙስና ወንጀል ተከሶ የኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ ማስረጃ እንደክሱ ያስረዳ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ አምኖ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ቢሰጥ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ ሆኖም ተጠቃሹ አዋጅ በአንቀጽ 55 ስር የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ፣ የወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በሚል ደንግጎ በአዋጁ አንቀጽ 58 ስር የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎችን ለይቶ ሲያስቀምጥ የፀረሙስና የልዩ ስነስርዓትና

ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ. 236/1993 እንደተሻሻለ መሻሩን፣ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው ደንግጓል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሥርዓት ሕጉ ላይ የተመለከቱት የይግባኝ አቀራረብ ስርዓትን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን ሲሆን በዚህ ሕግ አንቀጽ 184 እና 185 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች አንድ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 142(1) መሰረት ብይን ሲሰጥ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል መሆኑን አያሳዩም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መከላከያ ማስረጃ ሰምቶ በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካላቸው በስርዓቱ መሰረት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው ከታየና የመጨረሻ ፍርድ ካገኙ በኋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአቃቤ ሕግን ማስረጃ በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ ላይ ጭምር በስርዓቱ መሰረት የሰበር አቤቱታ አጠቃልለው ከሚያቀርቡ በስተቀር ከወዲሁ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ስለሰበር አቤቱታ አቀራረብ የተደነገጉትን ሕጎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ አቤቱታቸው ለሰበር ብቁ አይደለም ተብሎ ሊዘጋ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካቾች በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ መመርመር ሳያስፈልግ መዝገቡን ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት ዘግተናል፡፡ አመልካቾች በአቃቤ ማስረጃ ላይ ያላቸውን ሕጋዊ ቅሬታ በስርዓቱ መሰረት በሚያቀርቡት የሰበር አቤቱታ ወደፊት ከማቅረብ ግን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 74530

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ጀማል መሐመድ - ጠበቃ አቶ ጥላሁን ምትኩ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዓቃቤ ህግ - አቶ ታምራት ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 87188 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 105387 በሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ብልጽግና ለማግኘት አስቦ መስከረም 6 ቀን 2003 ዓ.ም ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል በአራዳ ክ/ከተማ ጥበበ ሆስፒታል ፊት ለፊት ከሚገኘው አይከል የኪራይና የኮንትራት የትራንስፖርት ድርጅት ወደ ጎንደር ለመላክ ከአቶ ገ/መስቀል በርሔ የተረከባቸውን ጠቅላላ ግምታቸው ብር 181,675 (አንድ መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ብር) አመልካች ግንኙነቱ የሚስከትልበትን ግዴታና ኃላፊነት አጓድሎ ቢገኝ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚሉትን ጥያቄዎች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

አመልካች የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ተክለብርሃን በርሄ ንብረት የሆነ በአንድ ካርቶን የታሸገ እቃ ወደ ጎንደር እንዲልክለት የተጠሪ ሁለተኛ ምስክር ዳቆን ገብረመስቀል በርሔ መስከረም 6 ቀን 2003 ዓ.ም ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል እቃውን እንደታሸገ እሱ ባለቤት ሲያስረክበው እቃውን ወደ ጎንደር ለማጓጓዝ በመስማማት እቃውን እንደታሸገ ሰራተኞቹ አመልካች ባለበት መረከባቸውንና እቃውን ጎንደር ድረስ ለማጓጓዝ ከላኪው ብር 150 (አንድ መቶ ሃምሣ ብር) የተቀበለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰው ዋጋ በመቀበል አንድን እቃ የታሰበበት ሥፍራ ለማድረስ የሚገባው ግዴታ የእቃ ማጓጓዝ ውል እንደሆነ አግባብነት ያላቸውን የህግ፣ ማእቀፎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትና ከላይ የተገለጹት ተግባራት የግል ተበዳይና አንደኛ የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ተክለብርሃን በርሄና በአመልካች (በአይከል የኪራይና የኮንትራት

የትራንስፖርት ድርጅት) መካከል ህጋዊ ውጤት ባለው የእቃ ማጓጓዝ ውል የተቋቋመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

አቶ ተክለ ብርሃን በርሄና በአመልካች (በአይክል የኪራይና የኮንትራት የትራስፖርት ድርጅት) መካከል የተቋቋመው ህጋዊ ውጤት ያለው የእቃ ማጓጓዝ ውል የእቃው ላኪ ለአጓጓዥው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ የፈጸሙ ሲሆን አመልካች በውሉ መሰረት በልምድ መሰረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማጓጓዝ፣ በካርቶን የታሸገውን እቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሰረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን አቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማጓጓዝ፣ በካርቶን የታሸገውን እቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን አለመወጣቱ አመልካችን በፍታብሔር ተጠያቂ ከመሆን አልፎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቃቸው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡

ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ ዝርዝር ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ የወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቀቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገው የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሠረታዊ ባህሪ ይዘትና የሚስከትለው ኃላፊነትን የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ አማርኛ ቅጅ ቃል በቀል ሲነበብ ማንም ሰው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ ፣ የወሰደ ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል ፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 የተከሣሹ ወንጀል ሃሣብ ግምት የሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሃሣብ እንዳዋለው ይቆጠራል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የእግገሊዝኛውን ቅጅ ስንመለከት Breach of Trust የሚል ርዕስ ያለው አንቀጽ 675 Whoever with intent to obtain for Himself or to Procure for a third person an unjustifiable enrichment appropriates , or Procures for another, takes or causes to be taken misappropriates uses to his own benefit or that of a third person or disposes of for any similar act in whole or in part a thing or a sum of money which is the Property of another and which has been delivered to him in trust or for a specific purpose, is punishable , according to the circumstances of the case with simple

imprisonment or with rigorous not exceeding five years በማለት በንዑስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 3 The intent to obtain for himself or to Procure for third person an unjustifiable enrichment shall be presumed where the criminal is unable upon call, to produce or repay the thing or sum entrusted or at the time when he should have returned it or accounted there for በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች አይከል የኪራይና የኮንትራት የትራስፖርት ድርጅት ያለው  በመሆኑ በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማጓጓዝ በካርቶን የታሸገውን ዕቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሳ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን የሚወጣው እሱ ራሱ ብቻ በግሉ ዕቃውን በዕምነትና በአደራ ጎንደር ወስዶ በማስረከብ አይደለም፡፡ ዕቃውን በወኪሉ በሰራተኞቹ ወይም ከሌላ ሰው ጋር የዕቃ ማጓጓዝ ውል በመዋዋል ግዴታውን ሊፈጽም የሚችልበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አመልካች በውሉ መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ባይወጣ በውሉ መሠረት ዕቃውን ባለማስረከቡ አግባብነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ከሚጠየቅ በስተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 ተላልፏል ተብሎ በዕምነት ማጉደል  ወንጀል ሊጠየቅ የማይችል መሆኑን ከወንጀል  ሕግ አንቀጽ 65 ድንጋጌ ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማጓጓዝ በካርቶን የታሸገውን ዕቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ አንድ ለተወሰነ ግልጋሎት የሚለው አገላለጽ የእቃ ማጓጓዝ ውልን ይጨምራል በማለት የተከራከረ ቢሆንም የድንጋጌው ይዘት አንድ ሰው አንድን ንብረት ለአንድ አገልግሎት ለማዋል ኃላፊነት ተረክቦት ንብረቱን ለተባለው አገልግሎት ሳያውል  ሲቀር በዕምነት ማጉደል  ወንጀል የሚጠየቅ መሆኑን የሚመለከት እንጅ በማጓጓዝ ውሉ መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ እቃውን በማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ አጓዥ በዕምነት ማጉደል ወንጀል እንዲጠየቅ የድንጋጌው ይዘት መንፈስና ዓላማ የማያሣይ በመሆኑ በዚህ በኩል ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በካርቶን የታሸገውን ዕቃ የተረከበው በንግድ ድርጅቱ በኩል በማጓጓዝ ውሉ መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ በመድረግ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድረሶ ለተቀባዩ ለማስረከብ በማሰብ እንደሆነ በተጠሪ ማስረጃ ጭምር ተረጋግጧል፡፡

ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ባለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነወንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተሰጠውን ዋጋ ያለው ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ  ሰው ያደረገ የወሰደ ያስወሰደ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት  ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የአመልካች አድራጎት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገዉ የወንጀል ሃሣብ ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት  ይቻላል፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከላይ የዘረዘርነው የህግ የሃሣብ ሁኔታዎች አልተሟሉም ፡፡ ይህ ሁኔታ መሟላቱን ሳያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የሰጡት ውሣኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ዝርዝር ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 87188 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 105387 በሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጐ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ በማጓጓዝ በካርቶን የታሸገውን ዕቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን አለመወጣቱ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቀው ባለመሆኑ በነጻ ይሰናበታል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነጻ ተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 78793

ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ብስራት ወልደመስቀል - ጠበቆች 1. አበበ አሣመረና

2. ሙሉጌታ ወንድመአገኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ሕግ - ደሴ መንበር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጉቦ ማቀባበል ወንጀልን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው ክስ አመልካች የሕግ አማካሪና ጠበቃ ሆነው በወንጀል የሚፈለጉ ግለሰብ አቶ አትክልት ዘሪሁን ከወንጀል ተጠያቂነት እንዲያመልጡ ለማድረግ በማሰብ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግ የሆኑትን አቶ ተስፋማርያም ገብረ ትንሳኤ በእጁ ያለውን መዝገብ እንዲዘጋና ለዚህም ብር 5000.00 እንዲቀበላቸው በተደጋጋሚ በመወትወት መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም ከቀኑ በግምት 10፡30 ሰዓት ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ሓያ ሁለት ማዞሪያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ጌታሁን በሻ ህንፃ 3ኛ ፎቅ ባለው ካፌ ውስጥ የህጉና የሙያው ምግባር ከሚፈቅደው ውጪ ለባለስልጣኑ መ/ቤት አቃቤ ህግ አቶ ተስፋማርያም ገ/ትንሳኤ ብር 5000.00 ሲሰጡ እጅ ከፍንጅ በመያዛቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 429 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች ክሱ ደርሷቸውና በግልጽ ችሎት ተነቦላቸው ክሱን እንዲረዱት ካደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃል ጠይቆ ስለድርጊቱ አፈፃፀም አመልካች የክህደት ቃል በመስጠታቸው አቃቤ ህግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ ካሰማ በኋላ አመልካች ድርጊቱን መፈጸማቸው መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ የመከላከል መብታቸውን ጠብቆላቸው አመልካች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ያቀረቧቸው የመከላከያ ምስክሮች ቃል የማይታመን እና እርስ በራሱ የሚጣረስ መሆኑን በመግለጽ ውድቅ ከአደረገው በኋላ አመልካችን በተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱን በተመለከተም መጠኑን በቅጣት መመሪያው መሰረት በመመርመር አንድ አመት ከአራት ወር ፅኑ እስራትና በብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት

ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ምክንያቶችን ዘርዝሮ አቅርቧል። ይዘቱም ባጭሩ፡- አቃቤ ሕግ ክሱን በማስረጃ በበቂ ሁኔታ አላስደገፈም፣ የድርጊቱን አፈፃፀም የሚሸፍነው ድንጋጌ በዐቃቤ ህግ ተጠቅሶ የቀረበ አይደለም፣ የቅጣት አወሳሰኑም የቅጣት መመሪያውን መሰረት ያላደረገ ነው፣ ቅጣቱ እንዲገደብ የቀረበው ጥያቄም የታለፈው ያላግባብ ነው የሚሉትን የቅሬታ ነጥቦች በመዘርዘር ውሳኔው እንዲለወጥ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሁፍ መልሱን አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በዋናነት የቅሬታ ነጥብ ያደረገው የአቃቤ ሕግ ክስ በበቂ ማስረጃ አልተደገፈም፣ የመከላከያ ማስረጃዎች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው የሚለው ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ አተረጓጎም ስህተትን ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን አይደለም። በመሆኑም አመልካች የአቃቤ ሕግ ክስን ለማስረዳት የቀረቡት ምስክሮች እንደክሱ ኣላስረዱም፣ የሚታመኑ አይደሉም፣ የድርጊቱ አፈጻጸም በአግባቡ አልታየም በማለት ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች የፍሬ ነገር ክርክሮች በመሆናቸው ይህ ችሎት ሊቀበላቸው የሚገባቸው የክርክር ነጥቦች ባለመሆናቸው አልተቀበልናቸውም። በመሆኑም አመልካች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉን መስራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካች መፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። አመልካች ድርጊቱ ተፈፅሟል ቢባል እንኳ ጉቦ ማቀባበል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት በሰበር አቤቱታቸው ቅሬታቸውን ገልጸዋል። በመሰረቱ አንድ ሰው በወንጀል ሕግ ቁጥር 429 መሰረት ጉቦ ማቀባበል የወንጀል ድርጊት ሊጠየቅ የሚችለው ለራሱ ማናቸውንም አይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ስራን ለሚያከናውን ሰው ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለውን ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ አይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆነ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ አይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ መሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4) መሰረት ሲረጋገጥ ነው።

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ወንጀል አድራጊው ገንዘቡን ከሌላ ሰው ተቀብሎ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ አይነት ጉቦ ለማቀባበል በማዋል ድርጊቱን የሚፈጽም መሆኑን የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው። በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለባለስልጣኑ መ/ቤት አቃቤ ህግ ጉቦ ለመስጠት ያሉበት ዋናው ምክንያት በወንጀል የተከሰሰውን ሌላውን ሰው ከሕግ ተጠያቂነት ለማዳን ሲሉ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ

ከመረጋገጡም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው ሌላውን ሰው ከሕግ ተጠያቂነት ለማዳን ካላቸው ፍላጎት ስለመሆኑ በአቃቤ ሕግ ምስክሮች መነገሩን መሰረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት አመልካች ገንዘቡን ለማቀባበል የፈፀሙት ድርጊት መሆኑን በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ በእርግጥም ይኸው ፍሬ ነገር አመልካች ገንዘቡን በወንጀል ከሚፈለገው ሰው ተቀብለው ለባለስልጣኑ አቃቤ ሕግ ለመስጠት ያደረጉት ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ ለድርጊቱ መፈፀም መሰረት የሆነው ዋናው ነገር ሌላውን ሰው ከሕግ ተጠያቂነት ለማዳን ስለመሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች ከዚሁ ሰው ገንዘብ ስለመቀበላቸው ያለመረጋገጡ የጉቦ ማቀባበል ድርጊትን አያቋቁምም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ይልቁንም ዋናውና መታየት ያለበት የድርጊት ፈፃሚው ፍላጎት (Motive) ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በወንጀል የሚፈለግ ሰው በሕግ እንዳይጠየቅ ከመነጨ ፍላጎት ሕገወጥና የሚያስቀጣ ድርጊት እያወቁ በራሳቸው ፍላጎት ያደረጉ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አድራጎታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 429 ድንጋጌ ስር የሚወድቅ መሆኑን ከዚሁ ድንጋጌ እንዲሁም ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23( (1) እና (4)) እና 58(1(ሀ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘን በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም በአመልካች የተፈፀመው ድርጊት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 429 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚያሟላ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት በቅሬታ ነጥብነት ያቀረቡት ክርክር የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው የቅጣት መነሻው እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት፣ ወይም ከአስር አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የቅጣት መጠን አንድ አመት ከአራት ወር ፅኑ እስራት እና የብር 3000.00 መቀጮ ነው፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሳዩት ፍ/ቤቱ ቅጣቶቹን የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉት የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈጻጸሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍ/ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን ያሳያል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ቅጣት ያስተላለፉት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብለው ከአመዛዘኑና በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ስለመሆኑ ውሳኔው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ለአመልካች ሶስት ምክንያቶችን በቅጣት ማቅለያነት ወስዶና ከቅጣት መመሪያውም ጋር አዛምዶ ቅጣቱን የጣለው መሆኑን ውሳኔው በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን የቅጣት መጠኑ ከድርጊቱ አፈጻጸም አንጻር ሲታይም በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት የተቀመጡትን መሰረታዊ የሆኑ የቅጣት አጣጣል መርሆዎችን ያላገናዘበ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ቅሬታ (የቅጣት በዛ ክርክር ከሚሆን ውጪ) በቅጣት አወሳሰን ላይ የተጣሰ መርህ ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንዲሁም አመልካች ቅጣቱ ሊገደብ ይገባ ነበር በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 190፣ 192፣ እና 194 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ፍ/ቤት በቅጣት አጣጣሉ ጊዜ ግንዘቤ ሊወስድባቸው ስለሚገባቸው

ህጋዊ ምክንያቶች ያለገናዘበ በመሆኑ በዚህ ረገድም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 98894 የካቲት 22 እና 28 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77700 መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ቁጥር 195(2(ለ(2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. ውሳኔው የጸና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤቱ ይገለጽለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኖች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 66943

ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ታምራት ገለታ - ከጠበቃ በሻዳ ገመቹ ጋር ቀረቡ

2. ደጀኔ ስሜ
3. አዲሱ ሱልጣን
4. ኤልሣቤጥ አበራ

- ቀድሞ ጉዳያቸው አያስቀርብም ተብሏል

ተጠሪ፤ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - አቶ ዮሐንስ ግርማይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሰው ግድያና የማታለል ወንጀል ስራ መፈጸሙ በተረጋገጠበት አጥፊ ላይ የወንጀሉ ውጤት ስለመሆናቸው የተረጋገጡት ንብረቶች ለመንግስት ውርስ መሆን የሚችሉ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተነሳው በአሁኑ አመልካቾችና በሌሎች ሁለት ግለሰቦች በጠቅላላው በስድስት ሰዎች ላይ የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተባቸው ክስ መነሻ ነው፡፡

በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የሆነው ያሁኑ 1ኛ አመልካች ታምራት ገለታን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረበባቸው ስድስት ክሶች ሲሆኑ ከእነዚህ ክሶች 1ኛው ክስ፡- አመልካች በ1949 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ)) 522(1ሀ እና ሐ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1999 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ ጊዜአትና ቦታዎች በጥንቆላ ተግባር ሰዎችን ከታመሙበት የበሽታ አይነት አድናለሁ በማለት ከተለያዩ ነገሮች የተቀመመ ውህድ በማጠጣት አቶ ተስፋ ተሾመ (አቶ ተስፋ ወረኢሉ)፣ ኢብራሂም ባርጌቾ፣ የአባቱ ስም ያልታወቀ ፈጠነ የተባለ ግለሰብ፣መሐመድ አረጋ፣ እና መካ አብዲላጊ የተባሉትን ግለሰቦች በግፍ ገድሏል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስ ደግሞ በ1996 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ)) እና 539(1ሀ(ሐ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ ላይ በተገለጸው አኳኋን ሚች ወሰኔ ፈረደን በግፍ ገድሏል የሚል ነው፡፡3ኛ ክስ ደግሞ በ1949 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1ሀ)፣27(1) እና 522(1(ሐ)) የተመለከተውን በመተላለፍ ከኤች አይ ቪ ቫይረስ አድናለሁ በማለት ለወ/ሮ ቬነስ ዩሐንስ በጊዜው የምትወስደውን ዘመናዊ መድኃኒት እንድትተው በማድረግ ውህዱን በተደጋጋሚ በመስጠት በከፍተኛ ህመም ወስጥ እንድትወድቅ በማድረግ በውጪ አገር ህክምና የዳኑ በመሆኑ በግፍ ሰው ለመግደል ሞክረዋል የሚል ሲሆን ሌሎች ሶስት ክሶች ደግሞ የማታለል ተግባሮችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ይኸውም 4ኛው ክስ በ1949 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1ሀ) እና 656(ሀ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከ1991 ዓ.ም. የአባቱ ስም ካልተጠቀሰው መንግስቱ ከተባለው የግል ተበዳይ በጥንቆላው እምነት ስር እንዲወድቅ በማድረግ በማታለል ብር 50,000.00(ሃምሳ

ሺህ) ፣ከአቶ አረጋ ይማምና ከወ/ሮ ረሒማ ሰኢድን በጥንቆላው ስር እንዲወድቁና ልጃቸውን ወደ ውጪ ለመላክ ሲሉ ቤት እንዲሸጡ በማድረግ ብር 13,000.00 መውሰዳቸውን፣ ከአቶ አብድረልሐሚድ መሀመድና ከወ/ሮ ማሪያም አብዱላሂ ደግሞ በጥንቆላው እምነት ስር እንዲወድቁ በማድረግ ብር 20,000.00 መውሰዳቸውን፣ከአቶ ተስፋዬ ታዬ እና ከአቶ ደረሰ ሰሙም በተመሳሳይ ዘዴ ሜሪኩሪ የተባለ ነገር ስለመሆኑ በጥንቆላው እንደአረጋገጡና እንዲገዙ በማድረግ የግል ተበዳዮች በብር 400,000.00 ከገዙት በኋላ ከራሱ ዘንድ እንዲያስቀምጥ በማድረግ መውሰዳቸውን፣ከአቶ አቶ ራሚ ያሲን ደግሞ በማታለል ብር 150,000.00 መውሰዳቸውን፣ ከአቶ እስማኤል ያሲንና ጀማል ከተባሉት ወንድማማቾች ደግሞ በተመሳሳይ የማታለል ዘዴ ብር 60,000.00(ስልሳ ሺኅ) መውሰዳቸውን የሚገልጽ ሲሆን 5ኛ ክስ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 696(1(ሐ)) ስር የተመከተውን በመተላለፍ በጥንቆላው ዘዴ በማታለል ወ/ሮ ወላንሳ አብርሃን መኖሪያ ቤታቸውን በስጦታ እንደሰጧቸው በማስመሰል አስፈርመው ቤቱንና ቦታውን መውሰዳቸውን የሚገልጽ ነው፡፡6ኛው ክስ ደግሞ በ1949 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 589(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በጥንቆላው ዘዴ በማስፈራራት የግል ተበዳይ ታየች ማሞ፣ ወ/ሮ ሜላት ሽፈራውን፣ ቬነሱ ዩሐንስን በተለያዩ ጊዜያት የግብረ ስጋ ግንኙነት ከ1ኛ አመልካች ጋር እንዲፈፅሙ አድርገዋል የሚል ነው፡፡አመልካች የተከሰሱባቸውን የወንጀል ድርጊቶችን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያሏቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበው ከተሰሙና ከተመረመሩ በኋላ የአመልካች የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው ማስረጃዎቻቸው ከተሰሙ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት አመልካችን በስድስቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በጠቅላላው በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ፣ አመልካች ካፈሯቸው ንብረቶች መካከል በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መ/ቤት የምዕራብ ዞን ፅ/ቤት በቁጥር ምዕ/ዞን/12069/200 በቀን 21/11/2001 በጻፈው ደብዳቤ በገለፀው መሰረት የሰሌዳ ቁጥር 2-60978 አ.አ እና 2-49372 አ.አ የሆኑ ተሽከርካሪዎች፣ አቢሲኒያ ባንክ ሐምሌ 27 ቀን 2001 በጻፈው ደብዳቤ በኡራኤል ቅርንጫፍ በአመልካች ስም በቁጠባ ሂሳብ ቁጥር 2151 መኖሩ የተገለጸውን ብር 153,351.72፣በፍቼ ከተማ ቀበሌ 04 ሆቴልና በቀበሌ 03 የሚገኝ ከልማት ባንክ የተገዛ ቦታ በቁጥር 145/ፓ-58/02 በቀን 22/11/2001 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ በአመልካች ስም መኖሩ የተረጋገጠው ንብረት፣ በአዳማ ከተማ የሚገኘው ቤት የፍትሓብሔር ክርክርን ውጤት በጠበቀ መንገድ፣ ብዛቱ 131 ሆኖ 1445 ግራም ወርቅ፣ ብርና ሌሎች አርቲፊሻሎችን ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ በሚል የተወሰነ ሲሆን ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ በተባሉት ንብረቶች የሶስተኛ ወገኖች መብት መጠበቅ ያለበት ስለመሆኑም ተገልፆ ተወስኗል፡፡የአሁኖቹ 2ኛ አመልካች(ደረጀ ስሜ) እና 3ኛ አመልካች (አዲሱ ሱልጣን)ን በተመለከተ ደግሞ በ4ኛው ክስ ላይ የተገለፀውን የማታለል ወንጀል መፈፀማቸው ብቻ ነው የተረጋገጠው ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) መሠረት እና በተጨማሪም በ1949 ዓ.ም፣ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 606 ጠቅሶ ጥፋተኛ በማድረግ በ2ኛው አመልካች ላይ የ5 ዓመት ጽኑ እሥራት እና ብር 5000 መቀጮ፣ በ3ኛ አመልካች ላይ የ4 ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 3000 መቀጮ ሲወሰን በአሁኗ 4ኛ አመልካች (ኤልሣቤጥ አበራ) በሚመለከት ደግሞ በ5ኛው ክስ ላይ የተገለፀውን የማታለል ወንጀል መፈፀሟ ሊረጋገጥባት ችሏል በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) መሠረት ጥፋተኛ በማድረግ የአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት እና የብር 3000 መቀጮ ወሰኖበታል፡፡ሌሎች ተከሳሾች ላይም ተገቢ ነው ያለውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚኅም በኂላ ሁሉም አመልካቾች በተወሰነባቸው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪም በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለዚሁ ፍርድ ቤት ይግባኙን አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ የአቃቤ ሕጉን ይግባኝ ውድቅ ሲያደርግ የ1ኛውን አመልካች ይግባኝ በተመለከተ በክሶቹ ላይ ተላልፏል ተብለው የተጠቀሱበት የሕግ አንቀጾች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/ መሠረት ተለውጠው 1ኛው አመልካች(ታምራት ገለታ) በ1ኛው ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 58/1/ እና 523 መሠረት፣ በ2ኛው ክስ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 58 እና 540 መሠረት እንዲሁም በ3ኛው ክስ በሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 58/1/ለ 27/1/ እና 523 መሠረት ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ድንጋጌዎች ያሻሻለ ሲሆን በሌሎች ድንጋጌዎች ስር የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ግን እንዳለ በማፅናት ቅጣቱን በተመለከተ ተደራራቢ የሆኑ ወንጀሎች መገኘታቸው ሲረጋገጥ ቅጣት ሊወሰን የሚችለውን መርህ መሰረት አድርጎ ከአሰላ በኂላ በጠቅላላው አመልካች በ25(ሃያ አምስት) አመታት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን በንብረት አወራረስ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ደግሞ በውርስ የተገኘ ንብረት እንዳይወረስ ጠቅሶ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ በ2ኛ አመልካችና (ደረጀ ስሜ) እና በ4ኛ አመልካች(ኤልሣቤጥ አበራ) ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የወሰነው የእሥራት ቅጣት በማሻሻል የእሥራቱ ቅጣት በአንድ ዓመት እንዲቀንስላቸው ተደርጎ ታሥረው የቆዩበት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሆኖ እያንዳንዳቸው በአራት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን በ3ኛ አመልካች (አዲሱ ሱልጣን) የተሰጠው ቅጣት ግን እንዳለ እንዲፀና፣ በቀለ ገለታ የተባለው ደግሞ በነፃ እንዲሰናበት ሲል ወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾች በጥፋተኝነት እና በእስራት ቅጣቱ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት ተቀባይነት ያጣ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው 1ኛ አመልካችን በተመለከተ ንብረቶቹ እንዲወረሱ የተሰጠው ትእዛዝ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98 ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለአቃቤ ሕግ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ትእዛዝ ሊሰጥ የቻለው ከወንጀል ፍሬ የተገኙ መሆናቸው ተረጋግጦ ስለመሆኑና ሕጉም የአስገዳጅነት ባህርይ ያለው በመሆኑ ነው በማለት በንብረቶቹ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸና ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ልዩ ድንጋጌዎች ስለንብረት መወረስ የማይደነግጉ በመሆናቸው ንብረቶቹ ሊወረሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች ንብረቶቹ እንዲወረሱ በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች የተከሰሱትና ጥፋተኛ የተባሉት በስድስት ክሶች ሁኖ የአመልካች ጠበቃ እንደጠቀሱት ሁሉም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው ልዩ ድንጋጌዎች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ የንብረት መወረስ ስለመኖሩ በግልፅ አያስቀምጡም፡፡እንዲህ ከሆነ የአመልካች ንብረቶቹ የሚወረሱበት አግባብ ስለመኖሩ ሕጉ በሌላ መንገድ አስቀምጧል

ወይ? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ይህን ጥያቄ ለመመለስ የአመልካች ንብረቶች የተያዙበትን አግባብ እና የክሶችን ይዘት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡አመልካች የተከሰሱባቸው ድንጋጌዎች በጥንቆላ ዘዴ ሰዎችን በመግደልና በማታለል ንብረታቸውን ወስደዋል፣ያላግባብም በልጽገዋል በሚል ምክንያት ሲሆን ንብረቶቹ የወንጀሉ ፍሬዎች ስለመሆናቸው አቃቤ ሕግ በክሱ በማስረጃ ዝርዝር ገልጾ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በውርስ ከአገኙት እና ራሳቸው በግል ጉልበታቸው፣ ገንዘባቸው እና እውቀታቸው ሊያፈሩ ከሚችሉት በላይ ሀብት አካብተው መገኘታቸውን ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሯል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎትም ተቀባይነት ማግኘቱን ውሳኔው ያስገነዝባል፡፡ እንዲህ ከሆነ ንብረቶቹ የወንጀል ፍሬ ናቸው የሚለው የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ህግ ስህተት ማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት የተለየ ድምዳሜ ሊያዝበት ወይም ሊለወጥ የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የዚህ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ስላለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነውና፡፡ በመሆኑም ንብረቶቹ የወንጀል ፍሬዎች ስለመሆናቸው ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባለቸው ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን እንዳለ የምንቀበለው ጉዳይ ሁኖ ወደ ሕጉ ስንመጣ ደግሞ በሕጉ ላይ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከአንቀጽ 98 ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወረስ ሊፈርድ እንደሚችል በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ ስር በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን በአንቀጹ ንኡስ አንቀጽ ሁለት ስር ደግሞ የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት እንደሚወረስ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ተደንግጓል፡፡ ከአንቀፅ 98(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የንብረት መውረስ ፍርድ ሊሰጥ የሚችለው ወንጀለኛው ንብረቱን ያገኘው የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ስለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ድንጋጌ የንብረት መወረስ እንደሚኖር በቅጣት መልክ ባያስቀምጥም ንብረቱ የወንጀሉ ፍሬ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛው ንብረት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን የግድ መፍረድ ያለበት መሆኑን ሕጉ በግልጽ ያሳያል፡፡

ከዚህ አንጻር ስንመለከተውም የአመልካች ጠበቃ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98(1) ድንጋጌን ብቻውን ነጥለው በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር የአንቀጹን ንኡስ አንቀፅ ሁለት ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጋር ያገናዘበ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ስለሆነም የአመልካች ንብረቶቹ የተገኙት በወንጀል ስራ ስለመሆኑና ንብረቶቹ የወንጀሉ ፍሬ ስለመሆናቸው ተረጋግጦ ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ የተሰጠው ውሳኔ በ1949 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 97"ም" ሆነ በ1996 ዓ/ም ከወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98(2) ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ ሕጉን የተከተለ እንጂ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው ከዚሁ የንብረት መውረስ ውጤት ጋር ተያይዞ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንደተገለፀው ግልጽ ሁኖ መቀመጥ ያለበት ነገር ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ በታዘዙት የአመልካች ንብረቶች የሶስተኛ ወገኖች መብት ካለ የማይነካ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ግልጽ ውሳኔ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውርስ የተገኙ ንብረቶች ሊወረሱ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ በንብረቶቹ ላይ ሶስተኛ

ወገኖች ያላቸው መብት እንዳይነካ የሚገልጽ በመሆኑ በዚህ ረገድ መብት አለን የሚሉትን ሶስተኛ ወገኖች የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔም መብታቸውን የማይነካ መሆኑ ሊታወቅ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ የንብረት ውርስ ውሳኔን ያጸናው የውሳኔ ክፍል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በወንጀሉ ተግባር ስለማግኘታቸው የተረጋገጡት ንብረቶች ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ መወሰኑ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡ ሆኖም የሶስተኛ ወገኖች መብት ግን የሚነካ ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁጥር 48915 ታህሳስ 28 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መጽናቱን እንዲያውቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 75922
ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1ኛ/ አፈወርቅ ሌሊሳ } ጉዳይ ተከታታይ በትናትናው ዕለት ቀርበው

2ኛ/ ውብሸት ደምል } ውሳኔውን መዝገብ ቤት ይስሙ ተብሏል፡፡

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ዐ/ሕግ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካቾች በተከሰሱበት የግድያ ወንጀል ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 539 የተመለከተውን በመተላለፍ አማረ ሙሉጌታ የተባለውን አስቀድሞ ለመግደል በነበራቸው ሀሳብ ሚያዝያ 05 ቀን 2003 ዓ.ም ከሌሊቱ 6፡00 እስከ 7፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በአዋሳ ከተማ በተለያዩ ሆቴሎች በመዘዋወር መጠጥ በማጠጣት በስካር እራሱን እንዲስት ካደረገ በኋላ በታቦር ክ/ከተማ በወጋኔ ዋጮ ቀበሌ ልዩ ስፍራው ማውንት አሌብ ት/ቤት ፊት ለፊት በመውሰድ 2ኛው ተከሳሽ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ እራሱን እንዳይከላከል ሲያደርግ 1ኛ ተከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በስለት የግራ ደረቱን ከወጋው በኋላ የፈፀሙት ወንጀል እንዳይገለፅ በሞትና ጣር ያለውን ሆስፒታል የወሰዱና ሆስፒታል ግቢ እንደገባ ህይወቱ በማለፉ በፈጸሙት ከባድ የግፍ አገዳደል ወንጀል ተከስዋል የሚል የወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ተከሳሽም ክደው በመከራከራቸው፤ የዐ/ህግ ማስረጃ ተሰምቷል፡፡ በዚህም ማስረጃ መሰረት እንዲከላከሉ፤ ተደርጎ እነርሱም በተራቸው፣ የመከላከያ ማስረጃ አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ሲሰማ የቆየው ፍ/ቤትም በወ/መ/ቁ. 10239 ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከድርጊቱ በፊት እና በኋላ፤ በድርጊቱ አፈፃፀም ጊዜ ተደርገዋል የተባሉትንና በዐ/ህግ ማስረጃ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በቀጥታ የወንጀሉን ድርጊት ተከሳሾች የፈፀሙት ናቸው በማለት የሚያስረዱ ባይሆንም፤ ድርጊቱ በተከሳሾች የተፈፀመ ለመሆኑ በአካባቢ ማስረጃነታቸው በቂና ለድምዳሜ አጥጋቢ መነሻ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም ድርጊቱን መፈፀማቸውን አረጋግጫለሁ ካለ በኋላ ይሁን እንጂ በዚህ አኳኋን የተረጋገጠው ማስረጃ እንደ ክሱ ዝርዝር ሁኔታ ተከሳሾች አስቀድሞ በነበራቸው ሀሳብ ተነሳስተውና ተዘጋጅተው የፈፀሙት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም ይልቁንም አድራጎታቸው በወ/ሕግ ቁጥር 540 ሥር የሚወድቅ ሆኖ ስለተገኘ በዚሁ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በቅጣት አጣጣል ረገድም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት እና የድርጊቱን አፈፃፀም በማገናዘብ እያንዳንዳቸው በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይህም ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልሉ ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት ቀርቦ ውሳኔው የሚነቀፍበት ምክንያት የሌለ መሆኑ ተገልፆ የአሁን ተጠሪዎች በመሰናበታቸው ለዚሁ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የሰበር ቅሬታቸውም ይዘት የእያንዳንዳችንን አድራጎት ለይቶ ያስረዳ የዓይን ምስክር አልቀረበብንም፤ አልተመሰከረብንም ምስክሮች የአካባቢ ናቸው፡፡ ሆነ ተብሎ ለተፈፀመ ድርጊት ተጠያቂነት የለብንም፡፡ ዐ/ሕግ ክሱን አሻሽላለሁ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ እንደጥያቄው አሻሽሎ አለማቅረቡ ሲታወቅ ለጊዜውም ቢሆን ክሱ ተቋርጦ መሰናበት ይገባን ነበር፡፡ በክሱ ላይ ሌሎች ግብረአበሮች እንዳሉ በመገለፁ እነርሱ ህግ ፊት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ብቻ እኛ ተሸክመን ሟችን ባደረስን መከሰሳችን አግባብነት የለውም ጥፋተኛ ናችሁ ከተባልንም ወጣትነታችንን፣ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበብን፣ የሟችን ህይወት ከደረሰበት አደጋ ለማትረፍ ያደረግነው ጥረት ሁሉ ሳይመዛዘን የተጣለው ቅጣት የበዛ ነው ሊቀነስልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የክልሉ ዐ/ህግ በዚህ ሰበር ጉዳይ በተጠሪነቱ ቀርቦ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤት የተደረገውን ክርክር መሰረት ያላደረገ መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲፀና ጠይቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል እንደመረመርነውም በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ መቅረብ የሚገባው የማስረጃ ዓነይት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት የሚችል ድርጊቱን ሲፈፅሙ አያቻለሁ፣ ሰምቻለሁ ወዘተ የሚል ቀጥተኛ ማስረጃ ብቻ ነው የሚል የተደነገገ ህግ በህግ ሥርዓታችን አይገኝም ይልቁንም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 137 እንደተደነገገው በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችለው ስለተያዘው አከራካሪ ነጥብ /ጭብጥ/ ማስረጃው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለጉዳዩ የሚያውቀውን ዝርዝር የምስክርነት ቃል ሁሉ የሚጨምር ነው፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ አመልካቾች በእኛ ላይ ቀርበው የተደመጡት ምስክሮች የዓይን ምስክሮች ሳይሆኑ የአካባቢ ናቸው፡፡ ስለሆነም ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በሚል አንድምታ ያቀረቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

ለሟች ሞት መንስኤ የሆነው ተግባር በአመልካቾች የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረጃው አረጋግጧል እስከተባለ ድረስ የትኛውን ተግባር የትኛው ተከሳሽ እንደፈጸመ ለይቶ ያስረዳ ማስረጃ አልቀረበብንም የሚለውም ክርክር ቢሆን የየግላቸው የወንጀል ተሳትፎ ተለይቶ አለመታወቁ በሐሳብም ሆነ በተግባር በመተጋገዝ በግብረአበርነት ከፈፀሙት ድርጊት ነፃ ናቸው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡ እንዲሁም ዐቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽላለሁ በማለት ሳያሻሽል ክርክሩ በቀረበው ክስ ቀጥሎ ከሆነ እንደትዕዛዙ አሻሽሎ ባለማቅረቡ ምክንያት የወንጀሉ ክሱ ለጊዜው ሊዘጋ እንደሚችል ስለዚሁ አግባብነት ባለው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. አልተመለከተም ክሱ ተሻሽሎ አለመቅረቡ የማሻሻያ ጥያቄው በከሳሽ በዐ/ሕግ ተነስቶ የነበረ ከመሆኑ አንፃር በተከሳሾች ላይ ጉዳት አድርሷል ለማለት አያበቃም ክሱ እንደፍርዱ በትዕዛዝ ባለማሻሻሉ ምክንያት በክርክሩ አካሄድ የመከራከር መብታቸውን እንዴት እንዳጣበበ እና በምን አኳኋን የፍትህ መጓደል እንደደረሰም አላስረዱም፡፡

በሌላ በኩል ስለዋናው ጉዳይ ለሟች ሞት መንስኤ የሆነውን፣ ተግባር ማን ፈፀመው? ለሚለው ዐብይ አከራካሪ ነጥብ ተከሳሾች በዕለቱ ዕለት አብረው ማምሸታቸውን፣ ከሁለተኛው ተከሳሽ ጋር፤

እደር አላድርም በሚል ትንቅንቅ ትግል በተከሳሾችና በሟች የነበረ መሆኑ፤ ሟች አላድርም ብሎ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከአጭር በ2 እና ሦስት ደቂቃ በሚቆጠር ጊዜ መከተላቸው፤ በዚህ ጊዜ ሟች በሰው እጅ ተጎድቶ ተከሳሾች ሟችን ተሸክመው ወደ ሆስፒታል ባመጡት ጊዜ ሟች ከአንገቱ ሥር ከደረቱ ላይ በስለት ነገር መወጋቱ፤ ተከሳሽም ፊታቸው ሁሉ ሳይቀር ደም በደም የነበረ መሆኑን እና ከምስክሮች የመገረም ቃል አገላለፅ ተነስተው "የሞተው መቼ እሱ ብቻ እኛም ሞተናል አይ የኛ ነገር አበቃ የእኛ ነገር" ተከሳሽ በሚል መናገራቸውን ሁሉ ፍ/ቤቱ እንደ በቂ የግምት መነሻ በመውሰድ ሟችን ለህልፈተ ህይወት ያበቃው በተከሳሾች አድራጎት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሚያየው ፍ/ቤት ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማረጋገጥ፤ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በማስረጃነቱ አከራካሪ ነጥብ የሆነውን በማስረዳት ረገድ ያለውን ታማኝነትና ሚዛን የመለካት ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተከናወኑ የዳኝነት ሥራ/ተግባራት በመሆኑ ጉዳዩ የህግ ጥያቄን የሚያስነሳ ሆኖ አይገኝም ምናልባትም የዚህ ማስረጃ አግባብነት ታማኝነትና ሚዛን ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 አንፃር ተገናዝቦ መታየቱንና አለመታየቱን በሚመለከት የህግ ጥያቄን ያስነሳል እንኳ ቢባል በዚህ ህግ በተቀመጠው የማስረጃ ሚዛን መለኪያ አኳያ ከላይ የተመለከተው የዐ/ህግ ማስረጃ ይታይ እንኳ ቢባል በህጉ መሰረት ከተቀመጠው ሚዛን የወረደ ስለሆነ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በብይን በነፃ መሰናበት ነበረባቸው የሚለውን የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡

ተከሳሾች በተራቸው እንከላከላለን በማለት ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃም ቢሆን በዕለቱ ዕለት በሟችና በ1ኛ ተከሳሽ ተፈጥሮ የነበረውን ቂም የሚያመለክትና በድርጊቱ አፈፃፀም ተጠያቂዎች ተከሳሾች እንጂ ሌላ ወገን አይደለም የሚለውን በማመላከት የዐ/ሕግ ማስረጃ የሚያጠናክር እንጂ በወ/መ/ሐ/ሥ/ሥ/ቁ/ 149 እንደተመለከተው ከወንጀሉ ተጠያቂነት ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በቅሬታቸው እንደገለፁት እና ከመደበኛ የሰበር ክርክር አቀራረብ ሥርዓት ውጭ በአቤቱታ እንደገለፁት ተከሳሾች በተከሰሱበት የወንጀል ጉዳይ ሌሎች ግብረአበሮች የነበሩ ስለመሆኑ ክርክሩ የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ እነዚህ አሁን አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀማቸው የወንጀል ህግ ሥርዓት የሚጠየቀውን ሚዛን በጠበቀ ማስረጃ የተረጋገጠባቸው መሆኑ እስከታወቀ ድረስ በዚህ አኳኋን ያቀረቡት የመከራከሪያ ነጥብ ከኃላፊነት ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የቀረበውም ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ እንደገና ሊታረም የሚችልበትን የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ በሰበር መ/ቁ 55532 በ28/2/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ አፅንተናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 75980

ሐምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረ ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ስማቸው ልንገርህ ዓለሙ በማ/ቤት ስለሆነ አልቀረበም

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የደቡብ ክልል ቅርንጫፍ

ዐቃቤ ሕግ  አቶ ደስታ ንጉሴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርተው ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀፅ 3 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ፣ ዋና ወንጀል አድራጊ በመሆን መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም በሀዋሳ ከተማ በታቦር ክፍለ ከተማ አላሙራ ከሚባለው ሥፍራ ከመካነ መቃብሩ ወደ ሪፈራል ሆስፒታል በሚያስሄደው መንገድ ላይ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ያሽከረክረው በነበረው የመለያ ቁጥር 3-39349/ኢ.አ/ በሆነው አይሱዙ መኪና የታክስ መጠኑ ብር 220,939.98 /ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ  ከዘጠና ስምንት ሣንቲም / የሆነ 11,508 /አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሥምንት ኪሎ ግራም/ የሆነ ህንድ አገር የተሠራ የጉምሩክ ቀረጥና ሥርዓት ያልተፈፀመበት ስኳር እንዲሁም በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሣሽ የነበረው በሚያሽከረክረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136 ኢ.አ በሆነ አይሱዙ መኪና የታክስ መጠኑ 10,297.80 /አንድ መቶ አስር ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም / የሆነ መጠኑ 5753 /አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሣ ሶስት ኪሎ ግራም/ የሆነ ህንድ አገር የተሠራ የጉምሩክ ቀረጥና ሥርዓት ያልተፈፀመበት ስኳር አስጭኖ ሲያጓጉዝ የፌዴራል ፖሊስ በደረሰው ጥቆማ መሠረት የተያዘ በመሆኑ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡

አመልካች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በክሱ በተገለፀው ጊዜና ሥፍራ አመልካች ሶስተኛው ተከሣሽ የነበረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136 /ኢ.አ/ ከጋቤና ውስጥ ከሶስተኛው ተከሣሽ ጋር ቁጭ ብሎ ሁለተኛው ተከሣሽ በሚያሽከረክረው የመለያ ቁጥሩ 3-39349 በሆነው አይሱዙ መኪናና ሶስተኛው ተከሣሽ በሚያሽከረክረው አይዙሱ መኪና መጠኑ በዐቃቤ ሕግ ክስ የተገለፀው የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ህንድ አገር የተሠራ ስኳር እንደጫኑ በቁጥጥር ሥር ያዋሉ መሆኑንና አመልካች በመጀመሪያ ሲያዝ ተሳፋሪ ነኝ ያላቸው ቢሆንም በማግስቱ ህጋዊ ነጋዴ መሆኑንና ህጋዊና ቀረጥ የከፈለ መሆኑን የገለፀላቸው መሆኑን ስኳሩን ሻሸመኔ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እንዲራገፍ ማድረጋቸውን በዝርዝር መሥክረዋል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ሹፌሮች መሆናቸውንና እያንዳንዳቸው በብር 1700 /አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር/ አመልካች የሚከፍላቸው መሆኑን ተስማምተው ዕቃውን እንደጫኑ ወዲያውኑ እንደተያዙ የተናገሩ መሆናቸውን መሥክረዋል፡፡ ተጠሪ ዕቃዎቹ ገቢ የሆኑበትን ሰነድ ፣ የተከሣሾች መቃወሚያና መንጃ ፈቃድ እንደዚሁም ተከሣሾች /አመልካች ጭምር/ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀፅ 2 ለፖሊስ የሰጡትን የተከሣሽነት ቃል ለሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረበ መሆኑን ከውሣኔው ተረድተናል፡፡

አመልካች ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም የመከላከያ ምስክሮችን ምሣ ጋብዟቸው ከበሉ በኂላ አመልካች ስልክ ተደውሎለት አናግሮ እንደተመለሰና ሀዋሳ ዱቄት የሚጭን ተመላሽ መኪና ስላገኘሁ ይቅርታ አድርጉልኝ ብሎ ወጥቶ እንደሄዱ የመሠከሩ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት በምስክርነት ቀርበው የመከላከያ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመከላከያ ምስክሮችም አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም እያንዳንዳቸው ብር 1700/አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር/ ሂሣብ አመልካች ሊከፍላቸው ተስማምተው ዕቃውን አዲስ አበባ ቃሊቲ ማሰልጠኛ ፊት ለፊት የጫኑ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ በሁለቱ አይሱዙ መኪኖች የተጫነውን ስኳር ይዘው የተገኙ ሰዎች የስኳር ኮርፖሬሽን ደንበኞች እንዳልሆኑና ስኳርም እንዳልሸጠላቸው በፅሑፍ የተረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው በማስፈር አመልካች የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበት መጠኑ በወንጀል ክሱ የተገለፀውን በህንድ አገር የተሠራ ስኳር በባለሀብትነት ጭኖ ሲያጓጉዝ በመገኘቱ ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት ዕቃ በመጫን የትራንስፖርት አገልግሎት የሰጡ መሆናቸው ተረጋግጦባቸዋል፡፡ የመከላከያ ማስረጃቸው የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚያጠናክር እንጅ የሚያስተባብል አይደለም በማለት አመልካችና በሥር ሁለተኛ ና ሶስተኛ ተከሣሽ የሆኑት ሰዎች በወንጀል ህግ አንቀፅ 32/3/ እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ አመልካች በሥምንት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 71,032/ሰባ አንድ ሺህ ሰላሣ ሁለት ብር /እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/1/ መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተያዘው ስኳር የእኔ ሣይሆን መሀመድ የተባለ በሀዋሳ ከተማ ውስጥ መጋዘን ያለው ነጋዴ መሆኑን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/2/ መሠረት የተከሣሽነት ቃሌን ሰጥቻለሁ፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ወዲያውኑ እንደተያዝኩ እኔ ተጓዥ መሆኔን ዕቃው የእኔ አለመሆኑን እንደተናገርኩ ከመሰከሩ በኂላ በማግስቱ ዕቃው የእኔ ነው ብሏል በማለት የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመቀበል ጥፋተኛ

መባሌ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች የሰጡት ቃል በእኔ ላይ በማስረጃነት ሊያዝብኝ አይገባም ፡፡ የቅጣት ውሣኔውም ተገቢ አይደለም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦበታል፡፡ አመልካች የክርክር ስልቱን በመለዋወጥ የሥር ፍርድ ቤት ያለበቂ ማስረጃ ፍርድ እንደተሰጠው ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ሚያዚያ 3 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በተጠሪ የተያዘው ስኳር የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት መሆኑን አላስረዳም፡፡ በተቃራኒው ማስረጃው ስኳሩ የጉምሩክ ሥርዓት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ፖሊሶች ቃሌ በማስረጃነት እንደሚቀርብብኝ ሣያስጠነቅቁኝ ዕቃው የእኔ ነው ብሏል በማለት የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ ጥፋተኛ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መረምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 32 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ የተወሰነው የቅጣት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት የሥር ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ክሱ በገለፀው ጊዜ ማለትም መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም አመልካች በሀዋሳ ከተማ አላሙራ ከተባለው ሥፍራ በመካነ መቃብሩ ወደ ሪፈራል ሆስፒታል በሚያስሄደው መንገድ ሞተር አጥፍተው ተከታትለው ቆመው በነበሩት ሁለተኛው ተከሣሽ በሚያሽከረክረው የመለያ ቁጥር 3-39349 አ.አ በሆነ መኪናና ሶስተኛ ተከሣሽ ያሽከረክረው በነበረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136 አ.አ በሆነ አይሱዙ መኪና ጋቤና ውስጥ ቁጭ ብሎ በቁጥጥር ሥር ያዋለ መሆኑን ፣ መኪኖቹ የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት ህንድ ሀገር የተሠራ ስኳር ጭነው መገኘታቸውን አመልካችንና ሌሎቹን ተከሣሾች በቁጥጥር ሥር ለማዋል የሄዱት የፌዴራል ፖሊስ አባላት መኪናው ላይ ያለው ዕቃ ባለሀብት ማን እንደሆነ ሲጠይቋቸው ለእያንዳንዳቸው ብር 1700 ለመክፈል ተስማምቶ አመልካች ያስጫነው ዕቃ መሆኑን ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች የገለፁ መሆኑን አመልካች በወቅቱ ተሣፋሪ ነኝ ያለ መሆኑንና በማግስቱ ዕቃው ቀረጥ የተከፈለበት የእኔ ንብረት ነው ያለ መሆኑን ይህንን የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ አመልካች ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ ያላስተባበለና ማስረጃው በሰነድ ማስረጃዎችና ሌሎቹ ተከሣሾች ያቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ቃል የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚያጠናክር ይዘት ያለው መሆኑን በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡

ዕቃውን አመልካችንና ዕቃውን የጫኑትን ሹፌሮች በቁጥጥር ሥር ያዋሉት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል በሁለት አይሱዙ መኪና ተጭኖ የነበረው የጉምሩክ ቀረጥ ያልተከፈለበት ህንድ አገር የተሠራ ስኳር በመኪናዎቹ እንደተጫነ በቁጥጥር ሥር ከማዋላቸው በፊት ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ አመልካችን ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች በመኪናዎቹ ላይ ከተጫነው ስኳር ጋር በቁጥጥር ሥር ሲያውሏቸው የነበረውን ሁኔታና አመልካችን ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሽ በቁጥጥር ሥር አውለው ወደ ካንኘ ሲወስዷቸው ስለነበረው ሁኔታ /circumstance/ እና ከዚህ ሂደት አመልካች ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ያሳዩት የነበረውን የባህሪ ሁኔታ ይፈፅሙት የነበሩትን ድርጊትና በቃላት ሲገልፁ ስለነበረው ሀሣብ አስረድተው የተመለሱ ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር የተጠሪ ምስክሮች በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /circumstantial evidence/ ሰጥተው የተመለሱ ናቸው፡፡ በአገራችን የህግ ሥርዓት ምስክሩ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች በአይኑ የታዘበውን በጆሮው የሰማውንና የሚያውቀውን ፍሬ ጉዳይ

ሊስመሰክር እንደሚችልና የምስክሩም ቃል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካችና የተጠሪ ምስክሮች አመልካች የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት ስኳር ጭነው በማከታተል ቆመው በቁጥጥር ሥር ከዋሉት መኪናዎች ውስጥ በአንደኛው ማለትም ከሶስተኛ ተከሣሽ ጋር ሶስተኛው ተከሣሽ ሲያሽከረክረው ከነበረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136/አ.አ/ ከሆነው አይሱዙ መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ እንዳገኙት ፣ ወዲያውኑ ሲጠይቁት ተጓዥ ነኝ በማለት መናገሩንና በቁጥጥር ሥር ውሎ ከሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ጋር ወደ ካንፕ እንደተወሰደ ካንፕ ታስሮ አድሮ በማግስቱ ዕቃው የእኔ ነው ህጋዊ የጉምሩክ ሥርዓት ተፈፅሞበታል በማለት መግለፁን ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ለእያንዳንዳቸው ብር 1700 /አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር/ ለመክፈል ተስማምቶ ዕቃውን ያስጫናቸው አመልካች መሆኑን በቁጥጥር ሥር በሚውሉበት ጊዜ እንደገለፀላቸው በማረጋገጥ የሰጡት ምስክርነት ቃል የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ / circumstantial evidence / እንደሆነና ይህም አመልካች በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/2/ ከሚሰጠው የተከሣሽነት ቃል የተለየ የማስረጃ አይነት መሆኑን ሣያገናዝብ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ምክንያቱም የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ በባህሪውና በይዘቱ አንድ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት ፣ ክስተቱ ሲፈጠር ወይም ድርጊቱ ሲፈፀምና ክስተቱ ከተፈጠረ ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ ያሉትን የአካባቢ ሁኔታዎች በማሣየትና በመግለፅ ዳኞች በጭብጥነት ስለተያዘው አከራካሪ ጉዳይ ሎጅካል ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ የማስረጃ አይነት መሆኑን “ circumstantial evidences is an evidence that tend to prove the matter by providing events or circumstances from which the occurrence of the matter at issue can be reasonably inferred circumstantial evidence not bearing directly the fact in dispute but make clear various attendant circumstances from which the judge might infer the occurrence of the fact in dispute ” በሚል መንገድ በህግ መዝገj ቃላትና በሌሎች አገሮች የማስረጃ ህግ ድንጋጌዎች የተገለፀውንና የእኛም አገር የህግ ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ህጋዊ ተቀባይነት ያለው የማስረጃ አይነት መሆኑን በግልፅ የደነገገው መሆኑን ግንዛቤ ወስጥ በሚያስገባ ሁኔታ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን የአካባቢ ሁኔታ የሚያስረዳ የምስክርነት ቃል መቀበሉ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪ ምስክሮች አመልካች አንደኛና ሁለተኛ ምስክር በቁጥጥር ሥር ከመዋላቸው በፊት ፣ በቁጥጥር ሥር ሲውሉና በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ፣ አመልካችና ተከሣሾች ስለአሳዩት ባህሪ ፣ ስለፈፀሙት ድርጊትና በቃላት ስለገለፁት ሃሣብ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ተጠሪ ካቀረባቸው ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችና በአመልካችና በሁለተኛና ሶስተኛ መከላከያ ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር በማገናዘብና በመመርመርና በመመዘን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማፅናቱ የበታች ፍርድ ቤቶች በህግ የተሰጣቸውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን በመጠቀም ተገቢ ነው ከሚሉት መደምደሚያ ላይ የደረሱ መሆኑን የሚያሣይና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የህግ ድንጋጌ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራትና ዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች በሁለት አይዙሱ መኪና ጭኖ ከተገኘው የስኳር መጠን ፣ ከአመልካች የወንጀል አፈፃፀም አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 71,032 /ሰባ አንድ ሺህ ሰላሣ ሁለት ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ የሰጡት ውሣኔ አመልካችን ቅር እንደሚለው መሠረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 12/ለ-2 መሠረት ሊፀና ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1.የደቡብ ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2 /ለ/ 2 መሠረት ፀንቷል፡፡

2. በአመልካች ላይ የተወሰነው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 77989

ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ለይኩን ብርሃኑ - ከጠበቃ አቶ ፍቅሬ ሞያ ጋር ቀረቡ

2. አቶ ምትኩ አብሹ - ጠበቃ ታደሰና መቶ

አለቃ ሽፈራው አመኑ ቀረቡ

3. አቶ ጌታሁን አስማረ - ጠበቃ አቶ ውብሸት ክብሩ ቀረቡ

4. አቶ ቸርነት ዋጋሪ - ጠበቃ አቶ ኃ/ማርያም ኃይሉ ቀረቡ

5. አቶ እንዳለ ቴኒ - ጠበቃ አቶ ውብሸት ክብሩ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐ/ህግ - አቶ አድማሱ አለማየሁ ቀረቡ

አንደኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77586 ፣ ሁለተኛ አመልካች በዚህ መዝገብ ማለትም በመዝገብ ቁጥር 77989 ፣ ሶስተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78427 ፣ አራተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77675 እና አምስተኛው አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78428 ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ አጣምረን በማየትና በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች ከላይ ቁጥራቸው በተገለፁት የሰበር መዛግብት የፌዴራል የመጀመሪያው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማፅናቱ መሰረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት በተናጠል ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በአመልካቾችና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ባልሆኑ ሌሎች አምስት ተከሳሾች ላይ መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፎ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ፣ አመልካቾች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 703

የተመለከተውን በመተላለፍ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የስራ አመራር በመሆን በተለያየ ደረጃ በሚሰሩበት ወቅት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከኦክቶበር 2009 ዓ.ም እና ዲሴንበር 2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ጉድለት በመፈፀም በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት የቀረበው የወንጀል ክስ ሲሆን ዝርዝሩም ሲታይ የሚከተለው ይዘት ያለው ነው፡፡

1. በሥር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆኑት አንደኛው አመልካች አቶ ለይኩን ብርሃኑ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲሰራ በለገሀር ቅርንጫፍ ፣ በአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ፣ በሀብተ ጊዮርጊስ ቅርንጫፍና ፣ በመርካቶ ቅርንጫፍ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ከውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድ ፣ አሰጣጥ ፣ አጠቃቀምና አጠያየቅ ጋር በተያያዘ የተፈፀመው ወንጀሎች እያወቀ በአዋጅ ቁጥር 592/2000 ዓ.ም በሚጥስ ሁኔታ የውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድና አጠቃቀም እንዲካሄድ በማድረግና የግል ባንኮች መያዝ ፣ የሚገባቸውን የውጭ ምንዛሬ መጠን በተመለከተ ከብሔራዊ ባንክ የወጣውን መመሪያ በመተላለፍ የውጭ ምንዛሬ በመያዝ ፣ ማውጣት የሚገባውን የአሰራር ሥርዓትና መመሪያ ባለማውጣት የወጡ ፣ መመሪያዎች ሲጣሱ የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ ፣ የውጭ ምንዛሬ ደንበኞች ተራ ቅደም ተከተል ሊጣስና በቅድሚያ የውጭ ምንዛሬ ሊሰጣቸው የማይገቡ ግለሰቦች እያወቀ ባለመስተካከሉና የባንኩ ቋሚ ሰራተኞች የውጭ ምንዛሬ ሲወስዱ እያየ እርምጃ ባለመውሰድ የስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

2. በስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው ሁለተኛ አመልካች አቶ ምትኩ አቦሽ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) ምክትል ፕሬዚዳንት የባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ፣ በለገሀር ቅርንጫፍ ፣ በአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ፣ በሀብተጊዮርጊስ ቅርንጫፍ እና በመርካቶ ቅርንጫፎች በውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድና አሰጣጥ የተፈፀሙ ጉድለቶችን ባለመስተካከሉና በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ያለ ኮሚቴው ፈቃድ በግል ትዕዛዝ የውጭ ምንዛሬ ግኘ ፈቃድ በመስጠት ፣ የውጭ ምንዛሬ ያለቅደም ተከተል ለሰዎች እንዲፈቀድላቸው ሲደረግ ባለመስተካከሉ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ እንዲይዝ ከተፈቀደለት የውጭ ምንዛሬ መጠን በላይ 28,974,000 (ሃያ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ሺ.ህ) የአሜሪካን ዶላር ይዞ በመገኘቱና ከዚህ ውስጥ 14,473,000 ዶላር/ብር ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ሣይደረግና ሣይመዘገብ እንዲያዝ ያደረገ በመሆኑ የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው የሚገባቸውን የባንኩን ደንበኞች በመከልከል የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው በማይገባቸው ሰዎች የውጭ ምንዛሬ በመስጠት በስራ አመራር ሂደት ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

3. በስር ፍ/ቤት አምስተኛ ተከሳሽ የሆነው ሶስተኛው አልካች አቶ ጌታሁን አላመረ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ከባንኩ መመሪያ ውጭ የውጭ ምንዛሬ ለግሉ በመፍቀድ ለግል ጥቅሙ በማዋሉና ለባንኩ ደንበኞች በበላይ የስራ ኃላፊዎች የተፈቀደውን የውጭ ምንዛሬ ለሌሎች ላልተፈቀደላቸው ሰዎች በመስጠት በስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

4.በስር ዘጠኛ ተከሳሽ የሆነው አራተኛው ተከሳሽ አቶ ቸርነት ዋጋሪ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ መርካቶ ቅርንጫፍ የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ያልተፈቀደላቸውን ደንበኞች በማስተናገድ ፣ የደንበኞችን የምዝገባ ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ

ያስምዝገባ ተራቸው ሌሎች ግለሰቦች የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኙ በማድረግ በስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

5. በስር ፍ/ቤት ስድስተኛ ተከሳሽ የሆነው አምስተኛው አመልካች አቶ እንዳለ ቴዶ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የውጭ ምንዛሬ የተፈቀደላቸውን የባንኩን ደንበኞች በመከልከል ላልተፈቀደላቸው ግለሰቦች የውጭ ምንዛሬ በመስጠት የስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል ፣ የሚል ክርክር ይዘት ያለው የወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡

ተጠሪ የቀረበው የወንጀል ክስ ኮፒ ለአመልካቾች ደርሷቸው የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን የመጀመሪያ ደረጃ ክስ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ አመልካቾች የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምንም ጥፋተኞች አይደለንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ፣ ተጠሪ ዘጠኝ ምስክሮች በማቅረብ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደረገ ሲሆን የወንጀሉን ድርጊት ያስረዳሉ የሚላቸውን የፅሁፍ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ለምስክርነት አቅርቦ ካሰማቸው ምስክሮች ውስጥ ሁለቱ የአዋሽ ባንክ አክሲዮን ማህበር የአስተዳደር ቦርድ አባላት ፣ ሶስቱ ደግሞ በባንኩ ውስጥ ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ካላቸው አስር ባለሀብቶች የተወከሉ መሆናቸውን ገልጸው ባንኩ በውጭ ምንዛሬ አያያዝ ፣ አፈቃቀድና አጠቃቀም ችግር ያለበት ስለመሆኑ የደረሳቸውን መረጃ ለማጣራት ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ምስክሮች ከቦርድ አባላትና ከባለመብቶች የተወጣጡ ኮሚቴዎች በአንድነት በባንኩ ሥራ አመራር በኩል የተፈፀሙ ተግባራት ሲያጣሩ ፣ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ እንዲያዝ የተፈቀደለት የውጭ ምንዛሬ የካፒታሉ 15% ብቻ መሆን ሲገባው ከዚያ በላይ ዶላር ይዞ መገኘቱንና በዚህ ምክንያት በብሔራዊ ባንክ ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) የተቀጣ መሆኑን፣ ሁለተኛ አመልካች ያለውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ፈቃድ በግሉ ለግለሰቦች ያለተራቸው የውጭ ምንዛሬ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ፣ በአዋሽ ባንክ ለገሀር ፣ አዲስ ከተማ ፣ ሀብተጊዮርጊስ ድልድይና በመርካቶ ቅርናጫፍ የውጭ ምንዛሬ የአፈቃቀድና አጠቃቀም ከፍተኛ ችግር የነበረበት ፣ ተመዝጋቢው ተራ የሚጠብቁ ሰዎች የውጭ ምንዛሬ ሳያገኙ ያልተመዘገቡና የባንኩ ደንበኛ ላልሆኑ ሰዎች የውጭ ምንዛሬ የተሰጠ መሆኑን ፣ አንደኛ አመልካች ይህንን ችግር በማስተካከል ማድረግ የሚገባውን ተግባር ያለመፈፀሙንና ለችግሩ መከሰት አመልካቾች የነበራቸውን ሚና በመዘርዘር መሥክረዋል፡፡ ምስክሮቹ አንደኛ አመልካች ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱና ማውጣት የሚገባውን መመሪያ ባለመወጣቱ ሁለተኛው አመልካች በኃላፊነት የተሰጠውን ተግባር በአግባቡ ካለማውጣቱ በተጨማሪ ዳንኤል ለተባለ የባንኩ ሰራተኛ ለእሱ ፀሐፊ የውጭ ምንዛሬ እንዲወስዱ ፈቅዶ የተገኘ መሆኑን ባደረጉት ማጣራት እንደተገነዘቡ የመሰከሩ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ዘጠነኛ ምስክር የባንኩ ኢንስፔክሽን መምሪያ ኃላፊ ሲሆኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸውን ስድስተኛ ሰባተኛና ስምንተኛ ምስክሮች የባንኩ ኢንስፔክሽን ሰራተኞች መሆናቸውን ገልጸው፣ ተጠሪ በወንጀል ክሱ በገለጸው ጊዜ ውስጥ በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መመሪያና በለገሀር ፣ አዲስ ከተማ ፣ ሀብተጊዮርጊስ ድልድይና መርካቶ ቅርንጫፍ የውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድና አጠቃቀም በማጣራት የፅሑፍ ሪፖርት እንዳቀረቡ ገልፀው አንደኛው አመልካች በውጭ ምንዛሬ በመፍቀድ ያልተሳተፉ መሆኑንና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሲያጋጥም ሁለተኛ አመልካች ሰብሳቢ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩትና በዚህ ክርክር

ተሳታፊ ያልሆኑት የኮሚቴው አባል ሆነው የውጪ ምንዛሬ ኮሚቴ መቋቋሙን ፣ ነገር ግን በመምሪያውና በአራቱ የባንኩ ቅርንጫፎች የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ከፍተኛ ችግር የነበረበት መሆኑን እንዳረጋገጡ ምስክሮች ለሥር ፍርድ ቤት ከሰጡት የምስክርነት ቃል ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሮቹ በመምሪያውና በአራቱ ቅርንጫፎች ያለውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ውሣኔ ለሁለተኛ አመልካች ለሶስተኛ አመልካች ለአራተኛ አመልካችና ለአምስተኛ አመልካች የውጭ ምንዛሬ ሰጥተው ያገኙ መሆኑን ፣ ሁለተኛው አመልካች ያለውጭ ምንዛሪ ኮሚቴ ውሣኔ በግሉ በርካታ የውጪ ምንዛሬ መፍቀጃ ቅፆች ላይ ፈርሞ ያገኙት መሆኑና መምሪያውና አራቱ ቅርንጫፎች የውጭ ምንዛሬ በማግኘት ተመዝግበው ተራ ለሚጠብቁ ደንበኞች የውጪ ምንዛሬ ሣይሰጡ ተመዝግበው ተራ ላልያዙና የባንኩ ደንበኛ ያልሆኑ ሰዎችን በማስቀደም የውጭ ምንዛሬ የሰጡ መሆኑን እንዳረጋገጡ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማስረዳት ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ሁለተኛው አመልካች የውጪ ምንዛሬ ካሚቴ ውሣኔ ሳይሰጥበት በግሉ 9,280,755 /ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ አምስት /የአሜሪካን ዶላር 2,938,535 ዩሮ /አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሰላሣ አምስት / ዮሮ እና 50,060/ ሃምሣ ሺህ ስልሣ / የእንግሊዝ ፖዉንድ የፈቀደ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑንና የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ለገሀር ቅርንጫፍ ከፈቀደው 6,196,760.88 /ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ስልሣ/ የአሜሪካን ዶላር ውስጥ 2,125,725.04 /ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ከዜሮ አራት/ የአሜሪካን ዶላር አለመከፈሉን ሶስተኛ አመልካች ሥራ አስኪያጅ አምስተኛው አመልካች የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆነው ሲሰሩበት የነበረው የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ለሶስተኛ አመልካች የንግድ ድርጅት የፈቀደው 426,792/አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሁለት/ የአሜሪካን ዶላር አለመከፈሉን አራተኛው አመልካች የውጪ ንግድ ክፍል ኃላፊ በመሆን ሲሰራበት የነበረው መርካቶ ቅርንጫፍ ከፈቀደው የውጪ ምንዛሬ 299,760 /ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሥልሣ የአሜሪካን ዶላር / አለመከፈሉን በአጠቃላይ በዚህ ሂደት ብር 3,154,328 /ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሣ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ስምንት የአሜሪካን ዶላር በህገ ወጥ መንገድ በውጭ ምንዛሬ ተሰጥቶ ለባንኩ ያልተመለሰ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ በዚህ ወንጀል በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆኑትና ተከሣሾች ስማቸው ከተራ ቁጥር 2 እስከ ተራ ቁጥር 5 የተገለፀው አመልካቾች ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሰነድ ማስረጃው እንደሚጠቁም ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካቾች በተጠሪ የወንጀል ክስ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ተጠሪ ያቀረበ መሆኑን በመግለፅ አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሥር ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 142 መሠረት ብይን ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን መሠረት አንደኛ አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ያልፈፀሙና በኃላፊነትም ልጠየቅ የማይገባኝ መሆኑን ያስረዱልኛል ያሏቸውን አራት የመከላከያ ምስክሮች አቅርበው ያስመሰከሩ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ እንደዚሁም አንደኛ አመልካች የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት እንዳቀረቡ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው ውስጥ አስፍሮታል፡፡ ሁለተኛው አመልካች በበኩሉ በነበረው ኃላፊነት የፈፀማቸው ተግባራት የሥራ አመራር ጉድለት አለመሆናቸውን የሚያስረዱ ሶስት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ያሰማ መሆኑንና የሰነድ ማስረጃ የቀረበ መሆኑን ሶስተኛና አምስተኛው አመልካች በጋራ አምስት የመከላከያ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃ በመከላከያ

ማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ፣ አራተኛው አመልካች አራት የመከላከያ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ከሥር ፍርድ ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኋላ አንደኛ አመልካች በባንኩ ኃላፊና የሥራ መሪ ሆነው እያለ ሥራዎችን ለሁለተኛ አመልካች በውክልና ከሰጡ በኋላ የተለያዩ ችግሮች እየተፈጠረ ስለመሆኑ ጥቆማ የደረሳቸው መሆኑንና ሀሜትና አሉባልታ ናቸው እያለ በማለት በዝምታ በማለፍ በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና በአራቱ ቅርንጫፎች በተከሰተው ብልሹ አሠራር ምክንያት በባንኩ ላይ ለደረሰው ጉዳት በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የመቆጣጠር የመከታተልና የባንኩን ሥራ የመምራት ኃላፊነት ባለመወጣቱ ተጠሪ /ዐቃቤ ሕግ / በወንጀል ክሱ የተገለፀውን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000/አስር ሺህ ብር / መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ክሱ የዘረዘራቸው የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ችግሮችን የፈፀሙ መሆኑን በሰውና በፅሑፍ ማስረጃ ያረጋገጠበት በመሆኑና ሁለተኛው አመልካች ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ይህንን የማያስተባበል መሆኑን ገልፆ ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000/አስር ሺህ ብር መቀጮ/ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ሶስተኛ አመልካችና አምስተኛው አመልካቾች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው በማለት በሁለት ዓመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራትና በብር 15,000/አስራ አምስት ሺህ ብር/ እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን አምስተኛው አመልካች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው ብሎ በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000/አስር ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተናጠል በተለያዩ መዝገቦች አቅርበዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ አንደኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77586 የሰበር አቤቱታ አቅርበው ተጠሪ በሰበር አቤቱታው መልስ የሰጠበት ሲሆን ሁለተኛው አመልካች በዚህ መዝገብ ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሶስተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78427 ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ፣ አራተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77675 ላቀረበው የሰበር አቤቱታና አምስተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78428 ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በዚህ መዝገብ በማጠቃለል ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች በየግላቸው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በተለያዩ መዝገቦች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ይዘት ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች ሆነ ብለንና አስበን የአዋሽ ኢንተርናችናል ባንክ /ኢ.ማ/ ላይ ጉዳት ለማድረስ የፈፀመነው የወንጀል ድርጊት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር ላይ የደረሰ ጉዳት መሆኑ በተጠሪ ማስረጃ አልተረጋገጠም አንድ ሰው በወንጀል የሚጠየቀው የግዙፍ ተግባር የሞራልና የህግ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ መሆኑን በወንጀል ህጉ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ይህ ሰበር ችሎት

በተመሣሣይ ጉዳይ ከዚህ በፊት አስገደጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካቾች የፈፀምነው ግዙፍ የወንጀል ድርጊት ያለ መሆኑና የወንጀል ሃሣብ / ሞራላዊ ሁኔታ መኖር ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ እኛ ፈፅምነው በተባለው ድርጊትና በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ / አ.ማ/ ላይ ደርሷል በሚለው ጉዳት መካከል የድርጊትና የውጤት ግንኙነት መኖርን አላስረዳም፡፡ አመልካቾች በተጠሪ የቀረበውን ክስና ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃችን አስተባብለን እያለን ጥፋተኛ መባላችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከአመልካቾች ጋር ተመሣሣይ ወንጀል ድርጊት ፈፅማችኋል ተብለው የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው ተከሣሾች ላይ ያስተላለፈውን የቅጣት ውሣኔ ሲገድብ በእኛ ላይ የወሰነው የቅጣት ውሣኔ አለመገደቡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን የሚል ይዘት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች ሆነ ብለው ጊዚያዊና ሠው ሠራሽ የውጪ ምንዛሬ እጥረት እንዲፈጠር ድርጊቱን መፈፀማቸው በሰውና በፅሑፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ አመልካችም ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ባለማድረግና የባንኩ የበላይ አመራር በመሆናቸው መፈፀም የሚገባቸውን ተግባር ያልፈፀሙ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በባንኩ ላይ የደረሱትን ጉዳት በገንዘብ በሚተመን መንገድ ብቻ ሣይሆን በባንኩ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ አልተሟላም በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት የሰውና የጽሑፍ መከላከያ ማስረጃ በተጠሪ በኩል የቀረበውን የወንጀል ክስና በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጠውን የወንጀል ድርጊት ለማስተባበል የማይችል መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ክስ ከመቅረቡ በፊት ዐቃቤ ህግ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42(1)ሀ መዝጋቱን እንደመከላከያ ያቀረቡት ቢሆንም ማስረጃ ሲገኝ ዐቃቤ ሕግ ክስ ለማቅረብ የሚከለክለው የህግ ድንጋጌ ባለመኖሩ ክስ ማቅረባችንና የሥር ፍርድ ቤትም ማስረጃችንን መዝኖ የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ በአግባብ ነው፡፡ አመልካቾች ሌሎች ተከሣሾች በገደብ መለቀቃቸውን የሰበር መከራከሪያ ሃሣብ አድርገው ማቅረባቸው የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ያነሷቸውን የመከራከሪያ ሃሣቦች የሚያጠናክር የመልስ መልስ በተናጠል አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካቾችና ተጠሪ በፅሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማጽናቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በማስረጃ እንዳረጋገጣቸውና አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃ እንዳላስተባበሏቸው በመግለፅ በውሣኔቸው ያስፈሯቸውን ፍሬ ጉዳዬች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

1. ተጠሪ በወንጀል ክስ ማመልከቻው በገለፀው ጊዜ ውስጥ ማለትም እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር ከኦክቶበር 2009 ዓ.ም እስከ ዲሴንበር 2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በአገር ደረጃ የውጭ ምንዛሬ እጥረት የነበረ መሆን ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ ባንኮች በቅደም ተከተል የውጭ ምንዛሬ ለደንበኞቻቸው የሚፈቅዱበትና የሚለቁበት ሥርዓት በመዘርጋት በቅደም ተከተል የማስተዳደር ኃላፊነት የነበረባቸው ቢሆንም የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና የለገሀር ቅርንጫፍ ፣ የመርካቶ ቅርንጫፍ ፣ የአዲስ ከተማ

ቅርንጫፍና የሀብተ ጊዮርጊስ ቅርንጫፍ በውጭ ምንዛሬ ለተመዘገቡ እና ተራ ለሚጠብቁ ሰዎች ሣይሰጡ ላልተመዘገቡትና የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው ለማይገቡ ሰዎች ጭምር የሰጡ መሆኑን ፣ በዚህም ባንኩ ለደንበኞቹ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ችግር የተፈጠረና መልካም ስምና ዝናው የተጐዳ የባንኩም ደንበኞች የሸሹት ስለመሆኑ ከባንኩ አስተዳደር ቦርድ እና በባንኩ ከፍተኛ አክሲዮን ድርሻ ካላቸው አስር ባለሃብቶች ተወክለው ሁኔታውን ያጣሩ የተጠሪ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባንኩ ኢንስፔክሽን ክፍል ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በገለፀው ጊዜ ውስጥ በውጭ ምንዛሬ አጠቃቀም ፣ ፈቃድ ላይ በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና በአራቱ ቅርንጫፎች ከፍተኛ ችግር የፈፀሙና በህገ ወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሪ ሊሰጣቸው የማይገባቸው ሰዎች የተሰጠ መሆኑን እንዳረጋገጡ፣

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲይዝ ከፈቀደለት በላይ ከብሔራዊ ባንክ እውቅና ውጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ መገኘቱና በዚህም ጥፋቱ በብሔራዊ ባንክ ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) የተቀጣ መሆኑ ፣ ሁለተኛው አመልካች ዳንኤል ለተባለ የባንኩ ሠራተኛና ለፀሐፊው ከህግ ውጭ የውጭ ምንዛሬ የሰጠ መሆኑ ፣ ሶስተኛ አመልካች ለግል የንግድ ድርጅት ለሌሎች ሰዎች የተፈቀደ የውጭ ምንዛሬ ወጭ አድርጐ የሰጠ መሆኑና በዚህ ድርጊት አምስተኛው አመልካች ሙሉ ተከፋይና ተባባሪ የነበረ መሆኑን ፣ አራተኛው አመልካች ለውጭ ምንዛሪ ላልተመዘገቡና ተራ ላልያዙ ሰዎች በቅድሚያ እንዲያገኙ ያደረገ መሆኑን እና  የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው ለማይገባቸው ሰዎች የሰጠ መሆኑ ፣ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) በለገሀር ቅርንጫፍ በመርካቶ ቅርንጫፍ ፣ በሀብተጊዮርጊስ ድልድይ ቅርንጫፍና በአዲስ ከተማ መጠኑ በርካታ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ወጭ አድርጎ ከሰጠ በኋላ የሒሳብ ምርመራ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ያልተከፈለው መሆኑ ፣ ከላይ በዝርዝር በታዩት የሥር አመራር ጉድለት ለደረሱ ጉዳቶች አመልካቾች ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል በቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መረጋገጡን በአመልካቾች በኩል የቀረበው የፅሑፍ የመከላከያ ማስረጃ ከላይ የተዘረዘሩት የሥራ አመራር ጉድለቶች በአመልካቾች ያልተፈፀሙ መሆናቸውን የማያሣዩ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

2. በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና በአራቱ ቅርንጫፎች የውጭ ምንዛሬ አያያዝ ፤ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ላይ ተፈፅመዋል የተባለ ችግሮች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ናቸው ካለን በማስከተል የሚነሣው ጥያቄ እነዚህ ችግሮች በወንጀል ህጉ በተዘረዘረው ግዙፍ ተግባር ውስጥ የሚካተቱና አመልካቾችን በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርጉ ናቸው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመመለስ በመጀመሪያ በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ የተፈፀመ ጉዳት የማድረስ ወንጀል መሠረታዊ ይዘት የሚዘረዝረውን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ ሰው ጥቅም የሥር አመራር ላይ የተፈፀመ ጉዳት የሚል ርእስ ያለው የወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ሶስት የተለያዩ ይህንን ወንጀል የሚያቋቁሙ ሁኔታዎችን የሚደነግግ ሲሆን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 1 " ማንም ሰው በሕግ ወይም በውል ግዴታ የሌላን ሰው ንብረት ጥቅም እንዲጠብቅ ወይም ሥራውን እንዲመራ በሕግ ወይም በውል ግዴታ አደራ ተቀብሎ በተሰጠው ሃላፊነት አላግባብ በመገልገል ወይም የተጣለበትን ግዴታ ባለመፈፀም በሚጠብቀው ንብረት ጥቅም ላይ ወይም ለሚሠራበት ድርጅት በሚፈጽመው አገልግሎት ላይ አስቦ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ " በወንጀል ኃላፊ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ

702 ንዑስ አንቀጽ 2 " ድርጊቱ በቸልተኝነት የተፈፀመ እንደሆነ " በወንጀል ኃላፊ እንደሚሆን የሚደነግግ ሲሆን፣ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 3 " ተከሣሹ ወንጀሉን የፈፀመው የንብረት ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ እንደሆነ " ለወንጀል ኃላፊ እንደሚሆን ደንግጓል፡፡ በመሠረታዊነት አንድ ሰው በሌላው ሰው ጥቅም ሥራ አመራር ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በወንጀሉ ኃላፊና ተጠያቂ የሚሆነው ከላይ ከዘረዘርናቸው ሶስት ሁኔታዎች አንደኛውን ወይም ሁለቱን ወይም ሁሉንም ድርጊቶች ፈጽሞ ሲገኝ እንደሆነ የወንጀሉን መሠረታዊ ይዘትና ባህሪ ከሚዘረዝረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 702 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ የጠቀሰው እና አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 703 በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 702 ከተደነገጉት 3 ድንጋጌዎች አንደኛውን በመተላለፍ ወንጀል የተፈፀመ መሆኑ ሲረጋገጥ ወንጀሉ ከብዶ የሚታይበትንና በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችልበትን ሁኔታ የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የወንጀል ህግ አንቀጽ 702 የተዘረዘሩት ወንጀሎች የማክበጃ ሁኔታዎችን የሚዘረዝር ድንጋጌ ሲሆን አንደኛው የማክበጃ ምክንያት አመልካቾች በተከሰሱበትና ጥፋተኛ ሆነው በተገኙበት በወንጀል ህጉ 703 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተደነገገው ነው፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 703 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ ቃል በቃል ሲነበብ ፣ "ወንጀሉ የተፈፀመው በተሰጠው ሥልጣን ሥራውን በማከናወን ላይ በሚገኝ ፣ ወይም በተለይ ታማኝነት በተሰጠው ሞግዚት ፣ ጠበቃ ፣ ውል አዋዋይ ፣ የባንክ ሠራተኛ ፣ የንብረት አስተዳዳሪ ወይም የሒሳብ አጣሪ ወይም ሹመት ሥልጣን ባገኘ ወይም የተለየ እምነት በተጣለበት ማንኛውም ሌላ ሰው የሆነ እንደሆነ ወይም የዚህ ዓይነት ተመሣሣይ ኃላፊነት በተሰጠው በማንኛውም ሰው እንደሆነ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል " የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የሚከብደው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውንና ሆነ ተብሎ የተሠራውን ወንጀል ወይም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንኡስ አንቀጽ 3 ለራስ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ታስቦ የተሰራው ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘረውን ወንጀል ብቻ የሚያካብድ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ድንጋጌው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀውንና በቸልተኝነት የተሰራን ወንጀል የሚያከብድ በአጠቃላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 የተዘረዘሩትን ሦስት የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሞች የሚያከብድ ድንጋጌ መሆኑ " ከባድ ሁኔታ " ከሚለው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 703 ርዕስና ከድንጋጌው አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ካየነው አንደኛ አመልካች የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ/አ.ማ/ ፕሬዝዳንት ሆነው ሲሰሩ በኃላፊነታቸው ማድረግ የሚገባቸውንና ጥንቃቄ ባለማድረግ፣ መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በወቅቱ ባለመውሰድ በባንኩ ሥራ አመራር ላይ ጉዳት ያደረሱ በመሆናቸው ፣ ይህንን ተግባር ሆነ ብለው አልፈፀሙትም ቢባል እንኳን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ በቸልተኝነት የተፈፀመን ወንጀል አክብዶ የሚደነግገው በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች 1ኛ አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 የተዘረዘውን የግዙፍ ተግባር ፣ የሃሳብና የሕግ ሁኔታውን የሚያሟላና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛ አመልካች የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የአለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ኃላፊና የባንኩ የውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ ሲሰራ ያለኮሚቴው ፈቃድ በግሉ የውጭ ምንዛሬ በመፍቀድ

ኃላፊነቱን አላግባብ የተገለገለ መሆኑና ዳንኤል የተባለ የባንኩ ሠራተኛና በወቅቱ ፀሐፊው የነበረችውን ሴት ለመጥቀም በማሰብ አላግባብ የውጭ ምንዛሬ የፈቀደላቸው በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘረውን ግዙፍ የወንጀል ተግባር የፈፀመና የወንጀል ሞራላዊ ሁኔታ የተሟላ በመሆኑ ይህንን ወንጀል በሚያከብደው በወንጀል ሕግ ቁጥር 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች የሶስተኛው አመልካች የግል ጥቅም ለማግኘት ሲል ለራሱ የንግድ ድርጅት ለሌሎች ሰዎች የተፈቀደ የውጭ ምንዛሬ ለሶስተኛው አመልካች የንግድ ድርጅት እንዲወስድ ማድረጋቸው ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑና ሌሎች ግድፈቶችን መፈፀማቸው ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚሸፈን በመሆኑና ይህንን ወንጀል በሚያከብደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ መሆኑ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ አራተኛው አመልካች በመርካቶ ቅርንጫፍ የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ በውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ላይ ከፍተኛ ችግር ከፈጠሩት የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች አንደኛው እንደነበር የተረጋገጠበት በመሆኑና ወንጀሉን ሆነ ብዬ አልሰራሁትም ቢልም አድራጎቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚሸፈን በመሆኑ ይህንን ወንጀል በሚያከብደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ ስንመለከተው አመልካቾች በተለያየ የሀሳብ ሁኔታ ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑንና ከተለያየ የወንጀል ሃሳብ የተፈፀሙትን አድራጎቶች አጠቃልሎ በሚይዘውና በሚያከበደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌ ይዘትና መሠረታዊ ባህሪ ያገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡

3. የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ በሚደርስ መቀጮ የሚያስቀጣ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በአመልካቾች በኩል ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችና በተጠሪ በኩል የቀረበውን የቅጣት አስተያየት በመመርመርና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት በማድረግ የቅጣት ውሣኔውን የሰጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን መሠረት ያደረገ ፣ የአመልካቾችን የወንጀል አፈፃፀምና ግላዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት በተመሣሣይ ሁኔታ በወንጀል ተከስሰው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ተከሳሾች ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ የገደበው ሲሆን በእነሱ ላይ ቅጣቱ እንዲፈፀም የሰጠው ውሣኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 190 እና አንቀጽ 192 ድንጋጌ መሠረት ያላደረገ መሆኑን በመዘርዘር በሰበር አቤቱታቸው ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔውን የገደበላቸው ተከሳሾች የቅጣት ውሣኔው ሊገደብላቸው የሚገባቸው ነበሩ ወይስ አልነበሩም በሚለው ነጥብ ተጠሪ የሰበር አመልካች ሆኖ ያልቀረበ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት የሚያየውና የሚመረምረው ነጥብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሆኖም አመልካቾች የቅጣት ውሣኔው ሊገደብልን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በሕጉ ሰፊ ፈቅድ ሥልጣን የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት ያልተቀበለው በመሆኑና ይህንን መከራከሪያ

ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾችን ቅጣት ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ያልሰጡበትና በአንፃሩ የአመልካቾችን ቅጣት ሊፈፀም ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ ያፀደቀው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በእኛም በኩል የቅጣቱ መፈፀም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 በሁለተኛው ፓራግራፍ የተቀመጠውን ግብ የሚያሳካ በመሆኑና ቅጣቱን ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተሟልተዋል የሚለው ክርክር የሕግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ ስላላገኘነው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች የተወሰነባቸውን የቅጣት ውሣኔ እንዲፈፅሙ የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ የተደነገገውን በመተላለፍ በተለያየ የሥራ ኃላፊነት ተመድበው ሲመሩት በነበረው የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ/አ.ማ/ የሥራ አመራር ጥቅም ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/-2 መሠረት አፅንተነዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች አቶ ለይኩን ብርሃኑ ፣ ሁለተኛ አመልካች አቶ ምትኩ አበሹና አራተኛው አመልካች አቶ ቸርነት ዋጋሪ እያንዳንዳቸው በዚህ ጉዳይ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሶስተኛው አመልካች አቶ ጌታሁን አስማረና አምስተኛው አመልካች አቶ እንዳለ ቴኒ በዚህ ጉዳይ ተጠርጥረው እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራትና በብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 77592

ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ተካልኝ ጌታቸው - አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- የፌ/ዐ/ሕግ - አቶ አበባው መንግስቱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ የአሁኑን አመልካችን ጨምሮ በ6 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም በ5ኛ ክስ 5ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ተከሳሾቹ በኢ/ፌ/ዲሪ/ወ ህግ አንቀጽ 32(1)(ለ) እና 692(1) በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት በማሰብ ለወንጀሉ አፈፃፀም እንዲረዳ ሌላ ያልተያዘ አባሪያቸው ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በ1ኛ ክስ የተጠቀሰውን ቼክ አመነዛዘር ላይ በመመካከር ለዚሁ ይጠቅማል ያለውን 3ኛ ተከሳሽን ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በማገናኘት፣ 3ኛ ተከሳሽ 4ኛ ተከሳሽን ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር እንዲገናኝ በማድረግ፣ እንዲሁም 4ኛ ተከሳሽ 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾችን ከ1ኛና 2ኛ ተከሳሾች ጋር አገናኝቶ በ6ኛ ተከሳሽ አማካይነት በቼኩ ላይ የተጠቀሰው ገንዘብ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ ወደ ወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ በ6ኛ ተከሳሽ በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሳብ እንዲተላለፍ ከተደረገ በኋላ 3ኛ ተከሳሽ ብር 100,000፣ 4ኛ ተከሳሽ ብር 100,000 እና 5ኛ ተከሳሽ ብር 50,000 ወስደው ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በመላ ሀሳባቸው እና አድራጎታቸው በወንጀል ድርጊት እና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት የማታለል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካችም ወንጀሉን አለመፈፀሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ ክሱ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በሰጠው ፍርድ 5ኛ ተከሳሽ ከባንኩ ተጭበርብሮ ከወጣው ብር 750,000 ውስጥ ብር 50,000 መውሰዱን ለፖሊስ የተከሳሽነት ቃሉን ሲሰጥ በቦታው የነበሩ የከሳሽ የደረጃ ምስክሮች መስማታቸውን ያረጋገጡ ሲሆን የተከሳሹ የመከላከያ ምስክሮች ደግሞ የተከሳሽ ቤት ሲበረበር ከማየታቸው በስተቀር ተከሳሹ ወንጀሉን አለመፈፀሙን አላስረዱም በሚል በወ/ሕ/ቁ/ 692 (1) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በ3 ዓመት እስራትና በ5,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(2)(ለ)(2) መሰረት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ፍርድ በማጽናቱ አመልካች በከፍተኛው ፍ/ቤት ፍርድ እና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

• ክሱን ባቀረብኳቸው የመከላከያ ምስክሮች አስተባብዬ እያለሁ ፍርድ ቤቶቹ ማስረጃዎቼን በአግባቡ ሳይመዝኑ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፉብኝ ተገቢነት ያለው አይደለም

• በወንጀሉ አመልካች አግኝቷል በሚል በማስረጃ የተረጋገጠው ብር 50,000 ሆኖ ከተረጋገጠው ውጪ ብር 250,000 እንደወሰድኩ ተቆጥሮ ከቅጣትና መቀጫ እርከን መነሻው በማጋነን በተሳሳተ ስሌት የተወሰነብኝ ስለ ቅጣት አወሳሰን የወጣውን መመሪያ ያልተከተለ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪ መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል በተባለው ጭብጥ መነሻ በሰጠው መልስ፡- አመልካች የተከሰሰውና ጥፋተኛ ሆኖ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በአታላይነት ወንጀል በወ/ህ/አንቀጽ 692(1) ስር ሲሆን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻለው ወንጀሉ ለራስ ተገቢ ያለሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ አመልካችም በፈጸመው ወንጀል ለራሱ የደረሰው ጥቅም ብር 50,000 ቢሆንም ሌሎች በወንጀሉ የተሳተፉትም ቀሪውን ገንዘብ ተከፋፍለው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ በመሆኑ ምክንያት ድርጅቱ ያጣው ብር 750,000 ስለሆነ አመልካችም ራሱ ጥቅሙን ከማግኘቱም ባሻገር ሌሎችም ጥቅም እንዲያገኙ ሀሳብ የነበረው በመሆኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ሌሎች ተከሳሾች ያገኙትን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ጭምር የወሰነ ስለሆነ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም ከፍተኛው ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ወደ ተያዘው ጭብጥ ከመመለሳችን በፊት አመልካች ለዚህ ችሎት ካቀረባቸው ቅሬታዎች አንዱ ክስ የቀረበበትን ወንጀል አለመፈጸሜን በመከላከያ ምስክሮቼ አስተባብዬ እያለሁ ፍርድ ቤቶቹ የግራቀኙን ማስረጃዎች በአግባቡ አልመዘኑም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በማመዛዘን የተጠሪ ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የአመልካች የመከላከያ መስረጃዎች ማስተባበል ባለመቻላቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፋቸውን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የማጣራት ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች በተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መነሻ በተሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተፈፀመውን ስህተት ከሚያርም በስተቀር የፍሬ ጉዳዮች እንደገና ሊያጣራ የሚችልበት ወይም በስር ፍ/ቤቶች የተሰሙትን ማስረጃዎች የሚመዝንበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ወደ ጭብጡ ስንመለስ አመልካች የሚከራከረው ወስዷል ከተባለው የገንዘብ መጠን አንጻር ቅጣቱ የቅጣት አፈፃፀም መመሪያን የተከተለ አይደለም በሚል ሲሆን ይህንኑ የአመልካችን ክርክር አመልካች ጥፋተኛ ነው ተብሎ የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት የወ/ህ/አንቀጽ 692(1) አንጻር መመርመሩ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1) እንደተደነገገው ማንም ሰው የማይገባውን ብልጽግና ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ ራሱን ወይም የሶስተኛውን ወገን ንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት እንዲፈጸም ማድረጉ

የተረጋገጠ እንደሆነ የአታላይነት ወንጀል ፈፅሟል ለማለት የሚቻል ይሆናል። በዚህ በተያዘው ጉዳይም አመልካች የግል ተበዳይ የሆነውን የሙገር ሲሚንቶ ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኢንተርፕራይዝ ማህበርን ገንዘብ ከሌሎች ወንጀል ፈጻሚዎች ጋር በመሆን በፈጸመው የማታለል ተግባር ገንዘቡ ከተቀመጠበት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጠመንዣ ያዥ ቅርንጫፍ ወደ ወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ ብር 750,000 እንዲዛወር በማድረግ ከዚሁ ከተዛወረው ገንዘብ ውስጥም የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ ተከፋፍለዋል።

በክፍፍል ከደረሰው ገንዘብ ውስጥም አመልካች የወሰደው ብር 50,000 መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በድንጋጌው መሰረትም ይህን ገንዘብ ለግል ጥቅሙ አውሎታል ተብሎ ይወሰዳል። በዚሁ የወንጀል ድርጊትም ሌሎች ተከሳሾች ጭምር ጥቅም እንዲያገኙ አድርጓል። በመሆኑም አመልካች ወንጀሉን የፈፀመው ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የነበሩት ሌሎች ተከሳሾችም ጥቅም እንዲያገኙ በሚል ስለሆነ ወንጀል የመስራት ሀሳቡ ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ብቻ በሚል የተሰራ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም። በመሆኑም የቅጣቱ መጠንም ራሱ በወሰደው የገንዘብ መጠን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ወንጀል ለመስራትና ውጤቱን ለመቀበል በመስማማት ሆነ ብሎ ከፈጸመው የወንጀል ድርጊት ከባድነት አንጻር ሊሆን ይገባል።

በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት በጠቅላላው ከግል ተበዳይ ማህበር በተወሰደው የገንዘብ መጠን መሰረት የቅጣት ውሳኔ በአመልካች ላይ ያስተላለፈው እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያፀናው ተገቢና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 95136 በቀን 28/07/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 67826 በቀን 03/04/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(2)(ለ)(2) መሰረት አጽንተናል።
2. አመልካች ላይ በጠቅላላው ከተበዳይ ማህበር በማታለል ወንጀል በተወሰደው የገንዘብ መጠን የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በአግባቡ ነው ብለናል። ስለሆነም ጥፋተኛ ነው በተባለበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1) ስር በ3 ዓመት እስራትና በብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) እንዲቀጣ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል።

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 67408

ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ፋሲል በላይነህ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - አደናይ ተ/ብርሃን ቀረቡ

መዝገቡ ተመረምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በሕግ አግባብ የተወከለ ሰው በውክልና ስልጣኑ ከወካዩ የተረከባቸውን ንብረቶች ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ ሲረጋገጥ በወንጀል የሚጠየቅበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ የተጀመረ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል መቅጫ ሕግ አንቀጽ 676(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ሚያዚያ 23 ቀን 2002 ዓ.ም. ሰዓቱ በውል በማይታወቅበት በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ስጋ መደዳ አከባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሪት አዲስ አያል የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ/ም ውክልና ሰጥታው በውክልና መሰረት የንግድ ድርጅት ለሁለት አመት ኮንትራት ይዞ ሲሰራ፡- 1ኛ/ የቤት ኪራይ አስራ ስምንት ሺህ ብር፣ 2ኛ/ ቪዲዮ ካሜራ አስራ ሁለት ሺህ ብር የሚያወጣ፣ 3ኛ/ አንድ ብርድ ልብስ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር የሚያወጣ፣ 4ኛ/ የተለያዩ ንብረቶች ግምታቸው አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሁለት ብር የሚያወጡ በአጠቃላይ ግምት ብር 48,000.00 (አርባ ስምንት ሺህ ብር) የሚያወጡ ንብረቶችን ተረክቦ መልስ ሲባል አልመልስም በማለት በፈጸመው ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ አመልካች ጉዳዩ የፍትሓብሔር እንደመሆኑ መጠን በወንጀል የሚጠየቁበት አግባብ የለም በማለት የክስ ተቃውሞ አቅርበው የነበሩ ሲሆን ይኸው ተቃውሞ ውድቅ ሆኖ ግን ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ የክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ካሰማ በኋላ አመልካች የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት የመከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ክስ በቀረበበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በአምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ አሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውን ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የፍትሓብሔር ጉዳይ ከሚሆን በስተቀር በወንጀል የሚያስጠይቅበት አግባብ የለም፣ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክሱ አላስረዱም፣ የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገውም ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ቀርቦ በጽሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው በመሆኑ በሰበር ችሎት የሚታይ አይደለም፣ ቅጣቱም ለድርጊቱ ተመጣጣኝና የቅጣት መመሪያውን መሰረት አድርጎ የተሰጠ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀጽ 24፣ 57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት መውሰዳቸው የተረጋገጠውን ንብረት ግምቱ በአቃቤ ሕግ ክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውን ያህል ባይሆንም በወኪልነት ስልጣናቸው ከግል ተበዳይ የተረከቡት ሆኖ እንዲመልሱ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ምክንያት ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ጉዳዩን በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ በሚያውቁት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን የአመልካች መከላከያ ማስረጃዎች ያላስተባበሉ መሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች በሚገባ መረጋገጡን ውሳኔው ያሳያል፡፡ አመልካች የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል የሚታመን አይደለም፣ የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ሲታይም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ከሰበር ችሎቱ ስልጣን አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡ አመልካች የግል ተበዳይን ንብረት በውክልና ስልጣናቸው ወስደው ሊመልሱ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ተረጋግጧል ከተባለ ይህ አድራጎት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

አንድ ወኪል ከወካዩ በውክልና ስልጣኑ የወሰደውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ካለሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 676(2) ድንጋጌ የሚጠየቅ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለሆነም በውክልና ስልጣኑ መሰረት አደራ የተቀበለ ተዋዋይ ወገን እምነት አጉድሏል ተብሎ በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ ስለእምነት ማጉደል የሚደነግጉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችም ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 676(2) መሠረት ወንጀል ነው ተብሎ የተጠቀሰው የወኪሉ

ድርጊት በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን ከወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) እና ተጠቃሹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልጽ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ለጉዳዩ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለው የፍትሓብሔር ይዘት ብቻ ባለው ጉዳይ ነው ለማለት ስላልተቻለ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወ/መ/ሕ/አንቀጽ 23(2) እና 676(2) ደንጋጌዎችን ያገናዘበ ሆኖ በመገኘቱ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የቅጣት አጣጣል መርሆዎችን የጣሰ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87549 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103799 መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በወንጀል መጠየቃቸው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መፅናቱን በማወቅ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 73569

ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አቶ ደረጀ ጎሳዬ - ጠበቃ ወገኔ ካሳሁን ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቤ ሕግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥየቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል በሶስት ምድብ የተከፈለ ክስ ቀርቦበት ፍርድ ቤቱ ለአመልካች የዋስትና መብቱን ጠብቆለት አመልካች ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ ብር) አስይዞ የተጠበቀለትን የዋስትና መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሲፈልግ በቼክ ጉዳይ በወንጀል ተከሶ የእስር ቅጣት በመፈረዱ ምክንያት ማረሚያ ቤት በመግባቱ የዋስትና መብቱን ሊጠቀምበት ያለመቻሉን ገልጾ በክርክር ሂደት ላይ ላለው ጉዳይ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስለትና ጉዳዩን ከማረሚያ ቤት እየተመላለሰ እንዲከታተል ይደረግ ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታው በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75 መሠረት ይግባኙ የቀረበበት መሆኑን ገልፆና ይህ ድንጋጌ የሚያገለግለው የዋስትና መብት ሲነፈግ ይግባኝ ለማቅረብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች በሌላ ወንጀል በተፈረደው ፍርድ መሠረት ማረሚያ ቤት የሚቆይ በመሆኑ ለሌላ ጉዳይ የተጠበቀው የዋስትና መብት ተግባራዊ የማይሆን መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ለጉዳዩ የተያዘው ገንዘብ እንዲመለስ መጠየቁ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በሌላ መዝገብ ፍርደኛ በመሆኑ ከማረሚያ ቤት ተመላልሶ መከራከር የሚችል ቢሆንም ለዋስትና ያስያዘው ገንዘብ አይመለስለትም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ተጠሪ ቀርቦ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር

በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የዋስትና ገንዘብ ያስያዘው በተጠሪ መስሪያ ቤት አቃቤ ሕግ የተለያዩ የጉምሩክ ሕግ ድንጋጌዎች ተላልፏል ተብሎ በቀረቡት ሶስት ክሶች የዋስትና መብት በፍርድ ሲጠበቅለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቼክ ጉዳይ ተከሶ የአራት አመት ከስድስት ወር ፍርደኛ ሆኗል፡፡ ገንዘቡ እንዲመለስለት የሚጠይቀውም ፍርድ ቤት ያለውን የጉምሩክ ወንጀል ክርክርን ከማረሚያ ቤት በመመላለስ የሚከታተል መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡

በመሰረቱ ዋስትና ሕገ መንግሥታዊ መብት መሆኑንና ይህ መብት በልዩ ሁኔታ በሕጉ ክልከላ ካልተደረገ በስተቀር ለተከሰሱ ሰዎች ሊጠበቅ የሚችል መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 19(6) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ በሕጉ አግባብ የዋስትና መብት ሲፈቀድ ደግሞ የተከሳሹ ፍርድ ቤት መቅረብ እውን እንዲሆን ተከሳሹ ገንዘብ እንዲያስይዝ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚደረግ መሆኑን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 69(1) ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ የዋስትና መብት የተፈቀደለት ተከሳሽ መብቱን ለመቀጠም የማያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን በመግለፅ መብቱን ለመጠቀም ካልፈለገ ደግሞ መብቱ የራሱ ይሆናል፡፡ በፍርድ ቤት የተፈቀደለትን የዋስትና መብት ያለመጠቀም ፍላጎት ደግሞ የዋስትና መብት እንደተፈቀደ ወይም ከተፈቀደና ተከሳሹ መብቱን መጠቀም ከጀመረ በኋላም ሊመጣ ይችላል፡፡ ሕጋዊ ምክንያት እስካለው ድረስ በማንኛውም ደረጃ ተከሳሹ በሕጉ አግባብ የተፈቀደለትን የዋስትና መብት የመተው ፍላጎቱ ሊጠበቅለት የሚገባው ጉዳይ እንጂ ይህንኑ መብቱን ለመከላከል የሚያስችል ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ትኩረት ሊያደርግና ሊቆጣጠረው የሚገባው ቁልፍና ዋናው ነገር በፍርድ ቤት ክስ የቀረበበት ሰው ቀጠሮውን ተከታትሎ የሚቀርብበት ትዕዛዝ መስጠቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተከሳሽን የዋስትና መብት በማክበር ተገቢውን ዋስትና በማስጠራት ወይም ተከሳሹ ማረሚያ ቤት ሆኖ ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 68 እና 69 ድንንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብቱ ከተከበረለት በኋላ በሕጋዊ ምክንያቶች መብቱን በመተው ጉዳዩን ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል ፍላጎት ያለው መሆኑን ሲገለጽ ሊነፈግ አይገባም፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ ያልተቀበለው አመልካች በዋስ የተለቀቀበት መዝገብ እልባት ያላገኘና ማረሚያ ቤት በሌላ ወንጀል ገብቷል የተባለውም በውሳኔ ይሁን በሌላ ምክንያት አልተረጋገጠም በሚል ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ይግባኙ የሚቀርበው የዋስትና መብት ሲከለከል ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በሌላ ወንጀል ፍርደኛ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75"ን" ለአቤቱታው መሠረት ማድረጉም አቤቱታውን ለማስተናገድ ፍርድ ቤቱ አልችልም ብሎ ውድቅ ለማድረግ ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ፍርድ ቤቶቹ አመልካች እልባት ያላገኘውን ጉዳይ ከማረሚያ ቤት በመመላለስ የፍርድ ቤትን ቀነ ቀጠሮውን አክብሮ የሚከታተልበት አግባብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ትዕዛዝ በመስጠት ይህንኑም እንዲፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ማስተላለፍ ሲገባቸው ሕጋዊ መሠረት የሌላቸውን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ከአመልካች የንብረት መብትና መብቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ፍሬ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 68 እና 69 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174010 የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 106592 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ/ም የጸናው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174010 በቀረቡት ክሶች ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስለት ብለናል፡፡ አመልካች በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል የማሰሪያ ዋራንት ለማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ለአመልካች ገንዘቡን እንዲያስመልስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ሀ

የሰ/መ/ቁ 65566

ታህሣስ 4 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የመከላከያ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ- ሃምሣ አለቃ ተስፋዬ ቦያለው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የመከላከያ ሠራዊት አባል በመደበኛ ፍርድ ቤት የቀረበበትን የወንጀል ክስ ለመከላከል የሚያስችለው የህግ ድጋፍ መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የመከላከያ ሠራዊት አባል በሆኑት ሀምሣ አለቃ ቴውድሮስ ሃይለስላሴ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/11ሀ በመተላለፍ ባለ አንድ መቶ ሐሰተኛ የብር ኖት (100) ይዘው ተገኝተዋል የሚል የወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ተከሣሳሹ የተከሰሱበት የወንጀል ክስ ተገቢውን የህግ ድጋፍ እንዲያደርግና በተከላካይ ጠበቃ እንዲታገዝ የመከላከያ ሠራዊት መከላከያ ጠበቃ መድቧል፡፡ የዞኑ አቃቤ ህግ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መከላከያ ሚኒስቴር ተከላካይ ጠበቃ የሚያቆመው በመደበኛ ፍ/ቤት በሚያስከስሱ ወንጀሎች ሣይሆን በጦር ፍ/ቤት በሚያስከስሱ ወንጀሎች ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የመከላከያ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ ተከሳሹን ወክሎ ለመከራከር አይችልም የሚል መቀወሚያ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የዞኑ አቃቤ ህግ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል የመከላከያ ወታደራዊ ተካላካይ ጠበቃ ለተከሳሹ የህግ ድጋፍ የመስጠት በተከላካይ ጠበቃነት ቆሞ ለመከራከር አይችልም የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅረቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አፅንቶታል፡፡ አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል የሆነውን ተከሳሽ እንድንከላከል የበታች ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 27/1988 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በወታደራዊ ተከላከይ ጠበቃ እንዲታገዙ አዋጅ ቁጥር 27/1988 የሚፈቅደው በወታደራዊ ፍርድ ቤት በሚከሰሱበት ጊዜ ብቻ ስለሆነ ለተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን

መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የመከላከያ ሠራዊት አባል ያሆኑት ሃምሣ አለቃ ቴድሮስ ሀይለስላሴ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 361 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል የሚል የወንጀል ክስ በተጠሪ በኩል ቀርቦበታል፡፡ የመከላከያ ሠራዊት አባሉ የተከሰሱበት ወንጀል ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 361 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አዋጅ ቁጥር 27/88 በአዋጅ ቁጥር 123/90 እንደተሻሻለ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው የህግ ማእቀፍ ሲሆን በዚህ መዝገብ የተያዘው ጭብጥ የአዋጅ ድንጋጌ ብቻ ሣይሆን የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ተፈፃሚነት መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተከላካይ "ስለማቆም" የሚል ርእስ ያለው የአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ፤ "ራሱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም ለማይችል ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰው መንግስት ተከላካይ ጠበቃ ይመደብለታል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን የእንግሊዘኛው ቅጅ "the state shall provide a defence counsel to a person charged with an offence punishable by imprisonment not less than five years and un able to retain a counsel" በሚል መንገድ የተደነገገ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ የአንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 በዚህ "አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በተከላካይ ጠበቃነት ለማቆም የሚችለው ከሠራዊቱ አባል መካከል ይሆናል፡፡ በማለት በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከላይ የተገለፀው የህግ ድንጋጌ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በወታደራዊ ፍርድ ቤትም ሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ክስ ሲቀረብበትና በራሱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የማይችል በሆነ ጊዜ መንግስት የህግ እውቀትና ልምድ ያለው የመከላከያ ሰራዊት አባል የሆነ ተከላካይ ጠበቃ በነፃ የማቆምና የመከላከል ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 27/88 አንቀጽ 35 መንግስት ለሠራዊቱ አባላት በነፃ ተከላካይ ጠበቃ በማቆም የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ እንዲከላከል በህግ የሚገዳድበትን ዝቅተኛ መስፈርት (minimum standard) የሚደነግግ ሲሆን የአገር መከላከያ ሚኒስትር የመከላከያ ሠራዊት አባላት በግዳጅ ላይ እያሉ ፈፀመውታል ተብሎ በተከሰሱበት ከ5 አመት እስራት በታች በሚያስቀጣ ወንጀል ተከላካይ ጠበቃ በነፃ ለማቆምና ለመከላከል ከፈለገ በወታደራዊ ፍ/ቤትም ሆነ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝ መደበኛ ፍ/ቤት ተከላካይ ጠበቃ በመወከልና በነፃ የቀረበውን የወንጀል ክስ መከላከል የአዋጁ አንቀጽ 35 ድንጋጌዎችን የሚገድቡት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረፅ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀፅ 35 ድንጋጌዎች በወንጀል የተከሰሱ የመከለከያ ሠራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ የማግኘት መብት እንዳላቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገውን በማጣብብና በተሻሻለ ሁኔታ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ተፈፃሚ በሚያደርግ መንገድ መተርጐምና ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከ5 አመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በወታደራዊ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜና ተከሳሹ በግሉ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ሲሆን የመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ድጋፍ በነፃ ማግኘት በአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 35 የተደነገገ የሠራዊቱ አባል

መብትና የአገር መከላከያ ሚኒስትር ህጋዊ ግዴታ ሲሆን የሠራዊቱ አባል በአምስት ዓመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በመከላከያ ፍርድ ቤት ክስ በቀረበበት ጊዜ የአገር መካከላያ ሚኒስትር በነፃ የተከላከይ ጠበቃ ድጋፍ የሠራዊት አባል ማግኘት አለበት ብሎ ካመነ የመከለከያ ወታደራዊ ጠበቃ በነፃ የህግ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርግለት በማድረግ መከላከል የሚችል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች ይዘትና ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ የመከላከያ ሠራዊት አባል በመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ነፃ የህግ ድጋፍ የሚያገኘው በወታደራዊ ፍርድ ቤት በወንጀል ሲከሰስ ብቻ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበውን የህግ መሠረት የሌለው መቃወሚያ በመቀበል ተከሣሹ በመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ነፃ የህግ ድጋፍ እንዳያገኝ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ብይን ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በመደበኛ ፍርድ ቤት በወንጀል በተከሰሱበት ጉዳይ በነፃ የህግ ድጋፍና እገዛ የማድረግና የመከላከል መብት አለው በማለት ወስነናል፡፡

ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 63014

ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ወርቅነህ ከንባቶ

2. ወ/ሮ አመለወርቅ ዳሌ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ክልል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካቾች በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ ለ እና አንቀፅ 33 እና በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በወንጀል ግብረ-አበርና ልዩ ተካፋይ በመሆን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዘው የመገኘት ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ክርክር በሥር አንደኛ ተከካሽ የሆነው አንደኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ከተቀጠረበት ከመስከረም 1984 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ የታክስ አስተዳደርና ገቢ ሰብሳቢ ሆኖ የተለያየ የደረጃ እድገት እያገኘ እንደሠራ ገልፆ፣ አንደኛ አመልካች በሕጋዊ መንገድ በመንግስት ሥራው የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከብር 90,220 /ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ብር/ የሚበልጥ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተከሶቾች፡-

- ሁለተኛ ተከሳሽ ዳሸን ባንክ በሒሳብ ቁጥር 50165201 ብር 332,363.63 /ሦስት መቶ ሠላሳ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት ብር ከስልሣ ሶስት ሣንቲም/ ተቀምጦ ይገኛል፡፡
- አንደኛ ተከሳሽ በዳሸን ባንክ በሂሳብ ቁጥር 501651238200114004 ብር 1,646,371.24 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አንድ ብር ከሃያ አራት ሣንቲም/ በስሙ የሚገኝ ሲሆን
- አንደኛ ተከሳሽ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 24499 ብር 46,802.11 /አርባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ በስሙ የሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ አለው
- ተከሳሾች በልጃቸው በደስታ ወርቅነህ ስም ብር 55,931.92 /ሃምሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አንድ ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም/ ግምት ያለው የመኖሪያ ቤት አላቸው፡፡ በጠቅላላው ተከሳሾች ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማንያ አንድ ሺ አራት መቶ ስልሣ ስምንት ብር

ከዘጠና ሣንቲም/ ምንጩ ያልተወቀ ሀብት ያላቸው በመሆኑ የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ክሱን ሊያስረዱ ይቻላሉ የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካቾች ክሱ ከደረሳቸውና እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምንም ጥፋተኞች አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች በበኩላቸው በተጠሪ ክስ የተዘረዘረው ገንዘብ ሕጋዊ ምንጭ የሚሏቸውን በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች

- በወንዶገነት ወረዳ አባያ ቀበሌ ከ1984 ዓ.ም ከቤተሰብ የተሰጣቸው 2.5 ሄክታር መሬት ያላቸው መሆኑንና ጫት የተከሉ በመሆኑ በዓመት ከመቶ ስልሳ ሺህ ብር በላይ እንደሚያገኙ፣
- በሌላ በኩል 0.25 ሄክታር የሆነ መሬት እንዳላቸውና የሸንኮራ አገዳ በማልማት በዓመት ከሃያ አምስት ሺህ ብር በላይ እንደሚያገኙና በዚህ ገቢ ቤቱን እንደገዙት፣
- በሁለተኛ ተከሳሽ ስም በዳሽን ባንክ የነበረው ገንዘብ፣ ብር 5,000,000፣ የሚሰራ ፕሮጀክት አንደኛ ተከሳሽ ቀርያ፣ ከባንክ ብድር ሲጠይቅ አንድ ሶስተኛ አሳይ በመባሉ በብድር የተገኘና ከሁለተኛ አመልካች አካውንት ወጥቶ በአንደኛው አመልካች አካውንት እንደገባና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደ መሆኑን፣
- በአንደኛው አመልካች ስም ከዳሽን ባንክ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,120,500.00 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ አምስት መቶ ብር/ የጋራራም ላንች እና የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ክስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች የተጠሪን ክስና ማስረጃ ያስተባበለ መሆኑን ገልፆ ከተሰሱበት ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 149 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ማጣሪያ ካደረገና ተጨማሪ ምስክሮች ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አፅንቷል፡፡ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት የሌለው በመሆኑ የተጠሪን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል አይችልም በማለት አንደኛ አመልካች በሶስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ክስ የቀረበበት ንብረት እንዲወረስ፣ ሁለተኛ አመልካች በአንድ ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ፣ ቅጣቱ እንዲገደብና በስሟ ያለና ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲወረስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ታህሣሥ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም እንጂ ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ ዐቃቤ ሕግ በክሱ የጠቀሰውን ገንዘብ ከየት እንዳገኘው አስረድተን እያለ ፍርድ ቤቱ የእኛን የመከላከያ ማስረጃ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ገንዘብም እንዲወረስ መደረጉ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካቾች ያቀረቡትን የፍሬ ጉዳይ ክርክር የመመርመር ሥልጣን የለውም፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን አመልካቾች የወንጀል ክስ ከቀረበባቸው በኋላ በተለይም በይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ ያመጡት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው፡፡ አመልካቾች ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለገቢ ምንጫቸው ያቀረቧቸው ምስክሮችና ማስረጃዎች ታዓሚነት የሌላቸውና የተጠሪን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል የሚችሉ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ውሣኔና የሰጠው በተጠሪ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ይዘት፣ ታዓሚነትና ክብደት በዝርዝር በመመርመር በመመዘን እንደዚሁም በአመልካች በኩል የቀረበውን የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና የማስረጃውን ታዓሚነትና ክብደት በመመዘን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠው የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት ፈፅመዋል የሚለውን ስህተት ለማረም የማስረጃ ምርመራና ምዘና በመፈፀም ነው፡፡

ይህም ፍሬጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌላ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የፈፀሙት ስህተት ቢኖር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ፍሬጉዳይ አጣርቶና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የማረም ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ እንድናይ የሚያስገድደን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ለ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንደሚኖረውና ክርክሩ በሕግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 75 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ሥልጣን ያለው መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን የፌዴራል ሕገ-መንግስት፣ የክልሉ ሕገ-መንግስት፣ የክልሉ አዋጅ ቁጥር 43/1994 ድንጋጌዎች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፍሬጉዳይ የማጣራት፣ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የሚሰጡ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና በመመመዘን የተጠሪን ማስረጃ የወንጀል ክሱን የማስረዳት ብቃትና ታማኝነት አለው፡፡ የአመልካቾች ማስረጃ ታዓሚነትና ክብደት የሌለው ነው በማለት የደረሰበትን መደምደሚያና፣ የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የደረሰበትን መደምደሚያ መሠረት በማድረግ በአመልካቾች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከላይ የገለፅናቸውን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፍሬጉዳይ የማጣራት፣ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ሥልጣን የለውም ማለት፣ በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ወይም የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት፣ መሠረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርዓት ሳይከተሉ፣ መመስረት የሚገባቸውን ጭብጥ ሳይመሰርቱና ጭብጥን የማስረዳት ሁኔታ /Burden of proof/ ያለበት ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና መጣራት የሚገባውን ፍሬጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡትን ውሣኔ በሰበር ታይቶ የማረምና በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌሎች የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት፣ በሕግ የማስረዳት ግዴታ ያለበት አካል ግዴታውን የተወጣ መሆኑን በአግባቡ በመመርመርና በመመዘን እንደዚሁም መጣራት የሚገባውን ፍሬጉዳይ አጣርተው እንዲወስኑ ትዕዛዝ የመስጠትና ጉዳዩን የመመለስ የዳኝነት ሥልጣን የለውም ማለት እንዳልሆነ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዝርዝር የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ቢሆንም በውሣኔው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 በተከራካሪ ወገኖች ከሚጥለው የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ አንፃር አመልካቾችና ተጠሪ በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም? የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾችና በተጠሪዎች መካከል ያለውን አከራካሪ የፍሬጉዳይ ጭብጥ ለመወሰን መጣራት የሚገባቸውን ፍሬጉዳዮች በማጣራትና የግራ ቀኙን ማስረጃ የሕጉ ድንጋጌ የሚጥልባቸውን የማስረዳት ግዴታ መሠረት በማድረግ በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም? የሚሉትን ጭብጦች በውስጡ የያዘ መሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ከላይ የገለፅናቸውን ጭብጦች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአግባቡ በማየት ውሣኔ የሰጡባቸው መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካቾች የተከሰሱበት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ተጠሪና አመልካች ያለባቸውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ዝርዝር ይዘት ተመልክተናል፡፡ “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ” የሚል ርዕስ ያለው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 በንዑስ አንቀጽ 1 “የመንግስት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው
/ሀ/ የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ወይም፣
/ለ/ ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፣

የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር እንደሁኔታው የንብረቱ መወረስ ወይም ለባለቤቱ መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ተጠሪ አንደኛ አመልካች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ጉዳይ በወንጀል ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በክልሉ በተለያየ ደረጃ የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ እየሰራ ያገኘው የተጣራና የታወቀ ገቢ ብር 90,220 /ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ብር/ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳለው በክሱ ከገለፀ በኋላ አመልካቾች በስማቸው በተለያዩ ባንኮች ባላቸው ሂሳብና በልጃቸው ስም የገዙት ቤት ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ያላቸው በመሆኑ ምንጩ ያልተወቀ ሀብት ይዘው ተገኝተዋል በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ አንደኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ በነበረበት ጊዜ ያገኝ የነበረውን ገቢ፣ ሁለተኛ አመልካች የቤት እመቤት መሆናቸውንና ንብረቱ በጥሬ ገንዘብ ያለ በስማቸው ያለ መሆኑንና አመልካቾች በልጃቸው ስም ቤት ያላቸው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳቀረበ ፍሬጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ የተገኘው ገንዘብና ቤቱን የሠሩበትን ሀብት ምንጭ ለማስረዳት የመከላከያ ማስረጃዎች እንዳቀረቡ ከሥር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎቱ ከሰጡት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች ተጠሪ ያቀረበውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ፍሬጉዳይ ማለትም በግልፅ ከሚታወቀውና አንደኛ አመልካች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት ሠራተኛነት ያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ በላይ በባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው የተገኘው ጥሬ ገንዘብና በልጃቸው ስም ቤት የሠሩበት ሀብት ማለት ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የዐቃቤ ሕግን ክስና ማስረጃ ሊያስተባብሉ የሚችሉ አንድ አንድ ፍሬጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው በቂ ይሆናል ወይስ አይሆንም የሚለውን ነጥብ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ከተደነገገው የማስረዳት ግዴታ አንፃር መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻለው ዐቃቤ ሕግ የመንግስት ሠራተኛ የሆነው ወይም የነበረው ሰው ያገኝ የነበረውና የሚያገኘው ገቢ ምን ያህል እንደሆነና የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ስምም ሆነ በቤተሰቡ ስም ከሕጋዊ ገቢው ውጭ ይዞት የሚገኘውን የገንዘብና የንብረት ግምት የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት ሠራተኛ የነበረው ሰውና ከእሱ ጋር በልዩ አባሪነት የተከሰሰ ሰው የመንግስት ሠራተኛው ሲያገኝ ከነበረውና ከሚያገኘው ገቢ በላይ ይዞት የተገኘው ገንዘብ ወይም ሀብት ትክክለኛው ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ፣ "….የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት እንደገባ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር" ምንጩ ያልተወቀ ሀብት ይዞ በመገኘቱ /በመገኘታቸው/ ጥፋተኛ ተብለው በሕጉ የተደነገገው ቅጣት ሊጣልባቸው እንደሚችል በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ዐቃቤ ሕግ በግልፅ ከሚታወቀው ሕጋዊ ገቢ በላይ ነው በማለት በክሱ የገለፀውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ሀብት ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ በተከሳሾች ላይ የሚወድቅ መሆኑን ነው፡፡ የተከሳሾች የማስረዳት ግዴታም ዐቃቤ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሾች ሌላ ገቢ የሚያገኙበት ሥራ ወይም የገቢ ምንጭ ያላቸው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጅ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አንደኛው አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ከሚያገኘው ደመወዝ /ሕጋዊ ገቢ/ በላይ በስማቸው በተከፈተ የባንክ ሂሳብና በልጃቸው ስም ቤት የተሰራበትና እንደያዙት የተረጋገጠው በአጠቃላይ መጠኑ ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ የሆነ ገንዘብና ሀብት ምንጩ በአንደኛ አመልካች ስም በወንዶገነት ወረዳ አባዮ ቀበሌ ካለው 2.5 ሄክታር የመሬት ይዞታ ላይ ካለሙት የጫትና የቡና ሰብል ሽያጭ፣ በሁለተኛ አመልካች ስም 0.25 ሄክታር መሬት ላይ ካለሙት የሸንኮራ አገዳ እንደሆነ፣ ከፊሉን በብድር ከግለሰብ ያገኙት መሆኑንና ከፊሉ የጋራራሙ ላንቶ የእንስሳት ማድለብና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዳቀረቡ ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ችሎት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡

ሆኖም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች አንደኛ አመልካች ከሚሰራው የመንግስት ስራ በተጨማሪ ሌላ የገቢ ምንጭ የነበረው መሆኑን የሚያሣዩ ማስረጃዎች መሆናቸውን በመመልከት ብቻ መጣራት የሚገባቸው ፍሬጉዳዮችን ሳያጣሩና በተለይም አመልካቾች በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከሕጋዊ ገቢያቸው በላይ የያዙ መሆናቸውን ብር 2,081,468.90 ያገኙበትን ትክክለኛ የገቢ ምንጭ የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የማስረዳት ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በሕጉ በአመልካቾች ላይ የተጣለውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ መሠረት በማድረግ ተገቢውን ማጣራት አድርገው መርምረውና መዝነው ውሣኔ የሰጡ አለመሆናቸውን ከውሣኔያቸው ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ ምክንያቱም

/ሀ/ አመልካቾች በስማቸው እንዳለና ጫት፣ እንስት፣ ቡናና ሸንኮራ አገዳ እያለማን ገቢ እናገኝበታለን ያሉት 2.25 ሄክታር መሬት በተመለከተ አመልካቾች የእርሻ መሬቱ ባለይዞታ ናቸው ወይስ አይደሉም? የእርሻ መሬቱ ባለይዞታ ከሆኑ የእርሻ መሬቱን በይዞታነት የያዙት መቼ ነው? መሬቱን በማልማት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ተክሎች በማልማት ምርት ገቢ ማግኘት የጀመሩት መቼ ነው? ከመሬቱ የሚገኘው ገቢና መሬቱን ለማልማትና ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ የሚወጣው ወጭ ምን ያህል ነው? አመልካቾች ከመሬቱ ተጣርቶ የሚደርሳቸው ገቢ ምን ያህል ነው የሚለው ፍሬጉዳይ በአግባቡና በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ባልታወቀበት ሁኔታ ከቀበሌና ከዞኑ ግብርና ጽ/ቤት የተፃፉ ደብዳቤዎችን ብቻ መሠረት በማድረግ አመልካቾች ከእርሻ የሚያገኙት ገቢ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ መወሰኑ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 በአመልካቾች ላይ የሚደነግገውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ ተጣርቶ የተወሰነ አለመሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ፣

/ለ/ አመልካቾች በባንክ ሒሳባቸው ውስጥ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,120,500 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ አምስት መቶ ብር/ በአንደኛው አመልካች ስም የተቀመጠ ከፊሉ የጋራራሙ ላንቶ የእንስሳት ማድለብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገንዘብ ከፊሉ ደግሞ የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን ለማስረዳት የማህበራቱ ቃለ-ጉባኤና አባላት በማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነታቸው የተወሰኑ የግል ማህበራት የሚመሰርቱት የማህበሩ ዋና ገንዘብ ልክና የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መግባቱን የሚያስረዳ መግለጫ ሲቀርብ መሆኑ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 519 ንዑስ አንቀጽ /መ/ እና /ሰ/ በአስገዳጅነት

የተደነገገ በመሆኑ እነዚህ የንግድ ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው ተመዝግበው ከሆነ ሲመዝገቡ ያስመዘገቡትና ገቢ ያደረጉት የማህበሩ ዋና ገንዘብ ምን ያህል ነው? ማህበራቱ በካፒታልነት ካስመዘገቡት ካፒታል በላይ በአመልካቾች ስም ለማህበር መመስረቻ የተዋጣው ገንዘብ አለ በማለት የሚፅፉቸው የተለያዩ ማስረጃዎች ሕጋዊ ተቀባይነት፣ ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚሉት ነጥቦች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመሰራረት፣ መዋጮ አከፋፈል፣ የማህበሩ ዋና ገንዘብና ገንዘቡ ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ የተቀመጡ ሕጋዊ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ፣ መጣራት የሚገባቸው ፍሬጉዳዮች ተጣርተውና ማስረጃዎቹ አመልካቾች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ያለባቸውን የማስረዳት ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ተጣርተው ውሣኔ የተሰጠበት ሆኖ አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የዘረዘርናቸውን መጣራት የሚገባቸውን ፍሬጉዳዮች ሳያጣራና አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለባቸውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ የተወጡ መሆኑን ያለመሆኑን የሚያሣዩና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት ያደረጉና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ውሣኔ ያልሰጡበት በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና በመመዘን የሰጠው ውሣኔም ሆነ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን ፍሬጉዳዮችን ሳያጣራና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የአመልካቾችን ማስረጃ ተቀባይነት ሳይመረምሩ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችና ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥሱና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ናቸው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከዚህ በፊት ጉዳዩን ያላዩት ዳኞች በመሰየም በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 2/ሀ/ እና /ለ/ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማጣራትና የማስረጃዎቹን ተቀባይነት፣ ክብደትና ተዓሚነት በመመዘን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149/1/ መሠረት ፍርድ እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

# የንግድ ህግ

የሰ/መ/ቁ. 54117

ጥቅምት 13 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አ.ማ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመድን ውልን መሰረት ያደረገ የገንዘብ ክፍያ ይተካልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣቸውን የደንበኛውን የኩርቱ ኢንተርናሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር ንብረት የሆኑትን 1,200 ኅማዎችን ተጠሪ ለማጓጓዝ የተረከበ ቢሆንም እነዚሁ ኅማዎች ተጠሪ በባህር ላይ በደረሰ ግጭት መጥፋታቸውን በመግለፁ አመልካች ከደንበኛው ጋር ባለው የመድን ውል መሰረት ለጠፉት ኅማዎች ግምት ብር 269,293.20 (ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከሃያ ሳንቲም) ወጪ አድርጎ ለደንበኛው መክፈሉን ገልፆ ተጠሪ ባለው የመጓጓዣ ውል መሰረት ለአመልካች ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ከተለያዩ ወጪዎችና ኪሳራዎች ጋር እንዲተካለት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ክስ በሰጠው መከላከያ መልስም አመልካች ክስ ለመመስረት የሚያስችለው መብትና ጥቅም የሌለው መሆኑን ለክሱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ኅማዎቹ በባህሩ ላይ ሊወድቁ የቻሉት በባህር ላይ በደረሰው የግጭት አደጋ ምክንያት ነው፣ ጉዳቱ የደረሰው በአጓጓዡ ጥፋት ወይም በአጓጓዡ ወኪሎች ወይም ሰራተኞች ጥፋት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎ ተጠሪን ከክሱ ነጻ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ኅማዎቹን በአግባቡና በጥንቃቄ ሳይጭናቸው በመቅረቱ ግጭቱ በደረሰበት ጊዜ ተወርውረው ባህር ውስጥ የገቡ መሆኑ እየታወቀና ይህንኑ ሁኔታ ከባህር ሕጉ አንቀፅ 196(2) ድንጋጌ ይዘት ጋር ፍርድ ቤቱ ማገናዘብ ሲገባው ተጠሪን ከክሱ መሉ

በመሉ ነጻ መልቀቁ ሕጋዊ አይደለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች ደንበኛ (ኩርት ኢንተርናሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር) ንብረት የሆነውን 1,200 ጎማዎችን አጓጉዞ ለማድረስ መረከቡንና ጎማዎቹ በባህር ላይ በነበረው ጉዞ በደረሰው ግጭት ምክንያት የጠፉ መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱት ፍሬ ነገር መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ባለበት የመድን ውል ለደንበኛው በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ከከፈለ በኋላ ገንዘቡ እንዲተካለት ነው፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ሲሆን ለዚህ በቀዳሚነት የሚያቀርበው ክርክር ጎማዎቹ በባህር ላይ በደረሰው የመርከቦቹ ግጭት አደጋ የጠፉ እንጂ በተጠሪ ችግር ወይም ሰራተኞች ጥፋት አይደለም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በባህር ላይ እቃ አመላለሽ ያለበትን ኃለፊነት በተመለከተ የባህር ሕጉ በቁጥር 196 ስር ያስቀመጠ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት እቃ አመላላሽ ሁለት ሰፊና ዋና ዋና ግዴታዎች አሉት፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ አንድን መርከብ በሙሉ በመከራየት (ቻርተር ፓርቲ) እቃን የሚያጓጉዝ ባለመርከብ ስላለበት ግዴታ የባህር ሕጉን ቁጥር 138 በማጣቀስ የሚደነግግ ሲሆን የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በመርከቡ ላይ የተጫኑትን እቃዎች በጥንቃቄና በሚገባ ለመጫን፣ ለአጠባበቃቸው በሚገባ አቀማመጥ እንዲደረደሩ፣ ስለጉዞዋቸው፣ ስለ ጥበቃቸው፣ ስለ መልካም አያያዛቸውና ስለ ማራገፉ መልካም አፈጻፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አጓዡ በሕጉ የተጣሉበትን እነዚህን ግዴታዎች ካልተወጣ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ውስጥ አመላላሹ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የተደረገው ውል የማይፀና ስለመሆኑም የባህር ሕግ ቁጥር 205 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የአመላላሹ መከላከያ ሊሆኑ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች በባህር ሕጉ ቁጥር 197 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከላይ የተመለከቱት የባህር ሕግ ድንጋጌዎች የአመላላሽን ኃላፊነት ሊያስከትሉና ቀሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶችን የሚደነግጉ ሲሆን ኃላፊነትን በተመለከተ ቀሪ ከሚያደረጉ ምክንያቶች ውስጥ አመላላሽ በእቃው ጉዳት የደረሰው በባህር ላይ በደረሰው የግጭት አደጋ (accident of the Sea) መሆኑ፣ ከአመላላሹ ጥፋት ወይም በእርሱ ወኪሎችና አሽከሮች ቸልተኝነትና ጥፋት ምክንያት ያለመሆኑና በአግባቡ ማስረከቡን መረጋገጡ ስለመሆኑም ያስገነዝባሉ፡፡ የእቃው እርክክብ ተፈጽሟል የሚባለው ደግሞ መቼና በምን ሁኔታ ሲፈጸም እንደሆነም ድንጋጌዎቹ በተለይ ከባህር ሕጉ ቁጥር 180(3) ጋር ተዳምረው ሲነበቡ ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ የተረጋገጠ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች የሚጸኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ብቻ መሆኑ፣ የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን፣ ነገር ግን መርከቡ የተከራየው በኪራይ ሰነድ (በቻርተር ፓርቲ) የሆነ እንደሆነ የሚሰጠው የጭነት

የማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን የመሳሰለው ሌላ ሰነድ በአመላላሹና በሰነድ አምጪው መካከል ያለው ግንኙነት ከሚመራበት ጊዜ አንስቶ በዚሁ በሚሰጠው የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ላይ ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ፣ የሚፀኑትም እቃዎቹ ከመርከብ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሶስት በተለይ ሲታይም "…..ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ "በሚል በኃይል ቃል ማስቀመጡ አመላላሹ በማራገፍ ሂደት ለሚከሰቱ ጉዳቶቹም ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በግልጽ የሚሳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ተጠሪን ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት በማለት የሚከራከረው ኀማዎቹ በባህር ላይ እንዲወድቁ የሆነው ተጠሪ ኀማዎቹን በመርከቡ ላይ በጥንቃቄና በሚገባ በመጫን፣ በሚገባ አቀመማጥ እንዲደረዱ ማድረግ (stow) ያለበት ስለመሆኑ በባህር ሕጉ አንቀፅ 196(2) ስር የተመለከተውን ግዴታ አልተወጣም የሚል ምክንያት በመጠቀስ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በማስረጃነት የቀረበው የባለሙያ ሰርቬይ ሪፖርት ኀማዎቹ ወደባህር የገቡት በመርከቦቹ ግጭት መሆኑን እንደሚያሳይ፣ አመልካች ኀማዎቹ በሌላ ምክንያት የጠፉ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የሌለ መሆኑንና በባህር ሕጉ አንቀጽ 197(1(ሐ)) ስር በባህር ላይ ለደረሰው ጉዳት ወይም ድንገተኛ መሰናክል ምክንያት ለደረሰ ጉዳት አመላላሹ ኃላፊነት እንደሌለበት መደንገጉንና ጉዳቱ በሌላ ምክንያት የተከሰተ ነው ከተባለም በባ/ሕ/ቁጥር 197(1(ከ))ስር አመላለሹ ኃላፊነት የሚኖርበት በአመላላሹ ጥፋት ወይም በእርሱ ወኪሎችና አሽከሮች ቸልተኝነትና ጥፋት ምክንያት መምጣቱ ሲረጋገጥ መሆኑንና በአመልካችና በተጠሪ መካከል ባለው ክርክር ግን የአመላላሹ ጥፋት ወይም የእርሱ ሰራተኞች ቸልተኝነት መኖሩ ያለመረጋገጡን በመተንተን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ተጠሪ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ አልተወጣም በማለት ክስ የመሰረተ እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ ሊያስረዳ የሚችል ለጉዳዩ አግባብነትና ጥንካሬ ያለውን ማስረጃ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በውሉ የተጣለበትን ግዴታ በመወጣት ሂደት ውስጥ በነበረበት ጊዜ በተለይም ኀማዎቹ በመርከቡ ሲጫኑ ጥንቃቄ ባለማድረግ በተገቢው አኳኋን ያልደረደራቸው ከሆነና በዚህ ምክንያት ኀማዎቹ በመርከቦቹ ግጭት ጊዜ ወደባህሩ ተወርውረው የገቡ ናቸው ተብሎ በአመልካች ክርክር እስከቀረበና በተጠሪ ደግሞ የአመልካች ክርክር እስከተካደ ድረስ የአመልካችን ክርክር የማስረዳት ግዴታ የራሱ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ክርክሮች የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሥርዓት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ለጉዳዩ ተገቢ ነው የተባለው የባለሙያ ሰርቬይ ሪፖርት ቀርቦ በማስረጃነቱ ሊሰጠው የሚችለው ክብደት በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ማስረጃው የተጠሪን ጥፋት ሊያስረዳ የማይችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ይህ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ስለሆነም በጉዳዩ ላይ የቀረበው ማስረጃ ክብደቱ ተመዝኖ የተጠሪን ጥፋት ሊያስረዳ አይችልም ተብሎ ፍሬ ነገርን በሚያጣሩና ማስረጃን በሚመዝኑ ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ከተደረሰ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ ሊለውጠው የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ለማስረጃው የሚሰጠው ዋጋ የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነው ከተባለ ደግሞ በባ/ሕ/ቁጥር 196(2) እና 197(1(ሐ)) እና (ከ)) ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ ተጠሪ ለጉዳዩ ኃላፊ የሚሆንበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ አጓጓዥነቱንና እቃው በመርከቦቹ ግጭት ምክንያት ከመርከብ ወደ ውሃ በመውደቅ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ሳይክድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር

በአመልካች ማስረጃ ተጠሪን ተጠያቂ ሊያስደርግ በሚችል በበቂ ማስረጃና ሕግ ያልተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡ መሆኑን የተገነዘበን በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87610 ሐምሌ 03 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71115 ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 60385

ጥቅምት 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ውልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

**አለመልካች፡-** ጎልደን ሮዝ አግሮ ፋርምስ ኃ/የተ/የግ ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፡-** አቶ ሐሊፎም ተስፋ ማሪያም - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍረድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌደ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀረቦ የነበረው ክስ የሠሌዳ ቁ. 3-24690 ኢት እና የልዩ ተጐታች/ተሳቢ/ ሠሌዳ ቁ. 3-09435 ኢት የሆነ የከሣሽ ተሽከርካሪዎች ናይትሪክ አሲድ የተባለ በኮንቴነር የታሸገ የተከሣሽ ንብረት/ጭነት/ ናይኮን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም ታሪንሶ አፍሪካን ትራንዚት በሚባል ተወካይ አማካይነት በከሣሹ ተሽከርካሪዎች ተጭኗል፡፡ ጭነቱን ወደ አዲስ አበባ ለማጓጓዝ እንደተጀመረ በኢትዮጵያ ጅቡቲ ድንበር አካባቢ ሲደርስ አሲድ የተጫነበት ኮንቴነር በየአቅጣጫው ማፍሰስና ማንጠባጠብ ጀምርዋል፡፡ በዚህም በዋናው የከሣሽ ጎታች (power unit) ተሽከርካሪ ላይ መጠነኛ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ልዩ ተጎታቹ /ተሳቢ/ ግን በአሲዱ ሳቢያ በጉማው፣ በቸርኬው፣ ፖንሲውና በሌሎች አካላት ላይ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ በአገልግሎት ላይ ማዋል እንደማይችል የባለሙያው ሪፖርት አረጋግጧል፡፡ በዚህ የተነሣ ተከሣሽ ከከሣሹ ጋር ባደረገው ድርድር መሠረት ዋናውን ተሽከርካሪ በጥገና የሚያስፈልገውን ወጪ እንደሚከፈል ወይም እንደሚያሠራ ልዩ ተጎታቹ ግን ከጥቅም ውጪ ስለሆነ ባለሙያው ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ዋጋውን እንደሚከፍል በጊዜው በቃል ተሰማምቷል፡፡ በመሆኑም ልዩ ጎታች ላይ ለደረሰው ጉዳት ለጥገና የሚያስፈልገውን ብር 26,154 (ሃያ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሣ አራት ብር ) ልዩ ተጎታች ወይም ተሳቢ ለመተካት የገበያ ዋጋ ብር 265,000 (ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ብር) እንዲሁም የተቋረጠ ገቢ 68,427.70 (ስልሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሰባ ሣንቲም) ይሆናል፡፡ ባጠቃላይ ተከሣሽ ብር 359,581.70 (ሦስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ አንድ ከ ሰባ ሣንቲም) ከእነ ህጋዊ ወለድ ጭምር እንዲከፍል እንዲወስንበት በማለት ነው፡፡

ተከሣሽ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተከሣሽ የዕቃው ተረካቢ እንጂ ላኪ አይደለም፣ ታሪንሶ አፍሪካ ትራንዚት ሰርቪስ ወይም ኒካን ኃለ/የተ/የግል ማህበር የተከሣሽ ወኪሎች አይደሉም፣ ተከሣሽ ለደረሰው ጉዳት ለከሣሽ ለመክፈል የገባው አንዳችም ስምምነት የለም፣ ተከሣሽ በከሣሽ ንብረቶች ወይም አሮጌ ተሽከርካሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት በአዲስ ለመተካት ኃላፊነት የለበትም፣ ከሣሽ በሰሌዳ ቁ. 3.09435 ኢት ተሳቢ ዋጋ ብር 265 000 ነው ያለውን በተመለከተ ሊከፍል

የሚገባው የካሣ መጠን በተሸከርካሪው ዋጋ ላይ ለአገልግሎት ዘመን ታስቦ የሚሆነውን የእርጅና እና የአሞርታይዘሽን ቅናሽ ታስቦ ለሚኖረው የተሸከርካሪ ዋጋ ነው እና ተቋረጠ ለተባለው ገቢ በአመታዊ ገቢው መሠረት ከግብር አስገቢ መሥሪያ ቤት የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኂላ ተከሣሽ ለቀረበው ክስ ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ከያዘ በኂላ ዕቃውን በከሣሽ መኪና /ተሸከርካሪዎች/ ላይ ያስጫነው የናይኮን ኃል/የተ/የግል ማህበርም ሆነ ታሪንስ አፍሪካን ትራንዚት ሰርቪስ የተከሣሽ ወኪሎች መሆናቸውን ባለማስረዳቱና ተከሣሽ የደረሰውን ጉዳት ለመካስ የተዋዋለ ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃ ባለመኖሩ ተከሣሽ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማስቀረብ ግራ ቀኙን ካከራከር በኂላ የአሁን አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ከወሰነ በኂላ የካሣውን መጠን በተመለከተ ከሣሽ ቀረብኝ የሚለውን ገቢ በተመለከተ የቀረበውን ነጥብ ውድቅ በማድረግ በሁለቱም ተሸከርካሪዎች ደረሰ የተባለውን በአጠቃላይ ብር 291,154 (ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ብር) ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን የአመልካች ጠበቃ በቀን 30-12-2002 ዓ.ም በሦስት ገጽ የፃፈው የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ለባለቤቱ ለማድረስ የተረከበውን እቃ በአግባቡ ሳያደርስ በመቅረቱ ሊጠየቅ ሲገባው አሲዱ ተሸከርካሪዎቹ ላይ ፈሷል በማለት ያቀረበው ክስ ስለአጓጓዥ ግዴታዎች ተብለው በንግድ ሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የሚፃረር በመሆኑ ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳ የተሸከርካሪዎቹ የአገልግሎት ዘመን እርጅና ተቀናሽ ሳይደረግ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የ3 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ የአጓጓዥን ኃላፊነት በተመለከተ ተሸከርካሪው በመገልበጥ ወይም በመገጨት የደረሰ አደጋ ሳይሆን በዕቃው በራሱ አስተሻሸግ ጥፋት በመሆኑ እና የደረሰውን ጉዳት አግባብነት ባለው ባለሙያ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ያስገመቱት በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም፡- አመልካች የራሱ ንብረት በሆነውና በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ በተጫነው ናይትሪክ አሲድ መፍሰስ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአመልካች ንብረት የሆነው እና በመፍሰስ በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ ጉዳት አድርሷል የተባለው ናይትሪክ አሲድ በኮንቴነር እንደታሸገ ከጅቡቲ ወደብ በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ ያስጫነው አካል

ናይኮን ኃላፊነቱ የተ/የግል ማህበር ወይም ታሪንሶ አፍሪካን ትራንዚት ሰርቪስ የአመልካች ወኪል ስለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ያረጋገጠው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ አከራካሪ አልሆነም፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 561 እና ተከታዮቹን በምንመለከትበት ወቅት የማጓጓዝ ሂደቶችን በሚመለከት ተሣታፊ አካላት መካከል ላኪ፣ ተቀባይና አጓጓዥ ኃላፊነቶች በሰፊው ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በዚህ ጉዳይ ጉዳት አድርሷል የተባለው የአመልካች ንብረት የሆነው ናይትሪክ አሲድ አደገኝነት ያለው ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ በአግባቡ መታሸግ ያለበት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም በአግባቡ መታሸጉን ማረጋገጥ ያለበት ወገን ደግሞ የላከው ስለመሆኑ በንግድ ሕግ ቁ. 578(2) ሥር የተደነገገ በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ደግሞ ላኩ ሊባሉ የሚገባቸው ከጅቡቲ ወደብ እቃውን ያስጫኑት የአመልካች ወኪሎች በመሆናቸው እና አመልካች እንደ የእቃው ባለቤትነት ይሄ መርዘማነት ያለው ንብረት ከመጫኑ በፊት በአግባቡ ስለመጫኑ የማስረዳት ኃላፊነቱ የተጣለበት በመሆኑ ይሄንን ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከላይ የተጣለበትን የህግ ኃላፊነት ስለመወጣቱ ካለማስረዳቱም በላይ የአሁን ተጠሪ የተጫነው ናይትሪክ አሲድ በአግባቡ ያለመታሸጉን እያወቀ የጫነ ስለመሆኑ እና በዚሁም የተነሣ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር የሌለ በመሆኑ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚሁ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ሕግ ቁ. 2069(1)ን በመጥቀስ አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ማመልከቱ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ ያለመሆኑን ይሄ ችሎት የተረዳው ሲሆን ከውጤቱ  አኳያ ግን ከላይ በዚህ ችሎት እንደተመለከተው አመልካች ኃላፊነት አለበት ወደ ሚለው መደምደሚያ የደረሰ በመሆኑ ምክንያቱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 342 መሰረት በመለወጥ የተሰጠውን የኃላፊነት ውሣኔ ተቀብለናል፡፡ በዚህ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡትን የኃላፊነትና የካሣ መጠን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54167 ሐምሌ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 78535 ህዳር 3 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በቀን 11-2-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በትውስት የመጣው የመዝ.ቁ.05737 የሆነ መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 69603

ህዳር 08 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ሀብተወልድ ዘርጋው የጄትሮ የስራ አመራር የማማከር

አገልግሎት ድርጅት ባለንብረት - ጠበቃ ተስፋ አዱኛ ቀረቡ

**ተጠሪ፤-** 1. አቶ ሳሙኤል አሰፋ የጄትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት

ወይም ዩቶር ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት- ራሣቸው ቀረቡ

2. የንግድ ሚኒስቴር - ነ/ፈጁ ተካልኝ ከድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሰረት የሚሰጣቸው የንግድ ስም ጉዳዮች ውድቅ የሚደረጉበትን አግባብና ቅሬታ ያለው ወገን ሊከተለው ስለሚገባው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ ክሱ የተመሰረተውም ባሁኑ ተጠሪና በንግድ ሚኒስቴር ላይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተጠሪና በንግድ ሚኒስቴር ላይ የመሰረተው የክስ ይዘት ባጭሩ፡- በንግድ ሚኒስቴር የተመዘገበውና ያሁኑ ተጠሪ የሚጠቀምበት ጄትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት (Jethro leadership and managemet institute) የሚለው የንግድ ስም አመልካች ከተጠሪ ቀደም ብለው ካስመዘገቡት ጄትሮ የስራ አመራር የማማከር አገልግሎት (Jethro management consultancy service) ከሚለው የንግድ ስም ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ የአመልካችን ተቃውሞ ሳይቀበል ይሄ ተመሳሳይ የንግድ ስም እንዲመዘገብ ማድረጉ በአመልካች ላይ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የሚያስከትል መሆኑን ዘርዝረው 1ኛ ተጠሪ "Jethro" በሚለው የንግድ ስም እንዳይጠቀም እንዲወሰንላቸው፣ 2ኛ ተጠሪም ለ1ኛ ተጠሪ የመዘገበውን የንግድ ስም እንዲሰርዝ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎችም በተከሳሽነታቸው ቀርበው በሰጡት መልስም የንግድ ስም ፈቃድ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 ሲሰጥ ተቃውሞ የሚያቀርበው ወገን ለንግድ ሚኒስቴር ተቃውሞውን በማቅረብ ጉዳዩ ከታየ በሁዋላ ቅሬታ ካለው በይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይታያል እንጂ ቀጥታ ክስ የሚመሰረትበት ጉዳይ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ውጪ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት

የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61"ን" መሰረት በማድረግ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ እንጂ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አይደለም በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231(ሀ)(ለ) መሰረት ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ የማስተናገድ ስልጣን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁኖ እያለ ጉዳዩ በይግባኝ ነው የሚታየው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሥር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61 መሰረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ 2ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6፣ 7፣ 30 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ የመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህንኑ ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ የሚያስፈልጉትና ሊከተላቸው የሚገባቸው ስርዓቶች በአዋጁ ተዘርዝረው ተደንግገው እናገኛለን፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 2(9) እና (16) ድንጋጌዎች ከአዋጁ አንቀጽ 61 ድንጋጌ ጋር ተጣምረው ሲነበቡ ንግድ ሚኒስቴር የንግድ ስም በመመዝገብ ሂደት የሚቀርበውን አቤቱታ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን አስተዳዳራዊ ውሳኔ መስጠት የሚችል መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ ጉዳዮች ብቻ አቤቱታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 61 ድንጋጌ የሚያስቀምጥ ሲሆን በድንጋጌው አቤቱታው ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት አግባብ የተመለከተ ቢሆንም አቤቱታው ቀጥታ ክስን ወይም ይግባኝን የሚመለከት ስለመሆኑ በግልጽ ሁኔታ በድንጋጌው ተቀምጧል ለማለት አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ 2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት (The right to Appeal) እንዳለው ከማስቀመጡ ውጪ ይግባኙ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች በየትኛው እርከን ለሚገኝ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ግልጽ በሆነና አሻሚነት በሌለው አነጋገር አያስቀምጥም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕጉን መተርጎም ተገቢ ይሆናል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61 ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው "በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ" በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "Submission of Complaints on Administrative Decisions)" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ የድንጋጌው እንግሊዝኛ ትርጉም ዝርዝር ሲታይ Any person or a business person or a commercial representative against whom an administrative decision has been taken by the registering 0ffice or the appropriate authority may lodge appeal in connection with his complaints to regular courts only on matters of law. በሚል የተቀመጠ መሆኑን ያስረዳል፡፡ እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ

የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራረብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣ የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን ሕግና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ " Black's Law Dictionary" ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተረጎም A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially, the submission of a lower court's or agency's decision to a higher court for review and possible reversal. በሚል ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ አንድ ፍርድን ወይም ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ/ ውሳኔ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደረግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርዓት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሐብሔር ወይም በሌሎች ሕጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል፣ እንዲለውጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61 ድንጋጌ 2ኛ ተጠሪ በሰጠው የአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ አቤቱታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ "አቤቱታ" የሚለው የአማርኛ ሐረግ በእንግሊዝኛው "Appeal" በሚለው ቃል ተተርጎሞ መቀመጡ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሕጉ አነጋገር በፍሬ ነገር ላይ አቤቱታ ማቅረብ የማይቻል መሆኑ መቀመጡ ቴክኒካዊ በሆኑ ምክንያቶች አስተዳደራዊ አካሉ የሚሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑ ታምኖበት በመሆኑ ፍሬ ነገር ላይ አቤቱታ እንደማይቀርብ ተከልክሎ በሕግ ነጥብ ላይ ብቻ ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ውጤት ያለው ማድረግ ያስችላል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን 2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ሕጎች አውደ ንባብ (contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም፡፡ በሕጉ የተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ሥልጣን ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በቀጥታ ክስ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 181815 ታህሳስ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103990 መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. 2ኛ ተጠሪ የንግድ ስም ምዝገባን አስመልክቶ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለበት ወገን ያለው መፍትሔ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መመስረት አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 63454

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-ዳት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር ባለቤት ዶ/ር ጤናዬ አብተው አልቀረቡም

ተጠሪ፡-1.የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ፅ/ቤት- ነ/ፈጅ ታምሬ ሀይሌ ቀረበ

2. ሲቫ ሳንቴ አሊማሊ ኤስአ/በፈንሳይ አገር የተመዘገበ- ጠበቃ ጥላሁን ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 501/98 መሰረት በሚሰጡት ውሳኔዎች ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚገባበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡የአሁኑ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ መሰሪያ ቤት ላይ የመሰረቱት የክስ ይዘት ባጭሩ፡-አመልካች በሕንድ ሀገር ከሚገኝ አሺሽ ላይፍ ሳይንስ ከተባለ ድርጅት "VEREVIN" የተባለ የእንስሳት መድኃኒት እያስመጣ በኢትዩጵያ ለማከፋፈል ሙሉ እውቅና ያለው መሆኑን፣ ይህን "VEREVIN" የሚለውን ስምና ተጨማሪ ALS የሚል በቀይ ሳጥን ያለመስቀል የሰራን ምስል በንግድ ምልክትነት እንደሚዘገብልን በማለት ለተከሳሽ አመልክተው ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን ገልጾ ይኸው የንግድ ምልክት እንዲመዘገብላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም አመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ እንዲደረግለት ከማመልከቱ በፊት "VEREVIN" ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት ለእንስሳት መድሃኒትነት ምርት ተጠሪ በመመዝገቡ ምክንያት የአመልካችን ጥያቄ አሳካሪ የንግድ ምልክት በሚል መነሻነት አለመመዝገቡን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም ወደ ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ተካፋይ ሁኖ በሠጠው መከላከያ መልስ አመልካች እንዲመዘገብለት የጠየቀው የንግድ ምልክት ጣልቃ ገቡ ካስመዘገበና "VEREBIN" ተብሎ ከሚታወቀው ጋር ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ ሊመዘገብለት አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ እና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ከአጣራ በሁዋላ አመልካች እንዲመዘገብላቸው የጠየቁት ምልክት በአጻጻፉና በአጠራሩ ከጣልቃ ገቡ ምልክት ጋር ተቀራራቢ እንደሆነና ተጠቃሚውን ሊያሳክር እንደሚችል መረጋገጡን ገልፆ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት

ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የአመልካች የንግድ ምልክት እንዲመዘገብላቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአመልካች የንግድ ምልክት ሊመዘገብ አይገባም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 2(4)፣3 እና 8(4) ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ወደ ኢትዮጵያ እያስመጣ የሚያከፋፍለው ምርት "VEREVIN" የሚባለው በሕንድ ሀገር ተመዝግቦና ተመርቶ የሚሠራጭ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም ወደ ኢትዮጵያ እያስመጣ የሚያከፋፍለው ምርት "VEREBIN" የሚባለው በፈረንሳይ ሀገር ተመዝግቦና ተመርቶ የሚሰራጭ ከመሆኑ አኳያ የአመልካች ምርት በኢትዮጵያ ውስጥ አይመዘገብም ተብሎ በ1ኛ ተጠሪ መከልከሉን ከ2ኛ ተጠሪ ምርት ጋር ተቀራራቢ በመሆኑ ተጠቃሚውን ያሳክራል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ መቅረቡና በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ ባግባቡ መሆን ያመሆኑ ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ቀጥታ ክስ መሆኑንና ጥያቄአቸውም 1ኛ ተጠሪ አለመዘግብም ያለው የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ እንዲወሰንላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀጽ 6(1) መሰረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው የአእምሯዊ ንብረት ሕግ መሰረት ምርመራ በማካሄድ ውሳኔ የመስጠትና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 36 መሰረት በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን በማየት ፈራሽ የማድረግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በግልፅ ያስገነዝባሉ፡፡አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ሲታይም አመልካች መስሪያ ቤት ስለንግድ ምልክቱ ምዝገባ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 49 ሲታይ ደግሞ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትን ያሳያል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 47 መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ በተመለከቱት ጉዳዩችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በሚል የሚደነግግ ነው፡፡እንግዲህ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሰኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት(The Right to Appeal) እንዳለው በግልፅ ከማስቀመጡ ውጪ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ የሚቀርብበት ጉዳይ ስለመሆኑ የሚያመላክተው ሁኔታ የለም፡፡በሌላ በኩል አግባብነት ያላቸው የአእምሯዊ ንብረት

ሕጎች ሲታዩ 1ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ የሚችለው በይግባኝ ስርዓት ስለመሆኑ እና ይህን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ደግሞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ከአእምሯዊ ንብረት ሕጎች ጋር ተጣምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ጉዳይ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59025 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው "ይግባኝ የማቅረብ መብት" በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "The Right to Appeal" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራርብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን ሕግና ለመስሪያ ቤቱ ስልጣን የሚሰጡ ሌሎች ተዛምጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ" **Black's Law Dictionary**" ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተርጎም "A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially; the submission of a lower court's or agency's decision to a higher court for **review** and **possible reversal.** በሚል ያስቀምጣል፡፡ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ የአንድ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ/ውሳኔ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደርግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርአት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 320(1) የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሓ ብሔር ወይም በሌሎች ሕጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሓ ብሔር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል፣እንዲለውጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ ፅ/ቤቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ "የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው ሐረግ አቀራረፁና ይዘቱ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡እንዲሁም አመልካች የተቋቋመው አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈጻሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 320/95 በመግቢያው ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 2 ደግሞ "አእምሯዊ ንብረት" እና "ፓተንት" የሚሉትን ቃላት ትርጉም አስቀምጧል፡፡በዚህም መሰረት አእምሯዊ ንብረት ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣የንግድ ምልክትን፣የምስክር ወረቀትንና ኮፒ ራይትን እንደሚጨምር

በአዋጁ አንቀፅ 2(1)ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ፓተንት ማለት ደግሞ የፈጠራ ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ፣በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዲስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/187 መሰረት በፈጠራ፣በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት፣የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2(2) ስር በግልፅ ሰፍሮ እናገኛለ፡፡ይህ መስሪያ ቤት ከሚያስፈጽማቸው ሕጎች መካከል አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንዱ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 2(9 እና 15) ድንጋጌዎች ሲታዩም በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ በግልፅ ያሳያሉ፡፡በሌላ በኩል የፈጠራ፤የአሰነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ስር የይግባኝ ሰልጣኑ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ አንቀፅ 2(1) እና 54 ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ሲነበቡ የሚያሳዩት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሁኖ አግኝተናል፡፡እነዚህ ሕጎች በአመልካች መስሪያ ቤት ይፈጸማሉ ተብለው ከተጠቀሱት ሕጎች መካከል ውስጥ ሲሆን አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙ የሚቀርበው በግልፅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች መስሪያ ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 320/1995 መስሪያ ቤቱን ለማቋቋም ያስፈለገበትን አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈጻሚነታቸውን የሚከታተል አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን በግልጽ ያስፈረ ሲሆን ይህ ምክንያት አመልካች መስሪያ ቤት ተመሳሳይ የአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው አካል ከመሆኑ ተዳምሮ ሲታይ ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ይታያሉ፣ወይም በተወሰኑት ይግባኝ፣በተወሰኑት ደግሞ ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ውጤት ያለው ማድረግ ያስችላል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ሕጎች አውደ ንባብ (Contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም አመልካች መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም፡፡በሕጉ የተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባለቸው የፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ሥልጣን ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ሲጠቃለልም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀፅ 6፣17፣36 እና 49 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ከይግባኝ ትርጉምና አመልካች መስሪያ ቤት ከተቋቋመበት አላማና አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈፅማቸው ከአዋጅ ቁጥር 501/98 ውጪ ያሉት ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች ከዘረጉት የይግባኝ አቀራረብ ሥርኣት አንጻር ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ላይ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የሚከበር እንጂ በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አለመሆኑን፣ይግባኙ መቅረብ ያለበት ደግሞ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ከላይ የተመለከተው የሕግ ትንታኔ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59025 በቀረበው ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ላይ የተሰጠ ሲሆን ይህ የሕግ ትርጉም ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ነው፡፡በመሆኑም በሕጉ አግባብ እስካልተለወጠ ድረስ ለዚህ ጉዳይም ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አግኝናል፡፡በዚህም መሰረት የፍርድ ቤት የስረ ነገር ሥልጣን በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብም በፍርድ ቤቱ አነሳሽነትም መነሳትና ቀድሞ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1ለ)) ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ በማየት ማስተናገዱም ሆነ ይህንኑ ስህተት ሳያርሙ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችም በፍሬ ጉዳዩ ላይ የበኩላቸውን ውሳኔ መስጠታቸው ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59025

ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 113848 ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም.፣የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 50700 ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም. እንዲሁም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 76501 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የንግድ ምልክት ምዝገባ አቤቱታ ላይ አመልካች በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 36935

የካቲት 27 ቀን 2004ዓ.ም.

ዳኞች፡- መሥፍን ዕቁበዮናስ

አማረ አሞኘ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - አቶ ብርሃኑ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አቶ አዲሱ ዱሬሳ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 36819 መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብሔር ይግባኝ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 27357 መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለብድር ውል የተሰጠ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሚያስከትለውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነው አቶ መሐመድ አብደላ አንደኛ ተከሳሽ፣ አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ (ተጠሪ) ለሥር ፍ/ቤት ታህሳስ 7 ቀን 1997 ዓ/ም ባቀረበው የክስ ማመልከቻ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) ደንበኛ አንደኛ ተከሳሽ አቶ መሐመድ አብደላ፤ ከከሳሽ ድርጅት የወሰደውንና መጠኑ ብር 1,930,066.61 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሺህ ስድሳ ስድስት ብር ከስድሳ ሳንቲም) የብድር ገንዘብ አልከፈለም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ አንደኛ ተከሳሽ በብድር የወሰደውን ገንዘብ የማይከፍል ከሆነ እሱ እስከ ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ሥድስት መቶ ሺህ ብር) የሚከፍል መሆኑን በቁጥር YO/BOF/0478/00 በማረጋገጥ ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥቶኛል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ እዳውን በብድር ውሉ መሰረት አልከፈለም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ በሰጠው የዋስትና ግዴታ መሰረት አንደኛ ተከሳሽ ያልከፈለውን ብድር ዕዳ እንዲከፍለኝ ብጠይቀው ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ተከሳሽ ለብድሩ አከፋፈል በሰጠው ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ግዴታ መሰረት አንደኛው ተከሳሽ ያልከፈለውን የብድር ገንዘብ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚለቅ ድረስ ከሚታሰብ 13.5 ፐርሰንት ወለድና በዚህ ክስ ምክንያት ተከሳሽ ያወጣውን ወጪ ጨምሮ ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ከክሱ ጋር በማያያዝ ያቀረበ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በውሳኔው አስፍሯል፡፡

ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) መቃወሚያና መከላከያ መልስ ለሥር ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ የተቋቋመው ለንብረት፣ ለሰው አካልና ህይወት፣ ለኃላፊነት የመድን ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ የተከሳሽ ባለ አክሲዮኖችና የአስተዳደር ቦርዱ በማያውቁት ሁኔታ ከመድን ሥራ ውጭ ተበዳሪውን ዕዳ ለመክፈል የተሰጠው ዋስትና ግዴታ ሰነድ ከሁለተኛ ተከሳሽ መመስረቻ ጽሁፍ መተዳደሪያ ደንብ፣ ስለ መድን ሥራ ፈቃድ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/1986 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተደነገገው ውጭና ሁለተኛ ተከሳሽ ከተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ ውጭ የሆነ ተግባር ነው፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ተራ የመድን ሽፋን ሰጭ የኢንሹራንስ ድርጅት ነው፡፡ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ በተለይም ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ሰነድ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ ልዩ የዋስትና ኩባንያ የሚሰጥ እንጂ በተራ መድን ድርጅት ሚሰጥ የዋስትና ሰነድ አይደለም፡፡ ከሳሽ ይህንን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የፈጸመው ተግባር ህገወጥ ነው፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ላቀረበው ክስ ሁለተኛ ተከሳሽ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ ከሳሽ ሁለተኛ ተከሳሽን የሚከስበት ምክንያት የለም፡፡

የሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ እንድፈርም ልዩና ግልጽ የሆነ ሥልጣን አልተሰጠውም፡፡ ከሳሽ ሥልጣን የሌለው መሆኑን እያወቀ ዋና ስራ አስኪያጁ የፈረመውን የገንዘብ ዋስትና ሰነድ በመቀበል የፈጸመው ተግባር ከጅምሩ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ በመሆኑ ከሳሽ ተከሳሽን የሚከስበት ምክንያት የለም፡፡ በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ሊጠየቅ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ መሆኑ በንግድ ህጉ አንቀጽ 674 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ የሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለከሳሽ ዋስትና ሰነድ ሰጥቷል የሚባል ቢሆን የዋስትና ሰነዱ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1725(ሀ) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727(ለ) በሚደነግጉት መሰረት በሁለት ምስክሮች ያልተፈረመ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው፡፡ ከሳሽ አንደኛ ተከሳሽ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ የወሰደ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ከሳሽ ተበዳሪው አንደኛ ተከሳሽ ምን ያህል እንደከፈለና ምን ያህል ዕዳ እንደሚፈለግበት የሒሳብ መግለጫ አላቀረበም፡፡ የከሳሽ ክስ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ ዕዳውን ያልካደ በመሆኑ የብድር ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ከወሰደው የብድር ገንዘብ እስከ ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ሰነድ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ዋስትና ሰነዱ ከመጀመሪያው ፈራሽና በህግ ፊት ውጤት የሌለው ነው በማለት ያነሳቸው ክርክሮች የህግ ድጋፍ የላቸውም፡፡ ከሳሽ ሁለተኛ ተከሳሽ በሰጠው የዋስትና ግዴታ ሰነድ መሰረት ገንዘቡን እንዲከፍለው መጋቢት 30 ቀን 1994 ዓ/ም እና ጥቅምት 8 ቀን 1995 ዓ.ም. ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን ስላስረዳ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም፡፡ የወለድ መጠኑም በብሄራዊ ባንክ የወጣውን የወለድ ተመን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሁለተኛው ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ አንደኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ወስዶ ካልከፈለውና ክስ ከቀረበበት የብድር ገንዘብ ውስጥ ብር 1,600000 (አንድ ሚሊዮን ሥድስት መቶ ሺህ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍታብሄር ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍታብሄር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የከፍተኛው ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ነው። አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸውን መከራከሪያዎች በሰበር አቤቱታው በመዘርዘር አቅርቧል። መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት በአመልካች መመስረቻ ጽሁፍ፣ በመተዳደሪያ ደንቡ፣ ስለ መድን ንግድ ሥራ ፈቃድ በወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 ድንጋጌዎች ከተፈቀደው ውጭ የሆነ ተግባር ነው። አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የዋስትና ሰነድ ህገ ወጥና ምንም አይነት ተጠያቂነት እንደማያስከትል በመዘርዘር ያቀረብኩትን ክርክር የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማለፍ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ህግ ቁጥር 363 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራትን ከማከናወን ውጭ ሌሎች ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደማይችል ተመልክቷል። የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ እንዲፈርም በንግድ ህግ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ልዩና ግልጽ የሆነ ሥልጣን አልተሰጠውም። የድርጅቱ ማኔጂንግ ዳይሬክተር የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የዋስትና ውል፣ መያዥያ ውል የመዋዋል ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ውሉ ከጅምሩ ህጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ ነው።

የስር ፍ/ቤት አመልካች የሰጠው የዋስትና ሰነድ ነው በማለት በተመሳሳይ ጉዳይ ሌሎች ችሎቶች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት ከሰጡት የህግ ትርጉም የተለየ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። የዋስትና ሰነዱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው የሚባል ከሆነ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የሁለት ዓመት የይርጋ መከራከሪያ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ያለበት ነው። በአመልካች የተሰጠው የዋስትና ሰነድ በህግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው በማለት ያቀረብኩትን ክርክር ህጉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም የታለፈ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል። አመልካች የዋስትና ሰነዱን የሰጠው በተጠሪና ብድሩን በወሰደው በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው መሐመድ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ ከመውሰዱ በፊት ነው። በአመልካችና በተበዳሪው መካከል የብድር ውል ከመፈረሙ በፊት የወጣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ህጋዊ ውጤት የሚኖረውና አመልካችን የሚያስገድድ አይደለም በማለት ያቀረብኩት ክርክር መታለፉ መሰረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ነው። የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የዘረዘርናቸው ተደራራቢ መሰረታዊ የህግ ስህተቶች የተፈጸሙበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል።

አመልካች መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ/ም ጽፎ ላቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2001 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የአመልካች መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 4 አመልካች የተቋቋመው ከሌሎች ስራዎች በተጨማሪ አጠቃላይ መድን ሥራና የረዥም ጊዜ መድን ዋስትና ለመስጠት እንደሆነ ይገለጻል። አመልካች በህግ ያልተከለከሉ ሁሉንም የመድን ስራዎች ለመስራት ይቻላል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኢንሹራንስ ድርጅቶች ስለሚሰሩት አጠቃላይ የመድን ስራና የረዥም ጊዜ የመድን ዋስትና ሪፖርት የሚያደርጉበትን ለመወሰን ባወጣው መመሪያ የገንዘብ ዕዳ ለመክፈል የሚሰጥ ዋስትና በጠቅላላ የመድን ስራ ዘርፍ ውስጥ ከሚካተቱት ተግባራት አንደኛው እንደሆነ ይገለፃል። ለገንዘብ ዕዳ የሚሰጥ ዋስትና አንዱ የመድን አገልግሎት መሆኑ ለጽንሰ ሀሳቡ በህግ መዝገበ ቃላት የተሰጠው ትርጉም ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23/2000 እና 24/2004

ለገንዘብ ዕዳ የሚሰጥ ዋስትና በመድን ድርጅቶች የሚሰራ ተግባር እንደነበር በመግለጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

የአመልካች ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4(3) አመልካች የተቋቋመው በአጠቃላይ የመድን ሥራና የረዥም ጊዜ መድን ዋስትና ከመስጠት በተጨማሪ ለኢንቨስትመንት አመች በሆኑ ሌሎች ሥራዎችን መስራትና እነዚህን የንግድ ዓላማ ለመተግበር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያግዝ ማንኛውንም የንግድ ሥራ እንደሚሰራ የሚያረጋግጥ በመሆኑ አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት ይችላል፡፡ አመልካች ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ የስር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች የሰጠውን የብድር ክፍያ የዋስትና ግዴታ ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ወይም የሚተላለፉ ገንዘብ ሰነድ ነው በማለት ክስ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ የይርጋው ጊዜ የሚታሰበው በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1845 በተደነገገው መሰረት በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታደግም፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ በህግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለው ነው ያለው አግባብነት የለውም፡፡ የዋስትና ሰነዱ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1922፣ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1925 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1725 የተደነገገውን ፎርም ያሟላል አመልካች የዋስትና ሰነዱን የሰጠው በተጠሪና ብድሩን በወሰደው በስር አንደኛ ተከሳሽ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ ከመውሰዱ በፊት ስለሆነ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመፈረም ሥልጣን አለው፡፡ የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ አንቀጽ 33 እና አንቀጽ 35 የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመስጠት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚደነግጉ በመሆኑ የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ የአመልካች ስራ አስኪያጅ የዋስትና ሰነድ የመፈረም ሥልጣን የለውም የሚባል ቢሆን፣ አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1808 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው መሰረት በሁለት ዓመት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ያላቀረበ በመሆኑ በሰበር ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ለውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በስር ፍ/ቤት መከራከሪያ አድርጎ ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እንዲያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከርና ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ አምስት ገጽ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በዚህ መዝገብ ግራ ቀኙ የሚከራከሩባቸው ጉዳዮች ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ.40187 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ናቸው፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ ያቀረቧቸው ክርክሮች ውሳኔ ሊያገኙ የሚገባቸው የህግ ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠቱ አመልካቹ የኢንሹራንስ ኩባንያ ከተፈቀደለት፣ ከተቋቋመበትና ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ከተመዘገበበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተፈፀመ ተግባር በመሆኑ፣ በህግ ተጠያቂ ልሆን አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር፣ የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም?
2. አመልካች የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ የዋስትና ሰነድ ለማውጣት ሥልጣን ሳይኖረው ፈርሞ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ በመቀበል ተጠሪ ለፈጸመው ተግባር

ህጋዊ ተጠያቂነት የለብንም፣ በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር መታለፉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?

3. አመልካች ለተጠሪ የተሰጠው የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃለፊነት የማያስጠይቅ ነው፣ በማለት ያቀረበው ክርክር መታለፉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?

4. ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም?

5. አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይስ አይጠይቅም? አመልካች በኃላፊነት ይጠይቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው።

1/ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 40187 የሰጠው ሰፊ ትንታኔ በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ ላቀረቡት ክርክር ገዥነት ያለው ነው።

ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 86/86 የመድን ንግድ ሥራ ዓይነቶች የሚላቸው ሕግ አውጭው በአዋጁ ትርጉም የሰጣቸውን ጠቅላላ የመድን ንግድ ሥራ፣ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ መድን ንግድ ሥራ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲ(ፖሊሲ)፣ አብይ የመድን ንግድ ሥራ፣ ህይወት መድንና የጠለፋ መድን ሥራዎችን ብቻ እንዳልሆነ

« መድን ንግድ ሥራ ዓይነቶች ወይም የንግድ ሥራ ዓይነት ወይም ሌሎች ሥያሜዎች ባንኩ በዚህ አዋጅ በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገግ ትርጉም ይኖራቸዋል» በማለት በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 በግልጽ ደንግጓል።

ይህ ድንጋጌ አዋጁ ሲወጣ ትርጉም ያልተሰጣቸውና ያልተገለጹ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንበት ሂደት በተቆጣጣሪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ትርጉም የሚሰጣቸውና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲፈጽሟቸው የሚፈቀዱ መድን ንግድ ስራ ዓይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉና የንግድ ሥራዎቹም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ትርጉም የሚሰጣቸው መሆኑን ይደነግጋል። ድንጋጌው የመድን ንግድ ሥራ እንዲሰራ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያ፣ በአዋጁ የተተረጎሙና የተገለጹትን የመድን ንግድ ሥራዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች በብሔራዊ ባንክ ትርጉም የሚሰጣቸውን፣ የሚገለጹትና የሚፈቀዱለትን የመድን ንግድ ሥራ ዓይነቶች ለመስራት እንደሚችል የሚደነግግ ነው።

አከራካሪው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) ምን ዓይነት የህግ ተግባር እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23 /2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትርጉም ሰጥቶታል። የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ማለት በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 " Financial gurantee bond shall mean an obligation undertaken by an insurance company to pay for the lending bank or another creditors or supplier all outstanding claims arising from the non payment by debtor or debtors" የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2002 እና 2004 ዓ/ም ባወጣው መመሪያ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ ከልክሏል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ በግልፅ

የተከለከሉ መሆኑን የደነገገው በመመሪያ ቁጥር 23 /2002 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/ 2004 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ብሔራዊ ባንክ መድን ንግድ ስራ የሚሰሩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ በመመሪያ በግልጽ ከመከልከሉ በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተሰጡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች የሚኖራቸውን ህጋዊ ውጤት ባወጣው መመሪያ ግልጽ አድርጓል፡፡ በኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ከመከልከላቸው በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የተሰጡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች የፀኑና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 24/ 2004 አንቀጽ 3 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23 /2002 እና መመሪያ ቁጥር 24 /2004 በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከላቸው በፊት፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የመስጠት ሥራን እንደ አንድ የመድን ንግድ ሥራ አይነት ሲያከናውኑት የኖሩት ተግባር እንደነበርና ይህም ተግባራቸው ህጋዊ ውጤት ያለውና ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 4/ 2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ በመጀመሪያ መመሪያ ቁጥር 23 /2002/ በማውጣት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ የከለከላቸው፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከተቋቋሙበት መድን የንግድ ዓላማ ውጭ የሆነ ስራ ነው በማለት አይደለም፡፡ በኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ የተደረገው ክልከላ መነሻ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሌላውን ሰው ዕዳ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሲሰጡ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት በገቡት የዋስትና ግዴታ መሰረት ለባለመብቱ (አበዳሪው) የከፈሉትን ገንዘብ ከባለዕዳው ለማስመለስ የሚያስችላቸው በቂ መያዥያ ሚሆን የተበዳሪው ንብረት ወይም ገንዘብ የማይዙ ወይም የማያገኙ በመሆኑና በአገሪቱ አስተማማኝ የሆነ የጠለፋ መድን ዋስትና የሌለ በመሆኑ ምክንያት፣ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመከላከል በማሰብ መሆኑን በመመሪያው መግቢያ ላይ በግልጽ አስፍሮታል፡፡

ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ በማውጣት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከሉ በፊት ወጭ አድርጎ ለተጠሪ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Finanicial Gurantee Bonds) መስጠት ከተቋቋምኩበት የንግድ ዓለማ ውጭ የተፈጸሙ ተግባር በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና አመልካችን በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የማይችል ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ አውጥቶ ከመከልከሉ በፊት ለተጠሪ የሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Finanicial Gurantee Bonds) ፣አመልካች እንዲሰራ ከተፈቀደለት መድን ንግድ ሥራና ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተሰጠ ሰነድ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2/ ሁለተኛው ጭብጥ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶቹ ወጭ በሆኑበት ወቅት የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ የነበረውን ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የዋና ስራ አስኪያጁን ስልጣን መገደብና የስራ አስኪያጁ ስልጣን ላይ የተደረገውን ገደብ በንግድ መዝገብ ውስጥ በሚጻፈው ቃል እንድገባለትና እንድመዘግብለት በግልጽ ባቀረበው ማመልከቻ ውስጥ በመግለጽ፣ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑ በግልጽ በንግድ መዝገብ በተመዘገበው ቃል ውስጥ እንዲመዘገብ ካላደረገ በስተቀር የህንን መከራከሪያ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊያደርገው አይችልም፡፡ ይህንንም ከንግድ ሁጉ አንቀጽ 36 አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ድንጋጌዎች አቀራረጽና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ ወይም የተገደበ መሆኑን በንግድ መዝገብ በሰፈረው ቃል ውስጥ አለማስመዝገቡ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

አመልካች በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ መሆኑ እንደተገለጸ በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ሆኖም ይህ የአመልካች ክርክር የንግድ ሕጉ በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 ስራ አስኪሃጅነት ሥልጣን ያለው ሰው አንድ ቅርንጫፍ ሥራ ለማስኬድ ብቻ ሥልጣን በመስጠት ስልጣኑን የተወሰነ ለማድረግ ይቻላል፣ ስለሆነም እንደዚህ ያለው የስልጣን መቀነስ ማስታወቂያ በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር በዚህ ህግ አንቀጽ 121 መሰረት መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም በማለት በግልፅ የደነገገውን ያላገናዘበ ነው፡፡ በተለይም የአመልካች ክርክር በግኝት ህጉ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) እና የንግድ ህጉ በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 ሌላው አይነት  የስልጣን መቀነስ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም በማለት ለሶስተኛ ወገኖች በግልጽ የሰጠውን ጥበቃ ያላገናዘበና የህግ ድጋፍና መሰረት የሌለው ነው፡፡ ሕግ አውጭው እነዚህን ድንጋጌዎች የደነገገው በግብይት ሂደት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ ጋር ውል የሚዋዋሉ ሰዎች የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መመርመርና ማንበብ እንደሚያስፈልጋቸውና ድርጅቱ በንግድ መዝገብ ያስገነዘባቸውን ፍሬ ጉዳዮች ብቻ በማየት ከአመልካች ጋር በቅን ልቦናው የሚዋዋሉ ሶስተኛ ወገኖች ውለታው በህግ ተፈጻሚነት የሚኖረው መሆኑን በማረጋገጥ ከፍተኛ ጥበቃ ለመስጠት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች አመልካች ዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣን ሳይኖረው ለፈረማቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች በኃላፊነት አልጠየቅም በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ሥህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3/ ሶስተኛ ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ የተሰጠውን የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃላፊነት የማያስጠይቅ ነው፣ በማለት ያቀረበውን ክርክር የህግ መሰረት ያለው መሆኑን መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ በመጀመሪያ የዋስትና ሰነዱ አመልካች ለሌላ ሰው ዕዳ ማለትም የአቶ መሐመድ አብደላ የብድር ዕዳ ለመክፈል የተሰጠ ሰነድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሰነዱ ስለዋስትና ግዴታ በፍታብሄር ህግ አንቀጽ 1922 የተደነገጉትን መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች የሰጠው የዋስትና ሰነድ መሆኑንና በፍታብሄር ህግ አንቀጽ 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን መሰረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟሉ መሆኑን በስር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ የፍታብሔር ሕግ አንቀጽ 1725 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) የፍታብሄር ሕግ አንቀጽ 1727 በተደነገገው መሰረት በተጠሪና በሁለት ምስክሮች አልተፈረመም በማለት ተከራክሯል፡፡ ሆኖም ይህ የአመልካች ክርክር (Finanicial Gurantee Bond) እንደማንኛውም የዋስትና ውል በተዋዋይ ወገኖች የሚዘጋጅ ሰነድ ሣይሆን የመድን ንግድ ሥራ እንዲሰራ የተፈቀደለት የኢንሹራንስ ኩባንያ በተሰጠው ልዩ ፈቃድ

ተጠቅሞ፣ የሚዘጋጀውና የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል ራሱን ግዴታ ውስጥ የሚያስገባበት የማገቻ ሰነድ እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/ 2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 ለገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) የተሰጠውን ትርጓሜ ግንዘቤ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

እንደዚሁም አመልካች የሰጠው የማገቻ ሰነድ (Bond) የግድ በምስክሮች መረጋገጥ የሌለበት መሆኑን ሕግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 110/1990 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ለማገቻ ትርጉም ሲሰጥ "አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል" በማለት ከተጠቀመው አገላለጽና በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ለዋስትና ሰነድ ከተሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ሥያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳያወጡ በመመሪያ ከመከልከላቸው በፊት ወጭ ያደረጓቸው የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነዶች (Finanicial Gurantee Bond) የጸኑና ህጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን " Finanicial Gurantee Bond or other unconditional bonds issued by insurance conpanies and outstanding before the effective date of these directives shall remain enforce until the expiry date or shall be phased out in line with an action plan submitted by each insurance company and agree with the bank" በማለት የገለጸውን የመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ የሚቃረንና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተበዳሪው አቶ መሐመድ አብደላ ከተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ባይከፍል እሱ የሚከፍል መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን የማገቻ ሰነድ ልዩ ባህሪ ያለውና በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚዘጋጅና ወጭ የሚደረግ የማገቻ ሰነድ በመሆኑ፣ አመልካች ሰነዱ በሁለት ምስክሮች ስላልተረጋገጠ የዋስትና ሰነዱ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

4/ አራተኛው ጭብጥ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? አመልካች የሰጠው ሰነድ የመድን ውል አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል የአንድነት የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የዋናውን ባለ ዕዳ ግዴታ ነጻ የሚያደርጉ የይርጋና ሌሎች መከራከሪያዎች በማቅረብ ከኃላፊነት ነጻ እንደሚሆን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ እንቀጽ 1 ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋሱ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ ገደብ በዋናው ባለዕዳ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ እንደሆነ፣ በዋናው ባለዕዳ ላይ የተጀመሩ ክሶች ለዋሱ መቆጠር የጀመረለት የይርጋ ዘመን ያቋርጡበታል በማለት ፍታብሔር ህግ ቁጥር 1929 የደነገጉትን ምክንያት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአበዳሪው በተጠሪና በተበዳሪው አቶ መሐመድ አብደላ መካከል የተደረገው የብድር ውል ላይ ተፈጻሚነት ያለው ስለ ውሎች በጠቅላላው የሚደነግገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው፡፡ የአመልካች (የዋሱ) ግዴታ ቀሪ የሚሆነው የዋናው ባለዕዳ ግዴታ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍታብሄር ህግ ቁጥር 1845 እንደሆነና ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር መቀበላቸውና ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

5/ አምስተኛው ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይም አይጠየቅም? በኃላፊነት ይጠየቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው? ሚለው ነው፡፡ አመልካች አቶ መሐመድ አብደላ ከተጠሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በብድር ውሉ መሰረት ካልከፈለ እስከ ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ሥድስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ለተጠሪ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥተዋል፡፡ ተበዳሪው ዕዳውን በብድር ውሉ መሰረት አለመክፈሉ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የዋስትና ግዴታ እስከሰጠበት ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ስድስ መቶ ሺህ ብር) ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1930፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1924 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1922 ንዑስ አንቀጽ 2ን የመሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደዚሁም የስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ምክንያት ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብና ሌሎች ወጪዎች አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1931 ን መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር ባየናቸው ጭብጦች ላይ የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 36819 መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 27357 መጋቢት 10 ቀን 2000 የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፣ ለሚመለከተው ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 47004

መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት- ነ/ፈጅ ናሆም ሽዋንግዛው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ባሌ ገጠር ልማት ድርጅት - ጠበቃ በሻዳ ገመቹ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች ሰጠ የተባለው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና (performance Bond) የሚገዛበት የሕግ ክፍልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ የመድን ውልን መሠረት ያደረገ ነውና በንግድ ሕግ ቁጥር 674 በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል የግልግል ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የሚገዛው በፍትሐ ብሔር በተመለከተው የዋስትና ድንጋጌዎች እንጂ በንግድ ሕጉ በተመለከቱት ባለመሆኑና ይርጋውም የአስር አመት ጊዜ ሁኖ ያላለፈበት ነው ተብሎ በጉባኤው ውሣኔ መሻሩን በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ ለስራ ተቋራጩ የተሰጠው አረቦን /Premium/ ማስከፈል በመሆኑ፣ ይህንን ቦንድ የሰጠው የመድን ድርጅት መሆኑን እና እንደመቼውም የመድን ውሎች ኮንትራክተሩ ለሶስተኛ ወገን ጥቅም መድን የገባ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሕጋዊ ድጋፍ የሌላቸው ምክንያቶች /ትንታኔዎችን/ በመስጠት የግልግል ጉባኤው አብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ በንግድ ሕግ ቁጥር 654 እና በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን አሰራሮችን የሚፃረር ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ሰጠ የተባለው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ የሚገዛው በንግዱ ሕጉ ስለመድን በተመለከቱት ድንጋጌዎች ነው ወይስ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለ ዋስትና በተመለከቱት ድንጋጌዎች ነው የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲያቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ለሰበር ችሎት በሰጠው መልስም ተጠሪ ለሚያስራው መንገድ የጨረታ አሸናፊ የሆነው አክሱም ኮንስትራክሽን በኮንስትራክሽን ውሉ አንቀጽ 6 መሠረት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና /Performance bond/ ለማቅረብ በገባው ግዴታ መሠረት የአሁን አመልካች ስራ ተቋራጩ ለሚያደርሰው ማናቸውም የውል ቃለ አለመጠበቅ እስከ ብር 1,101,890 ኃላፊነት

በመውሰድ ጥቅምት 10 ቀን 1989 ዓ.ም የተፈረመ የመልካም ሥራ ዋስትና ለተጠሪ መስጠቱን፣ ኮንትራክተሩ በውሉ የገባውን ግዴታ ባለመውጣቱ በቀረበው ክስ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች የተሰጠው ሰነድ በፍ/ብ/ሕጉ የተመለከተው ዋስትና ሁኖ በንግድ ሕጉ የሚገዛ የመድን ሽፍን አይደለም በማለት በ10 ዓመት በይርጋ አይታገደም ሲል የጉባኤውን ብይን መሻሩ ሕጋዊ ነው፤ ሰነዱ የተፃፈው "surety" ተብሎ እንጂ "insurer" አለመባሉን፣ ሕንፃ ተቋራጩ "contracter" እንጂ "insured" ተብሎ አለመገለጽን፤ ሌሎችም በውሉ ውስጥ የተጠቀሱት የተዋዋዮች ወገኖች ስያሜ በፍ/ብ/ሕግ የተጠቀሰውን እንጂ በንግድ ሕጉ የተጠቀሰውን "መድን ሰጪ" እና "መድን ተቀባይ" ያልተባለ መሆኑን፣ የግዴታ አቀባበል ባሕርያትም የመድን ውልን የሚመለከት መሆኑን አመልካች በግልጽ "ዋስ" ተብሎ መግለጽን፤ እንዲሁም ስለ "performace bond" እና "bond" በተለያዩ የሕግ መዝገብ ቃላት እና በመረጃ መረብ የተሰጡትን ትርጓሜዎች እና መሠረት ልማት በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የተዘጋጀ "የሲቪል ስራ ፕሮጀክቶች የውል እስታንዳርድ" አካል በተደረገው ፌዲክ ሰነድ /FIDIC/ የተሰጠውን ትርጉም የሚያሳየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ መሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቅርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ለጭብጡ ምላሽ ለመስጠት ያመች ዘንድም የኮንስትራክሽን ስራ ልዩ ባህሪይን መመልከት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ ወይም (ቦንድ) ትርጉሙን ማየትና የዚህን ሰነድ ዓላማ ከኢንሹራንስ ውል ልዩ ባህርይ አንፃር ማየቱ አግባብነት ያለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀው የኮንስትራክሽን ውል መንገድ፣ ሕንፃ፣ የሃይል ማመንጫ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ የባቡር ሐዲድ፣ የውሃና ግድብና ቁፋሮ እና ሌሎች የሲቪል ምህንድስና ስራዎች ለማስገንባትና ለመገንባት የሚደረግ ውል ሲሆን የውሉ አመሰራትና ውጤት በፍትሐ ብሔር ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የሚገዛ ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ውል ባሕርይው ሲታይ በተዋዋይ ወገኖች ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን በበርካታ የውል ትስስሮች የተያያዘና ውሉን ለመዋዋልም ሆነ ለመፈፀም ብዙ ስራዎችን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ አፈፃፀሙ ረዘም ያለና ተገቢውን ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑ ይታመናል፡፡
ወደ መልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ /ቦንድ/ ትርጉሙንና ዓላማ ስንመጣ ደግሞ ታዋቂው የብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት፡-
"Peroformance bond is a bond given by a surety to ensure the timely performance of contract, a third parties agreement to guarantee the completion of construction contract upon the default of the general contractor. Also termed as completion bond, surety bond contract bond." Suretyship bond a contractual arrangement between the surety, the principal and the oblige where by the surety agrees to protect the oblige if he default in perfoming the principals'' contractual obligation." The bond is the instrument which binds the surety" በማለት የሚተረጉመው ሲሆን ከዚህም በቀላሉ መረዳት የሚቻለው የመልካም ሥራ አፈፃፀም /ቦንድ/ ሰነድ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውል ስለመፈፀሙ ለማረጋጥ የሚሰጥ ሰነድ፣ ሶስተኛ

ወገን የሆነ አካል ስራ ተቋራጩ የኮንስትራክሽን ውሉን ካልፈፀመ ስራው በውል መሠረት እንዲፈፀም የሚሰጠው የዋስትና ሰነድ መሆኑን፣ ቃሉም የአፈፃፀም /ማስጠንቀቂያ/ ሰነድ፤ የዋስትና ሰነድ፣ የውል ሰነድ በሚሉ ቃላቶች ሊተካ የሚችል መሆኑን፣ የዋስትና ሰነድ ሰጪ ዋስ ተብሎ የሚጠራ ሶስተኛ ወገን መሆኑን፣ ይህም በባለገንዘብ እና በባለ እዳ መካከል የተደረገን ውል አፈፃፀም ለመጠበቅ የሚገባ ግዴታ መሆኑም፣ እና ዋሱ ግዴታ የገባበት ሰነድ መጠሪያም ቦንድ የሚባል ሰነድ መሆኑ ነው፡፡ ከላይ የተመለከተው የሕግ መዝገብ ቃላት የቃሉ ፍቺ ስለ መልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳይ ሁለት ውሎች የሚደረጉ መሆኑን እና ሶስት ወገኖች መኖራቸውን ያመለክታል፡፡ ይህንን ዓይነት የዋስትና ሰነድ /ቦንድ/ የማውጣት ወይም በመስጠት የሚታወቁት በዋናነት ባንኮች እና መድን ድርጅቶች እንደሆኑም ያመለክታል፡፡

በአገራችን የሕግ ማእቀፍ ውስጥ ያሉትን አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ስንመለከትም ስለ ቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 2/2/ የአማርኛ ቅጂ፡-
“ማገቻ” ማለት የተወሰነ ነገር በመፈፀሙ ወይም ባለመፈፀሙ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚያገባበት ማንኛውም ሰነድን ይጨምራል” በማለት ሲያስቀምጥ የእንግሊዝኛ ቅጂው ደግሞ፡-
“Bond includes any instrument…whereby a person obliges him self to pay money to another” በሚል አስቀምጦታል፡፡
በዚህ አዋጅ “ቦንድ ወይም ማገቻ” ሰፋ ያለ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን በተግባር የሚታወቁት በርካታ የቦንድ ዓይነቶች እንዳሉና እነዚህም በትርጉም ውስጥ ሊሸፈኑ እንደሚችሉ ተጠቃሹ አዋጅ ያሳያል፡፡ በዚህ መሠረት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና /performance bond/ bid bond ወይም /የጨረታ ሰነድ/ bail bond /የዋስትና ወረቀት/ /Treasury bond/ /የግምጃ ቤት ሰነድ/ የመሳሰሉት ትርጉሙ ሊያጠቃልል ይቻላል፡፡ እነዚህ ሰነዶች የተወሰነ የገንዘብ ነክ ግዴታ መፈጠሩን የሚያመለክቱ የገንዘብ ሰነዶች አሊያም እንደ አግባቡ የዋስትና ሰነዶች ሆነው ሊያገለግሉ የታሰቡ መሆናቸውን ከትርጉማቸው ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ የዋስትና ሰነድ ማለት ለፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈፀም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ነገር ሲሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል በማለት በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2(18) 18 ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ ይህንኑ አዋጅ ቁጥር 57/1989 ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቀጥር 648/2001 አንቀጽ 2(20) ስር ደግሞ የዋስትና ሰነድ ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታ ለመፈፀም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ማንኛውም ሰነድ ሲሆን፣የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች ስለቦንድ ትርጉም የተሰጠ ሲሆን አከራካሪውን ጉዳይ ሊገዙ ይችላሉ ተብለው በተከራካሪ ወገኖች ለክርክር መሰረት በሆኑት የፍትሐ ብሔር ሕጉና የንግድ ህጉ ግን በዚህ ረገድ በግልጽ የተቀመጡ ወይም አመልካች የሆኑ ድንጋጌዎች የሉም፡፡ በአንድ ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ስለአንድ ቃል ግልጽ የሆነ ትርጓሜ ያለማስቀመጡ ከታመነ በስራ ላይ ባሉት ሕጎች ውስጥ ያለውን ትርጉም መፈተሽና ለአከራካሪው ቃል ትርጓሜ መስጠት የሚፈቀድ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያሣዩት ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ነገረ ፈጅ ስለአመልካች የስራ አፈፃፀም ትርጉም ለመስጠት የኢንሹራንስ ውሉን ከሚገዙ ሕጎች ውጪ ያሉትን ሌሎች ሕጎችን ለውሣኔው መሠረት ማድረግ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የሚያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት ሕጎችን መሰረት በማድረግም የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መሠረታዊ ባሕርይ

ከኢንሹራንስ ውልና ከዋስትና ውል ማነፃፀሩ ጉዳዩን የሚገዛውን የሕግ ማእቀፍ ለመለየት የሚያስችል ሁኖ አግኝተናል፡፡

በዚህም መሰረት ስለ የመድን /ኢንሹራንስ/ ውል ምንነት እና አፈፃፀሙን ስንመለከት ደግሞ በ1952 ዓ/ም በወጣው የንግድ ሕግ በአንቀጽ 654 እስከ 712 ተደንግጐ እናገኛለን፡፡ የመድን ውሎች በጽሑፍ ከመደረጋቸውም በላይ "ፖሊሲ" በሚል ልዩ ሰነድ ላይ መደረግ ያለባቸው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725(ለ)፣1720፣1727 እና 1719(2) እንዲሁም ከን/ሕ/ቁጥር 657(1) ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመድን ውሉ የሚፀናው ሲፈረም መሆኑን የተመለከትን ሲሆን በመድን ስራ ትልቁ ነገር ተብሎ ሊወሰድ የሚችለው የአረቦን ጉዳይ ሲሆን መድን ሰጪዎች በመድን ገቢዎች ላይ ለሚደርሰው አደጋ ካሣ የመክፈል ግዴታ የሚገቡት ከመድን ገቢዎች በአረቦን መልክ ገንዘብ ስለሚሰበሰቡ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመድን ውል ከሚታወቁት ነጥቦች መካከል አንዱ የመድን ጥቅም /insurable interest/ የሚባለው ሲሆን ይህም ከመድን ሰጪው ካሣ የሚቀበለው ጉዳት በደረሰበት እለት ጉዳት በደረሰበት ንብረት ወይም እቃ ላይ የመድን ጥቅም ያለው ሰው መሆኑን የሚያስገነዝበን ሲሆን የመድን ጥቅም የሌለው ሰው ካሣ ለመጠየቅ የሚያስችለው የሕግ መሰረት የለውም፡፡ የመድን ጥቅም ያለው ሰው ሲባል እንግዲህ በደረሰው አደጋ ወይም ጉዳት በትክክል የተጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ሰው ስለመሆኑ ይታመናል፡፡ ጠቅለል ተደርጐ ሲታይ በን/ሕ/ቁጥር 654(1) ስር እንደተመለከተው የኢንሹራንስ ውል ኢንሹራንስ ሰጪ ተብሎ የሚጠራ ሰው ፕሪሚየም ተከፍሎት አንድ አይነት አደጋ ሲደርስ ተጠቃሚ ተብሎ ለሚጠራ ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል የሚገባው ግዴታ ሲሆን በንብረት ወይም በሰው ሕይወትና ጤንነት ወይም በሌላ መብት ላይ የአደጋው መድረስ የውሉን ውጤት ለማስገኘት መሠረታዊ ሁኔታ በመሆኑ የአደጋው አይነት ብዙ በመሆኑ በኢንሹራንስ የሚሸፈነው አደጋ በውሉ ላይ የተመለከተው ብቻ ይሆናል፡፡ በአንፃሩ የዋስትና ውል የፍ/ብ/ሕጋችን አንቀጽ 1920 እስከ 1951 ተደንግጓል፡፡ እነዚህን የሕግ ድንጋጌዎች በማነፃፀር የዋስትና ውል ልዩ ባህርያትን ስንመለከት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1921 ድንጋጌ የዋስትና ውል በችሮታ ላይ የተመሰረተ ግዴታ መሆኑን፤ እንዲህም ሲባል ዋሱ ዋስ በመሆኑ የሚያገኘው ጥቅም የሌለ በመሆኑ አንድ ሰው ባለእዳው ሳይጠይቅ ወይም ሳያውቅ ዋስ መሆን እንደሚችል መመልከቱ ግንኙነቱ የግድ ጥቅም ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ የዋስትና ውል ሌላው ልዩ ባሕርይ ውሉ ደባል መሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1926(1) ስር እንደተመለከተው አቢይ ግዴታ ሲቀር የዋስትናው ግዴታ አብሮ የሚቀር መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ የዋስትና ውል እንዲኖር በዋስትና ሊረጋገጥ የሚልች ግዴታ መኖር አለበት፡፡ እንዲሁም የዋስትና ውል ግልጽና የማያሻማ ግዴታ መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922(1) እና (2) ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ በስተጀርባ ያለው ምክንያትም ዋስትና አንድ ሰው ራሱ በግል ተጠያቂ ለማይሆንበት ግዴታ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ብሎ የሚሰጠው ማረጋገጫ በመሆኑ ግዴታ ገቢው በግልጽ ተረድቶ ግዴታ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ኃላፊነቱን መሸከም ተገቢ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ የዋስትና ውል  ግዴታ ከዋናው ግዴታ እኩል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1924(1) ስር የተመለከተ ሲሆን ውሉ ለባለ ገንዘቡ ብቻ የሚሰጥ ማረጋገጫ በመሆኑ ውጤት የሚኖረው በተዋዋዮቹ ማለትም በዋሱና በባለ ገንዘቡ መሃል ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 (3) ስር እንደተመለከተው ሌላው የዋስትና ውል ልዩ ባሕርይ የዋስትና ውሉ የዋሱን ግዴታ መጠን በግልጽ ማስቀመጥ ያለበት መሆኑ ሲሆን የዋስትና ገንዘብ መጠን ዋስትና ውል ላይ በግልጽ ካልተቀመጠ ዋስትናው ውጤት የለውም፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1920 እስከ 1951 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የዋስትና ውል ማለት ሁለት ሰዎች ባደረጉት የባለገንዘብነትና የባለእዳነት ግዴታ ግንኙነት ውስጥ ከእነዚህ ተዋዋዮች ውጭ

የሆነ ሌላ ሶስተኛው ባለእዳው እዳውን በሙሉ ወይም በከፊል ያልከፈለ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም ግዴታውን በውሉ በተመለከተው አኳኋን በአግባቡ ያልተወጣ ከሆነ እኔ በባለእዳው ሥፍራና አቋም ሁኜ እዳውን እከፍላለሁ ወይም ግዴታውን እወጣለሁ ሲል ለባለገንዘቡ ማረጋገጫ የሚሰጥበት በሕግ አግባብ መቋቋሙ ከተረጋገጠ ከስተጀርባው ለአፈፃፀሙ የሕግ ጥበቃ የሚያገኝ ውል ነው።

ሌላው ከላይ እንደተመለከትነው የዋስትና ግዴታ ሰነድ ብዙ ሰነዶችን ሊይዝ የሚችል መሆኑ ከላይ የተመለከተ ሲሆን የገንዘብ ዋስትና ግዴታ (financial Gureantee Bond) የሚጠቅስ ነው። ይህ ሰነድ ምን አይነት የህግ ተግባር እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ዓ.ም አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ3 “Financial guarantee bond shall mean an obligation undertaken by an insurance company to pay for the lending bank or another creditors or supplier all outstanding claims arising from the non payemt by debtor or debtors” የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑ፣ ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1(1) እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ዓ.ም አንቀጽ 1(3) ለገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሰጠው ትርጉምና ከላይ በተጠቀሱት የሕግ ማእቀፎች ሕግ አውጭው የሰጠው ትርጓሜዎች ሲታዩ መሠረታዊ ባህሪውም ሆነ በይዘቱ የመድን ውል ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር የማይመሳሰልና መሠረታዊ መስፈርት የሚያሟላ ስላለመሆኑና መገዛት ያለበትም በንግድ ህጉ በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌዎች ሳይሆን በፍትሐ ብሔር ሕጉ ዋስትናን በተመለከተ በሚገዙ ሕጐች መሰረት ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 40187 በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ ሰነዱ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ሳይሆን የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ ነው። በብሔራዊ ባንክ ወጥቶ ተግባራዊ የሆነው ከላይ የተጠቀሰው መመሪያ ስለዚህ ሰነድ የሚሰጠው ትርጉም የለም። መመሪያው ትርጉም የሠጠው ስለገንዘብ ዋስትና ሰነድ ሲሆን ለዚህም “Financial guarantee bond” shall mean a bond payable on demand issued by an insurance company obliging such insurance compamy to pay to a lending bank or another creditor or supplier all outstanding claims arising form non-payment by principal debtor or debtrs; **በማለት ከገለፀ በሁዋላ** “unconditional bond” shall mean a bond other than financial gurantee bond issued by an insrance company that is payable to the beneficaiary on demand, without any preconditions attached to such payemnt” ሲል ያስቀምጣል። እንዲህ ከሆነ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የሐረጉ ስያሜ እንዳለ ሲታይ አንድ ሰው አንድን የተለየና የተወሰነ ስራ ለሌላ ሰው ለመስራት ግዴታ ከገባ ይኸው ሰው በውሉ መሠረት የገባውን ግዴታ መፈፀም የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ ሌላው ሰው የሚያቀርበው ውል ነው። በመሆኑም የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ ብሔራዊ ባንክ በውሉ የተገባው ግዴታ በአግባቡ መከናወን የሚችል በመሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ሰነድ በመሆኑ “uncondtional bond” ተብሎ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚወድቅ አይደለም።

ከኮንስትራክክሽን ሰዎች ጋር በተያያዘ ተፈጽሚነት አላቸው ከሚባሉት ሰነዶች መካከል አንዱ የ”ፊዲክ” የውል ፎርም ነው። አሰሪ የሆነው ተጠሪና የስራ ተቋራጭ ባደረጉት ውል የሥራና

ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሲቪል ስራዎች ፕሮጀክት ስታንደርድ የውለታቸው አካል እንዲሆን መስማማታቸው በፍሬ ነገረ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴ የሲቪል ስራዎች ፕሮጀክት ስታንዳርድ ደግሞ "The FIDIC form of contract" አካል ነው፡፡ ይህ የፌዲክ ውል ፎርሙ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ለኮንስራክሽን ስራው በውሉ መሠረት መከናወን ዋስትና የሚሰጥ ሰነድ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የኢንሹራንስ ፖሊሲ አይነተኛ ባህርይ መድን ገቢው የኢንሹራንስ ሽፋን በተሰጠው ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም (insurable interst) ያለው መሆኑን ይጠይቃል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ከስራ ተቆራጩ ጋራ ባደረገው ውል አከራካሪውን የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንዲቀርብ የፈለገበት አይነተኛ ምክንያት ተጠሪ ለሚሰራው መንገድ የጨረታ አሸናፊ የሆነው አክሱም ኮንስትራክሽን በኮንስትራክሽን ውሉ አንቀጽ 6 መሠረት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና /performance bond/ ለማቅርብ በገባው ግዴታ መሠረት የአሁን አመልካች ስራ ተቋራጩ ለሚያደርሰው ማናቸውም የውል ቃል አለመጠበቅ እስከ ብር 1,101,890 ኃላፊነት በመውሰድ ኮንትራክተሩ በውሉ የገባውን ግዴታ ባይወጣ በውሉ መሰረት ስራው ባለመስራቱ ለሚደርሰው ጉዳት አመልካች የሚከፍለው መሆኑን በማመን ነው፡፡ ተጠሪ የመንገድ ስራውን የሰጠው ተቋራጭ መንገዱን በውሉ መሰረት ባለመስራት ለተጠሪ ባለእዳ ከመሆን አልፎ አመልካች ለመልካም ስራ አፈፃፀም ለመክፈል በተሰማማው ገንዘብ መከፈል ወይም አለመክፈል ላይ የመድን መብት ወይም ጥቅም (insurable interest) ያለው ወገን አይደለም፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በአክሱም ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል የተደረገው ውል መድን ውል ነው፣ ተጠሪ ደግሞ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ሰነድ ስራ ተቋራጩ በውሉ በተመለከተው ጊዜና ሁኔታ የመንገድ ግንባታው ስራውን ካላከናወነ ተጠሪ በመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ የተገለፀውን ገንዘብ ለመክፈል በሰነዱ ውስጥ ለተገለፀው ስራ ብቻ ዋስትና የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰጠው የመልካም ሰራ አፈፃፀም ዋስትና የግዴታ ሰነድ ስራ ተቋራጩ ስራውን ባይሰራ አመልካች መጠኑ በሰነዱ የተገለፀውን ገንዘብ ለመክፈል የአንድነትና የነጠላ የዋስትና ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር አመልካች የሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ሰነድ በመሰረታዊ ባሕሪውና ይዘቱ የመድን ውል ሣይሆን ያልተነጣጠለ የዋስትና ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያሣይ ሰነድ በመሆኑ ሊገዛ የሚገባው በንግድ ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ሣይሆን በፍታሐ ብሔር ሕጉ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች የገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት የፍሬ ነገር እና የሕግ ምክንያቶች የመድን ውል ሳይሆን በፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1920 እና ተከታዮቹ የሚሸፈን የዋስትና ውል ነው፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ስር የተመለከተው የአስር አመት ይርጋ ጊዜም አላለፈም ተብሎ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 410054 መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል
2. የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ የኢንሹራንስ ውል ሳይሆን የዋስትና ውል በመሆኑ የሚገዛው በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 1921 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ የአስር ዓመት ጊዜ አላለፈበትም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ይግባኝ ባይ ዝርዝር የማቅረብ መብት ተጠብቋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 71134

ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ያሬድ ሲሳይ ከጠበቃ ግሩም አየለ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አልግሪን አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ጠበቃ ውቤ ጓዳ ቀረቡ

መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የማህበር ይፍረስልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው ክስ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ማህበሩ የሚፈርስበት በቂና ትክክለኛ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ወድቅ በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ውሣኔ በማጽናቱ የተፈጸመው መሠረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው አቤቱታ ተፈጸመ ያለውን መሠረታዊ የህግ ስህተት በማንሳት የተከራከረ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ማህበሩ አይፈርስም ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሱት ኃ/የተ/የግል ማህበር የተቀመጠውን የማፍረሻ ምክንያት ሳይሆን ስለማህበሮች በጠቅላላው የተመለከተውን በመሆኑ ፣ እንደዚህ ዓይነቱ ማህበር ፍጹም የሆነ መስማማት የሚጠይቅ ሁኖ እያለ እና አለመግባባቱ ፍርድ ቤት በደረሰበት ሁኔታ ብርቱ ጭቅጭቅ የለም በሚል መወሰኑ፣ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማህበሩን በውክልና ማስተዳደራቸው እና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8.11 ስር 3ኛ ወገን ሊወከል የሚችለው በሁሉም ጉዳዮች ሳይሆን አስፈላጊ ሁኖ በታየ ጊዜ ብቻ በመሆኑ፣ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ የማያውቅ፣ ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ፣ ስራ አስኪያጅ ማህበሩን ሀብት ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉት ሁኖ እያለ እና ጉዳዮችን በሽምግልና ታይቶ እልባት ማግኘት ባልቻለበት ሁኔታ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም በሚል ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ስራ አስኪያጅ ደግሞ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባት እንዲባል እና ሂሣብ እንዲጣራ የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ መስከረም 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው መልስ አንድ ማህበር ሲፈርስ በቂና ህጋዊ ምክንያቶች ሊሟሉ የሚገባቸው ስለመሆኑ በጠቅላላውም ሆነ በልዩ የማህበራት ማፍረሻ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቶ እያለ ይሄንን ባላሟላ መልኩ የቀረበው ክስ ተቀባይነት ማጣቱ በአግባቡ በመሆኑ፣ ማህበራት ደግሞ ከተቋቋሙበት ዓላማ አኳያ ያለበቂ ምክንያት የሚፈርሱበት አግባብ ባለመኖሩ፣ ድርጅቱም አመልካች እንደሚለው የከሰረ ሳይሆን ስራውን በአግባቡ እያከናወነ ያለ በመሆኑ፣ በድርጅቱ

ውስጥም ብርቱ ጭቅጭቅ አለ ለማለት የማይቻል በመሆኑ እና ስራውንም በአግባቡ እያከናወነ ያለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ማህበሩ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው በሚል ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ፍርድ ቤቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አከራካሪው ማህበር አይፈርስም የተባለበትን አግባብ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ማህበሩ እንዲፈርስ የጠየቀበት ምክንያት ስራ አስኪያጁ ከባንክ ቤት ለማህበሩ ስራ መበደር ያለባትን ገንዘብ ያህል ያልተበደረች ስለመሆኑ፣ የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅሚ አውላለች፣ ማህበሩም ኪሣራ ላይ ስለመሆኑ ማህበሩን በውክልና ማስተዳደሯ እና አለመግባባት ስለመፈጠሩ በማመላከት እንደሆነ መመልከት ይቻላል፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱት የበታች ፍርድ ቤቶች ለማህበር መፍረስ ምክንያት ሁነው የቀረቡት ነጥቦች በማስረጃ አልተረጋገጡም፣ ብርቱ ጭቅጭቅ አለ ለማለት የማያስችሉ፣ ከስራ አስኪያጅ ጋር አለመግባባት በራሱ ብርቱ ጭቅጭቅ ተብሎ ማህበርን ሊያፈርስ የሚችል አይደለም በሚል እና የማህበሩን ስራ አስኪያጅነት በውክልና ማስተዳደርን በተመለከተም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8/1/ ስር የተፈቀደ በመሆኑ አልተቀበልነውም በሚል ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው አመልካች ማህበሩ እንዲፈርስ ያቀረበውን ምክንያት በፍሬ ነገር ረገድ ያላስረዳ ስለመሆኑ ነው፡፡ የቀረቡት ምክንያቶች ደግሞ እስካልተረጋገጡ ድረስ ለማህበሩ ማፍረሻ ምክንያት ተደርገው የማይወሰዱ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ማህበር ሊፈርስ የሚችለው ደግሞ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 217፣ 218 ፣ 511 እና 543 መመልከት እንደሚቻለው በድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት በርካታ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሁነው በቂ እና ህጋዊ ምክንያት እንደዚሁም በአባላት መካከል ብርቱ ጭቅጭቅ መኖር ያለበት ስለመሆኑ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን የቀረበው ብርቱ ጭቅጭቅ ስለመኖሩ መሠረት ያደረገ ክርክር ሲሆን ይሄ ስለመኖሩ ደግሞ ያልተረጋገጠ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካች ለማህበሩ ማፍረሻ ምክንያት ነው በማለት ያቀረበውን ነጥብ እስካላስረዳ ድረስ ደግሞ ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት የለም ተብሎ መወሰዱ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

ሆኖም ግን አመልካች በማህበሩ የስራ አስኪያጅ አመራር ላይ የስራው በውክልና መተዳደርን ጨምሮ የተለያዩ ቅሬታዎች እንዳሉት ግልጽ ነው፡፡ አንድ የኃ/የተ/የግል ማህበር ስራው በአግባቡ አልተመራም በሚልበት ወቅት ባለው የማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ ወይም አግባብነት ባላቸው ህጎች እንዲስተካከል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 37/1/ ስር ፍትሕ የማግኘት መብትን ከሚመለከተው ድንጋጌ መመልከት ይቻላል፡፡ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማህበሩን በውክልና አስተዳድራለች ወይስ አላስተዳደረችም? ፣ አስተዳድራ ከሆነስ ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አኳያ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር ተገናዝቦ መፍትሔ የሚያገኝ ጉዳይ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ከቀረበው የማህበር ይፍረስልኝ ጉዳይ ጋር በማያያዝ በመተዳደሪያ ደንቡ የተፈቀደ ነው በማለት ማለፍ ለተነሳው ክርክር አግባብነት ያለው ድምዳሜ

ባለመሆኑ እና የማህበሩ የስራ አመራር እንዲስተካከል ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችል ፤ አሁን ከተነሳው ክርክር ጋር የሚታይ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ሁኖ አልተገኘም በመሆኑም ይሄም ጉዳይ አመልካች የማህበሩ የስራ አመራር አካሄድን በተመለከተ ጥያቄ ሲያቀርብ አብሮ ታይቶ እልባት ሊያገኝ ሚችል ነው ብለናል፡፡ ሆኖም በዚህ የማህበር ይፍረስልኝ የክርክር ነጥብ ላይ ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት የለም ተብሎ ውሣኔ መሰጠቱ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ አላገኘንም፡፡

ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች አከራካሪው ማህበር የሚፈርስበት በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል አመልካች ያቀረበውን ክስ ወድቅ ማድረጉ በአግባቡና የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 110861 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ 173919 በቀን 30/9/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ኃ/የተ/የግል ማህበር ይፍረስልኝ ክስ ወድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ ይሄ ውሣኔ አመልካች የማህበሩን የስራ አመራር ጉድለት በተመለከተ እንዲስተካከል በሚል ከመጠየቅ የሚከለክለው አይደለም፡፡
3. በዚህ ችሎት ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 40186

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መስፍን ዕቁበዮናስ

አማረ አሞኜ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) አቶ ብርሀኑ ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** ዳሽን ባንክ (አ.ማ) ነገረ ፈጅ አቶ ዮናታን አስፋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታሐብሔር መዝገብ ቁጥር 41632 የካቲት 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ይግባኝ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 24055 ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለብድር ውል የተሰጠ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሚያስከትለውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አንደኛ ተከሳሽ፣ አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ (ተጠሪ) ለሥር ፍርድ ቤት ነሐሴ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ባቀረበው የክስ ማመልከቻ፣ ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ከከሳሽ በብድር ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ የከፈለው ተቀናንሶ ብር 5,494,328.29 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) ውስጥ ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) መጠኑ 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የብድር ገንዘብ ተበዳሪው የማይከፍል ከሆነ እሱ የሚከፍል መሆኑን በማረጋገጥ መጋቢት 17 ቀን 1993 ዓ.ም የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የሰጠ ሲሆን ይህንኑ የገንዘብ የዋስትና ሰነድ፣ የካቲት 5 ቀን 1994 ዓ.ም፣ መጋቢት 11 ቀን 1995 እና የካቲት 22 ቀን 1996 ዓ.ም አድሶታል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ብር 5,494,328.29 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሀያ ዘጠኝ ሳንቲም) ዕዳ አለበት፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ በሰጠው ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ግዴታ መሰረት እንዲከፍለኝ ብጠይቀው ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ተከሳሽ ለብድሩ አከፋፈል በሰጠው የዋስትና ግዴታ መሰረት አንደኛ ተከሳሽ ከሚፈለግበት ዕዳ ውስጥ 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር) ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ

ከሚታሰብ አሥራ አራት ፐርሰንት ወለድና በዚህ ክስ ምክንያት ከሳሽ ያወጣውን ወጭ ጨምሮ ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከሳሽ ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችና ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ከክሱ ጋር በማያያዝ ያቀረበ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው አስፍሯል፡፡

በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው (አመልካች) የመጀመሪያ ክስ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ድርጅቱ የተቋቋመው ለንብረት፣ ለሰው አካልና የሕይወት፣ ለኃላፊነት የመድን ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ የሁለተኛ ተከሳሽ ባለ አክሲዮኖችና የአስተዳደር ቦርዱ በማያውቁት ሁኔታ ከመድን ሥራ ውጭ የአንደኛ ተከሳሽን የብድር ዕዳ ለመክፈል የተሰጠው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ከሁለተኛ ተከሳሽ መመስረቻ ጽሁፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ ስለ መድን ሥራ ፈቃድ የወጣውን ህግ የሚጥስ በመሆኑ ሁለተኛው ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም፡፡ የሁለተኛው ተከሳሽ ሥራ አስኪያጅ በፍታብሔር ህጉ፣ በአፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ሕጉ የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራትን ከማከናወን ውጭ ሌሎች ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደማይችል በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና ሰነድ በመቀበል ለከሳሽ የፈጸመው ተግባር ከጅምሩ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ በመሆኑ ከሳሽ ሁለተኛ ተከሳሽን የሚከስበት ምክንያት የለም፡፡ በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ሊጠየቅ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ መሆኑ በንግድ ህጉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ፡፡

የሁለተኛ ተከሳሽ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥቷል የሚባል ቢሆን ሰነዱ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1725(ሀ) እና የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1727(ለ) በሚደነግጉት መሰረት በሁለት ምስክሮች ያልተፈረመ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው፡፡ ከሳሽ በሁለተኛ ተከሳሽ ተሰጥቶኛል የሚለው ሰነድ ገንዘብ መጠኑ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) መሆኑን ያሳያል፡፡ ከሳሽ ሁለተኛው ተከሳሽ በሰነድ ከሰጠው ዋስትና በላይ እንዲከፈለው ያቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ከሳሽ ብድሩን ለወሰደው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ የወሰደ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ከሳሽ እዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ የሚታሰብ አሥራ አራት ፐርሰንት ወለድ ሁለተኛ ተከሳሽ እንዲከፍለው ያቀረበው ክስ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2479 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚጥስና የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ፡፡ ከሳሽ ከሁለተኛ ተከሳሽ ተሰጥቶኛል የሚለው የዋስትና ሰነድ ከሳሽ ከተበዳሪው ጋር ያደረገው ብድር ውል የተደረገበት ጊዜና የብድሩ መጠን የሚገናኝ ባለመሆኑ ሁለተኛ ተከሳሽ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡ የከሳሽ አድራጎት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለ ገንዘብ ዋስትና ሰነዶች ያወጣውን መመሪያ በመጣስ የተፈጸመ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሆኖ እንዲሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ ክሱን ለመከላከል ይጠቅሙኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ከመልሱ ጋር በማያያዝ ያቀረበ መሆኑንና ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ተበዳሪውን ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የብድር ሂሳብ መግለጫ ከሳሽ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የብድር የሂሳብ መግለጫ ቀርቦለታል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሁለተኛ ተከሳሽ ሥራ አስኪያጅ ወጭ አድርጎ በሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች በኃላፊነት ይጠየቃል ወይስ አይጠየቅም? ሁለተኛ ተከሳሽ በኃላፊነት የሚጠየቅ ቢሆን የመክፈል ኃላፊነቱ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች መሥርቷል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሽ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶችን መስጠት ከተቋቋመበት

ዓላማ ውጭ የሆነ ተግባር አይደለም፡፡ ተከሳሽ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ክልከላ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የሰጣቸው ገንዘብ ዋስትና ሰነዶች ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡ የተከሳሽ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶችን የመፈረም ሥልጣን በንግድ ህጉ የተሰጠው በመሆኑና ሁለተኛ ተከሳሽ በህጉ መሰረት የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን ያልገደበ በመሆኑ፣ ሥራ አስኪያጁ ለከሳሽ ፈርሞ በሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው በንግድ ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ስለሆነ የከሳሽ ክስ በይርጋ አይታገድም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከሚፈለግበት ዕዳ ውስጥ ሁለተኛ ተከሳሽ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ከሣሽ ማስጠንቀቂያ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 15 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን ክርክሮች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተቋቋመው አጠቃላይ የመድን ሥራና የረዥም ጊዜ የመድን ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ አመልካች ከመድን ሥራ ውጭ የብድር ዕዳ ለመክፈል የዋስትና ግዴታ ሰነድ ለመስጠት አይችልም፡፡ ገንዘብ ዋስትና መስጠት በአመልካች መመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣ ስለ መድን ሥራ ፈቃድ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 ድንጋጌዎች ውጭና አመልካች ከተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ ውጭ የሆነ ለባንክ ብቻ የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ ይህንን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የፈጸመው ተግባር ህገ-ወጥና ምንም አይነት ተጠያቂነት አያስከትልም፡፡ የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ሕግ ቁጥር 363 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራትን ከማከናወን ውጭ ሌሎች ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ እንዲፈርም በንግድ ህግ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ልዩና ግልጽ የሆነ ሥልጣን አልተሰጠውም፡፡ ሥራ አስኪያጁ የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አንድና ተመሳሳይ አድርጎ በመውሰድ ከጅምሩ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ የሆነውን፣ ተግባር ህጋዊ ውጤት አለው በማለት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የሰጠው የዋስትና ሰነድ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት የህግ ትርጉም ከሰጠ በኋላ አመልካች ያቀረበውን ሁለት ዓመት የይርጋ መከራከሪያ ውድቅ ማድረጉ እርስ በርሱ የሚቃረንና ወጥነት የሌለው ነው፡፡ በአመልካች ተሰጠ የተባለው የዋስትና ሰነድ በሕግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው፡፡ የዋስትና ሰነዱን የሰጠው በተጠሪና ብድሩን በወሰደው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ ከመውሰዱ በፊት ነው፡፡ በአመልካችና በተበዳሪው መካከል የብድር ውል ከመፈረሙ በፊት የወጣ ሰነድ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት ሊኖረውና አመልካችን የሚያስገድድ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የዘረዘርናቸውን ተደራራቢ መሰረታዊ የህግ ሥህተቶች የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ለአመልካች የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2001 ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በሕግ ያልተከለከሉ ሁሉንም የመድን ሥራዎች ለመሥራት ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23/2000 እና 24/2004 ለገንዘብ ዕዳ የሚሰጥ ዋስትና በመድን

ድርጅቶች የሚሰራ ተግባር መሆኑን በመግለጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች ክፍያ እየተቀበለ መድን አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ የድርጅቱ ማኔጅንግ ዳይሬክተር ተገቢውን አረቦን በማስከፈል የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመስጠት ሥልጣን አለው፡ ከዚህ በተጨማሪ ንግድ ህጉ አንቀጽ 35 የድርጅቱ ማኔጅንግ ዳይሬክተር የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመስጠት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ የአመልካች ማኔጅንግ ዳይሬክተር የፈፀመው ተግባር ህጋዊ ውጤት አለው፡፡ አመልካች ክሱ ሁለት ዓመት የይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረብኩትን መከራከሪያ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣው 23/2002 ለገንዘብ ዕዳ ስለተሰጠ የዋስትና ሰነድ መመሪያ አውጥቷል፡ አመልካች ሰነዱን የሰጠው 1993 ዓ.ም ሲሆን ሰነዱን በየዓመቱ ሲያድስ ቆይቶ ይህንኑ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ መስከረም 5 ቀን 1997 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 መሰረት እንዲራዘም ያደረገ በመሆኑ የይርጋ ጊዜ ገደቡ አላለፈም፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ በሕግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው በማለት ያቀረበው ውሉ የመድን ፖሊሲ አወጣጥ ፎርም የሚያሟላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ የህግ ስሕተት የሌለበት በመሆኑ ሰበር ችሎቱ በማጽናት እንዲያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከር ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም. የተጻፈ ስድስት ገጽ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በመጀመሪያ አመልካች የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ህጋዊነትና የሰነዱን ሕጋዊ ባሕሪና ሰነዱ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ነው ወይስ አይደለም? በሚሉት ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቧቸውን ክርክሮች ቅድሚያ በማየት መወሰን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች የሰጠሁት የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ምንም አይነት ኃላፊነትን የማያስከትልና ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት ያቀረባቸው መከራከሪያዎች የህግ መሰረት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ የሚከተሉትን ዝርዝር ጭብጦች በቅደም ተከተል አይተናል፡፡ በሰበር የታዩት ዝርዝር የህግ ጭብጦችም፡-

1/አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት አመልካቹ የኢንሹራንስ ኩባንያ ከተፈቀደለት፣ ከተቋቋመበትና ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ከተመዘገበበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተፈጸመ ተግባር በመሆኑ፣ በህግ ተጠያቂ ልሆን አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር፣ የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም?

2/ አመልካች የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ለማውጣት ሥልጣን ሣይኖረው ፈርሞ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ በመቀበል ተጠሪ ለፈጸመው ተግባር ህጋዊ ተጠያቂነት የለብኝም፣ በማለት ያቀረበውን ክርክር በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት የታለፈው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?

3/አመልካች የተሰጠው የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃላፊነት የማያስጠይቅ ነው፣በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ያለፉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ?

4/ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም?

5/አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይስ አይጠቅም? በኃላፊነት ይጠየቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው?

1/የመጀመሪያው ጭብጥ አመልካች እንዲሰራው ከተፈቀደለት መድን ንግድ ሥራና ከተቋቋመበትና ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ከተመዘገበበት የንግድ ዓላማ ጋር የተያያዘ ነው። አንድ የንግድ ድርጅት በንግድ መዝገብ ውሰጥ ያስመዘገበውንና በጋዜጣ ታትሞ የወጣውን ጉዳይ መከራከሪያ ሊያደርገው እንደሚችልና ሶስተኛ ወገኖች በንግድ መዝገብ የገባውን ጉዳይ አላውቅም ነበር ብለው ማስረጃ ማቅረብ የማይፈቀድላቸው መሆኑን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል። አመልካች በህግ ከተፈቀደለትና ኩባንያው ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ በተፈጸመ ተግባር በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም በማለት የሚከራከረው፣ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 26ና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያላቸው በመሆኑ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም በማለት ነው።

ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት የንግድ ሕጉ አንቀጽ 26ና አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 2 ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በመጀመሪያ አመልካች ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ የተበደረውን ገንዘብ ካልከፈለ አመልካቹ እስከ 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚከፍል መሆኑን በመግለጽ የሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ አመልካች እንዲሰራው ያልተፈቀደለት፣ አመልካች ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የሆነ፣ አመልካች ከሚሰራው የመድን ንግድ ሥራ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ወይም አመልካች እንዳይሰራው በህግ በግልጽ የተከለከለ ተግባር መሆኑ ሲረጋገጥ በመሆኑ በመጀመሪያ ይህንን ነጥብ ቅድሚያ በመስጠት አይተነዋል፡

አከራካሪው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ምን አይነት የህግ ተግባር እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉም ሰጥቶታል። የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ፣ በመመሪያ ቁጥር 23 /2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 " Financial guarantee bond shall mean an obligation undertaken by an insurance company to pay for the lending bank or another creditors or supplier all outstanding claims arising from the non Payment by debtor or debtors. " የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2002 ዓ.ም ና 2004 በወጣው መመሪያ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ በግልጽ ከልክሏል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ በግልጽ የተከለከሉ መሆኑን "Insurance companies are prohibited from issuing a Financial Guarantee Bond, by whatever name it may be referred to, in any form what so ever." በማለት በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገ ሲሆን Insurance companies are prohibited from issuing a Financial Guarantee Bond, by whatever name it may be referred to, in any form wether conditional or otherwise. በማለት በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ግልጽ ክልከላ አድርጎበታል፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመድን ንግድ ሥራ የሚሰሩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳይሰጡ በመመሪያ በግልጽ ከመከልከሉ በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተሰጡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች የሚኖራቸውን ህጋዊ ውጤት ባወጣው መመሪያ ግልጽ አድርጓል፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ከመከልከላቸው በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የተሰጡ የገንዘብ የዋስትና ግዴታ ሰነዶች የጸኑና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23/2002 እና መመሪያ ቁጥር 24/2004 በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከላቸው በፊት፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የመስጠት ሥራን እንደ አንድ የመድን ንግድ ሥራ አይነት ሲያከናውኑት የኖሩት ተግባር እንደነበርና ይህም ተግባራቸው ህጋዊ ውጤት ያለውና ኃላፊነትን የሚያስከትል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመጀመሪያ መመሪያ ቁጥር 23/2002 በማውጣት፣የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳይሰጡ የከለከላቸው፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከተቋቋሙበት የመድን የንግድ ዓላማ ውጭ የሆነ ሥራ ነው በማለት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የክልከላ መነሻ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሌላውን ሰው ዕዳ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሲሰጡ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት በገቡት የዋስትና ግዴታ መሰረት ለባለመብቱ (አበዳሪው) የከፈሉትን ገንዘብ ከባለዕዳው ለማስመለስ የሚያስችላቸው በቂ መያዣ የሚሆን የተበዳሪው ንብረት ወይም ገንዘብ የማይዙ ወይም የማያገኙ በመሆኑና በአገሪቱ አስተማማኝ የሆነ የጠለፋ መድን ዋስትና የሌለ በመሆኑ ምክንያት፣ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመከላከል በማሰብ መሆኑን በመመሪያው መግቢያ ላይ በግልጽ አስፍሮታል፡፡

ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ በማውጣት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከሉ በፊት ወጭ አድርጎ ለተጠሪ የሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Financial Guarantee Bonds) ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተፈጸሙ ተግባራት በመሆናቸው ሕጋዊ ውጤት የሌላቸውና አመልካችን በኃላፊነት ሊያስጠይቁ የማይችሉ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ አውጥቶ ከመከልከሉ በፊት ለተጠሪ የሠጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Financial Guarantee Bonds)፣አመልካች እንዲሰራ ከተፈቀደለት የመድን ንግድ ሥራና ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተሰጡ ሰነዶች በመሆናቸው ሕጋዊ ውጤት የላቸውም በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2/ ሁለተኛው ጭብጥ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶቹ ወጭ በሆኑበት ወቅት የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረውን ሥልጣንና ሊፈጽማቸው የሚችላቸው የህግ ተግባሮች ምንድን ናቸው?

አመልካች የዋና ስራ አስኪያጁን ሥልጣን በህግ የተቀመጡ ሁኔታዎች በማሟላት ገድቧል ወይስ አልገደበም የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4 እና በአንቀጽ 6 የተደነገጉትን ልዩ መስፈርቶች በማሟላት ተመዝግቦና ፈቃድ አግኝቶ የመድን ንግድ ሥራ የሚያከናውን የአክሲዮን ማህበር (የኢንሹራንስ ኩባንያ) ነው፡፡ የመድን ንግድ ሥራ ለማከናወን የተቋቋመና ፈቃድ ያገኘ የአክሲዮን ማህበር

• የመድን ሥራውን በዋና ኃላፊነት የሚመራለት ሥራ አስኪያጅ የሚኖረው መሆኑ፣

• ሥራ አስኪያጁ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መሆን እንደሚገባውና ሥራውን የሚሰራው በብሔራዊ ባንኩ ስምምነትና ዕውቅና እንደሚሆን፣

• የስራ አስኪያጁ ማንነት የትምህርት ደረጃ ችሎታና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ የስራ አስኪያጆችንና ረዳቶችን ዝርዝር ሁኔታዎች ለመመዝገብ ባዘጋጀው መዝገብ የሚመዘገብ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 32፣ አንቀጽ 33ና አንቀጽ 34 ድንጋጌዎችን ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም አዋጁ ከላይ የተቀመጡትንና በብሔራዊ ባንክ የሚወጡ መስፈርቶችን ማሟላቱ ተረጋግጦ የኢንሹራስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ስለሚኖረው ሥልጣንና ኃላፊነት አዋጁ በዝርዝርና በግልጽ አይደነግግም፡፡ አዋጅ ቁጥር 86/1986 “ሥራ አስኪያጅ” ማለት በማናቸውም የማዕረግ ሥም ቢጠራም የድርጅቱን ሥራን ለመምራት በዋና ኃላፊነት የሚጠራ ሰውና ለእርሱ ወይም ለምክትሉ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የኩባንያው ኃላፊዎች ናቸው፤ በማለት አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 20 ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ለኢንሹራስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የተሰጠው ትርጓሜ የሥራ አስኪያጁን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመገንዘብ ጠቀሜታ ያለውና አመላካች (indicative) የሆነ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም ድንጋጌው የኢንሹራስ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለውን ዝርዝር ሥልጣንና ሊፈጽማቸው የሚችላቸው የህግ ተግባሮች ለመወሰን በቂ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አከራካሪዎቹን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች በተሰጡበት ጊዜ የነበረውን ሥልጣንና ሊፈጽማቸው የሚችላቸው የህግ ተግባሮች ለመወሰን አግባብነት ካላቸውና ከላይ ከጠቀስናቸው የአዋጅ ቁጥር 86/1986 ድንጋጌዎች በተጨማሪ የአንድ አክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ በንግድ ሕጉ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በንግድ ሕጉ መሰረት ስለተቋቋሙ የአክሲዮን ማህበራት ፕሬዝደንት፣ ዋና ሥራ አስኪያጅና ጸሐፊ ሥልጣን የሚደነግገው የንግድ ሕግ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥራ አስኪያጁ በአስተዳደሩ ምክር ቤት እንደሚሾምና የስራ አስኪያጁን ሥልጣን በተመለከተ የንግድ ህጉ አንደኛ መጽሐፍ፣ አንቀጽ 34፣ አንቀጽ 35፣ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) እና አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለ ሥራ አስኪያጁ አመዳደብ (ሹመት) የሚደነግገው ክፍል ከላይ በዝርዝር የተገለጹት ማሻሻያዎች በአዋጅ ቁጥር 86/86 ድንጋጌዎች ተደርገውበታል፡፡ በሌላ በኩል በንግድ ህጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ተገቢነት እንዳላቸው የተደነገጉት ድንጋጌዎች የአመልካች ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ በወቅቱ የነበረውን ሥልጣን ለመወሰን ገዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ የድንጋጌዎቹን ይዘት ስንመለከት

• የንግድ ሕግ  አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ(ረ) የአክሲዮን ማህበሩ (አመልካች) በሥራ አስኪያጅነት የሾመውን ሰው በንግድ መዝገብ ማስመዝገብ እንደሚገባው  የሚደነግጉ ናቸው፡፡

• የንግድ ሕግ  አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 ከላይ በተገለጹት የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ንግድ ድርጅቱ ባይፈጽም የሚከተለውን ውጤት ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው የአክሲዮን ማህበሩ (አመልካች) የሥራ አስኪያጁን ሹመት በንግድ መዝገብ ሳያስገባ ቢቀር እንኳን ሥራ አስኪያጁ  ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ሥራውን ለማከናወን የሚችል መሆኑን የሚደነግግ  ይዘት ነው፡፡

• "ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን" የሚል ርዕስ ያለው የንግድ ሕግ  አንቀጽ 35"  ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያገናኙት ጉዳዮች ሁሉ ሥራ አስኪያጁ ከነጋዴው ሥራ ጋር  ነክነት ያላቸውን ማናቸውም ግዴታዎች ለመፈረምና የሚተላለፉ ሰነዶችን (ኔጎሽብል ኢንስትሩመንትስ) ጭምር መፈረም ሥልጣን እንዳለው ይቆጠራል"  በማለት በንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን፣

•  "የንግድ ሕጉ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ( ሰ) ነጋዴው ወይም የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን የቅርንጫፉን ወይም የውክልናውን ሥራ ብቻ በማካሄድ የተወሰነ መሆኑ በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ የሌሉ ከሆነ ቅን ልቦና ያላቸው ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆኑ  አይችሉም"  በማለት ይደነግጋል፡፡

• የአንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 2  በሥራ አስኪያጁ ሥልጣን  ላይ  ሕግ  አውጭው  የተጣለውን ገደብ ምን እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን "ሥልጣን ያለው ሥራ አስኪያጅ በግልጽ ሥልጣን ካልተሰጠው በስተቀር የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መያዣ ማድረግ፣ ንግድ መደብሩን መሸጥ፣ ማከራየት ወይም በዕዳ ማስያዝ አይችልም" በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡

አመልካች  ዋና ሥራ አስኪያጁ የፈጸመው ተግባር  ከነበረው ሥልጣን ውጭ ነው በማለት በተጠሪ ላይ ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሚኖረው ከሁለት ሁኔታዎች አንደኛው መሟላቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጁ  ህግ አውጭው አስገዳጅ  በሆነው በንግድ ህግ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 የደነገገውን ክልከላ ወይም የስልጣን ገደብ በመተላለፍ አመልካች በግልጽ ሥልጣን ሳይሰጠው በድንጋጌው ከተዘረዘሩት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ተግባራት የፈጸመ መሆኑ የተረጋገጠ  ሲሆን  ነው፡፡ ሁለተኛው የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፈቃጅነት ባለው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ሥልጣን አመልካች የንግድ ህግ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ(ሰ) የተደነገገውን መስፈርት በሚሟላት የገደበው ሆኖ እያለ አመልካች ያስቀመጠውን የስልጣን  ገደብ  በመተላለፍ ሥራ  አስኪያጁ  ተግባሩን የፈጸመ መሆኑ  ሲረጋገጥ  ነው፡፡

ከላይ በሕግ የተቀመጡትን ሁለት መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የአመልካችን ክርክር መዝነናል፡፡  የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ ተበዳሪው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ ተበድሮ የወሰደውን ገንዘብ በብድር ውሉ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ፣ አመልካች በዋስትና ሰነዱ  እስከገለጸው ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚከፍል መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ፈርሞ የሰጠ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ የፈጸመው ተግባር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 4 ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ወጭ አድርጎ የመስጠት የመድን ንግድ ሥራ አይነት እንደሆነ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ እንደዚሁም የአመልካች ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዱን የፈረመው የኢትዮጵያ

ብሔራዊ ባንክ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ወጭ እንዳያደርጉ በመመሪያ ከመከልከሉ በፊት ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ተረጋግጧል።

የአመልካች ሥራ አስኪያጁ የፈጸመውና በዚህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ተግባር የአመልካችን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መያዣ ማድረግ ወይም ንግድ መደብሩን መሸጥ ወይም ማከራየት ወይም ኩባንያውን በዕዳ የማስያዝ ተግባር አይደለም። ስለሆነም አመልካች የንግድ ሕግ ቁጥር 35 ንዑስ አንቀጽ 2 በመጥቀስ ሥራ አስኪያጁ የፈጸመው ተግባር ፈራሽና ሕጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የድንጋጌውን ይዘት ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል። ሁለተኛው አመልካች "የንግድ ሕጉ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) የተደነገገውን መስፈርት በማሟላት የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንዳይፈርም ወይም ተመሳሳይ በሆነ ሌላ አገላለጽ የዋና ሥራ አስኪያጁን ሥልጣን ያልገደበ መሆኑንና በሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ላይ አድርጌአለሁ የሚለውን ገደብ ወይም ቅነሳ በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ ያላስመዘገበ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል። አመልካች የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑንና ሥልጣኑ መገደቡ በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ ያላስረዳ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። ይህም በመሆኑ ዋና ሥራ አስኪያጁ አመልካች እንዲሰራው በወቅቱ ተፈቀደውለት የነበሩ የመድን የንግድ ሥራዎች ጋር ግንኙነት የነበራቸውን ተግባራት የመፈጸም ሙሉ ስልጣን እንደነበረው ግምት የሚወሰድ መሆኑን ከንግድ ሕግ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል። የንግድ ሕጉ አንቀጽ 36 ድንጋጌዎችም ይዘታቸው ግልጽና ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው።

አመልካች የዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣን የቀነሰ መሆኑን በንግድ መዝገብ ሳያስመዘግብ፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ ተገድቧል። ሥራ አስኪያጁ በመተዳደሪያ ደንብ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የፈጸመው ተግባር ህጋዊ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት ሶስተኛ ወገን የሆነውን ተጠሪን ለመቃወም ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆኑን መርምረናል። አንድ የአክሲዮን ማህበር በንግድ መዝገብ እንዲያስመዘግባቸው ህግ ግዴታ ያደረገበት ጉዳዮች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 323 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግገዋል። በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 6 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 323 ንዑስ አንቀጽ 2 የአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ፣ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ማሕበሩ ህጋዊ ህልውና እንዲገኝና እንዲመዘገብ ሥልጣን ላለው አካል ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋር ተያይዘው መቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋሉ። የአመልካች ክርክር የድርጅቱ የመመስረቻ ጽሑፉና መተዳደሪያ ደንቡን የአክሲዮን ማህበሩ እንዲመዘገብ ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር አያይዘው መቅረባቸው ብቻውን የአክሲዮን ማህበሩ በመመስረቻ ጽሑፉና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ጉዳዮች በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ እንዳስመዘገበ የሚያስቆጥረው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ እንድናይ የሚያስገድድ ነው።

አክሲዮን ማህበሩ በንግድ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብለት ሥልጣን በሕግ ለተሰጠው አካል በሚያቀርበው ማመልከቻ እንዲገልጻቸው በህግ የሚገደደው፤ የማህበርተኞች ስም፣ ዜግነት አድራሻና ለመግዛት የፈረሙት የአክሲዮኖች ብዛት፣ የማህበሩ መጠሪያ፣ የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤትና ያሉት ከሆነ የቅርንጫፎች ሥፍራ፣ ማህበሩ የቆመበት ጉዳይ፣ የተፈረመና ገቢ የሆነውን ገንዘብ ልክ፣ የአክሲዮኑ ዋጋ ብዛቱ፣ አይነትና የአክሲዮኑ ልዩነት፣ በአይነት የተደረጉ መዋጮዎች ዋጋና የአገልግሎት አይነት፣ አስተዳዳሪዎቹን ብዛት ሥልጣን እንደዚሁም ለማህበሩ

እንደራሴ የመሆን አኳኋን፣ የተቆጣጣሪዎች ብዛትና ማህበሩ የሚቆይበትን ጊዜ መሆኑን የንግድ ሕጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 313 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7፣ ከንዑስ አንቀጽ 10 እስከ ንዑስ አንቀጽ 12 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል። እንደዚሁም የአክሲዮን ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የሾመ መሆኑንና የሥራ አስኪያጁን ማንነት ካልሆነ በስተቀር የስራ አስኪያጁ ሥልጣን ወሰን በንግድ መዝገብ በሚገባው ቃል ውስጥ ማስመዝገብ ህጉ ግዴታ ያላደረገው ተግባር መሆኑን ከንግድ ህጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ(ረ) ድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘት ለመረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል የአክሲዮን ማህበሩ የሚጠቀመው ሆኖ ካገኘው የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን መገደብና የስራ አሰኪያጁ ሥልጣን ላይ የተደረገውን ገደብ በንግድ መዝገብ ውስጥ በሚጻፈው ቃል እንዲገባለትና እንዲመዘገብለት በግልጽ በሚያቀርበው ማመልከቻ ውስጥ በመግለጽ፣ የስራ አሰኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑ በግልጽ በንግድ መዝገብ በተመዘገበው ቃል ውሰጥ እንዲመዘገብ ካላደረገ በስተቀር በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊያደርገው እንደማይችል ከንግድ ህጉ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ድንጋጌዎች አቀራረጽና ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

በመሆኑም አመልካች የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ ወይም የተገደበ መሆኑን በንግድ መዝገብ በሰፈረው ቃል ወሰጥ ሳያስመዘግብ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር፣

• የንግድ ሕጉ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ያለው ሰው የአንድ ቅርንጫፍ ሥራ ለማስኬድ ብቻ ሥልጣን በመስጠት ሥልጣኑን የተወሰነ ለማድረግ ይቻላል፤ ስለሆነም እንደዚህ ያለው የስልጣን መቀነስ ማስታወቂያ በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር በዚህ ህግ አንቀጽ 121 መሰረት መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም በማለት በግልጽ የደነገገውን የሚተላለፍና፣

• በተለይም በንግድ ህጉ አንቀጽ 121 ንኡስ አንቀጽ(ሰ) እና የንግድ ህጉ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 ሌላው አይነት የስልጣን መቀነስ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም።

በማለት ለሶስተኛ ወገኖች በግልጽ የሰጠውን ጥበቃ ያላገናዘበና የሕግ ድጋፍና መሰረት የሌለው ነው። ሕግ አውጭው እነዚህን ድንጋጌዎች የደነገገው በግብይት ሂደት ውስጥ ከአመልካች ጋር ውል የሚዋዋሉ ሰዎች የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ መመርመርና ማንበብ እንደማያስፈልጋቸውና ድርጅቱ በንግድ መዝገብ ያስመዘገባቸውን ፍሬ ጉዳዮች ብቻ በማየት ከአመልካች ጋር በቅን ልቦና የሚዋዋሉ ሶስተኛ ወገኖች ውለታው በህግ ተፈጻሚነት የሚኖረው መሆኑን በማረጋገጥ ከፍ ያለ ጥበቃ ለመስጠት ነው። በአጠቃላይ ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች አመልካች የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣን ሳይኖረው የፈረማቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች እኔ በኃላፊነት አልጠየቅም በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

3/ ሶስተኛ ጭብጥ አመልካች የሰጠውን የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃላፊነት የማያስጠይቅ ነው፣ በማለት ያቀረበውን ክርክር የህግ መሰረት ያለው መሆኑን መመርመር

የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህንን ነጥብ ለመወሰን በመጀመሪያ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ ፈርሞ የሰጠው ሰነድ በመሰረታዊ ባህሪውና ይዘቱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው ወይስ የዋስትና ሰነድ የሚለውን ነጥብ ማየት ይጠይቃል፡፡ አመልካች ወጭ አድርጎ ለተጠሪ የሰጠው ሰነድ Financial Guarantee Bond በማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ግልጽ ያደረገውን በኢንሹራንስ ኩባንያ የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነዱን ሊያሟላው የሚገባውን ፎርም፣ የሰነዱን ባሕሪና የሚስከትለውን ውጤት ለመወሰን ሕግ አውጭው ለገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሰጠውን የህግ ትርጓሜ መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የዋስትና ሰነድን በተመለከተ ሕግ አውጭው በተለያየ ጊዜ ባወጣቸው የህግ ማዕቀፎች ይዞታቸው ተመሳሳይ የሆኑ ትርጓሜዎችን የተጠቀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ዝርዝሩን ስንመለከት፡-

- የዋስትና ሰነድ ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈጸም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ነገር ሲሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል በማለት በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 57/1989 ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 20 የዋስትና ሰነድ ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈጸም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ማንኛውም ሰነድ ሲሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል፣ የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

- ቦንድ የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ማገቻ የሚል ፍች የሰጠው አዋጅ ቁጥር 110/1990 ማገቻ የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ፣ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል በማለት በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥረ 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 የሰጠው ትርጉምና ከላይ በጠቀስናቸው የህግ ማዕቀፎች ሕግ አውጭው ተመሳሳይነት ባላቸው አገላለጾች የሰጣቸውን ትርጓሜ ስንመለከት አመልካች ወጭ አድርጎ የሰጠው ሰነድ በመሰረታዊ ባህሪውም ሆነ ይዘቱ የመድን ውል ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የኢንሹራንስ ፖሊሲ በመሰረታዊ ባህሪው መድን ገቢው የኢንሹራንስ ሽፋን በተሰጠው ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም (Insurable Interest) ያለው መሆኑን ይጠይቃል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከአመልካች አከራካሪውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ለማግኘት ከአመልካች ጋር ውል የተዋዋለው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዋናው ፍላጎቱ ተጠሪ በብድር የሚሰጠውን ገንዘብ ተበዳሪው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባይከፍለው አመልካች የሚከፍለው መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ተጠሪ በማየትና ስለ ብድሩ አከፋፈል ከተበዳሪው ውጭ የሆነ አስተማማኝ ዋስትና ያለው መሆኑን በማመንና በማረጋገጥ የብድር ገንዘቡን እንዲለቅለት ማድረግና ገንዘቡን መበደር ነው፡፡ ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል

ማህበር አመልካች የሰጠውን የዋስትና ሰነድ አስይዞ  የብድር ገንዘቡን ከወሰደ በኋላ ተጠሪ የሰጠውን ብድር ገንዘብ  የመክፈል ግዴታ ያለበት ባለዕዳ ነው፡፡  የተበዳሪው ባለዕዳነት አመልካች በሰጠው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት ለተጠሪ የብድር ገንዘቡን ከከፈለ በኋላም የሚቀጥልና አመልካች  ተጠሪን (አበዳሪውን) በመተካት  ሊጠይቀውና ሊከታተለው የሚችለው ነው፡፡ የአመልካች ደንበኛ የሆነው  ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በጉዳዩ ዘላቂ ባለዕዳ  ከመሆን አልፎ ተጠሪ በብድር የሰጠውን ገንዘብ  የመክፈል  ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም (Insurable Interest) ያለው ወገን ባልሆነበት ሁኔታ በአመልካችና በግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መካከል የተደረገው ውል የመድን ውል ነው ተጠሪ ደግሞ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም ፡፡

በአንጻሩ አመልካች በሰጠው ሰነድ ከተጠሪ የአጭር ጊዜ የብድር ገንዘብ የወሰደው ግሬስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በብድር ውሉ በተገለጸው ጊዜ ዕዳውን ካልከፈለ አመልካች እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ለመክፈል በሰነዱ ውስጥ ለተገለጸው ጊዜ ብቻ ዋስትና የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ግሬስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር  ከተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ተበዳሪው ባይከፍል አመልካች እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የአንድነትና ያልተነጣጠለ የዋስትና ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ  ሰነድ  ነው፡፡  ከዚህ አንጻር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ከላይ በዝርዝር የሰጠናቸውን ምክንያቶች ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ አመልካች ሰነዱ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን  ክርክር  መዝነናል፡፡  በመጀመሪያ የዋስትና ሰነዱ አመልካች የሌላ ሰው ዕዳ ማለትም የግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የብድር ዕዳ ለመክፈል የተሰጠ ሰነድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሰነዱ ስለዋስትና ግዴታ በፍታሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1922  የተደነገጉትን መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡  ሕጉን ሲተረጉሙ ሰነዱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የደረሱ ቢሆንም አመልካች የሰጠው ሰነድ በፍታሐብሔር ህግ አንቀጽ 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን መሰረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ ይዘት ተረድተናል፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ የፍታሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1725 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና የፍታሐብሔር ሕግ  አንቀጽ 1727 በተደነገገው መሰረት በተጠሪና በሁለት ምስክሮች አልተፈረመም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም ይህ የአመልካች ክርክር ( Financial Guarantee Bond) እንደ ማንኛውም የዋስትና ውል በተዋዋይ  ወገኖች የሚዘጋጅ ሰነድ ሣይሆን የመድን ንግድ ሥራ እንዲሰራ የተፈቀደለት የኢንሹራንስ ኩባንያ በተሰጠው ልዩ ፈቃድ ተጠቅሞ፣ የሚያዘጋጀውና የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል ራሱን ግዴታ ውስጥ የሚያስገባበት የማገቻ ሰነድ እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1  እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 ለገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የሰጠውን ትርጓሜ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ አላኘነውም፡፡ እንደዚሁም አመልካች የሰጠው የማገቻ ሰነድ (Bond) የግድ በምስክሮች መረጋገጥ የሌለበት መሆኑን ሕግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 110/1990  በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ለማገቻ ትርጉም ሲሰጥ “አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ

ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል" በማለት ከተጠቀመው አገላለጽ እና በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ለዋስትና ሰነድ ከሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ችለናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ሥያሜ የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳያወጡ በመመሪያ ከመከልከላቸው በፊት ወጭ ያደረጓቸው የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነዶች (Financial Guarantee Bond) የጸኑና ህጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን " Financial Guarantee Bond or other unconditional bonds issued by insurance companies and outstanding before the effective date of these directives shall remain enforce until the expiry date or shall be phased out in line with an action plan submitted by each insurance company and agreed with the bank." በማለት የገለጸውን የመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ የሚቃረንና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተበዳሪውን ግሬስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ባይከፍል እሱ የሚከፍል መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን የማገቻ ሰነድ ልዩ ባህሪ ያለውና በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚዘጋጅና ወጭ የሚደረግ የማገቻ ሰነድ በመሆኑ አመልካች ሰነዱ በሁለት ምስክሮች ስላልተረጋገጠ ሰነዱ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

4/ አራተኛው ጭብጥ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚል ነው አመልካች የሰጠው ሰነድ የመድን ውል አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል የአንድነት የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የዋናውን ባለዕዳ ግዴታ ነፃ የሚያደርጉ የይርጋና ሌሎች መከራከሪያዎች በማቅረብ ከኃላፊነት ነፃ እንደሚሆን ከፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋሱ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ የጊዜ ገደብ በዋናው ባለዕዳ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ እንደሆነ፤ በዋናው ባለዕዳ ላይ የተጀመሩ ክሶች ለዋሱ መቆጠር የጀመረለት የይርጋ ዘመን ያቋርጡበታል በማለት ሕግ አውጭው የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1929 የደነገገበትን ምክንያት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአበዳሪው በተጠሪና በተበዳሪው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መካከል የተደረገው ብድር ውል ላይ ተፈጻሚነት ያለው ስለ ውሎች በጠቅላላው የሚደነግገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ የአመልካች (የዋሱ) ግዴታ ቀሪ የሚሆነው የዋናው ባለዕዳ ግዴታ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ በፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የይርጋ የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ንግድ ህግ 674 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሆነ አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር መቀበላቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ የፍታሐብሔር ህግ አንቀጽ 1845 በመሆኑ አመልካች የይርጋ ክርክር መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5 አምስተኛው ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይም አይጠየቅም? በኃላፊነት ይጠየቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው? የሚለው ነው፡፡ አመልካች ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በብድር ውሉ መሰረት ካልከፈለ እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ለተጠሪ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥቷል፡፡ ተበዳሪው ዕዳውን በብድር ውሉ መሰረት አለመክፈሉ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላበደረው ብድር የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የሰጠው ብድር ውሉ ከመደረጉ በፊት መሆኑን ገልጾ መጀመሪያውኑ ላልነበረ የብድር ውል የተሰጠ ዋስትና ግዴታ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የቀረበው ክርክር በፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1925 ንዑስ አንቀጽ 1 ወደፊት ለሚመጣ ወይም በአንድ አይነት ሁኔታ ለሚመጣ ግዴታ ዋስ መሆን ይቻላል በማለት የደነገገውን ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ አመልካች የሰጠው የዋስትና ግዴታ ሰነድ አመልካች እዳውን በአንድነት ለመክፈል የሚያረጋግጥ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተበዳሪው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ተጠሪ ማጭበርበር ተግባር ፈጽመዋል በማለት ለሰበር በሰጠው የመልስ መልስ ያቀረበው ክርክር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ መስማት ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያልተነሳና ያልተጣራ የፍታሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ክርክር ለሰበር ችሎት በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በሰጠው የገንዘብ የዋስትና ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል በማለት የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአመልካችን የኃላፊነት መጠን በተመለከተ ዕዳን ለመክፈል ዋስ የሆነ ሰው ዕዳው ወለድ የሚያስከፍል እንደሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር በዋስትናው ውል ውስጥ በተወሰነው ገንዘብ ልክ በወለዱም እንደተዋሰ እንደሚቆጠር የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1930 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የሰጠው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ድረስ ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ሰነዱ ስለወለድ ተቃራኒ ቃል የሌለው መሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ለብድሩ ያለበት ዋስትና ግዴታ እስከሰጠበት ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1930፣ የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1924 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ያደረገና የህግ ስሕተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በበታች በስር ፍርድ ቤት ከታህሳስ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች በህግ የተደነገገውን ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ እንዲከፍል የወሰነው አመልካች በገባው ዋስትና ግዴታ መሰረት ባለመፈጸሙ ምክንያት ኃላፊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ምክንያት ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለው ገንዘብና ሌሎች ወጭዎች አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1931 መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር ባየናቸው ጭብጦች ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነውና የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የሰጠው ገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው

ለይርጋው ክርክር  አግባብነት ያለው የንግድ ሕጉ አንቀጽ 674 ንኡስ አንቀጽ 1 ነው በማለት የሰጡት ህግ ትርጉምና ምክንያት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ የደረሱበት መደምደምያ ተገቢ  ሆኖ ስላገኘነው በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሰጡትን የህግ ትርጉምና ምክንያት ብቻ በመለወጥ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታሐብሔር መዝገብ ቁጥር 41632 የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ይግባኝ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 24055 ሐምሌ 30 ቀን  2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ምክንያቱ ብቻ ተሻሽሎ ጸንቷል፡፡

2/ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

3/ በዚህ ችሎት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፣ ለሚመለከተው ይተላለፍ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 63200
ታህሣሥ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** 1. ጣና ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ ሰለሞን ተሾመ ቀረቡ

2. ሚስስ ሴቬሪና ሴቲ

3. ሚስ አምብራ ዴልጋውዲዮ } ጠበቃ አበበ አሣመር ቀረቡ

4. ሚስ ጂያዳ ዴልጋውዲዮ

**ተጠሪ** ፡- ሚስተር አልቸዲ ዴልጋውዲዮ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያለአግባብ ከስራ አስኪያጅነት ተነስቻለው የሚል ክስን የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እንዲሁም 2ኛ ተከሳሽ የ4ኛ ተከሳሽ ተወካይ በመሆን ህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም አድርገነዋል ባሉት ስብሰባ የማህበሩን ደንብ እና መመስረቻ ፅሑፍ በማሻሻል 1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪያጅነት እንዲነሱ ተደርጎ የ2ኛ ተከሳሽ ልጅ 3ኛ ተከሳሽ ምክትል ስራ አስኪያጅ እንዲሆኑ ተደርጎ ቃለ-ጉባኤ የተያዘበት ቀኑ ሳይፃፍበት ከሳሾች ሳይጠሩ የተደረገው ውሳኔ ሀሰተኛ እና ህገ-ወጥ በመሆኑ፣ 1ኛ ከሳሽ ም/ስራ አስኪያጅ የሆነው የግራቀኙን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በመሆኑ፣ 1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪያጅነታቸው መነሳታቸው ያለአግባብና መስተካከል ያለበት መሆኑን በስብሰባ ተማምነን ረቂቅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ በረቂቁ ላይ አስተያዬት ከሰጠን በኋላ በውልና ማስረጃ ለማስመዝገብ ፍቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩ በመሆናቸው፣ በ1995 ዓ.ም በተደረገው የመመስረቻ ፅሑፍ ማሻሻያ የኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛ አካል ሆኖ እያለ ከህግ ውጪ የጠቅላላ ጉባኤውን ስልጣን በሙሉ ለዋና ስራ አስኪያጅ በህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም በመሰጠቱ፣ የሒሳብ ሰነዶችንም እንዳናይ የተደረግን በመሆኑ ተከሳሽ ከዋና ስራ አስኪያጅነታቸው እንዲነሱ አልያም በአግባቡ እንዲሰሩ፡፡ እንደዚሁም ህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም የተደረገው የመመስረቻና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ፅሑፍ እንዲሻር፣ 1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪጅነታቸው ሊነሱ አይገባም እንዲባልልኝ፣ የሒሳብ ሰነዶችን የመመልከት መብታችን እንዲከበርልን የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሾች መልስ እንዲሰጡበት ታዘው በሰጡት

መልስ 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ መተዳደሪያ ደንቡና መመስረቻው በህጉ አግባብ የተደረገና በሚመለከተው አካል የፀደቀ ነው፣ ቀኑም በፀደቀበት ቀን ታትሟል፣ 1ኛ ከሳሽ ም/ስራ አስኪያጅ የሆኑት በተሻሻለው የመመስረቻ ጽሁፍ እና ኩባንያው ሲመሰረትም ስራአስኪያጅ አይደሉም፣ 1ኛ ከሳሽ ጥሪ ተደርጎላቸው በስብሰባው ላይ አልተገኙም፣ የመጨረውሻን የስብሰባ አጀንዳ አውቀው የተለያዩ ሃሳቦችን በማቅረብ በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት ቀርቦ አልፈረሙም፣ ሰነዶቹም ተፈርሞባቸዋል፣ አለመግባባት ተፈጥሮ በስምምነት ለመጨረስ ተሞክሮ ሳይሳካ በመቅረቱ በአብላጫ ድምጽ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በመሆናቸው በዚያው መልኩ የተወሰነ በመሆኑ፣ ሰነዱን አስፈቅደው ኮፒውን መውሰድ ስለሚችሉ ማስጠንቀቂያው ተቀባይነት አለው እና 2ኛው ተከሳሽ ስራቸውን በአግባቡ የተወጡት በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ ያቀረቡት መልስ በቀጥታ የአንደኛ ተከሳሽ መልስ ጋር ተመሳሳይ ስለመሆኑ ተመልክቶ ሳይመዘገብ በበታች ፍርድ ቤቶች ታልፎአል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኙን ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ አራት የተለያዩ ጭብጦችን በመያዝ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በተደረገው ስብሰባ የመተዳደሪያ ደንቡ ሊሻሻል ስለመቻሉ በተመለከተ በንግድ ህጉ ቁ. 536(2) መሰረት የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ¾ ባላቸው ባለአክሲዮን የድምጽ ብልጫ መወሰን እንዳለበት ስለሚያመላክት እና ተከሳሾች ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ 77.50% በመሆኑ የተደረገው የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ህጋዊ አይደለም የሚባልበት አግባብ የለም፤ አንድ ስራ አስኪያጅ በስብሰባ የቀረቡትን እና የተወሰኑትን ዉሳኔዎች የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በንግድ ህግ ቁ. 533 ስር የተደነገገ በመሆኑ ይሄንኑ ኃላፊነታቸውን መወጣት ያለባቸው ስለመሆኑ ወስኗል፤ የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች ያደረጉትን ስብሰባ በተመለከተ በሚመለከተው ባለስልጣን ፊርማ እና ማህተም የተረጋገጠ እና ቀንም ያለው በመሆኑ የባለስልጣኑ ፊርማ እና ማህተም ያረፈበት ቀን ማሻሻያው እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት ከሳሾች ቀኑ የማይተወቅ ነው በማለት ያነሱትን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም 2ኛ ተከሳሽ ከስራ አስኪያጅነት እንዲነሱ በከሳሾች በኩል የተነሳውን ክስ ውድቅ ሲያደርግ በሌላ በኩል በባለአክሲዮኖች በተደረገው ስብሰባ የ1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪያጅነት መነሳትም በተመሳሳይ በምክንያት ያልተደገፈ ባለመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ የተደረገው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ክፍል ተሽሯል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በመጀመሪያ ደረጃ ምክትል ስራ አስኪያጅ ስራ አስኪያጅን በሚመለከቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ሊከራከር አይገባውም በማለት የተነሳውን ክርክር በተመለከተ ስለስራ አስኪያጅ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ከንግድ ህግ ቁ.525 እና ተከታዮቹን ስንመለከት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ስራ አስኪያጆች ሊሾሙ የሚችሉበትን አግባብ ስለሚያስቀምጥ እንደዚሁም ህጉ ለእነዚህ ኃላፊነቶች በእነዚሁ ድንጋጌዎች የሚስተናገዱ እንጂ ለእያንዳንዱ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል ተብሎ ስለማይታሰብ ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም ብለናል፡፡ በመቀጠል አመልካች በቅሬታቸው አጥብቀው የሚከራከሩት በመተዳደሪያ ደንባችን አንቀጽ 2(2.4) ውስጥ ስራ አስኪያጅ በማህበርተኞች ጠቅላላ ጉባዔ የሚሻር ስለመሆኑ ተመልክቶ እያለ ያለበቂ ምክንያት ሊሻር

አይገባም መባሉ አግባብነት የለውም፣ የተባረረው ያለበቂ ምክንያት ነው ቢባል እንኳ በንግድ ህግ ቁ.527(3) መሰረት ኪሳራ ከሚቆረጥለት በስተቀር ወደ ስራ አስኪያጅነቱ ፍርድ ቤት የሚመልስበት አግባብ የለም፡፡ እንደዚሁም በባለ አክሲዮኖች የተደገረገው ስብሰባ ህጋዊ ነው ተብሎ ተወስኖ እያለ በሌላ በኩል ም/ስራአስኪያጅ የተነሳበትን የቃለ-ጉባኤ ክፍል መሰረዙ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ከምክትል ስራ አስኪያጅነት የተሻርኩት በጠቅላላ ጉባኤ ሳይሆን ተከሳሾች እናት እና ልጅ በመሆን ያደረጉት በመሆኑ የመመስረቻው ጽሑፍ አንቀፅ ተጠቅሶ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ በንግድ ህግ ቁ. 527(3) ስር የተጠቀሰው ፍርድ ቤት ሊቀበለው የሚችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ስራ አስኪያጅ ሊሻር የማይችል ስለመሆኑ በመመስረቻ ጽሑፍ ስለተቀመጠ ወይም ስላልተቀመጠ ሳይሆን ህግ በመሆኑ ሊተገበር ይገባል፡፡ እንደዚሁም በ1995 ዓ.ም በተሸሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ ም/ስራአስኪያጅ የሆንኩት ከድርጅቱ ህልውና እና የአክሲዮን አባላቱ መብት ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ በመሆኑ ይሄውም 2ኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ ሆነው የተጠሪን ድርሻ ጨምሮ የሌሎች ሁለት ባለአክሲዮኖች እንጀራ እናት በመሆናቸው አድሎ እንዳይፈጽሙ ታስቦ በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረዉ ጭብጥ የመልስ ሰጪ ወደ ምክትል ስራ አስኪያጅነት ይመለስ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ የተያዘውን ጉዳይ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በንግድ ህጉ ቁ. 525 እስከ 537 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የአንድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ አስኪያጅ የሚመረጥበት እንደዚሁም የሚሾምበት አግባብ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምረው በመመስረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 2(2.4) ስር በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ስራ አስኪያጅን ማንሳት የሚቻል ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር በተመለከተ በዚህ መልኩ ማንሳት እንደሚቻል ስምምነት ቢኖርም ያለበቂ ምክንያት እና በአባላት ፍቃድ ብቻ መሰረት በማድረግ ማንሳት የሚቻል ስለመሆኑ በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር ባለመኖሩ ከላይ የተመለከተውን የመመስረቻ ጽሑፍ ድንጋጌ በመጥቀስ የቀረበው ክርክር ከንግድ ህግ ቁ.527(4) ጋር አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእርግጥ የአሁን ተጠሪ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የተሾመው በመመስረቻ ጽሑፉ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፤ በመመስረቻ ጽሑፍ የተመረጠ ስራ አስኪያጅ ለመሻር ደግሞ መመስረቻ ጽሑፍን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን የ¾ኛ ካፒታል ድርሻ ባላቸው አባላት መደገፍ ያለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ.527(1) እና 536(2) አጠቃላይ ንባብ የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ በዚህ ጉዳይ ስብሰባውን ያደረጉት የአመልካቾች ወገን 77.50% የካፒታል ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በሌሎቹ የመመስረቻ ሰነዱን ማሻሻል በተመለከተ ህጋዊ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በማረጋገጥ ተቀብለዋል፡፡ ሆኖም ግን ስራ አስኪያጅን ስለመሻር በተመለከተ በንግድ ህግ ቁጥር 527 ስር የተደነገጉትን አንድ በአንድ ስንመለከት ከላይ የተመለከተው እና ስራ አስኪያጅን ለመሻር የሚያስፈልገው ድምጽ በንግድ ህግ ቁ.527(1) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሦስት ስር ስራ አስኪያጅ ፍርድ ቤት ሊቀበለው በሚችል በቂ ምክንያት ካልሆነ ሊሻር እንደማይችል፣ የተሻረው ስራ አስኪያጅ ከተሻረበት ጊዜ አንስቶ ስራውን መስራት የማይችል ስለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱም የተሻረበት በቂ ምክንያት ያለመሆኑን የተረዳው እንደሆነ የተሻረው ስራ አስኪያጅ ኪሳራ እንዲያገኝ ለመወሰን ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሄ በንግድ ህግ ቁ.527(3) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል ከተመለከተው ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድ ቀጥሎ የመጣ በመሆኑ ስራ

አስኪያጅን ከስራ ለማንሳት መሟላት እንዳለበት በተለየ የሚደነግገውን ቅድመ ሁኔታዎቹ ስለመሟላት ወይም አለመሟላት መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የስራ አስኪያጅን መሻር በተመለከተ ፍርድ ቤት ሊያምንበት የሚችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ሊሻር እንደማይችል በግልጽ የደነገገ በመሆኑ ፍርድ ቤት ስራ አስኪያጁ የተሻረበትን አግባብ በመመርመር እንደጉዳዩ አግባብ እየተመለከተ ወደ ስራው ሊመልስ የሚችልበት ምንም ህጋዊ አካሄድ የለም በማለት በአመልካቾች በኩል የተነሳው ክርክር በህጉ በግልጽ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በንግድ ህግ ቁ.527(3) ሁለተኛው እና ሶስተኛውን አረፍተ ነገር በተመለከተ ከኃላፊነት የተሻረ ስራ አስኪያጅ ወዲያውኑ እና ለዘለቄታው ስራውን ያቆማል መባሉ ስራ አስኪያጁ የተሻረበትን አግባብ ለመመርመር ለፍርድ ቤት የተሰጠውን ስልጣን የሚነካ እና የሚቃረን ካለመሆኑም በላይ ያለአግባብ የተሻረ ስራ አስኪያጅ ፍርድ ቤቱ ኪሳራ እንዲቆረጥለት መወሰን መቻሉ ፍርድ ቤቱ ማድረግ የሚችለው ኪሳራን መቁረጥ ብቻ ነው ከሚል ባለመሆኑ እና እንደየ ጉዳዩ አግባብ ለመወሰን እንዲችል ፈቃጅ (permissive) በሆነ መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ ፍርድ ቤት ኪሳራ ቆርጦ ከማሰናበት ውጪ ስራአስኪያጁ የተሻረው ያለአግባብ መሆኑን ቢረዳም ወደ ስራው እንዲመለስ የሚወስንበት አግባብ የለም በማለት የተነሳውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ምክንያቱም ያለበቂ ምክንያት ሊሻር የሚችል ስራ አስኪያጅ እንደሚኖር ሁሉ በበቂ ምክንያትም የሚሻር ስራ አስኪያጅ ሊኖር ስለሚችል ፍርድ ቤቶች እንደየጉዳዩ አግባብነት በመመልከት መወሰን እንዲችሉ ፈቃጅ በሆነ መልኩ የተቀረጸ ድንጋጌ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ያለበቂ ምክንያት የተሻረም ቢሆን እንደየጉዳዩ አግባብነት ኪሳራ ተከፍሎት እንዲሰናበት ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል ማለት ነው፡፡

በሌለ በኩል በንግድ ህግ ቁ. 527(3) ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ ከአቀማመጡ አኳያ በተለየ ሁኔታ ስራአስኪያጅን ለመሻር የተመለከተውን ድንጋጌ ያስቀመጠው በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ አራት ስር የተቀመጠው ሲሆን ይሄውም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በማህበርተኞች ነጻ ፍቃድ (at the pleasure of the members) ሊሻር የሚችል ስለመሆኑ የተስማሙ እንደሆነ በማለት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት መልኩ የተስማሙ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የሌለ እና አመልካች በቅሬታው ላይ ያነሳው በጠቅላላ ጉባኤ ማንሳት እንደሚቻል በመመስረቻ ጽሑፉ ተመልክቷል የሚል ሲሆን ይሄ ማለት ደግሞ በንግድ ህግ ቁ 527(4) ስር የተመለከተውን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካቾች ተጠሪን ከም/ስራአስኪያጅነት ለማንሳት ያቀረቡት በቂ ምክንያት ያለመኖሩን በበታች ፍርድ ቤት በፍሬ-ነገር የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በክርክር ሂደት ግልጽ የሆነው ደግሞ ግራቀኙ የሚያስተዳድሩት ድርጅት እንደማንኛውም ተቀጣሪ ስራ አስኪያጅ ሳይሆን በውርስ የተላለፈላቸውና አመልካቾች በአንድ ወገን በመሆን ተጠሪ ደግሞ በሌላ ወገን በመሆን የተለያዩ ፍላጎቶች በመከሰታቸው የተጠሪ ከም/ስራአስኪያጅነት አለመነሳት በአግባቡ መሆኑን የሚያጠናክር ነጥብ ነው፡፡

ባጠቃላይ የአሁን ተጠሪ ከምክትል ስራአስኪያጅነት የተነሳው ያለአግባብ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተመልክተው ወደ ስራው ይመለስ በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.94715 ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 140096 በቀን 05-9-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ ከምክትል ስራአስኪያጅነቱ የሚሻርበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ጥር 02 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ሀ

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ 69291

ህዳር 8 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ጀማል አማን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ተዋበች ፈረዶ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የእርሻ መሬት ይዞታና የመጠቀም መብትን የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአርሲ ዞን የጉፉ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ተበድሬ በወለድ አግድ ሶስት ቀርጥ የሚሆን መሬት ህዳር 10 ቀን 1990 ዓ.ም በተፃፈ ውል ሰጥቸዋለሁ፡፡ መሬቱን እንዲለቅልኝ ብጠይቀው እንቢተኛ ስለሆነ በፍርድ ተገድዶ ይልቀቅልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች መሬቱን ብር 1020 ተቀብላ ከሰጠችኝ በኋላ በገንዘቡ ችግሯን ከተወጣች በኋላ መሬቱን እንዲለቅላት መጠየቁ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ከሰጠችው ሶስት ቀረጥ መሬት አንድ ቀርጥ መሬት ብቻ ለተጠሪ ይልቀቅላት በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሉ ለህግ ተቃራኒ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪ መሬት ላይ የሰራውን ቤት አንስቶ መሬቱን ለተጠሪ ያስረክብ በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር

ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መሬቱን ይዞ አስራ አንድ ዓመት እንደቆየና የተጠሪ ክስ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ መሬቱን እንድለቅ መወሰኑ ስህተት አለበት፡፡ ግምቱ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ ብር/ የሚያወጣ ባህር ዛፍ ተክየበት እያለ እንድለቅ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ሰበር ችሎት ፍርድ ቤት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች መሬቱን የያዘው በውል ነው፡፡ ስለዚህ ይርጋን መከራከሪያ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ አመልካች ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ስለከፈለ መሬቱን ይዞ የሚቆይበትና የእኔን የመሬት ባለይዞታነትና ተጠቃሚነት መብት የሚያሳጣበት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የክልሉ አዋጅ ቁጥር 130/1999 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1810 እና 1845 በመጥቀስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል ጉዳዩን እንደመረመርነው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ? ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ከተጠሪ ጋር ህዳር 10 ቀን 1990 ዓ.ም አድርጌዋለሁ የሚለውን ውል ይዘትና መሠረታዊ ባህሪ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የተለያየ ንብረት አፍርቸበታለሁ የሚለው የእርሻ መሬት የተጠሪ ህጋዊ ይዞታ መሆኑን አልካደም፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ችግር አጋጥሟት እኔ ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ለችግር ማቅለያ እንዲሆናት ሰጥቻት ተጠሪ የእርሻ መሬቱን እኔ እንድጠቀምበት ሰጥታኛለች፡፡ የእርሻ መሬቱንም ከሰጠችኝ አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ ተጠሪ የእርሻ መሬቴን ይልቀቅልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ነው፡፡ በእኛ በኩል አመልካች ከተጠሪ ጋር ህዳር 10 ቀን 1990 ዓ.ም የተዋዋለው ውል በመሠረታዊ ይዘቱ አመልካች ለተጠሪ በሰጣት ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ መክፈያ እንዲሆን ተጠሪ ሶስት ቀርጥ መሬት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲጠቀምበት ግዴታ የገባች መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ውሉ በመሠረታዊ ይዘቱም ሆነ በባህሪው ተጠሪ በመሬቱ ላይ ያላትን የመጠቀምና  የይዞታ መብት ለዘለቄታው ለአመልካች በብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ለመሸጥ የተስማማች መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግስትና የህዝብ ሀብት መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት ሆኖ ማናቸውም ኢትዮጵያ አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀምና  ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ መንግስት የአርሶ አደሮችን የመሬት ባለይዞታ የመሆን መሬት የመጠቀምና ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት ህጋዊና ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/93 እና በኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/99 በማውጣት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ አንድ አርሶ አደር የእርሻ መሬቱን ከሶስት ዓመት በላይ በኮንትራት መስጠት እንደማይችል የደነገገ ሲሆን ማንኛውም አርሶ አደር መሬቱን በኮንትራት

ለሌላ ሰው ሲሰጥ ውሉ ሊያሟላቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ይዘረዝራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንድ አርሶ አደርን የመሬት ይዞታና በመሬት የመጠቀም መብት በውል በመውሰድ በመሬቱ ላይ ቋሚና ተንቀሣቃሽ ሀብት ያፈራ ሰው ንብረቱን አፍርሶ በመውሰድ መሬቱን የመልቀቅ ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 6 ተደንግጓል፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርጌዋለሁ የሚለው ውል በመሠረታዊ ይዘቱና ሞራላዊ ባህሪው በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 እና በህገመንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀምን ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት የሚጥስ ከሆኑ በኋላ የፌደራል መንግስት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 130/99 ድንጋጌዎች የሚቃረን ህገወጥ የሆነ ውል ነው፡፡ ውሉ ህገወጥ ውል በመሆኑ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ብር 1020 /አንድ ሺ ሃያ ብር/ በመክፍል የተጠሪን ሶስት ቀረጥ የእርሻ መሬት ለዘለቄታው ለመውሰድ የተዋዋለው ውል ህገወጥ ውል በመሆኑ ውሉ ፈራሽና ውጤት አልባ ነው በማለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የህገ መንግስቱንና የፌደራሉ መንግስት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 130/99 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተሰጠና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሀምሌ 6 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 69302
ታህሣሥ 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሽለማ ነገሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፋይሣ መንግስቱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኖኖ ቤንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ የእርሻ መሬትን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በኖኖ ቤንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በኖኖ ቤንጃ ቀበሌ ውስጥ በሰሰኮ ጎጥ ጋሴ ቀርጫ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ የተለያዩ አትክልቶች አርባ ግንድ ባህር ዛፍ አራት ግንድ ጌሾ አባቴ ተክሎ ሲጠቀምበት የኖረውን መሬት ተከሣሽ በሥልጣኑ ይዞታል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች መሬቱን እኩል ያካፈሉን ሲሆን መሬቱ የአባቴ በመሆኑና ለእኔ ሊደርሰኝ ስለሚገባ የእርሻ መሬቱን እንዲለቅልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የአሁን አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ክስ የቀረበበትን መሬት ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት የከሣሽ አባት በህይወት እያለ የነበረውን ባህር ዛፍ ገዝቼ መሬቱን በ1981 ዓ.ም. ተመርቼ ይዤው እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ፡፡ መሬቱ በአሉ ኤልፈታ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን አባቱ መሬቱን ለቆ ወደ ደጋ ሲባ ቀበሌ ሄዷል፡፡ መሬቱ የራሴ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የኖኖ ቤንጃ ወረዳ መሬትና የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት አመልካችም ሆነ ተጠሪ በመሬቱ ላይ ግብር እየከፈሉ አይደለም፡፡ በፊት መሬቱ የከሣሽ አባት ነበር በማለት ማስረጃ በመስጠቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ የሰው ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ የቀረቡት ምስክሮች የከሣሽ የተጠሪ አባት 1985 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ከዚህ በኋላ ተከሣሽ አመልካች መሬቱን ይዞ የሚገኝ መሆኑን እና ግራ ቀኙ በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን የተጠሪ ምስክሮች የመሠከሩ ሲሆን የአመልካች ምስክሮች አመልካች ተመርቸዋለሁ በማለት መሬቱን እንደያዘ ፣ ከቦታው ድረስ ሄደው እንደሚያውቁ መሥክረዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የእርሻ መሬቱ የከሣሽ አባት የነበረ ስለሆነ ተከሣሽ መሬቱን ይልቀቅ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታውን አልተቀበሉትም፡፡

አመልካች 1981 ዓ.ም መሬቱ ባዶ መሆኑን አመልካች ለእኔ ተሰጥቶኛል፡፡ አመልካች በህጋዊ መንገድ በይዞታዬ አድርጌ አሥራ ሁለት ዓመት ከተጠቀምኩበት በኋላ ተጠሪ የአባቴ መሬት ነበር በማለት ክስ አቅርቧል ፡፡ ከዚህ በፊት በዚሁ ጉዳይ የተጠሪ ወንድም ክስ አቅርቦብኝ የማህበራዊ ፍርድ ቤት መጋቢት 4 ቀን 1994 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም በፍርድ በተቋጨ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሀምሌ 21 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ አመልካች ያነሣው የይርጋ ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ መሬቱንም አስራ ሁለት ዓመት አልያዘም፡፡ እኔም አካለመጠን ያልደረስኩ ነበርኩ አመልካች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ወስኖልኛል ያለው በሥር ፍርድ ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፡፡ ስለዚህ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሀምሌ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለረዥም ጊዜ መሬቱን በይዞታየ አድርጌ እየተጠቀምኩበት ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር በማለፍ መሬቱን ለተጠሪ እንዲለቅ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች የክርክሩ መነሻ የሆነውን የእርሻ መሬት የያዘው ከመቼ ጀምሮ ነው? ተጠሪስ አመልካች የእርሻ መሬቱን እንዲለቅለት ክስ ያቀረበው መሬቱን አመልካች ከያዘው ከስንት ጊዜ በኋላ ነው የሚሉትን ነጥቦች መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች የክርክሩ መነሻ የሆነውን የእርሻ መሬት 1981 ዓ.ም. ጀምሮ ይዥዋለሁ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን የእርሻ መሬት የተጠሪ አባት 1985 ዓ.ም በሞት ከተለየበት ጊዜ ጀምሮ የያዘው መሆኑ ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረባቸው ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡

የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መነሻ በማድረግ ተጠሪ አመልካች የሟች የአባቱን ይዞታ መሬት እንዲለቅለት ክስ እስካቀረበበት 2003 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ አመልካች ለአሥራ ስምንት ዓመት የእርሻ መሬቱን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1140 በሚደነግገው መሠረት በእጁ አድርጎ በእውነት ሲያዝበት የኖረ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበው ሟች ወላጅ አባቴ በመሬቱ ላይ የነበረው የይዞታና በመሬቱ የመጠቀም መብት በውርስ ለእኔ ተላልፎልኛል በማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የአርሶ አደር አባታቸውን ወይም እናታቸውን የእርሻ መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ያላቸው ወራሾች በውርስ ተላልፎልናል የሚሉትን መብት ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚችሉት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ነው? በሌላ አነጋገር የእርሻ መሬት የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር በሚቀርብ ክስ ላይ የይርጋ የጊዜ ገደቡ ምን ይሆናል? የሚለው

ነጥብ ነው፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆንና ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑሰ አንቀፅ 4 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል ያወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቀቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 የመሬት ባለይዞታ የሆነና በመሬቱ የመጠቀም መብት ያለው ሰው ለሁለት ዓመት ያህል መሬቱን በመተው ከአካባቢው ከጠፋ የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም መብቱ ቀሪ እንደሚሆን ይደግጋሉ፡፡ ሆኖም የህግ ማዕቀፎቹ የእርሻ መሬት ባለይዞታና የመጠቀም መብቴ በሌላ ሰው ተደፍሮብኛል የሚል አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ ያለበት በስንት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የፌዴራሉ አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/1999 በግልፅ አይደነግጉም፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለውን የይርጋ ህግ ድንጋጌ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብት በማያጣብብ ሁኔታ አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች በመተርጎም ውሣኔ መስጠት የሚገባው ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች ስንመረምር በመጀመሪያው ድንጋጌ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ሆኖም ድንጋጌው በተለያየ መንገድ የይዞታና በመሬት የመጠቀም መብታቸውን በሌላ ሰው የተደፈረባቸው አርሶ አደሮች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም መብት በፍርድ ቤት ተከራክረው በማስከበር ሰፋ ያለ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ በገጠር መሬት ላይ ያለን የባለይዞታነትና በመሬት በመጠቀም በሚቀርብ ክርክር ላይ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 2 ተመራጭ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ማንኛውም አርሶ አደር ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በእርሻ መሬት ላይ ያለውን የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር ተገቢውን ትጋት የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በሌሎች የይርጋ የጊዜ ገደብ በግልፅ ባልተደነገገላቸው ጉዳዮች ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ለፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1677/1/ እና ለፍትብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አርሶ አደሮች በህገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የመሬት ባለይዞታነትና በመሬት የመጠቀም መብት በፍርድ ከስሰው ለማስከበር ሰፋ ያለ እድል የሚሰጠው የፌዴራል አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሠረታዊ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አግኝተዋል፡፡ ስለሆነም ይዞታውን በሌላ ሰው የተነጠቀ አርሶ አደር ወይም ወራሾቹ ይዞታው በሌላ ሰው ከህግ ወይም ከውል ውጭ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ውስጥ የእርሻ መሬት የባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ካላቀረበ ክሱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1677/3/ እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 በተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡

2. ተጠሪ አመልካች በ1985 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ወላጅ አባቱ የእርሻ መሬት ሊለቅልኝ ይገባል በማለት ያቀረበው በ2003 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረበው አመልካች የእርሻ መሬቱን ለአሥራ ስምንት ዓመት ይዞ ከተጠቀመበት በኂላ መሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች መሬቱን ለአሥራ ስምንት ዓመት የያዘ መሆኑን በመግለፅ ተጠሪ ክስ ሊያቀርብብኝ አይገባም የሚለውን ክርክር ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ

ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት እንዳቀረበ ተገንዝበናል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ጉዳይ ገብቶ የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በመጀመሪያ አመልካች ባነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ መቃወሚያ ላይ ብይን መስጠት እንዳለበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ አመልካች የአባቱ ይዞታ የነበረውን መሬት እንዲለቅለት ክስ ያቀረበው አመልካች መሬቱን 1985 ዓ.ም ጀምሮ ይዞ አሥራ ስምንት ዐመት ከቆየ በኋላ መሆኑ በተጠሪ ምስክሮች ጭምር ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1677/1/ እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ አመልካች መሬቱን እንዲለቅለት ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በማለፍ መሬቱን ለተጠሪ እንዲለቅ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኖኖ ቤንጃ ፍርድ ቤት ፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች መሬት እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች መሬቱን ለተጠሪ የመልቀቅ ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ 69821

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** አቶ ጥላሁን ጎበዜ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ መከተ ኃይሉ - ቀረቡ

2. አቶ አወቀ ሙጨ - በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግሥት በፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ የተጀመረ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሣሾች በ1989 ዓ.ም በተደረገው የመሬት ሽግሽግ የተመራሁትን ስለያዙብኝ እንዲለቁልኝ በማለት አዋሣኙን በመጥቀስ እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡ ተከሣሾች በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሠጡበት ታዘው በሰጡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት ከ1989 ዓ.ም. በፊትም የራሳቸው የነበረ ስለመሆኑ፣ በ1989 ዓ.ም. የመሬት ሽግሽግ ሲደረግ ለተከሣሾች የተቆጠረ ስለመሆኑ፣ በ1997 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው የሚጠቀሙበት የራሳቸው ይዞታ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ የወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተከሣሾች በዚህ አከራካሪ በሆነው የእርሻ መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ስለተሰጣቸው ያለአግባብ የተሰጠ የይዞታ መረጋገጫ ከሆነ ይዞታውን ለሰጠው አካል ከማቅረብ ውጭ በቀረበው ክስ መሬቱ የከሣሽ ነው በማለት ማስለቀቅ አይቻልም በማለት በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ክስ መቅረቡ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የበታች ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር ተከሣሾች ለክርክር ምክንያት የሆነውን የእርሻ መሬት ለከሣሽ (አመልካች) እንዲያስረክቡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በዚህ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎአል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች በቀረበው ክስ ላይ ውሣኔ የሰጡት ተገቢውን የማጣራት ሂደት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አዋጅ ቁ. 133/98 አንቀጽ 24(4) እና ይሄንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው የደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 20(4) የይዞታ ማረጋገጫ የያዘ ሰው የመሬቱ ባለይዞታ እንደሆነ እንደሚገመት ይደነግጋል፡፡ ይሄ ማለት ግን በህጉ የተቀመጠው የባለይዞታነት ግምት ሊስተባበል የማይቻል በራሱ ብቻ አሳሪ ማስረጃ ስለመሆኑ የተመለከተ ነገር የለም፡፡

በአንድ የፍትሐብሔር ክርከር በህጉ በተለየ ሁኔታ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱ የተገደበ ካልሆነ በጽሑፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት፣ በተከራካሪዎች እምነት፣ ወይም በመሓላ ማስረጃ ማስረዳት እንደሚቻል በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 2002፣ 1195፣1196 እና በተለያዩ ህጎች ውስጥ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቶችን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማ፣ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ተከሣሾች ይዞታዬን ይዘውብኛል እና እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎችም የራሳቸውን መከራከሪያና በ1997 ዓ.ም የተሰጣቸውን የይዞታ ማረጋገጫ አቅርበዋል፡፡ ይሄ በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያላቸውን ማስረጃ በመስማት እና ከሌላ የመንግሥት አካላትም መቅረብ ያለበትን ማስረጃ በመቀበልና የቀረቡትን ማስረጃዎች በማመዛዘን ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ያቀረቡ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡ የይዞታ ማረጋገጫም ቢሆን እንደአንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለውና ሊመዘን የሚችል እንጂ ወሣኝ (conclusive evidence) ባለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመቀበል እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች በመቀበል ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባ የይዞታ ማረጋገጫ ሊስተባበል እንደማይቻል ማስረጃ በመውሰድ እንደዚሁም መስተባበል ካለበት የይዞታ ማረጋገጫውን ለሰጠው አካል አቤቱታ በማቅረብ ብቻ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ በግራቀኙ ማስረጃ ጉዳዩን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን እንደሌለው በመውሰድ የቀረበውን ክስ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ያስቀርባል አያስቀርብም በማለት ተገቢውን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ለተጠሪዎች የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠበትን አግባብ የወረዳው የመሬት አስተዳደር አካል መግለጫ እንዲሰጥበት ማድረጉ ተጠሪዎች የክርክሩ አካል ባልተደረጉበት ጊዜ በመሆኑ አግባብነት ያለው የማስረጃ አሰባሰብ ስርአት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡ ምክንያቱም ማጣራቱ ተገቢ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ግራቀኙ የክርክሩ አካል በሆኑበትና የእኩልነት መርህን በጠበቀ መልኩ መከታተልና በቀረበው ማስረጃ ላይ አስተያዬት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ መደረግ ነበረበት፡፡

ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የእርሻ መሬት የማን ይዞታ ነው? የሚለውን ነጥብ በግራቀኙ ማስረጃ በማጣራት እንደዚሁም ከሌላ የመንግስት አካልም ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል አስፈላጊ ከሆነም ይሄው ስርአት ተፈፅሞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ሲገባው መሰረታዊ የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ስርአት ባልተከተለ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የመዝ.ቁ. 07860 ሚያዝያ 24 ቀን 2003ዓ.ም በዋለው ችሎት፣የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.25228 በቀን 03-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 21099 በቀን 11-10-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት መዝ.ቁጥር ባልተጠቀሰ በቀን 15-4-2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የእርሻ መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ በመያዛቸው ብቻ ሊስተባበል አይችልም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው አግባብነት ያለው አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት ግራቀኙ አከራካሪ በሆነው የእርሻ መሬት ላይ ያላቸውን ማስረጃ መስማትና ሌሎች ተገቢ ናቸው የሚለውን ተጨማሪ ማስረጃዎች ከሚመለከተው የመንግስት አካል በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 59504

የካቲት 27ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. አቶ እንዳለ ወርቅነህ - አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ብዙነሽ ሰንበቶ - አልቀረቡም

3. አቶ ኪዳኑ ቦቦ - ቀረቡ

4. አቶ ተስፋዬ ፈይሳ - አልቀረቡም

5. ወ/ሮ በላይነሽ ታደሰ -አልቀረቡም

6. ወ/ሮ ዙፋን ታደሰ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ተሸለ ቱቾ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄ የሚስተናገድበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካች ስድስት ክፍል ቤቶች የካርታ ቁጥሩ 968/አንቀፅ/ 96 የሆነውን በነቀምቴ ከተማ በዳርጌ አስተዳደር ክፍል ውስጥ የሚገኘውን በዚህ ሰበር ችሎት ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት ለተጠቀሱት በብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ) ሸጠው ስም በማዛዋወር ላይ እንዳሉ ሰምተው ከነቀምት ከተማ አስተዳደር ላይ አጣርተው ይህን ቤት ለመግዛት ቀዳሚ መብት እንዳለቸው ማመልከታቸውን፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ተጠሪ የንግድ ድርጅታቸውን ከመግዛታቸው በፊት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ንብረት የነበረ ሆኖ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በእዳ ይዞ ይኸው አካል በሕግ አግባብ የሸጠላቸው መሆኑን፣ በዚህ አግባብ በገዙት ንብረትም የባለቤትነት ማስረጃ የካርታ ቁጥር 352/አንቀጽ/2000 በሆነው ተሰጥቷቸው ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት የተጠቀሱት አመልካቾች ከገዙት ቤት ጋር በግድግዳ፣ በጣሪያውና በአንድ ምሰሶ ተያይዞ የተሰራ መሆኑን፣ ይህን ቤት አሳልፎ ለሶስተኛ ወገን መሸጥ ማለት አንድን ቤት ለሁለት ከፍለው መሸጥ መሆኑንና ይህም የተጠሪን መብት የሚጎዳ መሆኑን ዘርዝረው ገዥዎች የገዙትን ዋጋ ተጠሪ ከፍለው በቀዳሚነት የመግዛት መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም በተጠሪና በሻጮች መካከል

በቤቶቹ ላይ የጋራ መብት ስለመቋቋሙ የሚያሳይ ውል የሌለ መሆኑን፣ የቤቱ ጣሪያና ግድግዳ አንድ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ የግዥና የሽያጭ ውሉም ተመዝግቦ የባለቤትነት ማስረጃ ሊሰራ ቁጥር ስለመስጠታቸውና ተጠሪ የቅድሚ ግዥ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ጉዳዩን ተገቢ ነው ባለው መንገድ ከአጣራ በኋላ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1281 መሰረት በቤቱ ላይ የጋራ መብት ማቋቋማቸው መረጋገጡን፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1261፣ 1386 እና 1388 ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪ በግዥ የተላለፈውን ቤት በቀዳሚነት የመግዛት መብት እንዳላቸው የሚያሳይ መሆኑን ገልፆ ተጠሪ የቤቱን ዋጋ ከፍለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ይግዙ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የኸው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በቤቱ ላይ የቀዳሚነት መብት አላቸው ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች የተወሰነው በቤቱ ላይ ግራ ቀኙ ያቋቋሙትን መብት አይነት፣ መብቱ የተቋቋመበትን መንገድና ጊዜ እንዲሁም የጋራ መብት ያላቸው ሰዎች የቀዳሚነት መብት የሚኖራቸው ምን ምን ሕጋዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው የሚለውን ሕጋዊ ጥያቄዎች ተገቢውን ምልከታ ያላደረገና በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ውጪ የተሰጠ ስለመሆኑ ዘርዝረው ውሳኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቤቶች ለመግዛት የቅድሚያ መብት አለው የተባለው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በፅሁፍ በሰጡት መልስ የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ ስለጋራ ባለሀብቶች የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ በመሆኑ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ውሳኔው እንዲፀናላቸው የተከራከሩ ሲሆን አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ስድስት ክፍል ቤቶች የካርታ ቁጥሩ 968/አንቀጽ/ 96 የሆነውን በነቀምቴ ከተማ በዳርጌ አስተዳደር ክፍል ውስጥ የሚገኘውን በዚህ ሰበር ችሎት ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት ለተጠቀሱት በብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ) ሸጠው ስም ለማዘዋወር ላይ እንዳሉ ሰምተው ከነቀምት ከተማ አስተዳደር ላይ አጣርተው ይህንን ቤት ለመግዛት ቀዳሚ መብት እንዳለቸው በማመናቸው መሆኑን፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ተጠሪ የንግድ ድርጅታቸውን ከመግዛታቸው በፊት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ንብረት የነበረ ሆኖ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በእዳ ይዞ የኸው አካል በሕግ አግባብ ለተጠሪ የሸጠላቸው መሆኑን፣ በዚህ አግባብ በገዙት ንብረትም የባለቤትነት ማስረጃ የካርታ ቁጥር 352/አንቀጽ/2000 በሆነው የተሰጣቸው መሆኑን፣ ይኸው ቤት ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት የተጠቀሱት አመልካቾች ከገዙትና ለክርክሩ ምክንያት

ከሆኑት ቤቶች ጋር በአንድ በኩል በግድግዳ በአንድ በኩል ደግሞ ብሎኬት የተሰሩ ስለሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የምስራቅ ወለጋ ዞን ስራና ከተማ ልማትና ጽ/ቤት በባለሙያ አረጋግጦ ማስረጃ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡

1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለሌሎች አመልካቾች ሽጡ የተባሉት ቤትና ተጠሪ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ገዙ የተባለበት ቤት የተያያዙበት ግድግዳና ጣሪያ የጋራ ባለሀብትነት መብት በሕግ አግባብ የተቋቋመ ነው፡፡ በህጉ መሰረት የተፈጠረ የጋራ ባለሀብትነት ደግሞ የሚገዛው አግባብነት ባለው ህግ ነው፡፡ ከፍ/ህ/ቁ 1259-1277 ያሉት ድንጋጌዎች የሚያሳዩትም ይህንኑ ነው፡፡ የፍ/ህ/ቁ 1260/1/ ድንጋጌ የሚገልጸው ደግሞ እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት ድርሻውን ለመሸጥ ወይም በሌሎች መንገዶች የማስተላለፍ ወይም ለማስያዝ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስልጣኖች ሌሎች የጋራ ባለሀብቶች እየተቃወሙ ቢሆን እንኳን ባለድርሻው የጋራ ባለሀብት የሚተገብራቸው፣ በህግ የተጠበቁ ናቸው፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1281(1) ድንጋጌ ስር እንደተመለከተው ያንድ ቤት ልዩ ልዩ ፎቆች ወይም ለመኖሪያ የተመደቡ ክፍሎች (አፓርታማ) የልዩ ልዩ ባለሀብቶች ንብረት በሆኑ ጊዜ ተቃራኒ የሆነ ሰነድ ከሌለ ከእነዚህ ሀብቶች አንዱ ክፍል ለአንደኛው ባለንብረት የግል አገልግሎት የሚጠቅም እንዲሆን ከተደረገው በቀር የመሬቱና የሌላውም የቤቱ ክፍሎች የጋራ ንብረት እንደሆኑ የሚቆጠሩ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1289(1) ድንጋጌ ስር ደግሞ እያንዳንዱ የጋራ ባለንብረት የአንድነት ሀብት ባልሆነው ክፍል ንብረቱ ላይ ህግ ለባለሀብቱ የሚሰጣቸው መብቶች እንደሚኖሩት ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1289(2) ድንጋጌ በተለይ ሲታይ ደግሞ የግሉ የሆነውን ለመኖሪያ የተመደቡትን ክፍሎች (አፓርታማ) ወይም ፎቅ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከራየት ወይም በዋስትና ለማስያዝ ባለሀብት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1290 ደግሞ የአንድነት ያልሆኑት ክፍሎች ላይ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1289 ስር የተመለከቱት መብቶች ያሉት ባለሀብት የተጣለበት ገደብ መኖሩ ተመልክቷል፡፡ ይህም ምንጊዜም የማይንቀሳቀሰውን ንብረት የተመደበበትን አግልግሎት አክብሮ መጠበቅ፣ እንዲሁም የተከፈለ ድርሻ የሆነው ንብረት እንዲያገለግል የተመደበበት ጉዳይም ሆነ የመጠቀሚያውን አይነተኛ ነገር ሌሎቹን ባለሀብቶች በሚጎዳ ሁኔታ ለመለወጥ ያለመቻል በሕጉ የተጣለበት ገደብ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያሳዩት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በጋራ ባለመብት የሚያደርጋቸው የንብረቱ ክፍል ካለ በዚሁ የጋራ ባለንብረት በሚያደርጋቸው የንብረቱ ክፍል ባለሀብቶቹ የሚኖራቸው መብት ለአንድ ባለሀብት ህጉ የሰጣቸው መብቶች ስለመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተደነገጉትን የንብረት ህግ ድንጋጌዎችን ስንመለከት ባለቤትነት ከሁሉ የሰፋ መብት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በህግ የተቀመጡትን ገደቦችንና ወሰኖችን (Restriction and Limitation) ሳያልፍ የአንድ ንብረት ባለቤት በንብረት እንደፈለገው የመጠቀምና የመገልገል መብቱና ነፃነቱ በህግ የተከበረለት ስለመሆኑም ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ፡፡ ለባለሀብቱ የባለቤትነት መብት ከሚሰጣቸው መብቶች መካከልም ንብረቱን በህጉ አግባብ ማስተላለፍ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1184 እና 1185 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በአጠቃላይ የባለቤትነት መብት ከሁሉ የሰፋ መብት ሲሆን በህጉ ከተጣሉት ገደቦች ውጪ የሚነካ ወይም ለሌላ ተላልፎ እንዲሰጥ የሚደረግ መብት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሕጉ የጋራ ባለሀብት በህጉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባቸው መብቶች ምን እንደሆኑ ለይቶ አስቀምጧል፡፡

በዚህም መሰረት የፍ/ህ/ቁ. 1261፣ 1388 እና 1406 ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ የጋራ ባለሀብቶች ያልተከፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም 3ኛ ወገን በፊት፣ ሊሸጥ የታሰበውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር

1281፣ 1289 እና 1290 ድንጋጌዎች ተግባራዊ የሚደረጉበትን አግባብ የሚገድቡ አይደሉም፡፡ ይልቁንም በበንብረቱ ላይ ባለሀብቶች ያላቸው ድርሻ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1281፣ 1289 እና 1290 ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዛ መሆኑ ከተረጋገጥው ውጪ የጋራ የሆነው ሀብት ሊሸጥ ሲታሰብ የጋራ ባለሀብቶች ከማንኛውም 3ኛ ወገን በፊት ሊሸጥ የታሰበውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ቤት በአንድ በኩል ግድግዳውና ጣሪያው የተያያዘ መሆኑ በሌሎች ክፍሎች ባለሀብቱ ያለውን መብት በፈለገው የገበያ ዋጋና ግዥ ወይም ለመለወጥ ሳይችል በአንድ በኩል የግድግዳው ባለሀብት ለሆነው ባለሀብት አጠቃሎ እንዲሸጥ በህግ ገደብ አልተጣለበትም፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እንዲገዙት የወሰኑት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው የፍ/ብሕ/ቁጥር 1281፣1289 እና 1290 ድንጋጌዎች ይዘት በፍሬ ነገር ደረጃ ቤቱ የተያያዘው በአንድ በኩል በግድግዳና ጣሪያ ስለመሆኑ ከተረጋገጠው ነጥብና ከተጠሪ ዳኝነት ይዘት ጋር በአግባቡ ሳያገናዝቡ እና በተጠሪ ላይ ሊደርስ ይችላል የተባለው ጉዳትም ሳይረጋገጥ ነው፡፡ ለአንድ ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ እያለ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ደግሞ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 12896 ጥር 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11851 20710 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ ፀንቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 100754 ነሀሴ 12 ቀን 2002 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በነቀምቴ ከተማ በዳርጌ አስተዳደር ክፍል በካርታ ቁጥር 968/አንቀጽ/ 96 በሆነው በ1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ ያለው ስድስት ክፍል ቤቶች ለተጠሪ በቅድሚያ የሚሸጡበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 64014

የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዶ/ር ገነት ሥዩም - ጠበቃ ተስፋዬ ተገኘወርቅ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 አስተዳደር ፅ/ቤት - ነገረ ፈጅ

አሸናፊ ሥዩም ቀረቡ

2. ወ/ሮ አመለወርቅ ሙላቴ } ጠበቃ ላውጋለት ፀጋ ቀረቡ፡፡

3. አቶ ባህረ ወ/ጊዮርጊስ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሕግ ውጪ የተያዘብኝ ቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

የአመልካች የክስ ይዘትም አመልካች የደርግ መንግስት በስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በነበራቸው የፖለቲካ አመለካከት ሀገር ውስጥ ለመኖር ባለመቻላቸው ተሰደው ውጭ ሀገር መቆየታቸውን፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 ክልል ውስጥ የሚገኘውና በካርታ ቁጥር 11442 የሚታወቀውን በ1985 ዓ/ም በቁጥር 15/31238 የሆነ የከተማ ቤት የባለቤትነት ደብተር ከከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የተሰጣቸው መሆኑን፣ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የቤት ቁጥሮች 268፣ 269 እና 270 በሚል መለያ ሰጥቶ ለ2ኛ፣ 3ኛ እና ለአቶ ዘሚካኤል ኃይሌ አከራይቶ ጥቅም እያገኘበት መሆኑን፣ ቤቱን 1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክባቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥተውም ፈቃደኛ ሁኖ ያለመገኘቱን ገልፀው ቤቱን ለሕጋዊ ባለቤት እንዲያስረክብ፣ ተከራዮችም ቤቱን እንዲለቁ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አከራካሪው ቤት በህግ በመንግስት መወረሱንና በፍርድ ቤት ስልጣን ስር የማይወድቅ መሆኑንና አመልካች ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ቤቱ በሕግ የተወረሰ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ሌሎች ተጠሪዎችም ቤቱን ለረዥም አመታት ተከራይተው የሚጠቀሙበትና በ1ኛ ተጠሪ የሚተዳደር መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ

ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረቡትን መቃወሚዎችን ውድቅ አድርጎ ፍሬ ጉዳዩን መርምሮ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት አመልካች መሆናቸው ተረጋግጧል በማለት ቤቱን ተጠሪዎች ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩና 1ኛ ተጠሪ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተደረገ በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አለኝ የሚሉት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መምከኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345(1ለ)) ድንጋጌን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በ1985 ዓ/ም ለአመልካች የተሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ ደብተሩ መክኗል ተብሎ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ መብት የላቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የነበረው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ሕጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ውሳኔው ሊጸና ይገባል ሲሉ በፅሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፣ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሠረቱ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ንብረታቸው መሆኑን መጥቀሳቸውንና ይህንኑ መብታቸውን ያሳያል ያሉትንና በ1985 ዓ/ም በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሰጠኝ ያሉትን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ለማስረጃነት ማቅረባቸውን፣ የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት መከላከያ መልስ አመልካች በቤቱ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፣ አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ተወርሶ 1ኛው አመልካች ለረዥም አመታት የሚስተዳድረው መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸውን፣ ይህንኑ የተጠሪዎችን ክርክር የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በአመልካች በኩል የቀረበውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርና ቤቱ ምትክ ያልተገኘበት ወይም ካሳ ያልተከፈለበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት መሆኑን፣ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ የይግባኝ ክርክር ሲደረግ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ አመልካች አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሰረዘ መሆኑንና ማስረጃው ሳይቀርብ የቀረበትን ምክንያት ገልፆ ማስረጃው እንዲቀርብ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ የባለቤትነት ደብተሩ መምከኑን የሚያሳየውን የ1ኛ ተጠሪ ማስረጃ ተቀብሎ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ ጋር በክሱ መሰማት ወቅት ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 234 ድንጋጌ ሲታይም በተከሳሹ ላይ ተመሳሳዩን ግዴታ ይጥላል፡፡ በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/3/ የሠነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀን

ቀጠሮ በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ካልቀረበ በቀር ማስረጃው ሊቀርብ ወይም ይቅረብልኝ ተብሎ ሊጠየቅ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ ይሄው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር በተመለከተው አኳኋን ማስረጃዎቹ ሣያቀርቡት የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡

የማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሌላው ደንብ የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ዓይነት ሠነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የማዘዝ ህጋዊ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145/1/ ድንጋጌም በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሠነድ የፁሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሠጠበት መዝገብ ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ በራሡ አነሣሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት እንዲቀርብለት ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ውሣኔ የሠጠው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345((1(ለ)) ድንጋጌ መሰረት የ1ኛ ተጠሪን የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄን ተቀብሎ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የማስረጃው መቅረብ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ተገቢ መሆኑን ማረጋገጡን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካችን የባለቤትነትን መብት ሰርዟል የተባለው ማስረጃ ግን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በኋላ የተሰረዘበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን አመልካች ክርክር እንዲያቀርቡ እድል የተሰጠ ስለመሆኑ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልጽ አያሳይም፡፡ በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ይህንኑ የምስክር ወረቀት በስሙ የተፃፈለት ሰው የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሕጉ የሚወሰደው ግምት ስለመኖሩ፣ ይኸው ግምት ግን አሳሪ ያለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር ተዳምሮ ሲነበብ ያስረዳል፡፡ በሌላ አገላለፅ በአስተዳደር አካሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ነው ተብሎ የምስክር ወረቀት መስጠት ማስረጃውን ድምዳሚ ወይም አሳሪ (Conclusive Evidence) የሚያደርገው አይደለም፡፡ ይልቁንም ይኸው ማስረጃ የተሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ስለመሆኑ ማስረዳት ከተቻለ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው ሕጋዊ ግምት ሊስተባበል የሚችል (rebuttable legal presumption) መሆኑን ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአስተዳደር አካሉ የሰጠውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በሌላ ጊዜ መሰረዙ ከታወቀ ማስረጃው የተሰረዘበት አግባብ ከሕግ ውጪ መሆን ያለመሆኑ ተጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ ይኸው አካል ካርታውን አምክኗል ስለተባለ ብቻ ማስረጃው ክርክር ሳይደረግበት ተቀባይነት የሚያግኝበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የአስተዳደር አካሉ የሰጠውን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በሌላ ጊዜ ሲሰርዝ ማስረጃው የተሰረዘበት ሰው የአስተዳደር አካሉን እርምጃ ክርክር ሊያቀርብበት አይገባም፣ በፍርድ ቤትም ሊጣራ የሚገባው አይደለም ከተባለ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 40(1 እና 2) የተረጋገጠውን የንብረት መብት ዋስትና ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ነው፡፡ አንድ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1206 መሰረት በንብረቱ ላይ የሚያቀርበው የመፋለም ክስ ተገቢው መጣራት ተደርጎና የመከራከር መብቱ በአግባቡ ሳይጠበቅለት ውድቅ የሚሆንበት አግባብም የለም፡፡ ፍርድ ቤት እውነትን ለማውጣት ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋቸውን ስለ ማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህ

ድንጋጌዎች ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው የክርክሩ አካሄድ በተሟላ አኳኋን ሲመራ መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡ የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት ሕጋዊ አይሆንም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች የተያዘው የባለቤትነት ማስረጃ ወረቀት በየካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. የመከነን መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብ መደረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345(1(ለ)) ድንጋጌን የጣሰ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ቢሆንም የአመልካችን የባለቤትነት ማስረጃ አመከነ የተባለው ማስረጃ የመከነበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ፣ የቤቱ ትክክለኛ ባለቤት ማን እንደሆነ ግን ተገቢው ማጣራት ሳይደረግ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ቤቱ የአመልካች አይደለም ተብሎ መወሰኑ ፍርድ ቤቶቹ የክርክሩን አመራር ከላይ በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች አለመምራታቸውንና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195፣ 1196 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጉዳዩን ያለመመልከታቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጡት የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ድንጋጌዎች በማይደግፋትና የፍርድ አካሄዱ ባልተሟላበት ሁኔታ በመሆኑ በየእርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ውሣኔ እና ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሊሻሩ የሚገባና የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉንም መከራከሪያ ነጥቦችንና የአመልካችን የባለቤትነት መብት አምክኗል የተባለው ማስረጃ የመከነበትን ሕጋዊ አግባብ እንዲሁም በአጠቃላይ የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለቤት ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝና ተገቢውን ማጣራት ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ውሳኔ እንዲሰጡበት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 58891 ጥቅምት 12 ቀን 2003 ዓ.ም የተሠጠው ትዕዛዝ፣ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 78798 መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 135792 ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡

2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 135792 ክርክሩን ቀጥሎ አመልካች አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት ደብተር 1ኛ ተጠሪ የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. ያመከነበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን፣ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት ማን እንደሆነ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን ማስረጃዎችን በመስማትና ተገቢነት አላቸው የሚሏቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ በማስቀረብ ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ ይሠጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ.70801

የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፎዚያ ቃዲ - የቀረበ የለም

መዝገቡ የተቀጠረው፤- ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የፍ/ቤት ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ክልል ወሰን ሊያልፍ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት በመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በሥር የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በግዥ ባገኘሁት የንግድ ድርጅት ላይ የአሁን ተጠሪ ሁከት የፈጠሩብኝ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ መሥርቷል፡፡

ተጠሪም ባመለከተው ክርክር የተነሳበት ንብረት ሊገመት ስለሚቻል ተገምቶ ተገቢው የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት ሊቀርብ ሲገባ ይህንኑ ሥርዓት አሟልቶ የቀረበ አይደለም፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረበው ውል የብድር እንጂ የሽያጭ አይደለም፡፡ መፃፍ ስለማልችል በተንኮል የተዘጋጀ ካልሆነ በቀር በእኔ የተደረገ አይደለም ስለሆነም ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ በህግ ፊት በማይፀና ውል ንብረቱ በእጅ ገብቷል ማለት ስለማይቻል እና በህግ ማሟለት የሚገባውን ሂደት ባላሟላ ውል ደግሞ በሁከት ክስ ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ስለሆነም ክሱ በፍ/ብ/ሥ./ሥ/ሕ/ቁ 33(2) መሰረት ውድቅ ነው የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

በዚህም የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት በበላይ ፍ/ቤቶች የሰበር ሰሚ ችሎቱን ጨምሮ በየደረጃው ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ዳኝነት ላይ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚልበትን ዝርዝር ነጥቦች አመልካች በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ የተነሳ ሲሆን፤ ተጠሪም ከላይ በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው ነጥብ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን አጠናቀዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በከሳሽነት የተሰየመ ወገን አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጄ ገብቷል በይዞታ ላይ እያለ ሁከት ተፈጠረብኝ የሚል ክስ ትክክለኛውን የሁከት የህግ ፅንሰ ሀሳብ ተከትሎ ማቅረቡ ከተረጋገጠ፤ ለዚሁ ክስ በተከሳሽነት የተሰየመው ወገን ከተሰማ በኋላ በፍ/ቤቱ ሊሰጥ የሚገባው ዳኝነት ሁከት ተፈጥሯል ይወገድ፤ ወይም የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት የሚወሰን እንጂ በከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ወይም የሚያስችል ምክንያት አይኖርም፡፡ ከሳሹ የክሱን ምክንያት ዘርዝሮ ሊያገኝ የሚገባውን ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 224 ሲጠይቅ፤ ውሳኔው ይህንኑ የጠየቀውን ዳኝነት ማግኘት የሚቻል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለይቶ ማዘዝ ስለሚገባ የወረዳው ፍ/ቤት ሁከት የተፈጠረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ካለ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት መወሰን ሲገባው ከዚህ አልፎ በሌላ የክርክር መስመር ታይቶና ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ሁሉ አካቶ ያለ ቦታው የሽያጭ ውሉ ዋጋ ያለው ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ዳኝነት መስጠቱ ከተጠየቀው ዳኝነት ክልል የወጣ በመሆኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካችም በክስ ማመልከቻው ዘርዝሮ ያቀረበው እና የጠየቀው ዳኝነት ተዳምሮ ሲታይ በሽያጭ ውል ምክንያት በእጁ የገባው የንግድ ድርጅት በተጠሪ ተወስዶበት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 226 (3) እንደተመለከተው የተወሰደን እና ተለይቶ የታወቀን ንብረት ለማስመለስ የተፈለገ እንደሆነ የዚህኑ ንብረት ዋጋ ተገምቶ የሥረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ተገቢውን በመክፈል ክሱን አቅርቦ በዚሁ የክስ መስመር ተገቢውን ክርክርና ንጥጥር ተደርጎ ተገቢውን ዳኝነት ማግኘት ሲገባ በሥር የወረዳው ፍ/ቤት ክስ የቀረበበት መንገድ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 እንደተመለከተው በሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚገባው ጉዳይ በንብረት ላይ የተፈጠረን ሁከት ለማስቆም (cessation of intereference) ወይም ከሁከት መፍጠር ተግባሩ እንዲታገድ (injuction) ለመጠየቅ እንጂ የተወሰደን ንብረት እንደገና ወደ እጁ ለማስገባት የሚያስችል አይደለም፡፡

ከእነዚህ ሁለት ሐተታዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በዚህ ጉዳይ የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45352 በ26/4/03፤ ይግባኝ ሰሚው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10876 በ16/5/2003 ዓ.ም. እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 129205 በ11/08/2003 ዓ.ም የሰጡት ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ንብረት በሽያጭ ውል ካገኘ በኋላ በተከሳሽ ድርጊት ከእጁ ወጥቶ ከተገኘ ወይም በተከሳሽ ቁጥጥር ሥር ይገኛል ካለ የህንኑ የሽያጭ ውል ያለውን መነሻ አድርጎ ንብረቱን መልሶ ወደ እጁ ለማስገባት እንደ ሥርዓቱ ዳኝነት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ የሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ሳቢያ ለወጣው ማናቸውም ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 57186

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ሶስና ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ከፈሉ ታረቀኝ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገን የባለሃብትነት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ክልለ ወስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 031 የሆነ ቤት በውርስ ከአባታቸው ያገኙትና የተላለፈላቸው መሆኑንና የአሁኑ ተጠሪ ይገባኛል በማለት የያዘባቸው መሆኑን ገልፀው ቤቱ የግል ቤታቸው መሆኑ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ ቤቱ የተጠሪ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ተጠሪ ከስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ጠቅሶ ሲያቀርብ በፍሬ ነገር ደረጃ ክርክር ደግሞ አከራካሪው ቤት በአዋጅ የተወረሰና ለተጠሪ የባለቤትነት ደብተር የተሰጣቸው ከአሰራርና ከደንብ ውጪ በመሆኑ ደብተሩ ስልጣን ባለው አካል መመዘኑንና በተሰረዘ ደብተር ደግሞ ተጠሪ ሊያገኙ የሚችሉት መብት የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች በፍርድ ኃይል መብቱን ከአጣ በኋላ የአከራካሪው ቤት የተጠሪን ባለሃብትነት የሚያሳይ ማስረጃ በአስተዳደር አካሉ መክኗል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ቤቱን አመልካች ለተጠሪ ለቆ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በሕግ አግባብ ተወርሶ በአመልካች የሚተዳደር ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የቤቱ ባለመብት የሚያደርጋቸው ማስረጃ በሌለበትና የነበረውም በተሰረዘበት ሁኔታ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወረቀት የተሰረዘ መሆኑ እየታወቀ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት

እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ተጠሪ በፅሑፍ በሰጡት መልስ አከራካሪው ቤት በውርስ ተላልፎላቸው በሕግ አግባብ የባለቤትነት ደብተር የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ አመልካች በፍርድ ሃይል መብቱን ያጣ መሆኑ ተረጋግጦ በተሰጠው ውሣኔ ደብተሩ ተሰርዟል በሚል ምክንያት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት የሚችልበት አግባብ የለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲፀናላቸው ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በፅሑፍ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት አመልካች ቤታቸውን ያላግባብ የያዘባቸው መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን አመልካች ደግሞ ቤቱን በሕግ አግባብ የያዘው መሆኑን ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑን ፣ የስር ፍርድ ቤትም አከራካሪው ቤት ባለቤትነት የማን ነው? የሚለውን ጭብጥ ከያዘ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ አከራካሪውን ቤት ተጠሪ በውርስ ከአባታቸው ያገኙት መሆኑን ፣ ይህን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃም ያቀረቡ መሆኑን ፣ ተጠሪ ከሌላ ግለሰብ ጋር ባደረጉት ክርክርም ቤቱ የተጠሪ መሆኑን ተረጋግጦ ከመወሰኑም በላይ አመልካች ውሣኔው መብቱን ይነካል በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ሳይቀበለው የቀረ በመሆኑን ፣ ይህ ከሆነ በኂላ አመልካች ተጠሪ በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትንና ሚያዚያ 01 ቀን 1994 ዓ.ም. ተሰጠኝ በማለት ያቀረቡት የካርታ ቁጥር 9/05531 መሰረዝ በሕግ አግባብ የተጠሪን ባለሃብትነት ቀሪ የሚያደርግ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱን ነው፡፡ አመልካች ቤቱ በሕግ አግባብ የተወረሰ ስለመሆኑ ገልፆ በዚህ ረገድም ማስረጃ ያለው መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩንም ከውሣኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ ክርክሩ በይዘቱ አመልካች ቤቱን ያላግባብ ይዟል የሚለውን የተጠሪን ክስ መሠረት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀድመው ከሌላ ግለሰብ ጋር በአደረጉት ክርክር አመልካችም ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ክርክሩ ተቀባይነት አጥቶ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ነኝ በማለት የአፈጻጸም ክስ ያላቀረቡ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቱም አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 99213 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታውን አቅርቦ ተቀባይነት አጥቷል በማለት በፍርድ ሐተታው ላይ ያሰፈረው አገላለፅ የአመልካችና የተጠሪ ማስረጃዎች ተሰምተው ክርክሩ ተደርጎ ፍርዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360 መሠረት የማይለወጥ ነው ተብሎ የፀና መሆኑን የሚያሳይ አለመሆኑን የማያስገነዝበን ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ ራሳቸው ክስ ሲመሰርቱ በአመልካች ላይ በአዲስ መልክ ቀጥታ ክስ ማቅረባቸውም በአመልካች ላይ ቀድሞ ያረፈ ፍርድ መኖር ያለመኖር ላይ ጥያቄን የሚያስነሳ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ማጣቱን ሳይሆን ይኸው አቤቱታ ተቀባይነት ያጣበት ስርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 359 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የተስተናገደ መሆን ያለመሆኑን፣ ተጠሪ ከሌላ ግለሰብ ጋር አደረጉ የተባለው ክርክርና የተሰጠው ውሣኔ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ሲያቀርብ የተለወጠ መሆን ያለመሆኑን የሚገልፅ መሆኑን ያለመሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባ ነበር ፡፡ ይኸው ግልጽ አለመሆኑ በእርግጥም አመልካችም በሕግ አግባብ በተካሄደው ክርክር ተሸናፊ ከሆነ በሁዋላ በስራው ባገኘው ሥልጣን በመጠቀም ካርታውን ማምከኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ

እንዳይታይ የሚያደረግ ሁኖ ነው፡፡ ቀድሞ የተወሰነ ውሣኔ ካለም ተጠሪ በአዲስ መልክ ክስ የአቀረበቡት ምክንያትም ሊጣራ የሚገባው እና ሥነ ሥርዓታዊ መሆኑ ምላሽ የሚያስፈልገው ነበር፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያስፈረዱት ፍርድ የሌለ መሆኑን አምነው አዲስ ክስ ከአቀረቡ ደግሞ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው የቤቱ ባለቤት ማን ነው የሚለው ነጥብ ሁኖ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች መሰማትና ተገቢ ሆኖ ከተገኘም ፍርድ ቤቱ በራሱ መነሻነት ፍሬ ነገሩን በማጣራት ትክክለኛውን ፍርድ መስጠት ነው፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአስተዳደር አካሉ የሚሰጠው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ ማረጋገጫው የተሠጠው ሰው የምስክር ወረቀቱ ለተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195/1/ ድንጋጌ ከሰፈረው ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ሕጋዊ ግምቱ ሊስተባበል የሚችል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ጋር ተዳምሮ ሲነበብ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ደምዳሚ ማስረጃ (conclusive evidence) ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች አለ የሚል ወገን በማናቸውም ማስረጃ ሊያስተባብለው የሚችለው ማስረጃ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የአስተዳደር አካሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 መሠረት የሰጠውን የባለሃብትነት ማረጋገጫ ደብተርን በሌላ ጊዜ ከሰረዘው ይኸው ተግባሩ በፍርድ ቤት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/2/ እና 37 ድንጋጌዎች አንፃር ተዳምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ አስተዳደር አካል ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው አንዴ የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር ከሰረዘ ይኸው አካሄድ ሕጋዊ አይደለም የሚለው ሰው በፍርድ ቤት መብቱን ለማስከበር ክስ ሊያቀርብ የሚገባና ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ እና የንብረት ባለቤትነት መብትን ከሚጠብቁ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በአዲስ መልክ በቀረበው በተጠሪ ክስ ላይ ተጠሪ አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መሰረዙን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን ክሱ በአዲስ መልክ የቀረበ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ተጠሪ አለኝ የሚሉትን ካርታ የሰረዘው በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርአትና አሰራር ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ በግራ ቀኙ ማስረጃ እና ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ተጣርቶ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ፣ 1196 እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የንብረት መብት ሕጎች ጋር ተዛምዶ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ሁኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ አዲስ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ወደ ጎን በመተው ወይም ቀድሞ ተጠሪ ከሌላ ግለሰብ ጋር ሲያደርጉ በነበሩት ክርክር በአመልካች ላይ የተሰጠው ውሣኔ አመልካች የቤቱ ባለሃብት አይደለም የሚል መሆን ያለመሆኑን በግልጽ ሳያረጋግጥ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ ተብሎ መወሰኑ የክርክሩ አካሄድ በተሟላ ሁኔታ ተከናውኖና ተጣርቶ ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አንድ ክርክር በተሟላ የሥነ ሥርዓት አካሄድ ካልተመራ ደግሞ በውጤቱ የተከራካሪ ወገኖችን መሰረታዊ መብት የመጎዳት አጋጣሚ የሰፋ እንዲሆን የሚያደረግ መሆኑ የሚታመን ስለሆነ ተቀባይነት የሌለውና መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባውና በፍሬ ነገር ደረጃ በተገቢው መንገድ ያልተጣሩ ነጥቦች ተጣርተው ጉዳዩ እንደገና በስር ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ማድረጉ ተገቢ ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77189 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91229 ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ.ም. በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 77189 እንዲቀጥል በማድረግ በቤቱ ላይ አመልካችን ባለመብት እንዳይሆን በሕጉ አግባብ ተመርቶ የተሰጠ ውሣኔ መኖር ያለመኖሩን ፣ የቤቱ ሕጋዊ ባለሃብት ማን እንደሆነ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን በመስማትና ተገቢውን ማጣራት ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ ቁ. 65140

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- ወ/ሮ በላይነሽ ቢያድግልኝ ቀረበች፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቴር ገበሬ አልቀረበችም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኮንዶሚኒየም ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ በመጠየቅ በቀረበው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው አመልካች ስትሆን፣ ከተጠሪ ጋር ያደረገችው የቤት ሽያጭ ውል የኮንደሚኒየም ቤት ለተወሰኑ ዓመታት በሽያጭ እንዳይተላለፍ የሚከለክለውን ሕግ በመቃረን የተደረገ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንዲፈርስላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪ በበኩልዋ ለክሱ በሰጠችው መልስ ውሉ የሚፈርስበት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ ከዚህ ሌላ ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር በመመርመር ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች በ22-11-2003 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታ አቅርባለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የቤቱ ሽያጭ ውሉ አይፈርስም የተባለው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርመረናል፡፡

አመልካች  ውሉ መፍረስ አለበት ለሚለው ክርክር መሠረት ያደረገችው ዋነኛው ነጥብ የሕግ ክልከላ ነው፡፡ በእርግጥ ውሉ የተደረገው በስህተት እና በድንገተኛ ተንኮል ነው የሚል መከራከሪያም እንዳለት ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ሕጉ በኮንዶሚኒየም (በጋራ ህንፃ) ላይ ቤት በእጣ የደረሰው ሰው እጣው ከደረሰው ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ ቤቱን መሸጥ አይችልም የሚል እንደሆነ በመግለጽ ስለመከራከርዋም ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራል

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ያልተቀበለው መሸጥ የሚከለክል በሕግ ደረጃ የወጣ አዋጅ የለም፤ የሚከለክል ደንብ ወይም መመሪያ አለ ቢባል እንኳን ከሣሽ (አመልካች) ቤቱን ለተከሣሽ (ተጠሪ) በሽያጭ ለማስተላለፍ ስምምነትም በሰጠችበት ወቅት የዚህ ግንዛቤ እንደነበራት ግልጽ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት እንደሆነ ውሣኔው ያመለክታል፡፡ አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የምትለው በዚህ መልክ የተሰጠውን ውሣኔ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩልዋ ለሰበር አቤቱታው በሰጠችው መልስ አመልካች የጠቀሰቻቸው አዋጅም ሆነ ደንብ ቤቱን እንዳይሸጥ በግልጽ አይከለክሉም፡፡ አመልካች ቤቱን የሸጠችልኝ ወዳና ፈቅዳ በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክራለች፡፡

ከቀረበልን ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው በኮንዶሚኒየም (የጋራ ቤት ህንፃ) የተያዘ ቤት እንዳይሸጥ ለተወሰኑ ዓመታት ክልከላ ያደርጋል ተብሎ የተጠቀሰው "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፖብሊክ የጋራ ህንፃ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር 370/1995" ነው፡፡ ይህ አዋጅ በእርግጥ በጋራ ህንፃ ቤት በእጣ የደረሰው ቤቱ ለሌላ ሰው ስለሚሸጥበት ሁኔታ በሚመለከት በግለጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን የከተማው አስተዳደሮች አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ለማውጣት እንደሚችሉ በአንቀጽ 42 ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ማስቀመጡን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1281 እስከ ቁጥር 1360 ያሉት ድንጋጌዎች በአዋጅ መሠረት በሚስተዳደር የጋራ ህንፃ ላይ ተፈፀሚ እንደማይሆኑ እንደዚሁም ማንኛውም ሕግ፣ ልማድ ወይም አሠራር በአዋጅ የተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው በአንቀጽ 43 ስለመደንገጉም ተመልክተናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የሚገኝበት የጋራ ህንፃ (ኮንዶሚኒየም) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚተዳደሩት አንዱ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ ቁ. 370/95 ተፈጻሚ የሚሆነው በአዲስ አበባ እና በድሮው ከተማ አስተዳደሮች ላይ እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 3 የተደነገገ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤትም በአዋጁ በተሰጠው አዋጁን ለማሰፈጽም የሚረዳ ደንብ የማውጣት ስልጣን መሠረት አዋጅ ቁ. 19/97 አውጥቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(2) እንደተመለከተውም በኮንዶሚኒየም ቤት ያገኘ (በእጣ የተሰጠው) ሰው የቤቱን ጠቅላላ ዋጋ ከፍሎ ቢያጠናቅቅ እንኳ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ (በእጣ ካገኘ) በኃላ አምስት ዓመት ሲሞላው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን የተለመደ አሠራር ወይም ሕግ በአዋጁ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፀሚነት እንደሌለውም በአንቀጽ 21 ተመልክቷል፡፡

እንደሚታየው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በወጣው አዋጅ የተቀመጠው የያዝነውን ክርክር የሚመለከተው ድንጋጌ ማለት ነው በኮንዶሚኒየም ቤት ያገኘ ሰው ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚችልበት አግባብ በሕግ ገደብ ተጥሎበታል፡፡ በእርግጥ ገደቡ በጊዜ (በዓመታት) የተወሰነ በመሆኑ ጊዜአዊ ቢሆንም፤ ጊዜው ከመድረሱ በፊት የሚደረገው ሽያጭ ግን ሕግን የጣሰ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለውሉ አመሠራረት በተመለከተ የተደነገገው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1678 አንድ ውል የሚፀና ውል ነው ሊባል የሚችለው በቂ ሲሆን እርግጠኛነት ባለው በሚቻልና ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው አከራካሪ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሃይለ ቃል ውሉ ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንዳለበት የሚገልጽ ነው፡፡ ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጪ የሆነ ነው በተባለ ጊዜም ውሉ ይፍርስ ዘንድ ለመጠየቅ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808(2) ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የውል ይውረስልኝ ክርክር ውድቅ ለማድረግ

የሰጠው ምክንያት ከዚህ አንፃር ሲታይ ሕጉን በአግባቡ ያለገናዘብ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል በሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት የተደረገ ስለመሆኑ ባለከራከረበት ሁኔታ አይፈርስም ተብሎ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31385 ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 110331 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ (የኮንዶሚኒየም ቤት) ውል በሕግ ክልከላ የተደረገበት ስለሆነ ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 67011

መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሾች

1. ወ/ሪት ሕሊና ፍቃዱ
2. መቅደስ ፍቃዱ } ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ጥሩነሽ ኃየሌ

2. አቶ ቴዎድሮስ መኮንን } በ2ኛ ተጠሪ ተወካይነት ቀረቡ

3. በአራዳ ክ/ከተማ የቀበሌ 03/09 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነገረፈጅ ናዝሬቱ ፈለቀ

ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባለሀብትነት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ የወላጅ እናታችን የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/09 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 615 የሆነ ከወላጅ አያቴ ከአቶ ወንድተገኝ በላይነህ በውርስ የተላለፈላትን የተፈቀደ ቤት ከሳሾች የእናታችን የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሾች መሆናችንን በፍርድ ቤት አረጋግጠናል፤ ቀደም ሲል የከሳሾች ወላጅ እናት በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ መስርተው ቤቱን እንዲለቁ የተወሰነባቸው ሲሆን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅሬታ አቅርበው በመዝ.ቁ.11399 በቀን 04-6-96 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ከሳሽ ደብተር ወይም ካርታ አውጥተው ቤቱን ለማስለቀቅ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ አውራሻችን ወ/ሮ ጣይቱ ከበደ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ በካርታ ቁ. አ03/09/0673 መስከረም 12 ቀን 1998 ዓ/ም የተሰጣቸው ሲሆን የቤትና ቦታ ግብር ከፍለዋል፡፡ ነገር ግን የከሳሾች አውራሽ በቤቱ ላይ ግብር እየከፈለች መሆኑን እያወቁ 3ኛ ተከሳሽ በህገ-ወጥ አሰራር ቤቱን በማከራየት የሚጠቀም ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የቤቱ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ከተሰጠበት መስከረም 12 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን እንዲለቁ ቢጠየቁም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንዲያስረክቡ እንደዚሁም የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡ ተከሳሾች በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ታዞ መልስ የሰጡ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ የሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው

ቤት የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤትን የመንግስት ባደረገው አዋጅ ቁ. 47/67 የተወረሰ ቤት በመሆኑ ከሳሾች በዚህ ቤት ላይ መብት የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ከሳሾች ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት በዚህ ቤት ላይ በ1998 ዓ.ም. የተሰጣቸውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ሲሆን ቀድሞ በዚሁ መልክ ተሰጥቶ የነበረው ካርታ መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰረዘ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበውን ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩም ያስቀርባል በመባሉ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሁፍ ሰምቷል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል አከራካሪ በሆነው ቤት ላይ የቀረበው የአመልካች የባለሃብትነት ጥያቄ ተሰጥቶ የነበረው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ተሰርዟል በማለት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ያደረጉት በአንድ በኩል የባለሀብትነት ማረጋገጫ ካርታ በሚመለከተው የአስተዳደር ባለስልጣን የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሀብት ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ እና በዚሁም መሰረት የአመልካቾች አውራሽ በ1998 ዓ/ም ካርታ በስማቸው በዚሁ አከራካሪ ቤት ላይ የተሰጣቸው በመሆኑ የዚሁ ቤት ባለሃብት ተደርገው የሚወሰዱ ስለመሆኑ በማመላከት በሌላ በኩል ደግሞ በ1998 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው ይሄው ካርታ የሚመለከተው መስተዳደር አካል ግራ ቀኙ በክርክር ላይ ባሉበት ወቅት መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰረዘ በመሆኑ ባለሃብትነታቸውን የሚያረጋግጠው ካርታ በመሰረዙ ምክንያት መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተነሳውን ክርክር ስንመለከት በእርግጥ አንድ የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠው የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሄንን የምስክር ወረቀት ለያዘ ሰው ባለሃብት ስለመሆኑ ግምት የሚያሰጠው ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1195/1/ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው አግባብነት በሌለው መልኩ በሆነ ጊዜ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል የሚቻል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1196 ስር የተደነገገ በመሆኑ እና ስራውን በአግባቡ ያልተወጣ የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ኃላፊነት ሊያስከትልበት የሚችል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1198 ስር ተመልከቷል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው አንድ ለማይንቀሳቀስ ንብረት የተሰጠ የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለሃብትነትን በተመለከተ የህግ ግምት የሚያሰጥ ቢሆንም በሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል፣ በተቃራኒው ከሚቀርቡት ማስረጃዎች ጋር ሊመዘን የሚችል እንጅ ማስተባበያ ሊቀርብበት የማይችል ወሳኝ /conclusive evidence/ ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ አንድ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ተገቢውን ስርዓት እና ደንብ መከተል እንዳለበት ሁሉ የተሰጠን የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲሰረዝ አግባብነት ያላቸውን ስርዓቶችን መከተል ያለበት ስለመሆኑ እና የዚህ አፈፃፀም ሂደትም በአግባቡ ስለመፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1195 እስከ 1198 ድረስ ካሉት ድንጋጌዎች ዓላማ፣ ይዘት እና መንፈስ

መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ በክርክር ላይ ባሉበት ወቅት ለአመልካቾች አውራሽ ተሰጥቶ የነበረው የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተሰርዟል በመባሉ ብቻ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ማድረግ ያለባቸው የቀረበው ክስ የባለሃብትነት ክርክር እስከሆነ ድረስ በግራ ቀኙ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች በመመዘን እና የካርታውን መምከን በተመለከተም የእርምጃው አግባብነት ባጠቃላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ተመዝኖ የሚታይ ሆኖ እያለ በንብረቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረው ካርታ በመምከኑ ብቻ ክሱን ውድቅ ማድረግ ከላይ የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ዓላማ እና ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት አከራካሪው ቤት የአውራሻቸው አያት የአቶ ወንድተገኝ በላይነህ የምርጫ ቤት እንጂ በመንግስት የተወረሰ ቤት አይደለም በማለት ሲሆን 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የተወረሰ ቤት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይም የበታች ፍ/ቤቶች አከራካሪው ቤት የተወረሰ ስለመሆኑ ወይም የተወረሰ ስላለመሆኑ ጭብጥ በመያዝ ያጣሩት ነጥብ የሌለ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሚያከራከረው ቤት የተወረሰ ስለመሆን ወይም አለመሆን ክርክር በተነሳ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ የሚቀርቡትን ማስረጃ በመመልከት የተወረሰ ነው ወይም ያልተወረሰ ቤት ነው በማለት ውሳኔ ሊሰጡበት የሚችሉ ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ይሄ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.24627 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ ፍ/ቤቶች በተመሳሳይ በዚህም ጉዳይ መወሰን የሚችሉ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍ/ቤቶች ከላይ እንደተመለከተው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ጭብጦች በመያዝ እና በግራ ቀኙ ማስረጃ ሳያጣሩ ውሳኔ መስጠታቸው በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.246 እስከ 248 ድረስ ያሉትን የጭብጥ አመሰራረት እና ክስ ማጣራትን በተመለከተ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው ብለናል፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የደረሱት ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ እና በማጣራት ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.95545 በቀን 17-5-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.76167 በቀን 11-8-2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪውን ቤት በተመለከተ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው መሰረት ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ እና በግራ ቀኙ ማስረጃ በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3.በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ 67631

ሚያዝያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የአቶ አሰፋ አባዲዮ ባለቤት እና ወራሾች - አልቀረቡም

**ወራሾች፡-**
1. ወ/ሮ ፅጌ ሽኔ
2. አቶ ዋሚ አሰፋ
3. አቶ እስጢፋኖስ አሰፋ
4. ወ/ሮ ሚሚ አሰፋ
5. ወ/ሮ ፋሲካ አሰፋ
6. አቶ ሱራፌል አሰፋ
7. ወ/ሮ ጫልቱ አሰፋ

} አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አቶ ጌታቸው ምንተስኖት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ንብረት ነው በሚል ንብረት ያስመለሰ ወገን፤ የንብረቱ አመላለስ አግባብነት የሌለው ሆኖ መገኘቱ ከተረጋገጠና ንብረቱ ወደ ባለቤቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ ከተደረገ ንብረቱ ያለአግባብ በዕጁ በቆየበት ጊዜ ንብረቱ ያስገኝ የነበረውን ገቢ ወይም የታጣ ገቢ ጭምር የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች መጋዘን ከአዋጅ ውጭ ተወርሶብናል በማለት በ1992 ዓ.ም አቤቱታ በማቅረባቸው ይህንኑ ንብረት ሰኔ 29 ቀን 1997 ዓ.ም ተረክበዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ንብረት ያለአግባብ ወደ አሁን አመልካቾች እጅ ሊገባ የቻለ መሆኑ ተጣርቶ እንደገና ወደ መንግስት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡

የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይህ መጋዘን ተገቢ ባልሆነ መንገድ በማስወሰናቸው የተነሳ ንብረቱ ሊያስገኝ ይችል የነበረውን ጥቅም በማስላት በጠቅላላው ብር 687,742.00 /ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሁለት/ ብር ይክፈሉ በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡

የአሁን አመልካቾችም በተከሳሽነት ንብረቱን ስልጣን ባለው አካል አስወስነን የተረከብነው በመሆኑ የታጣ ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት የለብንም፤ይመለስ በመባሉ ለታጣ ጉዳት ኃላፊ ልንሆን አይገባም፤ ለጉዳዩ አግባብነት ባለው አዋጅ አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት እንደ ከሳሽ አቀራረብ ከሆነ የታጣ ጥቅም ለመጠየቅ መብት አይሰጠውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአሁን አመልካቾች አውራሽ ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ ንብረቱ ተመልሶላቸዋል፣ በ1997 ዓ.ም ተረክበዋል፡፡ በተጭበረበረ ማስረጃ መሰረት የተወሰዱ ቤቶች በድጋሚ ወደ መንግስት እንዲመለሱ ለማድረግ በወጣው ህግ አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት ጉዳዩ ታይቶ ይኸው ንብረት እንደገና ወደ መንግስት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ተከሰን አልተቀጣንም ቢሉም ቦርዱ ለታጣ ጥቅም ሊጠየቁ የሚችሉ መሆኑን ገልፆ ወስኗል፡፡ በወንጀል ጉዳይም አለመጠየቅ የፍ/ብሔር ኃላፊነትን አያስቀርም የሚለውን ትንተና መሰረት አድርጎ ንብረቱን ያለአግባብ እንዲመለስ በማድረጋቸው ሳቢያ መንግስት ያጣውን ጥቅም የመተካት፤ የመካስ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ከወሰነ በኋላ የታጣውን ጥቅም በሚመለከት ብር 92,786 መሆኑን ለይቶ ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅድቆታል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበውም በዚህ አኳኋን የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለትና ምክንያቱን በመጥቀስ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ሲሆን፤ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሰው ጥፋተኛ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ለታጣ ጥቅም ኃላፊ መባላቸው አግባብ ነው አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለመለየት ሲባል ተጠሪ ቀርቦ በዚህ ነጥብ ላይ ክርክሩን በፅሑፍ አቅርቧል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ሁለቱም ወገኖች ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ካቀረቡት የተለየ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ ይህንኑ ክርክር ከስር ፍ/ቤቶች ዳኝነትና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ከአዋጅ ውጭ እንደተወረሰ በማስመሰል ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ታይቶ ንብረቱ ወደ አመልካቾች መመለሱንና በኋላ ግን በዚህ አኳኋን ያለአግባብ የተመለሱ የመንግስት ንብረቶችን እንደገና ለማስመለስ ሲባል በወጣው አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት የአመልካቾች ጉዳይ እንደገና ተመርምሮ ንብረቱን ወደ መንግስት እጅ እንዲመልሱ መደረጉን በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አከራካሪ ሆኖ የተገኘውና በሰበር ችሎት ጉዳዩ ቀርቦ እንዲተረጎም የተደረገበት ዋናው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 572/2000 አንቀጽ 6 እንደተመለከተው ያለአግባብ ንብረት ያስመለሱ ሰዎች ላይ

የወንጀል ክስ ሊመሰረትባቸው እንደሚችል እና ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኙም ከወንጀሉ ቅጣት በተጨማሪ መንግስት ያገኝ የነበረውን ጥቅም በማጣቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል በሚል መደንገጉ ለጉዳት ካሣ ጥያቄ በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት ቅድመ ሁኔታ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ይህንኑ አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን በቅድሚያ ለጉዳዩ በተለይ አግባብነት ባለው አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸው በማቆራኘት፤ ዐውደ ንባቡን መሰረት በማድረግ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አለአግባብ የተመለሱ የመንግስት ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቻለው ቀደም ሲል ንብረቱ በቂ ባልሆኑ ወይም ሐሰተኛ በሆኑ ማስረጃዎች ለአመልካቾች እንዲመለሱ ተደርጎ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ሁለተኛ አንቀጽ እና ንብረቶችን ለማስመለስ ኃላፊነት የወሰደውን አካል አዳዲስ ሥልጣንና ተግባር በሚዘረዝረው አንቀጽ 4 ንዑስ ቁጥር 6 ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የማስመለሻ ምክንያቶች አንድም በቂ ባልሆነ ምክንያት ወይም ደግሞ በሐሰተኛ ማስረጃ የተነሳ ተረክበውት የተገኙ እስከሆነ ድረስ ያለአግባብ ንብረት ያስመለሱ ሰዎች ሁሉ የወንጀል ክስ ይቀርብባቸዋል ማለት አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ የመንግስት ንብረት ወደ ግለሰቦች እጅ ሊገባ የቻለው በቂ ባልሆነ ምክንያትም ሆነ ወይም በሐሰተኛ ማስረጃ መሰረት ያለአግባብ እንዲመለስ የተደረገ የንግድ ድርጅት የተዘጋ ወይም ሊነጣጠል በማይችል ሁኔታ ከሌላ ንብረት ጋር የተቀላቀለ ከሆነ በርክክቡ ወቅት የነበረውን ንብረት ግምት ከእነ ወለዱ ለመንግስት እንዲከፈል ይደረጋል በሚል፤ የሚከፈለውም ወለድ የሚታሰበው ድርጅቱ ያለአግባብ ከተመለሰበት ቀን ጀምሮና በባንክ የማበደሪያ ወለድ ተመን መሰረት ይሆናል በማለት በአንቀጽ 5(2)(ለ) እና 5(3) ከተደነገገው መረዳት የሚቻለው በወንጀል ሊያስጠይቅ በማይችል በቂ ባልሆነ ምክንያት ንብረቱ የተመለሰ መሆኑ ቢታወቅም እንኳ ንብረቱን ከመመለስ ጋር ወለድ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ወለድ ደግሞ የታጣ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ለማስከፈል ሲባል እንደማካካሻ በህጉ የተቀመጠ አንዱ መንገድ ስለመሆኑ ስለ ውልና ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነት በህግ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዋጁ አንቀጽ 6 በወንጀሉ ጥፋተኛ ሆነው ከተጣለባቸው ቅጣት በተጨማሪ መንግስት ያገኝ የነበረውን ጥቅም በማጣቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል በሚል የተደነገገው በፍ/ብሔሩ ጉዳይ የታጣ ጥቅምን ለመጠየቅ በወንጀሉ ጉዳይ አስቀድሞ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት ቋሚ ማሚያ መስፈርት ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ አይችልም፡፡

ይልቁንም በዚሁ አንቀጽ 6 በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ከመገኘትና ከመቀጣት ባሻገር የጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ የሚደረጉት ንብረቱን ተረክበው በእጃቸው አድርገው የተገለገሉበት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በንብረቱ ሳይገለገሉ፤ ነገር ግን ንብረቱ ያለአግባብ እንዲመለስ በማስደረጉ ረገድ ተባባሪ ሆኖ የተገኘን ማናቸውም ሰው ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ በድንጋጌው ስር በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና የቅጣት መጣል ያለአግባብ በሐሰተኛ ማስረጃ ንብረት የማስመለስ ተግባር ሊያስከትል የሚችለውን የጎላ ኃላፊነት ለማመልከት እንጂ ምንጊዜም እና በማናቸውም ምክንያት የጉዳት ካሳ ክስ ለማቅረብ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና ቅጣት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊወሰድ የሚገባ መሆኑን ሊያሳይ የሚችል ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ 6 የወንጀል ኃላፊነትን በሚመለከት የተጠቀሰው አንድን ንብረት አንድ ሰው ያለአግባብ ወስዶ በተገኘ ጊዜ ንብረቱ በእጁ በነበረበት ጊዜ ያለአግባብ በበለፀገበት መጠን ከመካስ ጋር ንብረቱን የመመለስ ግዴታ አለበት በሚል በአጠቃላይ በፍ/ብሔር ህጉ የተመለከተውን ኃላፊነት የተካ ልዩ የሆነ አዋጅ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 572/2000 አንቀጽ 6 የተመለከተውን የወንጀል ኃላፊነት ለፍትሐብሔሩ ኃላፊነት ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ አድርገው በመተርጎም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፑብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/80 አንቀጽ 10 መሰረት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድን የመጨረሻ ፍርድ ሊያርም የሚችለው በፍርዱ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 60439 የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት አፅንተናል፡፡
2. አመልካች በሰበር ደረጃ ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ የሰበር ክርክር ሳቢያ ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ በየግላቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 69160

ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች:- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዶፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች:-** አቶ ሶሬሳ ጋሪ ከጠበቃ አቶ መልካም አለማየሁ ጋር ቀረቡ
**ተጠሪ:-** አቶ አብርሃም ፍቃዱ - ቀረቡ
መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው አመልካች ለተጠሪ የሰጠሁትን ገንዘብ ብር 280,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር) ይመልስልኝ በማለት ያቀረበው የክስ አቤቱታ እና የጠየቀው ዳኝነት የገንዘብ አደራን መነሻ ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመለየትና ጉዳዩን ከማስረጃ አቀባበል ስርዓት አንፃር ተመልክቶ ተገቢውን የህግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡ የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ የአሁኑን አመልካች መኪና ለመግዛት ወስኜ እያለ በመካከሉ ወደ ቻይና ሀገር ለመሄድ በማቀዴ የመኪናውን ዋጋ ተጠሪ እንዲከፍሉልኝ ብር 280,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር) በአደራ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ብሩን እንዲከፍሉኝ ብጠይቅ ዛሬ ነገ እያሉ ፍቃደኛ ስላልሆኑ ይመልሱልኝ በማለት በአሁን ተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ የሥጋ ዝምድና፣ የሥራ ሽርክና ወይም የውክልና ግንኙነት ሳይኖረን ይህንን ብር ሰጠሁ የሚሉት ሐሰት ነው፡፡ አልሰጡኝም፡፡ በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ከዋናው የክርክር ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር ላይ በመመርኮዝ ከሳሽ የአሁን አመልካች ገንዘቡን በአደራ ሰጠሁ የሚለው ገንዘብ ተቀባዩ እንዲገለገልበት ፈቅዶ ከሆነ የግራ ቀኙ ክርክር በፍ/ብ/ህ/ቁ 2782(1) እንደተደነገገው የብድር ውልን በሚመለከቱት ደንቦች መሠረት ሊገዛ ወይም ሊወስን የሚገባው ነው፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ገንዘቡን ለተከሳሽ ለአሁን ተጠሪ የሰጠሁት የመኪና ግዥ ዋጋ እንዲከፍሉልኝ ነው በሚል ምክንያት ሰጠሁ ካሉ ገንዘቡ ሳይታሸግና ሳይዘጋበት መሰጠቱን ያሳያል ገንዘብ ሳይታሸግና ሳይዘጋበት ተሰጥቶ ከሆነ ደግሞ ገንዘብ ተቀባዩ እንዲገለገልበት ተፈልጎ እንደተሰጠ ስለሚቆጠር ይህ የግራ ቀኙ ጉዳይ ስለ ገንዘብ ብድር በሚመለከቱት ደንቦች መሠረት ሊጣራ የሚገባው ነው፡፡ ከእነዚህም ደንቦች መካከል በፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 እንደተመለከተው ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የተሰጠን የብድር ገንዘብ ለማስረዳት መቅረብ የሚገባው የማስረጃ አይነት የጽሑፍ እንጂ የሰው ምስክርነት ቃል አይደለም፡፡ ከሳሽ ክሱን ለማስረዳት የቆጠረው የሰው ማስረጃ ስለሆነ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም ስለዚህ ክሱ ወድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት ተቀባይነት የለውም በሚል በመዘጋቱ ምክንያት ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ ችሏል፡፡

በሰበር ቅሬታው ላይ የአሁን አመልካች ያቀረቡት እና በሰበር ፍ/ቤቶች ዳኝነት ያላረፈበት አንዱ የክርክር ነጥብ ለዚሁ የፍታብሔር ብይን መነሻ በሆነው ገንዘብ ምክንያት  በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ቀርቦ ጉዳዩ ሲታይ ከቆየ በኋላ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ተጥሎበታል፡፡ ይህንን ማስረጃ በክሱ ሂደት ለስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በማስረጃነት ባቀርበውም ፍ/ቤት አልተመለከተልኝም የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሥር ፍ/ቤት ያልተሰማና ያልታየን ማስረጃ እንደ አዲስ በሰበር ደረጃ ባለ ክርክር ለማቅረብ ስነ ስርዓት ህጉ ሰለማይፈቅድ ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በቀር ሁለቱም ወገኖች በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡትን ክርክር የሚያጠናክር በመሆኑ በድጋሜ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ አቤቱታ ከተገለፁት የፍሬ ነገር ዝርዝር ጉዳዮች ገንዘቡን በአደራ ሰጥቻቸዋለሁ የሚል ሀረግ እንደታከለበት ይመልከት እንጂ ዝርዝር የክስ ምክንያቱን ማየት እንደሚቻለው ገንዘቡን ለተጠሪ ሰጠሁ የሚሉበት ምክንያት እራሳቸው አመልካች ለፈፀሙት ውልና ግዥ ለክፍያ እንዲውል ክፍያውን እንደ አመልካች ሆነው እንዲፈፅሙላቸው እንጂ ገንዘቡ የተሰጠው ተጠሪ በእጃቸው አድርገው በአደራ እንዲያቆዩላቸው  የሚገልጽ አይደለም፡፡ አደራ የሚለው ቃል መካተቱ የክሱን ጉዳይ በፍ/ብሔር ህጉ የተመለከተውን የአደራ የህግ ጽንስ ሀሳብ ሊያመለክት የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች እንደ አባባላቸው ገንዘቡን ለተጠሪ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም? የሚለውን ክርክር ለማስረዳት የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 መሰረት ዘርዝሮ ያቀረባቸው የሰው ማስረጃዎች ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ ክሱ ከጅምሩ በህግ በተፈቀደ ማስረጃ ተደግፎ እንዳልቀረበ ተቆጥሮ ወድቅ ነው መባሉ የክሱን አርእስተ ጉዳይ እና ጉዳዩን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃና የማስረጃ አቀባበል ስርዓትን ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ እንደገለጸው ጉዳዩን የሚያስረዳልኝ በወንጀል ችሎት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔና ቅጣት የስር ፍ/ቤት ሊመለከትልኝ አልቻለም በማለት የአሁኑ አመልካች ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 222 እና 223 በሚያዘው መሠረት የቀረበ አለመሆኑን ተረድተናል፡፡ ይልቁንም ክሱ ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀረበ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በወንጀል ችሎት ጥፋተኛ መባሉ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ሆኖም ይህ ማስረጃ እንደ ሥርዓቱ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ግራ ቀኙ በየፊናቸው ለሰበር ሰሚ ችሎት ለማስረዳት ካቀረቡት የጽሑፍ ክርክር መገንዘብ እንደተቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የፍ/ብሔር ክስ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ብይን ሰጥቶ የነበረ መሆኑንና ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ይህንኑ እርሱ በሌለበት እንዲታይ የሚያደርገውን ብይን ለማስነሳት ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ በሆነ በወንጀል እስር ምክንያት ማረሚያ ቤት የነበረ መሆኑን በማስረዳት አቅርቦት በዚህም ሳቢያ ጉዳዩ እርሱ ባለበት ታይቶ ሊወሰን መቻሉን አስመልክቶ የአሁን አመልካች ያቀረበውን ክርክር የአሁን ተጠሪ አላስተባበለም፡፡ በዚህ አኳኋን በእራሱ ተከሳሽ በነበረው ወገን የቀረበን ማስረጃ እኔ ሳላውቀው እንደ አዲስ የቀረበ ማስረጃ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ  239 የተመለከተውን ሥርዓት የሚያሟላ አይደለም በሚል የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የማስረጃ ማቅረቢያ ጊዜንና ደረጃ አስመልክቶ የተመለከተውን ሥርዓት እና የህጉን መነሻ ዓላማ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡

አመልካችም ቢሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት ለማረጋገጥ የቀረበን ማስረጃ በአንድ በኩል ከቁጥር 78 አንፃር የበኩሉን ክርክር ማቅረብ ወይም ማስረጃነቱን የሚቀበለው ከሆነም ሲያየው ጉዳዩ ያለውን አግባብነት በማሳየት እንደ ሥርዓቱ በማስረጃ እንዲታይለት መጠየቅ እንጂ በቁጥር 78 መሠረት ተከሳሹ ባለበት ክርክሩ ይታያል ወይስ አይታይም የሚለው ጭብጥ ለመለየት በተደረገው የክርክር ደረጃ ማስረጃው እኔንም እንደሚጠቅመኝ ገልፀው ተከራክሪያለሁ ሆኖም ፍ/ቤቱ አለተመለከተልኝም የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የእራሱን የክርክር አቀራረብ ጉድለት ከሚያሳይ በቀር ፍ/ቤቱ የፈፀመውን የጉዳይ አካሄድ ጉድለት አይመለከትም፡፡

ይሁን እንጂ ማስረጃው ከፍ/ብሔር ክርክሩ ዘግይቶ መገኘቱን ክርክሩ ለደረሰበት ደረጃ እና ማስረጃው ለክርክሩ ካለው አግባብነት አንፃር በማየት ጉዳዩን ሲመለከተው የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ይህንኑ ማስረጃ በማቅረብ ረገድ የፈፀመውን የአቀራረቡ ሥርዓት እንዲታረምና እንዲስተካከል በማድረግ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል መቀበል ይችል የነበረ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 137፣256 እና 91 ደንጋጌዎች አመልካች ናቸው፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይህ ጉዳይ በይዘቱ ገንዘብ አደራ ክርክር እንደሆነ በመቁጠር ይህንንም ክርክር ለማስረዳት የቀረቡት የሰው ማስረጃዎች ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም በማለት የተሰጠው ትርጉም መሰረታዊ የሥነ ሥርዓት ህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፤ እንዲሁም የአሁን ተጠሪ በዚሁ ጉዳይ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበትና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠበት የወንጀል ፍርድ ለፍትሐብሔሩ ክርክር በማስረጃነት ቀርቦ ሊታይ የሚችልበት ሥርዓትና አግባብ እያለ ሳይታይ በዝምታ መታለፉም ከማስረጃ አቀባበል ሥርዓት አንፃር የታለፈ ጉድለት በመሆኑ እነዚህ በጉዳዩ አመራር ሂደት የተከሰቱት ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለቶች የታረሙ ሆኖ በማግኘታችን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስ አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት የሚከለተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 34280 መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በመ/ቁ. 107513 ግንቦት 2 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፍርድ ሐተታው እንደተገለፀው የግራ ቀኙ ገንዘብ ነክ ክርክር የአደራ ገንዘብ የሚመለከት ሳይሆን የአሁን ተጠሪ የመኪና ግዥ ዋጋ እንደ አመልካች እንደ ሥር ተከሳሽ ሆኖ ለመክፈል ብር 280,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር) ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የሚመለከት በመሆኑና ይህንንም በሰው ማስረጃ ለማስረዳት ህግ ስለማይከለክል እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ጉዳዩን ለማስረዳት የቀረበውን የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ በማስረጃነቱ ተይዞ በተሟላ የክርክር አካሄድ ግራ ቀኙን በማሰማት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መዝገቡን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡
3. ይህ የሰበር ክርክር ስለተገኘው ወጪና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ 67691

ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር

ነገረ ፈጅ አቶ አማረ ከፍያለው - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ አለምፀሐይ ወልዴ ጠበቃ አቶ ፀጋዬ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በሁከት ይወገድልኝ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበችው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በቂርቆስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ቁጥሩ 059 ከመንግስት ተከራይተው ብቻቸውን በመኖር ላይ እያሉ አመልካች ነሐሴ 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብደቤ በባለቤትሽ ስም የመኖሪያ ቤት ያለሽ በመሆኑ የያዝሽውን የቀበሌ ቤት እንድትለቂ የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል፡፡ ስለዚህ ባል ያለኝ ወይም የሌለኝ መሆኑን በአግባቡ ሣያረጋግጥ ቤቱን እንድለቅ ማስጠንቀቂያ በመፃፍ የፈጠረብኝ ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ ጋር ያለን ከቤት ኪራይ ውል የመነጨ ግንኙነት ነው፡፡ ከሣሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ሁለት ልጆች በትዳር ከወለዱላቸውና አብረዋቸው በሚኖሩት ባለቤታቸው አቶ ክፍሉ ኢሣያስ ስም ቤት እንዳላቸው ስለተረጋገጠ ከቀበሌ የተከራዩትን ቤት እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ መስጠታችን ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ (ከሳሽ) በባለቤታቸው ስም መኖሪያ ቤት ያላቸው በመሆኑ አመልካች (ተከሣሽ) የቀበሌውን ቤት እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ተገቢ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰረዞታል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለከተማው የሰበር ችሎት አቅርበዋል የከተማው የሰበር ችሎት ተጠሪ ከአቶ ክፍሉ ኢሳያስ ጋር ጋብቻ ያላቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በባለቤታቸው ስም የግል የመኖሪያ ቤት እንዳላቸው ተረጋግጦ እያለ ከአመልካች የተከራዩትን ቤት እንዳይለቁ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ከአቶ ክፍሉ ኢሣያስ ጋር ጋብቻ ወይም የጋብቻ ሁኔታ የሌለን መሆኑ ስለተረጋገጠ የከተማው ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በተጠሪ ላይ ሁከት ፈጥሯል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ የሚኖሩበት የቤት ቁጥር 059 ባለሀብት መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በዚሀ ቤት ውስጥ የሚኖሩበት ከአመልካች ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል መሠረት መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ እና በየደረጃው ባቀረቡት ክርክር አረጋገጠዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በኪራይ ውል የያዙትን ቤት እንዲለቁ እና የኪራዩን ውል ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? አመልካች በኪራይ ውሉ ይገደዳል ወይስ አይገደድም? የሚሉት ጭብጦች በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የኪራይ ውልና አግባብነት ያላቸውን የህግ ማእቀፎች መሠረት በማድረግ የሚታይ ነው፡፡

አንድ ሰው በሌላው ሰው ላይ ሁከት ፈጠረ ተብሎ ውሣኔ የሚሰጠው የሌላ ሰውን ይዞታ የወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የፈጠረበት መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱ ባለሀብት የሆነው አመልካች ቤቱን በኪራይ የያዙት ተጠሪ እንዲለቁለት ማስጠንቀቂያ መፃፉና የኪራይ ውልን የማቋረጥ ሀሣብ ያለው መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2966 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማሳወቁ ከአከራይ ተከራይ ውልና ግንኙነት አንፃር የሚያታይ እንጂ እንደ ሁከት ተግባር የሚቆጠር አይደለም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ለአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በግልፅ ያቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ አከራዩ አመልካች ከህግ ውጭ የኪራይ ውልን ለማቋረጥ ማድረጉ ተገቢ ስላልሆነ በኪራይ ውሉ እንዲገደድ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ሣይሆን አመልካች ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሁከት እየፈጠረብኝ ስለሆነ ሁከቱ ይወገድልኝ የሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁከት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ መወሰን ሲገባው አመልካች የኪራይ ውሉን ያቋረጠው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስ ሲሆን የከተማው የሰበር ችሎትም አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጠረው ሁከት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ብቻ በመወሰን ውሣኔ መስጠት ሲገባው አመልካች የኪራይ ውልን ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ የሰጠው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ሁከት ፈጥሮብኛል ሁከቱ ይወገድልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ እያለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከጠየቀችው ዳኝነት በመውጣት አመልካች የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ላይ ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የፈፀመው የሁከት ተግባር የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ይኸ ውሣኔ ተጠሪ የኪራይ ውሉን መሠረት በማድረግ ሥልጣን ላለው አካል መብቱን ከመጠየቅ የሚገድባት አይደለም፡፡ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

# ባንክ እና ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁ. 68708

ታህሣስ 05 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የአቶ ናስር አባጃቢር አባጅፋር ሚስትና ወራሾች

1. ወ/ሮ ሊያ ታምራት
2. ፍራአል ናስር አባጃቢር
3. ፍሮሜ ናስር አባጃቢር

ጠበቃ ድጋፌ ለገሠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ባይሣ ኤደሣ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች አውራሽ ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ሰኔ 01 ቀን 1992 ዓ.ም እና ህዳር 22 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው የብድር ውል በዋስትና ያስያዙት ንብረት በሐራጅ በተሸጠበት ወቅት ተጠሪ ሆነ ብሎ በእዳ ከያዘው ንብረቶች ውስጥ በሐራጅ መካተት የሚገባቸውን ንብረቶችን ባለማካተቱና ንብረቱ በተገቢው መንገድ ባለመሸጡ ከሣሽ ብር 1,280 ,556.70 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሺህ አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ብር ከሰባ ሣንቲም/ ያጡ መሆኑን ገልጸው ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ ከእነ ወለዱ እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበው ክርክርም ሐራጁ ከተከናወነ ከሶስት ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ክሱ መቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ድንጋጌ መሠረት የማይፈቀድ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የከሣሽ ጥያቄ ንብረቱ በሐራጅ በመሸጡ ላይ የቀረበ ተቃውሞ ሳይሆን በሐራጅ ጊዜ መካተት የሚገባቸው ንብረቶች ሣይካተቱ ቀርተው ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ነው የሚል ምክንያት በመያዝ ይኸው ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 447/1/ መሠረት በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ ይገባ ነበር በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የስር ከሣሽ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ለክርክሩ ምክንያት በሆኑት ንብረቶች ላይ የተካሄደው የሐራጅ ሽያጭ ይፍረስልኝ ወይም ይሰረዝልኝ ሳይሆን ንብረቶችን ያለዋጋ ስለአስተላለፋቸው ግምታቸውን ተጠሪ ሊከፍል ይገባል የሚል ሁኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ በመጥቀስ ክሱ በሁለት ወር ይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ተጠቅሶ ክሱ በሁለት ወር ይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርበ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ ከህጉ ጋር አገናዝቦ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካቾች አውራሽና በተጠሪ መካከል የብድር ውል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ብድሩ የተወሰደውም በተለያዩ ጊዜአት ሁኖ ተበዳሪው ገንዘቡን ሊመልሱ ባለመቻላቸው ተጠሪ በብድር ውሉ በመያዣነት የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት በሐራጅ መሸጡን ተበዳሪው ግንቦት 05 ቀን 2002 ዓ.ም ለመሰረቱት ክስ መሠረት ያደረጉት ምክንያትም ተጠሪ በዋስትና የያዘውን ንብረት ታህሣስ 20 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሸጥ በሐራጁ መካተት የሚገባቸውን ንብረቶች ሳያካትት ቀርቶ ያለዋጋ ማስተላለፉን የሚገልጽ ሁኖ የጠየቁት ዳኝነት የእነዚህ ንብረቶች ግምት እንዲከፈላቸው መሆኑን ነው፡፡ የስር ከሣሽ ከሐራጅ መሰረዝ ወይም መፍረስ ጋር አያይዘው ያነሱት የዳኝነት ጥያቄ የሌለ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የአንድ መብትና ግዴታ ምንጭ ህግ ወይም ውል ነው በህግ ወይም በውል ጥበቃ ያገኘ መብት ወይም ግዴታ ጉዳት ሲደርስበት ወይም ተገቢው ካሣ የሚያስከፍል ከሆነ በህጉ ተለይቶ በተመለከተው የጊዜ ገደብና አካል ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥ ክስ ሊቀርብበት የሚገባው ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የስር ከሣሽ ለክሳቸው መሠረት ያደረጉት ተጠሪ ባንክ ለብድሩ በዋስትና የተሰጡትን ንብረቶች በሐራጅ ሲሸጥ በሐራጅ መካተት የሚገባቸውን ንብረቶችን ሳያካትት በመቅረቱ ያለዋጋ ንብረቶችን በማስተላለፍ ጉዳት በማድረሱ የንብረቶችን ግምት ሊከፍል ይገባል በማለት ነው፡፡ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በሐራጅ መሸጥ እንዲችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አዋጅ ቁጥር 98/90 እና አዋጅ ቁጥር 216/92 መሠረት የህግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ባንኩ መያዣውን ሲሸጥ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓትም በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ከቁጥር 394 እስከ 449 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ስለመሆኑም አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሲታይም የሐራጅ ሽያጩ ሂደት በህጉ አግባብ ካልተፈጸመ እና ይህ በተገቢው መንገድ ከተረጋገጠ ህጉ ባንኩን ለተፈጸመው ስህተትና ውጤቱ ተጠያቂ እንደሚያረገው ያስገነዝባል፡፡ አመልካች በተጠሪ ደርጊት ከላይ በተገለጸው አግባብ የተፈጸመባቸው እና የጉዳት ኪሣራ የጠየቁም አይደለም፡፡ ለክሳቸው መሠረት ያደረጉት በአዋጁ መሠረት አመልካች ሐራጁን ሲያወጣ መካተት የሚገባቸው ንብረቶች ሳይካተት ቀርቷል የሚል ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ የአመልካቾች አውራሽ የዳነኝት ጥያቄ መሠረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027 እና 2028 መሠረት የጉዳት ካሣ የሚጠየቅበትን አግባብ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ንብረት በሐራጅ ሲሸጥ በሐራጁ መካተት የሚገባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 423/2/ ስር

ተዘርዝረዋል፡፡ ይህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 6 መሠረት ባንኩ የሐራጁን ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ሊከተላቸው ይገባቸዋል ተብለው ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስር የሚገኝ ነው፡፡ ይህን ደንጋጌ ባለመከተል የሚደርሰው ጉዳት /DAMAGE/ ደግሞ የሚጠየቀው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 7 መሠረት ነው፡፡ አንድ ሰዉ ህግን በመጣስ በሌላ ሰው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ከውል ውጪ ኀላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027፣ 2028 ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2035 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የውል ግንኙነትን መሠረት በማድረግ በሚካሄድ እንቅስቃሴና በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሰጠውን ስልጣን ለመጠቀም መነሻ ያደረገ እርምጃን ለመውሰድ በህጉ የተመለከተውን ስርዓት ያለመከተል እንደጥፋት በመቁጠር ባንኩ ካሣ እንዲከፍል አዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 7 ስለሚደነግግ እና ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2037 ድንጋጌ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ከላይ በተመለከተው መንገድ የሚጠየቀው የጉዳት ካሣ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143/1/ ድንጋጌ መሠረት እስከ ሁለት ዓመት ክስ ሲቀርብ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ስር የተመለከተው የሁለት ወር የጊዜ ገደብ የሐራጅ ይፍረስልኝ ወይም ይሰረዝልኝ ጥያቄን የሚገዛ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ፣ 98/1990 እና 216/1992 በተዘረጋው ስርዓት መሠረት ሐራጁ በሚከናወንበት ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 394 እስከ 449 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎችን ባለመከተል የሚደርሰውን ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በፎርክሎዠር ሕግ መሠረት የሚከናወን ሐራጅ በፍ/ቤት የሚሰርዝበትአግባብ የሌለ ሲሆን ሐራጁ በሕግ አግባብ ያለመከናወን በባንኩ ላይ የጉዳት ካሣ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ተቀምጧልና፡፡

በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች የአመልካች አውራሽ ጥያቄ የጉዳት ካሣ ጥያቄ ሆኖ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ውድቅ ማድረጋቸው በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143/1/ ድንጋጌ ስር የተመለከተው የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ማለፍ ያለማለፉ ሲታይ የአመልካቾች አውራሽ ክስ የመሰረቱት ግንቦት 05 ቀን 2002 ሲሆን ንብረቶቹ በሐራጁ ላይ ሳይካተቱ ተሸጡ የተባሉት ጊዜ ደግሞ ታህሣስ 20 ቀን 1999 ነው፡፡ ይህም ጊዜ ሲሰላ የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ከአለፈ በሁዋላ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ክሱን ውድቅ ማድርጋቸው በውጤት ደረጃ የምንቀበለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 92618 ጥቅምት 26 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/በት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64130 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ብይን ውጤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 342 መሠረት ምክንያቱ ተለውጦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143/1/ መሠረት በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ. 70824

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ወጋገን ባንክ አ.ማ ነ/ፈጅ ገቢሣ ተሬሣ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. አቶ ብሩክ ጫካ

2. ወ/ሮ አማረች ጫካ

3. ወ/ሮ ሂሩት ጫካ

4. አቶ ከበደ ጫካ

5. ወ/ሮ አለምጸሀይ ጫካ

6. ወ/ሮ አዳነች ጫካ

7. አቶ ጌታሁን ጫካ

ጠበቆች 1. አማን አሰፋ

2. ቴዎድሮስ ምህረት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አበዳሪ ባንክ ለሰጠው ብድር ሁለትና ከዚያ በላይ መያዣ ይዞ ቆይቶ ብድሩ ባለመመለሱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት መያዣውን ለመሸጥ ሲንቀሳቀስ ከመያዣዎቹ መካከል ቀድሞ መሸጥ ያለበት ንብረት የትኛው እንደሆነ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽ፣አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የመሠረቱት ክስ ባጭሩ፡- አመልካች ለሚለማ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሠጠው ብር አምስት ሚሊዮን የኦቨር ድራፍት ብድር በዋስትና መያዥነት ተበዳሪው በቡራዩ ከተማ ካለው መጋዘን ቤት በተጨማሪ በውርስ የተገኘውን የተጠሪዎችን መኖሪያ ቤት በተጨማሪ መያዥነት አስይዞ እንደነበር፣ተበዳሪው የተበደሩትን ብድር ያልመለሱ መሆኑን፣አመልካች ለሠጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን የተበዳሪውን መጋዘን ሸጦ ለብድሩ ማስመለሻ ማድረግ ሲገባው የባለዳውን መጋዘን ትቶ የተጠሪዎችን የውርስ ቤት በሐራጅ ሊሸጥ እንደማይገባ ዘርዝረው በተጠሪዎች ቤት ላይ

የጀመረውን የሐራጅ ሽያጭ አቁሞ በመጀመሪያ የተበዳሪውን ንብረት የዕዳው ማስመለሻ አድርጐ እንዲቀጥል፣የተጠሪዎችን የቤት ካርታ እንዲመልስ ይወሠንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ በአዋጅ ቁ 97/90 እና 216/92 መሠረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ እዳው አለመከፈሉና ቤቱ መያዣ መሆኑ ባለመካዱ ተጠሪዎች ክስ ለማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን፣ተበዳሪ ካልከፈለ በቅድሚያ በአንደኛ ደረጃ የተያዘው የተበዳሪው ንብረት ይሸጣል የሚል ስምምነት ባለመኖሩ በዚህ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣የፍ/ሕጉን ድንጋጌዎች በመጥቀስ የቀረቡ ክርክሮች ከአዋጅ ቁ 97/90 ድንጋጌ ውጪ መሆናቸውን፣አመልካች ከአዋጅ ቁ 97/99 አንፃር ያመነበትን ንብረት መሸጥ የሚችል መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከሣሽና ተከሣሽ በቅድሚያ የባለዕዳው ንብረት ሊሸጥ ይገባል በማለት በመያዣ በተሠጠ ንብረት ላይ የተጀመረ ሐራጅን ለማስቆም ይችላል? ወይንስ አይችልም? የሚል ጭብጥ መስርቶ መዝገቡን በመመርመር ባንክ የሠጠው ብድር ሣይመለስ ሲቀር መያዣውን በመሸጥ የባለቤትነት መብት እንዲዛወር ለማድረግ ካባለዕዳው ጋር መስማማትና በዚሁ ስምምነት ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት መደንገጉን፣ክስ በቀረበበት ጉዳይም ከሣሽ በመያዣ የሰጡት ቤት ዕዳ ካልተከፈለ ባንኩ እንዲሸጥ መስማማቱን የመያዣ ውሉ የሚያሳይ መሆኑን፣ይህ ሥርዓት በአዋጅ ለባንኩ የተፈቀደው ባንኩ የሰጠውን ብድር በፍጥነት መሠብሰብ የማስቻል ዓላማ የያዘ መሆኑ ግልጽ መሆኑን፣አመልካች በአዋጅ የተሠጠውን ሥልጣን ተፈፃሚ ለማድረግ ሲንቀሣቀስ ተጠሪዎች የፍትሓ ብሔር ሕጉ ስለተራ ዋስትና የደነገገውን መነሻ በማድረግ በቅድሚያ የባለዕዳው ንብረት ሣይሸጥ ባንኩ በተጠሪዎች ንብረት ላይ ሐራጅ መቀጠል አይችልም በማለት መከራከራቸው አግባብነት የሌለውና አዋጁን የሚቃረን መሆኑን በመዘርዘርና በምክንያትነት በመያዝ የተጠሪዎችን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በመያዣነት የቀረበው የተጠሪዎችን ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ በአመልካች ዘንድ እንደሆነ አመልካች በቅድሚያ ለዚሁ ብድር በመያዣ የያዘውንና በቡራዩ ከተማ የሚገኘውን የተበዳሪውን ንብረት በጨረታ ሽጦ የሰጠውን ብድር ያስመልስ፣አመልካች የሚሸጠው የተበዳሪው መጋዘን ብድሩን በሙሉ ካላስመለሰለት የተጠሪዎችን የመያዣ ንብረት ሽጦ ቀሪውን ብድር ያስመልስ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለውጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአዋጅ ቁ 97/90 ዋና ዓላማ በፍ/ቤት የሚፈጀውን ጊዜ በማሣጠር ለልማት እንቅስቃሴው የሚሠጡ ብድሮችን ወቅቱን ጠብቆ እንዲሠበሰብ ማስቻል መሆኑን፣የደረሠ ጉዳትን ከሚመለከት ጉዳይ በስተቀር ጉዳዮች ወደ ፍ/ቤት ለመምጣት የማይችሉ መሆኑን፣ ወደ ፍ/ቤት መምጣት ይችላሉ ከተባለ ወደ ነበርንበት መመለስና ባንኮችም ብድራቸውን በጊዜው እንዳይሠበስቡ የሚያደርጋቸው መሆኑን፣በተጠሪዎች የተጠቀሱት የፍትሓ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን፣በሕጉ አግባብ በተደረገው ውል መሰረት አከራካሪው ንብረት መያዣ መሆኑ ያለመካዱን፣እንዲህ ከሆነ ደግሞ ግራ ቀኝ የሚገዙት በውሉ መሆኑን፣በውሉ ደግሞ መጀመሪያ የተበዳሪውን ንብረት ሽጠህ ነው ወደ እኔ የምትመጣው የሚል ስምምነት የሌለ መሆኑን፣ውሉ የሚለው ዕዳው ካልተከፈለ ንብረቱ ይሸጣል ስለመሆኑ፣ የተበዳሪው መጋዘን ብር 12 ሚሊዮን

ያወጣል የተባለውም በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ ተበዳሪው በርካታ እዳ እንዳለባቸው እና ተጠሪዎችም የተበዳሪው ድርጅት እዳ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው መሆኑን፣ የመያዣውን ንብረት የመሸጥ መብት መያዣ ያገኙ ባንክ እንጂ ተበዳሪው ከመያዣዎቹ ውስጥ መያዣ ያገኙን ባንክ ይህን ሽጥ ይህን ደግሞ አትሽጥ የማለት መብት የሌላው መሆኑንና መብቱ የአመልካች ባንክ መሆኑን፣ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ 97/90 አፈጻጸም ላይ ጣልቃ የሚገባቡት መንገድ የተለየ መሆኑን በመዘርዘር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርመሮም አመልካች በቅድሚያ የተበዳሪውን ንብረት ሽጦ ለእዳ መመለሻ ያውል የመባሉን እና ሌሎች ነጥቦችን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ የሰጡት መልስ ባጭሩ፡- የአዋጅ ቁጥር 97/90 ዓላማ ባንኮች በመያዣ የሚያዟቸውን ንብረቶች ለፍ/ቤት ማመልከት ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው መሸጥ እንዲችሉ ሆኖ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለውን በውል ላይ የተመሠረተ እኩልነትን ያረጋገጠ መሆኑን፣አመልካች የሰጠውን ብድር እጥፍ የሚሸፍን ንብረት በእጁ እያለ የተጠሪዎችን መኖሪያ ቤት ለመሸጥ መንቀሣቀሱ ቅን ልቦና የሌለው አካሄድ መሆኑን፣ተበዳሪው ከአመልካች ዘንድ በመያዣ የተያዘውን በቡራዩ ከተማ የሚገኘውን መጋዘን ሸጬ የብድሩ መመለሻ እንዳደርግ ይፈቀድልኝ ብሎ ጥያቄ አቅርቦ በአመልካች ትብብር መከልከሉ ያላግባብ መሆኑን፣ተጠሪዎች የተበዳሪው ንብረት በቅድሚያ እንዲሸጥ ጠቁመው በአመልካች ጥያቄአችን ውድቅ ተደርጎ የተጠሪዎች ንብረት ለመሸጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ትክክል አይደለም ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መወሰኑ የተጠሪዎችን በሕግ ፊት እኩልነትና ፍትሕ የማግኘት መብትን ያረጋገጠና በሕግ፣ በሞራልና ከአመክንዮ ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣የብድሩን መጠን በተመለከተ አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ የጠቀሰውም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን በመዘርዘር የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ ምንም የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የተጠሪዎች ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካች በመያዣ ከያዛቸው ንብረቶች መካከል አንዱ የሆነውን የተጠሪዎችን ንብረት ከመሸጡ በፊት ሌላ መያዣ የሆነ የተበዳሪ ድርጅት መጋዝን ስለአለ ይህንኑ መጋዝን ቀድሞ ሊሸጥ ሲገባ የተጠሪዎችን መኖሪያ ቤት ለመሸጥ መንቀሳቀሱ ተገቢ አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን፣የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ሊያሳልፍ የቻለው አከራካሪው ንብረት በመያዣ መሰጠቱን አረጋግጦ ከዚሁ ንብረት ጋር በመያዣነት የተሠጠ የተበዳሪ ንብረት ስላለ ይኸው ቀድሞ ሳይሸጥ የተጠሪዎች ንብረት መያዣ በመሆኑ ብቻ የሚሸጥበት አግባብ የለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በሐራጅ መሸጥ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 የሕግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ባንኩ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ከቁጥር 394- 449 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች

ስር በተመለከተው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 97/90 በአንቀጽ 6 በግልጽ አስፍሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 እና 4 መሰረት እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 216/19992 በተደረገው ማሻሻያ ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት በዋስትና የተቀበሉትን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የብድር እዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከሰላሳ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዢው ለማዛወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው አበዳሪው ባንክ በዋስትና የያዛቸውን ንብረቶች የብድር ገንዘቡን ካልተመለሰለት ያለማንም ጣልቃ ገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎችን በመከተል በሐራጅ ሸጦ ለእዳው ክፍያ ማዋል እንደሚችልና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈጸመው ስህተት ቢኖርና በዚህም በባለእዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለእዳው ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የአዋጆቹ ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይም የሕጎቹ ዓይነተኛ አላማ ባንኮች የሚሰጧቸውን ብድሮች በተቀላጠፈ አኳኋን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይህ ስለመሆኑም አዋጅ ቁጥር 97/1990 መግቢያው ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

ባንክ ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች መሠረት በመያዣ የያዘውን ንብረት አስገምቶ ሐራጅ ቢያወጣና ቢሸጥ ወይም በሕጉ መሠረት ቢረከብ ግምቱን ወይም በመያዣ የተሰጡትን ንብረቶች አሻሻጥ ቅደም ተከተል ምክንያት በማድረግ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዲያይ፣እንዲያስገምት ወይም ከመያዣዎቹ አንዱ ቀድሞ መሸጥ አለበት ብሎ ለመወሰን የሚያስችል ከሕግ የመነጨ ሥልጣን የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ መግቢያ በማድረግ መያዣው በብድሩ ወቅት በተገመተበት ግምት እንዲያዝ መጠየቅም ሆነ በሐራጅ ወቅት የወጣው መነሻ ግምት አነስተኛ ነው ብሎ ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ከፍ/ቤቱ ስልጣን ውጪ ከመሆኑም በላይ አዋጁ የወጣበትን ዓላማም ከግብ እንዳይደርስ የሚያደርግ ጭምር ስለመሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ይህ የሕጉ አጠቃላይ ቅርፅ የሚያስገነዝበን ሌላው ቁም ነገር በመያዣ ውሉ የተቀመጡት ንብረቶች ተለይተው የታወቁ እስከሆነ ድረስና የተያዙበት አግባብም አንዱ መያዣ ከሌላው በቅደም ተከተል የሚሸጥ አለመሆኑን የሚያሳይ ከሆነ ከመያዣዎች ውስጥ ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ሳይሸጥ አነስተኛ ግምት ያለው ቀድሞ ሊሸጥ አይገባም በሚል የሚቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የመያዣ ውሉንና ከላይ ከተጠቀሱት አዋጆች አላማ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ፍርድ ቤት የሐራጁን ስርዓት በማስቆም የሚያስተናግድበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ባንክ የሐራጅ ሽያጩን የሚያከናውነው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 394-449 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ የሐራጁ ሽያጭ ሂደት በሕጉ አግባብ ካለተፈፀመ እና ይህ ከተረጋገጠ ሕጉ ባንኩን ለተፈፀመው ስህተትና ውጤቱ ተጠያቂ ያደርገዋል፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ የምንገነዘበው ሐቅ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች ተላልፎ በመያዣው ላይ ሽያጭ ከተፈፀመ ሃላፊነቱ የባንኩ እንደሆነም በግልጽ ያሣያል፡፡ ከላይ የተመለከቱት የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተጥሰዋል የሚለው ክርክር በባንኩ ላይ በፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ባንኩ ሐራጁን እንዳያከናውን በማድረግ ሳይሆን የሐራጅ ስርአቱ ከተከናወነ በሁዋላ ስለመሆኑም የሚታመን ነው፡፡ ጥያቄው ከሐራጁ በፊት በፍርድ ቤት ሊታይና ሐራጁ እንዲቆም ሊደረግ ይችላል ከተባለ ከላይ እንደተገለጸው በፎርክሎዠር ሕጎች የታሰበው የብድሮች በተቀላጠፈ ሁኔታ የመሰብሰብ እድል የተገደበ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ይዘቱ ሲታይ አመልካች በመያዣ ከያዛቸው ንብረቶች መካከል የመኖሪያ ቤቱ ከመሸጡ በፊት ለእዳው ተመጣጣኝ የሆነ መጋዘን ስላለ ይህንኑ ንብረት መሸጥ አለበት የሚልና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር

394(2) ስር የተመለከተውን የስነ ስርዓት ሕግ አጠቃላይ መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በእርግጥ ይኸው ድንጋጌ ባንኩ እንዲከተለው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ግዴታ የተጣለበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው ድንጋጌ ተጥሷል የሚለው ወገን በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚያቀርበው የሐራጅ ስርዓቱ እንዲቆም በማድረግ ሳይሆን ይኸው ድንጋጌ በሐራጅ ጊዜ በባንኩ ባለመጠበቁ የደረሰ ጉዳት ካላ ይህንኑ በማረጋገጥ ነው፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪዎች አመልካች በመያዣ ከያዛቸው ንብረቶች መካከል ከፍተኛ ግምት ያለውን የተበዳሪውን መያዣ ሊሸጥ ይገባል እንጂ በመያዣ የተሠጠውንና አነስተኛ ግምት ያለውን መኖሪያ ቤት አመልካች ሊሸጥ አይገባም በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በፍርድ ቤት የሚስተናገድ አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና 216/1992 ዓይነተኛ አላማን ከተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ እንዲሁም አከራካሪው ንብረት በሕግ አግባብ በተቋቋመ የመያዣ ውል መሰረት የተያዘ ከመሆኑ አንፃር በመመርመር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማስተናገድ ስልጣን ያለው መሆን ያለመሆኑን ማገናዘብ ሲገባው አመልካች ከያዛቸው ንብረቶች መካከል የተበዳሪ ድርጅት መጋዘን ከፍተኛ ግምት ስላለው የተጠሪዎች መኖሪያ ቤት ከመሸጡ በፊት ቀድሞ መሸጥ አለበት ሲል የሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/1992 ስር የተመለከቱትን ግልፅ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ሁኖ አግኝተናል፡፡ ግልጽ ሕግ ደግሞ ውጤት እንዳይኖር የሚደረግበት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትም ሆነ የሕግ አተረጎጎም ደንብ የለም፡፡ በመሆነም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ስላገኘን የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 66087 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በሕግ አግባብ በተቋቋመ የመያዣ ውል ከተያዙት ንብረቶች መካከል የትኛው ንብረትና የማን ንብረት መሸጥ አለበት የሚለው ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለው የዋስትና መያዣዎችን ባንኮች ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሸጠው ለዕዳ ክፍያ ማዋል የሚችሉ ስለመሆኑ ከተደነገገው ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በተሠጠው ስልጣን መሰረት በተጠሪዎች መኖሪያ ቤት ላይ የጀመረው የሀራጅ እንቅስቃሴ የተበዳሪው ንብረት የሆነውና የብድሩ መያዣ መጋዝን ከተሸጠ በሁዋላ ሊከናወን ይገባል ብሎ ፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችልበት ከሕግ የመነጨ ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99689 የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
4. በዚህ የክርክር ደረጃ ያለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 69966
ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ በላቸው እሸቴ - ጠበቃ አቶ ወርቅዬ አባይነህ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረ ፈጅ ማህሌት ዓለሙ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ለደረሰው አደጋ ተጠሪ ካሣ የመክፈል ከውል የመነጨ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም በሚለው ነጥብ ሲከራከሩ ቆይተው ተጠሪ አደጋውን ያደረሰው ጉዳት በመድን ውሉ መሠረት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

የዚህ ክርክር መሠረታዊ ጉዳይ አመልካች ማንነታቸው ባልታወቀ ግለሰቦች በእሳት የተቃጠለችው ቁጥር ኮድ 3-02549 ለሆነችው መኪና በመድን በውሉ የተሰጠው ሽፋን ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ በመሆኑ በዚህ መሰረት ሊከፈል ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ መኪናው አደጋ በደረሰበት ጊዜ  የነበረው ዋጋ ብር 95,099.92 እንደሆነ በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቷል፡፡ ልከፍል የሚገባው ይህንን ገንዘብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት መኪናዋ አደጋ ሲደርስ የነበራትን ዋጋ አመልካች እንዳልተቃወመ በውሣኔው ገልፆ፣ ተጠሪ ብር 95,099.92 /ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሰኔ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ሒሳብ ፕሪሚየም ሲሰበሰብ ቆይቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የንግድ ሕግ ቁጥር 654/1/ እና የንግድ ሕግ ቁጥር 665/1/ መሠረታዊ ድንጋጌዎች የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ኅዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር መልስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የንግድ

ሕግ ቁጥር 678 በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ሊከፈለው የሚገባው መድን የተገባለት መኪና በአደጋው ጊዜ የነበረትን ዋጋ ያህል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በንግድ ሕጉ እውቅናና ጥበቃ ስለተሰጣቸው የኢንሹራንስ /የመድን ሽፋን/ አይነቶችንና ባህሪያት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በንግድ ሕጉ እውቅና የተሰጠው የመጀመሪያው የኢንሹራንስ ውል የደረሰን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት /Indemnity Insurance/ የሚደረግ ውል እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 654 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን፣ የደረሰን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት /Indemnity Insurance/ የሚደረግ የኢንሹራንስ ውሎች በንብረት ላይ ለሚደረስ ጉዳትና በፍታብሔር የሚመጣ ኃላፊነት /Indemnity Insurance/ የሚያካትት እንደሆነ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሁለተኛው ዓይነት የኢንሹራንስ ውል የደረሰን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት ሳይሆን አደጋው ሲደርስ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ ለተጠቃሚው ወይም የመድን ውል ለገባው ሰው ለመስጠት የኢንሹራንስ ውል (non Indemnity Insurance or capital insurance) እንደሆነና ይህም ለህይወት ወይም በአካል ጉዳት ወይም በሕመም ለሚደርስ አደጋ የሚሰጥ የመድን ሽፋን እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 654 ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ የንግድ ሕጉ በተለያየ መንገድ ፈርጆ ያስቀመጣቸው እነዚህ ሁለት አይነት የመድን ውሎች በይዘታቸው፣ በባህሪያቸውና በሚኖራቸው ውጤት የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ሁኔታ መኖሩን ሕግ አውጭው በምዕራፍ ሁለት ማለትም ከንግድ ሕጉ አንቀፅ 657 እስከ አንቀፅ 674 ጠቅላላ የመድን ሕግ ድንጋጌዎችን፣ በምዕራፍ ሶስት ማለትም በንግድ ሕጉ ከአንቀፅ 675 እስከ አንቀፅ 688 ስለጉዳት ኪሣራ ኢንሹራንስ ላይ ልዩ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን፣ በምዕራፍ ሶስት ማለትም ከአንቀጽ 689 እስከ አንቀፅ 712 የሰዎች ኢንሹራንስ ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን ልዩ ድንጋጌዎች በመደንገግ በግልጽ አሳይቶናል፡፡

የንግድ ሕግ አንቀጽ 665 በአጠቃላይ ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት እና ለሰዎች ኢንሹራንስ ላይ ተፈፃሚነት ያለው ጠቅላላ ድንጋጌ ሲሆን፣ በይዘቱ የመድን ሽፋን የሚሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያ ለመድን ገቢው ወይም ለተጠቃሚው ሊከፍለው የሚችለው ወይም ሊከፍለው የሚገባው የኢንሹራንስ ገንዘብ በመድን ውሉ ከተገለፀው ሊበልጥ የማይችል መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ንግድ ሕግ አንቀፅ 678 ስለንብረት የተደረገ ኢንሹራንስ ውል የሚኖረውን ውጤት በልዩ ሁኔታ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡ በመርሕ ደረጃ ለንብረት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን አደጋው በደረሰበት ጊዜ ንብረቱ የነበረውን ዋጋ የሚያካክስ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ በንብረት የሚደረግ ኢንሹራንስ መሠረታዊ ዓላማው ንብረቱ በመጎዳቱ ወይም ንብረቱ በመውደሙ በባለንብረቱ ላይ የደረሰውን ኪሣራ ለመተካት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የንብረቱ ዋጋ ከተሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በልጦ ሲገኝ መድን ገቢው በመድን ውሉ ሽፋን ከተሰጠው ዋጋ በላይ ላለው ገንዘብ ራሱ የመድን ሽፋን እንደሰጠ ተቆጥሮ፣ መድን ሰጭው በውሉ የተገለፀውን ዋጋ ብቻ የሚከፍል ስለመሆኑ፣ የዕቃው ዋጋ ከተሰጠው የመድን ሽፋን አንሶ ሲገኝና መድን ገቢው የማታለል፣ የማጭበርበር ተግባር ያልፈፀመ በሆነ ጊዜ የዕቃው እውነተኛ ዋጋ የሚከፈለው መሆኑን በንግድ ሕጉ አንቀፅ 680 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አንድ ሰው አንድን

ንብረት ለተመሣሣይ አደጋ ለተለያዩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የመድን ሽፋን እንዲኖረው ቢያደርግ የመድን ሽፋን የሰጡት ኩባንያዎች በውላቸው ፕሮፖርሽናል በሆነ መንገድ አዋጥተው የዕቃውን ዋጋ ብቻ የሚክሱት ስለመሆኑና አንድ ሰው ከዕቃው ዋጋ በላይ የሆነ ገንዘብ አንድን ዕቃ በተለያየ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሽፋን እንደሰጡት በማድረግ ሊያገኝ እንደማይችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 681 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከገለፅነው መሠረታዊ ድንጋጌዎች አንፃር ስንመለከተው የአመልካች መኪና ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የነበራት ዋጋ በመድን ውሉ ከተገለፀው ያነሰ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የሚከፍለው በውሉ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ሳይሆን ንብረቱ በአደጋው ውድመት ሲደርስበት የነበረውን ዋጋ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የንግድ ሕግ አንቀፅ 678 እና የንግድ ሕግ አንቀፅ 680 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ስለንብረት ጉዳት የተደረገ የመድን ውል የሚኖረውን ውጤት የሚደነግጉ ሌሎች ልዩ ድንጋጌዎችን ይዘት፣ ባህሪያትና ውጤት ያገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ 74898

ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1- አቶ ፍቃዱ ተስፋዬ ቀረቡ

2- አቶ በጡሬ ሲማ

3- ወ/ሮ ዘብደሩ ወት አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የባለእዳው ንብረት እዳውን ሊሸፍን ባለመቻሉ በከፊል ተፈፅሞ ከቆየ በኋላ የፍርድ ባለመብት የባለእዳውን ንብረት አፈላልጎ በማግኘት አፈፃፀሙን ለመቀጠል ሲፈልግ ይርጋው ሊቆጠር የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የአፈፃፀም ክሱ /ክርክሩ/ የጀመረው በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በአፈፃፀም ክሱ እንደተመለከተው ለአቶ ፈቃዱ ተስፋዬ የሠጠው ብድር በወሉ መሠረት ባለመከፈሉ በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ የአፈፃፀም ተከሣሾች /የአሁኑ ተጠሪዎች/ በአንድነት እና በነጠላ ያለባቸውን ቀሪ እዳ ብር 147,922.00 /አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ብር /እንዲከፍሉ ሕዳር 2 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት መወሰኑን ፣ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት በአገኘው መብት አፈፃፀሙን በራሱ ቀጥሎ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. በዝዋይ ከተማ 02 ቀበሌ ውስጥ በአቶ ፍቃዱ ተስፋዬ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውንና ቁጥር 21/164/80 የሆነውን ቤት በብር 50,400.00 በመሸጥ ይህንኑ የሽያጭ ገንዘብ ከእዳው የቀነሰ ሲሆን በወቅቱ የባለእዳዎች ንብረት ባለመኖሩ አፈፃፀሙን መቀጠል ያለመቻሉን ፣ ከዚህ በኋላ የዋናው ተበዳሪ ዋስ በሆኑት በአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ንብረት ማግኘቱን ገልጾ ቀድሞ በፍርድ ቤት በአገኘው ውሣኔ መሠረት አፈፃፀሙን በዚሁ በዋሱ ንብርት እንዲቀጥልለት ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአፈፃፀም መዝገቡ የቀረበው በፍርድ ቤቱ ውሣኔ ከተሰጠ ከአስራ አራት አመታት በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ቀሪ እዳ መኖሩን አውቋል ሊባል የሚችለው የአቶ ፈቃዱ ተስፋዬ ንብረት ሸጦ ቀሪ እዳው መኖሩን ከአወቀበት ጊዜ ጀምሮ ሁኖ እያለ ይርጋው ከሕዳር 02 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ነው መቆጠር ያለበት ተብሎ የአፈፃፀም መዝገቡ መዝጋቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም

የአመልካች የአፈፃፀም መዝገብ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች የብድሩን ገንዘብ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመክፈላቸው አመልካች በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦባቸው ፍርድ ቤቱ ሕዳር 02 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱን ይህንኑ ውሣኔ መሠረት በማድረግ አመልካች አፈፃፀሙን በፍርድ ሳይቀጥል ቆይቶ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት በአገኘው መብት አፈፃፀሙን በራሱ ቀጥሎ ግምቱ ብር 50,400.00 /ሃምሳ ሺህ አራት መቶ ብር/ የሆነውን የዋናውን ተበዳሪ ንብረት ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም በመሸጥ በፍርድ ቤቱ ከተወሰነበት ከብር 147,922.00 ገንዘብ ውስጥ ተቀናሽ ማድረጉንና ከዚህ በኋላ በመያዣነት ያልተያዘ የዋሱ ንብረት ተገኝቷል በሚል ምክንያት አፈፃፀሙን በፍርድ ቤት በኩል ለመቀጠል ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም መንቀሳቀሱን ነው፡፡ ከዚህ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የዋናውን ተበዳሪ ቤት ለእዳው መክፈያ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም ቢያውልም የቤቱ ግምት እዳውን ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈን መቅረቱን ነው፡፡ የዋናውን ባለዕዳ ቤት ሽጦ ከእዳው ተቀናሽ ቢያደርግም በዚህ ረገድ ተከፈለ ሊባል የሚችለው ዕዳ በተጠሪዎች ላይ የሚፈለገውን አጠቃላይ ዕዳ የሚሸፍንለት ሆኖ ባለማግኘቱ ቀሪው ዕዳ እንዲከፈለው በመጠየቁ የአፈፃፀም ክስ መስርቶአል፡፡ አመልካች የዋሱን ቤት ሽጦ የሸያጩን ገንዘብ ከእዳ ተቀናሽ የአደረገበት ጊዜ ቀሪ እዳ የሚፈልግ መሆኑን ያረጋገጠበት ጊዜ ነው የሚባል ከመሆኑም በላይ ባለእዳዎች በዚህ ጊዜ እዳውን ለመሸፈን የሚያስችል ንብረት የነበራቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡

ለአፈፃፀም የሚውል የባለእዳ ንብረት ከሌለ አፈፃፀሙ መቀጠል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329/2/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳውን እንደፍርዱ ለመፈፀም የማይቻል መሆኑን ከአረጋገጠ ፍርዱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ እንደማይሰጥ ሆኖም ለመፈጸም ችሎታ በሚያገኝበት በማናቸውም ጊዜ እንዲፈፀም ትእዛዝ ከመስጠት እንደማይታገድ ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 384 ድንጋጌ ልዩ ሁኔታ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 384 ስር የተመለከተው የአስር አመት የጊዜ ገደብ የፍርድ ባለመብት ምንም እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቆይቶ ፍርዱን ለማስፈፀም ሲንቀሳቀስ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ በኩል በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ቡድሩን ለማስመለስ ስልጣን የተሰጠው ባንክ አፈፃፀሙን ራሱ የሚመራው ቢሆንም የባለእዳው መያዣ የሆነ ንብረት ያለመኖሩንና መያዣ በሆነ ንብረት እዳውን መሸፈን ካልቻለ አፈፃጸሙን መቀጠል ያለበት ይህንኑ ከአረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች በባለእዳው ንብረት ላይ ሕዳር 23 ቀን 1990 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ለአፈፀፀም ሊቀርብ የሚገባው በአስር አመት በመሆኑ አመልካች ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም በዋናው ባለእዳ ንብረት ላይ አፈፃፀም መቀጠሉ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጥ ሕጋዊ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም አዲሱ ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ከሕዳር 23 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን ከግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደገና እንደአዲስ የይርጋ ዘመን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1852 መሠረት ሲቆጠር አመልካች

የአፈጻጸሙን ክስ ያቀረበው ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ በሕጉ የተመለከተው የአስር አመት የይርጋ ጊዜ አላለፈም፡፡ ስለሆነም ከግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ አስር ዓመት አልሞላም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የይርጋውን ጊዜ ያሰሉት ከህዳር 23 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ የአስር ዓመትን የይርጋ ጊዜ መሠረት በማድረግ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሳቸው በህጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሆነ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 29879 ሕዳር 19 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 137198 ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ በመሆኑም የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በአፈፃፀም ክሱ ስረ ነገር ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች የሚያቀርቡለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 67225

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አደነ ንጉሴ

አመልካች፡-አቶ ኤርሚያስ ሓይሉ የሆነስት የረር ማኔጂንግ ዳይሬክተር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃኑ ዳምጠው ወኪል አስፋው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገ የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች እና በአቶ በላይ አያሌው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነና በስር ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ በላይ አያሌው ይሽከረከር የነበረ የሰሌዳ ቁጥር 3-28569 እና ተሳቢው 3-070339 የሆነ ተሽከርካሪ በኋላ ገጭቷአቸው በቀኝ እግራቸው ላይ ተሳቢው ቆሞባቸው እግራቸውን ከጥቅም ውጪ ያደረገባቸው መሆኑን፣በዚህም ምክንያት አሽከርካሪው በወንጀል ተከሶ የተቀጣ መሆኑን፣በወቅቱ ተጠሪ በግል ድርጅት ተቀጥረው በወር ብር 1500.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) እያገኙ ሲሰሩ እንደነበርና ይኸው ገቢ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልጸው ወደፊት ለሰላሳ አመት አመታት ቢኖሩ ሊያገኙ የሚችሉትን የገቢ መጠን በማስላት አጠቃላዩን ደምረው ብር 920,000.00 (ዘጠኝ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ ለክሱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን እና የጉዳት ካሳ መጠኑም እጅጉን የተጋነነ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ግን በሌሉበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን በመኪናው ባለንብረትነቱ ለተጠሪ አካል ጉዳት ኃላፊ በማድረግና የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተም የተጠሪ ወርሃዊ ገቢው እንዲጣራ ፍርድ ቤቱ ሲፈልግ አመልካች ትእዛዙን ሊያከብር ባለመቻሉ ታልፎ ተጠሪ በወር 1200.00 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንደሚያገኙ ግንዛቤ በመውሰድ ይህንኑ የገቢ መጠን አካላቸው ላይ ደረሰ ከተባለው የ70% (ሰባ ከመቶ) ጉዳት እና ተጠሪ ወደፊት ለሃያ አመታት ሊኖሩ እንደሚችሉ በመውሰድ አስልቶ ብር 201,600.00 (ሁለት መቶ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ሊሆን እንደሚገባ፣ከዚሁ የጉዳት ገንዘብ ውስጥም ተጠሪ ብር 92,300.00 (ዘጠና ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ብር) በአመልካች

የተከፈላቸው መሆኑን አረጋግጦ ቀሪውን ብር 109,000.00 (አንድ መቶ ዘጠኝ ሺህ ብር) አመልካችና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆኑት አቶ በላይ አያሌው በአንድነትና በነጠላ እዲከፈሉ ሲል ወስኗል። በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ብሔረዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል። ከዚኅም በኂላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑም ሆነ የጉዳት ካሳ ስሌቱ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታቸው ተመርምሮም ይህ ችሎት እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ አመልካች ይካስ የተባለውን ገንዘብ አከፋፈል አስመልክቶ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095(2) አንጻር ሲታይ አመልካች በአንድ ጊዜ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ማየት እንዲቻል ሲባል ነው። ተጠሪ ቀርበውም የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ተገቢነት ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል ሲሉ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካችም ነሐሴ 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አከፋፈሉ በአንድ ጊዜ እንዲሆን መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095(2) ድንጋጌ አንፃር ለማየት ሲባል ነው።

ተጠሪ በግል ድርጅት ተቀጥረው በስራ ላይ የነበሩ መሆኑና ሲያገኙት የነበረው የገቢ መጠንን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት ተጠሪ የሚቀርባቸውን ገቢና ከጉዳቱ ጋር ተያይዘው የወጡትን ወጪዎች በመለየትን የካሣ መጠኑን መወሰናቸውን የውሳኔአቸው ይዘት በግልጽ ያሳያል።

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል። በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታ መሰረት ስናደረግ በካሳ አተማመኑ ላይ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ሳይገቡ በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ስለመሠጠቱ የሚያሳይ ነገር ያለ ሁኖ አልተገኘም። ተጠሪ አካላቸው በሕገ መንግስቱም ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን ካሳው ሲወሰንም ይህንኑና ጉዳቱ በአመልካች የወደፊት ኑሮ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አጠቃላይ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል እንጂ ተጠሪ 70% (ሰባ ከመቶ)

ጉዳት ቢደርስባቸውም ይሰሩ የነበሩትን ስራ ላለመስራት ወይም ሌላ ስራ ላለመስራት እንቅፋት አይሆንባቸውም በሚል ምክንያት ብቻ ካሳው ሊቀነስ ይገባል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ይህም ጥቅም ማቴሪያሊዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራሊዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን /future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡

በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመሥራት አቅምን /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሐዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ላለማጋነንና ላለመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣዳሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለመሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍረድ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2101 እና 2102 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማሳጣት ከአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አለማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ አይሆንም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነ መኪና በስር 2ኛ ተከሳሽ ሲሽከረከር ተግጭተው በአካላቸው ላይ 70% (ሰባ ከመቶ) ጉዳት መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የመኪናው ባለንብረት በመሆናቸው፣የስር 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ በጥፋታቸው መሰረት ተጠሪ ካሳ የማይከፈሉበት ምክንያት የሌለ ሲሆን በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰላው የካሳ መጠንም ከላይ የተመለከቱትን የካሳ አተማመን መንገዶችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው ከሚባል በስተቀር ጉልሕ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደዋናውና በዚህ ችሎት የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስም የጭብጡ መነሻ የካሳው አከፋፈል መንገድ በጡረታ መልክ በየወሩ እንዲከፈል መወሰን ሲገባ በአንድ ጊዜ እንዲከፈል የተወሰነው ያላግባብ ነው የሚለው የአመልካች ቅሬታ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህም መሰረት ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095(2) ድንጋጌ ሲታይ አርዕስቱ "ስለሞት አደጋና የሟች አንዳንድ የቅርብ ዘመዶች ስላላቸው መብቶች በሚል የተቀመጠ ሲሆን ይዘቱም ሲታይ ለእነዚህ ወገኖች የጉዳት ካሳ አከፋፈለን የሚደነግግ በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ደግሞ ተጎጂው ራሳቸው ክስ አቅርበው የጉዳት ካሳ በመጠየቅ ላይ ያሉና በሕይወት ያሉ በመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ ሲታይም የጉዳት ካሳ አከፋፈል በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን በአቀራረፁና ይዘቱ ለፍርድ ቤቱ ፈቃድ የሠጠ ከመሆኑ አንፃር የካሣው አከፋፈል በጡረታ መልክ ሊሆን ይገባል የሚለው የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08405 መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 106316 ታህሳስ 07 ቀን 2003 ዓ.ም. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 117820 መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ተብለው ብር 109,300.00 (አንድ መቶ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ብር) ከአቶ በላይ አያሌው ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 63231

ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢትዩጵ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ኬርጋ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አቶ ወልደ ሚካኤል ሻንቆ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክልላዊ መንግስት በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ከሳሽነት ነዉ፡፡ የካሳ ክፍያ ክሱን የተመለከተዉ ይሄዉ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመስማት አመልካች በዘረጋዉ የኤሌክትሪክ መስመር ላይ እሳት በመፈጠሩ ምክንያት በተከሰተ አደጋ በተጠሪ የተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ላይ ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ፣በዚህም ጉዳት ምክንያት የቀኝ እጁ ያለመንቀሳቀስ ችግር፣የቀኝ ቀለበት ጣት እና ትንሽ ጣት መቆረጥ፣የቀኝ መካከለኛ ጣት፣አመልካች ጣት እና የትልቁ ጣት መድረቅ እና ከአገልግሎት ዉጪ መሆን፣የቀኝ እግር 5ኛ ጣት መቆረጥ እና ስቃይ ደርሷል፤ በተጠሪ ላይ 63% ከፊል አቋም የአካል ጉዳት በመድረሱ እንደድሮዉ የማስተማር ስራዉን ማከናወን ባለመቻሉ፣ ስራዉን በአግባቡ በሚያከናዉንበት ወቅት የወር ጥቅል ደመወዙ ብር 1,692.00 /አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት/ ሁኖ ከዚህ ዉስጥ በእጅ የሚደርሰዉ 1,403.42 ብር /አንድ ሺህ አራት መቶ ሶስት ብር ከአርባ ሁለት ሳንቲም/ በመሆኑ እስከ ጡረታ መዉጫ ዕድሜ ታስቦ፣ የተለያዩ ወጪና ኪሳራ እንደዚሁም የሞራል ካሳን ጨምሮ ባጠቃላይ 139,228.26 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ከሃያ ስድስት ሳንቲም/ አመልካች ድርጅት እንዲከፍለዉ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበዉ ቅሬታ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 07-4-2003 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያላቸዉን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- አመልካች ኃላፊ ሊሆን በማይችልበት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ከ2124 እስከ 2136 ድረስ በተዘረዘሩት በሌላ ሰዉ ጥፋት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል መደረግ የሌለበት በመሆኑ፣አደጋዉ ሊፈጠር የቻለዉ የከሳሽ ጎረቤት አቶ ማቴዎስ የቴሌቪዥን አንቴና የሰቀሉበት የባህር ዛፍ እንጨት ከሌሊቱ በግምት 9፡15 ላይ በነፋስ ኃይል ተገፍትሮ በአከባቢዉ ከሚገኘዉ የኤሌክትርክ መስመር ላይ ሲወድቅበት ቴሌቪዥኑ ከፍተኛ ድምጽ ሊያሰማ መቻሉ፣ይሄዉ ጎረቤታቸዉ ቤታቸዉ ውስጥ በከፍተኛ ብርሃን ሲሞላ አይተዉ የድረሱልኝ ድምጽ ማሰማቱ፣ተጠሪም በዚህን

ወቅት ደርሰዉ መስመሩን ለማላቀቅ ሲሞክሩ የደረሰባቸዉ በመሆኑ ብቻ አመልካች በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2069 መሰረት ኃላፊነት አለበት ሊባል የማይገባ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ አግባብነት የሌለዉና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ሌላዉ የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ በየወሩ ያገኝ የነበረዉ ደመወዝ በቀለብ መልክ እንዳይቋረጥበት ዕድሜዉ 70 ዓመት እስኪሞላቸዉ እንዲከፈል ሆኖ እያለ በደረሰዉ ጉዳት መጠን ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠቱ እና ይሰሩበት የነበረዉ መስሪያ ቤት የጡረታ መብታቸዉን እንዲጠብቅ ዉሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነዉ፡፡

የቀረበዉ ቅሬታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2069 መሰረት በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት በበታች ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር በሚል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ቀርቦ መልሱን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የሰጠዉ የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- የቀረበዉ ቅሬታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት አይደለም፣ አመልካች ሌላ ሰዉ ባጠፋዉ ጥፋት ኃላፊ ሊሆን አይገባዉም ለሚለዉ ቅሬታ አመልካች በበታች ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለዉ አመልካች በዘረጋዉ የኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ጉዳት በመድረሱ በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ደግሞ ምንም ዓይነት ጥፋት ባይኖርም በሰራዉ አደገኛ ስራ ምክንያት በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2069 መሰረት ኃላፊነት ስላለበት በመሆኑ፣ የካሳ መጠኑን በተመለከተም የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ምክንያት የቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ የመልስ መልስ ቅሬታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገዉ የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በቅድሚያ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ የበታች ፍ/ቤቶች በቀረበው ክስ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የኃላፊነት እና የካሳ መጠን ውሳኔ የሰጡበት ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

በእርግጥ በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2027 ስር ከውል ውጭ ኃላፊነት የሚመጡበትን አግባቦች የሚያመለክት ሲሆን በተለይ የዚህ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ስር አንድ ሰው በህጉ ላይ እንደተመለከተው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስራ ከሰራ ወይም በእጁ የያዘው ነገር በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ኃላፊ እንደሚሆን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው ኃላፊነት ሊመጣበት የሚችለው ጥፋትን መሰረት አድርጐ ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2028 እና ተከታዮቹ እንደዚሁም ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊነት ሊመጣበት እንደሚችል ከፍትሐብሔር ህግ ቁ.2066 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ እንደየ ኃላፊነቱ ዓይነት መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የኤሌክትሪክ መስመሩ በራሱ ጉዳት አድርሶ ሳይሆን የጎረቤት የቴሌቪዥን አንቴና በተዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ላይ በመውደቁ እና ከፍተኛ ድምጽ በዚህ ምክንያት በመፈጠሩ ጎረቤቶቹ የድረሱልኝ ድምጽ በማሰማታቸው አመልካች ለእነዚሁ ጎረቤቶች እርዳታ ለማድረግ ሲሄድ ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ኃላፊነት አለበት ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት በደፈናው በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2069 መሰረት አመልካች አውቆ የሰራው ጥፋት ባይኖርም አጥፊ ሳይሆን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በመጥቀስ ነው፡፡

ሆኖም አመልካች ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም?፣ ኃላፊነት አለበት ከተባለስ በየትኛው የህግ አግባብ እንደሆነ ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት ሊጣሩ የሚገባቸው በርካታ ነጥቦች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ መጣራት ካለባቸው ነጥቦች መካከል በተጠሪ ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው አመልካች እንደሚለው የተጠሪ ጎረቤት የቴሌቪዥን አንቴና በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ በመውደቁ ምክንያት ነው ወይስ በሌላ ምክንያት?፣ ጉዳቱ ሊደርስ የቻለው በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ፣ አመልካችን ጥፋት ሳይኖር ኃላፊ ሊያደርጉ የሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎችን ስለመፍጠሩ የሚያመላክት ነጥብ ስለመኖር ወይም አለመኖር፣ ወይም ጥፋትን መሰረት ያደረገ ኃላፊነት ሊያመጣ የሚችል እና አመልካች በስራው ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ ሳያደርግ የቀረ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በግራቀኙ ማስረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች መንጠር የነበረባቸው ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ሳይነጥሩ በዚህ ጉዳይ የበታች ፍ/ቤቶች ወደ ድምዳሜ መድረሳቸው በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 246፣247 እና ተከታዮቹ እንደዚሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ፣ 259 እና ተከታዮቹ ስር የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ጭብጥ ስለመያዝ፣ ክስ ስለመስማት እና ማስረጃን ስለመመርመር በተመለከተ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ዓላማ፣ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ የሰጡት ተገቢው ማጣራት ባልተደረገበት ሁኔታ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የኃላፊነት እና የካሳ ክፍያ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢው መጣራት ሳይደረግበት በመሆኑ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ/ብሔ/ክል/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.50846 በቀን 24-03-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.06278 በቀን 19-2-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡
3. የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርድ ሀተታው በተመለከተው አግባብ የቀረበውን ክስ በግራ ቀኙ ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 69428

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ነገረ ፈጅ አቶ ነጌሣ አሊ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- መሐመድ አባ አሊ
2- ዘሀራ አባኑር } አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ አመልካች እንዲከፍል የሰጡትን ውሣኔ ህጋዊነት አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች ለሞራል ካሣ በድምሩ ከአንድ ሺህ ብር በላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ አመልካች የተጠሪዎች ልጅ በመሞቱ ምክንያት እንዲከፍል የተወሰነበትን የካሣ ገንዘብ በተመለከተ ለሰበር ችሎት ጭብጥ ሆኖ ያልቀረበ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የፀናና ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡

የሞራል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚከፈለው የካሣ መጠን በማናቸውም ሁኔታ ከብር አንድ ሺህ ብር /ብር 1000/ መብለጥ የሌለበት መሆኑን "የጉዳት ካሣውም በማናቸውም ምክንያት ከብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ የበለጠ ሊሆን አይችልም" በማለት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2116 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል፡፡ ይህም በአደጋው ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ብዙ ቢሆንም ለእነርሱ የሚከፈለው የሞራል ካሣ ተደምሮ ከብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ ሊበልጥ የማይገባው መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ልጃቸው በአደጋው በመሞቱ ምክንያት ለደረሰባቸው የሞራል ጉዳት ለእያንዳንዳቸው ብር 1000/ አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ አመልካች የሞራል ካሣ እንዲከፍል

የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2116 ንዑስ አንቀፅ 3 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ብር 52,200 /ሃምሣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ካሣ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ብቻ የሞራል ካሣ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 68613

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሐጂ መሐመድ አመዴ ጠበቃቸው አቶ ብሥራት መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መኮንን መስፍን ጠበቃቸው አቶ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት በሆኑት የአሁኑ ሰበር ተጠሪና 2ኛ የፍርድ ባለ ዕዳ በሆኑት የሰበር አመልካች መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክስ የፍርድ ባለእዳው የሆነው ቤት ለእዳው እንዲሸጥ የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ የፍርድ ባለዕዳው በዋናነት የሚከራከሩት በፍርድ ባለ መብት ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በአራት ተከሣሾች ላይ ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን /እንዲንከፍል የተወሰነብን በመሆኑ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ መክፈል የሚገባኝ ብር 250,000 እና የዚሁ ወለድ ነው በሚል ነው፡፡

የፍርድ ባለመብቱ በበኩላቸው ለፍርድ ባለዕዳው ክርክር በሰጡት መልስ እዳው የመጣው በወንጀል ሀላፊነት በመሆኑ ሀላፊነቱ የሚከፋፈል ባለመሆኑ የፍርድ ባለእዳው ድርሻቸውን ብቻ ለመክፈል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በዋናው ፍርድ የፍርድ ባለዕዳዎቹ ለካሣው ክፍያ ሀላፊነት አለባቸው ስለተባለ የፍርድ ባለእዳው ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የማይጠየቁበት ምክንያት የለም ብሏል፡፡ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለዕዳው ያቀረቡትን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አመልካችም በሰበር ቅሬታቸው በዋናነት የጠቀሱት የፍርድ ባለዕዳዎቹ ሀላፊነት ያልተነጣጠለ ነው ከተባለ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ መሠረት ያላደረገ ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች ገንዘቡን ከፍለው ከሌሎች የፍርድ ባለዕዳዎች ከሚጠይቁ በስተቀር በድርሻቸው ብቻ ለመክፈል ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ያልተነጣጠለ ሀላፊነት ስላለባቸው በአፈጻጸም ክስ የቀረበውን ገንዘብ መክፈል አለባቸው በሚል የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለዚህ አፈፃፀም ክስ መነሻ የሆነውን ፍርድ በመ/ቁ 11789 የሰጠው የፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን የቀበረውም ክስ የአሁኑን የሰበር አመልካች ጨምሮ በመዝገቡ ተከሣሾች የሆኑት በከሣሽ ንብረት ላይ ላደረሱት ጉዳት ብር 1,457,934.50 ባልተነጣጠለ ሀላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንባቸው የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሁኑን የሰበር አመልካች ጨምሮ 4 ተከሣሾች ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለባቸው በሚል ብር 1,000,000/አንድ ሚሊዮን ብር/ ክሱ ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለከሣሽ ይክፈሉ ብሎ መወሰኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይ አመልካች እና በመዝገቡ ሀላፊነት አለባቸው የተባሉ ተከሣሾች ገንዘቡን እንዲከፍሉ ከመወሰኑ በስተቀር አከፋፈሉን በተመለከተ ሀላፊነት አለባቸው የተባለውን የገንዘብ መጠን እያንዳንዳቸው ድርሻቸውን እንዲከፍሉ በሚል በግልጽ ተለይቶ አልተወሰነም፡፡ የአመልካች የክስ አቀራረብም ቢሆን የጉዳቱን መጠን በገንዘብ ተምኖ በማቅረብ ተከሣሾቹ ባልተነጣጠለ ሀላፊነት እንዲከፍሉ የሚል እንጂ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ በድርሻቸው ከፋፍለው አልጠየቁም፡፡ በፍ/ህ/ቁ 2155/1/ ብዙ ሰዎች አንድ በሆነ ጉዳይ ለደረሰው ጉዳት ካሣን እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ በአንድነት እያንዳንዳቸው ሀላፊ እንደሚሆኑ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የካሣው አከፋፈሉም ቢሆን ለበደሉ ተግባር አነሳሽ በሆነው ፣ በዋናው ወንጀል አድራጊና በበደሉ ተግባር ተባባሪ በሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት የማይደረግ መሆኑን በዚሁ በተጠቀሰው ደንጋጌ በንዑስ ቁጥር 2 ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ባልተነጣጠለ ሀላፊነት በአፈጻጸም የማይገደዱበት ምክንያት የለም በሚል ዕዳውን በድርሻቸው መጠን ለመክፈል ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጉ ዋናውን ፍርድ መሠረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ በፍ/ህ/ቁ 2155 ስለአንድነት ሀላፊነት የተደነገገውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝም ሆነ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ በማጽናት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 56822 በቀን 30/6/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 67086 በቀን 03/09/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ያልተነጣጠለ ሀላፊነት ያለባቸው ስለሆነ የአፈፃፀም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገደዳሉ በሚል የፌ/ከ/ፍርድ ቤትና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወሰኑት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ባልተነጣጠለ ሀላፊነት የተወሰነባቸውን ገንዘብ ከከፈሉ በኋላ ከድርሻቸው በላይ የከፈሉትን ገንዘብ ከመጠየቅ ይህ ውሣኔ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤትን ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 65395

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ ትዕዛዝ ኮሬ አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረ ፈጅ አቶ ገብረ መድህን ባህታ

ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ስለመጠየቅና የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከካሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ተከራይቶ የንግድ ሥራ የሚያከናወንበት የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/05 ቁጥር 382 በሆነ ቤት የሚያከናውነው "ዮድ አቢሲኒያ የባህል ምግብ አዳራሽ" የሚል የንግድ ስም የሚጠራ ድርጅት ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ተከሳሹ /ተጠሪ/ ሊቆጣጠረው በሚገባው የኤሌትሪክ መስመር ላይ የተፈጠረው ብልሽት ባስከተለው ቃጠሎ በንብረቱ ላይ ውድመት ደርሶብኛል፡፡ ስለዚህ ለጉዳቱ ተከሳሽ ኃላፊ በመሆኑ ብር 1,024,563.02 /አንድ ሚሊዮን ሃያ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሣ ሶስት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የእሳት አደጋው ደርሶ ንብረቱ ከመውደሙ በፊት የተበጠሰ ኤሌትሪክ የለም፡፡ የቃጠሎው ምክንያት ኤሌትሪክ ስለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ መስመሩ ሲዘረጋ የንግድ ድርጅቱ አልነበረም ስለዚህ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም የሚል የፅሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ለመመሥረት እንዲመቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አመልካች ተጠሪ ላደረሰው ጉዳት በጥፋት ላይ የተመሠረተ ኃላፊነት አለበት፡፡

የኤሌክትሪክ መስመሩ ተበጥሶ በከሳሽ ድርጅት ላይ በማረፉ ምክንያት የእሳት ቃጠሎ የተነሳ በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተከሳሽ /ተጠሪ/ በበኩሉ እሳቱ የተነሳው የኤሌትሪክ መስመሩ በመበጠሱ ምክንያት አይደለም፡፡ የኤሌትሪክ መስመሩ ያልተበጠሰ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብንም የሚለው የመከራከሪያ ነጥባቸው መሆኑን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረቡት የቃል ክርክር አስመዝግበዋል፡፡

አመልካች /ተከሳሽ/ የእሳት ቃጠሎው የተነሳው ተጠሪ /ተከሳሽ/ ከዘረጋው የኤሌትሪክ መስመር መሆኑን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የፅሑፍና የሰው ምስክሮች አቅርቧል፡፡ ተጠሪም የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ከዚህ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ኃላፊነት አለበት ከተባለ ተከካሽ ለከሳሽ ምን ያህል ካሣ ሊከፍል ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች በመመሥረት፣ ከሳሽ የተከሳሹ ኃላፊነት በጥፋት ላይ የተመሰረተ ነው ብሏል፡፡ የከሳሽ የሰነድ ማስረጃዎች ድርጅቱ የተቃጠለው ከሣሽ በዘረጋው የኤሌትሪክ መስመር መሆኑን ያሣያሉ፡፡ የከሳሽ የሰው ምስክሮችም ቃጠሎም የደረሰው የኤሌትሪክ መስመሩ ተበጥሶ በቤቱ ቆርቆሮ ላይ ከወደቀ በኋላ በተፈጠረው እሳት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ከሳሽ ቃጠሎው የደረሰው ተከሳሽ ሆን ብሎ ወይም በቸልኝነት በፈፀመው ተግባር መሆኑን "የማያስረዱ" በመሆኑ ተከሳሽ ለጉዳቱ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን ስላላስረዳ የተከሳሹን ማስረጃ ታዓሚነትና ክብደት መመርመር አስፈላጊ አይደለም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት የእሳት ቃጠሎው የተነሳው አመልካች በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የኤሌትሪክ መስመር ተበጥሶ በቤቱ ጣሪያ ላይ በማረፉ ምክንያት መሆኑን አመልካች በማስረጃ እንዳረጋገጠ በውሣኔው ውስጥ በግልፅ አስፍሯል፡፡ ተጠሪ በባለቤትነት የያዛቸው የሚያዝባቸውና የሚቆጣጠራቸው የኤሌትሪክ መስመሮች በተለያዩ ምክንያቶች ተበላሽተው ወይም ተበጥሰው በሌላው ሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋ እንዳያደርሱ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የተጠሪ የኤሌትሪክ መስመር አደጋው ከመድረሱ በፊት ደርሶበት አመልካች ሪፖርት አድርጎ ከተጠገነ በኋላ ተጠሪ ያደረገው ጥገና አስተማማኝ ባለመሆኑ ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን አስረድቻለሁ፡፡ ይህም የተጠሪን ቸልተኝነት የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ ሣይመዝን ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከፖሊስ ያቀረቡትን ማስረጃ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ የኤሌትሪክ መስመሩ ባለቤት ስለሆነ ብቻ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ አይገባም፡፡ የእሳት ቃጠሎው የተነሳው ከተጠሪ የኤሌትሪክ መስመር ሳይሆን በአመልካች ወጥ ቤት በተነሣ የእሳት ቃጠሎ ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ ሙያዊ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም

በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰንና የሥር ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ተገቢውንና ትክክለኛውን ጭብጥ የመሠረተና የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ለመረዳት እንድንችል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 74139 በትዕዛዝ በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ የተገለፀውን መሠረታዊ ጭብጥ ተጠሪ የኤሌትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈልና የኤሌትሪክ ኃይል የመሸጥ ተግባር ሲያከናወን በምን ዓይነት የጥራት ደረጃ /quality standard/ ማከናወን አለበት የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ማንኛውም ኤሌትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራዎችን እንዲሠራ የተፈቀደለት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 86/1989 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ በሚመለከት የወጡ ሕጐችንና በኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ የተወሰኑትን የጥራት ደረጃዎች በማክበር ሥራውን ማከናወን እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 86/1989 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ የኤሌትሪክ አቅርቦትን የመስመሮች እና የመሣሪያዎች ደህንነት በሚመለከት አቅርቦት፣ መስመሮችና መሣሪያዎች በተዘረጉበት የአካባቢ ሁኔታዎች የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በቂ ኃይል የመሸከምና የኢንሱሌሽን ብቃት እንደዚሁም በብልሽት ወቅት ሊከሰት የሚችለውን የኤሌትሪክ መጠን የመቋቋም ችሎታና በቂ የመካኒካል ጥንካሬ ደረጃ ሊኖራቸውና በሰው፣ በእንስሳት በንብረት ላይ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ሊገነቡ፣ ሊገጣጠሙ፣ ሊጠበቁና ሊጠገኑ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 86/1989ን ለማስፈፀም የሚኒስሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀፅ 35 የሚደነገግ ሲሆን ማንኛውም ኤሌትሪክ ለመሥራት ለማሰራጨትና ለመሸጥ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ሥራውን ሲያከናውን የሰውን ሕይወት፣ ንብረትና የአካባቢ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ እንዳለበት በደንብ ቁጥር 49/91 አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች አደጋው ከመከሰቱ በፊት በመስመሩ ላይ ብልሽት ተከስቶ የነበረና ይህንንም ለተጠሪ አመልካችና ሌሎች በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች አሳውቀው ተጠሪ መስመሩን የጠገነ መሆኑን፣ ተጠሪ የጥገና ሥራውን ካከናወነ በኋላ የኤሌትሪክ መስመሩ ተበጥሶ ከአመልካች ድርጅት ቆርቆሮ ላይ በማረፉ የእሳት አደጋ በማስነሳቱ አመልካች መስመሩን በንብረት ላይ ጉዳት በሚያስከትል ሁኔታ የመጠገንና የመጠበቅ ግዴታውን ባለመወጣቱ ንብረቱ ወድሞብኛል፣ ተጠሪ ኃላፊነት አለበት በማለት በቃልና በፅሑፍ ያቀረበ ቢሆንም በቃል ክርክር ወቅት ዋናው የመከራከሪያ ጭብጡ በአመልካች ድርጅት ላይ ውድመት ያስከተለው የእሳት አደጋ በኤሌትሪክ መስመሩ ብልሽት ወይም መበጠስ ምክንያት የደረሰ አይደለም የሚለው ነጥብ እንደሆነ ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም በትራንስክራይበር ማሽን የተቀዳውና በፅሑፍ ተገልብጦ ከሥር ፍርድ ቤት ጋር ከተያያዘው የተጠሪን ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አንድ ፍርድ ቤት የክርክሩን ጭብጥ የሚመሰርተው ከሳሽ ያቀረበውን የክስ ማመልከቻና ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸውን የፅሑፍ ማስረጃዎች ተከሳሽ ያቀረበውን የመከላከያ መልስና የመከላከያ ማስረጃዎች እንደዚሁም ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የቃል ምርመራ ሲያደርግ ተከራካሪዎች ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ መሆን እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች በግልፅ ይደነግጋሉ፡፡ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ለተነሳው የእሳት አደጋ ዋናው መንስኤ አመልካች በአግባቡ ሊጠብቀውና ሊጠግነው ከሚገባው የኤሌትሪክ መስመር የኤሌትሪክ ሽቦ ተበጥሶ በአመልካች ድርጅት የጣሪያ ሽፋን /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ነው ወይስ አይደለም?

በሚለው ነጥብ ላይ ሰፊ ልዩነት ያላቸው መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት በቃልና በፅሑፍ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ሊመሰርተው የሚገባው ጭብጥ የእሳት አደጋው የተከሰተው በኤሌትሪክ መስመሩ ብልሽትና የኤሌትሪክ ሽቦው ተበጥሶ በአመልካች ድርጅት የጣሪያ ክዳን /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ነው? ወይስ በአመልካች ኩሽና በተከሰተ ድንገተኛ የእሳት አደጋ የሚለው ጭብጥ መሆን ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችን ብቻ ሣይሆን ተጠሪ ይህንን ጭብጥ ለማስረዳት ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች መመርመርና ተጠሪ ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ስማቸውን የጠቀሳቸውንና የሰማቸውን ሁለት ምስክሮች ቃል መመርመርና መወሰን ይገባዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የእሳት አደጋው የተከሰተው ተጠሪ በሚያስተዳድረው የኤሌክትሪክ መስመር ላይ በተከሰተ ብልሽትና የኤሌትሪክ ማስተላለፊያ ሽቦው ተበጥሶ ከአመልካች ድርጅት የጣሪያ ክዳን /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ምክንያት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ፣ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 86/1989፣ በደንብ ቁጥር 49/91 እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ ያወጣቸውን የጥራት ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ አሟልቶ መስመሩን የመጠገንና የመጠበቅ ግዴታውን የተወጣ መሆኑን የማስረዳት ሸክሙን ተዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ በማቅረብ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ጭብጥ በመመዘን፣ አመልካች በተጠሪ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ምክንያት ለተከሰተው የእሳት አደጋና በንብረት ላይ ለደረሰው ውድመት ተጠሪ በኃላፊነት ሊጠየቅ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክስ መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ሲገባው፣ የሥር ፍርድ ቤት ትክክለኛውን ጭብጥ ሣይመሰረት፣ ተጠሪ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫው ስማቸውን የገለፃቸው ምስክሮች ቃል ሣይሰማና የፍታብሔር የማስረጃ ምዘና መርህን መሠረት በማድረግ ከአመልካችና ከተጠሪ የተሻለና ሚዛን የሚደፋ ማስረጃ ያቀረበው የትኛው ነው? የሚለውን ነጥብ ይዞ የአመልካችና የተጠሪን ማስረጃ ተዓሚነትና ክብደት ሣይመዝን የአመልካችን ማስረጃ ብቻ በመመርመርና በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ ስለ ጭብጥ አመሰራረት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 246፣ 247 እና 248 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ጉዳይ የተሻለና ሚዛን የሚደፉ ማስረጃ ያቀረበው ጉዳዩን እንዳስረዳ ይቆጠራል የሚለውን የፍታብሔር የማስረጃ አመዛዘን መርህ ያልተከተለና የተጠሪን የመከላከያ ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ተዓሚነትና ክብደት አልመረመረም፣ አልመዘነም፡፡ እንደዚሁም የሥር ፍርድ ቤት በወቅቱ በአካባቢው ተጠሪ የኤሌትሪክ ኃይል የማከፋፈል፣ የማሰራጨትና የመሸጥ ሥራ ሲያከናውን ሊያደርጋቸው የሚገቡ ቴክኒካል፣ ሜካኒካልና ሌሎች የጥንቃቄ መስፈርቶችን ያሟላ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 86/1989፣ ደንብ ቁጥር 49/1991 እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ ያወጣቸውን የጥራት ደረጃዎች መሠረት በማድረግ መመርመርና መመዘን ሲገባው ይህንን ያላደረገ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የፈፀማቸውንና ከላይ የዘረዘናቸውን ስህተቶች ሣያርም ውሣኔውን አፅንቶታል፡፡

በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በጉዳቱ በኃላፊነት አይጠየቅም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ድርጅት ላይ የደረሰው የእሳት አደጋ መንስኤ /ምክንያት/ ተጠሪ የሚያስተዳድረው የኤሌትሪክ መስመር ሽቦ ተበጥሶ ከአመልካች ድርጅት ጣሪያ /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ነው ወይስ አይደለም? አደጋው የደረሰው የኤሌትሪክ መስመሩ ተቆርጦ በተጠሪ ጣሪያ /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ምክንያት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ፣ ተጠሪ በአካባቢው የኤሌትሪክ ኃይል ሲያሰራጭ፣ መስመሩን ሲዘረጋና እድሳት ሲያደርግ በአዋጅ ቁጥር 86/1989፣ በደንብ ቁጥር 49/1991 እና በኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ የወጡትን የጥራት ደረጃዎች በማሟላት አገልግሎቱን የሰጠ መሆኑንና ተጠሪ ማድረግ የሚገባውን ማናቸውንም ጥንቃቄ ያደረገ መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያስረዳል ወይስ አያስረዳም? ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ የተወጣ መሆኑን ካላስረዳ ለደረሰው ጉዳት ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት በኃላፊነት ይጠይቃል ወይስ አይጠየቅም? ተጠሪ በኃላፊነት ይጠየቃል ቢባል ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ስንት ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝና የአመልካችንና የተጠሪን የፅሑፍ ማስረጃና የምስክሮች ቃል በመመርመርና በመመዘን አስፈላጊም ከሆነ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ ሙያዊ ማብራሪያ እንዲያቀርብ በማድረግ በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
4. በትውስት የመጣው የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ- 74111

ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የማህደር ኤጀንሲ ባለቤት ወ/ሮ አለምነሽ ኤርሞ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሪት አለም መስፍን ተወካይ ገበየ ደጉ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሣሽ ከሣሽን ወደ ቤይሩት ለስራ ብር 8000 በማስከፈል የተከች ሲሆን አሰሪዬ ከ3ኛ ፎቅ ወርውራኝ በግራ እግሬ ላይ 30% ዘላቂ ጉዳት ደርሶብኛል፣ በተጨማሪም አሰሪዬ የስድስት ወር ደመወዝ በወር 100 ዶላር ወይም ብር 1300 ያልከፈሉኝ ሲሆን ለህክምና እና ትራንስፖርት እንዲሁም ለምግብ ወጪ አውጥቼያለው፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ ለደረሰብኝ ጉዳት ኃላፊ ስለሆነ ወደፊት በወር ብር 130 የቀረብኝ ሆኖ ለ33 ዓመት በጉዳት ምክንያት ያጣሁትን እና ሌሎች ወጪዎችን ጨምሮ ብር 200430 /ሁለት መቶ ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ብር/ ተከሣሽ እንዲከፍል እንዲወስንልኝ የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሣሽ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ ተከሣሽ ብር 8000 /ስምንት ሺህ ብር/ አልተቀበለም፣ ተቀብሎ ቢሆንም ይመልስልኝ ማለት አይችሉም፣ በአሠሪያቸው ያልተከፈላቸው ደመወዝም የለም፣ የስድስት ወራት ደመወዝ በዌስተርን ዩኒየን ለአቶ አያልነህ ገና ተልኳል፡፡ የከሣሽ ደህንነት እንዲጠበቅ ተገቢውን አድርገናል፣ አሰሪዋ ከፎቅ የወረወረቻት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ ተከሣሽም በሰብአዊነት አሣክሜያታለሁ እንደዚሁም ጉዳቱ የደረሰው ከካንሰር በሽታ ጋር በተያያዘ እንጂ በመውደቋ ባለመሆኑ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክራለች፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመቀበል ጉዳቱ የደረሰው በመውደቋ ምክንያት ስለመሆኑ የቀረቡት ማስረጃዎች አያስረዱም በማለት የተጠየቀውን የጉዳት ካሣ ክስ ውድቅ ሲያደርግ ተከሣሽን ወደ ውጭ አገር ለመላኪያ በሚል ብር 8000 /ስምንት ሺህ ብር/ በአዋጅ ቁ. 632/2001 መሰረት መቀበል የሌለባቸውን የተቀበሉ በመሆኑ ለከሣሽ እንዲመልሱ እና የከሣሽን ደመወዝ በተመለከተ የስድስት ወራት ደመወዝ ስለመላኩ ማስረጃ ስለቀረበ ሁኖም ግን ከሣሽ የሰራችው ለ11 ወራት በመሆኑ የቀሪዎቹን የ5/አምስት ወራት/ ደመወዝ ተከሣሽ እንዲከፍሏት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተጠሪ በተላከችበት አገር አሰሪዋ ከ3ኛ ፎቅ ላይ ተወርውራ በእግሯ ላይ ጉዳት የደሰረ ስለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት በዊልቸር እየተንቀሳቀሰች እንደሆነ ከማረጋገጡ በላይ የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ አመልካች ከቤይሩት አገር አስመጡ የተባለው እና ተጠሪ ከጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ያቀረቡት የህክምና ማስረጃዎች ሲሆን 30% ቋሚ የአካል ጉዳት የደሰረባት ስለመሆኑ ስለሚያመላክቱ አመልካች ከሰጠችው የምስክርነት ቃል ጋር አንድ ላይ ስንመለከት በአሰሪዋ ከፎቅ ላይ በመወርወሯ ምክንያት ከላይ የተመለከተው ጉዳይ የደረሰባት ስለመሆኑ ያረጋግጣል በማለት 157440/ አንድ መቶ ሃምሣ ሰባት ሺህ አራት መቶ አርባ ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንድትከፍል በማለት ክፍያው የሚፈጽምበትን አግባብ በማመላከት እና የሞራል ካሣ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በተጨማሪ እንዲከፈላት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙ ክርክር በጽሑፍ ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊት አለባቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር በሚል በመሆኑ የተያዘው ጉዳይ በዚህ መልኩ ቀደም ሲል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ አገልግሎት ሥራ የተሰማራ እንደመሆኑ መጠን የአዋጅ ቁ. 632/2001 አጠቃላይ ንባብ መገንዘብ እንሚቻለው በተለይ ወደ ውጭ አገር ለስራ የሚሄዱ ኢትዮጵያዊያን መብታቸው፣ ድህንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆላቸው ወደ ስራ የሚሰማሩበትን አግባብ ለማመቻቸት በመሆኑ እና ይሄንንም ኃላፊነት መወጣት ያለባቸው በዚሁ ስራ የተሰማሩት እንደአመልካች ዓይነት ድርጅቶች ስለመሆናቸው ያስገነዝባል፡፡ አመልካችም ቢሆን በበታች ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የተጠሪ ድህንነት እንዲጠበቅ ተገቢውን ሁሉ አድርጌአለሁ በሚል እንጂ ኀላፊነት የለብኝም በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ አሰሪዋ ላደረሰችው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በሚል የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው የደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት ከምን የተነሣ እንደሆነ አመልካች ተጠሪ ባለባት የካንሰር በሽታ እንጂ በመውደቅ የደረሰ አይደለም በሚል ተከራክራለች፡፡ ተጠሪ በበኩሏ ጉዳት የደረሰብኝ አሰሪዬ ከ3ኛ ፎቅ ላይ ስለጣለችኝ የደረሰብኝ ነው በማለት ተከራክራለች፡፡ ይሄን ክርክር በተመለከተ በተለይ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በመውደቋ ምክንያት ቋሚ 30% የአካል ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል ወደ ሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡ ይሄው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ፀንቷል፡፡ በተጠሪ አካል ላይ የደሰረው ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰው በመወድቅ ምክንያት ነው ወይስ በሌላ ምክንያት የሚለውን ክርክር ደግሞ የፍሬ ነገር እንጂ የመሠረታዊ የህግ ስህተት ክርክር ባለመሆኑ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ሊነሣ የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ የክርክር ነጥብ ላይ ደግሞ የበታች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ የደረሰው በደረሰባት የመውደቅ አደጋ ምክንያት እንደሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ማስረጃን

መመዘን እና ፍሬ ጉዳይን ማጣራት ደግሞ የበታች ፍርድ ቤቶች ስልጣን በመሆኑ እና የዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማቃናት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ. ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10 ስር የተመለከተ በመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደረሰበትን ድምዳሜ እንዳለ የምንቀበለው ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት በመውደቋ ሣይሆን በሌላ በሽታ ምክንያት ነው በማለት የምታነሣው ክርክር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ የሚስተናገድ ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡ አመልካችም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባት ተብሎ ለተጠሪ ካሣ እንድትከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡

ባጠቃላይ የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት አመልካች ኃላፊነት አለባት በማለት ካሣ እንድትከፍል መወሰኑ እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንን ውሣኔ ማጽናቱ በአግባቡና የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 72389 ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 103953 ሐምሌ 06 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት ኃላፊነት አለባት በማለት በፌ/የከፍተኛ እና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ታህሣስ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

# ጉምሩክ

# /ቀረጥ/

# ግብር

የሰ/መ/ቁ. 54889

መስከረም 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ህግ አቶ ሽመልስ አበበ

ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ገብረፃዲቅ - ጠበቃ አቶ አበበ ታዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሻሽሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 64/4 እንደተሻሻለ በመተላለፍ የጋራ ንብረቱ በሆነውና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ የሆነውን መኪና በሹፌርነት እያሽከረከረ እያለ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ በህግ የተከለከለ ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ከቡታጅራ ወደ አዲስ አበባ ለማስገባት ሲሞክር ነሐሴ 1 ቀን 2000 ዓ.ም. ከሌሊቱ ዘጠኝ ሠዓት ሰበታ ከተማ ስለተያዘ የጉምሩክን ህግ የመጣስ ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪ ሲያሽከረክረው በነበረው መኪና ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ተጭኖ የተገኘ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ እንዲሁም ወንጀሉ የተፈፀመበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ የሆነው መኪና የተጠሪው የአቶ ንጉሴ ገ/ፃዲቅ እና የአቶ ጌታቸው ገዛኸኝ የጋራ ሀብት መሆኑን የሚያስረዳ የመኪናውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ደብተርና ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የተፃፈ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በወቅቱ እሱ ወባ ተነስቶበት ታሞ የነበረ መሆኑን ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ከእኔ እውቅና ውጭ የተጫነ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኂላ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው ክስ የጠቀሰውን አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 64/4/ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 113/2/ መሠረት ወደ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 74 በመለወጥ ተጠሪ ከላይ የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 74 እንደተሻሻለው በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን

የቅጣት አስተያየት ከሰማ በኋላ ተጠሪ በሶስት ዓመት እስራት እንዲቀጣና የተያዘው ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያለበት የህግ ድንጋጌና የሰጠውን የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 60/89 እና የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ የተደነገገውን በመተላለፍ በሀላፊነት ይዞ በሚያሽከረክረውና የጋራ ንብረቱ በሆነው መኪና ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ይዞ መገኘቱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የመጓጓዥያ ሀላፊ የሚለው ሀሳብ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2/14/ ግልፅ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ድንጋጌ በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት ማንኛውም መጓጓዥያ በጉዞ ላይ እንዳለ እንዲይዝ፣ እንዲቆጣጠር ወይም ሥራውን እንዲመራ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ወኪሉን የሚያጠቃልል መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የተጠሪ አድራጎት በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 በአንቀፅ 64/4/ እንደተሻሻለው የሚሸፍን ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የህጉን ድንጋጌ ግልፅ ይዘት በመተላለፍ ተጠሪ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 የተመለከተውን በተመላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት ተይዞ የነበረው መኪና ለተጠሪ እንዲመለስለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 79፣ አንቀፅ 80/1/ አንቀፅ 81 የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲሻሽልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታህሣሥ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መልስ በመኪናው ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ ተገኝቷል በተባለበት ዕለት በመኪናው ውስጥ የነበርኩ ቢሆንም እኔ ወባ ታምሜ ስለነበረ ህጋዊ መንጃ ፈቃድ ያለው የመኪና ረዳት ሹፌር አቶ ሀይሉ ቢሰጠኝ መኪናውን ያሽከረክር እንደነበርና ልባሽ ቦንዳ ጨርቁ በመኪናው ላይ መጫኑን የማላውቅ መሆኔን በመከላከያ ማስረጃ አስረድቻለሁ፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ባቀረበው የወንጀል ክስ የጠቀሰውን የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4 ድንጋጌ በመለወጥ በአዋጁ አንቀፅ 74 በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ብለው የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔና ትዕዛዝ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪ የጋራ ንብረቱ በሆነውና በወቅቱም በሀላፊነት ይዞት በነበረው መኪና ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ መገኘቱን የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ አረጋግጧል፡፡ ይህ የተጠሪ አድርጎት በየትኛው የህግ ድንጋጌ ያስጠይቃል የሚለውን ስንመለከት "በማጓጓዣው የውጭም ሆነ የውስጥ አካል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ክልከላ፣ ገደብ ወይም ቁጥጥር የተደረገበትን ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃን ሲያጓጉዝ ከተገኘ ይህንን የወንጀል አድራጎት ለመከላከል ተገቢነት ያላቸውን ጥንቃቄዎች ሁሉ መውሰዱን ካላሥረዳ ዕቃው ወይም ማጓጓዥያው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ የማያንስ የገንዘብ መቀጮ እና ከአሥራ አምስት እስከ ሀያ ዓመት በሚደርስ

እስራት ይቀጣል በማለት በደነገገው በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4 ድንጋጌ የሚሸፈን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት የማንጓኸርያ ሀላፊነትን የሚደነግገውን የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4 በመጥቀስ አመልካች ያቀረበውን ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2/ በመቀየር ተጠሪ ህገ ወጥ ዕቃዎችን ይዞ ስለመገኘት በሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 74 ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ የተጠሪን ግዙፍ ተግባር ሞራላዊ ሁኔታ አግባብነት ካለው የህጉ ድንጋጌ ጋር ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2//ለ-2/ መሠረት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋኝነት ውሣኔ በማሻሻል ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 64/4 የተደነገገውን በመተላለፍ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ የጋራ ባለሀብት በሆነበት መኪና ሲያስገባ የተያዘ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

የቅጣቱን መጠን በተመለከተ፣ ተጠሪ በሶስት ዓመት እስራት እንዲቀጣና የተያዘው ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ እንዲወረስ የበታች ፍርድ ቤቶች ወስነዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ከዚህ የቅጣት ውሣኔ በተጨማሪ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ድንጋጌ መሠረት ተጠሪ አቶ ጌታቸው ገዛኸኝ ጋር የጋራ ባለንብረት የሆነበት የሰልዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ የሆነው መኪና ላይ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ ሊወረስ እንደሚገባው ከህጉ ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሣኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ ላይ ያለው የባለሀብትነት ድርሻ ተወርሶ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2/መ/ መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከአቶ ጌታቸው ገዛኸኝ ጋር የጋራ ባለሀብት የሆነበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ በመሆነው መኪና ላይ ያለው ድርሻ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 64/4 መሠረት ወስነናል፡፡
3. ይኸ ውሣኔ አቶ ጌታቸው ገዛኸኝ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ በሆነው መኪና ላይ ያላቸውን ግማሽ የጋራ ባለሀብትነት የሚነካ አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ. 64115

ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡-1. አቶ አህመድ ሁሴን
2. አዞ ግሎባል ኃ.የተ.የግል ማህበር
} ጠበቆች ወርቅነህ በረደድና ሙሉጌታ ወንድም አገኘሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - ዐ/ህግ ፍስሐ ዓለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የጉምሩክ ወንጀልን ተከትሎ ሊጣል ስለሚገባው ቅጣትና ፍርድ ቤቱ በቅጣት አጣጣል ሊከተለው ስለሚገባው ስርዓት የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾችና በሌሎች አምስት ሰዎች የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93(1(መ) እና (2) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በአመልካቾች አማካኝነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ የባትሪ ድንጋይ ባልተሟላ ሰነድ ቀረጥና ታክስ ሳይከፍሉ ፣ ፍተሻ ሳይደረግ ፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይጠናቀቅ በማን እንደተዘጋጀ ባልታወቀ የእቃ መልቀቂያ እንዲለቀቅ በማድረግ የጉምሩክ ማጭበርበር ወንጀል ፈፅመዋል፣ እንዲሁም በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 97 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከላይ የተገለፀውን እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት እንዲቆይ በማድረጋቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓትን የማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ክሱን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች የወንጀል ድርጊቶቹን ስለመፈፀማቸው አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ በማመን አመልካቾች እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቶ አመልካቾች አሉን ያሏቸውን ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የተከሰሱባቸውን ወንጀሎች ያለመፈጸማቸውን በመካላከያ ማስረጃዎቻቸው አስረድተዋል ፣ በዚህም ምክንያት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አስተባብለዋል በሚል ምክንያት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 149(2) መሰረት ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ኢግዚብትን በተመለከተ ግን 1ኛ አመልካች በማጭበርበር ስራ ባይሳተፉም እንደባለንብረት ተከታትለው ጉዳዩን ከማስፈጸም አንፃር ያደረጉት ጥረት ስለመኖሩ አላስረዱም በማለት ንብረቱ ሊመለስላቸው የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲል በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 106 መሰረት ለመንግስት እንዲወረስ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን

ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ሀ)) ስር የተመለከተው መሆኑን በመለየት በስር ፍርድ ቤት ንብረቱ ለመንግስት ውርስ ይሁን ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሕጋዊ መሆኑን በመቀበል ውሳኔን በውጤት ደረጃ አንፅቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካቾች ከወንጀል ተግባሩ ነፃ ተብለው ከተወሰነ በሁዋላ በኢግዚቢትነት የተያዘው እቃ በመንግስት እንዲወረስ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ለ)) ድንጋጌ አኳያ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ከተከሰሱበት ወንጀል ነጻ የተሰናበቱ ቢሆንም በተጠሪ መስሪያ ቤት የነበረው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ሀ)) መሰረት ሊወረስ ይገባል የመባሉን አግባብነት ከተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 104(3(ለ)) ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ከሌሎች ሰዎች ጋር በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበባቸው 1ኛ አመልካች ወደ ሀገር ውስጥ ባትሪ ድንጋይ ለማስገባት በዲክላራሲዮን ቁጥር C-22074 በስር ተከሳሽ በነበሩት የጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅትና ሰራተኞች አማካኝት ዲክላራሲዮን ሲቀርብ ለጉምሩክ ባለስልጣን የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ለሚቀርበው ዲክላራሲዮን ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበው የእቃ ማስጫኛ ሰነድ( packing list/ ብዛቱ 60,480 ደርዘን ኦሴል ባትሪ ድንጋይ ወደ አገር ውስጥ እንደሚገባ የሚገልፅ ሰነድ ለውጭ ምንዛሪ ማስፈቀጃ ለአቢሲኒያ ባንክ በሚቀርበው 100,800 ደርዘን ኦሴል ባትሪ ድንጋይ ወደ አገር ውስጥ እንደሚገባ አድርጎ በማቅረብ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ያልተፈፀመበትና የቀረጥና ታክስ መጠኑ ብር 278,247.09 (ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሰባት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሳንቲም) ሳይከፈልበት በ2ኛ አመልካች መጋዘን በተደረገ ብርበራ ብዛቱ 4200 ካርቶን የሆነ ኦሴል ባትሪ ድንጋይ ተከማችቶ በመገኘቱ የጉምሩክ ማጭበርበር ወንጀልና የጉምሩክ ስነሥርዓትን የማሰናከል ወንጀል ተከሰው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አስተባብለዋል በማለት በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን ፣ ለወንጀል ድርጊቶች መሰረት የሆነውን የባትሪ ድንጋይ ግን ለመንግስት እንዲወረስ በማለት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በክፍል አራት በጉምሩክ ሥራ ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ይኸው የአዋጁ ክፍል በምዕራፍ አንድ በባለስልጣኑ ሠራተኞች ስለሚፈፀሙ ወንጀሎችና ቅጣታቸው ሲደነግግ በምዕራፍ ሁለት ስር በተለይም ከአንቀፅ 92 እስከ 108 ድረስ በተደነገጉት ድንጋጌዎች በሌሎች ሰዎች ስለሚፈፀሙ የጉምሩክ ወንጀሎችና የቅጣት አይነትና መጠን እንዲሁም ስለፍርዱ ቤቱ ስልጣን የሚደነግግ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የበታች ፍርድ ቤቶች የቅጣት ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 104(3(ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት ማድረጉ

ያሳግባብ ነው ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የአዋጁ አንቀጽ 104(3(ለ)) ስር የተመለከተው ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ሁለቱ ንዑስ ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ወይም ነጻ የማድረግ ውሳኔ በውርስ ላይ ስለሚኖረው ውጤት በሚደነግገው አንቀጽ ስር ያሉ ሲሆን ተፈጻሚ የሚሆኑበት አግባብ የተለያየ መሆኑን የድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 104(3(ሀ)) ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው የአዋጁን ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው በነፃ የተሰናበተ ከሆነ ፍርድ ቤቱ እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት ስለመሆኑ የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካገኘው የውርስ ትዕዛዝ የሚሠጥበትን አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በፊደል "ለ" ስር የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት ስለመሆኑ የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት እቃው ወይም ማጓጓዣው ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰው እንዲመለስ የሚደረግበትን አግባብ የሚደነግግ ነው፡፡ ሁለቱ ድንጋጌዎች ይዘታቸው ሲታይ የሚፈጸሙበት አግባብ እጅጉን የተለያየ ነው፡፡ በጉምሩክ ወንጀል የተከሰሰ ሰው በነፃ የተለቀቀ ቢሆንም ወንጀሉ የተፈጸመበት እቃ ወይም ማጓጓዣ የሚወረሰው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት ስለመፈፀሙ ፍርድ ቤቱን የሚያጠግብ ማስረጃ ሲቀርብ ሲሆን ማስረጃው አጥጋቢ ካልሆነ ብቻ ፍርድ ቤት እቃውን ወይም ማጓጓዣውን እንዳይወረስ በማድረግ ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ሊያዝ የሚገባው መሆኑን ድንጋጌዎቹ እንደየቅደምተከተላቸው ያሳያሉ፡፡ ለጉዳዩ የቀረበው ማስረጃ አጥጋቢ መሆን ያለመሆኑ ደግሞ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ለወንጀሉ ክስ መሰረት የሆነው የባትሪ ድንጋይ በአዋጁ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2(1) ስር ስለእቃ የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟላ ሲሆን ከአመልካቾች ጋር በስር ፍርድ ቤት ተከሰው በነበሩት የተወሰኑት ሰዎች የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ በስር ፍርድ ቤት የተያዘው ንብረት የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ ባቀረበው ማስረጃ በአጥጋቢ ሁኔታ ማስረዳቱን በውሳኔው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡ ይህ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የማስረጃው አጥጋቢ መሆን ያለመሆኑ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ለ)) ድንጋጌ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ለወንጀል ድርጊቱ መሰረት የሆነው እቃ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት መሆኑን አቃቤ ሕግ በአጥጋቢ ማስረጃ አስረድቶ በመገኘቱ ፍርድ ቤቶቹ እንዲወረስ ያዘዙ መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዋጅን አንቀጽ 104(3)(ሀ)) ድንጋጌ ለምክንያቱ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90364 ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ሀ)) ድንጋጌ በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 66474

ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አደቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የአቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ት/ቤት - ጠበቃ ዶ/ር ዘውድነህ በየነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአቃቂ ቃልቲ ክፍል ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት - ዐቃቤ ህግ ቶላኒ ታከለ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍ/ቤት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የቤትና የቦታ ኪራይና ግብር አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት አመልካች 1968 ዓ.ም እስከ 1992 ዓ.ም ያልከፈለው የቦታ ኪራይ የከተማው ቤት ግብርና መቀጮ ብር 734,110.20 /ሰባት መቶ ሰላሣ አራት ሺህ አንድ መቶ አስር ብር ከሃያ ሣንቲም/ እንዲከፈል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የሰጠው መሆኑን ገልጾ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግብር ውሣኔውን እንዲያስፈጽም ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ ነው፡፡

አመልካች የበጐ አድራጐት ድርጅት በመሆኑ የቦታ ኪራይና ግብር ከመክፈል ነጻ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ባለመቀበል በመወሰኑና የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናታቸው ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ቀርቦ የስር ፍ/ቤት አመልካች ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ስለመሆኑ ወይም የበጐ አድራጐት ድርጅት መሆኑን አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ በስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42319 ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በሰጠው መመሪያ መሠረት አመልካች የበጐ አደራጐት ድርጅት ስለመሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ማህበር ኤጀንሲ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በማድረግና አመልካች ከተማሪዎች ወርሀዊ ወይም ዓመታዊ ክፍያና የመመዝገቢያ ክፍያ የሚያስከፍል መሆኑን አመልካች በግቢው ውስጥ ገቢ የሚያስገኙ የተለያዩ የጓሮ አትክልት ልማት የዶሮ እርባታ የከብቶች ወተትና የወተት ተዋጽኦ ገቢ የሚያገኝ መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ ከወፍጮ ቤት አገልግሎት ከሱቅና ለስላሣ ሽያጭ ገቢ የሚያገኝ መሆኑን ትምህርት ቤቱ ትፍፋማ ሊሆን የሚችል ቢሆንም ባለው ብልሹ አስተዳደር ምክንያት ትፍፋማ እንዳልሆነ

በመግለጽ  የኪራይና የቤት ግብር ከመክፈል ነጻ የሚያደርጉ የበጐ አድራጐት ድርጅት መስፈርት አያሟላም፡፡ ብር 611,798.20 /ስድስት መቶ አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሃያ ሣንቲም/ ለፍርድ ባለመብቱ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ አልተቀበለውም፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ የከተማው የሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

መጋቢት 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የአቃቂ አድቬንቲስት ሚስዮን ትምህርት ቤት ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም አይደለም፡፡ ትምህርት ቤቱ በንግድ ህግ ቁጥር 5 መሠረት የንግድ ፈቃድ ከንግድ ቢሮ አውጥቶ የተቋቋመ አይደለም፡፡ ስለሆነም ትምህርት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 14 መሠረት ከግብር ነጻ  መሆን ሲገባው በተጠሪ የተወሰነውን ግብር እንዲከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በአፈጻጸሙ ክስ ላይ ያቀረበውን የይርጋ  መቃወሚያ በማለፉ ከሀያ አራት ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በማስተናገድ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 384/1/ የሚጥስ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ሲመልስለት እንዲጣራ ትዕዛዝ የሰጣቸውን ጉዳዮች በአግባቡ ሣያጣራ የሰጠው ውሣኔ በመሆኑ በትኩረት ሊታይልን ይገባል፡፡ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን ማህበራት ኤጀንሲ በዚህ ጉዳይ ማስረጃ የመስጠት ስልጣን ያሌለው ሆኖ እያለ በህግ የተሰጠውን ስልጣን በመተላለፍ የሰጠውን አስተያየት መሠረት በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ተቋሙ ሀይማኖታዊ ተቋም ሆኖ እያለ ተጠሪ የወሰነውን ግብር እንዲከፍል የሰጠውን ውሣኔ እንዲፈጽም የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል ግንቦት 26 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ከኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የተለየ ህልውና ያለው የትምህርት ተቋም እንጂ ሀይማኖታዊ ተቋም አይደለም፡፡ የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ከትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ ተሰጥቶት ቁጥራቸው ከሁለት ሺህ በላይ ከሆኑ ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ክፍያ በማስከፈል የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ በስሙ ስፋቱ 129051 ካሬ ሜትር ቦታ በውል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከስራና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰጠው ተቋም ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎች ከሚያስከፍለው ከፍተኛ ክፍያ በተጨማሪ በይዞታው ሥር ባለ ቦታ ላይ የተለያዩ ምርት እያመረታና የንግድ ስራ እያከናወነ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኝ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የበጐ አድራጐት ድርጅት አለመሆኑ በአዲስ አበባ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የክትትልና ድጋፍ ክፍል ተረጋግጧል፡፡ ትምህርት ቤቱ ከሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በርቀት የሚገኝ ከመሆኑም በላይ ለአማኞች የተዘጋጀ የጸሎት ማከናወኛ ስፍራ ሣይሆን በሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ የተሰጠው የትምህርት ግልጋሎት የሚሰጥና ሌሎች ከፍተኛ የንግድ ስራዎችን የሚያከናውን ተቋም በመሆኑ አመልካች አዋጅ ቁጥር 80/68 አንቀጽ 14 በመጥቀስ የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 384 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክርም የድንጋጌውን ይዘት ያልተከተለ ነው፡፡ አመልካች በ1997 በተደረገው ግብር ማሻሻያ መሠረት ተጠሪ ግብሩን አላሻሻልንም በማለት ያቀረበው ክርክር በወቅቱ መሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች

አመልካች አሟልቶ ያልፈጸመ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቹ ግብር ላለመክፈል ለረዥም ጊዜ ጥረት የሚያደርግ በመሆኑና የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ እንዲያጸናልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ትምህርት ቤቱ የሙያ ፈቃድ ያለው መሆኑ ራሱን የቻለ ህልውና ያለው ተቋም የሚያደርገው አይደለም፡፡ ትምህርት ቤቱ በቤተክርስቲያኑ ስር ያለ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗ ለትርፍ ያልተቋቋመች ናት፡፡ በትምህርት ቤቱ የቅጥር ግቢ የጸሎት ቤት አለ፡፡ አስር ዓመት ያለፈውን ግብር እንድንከፍል መጠየቁ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ግብር እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ በወሰነው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢነው ወይስ አይደለም የሚለው መሠረታዊ ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ለክርክሩ መሠረት ያደረገው የህግ ድንጋጌ ይዘትና ድንጋጌው አሁን ባለው የህግ ሥርዓት ሊሰጠው የሚገባውን ትርጓሜ መመልከት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች የቦታ ኪራይና የቤት ግብር የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረው የከተማ ቦታውንና የቤት ግብር ለማስከፈል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 14 በመጥቀስ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 14 ከኪራይና ከግብር ነጻ ስለመሆን የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን በይዘቱም አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 1 ከዚህ የሚከተሉት ከኪራይና ከግብር ነጻ ይሆናሉ፡፡

ሀ/ የህዝብ መንገዶች አደባባዮች መዝናኛዎችና የስፖርት ቦታዎች መካነመቃብር

/ለ/ ጸሎት ቤቶችና ቅጥር ግቢያቸው ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች የበጐ አድራጐት ድርጅቶች የመዝናኛና የስፖርት ቦታዎች

/ሐ/ ከጠቅላይ ግምጃ ቤት በሚሰጥ በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በማለት የሚደነግግ ሲሆን የአንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 2 የዓመት ኪራይ ግምታቸው እስከ ሶስት መቶ ብር የሆኑ ቤቶች ከግብር ነጻ ይሆናሉ በማለት ይደነግጋል፡፡

ይህ አዋጅ በመጋቢት ወር 1968 ዓ.ም የወጣ ሲሆን ለጸሎት አገልግሎት ለመስጠት ታስበው ከተገነቡ የሀይማኖት ተቋማትና ቅጥር ግቢያቸው ውጭ በሀይማኖት ተቋማት ባለሀብት የሆኑባቸው ሌሎች ህንጻዎችና የንግድ ድርጅቶች የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ከመክፈል ነጻ የማያደርግ መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ /ለ/ "ጸሎት ቤቶችና ቅጥር ግቢያቸው" በሚል መንገድ ከገለጸው አገላለጽ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቱን ያቋቋመችው ትርፍ ለማግኘት አይደለም የሚል መከራከሪያ በአመልካች በኩል የቀረበ ቢሆንም አመልካች ትምህርት ቤቱ ያለትርፍ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ሀላፊነቱን አልተወጣም፡፡ በአንጻሩ ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠውን ዕውቅና እና ፈቃድ በመጠቀም ከሁለት ሺህ

በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን በአገሪቱ ውስጥ በትርፍ የተቋቋሙ የግል ትምህርት ቤቶች ከሚያስከፍሉት ክፍያ የማይተናነስ ክፍያ እየሰበሰበ የሚያስተምርና ሌሎች ትርፍ የሚያስገኙ የንግድና የግብር ተግባራትን የሚያከናውን ስለመሆኑ ተጠሪ በቂ ማስረጃ እንዳቀረበ የስር ፍ/ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 80/68 አሁን ያለውን ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ጋር ተጣጥመው ከወጡ ህጐች ጋር ተጣምሮ መተርጐምና ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡ አዋጅ ቁጥር 80/68 በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ እያሻሻለ ባወጣው የአዲስ አበባ ቻርተር መሠረት የከተማው አስተዳደር ከተሰጠው ህግ የማውጣትና ህግ የማስፈጸም ስልጣን ባገናዘበ መልኩ መተርጐምና ስራ ላይ መዋል ያለበት የህግ ማዕቀፍ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስናየው በአዲስ አበባ ከተማ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ከአዲስ አበባ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር ውል እየተዋዋሉ የበጐ አድራጐት ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆኑንና የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት የበጐ አድራጐት ተግባር ለመስራት ከከተማው አስተዳደር ጋር የፕሮጀክት ውል በመዋዋል አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተቋም እንዳልሆነ በጽሁፍ ማረጋገጫ የሰጠ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 80/1968 አሁን በአገራችን ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ስለሚመዘገቡበትና ስራቸውን ሲያከናውኑ ሊደረግ ስለሚገባው ክትትልና ቁጥጥር በዝርዝር የሚደነግገውና የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲን የሚያቋቁመው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣም መንገድ መተርጐምና ስራ ላይ መዋል ያለበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ትምህርት ቤቱ በአሁኑ ወቅት በበጐ አድራጐት ድርጅትነት የተመዘገበ ወይም ያልተመዘገበ መሆኑን የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና የማህበራት ኤጀንሲን መግለጫ መጠየቁ ተገቢና መፈጸም የነበረበት ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 80/68 አንቀጽ 14 /ለ/ ከቦታ ኪራይና ከቤት ግብር ነጻ አለመሆኑን አመልካች ተማሪዎችን ክፍያ በማስከፈል የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥና ሌሎች ትርፍ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰራ ተቋም መሆኑን ተጠሪ አስረድቷል፡፡ አመልካች የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ንብረትነቱ የኢትዮትጵያ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መሆኑን በመጥቀስ ትምህርት ቤቱ የራሱ የህግ ሰውነት የለውም ከሚል ውጭ ትምህርት ቤቱ ከሌሎች ለንግድ ከተቋቋሙ የግል ትምህርት ቤቶች በተለየ ሁኔታ ነጻ ወይም ትርፍ የማያስገኝ ተግባር ሲያከናውን የኖረ መሆኑን አላስረዳም፡፡

ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና ፈቃድ አግኝቶ ትውልድ በትምህርት የማነጽ ሀላፊነት እየተወጣ ባለበት ሁኔታና በትምህርት ቤቱ ስም 129051 ካሬ ሜትር ቦታ በይዞታው ስር አድርጐ የሚያዝበትና ለዚህም የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከከተማው አስተዳደር የተሰጠው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ትምህርት ቤቱ የራሱ የሆነ ህልውና የሌለው ተቋም በመሆኑና ትምህርት ቤቱ የተቋቋመው በኢትዮጵያ ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በመሆኑ ከቦታ ኪራይና ከቤት ግብር ነጻ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የአዋጅ ቁጥር 80/68 አንቀጽ 14 /ለ/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማና የአዋጁን ድንጋጌ አሁን ካለው ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ ስራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ከዚህ አንጻር የበታች ፍ/ቤቶች የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት የቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች የቦታ ኪራይና የቤት ግብር የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑ ከላይ በዝርዝር ገልጸነዋል፡፡ በማስከተል የሚነሳው ጥያቄ አመልካች መክፈል የሚገባው የቦታ ኪራይና የቤት ግብር መጠን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ እንዲከፍል ከወሰነው ግብር ውስጥ የይርጋ ዘመን ያለፈበት አለ በማለት የተከራከረ ሲሆን የስር ፍ/ቤት ይህንን የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል ይርጋው አልፎበታል የሚለውን ገንዘብ ተጠሪ ካቀረበው ጥያቄ ላይ በመቀነስ ይርጋው አላለፈበትም ያለውን ገንዘብ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የይርጋን መቃወሚያ ለማቅረብ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁ. 384 በመጥቀስ የተከራከረ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ፍርድ ለማስፈጸም የተቀመጠ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚመለከት በመሆኑና ተጠሪ ለአመልካች የግብር ውሣኔ ማስታወቂያውን ከሰጠው በኋላ አስር ዓመት ከመሙላቱ በፊት ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረበ በመሆኑ ድንጋጌው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የቦታ ኪራይና የቤት ግብር በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 80/68 እና በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 36/1968 በተቀመጠው ተመን መሠረት የመሬት ኪራይና የቤት ግብር የመክፈል ሀላፊነት ያለበት ተቋም ወይም ግለሰብ ግብሩን በየዓመቱ የካቲት ሰላሣ ቀን ድረስ እንደሚከፍል በአዋጅ አንቀጽ 8 ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ መሠረት የሚከፈለውን ኪራይና ግብር በተወሰነው ጊዜ ያልከፈለ ግለሰብ ቤተሰብ ወይም ድርጅት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር የኪራዩን ወይም የግብሩን አምስት በመቶ በመቀጫነት እንደሚከፍል ሆኖም መቀጫው ከዋናው ሂሣብ ከሀምሣ በመቶ መብለጥ እንደሌለበት የአዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 16 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ስንመለከተው አመልካች የቦታው ኪራይ ወይም የቤት ግብር ጥያቄው በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍና መሠረት የሌለው በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት እና ድጋፍ የሌለው በመሆኑና የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ መጣራት የሚገባቸውን በማጣራትና አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማስቀረብ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ መሆኑን በማረጋገጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁጥር 69677

ታህሳስ 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዳሽን ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ አዲስ ታደለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኑረዲን መሐመድ - ጠበቃ አብራር አደም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቤት ኪራይ የሚከፈለውን የታክስ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የፍርድ ባለመብት የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በመሰረቱት የአፈጻጸም ክስ በግልግል ዳኞች ታይቶ የተወሰነው የቤት ኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ እንዲፈጸምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለእዳ የሆነው የአሁኑ አመልካች እንደፍርዱ እንዲፈፅም የማይገደድበት ምክንያት ካለው ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም እንደፍርዱ ፈጽሞ እንዲቀርብ በማዘዙ አመልካች ቀርቦ የቤቱን ኪራይ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሰረት ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆኑን፣ ነገር ግን ለፍርድ ባለመብቱ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ 2% የተቀናሽ ግብር በመቀነስ ለመክፈል ቢሞክርም ተጠሪ ግብሩ ሊቀነስብኝ አይገባም በማለት ሊቀበሉ ያልቻሉ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግልግል ዳኞች በሰጡት ውሳኔ ተጠሪ ተቀናሽ ግብር መክፈል እንዳለባቸው አልተመለከተም ፣ ማን መክፈል እንዳለበትም አልተጠቀሰም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ አመልካች ሙሉውን ክፍያ ለተጠሪ እንዲፈፅሙ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2) መሰረት የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት ተቀናሽ የኪራይ ግብር ለማስቀረት ሲንቀሳቀስ ይህንኑ ለማድረግ ውሳኔ አላረፈበትም ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ አይደለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች በግልግል ዳኞች ውሳኔ አልተሰጠበትም በሚል ምክንያት አመልካች ተቀናሽ የኪራይ ገንዘብ ማስቀረት አይችልም በማለት መወሰናቸው ከአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53፣ 91 እና 101 ድንጋጌዎች አንጻር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስም አመልካች በግልግል ዳኞች ዘንድ በነበረው ክርክር ተቀናሽ የኪራይ ገንዘብ መኖር ያለመኖሩን ገልፆ ባልተከራከረበትና በግልግል ዳኞች የተሰጠ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ የተጠሪ የኪራይ ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያሳይ የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን ማስታወቂያ ሳይኖር ግብሩ ሊቀነስ ይገባል የሚለው የአመልካች ክርክር የፍርድ አፈጻጸም ስርዓቱን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስም የአመልካች ግዴታ ከሕግ የሚመነጭ በመሆኑ ፍርድ

አላረፈበትም ተብሎ በአፈጻጸም መዝገብ የሚታለፍ አይደለም በማለት የሰበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪው በኪራይ ይዞ እንደተገለገለበት እንዲሁም ቤቱም ለአመልካች ጥቅም በአገልግሎት ላይ በመዋሉ ምክንያት አመልካች ለተጠሪ የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል በግልግል ዳኞች ተወስኖ ይኸው ውሳኔ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ተጠሪ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍተው አመልካች በፍርድ ባለእዳነቱ ቀርቦ ስለፍርድ አፈፃፀም ሲያስረዳ ለተጠሪ ከሚከፍለው ገንዘብ ውስጥ ተቀናሽ ገንዘብ ሁለት ከመቶ (2%) የሚከፈል የኪራይ ገቢ ግብር ያለ ስለመሆኑ ለተጠሪ ገልፆ ቀሪውን ገንዘብ ለተጠሪ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ቢያሳውቅም ተጠሪ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ጠቅሶ ተቀባይነት ማጣቱን ፣የስር ፍርድ ቤት ግብሩ መከፈል ያለበት መሆኑን አምኖና ተጠሪ ለታክሱ ኃላፊነት የለባቸውም ሳይል የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያልተቀበለው ውሳኔ አላረፈበትም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ፍርድ የሚፈጸመው በሕጉ አግባቡ ፍርድ ያረፈበት ስለመሆኑ ተረጋግጦ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ውስጥ ተቀናሽ ማስቀረት አለብኝ በማለት የሚከራከረው ለአፈጻጸሙ መሰረት በሆነው የግልግል ዳኝነት ፍርድ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ውሳኔ አርፎበታል በሚል ምክንያት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2) ድንጋጌዎች በሕግ የተጣለብኝ ግዴታ አለ በማለት ነው፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53(1) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2) ድንጋጌዎች መሰረት ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት ከተወሰነ ማናቸውም ክፍያ ላይ ግብሩን የማስቀረት ግዴታ (Duty of withholding of Income Tax on payments)ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ግዴታ ያለመወጣት ደግሞ በወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስከትል እንደሚችል የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 91 እና 101 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡ ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት በሕግ ከተለዩት ክፍያዎች መካከል ደግሞ የህንጻ ኪራይ ገቢ ስለመሆኑ የደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2(ሸ)) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ እንዲያስቀር በሕግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን ለመወጣት በአፈጻጸም መዝገብ በቀረበው ክርክር ቢያነሳ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ ይህንኑ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386(2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው እንደፍርዱ የማይፈጽምበት ሕጋዊ ምክንያት ካለው ይህንኑ እንዲያስረዳ እድል እንዲሰጠው የሚያደርግ መሆኑ ሲታይ የፍርድ ባለእዳው በሕግ የተጣለበትን ግዴታንም ቢያስረዳ እንደፍርዱ ላለመፈጸም በቂና ህጋዊ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የግዴታ ምንጭ ሕግ ፣ በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎችና የፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑ የሚታመን በመሆኑ በሕግ የተጣለውን ግዴታ የፍርድ ቤት ወይም ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን ባለው አካል ታይቶ ፍርድ አላረፈበትም በሚል ምክንያት ውድቅ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በሕግ በተጣለበት ግዴታ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ያስቀረን አካል ከግብሩ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ካለው ገቢ

ጋር ተያይዞ በተነሳው ክርክር ከገቢው ግብሩን ለመቀነስ እንዲችል የተሰጠ ውሳኔ የለም በማለት በአፈጻጸም መዝገብ ግብሩን ሳይቀንስ ሙሉውን ገቢ እንዲከፍል ማስገደድ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታውን ለመወጣት በእጁ ያስገባውን ገንዘብ እንዲለቅ የሚያደርግና በውጤቱ ደግሞ ባለግዴታውን ለአላስፈላጊ ውዝግብ የሚዳርግ ነው፡፡ሲጠቃለልም አመልካች በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት ሲል ያቀረበው ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53 እና ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24(2) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386(2) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይ ሕጋዊ በመሆኑ በአፈጻጸም መዝገብ ላይ ፍርድ ሳያርፍበት ሊያነሳ አይችልም በማለት የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 170985 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 98673 ግንቦት 11 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 53 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24(2) የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት የተቀናሽ ሂሳብ ጥያቄን በአፈፃጸም መዝገብ ላይ ቢያነሳ የሚከለከልበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ውስጥ 2% (ሁለት ከመቶ) ተቀናሽ ገቢ ማስቀረት ይችላል ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 74753

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡ ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ሐበሻ የባህል ማዕከልና
የስእል ጋለሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር
2. አቶ በድሩ ሙዘይን
3. ወ/ሪት መስከረም ጫላ
} ጠበቃ መስፍን አደሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓቃቤ ህግ - ሽመልስ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ተያይዞ የተነሳን የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- 1ኛ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 50//መ/2// ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከጥቅምት 01 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በወጣው የህዝብ ማስታወቂያ መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ በመሆኑ ለሚያከናውናቸው ግብይቶች ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በሚወጣ ፊስካል ደረሰኝ መጠቀም ሲገባው በቀን 06/05/2002 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 5:00 ሰዓት አካባቢ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከሚወጣ ደረሰኝ ውጭ በሆነ ደረሰኝ ባለ 8.1 ግራም የሆነ የአገር ውስጥ የአንገት ሐብል በብር 93.15 የድርጅቱ ሰራተኞች በሆኑት ሶስተኛ አመልካች አማካኝነት ግብይት ፈጽሟል በሚል ሲሆን የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ የ1ኛ አመልካች ድርጅት ስራ አስኪያጅ ሁነው ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው በአንቀፅ 50/መ(2)/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ 1ኛ አመልካች የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን የመጠቀም ግዴታ እያለበት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ውጪ ግብይት እንዲከናወን አድርገዋል በሚል ነው፡፡ ሶስተኛ አመልካችም የተጠቀሰውን አዋጅ አንቀጽ 55 እና በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 50/መ/2// ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ አመልካች ድርጅት ውስጥ የሽያጭ ሰራተኛ በመሆን ሲሰሩ ከሽያጭ መመዝገቢያ ደረሰኝ ውጪ በሆነ ደረሰኝ ባለ 8.1 ግራም የሆነ የሐገር ውስጥ ሀብል በብር 93.15 በመሸጣቸው የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ ያላቸው መሆኑን ገልፀው ፍርድ ቤቱም ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎ ስለድርጊቱ

አፈፃጸም ድርጊቱ መፈጸሙን አምነው ጥፋተኛ አይደለንም በማለት በመከራከራቸው አቃቤ ሕጉ አሉን ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ እንዲያሰማ ተደርጓል፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ቀርበው ሽያጩ ከሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ከሚወጣ ደረሰኝ ውጪ በሆነ ደረሰኝ መከናወኑን በማረጋገጣቸው አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ አመልካቾች የሰውና የሰነድ ማስረጃዎቹን በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበው አስምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካቾች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያለመቻላቸውን ገልፆ የመከላከያ ማስረጃዎችን ቃል ውድቅ ከአደረገ በሁዋላ አመልካቾችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት ጥፋተኛ አድርጎ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን እያንዳንቸውን በሶስት ወር ቀላል እስራት፣1ኛ አመልካችን ደግሞ በብር 7,000.00 (ሰባት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም የወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ የሚመለከተው የወርቅና የብር ጌጣጌጥ የንግድ ፈቃድ ስራ ላይ የተሰማሩትን ነጋዴዎች ሁኖ አመልካቾች የንግድ ፈቃድ ደግሞ የሚመለከተው የባህል እቃዎችንና ስእሎችን መሸጥ በመሆኑ ማስታወቂያው አይመለከተንም የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ጥቅምት 1 ቀን 2002 ዓ/ም ለሕዝብ የተሰጠ ማስታወቂያ አመልካቾችንም የሚመለከት ነው ተብሎ አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ቀርቦ በጽሑፍ መልሱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካቾች ጥፋተኞች ተብለው መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሲሆን ቅጣት ጋር ተያይዞ የቀረበው ክርክር በዚሁ ጭብጥ እልባት የሚያገኝ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካቾች በተጠሪ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌዎች መሰረት የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው ተጠሪ በሕጉ አግባብ አስረድቷል? ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ጥያቄን በማንሳት በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃዎች ከተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች እና አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

አመልካቾች ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከሚወጣው ደረሰኝ ውጪ በሌላ ደረሰኝ ግብይት መፈጸማቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. ለሕዝብ የተሰጠው ማስታወቂያ የንግድ ፈቃዳችንን የሚመለከት አይደለም በማለት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የአመልካቾች ንግድ ፈቃድ የባህል እቃዎችና የስዕል ውጤቶችን የሚመለከት ቢሆንም ድርጅቱ የባህል ጌጣጌጥና ወርቅ የሚሸጥበት እንደነበረ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. የወጣው ማስታወቂያ አመልካቾችን ይመለከታቸዋል በሚል ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም አመልካቾች የሚከራከሩበት የንግድ ፈቃድ አመልካቾች የሚሉትን የንግድ ስራ የሚመለከት መሆኑን፣ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. ለሕዝብ የተሰጠው ማስታወቂያም የወርቅና

የብር ጌጣጌጥ ነጋዴዎችን የሚመለከት መሆኑን እንዲሁም አመልካቾች የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ባይገዙም በእለቱ ለተከናወነው ግብይት ግን ከሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ውጪ በሆነ ደረሰኝ ግብይቱን መፈፀማቸውን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጠው አመልካቾች የወንጀል ተጠያቂያነት አለባቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ማስታወቂያው ይመለከታቸዋል፣ በሚመለከተው አካል ከተሰጠው የንግድ ፈቃድ ውጪ ስራውን ሲሰሩ የተገኙ መሆኑም ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ የአንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂነት የሚኖረው ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ በአንቀፅ 23(2) ስር በግልፅ አስፍሯል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች የሐሳብ ክፍል እና ሕጋዊ ተዋጽኦዎች በሚገባ የተሟሉ መሆን ያለመሆኑን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አመልካቾች የተከሰሱት ሽያጩን ከሽያጭ ማሽን በሚወጣው ደረሰኝ መሸጥ ሲገባቸው ከማሽኑ ባልወጣው ደረሰኝ ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ ለዚህም ተጠሪ ተጥሷል  የሚለው የሕግ ማዕቀፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 139/1999 ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌም በደንቡ በአንቀጽ 5(1(ለ)) ስር የተመለከተው ሁኖ ይዘቱም የሽያጭ መሳሪያውን ጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው በመሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችለው ፈቃድ ላይ በተመለከተው የንግድ ስራ ብቻ ነው በሚል በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ደንብ ድንጋጌ መሰረትም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ገዝተው የመጠቀም ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች በየምድባቸው መሳሪያውን ገዝተው መጠቀም የሚጀምሩበትን የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ በሕዝብ ማስታወቂያ እንዲወጣ እንደሚደረግ በአስገዳጅነት ደንግጎ ይገኛል፡፡ የድንጋጌው ይዘት ሲታይም የሽያጭ መሳሪያውን የመጠቀም ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች ማስታወቂያው ሲነገራቸው የንግድ ፈቃድ የስራ ዘርፍ በግልፅ ተለይቶ የሚነገራቸው መሆኑን ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች በወንጀሉ ተጠያቂ የሆኑት የንግድ ፈቃዳቸው ወርቅና የብር ጌጣጌጥ በሚመለከት ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም የወጣው የህዝብ ማስታወቂያ ይመለከታቸዋል ተብሎ ቢሆንም የንግድ ፈቃዱ የሚያሳየው ግን የባህልና የስእል ውጤቶቹን የመሸጥ የንግድ ስራ ፈቃድ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም የወጣው የህዝብ ማስታወቂያ የአመልካቾችን የንግድ ዘርፍ ይመለከታል ለማለት የሚቻል ያለመሆኑን ከደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 5(1(ለ)) እና ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 23(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ የተጠሪ ማስታወቂያ የአመልካቾችን የንግድ ፈቃድ የሚመለከት ካለመሆኑም በላይ አመልካቾች ሽያጩን የፈፀሙት ከማሽን ባልወጣ ደረሰኝ መሆኑ ሲታይ ደግሞ አመልካቾች ድርጊቱን ለመፈፀም የነበራቸው የሓሳብ ክፍል ከድርጊቱ አፈጻጸም አንፃር ሊታይ የሚገባው እና ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ይዘትም አኳያ ሲታይም ሕጉ የሚጠይቀው መመዘኛ ያልተሟላ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከሃሳባቸው በላይ ሊቀጡ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ ሲጠቃለልም ሕጋዊና ሞራላዊ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ አመልካቾች በወንጀሉ ተጠያቂ መደረጋቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ይዘት ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 169689 ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ፣እንዲሁም ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 105743 ህዳር 20 ቀን 2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት ነገሮች ተጣምረው ባልተገኙበት ሁኔታ በወንጀል የሚጠየቁበት ምክንያት አላገኘንም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## ት ዕ ዛ ዝ

1. አመልካቾች በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ዛሬውኑ ከስር እንዲፈቱ ብለናል፡፡ ለማረ/ቤቱ መፍቻ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 66350

ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ቴዎድሮስ ደበላ ጠበቆች ሽፈራው ጉሌና ተኮላ መሸሻ ቀረቡ
ተጠሪ፡- የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስሥልጣን የልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ
ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ተወዳጅ ሲማ ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በሚሰጠው የግብር ማስታወቂያ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ለግብር ጉባኤ ለማቅረብ የተፈቀደውን ጊዜና የጊዜውን ስሌት የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም አሻሽለው ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ባለው የግብር ዘመን እንዲከፈል የተወሰነብኝ የንግድ ስራ ገቢ ግብር ያላግባብ እና ከአቅሜ በላይ ነው ፣ ይህንኑ ቅሬታ ለተጠሪ መስሪያ ቤት አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ባቀርብም ኮሚቴው ተመሣሣይ ውሣኔ አስተላልፎብኛል በማለት ጉባኤው አመልካችን ያቀረቧቸውን ማስረጃዎችንና የግብር ማህደራቸውን በማስቀረብ ጉዳዩን በመመርመር ፍትሐዊ ዳኝነት እንዲሰጥ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ የአመልካች ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቀረበው በሕጉ የተመለከተው የሰላሣ ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከአለፈ በሁዋላ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ መቃወሚያ መሠረት ይግባኙ ውድቅ እንዲሆንና ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ ፍሬ ጉዳዩም ተቀባይነት የለውም የሚልባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ጉባኤም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ይግባኙ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 107/2/1/ በሚደነግገው መሠረት በሰላሣ ቀናት ውስጥ ያልቀረበ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለማስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሬጅስትራርን በመጥራት ጉዳዩን ከአጣራ በሁዋላ የሰላሣ ቀናት ጊዜ ሳያልፍ አመልካች ይግባኛቸውን ማቅረባቸው ተረጋግጧል በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤን ውሣኔ ሽሮ በፍሬ ነገሩ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ለጉባኤው መልሶለታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ችሎቱ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የይግባኝ አቤቱታውን ለግብር

ይግባኝ ጉባኤ አቅርበው አመልካች የተጠሪ መስሪያ ቤት ሃምሣ ፐርሰንት /50%/ የይግባኝ ማስያዣ እና የዳኝነት ሂሣብ እንዲከፍል የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሬጅስትራር አመልካችን ሲያዝዙ አመልካች የተተመነውን ሂሣብ በባንክ ሲፒኦ አሰርተው ካስገቡ በሁዋላ የሲፒኦ ማስረጃ ስለማንቀበል ሲፒኦው ወደ ደረሰኝ መለወጥ አለበት በማለት አቤቱታቸውን ሬጅስትራሩ ባለመቀበላቸው ለተከሰተው የጊዜ ማለፍ አመልካች የሚቀጡበት አግባብ የለም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የይግባኝ ማስያዣና የዳኝነት ሂሣብ በሲፒኦ መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም. አሰርተው ለፋይናንስ ቢሮ መጋቢት 13 ቀን 2002 ዓ.ም. ብር 223,696.52 /ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከሃምሣ ሁለት ሣንቲም /ለዳኝነት ብር 8303.48/ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሶስት ብር ከአርባ ስምንት ሣንቲም/ ከፍለው ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በወቅቱ አቅርበው እያለ የጉባኤው ሬጅስትራር ሲፒኦውን ወደ ደረሰኝ መለወጥ አለበት በማለት አቤቱታውን ባለመቀበላቸው የይግባኝ ማቅራቢያ ጊዜ አልፏል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር በሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ በCPO መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በማሰራት ከተጠሪ ቢሮ ሰላሣ ቀን ከማለፉ በፊት ቀርበው የነበሩ መሆኑና ተጠሪ የገቢ ግብር ይግባኝ ለማቅረብ በCPO አመልካች ያቀረቡትን መያዣ ደረሰኝ ቆርጦ 13/07/2002 ዓ.ም የሰጠ ሲሆን የገቢ ግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በመያዣነት ያቀረቡትን CPO ወደ ደረሰኝ ካልተለወጠ በማለት ሬጅስትራሩ ሳይቀበለው ቀርቶ በ13/7/2002 ዓ.ም ግን ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

በመሰረቱ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 107 ድንጋጌ መሠረት አንድ በማንኛውም ግብር /ታክስ አወሳሰን ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ በአንቀፅ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር የተቀመጡትን ግዴታዎችን አሟልቶ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጅ አንቀፅ 107/2/ ስር የተመለከቱት ግዴታዎች ግብር ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የግብር መጠን 50% /ሃምሣ ከመቶ/ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማስያዝ እንደአለበትና ይግባኙንም የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ በደረሰው ወይም በአቤቱታው ኮሚቴ ውሣኔ በተሰጠ በሰላሣ ቀን ወስጥ መቅረብ እንደአለበት የሚያሳዩ ስለመሆናቸው ንኡስ ድንጋጌው በፊደል “ሀ” እና “ለ” ስር ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 108 ድንጋጌ ሲታይም ይግባኙ የቀረበበት ቀን የሚባለው በቀጥታ ለይግባኝ ጉባኤው የቀረበ ሲሆን ይግባኙ ለመዝገብ ቤት የተመዘገበበት ቀን ወይም በሪኮማንዴ የተላከ ሲሆን በፖስታ ቤት የተመዘገበበት ቀን እንደሚሆን አስቀምጧል፡፡

አመልካችም ሆነ ተጠሪ በዚህ የህግ ይዘት ላይ ክርክር የላቸውም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው አመልካች በጊዜ ገደቡ ይግባኛቸውን አቅርበዋል? ወይስ አላቀረቡም? የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ መያዣው በሚፈፀመበት ሥርአት በCPO አሰርተው ለተጠሪ ጊዜው ከማለፉ በፊት ማቅረባቸው ከተረጋገጠ በCPO ለክፍያ ያቀረበውን ገንዘብ አወራርዶ ደረሰኝ ለመስጠት ተጠሪ በአጋጠመው የአሰራር ወይም ሌላ ችግር ምክንያት ቀናት ወይም ወራት ቢወሰድበት ይግባኝ ባዩ ይግባኝ ለማለት መክፈል ያለበትን ገንዘብ በጊዜው አልከፈለም ሊባል ይገባዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከሕጉ አጠቃላይ መንፈስና ዓላማና ሕግ አውጭው ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብ አንፃር መመርመርና ውሣኔ ማግኘት አለበት፡፡ ሕግ አውጭው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሰዎች የውሣኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው በሰላሣ ቀን ውስጥ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 50% /ሃምሣ ከመቶ/ ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በማስያዝ ይግባኝ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 107/2ሀ/ ሲደነግግ ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ለማስገደድ እንጅ ገንዘቡ ገቢ ግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ደረሰኝ ሣይሰጥ ቢቆይ በመሥሪያ ቤቱ የአሰራር ችግር ምክንያት የግብር ከፋዩ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንዲጣበብ በማሰብ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪ ክፍያ የሚቀበልበትን ሥርአት በማሟላት ማለትም በCPO መክፈል አለብህ ተብሎ የተወሰነበትን የንግድ ገቢ ግብር 50% የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሰላሣኛው ቀን ማለትም 10/07/2002 ለተጠሪ ገቢ አድርጓል፡፡ ይህም አመልካች ከላይ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ለተጠሪ ገቢ ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ሰላሣ ቀኑ ከማለፉ በፊት በCPO ገቢ ለሆነለት ገንዘበ ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠው ከሶስት ቀን በኋላ ማለትም 13/7/2002 መሆኑ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለበትን ገንዘብ አመልካች ከሰላሣ ቀን በኂላ ነው ገቢ ያደረገው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተከሰተውን ችግር አጣርቶ ችግሩ የአመልካች ያለመሆኑን በመደምደም ይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካች ችግር አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተለየ ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በኩል ያሉ የአሰራር ችግሮችና ክፍተቶች መሰረታዊ የሆነውን የአመልካችን ይግባኝ የማቅረብ መብት በማያጣብብ ሁኔታ በመተርጐም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሣኔ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መቀበሉ የሕጉን ድንጋጌ አተረጋጐምና ተፈፃሚነት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 14957 ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14285 ሕዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. የአዲስ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት በመያዣነት መክፈል የሚገባውን ገንዘብ ለተጠሪ ያስያዙ በመሆኑ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመርና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሶ መላኩ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 69921

ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር ጠበቃ ዮሐንስ ዘለቀ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ተወዳጅ ሲማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የንግድ ሥራ ገቢ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች የ2000 ዓ.ም የበጀት ዘመን ብር 472,594.89 /አራት መቶ ሰባ ሁለት ሺህ አምሥት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሰማኒያ ዘጠኝ ሣንቲም/ ያልተጣራ ትርፍ ያገኘ መሆኑን የሚያሣይ የሒሣብ መዝገብ አቅርቦ ብር 83,507.02 /ሰማኒያ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ የንግድ ሥራ ከፍሏል፡፡ ተጠሪ አመልካች በአመቱ ውስጥ ያገኙት ጠቅላላ ገቢ ብር 5,647,298.90 /አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሥምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን አመልካች ያቀረበው የሂሣብ መዝገብ የሚያሣይ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች የተሠማራበት የፅሕፈት መሣሪያ አስመጭነት ሥራ ዘርፍ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልተው ከገቡበት አሥራ አምስት ፐርሰንት ያልተጣራ ትርፍ የሚገኝ መሆኑ በአዲስ አበባ አስተዳደር ገቢዎች የተጠና ጥናትና የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ያለ መሆኑን በመግለፅ በዚሁ ስሌት አመልካች ብር 303,610.71 / ሶስት መቶ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ አስር ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም /ያልተጣራ ትርፍ ስላለ በዚሁ ስሌት ግብር እንዲከፍል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ተጠሪ ለአመልካች ሰጥቷል፡፡

አመልካች ተጠሪ በሰጠው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርቧል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሰጠውን የገቢ ግብር ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው አቤቱታቸው ተቀባይነት አልተገኘም፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ያቀረብኩት የሂሣብ መዝገብ የዋጋ ማሣነስ ወይም underinvocing የሌለው ነው፡፡ አመልካች የሒሣብ መዝገቡን ተቀብሎታል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 14 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ ተጠሪ አመልካች ባቀረቡት የሒሣብ መዝገብ ላይ ያሉትን ጥቃቅን ስህተቶች በማረም ውሣኔ የሰጠው የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ ቀደም ብሎ በተዘጋጀ መመሪያና ቼክ ሊስት መሠረት በማድረግ አመልካች ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ ያቀረብኩትን የሒሣብ መዝገብ ከተቀበለ በኋላ በተሰማራሁበት የፅሕፈት መሣሪያዎች አስመጭነት ንግድ ዘርፍ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በግምት የተዘጋጁ የትርፍ ተመን መሠረት የግብር ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69/1/ ግብር ከፋዩ ምንም አይነት የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሣብ መዝገቡንና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላሣወቀ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን ይችላል በማለት ይደግጋል፡፡ ተጠሪ አመልካች በዓመት ውስጥ አስገብቸዋለሁ በማለት በሒሣብ መዝገብ ያሣወቀውን ብር 5,647,298.90 እና ሌሎች የወጪ መግለጫዎች የተቀበለ መሆኑ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ባቀረበው ክርክር አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በበጀት ዓመቱ አግኝቻለሁ በማለት መግለጫ ያቀረበበት ያልተጣራ ትርፍ በዘርፉ ይገኛል ተብሎ በጥናት ከተረጋገጠው እና በመመሪያ ከተወሰነው አማካኝ ያልተጣራ ትርፍ በታች መሆኑን በማገናዘብ ይህንን የሒሣብ ስህተት በማስተካከል የግብር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የሒሣብ መዝገብ በከፊል በመቀበልና በከፊል በማስተካከል አመልካች ተጨማሪ የገቢ ግብር እንዲከፍል መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 71 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የህጉ ድንጋጌ ተጠሪ አመልካች ያቀረበው የሒሣብ መዝገብ ሙሉ በሙሉ የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካገኘ የአመልካችን የሒሣብ መዝገብ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ግብሩን በግምት የመወሰን ሥልጣን ለተጠሪ ይሰጠዋል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች ያቀረበው የሒሣብ መዝገብ በከፊል ተቀባይነት ያላቸው የሒሣብ መግለጫዎችን የያዘ በከፊል ደግሞ የሒሣብ አያያዝና የአሠራር ስህተት ያለበት ሆኖ ቢገኝ ተጠሪ በሂሣብ አያያዝ የተፈጠሩ ስህተቶችን በማስተካከል የግብር ውሣኔ ከመስጠት የአዋጅ አንቀፅ 69 ድንጋጌዎች የሚገድቡ /የሚከለክሉ/ አይደሉም፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው ተጠሪ አመልካች በ2000 ዓ.ም የበጀት ዓመት የፅህፈት መሣሪያዎችን በማስመጣት ስላገኘው ጠቅላላ ገቢና ስለሌሎች ወጭዎች ያቀረበውን የሂሣብ መግለጫ ተቀብሏል፡፡ ሆኖም አመልካች በበጀት ዓመቱ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን የፅሕፈት መሳሪያ በመሸጥ አግኝቸዋለሁ ብሎ በሒሣብ መዝገቡ መዝግቦ የያዘው ያልተጣራ ትርፍ የፅሕፈት መሣሪያዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት እንደሚገኝ በጥናት ተለይቶ ከተያዘው አማካኝ ያልተጣራ የትርፍ መጠን ዝቅተኛ ሆኖ በመገኘቱ አመልካች በዓመት ውስጥ ስላገኘው ያልተጣራ ትርፍ ሠርቶ ያቀረበውን የሂሣብ መግለጫ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ብሎ አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም ያልተጠራ የትርፍ መጠን ለመወሰን የወጣውን መመሪያና ቼክ ሊስት መሠረት በማድረግ የአመልካችን ያልተጣራ የትርፍ መጠን የሒሣብ መግለጫ በማስተካከል አመልካች ተጨማሪ የገቢ ግብር እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

- የአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፤ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

  መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ.65041

የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ሐጎስ ወልዱ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- አቶ አንዳርጌ እሸቱ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ክስን የሚመለከት ስሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሌሎች ግብረ አበሮች ጋር ፈጽሟል በሚል ከተከሰሰበት አጣቃላይ አራት ክሶች መካከል በሌሎች ሁለቱ ክሶች በነጻ ሲሰናበት በ4ኛ እና 5ኛ ክስ ስር በተመለከቱት የጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 100 ስር ለምርመራ ሳምፕል በማለት አንድ ፓኬት ባትሪ ወስዶ ባለመመለሱ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 95/ሀ/ ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ ምንም ዓይነት የጉምሩክ አስተላላፊነት ፍቃድ ሳይኖረዉና ከጉምሩክ ባለሥልጣን ፍቃድ ሳያገኝ በክሱ የተመለከቱት ተሽከርካሪዎች የጫኑት የባትሪ ድንጋይ ጭነት የታሸገበትን ፕሎምፕ በመበጠሱ ተከሳሹ በፈጸመዉ እሽጎችን በመፍታት እና ምልክቶችን በማንሳት የወንጀል ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ለሁለቱ የወንጀል ድርጊቶች በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ዉሳኔ በመስጠቱ እና የተሰጠዉም የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና የቅጣት ዉሳኔ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጽናቱ የተፈጸመዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነዉ፡፡

አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ያላቸዉን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን የካቲት 03 ቀን 2002ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ ፍሬ-ሃሳብ፡- ለናሙና የተወሰደን ዕቃ አልመለሰም በማለት በበታች ፍርድ ቤቶች የተላለፈበትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በተመለከተ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አሽከርካሪዉ ላደረገለት ትብብር በስጦታ መልክ ሰጥቶት ይዞ የሄደ እንጂ መጀመሪያ ላይ ለናሙና የተወሰዱትን የመለሱ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ያለአግባብ በመሆኑ፣ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ የጭነት ማሸጊያ በመፍታት ወንጀልም ስር የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በክሱ በተመለከተዉ መሰረት ያስረዱት ነጥብ ሳይኖር የተወሰነብኝ በመሆኑ እና ባጠቃላይ የቀረቡብኝ ክሶች በበቂ ማስረጃ ያልተረጋገጡ ከመሆኑም በላይ በመከላለከያ ምስክሮች የተከላከልኩ በመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተላለፈብኝ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የቅጣት ዉሳኔን በተመለከተም ከብዶ የተወሰነ በመሆኑ አግባብነት የሌለዉ ነዉ በማለት የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ ተሽሮ በነጻ እንድሰናበት፤ ይሄ የማይቻል ከሆኑ ደግሞ

የእስራት ቅጣቱ ቀሎልኝ በገደብ እንድታለፍ በሚል ነዉ፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ግንቦት 6 ቀን 2003ዓ.ም በሶስት ገጽ በተጻፈ የሰጠዉ የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- አመልካች ጥፋተኛ በተባለባቸዉ ሁለቱም የወንጀል ድንጋጌዎች ስር ባቀረብናቸዉ ምስክሮች የተረጋገጠ እና ያልተከላከለ በመሆኑ የተላለፈበት የጥፋተኝነት ዉሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ የሌለ በመሆኑ እና የተላለፈበት የቅጣት ዉሳኔም ስንመለከት እጅግ ያነሰ በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘዉ ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ከተከሰሰባቸዉ የጉምሩክ ወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መካከል በአዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 100 ስር ለናሙና የወሰደዉን ዕቃ ያልመለሰ ስለመሆኑ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 95/ሀ/ በተሸከርካሪዉ ላይ ያለዉ ጭነት የታሸገበትን መሸጊያ ስለመፍታቱ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ አሁን በአመልካች እየተነሳ ያለዉ ክርክር የቀረበዉ የዐቃቤ ህግ ምስክር በክሱ መሰረት አላስረዳም የሚል ሲሆን ይሄ ደግሞ የፍሬ-ጉዳይ ክርክር እንጂ የመሰረታዊ የህግ ስህተት ጥያቄ ባለመሆኑ እና ማስረጃን የመመዘን እና ፍሬ-ጉዳይን የማጣራት ስልጣን ደግሞ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ወይም በይግባኝ ያየዉ ፍርድ ቤት በመሆኑ እና የዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማቃናት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ህገ-መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 ስር የተደነገገ በመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ የተደረሰበትን መደምደሚ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ይዘን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስንመለከት በአዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 95/ሀ/ መሰረት ማንኛዉም ሰዉ አግባብ ካለዉ የባለስልጣኑ ሹም ፊቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ወቅት የዕቃዎች መያዣ ላይ የተደረገዉን ማሸጊያ የፈታ ወይም ያላቀቀ እንደሆነ በዚህ ድንጋጌ ስር የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠዉን ፍሬ-ነገር ስንመለከት የአመልካች ድርጊት የወንጀል ኃላፊነቱን ሊያቋቁም የሚችል ተግባር የፈጸመ ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ስለሚቻል በዚህ የወንጀል ህግ ስር አመልካች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡ ሌላኛዉን የወንጀል ኃላፊነት በተመለከተ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 100 ን ስንመለከት ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ለናሙና የወሰደዉን ዕቃ ያልመለሰ ወይም በዕቃዉ የተገለገለ ወይም ዕቃዉ እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ በማለት የሚደነግግ ሲሆን አመልካችም በዚሁ መልኩ ለናሙና የወሰደዉን ዕቃ ሳይመልስ የቀረ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነጥብ በመሆኑ የወንጀል ኃላፊነቱን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራትን የፈጸመ ስለመሆኑ ከተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች እና የወንጀል ድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡ በአመልካች ላይ የተላለፈዉን የቅጣት ዉሳኔ በተመለከተም በቅጣት አጣጣሉ ሂደት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት ነጥብ ባለመኖሩ በዚህ ዙሪያ የተነሳዉን ቅሬታም አልተቀበልነዉም፡፡

ባጠቃላይ በአመልካች ላይ የተላለፈዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በአግባቡ እና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.91025 ጥር 20 ቀን 2003ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 155110 በቀን 8-6-2002ዓ.ም እና በቀን 22-6-2002 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.195(2(ለ(2))) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በአመልካች ላይ የተላለፈዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡

3. የበታች ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የጸና ስለመሆኑ ለሚመለከተዉ ማረሚያ ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 68422

መጋቢት 14 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1. ጀሪኮ ሰርቪስ - ደሳለኝ መስፍን ቀረቡ

2. አቶ ሀሰን አብደላ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የወሰነው የገንዘብ መቀጮ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአንደኛ አመልካች ላይ ያቀረባቸውን ሶስት የወንጀል ክሶችና የተጠሪን ማስረጃዎችና የአንደኛ አመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ አንደኛ አመልካች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከጥቅምት 1 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ከተመዘገበ በኋላ እስከ ሰኔ 2000 ዓ.ም. ለተከናወነው ግብይት መክፈል የሚገባውን ለብር 161,870.13 ተጨማሪ እሴት ታክስ ባለመክፈሉ የአዋጅ ቁጥር 255/94 አንቀጽ 49 በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ እንደዚሁም አንደኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 50/መ/1 እና የወንጀል ሕግ አንቀፅ 34 በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት ወንጀል ለሚፈረድበት የአምስት ዓመት ፅኑ እስራት ወደ ገንዘብ በመለወጥ ብር 100,000 እንዲቀጣ፣ እንደዚሁም አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 50/መ/1 በመተላለፍ ጥፋተኛ በሆነበት ወንጀል ከሚወሰንበት ቅጣት ብር 50,000፣ ለሁለቱ ወንጀሎች ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ አንደኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሰሰበት ግብር ባለመክፈል ወንጀል በነፃ መሰናበት ተገቢ አይደለም፡፡ እንደዚሁም የበታች ፍርድ ቤት በጣምራ የገንዘብ መቀጮ መወሰን ሲገባው ሳይወሰን ማለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን አመልካቾች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔውን በመቃወም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ

አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ይግባኝ መዛግብት በማጣመር የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አንደኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 የእስራት ቅጣት ብቻ ሣይሆን የገንዘብ መቀጮ የሚደነግግ ነው በማለት የቀረበውን ይግባኝ በመቀበል የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 45 መሠረት በማድረግ የገንዘብ ቅጣቱን አስልቶ አንደኛ አመልካች ብር 604,546.74 /ስድስት መቶ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሣንቲም/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ወደ ይግባኙ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለፅ የአመልካችን ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አንደኛ አመልካች የሰበር አቤቱታው በሰበር ማጣሪያ ችሎት ውድቅ ከተደረገው ከሁለተኛ አመልካች ጋር ሚያዝያ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በጋራ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሆኖ ባልተገኘበት የሕግ ድንጋጌ ቅጣት የወሰነበት መሆኑን የገለፀ ሲሆን በተለይ ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በእስራት ቅጣት ብቻ እንደሚቀጣ የሕጉ ድንጋጌ በግልፅ ደንግጎ እያለ ድንጋጌው በጣምራነት ገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ አድርጎ የተረጎመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግልፅ የሆነውንና ትርጉም የማያስፈልገውን የሕግ ድንጋጌ በመተርጎም በአስተዳደራዊ ቅጣት ሊወሰን የሚገባውን የገንዘብ መቀጮ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ሊከፍለው የሚገባው የወንጀል መቀጮ ነው በማለት የገንዘብ ቅጣቱን የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 45 መሠረት በማስላት የሰጠው ውሣኔ የሕጋዊነት መርህን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌ በአቀራረፅም ሆነ በይዘቱ ጥፋተኛው በእስራት ቅጣት ብቻ ሣይሆን በመቀጮ የሚቀጣ መሆኑን የሚደነግግ ነው በማለት ሰኔ 9 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም አንደኛ አመልካች በእስራትና በመቀጮ እንዲቀጣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 285/1994 አስራ ሶስት ክፍሎችና 66 አንቀፆች ያሉት መሆኑን የአዋጁን ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አቀራረፅና አደረጃጀት ስንመለከት አዋጁ በአስራ ሶስት ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ የአዋጁ ክፍል አንድ ትርጓሜና ሌሎች ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን የአዋጁ ክፍል ሁለት ታክስ ስለመጣልና ከታክስ ነፃ ስለሚሆኑ ግብይቶች ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ ክፍል ሶስት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የሚከናወኑበት ቦታ ጊዜና ዋጋ ገዥነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የያዘ ነው፡፡ ክፍል አራት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች እሴትና የገቡበትን ጊዜ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዙ ሲሆን ክፍል አምስት ስለምዝገባ የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የሚደነግግ ነው፡፡

የአዋጁ ክፍል ስድስት ስለታክስ ስሌት የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ክፍል ሰባት ስለተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደራዊ ሥርዓት ገዥነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ያካተተ ሆኖ

እናገኘነዋን፡፡ የአዋጁ ክፍል ስምንት የታክስ አሰባሰብና አፈፃፀም የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን፣ በክፍል ዘጠኝ ስለ ሂሳብ ሰነዶች በክፍል አስር ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሥርዓት ገዥነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ የአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ስለ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በሚደነግጉ ድንጋጌዎች የተዋቀረ ሲሆን ክፍል አስራ ሁለት የወንጀል ጥፋቶችን የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ የአዋጁ ክፍል አስራ ሶስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የሚደነግግ ነው፡፡

አከራካሪው አንቀፅ 49 በአዋጁ በአስራ ሁለተኛው ክፍል ውስጥ የተደነገገ ድንጋጌ ሲሆን ይዘቱን ስንመለከተው "ሕጉን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል" የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል፡፡ ድንጋጌው "ሕግን በመጣስ የተሰበሰውን ታክስ ያላሳወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማንኛውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሠረት ከሚጣልበት በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል" በማለት ይደነግጋል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌ የእንግዚኛ ቅጅ A person who evades the declaration of payment of tax, or a person who, with intention to defraud the government; applies for refund he is not entitled to, commits an offence and, in addition to any penalty under section 11, may be prosecuted and on conviction, be subject to a term of imprisonment of not less than five/5/ years" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ከላይ የተገለፀው የአዋጅ አንቀፅ 49 ድንጋጌ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀ፣ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ወይም መንግስት ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ሰው በክፍል አስራ አንድ የተዘረዘረውን አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስቀጣ ፍታብሔራዊ ጥፋት የፈፀመ መሆኑ በተጨማሪ ወንጀል እንደፈፀመ የሚቆጠርና በወንጀልም ተጠያቂ እንደሚሆን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም አንቀፅ 49 ድንጋጌን በመተላለፍ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ላይ የሚጣለው የወንጀል ቅጣት ከአምስት ዓመት የማያንስ የእስራት ቅጣት መሆኑን ድንጋጌው "በመሆኑም በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሠረት ከሚጣልበት በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል" በማለት የደነገገውንና በእንግሊዝኛ ቅጅ "in addition to any penalty under section 11, may be persecuted and on conviction to subject to the term of imprisonment not less than five years" ከሚለው የድንጋጌው አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት እንችላለን፡፡

የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን በሚያስተዳድረው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ከአንቀፅ 45 እስከ አንቀፅ 47 የተደነገጉትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለመወሰንና ለማስከፈል ግብር ከፋዩ በአዋጁ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ መሆኑን በማረጋገጥ የሚወስነው ሲሆን አስተዳደራዊ ቅጣቱን ለመወሰንና ቅጣቱን ለማስፈፀም የግብር ከፋዩ በወንጀል መከሰሱና በፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግብር ከፋዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሥልጣን ባለው የመንግስት መሥሪያ ቤት በአዋጁ በክፍል አስራ አንድ ከተደነገጉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በአንደኛው ወይም በሁሉም የተቀጣ መሆኑ፣ በዚያው ጉዳይ የሚቀርብበትን የወንጀል ክስና ቅጣት የማያስቀርለት መሆኑን አንቀፅ 49 ግልፅ የሚያደርግ ድንጋጌ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 49 ግብር ከፋይ በአዋጅ ክፍል አስራ አንድ ከተደነገጉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በአንደኛው ወይም በሁሉም መቀጣቱ በወንጀል ከመከሰስና ተጠያቂ ከመሆን የማያስቀር መሆኑን ከሚደነግግ ውጭ በአንቀፅ 49 ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ የወንጀሉን ጉዳይ ያየው ፍርድ ቤት ጥፋተኛውን ከአምስት ዓመት በማያንስ የእስራት ቅጣትና በአዋጅ ክፍል አስራ አንድ የተደነገገውን የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ውሣኔ መስጠት የሚችል መሆኑን የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ አለመሆኑን ከላይ በዝርዝር ያየነው የአዋጁን አወቃቀር የድንጋጌውን አቀራረፅና ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤት በሕግ በግልፅ ከተደነገገው በቀር የወንጀል ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን እንደማይችል በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 በሁለተኛው ፓራግራፍ ተደንግጓል፡፡ ችሎቱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 በሚደነግገው መሠረት ድንጋጌውን አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ሲያውጅ ሕግ አውጭው ሊደርስበት ያሰበውን ግብና የድንጋጌውን መንፈስና ዓላማ ለመረዳት የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 285/94 ከማወጁ በፊት በረቂቅ አዋጁ ላይ ውይይት ያደረገበትን ቃለጉባኤ በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡ የሕግ አውጭ ምክር ቤት ውይይት ቃለ ጉባኤ የሚያስረዳው ሕግ አውጭው በፍርድ ቤት የሚወሰኑ ቅጣቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶችና ውሣኔዎችን የማጣመር ሀሳብና ፍላጎት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሕግ አውጭው ሕጉን ሲያወጣ ባደረገው ውይይት አስተዳደራዊ ውሣኔዎችና ቅጣቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የራሱ የሆነ ድርሻና ዓላማ ያለው፣ በፍርድ ቤቶች ከሚወሰኑ ውሣኔዎችና ቅጣቶች ጋር ሳይያያዝ መታየት የሚገባው መሆኑን የሚያከራሩ ሀሳቦች እንዳሉበት ተረድተናል፡፡ ስለሆነም አንቀፅ 49 "በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሰረት ከሚጣልበት በተጨማሪ" የሚለው ቃል ወይም በእንግሊዝኛው "in addition to any penalty under section 11" የሚለው አገላለጽ ግብር ከፋዩን በአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ከተዘረዘሩት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቅጣቶች መቀጣቱ በወንጀል ከመከሰስና ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት መቀጣቱን የማያስቀርለት መሆኑን ለማሣየት የገባ እንጅ፣ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ከአምስት ዓመት በማያንስና በአዋጁ ክፍል አስራ አንድ መሠረት እየተሰላ በመቀጮ የሚቀጣ መሆኑን ለመደንገግ የገባ አለመሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የገለፅነውን አተረጓጎም ሕግ አውጭው የገንዘብና የእስራት ቅጣትን በጣምራ ሲደነግግ፣ ድንጋጌዎቹን ለመቅረፅ የተጠቀመባቸውን የሕግ አቀራረፅ ጭብጦች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ሕግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 50 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/....ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ መቀጫና ከአንድ ዓመት በማያንስ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡ በአንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/...ከብር ሃያ ሺህ በማያንስና ከብር መቶ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል" በማለት የገንዘብ መቀጮውንና የእስራት ቅጣቱን በጣምራ የሚወስኑ ቅጣቶች መሆናቸውን በግልፅ በማስቀመጥ ከተጠቀመባቸው የሕግ አቀራረፅ ጥበቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ከእስራት ቅጣት ጋር በጣምራ ጥፋተኛው በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 የድንጋጌውን አቀራረፅ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም ሕግ አውጭው ሊያሣካው የፈለገውን ግብ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰራውን የሕግ ስህተት ሳያርም ማለፉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 የሰጡት የሕግ ትርጉምና ለሕጉ የሰጡትን ትርጉም መነሻ በማድረግ የወሰኑት የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አንደኛው አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘባቸው ወንጀሎች ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ መቀጮ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡
4. አንደኛው አመልካች በቁጥር 3 ከተወሰነው መቀጮ ውጭ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጨምሮ የወሰነውን ብር 454,546.74 /አራት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሣንቲም/ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ 65361

ሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዘመነ ዮሐንስ ጀኔራል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ሙሉጌታ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳውድ ኢብራሂም ጠበቃ ክፍሌ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የመጋዘን ኪራይ ውል አከፋፈል የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ለተከራየው መጋዘን የስድስት ወር ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) እንዲከፍለው ተጠሪ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ የምከፍለው፣ የመንግስት ግብር ቅናሽ ተቀንሶ መሆን ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ግብር ሣይቀንስ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ግብር ሣይቀንስ የቤቱን ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) ለተጠሪ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ አዋጅ ቁጥር 286/1994 ድንጋጌዎችን የሚጥስና በእኔም ላይ የወንጀል ተጠያቂነት እና አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትል ስለሆነ በሰበር ይታረም በማለት የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የግብር እዳውን እኔ ከፍያለሁ፡፡ እሱ የኪራይ ውሉን አስመዝግቤያለሁ፡፡ ስለዚህ አመልካች የሚቀነስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከጠቅላላ ግብር መክፈላቸው አመልካች ቀንሶ እንዲያስቀር በሕግ የተጣለበትን ግዴታ የሚያስቀር አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪን መጋዘን በወር ብር 13,000 (አስራ ሶስት ሺህ ብር) የተከራየ መሆኑና አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው የስድስት ወር ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) እዳ ያለበት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪን የሚያከራክራቸው አመልካች የኪራይ ገንዘቡን በጥቅሉ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 መሠረት መቀነስ የሚገባውን ግብር ቀንሶ ቀሪውን ሊከፍል ይገባዋል የሚለው ነጥብ ነው፡፡

አመልካች ማናቸውንም የአገልግሎት ግዥ ሲፈፀም ሻጩ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካለው የገዛውን አገልግሎት ወይም እቃ ዋጋ ሁለት ፐርሰንት፣ሻጭ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌለው ሰላሳ ፐርሰንት ቀንሶ በማስቀረት ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑ በአዋጅ 286/94 አንቀጽ 83 እና አንቀጽ 91 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባደረግሁት የኪራይ ውል፣ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ተከራይ ሣይሆን አከራዩ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት (የመዋዋል) ነፃነት የሚኖራቸው ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ባሉ ጉዳዩች እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1711 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የተጠሪን መጋዘን የተከራየው አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ የመንግስት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 56 እና አንቀጽ 91 በግልጽ ተወስኗል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ህግ በአስገዳጅነት የደነገገውን ግዴታ ለማስቀረት የሚችል ውል የመዋዋል መብት የላቸውም፡፡ አመልካችና ተጠሪ በህጉ በአስገዳጅነት የተደነገገውን በመተላለፍ ውል ተዋውለው ቢገኙ ውሉ ህግን የሚቃረን በመሆኑ ፈራሽና ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 56 እና አንቀጽ 91 ድንጋጌዎችና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1716 ድንጋጌዎች ጋር በማጣመርና በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 ዓ.ም የተጣለበትን ህጋዊ ግዴታ በመተላለፍ ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ግብር ሣይቀንስ እንዲከፍለው ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1718 ድንጋጌ መሠረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አስገዳጅ ድንጋጌዎች መሠረት የግብር ገንዘብ ሣይቀንስ የስድስት ወር የቤት ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካቀረበ ሁለት ፐርሰንት ተጠሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ ሰላሣ ፐርሰንት በመቀነስ የስድስት ወር የመጋዘን ኪራይ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ 72824

ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት

ተጠሪ፡-አቶ ሚሊዮን አሰፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ በሕጉ አግባብ ደረጃው ተለይቶ ግብሩን ሲከፍል የቆየ ግብር ከፋይ የገቢ መጠኑ ሲሻሽል የግብር ከፋይነቱ ደረጃ ለወጥ የሚወሰነው በግብር አስገቢው ባለስልጣን ነው ወይስ በግብር ከፋዩ ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሲሆን በዚህ አካል ይግባኝ ያቀረቡት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ተጠሪ ለዚህ አካል ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በጥብቅና አገልግሎት የጥብቅና ፈቃድ በደረጃ "ሐ" ከፋይነት ያወጡ መሆኑ፣የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይነት ወደ ደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት እንዲሻሻል የሰጠው ውሳኔ ሳይኖር ተርን ኦቨር ታክስ አሳውቀህ አልከፈልህም፣የ ደረጃ ለ ግብር ከፋይ ሁነህ መዝገብ ሳትይዝ ቀርተሃል በሚል መዝገብ ባለመያዝ ቅጣት የጣለባቸው መሆኑንና ይህ ተግባር ከአዋጁ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 48(1)፣89(1) እና ከደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 22(2) ድንጋጌዎች አንፃር ሕጋዊ ያለመሆኑን ገልፀው የአመልካች መስሪያ ቤት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ጉባኤውም የአሁኑ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን አመልካች ባቀረበው መልስም ተጠሪ አመታዊ ገቢያቸው ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በላይ በመሆኑ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ መሆናቸውን እንደሚያሳይ፣የደረጃ ለ ግብር ከፋይ ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ እስካልሆነ ድረስ በደረጃው የሚጣለውን ማንኛውንም ታክስ መክፈል እንደሚኖርበት፣ በዚህም መሰረት በተቀመጠው የመክፈያ ወቅት ሊከፍሉ እንደሚገባ ስለሚታወቅ ሊከፍሉ እንደሚገባ፣ ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቱም በወቅቱ ባልከፈለውና ሊከፈል በሚገባው ግብር መነሻነት መዝገብ ካለመያዝ መቀጫ መጣሉ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መሆኑን፣ተርን ኦቨር ታክስ በአዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 3 መሰረት ከታክስ ነፃ ካልተደረገ በቀር በተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ከአገር ውስጥ በሚሸጧቸው እቃዎችና አገልግሎት ላይ ተርን ኦቨር ታክስ እንደሚከፈል በግልፅ የተቀመጠና ተጠሪ ቅሬታ በቀረበባቸው ዘመናት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ባለመሆናቸው የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ

እንደአለባቸው፣መዝገብ ባለመያዝ የተጣለው ቅጣትም ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በስተቀር በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ በሙሉ /በከፊል/ የሚከራዩ ሕንጻዎች ባለቤት የሆኑ የሒሳብ መዝገብና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ በህግ የተጣለባቸው መሆኑን፣ማናቸውም የግብር ከፋይ ለአንድ የተወሰነ የግብር ዘመን መያዝ የሚገባውን ተገቢ የሂሳብ መዝገብና መግለጫ ያልያዘ እንደሆነ የተወሰነበትን ግብር 20% መቀጫ እንደሚከፍል በሕጉ መመልከቱን፣ተጠሪውም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ በመሆናቸው የሂሳብ መግለጫ ለመያዝ ግዴታ ባለመወጣታቸው የተቀጡ መሆኑንና ይህንንም ለማድረግ የአሁኑ አመልካች በሕጉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ ክርክሩ በዚኅ መልክ የቀረበለት ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የደረጃ "ለ" ከፍይነት ደረጃውን ራሱ መለወጥ ነበረበት የሚለው የአሁኑአመልካች ክርክር የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑንና ከ1999 እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ፍሬ ግብር አመልካች ከተጠሪ ሙሉ በሙሉ ከተቀበለ በኂላ መቀጫው መወሰኑ የህግ ድጋፍ እንደሌለው በምክንያትነት ይዞ የአመልካችን ውሳኔ ውድቅ አድርጎ ተጠሪ መቀጫውን ሊከፍሉ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ተጠሪ የግብር ከፋይነት የደረጃ ለውጡን ራሳቸው አውቀው የደረጃ ለ ግብር ከፋይ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ሲገባቸው የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት የደረጃ ለውጥ ውሳኔ አላሳወቀኝም በማለት የሚያቀርቡት ክርክርና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የጉባኤውን ውሳኔ በመሻር በመቀጫ ላይ የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት በተጠሪ ላይ የሰጠውን ውሳኔ አስመልክቶ ጉባኤው የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል፡፡ ከዚህም በኂላ የአሁኑ ተጠሪ የሠበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ የደረጃ ለውጥ ውሳኔ መሰጠት ያለበት በግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት እንጂ በግብር ከፋዩ ሊሆን አይገባም በሚል ምክንያት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የጉባኤው ውሳኔ በድምጽ ብላጫ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ሁነው ቆይተው ገቢያቸው ማደጉን ራሳቸው አውቀው በደረጃ ለ ፍሬ ግብሩን ሲከፍሉ ከቆዩ በኂላ የደረጃ ለውጥ ስለመኖሩ አመልካች መስሪያ ወስኖ ስላላሳወቀኝ በደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት መዝገብ የመያዝ ግዴታ የለብኝም በማለት የሚያቀርቡትና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ያገኘው ክርክር ሕጋዊ ድጋፍ የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ ታምኖ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ የአመልካች መስሪያ ቤት ክርክር የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን ያሳያሉ ያኲቸውን ምክንያቶችን አንስተው ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች መስሪያ ቤት ነ/ፈጅም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙኝ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የግብር ከፋይ ደረጃ ለውጥ መኖሩን የመወሰን ስልጣን የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ስልጣን ነው? ወይስ የግብር ከፋዩ ነው? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የተሰማሩበት የገቢ ማስገኛ ስራ 1ኛ ደረጃ የጥብቅና ስራ ሲሆን የተጠየቁትም የ1999፣2000 እና የ2001 ዓ.ም. የግብር ዘመን መዝገብ ባለመያዛቸው ቅጣት እንዲከፍሉ እንዲሁም በ1999 እና 2000 ዓ.ም. የግብር ዘመን የተርን ኦቨር ታክስ ፍሬ ግብር፣ገቢን ባለማስታወቅ ግብር በጊዜ ባለመክፍል ቅጣት እንደተወሰነባቸው የአመልካች መስሪያ ቤት የውሳኔ ማስታወቂያ የሚገልጽ መሆኑን ተጠሪ የአመልካች መስሪያ ቤትን ውሳኔ እየተቃወሙ ያሉት የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ በመሆን ገቢዬን ሳልደብቅ ያስታወቅሁና የተወሰነውን ግብር የከፈልኩ ስለሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን ደረጃዬን ሳይለውጥ በደረጃ ለ ግብር ከፋይ፣የተርን ኦቨር ታክስ ክፈል፣ገቢ ባለማስታወቅና በጊዜ ባለመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ልቀጣ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን፣ተጠሪ አመታዊ ገቢአቸው ብር 100,000.00 ስለመሆኑ ገልፀው በዚህ አግባብ ጥሬ ግብሩን ሲከፍሉ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡

በመሰረቱ ግብር አስፈላጊነቱ ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ሕጉ ይህንኑ የግብር አስፈላጊነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የግብር አሰባሰብ ስርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ በማሰብ በግብር ከፋዩም በአጠቃላይ፣እንደታክስ ከፋይነቱ ደረጃና እንደ ታክሱ አይነት በታክስ ከፋዩ ላይ የጣለው ግዴታ ያለ ሲሆን በግብር ሰብሰቢ መስሪያ ቤት ላይም የጣለው ግዴታ መኖሩ የሚታወቅ ነው፡፡ሁሉም የግብር ከፋይ ተገቢ በሆነው የሂሳብ አያያዝ ስርኣትና የታክስ ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠውና በሚፈቀደው አኳኋን የሒሳብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን አሰናድቶ በስራ ሂደቱ መጠቀም ግዴታው ተብሎ ከሚጠቀሱ ነጥቦች አንዱ ስለመሆኑ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 608/2001፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001፣ ከተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 611/2001፣ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 610/2001 እንዲሁም ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 እና በስራ ላይ ካሉት ሌሎች አዋጆች፣ደንቦች፣መመሪያዎች ጠቅላላ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ሕጎችን ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤትን ከአቋቋመው አዋጅ ቁጥር 587/2001 ጋር አንድ ላይ ስንመለከትም ግብር ሰብሰቢ መስሪያ ቤት ግብር የሚሰበሰብበትን ጊዜና ቦታ፣እያንዳንዱ ግብር ከፋይ የሚከፍለውን የግብር መጠን እንዲሁም ግብር የሚሰበሰብበትን ሁኔታ የግብር መስብሰቢያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት በማያሻያማና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ለግብር ከፋዩቹ ማሳወቅ ያለበት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ይህ በታክስ ስርዓት ግልጽነት እንዲኖር የሚያደርግ ሲሆን በታክስ ሕግ ጽንሰ ሀሳብም ሙሉ ተቀባይነት ያለውና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 12 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይም በአግባቡ ሊተገበር የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ከላይ የተጠቀሱት ሕጎች፣ደንቦችና በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎች በአጠቃላይ ሲታዩ ለግብር ሰብሰቢው መስሪያ ቤት ስልጣን ሰጪ ሲሆኑ መስሪያ ቤቱ ግብርን በወቅቱ የማስከፈል፣ግብር ከፋዩቹ የገቢና ወጪ ሰነድ ካልያዙ የግብር ክፍያ መጠንም ተምኖ የማስከፈልን፣ግብር ከፋዩ በግብሩ አከፋፈል ስርኣት የግብር ህጎችን፣ደንቦችንና አግባብነት ያላቸውን መመሪያዎችን ጥሶ ከሆነ በሕግ እንዲጠየቅ ማድረግን፣የግብር ከፋዩን ንብረት መያዝንና የመሳሰሉት ስልጣንና ተግባራት ያሉት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡እነዚህን ስልጣንና ተግባራት ለመወጣት ደግሞ ግብር ከፋዬችን ደረጃውን የመለየት እና በተገቢው መንገድ ማሳወቅ ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ሕጉ በግብር ከፋዩ ላይ ከጣላቸው መሰረታዊ ግዴታዎች መካከል

ገቢን ማሳወቅና በሕጉ አግባብ ግብሩን መክፈል ነው፡፡ገቢን የማሳወቅ ተግባር ለግብር ከፋዩ ደረጃ አወሳሰን ወሳኝ ሂደት ሲሆን ግብርን ለመክፈልም ቀድሞ መሟላት ያለበት ሁኔታ ነው፡፡ይህ የማሳወቅ ተግባር ደግሞ በሕጉ አግባብ ለእያንዳንዱ የግብር አይነት በሕግ በተቀመጠለት ጊዜና ባለስልጣኑ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ተገቢውን ማስረጃ /ቅፅ /በመሙላት መካሄድ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡በአግባቡ ያልተያዘ መዝገብም ሆነ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ያልተከናወነ ገቢውን አሳውቆ ግብር መክፈል ድርጊት መቀጫን የሚያስከፍል ከመሆኑም በላይ በወንጀል ጭምር ሊያስቀጣ የሚችል ነው፡፡

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 11፣ 14 እና 17 ድንጋጌዎች ስር እንዲሁም በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 18 ስር የግብር ከፋዮች ደረጃ ተዘርዝሯል፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች ለግብር ከፋዮች ደረጃ መሰረት ያአደረጉት አንዱ መነሻ የግብር ከፋዩን የአመታዊ ገቢ መጠን ነው፡፡የደንብ ቁጥር 78/1994 የእያንዳንዱ ደረጃ ግብር ከፋይ ስላለበት ግዴታ በግልጽ ያሳያል፡፡በዚህም መሰረት የደንቡ አንቀፅ 19 መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች ደረጃ "ሀ" እና ደረጃ "ለ" መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 48(1) ድንጋጌ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለባቸው መሆኑን ሲደነግግ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቀጥር 308/1995 አንቀፅ 10 ደግሞ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብና ታክሱን የመክፍል ግዴታ የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡አንድ ግብር ከፋይ በወጣለት ደረጃ መሰረት ግብር የመክፍሉ ሁኔታ ሊቀጥል ወይም ሊለወጥ የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩም ደንብ ቁጥር 286/1994 በአንቀፅ 22(2) ስር ተደግንጓል፡፡በዚህ ድንጋጌ አግባብ የግብር ከፋይ ደረጃ በነበረው ደረጃ እንዲቀጥል ወይም እንዲለወጥ የሚደረገው ግብር ከፋዩ የሚያቀርበውን መግለጫ፣መረጃዎችንና የአከባቢ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህ ተግባር በግብር አስገቢው ባለስልጣን መስሪያ ቤት ሊከናወን የሚችለው ለጉዳዩ ያገኛቸውን ማስረጃዎች በመመርመርና ክብደታቸውን በመመልከት ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ሕግ አውጪው በደንቡ አንቀፅ 18 ስር ለግብር ከፋዮቹ ደረጃ ከአወጣላቸው በኂላ በዚሁ አግባብ ደረጃው ቀጣይነት ሊኖር የማይችልበት አጋጣሚ እንደሚኖር በመገመት የደረጃ ለውጡን ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ሊወስን የሚችበትን አግባብ በደንቡ አንቀፅ 22(2) ስር በግልፅ አስፍሯል፡፡ይህ ድንጋጌ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የደረጃ ለውጡን ሊወስን ይችላል ብሎ ፈቃጅነት ባለው ሁኔታ መደንገጉ ግልፅ ሲሆን ይኸው የድንጋጌው ቅርፅና ይዘት ግን የደረጃ ለውጡ በግብር አስገቢው ባለስልጣን ሳይወሰን ቢቀር ግብር ከፋዩ በራሱ የደረጃ ለወጡን መወሰን ያለበት ስለመሆኑ አያስገነዝብም፡፡ግብር ከፋዩ በራሱ ጊዜ የደረጃ ለውጡን መወሰን አለበት ከተባለ በግብር አሰባሰብ ስርዓት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተእፅኖ ሊያስከትል እንደሚችል የሚታመን ነው፡፡የኸውም ግብር ከፋዩ ገቢውን አሳንሶ በማቅረብ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ሳይከፍል እንዲቀር የማድረግና በታክሱ ስርዓቱ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲስፋፋ ሰፊ በር የሚከፍት መሆኑ ይታመናል፡፡የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣኑን ከአቋቋመው አዋጅ ቁጥር 587/2001ም ሆነ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 38 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው የግብር አስገቢው ባለስልጣን በግብር ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ስራ በማድረግ የግብር ስርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ የማድረግ ሃላፊነት ና ተግባር የተሰጠው መሆኑን ሲሆን ይህንኑ የባለስልጣኑን ሃላፊነትና ተግባር ውጤታማ እንዲሆን ከግብር ከፋዩ የሚጠበቀው ግዴታ በሕጉ የተጣሉበትን ግዴታ መወጣት ነው፡፡በግብር ከፋዩ ላይ በሕጉ የተጣሉበት ግዴታዎች በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በወጣለት ደረጃ መሰረት ግብሩን በወቅቱ፣በተገቢው ቦታና ሁኔታ መክፈል እንጂ ደረጃውን ጭምር ግብር ከፋዩ አውጥቶ ግብርን እንዲከፍል አይደለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ሁነው ከ1999 እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ያገኙትን ገቢ ሳይደብቁ ገቢያቸውን ለአመልካች መስሪያ ቤት ማሳወቃቸው፣ግብር ባለመክፈል ወይም አሳንሰው በማሳወቃቸው የተወሰነባቸው ቅጣት የሌለ መሆኑ፣በአዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 10(2(ሐ)) መሰረት ተጠሪ ግዴታቸውን አልተወጡም የሚል ክርክር በአመልካች በኩል ያለመቅረቡን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ጉባኤው ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች አሁን አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪው ገቢያቸው ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በላይ መሆኑን እያወቁ የግብር ከፋይነት ደረጃቸውን ከደረጃ "ሐ" ወደ ደረጃ "ለ" ራሳቸው ከፍ አድርገው በመወሰን የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ያለበትን መዝገብ የመያዝ ግዴታ መወጣት ነበረባቸው በማለት ነው፡፡ይሁን እንጂ ከላይ በዝርዝር ከተመለከትናቸው የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና አላማ አንጻር ሲታይ አንድ ግብር ከፋይ ገቢውን በሕጉ አግባብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ከማሳወቅ ውጪ ደረጃውን ራሱ ሊወስን እንደሚገባ በሕጉ ግልጽ ግዴታ የተጣለበት ባለመሆኑና የግብር ከፋዩን ደረጃ ለውጥ የመወሰን ስልጣን የግብር አስከፋዩ መስሪያ ቤት በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ላይ መቀጮ የሚጥልበት ሕጋዊ መሰረት የለም፡፡የአመልካቹ ክርክር የግብር ከፋዩን መብትና ግዴታ ከግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ሃላፊነትና ተግባር ጋር ያላገናዘበና ለታክስ ስርዓቱ ውጤታማነትና ቀልጣፋነትም አሉታዊ ውጤት ያለው በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በአንፃሩ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 38፣የደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 18 እና 22፣የአዋጅ ቁጥር 308/19995 አንቀፅ 10(2(ሐ)) እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 587/2001 እና ተቀባይነት ያላቸውን የታክስ ህግ መርሆችን ያገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 16215 ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በአብላጫ ድምፅ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአንድ ግብር ከፋይ ደረጃ ለውጥ ሊወሰን የሚገባው በግብር ከፋዩ ሳይሆን በግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 69602

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1.አቶ አካሉ አለሙ - ጠበቃ ወልደሥላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ፡፡

2. አቶ ተስፋዬ ጸጋዬ - ጠበቃ መብራቱ መለሰ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 69392 ጋር እንዲጣመር የታዘዘ በመሆኑ ሁለቱም መዛግብት ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጉምሩክ አዋጅ ጋር የተያያዘ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- 1ኛ አመልካች አቶ አካሉ ዓለሙ እ.ኤ.አ ከ1990 እስከ አፕሪል 2004 ድረስ ከአሜሪካ ቆይተው ወደ አገራቸው ሲመለሱ በተሰጣቸው የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት በመቀጠም የሰሌዳ ቁጥር 2-544552 አ.አ. የሞተር ቁጥር LM7-5892294፣ የሻንሲ ቁጥር 4T23 F 13 C64 UZ 79592 ቶዮታ፣ ከጃፓን መኪና አስገብተው ለአሁኑ ሁለተኛ አመልካች አቶ ተስፋዬ ጸጋዬ አሳልፈው በመስጠት እንዲጠቀሙበት ማድረጋቸውን፣ እንዲሁም ይህንኑ ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ለግል መገልገያ የገባ በማንኛውም አገልግሎት ላይ የማይውል መሆኑን እያወቁ ለብር 259,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ብር) ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ መኪናውን በመያዣነት በመስጠት ብድር የወሰዱ መሆናቸውን፣ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ ከላይ የተገለጸውን መኪና ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ከአንደኛው አመልካች ተቀብለው እየተገለገሉበት እያለ ሕዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 9፡00 ሰዓት ሜክሲኮ አደባባይ ከሚባለው አካባቢ ሲያሽከረክሩ የተያዙ መሆናቸውን በመዘርዘርና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1(ሀ(ለ)) እና የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989 እንደተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀፅ 73(1(ሀ እና ለ)) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፈዋል በሚል አመልካቾች በወንጀል እንዲጠየቁ ክስ ማቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች በዚህ መልኩ የቀረበባቸውን ክስ ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያነት አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካቾች መከላከያ ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መሆናቸውን ጠቅሶ የዐቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ የሚችሉ አይደሉም በሚል ምክንያት ክብደት ባለመስጠት ውድቅ አድርጎ አመልካቾችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት ጥፋተኛ

አድርጎ አንደኛውን አመልካች በዘጠኝ ወር፣ ሁለተኛውን አመልካች ደግሞ በስድስት ወር እስራት፣ እንዲሁም ብር 170,603.21 (አንድ መቶ ሰባ ሺህ ስድስት መቶ ሶስት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም) እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን የእስራት ቅጣቱን እያንዳንዳቸው በሁለት አመት ገደብ ሁነው በውጪ እንዲጨርሱ፣ በኢግዚብትነት የተያዘው መኪና ደግሞ ለመንግስት እንዲወረስ ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይት አላገኙም። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በተለያዩ መዛግብት ያስከፈቱ ቢሆንም ጉዳዮቹ አንድ ላይ ተጣምረው እንዲታዩ ተደርጓል። የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አንደኛው አመልካች በውጪ አገር ባፈሩት ገንዘብ በአገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ በሕጉ አግባብ ፈቃድ ወስደው አከራካሪውን መኪና በመያዣነት በባንኩ መመሪያና አሰራር መሰረት ያስያዙ መሆኑና ለጥገና ለሁለተኛው አመልካች አሳልፈው የሰጡ መሆኑ በሰውና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ ጥፋተኛ መባላቸው ያላግባብ መሆኑን፣ 2ኛ አመልካችም ተሽከርካሪውን በወቅቱ ይዘው የተገኙት ባላቸው ሙያ የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ለመስጠት ሁኖ እያለ ጥፋተኛ መባላቸው ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የሠጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ክሱን ሊመሰርት የቻለው 1ኛ አመልካች ያለቀረጥ መብት ተጠቃሚ በመሆን ከውጪ ያስገቡትን የቤት መኪና በሕግ ላልተፈቀደለት ሰው አገልግሎት ላይ እንዲውል አድርገዋል፣ እንዲሁም ተሽከርካሪውን ለግል መገልገያ የገባና ለሌላ ማናቸውም አገልግሎት ላይ የማይውል መሆኑን እያውቁ ከባንክ ለወሰዱት ብድር መያዣ ሰጥተው ተገኝተዋል በሚል ሲሆን 2ኛው አመልካችም የ1ኛ አመልካች መኪና ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ከ1ኛ አመልካች ተቀብለው እየተገለገሉበት እያለ ተይዘዋል በሚል መሆኑን ነው። 1ኛ አመልካችም ሆነ 2ኛ አመልካች መኪናው በሕጉ (አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 73(2) እንደተሻሻለ) ቤተሰብ ተብለው ከተቀመጡት ውጪ በሆነ ሰው ሲሽከረከር በተጠሪ መያዙን ሳይክዱ መኪናው በተያዘበት ወቅት መኪናውን ሲያሽከረክሩት የነበሩት የአሁኑ 2ኛ አመልካች መኪናውን በወቅቱ ይዘው የተገኙት ለጥገና ወደ ጋራዥ ለመውሰድ ነው የተያዘው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው። በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካቾችን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምረው የአመልካቾች መከላከያ ማስረጃዎች ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ሊታመን የሚችል አይደለም በሚል ነው። በሌላ አገላለፅ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ፍሬ ነገርን አጣርተውና ማስረጃቸውን መዝነው ነው። የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ የሚያሳየው አመልካቾች የመከላከያ ጭብጣቸውን ለማስረዳት የአቀረቧቸው ማስረጃዎች ታይተው ክብደት የሚሰጣቸው ባለመሆኑና የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎች ሊያስተባብሉ ያልቻሉ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በመገንዘብ ውሳኔ መስጠቱን ነው። እንግዲህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግና ማስረጃን በመመዘን የተሰጠ ነው ከተባለ የአመልካች የሰበር ቅሬታ የሚያሳየው የስር ፍርድ ቤት ፍሬ

ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ረገድ ስህተት ሰርቷል የሚል ይዘት ያለው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ይህንኑ ስህተት ማረም ነው፡፡ በመሆኑም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን ሊያሟላ የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች መኪናው ለቤተሰብ አገልግሎት ሲውል የነበረ መሆኑን ባላስረዱበት ሁኔታ የሕግ ጥያቄ የሚነሳበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡ እንዲሁም ለግል መገልገያ ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መኪናን ከባንክ ብድር ለመውሰድ የባንኩን መመሪያና ስርዓት መሰረት በማድረግ በመያዣ መስጠትም ከአዋጅ ቁጥር 280/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 60/1989 ማሻሻያ ከሆነው አዋጅ ቁጥር 345/1995 የተፈፃሚነት ጊዜ ቅደም ተከተል አኳያ ከሚኖረው የሕጎቹ አተረጓጎም መርህ አንፃር ሲታይ 1ኛ አመልካችን ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ሊያደርጋቸው የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ እንዲሁም 1ኛ አመልካች የተከሰሱት ለቤተሰብ አግልግሎት እንዲውል ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መኪና ለብድር መያዣነት ሰጥተዋል በሚል እንጂ ለኢንቨስትመንት የተፈቀደላቸውን መኪና ለብድር መያዣ ሰጥተዋል በሚል ባለመሆኑና አቃቤ ሕጉም እንደክሱ ያረጋገጠ በመሆኑ 1ኛ አመልካች አዋጅ ቁጥር 280/1994ን መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካቾች ያቀረቡት ቅሬታ የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ ሲሆን የአመልካቾች የቅሬታ ይዘት አመልካቾች እያንዳንዳቸው ብር 170,603.21 ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ይህንኑ ገንዘብ እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ የወሰነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጥቅሉ አመልካቾች ብር 170,603.21 የገንዘብ መቀጮ ሊከፍሉ ይገባል በማለት በሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በማቅረቡ ነው፡፡ ከዚህ ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው የገንዘብ መቀጮው አመልካቾች እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ እኛም የውሳኔውን ሕጋዊነት ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 345/1995 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73(1) በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ በእስራትና በገንዘብ መቀጮ በጣምራ የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊት ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነና ወንጀልና የወንጀል ቅጣት ግላዊ መሆናቸውንና ከአንዱ ወደ ሌላው የማይተላለፍ መሆኑ በ1996 በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 41 ስር ከተደነገገው መሠረታዊ መርህ ለመረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የገንዘብ መቀጮ የወሰነው የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል አመልካቾች ያላቸውን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችና በህጉ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የገንዘብ መቀጮ መነሻ በማድረግና በማገናዘብ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዳቸው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የህግ ድንጋጌ በወቅቱ ለመንግሥት ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ ገንዘብ መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ሊወሰን የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

በመሰረቱ ወንጀል በመፈፀሙ የሚወሰነው የገንዘብ ቅጣት በወንጀል ሕጉ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍታብሔር ለመንግሥት ሣይከፈለው የቀረውን ቀረጥና ታክስ በአንድነትና

በነጠላ እንዲከፍል ለማድረግ ከሚቀርብ ክስና ከሚሰጥ ውሳኔ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አይነት ለሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች በአጥፊዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍታብሔር ክርክር ጊዜ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ጋር ተመሳሳይነት የሌለውና በእያንዳንዱ አጥፊ ላይ ሊጣል የሚገባው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 48956 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሕጉ አግባብ አልተለወጠም፡፡ በመሆኑም በአመልካቾች ላይ የተጣለው የገንዘብ ቅጣት ከሰ/መ/ቁጥር 48956 የሕግ ትርጉም አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ አመልካቾች ለድርጊቱ በወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውም ሆነ እያንዳንዳቸው ለመኪናው ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መክፈል ያለበት ገንዘብ ለፈፀሙት ወንጀል በመቀጫነት እንዲከፍሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ሁኔታ በሰ/መ/ቁጥር 48956፣ 47087 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከተሰጡት ውሳኔዎች ጋር የተጣጣመ በመሆኑ ውሳኔው የወንጀል ህጉን መሠረታዊ የማስረጃ አመዛዘንና የቅጣት አወሳሰን መርሆች የተከተለና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

- በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 153922 ጥቅምት 09 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ፣ ይኸው ፍርድ ቤት በተጠቃሹ መዝገብ ህዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102670 በቀን 17/08/2003 ዓ.ም. በመ/ቁጥር 102888 ሚያዚያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ፀንተዋል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

# ውክልና

የሰ/መ/ቁ. 50985

ሕዳር 5 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- አቶ ስሻህ ክፍሌ - አልቀረቡም

2- አቶ ሰጡኝ በቀለ ጠበቃ ጌትነት ያሻነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- ወ/ሮ አፀደ ዱቤ - አልቀረቡም

2- ወ/ሮ አዛለች ዱቤ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ከውክልና ሥልጣን ውጭ የተፈፀመ የቤት ሽያጭ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ አመልካች የተከሣሽ ከሣሽ ተጠሪዎች የከሣች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክራቸው ይዘትም የአንደኛ ተጠሪ ልጅና የሁለተኛ ተጠሪ ወንድም የሆነው አንደኛው አመልካች የማይንቀሣቀስ ንብረት እንዲሸጥ ፣ እንዲለወጥ ፣ ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላለፍ የተሰጠው ልዩ የውክልና ሥልጣን የለም፡፡ በአደራ እንዲያስተዳድር የሰጠነውን በመተሀራ ከተማ የሚገኝ ቤት ለሁለተኛው አመልካች በመሸጥ ስመሃብቱ የተዛወረ መሆኑን ገልፀው ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በተከሣሽነት ቀርበው ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት ሁለተኛው አመልካች ቤቱን ውክልና ካለው ሰው የገዛሁት ነው የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን ሁለተኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ ቤቱን ከገዛሁ በኋላ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ወጭ በማድረግና በማሻሻል ገንብቻለሁ፡፡ ስለዚህ የገነባሁት ቤት ባለሀብት ነህ ተብሎ እንዲወሰንልኝ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ገንዘቡን በጋራና በተናጠል እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች በከሣሽ ተከሣሽነት ቀርበው አንስተዋል።

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ ቤቱን የሸጠው በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪዎች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ይግባኝ አልተቀበለውም። ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪዎች አንደኛ አመልካች የማይንቀሣቀሥ ሀብት እንዲሸጥ ልዩ የውክልና ሥልጣን ያልሰጡ በመሆኑ አንደኛው አመልካችና በሁለተኛው አመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው። ሁለተኛ አመልካች ከፈለገ አንደኛ አመልካችን ከሚከስ በስተቀር በተጠሪዎች ላይ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል።

አመልካቾች ታህሣሥ 6 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000/1/ በመጥቀስ ያቀረብነውን ክርክር አላግባብ አልፎታል። ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች የሰጡት ውል አንደኛ አመልካች እንደነሡ ሆኖ እንዲከራከርላቸው ፣ ማናቸውም አቤቱታ አቅርቦ እንዲያስፈፅምላቸው ቃለመሃላ ፊርሞ እንዲያቀርብ እነሡን በሚመለከት ማስረጃ እንድቀበል በእነሡ ስም ውል እንዲዋዋል ዕርቅ እንዲደራደር ገንዘብ እንዲቀበል እና በተጠሪዎች ስም የሚዛውር ንብረት ፎርማሊቲ እንዲያሟላ እንዲያዛውር የሚል ይዘት ያለው ነው። አንደኛ አመልካች ውል እንዲዋዋል በተሰጠው የውክልና ሥልጣን ተጠቅሞ የተዋዋለውን የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። ውሉ አይፈርስም እንጅ ይፈርሳል ቢባል ብር 250,000 በማውጣት አሻሽዬ የገነባሁት ሲሆን ስመሀብቱም ወደ ሁለተኛ ተጠሪ የዞረ በመሆኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ታይቶ ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባው በመሆኑ ይህ ነጥብ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል። ተጠሪዎች በቃል ባቀረቡት ክርክር አንደኛ አመልካች የማይንቀሣቀሥ ንብረት በተጠሪዎች ስም እንዲያዛውር እንጂ በተጠሪዎች ስም ያለን የማይንቀሣቀሥ ንብረት ለሌላ ሰው እንዲያስተላልፍ የተሰጠው ልዩ ውክልና የለም። ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም። ሁለተኛ አመልካች ብር 150,000 እንድንከፍለው ያቀረበው ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች በቃል ክርክር የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ሣያጣራና ማስረጃ ሣይመዝን ሁለተኛ አመልካች ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አልፎታል ስለዚህ የሁለተኛ አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በአግባቡ ታይቶ ውሣኔ አልተሰጠበትም በማለት ተከራክሯል።

ከሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር የቀረበው የሰበር አቤቱታና በግራ ቀኙ የተደረገው የቃል ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሁለተኛው አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ ተሰጥቶበታል ወይስ አልተሰጠበትም? የሁለተኛው አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ አልተሰጠበትም የሚባል ቢሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሁለተኛ

አመልካች አንደኛ አመልካችን እንጂ ተጠሪዎችን መክሰስ አይችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች መጋቢት 13 ቀን 1985 ዓ.ም በምዕራብ ሸዋ ዞን የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በማረጋገጥ የሰጡትን የውክልና ሥልጣን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች የሰጡት የውክልና ሰነድ ይዘት ስንመለከተው " ወካዮች በምንከስበትም ሆነ በምንከሰስበት ሁሉ ተወካይ የአንደኛ ተወካይ ልጅ ፣ የሁለተኛ ተወካይ ወንድም እንደመሆኑ መጠን ስለእኛ ሆኖ እንዲከራከርልን ማናቸውም አቤቱታ አቅርቦ እንዲያስፈፅምልን ፣ ቃለመሃላና ማረጋገጫ ፈርሞ እንዲያቀርብ ፣ እኛን የሚመለከቱ ሁሉን ማስረጃዎች እንዲቀበልልን በእኛ ስም ውል እንዲዋዋል ፣ ዕርቅ እንዲደራደር ፣ ገንዘብ እንዲቀበልልን በእኛ ስም የሚዘዋወር ንብረት ማናቸውም ፎርማሊቲ እያሟላ እንዲያዛውርልን ከአቅሙ በላይ በሆነበት ጉዳይ ሌላ ወኪል ነገረ ፈጅ እንዲወክል በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2199 መሠረት የወከልነው መሆኑን እናረጋግጣለን " የሚል ነው፡፡ ይህ የውክልና ሥልጣን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 58 የተደነገገውን የነገረ ፈጅነት ሥልጣን እንዲኖረውና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2204 መሠረት አንደኛ አመልካች የአስተዳደር ሥራ እንዲሰራ ሥልጣን ከመስጠት ባሻገር አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች አውራሽ በአቶ ገ/ኪዳን ቦንጋ ስም የነበረውን ቤት ወደ ተጠሪዎች ስም ካዛወረ በኂላ ቤቱን ለሌላ ሰው ለመሸጥ የሚያስችለው የውክልና ሥልጣን እንዳልሆነ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች የሰጡትን ውክልና ሥልጣን ሰነድ ሙሉ ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተወካዩ ከአስተዳደር ሥራ በቀር ሌላ ሥራ ለመስራት የሚያስፈልግ ሲሆን ልዩ ውክልና እንዲኖረው አስፈላጊ መሆኑንና ተወካዩ ልዩ የውክልና ሥልጣን ከሌለው በቀር የማይንቀሣቀሡ ንብረቶችን ለመሸጥ ወይም አስይዞ ለመበደር የማይችል በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪዎች አንደኛ አመልካች ወደ ተጠሪዎች ሊዛወር የሚችል ማናቸውም ንብረት አስፈላጊውን ፎርማሊቲ በማሟላት በተጠሪዎች ሥም ለማዛወር የሚችል የውክልና ሥልጣን የሰጡት ሲሆን አንደኛ አመልካች ወደ ተጠሪዎች ሥም ያዛወረውን የማይንቀሣቀሥ ንብረት እንዲሸጥ ፣ እንዲለውጥ ፣ በማያዣነት አስይዞ እንዲበደር ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ የሚል ልዩ የውክልና ሥልጣን በግልፅ ያልሰጡት መሆኑ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች ከሰጡት የውክልና ሰነድ ይዘት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አመልካቾች ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች መጋቢት 13 ቀን 1985 ዓ.ም. በሰጡት የውክልና ሰነድ " በስማችን ውል እንዲዋዋል " በማለት የገለፀ በመሆኑ ይህ አገላለፅ ተጠሪዎች አንደኛው አመልካች የማይንቀሣቀሥ ሀብት ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ልዩ ውክልና እንደሰጡ ሊተረጎም ይገባል የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 መሠረት የሚሰጥ ልዩ ውክልና በይዘቱ በልዩ ውክልና የሚፈፀሙ እያንዳንዳቸውን ተግባሮች በግልፅ የሚያመለክት መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪዎች አንደኛ አመልካች " በስማችን ውል እንዲዋዋል " በማለት የሰጡት ውክልና አንደኛ አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2204 የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራት ለመፈፀም የሚያስችሉትን ውሎች በተጠሪዎች ስም ሊፈፅም እንደሚችል የሚያመላክት እንጂ የማይንቀሣቀሥ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ልዩ የውክልና ሥልጣን እንደተሰጠው ተደርጎ የሚተረጎምበት አግባብ የለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የውክልና ሥልጣን የሚተረጎመው ሣይስፋፋ በጠባቡ መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2181 ንዑስ አንቀፅ 3 የሚደነግግ ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች ለአንደኛ

አመልካች የሰጡት ውክልና ሙሉ ይዘት አንደኛ አመልካች በሌላ ሰው ስም ያለን ንብረት በተጠሪዎች ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ፎርማሊቲዎች በማሟላት ወደ ተጠሪዎች ሥም እንዲያዛውር የተወከለ መሆኑን እንጂ አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች በተሰጠው ውክልና ተጠቅሞ በተጠሪዎች ስም ያዛወረውን የማይንቀሣቀሥ ሀብት ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲሸጥ እንዲለውጥ ያልተወከለ መሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም አንደኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ሣይኖረው የተጠሪዎችን ቤት ለሁለተኛ አመልካች ለመሸጥ ያደረገው ውል ተጠሪዎችን የማያስገድድ ፈራሽ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች በአንደኛ አመልካችና በሁለተኛው አመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንልንና ቤታችንን እንድንረከብ በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ የደረሰው ሁለተኛ አመልካች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀፅ 234/1/ሀ/ መሠረት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛው አመልካች ቤቱንና ቦታውን በውል በመረከብ ተጠሪዎች ምንም አይነት ተቃውሞ ሣያቀርቡ በብር 150,000 ቤቱን የገነባሁ በመሆኑ የገነባሁት ቤት ባለቤት መሆኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1178 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1179 መሠረት ይወሰንልኝ፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ያወጣሁትን ብር 150,000 ለገዢው /ለሁለተኛ አመልካች/ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ሁለተኛ አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ላይ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያና ሌሎች የህግና የፍሬ ጉዳይ መከራከሪያዎችን እንዳቀረቡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ላይ ሁለተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክረ በመመርመር ተገቢውን ጭብጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 246 ፣ አንቀፅ 247 እና አንቀፅ 248 መሠረት በመመሥረትና የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ አልሰጠበትም፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የፍሬ ጉዳይ ወይም የህግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የተጠሪዎችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት የሰረዘው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሁለተኛው አመልካች ባቀረበው የተከሣሽነት ክስ ላይ የሰጡት ውሣኔ የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው የተከሣሽነት ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ያልተሰጠበት መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

3.ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር አይቶ የማረም እንደሆነ በህገመንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሁለተኛ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የተከሣሽነት ክስን መነሻ በማድረግ በሁለተኛ ተከሣሽና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ክርክር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተገቢው የፍሬ ጉዳይ ማጣሪያ ተደርጎለት ማስረጃ ተሰምቶና ተመዝኖ ውሣኔ አልተሰጠበትም፡፡ ስለሆነም የግራ ቀኙ ክርክር ከፍሬ ጉዳይና አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ያልተሰጠበትን የሁለተኛ አመልካች የተከሣሽነት ክስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጓዳኝ ጭብጥ አድርጎ በማየት ሁለተኛ አመልካች በአንደኛ አመልካች ካልሆነ በቀር ተጠሪዎች ላይ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 80

ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ እና ከላይ የዘረዘርናቸውን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አንደኛ አመልካች የተጠሪዎች ወኪል ነኝ በማለት ከሁለተኛው አመልካች ጋር ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውሉ ተጠሪዎችን የሚያስገድድና ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ በአንደኛ አመልካች የተጠሪዎች ወኪል ነኝ በማለት ከሁለተኛ አመልካች ጋር የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተጠሪዎችን የሚያስገድድና ፈርሽ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሁለተኛ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ለማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
4. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች በተጠዎች ላይ ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ፣ ተጠሪዎች ሁለተኛው አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ላይ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያዎችና ሌሎች የፍሬ ጉዳይና የህግ ክርክር ፣ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 72337

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ንግስቲ እምነት - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ቴዎድሮስ ተክሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቤት ልረከብ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ ተከሳሽ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡ ተጠሪ በወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች በአደራ እንዲጠብቁ ከተጠሪ አባት ሟች ተክሌ ኪዳኔ የተሰጣቸውንና በሎጊያ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ህጋዊ ወራሽ ለሆኑት ተጠሪ እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን በመግለፅ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱን በሕጋዊ ውክልና መሰረት ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለማስረከብ ልገደድ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች አቶ ተክሌ ኪዳኔ ኤርትራዊ በመሆናቸው ከአገር ሲወጡ ለአመልካች በሰጡት ውክልና መሰረት ቤቱን አመልካች ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ማስተላለፋቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት በውክልና ስልጣን የተፈፀመ ተግባር አመልካችን ቤቱን እንዲያስረክቡ አያስጠይቃቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩና ተገቢው ማጣራትና ተጨማሪ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ ጉዳዩ የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት መታየት የነበረበት ነው በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮ ጉዳዩ የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት እንዲታይ ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የዳኝነት ገንዘብ ሲከፈልበት የሚታይ ነው በማለት መመለሱ የስነ ስርዓት ሕጉን ያልተከተለ መሆኑን፣ እንዲሁም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጭብጡን ለውጦ ዋናውን ጉዳይ ሊመለከት የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌ መኖሩን ጠቅሶና ድንጋጌውን ከለየ በኋላ ዋናውን ጉዳይ መርምሮ አመልካች አለ የሚሉትን የውክልና ስልጣንና የሽያጭ ውል ማስረጃዎች በሚመለከታቸው አካላት በተለያየ ጊዜያት የተለያዩ መግለጫዎች የቀረቡባቸው በመሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን አጠራጣሪ የሚያደርገው መሆኑን፣ አመልካች አለ የሚሉት የውክልና ሰነድ ማስረጃ ይዘቱ ሲታይም አከራካሪውን ቤት ለማስተዳደር እንጂ ለመሸጥና ለመለወጥ የማያስችላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን ጠቅሶና የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ

በመሻር የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው የውክልና ስልጣን ማስረጃውን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያለመቀበሉ ከሰነዱ ይዘት ውጪ ነው በማለት ዘርዝረው ውሳኔው ተሽሮ ለተጠሪ በውክልና ስልጣኑ መሰረት ቤቱን የሸጡበት ዋጋ ሕጋዊ ተቀናሽ ሂሳቦች ካሉ የሚቀነሱ መሆኑ ተገልፆ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት ለአመልካች የተሰጠው ውክልና ቤቱን ከማስተዳደር ባሻገር ለመሸጥ የሚያስችል አይደለም በማለት አመልካች ከውክልና ሥልጣናቸው አሳልፈው ተገልግለዋል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረት ያደረገው በፍሬ ነገር ክርክር ላይ በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የመልሳቸውን ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪ አባት ሟች ተክሌ ኪዳኔ የሰጡት ፈቃድና ውክልና ሳይኖር አመልካች አከራካሪውን ቤት ለ3ኛ ወገን ማስተላለፋቸው ተረጋግጧል ተብሎ ነው በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው፡፡ የተጠሪ ክስ ሲታይም አመልካች ቤቱን በአደራ ለመጠበቅ ተረክበዋል የሚል ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከላይ ከተገለፀው ድምዳሜ ሊደርስ የቻለው አመልካች አለ የሚሉት የነሐሴ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. የውክልና ስልጣን ማስረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ የውክልና ውሉን መዝግቧል የተባለው የክልሉ ፍትሕ ቢሮ መግለጫ እንዲሰጥበት በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ሰነዱ በቢሮው ሊገኝ አልቻለም ብሎ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ ከሰጠ በኋላ በድጋሚ በፃፈው የማስተካከያ ደብዳቤ የውክልና ሥልጣን ማስረጃው በቢሮው ተረጋግጦ የተመዘገበና በተገቢው ማህበር ውስጥ ተያይዞ የሚታወቅ መሆኑን መግለፁና በሽያጭ ውሉ ላይ ማጣራት አድርጎ መግለጫ እንዲሰጥበት የታዘዘው የአስተዳደር አካልም መጀመሪያ በሰጠው መግለጫ ውሉ የማይታወቅ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ከገለፀ በኋላ በድጋሚ ማስተካከያ ነው ብሎ በፃፈው ደብዳቤ የሽያጭ ውሉ በሕጉ አግባብ የሚታወቅ መሆኑን ማስታወቁ የሰነድ ማስረጃዎቹ አጠራጣሪ መሆናቸውን ያሳያል፣ የውክልና ስልጣን ሰነዱም ቤትን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችል አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች ዘርዝሮ ነው፡፡

በቅድሚያ ተጠሪ ጉዳዩ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(39ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ያለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የውክልና ሰነዱ በመንግስት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ሆኖ እያለና የሰነዱ ይዘትም ልዩ ውክልና ሊባል የሚችል ሆኖ እያለ ማስረጃው ተቀባይነት ማጣቱ ያለአግባብ ነው በሚል መሆኑን ከቅሬታቸው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ቅሬታቸው በውክልና ማስረጃው ተቀባይነት ማጣቱ ላይ በመሆኑና የሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት ደግሞ የሕግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ስር የሚወድቅ እንጂ የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ ክርክር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የተጠሪ ተቃውሞ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

ወደ ዋናው ስንመለስም፤ በመሰረቱ የአስተዳደር መ/ቤት አንድ ጊዜ የሰጠው የደብዳቤ መግለጫ ትክክለኛ ያለመሆኑን በሌላ ጊዜ ከደረሰበት በዚሁ ላይ ሌላ ማስተካከያ ደብዳቤ ቢጽፍ መ/ቤቱ ሁለት ጊዜ የተለያየ ይዘት ያላቸውን ደብዳቤዎች በመጻፉ ብቻ ደብዳቤዎቹ ለማስረጃነት ዋጋ

ሊሰጣቸው አይገባም ብሎ ሁልጊዜ መደምደም የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ዋናውና ቁልፉ ነገር ከተፃፉት ደብዳቤዎች መካከል የትኛው ነው ትክክለኛ የሚለውን በተገቢው መንገድ ማጣራት ሲሆን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው ደብዳቤ ካለ ለዚሁ ተገቢው የማስረጃነት ዋጋ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አለ የሚሉትን የውክልና ስልጣንና የሽያጭ ውሉ በሚመለከታቸው አካላት ስለመኖራቸው በድጋሚ በተፃፉት የማስተካከያ ደብዳቤዎች ተረጋግጠዋል፡፡ እነዚህ ማስተካከያ ደብዳቤዎች ትክክለኛ ያለመሆናቸው ወይም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የተሰጡ ስለመሆኑ ተጠሪ ያነሱት ክርክር ካለመኖሩም በላይ ፍሬ ነገሩን ያጣሩት ፍ/ቤቶችም በዚህ ረገድ ያሉት ነጥብ የለም፡፡ በመሆኑም የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰነድ ማስረጃዎችን ዋጋ ያልሰጠበት ምክንያት ሕጋዊ ካለመሆኑም በላይ የውክልና ማስረጃውን በተመለከተም ማስረጃው ዋጋ የሌለው መሆኑን በውሳኔው ላይ ከአሰፈረ በኋላ ይዘቱን ተመልክቶ የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ነሐሴ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. የተደረገ የተባለው የውክልና ስልጣን ማስረጃ የተጠሪ አባት ለአመልካች አከራካሪውን ቤት እንዲጠብቁላቸው፣ እንዲያስተዳድሩላቸውና ሸጠው ገንዘቡን በመቀበል እንዲልኩላቸው በሚል የተቀመጠ ስለመሆኑ ይዘቱ ያሳያል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ የውክልና ስልጣን ለአመልካች የተሰጣቸው ስልጣን ቤቱን የማስተዳደር ነው፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ማከናወን የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2203 እና 2204 ስር በተመለከተው መሰረት የማስተዳደር ተግባራት የሚባሉትን እንጂ ቤቱን የመሸጥ የመለወጥ ተግባርን ጭምር አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በውክልና ስልጣኑ አመልካች ቤቱን ከማስተዳደር በተጨማሪ መሸጥና መለወጥ የሚችሉ ስለመሆኑ የሚያሳየውን የዓረፍተ ነገር ክፍል በመተው የተያዘ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በእርግጥ ለአመልካች በተሰጠው ውክልና ስልጣን ላይ አመልካች ምን ምን አይነት ተግባራትን ማከናወን እንደሚችሉ ከተዘረዘረ በኋላ የተጠቀሰው የፍትሓ ብሔር ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 2199 ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችል ስልጣን ልዩ ውክልና እንደሚያስፈልገው የፍ/በ/ሕ/ቁጥር 2205 በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ቁጥር ንዑስ አንድ ድንጋጌ ተወካዩ ከአስተዳደር ስራ በቀር ሌላ ስራ ለመስራት የሚያስፈልግ ሲሆን ልዩ ውክልና እንዲኖረው አስፈላጊ መሆኑን ሲያስቀምጥ ንዑስ ሁለት ድንጋጌ ደግሞ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መሸጥ ወይም አስይዞ መበደር የሚችለው ልዩ የውክልና ስልጣን ሲኖረው ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመሸጥ የሚያስችላቸው ልዩ ውክልና የላቸውም የተባለው በውክልና ሰነዱ የተዘረዘሩት የተወካዩ ኃላፊነቶች ሙሉ በሙሉ ይዘታቸው ሳይታይ ከመሆኑም በላይ በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2199 መሆኑ ለአመልካች የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ጠቅላላ ውክልና ስለመሆኑ ያሳያል በሚል ምክንያትም ጭምር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የውክልና ሰነዱ ይዘት በግልፅ ውክልና ተቀባዩ የተሰጠው ስልጣን የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለመሸጥ የሚያስችል ስለመሆኑ እየገለፀ ስለልዩ ውክልና አስፈላጊነት የተቀመጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2205 በውክልና ስልጣን ሰነዱ ያለመጠቀሱ ውክልናው ልዩ የውክልና ስልጣን አይደለም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ስለመሆኑ የሚያሳይ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ዋናውና ቁልፍ ነገር ለውክልና ተቀባዩ የተሰጡት ተግባሮች በዝርዝርና ግልጽ ሁኔታ ተጠቅሰው በውክልና ሰነዱ ላይ መገኘት እንጂ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ያለመጠቀሳቸው አይደለም፡፡ የሰነዱ ይዘት ግልጽ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በውክልና ስልጣን ሰጪውና በውክልና ስልጣን ተቀባዩ አልተጠቀሱም ተብሎ ሰነዱ ዋጋ

እንዲያጣ ማድረግ የተዋዋዮችን ሐሳብ ውጤት እንዳይኖረው የሚያደረግ በመሆኑ በውል አተረጓጎም ደንቦችም ተቀባይነት የሌለው አካሄድ ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የውክልና ሰነዱን ይዘት ሙሉ በሙሉ ሳይመለከትና በሰነዱ ላይ ስለልዩ ውክልና ሥልጣን የሚደነግገው የፍትሓ ብሔር ሕግ ድንጋጌ አልተጠቀሰም በሚል እምነት አመልካች ከተጠሪ አባት ቤቱን ለመሸጥ የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን የለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2179 ፣ 2205 እና 2005 /1/ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

የተጠሪ አባት ቤት በአመልካች የተሸጠው በሕጉ አግባብ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ነው ከተባለ ቀጥሎ መታየት ያለበት ተጠሪ ያላቸው መፍትሔ ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የውክልና ስልጣን ሰጡ የተባሉት ግለሰብ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው ከመረጋገጡም በላይ አመልካች ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ ለተጠሪ ወይም ሌሎች ሕጋዊ የሟች አቶ ተክሌ ኪዳኔ ወራሾች ሰጥቼአለሁ የሚል ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶችም ሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የላቸውም፡፡ ይልቁንም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የጽሑፍ መልስ ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ ለተጠሪ ከመክፈል ውጪ ቤቱን ለመመለስ የሚገደዱበት አግባብ የሌለ መሆኑን ግልጽ አድርገው ጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሕጉ አግባብ በተሰጠ የውክልና ስልጣን የተሸጠውን ቤት አመልካች እንዲያስረክቡ መጠየቅ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ባይኖርም ቤቱ ተሸጠ የተባለበትን ገንዘብ ግን በወራሽነት መብታቸው ልክ መሠረት ከአመልካች ከመጠየቅ አይታገዱም፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2310 ነሀሴ 12 ቀን 2003 ዓ.ም አመልካች አከራካሪውን ቤት ከማስተዳደር ባሻገር ለመሸጥ የሚያስችላቸው የውክልና ስልጣን የለም ተብሎ የተሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ አባት ነሐሴ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ማስረጃ በማስረጃነት ተቀባይነት የማይሰጥበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን የሰነዱ ይዘት ሲታይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመሸጥ የሚያስችላቸው በመሆኑ ሽያጩ የተከናወነው አመልካች በተጠሪ አባት በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ስለሆነ አመልካች ለተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቡ ሊገደዱ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ቤቱን የሸጡበትን የሽያጭ ገንዘብ ተጠሪ ካላቸው የወራሽነት መብት መጠን አንጻር ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

የሰ/መ/ቁ. 68498

ሰኔ 07 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ገብረ ክርስቶስ ገብረ እግዛብሔር

ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ

ተጠሪ፡- ሳባ እምነበረድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ነገረ ፈጅ አቶ ቴድሮስ ገብረ ዮሐንስ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነ በረድ ሽያጭ ውል አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በማዕከላዊ ዞን አድዋ ምድብ ችሎት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር 2781 ሜትር ኩብ እምነበረድ ከቫት ውጭ በብር 939,948 /ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር/ ለመግዛት ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ውል የተዋዋለና በዚህ ውል መሠረት ሻጭ /ተጠሪ/ 616.4 ሜትር ኩብ የእምነበረድ በብር 205,017.47 /ሁለት መቶ አምስት ሺህ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ አስረክቦኛል፡፡ ገዥው /አመልካች/ ብር 661,217.37 /ስድስት መቶ ስልሣ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰላሣ ሰባት ሣንቲም/ ቅድሚያ ክፍያ ከፍያለሁ፡፡ ተከሣሽ/ ተጠሪ/ በሽያጭ ውሉ መሠረት ዋጋው ከተጨማሪ እሴት ታክስ ውጭ ብር 734,930.55 የሆነ 2164.60 ሜትር ኩብ እብነበረድ አላስረከበኝም ስለዚህ በሽያጭ ውሉ መሠረት እብነበረዱን እንዲያስረክብ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ እስጢፋኖስ አስፋው የተባለ የድርጅቱ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በክርክር ጣልቃ እንዲገባ የጠየቀ ሲሆን ከከሣሽ /አመልካች/ ጋር የተዋዋልነው የእብነበረድ ሽያጭ የለም፡፡ ከሣሽ ብር 661,217.37 አልከፈለም፡፡ በህግ ፊት የፀናና ተጠሪን የሚያስገድድ የእብነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የድርጅቱ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባለት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሥር ፍርድ ቤት በወቅቱ የድርጅቱ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ የሆኑትንና በሽያጭ ውሉ ላይ የፈረሙት የተጠሪ የሥራ ኃላፊ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አድርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን ቃልና የተጠሪን

ምስክሮች ቃልና በግራ ቀኙ በኩል የፅሑፍ ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኋላ የተጠሪ የግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ ከከሣሽ /አመልካች/ ጋር የእብነበረድ ሽያጭ ውል የተዋዋለው ሥራ አስኪያጅ በቃል ትዕዛዝ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ ገብ ይህንን በማስተባበል አልተከራከረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች /ከሣሽ/ ለተከሣሽ /ተጠሪ/ ብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በቼክ የከፈለ ሲሆን ተከሣሹም 616.4 ሜትር ኩብ እምነበረድ ለከሣሽ /ተጠሪ/ አስረክቧል፡፡ ስለሆነም በከሣሽ /አመልካችና/ በተከሣሽ /ተጠሪ/ መካከል የፀና የእምነበረድ ሽያጭ ውል ያለ በመሆኑ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ውጭ ዋጋው ብር 734,930.35 የሆነ 2164.60 ሜትር ኩብ እምነበረድ የማስረከብ ግዴታ አለበት በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪን በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል የሽያጭ ውጭ የመዋዋልና የመፈረም ሥልጣን ያለው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ከሥልጣኑ ውስን ውጭ ከአመልካች ጋር የተዋዋለው የእምነበረድ ሽያጭ ውል ድርጅቱን የማያስገድድ በመሆኑ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አቶ እስጢፋኖስ አስፋው ከሥራ አስኪያጁ በተሰጠው የቃል ትዕዛዝ መሠረት የሽያጭ ውሉን መዋዋሉን በግልፅ በማመን መልስ ሰጥቷል፡፡ የሰው ምስክሮችም የሽያጭ ውሉ ተፈፅሞ እብነበረድ እርክክብ የተጀመረ መሆኑን በማረጋገጥ አስረድተዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የማረም ሥልጣን ያለው ቢሆንም በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳና በማስረጃ ያልተጋገጠ ፍሬ ጉዳይ በማንሣት ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሰበር ችሎት የህሊና ግምት መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሥራ አስኪያጅ ባይፈርምበትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል የተዋዋሉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪን የሚያስገድድ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 27 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው መልስ የተጠሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በውሉ ላይ ስላልፈረመበት ተጠሪ የሽያጭ ውሉን ለማቋቋም አስፈላጊ የሆነውን ፈቃዱን ሰጥቷል ለማለት አይችልም፡፡ በክርክሩ በተጠሪ ጠያቂነት ወደ ክርክር የገቡት ሰው በሥር ፍርድ ቤት የሰጡት መልስ ሽያጩ የእጅ በእጅ ስለሆነ የውል ሰነድ አያስፈልግም ነበር፡፡ የፅሑፍ ውክልና ሣይኖረኝ በቃል ተነግሮኝ በስህተት የፈረምኩት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ ተጠሪን የሚያስገድድ ውል አይደለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የፈረሙትና ተጠሪን የሚያስገድድ የፀና ውል አለመኖሩን በማረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች እኔ ስለተጠሪ ውስጣዊ አሰራር የማውቀው ነገር የለም፡፡ ከዚህ በፊት የገበያ ዋና ክፍል ኃላፊው የፈረሙበት የሽያጭ ውል ከተጠሪ ጋር ተዋውየ ውሉ ተፈፃሚ ሆኖልኛል፡፡ የፅሑፍ ውክልና አልተሰጠም በሚል ምክንያት ብቻ ውሉ አልተደረገም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን በቼክ

ሲከፈለው ተቀብሏል፡፡ ስለዚህ ውል የለም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ሀምሌ 7 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪና አመልካች የተዋዋሉት የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳይን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተፃፈውን ጭብጥ ለመወሰን ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የማዕከላዊ ዞን የአድዋ ምድብ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያረጋገጧቸውን ፍሬ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ በማየት የአመልካችንና የተጠሪን ምስክሮች ቃል የሰማውና የግራ ቀኙን የሰነድ ማስረጃ የመዘነው የአድዋ ምድብ ችሎት የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የእምነ በረድ ሽያጭ ውል የሚል ርዕስና ዝርዝር ይዘት ያለው የፅሑፍ ሰነድ የተፈራረሙ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ጠቅላላ ዋጋው ቫት ሣይጨምር ብር 939,948 /ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር/ የሆነ 2781 ሜትር ኩብ እምነበረድ ለመሸጥ መስማማቱን አመልካችና ተጠሪ ሰነዱን በተፈራረሙበት ዕለት አመልካች ብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በቼክ የከፈለ መሆኑንና ሰነዱን ከተፈራረሙ በኋላ ተጠሪ ከቫት ውጭ ዋጋው ብር 205,017.47 /ሁለት መቶ አምስት ሺህ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ የሆነ መጠኑ 616.4 ሜትር ኩብ እብነበረድ ለአመልካች ማስረከቡ በማስረጃ እንደተረጋገጠ በውሣኔው ገልፆል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪን በመወከል ፊርማቸውን በሰነዱ ላይ ያሣረፉት /የፈረሙት/ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተደርጎ ሽያጩ የእጅ በእጅ ሽያጭ ስለሆነ ሰነድ አያስፈልገውም ነበር፡፡ በስህተት ነው የፈረምኩት ሰነዱ ላይ የፈረምኩት ሥራ አስኪያጁ በቃል ትዕዛዝ ስለሰጡኝ ነው በማለት መልስ የሰጠ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው የገለፃቸውና ከላይ የዘረዘርናቸው ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛና የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጣቸው በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት በመሰረዝ አቋሙን በግልፅ አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሣየን ከላይ የተገለፁት ፍሬ ጉዳዮችን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተመሣሣይ መደምደሚያ ላይ የደረሡ መሆኑን ነው፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከላይ በዝርዝር የተገለፁትና ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮች በተጠሪና በአመልካች መካከል ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም. የእምነበረድ ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን ወይም ውል ያልተደረገ መሆኑን ወይም ውሉ ጉድለት ያለበት መሆኑን ለመወሰን ያላቸውን ፋይዳ የተረዱበትና አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች የተረጎመበት ሁኔታ መመልከቱ ሁለተኛው መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪን በመወከል በህግ የፀና ውል የመዋዋል ሥልጣን ያለው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በውሉ ላይ ያልፈረመ በመሆኑ ተጠሪና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ያደረጉት የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሁለት ሰዎች መካከል የሽያጭ ውል አለ ለማለት ሻጭ የሆነው ወገን ገዥ ለሆነው ሌላው ወገን ዋጋ በገንዘብ የተወሰነውን አንድ ነገር ገዥው ሊከፍለው ግዴታ በገባበት መሠረት ሊያስረክብና ባለቤትነቱን ሊያስተላልፍበት የሚገደድበት ውል ሲመሠርት እንደሆነ መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2266 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ለሽያጭ ውሉ ድርጅቱን በመወከል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1178/ሀ/ መሠረት ፈቃድና ስምምነቱን መስጠት የሚችለው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ በውሉ ላይ ሥራ አስኪያጁ ያልፈረመበት በመሆኑ በህግ ፊት የፀና የሽያጭ ውል የለም በማለት ይከራከራል፡፡ በእርግጥ ሥልጣን ያለው  ሥራ አስኪያጅ በንግድ ድርጅቱ ሥም በውክልና የመፈረምና ሥራውንም ለማካሄድ እንደሚችል በንግድ ህጉ አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን ፣ ሥራ አስኪያጁ የንግድ ድርጅቱ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማናቸውንም ግዴታ የመፈፀም ሙሉ ሥልጣን እንዳለው እንደሚገመት በአንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው የህግ ድንጋጌዎች ተጠሪን በመወከል የእምነበረድ ሽያጭ ውልም ሆነ ሌሎች ውሎችን የመዋዋል ሙሉ ሥልጣን ያለው የተጠሪ  ሥራ አስኪያጅ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡  እዚህ ላይ  የሚነሳው ጥያቄ የተጠሪን ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ያህል ሙሉ ሥልጣን የሌላቸው የተጠሪ የሥራ ኃላፊዎች በሚያደርጉት የሽያጭ ውል ተጠሪ በልዩ ሁኔታ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሁኔታ ይኖራል ወይስ አይኖርም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪ ውክልና ባለሙሉ ሥልጣን የሆነው ሥራ አስኪያጅ አመልካችና ተጠሪ ታህሣሥ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተዋዋሉት የእምነበረድ ሽያጭ ስምምነት ሰነድ ላይ ባይፈርምም፣  ተጠሪ ለአመልካች  እምነበረድ በመሸጥ የገባውን የውል ግዴታ ሰነዱ ከመፈረሙ በፊት ያውቀው እንደነበርና በውሉ ላይ ስምምነቱን በፊርማው ያረጋገጠው  የተጠሪ  የግዥ ክፍል ኃላፊ በውሉ ላይ የፈረመው ከተጠሪ ሥራ አስኪያጅ በተሰጠው የቃል ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት በሰጠው መልስ አረጋግጧል፡፡ ይህንን ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ አላስተባበለም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ "የእጅ በእጅ ሽያጭ ስለሆነ ውል አያስፈልግም? የፅሑፍ ውክልና ሳይኖረኝ በቃል ተነግሮኝ በስህተት የፈረምኩት ሰነድ" ነው በማለት የተከራከረ መሆኑን በግልፅ ያሰፈሩ ሲሆን የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በፅሑፍ ሣይሰጠው የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ የፈረመው ሰነድ ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ ከአመልካች ጋር የሚገባውን የእምነበረድ ሽያጭ ውል ግዴታ አስቀድመው አውቀውትና ተስማምተውበት ሰነዱን ሊፈርሙ የማይችሉ በመሆናቸው የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ውሉን እንዲፈርሙ የቃል ትዕዛዝ የሰጡ መሆናቸውን ተጠሪ በግልፅ ክዶ ካልተከራከረና ካላስተባበለ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ የሽያጭ ውሉን የፈረመው ከሥራ አስኪያጁ በተሰጠው የቃል ትዕዛዝ ነው የሚለውን ፍሬ ጉዳይ እንዳመነ የሚቆጠር መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀፅ 2/ሠ/ እና ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ድርጅቱን በመወከል የእምነበረድ ሽያጭ ውሉን እንድዋዋል በሰጠው የቃል ትዕዛዝ መሠረት የግዥ ክፍል ኃላፊው የእምነበረድ ሽያጭ ውሉን  ፈርሟል፡፡ የእምነ በረድ ሽያጭ  ውል በልዩ ፎርም  እንዲደረግ የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪን ድርጅት የመወከል ሙሉ ሥልጣን  ያለው ሥራ አስኪያጅ በልዩ ሁኔታ ከአመልካች ጋር የሚደረገውን የእምነበረድ ሽያጭ ውል ድርጅቱን በመወከል እንድፈራረም ለተጠሪ ግዥ ክፍል የሰጠው ውክልና የግድ በፅሑፍ  መሆን እንደሌለበት " ስለውሉ  አፈፃፀም ሕጉ አንድ አይነት ፎርም እንዲደረግ ያስገደደ እንደሆነ ውሉ የሚፈፀምበት

ሥልጣን በዚሁ አይነት ፎርም ለወኪሉ መስጠት አለበት " በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2180 ድንጋጌ ይዘትና ይኸው ድንጋጌ በተቃራኒ ሁኔታ ሲታረገም /acontrartio interpretation/ የሚኖረውን ውጤትና ተፈፃሚነት ወሰን በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም የተጠሪ ድርጅት ወኪልና ባለሙሉ ሥልጣን የሆነው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2215 ንዑስ አንቀፅ 3 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2180 መሠረት በማድረግ የሰጠውን የቃል ውክልና በመቀበል የተጠሪ ድርጅት የግዥ ክፍል ኃላፊ ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ከአመልካች ጋር ያደረገው የእምነበረድ ሽያጭ ውል በተጠሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ዕውቅና ስምምነትና ትዕዛዝ የተፈፀመ የሽያጭ ውል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ከላይ በዝርዝር ከተገለፀው በተጨማሪ ተጠሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቃል የሰጠው ትዕዛዝና ውክልና የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ከአመልካች ጋር ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የተፈራረመውን ሰነድ ከተሰጠው ሥልጣንና ውክልና ውጭ ነው በማለት ውሉን በመቃወም ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ ስለመኖሩ አላስረዳም፡፡ ተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊው የተፈራረመውን ውል ያፀደቀው መሆኑን በግልፅ ባያረጋግጥም ይህንን ሰነድ መሠረት በማድረግ የተቀበለውን የብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ቼክ ጥቅም ላይ ማዋሉና ሰነዱ ከተፈረመ በኂላ ከቫት ውጭ ዋጋው ብር 205,017.47 /ሁለት መቶ አምስት ሺህ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሳባት ሣንቲም/ የሆነ 616.4 ሜትር ኩብ እምነበረድ ለአመልካች ያስረከበ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃለፊ ከአመልካች ጋር ያደረገውን የእምነበረድ ሽያጭ ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2214 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች መሠረት ፈቅዶ እንደተቀበለው የሚያስቆጥረው ነው፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ ከገለፅናቸው አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ሣያገናዝብ በውሉ ላይ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ አለመፈረማቸውን ብቻ መሠረት በማድረግ በተጠሪና አመልካች መካከል የተደረገ የእብነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. ተጠሪና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የእምነበረድ ሽያጭ ውል ተዋውለዋል፡፡ በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል ህግ መሆናቸውና የህግ ያህል አስገዳጅነት ያላቸው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ውሉ ከተደረገበት ቀን አንስቶ በአንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ውስጥ 2781 ሜትር ኩብ እብነበረድ በብር 939,948 ለአመልካች ለመሸጥ በገባው የውል ግዴታ መሠረት ዋጋው ብር 205,017.47 ሣንቲም ከቫት ውጭ የሆነ 616.40 ሜትር ኩብ የእምነበረድ ብቻ ያስረከበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው ተጠሪ 2164.60 ሜትር ኩብ እብነ በረድ የማስረከብ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከፍትብሔር ህግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ ለሚስረክበው እብነበረድ በውሉ መሠረት ዋጋውን የመክፈልና የገዛውን ዕምነበረድ የመረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2303 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ውሉን በተዋዋለበት ቀን የብር 500,000 በቼክ ለተጠሪ ክፍያ የፈፀመ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች በውሉ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን ብር 439,948 /አራት መቶ ስላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር / መክፈል ቀሪውን 2164.60 ሜትር ኩብ እብነበረድ ተረክቦ የመውሰድ ኃላፊነት

አለበት ፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ በመሻር በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን የአድዋ ምድብ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ያፀናና ህጋዊ ውጤት ያለው የእምነበረድ ሽያጭ ውል ተዋውለዋል በማለት ወስነናል፡፡
4. በውሉ መሠረት ተጠሪ 2164.60 ሜትር ኩብ እምነበረድ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
5. በውሉ መሠረት አመልካች ከዚህ በፊት በቼክ ለተጠሪ ከከፈለው ብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በተጨማሪ ብር 439,948 /አራት መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር/ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ወስነናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 73291

ሀምሌ 4 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1/ አቶ አፅብሃ ወልዳይ } አቶ ሀይማኖት ቢተው ቀረቡ

2/ አቶ ቅባቱ ግደይ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዙሪያሽ አሰግድ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ ፀሐይ አበራ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርባ ልጄ የሆነችው ወ/ሮ ድንቄ መኮንን በአሶሳ ዞን ኩርሙክ ወረዳ በኩሙሩክ ከተማ ውስጥ ከወ/ሮ ምስራቅ ኣንጋሉ ገዝታና አስፋፍታ ስትመራው የነበረውን የድርጅት ቤት በውክልና እንዲስተዳድርላት ለአንደኛ ተከሳሽ የውክልና ሥልጣን ሀምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም ሰጥታው ሄዳለች፡፡ ወ/ሮ ድንቄ መኮንን ሀምሌ 29 ቀን 1998 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች በመሆኑ የአንደኛው ተከሳሽ /አንደኛው አመልካች/ የውክልና ሥልጣን ቀሪ ሆኗል፡፡ ተከሳሾች /አመልካች/ ሟች ከሞተች በኂላ ለሁለት ዓመት የቤት ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው ከዚያ በኂላ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ሆነው ስላልተገኙ ክስ ያቀረበበትን ንብረት እንዲለቁና በየወሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ ሂሳብ ኪራይ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካቾች በተከሳሽነት ቀርበው የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ አንደኛ አመልካች ከወ/ሮ ድንቄ መኮንን ሀምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. በተሰጠው የመሸጥና የመለወጥ የውክልና ሥልጣን መሠረት ቤቱን ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ለሁለተኛው ተከሳሽ /ሁለተኛ አመልካች/ የሸጡ መሆናቸውንና ገዥው ሁለተኛው አመልካችም ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ተረክበው እያለሙና እያስፋፉ የሚገኙ መሆኑን በማንሣት ተከራክረዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኂላ አንደኛው አመልካች ቤቱን ለሁለተኛ አመልካች ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. በተደረገ የሽያጭ ውል የሸጠ መሆኑንና ሽያጩም

ፍትህ ቢሮ ቀርቦ የፀደቀ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ አመልካቾችን በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርባ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አንደኛ አመልካች የሽያጭ ውሉን ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ በመቅረብ ያስመዘገበውና ስመሃብቱም ለገዥ ለሁለተኛው አመልካች እንዲዛወር ያደረገው ወካይም ወ/ሮ ድንቄ መኮንን ከሞቱ በኋላ በ2001 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም. በመሆኑ አንደኛ አመልካች የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ የፈፀመው ተግባር ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት አመልካቾች ክርክር የተነሳበትን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት በአብላጫ ድምጽ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት መስከረም 23 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሁለተኛ አመልካች የቤቱ ባለሀብት የሆነችው ወ/ሮ ድንቄ መኮንን የሰጠችው ውክልናን በሚመለከት ከአንደኛ አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት ብር 4000/ አራት ሺህ ብር/ በመግዛት እስከ ብር 400,000 /አራት መቶ ሺህ ብር/ በላይ በማውጣት ገንብቻለሁ፡፡ ስለዚህ ወደ ነበሩበት ይመለሱ ቢባል የማይቻል ሆኖ እያለ ውሉ ፈራሽ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች ታህሣስ 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሁለተኛ አመልካች ቤቱን የቤቱ ባለሀብት ወኪል ከሆነው አንደኛ አመልካች ገዝቸአለሁ በማለት የሚከራከረው የህጉን ፎርም ሳያሟላና ሟች በሞት ከተለየችና የአንደኛ አመልካች የውክልና ስልጣን ቀሪ ከሆነ በኋላ ከቅን ልቦና ውጭ የፈፁሙት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የቤት ሽያጭ ውሉ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ሟች ከሞተች በኋላ ቀርቦ የተመዘገበና አንደኛ አመልካች ይህንን ተግባር ያከናወነው ወካይዋ መሞቷንና የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ መሆኑን እያወቀ በመሆኑ በአንደኛ አመልካችና በሁለተኛ አመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውሉ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ሰበር ችሎት አንደኛ አመልካች በክልሉ ፍትህ ቢሮ በመቅረብ የሽያጭ ውሉን ያስመዘገበው ወካይዋ ወ/ሮ ድንቄ መኮንን ከሞተችና የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ በመሆኑ የቤት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ ወይም ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አከራካሪው ቤት የሟች ወ/ሮ ድንቄ መኮንን ሀብት የነበረ መሆኑና ድንቄ መኮንን አንደኛ አመልካች ይህን ቤት እንዲያስተዳድር እንዲሸጥ እንዲለውጥ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሀምሌ 16 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠችው መሆኗንና ወ/ሮ ድንቄ መኮንን ሀምሌ 29 ቀን 1998 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለየች መሆኑ የሚያከራክሩ ፍሬ ጉዳዮች አይደሉም፡፡

ወካዩ የሞቱ እንደሆነ በሥፍራው አለመኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ለመስራት ችሎታ ያጣ እንደሆነ ወይም በንግድ መውደቅ ኪሣራ ደርሶበት እንደሆነ ለጉዳዩ ተቃራኒ የሚሆን ውል ካልተገኘ በቀር

የውክልና ሥልጣኑ ወድያውኑ የሚቀር መሆኑን የፍታብሔር ሥ/ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ አንደኛ አመልካች በተሰጠኝ ውክልና መሠረት ለሁለተኛ አመልካች ቤቱን የሸጥኩት ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ወካይዋ ከመሞቷ በፊት ነው በማለት የሚከራከርና ሁለተኛ አመልካችም ይህንን የመከራከሪያ ነጥብ የሚያቀርቡ ቢሆንም የቤት ሽያጭ ውሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበው ሟች ወ/ሮ ድንቁ መኮንን በሞት ከዚህ ዓለም ከተለየች በኃላና የአንደኛ አመልካች የውክልና ሥልጣን በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ቀሪ ከሆነ በኃላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የአንድን ንብረት ባለሃብትነት በውል ለሌላ ሰው የሚተላለፈው ባለሃብት ወይም ባለሃብቱ የንብረቱን ባለቤትነት በውል ለሌላ እንዲያስተላልፍ የፀና ልዩ የውክልና ስልጣን ባለው ሰው እንደሆነ የህገ መንግስቱ  አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 ንዑስ አንቀጽ 2፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አንደኛ አመልካች ሟች ድንቁ መኮንን በሰጠችኝ ልዩ የውክልና ሥልጣን መሠረት ቤቱን በብር 4000 (አራት ሺህ ብር) ለሁለተኛ አመልካች የሸጠ መሆኑን በማረጋገጥ በክልሉ ፍትህ ቢሮ የውክልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ያስመዘገበው በ2001 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ይህም የሚያሣየው ሁለተኛው አመልካች በፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በኩል በ2001 ዓ.ም የሟች ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ቤት ለመግዛት ያደረጉት ውል የቤቱን ባለሃብትነት ለማስተላለፍ የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ከአንደኛው አመልካች ጋር የተደረገ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ አመልካች ለሁለተኛው አመልካች የድንቁ መኮንንን ቤት ለመሸጥ ያደረገው ውል ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የዘረዘርናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አነስተኛው ድምጽ የአንደኛው አመልካች ሟች ከሞተች በኃላ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በኩል ውሉን ማስመዝገቡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚሸፈን ተግባር እንደሆነ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የሽያጭ ውሉ የተደረገው ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም ተደርጎ ውሉ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ በ2002 ዓ.ም የተመዘገበ መሆኑን ጠቅሰው የአንደኛው አመልካች አድራጎት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚሸፈን ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ አመልካች ሁለተኛ አመልካች የቤት ሽያጭ ውል የፈፀመበት እርግጡን ቀን  ተብሎ የሚያዘው እነርሱ ውሉ የተደረገበት ቀን ነው ብለው በውሉ ሰነድ ላይ የፃፉት ቀን ሣይሆን የሽያጭ ውሉን የክልሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ተቀብሎ የመዘገበበት ቀን እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2015(ሀ) በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ የአመልካቾች ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቅጽ 2 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ወካዩ ከሞተ በኃላ ተወካዩ የቤት ሽያጭ ውል እንዲያከናውን ወይም የቤት ሽያጭ ውሉን ለመፈፀም የውክልና ስራውን እንዲቀጥል ለማድረግ ታስቦ የተቀረፀ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካቾች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን በመጥቀስ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛ አመልካች ገዝቸዋለሁ የሚሉትን ቤት ባለሃብትነት ለማስተላለፍ መብት ወይም የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር ያደረጉት ውል ከጅምሩ ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው

ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ከቀረበው ፍሬ ጉዳይ በእጅጉ የተለየውንና ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 47800 ሰጥቶት የነበረውን የህግ ትርጉም በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የቤንሻጉል ጉምዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ የማይገባትን ብልጽግና አግኝታለች የሚል ከሆነ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በተጠሪ ላይ ክስ የማቅረብ መብቷን ይህ ውሣኔ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 74538

ሐምሌ 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት አሊያት ይማም ሙዘይን - ጠበቃ የሺጥላ አሰፋ ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** አቶ እምነቴ እንደሻው - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የአሁን አመልካች ወኪል ናቸው በተባሉት እና በአሁን ተጠሪ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል አመልካችን ሊያስገድድ የሚችልበት አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ ሆነው በአሁን አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን፤ ይዘቱም፣ የአሁን አመልካች በወኪሏ አማካኝነት በ1994 ዓ.ም በተደረገ ውል በአዋሳ ከተማ በቀድሞ ከፍተኛ 02 ቀበሌ 04 ክልል በካርታ የምስክር ወረቀት ቁጥር 5045 የሚታወቀውን እና በ3000 ካ.ሜትር ያረፈውን ቤት በብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ ብር) ሸጠውልኛል፡፡ በዚህም የሽያጭ ውል መሰረት ብር 95,000.00 (ዘጠና አምስት ሺህ ብር) ውሉ በተደረገበት ዕለት ወስደዋል፡፡ ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) ደግሞ የካቲት 30 ቀን 1994 ወስደዋል፡፡ ስለዚህ ቀሪውን 185,000,00 ተቀብለው እንደውሉ እንዲፈጽሙ ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካችም በተከሳሽነት በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ውል ፈጸመ ለተባለው አባቴ ውል ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ የሰጠሁት የውክልና ሥልጣን የለም ስለዚህ በ1994 ዓ.ም. የሰጠሁት ውክልና ስለሌለ የሸጥኩትም ሆነ የተቀበልኩት ገንዘብ የለም፡፡ አይመለከተኝም የሽያጭ ውል ነው የተባለው በቅንብር እንደተመዘገበ ለማስመሰል የተደረገ እንጂ በአዋዋይ ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ ተሸጠ የተባለው ቤት አዋሳ ከተማ ስለሚገኝ ሊመዘገብ የሚችለው በዚሁ ከተማ አስተዳደር ሥር በሚገኘው መዝጋቢ አካል እንጂ በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ሊሆን አይችልም ይህ ተመዘገበ የተባለውም የሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ በቁጥር 1304/2003 በተፃፈ ደብዳቤ ይህ ውል በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ ውል ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን ገልፆ ማረጋገጫ ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም እኔ ለአባቴ የውክልና ሥልጣን ከሰጠሁበት ከጥር 14 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት የሽያጭ ውሉ ተደርጓል ስለተባለ እኔ ባልሰጠሁት የውክልና ሥልጣን ተደረገ በተባለው ረቂቅ ውል እና በሐሰት ተመዝግቧል የተባለው ውል እኔን የማይመለከተኝ ስለሆነ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንድሰናበት ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ በፍ/መ/ቁ 10287 ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተወካይና ከሳሽ በ1994 ዓ.ም የሽያጭ ውል በተዋዋሉበት ጊዜ ሻጩ ህጋዊ ውክልና ያልነበረው መሆኑ ቢታወቅም፣ ተወካዩ በ1994 ዓ.ም የገቡት ውል መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ/ም መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ውሉ በተመዘገበበት ጊዜ ምስክሮች ውል አዋዋይ ፊት ቀርበው የመሰከሩ ባለመሆኑ በውሉ አመዘጋገብ ጊዜ የተፈጠረው ጉድለት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ውል ከተመዘገበበት ከ1998 ዓ.ም በፊት ጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም ተከሳሽ ለወኪላቸው ውክልና የሰጡ ስለሆነና ተወካዩ ያለህጋዊ ውክልና በ1994 ዓ.ም የገቡት ውል የውክልና ሥልጣን ከተገኘ በኋላ በ1998 ዓ.ም በመመዝገቡ የሽያጭ ውሉን ረቂቅነት ያስቀረዋል፡፡ ስለዚህ በ1994 ዓ.ም. የተከሳሽ ወኪል እና ከሳሽ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ተወካዩ ህጋዊ ውክልና እስካገኘበት ጊዜ ድረስ ረቂቅ ነው የሚባል ቢሆንም ረቂቅ መሆኑ በሲዳማ ዞን መምሪያ በ1998 ዓ.ም ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ ህጋዊነቱን ስላገኘ ተከሳሽን ያስገድዳታል፡፡ ስለሆነም እንደውሉ ልትፈጽም ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ አቅራቢነት ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በ1998 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የምዝገባ ስራ የአመዘጋገቡን ሥርዓት ካላሟላ ቅሬታ ያለው ወገን በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 7 መሰረት ሥርዓቱን ጠብቆ መፍትሄ ማግኘት ከሚቻል በቀር የማስረጃውን ተቀባይነት ከወዲሁ ውድቅ ለማድረግ አይቻልም፡፡ በዚህም አንቀጽ መሰረት አመልካች አቤቱታ የማቅረብ መብቷ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ከዚህ በፊት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 20890 በሆነው በአመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ መካከል በነበረው ጉዳይ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን ጠቅሶ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው እና በ1994 ተደረገ የተባለው ውል በአዋዋይ ፊት የተደረገ ሆኖ ተገኝቷል የሚለውን መሰረት አድርጎ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናቱ የተነሣ የአሁን አመልካች በዚህ የፌዴራል ጉዳይ በሆነው የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚሉበትን የመከራከሪያ ነጥቦች በመዘርዘር ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም ቀርቦ ለሰበር አቤቱታው ዝርዝር መልስ ሰጥቶበታል ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስለጉዳዩ ያቀረቡትን የፅሁፍ ክርክር እንዳየነው ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው በሥር ፍ/ቤቶች ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከርና በማብራራት የቀረበ ከመሆኑ በቀር የይዘት ለውጥ ያለው አይደለም፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አነሳስና አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ለነገሩ መነሻ የሆነው የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው የአመልካች ወኪል የተባሉት ሻጭ ከንብረቱ ባለቤት ከአሁን አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ሳይኖራቸው በ1994 ዓ.ም ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረጉት ስለመሆኑና ይህም ውል በአዋዋይ ፊት ያልተደረገ ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ በዚህ አኳኋን የተደረገው ውል እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ የረቂቅነት ደረጃ እንደነበረውም የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዳኝነት ተረጋግጧል፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካች ጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም. ሻጭ ለነበረው ወገን የውክልና ሥልጣን የሰጡ የመሆኑን እና በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ በ1998

ዓ.ም. ተመዝግቦ ተገኝቷል የሚሉትን አውነታዎች (facts) በመያዝና ከዚሁም በመንደርደር በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል ረቂቅ መሆኑ ቢታወቅም በ1998 ዓ.ም በውል አዋዋይ ፊት የተመዘገበ ሆኖ ስለተገኘ ረቂቅነቱ ቀርቷል ህጋዊ ደረጃውን አግኝቷል፡፡ እንዲሁም ሻጭ ቤቱን በሸጠበት ጊዜ ከንብረቱ ባለቤት ከአሁን አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ሥልጣን የነበረው ባይሆንም ውሉ በአዋዋይ ፊት ቀርቦ ከመመዝገቡ በፊት ሻጭ በጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም. የውክልና ሥልጣን አግኝቷል፡፡ ስለሆነም በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል በወኪሏ በአሁን አመልካች እንደተደረገ ይቆጠራል የሚለውን አተረጓጎም በመከተል ውሉ የአሁን አመልካችን የማስገደድ ኃይል አለው የሚል ዳኝነት ሰጥተዋል፡፡

ይሁን እንጂ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው ፍርድ እንደተገለፀው ይህ ክርክር ያስነሳው የቤት ሽያጭ ውል በ1998 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ እንደተመዘገበ ገልፆ የአሁን ተጠሪ ቢከራከርም በሰነዱ ላይ በእማኝነት/በምስክርነት የተጠቀሱት ምስክሮች በአዋዋይ ፊት ቀርበው ያስመሰከሩ መሆኑን በፍሬ ነገር ረገድ አረጋግጧል፡፡ ከዚህም በቀር እራሱ ውሉን በእራሱ ፊት መደረጉን አረጋገጠ የተባለው የሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ በቁጥር ሲ/ዞ/ፍ/መ/1304/2003 በ14/10/2003 እና በቁጥር ሲ/ዞ/ፍ/መ/1403-03 በ06/11/03 ዓ.ም በተፃፈ ማረጋገጫ ውሉ የተደረገው አዲስ አበባ ወሎ ሰፈር፤ የምስክሮችም አድራሻ አዲስ አበባ መሆኑንና ምስክሮችም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ፊት ቀርበው የውሉን መደረግ አለማረጋገጣቸውን አረጋግጧል፡፡ በተለይም ውል አዋዋይ ፊት መሰከሩ ከተባሉት ምስክሮች መካከል ቅድስት በቀለ የተባለችውን አስቀርቦ እንዳረጋገጠው ውሉ አዲስ አበባ ወሎ ሰፈር ተደርጎ ምስክሮች በአዋዋይ ፊት ሳይቀርቡ እንዴት ተመዘገበ ሊባል እንደቻለ የአሁን ተጠሪ ቀርቦ እንዲያስረዳ ፍትህ መምሪያው ሲጠይቀው በተጠሪ ድርጅት ደብዳቤ በተረጋገጠ ተጠሪው በአዋሳ ከተማ ሊገኝ አይችልም በሚል ምክንያት ቀርቦ ሊያስረዳ ያልቻለ መሆኑንና ውሉ ተመዘገበ የተባሉትን ሂደት ሁሉ ካጣራ በኋላ ይህ 1994 ዓ.ም. ተደረገ ተብሎ በ1998 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ተመዘገበ የተባለው ውል በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው የውል አደራረግ ሂደትን የማረጋገጥ የመመዝገብ ሥልጣን ባለው አካል እና ክርክር ያስነሳውን ውል እንደ ሥርዓቱ በእራሱ ያልተመዘገበ መሆኑን እያረጋገጠ፣ ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ፍሬ ነገር በማስረጃ መረጋገጡን እየተረዱ የሥር የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህ የውል አመዘጋገብ ጉድለት እንደተጠበቀ ሆኖ.... በሚል አገላለጽ በዝምታ ማለፉ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 20890 በሆነው በአመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ መካከል ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ከዚህ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የማይመሳሰል እና ተመሳሳይ ትርጉም ሊከተል የማይችል መሆኑ እየታወቀ የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ያለቦታው በመጥቀስ ክርክር ያስነሳውና በ1994 ዓ.ም አ/አበባ ከተማ ወሎ ሰፈር ተደረገ የተባለው ውል በ1998 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ ተመዝግቧል ከሚል ውሳኔ መድረሳቸው ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው ትዕዛዞች፣ ብይኖች፣ ፍርዶች እና ማናቸውም ዳኝነት በተከራካሪ ወገኖች የተነሱትን ክርክሮች ከተከራካሪ ወገኖች ክርክር አንፃር በጭብጥነት በተያዙት ጉዳዮች በግራ ቀኙ የተሰማውን ማስረጃ መሰረት በማድረግና በዚህም በማስረጃ የተረጋገጠውን ጉዳይ ለመቀበልም ሆነ ውድቅ ለማድረግ የቻለበትን ምክንያትና አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት በማድረግ ሊሆን ይገባል በሚል

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182 እና 183 ስለፍርድ አፃፃፍ የተመለከተውን ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል ረቂቅ ሆኖ እስከ 1998 ዓ.ም የቆየ ቢሆንም በ1998 ዓ.ም ውል አዋዋይ ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ሆኖ ስለተገኘ ህጋዊነቱን አግኝቷል የሚለው የፍርድ መነሻ ሀሳብ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ሻጭ የተባለው ወገን ንብረቱን በ1994 ዓ.ም ሸጧል ከተባለ በኋላ የአሁን አመልካች ጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም ንብረቱን ሸጠ ለተባለው ወገን የውክልና ሥልጣን የመስጠታቸው ተግባር በእራሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 በተደነገገው መሰረት ህጉ የሚጠይቀውን ማሟያ አሟልቶ ባለመገኘቱ ምክንያት በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል የለም፤ ውሉ ረቂቅ ነው የተባለበትን ማናቸውም ክንውን ለመቀበል ህግ አያስገድዳቸውም፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን አመልካች በ1995 ዓ.ም. የሰጡት የውክልና ሥልጣን አገልግሎት የውክልና ሥልጣን ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሚከናወኑ ህጋዊ ተግባራት ተብሎ የተሰጠ መሆኑን ከሚያመለክት በቀር የውክልና ሥልጣን ከመስጠቱ በፊት ወኪሉ የፈፀመውንም ማናቸውም ተግባር ለመቀበል እንደፈቀዱ፣ እንደፈለጉ ያስቆጥራቸዋል ለማለት የሚያበቃ የህግ መሰረት የለውም፡፡

ምናልባትም ይህ ዘግይቶ የውክልና ሥልጣን የመስጠት የአመልካች ተግባር ቀደም ሲል ወኪል የተባለው ሰው ፈፀመ የተባለውን የሽያጭ ተግባር ለማፅደቅ መፈለጋቸውን ያሳያል በማለት መተርጎም እንዳይቻል ለዚሁ አግባብነት ባለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2190 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉት የውክልና ሥልጣን ኖሮ ተወካዩ ከውክልና ሥልጣኑ በላይ አሳልፎ ለፈፀመው ተግባር እና የውክልና ሥልጣን ዘመኑ ካበቃ በኋላ ወኪል የነበረው ሰው ለፈፀማቸው ተግባሮች እንጂ አሁን እንደተያዘው ላለው ፈፅሞ የውክልና ሥልጣን ባልተሰጠበት ጉዳይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ክርክር ያስነሳውና የቤት ሽያጭ የተባለው ውል የአሁን አመልካችን ሊያስገድድ የሚችል የህግ መሰረት በሌለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች ውሉ አመልካችን ይመለከታል፤ እንደውሉ እንዲፈፅሙ ይገደዳሉ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፤

## ው ሳ ኔ

1. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መ/ቁ 54799 በ19/12/2003 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ሀጂ ይማም ሙዘይን በውክልና ሥልጣን ከተጠሪ ከአቶ እምነቱ እንደሻው ጋር በ1994 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ወካይ ናቸው በሚል ምክንያት የአሁን አመልካችን ወ/ሪት አሊያት ይማምን ሊያስገድድ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ በየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 67376

ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቶች፡- 1- ወ/ሮ ንግስት ኪዳኔ  አልቀረቡም

2- አቶ ዐቁባይ ሚካኤል ገብረየሱስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- አቶ በለጠ ወልደሰማያት  ቀረቡ

2- አቶ ገብረ እግዚአብሔር ሐዲስ ከጠበቃቸዉ ከአቶ ሐጐስ አብርሃ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር አመልካቾች ከሣሽነት የተጀመረው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ ከሣሾች ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 በአሁኑ አጠራር በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 08/09 የሚገኘውን ቁጥሩ 486 የሆነውን የግል ቤታችንን ከሣሾች በ1992 ዓ.ም. ከሀገር ስንወጣ ለ1ኛ ተከሣሽ ውክልና በመስጠት የሄድን ቢሆንም 1ኛ ተከሣሽ ቤቱን የማስተዳደር እንጂ የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ሳይሰጣቸው ለ2ኛ ተከሣሽ የሸጡ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክቡን ፣ ያለአግባብ የበለጸጉበትን በወር ብር 3000 ስሌት ብር 72,000 ከነወለዱ እንዲከፍሉ ፣ ወደፊትም የሚኖረውን ውዝፍ ገንዘብ ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ፣ ቤቱን መመለስ የማይቻል ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተከሣሽ ብር 1,250,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልን ብለዋል፡፡

ተከሣሾችም ክሱ በፍ/ህ/ቁ 1810 መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ በፍሬ ነገሩ ላይ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሣሾችም ለይርጋ መቃወሚያው በሰጡት መልስ በፍ/ህ/ቁ 1810 የተጠቀሰው ይርጋ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው በፍ/ህ/ቁ 1710/2/ መሠረት በተንኮል፣ በማሳሳት፣ በሀይል ወይም በእድሜ መግፋት እና ከመጃጀት ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ ውሎች እንዲፈርሱ በሚል ለሚቀርብ ክርክር ሲሆን የከሣሾች ክስ ግን ከዚህ የተለየ በመሆኑ ለዚህ ክርክር አግባብነት የለውም፡፡ በእኛ እምነት ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ህ/ቁ 1845 ይርጋ ሲሆን ሽያጩን ካወቅነው ደግሞ ሁለት ዓመት ያልሞላው ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በሚል ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የመረመረው የፌ/ከ/ፍርድ ቤትም በሰጠው ብይን 1ኛ ከሣሽ ለ1ኛ ተከሣሽ ከሰጡት ውክልና ስልጣን ተከሣሹ አልፎ የከሣሽ ንብረት የሆነውን መኖሪያ ቤት የሸጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ስለውሎች በጠቅላላው ክፍል የተደነገጉት የይርጋ ድንጋጌዎች አግባብነት የላቸውም፡፡ በወካይና በተወካይ መካከል ለሚፈጠር አለመግባባት ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ክስ ለማቅረብ ቢፈለግ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በፍ/ህ/ቁ 2187 የተደነገገው ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሠረትም ክሱ

በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል። ሆኖም በተያዘው ጉዳይ ቤቱ ከተሸጠ ሁለት ዓመት ካለፈ በኂላ በውክልና ምክንያት በተሰራ ሥራ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው ነው ብሏል።

ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኂላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይንና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካቾች የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብም፡- ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ ከአገር ውጪ ስንኖር የነበርን ሲሆን ቤቱ መሸጡን ያወቅነው 2ኛ አመልካች ከወጪ ሀገር ከተመለስኩ ከሰኔ 07/2002 ዓ.ም. ጀምሮ ሆኖ እያለና ይህን ጊዜ ተጠሪዎች ሳያስተባብሉ አግባብነት የሌለውን በፍ/ህ/ቁ 1810 የተደነገገውን የሁለት ዓመት ይርጋ በመጥቀስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል የክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ተጠሪዎች ያላነሱትን በፍ/ህ/ቁ 2187 የተደነገገውን የሁለት ዓመት ይርጋ በመጥቀስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል መዝገቡን በብይን የዘጋውና የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያጸናው ያለአግባብ ነው የሚል ነው።

1ኛው ተጠሪ በሰጡት መልስ በጊዜው በነበረው አጠራር የክልል 14 መስተዳድር በ18/08/1992 ዓ.ም ከአገር የወጡ ኤርትራዊያን ንብረት በሰጡት ውክልና መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተወካዮቹ መሸጥ እንደሚችሉ ለውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ባስተላለፈው የመንግስት መመሪያ መሠረት ከራሴ ፈቃድ ውጪ ሽያጩን የፈጸምኩ ስለሆነና ሽያጩም ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ 11 ዓመታት ስላለፉት ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ የወሰኑት ተገቢ ነው በከፍተኛው ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያ ሳቀርብ ጠቅሼ ያቀረብኩት በፍ/ህ/ቁ 1810 የተደነገገውን የሁለት ዓመት ይርጋ ቢሆንም በ1ኛ አመልካችና በእኔ መካከል የነበረውን የወካይና ተወካይ ግንኙነት መነሻ በማድረግ አመልካቾች ቤቱን የሸጠው ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችለው ውክልና ሳይሰጠው ነው በሚል ላቀረቡት ክርክር ፍርድ ቤቶቹ አግባብነት ያለው ይርጋ በፍ/ህ/ቁ 2187 የተጠቀሰው የሁለት ዓመት ይርጋ ነው በሚል ክሱ በዚሁ በሁለት ዓመት ጊዜ ወስጥ ያልቀረበ ነው ሲሉ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው፣ አመልካቾች ሽያጩን ያወቅነው ሰኔ 07 ቀን 2002 ነው ቢሉም ይህን አባባላቸውን በማስረጃ አስደግፈው ለፍርድ ቤቶች ስላላቀረቡ ተቀባይነት የለውም ሲሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን/ ውሣኔ እንዲጸና ጠይቀዋል።

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የኤርትራዊያን ቤት ለኢትየጵያዊያን እንዲሸጥ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በመወሰኑ የኤርትራ መንግስት ሚዲያዎች ፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት ፣ የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን እና ሌሎች ወገኖች በግልጽ ሲሚገቱበት የቆየ የአደባባይ ሚስጥር ስለሆነና አመልካቾችም ይህን የአካባቢ ሁኔታ በግልጽ የሚያውቁት ጉዳይ ነው። በመሆኑም የሚያከራክረውን ቤት ሚያዚያ 1992 ዓ.ም ገዝቼ ስመ ሀብቱም ተዛውሮልኝ ይገኘ የምገኝ ሲሆን ይህንኑ ቤት ለመረከብ አመልካቾች ያቀረቡት ክስም በሁለት ዓመት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ ክሱ በፍ/ህ/ቁ 2187 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ሲሉ ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ብይን/ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው፣ ይህ ቢታለፍ ቤቱ ከተሸጠበት ጊዜ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ያለው ጊዜ ሲቆጠር 10 ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በፍ/ህ/ቁ 1845 መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ ተከራክረዋል። በዚህ ችሎት ደረጃም የግራ ቀኙ ወገኖች በቃል ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ ፍርድ ቤቶቹ ክሱን ወድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው የሚያከራክረው ቤት የተመዘገበው በ1ኛ የሰበር አመልካች ስም መሆኑንና 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስተዳድሩ ውክልና ሰጥተው ከ2ኛ አመልካቾች ጋር ወደ ኤርትራ ሀገር በ1990 ዓ.ም. ሄደው እያሉ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 05 ቀን 1992 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ቤቱን መሸጣቸውን ነው፡፡ አመልካቾችም በክሳቸው ሽያጩን በመቃወም እንዲፈርስ ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም ክስ ያቀረቡት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የማስተዳደር እንጂ የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ሳይሰጣቸው ለ2ኛ ተከሣሽ ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ አመልካቾች ቤቱ የተሸጠ መሆኑን ያወቁት 2ኛ አመልካች ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ በሰኔ 07/2002 ዓ.ም መሆኑን በክሳቸው ከመጥቀሳቸውም በላይ በቃል ክርክር ጊዜም በዚሁ በተጠቀሰው ቀን ሽያጩን እንዳወቁ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም ክሱን ለመቃወም በዋናነት የጠቀሱት የይርጋ ህግ የፍ/ህ/ቁ 1810 ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ ግን በወካይና በተወካይ መካከል ለሚፈጠር አለመግባባት ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜው በፍ/ህ/ቁ 2187 የተደነገገው ነው በሚል ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል ማለታቸውን ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የግራ ቀኙን ወገኖችን ለሚያከራክረው ጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ህግ ድንጋጌ የትኛው እንደሆነ መለየት ተገቢነት ያለው ነው፡፡ እንደራሴው በፈጸመው ውል ምክንያት የሿሚውና የእንደራሴው ጥቅሞች የሚቃወሙ የሆኑ እንደሆነ ይህን ውል የፈረመው 3ኛ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያውቀው የሚገባ የሆነ እንደሆነ በሿሚው ጥያቄ መሠረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ህ/ቁ 2187/1/ የተመለከተ ሲሆን በሿሚውም ውሉን ለማፍረስ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው የዚሁ አካባቢ ሁኔታ ስለመኖሩ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ መሆን እንዳለበት የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር 2 ይደነግጋል፡፡ ውክልና ተወካዩ ለወካዩ እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎችን በወካዩ ስም ለማድረግ የሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ 2198 የሚስገነዘብ ሲሆን ይህም ስምምነት ወካዩ የውክልና ስራ በሚፈጽምበት ጊዜ የወካዩን ህጋዊ ሁኔታዎች የመለወጥ ስልጣን የሚሰጠው በመሆኑ ተወካዩ የውክልናውን ስልጣን ተጠቅሞ ሲሰራ ለወካዩ ጥቅም ፍፁም ታማኝና በስራው ሁሉ የወካዩን ጥቅም ብቻ የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜም ይህንን ለወካዩ ፍፁም የሆነ ታማኝነትና ሙሉ ለሙሉ ለወካዩ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚከለክለው ፍላጎት ወይም ታማኝነቱን የሚከፋፍል ሁኔታ የሚያስከትል የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ተወካዩ ለስራው አፈጻጸም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በመሆኑም እንደራሴው የውክልና ሥልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን በወካይና በተወካይ መካከል የጥቅም ግጭት ያለ ስለመሆኑ አመልካቾች በክሳቸው ከላመግለጻቸውም ሌላ በቃል ክርክር ወቅትም በ1ኛ ተጠሪና በሿሚዋ መካከል የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ ያሉት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶቹ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በፈጸመው ውል ምክንያት የሻሚውና የ1ኛ ተጠሪ የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ አመላካች ነገር ባልተገኘበት ሁኔታ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለውን የፍ/ህ/ቁ 2187/2/ የተመለከተውን ይርጋ ለብይኑ / ለውሣኔ መሠረት ያደረጉት ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ተጠሪዎች በዋናነት ወዳነሱት የፍ/ህ/ቁ 1810 ይርጋ ስንመለስ አንድ ውል በሚመሰረትበት ጊዜ የችሎታ ወይም የፈቃድ ጉድለት ያለበት ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ችሎታ አልነበረኝም ወይም ፈቃዴን በአግባቡ አልሰጠሁም በሚለው ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ብቻ ውሉ ሊፈርስ

እንደሚችል፣ እንደዚሁም ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ለህግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና የውሉ አጻጻፍ ሥርዓትም ባልተጠበቀበት ወቅት ከተዋዋይ ወገኖች መካከል ወይም በሙሉ ጥቅም አለኝ በሚል 3ኛ ወገን አማካይነት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ቀርቦ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ሕ/ቁ 1808/1/ ተደንግጓል፡፡ የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረቢያ ጊዜን በተመለከተ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በፍ/ህ/ቁ 1810 ተጠቅሷል፡፡ ይህን የይርጋ ድንጋጌ በተመለከተ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 59139 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተፈጻሚነቱ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን ይህም የሚመለከተው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን ችሎታ ወይንም ፈቃድ ጉድለት ጋር ተያያዘ መሆኑን በፍርዱ ላይ አስፍሯል፡፡ በዚሁ መሠረትም ውሉ በችሎታ ማጣት ወይንም በፈቃድ ጉድለት እንዲፈርስ የሚጠይቅ ወገንም በሁለት ዓመት ውስጥ ክሱን ካላቀረበ በዚሁ በተጠቀሰው የፍ/ህ/ቁ 1810 ይርጋ መሠረት የሚታገድ ይሆናል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሙሉ እንዲጠብቁ ፣ እንዲቆጣጠሩ ፣ ክፍያዎችን ተሳስበው እንዲከፍሉ በአጠቃላይ ንብረቶቹን በተመለከተ በመንግስታዊ መ/ቤቶችና በህዝባዊ ድርጅቶች እየቀረቡ ጉዳዮችን እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ እንጂ ንብረቱን እንዲሸጡ ሥልጣን ሳይሰጣቸው በህገወጥ መንገድ ለ2ኛ ተጠሪ ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት የጠየቁት የችሎታ ወይም የፈቃድ ጉድለትን መሠረት አድርገው ሳይሆን የውሉን ሕገ ወጥነት በመጥቀስ ስለሆነ ተጠሪዎች ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት በፍ/ህ/ቁ 1810 የተደነገገው የሁለት ዓመት ይርጋ አግባብነት የለውም፡፡

ለዚህ ጉዳይ የፍ/ሕ/ቁ 1810 እና 2187/2/ ይርጋ አግባብነት የላቸውም ከተባለ ጉዳዩን ስለውሎች በጠቅላላው በተደነገገው ክፍል በሚገኘው በፍ/ህ/ቁ 1845 መሠረት መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በፍ/ህ/ቁ 1845 ድንጋጌ መሠረት ህግ በሌላ አኳን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ከላመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ መብት ያለው ወገን መብቱን በ10 ዓመት ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ ቀሪ እንደሚሆን በግልጽ የተጠቀሰ ሲሆን አመልካቾችም የሽያጭ ውሉ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስተላለፍ በፍ/ህ/ቁ 2205 መሠረት ልዩ ውክልና ሳይሰጣቸው የፈጸሙት ውል በመሆኑ ውሉ ህገ ወጥ ነወ እስከሚሉ ድረስ ይህንኑ ህገወጥ ነው የሚሉትን ውል እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ የሚችሉት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለሚሆን የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች የይርጋ ክርክር ለመወሰን አግባብነት ያለው ይሄው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ ይርጋው የሚቆጥርበትን መነሻ ጊዜን በተመለከተም አመልካቾች የቤቱን ሽያጭ ያወቅነው ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ.ም ነው በሚል የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ቤቱ የተሸጠው በሚያዚያ ወር 1992 ዓ.ም በመሆኑ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ምንም እኳን አመልካቾች ከሀገር በ1990 ዓ.ም የወጡ ቢሆንም ከነበሩበት ከኤርትራ መንግስት ሚዲያዎች ፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት ፣ የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን እና ሌሎች ወገኖች በግልጽ ስለንብረታቸው የሚያውቁት ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ የተጠቀሱት ምንጮች 1ኛ ተጠሪ ቤታቸውን የሸጡባቸው ስለመሆኑ ያሣውቃሉ ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርሱ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ የሰበር አመልካች እስካሁን ድረስ በውጪ ሀገር የሚኖሩ ስለመሆናቸው ክርክሩ የሚያመለክት ሲሆን 2ኛ ተጠሪም ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር

ነው፡፡ በመሆኑም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም አመልካቾች ውሉ እንዲፈርስ ክስ ያቀረቡት በፍ/ህ/ቁ 1845 የተደነገገው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶቹ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን በፍ/ህ/ቁ 2187/2/ የተደነገገውን የይርጋ ጊዜ በመጥቀስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በሁለት ዓመት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ የሰጡት ብይን /ውሣኔ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 59139 በፍ/ህ/ቁ 1810 እና 1845 የተደነገጉትን የይርጋ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት በተመለከተ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ብይኑ/ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 95609 በቀን 26/02/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይንና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 62492 በቀን 16/07/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽረናል፡፡
2. ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በፍ/ህ/ቁ 1845 የተደነገገ ሲሆን በዚሁ የይርጋ ድንጋጌ መሠረት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የክስ ማቅረቢያ 10 ዓመት ከማለፍ በፊት የቀረበ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳይ ላይ የግራ ቀኙን ወገን በማከራከርና ማስረጃዎችን ሰምቶ በመመዘን የበኩሉን ፍርድ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

# አዕምሯዊ ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 70500

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ኢንጅነር አድማሱ ገብሬ (ገብሬ አድማሱ) ጠበቃ ገንዘቡ ገ/አምላክ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ተከሣሽ የብሩክ ፊልምስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ባለቤት ከሆኑት የግል ተበዳይ አቶ ብሩክ መክብብ ጋር መንተዮቹ የሚል ርዕስ ያለው የአማርኛ ፊልም ለመሥራት ተዋውለው ሳለ የግል ተበዳይ ሳያውቁ በግል ተበዳዩ (ፕሮዲዩሰሩ) የተሠራውን ፊልም ከተጠናቀቀ በኋላ ከግል ተበዳይ ሠራተኞች ጋር በመመሳጠር ከተቀበለ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣቱ እና ርዕሱን በመቀየር ‹‹ለአባቷ›› የሚል ርዕስ በመስጠት የፊልሙ ባለቤት ሳይሆን የፊልሙ ባለቤት በመምሰል ለህዝብ እይታ በማቅረብ የቅጅና ተዘማጅ መብቶችን ለመጠበቅ የወጣውን አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 7(1)(ሀ) እና 36(1) ሥር የግል ተበዳይን የኢኮኖሚ መብት በመጣስ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በመካድ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በዚሁ በተከሰሰበት ወንጀል ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አመልካች በ2 ዓመት ከ6 ወራት እሥራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ካከራከረ በኋላ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአሁኑ አመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል የውል ግንኙነት ያለ ስለመሆኑ፣ በዚሁ የውል ግንኙነት መሠረት የግል ተበዳይ በአመልካች የሚቀርብለትን ድርሰት ወደ ፊልም ለመቀየር የተስማሙ ስለመሆኑ፣ በዚህ ስምምነት መሠረት ለመልካች ለሥራው ብር 800,000

ሊከፍልና የግል ተበዳይ ደግሞ ፊልሙን በማጠናቀቅ ለአመልካች የሚያስረክብና አመልካችም የፊልሙ ባለቤት እንደሚሆን የተሰማሙ ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በግራ ቀኙ መካከል በዚሁ የውል ግንኙነት መሠረት ያደረገ የፍትሐብሔር ክርክር እስከዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በመዝ.ቁ. 69247 ላይ እልባት ያገኘ ሲሆን አመልካች የፊልሙ ባለቤት ነው በማለት የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሣኔ እና በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፀደቀው የውሣኔ ክፍል በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎትም ያልተነካ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ የፍትሐብሔር ጉዳይ አከራካሪ ከሆነው ፊልም ግራ ቀኙ ያላቸው መብትና ግዴታ ምን እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ከሥራውም የሚገኘውን ትርፍ የሚከፋፈሉበትን አግባብ በተመለከተ ውሣኔ የተሰጠበት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን የወንጀል ኃላፊነት ለያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራት ስለመፈፀማቸው መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) መሠረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች የተከሰሰበት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ.410/1996 አንቀጽ 7(1)(ሀ) መሠረት ለሥራው ባለቤት የተሰጠን ተግባር ባለቤት ሣይሆን ባለቤት በመምሰል ፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች የፊልሙ ባለቤት ስለመሆኑ የግራ ቀኙ የተሰማሙበትን ውል መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሣኔ አልተሻረም፡፡ አመልካች የፊልሙ ባለቤት በተባለበት ሁኔታ ደግሞ የዚህ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ተጥሷል ማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩልም ባለቤት የሆነ ሰው ፊልሙን በእጁ አድርጎ መገኘቱ ከዚሁ ባለቤት ነኝ ከሚል ሃሣብ የተነሣ ከመሆኑ ባሻገር የወንጀል ተግባር ወይም የግል ተበዳይን የኢኮኖሚያዊ መብት በመጣስ ሃሣብ የፈጸመ ስለመሆኑ የወንጀል ሞራላዊ ፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ የተደነገጉት የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 57 እስከ 59 ደረስ ያሉት ድንጋጌዎች አያመለክቱም፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር የሞራላዊም ሆነ የህግ ፍሬ ነገሮች ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ባልተሟላበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በአመልካችና በግል ተበዳይ መካከል ያለው ግንኙነት የውል አፈፃፀምን የሚመለከት የፍትሐብሔራዊ ባህሪይ ያለው በመሆኑ አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር ሕጋዊ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 59998 ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.74529 በቀን 19-12-2002 ዓ.ም እና በቀን 21-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 195(2(ለ(1)) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር ሕጋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ከክሱ በነፃ እንዲሠናበት ብለናል፡፡

3. አመልካች በሌላ የወንጀል ጉዳይ የማይፈለግ ከሆነ ከማረሚያ ቤት እንዲለቀቅ ለሚመለከተው ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ. 68369

ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- ሳሙኤል ሃይሉ - ቀረቡ

2- ሆራይዘን ማተሚያ ቤት ኃ/የተ/የግል ማህበር -

ጠበቃ እንዳልካቸው ይላቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ስምረት አያሌው /ዘጠኝ ሰዎች/

1ኛ. ወ/ሮ ስምረት አያሌው 6ኛ. ቤተልሄም አያሌው

2ኛ. ወ/ሮ ፅዮን አያሌው 7ኛ. አዲስ አያሌው

3ኛ. ጳውሎስ አያሌው 8ኛ. ማህሌት አያሌው

4ኛ. የማነ አያሌው 9ኛ. ሙሉጌታ አያሌው

5ኛ. ፍሬሕይወት አያሌው - የሁሉም ጠበቃ ተስፋዬ ቀለመወርቅ -ቀረቡ

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 70380 ከሆነው ጋር አጣምረን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቅጅ መብት ሕግ ጥበቃ የሚደረገውን መብት ፣ የመብቱን ተጠቃሚዎችንና መብቱ ተጥሶ ሲገኝ በሕጉ ስላለው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ ተከሣሾች የአሁኑ አመልካቾች ነበሩ፡፡ የተጠሪዎች የክስ ይዘት ወላጅ አባታቸው አለቃ አያሌው ታምሩ በሕይወት ዘመናቸው ብዛት ያላቸው ሐይማኖት ነክ የሆኑ የፈጠራ ስራዎችን መስራታቸውን፣ የተለያዩ ፅሑፎችን ማዘጋጀታቸውን፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይም በመጣጥፍና በቃለመጠይቅ ዙሪያ ስብከቶችን ማዘጋጀታቸውንና በሕይወት ዘመናቸው የእነኚህ ስራዎች የፈጠራ ባለቤት የነበሩና ከሕልፈተ ሕይወታቸው በኂላም መብቶቹ ለወራሾች መተላለፋቸውን ፣ የአሁኑ 1ኛ አመልካች የባለመብቶችን ፈቃድ ሳያገኝ የሚቹን የፈጠራ ስራ የሆኑትን ፅሑፎች በጋዜጣ እና በመፅሄት ላይ የወጡ ቃለመጠይቆችን ፣ መጣጥፎችን ፣ የሟች የመንፈቅ መታሰቢያ ፖስተር ላይ የወሰዱትን የመፅሐፋን የሽፋን ሥእልና የሀዘን መግለጫ ግጥሞችን ጭምር በማሰባሰብ በ2ኛ ተጠሪ ማተሚያ ቤት አማካኝነት "ትምህርተ ሃይማኖት" በሚል ርዕስ ከሕግ ውጪ ማሳተሙን ገልፀው በአዋጅ ቁጥር 410/1996 መሠረት ህትመቱ እንዲቆም ፣ የታተሙት መፍሐፎችን

እንዲወገዱ የሞራል ካሣ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/፣ ሶስት ሺህ መጽሐፎች በገበያ በመሸጣቸው ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/፣ ተጠሪዎች ራሳቸው መጽሐፋን አሳትመው ቢሸጡ ኑሮ ይገኝ የነበረውን ገቢ ብር 250,000.00/ሁለት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቧቸው መከራከሪያ ነጥቦችም ሟች አለቃ አያሌው ታምሩ የስራው አመንጪ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያለመቅረቡን፣ የፅሑፍ ስራው የአለቃ አያሌው የግል ስራ ሳይሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ወቅታዊ ሐይማኖት ጥያቄዎችን አስመልክቶ ያላቸውን የእምነት አቋም በተመለከተ የጻፏቸው መሆናቸውን ስራውን ሲያቀርቡ ስራውን ለማሰራጨት መብቱ የእሳቸው ብቻ መሆኑን የሚያሳይ  ነገር ያለመኖሩን ፣ ጉዳዩ በሽምግልና እየታየ ባለበት ሁኔታ ክሱ ሊቀርብ እንደማይገባ የሚገልፁ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ሟች አለቃ አያሌው ታምሩ ስራውን የማሰራጨት መብታቸውን ባለመጠበቃቸው ስራው የራሳቸው የፈጠራ ስራ ነው ቢባል እንኳ ሌሎችን ከማሰራጨት ማገድ እንደማይችሉ የሟች አያሌው ታምሩ ስራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እውቀት መሠረት በማድረጉ የስራ አመንጪ ሊባሉ እንደማይችሉ ፣ ስራው ወጥ ስራ ያለመሆኑንና በሕግ ጥበቃ ሊያገኝ እንደማይገባ ሟች የጀመሩትን ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትምህርት ለሕዝብ ለማሰራጨታቸው አመልካቹ ሊከሰሱ እንደማይገባ ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች በበኩሉ በሰጠው መከላከያ መልስ አንደኛ አመልካች ለህትመት ባቀረቡት ፅሑፍ ምንጩ አለቃ አያሌው ታምሩ መሆናቸውን በመገለፁ የሚያስጠይቀው መሆኑን የወራሾችን ፈቃድ መጠየቅ ያለበት አሳታሚ እንጂ አታሚ ያለመሆኑን ፣ የሟች የፈጠራ ስራ ለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡን ፣ አታሚዉ በራሱ አነሳሽነት ያለማተሙንና የሟች አለቃ አያሌው ታምሩ ስራ ስለመሆኑ የማያውቅ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በሁዋላ ሁለተኛ አመልካችን /አታሚ ድርጅቱን/ ከክሱ ነፃ ሲያደርገው አንደኛውን አመልካች በተመለከተ ግን ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ፍሬ ነገር ክርክሮችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ለቁሳዊ ጉዳት ካሣ፣ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ/ ለሞራል ካሣ ፣ በድምሩ ብር 160,000.00 /አንድ መቶ ስልሳ ሺህ/ እንዲከፍሉ ፣ የሟች አለቃ አያሌው ታምሩን ስራ እንዳያሳትሙና መብቱን ከመጣስ ተግባር  እንዲቆጠቡ ፣ የታተሙትና ወደፊት የሚታተሙት መፅሐፍት እንዲወገዱ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛ አመልካች ለክሱ ኃላፊ በመባላቸው ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ሁለተኛ አመልካች ከክሱ ነፃ ተብሎ በመወሰኑ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ  ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁኑ አንደኛ አመልካች ያቀረቡትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ሲሰርዘው የተጠሪዎችን ይግባኝ ግን ተቀብሎ ከአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ጋር ከአከራከረ በሁዋላ አመልካችን ያለባለቤቱ ፈቃድ የተጠሪዎችን አውራሽ ፎቶ ግራፍ ከእነፈጠራ ስራቸው በመጽሐፍ አትሞ ማውጣቱ ተረጋግጧል በሚል ምክንያትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ፣ 29 እና 2027 ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ከአንደኛ አመልካች ጋር በአንድነት እና በነጠላ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተናጥል ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አንደኛ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃዎች ሳይሰሙ ውሣኔ መሰጠቱና ስራው የሚቹ ወጥ ስራ ያለመሆኑን ፣ ሚቹ ስራው ለሕዝብ እንዳይሰራጭ ባለደረጉበት ሁኔታ በቅጅ ሕግ ጥበቃ የሚሰጠው መብት ነው ተብሎ መወሰኑ ያለግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛው አመልካች ደግሞ አታሚ እንደመሆኑ መጠን ሶስተኛ ወገን እንዲታተም ባቀረበው ጽሑፍ የሚጠይቅበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ለክሱ መሠረት የሆነው ስራም የሚቹ ወጥ ስራ ሳይሆን ሚቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ በነበሩበት ጊዜ ቤተክርስቲያንን ወክለው መጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ ሲያስተምሩ የነበሩት የቤተክርስቲያኗ ስራ መሆኑና ሚቹም ያስተማሩትና መግለጫ የሰጡበት ስራቸው ከሃሣቡ አመንጪ ፈቃድ ውጪ ማባዛት ፣ ማሰራጨት ማተም ... ወዘተ የሚል ክልከላም ያስቀመጡት ሁኔታ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካቹ ለክሱ ኃላፊ መደረጉ ከሕግ ውጪ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ለክሱ ኃላፊ ተብለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደረጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሣኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሕግ ረገድ እንደሚከተለው ተመልክቶታል፡፡

በመሰረቱ አንድን የፈጠራ ስራ በትክክል ስራ ሊስብለው የሚችለውና ለቅጅ መብት ጥበቃ ብቁ የሚያደርገው ስራው የመጀመሪያ ስራ ወይም በባሕርይው ለየት ያለ ስራ ሲሆን መሆኑ የአዋጅ ቁጥር 410/1996 ይዘትና መንፈስን የሚያስገነዝበን ነጥብ ነው፡፡ ስራው የመጀመሪያ ስራ / original/ ወይም ባሕርይው ለየት ያለ ስራ ነው ሊያስብለው የሚችለው ደግሞ ውጤቱ የግለሰብ የፈጠራ ጥረት መሆን ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ሕጉም ጥበቃ የሚያደርገው የግለሰቡን የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ የፈጠራ ውጤት መኖሩ መረጋገጥ ደግሞ የፈጠራ ስራ ለቅጅ መብት ብቁ ከሚያደርጉት መመዘኛዎች /መለኪያዎች/ አንዱ ሲሆን ጥበቃ የሚደረገው ግለሰቡ ሐሳቡን የገለፀበት ቅርፅ እንጂ ሐሳብ ወይም በፈጠራ ስራው ውስጥ ያለው መረጃ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሃሣብ አገላለፅ ቅርጽ በቅጅ መብት ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን ሃሣቡ በራሱ ብቻ ግን አይሆንም፡፡ የሃሣቡን ይዘት ለሌሎች መግልፅ የፈጠራ ስራ መብት ጥሰትን የሚያስከትል ሲሆን ሌሎች ሰዎች ሃሣቡንና መረጃውን የራሳቸው ለየት ያለና ነፃ ስራ ተጠቅመው መገኘት የፈጠራ ስራ ውጤትን እንደመጣስ የማይቆጠር መሆኑን ሕጉ ለጥበቃው ካስቀመጠው መለኪያ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ የቅጅ መብት አይነተኛ አላማ ለስነ ፅሁፍ ፣ ኪነ ጥበብ እና ስነ ጥበብ ፈጠራዎች ሕጋዊ ጥበቃ ማድረግ ነው፡፡ የሕጉ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ በቅድሚያ የቅጅ መብት የሚጉናፀፉት የፈጠራ አመንጪዎች መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ በቅጅ መብት ውስጥ መብት ተብሎ የሚታወቁት ደግሞ የኢኮኖሚ መብቶችና የሞራል መብቶች ሲሆኑ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 እንደተደነገገው ከኢኮኖሚያዊ መብቶች አንዱ ተጥሶ በተገኘ ጊዜ የሞራል ጉዳት ጥሰት የሚኖር መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 የተመለከቱት ኢኮኖሚያዊ መብቶች ደግሞ ከአዋጅ አንቀፅ 9 እስከ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ ወይም የአንድ ሥራ ባለቤት፡-

ሀ/ ሥራን የማባዛት ፣

ለ/ ሥራን የመተርጐም ፣

ሐ/ ሥራን የማመሳሰል ፣ የማቀናበር ወይም ወደ ሌላ አይነት የመቀየር

መ/ በሽያጭ ወይም በኪራይ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን የማከፋፈል

ሠ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ከውጭ ሀገር የማስገባት

ረ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሣየት

ሰ/ ሥራን በይፋ የመከወን

ሸ/ ሥራን ብሮድካስት የማድረግ

ቀ/ ሥራን በሌላ መንገድ የማሰራጨት መብቶችን ራሱ ሊፈጽም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል ተብሎ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ተቀምጧል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ አመልካች የተጠሪዎች አባት የፈጠራ ስራ የሆኑትን ፅሑፎች በጋዜጣ እና በመፅሄት ላይ የውጡ ቃለመጠይቆችን ፣ መጣጥፎችን ፣ የሟች የመንፈቅ መታሰቢያ ፖስተር ላይ የወሰዱትን የመፅሐፉን የሽፋን ሥእልና የሀዘን መግለጫ ግጥሞችን ጭምር በማሰባሰብ በ2ኛ ተጠሪ ማተሚያ ቤት አማካኝነት “ ትምህርተ ሃይማኖት ” በሚል ርዕስ 1ኛ አመልካች ማሳተሙን ሳይክዱ የታተሙት ስራዎች የሟቹ ወጥ ስራዎች ሳይሆኑ ሟቹ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ሁነው ሲሰሩ በቤተክስቲያን ሐይማኖት የነበራቸውን አቋም የገለፁበት እንጂ የራሳቸው ወጥ ስራ አይደለም ፣ 1ኛ አመልካችም ለሕዝብ ከማሰራጨት በሟቹ አልተከለከሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክርክርም ሆነ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ክርክር የመጽሐፍ ገቢ ለሟች ቤተሰቦች እንዲሆን በማለት በመፅሐፉ መፃፋቸው የተረጋገጠ መሆኑ ሲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 83 እና 235 ድንጋጌዎች መሠረት የስራው ፈጠራ ባለቤት የተጠሪዎች አባት መሆናቸውን ማመናቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካችም ሆነ 2ኛ አመልካች የስራው የፈጠራ ባለቤት የተጠሪዎች አባት መሆናቸውን በግልፅ ሳይክዱ መቅረታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ መከላከያ ማስረጃ ያለመሰማቱ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት ያጣበበ ነው ለማለት ስላልተቻል በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

የተጠሪዎች አባት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ በነበሩበት ጊዜ ስለሐይማኖቱ የሰጡትን አስተያየት ማንም ሰው ለማሳተም የሚችልበት አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት ደግሞ ሐሳቡ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሐይማኖታዊ ትምህርት ነው ቢባል እንኳ ሟቹ ሐሳቡን የገለፁበት ቅርፅ ግን የራሳቸው የፈጠራ ስራ በመሆኑ በሕጉ ጥበቃ ለማግኘት የሚያስችለውን መመዘኛን ማሟላቱን የክርክሩ ፍሬ ነገሮች የሚያስረዱ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ሕጉ በዋነኛነት ጥበቃ የሚያደርገው የሐሳቡ አገላለፅ ቅርፅ እንጂ ሃሣቡን ራሱን አይደለም፡፡ 1ኛ አመልካች የተጠሪዎች አባት ስለሃይማኖቱ የገለፁበትን የሐሳብ አገለላጽ ቅርጽ ሳይለውጡ ሐሳቡ የተገለፀበትን መንገድ እንዳለ መውሰድና “ ትምህርተ ሐይማኖት ” የሚል ርዕስ በመስጠት ማሳተማቸውና ማሰራጨታቸው አልተካደም፡፡

ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 7 የተመለከተውን መብት መጣስ ነው። አመልካቾች የአዋጁን አንቀጽ 13 በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክርም ሲታይ ሕጉ ለሕዝብ ስለማሰራጨት እና ማባዛት እንደቅደም ተከተላቸው በአንቀፅ 2/6/ እና 2/25/ ስር የተመለከቱትን ትርጓሜዎችን የሚያሟላ አይደለም። በሌላ አገላለጽ የፈጠራ ባለቤት የፈጠራ ስራዎቹን እንዳይሰራጩ አልከለከለም ተብሎ አንድን የፈጠራ ስራ በመፅሐፍ መልክ ባልታተመበት ሁኔታ በሕግ አግባብ መብት ያላገኘ ሰው ለሕዝብ ትምህርት ነው ብሎ ማሰራጨት ወይም ማባዛት በአዋጅ አንቀጽ 13/1/ መሠረት የቅጅ መብት ጥሰት አይደለም ሊባል የሚችል አይደለም። በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2/6/ እንደተመለከተው ለሕዝብ ማሰራጨት ማለት የአንድ ስራ ክወና ፣ የድምፅ ሪከርድ ወይም ብሮድካስት ምስል ፣ ድምጽ ወይም ሁለቱን በሽቦ ወይም ያለሽቦ ማሰራጨትን የሚመለከት ሲሆን ማባዛት ማለት ደግሞ አንድን ስራ ወይም የድምጽ ሪከርዲንግ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የኤሌክትሮኒክ ማከማቻን ጨምሮ በማንኛውም አኳኋን ወይም መልክ ስራውን ወይም የድምጽ ሪከርዱን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቅጅዎች መገልበጥ መሆኑን ደግሞ የአዋጅ አንቀፅ 2/25/ ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል።

ከእነዚህ ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ የሚነሳው ድንጋጌ በአዋጅ አንቀፅ 13/1/ የሰፈረ ሲሆን ይዘቱም በዚህ አዋጅ ቁጥር 7/1/ሀ/ ፣ /ሸ/ እና /ቀ/ የተደነገገው ቢኖርም እስከተቻለ ድረስ የስራውን ምንጭና የስራ አመንጪውን ስም መጥቀስ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጅ መብት ባለቤቱ፣ የማባዛት ፣ ብሮድካስት የማድረግ ወይም ለህዝብ የማሰራጨት መብቱ የስራው አመንጪ ወይም የቅጅ ባለመብቱ መሆኑን በቅጅው ላይ በግልጽ የተጠቀሰ ነገር ከሌለ በወቅታዊ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ጉዳዮች ላይ በጋዜጣ ፣ በመፅሔት የወጡ ወይም ተመሳሳይ ባህሪ ኖሯቸው ብድሮድካስት የተደረጉ መጣጥፎችን በሌላ ጋዜጣ መጽሄት ማባዛት ፣ በብሮድካስቲንግ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ማድረሱን ሊከለከል አይችልም ተብሎ በግልፅ ተደንግጓል። የተጠሪዎች  አባት በሕይወት ዘመናቸው ብዛት ያላቸውን ሐይማኖትን ነክ የሆኑ የፈጠራ ስራዎችን መስራታቸው ፤ የተለያዩ ፅሑፎችን ማዘጋጀታቸውን ፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይም በመጣጥፍና በቃለመጠይቅ ዙሪያ ስብከቶችን ማዘጋጀታቸውንና የሚቹን የፈጠራ ስራ የሆኑትን ፅሑፎችን በጋዜጣ እና በመፅሄት ላይ ወጡ ቃለመጠይቆችን ፣ መጣጥፎችን ፣ ከሟች የመንፈቅ ዓመት መታሰቢያ ፖስተር ላይ የወሰዱትን የመፅሐፍን የሽፋን ሥእልና የሀዘን መግለጫ ግጥሞችን ጭምር በማሰባሰብ በ2ኛ ተጠሪ ማተሚያ ቤት አማካኝነት " ትምህርት ሃይማኖት " በሚል ርዕስ ታትሞ መውጣቱ ተረጋግጧል። ከዚህም በግልፅ መረዳት የሚቻለው እነዚህ ስራዎች ለህዝብ መረጃ አገልግሎት አላማ የሚባዙና የሚሰራጩ ከሆነ በስራው ባለቤት በወጡበት መንገድ ከሚሆን በቀር በመጽሐፍ መልክ ታትመው የሚባዙበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 13/1/ ድንጋጌ ከህዝብ ስለማሰራጨትና ስለማዛባት ሕጉ ከሠጠው ትርጓሜ ጋር ተዳምሮ ሲነበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።

በአዋጁ አንቀፅ 13/1/ ስር "....... መፅሔት...." የሚለው ቃል " Periodical " የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካው መሆኑን ሕጉ የሚያሳይ በመሆኑ ይኸው ቃል በማንኛውም መለኪያ መፅሐፍ የሚለውን ቃል አይተካም። ስለሆነም አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 13/1/ ድንጋጌን በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል። በመሆኑም የተጠሪዎች አባት በድንጋጌው በፊደል " ሀ " " ረ " እና " ቀ " የተመለከተው ወጥ( "ኦርጅናል" ) ሥራን የማባዛት ፣ የማሳተም ወይም በሌላ መንገድ የማሰራጨት መብት ተጥሷል። ይኸውም የፈጠራ ስራቸው ከአውራሾች ፈቃድ ውጪ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ በገበያ ላይ ውሎ በሕዝብ መነበቡ ነው። የሟቹ የፈጠራ ስራ ከወራሾቹ ፈቃድ ውጪ በ1ኛ

አመልካች አሳታሚነት በመጽሐፍ መልክ ገበያ ላይ ውሎ መነበቡ ኦርጅናል ሥራውን ወይም ቅጅውን ለሕዝብ ማሳየት/public display of original or copies of the work/ የሚለው በሕጉ የተመለከተው የሚች ወራሾች መብት ተጥሷል ማለት ነው፡፡ ይህ መብት ተጥሶ የሞራል ጉዳት በደረሰ ጊዜ የካሣው መጠን በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34/4/ መሠረት ከ100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር / የማያንስ የገንዘብ ካሣ ሊከፍል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት በተጠሪዎች ላይ የደረሰውን የህሊና ጉዳት ሞራል ካሣ 1ኛ አመልካች በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት 100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር / የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሁለተኛው አመልካች ከላይ የጠቅስናቸውንና ተቀባይነት የሌላቸው የሕግ ክርክሮችን ከማንሳቱም በተጨማሪ በአታሚነቱ የሚጠየቅበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ፣ 29 ፣ 2027 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው፡፡ ይኸው ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች በአከራካሪው መፅሐፍ የሚች አለቃ አያሌው ታምሩን ፎቶ ግራፍ ለጥፎ ማውጣቱን ፣ አሳታሚው አንደኛው አመልካች የሚቹን ፎቶ ግራፍ አትሞ ለማውጣት በቅድሚያ ስለመወከሉ ወይም ይህንን ለማድረግ ስልጣን ያለው መሆኑን ሁለተኛ አመልካች ያለማጣራቱን ፎቶውን የያዘው መፅሐፍ በገበያ ላይ መሰራጨቱን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡ ሁለተኛ አመልካችም እነዚህን ፍሬ ነገሮችን አልካደም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27/ ፣ 29 እና 2027 ድንጋጌዎች የማይጠየቅበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለጉዳዩ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአሁኑን አንደኛ አመልካችን በተመለከተ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88615 ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 62371 የካቲት 04 ቀን 2003 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63119 ሚያዚያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. አመልካቾች ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ለቁሳዊ ጉዳት ካሣ ፣ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ / ለሞራል ካሣ ፣ በድምሩ ብር 160,000.00/አንድ መቶ ስልሳ ሺህ/ እንዲከፍሉ፣ የሚች አለቃ አያሌው ታምሩን ስራ እንዳያሳትሙና መብቱን ከመጣስ ተግባር እንዲቆጠቡ፣ የታተሙትና ወደፊት የሚታተሙት መፅሐፍት እንዲወገዱ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በዚህ ችሎት በመ/ቁጥር 70380 ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁ. 64129

ህዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ኢስላሚክ ሪሊፍ ኢትዮጵያ - ጠበቃ ቃሲም መሐመድ - ቀረቡ
ተጠሪ፡- አቶ መሐመድ ሠይድ - የቀረበ የለም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክር በፍርድ ባለቀና የአፈጻጸም መዝገቡ ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሠረት የቀረበ ነው፡፡ በአሁኑ ተጠሪ ቀርቦ የነበረው የአሰራና ሰራተኛ ጉዳይ ክስ በአፋር ብሔ/ክልላዊ መንግስት በዞን 4 እዋ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ያገኘ ሲሆን ይዘቱ በተጠሪ ላይ የተፈጸመው የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው በማለት ሊከፍሉ የሚገባቸውንም ተያያዥ ክፍያዎች በማመላከት የተሰጠ ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ለክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በተጠሪ ላይ የተወሰደው እርምጃ ህገ ወጥ ስንብት መሆኑን በማጽናት ተያያዥ ክፍያዎችን በተመለከተ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የወሰነ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ አሁን አከራካሪ የሆነውና ለዚህ ቅሬታ መሠረት የሆነው የአሁን ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው የአፈጻጸም ማመልከቻ እና ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ማመልከቻ በመቀበል ግራ ቀኙን በማከራከር ታህሣስ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ የተመለከተውን ጉዳይ ማስፈጸም ያለበት ቀድሞውኑ በወረዳው ፍ/ቤት ላይ ተከፍቶ በነበረው የአፈጻጸም መዝገብ የወረዳው ፍ/ቤት እንጂ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ ስልጣኑ ካለመሆኑም በላይ የይግባኝ መብታችንን የሚያጣብብ በመሆኑ አግባብነት የለውም የሚል ሲሆን በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ ትዕዛዝ ሲሰጥ ቀድሞ ፍርድ ያላረፈበትን ክፍያዎች ሁሉ በመጨመር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ የአፈጻጸም ጉዳዩን ተመልክቶ ማስፈጸም ይችላል ከፍርድ ዉጪ ተጨምረዋል የተባሉትን ክፍያዎች በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የወሰናቸው በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ የተጠሪ የሥራ ውል ከህግ ውጪ ተቋርጧል ተብሎ የካሣ ክፍያ የ85 ቀናት ደመወዝ ይከፈለው ተብሎ የተሰጠው ፍርድ እያለ በአፈጻጸም ውሣኔው ላይ የ180 ቀናት ደመወዝ ይከፈለው የመባሉን አግባብነት የነበረ ቢሆንም

አሁን ችሎቱ ጉዳዩን ሲመለከተው ከተያዘው ጭብጥ በፊት የዞኑ ፍ/ቤት ያለውን ስልጣን መመልከት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት የአፈጻጸም መዝገቡን ተመልክቶ ትዕዛዝ መስጠቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክር በክልሉ የዞን አራት የእዋ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ያገኘ ስለመሆኑ ይሄ የወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የተወሰደው የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ስለመሆኑ የዞኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በተመሳሳይ የተቀበለውና ያጸናው ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበው ቅሬታ መሠረት የክፍያውን መጠን በተመለከተ ብቻ የወረዳውን ውሣኔ ያሻሻለው ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድን ፍርድ ማስፈጸም ያለበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ተመልክቶት ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የአፈጻጸም ሥርዓት የሚመራበትን አግባብ የሚያመለክተው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በተለይም በህጉ ከቁጥር 371- እስከ 385 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ዓላማ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ ይሄ አሰራር ደግሞ በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶች በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች ሊያሻሽሉ የሚችሉበት በርካታ አጋጣሚዎች ሊኖሩ ቢችሉም አፈጻጸሙ ግን አንድ ላይ ተጠቃሎ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው ፍ/ቤት እልባት ማግኘቱ ለተከራካሪዎች ወጪ ቆጣቢ ከመሆኑም በላይ በአፈጻጸም ሂደት በሚሰጡት ትዕዛዞች ላይ ቅሬታ ቢኖር እንኳ የይግባኝ መብት የማያጣብብ በመሆኑ ጠቀሜታው የጉላ ነው፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ በወረዳው ፍ/ቤት ፍርድ መሠረት የአፈጻጸም መዝገብ በወረዳው ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ያስከፈቱ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውም ውሣኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሻሻለ ቢሆንም አፈጻጸሙ መቀጠል ያለበት በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን አይቶ ፍርድ በሰጠው የወረዳ ፍ/ቤት መሆን ሲገባው የክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት የእዋ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻሉ ብቻ የአፈጻጸም መዝገቡን አስከፍቶ ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡ ባጠቃላይ የአፈጻጸም ክስ መስተናገድ ያለበት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የሰጠው ፍ/ቤት ሆኖ እያለ የክልሉ የዞን ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓቶችን የጣሰና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡
በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአፋር ብሔ/ክልላዊ መንግስት የዞን አራት ከፍተኛ ፍ/ቤት ታህሣስ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በመዝ.ቁ. 00039 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ጉዳይ የአፈጻጸም ክሱን በመጀመሪያ ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለበት በጉዳዩ ላይ በመጀመሪያ ፍርድ የሰጠው የወረዳ ፍ/ቤት እንጂ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመሆኑ በዚህ የአፈጻጸም መዝገብ ላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል፡፡
   የፍርድ ባለመብት በፍርዱ መሠረት ሊፈጸምለት የሚገባቸውን ነጥቦች በተመለከተ በወረዳው ፍ/ቤት ከመጠየቅ የሚከለክለው ነገር የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ.70378

ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች:- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቶች**:- 1- አቶ ልኡልሰገድ አጥላባቸው
2- አቶ ሱፊያን አራርሶ
3- አቶ ረመዳን ኢድሪስ
4- አቶ አብዱላዚዝ ኢብራሂም
} ጠበቃ አስፋው ገ/አሊፍ ቀረቡ

ተጠሪዎች:- 1- ፍሎራ ኢኮ ፓወር ኃ/የተ/የግል ድርጅት- ነገረ ፈጅ ሽመልስ ሣተናው ቀረቡ

2- የፍሎራ ኢኮ ፓወር ሠራተኞች ማህበር-ተወካይ ደሣለኝ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካቾች በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪ የሆኑ ተሽከርካሪዎች በሀራጅ በሚሸጡበት ወቅት ግዢ የፈጸሙ እና ፍርድ ቤቱም የሀራጅ ሽያጬን በተመለከተ በአግባቡ አልተከናወነም በማለት ሰርዞ አመልካቾቹም የተረከቡትን ማሽኖች እና ተሽከርካሪዎች እንዲመልሱ በመወሰኑ ፤ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውም ውሣኔ በክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት በመጽናቱ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልን በማለት አመልካቾችን በማመልከታቸው የቀረበ ነው፡፡

አመልካቾች ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ቅሬታ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉትን ነጥቦች ያቀረቡ ሲሆን ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ የአቤቱታ ፍሬ ሃሣብ :- የገዛናቸው ተሽከርካሪዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በህጉ አግባብ ባወጣው ሀራጅ መሠረት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ራሱ ያዘዘውን በራሱ መልሶ መሻሩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ፤ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ጨረታውን ተሳትፈን የገዛነውን ተሽከርካሪዎች እንድንመልስ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ ፤ በጉዳዩ ላይ ሃሣባችንን እንድናቀርብ ሳይደረግ የተደረገው ሀራጅ መሻሩ አግባብነት ሌለው በመሆኑ ፤ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት በተመለከተ የሚደረገውን ሀራጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 435 መሠረት መታየት ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445 ን በመጥቀስ ሀራጁ

እንዲፈርስ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ ፣ ለተሸከርካሪዎቹ የከፍልነውን ገንዘብ በተመለከተ ምንም ሳይባል መታለፉ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ 1ኛ ተጠሪ በቀን 4/2/2004 ዓ.ም በሶስት ገጽ እና 2ኛ ተጠሪም በቀን 30/1/2004 ዓ.ም በሶስት ገጽ በተጻፈ የጽሑፍ መልስ የሰጡ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ ፡- የፍርድ ባለዕዳ ግዙፍ እና የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ማሽኖችን እና ተሽከርካሪዎችን በቂ ዕውቀት ባለው ባለሙያ ሳይገመት የጨረታው ማስታወቂያ ህጉ በሚያዘው መሠረት ሳይወጣ ፣ የፍርድ ባለመብት በእጅ አዙር የገዛው ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ ጨረታው እንዲሰረዝ የተደረገ በመሆኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካቾች የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ የሚመለከተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን የሚመለከተውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 445 መሠረት በማድረግ ጨረታውን የመሰረዛቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከዚሁ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ጉዳዩ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪ የሆነው የሀራጅ ሽያጭ የተካሄደው በጋዜጣ ማስታወቂያ ሳይወጣ እና በወስጥ ማስታወቂያ ብቻ ሀራጅ መደረጉ ፣ በሀራጅ ሽያጩ ላይ የማጭበርበር ተግባር የተፈጸመ ስለመሆኑ እንደዚሁም ንብረቶቹ ከዋጋቸው በታች የተገመቱ እና የተሸጡ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት በእርግጥ በበታች ፍርድ ቤቶች የተከናወነው ሀራጅ እንዲፈርስ ሲደረግ የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 445 መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 432 እስከ 438 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች እና በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 በመሆኑ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አኳያ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት መመልከት ተገቢነት አለው፡፡

በዚሁ መሠረት በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ወይም የተከናወነውን ጨረታ መሰረዛቸው አግባብ ስለመሆን ወይም አለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 አኳያ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ድንጋጌ ርዕስ እንደሚያሳየው የሽያጩ ስርዓት በትክክል ያለመፈጸም ሽያጩን የሚያፈርስበት ሁኔታ በሚል የተቀመጠ በመሆኑ ፣ ወደ ድንጋጌው ይዘት ስንገባም በእርግጥ ለሽያጩ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ጉድለት በመገኘቱ ወይም የሽያጩ ስነስርዓት በትክክል አልተፈጸመም በማለት ብቻ የተከናወነው ጨረታ በሰበብ አስባብ ሊፈርስ እንደማይችል የሚደነግግ ቢሆንም በሂደቱ ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነን ሰው ካሣ እንዲከፍል መወሰን የሚቻል ስለመሆኑ ፈቃጅ በሆነ ሁኔታ የሚደነግግ ከመሆኑም በላይ እንደ ጉዳዩ አግባብ እየታየ የተከናወነው ጨረታ ፈርሶ የተሸጠውም ንብረት እንዲመለስ የሚወሰንበት አግባብ እንዳለ ከድንጋጌው አቀራረጽ ፣ ዓላማ ፣ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሚንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ በሚሸጥበት ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ስህተት ቢፈጸም ጨረታው የሚሰረዝበት አግባብ የለም በሚል መልኩ በአመልካቾች የሚቀርበው ክርክር የዚህን

የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓለማ ያላገናዘበ እና በሂደቱ ፍትሐዊነት ላይ ፍርድ ቤቶች ያላቸውን ሚና ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የተረጋገጡትን ፍሬ- ነገሮች በመመልከት የተከናወነው ጨረታ እንዲፈርስ ውሣኔ መስጠታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 አኳያ ሲታይ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ የሚያሰኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔውን ሲያስተላል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435ን መጥቀስ ሲገባቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 445. መጥቀሳቸው አግባብነት ያለው ድንጋጌ ባይሆንም ከውጤት አኳያ ግን ተቀባይነት ያለው መደምደሚያ በመሆኑ የተከናወነው ሀራጅ ይፍረስ መባሉ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ 64628 ላይ የፍርድ ባለመብት የነበሩት ግለሰብ የተከናወነው ጨረታ ሊፈርስ አይገባም በማለት በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ በተመሣሣይ ቅሬታቸውን አቅርበው ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ከአሁኖቹ ተጠሪዎች ጋር ተከራክረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የጸና እና በዚሁ ጭብጥ ላይ ንብረቶቹን ገዛን የሚሉት የአሁኖቹን አመልካቾች ክርክር ተመልክተን ከላይ በተመለከቱት ነጥቦች ምክንያት ተመሣሣይ መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተካሄደው የሀራጅ ሂደት ጉልህ ግድፈቶች ስለመከሰታቸው በፍሬ ነገር በተረጋገጠበት ሁኔታ ሀራጁ ተሰርዞ አመልካቾች የገዙትን ንብረት እንዲመልሱ በመባሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ 124624 በቀን 26/7/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቾች በመዝ.ቁ 107688 ላይ ያቀረቡትን ይግባኝ በመዝ.ቁ 107486 ላይ በማጠቃለል በቀን 03/5/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 18376 በቀን 7/1/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በሀራጅ ሽያጭ ሂደት ግዙፍ ግድፈቶች በሚኖሩበት ጊዜ የተከናወነው ሀራጅ እንዲሰረዝ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 65814

የካቲት 29 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሚ/ር ቼዛኖ ቤነኛ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ዘውዱ ወልደሥላሤ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች የአሁን ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳ ከአቶ ወንድወሰን ካሣ ቤት ገዝተው ያልከፈሉት የቤቱ ዋጋ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ አለ፡፡ ይህንንም ለማንም ሣያስተላልፉ ይዘው እንዲቆዩ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ ይህንን ገንዘብ ለፍርድ ባለእዳው እዳ መፈፀሚያ እንዲሆን በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በእኔ እጅ የነበረውን ገንዘብ ለመንግስት መከፈል ላለበት የካፒታል ጌይን ታክስና ሌሎች እዳዎች ከፍያዋለሁ በማለት መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የፅሑፍ መቃወሚያ አቀርበዋል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በእጃቸው የነበረውን የፍርድ ባለእዳ የቤት ዋጋ ለካፒታል ጌይን ታክስና ለሌሎች እዳዎች የከፈሉ በመሆኑ ገንዘቡ የፍርድ ማስፈፀሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ የፍርድ ባለመብቱ የፍርድ ባለእዳውን ሌላ ንብረት አጣርተው ያቅርቡ በማለት መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ አፅንቶአል፡፡ አመልካች የካቲት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የያዙት ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለፍርድ ባለእዳው የሚከፈል ገንዘብ በመሆኑ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳው ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህን ገንዘብ ተጠሪ ይዞ እንዲቆይና ለሌላ ወገን እንዳያስተላልፍ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ የፈፀመው ተግባር የሥር ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው የሚገባው አይደለም፡፡ የካፒታል ጌይን ታክስ የመክፈል ግዴታ የገዥ ሣይሆን የሻጭ ግዴታ ነው፡፡ አመልካች በገንዘቡ ላይ ከፍርድ የመነጨ የቀዳሚነት መብት ያለው ሆኖ እያለ ተጠሪ ገንዘቡን ለግል ጉዳዩ ተጠቅመውበታል ስለዚህ የተጠሪ አድራጎት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156ን የሚጥስ በመሆኑ ገንዘቡን ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የፍርድ ባለእዳው ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ በእኔ እጅ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠቱ የሚታመን ነው፡፡ ገንዘቡ በእኔ እጅ የቆየው የፍርድ ባለእዳ የሸጠለትን ቤት ወደ እኔ ስም ለማዘዋወር ሊከፍሉት የሚገባውን የመንግስት ግብር ለመክፈል ነው፡፡ ብር 84,580.47 /ሰማንያ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ ከፍዬ ቀሪው ብር 4,085.80 ለቦታ ቅጣት የከፈልኩ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ገንዘቡ የተከፈለው በፍርድ ባለእዳው በአቶ ወንድወሰን ካሣ መሆኑ የቀረበው ደረሰኝ ያሣያል ተጠሪ ከፍሏል ቢባል እንኳን ገንዘቡ ከፍርድ ባለእዳ ጋር ያደረገውን ውል ማስፈፀሚያ ያደረገው የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ በመጣስ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና ሊሰጠው አይገባም በማለት ሰኔ 26 ቀን 2003 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ይዘው እንዲቆዩ የታዘዘውን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ተጠሪ የፍርድ ባለ እዳው የሸጠልኝን ቤት ስም ለማዛወር ለካፒታል ጌይን ታክስና ለሌሎች እዳዎች ከፍያለሁ በማለት ያቀረቡትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት መቀበላቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን የሥር አመልካች ተጠሪ ለፍርድ ባለእዳው ያልከፈሉትን ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ለማድረግ ያቀረቡትን አቤቱታ፤ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና የአፈፃፀሙን ክርክር ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 29879 በትእዛዝ በማስቀረብ አይቶታል፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት የአፈፃፀም መዝገብ እንደተረዳነው የፍርድ ባለመብት የሆኑት አመልካች የፍርድ ባለእዳው አቶ ወንድወሰን ካሣ ለተጠሪ /አቶ ዘውዱ ወ/ሥላሤ የሸጡት ቤት ንብረትነት ሲዛወር የሚከፈል ብር በገዥው በተጠሪ እጅ ስላለ ገዥው ገንዘቡን ለባለእዳው ሣይከፍሉ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ እና ይህንንም ለመፈፀማቸው ቀርበው እንዲያስረዱ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ተጠሪ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለባለ እዳው ሣይከፍሉ ይዘው እንዲቆዩ አዟል፡፡ እንደዚሁም ፍ/ቤቱ የአሁን ተጠሪ በ ትእዛዙ መሠረት የፈፀሙ መሆኑን ወይም የማይፈጽሙበ ምክንያት ካለ በሚቀጥለው ቀጠሮ ቀርበው እንዲያስረዱ በማለት ሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም. ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ለተጠሪም የእግድ ትእዛዙን ከመጥሪያ ጋር ልኳል፡፡

የአሁን ተጠሪ መጥሪያው እና የእግድ ትእዛዙ ከደረሳቸው በኂላ ሐምሌ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ከጠበቃ ጋር ቀርበው ከተባለው ገንዘብ ውስጥ ብር 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ ለመንግስት ግብር ተከፍሏል በማለት አስረድተዋል፡፡ አመልካች የተጠሪ ክርክር ትክክለኛ አይደለም ተጠሪ ገንዘቡን በሞዴል 85 ገቢ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ይሰጠልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ መርምሮ ብይን ለመስጠት ለህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ብር 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ ለመንግስት ግብር የከፈሉ መሆኑን የሚያሣየው ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑን ገልጾ ይህ ፍ/ቤት ገንዘቡ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው ትእዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ ለመንግስት ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያሣየውን ህጋዊ ደረሰኝ ያቅርቡ በማለት ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ ደረሰኝ የሚያቅርቡ ቢሆን ለመጠባበቅ ለህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም. ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ ህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም. የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ባለፈው ቀጠሮ ደንበኛቸው ብር 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ ለመንግስት ግብር ከፍያለሁ ያሉት በስህተት

ነው ገንዘቡ ገና አልተከፈለም ወደ ፊት የቤቱ ንብረትነት ከሻጭ ወደ ገዥ ሲዛወር የሚከፈል በመሆኑ ልንጠየቅ የሚገባው ክፍያ አይደለም በማለት አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳውን ገንዘብ ለማንም ሣይከፍሉ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ በማለት ህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በእኔ እጅ የነበረውን ገንዘብ የፍርድ ባለእዳው መክፈል የሚገባቸውን የካፒታል ጌይን ታክስና ለትርፍ ቦታ ቅጣት ከፍያለው የሚሉት መጋቢት 26 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑን ለሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው ቁጥራቸው 981809 እና 931808 የሆኑ ደረሰኞች ያሳያሉ፡፡ ከላይ ይዘታቸውን የገለጽናቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጣቸው ትዕዛዞች ተጠሪ አከራካሪውን ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ የፍርድ ባለ ዕዳው ሊከፍለው ለሚገባው የግብር ዕዳም ሆነ በሌላ ምክንያት ወጭ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ይዞ እንዲቆይ ግልጽና የማያሻማ ትዕዛዝ ሰጥቶ እያለና ተጠሪም ይህንን የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ እያወቀ ገንዘቡን ለካፒታል ጌይን ታክስና በትርፍ ቦታ ቅጣት የከፈለ መሆኑን ነው፡፡

የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው በእጁ ያልገባ ከሌላ ሰው የሚጠይቀው በሚተላለፍ ሰነድ ያልተደገፈ ገንዘብ ያለው መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ገንዘቡን የመያዝ ወይም የማስከበሩ ሥርዓት የሚፈፀመው ፍርድ ቤት ግልጽ የሆነ ትእዛዛ እስከሚሰጥ ድረስ ለፍርድ ባለእዳው ገንዘብ መክፈል የሚገባው ሰው ይህንን የሚከፈለውን ገንዘብ ለማንም ሰው ሣይሰጥ በእጅ እንዲቆይ በማድረግ እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሀምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም፣ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም. እና ህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ ገንዘቡ አንድ ጊዜ ለግብር እዳ ተከፍሏል፡፡ ሌላጊዜ ደግሞ ወደፊት ለግብር እዳ የሚከፈልና ጊዜ የማይሰጥ ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ገንዘቡን ለማንም ሣይሰጥ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ ግልፅና የማያሻማ ተደጋጋሚ ትእዛዝ የሰጠ መሆኑንና ትእዛዙም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ እጅ ተይዞ እንዲቆይ ትእዛዝ የሰጠበት ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ ለአመልካች የእዳ መክፈያነት መዋል አለበት ወይስ ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳው የገዙትን ቤት ስም ለማዛወር መከፈሉ አስፈላጊ ለሆነው የካፒታል ጌይን ታክስ ክፍያ መዋል አለበት? የሚለውን ጭብጥ ያልወሰነውና ወደፊት መርምሮ ትእዛዝ የሚሰጥበት መሆኑን ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ይዞ እንዲቆይ ትእዛዝ የተሰጠበት ገንዘብ ለአመልካች እዳ መክፈያነት ይውላል ወይም ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳ የገዛውን ቤት ስመሀብት ለመዛወር ሻጭ (የፍርድ ባለእዳው) ለሚከፍሉት የካፒታል ጌይን ታክስ መክፈያነት ይዋል የሚለውን የሥር ፍርድ ቤት ሣይወሰንና ግልጽ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት አመልካች ከፍርድ ባለእዳው ጋር አድርጌዋለሁ የሚሉትን የቤት ሽያጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ስመሀብት ሻጭ (የፍርድ ባለእዳው) ወደ ገዥ (ተጠሪ) ለማዛወር በህግ እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠው የካፒታል ጌይን ታክስ ለመክፈል የሥር ፍርድ ቤት በተደጋጋሚ የሰጠውን የእግድ ትእዛዝ በመጣስ ገንዘቡን ወጭ ያደረግሁ መሆኑን ያሳዩልኛል የሚሏቸውን ደረሰኞች በማያያዝ ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን ትእዛዝ ለሰጠው ችሎት ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይኸው ተጠሪ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም፤ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም ተጠሪ ገንዘቡን ለማንም ሣይሰጡ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እዲነሣላቸው የሥነ ሥርዓት ህጉን መሠረት በማድረግ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ

ማያደርግ፣ ገንዘቡን በራሳቸው ፍላጎትና ግላዊ ውሣኔ የእሳቸውን መብትና ጥቅም ለሚያስከብር ተግባር /ክፍያ/ ወጭ ያደረጉት መሆኑን የሚያሣይ መሆኑን ተረድተናል፡፡

ፍርድ የሚያስፈፀመው ፍርድ ቤት አንድ ሰው የተወሰነ ነገር ከመፈፀሙ እንዲታገድ ትእዛዝ ሰጥቶ እያለ ትእዘዝ የተሰጠው ሰው በትእዛዙ መሠረት ሊፈፀም ሲችል ሆነ ብሎ ሳይፈፀም የቀረ እንደሆነ ወይም እንዳይፈፀም የተከለከለውን ነገር የፈፀም እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የእንቢተኛውን ንብረት እንዲያዝና እንዲሸጥ አድርጎ የተወሰነበትን ግዴታ እንዲፈፀም ለማዘዝና ተገቢ መስሎ ከታየውም ከንብረቱ ሽያጭ ለፍርድ ባለገንዘብ ካሣ ወይም ኪሣራ እንዲከፈል እንደሚወስን በፍታብሔር ህግ  400 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 156 ንዑስ አንቀጽ 2 የፍርድ ቤትን የእግድ ትእዛዝ ያላከበረው ሰው ንብረት ለፍርድ ባለገንዘቡ ገንዘብ መክፈያ በመሸጥ ለማስከፈል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ እንደሚሰጥ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ እግድን ያላከበረውን ሰው የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ በመጋፋቱ በችሎት መድፈር ወንጀል የወንጀል ቅጣት ሊወሰንበት እንደሚችል የፍታብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ይከበርልኝ በማለት የፍርድ ባለእዳው ሀብት የሆነ ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ ለማንም ሰው ሣይሰጥ በእጁ ይዞ እንዲቆይ የፌዴራል ከፍትኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ተደጋጋሚና ግልጽ ትእዛዝ እያወቀና ገንዘቡ የእግድ ትእዛዝ ሊሰጥበት አይገባም የሚል መቃወሚያ ሲያቀርብና በችሎት ሲከራከር ቆይቶ ፍርድ ቤቱ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሣይነሣና ተጠሪ ገንዘቡን የፍርድ ባለእዳ የሸጠውን ቤት ስመሀብቱ ለማዛወር ቅድመ ሁኔታ የሆነውን የካፒታል ጌይን ታክስና የትርፍ ቦታ ቅጣት መክፈያነት አውየዋለሁ በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት መቀበላቸው ተገቢነት የሌለውና ከላይ የጠቀስናቸው የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ማንም ሰው ህጉን በእጁ አድርጐ እንዲጠቀምና በራሱ ጉዳይ ዳኛ ሆኖ እንዲወሰን አይፈቀድለትም፡፡ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳው ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ በእሱ እጅ የነበረ መሆኑን በመጠቀም ገንዘቡን ለማንም ሰው አሳልፎ እንዳይሰጥ ወይም እንዳይከፈል ፍርድን የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት የሰጠውን ግልጽ የእግድ ትእዛዝ እያወቀ ሆነ ብሎ ገንዘቡን የፍርድ ባለእዳው ከእኔ ጋር ላደረገው የቤት ሽያጭ ውል ለሚፈለግበት የካፒታል ጌይን ታክስ እና የትርፍ ቦታ ቅጣት እጠየቃለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍታብሔር ህግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 400 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156 ድንጋጌዎችን የሚጥስና የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሆኖ እያለ ተጠሪ አመልካች ላቀረበው የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ ተጠያቂነት የለበትም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለማንም ሰው ሳይሰጥ ወይም ክፍያ ሣይፈጽም ፍርዱን በሚያስፈፀመው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ተደጋጋሚ ግልጽ ትእዛዝ በመጣስ የፍርድ ባለእዳው ከእኔ ጋር ባደረገው ውል ምክንያት ለነበረበት የካፒታል ጌይን ታክስና ለትርፍ ቦታ መቀጫ ክፍየዋለሁ የሚለውን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለፍርድ ባለመብት (አመልካች) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 409(1) የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 400 የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156(2) መሠረት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ህዳር 22 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለአመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ውጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 69385

የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዳሽን ባንክ (አ/ማ) ነገረ ፈጅ አቶ ካሴብ ተስፋዬ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ - ቀረቡ

2. አቶ ሐሴን አህመድ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረም በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በአፈፃፀም ክርክር ጣልቃ መግባትን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የነበራቸው ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ ወይም በአፈፃፀም የሚከራከሩባቸው ንብረቶች ተጠሪዎች በጋብቻ በነበሩበት ወቅት ለወሰዱት ብር 12,835,838.26 (አሥራ ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሀያ ስድስት ሣንቲም) በመያዣነት የተያዙ በመሆናቸው በአፈፃፀሙ ክርክር ጣልቃ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት ያቀረበውን ማመልከቻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንብረቶቹ ፍርድ ያረፈባቸው በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 170105 ታህሣሥ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ለወሰዱት ብድር በመያዣነት የያዛቸውን ቁጥራቸው አስራ ሁለት የሚሆኑ የማይንቀሣቀሱ እና የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመዘርዘር አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ባላቸው ክርክር መነሻ ንብረቶቹ በሀራጅ እንዲሸጡ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሰጥቶ ውክልና ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰጥቷል፡፡ አመልካች ዕዳው የተጠሪዎች የጋራ ዕዳ ንብረቶቹም የተመዘገቡ የብድር መያዣዎች መሆናቸውን በማስረዳት የቀዳሚነት መብት ለማስከበር በአፈፃፀም ክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ

በማለት አመልክቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች በአፈፃፀሙ ክርክር ጣልቃ እንድገባ ቢደረግ ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ንብረቶቹ የጋራ ንብረት መሆናቸው ፍርድ ያረፈባቸው ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሣሥረው የኖሩና ጋብቻቸው በፍች እንዲፈርስ የተደረገ መሆኑንና ሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ በመሆን በአፈፃፀም የሚከራከሩት በጋብቻ ወቅት የገኙትን የጋራ ሀብት እንዲከፋፈሉ የተሰጠን ውሣኔ ለማስፈፀም በተከፈተው መዝገብ ነው፡፡

አመልካች አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት ለመከፋፈል በሚያደርጉት የአፈፃፀም ክርክር ጣልቃ ለመግባት የሚጠይቀው አመልካችና ተጠሪ የፀና ጋብቻ ላይ በነበሩበት ወቅት ቁጥራቸው አስራ ሁለት የሚሆኑ የማይንቀሣቀሱና የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመያዝ ብር 12,835,838.26 ብድር የሰጠሁ በመሆኑ በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በማለት ነው፡፡ ከባል ወይም ከሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው ዕዳ የባልና የሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 ይደነግጋል፡፡ አመልካች ላበደረው ብድር በመያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች ሽጦ የብድሩ መክፈያ ለማድረግ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ የማያስፈልገው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለ ህግ አውጭው አውጥቷል፡፡ እንደዚሁም በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ፣ ወይም እንዳይከበር የመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በቡዙ ንብረት ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መቀወሚያ ያቀረቡት ወይም እንዲያዝ በታዘዘው ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለን የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ክርክር ላይ ተካፋይ ባይሆኑም በሚያዘው ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው በመቁጠር የሚያቀርቡትን አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር እንዳለበት፣ አቤቱታውንና ማስረጃውን መርምሮ ውሣኔ መስጠት እንደሚገባው በፍታብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 418 እና ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 419 ድንጋጌዎች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግና የፍታብሔር ህጉን ድንጋጌዎችና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ አመልካችና ተጠሪ በአፈፃፀም እንዲከፋፈሉአቸው ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ንብረቶች ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት ለማሣየት ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል ወደ ክርክሩ እንዲገባ መፍቀድ ሲገባቸው ንብረቶቹ ውሣኔ ስለተሰጠባቸው በአፈፃፀም ጣልቃ መግባት አይፈቀድም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በአፈፃፀሙ ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በመቀበልና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቀጥር 341 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

የሰ/መ/ቁ 73041

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** ወ/ሮ ሰይዳ ደበሌ - ጠበቃ ዕዮብ ገ/ህይወት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሸሪፍ ሽኩር - በሌሉበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችንና ተጠሪን በፍርዱ መሰረት በስምንት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለውን ቤት ተከራካሪዎች የተለያየ ድንበር በማሣያታቸውና ቦታውም ሰነድ አልባ በመሆኑ ለማካፈልም ሆነ ለመሸጥ አስቸጋሪ እንደሆነ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ጽ/ቤትና ቀበሌው የገለፁት መሆኑን ምክንያት በማድረግ አፈፃፀሙን መቀጠል አይቻልም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች መስከረም 12 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በጋብቻ ዘመን በጋራ ያፈራነውን ቤት እኩል እንድንካፈል የተሰጠውን ፍርድ ማስፈፀም አስቸጋሪ ነው በሚል ምክንያት አፈፃፀሙ መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ መጥሪያ አልቀበልም ስለማለቱ በቃለ መሀላ አረጋግጣ ማመልከቻ አመልካች ስላቀረበች መልስ የመስጠት መብቱን በማለፍ ጉዳዩን በሌለበት መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አፈፃፀም ለመቀጠል አስቸጋሪ ነው የተባለው ቤት አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሀብት መሆኑ ቀደም ሲል ፍርድ ተሰጥቶበታል፡፡ ቦታውና ቤቱ ግብር ሲከፈልበት የኖረ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ ቦታውን ለረዥም ጊዜ ይዘውት እንደነበሩ አመልካች በሥርና በሰበር ካቀረበችው ክርክር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በፍርዱ መሰረት ቦታውና ቤቱን ለማካፈል ወይም በሐራጅ ለመሸጥ አይቻልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገቡን የዘጋው ቦታው ሰነድ አልባ መሆኑን የመሬት አስተዳደር ባልስልጣንና የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር ፅፎልኛል በማለት ነው፡፡

የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378 መሰረት ሲቀርብለት፣ የፍርድ ባለዕዳው የሚያቀርበውን መልስ በመቀበል፣ ፍ/ቤቱ ተገቢ የሆነውን ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 386 ተደንግጓል፡፡ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት በመሆኑ እኩል እንዲከፈል፤ እኩል ማካፈል የማይቻል ከሆነ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ የተሰጠበት ንብረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡ ይህ ንብረት ካርታ ፕላን ባይኖረውም የማይንቀሳቀሰውን ንብረትና ይዞታ ለመለየት የሚያስችሉ ልዩ ምልክቶችንና የንብረቱን አዋሳኞች በመለየትና ግልፅ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረትና ቦታ ለፍርድ ባለመብትና ለፍርድ ባለዕዳ እኩል እንዲከፍሉ ትዕዛዝ ለመስጠት ወይም እኩል ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱና ቦታው ካርታና ፕላን የሌለው መሆኑንና የንብረቱን አዋሳኞች በጨረታ ማስታወቂያው ላይ በመግለፅ ንብረቱን በመሸጥ ለማካፈል የሚቻልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የፍርድ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በፍርድ አፈፃፀም ሂደት እንደዚህ አይነት ችግሮች ሲያጋጥሙት ለፍርዱ አፈፃፀም ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት መሆኑ በፍርድ ቀደም ብሎ የተረጋገጠው ቤት ሰነድ አልባ በመሆኑ ንብረቱን ለማካፈልም ሆነ ለመሸጥ አስቸጋሪ መሆኑን የአስተዳደር አካል ፅፎልኛል በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ፤ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 371 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ፍርድ የማስፈፀም ሥልጣንና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 392 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ሣያርም ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና በማየት ፍርዱን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆነውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/392 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመስጠት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

# የዳኝነት ሥልጣን

የሰ/መ/ቁ. 77175

ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡-አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኢትዮጵያ- ጠበቆች 1. ማርሻል ፍቅረ ማርቆስ ቀረቡ

2. ሰለሞን እምሩ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ጎሳዬ አየለ ቀረቡ

2.. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ

3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የመሬት አስተዳደርና የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁኖ በአመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም፡- በየካቲት 11 ቀን 1997 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሊዝ ቦርድ ባሳለፈው ውሳኔ በቀድሞው ዞን 3፣ ወረዳ 28 መር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ውስጥ (ባሁኑ አጠራር በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 ክልል ውስጥ የሚገኝ 303,000 ካ.ሜትር ቦታ በሊዝ እንዲሰጠው ተወስኖለት በከተማ ቦታ የምስክር ወረቀት ሴሪ ቁጥር 0710 እና በካርታ ቁጥር ሊዝ 0236 ተረክቦ ቦታው በአመልካች ይዞታ ስር እንደሚገኝ፣ ሆኖም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን ቁጥር መአግፈባ/502/03 በ8/02/2003 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ በ22/11/2002 በቃለ ጉባኤ ቁጥር 16/2002 አሳለፈ ያለውን ውሳኔ በመጥቀስ አመልካች ከክፍያ ነጻ በተሰጠው ቦታ ላይ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ ሳያከናውን ቆይቶ የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄ በማቅረቡ የሊዝ ውሉ ተሰርዞ ካርታው መክኖ ቦታው እንዲመለስ መወሰኑን፣ ይህም ከሕግና ከሊዝ ውል ስምምነቱ ውጪ መሆኑን፣ ግንባታው በጊዜ ገደቡ ውስጥ ካልጀመረ ውሉ እንደሚሰረዝ ግልፅ ስምምነት የሌለ መሆኑንና ግንባታው ሊዘገይ የቻለውም የካቲት 2002 ዓ.ም. ድረስ የቆየው አስተዳደሩ በውሉ አንቀፅ 3.1 በገባው ግዴታ መሰረት ቦታው ላይ የሰፈሩትን ሰዎች ካሳ ከፍሎ ባለማስናበቱና ለውጥን በተመለከተም አመልካች የፕሮጀክት ለውጥ እንዲደረግለት በውሉ እና በሕግ መሰረት ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችል ለውሉ መሰረዝ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ዘርዝሮ ውሉ መሰረዙ ያላግባብ ነው ተብሎ የሊዝ ውሉ ጸንቶ በይዞታው የመጠቀም መብቱ እንዲጠበቅለት ይወሰን

ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የሚያነሱት ክርክር ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንጂ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይደለም የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የሊዝ ውሉ የተሰረዘውና ካርታው የመከነው በውሉ እና በሕጉ መሰረት መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ነው፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክሱ የቀረበው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት ላይ መሆኑና የክሱ መሰረትም የሊዝ ውል መሆኑን ጠቅሶና የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(ሀ) ድንጋጌን ዋቢ በማድረጉ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ሁኖ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር የተያያዘ ባልሆነበት ሁኔታ ግንኙነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፍርድ ቤቶች ናቸው ተብሎ የተወሰነው አግባብነት ካለው ህግ ይዘትና በሰ/መ/ቁጥር 57435 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውጪ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው ተብሎ መወሰኑ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(መ)) ድንጋጌና በሰ/መ/ቁጥር 45091 ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሕጋዊ ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደረመረውም ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው? ወይስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሐምሌ 14 ቀን 1990 ዓ.ም በተፈረመ የከተማ ቦታ ሊዝ ውል ጠቅላላ ስፋቱ 303,000 (ሶስት መቶ ሶስት ሺህ) ካሬ ሜትር ቦታ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 ክልል ውስጥ ለዘጠና አመታት መውሰዱንና ተጠሪዎች አመልካች ቦታውን በጊዜ ገደቡ ሳያለማ ለአስራ ሶስት አመታት ይዞ በመቆየቱና የፕሮጀክት ለውጥ ለማድረግ ጥያቄ አቅርቧል በሚል ምክንያት የሊዝ ውሉን በመሰረዝ ካርታውን ያመከኑ መሆኑንና አመልካች የሚጠይቀው ዳኝነትም የሊዝ ውሉ እንዲጸናና በይዞታው የመጠቀም መብቱ እንዲጠበቅለት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37/1/፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4፣ 9፣ 231 እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 እንዲሁም ተሻሽሎ በወጣው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ፍርድ ቤቶች አንድን ጉዳይ ማየት እና ውሳኔ መስጠት የሚችሉት በሕግ በግልጽ ተለይተው በተሰጧቸው ጉዳዮች መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዱ ፍርድ ቤት በሕግ የተሰጠው ስልጣንም መጠበቅ ያለበት ከመሆኑም በላይ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ /ክርክር/ መሠረት ያደረገው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረገው የሊዝ ውል የተሰጠውን ቦታ በጊዜ ገደቡ አልለማም፣ የፕሮጀክት ለውጥ ተደርጎአል ተብሎ የሊዝ ውሉ መሰረዙና ካርታው መምከኑ ከሕግ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሲሆን የሊዝ ውል መሰረዝን ሕጋዊነት በተመለከተ ስራ ላይ ባለው የሊዝ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ የከተማው አስተዳደር በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ወይም ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑን የሚደነግግ ሕግ የለም፡፡ የከተማው አስተዳደር ካርታ የመስጠት የመሠረዝ፣ የማሻሻል፣ የማምከን፣ የማገድ እና አሻሽሎ የመስጠት ሙሉ ስልጣን ያለው ቢሆንም የሊዝ ውልን መሠረት አድርጎ የተሰጠውን ካርታ መልሶ ከሕግ ውጪ ሰርዞ ሲገኝ በእርምጃው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት እንዳያቀርብ የሚከለከልበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ስልጣንና ኃላፊነትን ለመደንገግ የወጣውና፣ ክርክሩ ሲጀመርም ሆነ ከተጀመረ በኋላ በስራ ላይ ያለው ሕግ ያሣያል፡፡ ይልቁንም የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና /መ/ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተጣምረው ሲታዩ የተያዘውን ጉዳይ አይነት የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ተቀብለውና አከራክረው ለመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 41(1(መ)) በተለይ ሲታይም የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ለከተማው ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ተፈፃሚነት ካላቸው ሕጎች ስንነሳም የሊዝ ውሉም ከደንብ ቁጥር 29/2002 አንቀፅ 15 እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3132 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በአስተዳደራዊ ውሎች ስር የሚሸፈን ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጠ በማለት የሚጠቅሱት መ/ቁጥር 57435 ሲሆን በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ግን በሊዝ ውል በተገኘው ቦታ ሁከት ተፈጠረብኝ በሚል ምክንያት ሁከቱ እንዲወገድ ዳኝነት የተጠየቀበት በመሆኑና እንዲህ አይነት ክርክር ከከተማው መሪ ፕላን አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ካልሆነ በስተቀር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስረ ነገር ስልጣን ስር አይወድቅም በሚል ምክንያትና የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(ሀ)) ድንጋጌ በዋቢነት ተጠቅሶ ሲሆን በመዝገቡ ያሉት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችና ለውሳኔው መሰረት የሆነው አብይ ምክንያት አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም በሰ/መ/ቁጥር 45091 በቀረበው ጉዳይ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የከተማው አስተዳደር አካላት ተከራካሪ ወገኖች ሲሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች እንጂ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይደለም በማለት የአዋጁ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(መ)) ድንጋጌን ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1)

አግባብም በሰ/መ/ቁጥር 57435 በቀረበው ጉዳይ ላይ በግልጽ ተለውጧል ለማለትም የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው በማለት የሰጡት ብይን ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና /መ/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሕጋዊ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት በውሣኔው ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 111380 ታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75753 ጥር 08 ቀን 2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን የሊዝ ውልን መሰረት አድርጎ የሚቀርበውን የውል አፈፃጸምና ተያያዥ ጉዳዮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ ስልጣን ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

የሰ/መ/ቁ. 66957

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡ የኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ነ/ፈጅ አቶ አብርሃም አሻ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የሐዋሳ ቁጥር 2 ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት፡-

1. አቶ ፊልጶስ ኪንዶ
2. ‹‹ ካሳሁን ይግዛው
3. ‹‹ ታመነ ተሰማ
4. ‹‹ ወንድሙ ጆፌ
5. ‹‹ ሀሳቡ ሀንቃሞ
6. ‹‹ ሲሳይ ዮሐንስ
7. ‹‹ አብሩ ዲቃሞ
8. ‹‹ አበበ ዱባሞ
9. ‹‹ ኤብሶ አታሮ
10. ‹‹ ተሾመ ሴዳሞ
11. ወ/ሮ አስቴር ሀናቃሞ
12. ‹‹ መስታወት አያሌው
13. አቶ ታደገ ቶማስ
14. ዶ/ር ኤልያስ አራጌ
14. አቶ ብርሃኑ ሉምቤሶ
16. ፓስተር ተፈራ ወልደማርያም
17. ወንጌላዊ መስከረም ኃይሌ
18. አቶ አብርሃም ጫፋሞ
19. ‹‹ ደነቀ አሻግሬ
20. ወ/ት ብርቱኳን ተስፋዬ
21. አቶ ኢያሱ ረጋሳ
22. ‹‹ ቡልቻ ላንጋኖ
23. ‹‹ ደስታ አኔቦ አቀረቡ
24. ‹‹ማርቆስ መለሰ
25. ‹‹ ማርቆስ ጋሉ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ክስ በአሁን ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በሐዋሳ ከተማ ከፍ/ፍ/ቤት ሲሆን ተከሳሽ ደግሞ የደቡብ ኢትዮጵያ ስራ መስክ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም የሐዋሳ ቁጥር 2 የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ህገ ደንብና መመሪያ መሰረት የተቋቋመች የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስትያኗ ከ300 እስከ 400 የሚደርሱ መዕመናንን አቅፋ በአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነትና የአምልኮ ስርዓት እየሰራች እያለ በ1967 ዓ.ም. ከወጣውና እስካሁን በስራ ላይ ካለው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 14 የተጠቀሰውን አብያተ ክርስቲያናት የሚቋቋሙበት፣ የሚዋሀዱበትና የሚፈርሱበት ሁኔታን ባልተከተለ መልኩ እንዲሁም አጥቢያ ቤተክርስቲያኗ እንድትዘጋ፣እንድትፍርስ የሚያደርግ አንድም ምክንያት ሳይኖር በታህሳስ 8-9/2001 ዓ/ም የሰበካው ጉባኤ ባደረገው ስብሰባ በሀሰትና በፈጠራ ብቻ የአጥቢያ ቤተክርስቲያኗ እንድትፈርስ ጉባኤው የወሰነ ስለሆነ ውሳኔው ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩሏ በሰጠችው መልስ ቤተክርስቲያኗ እንድትዘጋ የተወሰነው በአመጽና በክህደት ተግባር ሲሆን ከሳሾችም ከተጠቀሱት ድርጊቶች እንዲታቀቡ የተሀድሶ ሰበካ ተደርጎ እንዲሁም ከስህተታቸው ተመልሰው ለመተዳደሪያ ደንቡ ተገዢ ሆነው እንዲቀጥሉ በመንፈሳዊ ርህራሔ ቢለመኑም በእምቢተኝነት ስለጸኑ እርምጃው ተወስዷል ብላለች፡፡

የስር ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ፍርድ እንድትዘጋ ውሳኔ የተሰጠባት ቤተክርስቲያን የአመጽም ሆነ የክህደት ተግባር ስለመፈጸሟ አልተረጋገጠም፣ ቤተክርስቲያኗ የፈጸመቻቸው ድርጊቶችም ቢሆኑ ከኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብና በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት በመሆኑና የሰበካው ጉባኤ ውሳኔም ይሔንኑ የመተዳደሪያ ደንብና ማኑዋል የጣሰ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ሲል ሰርዟል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባይዋን አሰናብቷል፡፡
በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች አቤቱታዋን ለዚህ ችሎት ያቀረበች ስትሆን በዋናነት የጠቀሰቻቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- ተጠሪዎች ከእናት ቤተክርስቲያን የተሰጣቸው ውክልና ሳይኖር በስማቸው የመክሰስም ሆነ የመከሰስ መብት የላቸውም ፣ ቤተክርስቲያኗ የተመዘገበችው በአዲስ አበባ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም በሚል የቀረቡትን የመቃወሚያ ነጥቦችን አለመቀበላቸው ህግ ስህተት ነው፣
- አመልካች ሀይማኖታዊ ተልዕኮዋን ለማሳካት ቅርንጫፍ ቤተክርስቲያናትን የማስፋፋትና እንደአስፈላጊነቱ የአሰራር ስርዓቷን ተከትላ የመዝጋት ሙሉ መብት ያላት በመሆኑ የሐዋሳ ቁጥር 2 ቤተክርስቲያንን በመበተኗ ምክንያት ተጠሪዎች አንድም ያጡትን መብት ወይም ጥቅም ባላስረዱበት የተወሰነው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33 ዓላማ ውጪ ነው፣
- የስር ፍ/ቤቶች በማስረጃነት ከቀረበው የመተዳደሪያ ደንብ ገጽ 156 ቁጥር(3) መንፈስ ውጪ ደንቡን በመተረጎም ጥፋቶቹ እንደክህደት ወይም አመጽ የሚፈረጁ አይደሉም ሲሉ ቤተክርስቲያኗ እንድትበተን የተሰጠውን ውሳኔ መሻራቸው ያለ አግባብ ነው፣የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡-

• በፍ/ህ/ቁ/448(1) መሰረት ተጠሪዎች በቤተክርስቲያኒቱ አባልነታችን ያልተቀበልናቸውንና የቤተክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ የሚጥሱትን የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን ለማሻር ክስ የማቅረብ መብት አለን፣
• የስር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ተቀብለው አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም በሚል አመልካች ያቀረበችው መቃወሚያም ቢሆን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣
• አመልካች ሀይማኖታዊ ተልዕኮን ለማሳካት ቅርንጫፍ ቤተክርስቲያን የማስፋፋትና እንደአስፈላጊነቱም የአሰራር ስርዓቷን ተከትላ የመዝጋት ሙሉ መብት እንደአላት ብትገልጽም ይህ መብትና ነጻነት ገደብ የለሽ ባለመሆኑ በሀይማኖት ነጻነት መብቷ ሽፋን የራሷን ደንብ በመጣስ ለጥቂት ግለሰቦች ፍላጎት በሚል በብዙሀኑ ፍላጎት ላይ መጫን አይገባትም በሚል በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት ጠቅለል ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሰበካው ጉባኤ ቤተክርስቲያኗ እንድትፈርስ ውሳኔ ያስተላለፈው ቤተክርስቲያኗ በራሷ ስልጣን እንድያገለግሏት የተመደቡላትን ፓስተር እና ወንጌላዊ አባርራለች፣ ለፓስተር የቅስና ማዕረግ ሰጥታለች፣ አስራትና መባ ለዋናው መስሪያ ቤት አትልክም፣ የተሰጣት ፈቃድ ሳይኖር ለሌሎች የአጥቢያ አድቬንቲስት ቤተክርስቲናት አገልግሎት በመስጠት የክህደትና የአመጽ ተግባር በመፈጸሟ ምክንያት ከድርጊቷ እንድትታቀብ የተሀድሶ ትምህርት ቢሰጣትም ልትመለስ አልቻለችም በሚል ነው፡፡ የተጠሪዋ ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት በበኩላቸው የክህደት እና የአመጽ ተግባር አለመፈጸማቸውንና በአድቬንቲስት መሰረተ እምነትና የአምልኮ ስርዓት የሚሰሩ ስለመሆናቸው ተከራክረዋል፡፡ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመርመርና በ1967 ዓ/ም የወጣውን የኢትጵያ አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መመሪያ በምዕራፍ 14 አብያተ ክርስቲያናትን ስለማቋቋም፣ማዋሃድ እና ስለማፍረስ በተደነገገው ስር በገጽ 156 በቁጥር 3 ክህደት የሚለው ቃል በመመሪያው ያልተብራራ መሆኑን ጠቅሶ የክህደት እና አመጽ ድርጊቶች ናቸው ተብለው በአመልካች በኩል የተነገሩትን ከምስክሮች ቃል አንጻር ሲታይ ተቀባይነት የለውም፣ በከሳሾች በኩል የተፈጸሙ ድርጊቶችም ቢሆኑ በመመሪያው መሰረት በቤተክርስቲያኗ ማኑዋል መሰረት የተፈጸሙ ናቸው ብሏል፡፡

እንድትፈርስ የተወሰነባት ቤተክርስቲያን ማለትም የሐዋሳ ቁጥር 2 አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው የአመልካች ቤተክርስቲያን አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ስትሆን በአጥቢያው ቤተክርስቲያኑዋና በሰበካው ጉባኤ እንዲሁም በኢትዮጵያ 7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መካከል ሊኖሩ የሚችሉትን ከአምልኮና ከቤተክርስቲያኗ የውስጥ አስታዳደራዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በፍ/ቤት በመወሰን እልባት መስጠት የሚቻል መሆን አለመሆኑን መመርመር ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም የኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 (1)ን መመልከት ተገቢነት አለው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ማንኛውም ሰው (የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ያለው ድርጅት) በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (justiciable

matter) ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡ በዚሁ አነጋገር በፍርድ ቤት ወይም በሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ተቀብሎ አከራክሮ ውሳኔ ወይም ፍርድ ሊሰጥ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ መሆናቸውንና መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ፣ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 11(1) እና (3) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ መንግስትና ሀይማኖት በህገ መንግስቱ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ የመንግስት አንዱ ክፍል የሆነው ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪዎች ባላቸው ሀይማኖታዊ በሆነ አለመግባባት ወይም በአምልኮ ስርዓት ጣልቃ ገብቶ ህገ ደንቡን በመተርጎም የሚወስንበት የህግ መሰረት የለውም፡፡

በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን በፍርድ ሊወሰን የማይችለውን ጉዳይ ተቀብሎ አከራክሮ መወሰኑም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ተቀብሎ ማጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

- የሐዋሳ ከተማ ከፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 06162 በቀን 09/02/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 50948 በቀን 19/5/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
- ተጠሪዎች ያቀረቡት ጉዳይ በሚከተሉት ሀይማኖታዊ ስርዓት እና በሚመሩበት ደንብ መሰረት እልባት ከሚያገኝ በቀር በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ አይደለም ብለናል፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

የሰ/መ/ቁ. 69064

ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አክሊለ ገብሬ - ጠበቃ ኪሩቤል ኃ/ማርያም ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- አቶ መለኮት ክንፈሚካኤል - ጠበቃ ፍስሐ ሐጐስ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአደራ የተሰጠ የንግድ ድርጅት ልረከብ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም. የተጻፈ ሆኖ ይዘቱ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 የሚገኝ የቤት ቁጥር 164 የሆነ ንግድ ቤት በባለቤታቸው በአቶ ወልደማሪያም ወልደሚካኤል ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላም ሚስትነታቸውን አረጋግጠው የቤቱ ኪራይ በስማቸው መዛወሩን፣ ከተጠሪ ጋር በነበራቸው ቤተሰባዊ ቅርርብም ድርጅቱን እንዲሰሩበት በአደራ ሰጥተዋቸው ሲሰሩበት ከቆዩ በሁዋላ ድርጅቱን እንዲያስረክቧቸው ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልጸው ተጠሪ የንግድ ድርጅቱን ለቀው ቤቱን እንዲያስረክቡ፣ እስከሚያስረክቡ ድረስ ደግሞ በወር ብር 3,000.00 እየታሰበ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች በአደራ የወሰዱት የንግድ ድርጅት ቤት የሌለ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ክርክሩ መሰረት ያደረገው የአደራ ውሉን መሆኑን በመገንዘብ የንግድ ድርጅቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ በመሆኑ በዚህ ድርጅት ላይ የአደራ ውል ስለመኖሩ መረጋገጥ ያለበት በፍ/ሕ/ቁጥር 1723(1) በተመለከተው ሕጋዊ መስፈርት ነው በማለት እና አመልካች ደግሞ በፍ/ሕ/ቁጥር 1723(1) መሰረት የተደረገ የአደራ ውል ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም በማለት ክሳቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህም አመልካች ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በንግድ ድርጅት ቤት ላይ የሚደረገው የአደራ ውል በፍ/ሕ/ቁጥር 1723(1) ድንጋጌ መሰረት መደረግ ያለበት ነው ተብሎ የተወሰነው ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪም ጥሪ ተድርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደረመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በክሱ የጠየቁት ዳኝነት ቀበሌው በባለቤትነት የሚያስተዳድረውን ቤት የተከራይነት መብት ያላቸው መሆኑንና ይኸው መብት እያላቸው ድርጅቱን ተጠሪ እንዲሰሩበት በአደራ ሰጥተው ተጠሪ ሲሰሩበት ከቆዩ በኋላ እንዲያስረክቧቸው ሲጠየቁ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል መሆኑን፣ ተጠሪ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያደረጉት የአደራ ውል የለም ሲሉ በመከራከራቸው የስር ፍርድ ቤት የአደራ ውል አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም አግባብነት አላቸው ያላቸውን የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌዎችን በመመመርመር ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ኃላፊነት ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና በአዋጅ ቁጥር 408/1996 ተቀርሶ የተሰጠ ሲሆን በአዋጁ 361/1995 በአንቀጽ 41 ስር ደግሞ የስረ ነገር ስልጣናቸው በዝርዝር ተለይቶ ተሰጥቷል፡፡ በሕጉ ተለይተው ከተሰጡት የስረ ነገር ስልጣኖች መካከል ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን አንዱ ስለመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትም የከተማው ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ስለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ክርክሩ መሰረት ያደረገው የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድረውን ቤት የሚመለከት መሆኑ ብቻውን ሁሉንም ቤቱን መሰረት አድርገው የሚቀርቡትን ክርክሮች የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ለማስተናገድ ስልጣን የሚሰጣቸው አይደለም፡፡

በመሆኑም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው? ወይስ የሌላ ግለሰብ? ወይም ድርጅት? የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ወይም የድርጅት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ሕጋዊ ባለቤትነትን አስመልክቶ በአመልካች በኩል ክርክር የቀረበበት ሳይሆን የንግድ ድርጅቱ የሚገኝበት ቤት ባለቤት የሆነው ቀበሌም የክርክሩ ተካፋይ አልሆነም፡፡ የክርክሩ መሰረት የአደራ ውል ሆኖ ተካራካሪ ወገኖች ደግሞ ግለሰቦች ሲሆኑ የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የአደራ ውል አለ? ወይስ የለም? የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ይዞታ ወይም ከባለቤትነት በመለስ ያሉ ሌሎች መብቶች ክርክር ባለመሆኑ የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የቤት የይዞታ ክርክርንና ከባለቤትነት መብት በመለስ ያሉትንና ሌሎች ክርክሮችን በተመለከተ የዳኝነት ስልጣን በሕጉ የተሰጣቸው አደራ ውልንም የሚጨምር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የአደራ ውልን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ ክርክር በከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑም አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 408/1996 ድንጋጌዎች የሚያሳዩት ጉዳይ አይደለም፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን

ከማየቱ በፊት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 05273 ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15309 የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15663 መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በሁለት ግለሰቦች መካከል የአደራ ውልን መሰረት በማድረግ የሚነሳውን ክርክር አይቶ የመወሰን ውሳኔ የመስጠት የሥረ ነገር ስልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. አመልካች ያቀረቡት በአደራ የተሰጠ የድርጅት ቤት ልረከብ ጥያቄን ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድባቸውም ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 54990

ሕዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን -

**ተጠሪ፡-** አቶ ማርቆስ አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አመልካች የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው ለመወሰን የሚያስችል ሥልጣን ያላቸው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ የመሰረተው የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የሰ/ቁ/ 2-61006 አ.አ ተሽከርካሪ በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ግለሰብ ሲሽከረከር ግንቦት 07 ቀን 1999 ዓ.ም. የአመልካች ንብረት የሆነውን የሠ/ቁጥር 4-06809 ኢ.ት. መኪና በመግጨት ጉዳት በማድረሱ መኪናውን ወደ ነበረበት ለመመለስ የወጣውን ወጪ ብር 4,537.50 (አራት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ተከሳሾች በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በአመልካች መኪና ላይ ጉዳት አደረሰ የተባለው የሰ/ቁጥር 2-61006 የሆነውን መኪና ከሕዳር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ለአቶ ሄኖክ ታደሰ በሽያጭ ውል ያስተላለፍኩ ስለሆነ ግጭቱ በደረሰበት ጊዜ የመኪናው ባለንብረት ስላልሆንኩ ልከሰስ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ግጭቱን አደረሰ የተባለውን መኪና በግጭቱ ወቅት በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙ ያልነበሩ በመሆኑ ተጠያቂነት የሌለባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኋላ ተጠያቂ የሚሆነው መኪናውን የገዛው ሰው እንጂ ተጠሪ አይደሉም በማለት የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይኸው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የመኪና ባለቤት የሚታወቀው በሊብሬ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 256/60 አንቀፅ 6(1) እና የደንብ ቁጥር 360/69 አንቀፅ 4 ድንጋጌዎች ያሳያሉ በማለት ተጠሪን ለጉዳቱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይኸው ሰበር ሰሚው ችሎትም ወደ ጉዳዩ ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ክሱ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ሊታይ

የሚገባው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው የሥልጣን ጉዳይ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ መሆኑን በጭብጥነት ይዞ የአሁን አመልካች በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ አካል ነው፣ይህን መሰል ወገን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የሆነውን ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ተመልክተው ለመወሰን ከሕግ የመነጨ ሥልጣን የላቸውም በማለት በየደረጃው የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ከላይ የተጠቀሰው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 50(1) ስለማኅበራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጣቸውን ሥልጣን ያገናዘበ አይደለም፣በሁለቱም አዋጆች ላይ ሥልጣንን በሚመለከት ግጭት አለ እንኳ ቢባል አግባብነት ያለውን አተረጓጎም ልንከተል ይገባል፣ ከዚህ ቅደም ተከተል አንፃር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 361/1995 እንጂ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አይደለም፣ ስለሆነም የሕግ ስህተቱ ይታረምልን በማለት አመልካች በማመልከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል የፍትሐብሔር ሥልጣንን በሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 (1) እና (6) መሠረት በጉዳዩ የተካተተው የገንዘብ መጠን ምንም ይሁን ምን የፌዴራል መንግሥቱ አካል ወይም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት ወይም ማህበር ተከራካሪ የሆነበትን ማናቸውም ጉዳይ ተቀብለው ለማስተናገድ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ይህ አዋጅ በፌዴራሉ መንግስት የወጣ ሲሆን በሌላ በኩል ተመሳሳይ በሆነ አካል (በፌዴራሉ የሕግ አውጪ) የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 ላይ ደግሞ ተከራካሪ ወገን ማንም ይሁን ማን እስከ ብር 5000.00 ሊደርስ የሚችለውን የገንዘብ ክርክር ጉዳይ በአዲስ አበባ ሥር እስከተነሣ ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑ የተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(1) እና (6) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 ይዘትና መንፈስ ጋር ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ይህን ለማድረግም ተገቢውን የሕግ አተረጓጎም ዘዴ መከተል የግድ ይላል፡፡ ከእነዚህም የአተረጓጎም ዘዴዎች ልንከተለው የሚገባው አንዱ፤አንድን ክርክር ያስነሳውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የትኞቹ ፍ/ቤቶች ናቸው? የሚለውን አስመልክቶ በእኩል ደረጃ የሚገኙ ሕጎች /አዋጆች/ በተለያየ ሁኔታ ደንግገው ከተገኙ ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር በኋላ የወጣው ሕግ ከፍተኛና በልጦ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው የትርጉም መርህ ነው፡፡ በመሆኑም አዋጁ ቁጥር 361/1995 ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ጋር እኩል ደረጃ ላይ የሚገኝ ሕግ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 361/1995 በኋላ የወጣ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ቅድሚያ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/1እና 6/ ድንጋጌ መሠረት ይህ መሰል ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥር እንደሚወድቅ እየታወቀ ሕግ አውጪው ዘግይቶ ሥልጣንን በገንዘብ መጠን ወሰን አበጅቶ በሌላ አነስተኛ የፍርድ መድረክ ሥር ቀርቦ እንዲታይ ማድረጉ በክርክር ምክንያት የሚሰጠው ወጪና የሚባክነው ጊዜ ክርክሮች ከያዙት የገንዘብ መጠን ጋር የተመጣጠነ ሊሆን እንደሚገባው ታሳቢ በማድረግ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ሥልጣን ቀንሶ ለመስጠት ሲባል የወጣ ሕግ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተለይም ይህንኑ የትርጉም መስመር ይበልጥ የሚያጠናክረው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ተፈፃሚ

ከሚሆንበት ከድሬዳዋ ከተማ ጋር በተያያዘ የድሬዳዋ ከተማ ቻርተር ለማቋቋም በወጣው በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 41 ሥር ስለ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሲደነግግ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች እና ከኢንሹራንስ ጉዳይ በቀር ሌሎች ግምታቸው እስከ ብር 2500.00 ድረስ ያሉትን ገንዘብ ነክ ክርክሮች ለማየት ሥልጣን ያላቸው የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ከዚህ ቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 ሥር የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን ለመለየት መነሻ ከሆኑት 10 ንዑስ ጉዳዮች መካከል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድና የኢንሹራንስ ጉዳዮች ሊያስነሱ ከሚችሉት የተወሳሰበ የሕግ ጥያቄ አንፃር ሁለቱን ብቻ በመለየት የፌዴራል ሆነው እንዲቀሩ፣ ከሌሎች ጉዳዮች የሚነሳው ክርክር ግን ግምቱ እስከ 2500.00 እስካልበጠ ድረስ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወጥተው በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲታዩ መደረግ በገንዘቡ መጠን ትይዩ የሚታይበትን ፍርድ ቤት እና የክርክር ደረጃ ለመለየት ሆን ተብሎ የወጣ ሕግ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ይህም የሕግ አውጪው ሐሳብ ምን ነበር? የሚለውን የአተረጓጎም መርህ በመከተል ልንደርስበት የምንችለው ድምዳሜ ነው፡፡ ስለሆነም በተመሳሳይ አካል የወጡት ሕጎች ስለፍርድ ቤቶቹ ስልጣን ያስቀመጧቸውን ድንጋጌዎች ከሕጎች አወጣጥ ቅደም ተከተልና ሕጎችን እርስ በራሳቸው አጣጥሞ ከሕግ አውጪው ሐሳብ ጋር በማዛመድ ከመተርጎም የሕግ አተረጓጎም ደንቦች አንፃር ስንመለከተው የአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 ይዘት ከዚሁ ተለይቶ የሚታይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከሥልጣን አደላደል አንፃር የሕግ ጥበቃ የተደረገለት የአሁን አመልካች የፌዴራል መንግስት አካል ወይም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ መሆኑ ብቻ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የማያደርገው ሲሆን ተለይቶ መታወቅ ያለበት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በባሕርይው ሲታይ ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የሚያስነሳ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በመሰረቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስልጣን የተሰጠው ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ተቆርሶ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ የገንዘብ መጠንን መያዙ ብቻ ስልጣኑን ለቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች እንዲሆን የማያደርገው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ከአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀፅ 41 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር በማስተሳሰር ልንገነዘበው የምንችለው ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የሚያስነሳው የሕግ ጥያቄና የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረገው የገንዘብ መጠን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 መሰረት የሚወድቀው በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ሥልጣን ስር ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ክስ ያቀረበው ንብረቱ የሆነው ተሽከርካሪ በተጠሪ መኪና በመገጨት ጉዳት ስለደረሰበት የጉዳቱን ግምት ተጠሪ እንዲተኩለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ግጭቱን ያደረሰው መኪና የራሳቸው ንብረት የነበረ ሁኖ ግጭቱን አደረሰ በተባለት ጊዜ ደግሞ በሽያጭ ወደሌላ ሰው የተላለፈና ገዥው ሲጠቀሙበት በነበረበት ጊዜ በአመልካች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነቱ የማን ነው?፣የሻጩ ወይስ የገዡው?፣አንድ ሰው ከአዋጅ ቁጥር 256/60 እና ከደንብ ቁጥር 360/1969 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች አንፃር ሲታይ የመኪና ባለንብረት ነው የሚባለው መቼ ነው?፣የመኪና ባለንብረት መኪናው ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ ምንድነው? የሚሉትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከካሳ መጠኑ ጋር ተዛምደው የሚነሱት ክርክሮች በባሕርያቸው ሲታዩ ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የሚያስነሱ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም በእጃችን ያለው ጉዳይ ከራሱ ልዩ ባህርይ አንፃር ሲታይ ውስብስብ የሕግ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ስር የሚገኙ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ከብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር)

በታች የሆነውን ማንኛውንም የፍትሐብሔር ክርክር ለመመልከት ስልጣን አላቸው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 50(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተግባራዊ መሆን ያለበት ተከራካሪው ወገን የፌዴራል መንግስት አካል ወይም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ድርጅት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ሳይሆን የተከራካሪ ወገኖች በፌዴራል መንግስት አካልነት ወይም የተመዘገቡ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ የጉዳዩ ልዩ ባሕርይ እየታየ በጉዳዩ ላይ የሚነሳው የሕግ ጥያቄ ውስብስብነት በመመዘኛነት(መለኪያነት) ተይዞ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ላይ ያሉት ተከራካሪ ወገኖች ማንነት እና በክርክሩ የሚነሳው የሕግ ጥያቄን መሠረት በማድረግ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 50(1) አንፃር ተመልክቶ ባለው አግባብ ሊስተናገድ የሚገባው ሆኖ ሳለ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የአመልካችን የፌዴራል መንግስት አካል መሆኑን ብቻ በመመልከት ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር አይውድቅም ያለው የምክንያት ክፍል ተገቢነት የሌለው ቢሆንም የተያዘው ጉዳይ በተለይ ሲታይ ግን ባሕርይው ውስብስብ የሕግ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተገንዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9 እና 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የቀረበው ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ እንጂ በአዲስ አበባ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትርጓሜ ሕጎቹ ከወጡበት ዘመን አንፃርም ሆነ የሕግ አውጪውን ሃሣብ ከመፈለግ አንፃር ሊሰጥ የሚገባውን የሕግ አተረጓጎም ዘይቤ ያልተከተለ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት የምክንያት ክፍል ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ተገቢ ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 12394 በ21/05/2002 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 342 ምክንያቱን ለውጠን ውጤቱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት አፅንተነዋል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ከአመልካች ማንነትና ከገንዘቡ መጠን አንፃር ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ ከአዲስ አበባ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን የሚጀምር ቢሆንም የጉዳዩ ልዩ ባሕርይ ሲታይ ግን በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም ብለናል፡፡ የተያዘውን ጉዳይ አይነት የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 55273

ህዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- አቶ ዘውዱ ግዛው

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አየለች ደስታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በወንዶገነት ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በልጁ ስም የገዛው ቤት በገዢ ስም እንዲዛወርለት ክስ አቅርቦ የወረዳው ፍ/ቤት ቤቱ በገዢ ስም እንዲዛወር ሀምሌ 6 ቀን 2001 ዓ.ም. ውሣኔ ሲሰጥ ውሉ ህጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የተጠሪ ልጅ ወ/ሮ አይናለም እርቅነው ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ አቅርባለች፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በፊት የሰጠውን ውሣኔ በማጽደቅ ሀምሌ 6 ቀን 2002 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በወረዳውና በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪን በችሎት አስቀርቦ በማየትና ተጠሪ በዕድሜያቸው በጣም የገፉ ማየትም ሆነ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ አሮጊት መሆናቸውን በማረጋገጥ እንደዚሁም በውሉ ላይ ያለው የጣት አሻራ ፊርማ የተጠሪ መሆኑን ለማጣራት በውሉ ላይ የተገለጸው ምስክሮች በማጣሪያ ምስክርነት አስቀርቦ በመስማት የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ቀርበው ሣይከራከሩ ቀርበው እንደተከራከሩ በማስመሰል የቤት ሽያጭ ውሉ ተፈጻሚነት አለው በማለት የሰጠው ውሣኔ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1728 ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ ውሉ በመጀመሪያ ለወረዳው ፍ/ቤት ባቀረብኩት ክስ ክርክር ተደርጐበት ቤቱን የገዛሁት አካለ መጠን ባልደረሰ ልጄ ስም ስለነበር በእኔ በአባቷ ስም እንዲዛወር ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ የተጠሪ ልጅ ውክልና ሣይኖራት የክስ መቃወሚያ በህግ ከተፈቀደው ሥርዓት ውጭ አቅርባ ተሰርዞባታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በተከራካሪዋ ያልተነሳ ነገር ራሱ በዝርዝር በማስፈር የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ የተካደበት ነጥብ በሌለበት ሁኔታ ከህግ ውጭ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ጥር 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የወረዳው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ጉዳዩን አይቶ ሲወስን በፍ/ቤት ቀርቤ በቃል ክርክር እንዳመንኩ ተቆጥሮ በመዝገቡ በሌለሁበት ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ሀሰተኛ መሆኑን በውሉ ላይ ስማቸው የተገለጸውን ምስክሮች በማጣሪያ ምስክርነት በመስማት አረጋግጦ የወሰነው ውሣኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያቀረቡት አቤቱታ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተገለጸውን ጭብጥ ለመወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን ማንበብና መጻፍ አለመቻል ተጠሪ ማየት የማይችሉ በእድሜ የገፉ መሆኑንና በውሉ ላይ ስማቸው የተገለጹ ምስክሮችን በመስማት ፍሬ ጉዳይ በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔን ተገቢነት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ለ/ ተደንግጓል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን እንዳለው በክልሉ ህገ መንግስትና በክልሉ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ድንጋጌዎች መኖሩን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከገለጽናቸው የህግ ማዕቀፎች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ተጨማሪ ምስክር መስማትና ተጨማሪ ማስረጃ በመቀበል ማስረጃን በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ በክልሉ ጉዳይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ከማረም ስልጣኑ ውጭ በመውጣት ውሣኔ የሰጠ መሆኑን የሚያሣዩ ናቸው፡፡ የሰበር ሥርዓት በመሠረታዊ ባህሪው ከይግባኝ ሥርዓት የተለየ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በዚህ መዝገብ ተጨማሪ ምስክሮችን በመስማትና ሌሎች ፍሬ ጉዳዮችን በማጣራት ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔ የአመልካቹን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የመስማት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ አመልካች በፍሬ ጉዳይና በማስረጃ ምዘና ሂደት ተፈጽሟል የሚለውን ስህተት በይግባኝ የማሣየት መብቱን የሚያሳጣ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ባየበትና ተጠሪን አስቀርቦ በአካል በአየበት ወቅት ሣይሆን ወሉን በተዋዋሉበት ጊዜ ማየት የተሣናቸው ነበሩ ወይስ አልነበሩም? ተጠሪዋ በወቅቱ ማህይም ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ነበሩ ወይስ አይደሉም? የሚሉት ነጥቦች ግራ ቀኙ

በስር ፍ/ቤት ያልተከራከሩበትንና ማስረጃቸውን አቅርበው ያላሰሙበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውሉ ላይ ተጠሪ ስለመፈረማቸው ወይም አለመፈረማቸውና ስለውል አፈራረም የግራ ቀኙ ማስረጃ አቅርበው ማሰማትና መከራከር ካለባቸው በስር ፍ/ቤት እንጂ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ሊሆን እንደማይገባ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3 /ለ/ ና ከሌሎች የክልሉ የህግ ማዕቀፎች እንደዚሁም ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ በአሁኑ ወቅት ማየት የተሳናትና ማህይም ናት በማለት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ተጠሪ ውሉ ከአመልካች ጋር ተዋዋለች በተባለበት ወቅት ስለነበረው ሁኔታ አመልካች የበኩሉን ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ያልሰጠና ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች የጣሰ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የወንዶገነት ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ውሉን ከአመልካች ጋር በተዋዋሉበት ጊዜ ማየት የተሣናቸው ነበሩ ወይስ አልነበሩም? ተጠሪ ውሉን በሚዋዋሉበት ጊዜ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ነበሩ ወይስ አልነበሩም? ተጠሪ ውሉን ከአመልካች ጋር ተዋውለዋል ወይስ አልተዋዋሉም? በሚሉት ነጥቦች ላይ የአመልካችንና የተጠሪን ምስክሮቻቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግና በውሉ ላይ በምስክርነት ተገኝተው ፈርመዋል የተባሉትን ምስክሮች ቃል በመስማት አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርጌዋለሁ የሚለው ውል ፈራሽ ነው ወይስ አይደለም? ውሉ ፈራሽ ነው የሚባል ቢሆን ውጤቱ ምን ይሆናል በሚሉት ጭብጦች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

የሰ/መ/ቁ. 64845

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሀብቱ ሀጋዚ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- የኮምቦልቻ ግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ - አበበ ዘውዱ ቀረቡ

2- አቶ ዑመር የሱፍ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነችውን ኮድ 4-00242 የሆነች መኪና በሁለተኛው ተጠሪ በመሽከርከር ላይ እያለ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ገልፆ ያቀረበውን የካሣ ጥያቄ በመቀበል ፣ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊዎች ተጠሪዎች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 63,000 /ስልሣ ሶስት ሺህ ብር/ ካሣና ለህክምና የወጣውን ብር 11,277.90/አሥራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ይክፈሉ በማለት የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05073 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አንደኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪና አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ለደረሰው ጉዳት አመልካች በከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት አንደኛ ተጠሪ አመልካች ለህክምና ወጭ ያደረገውን ብር 11,277.90 /አሥራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ብቻ ይክፈል በማለት በመዝገብ ቁጥር 01663 ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረም ነው፡፡

አመልካች ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በከፊል በመሻር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመዘርዘር አመልክተዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ጭብጥ ተመርቶ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት መጥሪያ በመላኩ ተጠሪ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

እኛም በመጀመሪያ በሰበር የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ የይግባኝ ደረጃውን የጨረሰና በሰበር ለመታየት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው በሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከራከሩት ተከራካሪ ወገኖች የሁለት ክልል ኗሪዎች ናቸው፡፡ አመልካች የሐረሪ ክልል ነዋሪ ሲሆን ተጠሪ የኦሮሚያ ክልል የተቋቋመ የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመቀበል አከራክሮ የወሰነው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 4 በተሰጠው

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣኑ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የወሰነው በህገመንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣን ነው፡፡

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የፌደራል ጉዳይ ከሆነና የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣኑ አይቶ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና በተሰጠው ሥልጣን አይቶ ከለወጠው አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በመጀመሪያ ውሣኔው በይግባኝ እንዲታይለት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሣያቀርብና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥበት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዳኝነት አይቶ ውሣኔ የሚሰጠው በይግባኝ ታይተው የመጨረሻ ውሣኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አመልካች የይግባኝ ደረጃውን ሣይጨርስ ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲወሰንለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

**ው ሣ ኔ**

አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረብ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኝ ሣያመለክት በሰበር ችሎት ያቀረበውን አቤቱታ ለማስተናገድ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

የሰ/መ/ቁ. 73549

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች:- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች:-** የዲላ ዩንቨርስቲ - ነገረፈጅ ተዘራ ገዳሙ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** 1ኛ. አቶ የትናየት ጣፋ - የቀረበ የለም

2ኛ. አቶ ዳግም ጫላ - ቀረቡ

3ኛ. አቶ ነጌሳ ጥላሁን - የቀረበ የለም

መዝገቡ ያደረው ለውሳኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪዎች በዲላ ዩንቨርስቲ በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ከTA II ወደ GA II የደረጃ እድገት እንዲሰጠን በተለያዩ የስራ ክፍሎች የተወሰነ ሆኖ ያልተፈጸመ ስለመሆኑ በማመላከት የደረጃ እድገቱ እንዲሰጣቸው እና ክፍያውም ከተወሰነላቸው ቀን ጀምሮ እንዲከፈለን በማለት የቀረበውን ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ክልል የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር በመስማት የደረጃ እድገቱም እንዲሰጣቸው እና ክፍያውም እንዲፈጸምላቸው ውሳኔ ሰጥቷል፣ ይሄው ውሳኔ በክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤትም በመጽናቱ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ የቀረበ ነው፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያላቸውን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን ፍሬ ሃሳቡ:- ተጠሪዎች በክሳቸው የተመለከተውን የደረጃ እድገት እንዲያገኙ በትምህርት ክፍላቸው አማካኝነት ለፋኩልቲው ቀርቦ እና ፋኩልቲውም ለተቋሙ ኘሬዚዳንት አስተላልፎታል፣ ሆኖም ይሄ የደረጃ ዕድገት ሊተገበር የሚችለው የፌ/ሲቪል ሰርቪስ ውክልና ያለው የፌ/ትምህርት ሚንስቴር የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሲያጸድቀው በመሆኑ እና ይሄንን በማጽደቅ ያልመለሰ በመሆኑ የምፈጽመው የእድገት ጥያቄ የሌለ በመሆኑ በኋላ ላይ በትምህርት ሚንስቴር በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት ዩንቨርስቲው የሚያያቸው የእድገት ጥያቄዎች ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አሁን በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ግን ከመመሪያ ውጭ እንድንሰራ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም። ቀደም ሲል በዩንቨርስቲው የተጻፈው ደብዳቤም ቢሆን ተጠሪዎች ወደ ደረጃ GA-I እንዲያድጉ እንጂ ወደ ደረጃ GA-II ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጠት ውሳኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንድታረምልን የሚል ነው።

ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል የስር ፍርድ ቤቶች ይሄንን ጉዳይ አይተው ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆንን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.9 አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በመታዘዙ መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡ የተሰጠውም የመልስ ፍሬ ሃሳብ፡- ለፍርድ ቤቱ ያቀረብነው ክስ በመካከላችን ያለውን ውል ይፈጸም እንጂ ያቀረብነው የደረጃ እድገት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይሄንን የፍታብሔር ክስ መመልከት ይችላል፡ አስፈላጊውን ሰነዶች ፍርድ ቤቱ ከስራ ክፍላችን በማስመጣት መመልከት የሚችል በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችም የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ባቀረበው የመልስ መልስ አመልካች የመንግስት መስሪያ ቤት እንደመሆኑ መጠን የሚተዳደረው በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ይሄንን ክስ የማስተናገድ ስልጣን የላቸውም በሚል ቅሬታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ይሄንን ጉዳይ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ክሱን ተመልክተው ውሳኔ ሊሰጡበት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የደረጃ እድገት እንዲያገኙ በዩንቨርሲቲው የተለያዩ የስራ ክፍሎች የውሳኔ ሃሳብ የተጻጻፉ ስለመሆኑ፣ ሁኖም ግን በስተመጨረሻ ለትምህርት ሚንስቴር የተጻፈ የውሳኔ ሃሳብ ስለመኖሩ እና የትምህርት ሚንስተር የቀረበለትን የደረጃ እድገት በማጽደቅ ያልመለሰ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፣ ሆኖም ግን የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠየቀውን የደረጃ እድገት ጥያቄ የትምህርት ሚንስተር በማጽደቅ አልመለሰልኝም በማለት እጁን አጣጣፎ መቀመጥ የለበትም በማለት የደረጃ እድገቱም ሆነ ክፍያው እንዲፈጸምላቸው ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ ክርክር እና በታች ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ የሚቻለው አከራካሪው ጉዳይ የደረጃ እድገት የሚሰጥበትን አግባብ የሚመለከት እንጂ ተጠሪዎች እንደሚሉት የውል ግንኙነትን መሰረት ያደረገ የፍትሐብሔር ክርክር አለመሆኑን ነው፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ይሄንን የደረጃ እድገት ጥያቄ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመለከት ተጠሪዎች የዲላ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ስለመሆኑ እና መስሪያ ቤቱም የመንግስት መስሪያ ቤት ስለመሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የህግ ማዕቀፍ እንዳግባብነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መመልከት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የህግ ማዕቀፎች አጠቃላይ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ የፌዴራል የመንግስት ተቋም ባጠቃላይ እና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በተለይ የራሱ የሆነ የእድገት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አፈታት እና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚያከናውኑበትን አግባብ ያስቀመጡ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ይሄ ከሆነ ደግሞ የተጠሪዎች የደረጃ እድገት ክርክር በእነዚሁ አዋጆች በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ታይቶ እልባት ከሚያገኝ በስተቀር በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት እና ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ አይተው ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አይኖርም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩ ሲቀርብላቸው ስልጣን እንደሌላቸው በመገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 9፣231/1/ለ/ ፣244/2/ሀ/ መሰረት መመለስ ሲገባቸው ክሱን በመቀበልና በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ባቀረቡት የደረጃ እድገት ጥያቄ ላይ ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ክልል የጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 53540 በቀን 06-12-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 05259 በቀን 08-09-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመደበኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የደረጃ እድገት ጥያቄ በመመልከት ውሳኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡ ይህ ማለት ግን ተጠሪዎች መብታቸውን በህጉ በተቀመጠው ስርዓት መሰረት መብታቸውን ከመጠየቅ ይሄ ውሳኔ አያግዳቸውም፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 68573

መጋቢት 12 ቀን 2004 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ጌታቸው ደያስ ⎫ ወ/ሮ ፈንቱ ተስፋዬ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ፋንቱ ተስፋዬ ⎭

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሩቅያ ከድር

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 የተመለከተውን ድንጋጌ አፈፃፀምና ትርጉም የሚመለከት ሲሆን፤ ዝርዝር ጉዳዩም፣ የአሁን አመልካቾች በሻጭነት ተጠሪ በገዥነት ተሰይመው ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም አድርገውት በነበረው የቤት ሽያጭ ውል የተነሣ ግራ ቀኙ በመ/ቁ. 05508 በሆነው መዝገብ ላይ ውሉ ይፈርሣል ወይስ አይፈርስም? በሚለው ጉዳይ ላይ ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ክሱን ሲመለከት የነበረው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ የሽያጭ ውል ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ካልተደረገ በቀር የፀና ውል ሊሆን አይችልም፡፡ ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.21448 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ትርጉም የሰጠበት ስለሆነና ይህም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት በመ/ቁ. 05508 ላይ ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ሻጭ የነበሩት የአሁን አመልካቾች ከዚህ በፊት በግራ ቀኛችን መካከል ተደርጎ የነበረው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የሽያጭ ውል ከመደረጉ በፊት ወደነበርንበት ቦታ እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን ክስ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መሥርተዋል፡፡

ገዥ የነበሩትም የአሁን መልስ ሰጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ፊት እንዲመዘገብ አለመደረጉ የውሉን መፍረስ የማያስከትል ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 36887 በታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የተወሰነ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባም፤ የፀና ነው ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ በመ/ቁ. 06799 በ19/9/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከዚህ በፊት በመ/ቁ. 05508 በሆነው የግራ ቀኙ ጉዳይ ላይ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በተመሣሣይ ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 21448 በግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረት ነው፡፡ ይህ ውሣኔ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤት በይግባኝም የተሻረ አይደለም አሁን ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበው ክርክር ደግሞ የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተወሰነውን መሠረት በማድረግ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ማድረግ ይቻል ዘንድ ታይቶ እንዲወሰን ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.36887 በ10/4/2001 ዓ.ም የተለየ ውሣኔ ወይም ትርጉም መስጠቱ ለዚህ ለተያዘው ወደነበርንበት እንመለስ ጥያቄ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ሆኖም ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ክርክሩ በይግባኝ ቀርቦለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ከዚህ በፊት የሥር ፍ/ቤት በመ/ቁ.05508 በ23/10/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በጊዜው ትክክል የነበረ ቢሆንም በተመሣሣይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 36887 በታህሣሥ 18 ቀን 2001 ዓ.ም ውል መኖሩ እስካልተካደ ድረስ ውሉ የፀና ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ በዚህ አኳኋን በሰበር ሰሚ ችሎት ተስተካክሎ ከተወሰነ ወይም ከተተረጎመ ይህንኑ ከትርጉም በኋላ የተሰጠን ሁለተኛ ትርጉም መከተል የግድ ስለሆነ ከዚህ በፊት ፈርሷል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የፀና ነው በሚል ተስተካክሎ ሊወሰን ይገባል፡፡ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታረም ቀርቦ የሕግ ስህተት የተገኘበት ውሣኔ  አይደለም የሚል ዳኝነት በማግኘቱ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ሁለቱም ወገኖች በዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር ከዚህ በፊት በሥር ፍ/ቤቶች ያቀረቡትን ክርክር የደገመ እና ያብራራ ከመሆኑ በቀር በይዘቱ የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የሠፈረው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80/3/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም ያለባቸው ውሣኔዎች የሰበር ሥርዓት መዘርጋት እንዳስፈለገበት ዓላማ በሀገሪቱ ሕጐች ወጥ የሆነ አተረጓጐምና የሕግ አፈፃፀም ይኖራቸው ዘንድ ተከታይ በሆነው አዋጅ ቁጥር 454/97 እንደተደነገገው ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ የሀገሪቱ ፍ/ቤቶችና የዳኝነት አካላት በተመሣሣይ ተፈፃሚነት እንዳላቸው ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በሀገሪቱ በየደረጃው የሚገኙት ፍ/ቤቶችና ሌሎች አካላት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ትርጓሜ መሠረት ተመሣሣይ ጉዳዬችን በማየት መወሰን የሚችሉት ተመሣሣይ የሆነው ጉዳይ ክርክር ተደርጎበት ለውሣኔ በደረሰበት ጊዜ ሰበር ሰሚው ችሎት ትርጉም የሰጠበት ሆኖ ከተገኘ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በእጅ የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በመ/ቁ. 05508 በሆነው መዝገብ ላይ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ጉዳይ ክርክር ተደርጎበት ለውሣኔ በደረሰበት ጊዜ በተመሣሣይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ መሆኑን የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተገንዝቦ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 መሠረት ይህንኑ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመከተል ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተመለከተው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም በሌላ ጊዜ የተለየ ትርጉም ለመስጠት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተመሣሣይ በሆነው ጉዳይ በሌላ ጊዜ የተለየ ትርጉም መስጠቱ ቢታወቅ እንኳ የዚሁ በሌላ ጊዜ የሰጠው ትርጉም ተፈፃሚነት ወሰን የሕጉ ትርጉም ከተሰጠ በኋላ በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ ሳይወሰን ለሚነሱ ክርክሮችና ክርክሮች ተደርገው ለውሣኔ በደረሱ ጉዳዮች ላይ የሚገደብ እንጂ በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶችም ሆኑ ሌሎች የዳኝነት አካላት በጎንዮሽም ሆነ በላይኛው የክርክር እርከን ክርክር ተደርጎ በውሣኔ የተቋጨን ጉዳይ ሁሉ እየቀሰቀሱ እንደገና ለማየት በሚያስችል አኳኋን የተቀመጠ ሥልጣን ሰጭ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አልተደነገገም የሕጉ ዓላማም ውሣኔ የሚያሻቸው ጉዳዮች ዓይነት ከዚህ በፊት በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርበው ትርጉም ተሰጥቶባቸው ከሆነ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጐምና አፈፃፀም ማስፈን እንዲቻል በተመሣሣይ ታይተው እንዲወሰኑ ለማድረግ እንጂ ሥርዓቱን አሟጦ በውሣኔ የተቋጩን ጉዳይ ሁሉ እንደገና እየቀሰቀሱ የተረጋጋውን ሁኔታ ለማናጋት ወይም ተከራካሪ ወገኖችን ተገማች ላልሆነ የዳኝነት ሥርዓት ለመጋበዝ ተፈልጐ አይደለም፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዳኝነት ከላይ በዝርዝር እንደሰፈረው በአዋጅ ቁጥር 454/97 የተፈፃሚነት አግባብ ላይ የሰጡት ትርጓሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት በማረም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 106340 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 124793 በ14/7/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06799 በ19/9/2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ በመ/ቁ. 05508 በሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ታየቶ የመጨረሻ ዳኝነት ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ እንደገና ውሣኔውን ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 አንፃር አይቶ ለማረም የሚያስችል ሥርዓት የለም ብለናል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

## ቅጽ 12

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ /ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ውል** | | | | **1** |
| 1. | አግባብነት ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳይኖር የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራን ለመስራት የሚደረግ ውል ህጋዊና አስገዳጅ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ | 54249 | ጌታሁን አበበ ቦጋለ እና ሐሰን ገአስ ሁመድ | ጥቅምት 16/2003 | 2 |
| 2. | በህግ አግባብ ተመዝግቦ የሚገኝ የመያዣ ውል ተጠቃሚ የሆነ ወገን በህግ የተቀመጠው ጊዜ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስለት ከጠየቀ የንብረቱ አስያዥ ፈቃድ መኖሩ ሳይረጋገጥ ውሉ ሊታደስና ሊመዘገብ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058/1/ እና /2,/ 1632/2/ | 40109 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ ተክሌ ዋከኔ | ጥቅምት 01/2003 | 4 |
| 3. | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ በፍርድ ሃይል የኪራይ ውል እንዲዋዋል የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ | 42150 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ አቶ ዳንኤል ካሣ /ሀያ ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 29/2003 | 7 |
| 4. | ውልን በተመለከተ በህግ የተቀመጠውን ፎርም አልጠበቀም በሚል አቤቱታ ለማቅረብ ስለሚችለው ሰው /ወገን/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/ | 47617 | ቄስ ገ/ሚካኤል አለምነው እና ወ/ሮ መልኬ ደምሴ | ህዳር 30/2003 | 14 |
| 5. | የዋስትና ግዴታን ቀሪ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1925/2/ | 49041 | የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና አቶ ኤሣው መዓዛ /ሦስት ሰዎች/ | ህዳር 02/2003 | 17 |
| 6. | ከመኪና ሻያጭ ጋር በተገናኘ ሽያጩ ከመከናወኑ በፊት በነበረ የፍ/ቤት እገዳ መነሻነት ገገርው በባለቤትነት መብቱ መገልገል ሳይችል ቢቀር በሻጩ ላይ የሚኖር ኃላፊነትና የጉዳት ካሣውን በመወሰን በኩል የገገርው ተነፃፃሪ ግዴታ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2341/2/ 2281, 2336, 2329, 2360, 1802, 1790 | 52106 | እነ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ታደሰ አደራ | ህዳር 13/2003 | 20 |
| 7. | እቃን ለመግዛት በጨረታ ማስታወቂያ ያወጣ ድርጅት ተወዳዳሪዎች በጨረታ ላይ ከተነገረው የተለየን ዕቃ በማቅረብ ከተወዳደሩ በኋላ ድርጅቱ ተወዳዳሪ የሆነው አካል በጨረታ ሰነዱ ላይ ሞልቶ ያቀረበውን እቃ መሰረት በማድረግ ውል የተዋዋለ እንደሆነ ይህንኑ ውል ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1695/2/ | 53968 | እነ የምስራቅ ወለጋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ፀጋዬ ነጋ | ህዳር 13/2003 | 24 |
| 8. | በማህበር አባላት ስምምነት የሚወጣ ደንብን አስመልክቶ በማህበሩ አባላት መካከል ብሎም በማህበሩ እና በአባላት መካከል የሚነሱ | 54312 | አቶ ሃይላይ ተክላይ እና | ህዳር 28/2003 | 27 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለመግባባቶችን እልባት ለመስጠት በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ ስለ ውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676/1/ | | ውቁር የጨው አምራቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | | |
| 9. | ውል ጋር በተያያዘ ተዋዋይ የሆነ ወገን ውሉን የፈፀምኩት ተገድጄና ከፍላጐቴ ውጭ ነው በሚል የሚያደርገውን ክርክር ዳኞች (ፍ/ቤቶች) የዚህን ተዋዋይ ወገን እድሜ፣ ጾታ፣ የተዋዋይ ወገኖችን ልዩ ግንኙነት እና አጠቃላይ ተያያዥነት ያላቸው አኳኋኖች ጭምር መሰረት በማድረግ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1706/1/,1678/ሀ/,1809 | 55311 | ወ/ሮ ብርሃኔ አጥናፉ እና ኢንስፔክተር ዮሃንስ ተሲሳ | ህዳር 11/2003 | 31 |
| 10. | ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ከተስማሙ በኂላ አንደኛው ወገን ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ሌላኛው ተዋዋይ ስምምነቱ እንዲፈፀም ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/, 231 | 56368 | ዶ/ር ሰለሞን ነጋሽ እና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ | ህዳር 01/2003 | 37 |
| 11. | የመያዣ ውል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጐ ለማስረጃነት ዋናውን ሰነድ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ የዋናው ሰነድ ግልባጭ ስለመሆኑ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የዋናው ሰነድ ኮፒ እንደ በቂ ማስረጃ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011, 2008, 2009 | 56682 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አንዋር አብዱራህማን /ስምንት ሰዎች/ | ህዳር 14/2003 | 39 |
| 12. | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/ረ/ እና 2023 ለውሃ ፍጆታ ክፍያ ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2023, 2024/ረ/ | 48857 | የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 አስተዳደር ጽ/ቤት | ታህሳስ 12/2003 | 42 |
| 13. | • የተሸጠለትን ነገር የተረከበ ገገር የሽያጩን ዋጋ ወዲያውኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ገዥ ለሻጭ /በሽያጭ/ ለማስረከብ በውል ከተስማማው መካከል የተወሰነውን ክፍል ያስረከበ መሆኑና ሻጭም በተረከበው መጠን ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑ ለውሉ መፍረስ በቂ ምክንያት ሊሆን ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2278 | 49635 | ሂጦስ የገበሬዎች የህብርት ስራ ማህበር እና የምስራቅ ዱቄት ፋብሪካ | ጥር 23/2003 | 46 |
| 14. | አንድን ዕቃ በውል የተረከበ ሰው የተረከበው ዕቃ ጉድለት አለው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2291, 2292, 2298/1/ | 55229 | ወ/ሮ መሃዳ ይመር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ | ጥር 09/2003 | 50 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 15. | • የግንባታ ሥራን ለመንግስት ለመስራት ጨረታውን ያሸነፈ ሥራ ተቋራጭ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሥራ ተቋራጭ /ሰው/ በህጋዊ መንገድ ሊለቀቅ ወይም ሊያስተላልፍ የሚችልበት አግባብ<br>• ከአሰሪ ጋር ያልተደረገና ከሥራ ተቋራጭ ጋር የተደረገ የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውልና የሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3202/1/ እና /2/ 3205, 3206, 3244/1/, 2107 | 56252 | ተስፋዬ አበበ ሥራ ተቋራጭ<br>እና<br>ማዕረት ወርቁ ሥራ ተቋራጭ | ጥር 24/2003 | 53 |
| 16. | • ውሎችን ህገ ወጥ ናቸው ወይም በህግ የተቀመጠውን መስፈርት አላሟሉም (Unlawful contracts or illegal contracts) በሚል ለመለየት የሚቻልበት አግባብ እና የሚያስከትሉት ውጤት<br>• በመያዣ ተይዟል በሚል ባለገንዘብ በሆነ ባንክ በሐራጅ ንብረቱ የተሸጠበት ሰው ባንኩ ንብረቱን ለመሸጥ መብት የለውም በሚል /ውሉ እንዲፈርስ/ የሚያቀርበው የመቃወም አቤቱታ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 446,447<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6<br>አዋጅ ቁ. 216/92 | 43226 | ጌታ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | የካቲት 7/2003 | 58 |
| 17. | የከተማ ቦታ ውልን መሰረት በማድረግ በሊዝ የሚሰጥበትና ውሉ ሊቋረጥ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 15/1/ /ለ/, 16 | 54596 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ<br>እና<br>ወ/ሮ ላቀች መንግስቴ | የካቲት 09/2003 | 65 |
| 18. | ውልን መሰረት በማድረግ ቀብድ የተቀበለ ወገን የቀብዱን አጠፌታ በመክፈል ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1885/2/ | 56794 | አቶ ሳህሉ ሙሉጌታ<br>እና<br>እነ አቶ ሰለሞን ኤፍሬም /ሦስት ሰዎች/ | የካቲት 07/2003 | 71 |
| 19. | • ተዋዋይ ወገኖች ውል ባለመፈፀሙ አንዳቸው ለሌላቸው መቀጮ /ገደብ/ እንዲከፈል በማለት የሚደርሱበት ስምምነት ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በውል በተወሰነ የገንዘብ ቅጣት ላይ የሚታሰብ የወለድ ክፍያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1891, 1892/1/, 1889 | 58258 | ወ/ሮ ዮርዳኖስ ሃጐስ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀይማኖት ተፈራ | የካቲት 21/2003 | 75 |
| 20. | የእውቀት ሥራ /ግልጋሎት/ ውልን አሰሪ የሆነ ወገን በተናጠል ለማቋረጥ የሚችለው ባለሙያው ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለአሰሪው ከማስረከቡ በፊት ስለመሆኑና ባለሙያው ሥራውን አስመልክቶ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው የሙያውን ደንቦች በመጣስ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2637/2/, 2636/2/ና/1/ | 60469 | ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ<br>እና<br>ሙሉ አለም የስራ አመራር አማካሪዎች | የካቲት 21/2003 | 79 |
| 21. | ከመንግስት አስተዳደር መ/ቤት ጋር የሥራ ውል | 60951 | የኢትዮጵያ | ግንቦት 19/2003 | 83 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያደረገ ወገን እንደውሉ ለመፈፀም ባልቻለ ጊዜ የአስተዳደር መ/ቤቱ ተዋዋዩ ለውል ማስከበሪያ (contract security) በሚል ካስያዘው ገንዘብ ላይ ውሉ ባለመፈፀሙ የደረሰበትን የጉዳት ኪሣራ መቀነስ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 430/97 አንቀጽ 43<br>የመንግስት የግዢ መመሪያ ቁ. 117/5/ /ሀ-ሐ/ | | መንገዶች ባለስልጣን እና ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | | |
| 22. | • በሃዋላ የተላከን ገንዘብ ባንክ ለዕዳ ማስመለሻ በሚል ያለፍርድ መያዝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• በፍትሐብሔር ግንኙነት እዳን ለማቻቻል ስለሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1838/1/, 1840, 1841 | 64203 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ መሐመድ ሙሳ /አራት ሰዎች/ | ግንቦት 15/2003 | 87 |
| 23. | አንድን ስልጠና በአሰሪው ትብብር በውጪ አገር ተከታትሎ በምትኩ አገልግሎት ለመስጠት የተስማማ ሠራተኛ አስቀድሞ በውል የገባውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ሌላ /ተጨማሪ/ ስልጠና መጀመሩ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚያሳይና በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 | 46574 | ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ እና እነ ዮናስ ካሣ /ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 09/2003 | 90 |
| 24. | • ከመኪና ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ ከመኪናው ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ለገዢ አሟልቶ ያስረከበ መሆኑ ከተረጋገጠ ገዢ ስመ ሃብቱ በስሜ አልተዛወረም በሚል ምክንያት ብቻ ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ከመኪና ጋር በተገናኘ ስመ ሃብቱን ለማዞር አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ ስም እንዲዛወርለት ጥያቄ አቅርቦ መብቱ ሊረጋገጥለት ያልቻለ ሰው በሚመለከተው አካል ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ | 56569 | አቶ ዳዊት አሰፋ እና አቶ ተሻለ ደስታ | መጋቢት 23/2003 | 9.3 |
| 25. | • በጽሁፍ እንዲደረጉ በህግ የተደነገጉ የውል አይነቶች ህጋዊና የተሟሉ ናቸው ለማለት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች /መስፈርቶች/<br>• የቤት ሽያጭ ውል ምስክር ሳይኖርበት በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመደረጉ ብቻ ህጋዊና የሚፀና ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723/1/, 1727/2/, 2877 | 57356 | ወ/ሮ መሠረት በቀለ እና ወ/ሮ ኤልሳ ሶሞኔላ | መጋቢት 22/2003 | 98 |
| 26. | ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተያያዘ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለባለቤት ወይም ለወኪሉ ስለመሆኑ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17, መመሪያ ቁ. 1/97 | 55359 | አቶ ተድላ ማሞ ጌታቸው እና እነ አቶ ፍስሐ ሱመር /ሁለት ሰዎች/ | ሚያዝያ 21/2003 | 101 |
| 27. | • ተዋዋይ ወገኖች ውል ለማድረግ ነፃ ቢሆኑም ህግ የወሰናቸውና የከለከላቸውን ነገሮች ባለመገንዘብ /ባለማክበር/ የሚደረጉ ውሎች የማይፀኑ እና የማይፈፀሙ ስለመሆናቸው<br>• በመንግስትና በህዝብ መሬት ላይ ግለሰቦች አንዱ ሰጪ ሌላው ደግሞ ተቀባይ በመሆን የባለቤትነት መብት ሊመሰርቱ የማይችሉ ስለመሆኑ | 58157 | አቶ ዮሐንስ ታደሰ እና ወ/ሮ አማረች መንገሻ | ሚያዝያ 06/2003 | 107 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716 | | | | |
| 28. | ህጋዊ ባልሆነ የቤት ሽያጭ ውል አማካኝነት የተሰጠን ገንዘብ ለማስረዳት ህጉ የደነገገው ልዩ የማስረጃ አይነት የሌለና በማናቸውም ማስረጃ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472, 2001, 2019, 1808/2/, 1815, 2162, 2164 | 58636 | እነ አቶ ተሾመ ካሣ<br>እና<br>አቶ ቤዛ ኩሉ አዳም | ሚያዝያ 19/2003 | 111 |
| 29. | • የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች በመያዣ (pledge) ለሌላ ሰው ተሰጥተዋል ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ እና ውጤቱ<br>• መኪና በመያዣነት ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2825, 2832, 2830, 1186/2/, 2828, 1727, 2930, 2027, 2028, 2054 | 43582 | ራፒድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ድርጅት<br>እና<br>ኦርቢስ ንግድና ቴክኒክ ክፍል ሊሚትድ | ሰኔ 28/2003 | 114 |
| 30. | ጥሬ ገንዘብን በአደራ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ገንዘቡ በአደራ መልክ መሰጠቱን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችል ማስረጃ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2742 2782 2779 | 60204 | አቶ ታደሰ ደምሬ<br>እና<br>አቶ ጌታሁን ለቻሞ | ሰኔ 14/2003 | 120 |
| 31. | አንድን ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የሰጠ የመንግስት መ/ቤት በራሱ ጥፋት ጉዳት አድርሶ ከሆነ ወይም የሥራ ተቋራጩን ሥራ መደበኛ አፈፃፀም ከባድ ያደረገበት እንደሆነ ለሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የመክፈል ኀላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3259 | 61110 | አል ናይል ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን | ሰኔ 28/2003 | 124 |
| 32. | የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመላለስና የከፈልኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል ክስ መስርቶ ፍ/ቤት ጥያቄውን በህግ ፊት የሚፀና ውል የለም በማለት ውድቅ ያደረገበት ወገን ያለአግባብ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑና በመጀመሪያው ክስ ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበት ነው ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815, 1880/2/, 2001-2019, 2162, 2164<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216/2/3/ | 62134 | እነ ጣና ወ/ሰማያት<br>እና<br>ወ/ሮ አልማዝ አስጋሽኝ | ሰኔ 28/2003 | 132 |
| 33. | • የጠፋ ዕቃን ሳገኝ ወይም ሌላ ነገር ለፈፀመ ሰው ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ በተለጠፈ /በተነገረ/ ማስታወቂያ ወይም በአደባባይ ሊታወቅ በሚችል ሌላ አይነት ማስታወቂያ መሰረት ዕቃውን አግኝቶ የመጣ ወይም የተባለውን ሥራ የፈፀመ እንደሆነ የተስፋ ቃሉን የሰጠው ሰው የተገለፀውን ሽልማት /የገባውን ቃል/ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በውል የተገባ ግዴታ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከር ነው ለማለት ተዋዋይ ወገን ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ሊፈጽመው የማይችለው ግዴታ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>• በአንድ ከተማ የሚገኝና መጠኑ ተለይቶ የታወቀ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሽልማት መልክ | 62146 | ወ/ሪት ፍሬወይኒ ቴዎድሮስ<br>እና<br>ተርካንሬ ፕሮሞሽንና የማስታወቂያ ስራ ድርጅት | ሐምሌ 12/2003 | 135 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለመስጠት በውል የተገባ ግዴታ ሊፈፀም የማይችል ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1741-1762, 1714, 1711, 1736, 1734, 1689 | | | | |
| 34. | የደንበኛን ጉዳይ /ክርክር/ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና የውክልና ስልጣን የተሰጠው ጠበቃ በውል የገባውን ግዴታ በተገቢው ጊዜና ትጋት ለመወጣት አለመቻል በኃላፊነት የሚያስጠይቅና ለቅጣት የሚዳርግ ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2//ለ/ 3<br>አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 24/3/ /ለ-3/ | 66210 | አቶ ተስፋዬ ጉላ<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር | ሐምሌ 29/2003 | 140 |
| 35. | • ከቤት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ የስም መዛወር የሚፈፀመው በመንግስት አስተዳደር ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽመው የማይችልና ከህግ ወይም ከውል ይመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ስለመሆኑ<br>• የስም ይዛወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ | 33945 | አቶ ሳልህ ሁሴን<br>እና<br>ደግፌ ደርቤ | ጥቅምት 20/2001 | 143 |
| 36. | ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2782,2800,2802,2472 | 64887 | አቶ አደም የሱፍ<br>እና<br>አቶ አብዱሠላም ሙሐመድ | ሐምሌ 29/2003 | |
| 37. | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810/2/ ላይ የተመለከተው የይርጋ ገደብ ተፈፃሚ የሚሆነው ውል በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ ማጣት የተነሳ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810 | 48012 | አቶ ኡመር ከድር<br>እና<br>አቶ በዳዳ ሰቦቃ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 03/2003 | 147 |
| 38. | ተዋዋይ የሆነ ወገን ወይም ጥቅም ያለው ማናቸውም ሰው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጪ ነው ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው ወይም ለውሉ አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ ምክንያት በማቅረብ ወሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/ | 43379 | አበበ አበጋዝ<br>እና<br>ጥሩነሽ ተክሌ | ታህሳስ 25/2003 | 150 |
| 39. | የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በግዴታ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2330, 2329, 1778/ | 44873 | አቶ ሰሚር ሱሩር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ስንዱ ዱባለ | ጥር 13/2003 | 153 |
| 40. | • በብድር ከተወሰደ ገንዘብ አከፋፈል ጋር በተያያዘ ብድር መክፈያ ጊዜው የዘገየ እንደሆነ ለአበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፈለው ህጋዊ ወለድ ብቻ ስለመሆኑና ከዚህ ህጋዊ ወለድ በተጨማሪ በመቀጫ መልክ ለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2006/2/, 2005/1/, 2489, 1889 | 59882 | ወ/ሮ አሰገደች ዘርጋው<br>እና<br>አቶ አየለ ንዳኔ | የካቲት 21/2003 | 157 |
| | **ወንጀል** | | | | **161** |
| 41. | • ከ13 ዓመት እስከ 18 ዓመት ድረስ ባለው የዕድሜ | 46412 | የሐረሪ ክልል | ጥቅምት 30/2003 | 162 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክልል ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>• ድርጊቱን የፈፀመው ሠው ዕድሜ በዚሁ የእድሜ ክልል መገኘት የወንጀል ተጠያቂነቱን የማያስቀር ስለመሆኑ<br>የወ/ህ/ቁ. 626/1/, 211/1/, 48-56 | | ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>ቦና አህመድ<br>አሚን | | |
| 42. | ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ሰዎችን ወደ ውጪ አገር በመላክ ወንጀል የተከሰሰን ሰው ጥፋተኛ ነው ለማለት እና ቅጣት ለመጣል የሚቻልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 598/1/ /2/ | 54839 | አቶ ኢምራን<br>ጉደሣ አብዲ<br>እና<br>የፌዴራል<br>ዓቃቤ ሕግ | ጥቅምት 30/2003 | 165 |
| 43. | በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ ምንዛሪን በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከአገር ይዞ ለመውጣት መሞከር የሚያስከትለው ኃላፊነት /ውጤት | 47935 | የኢትዮጵያ<br>ገቢዎችና<br>ጉምሩክ<br>ባለስልጣን<br>እና ወ/ሮ<br>እየሩሳሌም<br>ወንዴ | ህዳር 30/2003 | 169 |
| 44. | ከዋስትና መብት ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ብዛትና ከባድነት መነሻ ሊያደርጉ ስለመቻላቸው<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.67/ሀ/ | 59304 | እነ አቶ<br>አያሌው ተሰማ<br>/ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>የኢትዮጵያ<br>ገቢዎችና<br>ጉምሩክ<br>ባለስልጣን | ህዳር 15/2003 | 171 |
| 45. | በወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብት እንዲከበርለት ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ትዕዛዙ ተነስቶ ዋስትናውን ሊከለከል ስለመቻሉ<br>የወ/መ/ሥ/ህ/ቁ. 74 | 59855 | ወ/ሮ ሊዊዛ<br>ሮርቤታ<br>እና<br>አቃቤ ሕግ | ህዳር 28/2003 | 174 |
| 46. | በሚያሽከረክረው መኪና ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ የነበረ ሰው ወድቆ ለህልፈተ ህይወት የተዳረገበት ሾፌር በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ | 52075 | አቶ ጌቱ<br>ብርሃኑ<br>እና<br>የፌዴራል<br>ዓቃቤ ሕግ | ታህሳስ 26/2003 | 177 |
| 47. | • በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርድ የተሰጠበት ተከሳሽ የሚያቀርበው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ<br>• በይግባኝ ደረጃ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ የጥፋተኝነት ፍርድ እንደመጨረሻ ውሣኔ ተቆጥሮ በሰበር እንዲታረም ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/, 197-202, 160, 164, 163, 195/2/ /ሀ/<br>የወንጀል ህግ ቁ. 522, 526<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 9, 10<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ | 57632 | ሰማኸኝ በለው<br>እና<br>የፌዴራል<br>ዓቃቤ ሕግ | ታህሳስ 25/2003 | 179 |
| 48. | ዓቃቤ ሕግ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረና ምርመራ የተደረገበትን ሰው ተከሳሽ ከሚሆን ይልቅ ምስክር ቢሆን የተሻለ ነው ብሎ ካመነ ይህንኑ | 57988 | ዮርዳኖስ አባይ<br>አሰፋ<br>እና | ጥር 10/2003 | 196 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለማድረግ የሚከለክለው ህግ የሌለ ስለመሆኑ | | የፌዴራል<br>አቃቤ ሕግ | | |
| 49. | • ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች<br>• የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ በሆነ ወገን ላይ ቅጣት ሊጥሉ ስለሚችሉበት ሥርዓት /አግባብ/<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136/1/, 148/1/ ,149 | 47755 | የፌዴራል አቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ ሚፍታህ ኑረዲን | ግንቦት 05/2003 | 198 |
| 50. | • በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የወንጀል ቁጥር 540 ወይም 541ን መሰረት በማድረግ ጥፋተኛ አድርጐ ለመወሰን የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀምን እንዲሁም መነሻ ሁኔታዎች በአግባቡ መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>• የወንጀል ህግ ቁጥር 78 "ን" ተፈፃሚ ለማድረግ ሊሟሉ ስለሚገባቸው መስፈርቶች<br>• ህጋዊ መከላከልን በማለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ በወንጀል ህግ ቁጥር 541 የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 78, 540, 541 | 57446 | ሃለቃ<br>ገ/እግዚያብሔር ኃይሉ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ | ግንቦት 19/2003 | 202 |
| 51. | የወንጀል እና የፍ/ብሔር ክሶች ተጣምረው ሊታዩ የሚችሉት በወንጀል ህግ ቁጥር 101 አግባብ ብቻ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 101 | 59045 | የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዓ/ሕግ<br>እና<br>እነ አቶ ጌታቸው አስራት<br>/አምስት ሰዎች/ | ግንቦት 16/2003 | 106 |
| 52. | በወንጀል ድርጊት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ሰው ከጉዳቱ በኋላ ተጐጂውን ወደ ህክምና ቦታ የወሰደው መሆኑ ብቻ በድርጊቱ የተፀፀተ መሆኑን ያሳያል በሚል ቅጣትን ከመነሻው በታች በመወረድ ቀልሎ እንዲወሰን ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 543/3/, 59/1/, 575/2/, 82/1/<br>የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ. 279/56 አንቀጽ 35 | 62332 | አቶ ዘለቀ ካሣዬ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | ግንቦት 29/2003 | 211 |
| 53. | በወንጀል ተከስሶ የቀረበ ተጠርጣሪ በፍ/ቤት በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተጣለበት በኋላ በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የማይችል ስለመሆኑ | 63741 | አቶ መሐመድ ሰኢድ አሊ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | ግንቦት 15/2003 | 213 |
| 54. | ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ እውነታ የተጠቀሰውን ወንጀል የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ጉዳይ የህግ ጭብጥ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊመረመር የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 675/1/ | 64813 | ያሲን አሕመድ መሐመድ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | ግንቦት 17/2003 | 215 |
| 55. | • የመወሰን ስልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ ያላቸው ሰዎች /ሰራተኞች/ በወንጀል ጉዳይ በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ<br>• የተቀጠረበትን የሙያ ሥራ በጥንቃቄና በአግባቡ አለመፈፀም በአዋጅ ቁ. 214/74 በስልጣን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ያስጠይቃል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ | 43049 | አረጋኸኝ መርዕድ<br>እና<br>የፌ/ስ/ፀ/ሙ/ኮ/ ዓ/ህግ | ግንቦት 26/2002 | 217 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 56. | አንድ ተከሳሽ በወንጀል ህግ ቁጥር 427/3/ መሰረት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በሚል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 427/1/, /3/ | 55047 | አቶ ነብይ በድሩ ሽፋ<br>እና<br>የፌዴራል ሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽን ዓ/ህግ | መጋቢት 05/2003 | 221 |
| 57. | ፍ/ቤት በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው በተመለከተ አስቀድሞ የፈቀደውን የዋስትና መብት በራሱ አነሳሽነት ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት አዲስ ነገር ተከስቷል ብሎ ካመነ ዋስትናው እንዲነሳ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 74 | 61275 | አቶ ኤልያስ ገረመው<br>እና<br>የኢት/ገ/ጉ/ባ/ዓ/ህግ | ሚያዝያ 18/2003 | 226 |
| 58. | • በከባድ የሰው መግደል ወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ ተከሳሽ ስለሚጠየቅበት አግባብ<br>• የተመሰረተበት ክስ በዓቃቤ ሕግ በኩል እንደክሱ አመሰራረት ያልተረጋገጠበት ቢሆንም ተከሳሹ የቀረበው ማስረጃ ከቀረበበት ክስ ባነሰ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተከሳሹ በነፃ እንዲሰናበት ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር /የሌለ/ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ /ሀ-ለ/, 539/1/ /ሀ/, 84, 86, 40, 445, 88<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 40, 445 | 45595 | የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>እነ ኢዮስያስ አበራ ገ/ሚካኤል /አምስት ሰዎች/ | ሰኔ 17/2003 | 229 |
| 59. | • በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ተከሳሽ ላይ የሚጣለውን የቅጣት አይነትና መጠን ለመወሰን ፍ/ቤቶች በህጉ ውስጥ ተካትተው የሚገኙትን የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችሉበት አግባብ<br>• የሞት ቅጣት ሊተላለፊ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 117, 32/1//ሀ-ለ/, 539/1//ሀ/, 84/1//ሀ-ሠ/, 183, 179, 180, 182, 88/2/, 87/1/ | 47831 | እነ መስታወት ጌታነህ /አራት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ህግ | ሰኔ 03/2003 | 240 |
| 60. | "የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት" በሚል በወንጀል ህጉ ውስጥ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ለማቋቋም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን /ያለመኖሩ/ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 693/1/ | 67947 | አቶ አዱኛ አንበሎ<br>እና<br>የፌዴራል አቃቤ ህግ | ሰኔ 15/2003 | 246 |
| 61. | • በህጉ በጠቅላላ የቅጣት ማቅለያነት የተመለከተን ምክንያት ወንጀሉን ለማቋቋም የቀረበ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያነት ሊጠቀሙበት የማይችሉ ስለመሆኑ<br>• ፍርድ ቤቶች በህጉ ለዳኞች የሚሰጠውን አመዛዝኖ ቅጣትን የመወሰን ስልጣን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሰረታዊ መርሆዎች ሊጥሱ የማይገባ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 82/2/, 189,86, 180, 179, 182, 184, 82/1/, 88/2/ | 59356 | የፌዴራል ዓ/ህግ<br>እና<br>በሪሁን ፍቃዱ | ሰኔ 03/2003 | 251 |
| 62. | በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ ከቀረበበት ሰው ጋር በተገናኘ በሚካሄድ የቅድመ ክስ ሂደት ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት እንደቀረበው የወንጀል አይነት በመመርመር ወደ ዋናው ክስ የመስማት ሂደት | 57938 | እነ አቶ አደም አብዱ /ሁለት ሰዎች/<br>እና | ሐምሌ 14/2003 | 256 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲገባ በሚል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 419<br>አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36/1//2/ | | የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ | | |
| 63. | • በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ በእስራት ሊያስቀጣ የሚችል በሆነ ጊዜ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/<br>አዋጅ ቁ. 239/93 አንቀጽ 2<br>አዋጅ ቁ. 236/93<br>የወንጀል ህግ ቁጥር 676/1/ | 63344 | የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/የሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽን<br>እና<br>እነ ላሉ ሰይድ አከልታ | ሐምሌ 28/2003 | 258 |
| 64. | ውልን /ስምምነትን/ መሰረት ባደረገ ግንኙነት አንድን ንብረት ወስዶ በውሉ መሰረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል የወንጀል ክስ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 23/2/, 24, 57, 58 | 65054 | ብሩክ ሚካኤል<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ህግ | ሐምሌ 14/2003 | 261 |
| 65. | • ዓቃቤ ህግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ<br>• አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር የሃሳብና የህግ ሁኔታዎችን መተላለፍ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112<br>የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ 23/2/ | 57644 | መ/ር አወት ተካ<br>እና<br>የትግራይ ዓ/ህግ | ሐምሌ 25/2003 | 264 |
| 66. | ተጨማሪ ማስረጃን ከመቀበል ጋር በተያያዘ በወንጀል ህግ ቁጥር 143/2/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ሲያመን ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚችል ስለመሆኑ በፈቃጅነት (permissive) የተቀመጠ እንጂ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ስላለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 143/2/ | 66767 | አቶ ተስፋዬ ተሾመ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ህግ | ሐምሌ 28/2003 | 269 |
| 67. | በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የጤና ችግር ከዋስትና መብት አኳያ ሲታይ ስላለው ህጋዊ ጥበቃ | 68407 | ወ/ሮ ውልታ ደሳለኝ<br>እና<br>የኦሮሚያ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ | ሐምሌ 14/2003 | 273 |
| 68. | • ወንጀልና የወንጀል ቅጣት የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>• የጉምሩክ ህግን በመተላለፈ ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች | 48956 | እነ ወ/ሮ ፍኖተ ፃድቅ አበራ<br>እና<br>የጉምሩክ ዓ/ህግ | መጋቢት 10/2002 | 276 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | /ተከሳሾች/ ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በእያንዳንዱ ጥፋተኛ ላይ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 41, 32/1/ሀ/<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 73/1/<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/ | | | | |
| 69. | አንድ ሰው በወር ደመወዝ ከሚያገኘው ገቢ ውጪ ሌላ ህጋዊ የገንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብትና ንብረት ባለቤት መሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 419 | 58514 | አቶ ሃንካራ ሃርቃ ሃያሞ<br>እና<br>የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ ህግ | ጥር 09/2003 | 278 |
| 70. | የንግድ ፈቃድ መብትን መጣስ በአዋጅ ቁ. 501/98 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነትን ስለሚያስከትልበት አግባብ | 69899 | እነ ዮሴፍ ሀይሉ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | ሐምሌ 29/2003 | 280 |
| 71. | በአሽከርካሪነት ሥራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በሌላ ሰው ላይ የሞት አደጋ ያደረሰ ሰው በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ የሚጠየቅ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 543/1/, /2/, /3/, 59/1/<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113 | 55649 | ኤልያስ ዲጋ<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ሕግ | መጋቢት 06/2003 | 286 |
| 72. | የወንጀል ክስ ቀርቦ ተከሳሹ እንዲከላከል በሚል በፍ/ቤት ብይን የተሰጠ መሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ እንደተሰጠበት በመቁጠር የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ | 59537 | አነዚር ኢብራሂም<br>እና<br>የቤ/ጉ/ክ/ስ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን | ሚያዝያ 19/2003 | 291 |
| 73. | አንድ የወንጀል ድርጊት በእርግጥም ተጀምሯል /ተፈጽሟል/ ለማለት የሚቻለው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደታሰበለት ግብ ለማድረስ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲቻል ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ ቁ. 27/1/ 540 555/ሀ//ለ/ | 63727 | ፋሲል ታምራት<br>እና<br>የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሳሽ | ሰኔ 13/2003 | 293 |
| **ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት** | | | | | **296** |
| 74. | በፍ/ቤቶች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ትዕዛዝ የተሰጠው ተከራካሪ ወገን ጥሪ ተልኮለት ቀርቦ መልሱን አልሰጠም በሚል ምክንያት ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን የሚሰጥ ትዕዛዝ በክርክሩ ውስጥ ያሉ ሌሎች ወገኖችን መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግን የሚጥስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70, 41/3/, 199 | 53844 | የወ/ሮ ቅጅነሽ አነስታል ወራሾች /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ስራና ከተማ ልማት ቢሮ | ጥቅምት 18/2003 | 297 |
| 75. | በፍርድ ለሌላ ሰው የተላለፈ ንብረት የእኔ ነው በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 421, 455 | 50835 | እነ አቶ ምናሴ ኢትሶ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 16/2003 | 300 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እና<br>ወ/ሮ ፋንታዬ<br>ተረፈ | | |
| 76. | • የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንደ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ ሁልጊዜ ጥብቅ የሆነ የሙግት ሥርዓትን ተከትሎ ጉዳዩን ማየት የሌለበት ስለመሆኑ<br>• የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን ለማየት ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ያህል ሊወስን ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 318/5/, 317/1/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3345 | 52942 | አቶ ገብሩ ኮሬ<br>እና<br>አቶ አመዲዮ<br>ፌዴሬቼ | ጥቅምት 18/2003 | 303 |
| 77. | ተከራካሪ ወገኖች የሚሟገቱበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ይህ እንዲፈፀም ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/ | 48608 | ወጋገን ባንክ<br>አ.ማ<br>እና<br>አቶ ሃብቶም<br>ረዘነ | ህዳር 02/2003 | 306 |
| 78. | • ተከራካሪ ወገኖች እንዲሰሙላቸው የሚቆጥሯቸው የሰው ማስረጃዎች የማስረዳት ብቃት ሊታወቅ የሚችለው ቃላቸው ከተሰማ በኋላ ስለመሆኑ<br>• የተቆጠሩ ማስረጃዎች የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ (relevancy and admissibility) ካልከለከለ በስተቀር በዝርዝር ሊሰሙ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• በሰው ማስረጃነት የተቆጠረ ኦዲተር በኦዲት ሪፖርት ላይ ከተመለከተው ውጪ /የተለየ/ ሊያስረዳ አይችልም በሚል ምክንያት ሊሰማ አይገባም ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ | 49502 | የኢትዮጵያ<br>የእህል ንግድ<br>ድርጅት<br>እና<br>እነ መርዕድ<br>ተፈራ /ስድስት<br>ሰዎች/ | ህዳር 01/2003 | 309 |
| 79. | • መጥሪያ በጋዜጣ ጥሪ ሊደረግ የሚገባው ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመጥሪያ አላላክ መንገዶች ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ከተከናወኑ በኋላ ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በአግባቡ ደርሷል ለማለት የሚላክለት ሰው ስም በተሟላ ሁኔታ ተገልጾ መላክ ያለበት ስለመሆኑ<br>• መጥሪያ በህጉ አግባብ እንዲደርሰው ሳይደረግ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን ትዕዛዙ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 94-110, 7870/ሀ/ | 53113 | እነ ወ/ሮ<br>አበበች በጅጋ<br>/ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ዶ/ር ተስፋዬ<br>አካሉ | ህዳር 03/2003 | 311 |
| 80. | በዋናው ክርክር ላይ በተሰጠ ፍርድ መብቱ የተነካበት ሰው በፍርድ አፈፃፀም ወቅት መብቱ ከተነካበት ሰው በተለየ ሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ማቅረብ የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 419 | 53607 | የምጥን መንደር<br>መኖሪያ ቤቶች<br>የህብረት ስራ<br>ማህበር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ባየች<br>አይገምት<br>/ሦስት ሰዎች/ | ህዳር 14/2003 | 315 |
| 81. | አስቀድሞ የተሰጠን ውሣኔ ለማስነሳት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ እንደሆነ ባልተካፈለበት ክርክር የተሰጠውን ፍርድ መቃወም የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 41 | 42714 | የአዲስ አበባ<br>ከተማ<br>አስተዳደር<br>የፍትህና ህግ<br>ጉዳዮች ቢሮ<br>እና እነ | ህዳር 08/2003 | 318 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | የሸቀጣ ሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት /ሦስት ሰዎች/ | | |
| 82. | ከሳሽ የሆነ ወገን ያቀረበው ክስ ውድቅ በተደረገበት ሁኔታ ተከሳሽ የዳኘነት ክፍያውን ለከሳሽ እንዲከፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215, 462 | 46281 | ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራወርቅ<br>እና<br>ይገረም ፈዬ | ታህሳስ 28/2003 | 320 |
| 83. | • ልዩ ዕውቀትና ክህሎትን መሰረት በማድረግ አንድ ጉዳይ ተመርምሮ የተሰጠ የሙያ አስተያየት ሊስተባበል የሚችለው በጉዳዩ ላይ የተሻለ የሙያ እውቀትና ክህሎት ባለው ባለሙያ ጉዳዩን መርምሮ በሚሰጠው አስተያየት ስለመሆኑ<br>• አንድን ሰው ለማጓጓዝ ውል የተዋዋለ ሰው በጉዞ ወቅት በተጓዡ ላይ ለደረሰ ጉዳት ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ከብር 40,000 መብለጥ የሌለበት ስለመሆኑ<br>• የጉዳት ካሣ መጠኑ ከብር 40,000 ሊበልጥ የሚችለው በንግድ ህግ ቁ. 599 የተመለከተው መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/<br>የንግድ ህግ ቁ. 597/1/ | 47960 | አቶ ታከለ ባልቻ<br>እና<br>ወ/ሮ አዜብ ፀጋዬ | ታህሳስ 12/2003 | 322 |
| 84. | • የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ህጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ብቻ ስለመሆኑ<br>• በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች የበላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ለማድረግ የሚችለው የማይቀበልበትን ምክንያት በውሣኔው ላይ በግልጽ በማስፈር እንጂ በደፈናው "በተገቢው አልተረጋገጡም" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ስላለመሆኑና በዚህ መልክ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 እና ተከታዮቹ | 58540 | ኪድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል<br>እና<br>ሲስተር ገነት ወንድሙ | ጥር 27/2003 | 326 |
| 85. | ሁለት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በሌላኛው ላይ የፍርድ ባለመብት ሆነው የአፈፃፀም አቤቱታው በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በቀረበ ጊዜ በፍርድ የበሰለው ገንዘብ በመቻቻል እንዲፈፀም በሚል በአንድ ፍርድ ቤት ተጠቃሎ እንዲታይ ለማድረግ የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 397 | 57378 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ<br>እና<br>ወ/ሮ አምሳለ ፀሐይ | ጥር 23/2003 | 329 |
| 86. | በባንክ በኩል ከተላከ ገንዘብ ጋር በተገናኘ በአግባቡ ለተላከለት ሰው አልደረሰውም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በላኪው ወይም በተላከለት ሰው ስም ክስ ቀርቦ ከተወሰነ በኋላ በሌላኛው /በላኪው/በተላከለት/ሰው/ ስም የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥህ/ቁ. 5 የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 51223 | ዳሽን ባንክ አ.ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀመልማል መኮንን | የካቲት 24/2003 | 332 |
| 87. | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 አቤቱታ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለት ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ የተሰጠበት ወገን በድጋሚ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 "ን" መሰረት | 53421 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋሴ<br>እና | የካቲት 22/2003 | 335 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማድረግ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 447, 354 | | አቶ ባንተይርጋ ወርቁ | | |
| 88. | በመጀመሪያ በቀረበ የክስ መከላከያ መልስ ያልተካተተን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልስ እንዲሻሻል በሚል ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ተካትቶ ሲቀርብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 244<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856 | 55973 | ወ/ሮ አፀደ ኤዶ<br>እና<br>አቶ ትኩ ዋቅሹም | የካቲት 21/2003 | 339 |
| 89. | • ሌሎች ሰዎች ተከራካሪ በሆኑበት ጉዳይ ንብረትን አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ፍርድ ከተሰጠ በኂላ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ<br>• አንድ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔው በኂላ የሚያቀርበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 153/3/, 418-421 | 56795 | አቶ ሙባረክ ከድር<br>እና<br>እነ ሚስተር ኑዋምባ ሲርር /አምስት ሰዎች/ | የካቲት 21/2003 | 342 |
| 90. | ፍርድ ቤቶች ከውሣኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፣ የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት በጠበቀ መልኩ ስለመሆኑ | 52546 | እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/<br>እና ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ | ታህሳስ 13/2003 | 347 |
| 91. | ክስ ለመስማት ቀጠሮ ከተሰጠ በኂላ ያልቀረቡ ከሳሾችን ከክርክሩ ውጪ እንዲሆኑ በማለት ትዕዛዝ የሰጠ ፍ/ቤት /ችሎት/ በራሱ ተነሳሽነት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ በማንሳት ከክሱ ውጪ የሆኑትን ከሳሾች የክሱ አካል በማድረግ የሚሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት ህግ ውጪ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73, 74, 78 | 55078 | ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግ/ማህበ ር<br>እና<br>እነ አሸናፊ አለሙ /ዘጠኝ ሰዎች/ | ታህሳስ 25/2003 | 350 |
| 92. | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 377 ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ | 52193 | የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መድህኒት ሃይሉ /ሁለት ሰዎች/ | ታህሳስ 27/2003 | 352 |
| 93. | ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሳሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት የሚኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 72, 78/1/ | 61846 | ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል<br>እና<br>ወሮ ፋጡማ አስማን | ግንቦት 29/2003 | 355 |
| 94. | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 እና 418 መሰረት በተሰጠ ፍርድ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበት ሥርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 359, 418, 222, 223, 137/3/ | 55842 | የኦሮሚያ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዮት<br>እና | መጋቢት 23/2003 | 358 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | እነ አቶ ካሣ ጭርሳ /አራት ሰዎች/ | | |
| 95. | በፍ/ብሔር ክርክር ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ /ጭብጥ/ ለማስረዳት የሚቀርብን የሙያ ምስክርነት (expert witness) ውድቅ በማድረግ ባለሙያ ባልሆኑ ምስክሮች የተሰጠ የምስክርነት ቃልን ሊቀበል የሚችለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/ | 65930 | የሱ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ደጀኔ በቀለ /ሁለት ሰዎች/ | ሰኔ 14/2003 | 362 |
| 96. | ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኝ ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች እውቅና ሊሰጠው ወይም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 456-461 | 59953 | ወ/ሮ አለምነሽ አበበ<br>እና<br>አቶ ተስፋዬ ገሰሰ | ሰኔ 02/2003 | 365 |
| 97. | • በህግ የተቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኂላ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድ የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>• ይግባኙ በጊዜው ሊቀርብ ያልቻለው የባለጉዳዩ ጠበቃ፣ነገረፈጅ ወይም ወኪል የሆነው ሰው ባለመቅረቡ ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋር በተያያዘ በተከሰተ ጉድለት መሆኑ ከታወቀ የማስፈቀጃ አቤቱታው በበቂ ምክንያት የተደረገ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326/2/ /1/ 323/2/ 325 | 57360 | አፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሐምሌ 15/2003 | 369 |
| 98. | በአንድ በመካሄድ ላይ ባለ የፍርድ ቤት ክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጥያቄ አቅርቦ በብይን ውድቅ የተደረገበት እና በሌላ መዝገብ ክስ መስርቶ መብቱን እንዲያስከብር በሚል ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አዲስ መዝገብ በማስከፈት ወይም በሌላ መዝገብ በመግባት የክርክር ተሳታፊ ከመሆን የሚያግደው ነገር የሌለ ስለመሆኑ ወይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | 62173 | ወ/ሪት ቤተልሄም ታደሰ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሂና ታደሰ /ሦስት ሰዎች/ | ሐምሌ 11/2003 | 371 |
| 99. | ግልጽነት የጐደለው ክስ /አቤቱታ/ በቀረበ ጊዜ ክሱ በተከራካሪዎች አነሳሽነት ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ ክሱ እንዲሻሻል ሳይደረግ በደፈናው የቀረበን የይገባኛል ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ፍርድ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91/1/ | 63699 | አጌኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት<br>እና<br>አቶ ጥሩነህ ይመር | ሐምሌ 15/2003 | 375 |
| 100. | ፍ/ቤቶች በባንክ ለተሰጠ ብድር መያዣነት የተሰጠ ንብረትን በአዋጅ ቁ. 97/90 ባንኩ ሲረከበው በብድሩ ገንዘብ እና በንብረቱ ወቅታዊ የዋጋ ግምት መካከል ያለውን ልዩነት ማስላት አስፈላጊ መሆኑን ባመኑ ጊዜ ይህንን ለማድረግ ልዩ የሂሳብ አዋቂ (expert witness) በመመደብ ለጉዳዩ እልባት ሊሰጡ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1//2/ | 61227 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ ኃይሉ አምቦ /ሁለት ሰዎች/ | ሐምሌ 14/2003 | 377 |
| 101. | • በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የእግዱ ትዕዛዝ | 61637 | ዶ/ር አልሑሴን በድልገዋድ | ሐምሌ 11/2003 | 380 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተጥሶ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ለሦስተኛ ወገን በተላለፈ ጊዜ ሊኖር ስለሚችል ውጤት<br>• እግዱ ተጥሶ በተከናወነው ተግባር መብቱ የተጐዳበት ሰው የእግዱን ትዕዛዝ በጣሰው ወይም እንዲጣስ ምክንያት በሆነው አካል ላይ ተገቢውን አቤቱታ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 156<br>አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 15/2/<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1204, 1206, 1184, 1185, 1195 | | እና<br>እነ ወ/ሮ ገነት ሐድጐ /ሁለት ሰዎች/ | | |
| 102. | በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት እውቅና ካልተሰጠው በስተቀር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የቀረበ አቤቱታ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ | 54632 | ወ/ሮ ራውዳ ሙሜ<br>እና<br>አምባሳደር አብደላ አብድራህማን | ግንቦት 29/2003 | 385 |
| 103. | የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ ስላለመሆኑ | 43453 | አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ /ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 15/2002 | 388 |
| 104. | የባለሙያ ማስረጃ ፍፁም ስላለመሆኑና ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ | 14981 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ | ግንቦት 04/1998 | 391 |
| 105. | በህግ /ፍርድ/ ኃይል የተወሰደ ንብረት ሊመለስ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349/1/ | 44238 | አቶ ማሞ ደምሴ /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሄር /ሦስት ሰዎች/ | ጥር 09/2003 | 393 |
| 106. | ከሀራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 እና 453 ትርጉምና ሊፈፀሙ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447, 453 | 56130 | ሊሲ. ታነሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እነ መአዛ አስፋው /ሦስት ሰዎች/ | ጥር 26/2003 | 397 |
| 107. | • ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሊባል በሚችል እክል /ችግር/ ምክንያት መሆኑን ያስረዳ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ<br>• "በቂ ምክንያት" በሚል የሰፈረው ሃረግ ሊተረጐም የሚገባው ተከሳሹ ቀና ልቦና ያለው መሆኑንና የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ነባራዊ ሁኔታዎችን | 54080 | እነ አቶ ላል ሮላንድ ቻፕማን<br>እና<br>አቶ ዜና ወ/ማሪያም | ጥቅምት 19/2003 | 401 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 72, 78/1/ | | | | |
| 108. | የልዩ አዋቂ ምስክሮች በፍ/ቤት የሚሾሙበት፣ የሙያ ግዴታቸውን የሚያከናውኑበት እና ፍ/ቤቶችም የሚቀርበውን ሙያዊ ምስክርነት ሊቀበሉ የሚችሉበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | 44522 | ጭላሎ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማህበ ር እና አፍሪካ ኢንጂነርስ ኮንስትራክሽን | ታህሳስ 15/2003 | 404 |
| 109. | ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለቃል ክርክር /ለመስማት/ በተቀጠረበት ዕለት ከሳሽ የሆነ ወገን በመቅረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 መሰረት የተዘጋ መዝገብን መነሻ በማድረግ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 74/2/ | 58487 | ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት እና ወ/ሮ እታገኝ ደሳለኝ | መጋቢት 22/2003 | 407 |
| 110. | በፍ/ቤት በተሰጠ ፍርድ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የተቀመጠው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትና የቀን አቆጣጠር ስሌት ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323/2/ | 59085 | ወ/ሮ ብርሃኔ አዱላ እና ግርማ አብዲሳ | መጋቢት 05/2003 | 410 |
| 111. | ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ ሠ, 234 | 59294 | አቶ በቀለ ጃፋር እና እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ማሞ | መጋቢት 19/2003 | 413 |
| 112. | አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ጋር በተያያዘ “ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ” በሚል የተቀመጠው ሃረግ ትርጉም<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 244/2/ | 62330 | አቶ አዱኛ አጃው እና ቀስቅስ አየነው | ሚያዝያ 03/2003 | 416 |
| **ባንክና ኢንሹራንስ** | | | | | **419** |
| 113. | በባንክ ከተቀመጠ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ትክክለኛው ገንዘብ አስቀማጭ ከሆነ ሰው ውጭ ለሆነ ሰው ገንዘብ ወጪ ተደርጐ የተከፈለ እንደሆነ ባንኩ በሃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም የባንኩን የተለመደ አሰራር ሳይከተል የሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ | 41535 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ግሎሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህ በር /አራት ሰዎች/ | ጥቅምት 03/2003 | 420 |
| 114. | በንግድ ህጉ የመድን ሰጪን ግዴታና ኃላፊነት በተመለከተ የቀረቡ ድንጋጌዎች መድን ሰጪው ከመድን ገቢዉ ጋር አንዳንድ ኃላፊነቶችን ለማስቀረት በሚል ከተስማሙባቸው ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝበው ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 664/1/ | 50199 | ግሎባል ኡንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ አያሌው ወርቁ | ታህሳስ 27/2003 | 423 |
| 115. | • ባንኮች ላበደሩት ገንዘብ በመያዣነት የያዙትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዕዳ መክፈያነት በሐራጅ ለመሸጥ የተሰጣቸውን ስልጣን በተግባር ሲያውሉ ህግን በመተላለፍ በባለዕዳው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>• በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ለመሸጠም የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ፈቃድ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ | 65632 | ህብረት ባንክ አ.ማ እና አቶ አሊ አብዱ | ሐምሌ 13/2003 | 427 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • አበዳሪ የሆነ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 የተሰጠውን ስልጣን /መብት/ ትቷል (waive) ሊባል ስለሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3, 6 | | | | |
| 116. | መድን ገቢ የሆነ ወገን ጉዳት የደረሰበትን መድን የተገባለት ንብረቱ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊጠገንለት /ሊካስ/ ያልቻለ መሆኑን በተረዳ ወቅት በዚህ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጉዳት ኪሣራ ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1802 | 47076 | አፍሪካ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና ወ/ሮ ጣይቱ አመዴ | መስከረም 25/2003 | 430 |
| 117. | ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለን ተበዳሪ ንብረት አበዳሪ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 በንብረቱ ግምት ከተረከበ በኂላ ቀሪውን ዕዳ በተመለከተ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846 | 56010 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ቃድሮ ኑሬ | ሐምሌ 29/2003 | 435 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | **408** |
| 118. | • የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ እና ሊከተል የሚችለው ውጤት<br>• የሊዝ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ3/2/<br>አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 2/7/, 15/1/ /ለ/ | 54697 | አዲስ ኢንተርናሽናል አካዳሚ እና እነ አቶ ሃይማኖት አበበ /ዘጠኝ ሰዎች | መስከረም 24/2003 | 439 |
| 119. | • ከአዋጅ ውጪ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተወስዶብኛል በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህጉ አግባብ የሚሰጠው ውሣኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊቆጠር የሚችልና ለአፈፃፀም የሚቀርብ ስለመሆኑ<br>• አንድን ጉዳይ የማየት ስልጣን ከፍርድ ቤት ውጪ ለሆነ አካል የተሰጠ በመሆኑ በዚህ አካል እየታየ ባለበት ተመሳሳይ ወቅት በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87<br>አዋጅ ቁ. 193/92<br>አዋጅ ቁ. 572/2000<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8 | 48316 | ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥቅምት 04/2003 | 444 |
| 120. | • የፌዴራል ጉዳይን በውክልና ስልጣን ተመልክቶ በክልል ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ መሰረት በማድረግ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ ስለሚቻልበት ሁኔታ /አግባብ/<br>• የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ በሚነሳ ክርክር ላይ እንደ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ብሎም በይግባኝ ደረጃ ባለ ክርክር ደግሞ እንደ ፌዴራል ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ የፌዴራል ጉዳዮችን ለማስተናገድ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• አዋጅ ቁ. 322/95 የተወሰኑ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በህገ መንግስቱ ተሰጥቷቸው የነበረውን የፌዴራል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው | 54577 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ሰለሞን ያቆብ | ህዳር 01/2003 | 447 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የማስተናገድ የውክልና ስልጣንን ብቻ የሚያስቀር እንጂ በይግባኝ ያላቸውን ስልጣን ጭምር የሚያስቀር ስላለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/, /5/<br>አዋጅ ቁ. 322/95 | | | | |
| 121. | የአ.አ. ከተማ አስተዳደር ማኀበራዊ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ተቋማት ተከራካሪ የሆኑበትንና የገንዘብ መጠናቸው ከ5000 ብር ያልበለጠ የፍ/ብሔር ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95<br>አዋጅ ቁ. 25/88 | 56118 | የኢትዮጵያ ቴሌ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማርያም | ህዳር 16/2003 | 451 |
| 122. | በውጭ አገር መንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 12/1/<br>የወንጀል ህግ ቁ. 263, 71 | 55299 | ዓለም ገብሩ<br>እና<br>የትግራይ ዓቃቤ ህግ | መጋቢት 19/2003 | 454 |
| 123. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ. 67/89 ሥር የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶችን የተመለከቱ ክርክሮችን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ያለ ንግድ ፈቃድ በመነገድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎችን በተመለከተ የቀረበ ክርክርን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ሺሻ ጋር በተገናኘ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን አይቶ ለመወሰን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 46<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/2/, 52 | 56893 | የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቤቱታና ምርመራ ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት<br>እና<br>እነ ወ/ሪት ፍሬህይወት ፍቃዱ /አስራ ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 22/2003 | 457 |
| 124. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>• የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር እስካልተያያዘ ድረስ በከተማው ፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣን ሥር የሚወድቅ ስላለመሆኑ<br>• የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ፍርድ እንዳልተሰጠ የሚቆጠርና ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ከቤት ይዞታ ጋር በተገናኘ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተሰጣቸው ስልጣን ሁከት ይወገድልኝ በሚል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲቀርብ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/1//4//ረ/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9 231 /1/ /ለ/ | 64703 | ሻምበል ለታይ ገ/መስቀል<br>እና<br>በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት | ሐምሌ 29/2003 | 641 |
| 125. | • የፖለቲካ ተሿሚ የሆነ ሰው ከሥራ ኃላፊነቱ መነሳቱን ተከትሎ ያለውን ቅሬታ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 63417 | አቶ ትዕዛዙ አርጋው<br>እና<br>የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ | ሐምሌ 15/2003 | 464 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | • ፍ/ቤቶች በዚህ መልኩ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 12/2/<br>የቤንሻንጉል ብ/ክ/መ/የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁ. 29/95 አንቀጽ 71 | | ም/ቤት | | |
| 126. | • የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከአዋጅ ውጩ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የቀረበን ጉዳይ አከራክሮና አጣርቶ የመወሰን ስልጣን በህግ የተሰጠውና ከፍ/ቤት ውጪ ያለ የዳኝነት አካል ስለመሆኑ<br>• ውሣኔውን ለማስፈፀምም አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚችልና የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለማስፈፀምም ማንኛውም የመንግስት አካል ተገቢውን ትብብር ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87 አንቀጽ 74/ሐ/ 7 4 /ሐ/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371/1/<br>አዋጅ ቁ. 146/91 አንቀጽ 26/2/ 28/2/ | 63627 | ሼህ አሸራቅ ሰይድ<br>እና<br>የቡታጅራ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር | ሐምሌ 14/2003 | 467 |
| 127. | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) አዋጅን በመተላለፍ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 52/4/ /5/ 41/2/<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49<br>የወንጀል ህግ ቁ. 349/1/ | 59723 | አብዱልፈታህ መሐመድ<br>እና<br>ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት | ሰኔ 16/2003 | 471 |
| 128. | • የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ አንድ ድርጊት ያልተገባ የንግድ ውድድር ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 11, 15<br>አዋጅ ቁ. 501/98<br>የንግድ ህግ ቁ. 133 | 55162 | ዩኒሊቨር ፒ.ኤል.ሲ.ፖርት ሰንላይት ሚራል ማርሲ ሳይድ<br>እና<br>ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | የካቲት 22/2003 | 473 |
| 129. | • አንድን ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሌላ የዳኝነት አካል ከሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዮን የማየት ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ<br>• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል በኤጀንሲው የተረጋገጠ ጉዳይን ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠ ነው በሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ለ/, 9/2/, 244/3/ እና 328/3/<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | 37964 | እነ አቶ መሐመድ ሁሴን የእነ አቶ መሐመድ ሁሴን ወራሾች /ሦስት ሰዎች/<br>እና<br>እነ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 27/2003 | 476 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 47/67 | | | | |
| 130. | • በአስተዳደራዊ ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ከሥራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሣኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 578/2000 አንቀጽ 19/1/ /ለ/<br>ደንብ ቁ. 155/2000 አንቀጽ 37/1/ /2/ | 51790 | እነ ወልዳይ ዘሩ /ስልሳ አንድ ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ | ግንቦት 16/2003 | 482 |
| 131. | • የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በተመለከተ የሚነሳ ክርክርን የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>• የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት<br>አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 3, 15<br>አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 49 | 47682 | አም.ኤ ሽሪፍ ኃ.የተ.የግ.ማህበር እና ታደሰ ኃ.የተ.የግ.ማህበር | መጋቢት 06/2003 | 486 |
| | **የንግድ ህግ** | | | | **409** |
| 132. | በቼክ ላይ የተፃፈለትን ገንዘብ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልጠየቀበት ሰው ወይም በይዞታው እያለ የታገደበት እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደ ተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያላግባብ የመበልፀግ ክስ ሊመሰርት የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 799 | 40173 | አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ አብዱልቃድር ጁሃር | ጥቅምት 05/2003 | 491 |
| 133. | የሐዋላ ወረቀት በይርጋ ስለሚታገድበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁ. 817/1/ /2/, 825 | 48242 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ቦጋለ መስቀሌ /ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 04/2003 | 496 |
| 134. | የአክስዮን ማህበር መሥራቾችና የአክሲዮን ድርሻ መብት ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ | 52269 | እነ አቶ ከድር ሀድ ሁሴን /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ጁሀር አልይ | ጥቅምት 17/2003 | 499 |
| 135. | • ቼክ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ለቼኩ መፃፍ /መውጣት/ ምክንያት ከሆነው ውል ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ውልን መሠረት በማድረግ የተፃፈ ቼክ ሌላው ወገን የውል ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በሚል ምክንያት ብቻ ቼኩን የፃፈው ወገን በቼኩ ከመጠየቅ ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁጥር 717 | 55077 | ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገኑ እና አቶ ግደይ አብርሃ | ህዳር 28/2003 | 501 |
| 136. | በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የጉዳት ካሣ አወሳሰን የባህር ህግ ቁ. 198/1/ /3/ | 52667 | ኒያላ ኢንሹራንስ አክስዮን | ታህሳስ 12/2003 | 503 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ<br>ንግድ መርከብ | | |
| 137. | • የአክስዮን ማህበር አባል በመሆን የሚገኝ መብትና ጥቅም ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ<br>• ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮን የሆነ ሰው ላለበት የግል ዕዳ አክሲዮኖቹ /በወቅቱ የገበያ ዋጋ/ ተሸጠው እንዲከፈል ለማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 522-524 | 57288 | የኢትዮጵያ<br>ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ አሸብር<br>ታደሰ /አምስት<br>ሠዎች/ | መጋቢት<br>19/2003 | 506 |
| 138. | በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት የአጓጓዡ የኃላፊነት አድማስ<br>የባህር ህግ ቁ. 196, 138, 205, 197, 180/3/ | 56480 | የኢትዮጵያ<br>ንግድ መርከብ<br>እና<br>የኢትዮጵያ<br>መድን ድርጅት | ሰኔ 14/2003 | 512 |
| 139. | • የአክስዮን ማህበር ወይም የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጅቱ የሚያዝበት ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በድርጅቱ ስም በሚያወጣው/ በሚሰጠው/ ቼክ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ<br>• የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ መስራቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከድርጅቱ ጋር በአንድነት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተናጠል ሊጠየቅ ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁ. 530 | 57932 | ተክሉ ካሣ<br>ገብረየስ<br>እና<br>ማርኮ ባርዚ | ሰኔ 30/2003 | 516 |
| 140. | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን እንዲሁም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 16/2/ 14 20<br>አዋጅ ቁ. 376/96<br>የንግድ ህግ ቁ. 137,138 | 58931 | የንግድና<br>ኢንዱስትሪ<br>ሚኒስቴር<br>እና<br>ታይገር<br>ሎጆስቲክ እና<br>የንብረት ጥበቃ<br>ኃ/የተ/የግል<br>ማህበር | ሐምሌ 15/2003 | 518 |
| 141. | • ከቼክ ጋር በተያያዘ "የግል ግንኙነት" በሚል የተቀመጠው ሀረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>• በቼክ የሚገደዱ ሰዎች ላይ አውጭው ክስ ለማቅረብ የሚችለው ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>• በቼክ በተከሰሰና ሰነዱን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለን "የግል ግንኙነት" በመቃወሚያነት ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ<br>• ቼክ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በህጉ የተዘረዘረ ባለመሆኑ ቼኩን የፃፈው ሰው ቼኩን የሰጠሁት ለዋስትናነት ነው በሚል ቼኩን ይዞ በመጣው ሰው ላይ "የግል ግንኙነትን" መሠረት በማድረግ የሚያቀርበው መቃወሚያ ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል ነው በሚል ውድቅ ሊደረግበት የማይገባ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 717/1/-/3/, 855, 881/1/, /ሀ/, 854, 640,868,752,850,827 - 840 | 24435 | ሀጂ መሃመድ<br>አደም<br>እና<br>አቶ ፍፁም<br>ግርማ | የካቲት 04/2000 | 521 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 142. | • ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ ሰው ከአባልነቱ ለመውጣት የሚችልበት ብሎም ማህበሩ ሊመሰረትና ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በሽምግልና ስምምነት ከመፋታት ጋር ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 510/2/<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ | 50537 | ሲ/ር መአዛ ዮሴፍ<br>እና<br>ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው | ግንቦት 02/2003 | 529 |
| 143. | • በንግድ ህጉ ቁጥር 683 "ወኪሎች" በሚል የተመለከተው የእቃ አስተላላፊነት ሥራን ለጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን የማያካትት ስለመሆኑ<br>• መድን ሰጪው ክስ ሊያቀርብባቸው የማይችላቸው ወገኖች ከመድን ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለመድን ገቢው ጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን ስለመሆኑ<br>የንግድ ሕግ ቁ. 683/3/ | 49295 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>እነ የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን<br>/ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 22/2003 | 535 |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | **543** |
| 144. | የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክት እና የንግድ ስምን አስመልክቶ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማያዛባና ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/1/, /2//ሀ/, እና /ሐ/<br>አዋጅ ቁ. 501/98<br>አዋጅ ቁ. 320/95 አንቀጽ 6/1/ | 57179 | ኢትዮ ሴራሚክ ኃ/የተ/የግ/ማህበ ር<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት<br>/ሁለት ሰዎች/ | የካቲት 22/2003 | 544 |
| 145. | • የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሚሰጣቸው ውሣኔዎች ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ያለው መብት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ማቅረብ ነው እንጂ የቀጥታ ክስ ማቅረብ ስላለመሆኑ<br>• የፌ/ጠፍ/ቤት ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ አስገዳጅ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/<br>አዋጅ ቁ. 25/88<br>አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 6, 17, 36, 49<br>አዋጅ ቁ. 320/95<br>አዋጅ ቁ. 410/96 | 59025 | የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ጥበበ አየለ | ግንቦት 19/2003 | 549 |
| **ውክልና** | | | | | **554** |
| 146. | • አንድ ሰው ለሌላ ሰው በሰጠው ፍፁም የውክልና ስልጣን መሰረት የተከናወነውን ተግባር ለማፍረስና መከራከሪያው ሊያደርገው የሚችለው ወካዩ ራሱ ስለመሆኑ<br>• የወካይ ወራሾች ወኪሉ የውክልና ስልጣን ወሰኑን ሳያልፍ የስራውን ተግባር የሚቃወሙበት ህጋዊ መሰረት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2189/1/ እና /2/ | 38721 | ካፒቴን ዮናስ ሕሉፍ<br>እና<br>እነ አቶ እስጢፋኖስ ኪዳኔ<br>/አራት ሰዎች/ | ህዳር 27/2003 | 555 |
| 147. | የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ በስተቀር ህጋዊ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 5/1//ለ/ | 59568 | አቶ ቴዎድሮ ስተስፋዬእና<br>አቶ ሙሉ አርጌ<br>/ሁለት ሰዎች/ | ሚያዝያ 05/2003 | 561 |